# የፍትህ ሚኒስቴር

## ማውጫ


ክፍል ሃያ ስድስት ........ 1
ግብርና እና የተፈጥሮ ሀብት ልማት ........ 1
ሀ) ግብርና ልማት ........ 1
ደንብ ቁጥር 4/1985 ........ 1
ስለዕፅዋት ኳራንቲን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 1
አዋጅ ቁጥር 1068/2010 ........ 14
ስለዕፅዋት አዳቃይ መብት የወጣ አዋጅ ........ 14
አዋጅ ቁጥር 488/1998 ዓ.ም ........ 30
የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ግብርና ሥርዓት አዋጅ ........ 30
አዋጅ ቁጥር 660/2002 የንብ ሀብት ልማትና ጥበቃ አዋጅ ........ 38
ደንብ ቁጥር 372/2008 ........ 46
የንብ ሀብት ልማትና ጥበቃ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 46
አዋጅ ቁጥር 674/2002 ዓ.ም የፀረ-ተባይ ምዝገባና ቁጥጥር አዋጅ ........ 59
አዋጅ ቁጥር 782/2005 ........ 84
የዕፅዋት ዘር አዋጅ ........ 84
ደንብ ቁጥር 375/2008 ዓ.ም ........ 97
የዕጽዋት ዘር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 97
ደንብ ቁጥር 361/2008 ........ 117
የዕጽዋት ዘር ብቃት ማረጋገጫና የተያያዥ አገልግሎቶችን ክፍያ ተመን ........ 117
መወሰኛ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 117
ለ) እንስሳት እና ቆዳና ሌጦ ........ 120
አዋጅ ቁጥር 267/1994 ........ 120
የእንስሳት በሽታዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ........ 120
አዋጅ ቁጥር 728/2004 ........ 132
የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ........ 132
ደንብ ቁጥር 325/2006 ........ 149
የእንስሳት መድኃኒትና መኖ ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ የአገልግሎት ክፍያን ........ 149

ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ............ 149

አዋጅ ቁጥር 814/2006 ............ 156

የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት አዋጅ ............ 156

ደንብ ቁጥር 339/2007 ............ 168

የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ............ 168

አዋጅ ቁጥር 819/2006 ............ 178

የቁም እንስሳት ግብይት አዋጅ ............ 178

ደንብ ቁጥር 341/2007 ዓ.ም. ............ 191

ስለቁም እንስሳት ግብይት የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ............ 191

ሐ) ቡና እና ሻይ ............ 203

አዋጅ ቁጥር 1051/2009 ............ 203

የቡና ግብይት እና ጥራት ቁጥጥር አዋጅ ............ 203

ደንብ ቁጥር 433/2011 ............ 225

የቡና ግብይት እና ጥራት ቁጥጥርን ለመደንገግ የወጣ ደንብ ............ 225

መ) የዱር እንስሳት እና ደኖች ............ 264

አዋጅ ቁጥር 541/1999 ............ 264

የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ............ 264

ደንብ ቁጥር 163/2001 ............ 274

የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የሚኒስትሮች ............ 274

ምክር ቤት ደንብ ............ 274

አዋጅ ቁጥር 1065/2010 ............ 336

የደን ልማት፣ ጥበቃ እና አጠቃቀም አዋጅ ............ 336

ሠ) የውሀና የዓሳ ሀብት ............ 355

አዋጅ ቁጥር 197/1992 ............ 355

የኢትዮጵያ የውሃ ሀብት አስተዳደር አዋጅ ............ 355

ደንብ ቁጥር 115/1997 ስለውሃ ሀብት አስተዳደር የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ...... 371

አዋጅ ቁጥር 315/1995 የዓሣ ሀብት ልማትና አጠቃቀም አዋጅ ............ 388

አዋጅ ቁጥር 534/1999 ............ 397

የተፋሰስ ምክር ቤቶችና ባለሥልጣናት አዋጅ ........ 397

አዋጅ ቁጥር 841/2006 ........ 407

የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማኅበራት አዋጅ ........ 407

ረ) የአከባቢ ጥበቃ ........ 439

አዋጅ ቁጥር 295/ 995 ........ 439

የአካባቢ ጥበቃ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ........ 439

አዋጅ ቁጥር 299/1995 ........ 443

የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ አዋጅ ........ 443

አዋጅ ቁጥር 300/1995 ........ 454

የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ ........ 454

ደንብ ቁጥር 159/2001 የኢንዱስትሪ ብክለት መከላከያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 465

ደንብ ቁጥር 207/2003 ........ 471

የአበባ ልማት ዘርፍ የአሠራር ሥነ ምግባር ስርዓት የሚኒስትሮች ........ 471

ምክር ቤት ደንብ ........ 471

አዋጅ ቁጥር 482/1998 ........ 480

የጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰብ ዕውቀት አርክቦት እና የማህበረሰብ ........ 480

መብቶች አዋጅ ........ 480

ደንብ ቁጥር 169/2001 ........ 499

የጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰብ ዕውቀት አርክቦትና የማህበረሰብ ........ 499

መብቶች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 499

አዋጅ ቁጥር 513/1999 ........ 518

የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ አዋጅ ........ 518

አዋጅ ቁጥር 571/2000 ........ 527

የጨረራ መከላከያ አዋጅ ........ 527

አዋጅ ቁጥር 655/2001 ........ 532

ስለደህንነት ሕይወት የወጣ አዋጅ ........ 532

አዋጅ ቁጥር 716/2003 የኦዞን ንጣፍን የሚያሳሱ ኬሚካሎችን ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ........ 544

አዋጅ ቁጥር 1223/2012 ....... 555

የማህበረሰብ ተፋሰሶች ልማት፣ አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ....... 555

አዋጅ ቁጥር 1025/2009 ....... 572

ስለጨረራና ኒውክለር መከላከያ የወጣ አዋጅ ....... 572

ክፍል አራት ....... 588

አዋጅ ቁጥር 1075/2010 ....... 592

ስለኢንዱስትሪ ኬሚካሎች ምዝገባና አስተዳደር የወጣ አዋጅ ....... 592

አዋጅ ቁጥር 109// 2010 ....... 601

የአደገኛ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ቁጥጥር አዋጅ ....... 601

ደንብ ቁጥር425/2011 ....... 620

የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ አያያዝ እና አወጋገድ ለመደንገግ የወጣ ....... 620

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ....... 620

ደንብ ቁጥር 429/2010 ....... 634

የሊድ ቀለምን ለመቆጣጠር የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ....... 634

ክፍል ሃያ ሰባት ....... 640

የመንግስት የልማት ድርጅቶች ....... 640

ሀ) የመንግስት ልማት ድርጅቶች አስተዳደር እና ፕራይቬታይዜሽን ....... 640

አዋጅ ቁጥር 25/1984 ....... 640

የመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ....... 640

አዋጅ ቁጥር 1206/2012 ....... 659

የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ወደግል  ስለማዛወር የወጣ አዋጅ ....... 659

አዋጅ ቁጥር 412/1996 ....... 671

የፕራይቬታይዜሽንና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣንን ....... 671

ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ....... 671

ደንብ ቁጥር 107/1996 ....... 673

የመንግሥት ልማት ድርጅቶች የትርፍ ድልድል የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ....... 673

ለ) የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ማቋቋሚያ ህጎች ....... 676

1) ለመንግስት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ የመንግስት ልማት ድርጅቶች ማቋቋሚያ ህጎች 676

ደንብ ቁጥር 22/1985 ........ 676

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ለማቋቋም የወጣ ........ 676

የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ........ 676

ደንብ ቁጥር 23/1985 ........ 678

አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ........ 678

ምክር ቤት ደንብ ........ 678

ደንብ ቁጥር 74/1985 ........ 680

ብሔራዊ አልኮልና አረቄ ፋብሪካ ለማቋቋም ........ 680

የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 680

ደንብ ቁጥር 76/1985 ........ 682

አሰላ ብቅል ፋብሪካ ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 682

ደንብ ቁጥር 106/1985 ........ 684

የኢትዮጵያ ቱሪስት ንግድ ሥራ ድርጅትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ........ 684

ምክር ቤት ደንብ ........ 684

ደንብ ቁጥር 107/1985 ዓ.ም ........ 686

የግዮን ሆቴሎች ድርጅትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 686

ደንብ ቁጥር 111/1985 ........ 688

የፍልውሃ አገልግሎት ድርጅትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 688

ደንብ ቁጥር 141/2000 ..... ኢትዮጵያ የምድር ባቡር ኮርፖሬሽንን ለማቋቋም የወጣ ሚኒስትሮች 690

ምክር ቤት ደንብ ........ 690

ደንብ ቁጥር 192/2003 ........ 692

የስኳር ኮርፖሬሽንን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 692

ደንብ ቁጥር 255/2004 ........ 695

የኢትዮጵያ የባሕር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 695

ደንብ ቁጥር 280/2005 ........ 698

የኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ...................... 698

ደንብ ቁጥር 365/2008 .................................................................................................. 701

የኢትዮጵያ የኮንስትራክሽን ዲዛይንና ሱፐርቪዥን ሥራዎች ኮርፖሬሽን ............................ 701

ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ደንብ.................................................................................... 701

ደንብ ቁጥር 366/2008 .................................................................................................. 705

የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽንን ለማቋቋም የወጣ.................................... 705

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ.................................................................................... 705

ደንብ ቁጥር 367/2008 .................................................................................................. 709

የኢትዮጵያ ማዕድን፣ ነዳጅና ባዮፊዩል ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ ........................................... 709

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ.................................................................................... 709

ደንብ ቁጥር 368/2008 .................................................................................................. 713

የኢትዮጵያ የግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች.................................. 713

ምክር ቤት ደንብ.......................................................................................................... 713

ደንብ ቁጥር 398/2009 .................................................................................................. 717

የፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽንን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ................. 717

2 /ለትራንስፖርት ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ የመንግስት ልማት ድርጅቶች ማቋቋሚያ ህጎች.......................720

ደንብ ቁጥር 298/2006 .................................................................................................. 720

የፐብሊክ ሰርቪስ ሠራተኞች የትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት ማቋቋሚያ ...................... 720

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ.................................................................................... 720

ደንብ ቁጥር 310/2006 .................................................................................................. 722

የኢትዮጵያ የክፍያ መንገዶች ኢንተርፕራይዝ ማቋቋሚያ ............................................... 722

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ.................................................................................... 722

ደንብ ቁጥር 406/2009 .................................................................................................. 724

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ............ 724

ደንብ ቁጥር 165/2001 .................................................................................................. 728

የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት ማቋቋሚያ............................................................ 728

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ.................................................................................... 728

ደንብ ቁጥር 462/2012 ........ 730

የኢትዮጵያ የማዕድን፣ ነዳጅና ባዮፊዩል ኮርፖሬሽንን እንደገና ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 730

ደንብ ቁጥር 177/2002 ........ 734

የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ፓርክ ኮርፓሬሽን ማቋቋሚያ ........ 734

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 734

ደንብ ቁጥር 197/2003 ........ 736

የኢትዮ-ቴሌኮም ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 736

ደንብ ቁጥር 302/2006 ........ 739

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ማቋቋሚያ ........ 739

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 739

ደንብ ቁጥር 303/2006 ........ 742

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ........ 742

ምክር ቤት ደንብ ........ 742

5) ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ የመንግስት ልማት ድርጅቶች ማቋቋሚያ ህጎች ........ 745

ደንብ ቁጥር 328/2006 ........ 745

የኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ግብዓቶች ልማት ድርጅት ማቋቋሚያ ........ 745

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 745

ደንብ ቁጥር 196/2003 ........ 747

የኢትዮጵያ የተስማሚነት ምዘና ድርጅትን ማቋቋሚያ ........ 747

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 747

ደንብ ቁጥር 331/2007 ዓም ........ 750

የኢትዮጵያ የግብርና ምርቶች የመጋዘን አገልግሎት ድርጅት ማቋቋሚያ ........ 750

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 750

ደንብ ቁጥር 369/2008 ........ 753

የኢትዮጵያ የንግድ ሥራዎች ኮርፓሬሽንን ማቋቋሚያ ........ 753

የሚኒስትሮች ምክርቤት ደንብ ........ 753

6) ለአገር መከላከያ ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ የመንግስት ልማት ድርጅቶች ማቋቋሚያ ህጎች ..................... 756
ደንብ ቁጥር 171/1986 ..... 756

የብራና ማተሚያ ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ..... 756

ደንብ ቁጥር 185/2002 ..... 758

የመከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ ማቋቋሚያ ..... 758

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ..... 758

ደንብ ቁጥር 186/2002 ..... 760

የመከላከያ ግንባታ ግብዓቶች ማምረቻ ድርጅት ማቋቋሚያ ..... 760

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ..... 760

ደንብ ቁጥር 187/2002 ..... 762

የመከላከያ ኮንስትራክሽን ዲዛይን ድርጅት ማቋቋሚያ ..... 762

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ..... 762

ደንብ ቁጥር 464/2012 ዓ.ም ..... 764

የመከላከያ ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ 764

ደንብ ቁጥር 475/2013 ዓ.ም ..... 766

የኢትዮ-ኢንጂነሪንግ ግሩፕ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ..... 766

7) ለግብርና ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ የመንግስት ልማት ድርጅቶች ማቋቋሚያ ህጎች ..... 770
ደንብ ቁጥር 52/1991 ብሔራዊ የእንስሳት ጤና ጥበቃ ኢንስቲትዩትን በልማት ድርጅትነት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ..... 770

8)ለትምህርት ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ የመንግስት የልማት ድርጅት ማቋቋሚያ ህጎች ..... 772
ደንብ ቁጥር 50/1991 ዓ.ም..... 772

የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት ማቋቋሚያ ..... 772

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ..... 772

9)ለጠቅላይ ሚኒስቴር ጽህፈት ቤት ተጠሪ የሆኑ የመንግስት የልማት ድርጅት ማቋቋሚያ ህጎች ..... 774
ደንብ ቁጥር 265/2004 ..... 774

የኢትዮጵያ የነዳጅ አቅራቢ ድርጅት ማቋቋሚያ..... 774

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ..... 774

10/ ለገንዘብ ሚንስቴር ተጠሪ የሆኑ የመንግስት ልማት ድርጅቶች ማቋቋሚያ ህጎች ..... 776
ደንብ ቁጥር 201/1987 ..... 776

የኢትዮጵያ መድን ድርጅትን ማቋቋሚያ የሚንስትሮች ........ 776

ምክር ቤት ደንብ ........ 776

ደንብ ቁጥር 202/1987 ........ 778

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ........ 778

ምክር ቤት ደንብ ........ 778

ደንብ ቁጥር 83/1995 ........ 780

የኢትዮጵያ ልማት ባንክን እንደገና ለማቋቋም የወጣ ........ 780

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 780

11) ለሆቴሎች እና ቱሪዝም ስራ ማሰልጠኛ ማዕከል ተጠሪ የሆኑ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ማቋቋሚያ ህጎች ........ 782

ደንብ ቁጥር 175/2002 ዓ.ም ........ 782

የገነት ሆቴል ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 782

12) ለኢንቨስትመንት ኮሚሽን ተጠሪ የሆኑ የመንግስት የልማት ድርጅት ማቋቋሚያ ህጎች ........ 784

ደንብ ቁጥር 326/2007 ........ 784

የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 784

ደንብ ቁጥር 431/2011 ........ 787

የመሬት ባንክና ልማት ኮርፖሬሽንን ለማቋቋም የወጣ ........ 787

ክፍል ሃያ ስምንት ........ 789

አዋጅ ቁጥር 985/2009ዓ.ም ........ 789

የህብረት ስራ ማህበራት አዋጅ ........ 789

ደንብ ቁጥር 106/1996 ........ 828

የኅብረት ሥራ ማኅበራት አዋጅ ቁጥር 147/1991 ለማስፈጸም የወጣ ........ 828

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 828

## ክፍል ሃያ ስድስት

## ግብርና እና የተፈጥሮ ሀብት ልማት

### ሀ) ግብርና ልማት

### ደንብ ቁጥር 4/1985

### ስለዕፅዋት ኳራንቲን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት የሚኒስትሮች ምክር ቤት የጠቅላይ ሚኒስትርንና የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 2/1983 አንቀጽ 4/2/ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "ስለዕፅዋት ኳራንቲን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 4/1985 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ፣**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፣ በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

   1. "መያዣ" ማለት ማንኛውም ቦርሣ፣ ቅርጫት፣ ማሸጊያ፣ ሣጥን ወይም ሌላ ማንኛውም ዓይነት መሸፈኛ ሆኖ ዕፅዋት ሊይዙ ወይም ሊታሸጉ ወይም ሊጠቀለሉ የሚችሉበት ዕቃ ነው፡፡
   2. "ቁጥጥር" ማለት በዕፅዋት ላይ ተባይ ወይም በሽታ መኖሩን ወይም አለመኖሩን ለማረጋገጥ በተመደበ ተቆጣጣሪ የሚደረግ ምርመራ ነው፡፡
   3. "ሚኒስትር" ወይም "ሚኒስቴር" ማለት እንደ አግባቡ የግብርና ሚኒስትር ወይም ሚኒስቴር ነው፡፡
   4. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡
   5. "ቦታ" ማለት ማንኛውም ሕንፃ ወይም ሥፍራ ሲሆን ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት ወይም ወደ ውጭ ለመላክ ሲባል ዕፅዋት የሚቀርቡበት፣ የሚከማቹበት፣ የሚዘጋጁበት፣ የሚታሸጉበት፣ የሚከፈቱበት ወይም የሚነጹበት ነው፡፡
   6. "የዕፅዋት የጤንነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት" ማለት በተባበሩት መንግሥታት የምግብና እርሻ ድርጅት እ.ኤ.አ. በ1951 በተደረገው ዓለም አቀፍ የዕፅዋት ጥበቃ ስምምነት በተገለጸውና እ.ኤ.አ. በ1979 በተሻሻለው ሞዴል መሠረት የተዘጋጀ የምሰክር ወረቀት ነው፡፡

7. “ዕፅዋት” አዝርዕትን፣ የዕፅዋትና የአዝርዕት ውጤቶችን እና ዘርን ይጨምራል፡፡
8. “የኳራንቲን ጣቢያ” ማለት ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ወይም ወደ ውጭ የሚላኩ ወይም በኢትዮጵያ በኩል ወደ ሌላ አገር የሚያልፉ በሀገር ውስጥ ከአንድ አካባቢ ወደ ሌላ አካባቢ የሚጓዙ ዕፅዋት የሚመረመሩበት፣ የሚያዙበት፣ የሚነጹበት፣ የሚቀርቡበት ወይም የሚወገዱበት የተወሰነ ቦታ ነው፡፡
9. “ማጓጓዣ”፣ “የተመረዘ” ፣ “ተቆጣጣሪ”፣ “ፈቃድ”፣ “ዕፅዋት”፣“አዝርዕትና የዕፅዋትና የአዝርዕት ውጤቶች”፣ “ማግለል”፣ “የዕፅዋትና የአዝርዕት ተባይ”፣ “የተወረረ”፣ “ማንጻት” እና ሌሎች ነገሮች የሚሉት ቃላትና ሐረጐች ዕጽዋትንና አዝርዕትን ለመጠበቅ በወጣው ድንጋጌ ቁጥር 56/1963 በአንቀጽ 2 የተመለከተው ትርጓሜ ይኖራቸዋል፡፡ [1]

---

[1] በዚህ ንዑስ አንቀፅ ውስጥ በማጣቀሻነት የተገለጸው ድንጋጌ(56)1963 በ19)27 (2005 አ. 782 በግልፅ ሳይነገር ስለተሻረና በተጠቃለሉ ህጎች ውስጥ ባለመካተቱ እንዲሁም በሻሪው ህግም ቃላቱ ባለመተርጎማቸዉ የድንጋጌው ትርጓሜ እንዲገባ ተደርጓል፡፡

1. “ማጓጓዣ” ማለት ማንኛቸውም አውቶሞቢል፤ ጭነት መኪና፤ የምድር ባቡር ፉርጎ፤ እንስሳ፤ በእንስሳ የሚሳብ ተሽከርካሪ፤ አይሮፕላን፤ ጀልባ፤ ወይም ማንኛቸውም ሌላ ማጓጓዣ ማለት ነው፡፡
2. “የተመረዘ” ማለት እንደ ባክቴሪያ፤ ፈንገስ ወይም ቫይረስ ባሉ በሽታ የሚያመጡ ነፍሳት የተጎዳ ወይም የተበከለ ማለት ነው፡፡
3. “ተወረረ” ማለት በትላትል፤ በዘመሚት፤ በኒማቶድ፤ ወይም በሌላ ዓይነት የዕፅዋት ወይም የአዝርዕት ተባይ የተጎዳ ወይም የተበከለ ማለት ነው፡፡
4. “ተቆጣጣሪ” ማለት ተቆጣጣሪ ተብሎ በሚኒስቴሩ የተሰየመ ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ ነው፡፡
5. “ፈቃድ” ማለት ዕፅዋት፣ አዝርዕት፣ የዕፅዋትና የአዝዕርት ውጤቶችና ሌሎችም ነገሮች ወደ ኢትዮጵያ እንዲገቡ፣ ወይም ከኢትዮጵያ እንዲወጡ የሚያስችል በሚኒስቴሩ የሚሰጥ ሰነድ ማለት ነው፡፡
6. “ዕፅዋት፤ አዝርዕት፣ የዕፅዋትና የአዝርዕት ውጤቶች” ማናቸውም ዛፎች፣ ቁጥቋጦች፣ ሐረጎች፣ የዛፍ ከንፎች ፤ የእንጭት ግርዝ፤ ሙጫዎች፤ ተያይዘዉ የበቀሉ ለጋዎች፣ ዕንቡጦች፣ ፍራፍሬዎች፣ ደረቅ የዉስጥ ፍሬዎችና ሌሎች ዘሮች፣ ሥራ ሥሮች ፣ ቅጽል ቅጠሎች፣ የአበባ ፍሬዎች፣ መሬት ለመሬት የሚሔዱ ሥሮች፣ ዝርዝሮች፣ ቅጠሎች፣ የአበባዎችና በተፈጥሮ በመድረቅ ወይም በፋብሪካ በመሠራት ሁኔታ ያሉ ከእነዚሁ የሚገኙ ዉጤቶች ማለት ነዉ፡፡
7. “ማግለል“ ማለት የዕፅዋትና የአዝርዕት ተባዮች፤ ዕፅዋት፤ አዝርዕት፤ የዕፅዋትና የአዝርዕት ዉጤቶችና ሌሎች ነገሮች ወደተወሰኑ ሥፍራዎች እንዳይገቡ ወይም ከተወሰኑ ሥፍራዎች እንዳይወጡ ለመቆጣጠር በማለት ማግለል፤ ከመሰሎቻቸዉ የዕፀዋትና የአዝርዕት ዓይነቶች ለይቶ ማሳደግ ወይም የዕፀዋትና የአዝርዕት ተባዮች እንዳያሰራጩ ለማድረግ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀዉ ክልል ዉስጥ ማሳደግ ማለት ነዉ፡፡
8. “የዕፅዋትና የአዝርዕት ተባይ” ማለት በማንኛዉም የእድገት ደረጃ ላይ ያለ ትል፤ ዘመሚት፤ ኒማቶድ፤ ቀንድ አዉጣ፤ ፕሮቶዞአ ወይም ሌላ የጀርባ አጥንት የሌለዉ እንስሳ፤ የጀርባ አጥንት ያለዉ እንስሳ ፤ ባክቴሪያ፤ ቫይረስ ወይም ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት ከማንኛዉም ጋር የሚዛመድ ወይም የሚመሳሰል ሕይወት ያለዉ ነገር ወይም ማንኛቸዉንም ዕፀዋት ወይም አዝርዕት ወይም የእዝርዕት የተዘጋጀ፤ የተሠራ ወይም በሌላ ዓይነት የተገኘ ዉጤት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሊጎዳ ወይም በሽታ ሊያመጣበት የሚችል ማንኛዉም ነገር ማለት ነዉ፡
9. “ የተወረረ” ማለት በትላትል፤ በዘመሚት፤ በኒማቶድ ወይም በሌላ ዓይነት የዕፀዋት ወይም የአዝርዕት ተባይ የተጎዳ ወይም የተበከለ ማለት ነዉ፡፡
10. “ማንጻት” ማለት አንድን ነገር ከመመረዝ ወይም ከመወረር ለማዳን በተባይ መግደያ መድኃኒቶች ማጠን ወይም መርጨት ፤ በቀዝቃዛ ወይም በሞቃት ቦታ ማኖር ፤ በሽታ የያዘዉን ክፍል መቁረጥ፤ ማጠብ ወይም ማጽዳት ማለት ነዉ፡፡

10. “ኳራንቲን” ወይም “ህክምና” ማለት እንደቅደም ተከተላቸው ማግለል ወይም ማንጻት ነው፡፡

3. <u>ስለዕጽዋት ኳራንቲን፣</u>

በዕፅዋት ተባይ ሊወረር ወይም ሊበከል የሚችል ማናቸውም ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባ ወይም ወደ ውጭ የሚላክ ወይም በሀገር ውስጥ ከአንድ አካባቢ ወደ ሌላ አካባቢ የሚንቀሳቀስ ዕፅዋት የኳራንቲን ምርመራ ማሟላት አለበት፡፡

4. <u>በተወሰነ ገደብ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ የሚፈቀዱ ዕፅዋት፣</u>

1. ማናቸውም ሰው ከሚኒስትሩ ፈቃድ ካልተሰጠው በስተቀር በሰንጠረዥ አንድ ላይ የተዘረዘሩትን ዕፅዋት ወደ አገር ውስጥ ማስገባት አይችልም፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት ወደ አገር ውስጥ የማስገባት ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ በሚኒስቴሩ ተዘጋጅቶ በሚሰጠው ፎርም መሠረት ይሆናል፡፡

5. <u>ወደ አገር ውስጥ ከመግባት የተከለከሉ ዕፅዋት፣</u>

1. ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ሁለት የተዘረዘሩት ዕፅዋት ወደ አገር ውስጥ ሊገቡ አይችሉም፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ቢኖርም፣ በሚኒስትሩ በሚሰጥ ልዩ ፈቃድ ለሳይንሳዊ ምርምር የሚያገለግሉ ዕፅዋት ወደ ሀገር ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ፡፡

6. <u>ስለዕፅዋት ጤንነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀትና ሌሎች መረጃዎች፣</u>

1. ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ አንድ ላይ የተዘረዘሩት ዕፅዋት ወደ ሀገር ውስጥ በሚገቡበት ጊዜ የዕፅዋት ጤንነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አብሮ መላክ ይኖርበታል፡፡ የምስክር ወረቀቱ በመያዣው ውጪያዊ አካል ላይ መታየት አለበት፡፡
2. በተቀባይ አገር ከተጠየቀ፣ ማናቸውም ዕፅዋት ወደ ውጭ በሚላክ ጊዜ የጤንነቱ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አብሮ መላክ ይኖርበታል፡፡
3. ማንኛውምንም ዕፅዋት ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት ወይም ወደ ውጭ ለመላክ የሚያገለግል መያዣ በመያዣው ውስጥ ስላለው ነገር ምንነት የት እንደተሠራ

---

11. “ሌሎች ነገሮች “ ማለት እርሻን ወይም ዕፀዋትን ወይም አዝርዕትን የሚጎዱ መሆናቸዉ የታወቀ ወይም ሊጎዱ የሚችሉ የዕፅዋት ባሕርይ ያላቸዉም ሆኑ የሌላቸዉ ማናቸዉም ነገሮች ማለት ነዉ፡፡ በዚህም ብቻ ሳይወሰን፤ አፈርን፤ መያዣዎችን፤ መሸፈኛዎችን፣ መጠቅለያዎችንና የመሳሰሉትን ይጨምራል፡፡

ወይም እንደተገኘ፣ ዕፅዋቱ የት እንደተባዛ፣ የባለቤቱ የላኪው፣ የአጓጓዡ ወይም የተቀባዩ ስምና ወደ አገር ውስጥ የሚገባበት ጣቢያ ስምና አድራሻ የሚገልጽ መረጃ በላዩ ላይ ሊጻፍ ይገባል፡፡

7. <u>ከኳራንቲን ነፃ ስለማድረግ፣</u>

የዚህ ደንብ አንቀጽ 3 ቢኖርም፣ ከዚህ ደንብ ጋር ተያይዞ በሚገኘው ሠንጠረዥ አንድ ውስጥ ከተመለከቱት ዕፅዋት ውስጥ፣

1. የተሟላ የኳራንቲን መሣሪያ ባለው የምርምር ተቋም አማካይነት ተመርምሮ ለሳይንሳዊ ጥናትና ምርምር ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባና ወደ ውጭ የሚላክ፣ ወይም
2. ተቀባይነት ያገኘን ደረጃ ጠብቆ የታሸገ በመተላለፍ ላይ የሚገኝ ከሆነ ተቆጣጣሪው ከኳራንቲን ምርመራ ነፃ ለማድረግ ይችላል፡፡

8. <u>ስለማከምና ስለማስወገድ፣</u>

1. ማናቸውም ዕፅዋት በተባይ የተመረዘ ወይም የተወረረ መሆኑ ከተረጋገጠ ተቆጣጣሪው በሚያመጣው ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ መሠረት እንዲታከም ወይም ተመልሶ ወደመጣበት አገር እንዲላክ ወይም እንዲወገድ ያደርጋል፡፡ ተቆጣጣሪውም የሕክምናውን ወይም የማስወገጃውን ዘዴ በጽሑፍ መዘርዘር ይኖርበታል፡፡
2. በተባይ የተመረዘ ወይም የተወረረ ማናቸውም ማጓጓዣ ወይም ቦታ ተቆጣጣሪው በሚያዘው መሠረት መታከም ይኖርበታል፡፡

9. <u>በዓለም አቀፍ መጓጓዣዎች ስለሚጠራቀም የምግብ ትራፊ ወይም ቆሻሻ፣</u>

1. በዓለም አቀፍ አውሮፕላን የሚጠራቀም የምግብ ትራፊ ወይም ቆሻሻ ነገር ሚኒስቴሩ አግባብ ካላቸው መንግሥታዊ ድርጅቶች ጋር በመተባበር በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ጉዳት በማያደርስበት ሁኔታ እንዲጠበቅ ያደርጋል፡፡
2. በጉዞ ላይ በሚገኝ መርከብና አውሮፕላን የሚጠራቀም የምግብ ትራፊ ወይም ቆሻሻ ነገር ውስጥ የሚገኝ ተባይ እንዳያመልጥ ትራፊው ወይም ቆሻሻው በሚገባ በታሸገ መያዣ ውስጥ መቀመጥ ይኖርበታል፡፡
3. ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ካላጋጠመ በስተቀር የምግብ ትራፊዎችን ወይም ቆሻሻ ነገሮችን ወደ መሬት መጣል የተከለከለ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ ሲፈጠር አግባብ ካለው ድርጅት በቅድሚያ ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል፡፡

10.<u>የኳራንቲን ጣቢያዎች፣</u>

1. ማናቸውም ዕፅዋት ወደ አገር ውስጥ የሚገባው ወይም ወደ ውጭ የሚላከው ከዚህ በታች በተመለከቱት የኳራንቲን ጣቢያዎች ይሆናል፡፡
   ሀ) ቀደም ሲል ተቋቁመው አገልግሎት በመስጠት ላይ በሚገኙ ነባር የኳራንቲን ጣቢያዎች፣
   ለ) ለወደፊት እንደአስፈላጊነቱ የሚኒስቴር መ/ቤቱ በሚያቋቁማቸው የኳራንቲን ጣቢያዎች፣
2. ተቆጣጣሪው የኳራንቲን ጊዜያዊ የማቆየት እርምጃ በሚወስድበት ጊዜ ሊደረጉ የሚገባቸውን ጥንቃቄዎች መግለጽ አለበት፡፡
3. ዕፅዋት የያዘ ማናቸውም የዕፅዋት መጓጓዣ አገር ውስጥ እንደደረሰ በቅድሚያ ተቆጣጣሪው እንዲያውቅ መደረግ ይኖርበታል፡፡

11.<u>የተቆጣጣሪው ሥልጣንና ኃላፊነት</u>

በዚህ ደንብና በሌሎች ድንጋጌዎች የተሰጡት ሥልጣንና ኃላፊነት እንደተጠበቁ ሆነው ተቆጣጣሪው፣

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 3 መሠረት ማናቸውም ዕፅዋት እንዲመረመር ማንኛውንም ሰው የማዘዝና ምርመራ የማካሄድ፣
2. የዕፅዋት ተባይ መኖሩን ለማረጋገጥና የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ለማስፈጸም ቦታዎችንና መጓጓዣዎችን እንዲያስመረምርና እንዲያስፈትሽ ማናቸውንም ሰው የማዘዝ፣
3. ተቆጣጣሪው በማንኛውም አካባቢ በመግባት አካባቢው በዕፅዋት ተባይ መመረዙን ወይም መወረሩን ለማረጋገጥ አሰሳ የማካሄድ፣
4. ማናቸውም ዕፅዋት፣ መጓጓዣ ወይም ቦታ ምርመራ ከተካሄደበት በኋላ በተባይ ተመርዞ ወይም ተወሮ ከተገኘ በዚህ ደንብ አንቀጽ 8 መሠረት ተገቢውን እርምጃ ለመውሰድ የመያዝ፣ የማሸግ ወይም ሌላ ተመሳሳይ እርምጃ የመውሰድ፣
5. ወደ ውጭ የሚላክ ወይም ወደ አገር ውስጥ የሚገባ ዕፅዋት የሚመለከት ማንኛውንም የምስክር ወረቀት፣ ፈቃድ ወይም ሌላ አግባብ ያለውን ሰነድ የመመርመር፣
6. ወደ አገር ውስጥ የሚገባ ወይም ወደ ውጭ የሚላክ ዕፅዋት ወይም ማናቸውም ማጓጓዣ ወይም ቦታ እርሻን ሊጎዳ በሚችል ተባይ ያልተመረዘ ወይም ያልተወረረ መሆኑን ለማረጋገጥ ተገቢ የተባይ ቁጥጥር እንዲካሄድ የማዘዝ፣

12.<u>የዕፅዋት ኳራንቲን ደንብን በተመለከተ የሚኒስትሩ ሥልጣን፣</u>

1. ሚኒስትሩ አንድ የተወሰነ አካባቢ በተባይ መወረሩን ካረጋገጠ አካባቢው በተባይ የተወረረ መሆኑን በይፋ በማሳወቅ አካባቢው እንዲታከም ወይም እንዲነፃ ያደርጋል፡፡
2. ሚኒስትሩ አዳዲስ የኳራንቲን ጣቢያዎች በአስፈላጊ አካባቢዎች ያቋቁማል፣ ዝርዝራቸውንም አግባብ ላላቸው ክፍሎች እንዲያውቁት ያደርጋል፡፡
3. ሚኒስትሩ በዚህ ደንብ ሠንጠረዥ አንድ እና ሁለት የተመለከተው ዝርዝር እንደአስፈላጊነቱ በማንኛውም ጊዜ የማሻሻል ሥልጣን አለው፡፡

13.<u>ስለክፍያ፣</u>

የዕፅዋት ኳራንቲን ምርመራ ወይም ቁጥጥር ለማድረግ ወይም በኳራንቲን አማካኝነት ለማከም ወይም ለማስወገድ የሚወጣውን ወጭ በሠንጠረዥ ሶስት በተመለከተው መሠረት ባለቤቱ ወይም አስመጪው ወይም ላኪው ወይም ተወካዩ ይከፍላል፡፡

14.<u>የቅጣት ውሳኔዎች፣</u>

ማናቸውም ሰው ይህንን ደንብ ተላልፎ ከተገኘ ወይም ያልፈጸመ እንደሆነ ዕፅዋትንና አዝርዕትን ለመጠበቅ በወጣው ድንጋጌ ቁጥር 56/63 ዓ.ም አንቀጽ 11 መሠረት ይቀጣል፡፡[2]

15.<u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ፣</u>

ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መስከረም 22 ቀን 1985 ዓ.ም**

**ታምራት ላይኔ**

**የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት ጠቅላይ ሚኒስትር**

[2] ድንጋጌ ቁጥር 56)1963 በ19)27 (2005 አ. 782 በግልፅ ሳይነገር የተሻረ በመሆኑ በሻሪዉ አዋጁ አንቀጽ 26 ውስጥ የተገለጸው ቅጣት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ሠንጠረዥ አንድ

## በተወሰነ ገደብ አገር ውስጥ እንዲገቡ የሚፈቀዱ ዕፅዋት

ተ.ቁ ስም

1. የግራር ዝርያዎች
2. የሸንኩርት ዝርያዎች እምቡጥ
3. አናናስ (ዘሩን ሳይጨምር
4. ቃጫ (ዘሩን ሳይጨምር
5. ለውዝ
6. አስፓራገስ (ዘሩን ሳይጨምር
7. የአጃ ዝርያዎች
8. የጐመን ዝርያዎች (ዘሩን ሳይጨምር
9. የቀይ ሥር ዝርያዎች (ዘሩን ሳይጨምር
10. የርግብ አተር (ዘሩን ሳይጨምር
11. የሻይ ተክል
12. የበርበሬ ዝርያዎች (ዘሩን ሳይጨምር
13. የሱፍ ተክል
14. የካስታኒያ ዝርያዎች
15. ፓፓያ (ዘሩን ሳይጨምር
16. ሽምብራ (ዘሩን ሳይጨምር
17. የሲትረስ ዝርያዎች (ዘሩን ሳይጨምር
18. የቡና ዝርያዎች
19. የኰኒፈር ቤተሰብ የፈረንጅ ጥድ፣ ጥድና ሸውሸዌ
20. የዱባ ቤተሰብ (ዘሩን ሳይጨምር
21. የዕጽዋት በሽታ የማያስከትሉ በካልቸር መልክ የተዘጋጁ እንደ ባክቴሪያ፣ ፈንገስ ኔማቶድስና የመሳሰሉት፣
22. እርድ (ዘሩን ሳይጨምር
23. ካሮት (ዘሩን ሳይጨምር
24. ዲይሰኮሪያ ዝርያዎች (ዘሩን ሳይጨምር
25. ኢስታሪያ ካርደሞመም (ዘሩን ሳይጨምር

26. ባሕር ዛፍ
27. ፋባሲኤ (ዘሩን ሳይጨምር
28. አትክልትና ፍራፍሬ
29. የምድር እንጆሬ ዝርያዎች (ዘሩን ሳይጨምር
30. አኩሪ አተር
31. የጥጥ ዝርያዎች
32. የሳር ቤተሰብ (ዘሩን ሳይጨምር
33. የገብስ ዝርያዎች
34. የፈረንጅ ሱፍ
35. ኪናፍ (ዘሩን ሳይጨምር
36. ስኳር ድንች
37. ሰላጣ (ዘሩን ሳይጨምር
38. ተልባ
39. ቲማቲም
40. የአፕል ዝርያዎች (ዘሩን ሳይጨምር
41. የማንጎ ዝርያዎች (ዘሩን ሳይጨምር
42. ካሳቫ
43. የአልፋልፋ ቤተሰብ ዝርያዎች
44. የሙዝ ዝርያዎች (ዘሩን ሳይጨምር
45. የትምባሆ ዝርያዎች
46. ሩዝ
47. የፓሽንፍሩት ዝርያዎች (ዘሩን ሳይጨምር
48. አቮካዶ (ዘሩን ሳይጨምር
49. የቦሎቄ ዝርያዎች (ዘሩን ሳይጨምር
50. ቴምር (ዘሩን ሳይጨምር
51. ቁንዶበርበሬ (ዘሩን ሳይጨምር
52. አተር
53. የፒሩነስ ዝርያዎች (ዘሩን ሳይጨምር
54. ዘይቱን (ዘሩን ሳይጨምር
55. የፓይረስ ዝርያዎች (ዘሩን ሳይጨምር

56. ጉሎ
57. የሮዝ ዝርያዎች (ዘሩን ሳይጨምር
58. የእንጆሬ ዝርያዎች (ዘሩን ሳይጨምር
59. ሸንኮራ አገዳ (ዘሩን ሳይጨምር
60. ሰካሊ ሴሪያለ
61. ሰሊጥ
62. ደበርጃን (ዘሩን ሳይጨምር
63. ድንች
64. የማሽላ ዝርያዎች
65. የጉራይፎሊየም ዝርያዎች
66. የስንዴ ዝርያዎች
67. የኡልመስ ዝርያዎች (ዘሩን ሳይጨምር
68. ባቄላ
69. የአደንጓሬ ዝርያዎች
70. የወይን ዝርያዎች (ዘሩን ሳይጨምር
71. በቆሎ
72. ዝንጅብል (ዘሩን ሳይጨምር

<u>**ሠንጠረዥ ሁለት**</u>

ወደ አገር ውስጥ ከመግባት የተከለከሉ ዕፅዋት፡፡

1. ብስባሽ (ኮምፖስት
2. በካልቸር መልክ የተዘጋጁ የዕፅዋት በሽታ ሕዋሳትና ናሙናዎች፣
3. የአርትሮፖድ ነፍሳት ቀንዳውጣዎችና ስላግ የዕፅዋት ተባዮች፣
4. ተባዮችን ይዘው ወደ አገር ውስጥ ሊገቡ የሚችሉ ዕፅዋት ነክ መጠቅለያዎች የሙዝ ቅጠል፣ የብርእ አገዳ እህሎች ገለባ፣ የቡና ገለባ፣ የጥጥ ተክልና ቁርጥራጩ እንዲሁም ያልተፈበረኩ የጥጥ ውጤቶች፣ የዕፅዋት አካል ርጋፊ፣ የሩዝ ገለፈት፣ የሸንኮራ አገዳ ተክልና ቁርጥራጩ
5. ከዕፅዋት ሥር የተያያዘም ሆነ ያልተያያዘ አፈር
6. ቀጥሎ የተዘረዘሩት በሰብል ላይ ከፍተኛ ጉዳት በማድረስ የታወቁ ባዕድ አረሞች፣
    1. አቡቲሎን ቲዎፍራሰቲ
    2. ኤጂሎፕስ ስሊንደሪካ

3. አግሮፖይሮን ሪፒንስ
4. አግሮስቲማ ጌታጉ
5. ኤሌክትራ አሮባንቸይድስ
6. ኤሌክትራ ቦጀሊ
7. አሊየም ቪኒያለ
8. አሉፒኩሬስ ማዩሱሮይድስ
9. አማራንተስ ሬትሮርፍሊክሰስ
10. የአምብሮሲያ ዝርያዎች
11. አስፖዲለስ ሪስቱሉለስ
12. ብራኪየሪያ ፕላንታጂኒያ
13. ብራሲካ ካበር
14. ሰንቸራስ ኡኪናተስ
15. ሰንቸሬስ ኢንሰርተስ
16. ኮንድሪላ ጀንሲያ
17. ክሮሞሊና አዶራታ
18. ሲርሰዩም አርቨንስ
19. የኲስኲታ ዝርያዎች
20. ዲጊታሪያ ሳንጊናሊስ
21. ኢክኖክሎአ ክሩስ - ጋሊ
22. ኤኮርኒያ ክራሲፐስ
23. ኢሉዲያ ካናዲንሲስ
24. ኢሜክስ ሰፓይኖሳ
25. ኢዩፎርቢያ ማርጂናታ
26. ኢዩፎርቢያ ኢሱላ
27. ጋሊየም አፖሪን
28. ሆርዲየም ጀባተም
29. ሐይድሪካ ቨርቲሲላታ
30. ሐይፐሪክም ፐርፎራቱም
31. አይፓሚያ ሄዲራሲያ
32. አይሰቸመም ሩሳሰም

33. ኮቻያ ሰኮፓሪያ
34. ላክቱካ ፑልቼላ
35. ሊሊየም ሪጂደም
36. ሜካኒየ ሚክራንታ
37. ሚሞሳ አነርሚስ
38. ሚሞሳ ፒግሪ
39. ሚሞሳ ፑዲካ
40. የአፑንቲያ ዝርያዎች
41. የኦሮባንቸ ዝርያዎች
42. ኦሪዛ ፖንክታታ
43. ፖርቲኒዩም ሐይሰተሮፎርስ
44. ፖሊጐንም ኮንቮልቩላስ
45. ሩኸስ ራዲካንሶ
46. ሩበስ ሹልጋሪስ
47. ሩሜክስ አስቶሴላ
48. ሳካረም ስፖንታንየም
49. ሳልቪኒያ ሞሊስታ
50. ስታሪያ ፋበሪ
51. ስታሪያ ቬሬዲስ
52. ሲሰም በሪየም አልቲሲመም
53. ሶላነም ኤሌንኅኒፎሊየም
54. ሰንቸስ አርቨንሲስ
55. ሶርገም ሐለፔንስ
56. ሰፐርማኮሲ ላቲፍሊያ
57. የስትራይጋ ዝርያዎች
58. ኤሌክስ ዩርፔየስ

## ሠንጠረዥ ሶስት

## ስለዕፅዋት ኳራንቲን አገልግሎት ክፍያ ዝርዝር

1. **ወደ አገር ውስጥ ስለሚገቡ ዕፅዋት፣**
   1. ለምግብነት ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገቡ ዕፅዋት ለምርመራ በአንድ መግቢያ ፈቃድ ---------------------------------------------------------------------------------------------- ብር 20
   2. በተራ ቁጥር (1 ከተመለከተው ውጭ ወደ ኢትዮጵያ ለሚገቡ ማናቸውም ዕፅዋት ለምርመራ፣

      ሀ) ከ1 ኩንታል በታች ለሆነ በሰርተፊኬት ወይም መግቢያ ፈቃድ --------- ብር 10

      ለ) ከ1 እስከ 10 ኩንታል ለሆነ በሰርተፊኬት ወይም በመግቢያ ፈቃድ ---- ብር 20

      ሐ. ከ10 ኩንታል በላይ እስከ 1000 ሺ ኩንታል ለሆነ በተራ ቁጥር (2 (ለ ሥር ከተጠቀሰው በተጨማሪ በየ10 ኩንታል -------------------------- ብር 50 ሳንቲም
   3. በተራ ቁጥር (1 ወይም (2 ሥር የተጠቀሱት ከምርመራ በኋላ ሕክምና የሚያስፈልጋቸው ሆኖ ሲገኝ ሕክምናው በትክክል መከናወኑን ለመቆጣጠር በሰዓት ------------------------------------------------------------------------------------------ ብር 15
   4. ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባው በዓሪን ሀውስ ውስጥ በማሳደግ ከተባይ ነፃ መሆኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ለምርመራ

      ሀ) ችግኝ ግርዝ ወይም ቁርጥራጭ እስከ 100 ከሆነ ለእያንዳንዱ የማሳደጊያ -------- ---------------------------------------------------------------------------------------- ብር 1.00

      ለ) ዘር ከሆነ መጠኑ በቁጥር እስከ 500 ለሚደርስ ለማሳደጊያ -------------- ብር 20.00

      ሐ. በተራ ቁጥር 4(ለ ከተመለከተው መጠን በላይ ከሆነ በተጨማሪ በየ100 ዘር ---- --------------------------------------------------------------------------------------- ብር 2.00
2. **ወደ ውጭ ስለሚላኩ ዕፅዋት፣**
   1. ወደውጭ የሚላኩ ዕፅዋት ምርመራ ተደርጐላቸው የጤንነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት እንዲሰጣቸው ለሚጠይቁ ለምርመራ፣

      ሀ) ከ1 ኩንታል በታች ለሆነ በሰርተፊኬት -------------------------------- ብር 10.00

      ለ) ከ1 ኩንታል እስከ 10 ኩንታል ለሆነ በሰርተፊኬት --------------------- ብር 20.00

ሐ. ከ10 ኩንታል በላይ እስከ 2000 ሺ. ኩንታል ለሆነ በተራ ቁጥር 1(ለ ሥር ከተመለከተው በተጨማሪ በየ10 ኩንታል ------------------------ ብር 50.00 ሳንቲም

መ. ከሌላ አገር ወደ ኢትዮጵያ ገብተው በነበሩበት ሁኔታ ተመልሰው ወደ ሌላ አገር ለሚሠራጩና ለሚከፋፈሉ በሰርተፊኬት ------------------------- ብር 5.00

2. ወደ ውጭ አገር የሚላከው በመስክ ላይ እያለ ምርመራና ቁጥጥር የሚያስፈልገው ሆኖ ሲገኝ ለመስክ ቁጥጥር በቀን ------------------------------------------------ ብር 20.00

3. ወደ ውጭ አገር የሚላከው ሕክምና የሚያስፈልገው ሆኖ ሲገኝ ሕክምናው በትክክል መከናወኑን ለመቆጣጠር በሰዓት ------------------------------------------- ብር 15.00

3. <u>ስለሚወገዱ ዕፅዋት</u>

1. አንድ ዕፅዋት እንዲወገድ በተወሰነው መሠረት የማስወገድ ተግባር በሚከናወንበት ጊዜ ተቆጣጣሪው በቦታው ተገኝቶ ለሚያደርገው ክትትል በሰዓት --------------- ብር 15.00
2. ዕፅዋቱን ለማስወገድ የሚያስፈልግ የመጓጓዣ፣ የሰው ጉልበትና ሌሎች ወጪዎች የሚሸፈኑት ጉዳዩ በሚመለከተው ሰው ይሆናል፡፡

## አዋጅ ቁጥር 1068/2010

## ስለዕፅዋት አዳቃይ መብት የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክሕገ መንግሥት ዜጎች የግል ንብረት ባለቤት የመሆን መብት እንዳላቸው ስለሚደነግግና የዕፅዋት አዳቃይመብት በዚህ ክፍል ውስጥ የሚስተናገድ ሆኖ በመገኘቱ እንዲሁም አዳዲስ ዝርያዎችን ከውጭ በማስገባት ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ለማድረግ ሲባል ዝርያውን ያፈለቁ ባለሃብቶች ከዝርያቸው ተጠቃሚ መሆን ስለሚገባቸው፤

ከዘርፉ የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ለማሳደግ የዕፅዋት አዳቃይ መብትን ከዓለም አቀፍ አሠራር ጋር በማጣጣም ዋስትና እንዲያገኝ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

ከአዳቃይ የምርምር ግኝት መጠበቅ ጋር ተያይዞ የሚነሳውን አለመግባባት ለመፍታት. ግልፅነትና ተጠያቂነት ያለበት የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የዕፅዋት አዳቃይ መብትን ከማበረታታት ጎንለጎን አዳዲስ የዕፅዋት ዝርያን ለማውጣት ግብዓት የሆነውን የዕፅዋት ብዝሀ-ህይወት ሀብት ከዚህ ቀደም የጠበቁትን፣ አሁን እየጠበቁ ያሉትንና ወደፊትም የሚጠብቁትን በአገራችን አርሶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለዘመናት የቆየውን የዕፅዋት ዘር የማቆየት፣ የመጠበቅና የማስተላለፍ ባህላዊ የማኅበረሰብ ዕውቀት እና ልማድ እንዲቀጥል ማድረግ አስፈላጊና ተገቢ በመሆኑ፤

ከዕፅዋት አዳቃይ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መብቶች፣ ክልከላዎችና ኃላፊነቶች ለመመዝገብ የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ በማውጣት የአዳቃዩን አስተዋጽኦ ማሳደግ በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ (55(1 መሠረት የሚከተለው ታውጇል፦

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የዕፅዋት አዳቃይ መብት አዋጅ ቁጥር 1068/2010" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

## የፍትህ ሚኒስቴር

1. “አመልካች" ማለት የዕፅዋት አዳቃይነት መብት እንዲሰጠው ለሚኒስቴሩ ማመልከቻ ያቀረበ ሰው ነው፤
2. “አዳቃይ" ማለት፦

   ሀ አዲስ የዕፅዋት ዝርያን አዳቅሎ ወይም አግኝቶና አበልፅጎ ያወጣ ሰው፤ ወይም

   ለ አዲስ የዕፅዋት ዝርያን አዳቅሎ ወይም አግኝቶና አበልጽጎ ያወጣውን ሰው ቀጥሮ ወይም ሥራውን ተኮናትሮ ያሠራ ሰው፤ ወይም

   ሐ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) ወይም (ለ) የተጠቀሰውን ሰው ወራሽ የሆነ ሰው፤

   ነው፤
3. "እውን ዘር" ማለት ለዕፅዋቱ መራቢያነት የሚያገለግል ከዕፅዋቱ የተገኘ ዘር ነው፤
4. "የንግድ ግብይት" ማለት አነስተኛ ይዞታ ባላቸው አርሶ አደሮች ወይም ከፊል አርብቶ አደሮች መካከል እንዲሁም አነስተኛ ይዞታ ባላቸው አርሶ አደሮች ወይም ከፊል አርብቶ አደሮች እና በኅብረት ሥራ ማኅበራቸው መካከል ከሚደረገው ግብይት ውጪ የሚደረግ ማንኛውም የዘር ንግድ ነው፤
5. "ስያሜ" ማለት የዕፅዋት አዳቃይነት መብት ለተሰጠበት ዝርያ የሚሰጥ የዝርያ መጠሪያ ስም ማለት ነው፤
6. "በዋነኛነት ጥበቃ ከተደረገለት ዝርያ የተገኘ ዝርያ" ማለት፦

   ሀ በዋነኛነት ከመጀመሪያ ዝርያ የተገኘ ወይም ዝርያው ራሱ በዋነኛነት ከመጀመሪያ ዝርያ የተገኘ ሆኖ ይኸውም ዝርያው በጄኖታይፕ ወይም በጄኖታይፖች ጥምረት አማካኝነት የሚገለጸውን የመጀመሪያውን ዝርያ ተፈላጊ ባህርያት ጠብቆ የያዘ፤

   ለ ጥበቃ ከተደረገለት የመጀመሪያው ዝርያ ልዩ መሆኑ በግልጽ የሚታወቅ፤ እና ሐ ዝርያውን ለማግኘት በሚደረገው ሂደትከሚፈጠረው ልዩነት በስተቀር ጥበቃ ከተደረገለት የመጀመሪያው ዝርያ ጋር ያሉት ዋና ዋና ባህርያት እንዲጠበቁሆነው የዚሁ ጥበቃ የተደረገለት ዝርያ ጄኖታይፕ ወይም ጄኖታይፖች ጥምረት ውጤት የሆነ፤

   ነው፡፡
7. "የአርሶ አደሮች ወይም የከፊል አርሶ አደሮችዝርያ" ማለት፦

   ሀ በአርሶ አደሮች ወይም በከፊል አርሶ አደሮች ማሣ ላይ በባህላዊ መንገድ የለማ እና የበለፀገ፤ ወይም

ለ አርሶ አደሮች ወይም ከፊል አርብቶ አደሮች በዋነኛነት ከተለያዩ ምንጮች ያዳቀሉት ወይም የመረጡት፣

የዕፅዋት ዝርያ ነው፤

8. "ጄኖታይፕ" ማለት የአንድን ዕፅዋት ሥነ ባህሪየሚገልፅ የዘረመል ስብስብ ነው፤
9. "ባለመብት" ማለት ከሚኒስቴሩ የዕፅዋት አዳቃይነት መብት የተሰጠው ሰው ነው፤
10. "ሕብረ-መነሻ ዝርያ" ማለት የአንድን የዕፅዋት ዝርያ አዳቅሎ ለማውጣት የታወቀ መጠን የያዘየዘር ሀረግ ወይም ግንድ ስብስብ ነው፤
11. "ዕፅዋት" ማለት ከእንስሳትና ከደቂቀ ዘአካላት ውጭ ያለ ማንኛውም ሕይወት ያለው የሚራባ አካል ነው፤
12. "የተጠበቀ ዝርያ" ማለት ሚኒስቴሩ በሰጠው የዕፅዋት አዳቃይ መብት የተጠበቀ አዲስ የዕፅዋት ዝርያ ነው፤
13. "ዘር" ማለት እውን ዘር፣ አኩራች፣ የተክል ቁርጥራጭ፣ ሥራ ሥር፣ ችግኝ ወይም ሌሎች ለዕጽዋት ማራባት የሚያገለግል ማንኛውም የተክል አካል ነው፣
14. "ሽያጭ" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የዕፅዋት ዘርን የማስተዋወቅ፣ የመገበያየት፣ ከውጪ የማስገባትና ወደውጪ የመላክ፣ የማጓጓዝ እና ሌሎች ሰዎች እንዲሸጡ ፈቃድ መስጠትን ያካትታል፤
15. "አነስተኛ ይዞታ ያለው አርሶ አደር ወይም አርብቶ አደር" ማለት በሕግ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሰርትፍኬት የተሰጠው፣ የመሬትይዞታው ከ10 ሄክታር ያልበለጠና በዋናነትየራሱንና የቤተሰቡን ጉልበት በመጠቀም የእርሻ ልማት የሚያካሂድና ኑሮው በዋናነት በግብርና ላይ የተመሰረተ አርሶ አደር ወይም ከፊልአርብቶ አደር ነው፤
16. "ዝርያ" ማለት በአንድ የዕፅዋት ስብስብ ውስጥ የታወቀ የመጨረሻ ዝቅተኛ ደረጃ ያለው የዕፅዋት ክፍል ሆኖ፦

ሀ ከአንድ ከታወቀ ጄኖታይፕ ወይም ከብዙ ጄኖታይፖች ጥምረት በሚመነጩ ባህርያት መታየት የሚገለጽ፤

ለ ካሉት ባህርያት መካከል ቢያንስ በአንዱከሌሎች ማናቸውም የዕፅዋት ስብስቦች የሚለይ፤ እና

ሐ ባህርያቱን ሳይቀይር መራባት በመቻሉምክንያት እንደ አንድ ዓይነት ሊወሰድ የሚችል፤

የዕፅዋት ስብስብ ነው፤

17."ሚኒስቴር" ማለት የእርሻና ተፈጥሮ ሀብትሚኒስቴር ነው፤

18."ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግየሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

19.ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው ሴትን ያካትታል።

3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅ ሚኒስቴሩ በመመሪያ እንዳይፈጸምባቸውከሚወስናቸው የዕፅዋት ጀነራ እና ዓይነቴዎችበስተቀር በሁሉም የዕፅዋት ቤተሰቦችና ዓይነቴዎችላይ በመላው አገሪቱ ውስጥ ተፈጻሚ ይሆናል።

<u>ክፍል ሁለት</u>

<u>የዕፅዋት አዳቃይ መብቶች</u>

4. <u>የዕፅዋት ዝርያ ጥበቃ ለማግኘት ማሟላት ያለበት መስፈርት</u>

1. የዕፅዋት ዝርያ ለጥበቃ ብቁ የሚሆነው፦

ሀ ማመልከቻ በሚቀርብበት ወቅት በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ በግልጽ በሚታዩ ባህርያት ከዚህ በፊት ከሚታወቁ ሌሎች ዝርያዎች የተለየ ስለመሆኑ በተለምዶ የሚታወቅ፤

ለ በእውን ዘር ወይም ያለ እውን ዘር የሚራባበትን የተለዩ ባህርያትን በሚመለከትበበቂ ሁኔታ ወጥነት ያለው፤

ሐ ከተደጋጋሚ ማራባትና ማባዛት ዑደት በኋላየተለየ ባህርያቱን ሳይለውጥ ይዞየሚቆይ፤እና

መ ማመልከቻ ከቀረበበት ቀን በፊት ዝርያውአዲስ የሆነና ዘሩ ወይም የተሰበሰበው የዝርያው ምርት በኢትዮጵያ ግዛት ከአንድ ዓመት ለበለጠ ጊዜ በንግድ ገበያ ላይ ያልዋለ፣ ወይም ከኢትዮጵያ ውጪ ከሆነ የዛፍ ወይም የወይን ዝርያ ከሆነ ከስድስት ዓመት ለበለጠ ወይም ሌሎች ዝርያዎች ከሆኑ ከአራት ዓመት ለበለጠ ጊዜ በንግድ ገበያ ላይ ያልዋለ፣

ሲሆን ነው፡፡

2. ይህ አዋጅ በጸናበት ቀን በንግድ ግብይት ላይ የሚገኙ ዝርያዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1 /መ መሠረት ለጥበቃ ብቁ የሚሆኑት፦

ሀ አዋጁ ከጸናበት ቀን ጀምሮ በሚታሰብ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ማመልከቻ ሲቀርብ፤ እና

ለ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 10 መሠረት የዕፅዋት የአዳቃይ መብት በዕፅዋት አዳቃዮች መብት መዝገብ ውስጥ ሲመዘገብ።

ይሆናል።

3. ሚኒስቴሩ የአርሶ አደር ወይም የከፊል አርብቶአደር ዝርያዎች የዕፅዋት አዳቃዮች መብትማግኘት እንዲችሉ ቀለል ያለ የተለየ፣ ወጥነትያለው እና ከቦታ ቦታ ሊቀያየር የማይችል የዝርያባህሪ መስፈርቶችን በመመሪያ ያወጣል።

4. ሚኒስቴሩ አቻ የሙከራ ዘዴ ከሚከተሉ አገሮችለተገኘ ተመሳሳይ ዝርያ የተደረገ የተለየ፣ ወጥነትያለው እና ከቦታ ቦታ ሊቀያየር የማይችል የዝርያባህሪ ሙከራ ውጤት ዕውቅና ሊሰጥ ይችላል፣

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/መ የተጠቀሰው ቢኖርም ሚኒስቴሩ ለአገሪቷ ብሔራዊ ጥቅም ያስገኛል ብሎ ካመነበት ከዚህ በፊት በውጭ አገር የተመዘገበን የዕፅዋት አዳቃይ መብት ተቀብሎ በዕፅዋት አዳቃዮች መብት መዝገብ ውስጥ እንዲመዘገብ ሊፈቅድ ይችላል፤ ሆኖም ግን የዕፅዋት አዳቃዮች መብት የቆይታ ጊዜ የሚሰላው በውጪ አገር ለመጀመሪያ ጊዜ መብቱ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ይሆናል።

5. <u>የዕፅዋት አዳቃይ መብት ወሰን</u>

1. በዚህ አዋጅ ከክልከላ ነፃ ስለመሆንና ስለገደቦች የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው የዕፅዋት አዳቃይ መብት ባለቤት መብቱ የተጠበቀ ዝርያን ዘር እና የዘር አካል፦

ሀ) መሸጥ ወይም ሌሎች ሰዎች እንዲሸጡ ፈቃድየመስጠት፤ እና

ለ) የማባዛት ወይም ሌሎች ሰዎች ለገበያ እንዲያባዙ ፈቃድ የመስጠት፣

ብቸኛ መብት ይኖረዋል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው መብት በሚከተሉት ላይም ተግባራዊ ይሆናል፦

ሀ) ዝርያው በዋነኛነት ጥበቃ ከተደረገለት ሌላ ዝርያ የተገኘ ሆኖ ነገር ግን ዝርያው የተገኘበት ዝርያ ራሱ በዋነኛነት ጥበቃ ከተደረገለት ሌላ ዝርያ የተገኘ ያልሆነ እንደሆነ፤

ለ) ጥበቃ ከተደረገለት ዝርያ ግልጽ የሆነ ልዩነት የሌላቸው ዝርያዎች፤ እና

ሐ) ዝርያዎቹን ለማምረት የተጠበቀውን ዝርያ በተደጋጋሚ መጠቀም የሚያስፈልጉ ዝርያዎች ላይ ተግባራዊ ይሆናል።

3. አዳቃዩ የተሻሻለ ዝርያውን ያበለጸገው የአርሶ አደሮች ወይም የከፊል አርሶ አደሮች ዝርያ ዱርበቀል ዕፅዋት እና ሌሎች ዝርያዎችን እና የማህበረሰብ

እውቀትን ተጠቅሞ ከሆነ የዕፅዋት አዳቃይ መብት የሚሰጠው እና ተግባራዊ የሚሆነው በሀገሪቷ የብዝሃ ህይወት ሃብትና የማህበረሰብ ዕውቀት አርክቦትና የማህበረሰብ መብቶች ህግ በሚፈቅደው መሠረት ሲሆን፤ ይኸውም፦

ሀ) ዝርያውን እና ከዝርያው ጋር የተያያዘ ዕውቀትን ለመጠቀም ቅድሚያ ይሁንታ ሲኖር፤ እና

ለ) የጋራ ጥቅምን የሚያስጠብቅ ስምምነት ላይ የተደረሰ ሲሆን፤

ነው፡፡

4. የመንግሥት የምርምር ተቋሞች የመብቱ ባለቤት ሲሆኑ ሚኒስቴሩ በመመሪያ በሚያወጣቸው መስፈርቶች መሠረት የሚሰጠው ፈቃድ የሕዝብ ሀብት መሆኑን የሚያንፀባርቅ መሆን አለበት፡፡

5. በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሰጥ ማንኛውም የዕፅዋት አዳቃይ መብት ምስክር ወረቀት እና ሌሎች አገልግሎቶች በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣው ደንብ መሰረት ተገቢው የአገልግሎት ክፍያ የሚፈጸምባቸው እና ሌሎች ዝርዝር መስፈርቶች የሚኖሩት ይሆናል።

## 6. <u>የዕፅዋት አዳቃይ መብት ተፈፃሚ የማይሆንባቸው</u>

የዕፅዋት አዳቃይ መብት በሚከተሉት ዝርያዎች ላይተፈፃሚ አይሆንም፦

1. በግል ለሚመረትና ለንግድ አገልግሎት በማይውል ዝርያ፤
2. ለሙከራ፣ ለምርምር ወይም ለትምህርት አገልግሎት በሚውል ዝርያ፤ ወይም
3. ሌላ ዝርያን ለማዳቀል በሚውል ዝርያ፡፡

## 7. <u>የአርሶ አደሮች ወይም የከፊል አርብቶ አደሮች መብቶች</u>

በዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች ቢኖሩም ጥበቃ የተደረገላቸው ዝርያዎችን በተመለከተ የሚከተሉት የአርሶ አደር ወይም የከፊል አርብቶ አደር መብቶች የተጠበቁና እውቅና ያገኙ ናቸው፦

1. አነስተኛ ይዞታ ያለው አርሶ አደር ወይም ከፊል አርብቶ አደር ያመረተውን ማንኛውንም ዝርያ ምርት ለዘርነት የማስቀመጥ፣ የመጠቀም፣ የመለዋወጥ እና ከንግድ ግብይት ውጭ የመሸጥ መብት፤
2. ማንኛውም አርሶ አደር ወይም ከፊል አርብቶ አደር ያመረተውን ዘር በቀጥታ ለኑሮው የሚደግፉ የምግብ ሰብልንና ሌላ ዓይነት ዘርን የማስቀመጥ እና የመጠቀም መብት፡፡

8. **በዕፅዋት አዳቃይ መብት ላይ ስለተጣሉ ገደቦች**

1. ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ በሚከተሉት ምክንያቶች ሚኒስቴሩ በዕፅዋት አዳቃይ መብት አጠቃቀም ላይ ገደብ ሊጥልይችላል፦

ሀ) የዕፅዋት አዳቃይ መብት የተሰጠው ማንኛውም ሰው የተጠበቀውን ዝርያ ዘር የሚፈልጉ የተጠቃሚዎችን ፍላጎት ማሟላት ካልቻለ ወይም ለማሟላት ፈቃደኛ ካልሆነ፣ ወይም

ለ) የዕዕዋት አዳቃይ መብት ሲተገበር በምግብ ዋስትና፣ በሕዝብ ጤና፣ በብዝሀ-ህይወት፣ በአካባቢ ላይ ወይም በሌሎች የሕዝብ ጥቅም በሆኑ ጉዳዮች ላይ ጉዳት የሚያደርስ መሆኑን በዚህ ጉዳይ ላይ ከሚመለከተው አግባብነት ያለው አካል ጋር በመመካከር የተወሰነ ከሆነ፡፡

2. በዕፅዋት አዳቃይ መብት ላይ ገደብ ሊጣል የሚችለው ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ በተገለጸው ሁኔታና መጠን መሠረት ሆኖ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሀ) የተጠቀሱት ሲሻሻሉ ገደቡ መነሳት አለበት፡፡

3. ሚኒስቴሩ በዕፅዋት አዳቃይ መብት አጠቃቀም ላይ ገደብ ለማድረግ ሲወሰን፦

ሀ የተጣሉ ገደቦችን ዝርዝር በመግለጽ የውሳኔውን ግልባጭ ለባለመብቱ መስጠት፤

ለ ገደብ ስለመጣሉ ለሕዝብ ማሳወቅ፤ እና

ሐ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሀ )መሠረትገ ደብ በመጣሉ ለባለመብቱ የሚከፈለውን ካሣ መወሰን፤

አለበት፡፡

9. **ግዴታ ፈቃድ**

1. በዚህ አዋጅ በአንቀጽ (8) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የሕዝብን ጥቅም ለመጠበቅ ሲባል ፍላጎት ያለው ማንኛውም ሰው ሲያመለክት ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የግዴታ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል።

2. ሚኒስቴሩ የግዴታ ፈቃድ ሊሰጥ የሚችለው፦

ሀ ባለመብቱ የተጠበቀውን ዝርያ ዘር ለጠቅላላው ሕዝብ ፍላጎት በሚበቃ መጠን የማያመርትና ለሽያጭ የማያቀርብ ከሆነና ሌሎች ሰዎች የተጠበቀ ዝርያውን ዘር እንዲያመርቱና እንዲሸጡ ፈቃድ የከለከለ እንደሆነ ወይምፈቃድ ለመስጠት ፈቃደኛ ሳይሆን የቀረ እንደሆነ፤ ወይም

ለ በብሔራዊ ደረጃ የምግብ ዋስትና ወይምየሕዝብን ጤንነት ለማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፤

ብቻ ነው፡፡

3. የግዴታ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ለባለመብቱ ሊከፍል የሚገባው የክፍያ መጠን፣ የግዴታፈቃዱ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ እና ሌሎች ዝርዝር ጉዳዮች በደንብ ይወሰናል።

4. የግዴታ ፈቃድ የተሰጠው ሰው የባለመብቱ ፈቃድ ያስፈልጋቸው የነበሩ ማናቸውንም ተግባሮች ለማከናወን ባለመብቱ የሚኖረውን ያህል መብት እና ተጠያቂነት ይኖረዋል፤ ይህም ሲደረግ በሚኒስትሩ እውቅና ይሆናል።

5. የግዴታ ፈቃድ መሰጠቱ ባለመብቱ ዝርያውን ከመጠቀም ወይም ሌሎች ሰዎች እንዲጠቀሙበት ፈቃድ ከመስጠት አያግደውም፡፡

6. ሚኒስቴሩ ከሚከተሉት በአንዱ ምክንያት የግዴታ ፈቃዱን ሊሰርዝ ወይም ሊያቋርጥ ይችላል፦

ሀ) የግዴታ ፈቃዱ የተሰጠበት ምክንያት አስፈላጊነት ያበቃ ወይም ሊቀጥል የማይችል ሲሆን ወይም፤

ለ) ባለፈቃዱ በተሰጠው ፈቃድ መሠረት ሥራውን በተገቢው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካልጀመረ ወይም ለመጠቀም በቂ ዝግጅት ካላደረገ ወይም፤

ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት ሚኒስቴሩ በሚወጣው ደንብ ውስጥ የተመለከቱ ግዴታዎች ያልተከበሩ እንደሆነ፤

ነው፡፡

10. **<u>የዕፅዋት አዳቃይ መብት ስለሚቆይበት ዘመን</u>**

ማንኛውም የዕፅዋት አዳቃይ መብት ጥበቃ ዘመን መቆጠር የሚጀምረው የዕፅዋት የአዳቃይ መብት ከተሰጠበት ዕለት አንስቶ ሲሆን ዓመታዊ ሰብሎችን በተመለከተ ለ20 ዓመት፤ ዛፎችን፣ የወይን ተክሎችን ወይም ሌሎች ቋሚ ተክሎችን በተመለከተ ለ25 ዓመትይሆናል።

11. **<u>የዕፅዋት አዳቃይ መብት ለማግኘት ብቁ ስለመሆን</u>**

1. ማንኛውም የዕፅዋት አዳቃይ ኢትዮጵያዊም ይሁን የውጭ ሀገር ዜጋ፣ ነዋሪነቱ ኢትዮጵያ ውስጥ ቢሆንም ባይሆንም፣ ዝርያው ኢትዮጵያ ውስጥ ይሁን ውጭ ሀገር የተዳቀለ አዲስ ላዳቀለው የዕፅዋት ዝርያ የዕፅዋት አዳቃይ መብት እንዲሰጠው ሊያመለክት ይችላል።

2. የአርሶ አደሮች ወይም የከፊል አርብቶ አደሮች የዕፅዋት ዝርያን በተመለከተ ዝርያውን ያበለጸገውን ማህበረሰብ የሚወክል ማንኛውም ሰው ለማህበረሰቡ የዕፅዋት አዳቃይ መብት እንዲሰጠው ሊያመለክት ይችላል።
3. ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ሰዎች የዕፅዋት ዝርያውን በጋራ ያዳቀሉ እንደሆነ የጋራ አዳቃዮች መብት ይሰጣቸዋል፤ ሆኖም ግን የጋራ መብት ካላቸው ሰዎች ውስጥ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎች የዕፅዋት የአዳቃዮች መብት በተናጠል ማግኘት የሚችሉት ዝርያውን በጋራ ካበለፀጉት ሰዎች ፈቃዱ እንዲሰጣቸው መስማማታቸውን የሚያስረዳ በሰነድ አረጋጋጭ በተረጋገጠ ጽሑፍ ሲያረጋግጥ ይሆናል።
4. አዳቃዩ የመንግሥት ወይም የግል ተቋም በሆነጊዜ የዕፅዋት አዳቃይ መብቱ በድርጅቱ ስምይሰጣል።
5. አንድን የዕፅዋት ዝርያ ሁለት ወይም ከሁለትበላይ የሆኑ ሰዎች ለየብቻቸው በተናጠል ያዳቀሉ እንደሆነ የዕፅዋት የአዳቃይ መብት የሚሰጠው በመጀመሪያ ማመልከቻ ለሚኒስቴሩ ላቀረበው ሰው ይሆናል።

12. <u>የዝርያ ስያሜ አጠቃቀም</u>

1. ማንኛውም በኢትዮጵያ ግዛት የሚኖር ሰው የተጠበቀ ዝርያን ዘር ለንግድ የሚሸጥ ከሆነ የተጠበቀውን ዝርያ ስያሜ መጠቀም አለበት፡፡
2. የዝርያ ስያሜው በጽሁፍ ጥቅም ላይ በሚውልበት ወቅት ስያሜው በግልጽ የሚለይና የሚነበብ እንዲሁም ስያሜው ከንግድ ምልክት፣ ከንግድ ስም ወይም ተመሳሳይ ምልክቶች ጋር የሚገናኝ በሆነ ጊዜ በግልጽ ተለይቶ ሊታወቅ የሚችል መሆን አለበት።

13.<u>በዝርያ ስያሜ አጠቃቀም ላይ ስለተጣሉ ገደቦች</u>

1. ለዕፅዋት አዳቃይ የሚሰጠው የተጠበቀ ዝርያ ስያሜ ከተመዘገቡ ተመሳሳይ ከሆኑ ዝርያ ዓይነቶች ጋር አንድ ዓይነት ወይም ከሌላ ዝርያ ስያሜ ጋር የሚያደናግር መሆን የለበትም።፡
2. በተመዘገ በዝርያ ስያሜ የተጠበቀ መብትዝርያውን በተመለከተ የመብት ጥበቃ ጊዜው ያለፈቢሆንም እንኳ የዝርያውን ስያሜ በነጻነትከመጠቀም የሚከለከል አይሆንም፡፡
3. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12 (1) መሠረት የተጠበቀውን ዝርያ ስያሜ እንዲጠቀም ግዴታ የነበረበት ሰው ቀደም ብሎ በተመዘገበ መብት ምክንያት የዝርያውን ስያሜ

እንዳይጠቀምበት የተከለከለ እንደሆነ ሚኒስቴሩ አዳቃዩን ሌላ ስያሜ እንዲያቀርብ መጠየቅ አለበት፡፡ ይህም ቀደም ብለው የተሰጡ የሶስተኛ ወገኖች መብት ላይ ጉዳት ማድረስ አይኖርበትም፡፡

## ክፍል ሦስት

## የዕፅዋት አዳቃይ መብት አስተዳደር

### 14.የሚኒስቴሩ ኃላፊነት

የዕጽዋት ዝርያ አዳቃዮች መብትን አስመልክቶ ሚኒስቴሩ የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፦

1. የዕፅዋት ዝርያ መብትን ለማስጠበቅ የሚቀርቡ ማመልከቻዎችን ይቀበላል፤ መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፤ የዕፅዋት አዳቃይ መብትን በተመለከተ ያስተዳድራል፤
2. የዕፅዋት ዝርያ መብትን የማስተዳደርና የዕጩ ዝርያዎችን ከሌላው የተለየ፣ ወጥነት ያለውናሊቀያየር የማይችል የዝርያ ባህሪ ሙከራያካሂዳል፤
3. በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 4 (4) ማመልከቻቸው መሰረት በቀጥታ ተቀባይነት የሚያገኙ ከሌላው የተለየ፣ ወጥነት ያለው እና ሊቀያየር የማይችል የዝርያ ባህሪ ሙከራ የተሠራባቸው ሀገራትን ስም ዝርዝር ይይዛል፤
4. በዚህ አዋጅ አንቀፅ /20 መሠረት የተጠበቁ ዝርያዎችን መዝገብ ይይዛል፤
5. በዚህ አዋጅ በአንቀጽ /27 መሠረት ሕግ በመተላለፍ የቀረቡ ጥቆማዎችን ያጣራል፤ይመረምራል፤ አግባብ ባለው ህግ ተጠያቂ እንዲሆን ያደረጋል፤

### 15.ስለማመልከቻ አቀራረብ

1. ለአዲስ የዕጽዋት ዝርያ የዕፅዋት አዳቃይ መብት እንዲሰጠው የሚፈልግ ማንኛውም አዳቃይ ማመልከቻውን ለሚኒስቴሩ በጽሑፍ ማቅረብ ይኖርበታል። ማመልከቻውም የሚቀርብበት፣የሚመረመርበት እና ውሳኔ የሚሰጥበት ዝርዝር ሁኔታና ሥርዓት ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡
2. ማንኛውም አመልካች ማመልከቻውን ሲያቀርብ በቃለ መሐላ አስደግፎ እና ደጋፊ መረጃዎችን በማያያዝ የሚከተሉትን ሁኔታዎች በሚገልጽ መልኩ ማቅረብ አለበት፦
   ሀ ዝርያውን ለማበልጸግ ወይም ለማዳቀል በዋናነት የተጠቀመበትን የብዝሀ-ህይወትሀብት ምንጭ፤
   ለ ዝርያውን ለማዳቀል ወይም ለማበልጸግ የተጠቀመበትን ብዝሀ-ህይወት ወይምየአራቢ ዘር በሕጋዊ መንገድ መገኘቱን፣ እንደጉዳዩ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5(3) መሠረት ጥቅምን ለመካፈል የተደረገ ቅድመ ስምምነት መኖሩን፣ እና

ሐ ዝርያው የደህንነተ ሕይወት አዋጅ ቁጥር 655/2001ን የማይፃረርና አመልካቹ ሁሉንም አስፈላጊ ዕውቅና ከሚመለከተው አካል ያገኘና ሌሎች ሕጎች የሚጠይቁትን መስፈርቶች ያሟላ መሆን አለበት።

16.**ቅደመ ውሳኔ እና ጊዜያዊ የመብት ጥበቃ ስለመስጠት**

1. ማመልከቻ በተቀበለ በ14 ቀን ውስጥ በዚህ አዋጅ መሠረትሙሉ ፍተሻ ለማድረግ ማመልከቻው ብቁ መሆኑን በማረጋገጥ ቅድመ ውሳኔ ይሰጣል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተሰጠው ቅድመ ውሳኔ አዎንታዊ ከሆነ ከውሳኔው ቀን ጀምሮ ማመልከቻው በመጨረሻ ተቀባይነት እስኪያገኝ ወይም ውድቅእስከሚሆን ጊዜ ድረስ ጊዜያዊ የዕፅዋት አዳቃይ መብት ይሰጠዋል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተሰጠው ቅድመ ውሳኔ አሉታዊ ከሆነ ማመልከቻው ውድቅ ተደርጎ ለአመልካቹ በተገለጸው የጊዜ ገደብ እንዲያውቀው ይደረጋል፡፡

17. **የተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ ስለማውጣት**

1. ሚኒስቴሩ የዕፅዋት አዳቃይ መብት ለማግኘትየሚቀርብ ማመልከቻን፦

   ሀ የአመልካቹን ማንነት፣ አድራሻ፤

   ለ የአዳቃይ መብት ለማግኘት የተጠየቀበት ዕጽዋት ዘር ዝርዝር መግለጫ፣

   በማካተት ተቃዋሚ ካለ እንዲቀርብ በአመልካቹ ወጪ የተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ ሰፊ ስርጭት ባለው የመገናኛ ዘዴ ለሕዝብ መገለጽ አለበት፡፡
2. ለአመልካቹ የዕፅዋት አዳቃይ መብት ቢሰጥ በህዝብጥቅም ላይ ጉዳት ይደርሳል ወይም ዝርያው የዕፃዋት አዳቃይ መብትን ለማስጠበቅ የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን አያሟላም ወይም አመልካቹ ለማመልከት መብት የለውም ብሎ የሚያምን ማንኛውም ሰው በማስታወቂያው በተገለጸው የጊዜ ገደብ ውስጥ መቃወሚያውን ለሚኒስቴሩ ማቅረብ ይችላል።
3. መቃወሚያው ላይ ምርመራ የሚደረግበትና ውሳኔ የሚሰጥበት ዝርዝር ሁኔታ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

18.**የዕፅዋት አዳቃይ መብት ስለመስጠት**

1. ሚኒስቴሩ የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላታቸውን ሲያረጋግጥ የዕፅዋት አዳቃይመብትይሰጣል፦

   ሀ) በዚህ አዋጅ በአንቀጽ (4)፣ (11) እና (15) የተጠቀሱት መስፈርቶች፣ ብቁነት እና ለማመልከት የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች የተሟሉ እንደሆነ፤

ለ) በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት የዕፅዋት አዳቃይ መብት ለአመልካቹ እንዳይሰጥ የሚያስከለክል ምክንያት የሌለ እንደሆነ፣

ሐ) ዝርያውን አዳቅሎ ለማውጣት ጥቅም የዋለውን የብዝሀ ህይወት አመልካቹ አግባብ ባለው የአርክቦት ሕግ መሠረት ያገኘ መሆኑን ያረጋገጠ እንደሆነ፣

መ) ማመልከቻ በቀረበበት አዲስ የዕፅዋት ዝርያ ላይ የዕፅዋት አዳቃይ መብት ቀደም ሲል ለሌላ ሰው ያልተሰጠ እንደሆነ፣

ሠ) ማመልከቻ በቀረበበት አዲስ የዕፅዋት ዝርያ ላይ ቀደም ሲል የአዳቃይ መብት ማመልከቻ ቀርቦ ውድቅ ያልተደረገ እንደሆነ፣ እና

ረ) የዕፅዋት አዳቃይ መብት ለማግኘት መከፈል ያለበት ክፍያ ሁሉ የተከፈለእንደሆነ፡፡

2. የዕፅዋት አዳቃይ መብት በዕፅዋት አዳቃዮች መብት መዝገብ ውስጥ ከመግባቱና በሚኒስቴሩ አማካኝነት ለሕዝብ ይፋከመደረጉ በፊት ለሌላ ሰው መስጠት፣ ማስተላለፍ ወይም ሌሎች ጉዳዮችን ተግባራዊ ማድረግ አይቻልም፡፡

3. ሚኒስቴሩ የዕፅዋት አዳቃይ መብት ሲሰጥ የዕፅዋት አዳቃይ መብት የተሰጠ መሆኑንሰፊ ሥርጭት ባለው የብዙሀን መገናኛ ዘዴ ለሕዝብ ያሳውቃል።

19. <u>የዝርያ ናሙና ማስቀመጥ</u>

ባለመብቱ የሰጠውን ዝርያ ናሙና በሚኒስቴሩ ዘንድ ማስቀመጥ ይኖርበታል።

20. <u>ዝርያውን ጠብቆ ስለማቆየት</u>

1. ባለመብቱ የዝርያውን ተፈላጊ ባህርያት መብቱ ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜያት ሁሉ የመጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡
2. ሚኒስቴሩ ዝርያው ባህርያቱን ጠብቆ የተያዘ መሆኑን ለማረጋገጥ ባለመብቱ ዝርያውን ወይም ስለዝርያው ሌላ አስፈላጊ መረጃ እንዲያቀርብ መጠየቅ ይችላል።

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>የዕፅዋት አዳቃይ መብት ስለማስተላለፍና ስለመሰረዝ</u>

21. <u>መብትን ስለማስተላለፍ</u>

1. የዕፅዋት አዳቃይ መብት በውል ወይም በሕግለሌሎች ሰዎች ሊተላለፍ ይችላል።
2. በውል የተላለፈ የዕፅዋት አዳቃይ መብት በዕፅዋት አዳቃዮች መብት መዝገብ ላይ ካልተመዘገበ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

22.**መብትን ስለመተው**

1. ማንኛውም የዕፅዋት አዳቃይ መብት የተሰጠው ሰው ለሚኒስቴሩ በማሳወቅ የዕፅዋት አዳቃይመብቱን መተው ይችላል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1 መሠረት ሚኒስቴሩ መብትን የመተው ማስታወቂያ ሲደርሰው ባለመብቱ መብቱን የተወ መሆኑን በዕፅዋት አዳቃዮች መብት መዝገብ ውስጥ መዝግቦ ሰፊ ሥርጭት ባለው ብዙሀን መገናኛ ዘዴ ለሕዝብ ይፋ ማድረግ ይኖርበታል።
3. የዕፅዋት አዳቃይ መብትን በሚመለከት በፍርድ ቤት ክርክር በመካሄድ ላይ ከሆነ ፍርድ ቤቱካልፈቀደ ወይም ተከራካሪዎቹ ወገኖች በፍርድ ቤት ካልተስማሙ በስተቀር ሚኒስቴሩ የመብት መተው ጥያቄውን ተቀብሎ አይመዘግብም፡፡
4. የዕፅዋት አዳቃይ መብቱን በገዛ ፈቃዱ የተወሰው በተጠበቀለት ዝርያ ምክንያት ለደረሰውወይም ለሚደርሰው ጉዳት ተጠያቂ ይሆናል።

23.**መብትን እንዲሰረዝ ስለማመልከት**

1. የዕፅዋት አዳቃይ መብት በመሰጠቱ ምክንያት ጥቅሙ የተነካበት ማንኛውም ሰው ተሰጥቶ የነበረው የዕፅዋት አዳቃይ መብት እንዲሰረዝና እንደሁኔታው እንዲተላለፍለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ (24 እና (25 በተገለጸው መሠረት ለሚኒስቴሩ ማመልከት ይችላል።
2. የዕፅዋት አዳቃይ መብት ለማሰረዝ የቀረበ ማመልከቻ የሚመረመርበት እና ውሳኔ የሚሰጥበት ሂደት ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይገለጻል።

24.**አለአግባብ የተሰጠ መብትን ስለማስተላለፍ**

1. የዕፅዋት አዳቃይ መብት ማግኘት የሚገባኝ እኔ ነኝየሚል ሰው አለግባብ ለሌላ ሰው ተሰጥቶ የነበረየዕፅዋት አዳቃይ መብት ለእሱ እንዲተላለፍለት ለሚኒስቴሩ ማመልከት ይችላል።
2. መብት እንዲዛወር የቀረበውን ማመልከቻና የባለመብቱን ምላሽ ከመረመረ በኋላ ሚኒስቴሩ ለማይገባው ሰው መሰጠቱንና ለአመልካቹ መሰጠት የሚገባው መሆኑን ካረጋገጠ መብቱ በዚሁ መሠረት እንዲዛወር ያደርጋል።

25.**መብትን ስለመሰረዝ**

1. ከሚከተሉት ምክንያቶች አንዱ ሲያጋጥም ሚኒስቴሩ የዕፅዋት አዳቃይ መብትን ይሠርዛል፦

ሀ) ዝርያው አዲስ አለመሆኑ ከተረጋገጠ ወይምመብት ከመሰጠቱ በፊት ቢታወቅ ኖሮ ማመልከቻውን ውድቅ ያስደርግ የነበረ እውነታ ካለ፤

ለ) ባለመብቱ የዕፅዋት አዳቃይ መብትን በሚመለከት መክፈል ያለበትን ክፍያ የመክፈያ ጊዜው የደረሰ ለመሆኑ ማስታወቂያ ከተሰጠው ዕለት አንስቶ በ90 ቀናት ውስጥ ያለበቂ ምክንያት ሳይከፍል የቀረ እንደሆነ፤ ወይም

ሐ) ባለመብቱ የዝርያውን መሠረታዊ ባህሪውን ሳይለውጥ ተንከባክቦ ያልያዘ ከሆነ፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ሚኒስቴሩ የሰጠውን የዕፅዋት አዳቃይ መብትለመሠረዝ ሲወስን፦

ሀ) ለባለመብቱ መብቱ ሊሰረዝ እንደሆነበጽሑፍ ያሳውቃል፤

ለ) ባለመብቱ ተቃውሞ ካለው የጽሑፍ ማስታወቂያ እንደደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ማስረጃ እንዲያቀርብ በጽሑፍ ያሳውቃል፤እና

ሐ) ተቃውሞ ቀርቦ ከሆነ ክርክሩን ሰምቶ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፤ ውሳኔው የአዳቃዩን መብት የሚያሰርዝ ከሆነ ይህንኑ ለህዝብ ያሳውቃል።

3. የዕፅዋት አዳቃይ መብት በተጭበረበረ ወይም በሀሰት ማስረጃ የተገኘ ከሆነ ሚኒስቴሩ መብቱን ሠርዞ የወንጀል ክስ እንዲቀርብበት አግባብ ላለው የፍትሕ አካል በጽሑፍ ያሳውቃል።

## ክፍል አምስት

## የዕፅዋት አዳቃይን መብት ስለመጣስ

### 26. መብት የመጣስ ድርጊት

የተጠበቀ ዝርያን በተመለከተ የባለመብቱን ፈቃድማግኘት የሚገባ ሆኖ ሳለ የባለመብቱን ፈቃድ ሳይገኝ የተፈጸመ ማናቸውም ድርጊት የዕፅዋት አዳቃይ መብትን የመጣስ ድርጊት ይሆናል።

### 27. መብት መጣስን ስለመቃወም

1. የዕጽዋት አዳቃይ መብቴ ተጣሰ የሚል ባለመብት መብቱን የጣሰውን ተጠርጣሪና መብቱ መጣሱን የሚያመለክቱ ድርጊቶችን በመግለጽ ከሌሎች ደጋፊ ማስረጃዎች ጋር በማያያዝ ማመልከቻውን በጽሁፍ ለሚኒስቴሩ ማቅረብ ይችላል።
2. ሚኒስቴሩ የቀረበለትን ማመልከቻ መርምሮ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ አስቀድሞ የተሰጠውመብት ታግዶ ይቆያል።
3. ሚኒስቴሩ ቅሬታው በቀረበለት በ30 የሥራ ቀናት ጊዜ ገደብ ውስጥ መርምሮ ውሳኔ መስጠትአለበት፡፡

4. አቤቱታ የቀረበበት ተከሳሽ፦

   ሀ) የቀረበበት አቤቱታ የዕፅዋት አዳቃይ መብት ጥሰት ክስን የማያስመሰርት መሆኑን፤ ወይም

   ለ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 22 በተጠቀሱት ምክንያቶች መሠረት የዕፅዋት አዳቃይ መብቱ የተተወ መሆኑን፣

   መቃወሚያ አድርጎ ሊያነሳ ይችላል።

5. ሚኒስቴሩ ባደረገው ምርመራ የዕፅዋት አዳቃይመብት ጥሰት መፈጸሙን ያረጋገጠ እንደሆነ ወዲያውኑ መብት የጣሰውን ሰው በማሳወቅ መብት ይጥሳሉ የተባሉትን ድርጊቶች እንዲያቆም ያዛል።

6. ሚኒስቴሩ የቅሬታ ማመልከቻው በቀረበ በ30 ቀናት ውስጥ ለባለመብቱ ውሳኔ ያልሰጠእንደሆነ ባለመብቱ አቤቱታውን ለመደበኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል።

7. ሚኒስቴሩ በሚሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን በዚህ አዋጅ አንቀጽ (30 መሠረት ለመደበኛፍርድ ቤት አቤቱታ ማቅረብ ይችላል።

28.<u>ዳኝነት ስለመጠየቅ</u>

1. ሚኒስቴሩ ወይም ፍርድ ቤት የዕፅዋት አዳቃዮች መብት ተጥሷል ብሎ ከወሰነ ባለመብቱ የሚከተለውን ዳኝነት በመደበኛ ፍርድ ቤት መጠየቅ ይችላል፦

   ሀ) የዕፅዋት አዳቃይ መብት ጥሰቱ እንዲቆም፤

   ለ) ለደረሰው ጉዳትተመጣጣኝ ካሣ እንዲከፈል፤

   ሐ) ከባለመብቱ እውቅና ውጪ የተሸጠው ወይም የተመረተው የተጠበቀ ዝርያ ምርት እንዲያዝ፡፡

2. ተከሳሹ ምንም ዓይነት የጥፋት ድርጊት ያልፈጸመ ሆኖ ሳለ በአንቀጽ 27 (2 መሠረት ከድርጊቱ እንዲቆጠብ ጊዜያዊ እግድ ተጥሎበት የደረሰበት ኪሣራ ካለ ለሚኒስቴሩ የመቃወሚያ ማመልከቻ በማቅረብ እገዳ እንዲጣልበት ያደረገውን አካልካሣ እንዲከፍለው ሊጠይቅ ይችላል።

<u>ክፍል ስድስት</u>

<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

29.<u>የወንጀል ተጠያቂነት</u>

የዕፅዋት አዳቃይን መብት የተላለፈ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ ተጠያቂ ይሆናል።

**30.ለፍርድ ቤት አቤቱታ ስለማቅረብ**

የዕፅዋት አዳቃይ መብት መስጠትን፣ መከልከልን፣ መሰረዝን ወይም መገደብን፣ አስገዳጅ ፈቃድ መስጠትንና መብት መተላለፍን በተመለከተ ሚኒስቴሩ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን ውሳኔው በደረሰው በ60 ቀናት ውስጥ ውሳኔውን በመቃወም ለመደበኛ ፍርድ ቤት አቤቱታ ማቅረብ ይችላል።

**31.ስለክፍያዎች**

"ከዕፅዋት አዳቃይ መብት ጥበቃ በተገናኘ የሚፈፀሙ ክፍያዎች መጠን በዘር አዋጅ ደንብ መሠረት ይፈፀማል።"

**32.ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህንን አዋጅለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል።
2. ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስአንቀጽ (1 መሠረት የወጣ ደንብን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ያወጣል፡፡

**33.የተሻሩ ህጎች**

1. የዕፅዋት አዳቃዮች መብት አዋጅ ቁጥር 481/1998 በዚህ አዋጅ ተሽሯል።
2. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

**34.አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።፡

**አዲስ አበባ የካቲት 22 ቀን 2010ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ፕሬዚዳንት**

## አዋጅ ቁጥር 488/1998 ዓ.ም

## የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ግብርና ሥርዓት አዋጅ

በተፈጥሮ ለሚመረቱ የግብርና ምርቶችና ከእነዚሁ ለሚገኙ የምግብ ሸቀጦች በሸማቾች በኩል ያለው ፍላጐት በዓለም አቀፍ ደረጃ እያደገ በመምጣቱ በሀገራችን በተፈጥሮ ግብርና ሊመረቱ ለሚችሉ ምርቶች አዲስ ገበያ የሚፈጥር በመሆኑ፤

እንደእነዚህ ላሉት ምርቶች ያለው የገበያ ዋጋም ከፍተኛና ለገጠሩ ኅብረተሰብ የተሻለ ዋጋና የኢኮኖሚ ዕድገት ለማስገኘት ጠቀሜታ ያለውና የአመራረት ዘዴውም የመሬትን ለምነት፣ ብዝሃ ሕይወትንና የአካባቢ ደህንነትን ለመጠበቅ አስተዋፅኦ ሊያደርግ የሚችል በመሆኑ፤

እያደገ የመጣውን የምርቱን ተፈላጊነት ለማርካትም የግብርና ምርቶችና የምግብ ሸቀጦች በተፈጥሮ ወይንም ሰው ሰራሽ የሆነ ኬሚካል ጥቅም ላይ ሳይውል የተመረቱ መሆናቸውን የሚገልጹ ወይንም ይህ ዓይነቱ እንድምታ ያላቸው ምልክቶች እየተደረጉባቸው ለሸማቾች በገበያ ውስጥ በመቅረብ ላይ የሚገኙ መሆናቸውን ማሳየቱ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በሀገራችን በመካሄድ ላይ የሚገኘው የግብርና ምርቶች የአመራረት ሥርዓት የተፈጥሮ ግብርና አመራረት ዘዴ የሚጠይቀውን መስፈርት የሚያሟላና በቀላሉ ምርቱን ለዓለም ገበያ ማቅረብ የሚያስችል በመሆኑ፤

ለተፈጥሮ የግብርና ምርቶች ገበያ ያላቸው አገሮችም እንደእነዚህ ያሉትን ምርቶች ለመጠቀም የሚያስችሉ ደንቦችን ያፀደቁና የኢንስፔክሽን ሥርዓቶችንም የዘረጉ በመሆናቸው፤

የተፈጥሮ የአመራረት ዘዴዎችን በመጠቀም የተመረቱ መሆናቸውን የሚገልጹ ምልክቶች የሚደረጉባቸው የግብርና ምርቶችን በሚመለከት የአምራቾችንና የሸማቾችን ጥቅም ለማስጠበቅ መሟላት የሚገባቸውን መሠረታዊ መስፈርቶች በሀገራችንም በግልጽ ማስቀመጥ የሚገባ በመሆኑ፤

ይህም የአመራረት፣ የአደረጃጀትና የአሰረጫጨት ሥርዓት በሌሎች አገሮች የተለመደና ተቀባይነት ያገኘ በመሆኑ በአገራችን እንዲሰራበት በተፈጥሮ ዘዴ የተመረቱ መሆናቸውን የሚጠቅሱ ምልክቶችን የሚጠቀሙ ኦፕሬተሮች የተወሰኑትን መሠረታዊ መስፈርቶች ማሟላታቸውን ለማረጋገጥ ዕውቅና ባላቸው የኢንስፔክሽንና የሰርተፊኬሽን አካላት በመደበኛነት በሚከናወኑ የክትትል ሥርዓቶች ውስጥ ማለፍ የሚገባቸው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55 (1 መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርእስ**

   ይህ አዋጅ “የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ግብርና ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 488/1998” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

   1. “ሚኒስቴር” ማለት የግብርናና የገጠር ልማት ሚኒስቴር ነው፤[3]
   2. “እውቅና” ማለት የኢንስፔክሽንና የሰርተፊኬሽን አካላት ኢንስፔክሽን ለማድረግና የሰርተፊኬሽን አገልግሎት ለመስጠት ብቃት ያላቸው ስለመሆኑ ሚኒስቴሩ በይፋ እውቅና የሚሰጥበት ሥርዓት ነው፤
   3. “የግብርና ምርት” ማለት በጥሬው ወይንም በተዘጋጀ መልኩ ከግብርና ተግባራት የመነጨና ለሰው ፍጆታ ወይንም ለእንስሳት መኖ ለገበያ የሚቀርብ ማናቸውም አይነት ምርት ወይንም ሸቀጥ ነው፤
   4. “የተፈጥሮ ግብርና ምርት” ማለት በአመራረቱ፣ አደረጃጀቱና በአሰረጫጨቱ ሰው ሰራሽ የሆኑ የኬሚካል ግብአቶችን ያልተጠቀመና በጄኔቲክስ ምህንድስና ዘዴ ያልተመረተ ወይንም ያልተዘጋጀ ምርት ነው፣
   5. “እንስሳት” ማለት ለምግብነት ወይንም ለምግብ ዝግጅት የሚውሉ የቀንድ ከብቶችን፣ አሣማዎችን፣ ፍየሎችን፣ በጎችን፣ የጋማ ከብቶችን፣ ዶሮዎችንና ንቦችን የመሳሰሉ የቤት ወይም በለማዳነት የሚረቡ እንስሳትን ያካትታል፤
   6. “የኢንስፔክሽንና ሰርተፊኬሽን ሥርዓቶች” ማለት በሚኒስቴሩ በግልጽ የጸደቁ ወይንም እውቅና የተሰጣቸው ሥርዓቶች ናቸው፤
   7. “ኢንስፔክሽን” ማለት ምርቶች በተፈጥሮ ግብርና ምርት መስፈርት መሠረት መመረታቸውን፣ መዘጋጀታቸውንና መሰራጨታቸውን ማረጋገጥ ነው፣
   8. “ኦዲት” ማለት የተፈጥሮ ግብርና ሥርዓት ሂደቶችና ተያያዥነት ያላቸው ውጤቶች ከሚጠበቁባቸው ግቦች ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ለመወሰን ስልታዊና ገለልተኛ በሆነ አሠራር የሚከናወን የማረጋገጫ ዘዴ ነው፤

[3] በ25)08 (2011 አ. 1097 አንቀጽ 9(6 መሰረት የግብርና ሚኒስቴር ሆኗል፡፡ በአዋጅ ውስጥ በዚሁ መሰረት ተተክቶ ይነበባል፡፡

9. "ሰርተፊኬሽን" ማለት እውቅና የተሰጣቸው የሰርተፊኬሽን አካላት የግብርና ምርቶች የቁጥጥር ዘዴዎች የሚፈለጉ መሥፈርቶችን የሚያሟሉ ስለመሆናቸው በጽሑፍ ወይንም ተመጣጣኝነት ባለው ሌላ መንገድ ማረጋገጫ የሚሰጡበት ሥርዓት ነው፤
10. "የሰርተፊኬሽን አካል" ማለት "በተፈጥሮ የተመረተ" በሚል ስያሜ የሚሸጥ ወይንም ይኸው ምልክት የተደረገበት የግብርና ምርት የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎችና በአዋጁ መሠረት የወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን ተከትሎ የተመረተ፣ የተዘጋጀ፣ እንዲያዝ የተደረገ፣ ለውጭ ገበያ የቀረበ ወይም ከውጭ ወደ አገር የገባ መሆኑን ለማረጋገጥ ኃላፊነት የተሰጠው የራሱ መለያ ምልክት ያለው ነጻ አካል ነው፤
11. "ምልክት" ማለት የኢንስፔክሽንና የሰርተፊኬሽን አካላት የሚታወቁበት በኢትዮጵያ አእምሮአዊ ንብረት ጽሕፈት ቤት ተመዝግቦ ዕውቅና ያለው የሕግ ጥበቃ የሚደረግለት የተፈጥሮ ግብርና ምርቶች መለያ ሆኖ የተፈጥሮ ግብርና ምርትን ለማስተዋወቅ በምርቱ ማሸጊያ ላይ የተጻፈ፣ የታተመ መሆኑን በግራፊክ መልክ የተቀረፀ ወይንም ከምርቱ ጋር አብሮ የሚቀርብ ወይንም ከምርቱ አጠገብ የሚታይ ምልክት ነው፣
12. "ኦፕሬተር" ማለት የተፈጥሮ የግብርና ምርቶችን ለገበያ ለማቅረብ የሚያመርት፣ የሚያዘጋጅ፣ ምልክቶችን የሚያደርግ ወደ ውጭ የሚልክ ወይንም ከውጭ ሀገር የሚያስገባ በኢንስፔክሽንና ሰርተፊኬሽን አካሉ ሰርተፊኬት የተሰጠው ማንኛውም ሰው ነው፣
13. "የተፈጥሮ ግብርና ምርት ካውንስል" ማለት የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር የሚያቋቁመው ሆኖ ከኢንስፔክሽንና ሰርተፊኬሽን አካላትና ኦፕሬተሮች አባል የሆኑበት በሰርቴፊኬሽንና በኢንስፔክሽን ላይ የሚነሱ ጉዳዮችን የሚያይ አካል ነው፡፡
14. "የተፈጥሮ ግብርና ምርቶች መስፈርት መመሪያ" ማለት ሚኒስቴሩ የተፈጥሮ ግብርና ምርቶች እንዴት እንደሚመረቱ፣ እንደሚደራጁና፣ እንደሚሰራጩ የሚያዘጋጀው መስፈርት ነው፣

3. <u>**የተፈፃሚነት ወሰን**</u>

ይህ አዋጅ የተፈጥሮ ግብርና አመራረት ሥርዓትን በመከተል የተመረቱ መሆናቸውን የሚገልጹ ምልክቶች በሚይዙ ወይንም እንዲይዙ የሚደረጉ የግብርና

ምርቶች አመራረት፣ አዘገጃጀት፣ አስተሻሸግ፣ ምልክት አደራረግ፣ ክምችት፣ ማጓጓዝ፣ ግብይት፣ ለውጭ ገበያ መላክና ወደ አገር ውስጥ ማስገባትን በተመለከተ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

4. <u>ዓላማ</u>

የዚህ አዋጅ ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፤

1. የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ግብርና ሥርዓት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለው ሆኖ ዕውቅና እንዲያገኝ ሁኔታዎችን የማመቻቸት፤
2. የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ግብርና ምርቶች ተፈላጊነት ባላቸው ዓለም አቀፍ ገበያዎች ውስጥ ሊገቡ የሚችሉ መሆናቸውን የማረጋገጥ፤
3. አሳሳች የሆኑ ምልክቶችን በመጠቀም በኢትዮጵያ የተፈጥሮ ግብርና ምርቶች ሸማቾች ላይ የማጭበርበር ተግባሮች እንዳይፈጸሙባቸው የመከላከል፤
4. የተፈጥሮ ግብርና ምርቶች በሚመረቱበት፣ በሚከማቹበት፣ በሚጓጓዙበትና ለገበያ በሚቀርቡበት ወቅት ኢንስፔክሽን የተደረገባቸውና በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የተወሰኑ መሥፈርቶችን የሚያሟሉ መሆናቸውን የማረጋገጥ፤ እና
5. የተፈጥሮ ግብርና ምርቶች አመራረት፣ ሰርተፊኬሽንና ምልክት አደራረግ ድንጋጌዎች ለሁሉም ኦፕሬተሮች ወጥነት ያላቸው እንዲሆኑ የማድረግ፡፡

<u>ክፍል ሁለት</u>

<u>የኢንስፔክሽንና ሰርተፊኬሽን ሥርአት</u>

5. <u>ቁጥጥር የሚደረግባቸው አካላት</u>

ማንኛውም የተፈጥሮ ግብርና ኦፕሬተር እውቅና በተሰጠው የኢንስፔክሽንና ሰርተፊኬሽን አካል በመመዝገብ ራሱን ለሀገሪቱ የተፈጥሮ ግብርና ምርት ኢንስፔክሽንና ሰርተፊኬሽን ስርአት ተገዥ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

6. <u>የኢንስፔክሽንና የሰርተፊኬሽን አካላት</u>

ማንኛውም እውቅና የተሰጠው የኢንስፔክሽንና የሰርተፊኬሽን አካል የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፤

1. በዚህ አዋጅና በአዋጁ መሠረት በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የተመለከቱት እንዲሁም አግባብነት ያላቸው ዓለም አቀፍ መመዘኛዎች መሟላታቸውን የማረጋገጥ፣

2. ሚኒስቴሩ እንደ አስፈላጊነቱ ጽሕፈት ቤቱንና መገልገያዎቹን እንዲሁም በሥሩ የተመዘገቡ ኦፕሬተሮችን እንዲመረምር የመፍቀድ፣
3. ሚኒስቴሩ ተግባሩን ለመወጣት አስፈላጊ ናቸው ብሎ የሚያምንባቸውን መረጃዎች የመስጠት፣
4. የኢንስፔክሽንና የሰርተፊኬሽን አገልግሎት የሰጣቸውን ኦፕሬተሮች በሚመለከት አመታዊ ሪፖርት ለሚኒስቴሩ የማቅረብ፡፡

## ክፍል ሶስት

## የእውቅናና የክትትል ሥርዓት

7. **የሚኒስቴሩ ስልጣንና ተግባር**

ሚኒስቴሩ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

1. እውቅና በሚሰጣቸው የኢንስፔክሽንና የሰርተፊኬሽን አካላት ሥራ ላይ የሚውል የተፈጥሮ ግብርና መስፈርት መመሪያ የማውጣት፣
2. ለኢንስፔክሽንና ሠርተፊኬሽን አካላት ዕውቅና የመስጠት፤
3. እውቅና በሚሰጣቸው የኢንስፔክሽንና የሰርተፊኬሽን አካላት ሥራ ላይ የሚውል የኢንስፔክሽንና የሰርተፊኬሽን ሥርዓት የመመስረት፣ ተግባራዊ እንዲሆን የመከታተልና ቁጥጥር የማድረግ፣
4. የተፈጥሮ ግብርናን የሚመለከቱ ተግባራትና ሕግጋት አግባብነት ካላቸው ዓለም አቀፍ ሕግጋት ጋር የተቀናጁና የተጣጣሙ እንዲሆኑ እያጠና የማቅረብ፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ የማድረግ፤
5. የሀገሪቱ የተፈጥሮ ግብርና ሥርዓት ከዓለም አቀፍ አሠራር ጋር የተገናዘበና ተመሳሳይነት ያለው በማድረግ ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ከሆኑ ተቋማትና ማህበራት ጋር ቅንጅት የሚፈጥርበትን ዘዴ የመሻት፤
6. የአገሪቱ የተፈጥሮ ግብርና ምርቶች በዓለም አቀፍ ዋና ዋና ገበያዎች ተቀባይነት እንዲያገኙ ለማድረግ የሚያስችሉ እርምጃዎችን የመውሰድ፤
7. በኢንስፔክሽንና በሰርተፊኬሽን አካል የተሰጠው ሰርተፊኬት በዓለም ደረጃ እንዲታወቅ የፕሮሞሽን ሥራ መሥራት፣ እስኪታወቅ ድረስም ተመሳሳይ ሥራ ከሚያካሂዱ ሌሎች ዓለም አቀፍ አካላት ጋር እንዲሰሩ ማድረግ፣
8. ይህን አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን በሚገባ ለማስፈጸም አስፈላጊ ሆኖ ባገኘው መጠን ሥልጣንና ተግባሩን ለሌሎች መንግሥታዊ መሥሪያ ቤቶች በውክልና የመስጠት፡፡

9. የተፈጥሮ ግብርና ምርት ካውንስል ማቋቋም፣ ተግባሩንና ኃላፊነቱን መወሰን፣
10. ዕውቅና ሲሰጥ መፈጸም ያለባቸውን የአገልግሎት ክፍያዎች በሚኒስትሮች ምክር ቤት ማስወሰንና እንዲሰበሰብ የማድረግ፣
11. ኃላፊነታቸውን በአግባቡ በማይወጡ የኢንስፔክሽንና የሰርተፊኬሽን አካላት ላይ ሊወሰዱ ስለሚችሉ እርምጃዎች መመሪያዎችን የማውጣትና የማስፈጸም፤
12. ለተፈጥሮ ግብርና ሥርዓት መዳበር የሚያግዙ የኤክስቴንሽን አገልግሎትና የሥልጠና ፕሮግራሞች እንዲጠናከሩ የማድረግ፤
13. የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ግብርና ምርት ሥርዓትና የዚህ አዋጅ አፈጻጸም በየጊዜው እንዲገመገም የማድረግ፤

8. <u>የተፈጥሮ ግብርና ምርቶች ሥርዓት ካውንስል</u>

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 9 መሠረት የሚቋቋመው የተፈጥሮ ግብርና ምርትና ሥርዓት ካውንስል ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ሆኖ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፣

1. በሚኒስቴሩ የሚሰየሙ አንድ ሰብሳቢና አንድ ፀሐፊ፣
2. ከኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት አንድ አባል፣
3. ከብዝሃ ሕይወት ኢንስቲትዩት አንድ አባል፣
4. ከአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን[4] አንድ አባል፣
5. ከግሉ የግብርና ልማት ዘርፍ የሚወከል አግባብነት ያለው አንድ አባል፣
6. ከንግዱ ሕብረተሰብ የሚወከል አግባብነት ያለው አንድ አባል፣ እና
7. ከኢንስፔክሽንና ሰርተፊኬሽን አካላት የሚወከል አንድ አባል፣

9. <u>የካውንስሉ ተግባርና ኃላፊነት፣</u>

ካውንስሉ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፣

1. የዕውቅና ጥያቄ የሚያቀርቡ የሰርተፊኬሽንና የኢንስፔክሽን አካላት ቴክኒካዊ የሆኑ ተፈላጊ ሁኔታዎችን የሚያሟሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የመጀመሪያ ደረጃ ምርመራ እንዲሁም ዕውቅና በተሰጣቸው ላይ የክትትል ምርመራ በማከናወን ለሚኒስቴሩ ለአስተያየት ማቅረብ፣
2. የቀጥታ ምርመራ ስለሚደረግበትና የምርመራ ናሙናዎች ስለሚወሰዱበት ሁኔታ የማጥናትና የመወሰን፣
3. የተፈጥሮ ግብርና ኢንስፔክሽንና ሰርተፊኬሽን አካላትን ሪፖርቶች የመገምገም፣

---

[4]በ25)08 (2011 አ. 1097 አንቀጽ 36(17 መሰረት የአካባቢ፣ ደን እና አየር ለውጥ ኮሚሽን ሆኗል፡፡

4. ሥራቸውን በአግባቡ ለማይወጡ የኢንስፔክሽንና የሰርተፊኬሽን አካላት የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ የመስጠት ወይም ለሚኒስቴሩ በማሳወቅ ዕውቅናቸው ለተወሰነ ጊዜ እንዲታገድ የማድረግ፣
5. ሥራቸውን በአግባቡ በማይወጡ የኢንስፔክሽንና የሰርተፊኬሽን አካላት ላይ መውሰድ ስለሚገባው ዕውቅናን የመሰረዝ እርምጃ የውሳኔ ሃሳብ ለሚኒስቴሩ የማቅረብ፣
6. ለተፈጥሮ ግብርና ኦፕሬተሮች የሚያገለግሉ ማንዋሎችንና የአፈጻጸም መከታተያዎችን የማዘጋጀት፣
7. ስላከናወናቸው ዋና ዋና ተግባራትና ስለተገኙ ውጤቶች በየዓመቱ ለሚኒስቴሩ ሪፖርት የማቅረብ፣

10.<u>የካውንስሉ ሰብሳቢ ሥልጣንና ተግባር</u>

ሰብሳቢው ሚኒስቴሩ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት፣

1. የካውንስሉን ሥራ ይመራል፣ ያስተባብራል፣
2. የካውንስሉን ስብሰባዎች ይጠራል፣ በሊቀመንበርነት ይመራል፣
3. የካውንስሉን ውሳኔዎች ለሚኒስቴሩ እያቀረበ በማፀደቅ በሥራ ላይ ያውላል፣

11.<u>የካውንስል ስብሰባ፣</u>

1. ካውንስሉ በሰብሳቢው ጥሪ በማንኛውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፣
2. ካውንስሉ የራሱን የስብሰባና የአሰራር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፣

12.<u>ክፍያዎች</u>

ሚኒስቴሩ በዚህ አዋጅ መሠረት ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሚደረገው ክፍያ ሚኒስትሩ መንግሥትን በማስፈቀድ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፣

13.<u>ዝርዝር የተፈጥሮ ግብርና ድንጋጌዎች</u>

1. የተፈጥሮ ግብርና ምርቶች በእርሻ ላይ የሚኖራቸውን የአመራረት ዘዴ፣ የተባይ መከላከልን፣ የተፈቀዱ ሥነሕይወታዊ መከላከያ ዘዴዎችን፣ ማጓጓዝን፣ ማከማቸትን፣ ማዘጋጀትን፣ ምልክት አደራረግንና ማስተዋወቅን እንዲሁም መሠረታዊ የኢንስፔክሽን መመዘኛዎችን፣ የጥንቃቄ እርምጃዎችንና ለኢንስፔክሽንና ለሠርተፊኬሽን አካላት ዕውቅና አሠጣጥን በሚመለከት መሟላት የሚገባቸው መሥፈርቶች በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጡ ደንቦች ይወሰናሉ።

2. በተፈጥሮ ግብርና የእጽዋት አመራረትንና የእንስሳት እርባታን በተመለከተ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጡ ደንቦች ያልተደነገገ ከሆነ ሚኒስቴሩ በዓለም አቀፍ ደረጃ የታወቁ መመዘኛዎች ተቀባይነትና ተፈጻሚነት እንዲኖራቸው ሊያደርግ ይችላል፡፡

14.<u>የኢትዮጵያ የተፈጥሮ የግብርና ምርቶች ዓርማ</u>

ሚኒስቴሩ፣

1. የኢትዮጵያን የተፈጥሮ ግብርና ምርቶች ዓርማ ይወስናል፤ እንዳስፈሳጊነቱም እንዲለወጥ ያደርጋል፤
2. ዓርማውን ለመጠቀም የሚያስችሉ ሁኔታዎችንና ክፍያዎችን ይወሰናል፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

15.<u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ በሚገባ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

16.<u>ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች</u>

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

17.<u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ መጋቢት 30 ቀን 1998 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ**

**ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

# አዋጅ ቁጥር 660/2002

## የንብ ሀብት ልማትና ጥበቃ አዋጅ

የንብ ሀብት ክምችት በሚገኝባቸው የአገሪቱ ክፍሎች የቤተሰብና የንግድ ንብ ልማት እንዲስፋፋ በማድረግ ሀብቱ ለፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ተገቢ አስተዋጽኦ እንዲኖረው ማድረግ በማስፈለጉ፤

የንብ ውጤት ምርትን ማሳደግና ለምግብ ዋስትናና ለድኅነት ቅነሳ የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ በዘላቂነት ማረጋገጥ በማስፈለጉ፤

የንብ ሀብት ልማቱ አግባብ ባለው መንገድ እንዲካሄድ ለማድረግ የንብ ብዝሀ ሕይወትና የማር ዕፅዋት ዝርያ እንዲጠበቅ ማድረግ በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ 55(1 መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

1. **<u>አጭር ርዕስ</u>**

   ይህ አዋጅ "የንብ ሀብት ልማትና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 660/2002 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **<u>ትርጓሜ</u>**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

   1. "ንብ" ማለት ማርና ለሎች የንብ ውጤቶችን የሚያዘጋጅ በኅብረት መኖር የሚችል አፅቄ ነፍሳት ሲሆን የጣዝማ ንቦችንና ሌሎች የንብ ዝርያዎችን አያካትትም፤
   2. "ኅብረንብ" ማለት በአንድ ቀፎ ወይም በኅብረት በተፈጥሮ የመኖሪያ ቦታ ውስጥ የሚኖሩ ሠራተኛ ንቦችን፣ ንግሥት ንብን፣ አውራ ንቦችንና የንብ እጮችንያካተተ ነው፤
   3. "የንብ ሀብት" ማለት በተፈጥሮና በቀፎ ውስጥ የሚገኙ ኅብረንቦችና የማር ዕፅዋት ክምችት ነው፤
   4. "የንብ ውጤቶች" ማለት ንቦች የሚያዘጋጁዋቸው ማር፣ ሰም፣ ጽጌብናኝ፣ የንብ ወተት፣ የንብ ሙጫ፣ የንብ ዕጭና የንብ መርዝ ናቸው፤
   5. "ቀፎ" ማለት ለኅብረንቦች መኖሪያ፣ መራቢያና ማር ማዘጋጃ ተብሎ የተሰራ ቤት ነው፤
   6. "ማናብ" ማለት ኅብረንቦችን በቀፎ ውስጥ በማኖር ወይም በማርባት ማር፣ ሰምና ሌሎች የንብ ውጤቶችን የማምረት ሥራ ነው፤

7. “አናቢ” ማለት ኅብረንቦችን በቀፎ ውስጥ የሚያረባ ሰው ነው፤
8. “ሰው” ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
9. “የጓሮ ንብ ልማት” ማለት በመኖሪያ ቤት አካባቢ ወይም በጓሮ ኅብረንቦችን በማኖር ወይም በማርባት ምርት የመሰብሰብ ሥራ ነው፤
10. “የመስክ ንብ ልማት” ማለት በጫካ፣ በቁጥቋጦ ወይም በእርሻ ማሳ ውስጥ ወይም አካባቢ ለኅብረንቦች ለኑሮአቸውና ለሥራቸው ምቹ ሁኔታ በመፍጠር የሚካሄድ የማነብ ሥራ ነው፤
11. “የንግድ ንብ ልማት” ማለት መተዳደሪያው ግብርና ባልሆነ ሰው ኅብረንቦች ለልማቱ አመች በሆኑ ቦታዎች በቋሚነት ተቀምጠው ወይም የማዟዟር ማናብ ዘዴ በመጠቀም የሚካሄድ የንብ ውጤቶችን በብዛት የማምረት ሥራ ነው፤
12. “በማዟዟር ማናብ” ማለት የማር ዕፅዋትን የማበብ ወቅት በመከተል ዕፅዋቱ በብዛት ወደሚገኝበት አካባቢ ኅብረንቦችን በማጓጓዝና ለተወሰነ ጊዜ ብቻ በማስቀመጥ ምርት የሚሰበሰብበት የማናብ ዘዴ ነው፤
13. “ማር” ማለት ንቦች ከተለያዩ የማር ዕፅዋት ፈሳሽ የአበባ ወለላን ተፈጥሮአዊ በሆነ መንገድ ቀስመው ወደ ቀፎአቸው በመውሰድና ራሳቸው ከሚያመነጩት የተፈጥሮ ንጥረ ነገር ጋር በማዋሃድ የሚያዘጋጁት የተፈጥሮ ጣፋጭ ምግብ ሲሆን የጣዝማ ንቦች የሚያዘጋጁትንና በሰው ሰራሽ ዘዴ በፋብሪካ ውስጥ የሚዘጋጀውን ማር አያካትትም፤
14. “የማር አደን” ማለት በማር ወቅት ንቦች በተፈጥሮ የሚኖሩበትን ሥፍራ ፈልጎ በማግኘት ያዘጋጁትን ማር የመሰብሰብ ሥራ ነው፤
15. “ማር ማምረት” ማለት በማር ወቅት በቀፎ ውስጥ የሚኖሩ ኅብረንቦች ያዘጋጁት ማር መድረሱን በማረጋገጥ ከቀፎው የማውጣት ተግባር ነው፤
16. “ማናቢያ መሣሪያ” ማለት ማንኛውም ዓይነት ቀፎ፣ የአናቢ ትጥቅ ወይም ለማር፣ ለሰም ወይም ለሌላ የንብ ምርት ማምረቻ የሚያገለግል ማናቸውም ሌላ ዕቃ ነው፣
17. “ዕፅዋትን ማራከብ” ማለት ንቦች ፈሳሽ የአበባ ወለላና ጽጌብናኝ ለመሰብሰብ በማር ዕፅዋት አበቦች ላይ ሲዘዋወሩ የአንዱን ዕፅዋት ወንዴ ዘር ከሌላው ዕፅዋት ሴቴ ዘር ጋር የማገናኘት ወይም የማዳቀል ሂደት ነው፤

18. “የንቦች ዕውደት” ማለት ኅብረንቦች የሚኖሩበትን ቀፎ፣ ዋሻ ወይም ሌላ ዓይነት የመኖሪያ ሥፍራ በከፊል ወይም በሙሉ ለቀው አዲስ ኑሮ ለመመሥረት ወደሌላ ሥፍራ የሚሄዱበት ክንውን ነው፤
19. “የከተማ ማናብ ሥራ” ማለት በከተማ ውስጥ ወይም አካባቢ የሚካሄድ የማናብ ሥራ ነው፤
20. “የመብረሪያ መንገድ” ማለት ንቦች ለሥራ ከቀፎ ሲወጡ ወይም ሲገቡ የሚበሩበት መንገድ ነው፤
21. “የንግሥት ንብ ርቢ” ማለት በተለያዩ የአሠራር ቴክኒኮች ወይም በሰው ሰራሽ ዘዴ ንግሥት ንብ የማራባት ሥራ ነው፤
22. “የንብ ምርምር” ማለት ለሳይንሳዊ ምርምርና ሙከራ ከማናብ ሥራ ጋር የተያያዘ በንቦች ዘር፣ በንቦች ሥነ ሕይወት፣ በሽታ፣ ማኔጅመንትና ሌሎች ሁኔታዎች ላይ የሚደረጉ ጥናታዊ ሥራዎችና ለቤተመዘክር የንብ ዘር የመሰብሰብ ተግባራትን ያካትታል፤
23. “ሚኒስቴር” ማለት የግብርናና የገጠር ልማት ሚኒስቴር ነው፤[5]
24. “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47(1 የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችን ይጨምራል፤
25. በወንድ ፆታ የተገለጸው ማንኛውም አነጋገር ሴትንም ይጨምራል።

3. <u>የንብ ሀብት ልማት</u>

1. ማንኛውም ሰው የራሱ ይዞታ በሆነ ጓሮ ወይም መስክ የንብ ልማት ማካሄድ ይችላል፡፡
2. እንዲያገግሙ በተከለሉ ቦታዎች፣ በማኅበራት ደን፣ በመንግሥት ደን ወይም በዱር እንስሳት ፓርክና ጥበቃ ቦታ ውስጥ የንብ ልማት ለማካሄድ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ይህንኑ ቦታ ለማስተዳደር ሥልጣን ከተሰጠው አካል የተሰጠ የጽሑፍ ፈቃድ መያዝ አለበት፡፡
3. የንግድ ንብ ልማት ወይም የንግድ የንግሥት ንብ ርቢ ለማካሄድ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው ሕግ መሰረት የተሰጠ የንግድ ፈቃድ መያዝ አለበት።

[5] በ25)08 (2011 አ. 1097 አንቀጽ 9(6 መሰረት የግብርና ሚኒስቴር ሆኗል፡፡

4. የንብ ምርምር ለማካሄድ የሚፈልግ ማንኛውም የውጭ አገር ሰው በሚኒስቴሩ የተሰጠ የጽሑፍ ፈቃድ መያዝ አለበት፡፡
5. የከተማ ማናብ ሥራ የሚያካሄድ ማንኛውም ሰው፡-

   ሀ መሠረታዊ የማናብ ሥልጠና የምስክር ወረቀት ያለው ወይም የሥልጠና የምስክር ወረቀት ያላቸውን ግለሰቦች ቀጥሮ የሚያሰራ መሆን፣

   ለኀብረንቦቹን እንስሳትና ሕፃናት በማይደርሱበት ቦታ ማስቀመጥ፣ እና

   ሐ የመብረሪያ መንገዳቸውን ከሦስት ሜትር ያላነሰ ከፍታ ባለው የግንብ፣ የዕፅዋት ወይም የጠቅጣቃ ሽቦ አጥር ማጠር፣

   አለበት፡፡
6. በማዟዟር የማናብ ሥራ የሚያካሄድ ማንኛውም ሰው፡-

   ሀ) ኀብረንቦችን ማስቀመጥ የሚያስችለውን መሬት ለመጠቀም በመሬቱባለይዞታ የተሰጠ የጽሑፍ ፈቃድ መያዝ፣

   ለ)ኀብረንቦቹን በሚያጓጉዝበት ጊዜ ንቦቹ እንዳይወጡና በአካባቢው በመዘዋወር ላይ የሚገኝ ሰው ወይም እንስሳ ላይ አደጋ እንዳያስከትሉ በጠቅጣቃ ሽቦ ወይም አየር ሊያስገባ በሚችል ጨርቅ መሸፈን እንዲሁም በመንገድ ላይ ከማሳረፍ ወይም ሰውና እንስሳት ከሚዘዋወሩበት አካባቢ ከማቆም መቆጠብ፣ እና

   ሐ) በሚጠቀምበት ቀፎ ላይ የራሱ የሆነ ምልክት ማድረግ፣አለበት።
7. ማንኛውም ሰው በዕውደት ላይ የሚገኙ ኀብረንቦችን አጥምዶ መያዝና መጠቀም ይችላል፣ ሆኖም ኀብረንቦቹ ከቀፎው የለቀቁበት አናቢ ወዲያው ተከታትሎ ያረፉበት ቦታ ከደረሰ አጥማጁ የባለቤትነት መብት አይኖረውም።
8. ማንኛውም አናቢ ለዕፅዋት ተራክቦ አገልግሎት ኀብረንቦችን በማከራየት ሲጠቀም ኀብረንቦቹ የተፈለገው ዓላማ በሚቀመጡበት አካባቢ በሚኖሩ ሰዎችና በሚዘዋወሩ እንስሳት ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት።

4. <u>የንብ ሀብት አጠባበቅ</u>

   1. ማንኛውም አናቢ በሥራው ሂደት የንብ ሀብቱን የመንከባከብና የመጠበቅ ኃላፊነት አለበት፡፡
   2. በደን ለበስ አካባቢ፣ በየቋጥኙ ወይም በየዋሻው የሚኖሩ ኀብረንቦች የሚያዘጋጁትን ማር በአደን የሚሰበስብ ማንኛውም ሰው በንቦቹና በተፈጥሮ ሀብቱ ላይ ጉዳት ሳያደርስ መሰብሰብ አለበት።

3. የሀገር ውስጥ የንብ ዝርያዎችን ከተዛማች የንብ በሽታዎች ለመከላከል፡-
   ሀ) ሕይወት ያላቸው የንብ ዝርያዎችን ወይም ያገለገሉ የማናቢያ ወይም የማቀነባበሪያ መሣሪያዎችን ወይም ቁሳቁሶችን ወደአገር ውስጥ ማስገባት የተከለከለ ነው፤
   ለ) ጥሬ ማር፣ ሰም ወይም ማንኛውም የንብ ውጤት ወደ አገር ውስጥ በሚገባበት ጊዜ በላኪው አገር አግባብ ያለው አካል የተፈረመ የጤናማነት የምስክር ወረቀት ተያይዞ መቅረብ አለበት፤
   ሐ) ወደ አገር ውስጥ በትራንዚትነት የሚገባ ያገለገለ የማናቢያ መሣሪያ ታሽጎ የሚያልፍ መሆኑ የታወቀ ካልሆነ በስተቀር የጤናማነት ምርመራ የምስክር ወረቀት ሊጠየቅበት ወይም የጤናማነት ምርመራ ሊደረግበት ይችላል።
4. ፈቃድ ያለው የንግሥት ንብ ርቢ የሚያካሂድ ሰው ካልሆነ በስተቀር ለልማትም ሆነ ለምርምር ሥራ ሕይወት ያላቸውን ንቦች ወደውጭ ለመላክ አይፈቀድም።
5. ማንኛውም የሰብል ጥበቃ የሚያካሂድ ሰው በፀረ-ሰብል ተባይ መከላከያ ኬሚካሎች ያለአግባብ አጠቃቀም ምክንያት ንቦች እንዳይመረዙና እንዳያልቁ ተገቢውን ጥንቃቄ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡
6. ማንኛውም ሰው ሆነ ብሎም ሆነ በቸልተኝነት በኅብረንቦች ላይ እሳት ቃጠሎ እንዲነሳ ማድረግ የለበትም።

5. <u>**የማናቢያ መሣሪያዎች አያያዝ**</u>

የማናቢያ መሣሪያዎችና ተዛማጅ ቁሳቁሶች ከኬሚካሎች ነፃ በሆነ መጋዘን የተከማቹ መሆን አለባቸው።

6. <u>**የመረጃ ልውውጥ**</u>

1. ጉዳዩ የሚመለከታቸው የክልል አካላት የንብ ሀብት መረጃዎችን በመሰብሰብና በማጠናቀር ለሚኒስቴሩ ይልካሉ።
2. ሚኒስቴሩ ከተለያዩ ምንጮች ስለንብ ሀብት የሚሰበስባቸውን መረጃዎችና የምርምር ውጤቶች በመገምገመና በማዘጋጀት ለክልሎችና ለሌሎች ተጠቃሚዎች እንዲደርሱ ያደርጋል፡፡

7. <u>**የንብ ሀብት ልማት ተቆጣጣሪ**</u>

1. በሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ባለው የክልል አካል የተመደበ የንብ ሀብት ልማት ተቆጣጣሪ፡-

ሀ) የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችና በአዋጁ መሠረት የወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን መከበራቸውን ለማረጋገጥ ወደ ማንኛውም አናቢ የሥራ ቦታ በሥራ ሰዓት በመግባት የማናቢያ መሣሪያዎችንና የአስተናነብ ሁኔታን የማየትና የመገምገም፣

ለ) ማንኛውም አናቢ ከሥራው ጋር የተያያዙ መረጃዎችን እንዲሰጠው የመጠየቅ፣ እና

ሐ) የቁጥጥር ተግባሩን ሲያከናውን ያገኛቸውን ይህን አዋጅ በሚተላለፉ ሰዎች ላይ ክስ ለመመስረት የሚያስችሉ መረጃዎችን ለሚመለከተው አካል የማስተላለፍ፣

ሥልጣን እና ተግባር ይኖረዋል።

2. ማንኛውም አናቢ ለንብ ሀብት ልማት ተቆጣጣሪ መረጃ በመስጠትና ለቁጥጥር ሥራው ክንውን ሁኔታዎችን በማመቻቸት የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

8. <u>ቅጣት</u>

በወንጀል ሕጉ የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር፦

1. ማንም ሰው ሥልጣን ከተሰጠው አካል የጽሑፍ ፈቃድ ሳይዝ እንዲያገግሙ በተከለሉ ቦታዎች፣ በማኅበራት ደን፣ በመንግሥት ደን ወይም በዱር እንስሳት ፓርክና ጥብቅ ቦታ በንግድ ልማት ላይ የተሰማራ ወይም የንግድ ፈቃድ ሳይዝ የንግድ ልማት ወይም የንግድ ንግሥት ንብ ርቢ ያካሄደ ከብር 2,000ሺ እስከ 5,000ሺ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ወይም አንድ ዓመት በሚሆን እሥራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል።

2. የንብ ሀብት ልማትና ጥበቃ መረጃዎችን በአግባቡ የያዘና ሲጠየቅም ለመስጠት ፈቃደኛ ያልሆነ ኅብረንቦችን በጠቅጣቃ ሽቦ ወይም በካኪ ጨርቅ ሳይሸፍን ያጓጓዘና የሰውና እንስሳት ዝውውር በሚበዛበት ቦታ ያቆመ ማንም ሰው ከብር 1,500 እስከ ብር 3,000 በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ወይም ከስድስት ወር እስከ አንድ ዓመት በሚሆን እሥራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል።

3. የንብ ሀብት ልማት ለማካሄድ ሲል በተፈጥሮ ሀብት ላይ ጉዳት የሚያደርስ፣ ወይም በንቦች ላይ የንብ በሽታ ለማስተላለፍ ምክንያት የሚሆን ወይም አላግባብ በሆነ የፀረ-ሰብል ተባይ መከላከያ ኬሚካል አጠቃቀም ምክንያት በንቦች እና በንብ ውጤቶች ላይ ጉዳት የሚያደርስ ወይም በማር አደን ወቅት በኅብረንቦች ላይ የእሳት ቃጠሎ የሚያደርስ ከብር 5,000 እስከ ብር 10,000 በሚደርስ

የገንዘብ መቀጮ ወይም ከሦስት ዓመት እስከ ሰባት ዓመት በሚሆን እሥራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል።

4. የንብ ሀብት ልማት ተቆጣጣሪው ሥራውን እንዳይሰራ ከአሰናከለ ከአስፈራራ ወይም ጉዳት ከአደረሰ ከብር 2,000 እስከ 5,000 ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ወይም ከሁለት እስከአምስት ዓመት በሚሆን እሥራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል።
5. ማንም የተከለሰ ወይም የተበከለ ወይም የተመረዘ የንብ ውጤት ሲያቀነባብርና ሲያጓጉዝ ከተገኘ ወይም ለኅብረተሰቡ ከሸጠ ወይም ከሰጠ ከብር 10,000 እስከ 15,000 ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ወይም ከአምስት እስከ አሥር ዓመት በሚሆን እሥራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል።
6. ማንም ሰው ያለፈቃድ ወይም ከተሰጠው ፈቃድ ተቃራኒ በሆነ ሁኔታ ሕይወት ያለው የንብ ዝርያ፣ የንብ ዘር፣ ያገለገሉ የማናቢያ መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች ከውጭ ከአስገባ፤ ከአገር ደግሞ የንብ ዘሮችን ወደ ውጭ አገር ከአስወጣ ወይም ለማስወጣት ከሞከረ ከብር 15,000 እስከ 20,000 ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ወይም ከአሥር እስከ አሥራ አምስት ዓመት በሚሆን እሥራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል።
7. ማንም ሰው ይኸንን አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን ከተላለፈ ወይም አፈጻጸማቸውን ያደናቀፈ እስከ አምስት ዓመት በሚሆን እሥራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል።

9. <u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል።
2. ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1 መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሚኒስቴሩ ሊያወጣ ይችላል።

10. <u>ተፈጻሚነት ለለማይኖራቸው ሕጎች</u>

ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሰራር በዚህ አዋጅ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

11.<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ታህሣሥ 15 ቀን 2002 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## ደንብ ቁጥር 372/2008

## የንብ ሀብት ልማትና ጥበቃ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2005 አንቀጽ 5 እና በንብ ሀብት ልማትና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 660/2002 አንቀጽ 9 መሠረት ይህን ደንብ አዉጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የንብ ሀብት ልማትና ጥበቃ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 372/2008" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ ፡-

   1. "አዋጅ" ማለት የንብ ሀብት ልማትና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 660/2002 ነዉ፤
   2. በአዋጁ አንቀጽ 2 የተሰጠ ትርጓሜ ተፈጻሚ ይሆናል፤
   3. "ነቁር"ማለት የስድስት ማዕዘን ቅርፅ ያለው የማር እንጀራ አንድ ክፍል ሲሆን የሠራተኛ ንብ የንግሥት ንብና የአውራ ንብ ዕጭ የሚያድግበት እንቁራ ወይም ፈሳሽ የአበባ ወለላ፣ ማርና ጽጌብናኝ የሚከማችበት ቦታ ነው፤
   4. "እንቁራ" ማለት በተለምዶ የማር እንጀራ የሚባለው የብዙ ነቁር ስብስብ ነው፤
   5. "የንግድ ንብ አናቢ" ማለት የንብ ዉጤቶችን ለማምረት ሲባል 500 እና ከዚያ በላይ የሆኑ ጎብረንቦች የማናብ ሥራ የሚያከናውን ሰው ነው፤
   6. "የንብ በሽታ" ማለት የንብ እጮችን የንብ ሙሽሬዎችን እና ጉልምስ ንቦችን ጤንነት የሚጎዳ ወይም የሚያጠቃ እንደ ኖሴማ፣ ቾክ ቡሩድ ቫርዋ፣ የመሳለለ ነው፤
   7. "የንብ ጠላት" ማለት የንብ እጮችን የንብ ሙሽሬዎችን፣ ጉልምስ ንቦችን እና የንብ ውጤትን የሚያጠቃ እንደ ጉንዳን፣ ሰም-በል ትል፣ ቀፎ ደፊ፣ ትንሹ የቀፎ ውስጥ ጥንዚዛ የመሳሰለ እንስሳ ወይም ነፍሳት ነው፤

8. “ኦርጋኒክ ማር” ማለት በኦርጋኒክ ማር አመራረት መሥፈርቶች መሠረት የተመረተ ማር ነው፡
9. “የማር ዕፅዋት” ማለት ለንቦች መኖ የሚሆን ፈሳሽ የአበባ ወለላ ወይም ጽጌብናኝ ወይም ሁለቱንም የሚያመርቱ ተክሎች ናቸው፤
10. “ጽጌብናኝ” ማለት ንቦች የንብ ዕጭ ለመመገብ ከማር ዕፅዋት አበባ የሚሰበስቡት ወንዴ ዘር ነው፤
11. “የተከለሰ” ማለት ከሰው-ሠራሽ ስኳር ፣ ሞላሰስ ፣ፓራፊን እና ከሌሎች ባዕድ ነገሮች ጋር የተቀየጠ ወይም የተደባለቀ የንብ ውጤት ነው፤
12. “ሰም” ማለት ንቦች በቀፎ ውስጥም ሆነ ለመኖሪያነት በሚመርጡበት ቦታ ለእጭ መራቢያ ለጽጌብናኝ ማከማቻና ለማር ማጠራቀሚያ የሚሆናቸውን ነቁር ወይም እንቆራ ለመገንባት የሚያመነጩት ንጥረ ነገር ሲሆን ከሌሎች እንስሳት፣ ከዕፅዋት፣ ከማዕድናትና በሰው ሠራሽ ዘዴ የሚዘጋጀውን ሰም አይጨምርም፤
13. “የንብ ዘር ማዳቀል” ማለት ምርታማ ያልሆነ የንብ ዘርን የተመረጠ ባህሪያት ካሉት የንብ ዘር ጋር በማዳቀል ማሻሻል ነው፡
14. “የማቀነባበሪያና ማሸጊያ ድርጅት” ማለት የንብ ውጤት የሚቀነባበርበትና የሚታሸግበት ድርጅት ነው፤
15. “ጥራት መቆጣጠሪያ ቤተሙከራ” ማለት የንብ ዉጤት ጥራት ምርመራ የሚደረግበት ክፍል ነዉ፣
16. “የንብ ዉጤት ገበያ” ማለት ማር፣ ሰም፣ ሮያል ጄሊ፣ የንብ እጭ፣የንብ መርዝ፣ ፕሮፖሊስ እና ጽጌብናኝ ሳይጣራ፣ ተጣርቶ ወይም ተጨማሪ እሴት ተደርጎበት በችርቻሮ፣ በጅምላ ወይም በጨረታ የሚሸጥበት ሥፍራ ወይም መደብር ነዉ፤
17. “ምዝገባ” ማለት የአናቢዎችን ስም፣ አድራሻ፣የማርቢያ ሥፍራ እና ሌሎች ተፈላጊ መረጃዎችን መመዝገብ ነዉ፤
18. “ኢንስፔክሽን” ማለት የደምበኛን መብትና የንግድ ሥነ-ምግባር ለመጠበቅ የንብ ዉጤቶች፣ የማናቢያ መሣሪያ እና ቁሳቁስ ጥራት፣ ደረጃ፣ ቅንብር፣ ክምችት፣ አጓጓዝ ግብይት ሂደት ላይ የሚደረግ የአሰሳና ቁጥጥር ሥርዓት ነዉ፤
19. “የምዘገባ ሰርተፊኬት” ማለት አናቢዎች ለመመዝገብ ያቀረቡት ማመልከቻ ተቀባይነት ሲያገኝ በተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ የሚሰጥ ሰርቲፊኬት ነዉ፤

20.“የደህንነት ሠርተፊኬት” ማለት የንብ ዉጤቶች ለምግብነት ለመዋል ጤናማ መሆናቸዉን እና ሰምና ፕሮፖሊስ ደግሞ ከአደገኛ ኬሚካል ቅሪቶች ነጻ መሆናቸዉን ወይም በባዕድ ነገሮች አለመከለሱ ተረጋግጦ ከተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ የሚሰጥ ማስረጃ ነዉ፤

21.“ተቆጣጣሪ ባለስልጣን” ማለት የእንስሳትና ዓሣ ሀብት ሚኒስቴር ወይም በክልል መንግስት ሥልጣን የተሰጠዉ አካል ነዉ፤

22.“ተቆጣጣሪ” ማለት በተቆጣጣሪዉ ባለሥልጣን የተሰየመ የንብ ሀብት ልማት ኢንስፔክሽን ባለሙያ ነዉ፤

23.“ማቀነባበር” ማለት ማርን ከሰም የመለየት ሂደት ነዉ፤

24.“ሚኒስቴር” ማለት የእንስሳትና ዓሣ ሀብት ሚኒስቴር ነዉ፤

25.“ማንኛዉም በወንድ ጾታ የተገለጸዉ የሴትንም ይጨምራል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የንብ ሀብት ልማትና ጥበቃ

## ንዑስ ክፍል አንድ

## የንብ ሀብት ልማት

3. ምዝገባ

1. አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ጎብረንቦችን በዘመናዊ መንገድ ልማት የሚ ያካሂድ ማንኛውም አናቢ ለዚህ ደንብ አፈጻጸም ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ በተወሰነው ጊዜ ገደብ ውስጥ በተቆጣጣሪው ባለሥልጣን ዘንድ መመዝገብ አለበት።
2. ማንኛውም አናቢ ከተቆጣጣሪዉ ባለሥልጣኑ የተሰጠውን የምዝገባ ምስክር ወረቀት በማናቢያ ስፍራው ለንብ ሀብት ልማት ተቆጣጣሪ በሚታይበት ግልጽ ሥፍራ ማስቀመጥ አለበት፡
3. ማንኛውም አናቢ በባለቤትነት ለያዘው ጎብረንብ ቁጥር መስጠት ወይም የተለየ ምልክት ማድረግ አለበት።
4. ቁጥር ወይም መለያ ምልክት የሌለው ጎብረንብ እንደሕገወጥ ተቆጥሮ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት አግባብ ያለው እርምጃ ይወስድበታል።

4. **የማናቢያ ስፍራ አወሳሰን**

   1. የጓሮ ወይም የከተማ ማናብ ሥራ ጓሮው ወይም የከተማ ቦታው ሊሸከመው በሚችለው ኀብረንቦች ቁጥርና በአካባቢው በሚገኘው የንቦች መኖ ግኝት የሚወሰን ይሆናል፡፡
   2. የጓሮ ወይም የከተማ ማናብ ሥራ የሚያካሂድ ማንኛውም አናቢ ኀብረንቦቹ በቤት እንስሳት ላይ የመናደፍ አደጋ እንዳያደርሱ ስለልማቱ በወጣው መመሪያ መሠረት ማከናወን አለበት፡፡
   3. በአዋጁ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ (2 መሠረት የጽሁፍ ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም አናቢ በአካባቢው የተፈጥሮ ሀብት ላይ ጉዳት ሳያደርስ የመጠቀም ግዴታ የሚጥል ውል በቅድሚያ ቦታዉን ለማስተዳደር ሥልጣን ከተሰጠው አካል ጋር መግባባት አለበት፡፡
   4. የአዋጁ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ (6 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም አናቢ ከንብ በሽታና ከንብ ጠላት ነጻ የሆኑ ኀብረንቦችን በማዟዟር ማናብ ይችላል።

5. **የህብረንቦች ዕውደትና ባለቤትነት**

   1. የአዋጁ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ (7 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በዕውደት ላይ የሚገኙ ኀብረንቦች ከቀፎ ወይም ከነበረበት መኖሪያ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ተከፍሎ የወጣ ሊሆን ስለሚችል ማንኛውም ሰው ባለቤት ነኝ ማለት አይችልም።
   2. ማንኛውም ሰው በዕውደት ላይ ያለን ህብረንብ ከአረፈበት ቦታ በሚይዝበት ወቅት በአካባቢው ሰውና በእንስሳት ደህንነት ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡
   3. የአዋጁ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ (7 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም አናቢ ወይም ጣውላ ነክ ባልሆኑ የደን ውጤቶች ተጠቃሚ ለመሆን ደን የሚያለማ ሰው በራሱ ይዞታ ላይ የማጥመጃ ቀፎዎችን በመስቀል ወይም በማንጠልጠል በዕውደት ላይ የሚገኙ ኀብረንቦችን ማጥመድና መያዝ ይችላል፡፡
   4. በመንግሥትና ማህበራት ደኖች፣ በፓርኮች ወይም በዱር እንስሳት ጥብቅ ቦታዎች በዕውደት ላይ የሚገኙ ህብረንቦችን ቀፎ በመስቀል ወይም በማንጠልጠል ማጥመድ ወይም መያዝ የሚቻለው ቦታውን ለማስተዳደር ሥልጣን ከተሰጠው አካል ፈቃድ ሲገኝ ብቻ ነው።

6. **የንግድ የንግሥት ንብ ርቢ**

1. የንግድ የንግሥት ንብ ርቢ ለማካሄድ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ከተቆጣጣሪው ባለሥልጣን ፈቃድ ማግኘት አለበት።
2. በንግሥት ንብ ርቢ ንግድ ሥራ የተሰማራ ማንኛ ሰዉ በተፈላጊ ባሕሪያቸዉ ተመርጠው በተቆጣጣሪዉ አካል እዉቅና ከተሰጣቸዉ ጎብረንቦች የረቡ የንግሥት ንቦች የሆኑትን ብቻ በሽያጭ ወይም በስጦታ ለሌሎች ማቅረብ አለበት፡፡
3. በንግሥት ንብ ርቢ ሥራ የተሰማራ ማንኛዉም ሰው የርቢ እና የግብይት መረጃን የመያዝና በተቆጣጣሪዉ አካል ሲጠየቅ የማሳየት ግዴታ አለበት፡፡
4. ለንግሥት ንብ ርቢ የሚውል ጣቢያ ወይም ያለበት መስፈርት ለዚህ ደንብ አፈጻጸም ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

7. <u>የንብ ዉጤቶች እና ማናቢያ መሣሪያዎች ንግድ</u>

1. ለገበያ የሚቀርብ ማንኛዉም የንብ ዉጤት በሚመለከተዉ አካል ተፈትሾ ከጥራትና ደህንነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ጋር ተያይዞ መቅረብ ይኖርበታል።
2. ለውጪ ገበያ የሚቀርቡ የንብ ውጤቶች፣ የማናቢያ መሣሪያዎች እና ቁሳቁሶች የንግድ ፈቃድ የሚሰጠው በንግድ ሚኒስቴር ይሆናል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2 የተጠቀሱ ምርቶችን ለማምረት የብቃት ማረጋገጫ እና ለምርቶቹ የጤና፣ የጥራት እና ደህንነት ምስክር ወረቀት የሚሰጠው በፌዴራል ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል።
4. በአገር ውስጥ ለሚካሄድ የንብ ውጤቶች፣ የማናቢያ መሣሪያዎች እና ቁሳቁሶች የንግድ ፈቃድ የሚሰጠው በሚመለከተው የክልል ወይም የከተማ አስተዳደር አካል ይሆናል።
5. የሚመለከተው የክልል ወይም የከተማ አስተዳደር አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4 የተመለከቱ ምርቶችን ለማምረት የብቃት ማረጋገጫ እና ለምርቶቹ የጤና፣ የጥራት እና የደህንነት ምስክር ወረቀት ይሰጣል።
6. የተካለሰ ወይም የተቀየጠ የንብ ውጤት ለሽያጭ ማቅረብ ወይም ማስተላለፍ የተከለከለ ነው።
7. አዳዲስ የማናቢያ መሣሪያዎችን ወይም ቁሳቁሶችን ከውጭ አገር የሚያስገባ ወይም በአገር ውስጥ የሚያመርት ማንኛውም ሰው ደረጃዉንና ጥራቱን ጠብቆ ማስገባት ወይም ማምረት አለበት።

8. በኢንስፔክሽን ወቅት የተገኘ ማንኛውም ደረጃውን ያልጠበቀ የማናቢያ መሣሪያ አገልግሎት እንዳይሰጥ ይደረጋል።

## 8. በንብ፣ በማናቢያ መሣሪዎች እና በንብ ዉጤቶች ላይ ምርምር ስለማካሄድ

1. የንብ ዘር ማሻሻል፣ከንብ ውጤቶች፣ ከማር ዕፅዋት እና ከንብ ማኔጅመንት ጋር የተያያዘ ምርምር ማካሄድ የሚፈልግ ማንኛውም የውጭ አገር ዜጋ ከተቆጣጣሪው ባለሥልጣን የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት።
2. ማንኛውንም ዓይነት የንብ ዘር የማዳቀል ሥራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው ሚኒስቴሩ ባወጣው መመሪያ መሠረት ማከናወን አለበት።
3. በማዳቀል የተገኘ የንብ ዘር መመዝገብ የሚችለው ሚኒስቴሩ ባወጣው መመሪያ መሠረት ሲፀድቅ ነዉ፡፡

## 9. የንብ ዉጤቶች አቀነባበር፣ አስተሻሸግ፣ አያያዝ፣ ምልክት አደራረግና አጓጓዝ

1. በአርሶ አደር ወይም በከፊል አርብቶአደር ደረጃ የሚካሄድ ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም የንብ ውጤቶችን የማቀነባበርና የማሸግ ሥራ የሚከናወነው በተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሁንታ በተሰጠው ሕንጻ ውስጥ መሆን አለበት።
2. የንብ ውጤት ማቀነባበሪያና ማሸጊያ ሥፍራዎች ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ከማንኛውም የውጤቱን ጥራትንና ደህንነት ከሚበክሉ ነገሮች የራቀ መሆን አለበት፡፡
3. ማንኛውም ለንብ ውጤቶች ማቀነባበሪያና ማሸጊያ የሚውሉ ቁሳቁሶች የውጤቱ ጥራትና ደህንነት የማያጎድፉ መሆን አለባቸው።
4. ለገበያ የሚቀርቡ የንብ ውጤቶች አቀነባበር፣ አስተሻሸግና አያያዝ በሚመለከተው ተቆጣጣሪ አካል በማንኛውም ጊዜ ቁጥጥር ሊደረግበት ይችላል።
5. ተቀነባብሮና ታሽጎ ለገበያ የሚቀርብ የንብ ውጤት ስለውጤቱ የሚገልጽ የተሟላ መረጃ በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋ ተጽፎ በመያዣው ላይ የተለጠፈበት መሆን አለበት።
6. የንብ ውጤቶች ምርት የሚከማቸውና የሚጓጓዘው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ ባወጣው መመሪያ መሰረት ሆኖ የኃይጅን መስፈርቶችን ማሟላት አለበት፡፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## የንብ ሀብትና የማር እጽዋት አጠባበቅና እና የአናቢ ግዴታ

### 10.የንብ ሀብት ጥበቃ

የአዋጁ አንቀጽ 4 እና 5 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ፡-

1. የማናቢያ መሣሪያዎችና ቁሳቁስ ማከማቻ ክፍል ንቦችን ሊበክሉ ከሚችሉ ነገሮች የራቀና የፀዳ መሆን አለበት፤
2. በቀፎ ኢንስፔክሽን ወቅት የንቦች ጉዳትና ዕልቂት እንዳይከሰት ጥንቃቄ መደረግ አለበት፡፡
3. የአገር ውስጥ የንብ ዘሮች እንዳይመናመኑና እንዳይጠፉ የዘቦታ እና ኢዘቦታ ጥበቃ መደረግ አለበት፤
4. በአገሪቱ የሚገኝ የንብ ዘር ዘረመል እንዳይበረዝና እንዳይሸረሸር ጥበቃ መደረግ አለበት፤
5. ከተቆጣጣሪዉ ባለሥልጣን ፈቃድ ሳይሰጥ ኀብረንብን ከቦታ ወደ ቦታ ለልማት ወይም ለንግድ ማዘዋወር የተከለከለ ነው፤
6. ማንኛውም ዓይነት የተቀነባበረ የንብ መኖ ወደ አገር ውስጥ በሚገባበት ወቅት ከላኪው አገር አግባብ ያለው አካል የተፈረመና የተሰጠ የጤናማነት የምስክር ወረቀት ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፤
7. ማንኛውም የንብ ውጤት፣ የተቀነባበረ የንብ መኖ፣ የመገልገያ መሣሪያዎችና ቁሳቁስ፣ የማር እንቆራ እና ከልማቱ ጋር ተያያዥነት ያለው ሌላ ነገር ወደ አገር ውስጥ በሚገባበት ወቅት ከኤርፖርት ወይም ከደረቅ ወደብ ከመውጣቱ በፊት መፈተሽ እና ደረጃውን የጠበቀ መሆኑ መረጋገጥ አለበት፤ ደረጃውን የማያሟላ ከሆነ በአስመጪው ወጪ ወደመጣበት አገር እንዲመለስ ወይም እንዲወገድ መደረግ አለበት፤
8. በዕውደት ላይ የተያዘ አዲስ ኀብረንብ ከንብ በሽታና ከንብ ጠላት ነፃ መሆኑ እስኪረጋገጥ ድረስ ሌሎች ኀብረንቦች ወደአለበት የማርቢያ ሥፍራ መግባት የለበትም፤
9. ለንቦች በመኖነት የሚሰጥ ማር ከንብ በሽታና ከንብ ጠላት ነፃ መሆኑ መረጋገጥ አለበት፤
10. በሚድን የንብ በሽታና የንብ ጠላት የተበከለ ኀብረንብ እስኪድን ድረስ ከጤናማ ኀብረንብ ተለይቶ በጊዜያዊ የማርቢያ ሥፍራ እንዲቆይ መደረግ ያለበት ሲሆን፣

በማይድን የንብ በሽታና የንብ ጠላት የተበከለ ኀብረንብ ከሆነ ከነቀፎው መወገድ አለበት።

11.<u>የማር ዕጽዋት ጥበቃ</u>

1. በደን፣ በተከለሉ ተራሮች፣ በፓርኮች፣ በጥብቅ ቦታዎች፣ በአፈርና ውኃ ጥበቃ ኀዳጎች፣ በእርሻ ማሳዎችና በመኖሪያ ቤት ዙሪያ እና አካባቢ የሚገኝ የማር ዕፅዋት እንዳይቆረጥ መጠበቅ አለበት፡፡
2. የማር ዕፅዋት ዝርያ ወደ አገር ውስጥ በሚገባበት ጊዜ በላኪዉ አገር አግባብ ያለዉ አካል የተፈረመና የተሰጠ የጤናማነት የምስክር ወረቀት ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዐስ አንቀጽ (2 መሠረት ወደ አገር ውስጥ የገባ የማር ዕፅዋት ለተጠቃሚዎች ከመሠራጨቱ በፊት ተላምዶ፣ ምርታማነቱና ከዕፅዋት በሽታ ነጻ መሆኑ በተቆጣጣሪው ባለሥልጣን መረጋገጥ አለበት፡፡

12.<u>የአናቢ ግዴታዎች</u>

1. የከተማ ማናብ ሥራ የሚያካሂድ ማንኛውም ሰው ኀብረንብን ከማህበራዊ ተቋማት፣ ህዝብ ከሚበዛባቸው አካባቢዎች እና ከፍተኛ ድምጽ ከሚያወጡ ፋብሪካዎች አካባቢ ከ 50 ሜትር በላይ ወይም ኬሚካል ከሚያቦኑ ወይም ከሚያተኑ ፋብሪካዎች ከሁለት ኪሎ ሜትር በላይ አርቆ ማስቀመጥ አለበት።
2. የመስክ ንብ ልማት ሥራ የሚያካሂድ ማንኛውም ሰው የንብ ልማት የሚካሄድባቸውን ሥፍራዎች ከአቧራ፣ ከጭስ፣ ከኬሚካል ብክለት እና ከመጥፎ ጠረን የፀዱ እንዲሆኑ ማድረግ አለበት፤ እንዲሁም ኀብረንቦችን ለጐርፍ አደጋ በተጋለጡ በወንዝ ዳር እና ለበሽታና ተባይ በሚያጋልጡ ረግረጋማ ቦታዎች ማስቀመጥ የለበትም፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥና የምዝገብ አያያዝ</u>

13.<u>የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት</u>

1. የንግድ ንብ ልማት ለማካሄድያ የንግሥት ንብ ርቢ ጣቢያ ወይም ማዕከል፣ የማናቢያ መሣሪያዎችና ቁሳቁስ ማምረቻ ድርጅት፣ የንብ ዉጤቶች ማቀነባበሪያና ማሸጊያ ድርጅት ወይም የንብ ዉጤቶች መሸጫ ድርጅት ለማቋቋም የሚፈልግ ማንኛውም ሰዉ ከተቆጣጣሪው ባለሥልጣን የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ፀንቶ የሚቆየው ለአንድ ዓመት ይሆናል።
3. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ከማብቃቱ በፊት ባሉት ሁለት ወራት ውስጥ መታደስ አለበት፡፡
4. የንግድ ንብ ልማት ወይም የንግድ የንግስት ንብ ርቢ የሚያካሂድ ማንኛውም ሰው የሚጠቀምበትን የኅብረንብ ማስቀመጫ ሥፍራ ወይም የአመራረት መንገድ ለዉጥ በሚያደርገበት ጊዜ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን ማሳደስ አለበት፡፡
5. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እና የንግድ ፈቃድ ሳይዙ የንግድ ንብ ልማት ማካሄድ፣ የማናቢ.ያ መሣሪያዎችና ቁሳቁስ ማምረቻ ድርጅት፣ ማቀነባበሪያና ማሸጊያ ድርጅት ወይም የንብ ውጤቶች መሸጫ ተቋም ማቋቋም የተከለከለ ነው፡፡
6. ማንኛውም የንብ ውጤቶች ማቀነባበሪያና ማሸጊያ ድርጅት የውስጥ ፅዳቱን በማያሟላና በዉጤቶቹ ላይ የጥራት ጉድለት በሚያስከትል ሁኔታ ሲሠራከተገኘ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲሆን ጉድለቱን እንዲያስተካክል የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ተገቢ ከሆነ የጊዜ ገደብ ጋር ይሰጠዋል።
7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6 መሠረት የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ደርሶት በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጉድለቱን ያላስተካከለ ወይም ለሁለተኛ ጊዜ ንጽሕናን አጓድሎ የተገኘ የማንኛውም ሰው የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ጉድለቱ እስኪስተካከል ድረስ ይታገዳል፡፡
8. በዚህ ደንብ መሠረት ግዴታውንና ኃላፊነቱን የማይወጣ የማንኛውም የንግድ ንብ አልሚ፣ የማናቢ.ያ መሣሪያዎችና ቁሳቁስ አምራች፣ የንብ ውጤቶች አቀናባሪና አሻጊ ወይም የንብ ውጤቶች መሸጫ መደብር የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰረዛል።
9. በማንኛውም መንገድ ሥራውን ያቆመ የንግድ ንብ ልማት ድርጅት፣ የማናቢ.ያ መሣሪያዎችና ቁሳቁስ ማምረቻ ድርጅት፣ የማቀነባበሪያና ማሸጊያ ድርጅት ወይም የንብ ውጤቶች መሸጫ መደብር ሥራውን እንደገና የሚጀምረው ተቆጣጣሪው ባለሥልጣን መርምሮ የዚህን ደንብ መስፈርት ያሟላ መሆኑን ሲያረጋግጥና ሲፈቅድ ብቻ ነው።

10.የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት መሟላት ያለበት ዝርዝር መስፈርት ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

14.<u>**የመዝገብ አያያዝ**</u>

1. የንብ ውጤቶች ማቀነባበሪያና ማሸጊያ ድርጅት እና የመሸጫ መደብር ምርት ማሰባሰብ፣ማቀነባበር፣ ማጓጓዝ እና ማሠራጨት የሚመለከቱ ሰነዶች እንዲሁም የማናቢያ መሣሪያዎችና ቁሳቁስ ማምረቻ ድርጅት የምርት ግብይት ሰነዶች ኃላፊነት በተሰጠው ሰው ከተፈረሙ ቦኋላ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን እንዲያያቸው ፋይል ተደርገው መቀመጥ አለባቸው፡፡
2. በማናቢያ መሣሪያዎችና ቁሳቁስ ማምረቻ ድርጅትና በንብ ውጤቶች ምርት ማቀነባበሪያና ማሸጊያ ድርጅት የምርት ተቆጣጣሪ ባለሙያ የሚሰራበት መመሪያና አሠራር በገበያ ላይ ከወጡ ምርቶች ውስጥ ችግር ቢከሰት ያለፈውን ሂደት በፍጥነትና በተሟላ ሁኔታ በማገናዘብ በአዲሱ ምርት ላይ ችግር እንዳይከሰት ለማድረግ የሚያስችል የምርት መዝገብ መያዝ አለበት።
3. የንብ ውጤቶች የማቀነባበሪያ ፣ የማሸጊያና የማናቢያ መሣሪያዎች ማምረቻና ከውጭ አስገቢ ድርጅቶች ቁጥጥር የተደረገባቸውን የጽሑፍ ሰነዶች ለኢንስፔክሽን ዓላማ ለሁለት ዓመት ጠብቀው ማቆየት አለባቸው።

<u>**ክፍል አራት**</u>

<u>**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**</u>

15.<u>**የተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ሥልጣንና ተግባር**</u>

ተቆጣጣሪው ባለሥልጣን የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. የንብ ሀብት ልማት፣ ጥበቃ፣ የንብና የንብ ውጤቶች ንግድ፣ የማናቢያ፣ የማቀነባበሪያ እና የማሸጊያ መሣሪያዎችን ንግድና አጠቃቀም በተመለከተ አግባብ ካላቸው ተቋማት ጋር በመተባበር የመቆጣጠር፤
2. የንብ ውጤቶችን፣ የማናቢያ መሣሪያዎችን፣ የንብ ውጤቶች የማቀነባበሪያ እና የማሸጊያ መሣሪያዎችን ደህንነት እና ብቃትን አግባብ ካላቸው ተቋማት ጋር በመተባበር የመቆጣጠር፤
3. በዚህ ደንብ መሠረት በንግድ ንብ ልማት የተሰማሩ የአናቢዎችን እና የንብ ቀፎ ቁጥር ወይም መለያ ምልክትን፣ በንብ ውጤቶች ማቀነባበሪያና ማሸጊያ ንግድ የተሰማሩ ሰዎችን፣ በንብ ውጤቶችና በማናቢያ መሣሪያዎች ንግድ

የተሰማሩ ሰዎችን እና ኦርጋኒክ ማር የሚመረትባቸውን አካባቢዎች በመለየት መዝግቦ የመያዝ፤

4. በማዟዟር ለሚካሄድ የኅብረንቦች ንግድ፣ ለማራከብ አገልግሎት እና ለማር ልማት በመንግስት ይዞታ ሥር በሚገኝ መሬት ላይ የሚያስቀምጡበት ሥፍራ የመፍቀድ፤
5. ይህንን ደንብ ተከትሎ በሚወጣ መመሪያ መሠረት በዕውደት ላይ የሚገኙ ኅብረንቦች ባለቤትነትን እና የማጥመድ ፈቃድን የማስፈጸም፤
6. ለንግድ ንብ ልማት ተስማሚ ሊሆኑ የሚችሉ አካባቢዎችን በመለየት ባለሀብቶች ለንግድ ንብ ልማት እንዲጠቀሙበት ፈቃድ የመስጠት፤
7. ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመሆን በዚህ ደንብ በአንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ (1 መሠረት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የመስጠት እና ይህንኑ የመቆጣጠር፤
8. የንብና የተጓዳኝሥራዎች ምርምር እንዲካሄድ ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን የመፍቀድ፤ የምርምር ዉጤቶችን መዝግቦ በመያዝ ዕውቅና የመስጠት፤
9. ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመሆን ከውጭ አገር የሚገቡ የንብ ውጤቶች፣ የማናቢያ መሣሪያዎች፣ የማቀነባበሪያና የማሸጊያ መሣሪያዎች ጥራትና ደህንነት የመቆጣጠር፤
10. ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመሆን ሕይወት ያለው የንብ ዘርና ዝርያ፣ ያገለገሉ የማናቢያ፣ የማምረቻና የማቀነባበሪያ መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ የመቆጣጠር፤
11. ከሚመለከታቸዉ ተቋማት ጋር በመሆን የንብ ውጤቶች ማቀነባበሪያና ማሸጊያ ድርጅቶችን አሠራር የመቆጣጠር፤
12. በማይድን የንብ በሽታና ጠላት ምክንያት የሚወገዱ ኅብረንቦችንና በዚህ በሽታና ጠላት የተበከሉ ቀፎዎችን፣ የጥራትና ደህንነት መስፈርት የማያሟሉ የንብ ውጤቶችን እና ደረጃን የማያሟሉ የማናቢያ መሣሪያና ቁሳቁሶችን የማስወገድ፤
13. በንብ ሀብት ልማትና ጥበቃ መስክ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ብቃት ያላቸው ተቆጣጣሪዎችን የመመደብ፡፡

16.<u>የንብ ሀብት ልማት ተቆጣጣሪ ስልጣንና ተግባር</u>

የአዋጁ አንቀጽ 7 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የንብ ሀብት ልማት ተቆጣጣሪ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል ፦

1. የንግድ ንብ አናቢዎች ቀፎ ቁጥር ወይም መለያ ምልክትን፣ የንብ ውጤቶች ማቀነባበሪያና ማሸጊያ ድርጅቶችን፣ በንብ ውጤቶችና በማናቢያ መሣሪያዎች ንግድ የተሰማሩ ሰዎችን እንዲሁም ኦርጋኒክ ማር የሚመረትባቸዉን አካባቢዎች የመመዝገብና የመቆጣጠር፤
2. ኅብረንቦችን በማዟዟር ለሚያናቡ አናቢዎች ኅብረንቦቹን እንዲያስቀምጡ የተፈቀደላቸው ሥፍራ በሥርዓት መያዙን መቆጣጠር፤
3. በከተሞችና በከተሞች ዙሪያ በማናብ ሥራ ላይ የተሠማሩ አናቢዎች በዚህ ደንብ መሠረት ልማቱን ማካሄዳቸውን የመቆጣጠር፤
4. የንግድ ንብ ልማት በሚካሄድባቸው አካባቢዎች የተፈጥሮ ሀብቱ በሥርዓት መያዙንና አገልግሎት መስጠቱን የመቆጣጠር፤
5. በዚህ ደንብ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ (1 መሠረት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተሰጣቸው ሰዎች መሥፈርቶችን አሟልተዉ እየሰሩ መሆናቸዉን የመቆጣጠር፤
6. ከሚመለከታቸዉ ተቋማት ጋር በመሆን በአገር ዉስጥ የተመረጡና ለገበያ የሚቀርቡ የንግስት ንብ፣የንብ ዉጤቶች፣የማናቢያ መሣሪያዎች፣የንብ ዉጤቶች የማቀናበሪያ እና የማሸጊያ መሣሪያዎች የጥራት፣ደህንነትና የብቃት ደረጃ ይህንን ደንብ ተከትሎ በሚወጣዉ መመሪያ መሠረት ተሟልቶ መመዝገቡን የመቆጣጠርና የማረጋገጥ፤
7. ሕይወት ያለው የንብ ዘርና ዝርያ፣ያገለገሉ የማናቢያ ወይም የማቀነባበሪያ መሣሪያዎች እና ቁሳቁሶች አገር ውስጥ እንዳይገቡ በጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያዎች በመገኘት ሥልጣንና ተግባሩን የሚገልጽ መታወቂያ በማሳየት ቁጥጥር የማካሄድ፤
8. በአገር ውስጥ የተመረቱና ለገበያ የሚቀርቡ የንግሥት ንብ፣ የንብ ውጤቶች፣ የማናቢያ ወይም የማቀነባበሪያ መሣሪያዎች ወይም ቁሳቁስ ወይም ከውጭ አገር የሚገቡ የማናቢያ ወይም የማቀነባበሪያ መሣሪያዎች ወይም ቁሳቁስ የጥራት፣ ደህንነትና ብቃት ደረጃ ያልተሟላ መሆኑን ሲያምን መያዝና ሥልጣን ላለው አካል ሪፖርት በማድረግ እርምጃ እንዲወስድ የማድረግ፤

9. ለሰዎች ምግብነት ለማዋል ጤናማ መሆኑ የሚያጠራጥር የንብ ውጤትን በቁጥጥር ሥር በማዋል ናሙና ወስዶ በጥራት መቆጣጠሪያ ቤተሙከራ የማስመርመር፤
10. በማይድን የንብ በሽታና በንብ ጠላት የተበከሉ ጎብረንቦችንና ቀፎዎችን፣ የጥራት፣ ደህንነት እና የደረጃ መስፈርት የማያሟሉ የንብ ውጤቶችንና የማናቢያ ወይም የማቀነባበሪያ መሣሪያዎች ወይም ቁሳቁስ እንዲወገዱ ለተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ በሪፖርት የማሳወቅ፤
11. የቁጥጥር ሥራዎችን ሪፖርት ለተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ በጽሑፍ የማቅረብ።

17. **<u>አለመግባባትን ስለመፍታት</u>**

1. የዚህን ደንብ አፈጻጸም በሚመለከት የሚከሰት ማንኛውም አለመግባባት ተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ ባቋቋመውና ባለጉዳዩ የሚወክለዉ ሰዉ በሚሳተፍበት የቴክኒክ ኮሚቴ ተመርምሮ ውሣኔ ይሰጥበታል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1 መሠረት የሚሰጥ አስተዳደራዊ ውሳኔ ባለጉዳዩ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ክስ አቅርቦ ፍትሕ ማግኘትን አያግድም።
3. የቴክኒክ ኮሚቴ የሚቋቋምበት ሥርዓት፣ የአባላት ብዛት እና ስብጥር እንዲሁም ዝርዝር አሠራር ሂደት ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

18. **<u>ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸዉ ህጎች</u>**

ይህን ደንብ የሚቃረን ማናቸውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

19. **<u>መመሪያ የማዉጣት ስልጣን</u>**

ሚኒስቴሩ ይህንን ደንብ ለማስፈጸም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

20. **<u>ደንቡ የሚፈጸምበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ጥር 25 ቀን 2008 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስትር**

## አዋጅ ቁጥር 674/2002 ዓ.ም

## የፀረ-ተባይ ምዝገባና ቁጥጥር አዋጅ

ፀረ-ተባይ ለተለያዩ አገልግሎቶች ማለትም ለሰብል ምርት፣ ለእንስሳት ልማት፣ ለሕዝብ ጤና ጥበቃ አገልግሎት መጠቀም በቀጣይነት እያደገ በመምጣቱ፤

ፀረ-ተባይ በሰው ልጆች፣ በእንስሳት፣ በዕፅዋትና በአካባቢ ላይ የሚያሳድሩትን ጎጂ ተፅዕኖ መቀነስ የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

ፀረ-ተባይን የማምረት፣ የማዘጋጀት፣ ወደአገር ውስጥ የማስገባት፣ ወደ ውጭ አገር የመላክ፣ የማጓጓዝ፣ የማከማቸት፣ የማከፋፈል፣ የመሸጥ፣ የመጠቀም፣ የማስወገድና ከነዚሁ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ሌሎች ተግባራት ለመቆጣጠር የሚያስችል የተሟላ ሕግ ማውጣት በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 55(1 መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የፀረ-ተባይ ምዝገባና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 674/2002" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

   1. "ዋነኛ ንጥረ ነገር" ማለት ፀረ-ተባይ ዝግጅት ውስጥ የሚገኝ ሥነ ሕይወታዊ ተጽዕኖ ያለው ክፍል ነው፤
   2. "የተከለሰ ፀረ-ተባይ" ማለት፡-

      ሀ) ማንኛውም ይዘቱ በሙሉ ወይም በከፊል የተጓደለ ወይም እንዲወጣ የተደረገ፣

      ለ) የተበላሸ መሆኑ ወይም ዝቅተኛነቱ በማንኛውም መልክ የተደበቀ፣

      ሐ) በውስጡ የሚገኝ ማንኛውም ነገር ሙሉ ለሙሉ ወይም በከፊል በሌላ ነገር የተተካ፣

መ) መጠኑን ወይም ክብደቱን ለመጨመር ሲባል ሌላ ነገር የተጨመረበት ወይም የተቀላቀለበት ወይም አብሮ የታሸገበት ጥራቱን ወይም ጥንካሬውን የሚቀንስ ወይም ከትክክለኛ ይዘቱ የተሻለ እንዲመስል የተደረገ፣

ሠ) ማንኛውም ይዘቱ በመለያ ምልክት ከተጠቀሰው ወይም በዚህ አዋጅ ውስጥ ከተፈቀደው መጠን በላይ ሆኖ የተገኘ፣ ወይም

ረ) ተፈጥሮው፣ ይዘቱ ወይም ጥራቱ ጉዳት እንዲያስከትል ተደርጎ የተለወጠ፣ ፀረ-ተባይ ነው፤

3. "ማስተዋወቅ" ማለት ፀረ-ተባይ ሽያጭን ወይም ጥቅምን ለማስፋፋት በህትመት፣ በኤሌክትሮኒክ ሚዲያ፣ በምልክት፣ በስጦታ፣ በሰርቶ ማሳያ ወይም በቃል ማስተዋወቅ ነው፤
4. "የታገደ ፀረ-ተባይ" ማለት ተመዝግቦ በጥቅም ላይ እንዳይውል በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ የተከለከለ ወይም በጥቅም ላይ እንዲውል ለማስመዝገብ ወይም ለተመጣጣኝ እርምጃ የቀረበለት ጥያቄ ከጤና ወይም ከአካባቢ ጉዳት አንፃር ተቀባይነት ያላገኘ ፀረ-ተባይ ነው፤
5. "የባዝል ኮንቬንሽን" ማለት የአደገኛ ቆሻሻ ድንበር ዘለል እንቅስቃሴንና ማስወገድን አስመልክቶ እ.ኤ.አ. ማርች 1989 የተፈረመው የባዝል ስምምነት ነው፤
6. "ሥነ ሕይወታዊ የመከላከያ አካል" ማለት ተባይን ለመከላከል የሚችል የተፈጥሮ ጠላት፣ ተቀናቃኝ፣ ተፎካካሪ ወይም ሌላ አካል ሲሆን ሥነ ህይወታዊ ኬሚካሎችንና ደቂቀ ዘአካላትን ይጨምራል፤
7. "ሥነ ሕይወታዊ ፀረ-ተባይ" ማለት በአመዛኙ እንደ ኬሚካል ፀረ-ተባይ ተዘጋጅቶ ጥቅም ላይ የሚውል ሥነ ሕይወታዊ የመከላከያ አካል ነው፤
8. "የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት" ማለት አንድ ሰው በምስክር ወረቀቱ ላይ በሚገለፀው መልኩ ፀረ-ተባይን ለመያዝ የሚፈለጉ መስፈርቶችን ያሟላ መሆኑን በማረጋገጥ የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው፤
9. "መያዣ" ማለት ማንኛውም ፀረ-ተባይ የተያዘበት፣ የተቀመጠበት፣ የታሸገበት ወይም የተሸፈነበት ሲሆን ከፀረ-ተባዩ ጋር ንክኪ ያለውን ማንኛውንም ነገር ይጨምራል፤

10. “ማስወገድ” ማለት የፀረ-ተባይ ቆሻሻን፣ ጥቅም ላይ የዋሉ መያዣዎችን ወይም የተበከሉ ቁሳቁሶችን ዳግም ለመጠቀም፣ ለማጥፋት ወይም ለመለየት የሚደረግ ማንኛውም ተግባር ነው፤
11. “ሥርጭት” ማለት ፀረ-ተባዮች ለአገር ውስጥ ወይም ለዓለም ገበያ በንግድ ሥርዓቱ የሚቀርቡበት ሂደት ነው፤
12. “ዝግጅት” ማለት ፀረ-ተባይ ለታለመለት ዓላማ ጠቃሚና ፍቱን እንዲሆን ወይም ገዢዎች በሚገዙት መልክ እንዲሆን የተደረገ የተለያዩ ነገሮች ድብልቅ ነው፤
13. “አደጋ” ማለት በሰው ወይም በእንስሳት ጤና፣ በአካባቢ ወይም በንብረት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ወይም ጉዳት ሊያስከትል የሚችል የአንድ ነገር አካል ወይም ሁኔታ ተፈጥሯዊ ባህሪ ነው፤
14. “መለያ” ማለት የተፃፈ፣ የታተመ ወይም በምስል የተቀረፀና በፀረ-ተባይ ቀጥተኛ መያዣና በቀጥተኛ መያዣዎቹ ውጫዊ መያዣ ወይም መጠቅለያ ላይ የተደረገ ወይም ከነዚሁ ጋር የተያያዘ መግለጫ ነው፤
15. “መፈብረክ” ማለት ፀረ-ተባይን ማሰናዳት፣ ማዋሀድ፣ ማዘጋጀት፣ መቀላቀል ወይም ለማሰራጨት ወይም በጥቅም ላይ ለማዋል እንዲችል ማድረግ ነው፤
16. “ሚኒስቴር” ወይም “ሚኒስትር” ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤[6]
17. “ጥቅም ላይ ሊውል የማይችል ፀረ-ተባይ” ማለት፡-
    ሀ) በባዝል፣ በስቶክሆልም ወይም በሮተርዳም ስምምነት መሠረት ከአካባቢና ከጤና አንፃር ጥቅም ላይ እንዳይውል የታገደ ወይም በጥብቅ ገደብ የተጣለበት፣
    ለ) በአያያዝ ጉድለት ወይም ለረዥም ጊዜ ከመከማቸት የተነሳ ይዘቱ የተበላሸ በመሆኑ ምክንያት በመለያው መሠረት ጥቅም ላይ ሊውል ወይም በቀላሉ ዳግም ሊዘጋጅና ጥቅም ላይ ሊውል የማይችል፣ ወይም
    ሐ) ለታለመለት ዓላማ መጠቀም የማይቻል፣ ፀረ-ተባይ ነው፤
18. “ማሸጊያ” ማለት የፀረ-ተባይ ምርት በጅምላ ወይም በችርቻሮ ሥርጭት ለተጠቃሚዎች የሚደርስበት መያዣውና የመከላከያ መጠቅለያው በአንድነት ነው፤

[6] በ25)08 (2011 አ. 1097 አንቀጽ 9(6 መሰረት የግብርና ሚኒስቴር ሆኗል፡፡

19. “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

20. “ፀረ-ተባይ” ማለት፡-

ሀ) የሰውና የእንስሳት በሽታ አስተላላፊዎችን ጨምሮ ማንኛውንም ተባይ፣

ለ) በማምረት፣ በማከማቸት፣ በማጓጓዝ ወይም በግብይት ሂደት በምግብ፣ በግብርና ምርቶች፣ በእንጨትና የእንጨት ውጤቶች ወይም የእንስሳት መኖ ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ወይም የሚያውኩ ተፈላጊ ያልሆኑ የዕፅዋት ወይም የእንስሳት ዝርያዎችን፣ ወይም

ሐ) በእንስሳት ውጫዊ አካላት የሚከሰቱ ነፍሳትንና ሌሎች ተባዮችን፣

ለመከላከል፣ ለማጥፋትና ለመቆጣጠር የሚያገለግል ማናቸውም ንጥረ ነገር ወይም የማናቸውም ንጥረ ነገሮች ድብልቅ ወይም ህይወት ያለው ነገር ሲሆን፣ የዕፅዋት ዕድገትን ለመቆጣጠር፣ ቅጠሎችን ለማርገፍ፣ ለማድረቅ ወይም ፍሬዎችን ለማሳሳት ወይም ያለጊዜያቸው እንዳይረግፉ ለመከላከል የሚውሉ ንጥረ ነገሮችን እና ከምርት ስብሰባ በፊትና በኋላ ጥራት እንዳይቀንሱ ለመከላከል የሚያገለግሉትን ንጥረ ነገሮች ያካትታል፤

21. “የፀረ-ተባይ ነጋዴ” ማለት ማንኛውም በፀረ-ተባይ ዝግጅት፣ ማምረት፣ ማሸግ፣ ዳግም ማሸግ፣ መለያ ምልክት ማድረግ፣ ወደ አገር ውስጥ ማስገባት፣ ወደ ውጭ አገር መላክ፣ ማከማቸት፣ መሸጥ፣ ማሰራጨት፣ ማጓጓዝ ወይም የፀረ-ተባይ አገልግሎት መስጠት ሥራዎች ላይ የተሰማራ ሰው ነው፤

22. “የቅድሚያ እሽታ አሰራር” ማለት በሮተርዳም ስምምነት ውስጥ በዓለም አቀፍ የንግድ ልውውጥ የተወሰኑ አደገኛ ኬሚካሎችና ፀረ-ተባዮችን በተመለከተ ባስቀመጠው መሠረት የታገዱ ወይም በጥብቅ ገደብ የተጣለባቸው ኬሚካሎችና በጣም አደገኛ የሆኑ ፀረ-ተባይ ዝግጅቶች የመረጃ ልውውጥና የአያያዝ ማሳወቅ አሰራር ነው፤

23. “ጥራት” ማለት በጥራትና ደረጃዎች ባለሥልጣን የወጡ ብሔራዊ ደረጃዎችን ወይም በኢትዮጵያ ተቀባይነት ያገኙ ዓለም አቀፍ ደረጃዎችን የመሟላት ሁኔታ ነው፤

24. “የሮተርዳም ስምምነት” ማለት በተወሰኑ አደገኛ ኬሚካሎችና ፀረ-ተባዮች የዓለምአቀፍ ንግድን አስመልክቶ እ.ኤ.አ. ሴፐቴምበር 1998 በሮተርዳም የተፈረመው የቅድሚያ እሽታ አሠራር ስምምነት ነው፤

25. “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47(1) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችን ይጨምራል፤
26. “አግባብ ያለው አካል” ማለት የጤና ጥበቃ ሚኒስቴርንና የምግብ፣ መድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አስፈጻሚ አካልን፣ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴርን፣ የሰራተኛና ማሕበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴርን፣ የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣንን፣ እንዲሁም የግብርና ዘርፍን፣ የሕዝብ ጤናን፣ የአካባቢ ጥበቃ እና ንግድና ኢንዱስትሪን በክልል ደረጃ የመምራት ኃላፊነት የተሰጣቸውን አካላት ያጠቃልላል፤
27. “ዳግም ማሸግ” ማለት ፀረ-ተባይን ለቀጣይ ሽያጭ እንዲመች ለማድረግ ከአንድ የንግድ እሽግ ወደ ሌላ አብዛኛውን ጊዜ አነስ ወዳለ እሽግ የሚገለበጥበትና እንደገና የሚታሸግበት የተፈቀደ አሰራር ነው፤
28. “የአጠቃቀም ገደብ የተጣለበት ፀረ-ተባይ” ማለት በሚኒስቴሩ ውሳኔ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሌላቸው ሰዎች እንዳይጠቀሙበት የተደረገና ሚኒስቴሩ በሚያዘጋጀው የአጠቃቀም ገደብ የተጣለባቸው ፀረ-ተባዮች ዝርዝር ውስጥ የተካተተ ፀረ-ተባይ ነው፤
29. “የሽያጭ ሥፍራ” ማለት ፀረ-ተባዮች የሚሸጡበት ሥፍራ ወይም ተቋም ነው፤
30. “መሸጥ” ማለት ፀረ-ተባዮችን ለሽያጭ ማቅረብ ወይም ለመሸጥ በማሰብ መያዝ ነው፤
31. “ጥብቅ ገደብ የተጣለበት ፀረ-ተባይ” ማለት አጠቃቀሙ በአብዛኛው የተከለከለ ሆኖ ለተወሰኑ አገልግሎቶች ብቻ ምዝገባ ተሰጥቶት ጥቅም ላይ የሚውል ፀረ ተባይ ነው፤
32. “የስቶክሆልም ስምምነት” ማለት የማይመክኑ ኦርጋኒክ በካዮችን የሚመለከት እ.ኤ.አ. ሜይ 2001 በስቶክሆልም የተፈረመው ስምምነት ነው፤
33. “ማከማቸት” ማለት ለሽያጭ ወይም ከሽያጭ ውጭ በቀጥታ ሥራ ላይ ለማዋል ተብሎ ፀረ ተባይ ማከማቸት ነው፤
34. “የንግድ ስም” ማለት አንድ ፀረ-ተባይ መለያ ተሰጥቶትና ተመዝግቦ ምዝገባ በተሰጠው ሰው ብቻ የማስፋፋት ሥራ የሚካሄድበትንና ከሌሎች አንድ ዓይነት ዋነኛ ንጥረ ነገር ከያዙ ፀረ-ተባዮች ተለይቶ የሚታወቅበት ስም ነው፤
35. በወንድ ጾታ የተገለፀው ማንኛውም አገላለጽ ሴትንም ይጨምራል።

## ክፍል ሁለት

## የፀረ-ተባይ ምዝገባ

3. **የምዝገባ አስፈላጊነት**

   1. ማንኛውም ፀረ-ተባይ ፍቱንነቱ፣ ደሕንነቱና ጥራቱ በመስክ ወይም በላቦራቶሪ ሳይሞከርና በሚኒስቴሩ ሳይረጋገጥ መመዝገብ አይችልም። ማንኛውም ሰው ያልተመዘገበ ፀረ-ተባይ ወይም ፀረ-ተባዩ የተመዘገበባቸውን ሁኔታዎች በሚፃረር
   2. መንገድ ማዘጋጀት፣ መፈብረክ፣ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት፣ ማሸግ፣ እንደገና ማሸግ፣ መሸጥ፣ ማሰራጨት፣ ማከማቸት ወይም መጠቀም አይችልም።
   3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም ሚኒስቴሩ ያልተመዘገበ ፀረ-ተባይን ለማከፋፈል ሳይሆን ለምርምር ወይም ለሙከራ ብቻ የሚውል መጠኑን በመወሰን ወደ አገር ውስጥ እንዲገባ ሊፈቅድ ይችላል፡፡
   4. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ድንጋጌ ቢኖርም ሚኒስቴሩ በአስገዳጅ ሁኔታዎች ምክንያት ያልተመዘገቡ ፀረተባዮች ወደ ሃገር ውስጥ እንዲገቡና አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ሊፈቅድ ይችላል።
   5. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (3) የተመለከቱት አስገዳጅ ሁኔታዎች ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ መመሪያ የሚወሰኑ ይሆናል፡፡

4. **የምዝገባ ማመልከቻ**

   1. ፀረ-ተባይ ለማስመዝገብ ለሚኒስቴሩ የሚቀርብ ማመልከቻ ለዚሁ ተግባር በተዘጋጀው ፎርም መሠረት ሆኖ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ የተዘረዘሩትን አስፈላጊ መረጃዎች መያዝ አለበት፡፡
   2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የቀረቡት መረጃዎች ያልተሟሉ ከሆነ ሚኒስቴሩ ይህንኑ ለአመልካቹ በጽሁፍ ያሳውቃል። አመልካቹም ማስታወቂያው ከደረሰው ጊዜ ጀምሮ በስምንት ሳምንታት ጊዜ ውስጥ የተጓደሉትን መረጃዎች አሟልቶ ማቅረብ አለበት፡፡
   3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተጠቀሰው መሠረት አመልካቹ ማመልከቻውን በጊዜ ገደቡ አሟልቶ ካላቀረበ ማመልከቻው ውድቅ ይሆናል፡፡
   4. በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ ያልሆነ አመልካች በየወቅቱ ግንኙነት ሊያደርግና ማንኛውንም መረጃ ለመስጠት የሚችል በአገር ውስጥ ቋሚ ነዋሪ የሆነ ወኪል ሊኖረው ይገባል፡፡

5. **<u>በምዝገባ ማመልከቻ ላይ ስለሚሰጥ ውሳኔ</u>**

1. ሚኒስቴሩ ለፀረ-ተባይ ምዝገባ የቀረበን ማመልከቻ ገምግሞ፡-
   ሀ) በማመልከቻው የቀረበው መረጃ የተሟላና ትክክለኛ መሆኑን፣
   ለ) ፀረ-ተባዩ ከታለመለት አገልግሎት አኳያ ፍቱንነቱን፣
   ሐ) በአያያዝና በአጠቃቀም መመሪያው መሠረት በሥራ ላይ ሲውል በሰዎችና በእንስሳት ጤና ላይ ጉዳት የማያስከትል መሆኑን፣
   መ) በአካባቢና ዒላማ ባልሆኑ ዝርያዎች ላይ የሚያደርሰው ተፅዕኖ ከሚሰጠው ጠቀሜታና ከሌሎች ተኪ አማራጮች ተፅዕኖ ጋር ሲነፃፀር አነስተኛ መሆኑን፣
   ሠ) የፀረ-ተባዩ ቅሪት ለረጅም ጊዜ በአካባቢው ውስጥ የማይቆይና በሚለወጥበት ወቅትም መርዛማ የማይሆን መሆኑን፣
   ረ) ሌሎች ተመሳሳይ ወይም የተሻለ ፍቱንነት ያላቸውና አደገኛነታቸው ዝቅተኛ የሆነ ፀረ ተባዮች አለመኖራቸውን፣
   ሰ) የመለያ ምልክቱ የሚፈለገውን መስፈርት ማሟላቱን፣
   ሸ) ለአጠቃቀም አመቺ መሆኑን፣
   ቀ) ከአገሪቱ ተጨባጭ የማህበራዊ ኢኮኖሚ እይታ አኳያ ፀረ-ተባዩ የሚሰጠው ጥቅም ከሚያስከትለው ጉዳት በላይ መሆኑን፣
   በ) በአለም አቀፍ ስምምነቶች ወይም በፀረ-ተባይ አማካሪ ቦርድ ምክር ላይ ተመስርቶ በሚኒስቴሩ ተቀባይነት ባገኘ ተመሳሳይ የምዝገባ ሥርዓት በሚከተሉ አገሮች ጥቅም ላይ እንዳይውል የተከለከለ ወይም በከፍተኛ ደረጃ የተገደበ ፀረ-ተባይ አለመሆኑን፣ እና
   ተ) አመልካቹ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣው ደንብ የተወሰነውን ክፍያ የፈጸመ መሆኑን፣

   ሲያረጋግጥ ፀረ-ተባዩ እንዲመዘገብ ይፈቅዳል።
2. ሚኒስቴሩ ፀረ-ተባይ እንዲመዘገብ ሲፈቅድ የሚከተሉትን ጨምሮ አስፈላጊ የሚላቸውን ገደቦች ሊያስቀምጥ ይችላል፦
   ሀ) በተወሰኑ አካባቢዎች የፀረ-ተባዩን አጠቃቀም መገደብ ወይም መከልከል፤
   ለ) ፀረ-ተባዩ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችልበትን ሰዓት ወይም ወቅት መገደብ፤
   ሐ) ፀረ-ተባዩ ጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት በአካባቢው ለሚገኙ ንብ አርቢዎች አስቀድሞ የማሳወቅ ግዴታ መጣል፤

መ) የተወሰኑ እፅዋት የሚያብቡበት ወቅት ፀረ-ተባዩ ጥቅም ላይ እንዳይውል መከልከል፤

ሠ) ፀረ-ተባዩ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ላላቸው ብቻ እንዲሸጥ መገደብ፤

ረ) ፀረ-ተባዩ ለተወሰኑ አገልግሎቶች እንዳይውል መገደብ።

3. ሚኒስቴሩ አንድን ፀረ-ተባይ ሲመዘግብ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ከተፈቀደው የመለያ ምልክት ቅጂ ጋር በማያያዝ ለአመልካቹ ይሰጣል። በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የተወሰኑ ገደቦችም በምዝገባ የምስክር ወረቀቱ ውስጥ መገለጽ አለባቸው።

4. ሚኒስቴሩ ለፀረ ተባይ ምዝገባ የቀረበለትን ማመልከቻ ካልተቀበለው ያልተቀበለበትን ምክንያት በመግለጽ ለአመልካቹ በጽሑፍ ያሳውቀዋል።

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት ፀረ-ተባይ እንዳይመዘገብ መወሰኑ በአመልካች ወይም በሌላ አመልካች ፀረ-ተባዩን በሌላ ጊዜ ለማስመዝገብ ማመልከቻ ማቅረብን አይከለክልም።

6. <u>**ምዝገባ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ**</u>

የፀረ-ተባይ ምዝገባ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ለአምስት ዓመታት የፀና ይሆናል።

7. <u>**የምዝገባ እድሳት**</u>

1. የፀረ-ተባይ ምዝገባ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ እንዳበቃ ለተመሳሳይ ጊዜ ሊታደስ ይችላል፡፡
2. የፀረ-ተባይ ምዝገባን ለማሳደስ ለሚኒስቴሩ የሚቀርብ ማመልከቻ ለዚሁ ተግባር በተዘጋጀው ፎርም መሠረት ሆኖ ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣው ደንብ የተዘረዘሩትን አስፈላጊ መረጃዎች መያዝና ምዝገባው ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ ከማለቁ ከ 90 ቀናት በፊት መቅረብ አለበት፡፡
3. ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የቀረበለትን ማመልከቻ መርምሮ ፀረ-ተባዩ በምዝገባው ወቅት የታዩ መስፈርቶችን አሟልቶ መቀጠሉን ሲያረጋግጥና አመልካቹ የተወሰነውን ክፍያ ሲፈጽም ምዝገባውን ያድስለታል።

8. **የምዝገባ ማሻሻያ**

1. ቀደም ሲል በተመዘገበ ፀረ-ተባይ መለያ ወይም መያዣ ላይ ለውጥ ለማድረግ ሲፈለግ ለውጥ የተደረገበትን መለያ ቅጂና እንደ አስፈላጊነቱ የማሸጊያ ዕቃውን ፎቶግራፍ በማያያዝ ለሚኒስቴሩ በጽሁፍ ማመልከት ያስፈልጋል፡፡
2. የቀረበው አዲሱ የፀረ-ተባዩ መለያ ወይም መያዣ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም ማንኛውንም ሌላ ሕግ ካልተፃረረ በስተቀር ሚኒስቴሩ ምዝገባውን አሻሽሎ ለአመልካቹ አዲስ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል።

9. **እንደገና ስለማስመዝገብ**

አንድን የተመዘገበ ፀረ-ተባይ አስመዝጋቢው የንግድ ስሙን፣ ዝግጅቱን የዋናው ንጥረ ነገር የቅልቅል መጠን ወይም አጠቃቀሙን ለመለወጥ ከፈለገ ወይም በሌላ ሰው ከተቀየረ ፀረ-ተባዩን ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት፣ ለማዘጋጀት፣ ለማምረት፣ ለማሸግ፣ እንደገና ለማሸግ፣ ለማከፋፈል፣ ለመሸጥ ወይም መለያ ለመስጠት ከፈለገ እንደገና ለማስመዝገብ ማመልከቻ ማቅረብ አለበት።

10. **ጊዜያዊ ምዝገባ**

1. አንድ ፀረተባይ አዲስ የተፈበረከ ወይም ለተለየ የግብርና ወይም የጤና ዘርፍ ተባይ መከላከል አገልግሎት አስፈላጊ መሆኑ ከተረጋገጠ ሚኒስቴሩ በሚወስናቸው ቅድመ ሁኔታዎች መሠረትና የተወሰነውን ክፍያ በማስከፈል አመልካቹ ጊዜያዊ ምዝገባው ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ከፀረተባዩ አጠቃቀምና ደህንነት ጋር በተያያዘ ተጨማሪ ሣይንሳዊና ቴክኒካዊ መረጃ ለማቅረብ ከተስማማ ለአንድ ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ጊዜያዊ ምዝገባ ሊፈቅድ ይችላል፦
   ሀ) አመልካቹ ጊዜያዊ ምዝገባው ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ከፀረ-ተባዩ አጠቃቀምና ደህንነት ጋር በተያያዘ ተጨማሪ ሳይንሳዊና ቴክኒካዊ መረጃ ለማቅረብ ከተስማማ፣ ወይም
   ለ) ፀረ-ተባዩ ሽያጭ ላይ የሚውለው ወይም የሚከፋፈለው በአገሪቱ ውስጥ በከፍተኛ ወረርሽኝ ደረጃ ለተከሰቱና በሰዎች ጤንነት፣ በቤት እንስሳት፣ በሰብል ወይም በተፈጥሮ ሀብት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ለሚያደርሱ ተባዮች መከላከያ ብቻ ከሆነ።

2. አመልካቹ ጊዜያዊ ምዝገባው እንዲራዘምለት ከጠየቀና ሚኒስቴሩ ተቀባይነት ያለው ሆኖ ካገኘው በሚወስናቸው ቅድመ ሁኔታዎች መሠረት ከአንድ ዓመት ላልበለጠ ተጨማሪ ጊዜ ጊዜያዊ ምዝገባውን ሊያራዝምለት ይችላል።
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) እና (2) የተመለከቱት ቅድመ ሁኔታዎች ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣው መመሪያ የሚወሰኑ ይሆናሉ።

11.<u>ምዝገባን ስለማገድና ስለመሰረዝ</u>

1. ሚኒስቴሩ በሚከተሉት ምክንያቶች የፀረ-ተባይ ምዝገባን ሊሰርዝ ይችላል፦
   ሀ) ፀረ-ተባዩ የተመዘገበው የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች በሚጻረር መልኩ ከሆነ፣
   ለ) ፀረ-ተባዩ በእፅዋት፣ በሰዎች ወይም በእንሰሳት ጤና ወይም በአካባቢ ላይ በሚያደርሰው ጉዳት ምክንያት ምዝገባው ሊቀጥል የማይገባው መሆኑ ሲታመንበት፤
   ሐ) ፀረ-ተባዩ ለተመዘገበለት ዓላማ ፍቱን አለመሆኑ በምርምር ሲረጋገጥ፤
   መ) ፀረ-ተባዩ ከገበያ ውጭ መሆኑ በአምራቹ ሲገለፅ፤
   ሠ) ምዝገባው የተፈቀደበት ቅድመ ሁኔታ ከተጣሰ፤ወይም
   ረ) ፀረ-ተባዩ ከተመዘገበ በኋላ ሚኒስቴሩ ባገኛቸው አዲስ መረጃዎች ወይም ቀደም ብሎ ግንዛቤ ውስጥ ያልገቡ ሁኔታዎች በመከሰታቸው የተነሳ የምዝገባው መሰረዝ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተጠቀሰው መሠረት ሚኒስቴሩ ማንኛውንም ምዝገባ ከመሰረዙ በፊት አስመዝጋቢው የምዝገባውን መሠረዝ የሚቃወም ከሆነ በ60 ቀናት ውስጥ ምክንያቱን በጽሁፍ እንዲያቀርብ ዕድል ይሰጠዋል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት አስመዝጋቢው ምክንያቱን በጽሁፍ ካቀረበበት ቀን ጀምሮ በ60 ቀናት ውስጥ ሚኒስቴሩ ውሳኔውን ለአስመዝጋቢው ያሳውቃል።
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የአስመዝጋቢው መቃወሚያ እስከሚቀርብና በንዑስ አንቀጽ (3) መሰረት የሚኒስቴሩ ውሳኔ እስከሚገለፅበት ጊዜ ድረስ የፀረ-ተባይ ምዝገባው ታግዶ ይቆያል፡፡
5. የፀረ-ተባይ ምዝገባ በዚህ አንቀጽ መሰረት ሲሰረዝ አስመዝጋቢው የምዝገባ የምስክር ወረቀቱን ለሚኒስቴሩ መመለስ አለበት፡፡

12.**መልሶ ስለመሰብሰብ**

1. የፀረ-ተባይ ምዝገባ ሲሰረዝ ሚኒስቴሩ እንደ አስፈላጊነቱ በሰዎች፣ በእንስሳት ወይም በእፅዋት ጤና ወይም በአካባቢ ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ለመከላከል ፀረ-ተባዩ እንዲሰበሰብ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡
2. እንዲሰበሰብ የተወሰነው ፀረ-ተባይ በእጁ የሚገኝ ማንኛውም የፀረ-ተባይ ነጋዴ ውሳኔው ከተላለፈበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ ለሚኒስቴሩ ሪፖርት ማድረግ አለበት።

13.**ምዝገባን እንደገና ስለመገምገም**

ሚኒስቴሩ በራሱ ተነሳሽነት ወይም ከፀረ-ተባይ አማካሪ ቦርድ በሚቀርብለት ሀሳብ መሠረት፡-

1. ፀረ-ተባዩ ከተመዘገበ በኋላ ባለው ጊዜ ውስጥ ፀረ-ተባዩን ለመገምገም በሚያስችሉ መረጃዎች ላይ ወይም ፀረ-ተባዩ ወይም ሌሎች በተመሳሳይ ምድብ የሚገኙ ወይም ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው ፀረ-ተባዮች በሰዎች፣ በእንስሳት ወይም በእጽዋት ጤና ወይም በአካባቢ ላይ የሚያደርሱትን ጉዳት፣ ፍቱንነትና ጥራት በሚገባ ለመገምገም በሚያስችሉ የአሠራር ሥርዓቶች ላይ ለውጥ ተደርጓል ብሎ ሲያምን፤
2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (1 በተመለከቱት መስፈርቶችና በተለያዩ ፀረ-ተባዮች አማካይነት የሚከሰቱ ድምር ውጤቶችን ጨምሮ ተያያዥነት ባላቸው ሌሎች ምክንያቶች ሳቢያ በሰዎች፣ በእንስሳት ወይም እጽዋት ጤና ላይ ወይም በአካባቢ ላይ የሚደርሰው አደጋ ተቀባይነት የሌለው ደረጃ ላይ መድረሱን ካመነ፤ ወይም
3. በአለም አቀፍ መድረኮች ላይ የሚነሱ ወይም በዓለም አቀፍ ድርጅቶች የሚተላለፉ አስተያየቶችን መሠረት በማድረግ፤

ቀደም ሲል የተመዘገበ ፀረ-ተባይ እንደገና እንዲገመገም ሊያደርግ ይችላል።

14.**ፀረ-ተባይ መዝገብ**

1. ሚኒስቴሩ በአገሪቱ የተመዘገቡ ፀረ-ተባዮችን ዝርዝርና መረጃ የያዘ መዝገብ ያደራጃል።
2. ሚኒስቴሩ በአገሪቱ ውስጥ የሚገኙ ፀረ-ተባዮች በእያንዳንዱ የፀረ-ተባይ የህይወት ዑደት ደረጃ ውስጥ ያላቸውን እንቅስቃሴና አጠቃቀማቸውን

ለመከታተል የሚያስችል የፀረ-ተባዮችን ዝርዝርና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች የያዘ ማዕከላዊ የመረጃ ቋት ወይም መዝገብ ቤት ይኖረዋል።

3. የመረጃ ቋቱ ወይም መዝገብ ቤቱ የሚከተሉትን ያካትታል፡-
   ሀ) ወደ ኢትዮጵያ የገቡ፣ በኢትዮጵያ የተመረቱና ጥቅም ላይ የዋሉ የፀረ-ተባይ ዓይነቶችንና መጠናቸውን፣
   ለ) በመንግሥትና በግል ይዞታ ሥር ባሉ መጋዘኖች የሚገኙ ፀረ-ተባዮችን፣
   ሐ) በክምችት ወይም በግብይት ሂደት እያሉ ጥቅም ላይ የማይውሉበት ደረጃ የደረሱ ፀረ-ተባዮችን፣
   መ) በፀረ-ተባይ ተቆጣጣሪዎች የተሰበሰቡና በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 32 መሠረት የተያዙ መረጃዎችን፣
   ሠ) አግባብ ባላቸው አካላት በተካሄዱ የክትትልና የአፈፃፀም ተግባራት የተገኙ መረጃዎችን፣
   ረ) በገበያ ላይ በሚገኝ የፀረ-ተባይ ዝግጅት ላይ የተደረገ የጥራት ምርመራ ውጤትን፣
   ሰ) በሮተርዳም ስምምነት የቅድሚያ እሽታ አሰራርን መሠረት በማድረግ ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ ይሁንታ የተሰጣቸው ወይም እንዳይገቡ የተከለከሉ ፀረ-ተባዮችን፣
   ሸ) የንግድ ፈቃድና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መረጃዎችን፣ እና
   ቀ) ሌሎች ለብቁ የፀረ-ተባይ አያያዝና አጠቃቀም ጠቃሚ ናቸው ተብሎ የሚታመንባቸውን መረጃዎች፡፡

4. የባለቤትነት መብት ካለባቸውና ምስጥራዊ ከሆኑ መረጃዎች በስተቀር በዚህ አንቀጽ መሠረት የተያዙት መረጃዎች ለህብረተሰቡ ተደራሽ እንዲሆኑ ይደረጋል፣ ሆኖም የመረጃዎቹ ቅጅ እንዲሰጡት የሚጠይቅ ማንኛውም ሰው ተገቢውን ክፍያ እንዲፈጽም ይደረጋል፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትና የንግድ ፈቃድ አሰጣጥ</u>

### 15.<u>የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቅት</u>

1. ማንኛውም ፀረ-ተባይ ለማምረት፣ ለማዘጋጀት፣ ለማሸግ፣ እንደገና ለማሸግ፣ መለያ ለመስጠት፣ ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት፣ ወደ ውጭ አገር ለመላክ፣ ለማከማቸት፣ ለመሸጥ፣ ለማከፋፈል፣ ለማጓጓዝ ወይም የፀረ-ተባይ አገልግሎት ለመስጠት

የሚፈልግ ሰው ለፀረ-ተባይ ንግድ ፈቃድ ቅድመ ሁኔታ የሆነውን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት፡፡

2. የሚከተሉትን በሚመለከት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው በሚኒስቴሩ ይሆናል፦

   ሀ) ፀረ-ተባይ ማምረትና ማዘጋጀት፤

   ለ) ፀረ-ተባይ ከውጭ ማስመጣትና ወደ ውጭ መላክ፤ እና

   ሐ) በፀረ-ተባይ የማጠን አገልግሎት፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ከተዘረዘሩት በስተቀር ለሌላ ማናቸውም የፀረ-ተባይ ንግድ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው የግብርና ዘርፍን ለመምራት ኃላፊነት በተሰጣቸው የክልል አካላት ይሆናል፡፡

4. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚስጥበት፣ የሚታደስበት፣ የሚታገድበትና የሚሰረዝበት ሁኔታ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ ይወስናል።

16.<u>የንግድ ሥራ ፈቃድ</u>

1. በዚህ አዋጅ አንቀፅ 15(2) መሠረት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለተሰጣቸው ሰዎች አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የንግድ ሥራ ፈቃድ የሚሰጠው በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር[7]ይሆናል።

2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 15(3) መሠረት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለተሰጣቸው ሰዎች የንግድ ስራ ፈቃድ የሚሰጠው የንግድና ኢንዱስትሪ ዘርፍን ለመምራት ኃላፊነት በተሰጣቸው የክልል አካላት ይሆናል።

17.<u>ወደ አገር ውስጥ የማስገባት ፈቃድ</u>

1. ማንኛውም ሰው በቅድሚያ ከሚኒስቴሩ ወደ አገር ውስጥ የማስገቢያ ፈቃድ ሳይሰጠው ምንም ዓይነት ፀረ-ተባይ ወደ አገር ውስጥ እንዲገባ ትዕዛዝ መስጠት አይችልም።

2. ሚኒስቴሩ፡-

   ሀ) የፀረ-ተባይ ማስገቢያ ማመልከቻው ሀሰተኛ ወይም ያልተሟላ ከሆነ፤

   ለ) በማመልከቻው የተጠቀሰው ያልተመዘገበ ፀረ-ተባይ የሆነ እንደሆነ፤

   ሐ) ወደ አገር ውስጥ እንዲገባ የተጠየቀው ፀረ-ተባይ አደጋ ወይም ጎጂ የፀረ-ተባይ ቅሪት ሊያስከትል የሚችል ከሆነ፤ ወይም

[7]በ22/12 (2008) አ. 916 አንቀፅ 9(10 መሠረት የንግድ ሚኒስቴር ሆኗል፡፡

መ) ፀረ-ተባዩን ወደ አገር ውስጥ ማስገባት የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች የሚፃረር ከሆነ፣የማስገቢያ ፈቃድ ሊከለክል ይችላል፤ ይህንንም ለአመልካቹ በጽሁፍከነምክንያቱ ይገልጽለታል፡፡

3. ማንኛውም ፀረ-ተባይ፡-

ሀ) አገር ውስጥ ሲደርስ ከተፈበረከ ጊዜ ጀምሮ ስድስት ወር የበለጠው ከሆነ፤

ለ) የምርመራ ውጤት የምስክር ወረቀትና የደህንነት መረጃ ሰነድ ከሌለው፤ ወይም

ሐ) በሚኒስቴሩ ኢንስፔክሽን ተካሂዶበት የመግቢያ የምስክር ወረቀት ካልተሰጠው፤

ወደ አገር ውስጥ መግባት አይችልም።

4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3(ሀ ቢኖርም ሚኒስቴሩ የተጠየቀው ፀረ-ተባይ ለምርምር ወይም ለሙከራ ከሆነ ወይም በፀረ-ተባዩ ቀሪ የመጠቀሚያ ጊዜ ጥቅም ላይ ውሎ ማለቅ የሚችል መሆኑን ካረጋገጠ አገር ውስጥ እንዲገባ ሊፈቅድ ይችላል።

5. ማንኛውም ሰው በቅድሚያ ከሚኒስቴሩ ወደ ውጭ የማስወጫ ፈቃድ ሳይሰጠው ፀረተባይ ወደ ውጭ፡ አገር መላክ አይችልም።

## ክፍል አራት

## ፀረ-ተባይ ማሸግ፣ መለያ መስጠት፣ ማስተዋወቅ፣ ማጓጓዝና ማስወገድ

### 18.ፀረተባይ ማሸግና መለያ መስጠት

1. ማንኛውም ሰው መያዣው፡-

ሀ) አደጋ በማያደርስ ሁኔታ ፀረ-ተባዩን ለማከማቸት፣ ለአያያዝና ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችል ካልሆነ፣ እና

ለ) በግልፅ ጎልቶ የሚታይ በአማርኛና በእንግሊዘኛ የተዘጋጀና የፀደቀ በቀላሉ የማይለቅ የመለያ ምልክት ያለው ካልሆነ፣

በስተቀር ፀረ-ተባይ ማሸግ ወይም እንደገና ማሸግ አይችልም።

2. ፀረ-ተባይ ከአንድ በላይ በሆነ መያዣ የሚያዝ ሲሆን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ለ ድንጋጌ ተግባራዊ የሚሆነው፡-

ሀ) ተለያይቶ የሚሸጥን አነስተኛ ፀረ-ተባይ መጠንን የሚወክል መያዣን፣ እና

ለ) ከአንድ በላይ ለየብቻ በችርቻሮ የሚሸጡ የፀረ-ተባይ መያዣዎችን የያዘ መያዣን፣

በሚመለከት ይሆናል፡፡

19. **ማስተዋወቅ**

1. ማንኛውም ሰው ያልተመዘገበ ፀረ-ተባይን ማስተዋወቅ አይችልም።
2. ፀረ-ተባዩ የተመዘገበ ቢሆንም ማስታወቂያው፡-

   ሀ) አሳሳች ከሆነ ወይንም ለማጭበርበር ሆን ተብሎ የተዘጋጀ ሆኖ ሲገኝ፣

   ለ) ከማንኛውም ፀረ-ተባይ ጋር ሀሰተኛ ወይም አሳሳች ማወዳደሪያዎች የሚያ ደርግ ከሆነ፣

   ሐ) "ጉዳት የማያደርስ"፣ "መርዛማ ያልሆነ"፣ "የማይጎዳ"፣ ወይንም "የማይመርዝ" የሚል ቃል ይዞ ከተገኘ፣

   መ) ገዥዎችንና ተጠቃሚዎችን መለያውን እንዲያነቡ የሚያሳስብ መግለጫ ያልያዘ ከሆነ፣ ወይም

   ሠ) ፀረ-ተባዩ ሲመዘገብ ከተጣሉ ገደቦች ጋር ተፃራሪ ከሆነ፣

   ማስተዋወቅ አይችልም።

20. **ማጓጓዝ**

1. ማንኛውም ሰው ጥብቅ የአጠቃቀም ገደብ የተጣለበት ፀረተባይን ሳይጨምርና ለግል ጥቅም የሚውል አነስተኛ መጠን ካልሆነ በስተቀር፡-

   ሀ) በመጓጓዣ የመንገደኞች ክፍል ውስጥ፣ ወይም

   ለ) በመጓጓዣ አንድ ክፍል ውስጥ ከእንስሶች ጋር ወይም ከምግብ፣ ከመኖ፣ ከመድሀኒቶች፣ ከአሻንጉሊቶች፣ ከልብሶች፣ ከኮስሞቲኮች፣ ከቤት ውስጥ ዕቃዎች ወይም ቢበከሉ አደጋ ሊያስከትሉ ከሚችሉ ሌሎች ነገሮች ጋር፣

   ማጓጓዝ አይችልም።
2. ፀረ-ተባይ ይዞ የነበረን ባዶ መያዣ የሚያጓጉዝ ማንኛውም ሰው ከማንኛውም ምግብ፣ መኖ ወይም እንስሳት በመለየትና ከነዚሁ ጋር እንዳይነካካ አድርጎ ማጓጓዝ አለበት፡፡
3. ፀረ-ተባይ የሚያጓጉዝ መጓጓዣ በፀረ-ተባይ ፍሳሽ ከተበከለ መጓጓዣው በሚኒስቴሩ ወይም በክልል ደረጃ የግብርና ዘርፍን ለመምራት ሃላፊነት በተሰጣቸው አካላት በሚወከል ባለሙያ ከብክለት ነፃ እንዲሆንና እንዲጸዳ የመጓጓዣው ባለቤት ለሚኒስቴሩ ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡

4. የፀረ-ተባዮች የማጓጓዝ ስርዓት ሚኒስቴሩ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመመካከር በሚወጣው መመሪያ መሠረት ይከናወናል፡፡

21.**ማስወገድ**

1. ማንኛውም ሰው ፀረ-ተባይን ወይንም የፀረ-ተባይ ቆሻሻን የሰውና የእንስሳት ጤናን ወይም አካባቢን በሚጎዳ ሁኔታ ማስወገድ አይችልም፡፡
2. ማንኛውም ፀረ-ተባይ ወደ አገር ውስጥ የሚያስገባ ወይም የሚሸጥ ሰው በይዞታው ሥር የሚገኙ ፀረ ተባዮች ጥቅም ላይ መዋል የማይችሉ ሲሆን በራሱ ወጪ የማስወገድ ኃላፊነት አለበት፡፡
3. ሚኒስቴሩ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመመካከር ጥቅም ላይ የማይውሉ ፀረ-ተባዮች አወጋገድን በተመለከተ መመሪያ ያወጣል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል።

**ክፍል አምስት**

**የጥንቃቄ እርምጃዎች**

22.**የሠራተኛ ደህንነት**

1. ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ ከተደነገገው ውጭ ወይንም ከፀረ-ተባይ ምዝገባ ጋር የተያያዙ ገደቦችን በሚቃረን መልክ ፀረ-ተባይን መጠቀም ወይንም ሠራተኛውን እንዲጠቀም ማድረግ ወይም ሌላ ሰው እንዲጠቀም ሃሳብ ማቅረብ አይችልም።
2. ማንኛውም አሠሪ ሠራተኛውን ፀረ-ተባይ እንዲጠቀም ሲያደርግ ወይም ሲፈቅድ ፀረ-ተባዩን በጥንቃቄ መያዝ የሚያስችሉ አስፈላጊ ነገሮችንና የመከላከያ ትጥቆችን ማቅረብና ሠራተኛው እነዚህኑ እንዲጠቀም ማድረግ አለበት።
3. ማንኛውም አሠሪ ሠራተኛን ከፀረ-ተባይ ጋር በተገናኘ ሁኔታ እንዲሠራ ሲያደርግ፡-
   ሀ) ሠራተኛው ሥራውን በብቃት ለመሥራት የሚያስችለውን መመሪያ እንዲያገኝ ማድረግ፣
   ለ) ሚኒስቴሩ ወይንም የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በሚወስነው መሠረት ሠራተኛው በየጊዜው የሕክምና ምርመራ እንዲያገኝ ማድረግ፣ እና
   ሐ) ሠራተኛው በአሰሪው ስለፀረተባዩ የሚገልፅ በቂ መመሪያና ተገቢውን የመከላከያ ትጥቅ ሣይሰጠው በፀረተባይ ምክንያት አደጋ ቢደርስበት አሰሪው የሕክምና ወጪውንና የጉዳት ካሣ መክፈል፣

   አለበት፡፡

## 23.አደጋዎችን ሪፖርት ስለማድረግ

1. ፀረ-ተባይ በተጓጓዘበት፣ በተከማቸበት፣ በተሸጠበት ወይም ጥቅም ላይ በዋለበት አካባቢ አደጋ መድረሱን የተረዳ ማንኛውም ሰው ስለደረሰው አደጋ ለሚኒስቴሩ ወይንም አግባብ ላለው የክልል መንግሥት አካል ሳይዘገይ ሪፖርት ማድረግ አለበት።
2. በፀረ-ተባይ የተመረዘ ሰው መኖሩን የተረዳ ማንኛውም ሐኪም ወይንም ሌላ የጤና ባለሙያ ስለደረሰው አደጋ ሳይዘገይ ለሚኒስቴሩ ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡
3. ሚኒስቴሩ እና የጤና ጥብቃ ሚኒስቴር እንዲሁም አግባብ ያላቸው የክልል አካላት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (2) መሠረት ሪፖርት የተደረጉ አደጋዎችን በተመለከተ የመረጃ ልውውጥ ማድረግ አለባቸው።

## ክፍል ስድስት

## የፀረ-ተባይ ምርመራ

## 24.ኦፊሴል ላቦራቶሪና ኦሴሳል መርማሪ ስለመሰየም

1. በዚህ አዋጅ መሠረት የፀረ-ተባይ ምርመራዎችን ለማከናወን ሲባል ሚኒስቴሩ ፀረተባይ ለመመርመር ተገቢውን መስፈርት አሟልቶ ያገኘውን ማንኛውንም የመንግሥት ወይም የግል ላቦራቶሪ በኦፊሴል ላቦራቶሪነት ሊሰይም ይችላል።
2. በዚህ አዋጅ መሠረት የፀረ-ተባይ ምርመራዎችን ለማከናወን ሲባል ሚኒስቴሩ ፀረ-ተባይ ለመመርመር ተገቢውን መስፈርት አሟልቶ ያገኘውን ማንኛውንም መርማሪ በኦፊሴል መርማሪነት ሊሰይም ይችላል፡፡

## 25.የምርመራ ውጤት የምስክር ወረቀት

ኦፊሴል መርማሪ የፀረ-ተባይ ምርመራ ካካሄደ በኋላ ምርመራውን ለማካሄድ የተጠቀመበትን የምርመራ ዘዴና በሚኒስቴሩ መመሪያ የተወሰኑ ሌሎች መረጃዎችን በመዘርዘር የምርመራ ውጤት የምስክር ወረቀት ይሰጣል።

## 26.የቅሪት ምርመራና በፀረተባይ የተነከረ አጐበር ሙከራና ክትትል

1. ባልተዘጋጁ የግብርና ምርቶች ላይ የሚደረግ የፀረ-ተባይ ቅሪት ምርመራ በሚኒስቴሩ ይከናወናል፡፡
2. ሚኒስቴሩ በግብርና ምርቶች ላይ መኖር የሚችለውን ከፍተኛ የፀረ-ተባይ ቅሪት መጠን በመወሰን ረገድ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይተባበራል።

3. በተዘጋጁ ምግቦችና በሰዎች ላይ ሊኖር የሚችለውን የፀረ-ተባይ ቅሪት በተመለከተ የቁጥጥር ተግባር በሚመለከታቸው አግባብ ያላቸው አካላት ይከናወናል።
4. በፀረተባይ የተነከረ አጎበር የፍቱንነት ሙከራና ክትትል በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ይከናወናል፡፡

## ክፍል ሰባት

## የፀረ-ተባይ አማካሪ ቦርድ እና ተቆጣጣሪዎች

### 27.የፀረ-ተባይ አማካሪ ቦርድ

1. የፀረ-ተባይ አማካሪ ቦርድ (ከዚህ በኋላ "ቦርድ" እየተባለ የሚጠራ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።
2. ቦርዱ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

   ሀ) በሚኒስትሩ የሚሰየም የሥራ ኃላፊ……………….ሰብሳቢ

   ለ) የፀረ-ተባይ ምዝገባ ኃላፊ ...............................አባልና ፀሐፊ

   ሐ) የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ተወካይ[8] .......................አባል

   መ) የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን[9] ተወካይ………………..”

   ሠ) የጥራትና ደረጃዎች ባለስልጣን[10] ተወካይ……………..…”

   ረ) የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ተወካይ…”

   ሰ) የብዝሀ ህይወት ጥበቃ ኢንስቲትዩት ተወካይ…………..”

   ሸ) የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ተወካይ ………“

   ቀ) የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን[11] ተወካይ………………”

### 28.የቦርዱ ተግባራት

1. ቦርዱ የሚከተሉት ተግባራት ይኖሩታል፡-

   ሀ) ደህንነቱ ከተረጋገጠ የፀረ-ተባይ አያያዝና አጠቃቀም አኳያ የሚቀረጹ ብሔራዊ ፖሊሲዎችን፣ ደንቦችን፣ መመሪያዎችንና የአገልግሎት ክፍያን በተመለከተ ሚኒስቴሩን ያማክራል፤

---

[8] በ25)08(2011 አ. 1097 አንቀጽ 9(15 መሰረት የጤና ሚንስቴር ሆኗል፡፡
[9] በ25)08(2011 አ. 1097 አንቀጽ 36(17 የአካባቢ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ሆኗል፡፡
[10] በ17)13 (2003 ደ. 193 የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ ሆኗል፡፡
[11] በ25)08(2011 አ. 1097 አንቀጽ 9(19 የገቢዎች ሚንስቴር ሆኗል፡፡

ለ) ፀረ-ተባይን የሚመለከቱ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ከመተግበር አኳያ ሚኒስቴሩን ያማክራል፤ በዚህ ረገድ በብሔራዊ ደረጃ ከሚወከል አካል ጋር በመተባበር ይሰራል፤

ሐ) በዚህ አዋጅ መሠረት የፀረ-ተባይ ምዝገባ፣ እድሳት፣ ማገድ፣ ማሻሻል፣ ምዝገባን መሰረዝ፣ የፈቃድ አሰጣጥ መስፈርቶችና ቅድመ ሁኔታዎችን በተመለከተ ሚኒስቴሩን ያማክራል፤

መ) የሚከተሉትን በተመለከተ በመመሪያዎች ዝግጅት ሚኒስቴሩን ያማክራል፡-

1) ጥቅም ላይ መዋል የማይቻሉ ፀረ-ተባዮች ማስወገድን፤
2) የፀረ-ተባይ አጠቃቀምን፣ አስተሻሸግን፣ መለያ አደራረግን፣ ማጓጓዝን፣ ማከማቸትን፣ ሥርጭትን እና የባዶ ፀረ-ተባይ መያዣዎች ማስወገድን፣
3) የተበከለ አፈርንና የተበከለ መሣሪያን፣ እና
4) የተቀበረ ፀረ-ተባይን፤

ሠ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 መሠረት ከሚቀርብ ማመልከቻ ጋር ከሚቀርቡ መረጃዎች ውስጥ የባለቤትነት መብት ያላቸውና ሚስጥራዊ የሆኑ መረጃዎችን ለመለየትና የመረጃ አያያዝና አጠቃቀምን ለማከናወን የሚያስችሉመስፈርቶችን በመቅረጽ በሚኒስቴሩ እንዲፀድቁ ያደርጋል፤

ረ) የአቅም ግንባታና የኤክስቴንሽን ፍላጎትን ይለያል፤

ሰ) የፀረ-ተባይ ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ያደርጋል፣ የፀረ-ተባይ ግዢ በዚህ አዋጅ መሠረት መፈፀሙን ያረጋግጣል፤

ሸ) በጥቅም ላይ የሚገኙ ፀረ-ተባዮችን በየወቅቱ ይገመግማል ወይም እንዲገመገሙ ያደርጋል፤

ቀ) የታገዱ፣ ጥብቅ ገደብ የተጣለባቸውና የአጠቃቀም ገደብ የተጣለባቸው ፀረ-ተባዮችን ዝርዝር ገምግሞ የማሻሻያ ሃሳብ ያቀርባል፣ ጥብቅ ገደብ የተጣለባቸውና የአጠቃቀም ገደብ የተጣለባቸው ፀረ-ተባዮችን አያያዝ በሚመለከትም ሃሳብ ያቀርባል፤

በ) የፍቱንነት ማረጋገጫ መረጃ አጠቃቀምን እንዲያግዝ ከኢትዮጵያ ጋር በበቂ ሁኔታ በግብርናና በአየር ንብረት ተመሳሳይነት ያላቸውን አገሮች በተመለከተ ሚኒስቴሩን ያማክራል።

2. ቦርዱ፡-

   ሀ) ከተሰጠው ማንኛውም ኃላፊነት ጋር በተያያዘ ምክር እንዲሰጠው ከአባላቱ ወይም ከአባላቱ ውጭ ወይም ከሁለቱ የተውጣጡ አባላትን የያዙ ንዑስ ኮሚቴዎች፣ እና

   ለ) በተለይም በጥቅም ላይ የዋሉ ፀረ-ተባዮች በሰዎች ጤናና በአካባቢ ላይ የሚያደርሱትን ጉዳት በተመለከተ ምክር ሊሰጡ የሚችሉ አግባብ ካላቸው ተቋማት የተውጣጡ ባለሙያዎችን የያዙ የቴክኒክ ኮሚቴዎችን፣

   ሊያቋቁም ይችላል፡፡

29.**<u>የቦርዱ አሰራር</u>**

1. ማንኛውም የቦርድ አባል የፀረ-ተባይ ምዝገባ ማመልከቻ አቅራቢ ከሆነ ሰው ጋር ወይም በቦርዱ በመታየት ላይ ካለ ጉዳይ ጋር በተያያዘ የገንዘብ ወይም ግላዊ ግንኙነት ካለው ሁኔታውን በጽሁፍ ለቦርዱ ማሳወቅ አለበት። ቦርዱም ማመልከቻው ወይም የተጠቀሰው ጉዳይ ሲታይ አባሉ እንዳይሳተፍ ማድረግን ጨምሮ ተገቢ የሆነውን እርምጃ ይወስዳል።
2. ቦርዱ ቢያንስ በዓመት አራት ጊዜ መሰብሰብ አለበት፡፡
3. ቦርዱ የስብሰባ ቃለ ጉባዔውን በአግባቡ መዝግቦ ማስቀመጥ አለበት፡፡
4. ቦርዱ የራሱን የአሰራር ደንብ ያወጣል።

30.**<u>የፀረ-ተባይ ተቆጣጣሪ</u>**

1. በሚኒስቴሩ ወይም የግብርና ዘርፍን በሚመራ የክልል አካል የተመደበ ተቆጣጣሪ በሥራ ሰዓት ያለማስጠንቀቂያ መታወቂያውን በማሳየት፡-

   ሀ) ይህ አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ ፀረ-ተባይ በማስመጣት፣ በመላክ፣ በማምረት፣ በማሸግ፣ እንደገና በማሸግ፣ መለያ ምልክት በማድረግ፣ በማከማቸት፣ በመሸጥ፣ በማከፋፈል፣ በማስተዋወቅና በመጠቀም ተግባር ላይ የተሰማሩትን ተቋሞች በየጊዜው የመቆጣጠር፣

   ለ) የተመዘገቡ ፀረ-ተባዮች የተመዘገቡበት ሁኔታ እየተከበረ መሆኑን ለማረጋገጥ የድህረ-ምዝገባ ቅኝት የማካሄድ፣

   ሐ) ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም አግባብነት ያላቸው የምስክር ወረቀቶች፣ ፈቃዶች፣ የንግድ ፈቃዶች፣ መዛግብቶች ወይም ሌሎች ዶክመንቶች እንዲቀርቡለት የመጠየቅና የመመርመር፣

መ) ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም አግባብነት ያላቸውን የምርት ናሙናዎች የመውሰድና ለምርመራ የማቅረብ፣

ሠ) ከዚህ አዋጅ ጋር በሚፃረር ሁኔታ ጥቅም ላይ ውሏል ብሎ ያመነበትን ወይም ለማስረጃነት ይጠቅማል ያለውን ማንኛውንም መሣሪያ፣ ፀረ-ተባይ፣ ሠነድ፣ መረጃ ወይም ከፀረ-ተባይ ጋር ግንኙነት ያለውን ሌላ ነገር ለዚሁ ተግባር የተዘጋጀ ደረሰኝ በመስጠት የመያዝ፣

ረ) የተከማቸ ፀረ-ተባይ ወይም ፀረ-ተባዩ የተከማቸበት ሁኔታ ከማናቸውም የዚህ አዋጅ ድንጋጌ ጋር የማይስማማ ሆኖ ሲገኝ የፀረ-ተባይ መጋዘኑን ወይም የመሸጫ ቦታውን የማሸግ፣

ሰ) የሥነ ህይወታዊ ፀረ-ተባይ ድርጅቶችና ርጭትን፣ አጠቃቀምና የሥነ ህይወታዊ ፀረ-ተባዮች ኢላማ ውስጥ እንዲገቡ በተፈለጉና ከኢላማ ውጭ በሆኑ ዝርያዎች ላይ ያላቸውን ተጽእኖ የመቆጣጠርና የመከታተል፣

ሸ) በዚህ አዋጅ መሠረት ማንኛውንም ዓይነት ሥራ በሚያከናውንበት ወቅት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የጉምሩክ ወይም የፖሊስ ባልደረቦችን እርዳታ የመጠየቅ፣እና

ቀ) በዚህ አዋጅ መሠረት በወጡ በደንቦችና መመሪያዎች የተወሰኑ ሌሎች የቁጥጥር፣ የክትትልና የቅኝት ሥራዎችን የማከናወን፣

ሥልጣን ይኖረዋል።

2. ማንኛውም ፀረ-ተባይ ተቆጣጣሪ የቁጥጥር ተግባሩን ሲያከናውን ይህንን አዋጅ ተላልፈው በሚያገኛቸው ሰዎች ላይ ክስ ለመመስረት የሚያስችሉ የተሰበሰቡ መረጃዎችን ለሚመለከተው አካል ሪፖርት የማድረግ ሃላፊነት አለበት፣ ሪፖርቱ የቀረበላቸው አካላትም ህጉን ለማስከበር የመተባበር ግዴታ አለባቸው።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1(ሠ መሠረት የተያዘ ንብረት አስፈላጊው ምርመራ ወይም የክስ ሂደት ከተፈጸመ በኋላ ወዲያውኑ ለባለቤቱ ይመለሳል፡፡ ሆኖም የተያዘው ፀረ-ተባይ ህገ ወጥ መሆኑ በፍርድ ቤት ከተረጋገጠ በዚህ አዋጅ መሠረት እንዲወረስ ወይም እንዲወገድ ይደረጋል፡፡

4. ማንኛውም በፀረ-ተባይ ተቆጣጣሪነት የተመደበ ሰው በዚህ ሥራ ላይ እያለ በፀረ-ተባይ ማስመጣት፣ ማምረት፣ መሸጥ ወይም ማከፋፈል ንግድ ሥራ ላይ ሊሳተፍ አይችልም።

## ክፍል ስምንት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 31.ክልከላዎች

1. ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት ያልታሸገና መለያ ያልተደረገበትን ፀረ-ተባይ ወደ አገር ውስጥ ማስገባት፣ ማከማቸት፣ ማጓጓዝ ወይም ለሽያጭ ማቅረብ አይችልም።
2. ማንኛውም ሰው ፀረ-ተባይን በመከለስ ወይም አንድን ፀረ-ተባይ ተከልሷል የሚል አሳማኝ ምክንያት ሲኖረው ፀረ-ተባዩን መሸጥ ወይም ማከማቸት አይችልም።
3. ማንኛውም ሰው በማናቸውም ሁኔታ የታገደን ፀረ-ተባይ ማዘጋጀት፣ ማምረት፣ ወደ አገር ውስጥ ማስገባት፣ ማሸግ፣ ዳግም ማሸግ፣ መለያ ማድረግ፣ መሸጥ፣ ማሰራጨት፣ ማከማቸት ወይም መጠቀም አይችልም።
4. ማንኛውም ሰው ከሚኒስቴሩ በጽሁፍ ፈቃድ ሳያገኝ ጥብቅ ገደብ የተጣለባቸውን ፀረ-ተባዮች ማዘጋጀት፣ ማምረት፣ ወደ አገር ውስጥ ማስገባት፣ ማሸግ፣ ዳግም ማሸግ፣ መለያ ማድረግ፣ መሸጥ፣ ማስራጨት፣ ማከማቸት ወይም መጠቀም አይችልም።

### 32.መዝገብ ስለመያዝ

1. ማንኛውም የፀረ-ተባይ ነጋዴ ወደሀገር ውስጥ ያስገባውን፣ ወደ ውጭ የላከውን፣ ያመረተውን፣ ያሸገውን፣ እንደገና ያሸገውን፣ ያከማቸውን፣ መለያ የሰጠውን፣ ያጓጓዘውን፣ ያከፋፈለውን ወይም የሸጠውን ፀረ-ተባይ መጠንና ሌሎች በሚኒስቴሩ መመሪያ መሠረት የሚፈለጉ መረጃዎችን መዝግቦ መያዝ እና እነዚህኑ መረጃዎች በተጠየቀ ጊዜ ለሚኒስቴሩ ወይም ለሚመለከተው አግባብ ያለው አካል ማስተላለፍ አለበት፡፡
2. ሚኒስቴሩ ማንኛውንም የፀረ-ተባይ ነጋዴ የፀረ-ተባይን ጥራት ወይንም ፀረ-ተባዩ በአካባቢ ወይንም በሰው፣ በእንስሳት ወይንም በዕፅዋት ጤንነት ላይ የሚያደርሰውን ተፅዕኖ በሚመለከት ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እንዲያስችል መረጃ እንዲያጠቃልል፣ ሙከራዎችን እንዲሰራ ወይንም ስለፀረ-ተባዩ ያለውን ሁኔታ እንዲከታተልና መረጃውን በተወሰነ ጊዜ ውስጥ እንዲያስተላልፍ በጽሑፍ ሊጠይቀው ይችላል።

3. በሚኒስቴሩና በሚመለከታቸው አግባብ ያላቸው አካላት መካከል ፀረ-ተባይን በተመለከተ በየጊዜው በሚቀርቡ ሪፖርቶች የመረጃ ልውውጥ ይደረጋል፡፡

## 33.ቅጣት

1. ማንኛውም ሰው፡-

   ሀ) ያልተመዘገበ ፀረ-ተባይ ወይም ምዝገባው የታገደ ወይም የተሰረዘ ፀረ-ተባይ እያወቀ የሸጠ እንደሆነ፤

   ለ) ጥቅም ላይ መዋል የማይችል ፀረ-ተባይ እያወቀ የሸጠ እንደሆነ፤

   ሐ) በሕግ የተደነገገውን የደረጃ መስፈርት በማያሟላ የፀረ-ተባይ መያዣ እያወቀ ፀረ-ተባይ የሸጠ እንደሆነ፤

   መ) ማንኛውንም ማመልከቻ፣ የምስክር ወረቀት ወይም በዚህ አዋጅ የተጠቀሱትን ሌሎች ሰነዶችን በሚመለከት ሆን ብሎ የሀሰት ማስረጃ የሰጠ እንደሆነ፤

   ሠ) የፀረ-ተባይ ተቆጣጣሪን ያሳሳተ ወይንም ያታለለ ወይንም ፀረ-ተባይን ወይም የፀረ-ተባይን መያዣ በሚመለከት የተወሰደ ናሙና ወይም ለምርመራ የተሰጠ ናሙናን በትክክል ፀረ-ተባይን እንዳይወክል ያዛባ እንደሆነ፤

   ረ) ሆን ብሎ ፀረ-ተባይ የከለሰ ወይንም የተከለሰ ፀረ-ተባይ የሸጠ ወይንም ያከማቸ እንደሆነ፤

   ሰ) የሰውን ወይም የእንስሳትን ጤና ወይም አካባቢን በሚጎዳ አኳኋን ወይም በዚህ አዋጅ ከተደነገገው ውጭ ፀረ-ተባይን፣ የፀረ-ተባይ ቆሻሻን ወይም የፀረ-ተባይ መያዣን ያስወገደ እንደሆነ፤

   ሸ) በዚህ አዋጅ መሠረት በሚኒስቴሩ የተሰጠ ፈቃድ ሳይኖረው ፀረ-ተባይ ወደሀገር ውስጥ ያስገባ እንደሆነ፤

   ቀ) የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይሰጠው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 15 በተመለከቱት የፀረ-ተባይ ንግድ ሥራዎች ላይ የተሰማራ እንደሆነ፤

   በ) በዚህ አዋጅ ከተደነገገው ውጭ ፀረ-ተባይ ያከማቸ፣ የተጠቀመ፣ ያጓጓዘ እንደሆነ፤

   ተ) ሆን ብሎ ከፀረ-ተባይ መያዣ ላይ ማንኛውንም መለያ የገነጠለ፣ የለወጠ፣ ያበላሸ ወይንም ያጠፋ እንደሆነ፤

   ቸ) በአካባቢ ላይ ጥፋት ሊያደርስ ወይም ሌላ ጉዳት ሊያስከትል የሚችልን መረጃ እያወቀ የደበቀ እንደሆነ፤

ነ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ (1 ወይም ንዑስ አንቀጽ (2(ሀ፣ (ለ፣ (ሐ ወይም (ሠ የተደነገገውን በመተላለፍ ፀረ-ተባይ ያስተዋወቀ እንደሆነ፤

የወንጀል ህግ የበለጠ ቅጣት የሚያስከትል ካልሆነ በስተቀር ከአምስት እስከ አሥር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራትና ከብር 25,000 እስከ 50,000 ብር በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል።

2. ማንኛውም ሰው፡-

ሀ) የፀረ-ተባይ ተቆጣጣሪ በዚህ አዋጅ መሠረት ተግባሩን ለመወጣት መረጃ ሲጠይቅ ለመተባበር ፈቃደኛ ያልሆነ እንደሆነ፤

ለ) ሆን ብሎ በፀረ-ተባይ ተቆጣጣሪ የታሸገን መጋዘን የከፈተ እንደሆነ፤

ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 32 መሠረት የተጠየቀውን መረጃ ያልሰጠ እንደሆነ፤

መ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ (2(መየተደነገገውን በመተላለፍ ፀረ-ተባይ ያስተዋወቀ እንደሆነ፣

ሠ) በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት የመከላከያ ትጥቆችን ሳያቀርብ ሠራተኛውን ፀረ-ተባይ ሥራ ላይ እንዲያውል ያደረገ ወይም የፈቀደ እንደሆነ፤

የወንጀል ህግ የበለጠ ቅጣት የሚያስከትል ካልሆነ በስተቀር እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ እሥራትና ከብር 10,000 እስከ ብር 30,000 በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል።

3. ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት በባለቤትነት የተያዘን ወይም ሚስጥራዊ የሆነ መረጃን እያወቀ የገለጸ እንደሆነ ከአንድ እስከ ሦስት ዓመት በሚደርስ እሥራትና ከብር 20,000 እስከ 25,000 ብር በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል።

4. ፍርድ ቤት የጥፋተኝነት ፍርድ ሲወስን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1፣ (2 ወይም (3 ከተመለከተው ቅጣት በተጨማሪ፡-

ሀ) ለጥፋቱ መፈፀሚያ የዋለ ማንኛቸውም ነገር እንዲወረስ ወይም እንዲወገድ እንዲሁም ከሽያጭ የተገኘው ገቢ እንዲወረስ፣ እና

ለ) በጥፋቱ ምክንያት ለተጎዳ ማንኛውም ሰው፣

1) የደረሰውን የጥፋት ወይም የጉዳት መጠን፣

2) የጥፋቱን ክብደትና ድግግሞሽ፣ እና

3) በጥፋተኛው በኩል የተገኙ የገንዘብ ጠቀሜታዎችን፣

ታሳቢ ያደረገ ካሳ እንዲከፈል ሊያዝ ይችላል፡፡

5. ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ መሠረት ጥፋተኛ ሆኖ ሲፈረድበት አግባብ ያለው አካል ከፀረ-ተባይ ጋር ተያያዥነት ያለውን ፈቃዱን ይሰርዛል።

34.<u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1 መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

35.<u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

1. ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በፀረ-ተባይ ምዝገባና ቁጥጥር የመንግሥት ምክር ቤት ልዩ ድንጋጌ ቁጥር 20)1982 እና በመድኀኒት አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 176)1991 መሠረት ተመዝግበው የነበሩ ፀረ-ተባዮች በዚህ አዋጅ መሠረትእንደተመዘገቡ ተቆጥሮ በዚህ አዋጅና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጡደንቦችና መመሪያዎች ይተዳደራሉ።
2. በመድኀኒት አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 176)1991 መሠረት በምዝገባ ሂደት ውስጥ የሚገኙ ፀረ-ተባዮች ይህ አዋጅ እንደጸና ባሉበት ደረጃ ለሚኒስቴሩ ይተላለፋሉ።

36.<u>የተሻሩ ሕጎች</u>

1. የፀረ-ተባይ ምዝገባና ቁጥጥር የመንግሥት ምክር ቤት ልዩ ድንጋጌ ቁጥር 20)1982 በዚህ አዋጅ ተሽሯል።
2. ይህን አዋጅ የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ አዋጅ የተመለከቱ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈፃሚነት አይኖረውም።

37.<u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ነሐሴ 09 ቀን 2002 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## የፍትህ ሚኒስቴር

## አዋጅ ቁጥር 782/2005

## የዕፅዋት ዘር አዋጅ

የኢትዮጵያ የዕጽዋት ዘር ሴክተር የአገሪቱን የግብርና ኢኮኖሚ እድገትና የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ ወሳኝ በመሆኑ፤

የተሻሻሉ የዕጽዋት ዝርያዎች ወደ ገበያ ውስጥ የሚገቡበትን ሁኔታ ማመቻቸት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ጥራቱን የጠበቀ የዕጽዋት ዘር ለአርሶ አደሩ፣ ለከፊል አርብቶ አደሩና ለሌሎች ዘር ተጠቃሚዎች ሊቀርብ መቻሉን ለማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 55(1 መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የዕጽዋት ዘር አዋጅ ቁጥር 782/2005" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

   1. "ዘር" ማለት ለዕፅዋት ማራባት የሚያገለግል እውን ዘር፣ አኩራች፣ የተክል ቁርጥራጭ፣ ሥራ ሥር፣ ችግኝ ወይም ማንኛውም የተክል አካል ነው፤
   2. "የጸደቀ ዘር" ማለት በአገር ውስጥ የተመረተ ወይም ከውጭ የገባ ሆኖ የኢትዮጵያን የዘር ጥራት ደረጃ መስፈርቶችን ማሟላቱ የተረጋገጠለት ዘር ነው፤
   3. "የአስቸኳይ ጊዜ ዘር" ማለት ምንጩ የታወቀና አጣዳፊ የዘር እጥረት ሲያጋጥም ችግሩን ለመፍታት የሚውል ዘር ነው፤
   4. "የተደነገገ ዘር" ማለት ማንኛውም ዝቅተኛ የዘር መስፈርት ያሟላ ወይም አስፈላጊው የጥራት ቁጥጥር የተደረገለት እና በገበያ ላይ ያለ ወይም ለገበያ እንዲውል ሚኒስቴሩ በዚህ አዋጅ በተሰጠው ስልጣን መሰረት በሚያወጣው መመሪያ የተወሰነ ዘር ነው፤

5. “የኢትዮጵያ የዘር ጥራት ደረጃ መስፈርቶች” ማለት በኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ የወጡ የተደነገገ ዘር ዝቅተኛ የብቅለት፣ የዝርያ ጥራት፣ የዘር ንፁህነት እና ሌሎች ጥራት የሚገለጽባቸው ደረጃዎች ናቸው፤
6. “የዘር ትውልድ ደረጃ” ማለት ተከታታይነት ያለው የዘር ትውልድ ብዜት ደረጃ ነው፤
7. “አራቢ ዘር” ማለት የዝርያው ባለቤት ወይም ወኪሉ በቀጥታ እየተቆጣጠረው የሚባዛና የሚቀርብ የመጀመሪያ ዘር ትውልድ ደረጃ ነው፤
8. “ቅድመ መስራች ዘር” ማለት ከአራቢ ዘር የሚቀጥል የዘር ትውልድ ነው፤
9. “መስራች ዘር” ማለት ከቅድመ መስራች ዘር የሚቀጥል የዘር ትውልድ ነው፤
10. “የተመሰከረለት ዘር” ማለት በትውልዱ ከመስራች ዘር የሚቀጥል የዘር ትውልድ ወይም ከመስራች ዘር ከሚገኘው ከ1ኛው፣ ከ2ኛው እና ከ3ኛው የዘር ደረጃ የሚገኝ ነው፤
11. “ልውጥ ህያው” ማለት ሰው ሰራሽ የሆነ ወይም ከሌላ ህያው የተወሰደ ይሁን ከቅሪት የተወሰደ ወይም እንደ አዲስ የተቀመመ ባይተዋር ዘረመል ወይም ሌላ ንጥረ ነገር ስለተከተተበት የዘረመሎች ይዘቱ ወይም የባህሪው ክስተት የተለወጠበት ሕያው ነው፤
12. “የጥራት ቁጥጥር” ማለት አንድ ዘር የኢትዮጵያን የዘር ደረጃ መስፈርት ማሟላቱን ለማረጋገጥ የሚከናወን የቁጥጥር ሂደት ነው፤
13. “ጥራቱ የተገለፀ ዘር” ማለት አነስተኛ ይዞታ ባላቸው በተደራጁ እና በተመዘገቡ ወይም በተመዘገቡ አርሶ አደሮች አማካኝነት የጥራት ደረጃውን ጠብቆ የተመረተ ዘር ነው፤
14. “ገደብ የተጣለበት ዘር” ማለት ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በአገር ውስጥ ገበያ ላይ እንዳይውል፣ ወደ አገር እንዳይገባና ከአገርም እንዳይወጣ የተከለከለ ዘር ነው፤
15. “ዝርያ” ማለት በአንድ የዕፀዋት ቤተሰብ ውስጥ የታወቀ የመጨረሻ ዝቅተኛው ደረጃ ያለው ሆኖ፡-
    ሀ) ከአንድ የተወሰነ ጄኖታይፕ ወይም ከብዙ ጄኖታይፖች ጥምረት የሚመነጩ ባህርያት መታየት የሚገልጽ፤

ለ) ካሉት ባህርያት ቢያንስ በአንዱ ከማናቸውም ሌሎች የዕፅዋት ስብስቦች የሚለይ፤ እና

ሐ) ባህርያቱን ሳይቀይር መራባት በመቻሉ ምክንያት እንደ አንድ ዓይነት ሊወሰድ የሚችል፤

የዕፅዋት ስብስብ ነው፤

16. "ሚኒስቴር" ማለት የግብርና ሚኒስቴር ነው፤[12]
17. "ዝርያ መልቀቅ" ማለት የተመዘገበው ዝርያ ለአገር ውስጥ ገበያ እንዲባዛ፣ እንዲመረት ወይም ዘሩ ለሽያጭ እንዲውል መፍቀድ ነው፤
18. "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 47(1) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችንም ይጨምራል፤
19. "የክልል ባለሥልጣን" ማለት በክልል ደረጃ ግብርናን በተመለከተ ሃላፊነት የተሰጠው አካል ነው፤
20. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
21. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል።

3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ አዋጅ በማንኛውም ዘር ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
2. ይህ አዋጅ፡-

ሀ) ማንኛውም ሰው ከእርሻ ምርቱ ጠብቆ በሚይዘውና በሚጠቀምበት ዘር፤

ለ) አነስተኛ የመሬት ይዞታ ባላቸው አርሶ አደሮች ወይም ከፊል አርብቶ አደሮች መካከል በሚደረግ ከእርሻ ምርት ተጠብቆ የሚያዝ የዘር ልውውጥ ወይም ሽያጭ፤

ሐ) ለምርምር ሥራ በሚውል ዘር፤ እና

መ) በደን ዘር፤

ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።

[12] በ25)08 (2011 አ. 1097 አንቀጽ 9(6 መሰረት የግብርና ሚኒስቴር ሆኗል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ዝርያ ስለመልቀቅና ስለመመዝገብ

### 4. ዝርያዎችን ስለመልቀቅ

1. ማንኛውም ዝርያ በአገር ውስጥ ተመርቶ ለአገር ውስጥ ወይም ለውጭ ገበያ ከመዋሉ በፊት በሚኒስቴሩ መጽደቅና መለቀቅ አለበት፡፡
2. ሚኒስቴሩ በየጊዜው የዕጩ ዝርያዎችን ቴክኒካዊ ብቃት የሚገመግሙ የዝርያ ገምጋሚ ኮሚቴዎችን እና የኮሚቴዎቹን ሪፖርቶች መሠረት በማድረግ ስለዝርያ መለቀቅ የውሳኔ ሀሳብ የሚያቀርብ ብሔራዊ የዝርያ አጽዳቂ ኮሚቴ ያቋቁሟል፡፡
3. የሚቋቋሙት ኮሚቴዎች አወቃቀርና አሠራር ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

### 5. ብሔራዊ የዝርያ መዝገብ

1. ሚኒስቴሩ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 መሠረት የተለቀቁ ዝርያዎችን በብሔራዊ የዝርያ መዝገብ ውስጥ እንዲካተቱ ያደርጋል፡፡
2. ብሔራዊ የዝርያ መዝገቡ የዝርያዎቹ ባለቤቶች ለመስራት ሳይችሉ ወይም ፍቃደኛ ሆነው ሳይገኙ ሲቀር ሚኒስቴሩ የሚመድባቸውን የዝርያዎቹን ጥራት የሚንከባከቡና አራቢ ዘርን የሚያመርቱና የሚያቀርቡ ሌሎች ሰዎችን ዝርዝር ያካትታል።

## ክፍል ሦስት

## ስለዘር ማምረትና ማከፋፈል

### 6. ዘር ስለማምረት

1. ለገበያ የሚሆን ዘር በማምረት ተግባር ላይ የሚሰማራ ማንኛውም ሰው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መያዝ አለበት፡፡
2. ለገበያ የሚሆን ዘር በማምረት ተግባር ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው የውስጥ የዘር ጥራት ቁጥጥር ስርአት መዘርጋት ይኖርበታል።
3. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ዘር አምራች አግባብነት ባለው ማንኛውም ሌላ ህግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የተመዘገቡ ዝርያዎችን መነሻ ዘር ከሚያባዙ ተቋማት አራቢ ዘሮችን፣ ቅድመ መሥራች ዘሮችን እና መሥራች ዘሮችን ማግኘት ይችላል።

7. **<u>የተቀናጀ የምርት ዕቅድ</u>**

1. ለአገር ውስጥ ፍጆታ የሚከናወን የዘር ማምረት ስራ በተቀናጀ መልኩ በእቅድ የሚፈጸም ይሆናል፡፡
2. ሚኒስቴሩ የሚከተሉትን መረጃዎች የያዘ የዘር ምርት መረጃ ቋት ያዘጋጃል፡-
   - ሀ) ዓመታዊ የምርት ዕቅድና የፈጻሚዎች የሃላፊነት ድርሻ፤
   - ለ) ዓመታዊ የዘር ምርት በዘር ዓይነት፣ በአምራችና በጥቅል፤
   - ሐ) ዘር ለማምረት ጥቅም ላይ የዋለ መሬት፣ መሠረተ ልማት እና ሌሎች ግብዓቶች፤ እና
   - መ) ለብሔራዊ የዘር ምርት አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች መረጃዎች፡፡
3. የዘር ምርት መረጃ ቋት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 የተመለከተው የዘር አምራቾችና አከፋፋዮች መዝገብ አካል መሆን ወይም ከመዝገቡ ጋር የተያያዘ መሆን አለበት።

8. **<u>ዘር ስለማከፋፈል</u>**

ለገበያ የሚሆን ዘር በማከፋፈል ተግባር ላይ የሚሰማራ ማንኛውም ሰው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መያዝ አለበት፡፡

9. **<u>የአምራቾችና አከፋፋዮች መዝገብ</u>**

ሚኒስቴሩ የዘር አምራቾችና አከፋፋዮች መዝገብ ይይዛል፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ጥራት መቆጣጠርና ማረጋገጥ</u>

10. **<u>ደረጃዎች</u>**

ሚኒስቴሩ የዘር ደረጃዎችን በማዘጋጀት ረገድ ከኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ ጋር ይተባበራል፡፡

11. **<u>የዘር ጥራት ፍተሻ ላብራቶሪዎች</u>**

1. ሚኒስቴሩ ፡ -
   - ሀ) በአገር ውስጥ የሚገኙ የዘር ጥራት ፍተሻ ላብራቶሪዎች በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለው የአሰራር ስርዓት እንዲጠቀሙ ያመቻቻል፤
   - ለ) ለላብራቶሪዎች እውቅና ለመስጠት መስፈርቶችን ያዘጋጃል፤
   - ሐ) በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለው የዘር ፍተሻ ላብራቶሪ ያቋቁማል ወይም ይሰይማል፤

መ) በክልል ደረጃ የሚገኙ የዘር ፍተሻ ላብራቶሪዎች ደረጃቸውን የጠበቁ መሆናቸውን ያረጋግጣል።

2. የክልል ባለሥልጣን በክልሉ የሚገኙ የዘር ፍተሻ ላብራቶሪዎች እውቅና የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡

12. <u>የዘር ጥራት ቁጥጥር</u>

1. የክልል ባለሥልጣን በክልሉ ውስጥ በሚመረትና ለአገር ውስጥ ገበያ በሚውል ዘር ላይ የጥራት ቁጥጥር ያደርጋል፡፡

2. ሚኒስቴሩ፡-

ሀ) ለዘር የጥራት ቁጥጥር ፍተሻ የአሰራር ስርዓትና መስፈርቶችን ያወጣል፤

ለ) ከውጭ የሚገባ ዘር ከኢትዮጵያ የዘር ጥራት ደረጃዎች ጋር መጣጣሙን ያረጋግጣል፤

ሐ) ለውጭ ገበያ በአገር ውስጥ የሚመረት ዘር የጥራት ደረጃው ከተቀባዩ አገር ደረጃዎች ጋር መጣጣሙን ያረጋግጣል፤

መ) ውጭ አገር ለተቋቋሙ ለማናቸውም ከኢትዮጵያ የዘር ጥራት ምርመራ ስርዓት ጋር ተመሳሳይነት አላቸው ብሎ ላመነባቸው የዘር ጥራት አረጋጋጭ ድርጅቶችና ለምርመራ ውጤታቸው እውቅና ሊሰጥ ይችላል፡፡

13. <u>የዘር ጥራት የምስክር ወረቀቶች</u>

1. እያንዳንዱ የክልል ባለሥልጣን በክልሉ ውስጥ ተመርቶና ተዘጋጅቶ ለአገር ውስጥ ገበያ የሚቀርበው ዘር፡-

ሀ) ዝርያው በብሄራዊ የዝርያ መዝገብ ውስጥ የተመዘገበ መሆኑን፤

ለ) የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በተሰጠው ሰው የተመረተና የተዘጋጀ መሆኑን፤

ሐ) በዚህ አዋጅ መሰረት ጥራቱ የተፈተሸና ከኢትዮጵያ የዘር ጥራት ደረጃ መስፈርቶች ጋር የተጣጣመ መሆኑን፤ እና

መ) ሚኒስቴሩ በመመሪያ የወሰናቸውን ሌሎች መመዘኛዎች የሚያሟላ መሆኑን፤

ሲያረጋግጥ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው ደንብ የተወሰነውን የአገልግሎት ክፍያ አስከፍሎ የዘር ጥራት ምስክር ወረቀት ጥራቱ ለተመሰከረለት ዘር ወይም ጥራቱ ለተገለፀ ዘር ይሰጣል ።

2. ሚኒስቴሩ ከውጭ የገባ ዘር፡-

   ሀ) በብሔራዊ ዝርያ መዝገብ የተመዘገበ ዝርያ መሆኑን፤

   ለ) የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በተሰጠው የዘር አስመጪ የገባ መሆኑን፤

   ሐ) በዚህ አዋጅ መሰረት የተመረመረና ከኢትዮጵያ የዘር ጥራት ደረጃዎች ጋር የተጣጣመ መሆኑን፤ እና

   መ) ሚኒስቴሩ በመመሪያ የወሰናቸውን ሌሎች መመዘኛዎች የሚያሟላ መሆኑን፤

   ሲያረጋግጥ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው ደንብ የተወሰነውን የአገልግሎት ክፍያ አስክፍሎ የዘር ጥራት ምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

3. ሚኒስቴሩ ወደ ውጭ የሚላክ ዘር፡-

   ሀ) በብሔራዊ የዝርያ መዝገብ ውስጥ የተመዘገበ ዝርያ መሆኑን፤

   ለ) የተመረተውና የተዘጋጀው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በተሰጠው ሰው መሆኑን፤ እና

   ሐ) ሚኒስቴሩ በመመሪያ የወሰናቸውን ሌሎች መመዘኛዎች የሚያሟላ መሆኑን፤

   ሲያረጋግጥ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው ደንብ የተወሰነውን የአገልግሎት ክፍያ አስክፍሎ የዘር ጥራት ምስክር ወረቀት ይሰጣል።

4. ማንኛውም የዘር ጥራት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት፡-

   ሀ) በሀሰተኛ፣ በተሳሳተ ወይም ባልተሟላ መረጃ የተገኘ ከሆነ፤ ወይም

   ለ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 15 መሠረት በዘሩ ላይ የድህረ ቁጥጥር ሙከራ ተካሂዶ ወይም እንደገና የጥራት ፍተሻ ተከናውኖ የኢትዮጵያን የዘር ደረጃዎች አሟልቶ ካልተገኘ፤

   ይሰረዛል፡፡

5. ሚኒስቴሩ ወይም የክልል ባለሥልጣን የዘር ጥራት ምስክር ወረቀት ከመሰረዙ በፊት ለባለቤቱ በማሳወቅ ቅሬታው የሚደመጥበትን እድል ይሰጠዋል።

14. <u>መለያ ምልክት ስለማድረግ</u>

ማንኛውም ዘር በሚኒስቴሩ መመሪያ መሠረት መለያ ምልክት ሳይደረገበት ለአገር ውስጥ ወይም ለውጭ ገበያ ሊቀርብ አይችልም።

15.**<u>ድህረ ቁጥጥር</u>**

ማንኛውም ዘር የዘር ጥራት የምስክር ወረቀት ተሰጥቶት ለገበያ የቀረበ ቢሆንም የጥራት ደረጃ መስፈርቱን አለማሟላቱን ለመጠርጠር ምክንያት ሲኖር ከተሰራጨው ዘር ላይ ናሙና ተወስዶ የላብራቶሪ ፍተሻ ይደረጋል፡፡

16.**<u>የጥራት ደረጃ መስፈርቶችን ስለማያሟላ ዘር</u>**

1. ፍተሻ የተደረገበት ዘር የጥራት ደረጃ መስፈርቶችን ካላሟላ የዘር ደረጃው ዝቅ እንዲል ወይም ውድቅ እንዲሆን ይደረጋል፡፡
2. ዘሩ ውድቅ እንዲሆን የተደረገበት ማንኛውም ሰው የሚከተሉት አማራጮች ሊሰጡት ይችላሉ፦
   ሀ) በራሱ ማሳ ላይ እንደገና በመዝራት በጥቅም ላይ ማዋል፤ ወይም
   ለ) ዘሩ የተበከለ ወይም በማናቸውም ምክንያት ለምግብ ወይም ለመኖ አገልግሎት የማይውል ሆኖ እስካልተገኘ ድረስ ለምግብነት ወይም ለመኖነት እንዲውል ለገበያ ማቅረብ፡፡
3. ውድቅ እንዲሆን የተደረገ ዘር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2 መሠረት በጥቅም ላይ ሊውል የማይችል ሆኖ ሲገኝ በሚኒስቴሩ መመሪያ መሠረት እንዲወገድ ይደረጋል፡፡

17.**<u>ዘር ከውጭ ስለማስገባትና ወደ ውጭ ስለመላክ</u>**

1. ማንኛውም ሰው በሚኒስቴሩ መመሪያ የተወሰኑ መስፈርቶችን አሟልቶ የማስገቢያ ወይም የመላኪያ ፈቃድ ከሚኒስቴሩ ካልተሰጠው በስተቀር ዘርን ወደ አገር ውስጥ ማስገባት ወይም ወደ ውጭ መላክ አይችልም።
2. ለዘር ማባዛት ዓላማ ወደ አገር ውስጥ የሚገባ ማንኛውም ዝርያ በብሔራዊ ዝርያ አጽዳቂ ኮሚቴ በፀደቀው አሠራር መሠረት በቅድሚያ የዝርያ ማረጋገጫና የማላመድ ሙከራ የተካሄደበት እና በዚህ አዋጅ መሠረትም በብሔራዊ የዝርያ መዝገብ የተመዘገበ መሆን አለበት፡፡ ሆኖም የግብርና ወጭ ንግድን ለማጠናከር ሲባል ያልተመዘገበ ዘር አባዝቶ ወይም ምርት አምርቶ ለውጭ ገበያ የሚቀርብበት ልዩ ሁኔታ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፡፡
3. ልውጥ ህያው ዘር ወደ አገር ውስጥ ሊገባ የሚችለው ሚኒስቴሩ አግባብ ካለው ህግ ጋር ስለ መጣጣሙ ከአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በቅድሚያ ማረጋገጫ ሲያገኝ ይሆናል።

4. ማንኛውም ሰው፡-
   ሀ) ገደብ የተጣለበት ዘርን ወደ ውጭ አገር መላክ ወይም ወደ አገር ውስጥ ማስገባት፤ ወይም
   ለ) በሁለተኛው ትውልድ ራሱን የማይደግም ተርሚኔተር ዘረ-መል ቴክኖሎጂ ያለበትን ዘር ወደ አገር ውስጥ ማስገባት፤

   አይችልም።

18. <u>የአስቸኳይ ጊዜ ዘር ስለማቅረብ</u>

በኢትዮጵያ ውስጥ አጣዳፊ የዘር እጥረት ሲያጋጥም ሚኒስቴሩ የአስቸኳይ ጊዜ ዘር እጥረት መፈጠሩን በይፋ የማሳወቅና ችግሩ ላጋጠማቸው አካባቢዎች የአስቸኳይ ጊዜ ዘር እንዲቀርብ የመፍቀድ ሥልጣን ይኖረዋል።

## <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት</u>

19. <u>የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አስፈላጊነት</u>

1. ማንኛውም የዘር አስመጪ ወይም ላኪ ከሚኒስቴሩ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት፡፡
2. ማንኛውም የዘር አምራች፣ አዘጋጅ፣ ጅምላ ሻጭ፣ አከፋፋይ ወይም ቸርቻሪ፡-
   ሀ) ሥራው በአንድ ክልል ውስጥ ተወስኖ የሚካሄድ ሲሆን ከክልል ባለስልጣን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት፤ ወይም
   ለ) ሥራው ከአንድ በላይ የሆኑ ክልሎችን የሚሸፍን ሲሆን ከሚኒስቴሩ የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት፡፡

20. <u>የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለመስጠት</u>

1. ሚኒስቴሩ ወይም የክልል ባለስልጣን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የቀረበለትን ማመልከቻ መርምሮ አመልካቹ በሚኒስቴሩ መመሪያ የተወሰኑትን መስፈርቶች የሚያሟላ መሆኑን ሲያረጋግጥ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው ደንብ የተወሰነውን የአገልግሎት ክፍያ አስከፍሎ የተጠየቀውን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡
2. ሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ያለው የክልል ባለስልጣን የአመልካቹ የብቃት ማረጋገጫ ጥያቄ ተቀባይነት ያላገኘ ከሆነ የክልከላውን ምክንያት በመግለጽ ለአመልካቹ ማሳወቅ አለበት፡፡

3. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቶች ጸንተው የሚቆዩበት ጊዜና የሚታደሱበት ሁኔታ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

21.<u>የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትን ስለማገድና መሰረዝ</u>

1. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ማንኛውም ሰው፡-
   ሀ) የምስክር ወረቀቱ የተሰጠባቸውን ሁኔታዎች ጠብቆ ማቆየት ካልቻለ፤ ወይም
   ለ) ይህን አዋጅ ወይም አዋጁን ለማስፈጸም የወጣ ደንብን ወይም መመሪያን ተላልፎ ሲገኝ፤

   ሚኒስቴሩ ወይም የክልል ባለስልጣን ጉድለቶቹን ተገቢ በሆነና ተለይቶ በተገለጸ የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲያስተካክል በማስገንዘብ የምስክር ወረቀቱን አግዶ ሊያቆየው ይችላል፡፡
2. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ማንኛውም ሰው፡-
   ሀ) የምስክር ወረቀቱን ያገኘው ሀሰተኛ ማስረጃ በማቅረብ ሆኖ ከተገኘ፤
   ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1 መሠረት ለምስክር ወረቀቱ መታገድ ምክንያት የሆነውን ጉድለት በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማስተካከል ካልቻለ፤ ወይም
   ሐ) የዚህን አዋጅ አንቀጽ 26 በመተላለፍ የወንጀል ድርጊት ፈጽሞ ከተገኘ፤

   ሚኒስቴሩ ወይም የክልል ባለስልጣን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱን ሊሠርዝ ይችላል፡፡
3. ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው የክልል ባለስልጣን የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን እንደሰረዘ በምስክር ወረቀቱ ላይ ተመስርቶ የተሰጠው የንግድ ፈቃድ እንዲሰረዝ ለሚመለከተው ፈቃድ ሰጭ አካል በጽሁፍ ያሳውቃል።

22.<u>መረጃ ስለመያዝና ተደራሽ ስለማድረግ</u>

ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ባለቤት፡-

1. እንደአግባቡ የእያንዳንዱን ማሳና የተመረተ ዘር፣ የተዘጋጀ ዘር፣ ያስመጣውን ዘር፣ ወደ ውጭ የላከውን ዘር፣ ያከፋፈለውን ወይም የቸረቸረውን ዘር በዝርዝር መዝግቦ መያዝ፤
2. የላብራቶሪ ምርመራ የተካሄደባቸውን የዘር ናሙናዎች ቢያንስ ለአንድ ዓመት ይዞ ማቆየት፤ እና

3. የያዛቸውን መረጃዎችና ናሙናዎች በዚህ አዋጅ አንቀጽ 23 መስረት በተመደበ ኢንስፔክተር ሲጠየቅ ማቅረብ፤

አለበት፡፡

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 23.የዘር ኢንስፔክሽን

1. ሚኒስቴሩ እና እያንዳንዱ የክልል ባለስልጣን የዚህን አዋጅና በአዋጁ መሠረት የወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን ተፈፃሚነት ለማረጋገጥ የዘር ኢንስፔክተሮችን ይመድባል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተመደበ የዘር ኢንስፔክተር፡-
   ሀ) አንድ ዘር አግባብነት ካላቸው የኢትዮጵያ የዘር ደረጃ መስፈርቶች ጋር የተጣጣመ መሆኑን በላብራቶሪ ምርመራ ለማረጋገጥ የዘሩን ናሙና ለመውሰድ ይችላል፤
   ለ) ለዚህ አዋጅና በአዋጁ መሠረት ለወጡ ደንቦችና መመሪያዎች አፈጻጸም አግባብነት ያላቸው የምስክር ወረቀቶች፣ የማስገቢያ ፈቃዶች፣ መዛግብቶችና ሌሎች ሰነዶች እንዲቀርቡለት መጠየቅና መመርመር እንዲሁም ኮፒ ማድረግ ይችላል፤
   ሐ) ይህ አዋጅና በአዋጁ መሠረት የወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ በማናቸውም የመንግስት የስራ ሰዓት ወደ ማናቸውም የዘር ማሳ፣ የዘር መጋዘን ወይም የዘር ማዘጋጃ ተቋም በመግባት ወይም በማናቸውም ሰዓት ማንኛውንም ዘር የጫነ ተሽከርካሪ በማስቆም ኢንስፔክሽን ማካሄድ ይችላል፡፡
3. የዘር ኢንስፔክተር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የዘር ኢንስፔክሽን ለማካሄድ በሚኒስቴሩ ወይም በክልል ባለሥልጣን የተሰጠውን የመታወቂያ ካርድ ለሚመለከተው ሰው ማሳየት አለበት፡፡
4. የዘር ኢንስፔክተር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የዘር ኢንስፔክሽን ሲያከናውን ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው የመተባበር ግዴታ አለበት።
5. ሚኒስቴሩ በአገሪቷ ውስጥ ተመሳሳይነት ያለው የቁጥጥር አሠራር ስርዓት እንዲኖር ያደርጋል፤ እንደ አስፈላጊነቱም ለክልሎች የጥራት ቁጥጥር ሥልጠናና ድጋፍ ያደርጋል፡፡

**24.የፌዴራልና የክልል መንግስታት ትብብር**

ይህን አዋጅና በአዋጁ መሠረት የሚወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን ወጥነት ባለው መልኩ ለመተግበር እንዲቻል የክልል ባለስልጣናት ከግብርና ሚኒስቴርና እርስ በርሳቸው በትብብር ይሰራሉ፡፡

**25.ስለቅሬታ አቀራረብ**

1. አዋጁን መሠረት ተደርጎ በተሰጠ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ሰው ውሣኔውን ካወቀበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለሚኒስቴሩ ወይም ለክልሉ ባለስልጣን ማቅረብ ይችላል፡፡
2. ማንኛውም ሰው በሚኒስቴሩ ወይም በክልል ባለስልጣን የተሰጠው ውሳኔ ካላረካው ቅሬታውን ለሚመለከተው የፍትህ አካል በ30 ቀናት ውስጥ ማቅረብ ይችላል፡፡

**26.ወንጀሎችና ቅጣቶች**

1. ማንኛውም ሰው ፡-
   ሀ) በዚህ አዋጅ መሰረት ያልተመዘገበና የጥራት ቁጥጥር ያልተደረገበት ወይም የኢትዮጵያን የዘር ደረጃ መስፈርቶችን የማያሟላ ዘር ለአገር ውስጥ ገበያ ያቀረበ፤ ወይም
   ለ) በዘር ማምረት፣ ማዘጋጀት፣ ግብይት ወይም የጥራት ቁጥጥር ሂደት የማጭበርበር ድርጊት እንዲፈፀም መደለያ የሰጠ፤

   እንደሆነ በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከአምስት እስከ አሥር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከ ብር 50,000 እስከ ብር 100,000 በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡
2. ማንኛውም ሰው፡-
   ሀ) የተሳሳተ የዘር ናሙና ለምርመራ ያቀረበ፤
   ለ) በዚህ አዋጅ መሠረት የተወሰደ ማንኛውንም ናሙና የቀየረ፤
   ሐ) በዚህ አዋጅ መሠረት ማንኛውንም ማመልከቻ ሲያቀርብ የተሳሳተ መረጃ የሰጠ፤
   መ) የመለያ ምልክት አደራረግን አስመልክቶ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 14 የተደነገገውን ያላከበረ፤ ወይም

ሠ) በዚህ አዋጅ መሠረት የተዘጋጀን ወይም የተሰጠን መዝገብ፣ የምስክር ወረቀት፣ የመለያ ምልክት ወይም ሌላ ሕጋዊ ሠነድ የለወጠ፣ የደለዘ ወይም ያጠፋ፤

እንደሆነ በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከሦስት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከብር 30,000 እስከ ብር 50,000 በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

3. ማንኛውም ሰው፡-

ሀ) የዘር ኢንስፔክተር ሥራውን ሲያከናውን ያልተባበረ ወይም በዚህ አዋጅ የተሰጠውን ሥልጣን በሥራ ላይ እንዳያውል ያደናቀፈ፤ ወይም

ለ) የዚህን አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች የተላለፈ፤

እንደሆነ በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ እስከ አንድ ዓመት በሚደርስ እስራትና ከብር 5,000 እስከ ብር 10,000 በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል።

4. ማንኛውም የሚኒስቴሩ ወይም የክልል ባለስልጣን ኃላፊ ወይም ሠራተኛ መደለያ በመቀበል ወይም በዝምድና ወይም በሌላ ግላዊ ግንኙነት በዚህ አዋጅ ወይም በአዋጁ መሠረት በወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች የተደነገጉ ተፈላጊ ሁኔታዎች ሳይሟሉ የዝርያ ምዝገባ እንዲከናወን ወይም የምስክር ወረቀት እንዲሰጥ ወይም የማስገቢያ ፈቃድ ወይም የማስወጫ ፈቃድ እንዲሰጥ ያደረገ እንደሆነ በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከአሥር እስከ አሥራ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከብር 20,000 እስከ ብር 50,000 በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል።

27. <u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን</u>

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል።
2. ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1 መሰረት የሚወጣውን ደንብ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

28. <u>የተሻሩ ህጎች</u>

የዕፅዋት ዘር አዋጅ ቁጥር 206/1992 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

29. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ የካቲት 8 ቀን 2005 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## ደንብ ቁጥር 375/2008 ዓ.ም

## የዕጽዋት ዘር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀጽ 5 እና በዕጽዋት ዘር አዋጅ ቁጥር 782/2005 አንቀጽ 27(1) መሠረት የሚከተለውን ደንብ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የዕጽዋት ዘር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 375/2008" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

   1. "አዋጅ" ማለት የዕጽዋት ዘር አዋጅ ቁጥር 782/2005 ነው፤
   2. በአዋጁ አንቀጽ 2 ውስጥ የተሰጠ የቃላት ትርጓሜ ተፈጻሚ ይሆናል፤
   3. "አዳቃይ" ማለት፡-

      ሀ) አዲስ የዕጽዋት ዝርያ አዳቅሎ ያወጣ ወይም በተገኘው አዲስ ዝርያ ላይ ማሻሻያ ያደረገ፤

      ለ) አዲስ የዕጽዋት ዝርያ አዳቅሎ ያወጣና በተገኘው አዲስ ዝርያ ላይ ማሻሻያ ያደረገ ሰውን ቀጥሮ ወይም ሥራውን ተኮናትሮ ያሰራ፤ወይም

      ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) እና(ለ) የተጠቀሱትን ሰዎች መብት ተክቶ የያዘ፣ ሰው ነው፤
   4. "ለማጓጓዝ የተዘጋጀ ጭነት" ማለት በአንድ የዕጽዋት ጤንነት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ብቻ ከአንዱ አገር ወደ ሌላ አገር የሚጓጓዝ ዕጽዋት ወይም የዕጽዋት ምርት መጠን ነው፤
   5. "መያዣ" ማለት ከረጢት፣ ጠርሙስ፣ ኬሻ፣ ሳጥን፣ በርሜል፣ ሻንጣ ወይም ቦርሳ፣ ቆርቆሮ፣ መጠቅለያ ያለው መያዣ ወይም ሌላ ዘር ለማስቀመጥ የሚያገለግል መያዣ ነው፤
   6. "ከሌላው የተለየ፣ ወጥነት ያለው እና ሊቀያየር የማይችል የዝርያ ባህሪ ሙከራ" ማለት ለተለያዩ የሰብል አይነቶች የወጣውን ከሌላው የተለየ፣ ወጥነት ያለው እና

ሊቀያየር የማይችል የዝርያ ባህሪ መስፈርት እጩ ዝርያው ማሟላት አለሚሟላቱ የሚረጋገጥበት የሙከራ አይነት ነው፤

7. "የማሳ ቁጥጥር" ማለት በኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ በወጣው የዘር ማሳ መስፈርት መሰረት ማሳው ደረጃውን ማሟላቱን ለማረጋገጥ የሚደረግ ሕጋዊ የማሳ ቁጥጥር ነው፤

8. "የመስክ መስፈርት" ማለት ዘርን በመስክ አምርቶ ለማጸደቀ አስፈላጊ የሆኑ መርሀ ግብሮች አካል ሆኖ ከሌላው ተመሳሳይ ሰብል ዓይነት)ኦፍታይፕ ያለው የአጎራባች ማሳ ርቀት፣ የሰብልፈረቃ፣ በማሳው ውስጥ የሚገኝ የተለየ ዝርያና ኦፍታይፕ፣ አረምና በሽታ የሚያካትት መስፈርት ነው፤

9. "ኦፍታይፕ" ማለት አንድ ዕጽዋት ከሚታወቅበት የእድገት እና ውጫዊ መገለጫዎች ማለትም በቅጠሉ ወይም አበባው፣ በቀለሙ ወይም በቅርጹ ወይም ቁመቱ የመሳሰሉት ተቀባይነት ካገኘው ከዝርያው ባህርያት ለወጥ ብሎ የታየ ከሆነ ነው፤

10. "አጎራባች ማሳ ርቀት" ማለት በዘረመል ወይም በንክኪ የሚፈጠረውን ብክለትና የዝርያ መቀላቀልን ለመከላከል በሁለት ተመሳሳይ ወይም ተቀራራቢ የሰብል ዓይነቶች መካከል የሚኖረው ዝቅተኛ የርቀት መጠን ነው፤

11. "መለያ ምልክት" ማለት ማንኛውም በዘር መያዣ ዕቃ ላይ የዘሩን ምንነት ለመለየት የተለጠፈ የጽሑፍ ወይም የሥዕል መግለጫ ነው፤

12. "የብሔራዊ የዝርያ ብቃት ማረጋገጫ ሙከራ" ማለት አዲስ ዝርያዎችን ለእርሻ ሥራ ለመጠቀም ያለው ፋይዳ እና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ባህሪያቸውን ከአካባቢው ወይም ቀደም ሲል ከተለቀቀ ዝርያ ጋር ለማነጻጸር የሚደረግ ሙከራነው፡

13. "የብሔራዊ ዝርያ የብቃት ሙከራ ግምገማ የቴክኒክ ኮሚቴ" ማለት አዲስ ዕጩ ዝርያዎች እንዲለቀቁ የሚቀርቡ ማመልከቻዎችን ለመገምገምና የዉሳኔ ሃሳብ ለማቅረብ በብሔራዊ ደረጃ የተቋቋመ ኮሚቴ ነው፤

14. "ብሔራዊ የዝርያ መዝገብ" ማለት በሀገር አቀፍ ደረጃ የተለቀቁ ዝርያዎች የሚመዘገቡበት የዝርያ መዝገብ ነው፤

15. "የብሔራዊ ዝርያ አጽዳቂ ኮሚቴ" ማለት የብሔራዊ ዝርያ የብቃት ሙከራ ግምገማ የቴክኒክ ኮሚቴ ሪፖርትን መሰረት በማድረግ ሚኒስቴሩ የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት የውሳኔ ሃሳብ ለማቅረብ የተቋቋመ ኮሚቴ ነው፤

16. “ቋሚ ስያሜ” ማለት አዲስ የተለቀቀ ዝርያ በብሔራዊ ዝርያ መዝገብ ውስጥ ሲመዘገብ የሚሰጥ ስያሜ ነው፤
17. “የታሸገ” ማለት የዘር መያዣውን በሚመለከት መያዣው በሚታሸግበት ወቅት እንዲጠብቅ የተደረገ እና እሽጉ የተከፈተ እንደሆነ ግን ስለመከፈቱ አመላካች የሆነ ማስረጃ የሚሆን ነገር ሳይተው እንዳይከፈት ተደርጎ የዘር መያዣው የታሸገ ነው።
18. “የዘር ሰርተፍኬሽን” ማለት ለሽያጭ የሚቀርበው ዘር ሕጋዊ የዘር ጥራት ቁጥጥር የሚደረግበት የጥራት ማረጋገጫ ሥርዓት ነው፤
19. “መጠኑ የታወቀ የዘር ክምችት” ማለት ወጥነት ያለው እና በአካል ሊለይ የሚችል መጠኑ የታወቀ ዘር ነው።

## ክፍል ሁለት

## ዝርያን ስለመልቀቅና ስለመመዝገብ

### 3. ዝርያዎችን ለመልቀቅ የሚያስፈልጉ መስፈርቶች

1. እጩ ዝርያዎች ከመለቀቃቸው በፊት ከሌላው የተለየ፣ ወጥነት ያለው እና ሊቀያየር የማይችል የዝርያ ባህሪ እና ዝርያውን ለእርሻ ሥራ ለመጠቀም ያለው ፋይዳ እና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ መስፈርቶቻቸው መገምገም አለባቸው።
2. የዝርያው ከሌላው የተለየ፣ ወጥነት ያለው እና ሊቀያየር የማይችል የዝርያ ባህሪ ሲገመገም የሚከተሉትን ባሕሪያት ማሟላት አለበት፦
   ሀ) በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ባህሪያት ከሌሎች ከተለቀቁ ዝርያዎች በግልጽ የሚለይ፤
   ለ) በባህሪው ወጥነት ያለው፤ እና
   ሐ) በተደጋጋሚ ሲባዛ የማይቀየር ባህሪ ያለው።
3. ዝርያውን ለእርሻ ሥራ ለመጠቀም ያለው ፋይዳ እና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ሲገመገም የሚከተሉትን ባህሪያት ማሳየት አለበት፦
   ሀ) ከተለቀቁት ዝርያዎች በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ እንደ ምርት መጠን፣ በሽታን የመቋቋም ብቃት፣ ሰብል የሚደርስበት ወቅት እና በመሳሰሉት ባህሪያት መብለጡን፣
   ለ) በተጠቃሚዎች ዘንድ በከፍተኛ ደረጃ መፈለጉን፡፡

4. **<u>ዝርያ ለማስለቀቅ የሚቀርብ ማመልከቻ</u>**

   1. ማንኛውም ሰው ዝርያ ለማስለቀቅ ዝርያው ከሌላው የተለየ፣ ወጥነት ያለው እና ሊቀያየር የማይችል የዝርያ ባህሪ ያለው ስለመሆኑ እና ብሔራዊ የዝርያ ብቃት ማረጋገጫ ሙከራ እንዲሰራለት ማመልከቻውን ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።
   2. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አፈጻጸም ሚኒስቴሩ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፡

5. **<u>የዝርያ ሙከራ</u>**

ሚኒስቴሩ በተለያዩ ሥነምህዳር ቀጠናዎች የብሔራዊ ዝርያ ብቃት ማረጋገጫ እና ከሌላው የተለየ ወጥነት ያለው እና ሊቀያየር የማይችል የዝርያ ባህሪ ሙከራዎች በማከናወን እና ሪፖርት በማዘጋጀት ለብሔራዊ የዝርያ ብቃት ሙከራ ገምጋሚ ቴክኒክ ኮሚቴ ለግምገማ ያቀርባል።

6. **<u>ዝርያ ለመልቀቅ የሚደረግ ግምገማ</u>**

   1. የብሔራዊ ዝርያ ብቃት ሙከራ ገምጋሚ የቴክኒክ ኮሚቴ ዕጩ ዝርያዎችን የሚገመግመው በዚህ ደንብ አንቀጽ 3 በተቀመጠው መስፈርት መሰረት የቀረበውን መረጃ በመተንተን እና የመስክ ግምገማ በማካሄድ ይሆናል፡፡
   2. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አፈጻጸም ሚኒስቴሩ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል።

7. **<u>የብሔራዊ ዝርያ አጽዳቂ ኮሚቴ የውሳኔ ሃሳብ</u>**

   1. የብሔራዊ ዝርያ አጽዳቂ ኮሚቴ ከዝርያ ሙከራ ገምጋሚ ኮሚቴ በሚቀርበው ሪፖርት መሰረት ሚኒስቴሩ የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት መነሻ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል።
   2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለሚኒስቴሩ የሚቀርብ የውሳኔ ሀሳብ፡

      ሀ) ዝርያው ሙሉ በሙሉ እንዲለቀቅ፤

      ለ) ዝርያው በጊዜያዊነት እንዲለቀቅ፤

      ሐ) ዝርያው በድጋሚ እንዲሞከር፡ ወይም

      መ) ዝርያው ውድቅ እንዲሆን፡

የሚጠይቅ ሊሆን ይችላል፡፡

8. **<u>ቋሚ ስያሜ</u>**

   1. አዳቃዩ ለአዲሱ ዝርያ ቋሚ ስያሜ የሚሰጠው በሚከተለው መሰረት ይሆናል፦

      ሀ) አጭር እና ግልጽ፤

      ለ) ዝርያውን ለመለየት የሚያስችል ሆኖ ነገር ግን ቁጥሮችን ብቻ ያልያዘ፤

ሐ) የዝርያውን ባህሪ ማንነት የማያደናግርና የማያሳስት፤

መ) በብሔራዊ የዝርያ መዝገብ ከተመዘገቡ የሌሎች ዝርያ ስያሜ ጋርተመሳሳይነት የሌለው፤ እና

ሠ) በኢትዮጵያ ውስጥ ወይም በሌላ አገር ቀደም ብሎ የተሰጠን መብት ሊጎዳ የማይችል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተውን መስፈርት አለመሟላት ስያሜውን ውድቅ ለማድረግ ምክንያት ይሆናል፡፡
3. የዝርያ ስያሜን አስቀድሞ ያስመዘገበ ሰው ከበቂ ምክንያት ጋር ለሚኒስቴሩ ማመልከቻ በማቅረብና የዕጽዋት ዘር ብቃት ማረጋገጫና የተያያዥ አገልግሎቶችን ክፍያ ተመን መወሰኛ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ የተወሰነውን ክፍያ በመፈጸም በሚኒስቴሩ ተቀባይነት ሲያገኝ የዝርያ ስያሜን አስቀይሮ ለማስመዝገብ ይችላል፡፡

9. <u>ምዝገባ</u>

ዝርያው እንዲለቀቅ ተቀባይነት ሲያገኝ ሚኒስቴሩ የሚከተሉትን መረጃዎች በብሄራዊ ዝርያ መዝገብ ውስጥ ይመዘግባል፡-

1. የሰብሉ ስም፣ የዝርያው ስም፣ የምዝገባ ቁጥር፣ የምዝገባ ቀን፣ የተለቀቀበት ዓመት፣ ዝርያው ከሌላው የተለየ፣ ወጥነት ያለው እና ሊቀያየር የማይችል የዝርያ ባህርይ እና አስፈላጊ ሲሆን የዝርያው የትውልድ ሐረግ፤
2. እንደአስፈላጊነቱ የተለቀቀበት ሁኔታ በገደብ፣ ለተወሰነ ወይም ለብዙ አካባቢዎች መሆን አለመሆን፤
3. ተጨማሪ መረጃዎች ማለትም የምርት አቅም፣ የመላመድ ሁኔታ፣ የጥራት ሁኔታ፣ በሽታና ተባይ የመቋቋም፤ እና
4. የዝርያው አስመዝጋቢ ወይም የዝርያውን ባህሪ ጠባቂ ሰው ስም፡፡

10. <u>ብሔራዊ የዝርያ መዝገብ</u>

ሚኒስቴሩ፡-

1. የብሔራዊ የዝርያ መዝገብን አደራጅቶ ይይዛል፤
2. አዲስ የተለቀቁ ዝርያዎችን በየጊዜው በብሔራዊ የዝርያ መዝገብ ይመዘግባል፤
3. ከምርት ውጭ የሆኑ ዝርያዎችን ከብሔራዊ የዝርያ መዝገብ ውስጥ ያስወጣል፤
4. በየአመቱ የዝርያ መዝገብን ያሳትማል፤ ለባለድርሻ አካላትም ተደራሽ ያደርጋል፡፡

11. **ምዝገባን ስለመሰረዝ**

1. ሚኒስቴሩ የማንኛውንም ዝርያ ምዝገባ በሚከተሉት ምክንያቶች ሊሰርዝ ይችላል፦
   ሀ) ለመለቀቁ ምክንያት የሆነውን ባህሪያት ካጣ ወይም መሠረታዊ ባህሪያቱን ከለወጠ ወይም ከቀነሰ፤
   ለ) በሰው ወይም በእንስሳት ጤንነትና በአካባቢ ደህንነት ላይ አደጋ የሚያስከትል ሆኖ ሲገኝ፤
   ሐ) አስቀድሞ በሌላ ስም ከተመዘገበ ዝርያ ጋር ልዩነት የሌለው ሆኖ ከተገኘ፤
   መ) ዝርያው በሐሰተኛ፣ በተሳሳተ ወይም ትክክል ባልሆነ መረጃ ላይ ተንተርሶ የተለቀቀ ወይም የተመዘገበ ከሆነ፡፡
2. በዚህ አንቀጽ መሰረት ሚኒስቴሩ የዝርያ ምዝገባን ከመሰረዙ በፊት ለአስመዝጋቢው በጽሁፍ በማሳወቅ በ15 የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታው የሚደመጥበትን እድል መስጠት አለበት፡፡

12. **የአገልግሎት ክፍያ**

1. ዝርያን ለማስለቀቅና ለማስመዝገብ የሚፈጸም የአገልግሎት ክፍያ በአዋጁ አንቀጽ 27(1) መሠረት በወጣው ደንብ የተወሰነው ክፍያ ይሆናል፡፡
2. ማንኛውም የአገልግሎት ክፍያ የሚከፈለው የአገልግሎት ጥያቄ ማመልከቻው በሚቀርብበት ወቅት ይሆናል፡፡

13. **የዝርያ አለቃቀቅና ምዝገባ ሂደትን ስለማስተዳደር**

ሚኒስቴሩ የብሄራዊ ዝርያ አለቃቀቅና ምዝገባ ሂደትን ለማስተዳደር የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፡-

1. አዲስ ዝርያዎችን ለማስለቀቅ የሚቀርቡ ማመልከቻዎችን በመመርመር ይቀበላል፤
2. የብሔራዊ ዝርያ ሙከራ ለማካሄድ ተስማሚ በሆኑ ሥነ-ምህዳር ቦታዎች ላይ የኮንትራት ውል ይዋዋላል፣ ሙከራዎችንም ያከናውናል፤
3. ለሁለት የምርት ወቅቶች ቢያንስ ሶስት ተመሳሳይነት ባላቸው ሥነምህዳር ቦታዎች ላይ ከሌላው የተለየ፣ ወጥነት ያለው እና ሊቀያየር የማይችል የዝርያ ባህሪ እና የብሔራዊ ዝርያ ሙከራ ያካሂዳል፤
4. ዝርያው ከኢትዮጵያ ውጪ ከዚህ በፊት የተለቀቀ ሆኖ አገር ውስጥ ለማስገባት የተፈለገ ከሆነ ተስማሚ በሆነ ሥነ-ምህዳር ዝርያው ለእርሻ ሥራ ለመጠቀም

ያለው ፋይዳ እና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እና ከሌላው የተለየ፣ ወጥነት ያለው እና ሊቀያየር የማይችል የዝርያ ባህሪ ሙከራዎችን ቢያንስ ለአንድ የሰብል ወቅት ያካሂዳል፤

5. ለብሔራዊ ዝርያ ብቃት ሙከራ ገምጋሚ ቴክኒካል ኮሚቴ አባላት ተልዕኮአቸውን እንዲወጡ የሎጂስቲክ ድጋፍ እንዲያገኙ ያመቻቻል፤
6. የብሔራዊ ዝርያ ብቃት ሙከራ ገምጋሚ የቴክኒክ ኮሚቴ ሪፖርቶችን ይቀበላል፣ ይተነትናል፣ የማጠቃለያ ሪፖርትም ያዘጋጃል፣ እንዲሁም ከሌላው የተለየ፣ ወጥነት ያለው እና ሊቀያየር የማይችል የዝርያ ባህሪ ሪፖርት ይቀበላል፣ የብሔራዊ ዝርያ አጽዳቂ ኮሚቴ ስብሰባን ያዘጋጃል፤ የስብሰባውንም ቃለ-ጉባኤ ይይዛል፤
7. በዚህ ደንብ አንቀጽ 10 መሰረት የጸደቁ ዝርያዎችን በብሔራዊ የዝርያ መዝገብ ላይ ያሰፍራል፤
8. ከመንግስት የምርምር ተቋማትና ማንኛውም የሕዝብን ጄነቲክ ሀብት ተጠቅሞ ዝርያን ያጎለበተ የግሉ ዘርፍ ለእያንዳንዱ ለተለቀቀ አዲስ ዝርያ ለረጅም ጊዜ እንዲቀመጥ አስፈላጊውን የዘር መጠን ለብዝሀ ሕይወት ጥበቃ ኢንስቲትዩት መስጠቱን ያረጋግጣል፤
9. በሕጋዊ መንገድ የተለቀቁትን ዝርያዎች የአራቢ ዘር ምርትንና ዝርያው ባህሪውን ጠብቆ እንዲቆይ መደረጉን ይከታተላል፤
10. የብሔራዊ ዝርያ መዝገብ ዝርዝርን በየጊዜው ክለሳ ያደርጋል፤
11. የብሄራዊ ዝርያ አጽዳቂ ኮሚቴ ተግባራትን በየጊዜው በመዳሰስ ውጤታማነታቸውን ለማሻሻል የሚረዱ ስትራቴጂዎችን ቀይሶ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

## <u>ክፍል ሶስት</u>

## <u>ስለዘር ማምረትና ማከፋፈል</u>

### 14.<u>የአምራች ግዴታዎች</u>

የተለቀቀ ዝርያ ዘርን የሚያመርት ማንኛውም አምራች፡-

1. በአዋጁ አንቀጽ 6 (1) መሠረት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የመያዝ፤
2. ለዘር አመራረት የወጣውን የዘር ጥራት ማረጋገጫ መስፈርት በሚያሟላ መልኩ የማምረት፤
3. በተቀናጀ የዘር ምርት እቅድ አወጣጥ ላይ የመሳተፍ፤ እና

4. ሚኒስቴሩ የዘር ምርት መጠን ወይም ጥራትን ለማሻሻል ባወጣው መመሪያ ለተመለከቱ መስፈርቶች ተገዢ የመሆን፤

ግዴታዎች አሉበት፡፡

## 15.የዘር አምራቾችና አከፋፋዮች መዝገብ

በአዋጁ አንቀጽ 9 መሰረት በሚኒስቴሩ የሚያዘው የተለቀቁ ዝርያዎች የዘር አምራቾች እና አከፋፋዮች መዝገብ በየጊዜው የሚከለስ ሆኖ ቢያንስ የሚከተሉትን ዝርዝር መረጃዎች መያዝ አለበት፡-

1. የዘር አምራቹ ወይም አከፋፋዩ ስምና አድራሻ፤
2. የሚመረተው ወይም የሚከፋፈለው የዘር አይነት ዝርያ፣ የዘር ደረጃ እና አምራች ሲሆን መሬቱ በሄክታር፤
3. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያለበት ሁኔታ፤
4. ዘሩ የተመረተበት ዓመተ ምህረት፡፡

## 16.የዘር ምርት ዕቅድና የመረጃ ቋት

1. ሚኒስቴሩ የክልል ባለስልጣናት ከመንግስትና ከግል ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በአዋጁ አንቀጽ 7 መሰረት የተመዘገበ ዝርያን ለማምረትና ለማከፋፈል የሚያስችል ስትራቴጂ ይነድፋሉ፡፡
2. በአዋጁ አንቀጽ 7 መሰረት ሚኒስቴሩ የሚይዘው የዘር ምርት መረጃ ቋት የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ ይኖርበታል፡-
   ሀ) ዓመታዊ የምርት እቅድና የኃላፊነት ድርሻ፤
   ለ) በተቋምና በጥቅል ለእያንዳንዱ የዘር አይነት ዓመታዊ የምርት መረጃ፤
   ሐ) ዘሩን ለማምረት የሚያስፈልገው መሬት፣ መሰረት ልማትና ሌሎች የሀብት ምንጮች፤ እና
   መ) ለብሄራዊ የዘር ምርት አስፈላጊ የሆነ ማናቸውም ጠቃሚ መረጃዎች፡፡
3. የዘር ምርት መረጃ ቋቱ በኤሌክትሮኒክ ፎርማት የሚዘጋጅ ሆኖ በዚህ ደንብ በአንቀጽ 15 መሰረት ከተዘጋጀው የተለቀቁ ዝርያዎች ዘር አምራቾችና አከፋፋዮች መዝገብ ጋር መሆን አለበት፡፡

## 17.የዘር ማከፋፈል

የዘር ማከፋፈል ሚኒስቴሩ በሚያወጣው ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ መሰረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡

## ክፍል አራት

## የዘር ጥራት መቆጣጠርና ማረጋገጥ

### 18.የዘር ጥራትን የመቆጣጠርና የማረጋገጥ ኃላፊነት

1. የክልል ባለስልጣናት በክልላቸው ውስጥ በሚመረቱ የቅድመ መስራች፣ መስራች እና የተመሰከረለት ዘር ላይ የጥራት ቁጥጥር በማድረግ "የጸደቀ ዘር" ወይም "ጥራቱ የተገለጸ ዘር" በሚል ስያሜ ለአገር ውስጥ ገበያ እንዲውል የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው።
2. ሚኒስቴሩ ለሚከተሉት ዘሮች የጥራት ቁጥጥር በማድረግ ማረጋገጫ የመስጠት ኃላፊነት ይኖረዋል፦

   ሀ) ከውጭ የገባ የተመዘገበ ዘር የጸደቀ ዘር ሆኖ ለአገር ውስጥ ገበያ እንዲውል፤

   ለ) በሀገር ውስጥ ተመርቶ ለውጭ ገበያ ለሚውል ዘር፤ እና

   ሐ) ለአስቸኳይ ጊዜ ዘር፡፡
3. የዘር የጥራት ደረጃ ቁጥጥር የሚከናወነው በኢትዮጵያ የዘር ደረጃ መሰረት ይሆናል።

### 19.የዘር ጥራት ምስክር ወረቀት ለማግኘት ብቁ ስለመሆን

የዘር ጥራት ምስክር ወረቀት ለማግኘት ብቁ ለመሆን ዘሩ፡-

1. የተመዘገበ ዝርያ፤
2. የተመረተው የፀና ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በያዘ አምራች፤ እና
3. ከሚታወቅ ምንጭ የተገኘ፤

   መሆንአለበት፡፡

### 20.የጸደቀ ዘር ወይም ጥራቱ የተገለጸ ዘር የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ

የጸደቀ ዘር ወይም ጥራቱ የተገለጸ ዘር የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ ከሚከተሉት ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፦

1. በክልል ባለስልጣናት በተዘጋጀው ቅጽ መሠረት ከተሞላ ሰነድ፤
2. የዘር እንስፔክሽን አገልግሎት ክፍያ ከተከፈለበት ደረሰኝ፤ እና
3. ከሚዘራው ዘር ከእያንዳንዱ መጠኑ ከታወቀ የዘር ክምችት መለያ ምልክት ከተወሰደ ዘር፡፡

## 21.<u>የጸደቀ ዘር የምስክር ወረቀት አሰጣጥ</u>

አግባብ ባለው ሰው ማመልከቻ ሲቀርብ የጸደቀ ዘር የምስክር ወረቀት አሰጣጥ የሚከተሉትን ደረጃዎች ማለፍ አለበት፡-

1. ዘሩ ላይ የመስክ ቁጥጥር መካሄድ፤
2. የዘር ዝግጅትና ናሙና መውሰድ፤
3. እውቅና ባለው ላቦራቶሪ ፍተሻ መደረግ፤
4. መለያ ምልክት መደረግና ከመያዣው ጋር ማሸግ ወይም መያያዝ፤
5. ሪፖርት መዘጋጀት።

## 22.<u>ጥራቱ የተገለጸ ዘር የምስክር ወረቀት አሰጣጥ</u>

1. ጥራቱ የተገለጸ ዘር ምስክር ወረቀት ለማግኘት አምራቹ በውስጥ የጥራት ቁጥጥር ስርዓቱ በኩል የሚከተሉትን ደረጃዎችን የሚያካትት ተግባራት ማከናወን አለበት፡-
   ሀ) በዘር ማምረት ወቅት የመስክ መስፈርቱ ጠብቆ መመረቱን የማረጋገጥ፤
   ለ) የዘሩን ምንጭና ደረጃ በተመለከተ መረጃ መያዝ፤
   ሐ) ዘር ማዘጋጀትና ማሸግ፤
   መ) ከመስፈርቱ ጋር መጣጣሙን ለማረጋገጥ ናሙና ወስዶ የዘር ጥራት ፍተሻ ማድረግ፤
   ሠ) መለያ ምልክት ማድረግና ከመያዣው ጋር ማሸግ ወይም ማያያዝ፤
   ረ) የመጨረሻ ሪፖርት አዘጋጅቶ ማቅረብ፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ (ረ) በሚቀርብ ሪፖርት መሰረት አምራቹ ጥራቱ የተገለጸ ዘር የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው አግባብ ላለው የክልል ባለስልጣን ማመልከት አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከቱ መረጃዎች መሟላታቸው ሲረጋገጥ የክልል ባለስልጣን ለአምራቹ ጥራቱ የተገለጸ ዘር የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

## 23.<u>የመስክ ቁጥጥር</u>

1. ሚኒስቴሩ ለእያንዳንዱ ሰብል ከኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ ጋር በመሆን የሚከተሉትን የሚያካትት ዝቅተኛውን የማሳ ደረጃ የመስክ ቁጥጥር መስፈርት ያዘጋጃል፡-
   ሀ) የተዘራው ዘር ደረጃ፤

ለ) የሰብል ፈረቃ፤

ሐ) የአጎራባች ማሳ ርቀት፤

መ) ከፍተኛው የሌሎች ዝርያዎች ወይም የኦፍታይፕ መጠን በመቶኛ፤

ሠ) ከፍተኛው የዘር ወለድ-በሽታዎች በመቶኛ፤

ረ) ከፍተኛው የውግዝ አረም በመቶኛ፤ እና

ሰ) ዝቅተኛው ተፈላጊ የመስክ ቁጥጥር ብዛት፡፡

2. የመስክ ቁጥጥሩ ትንተና የሚካሄድበትና ውጤት የሚገለጽበት አሰራር ቅደም ተከተል ሚኒስቴሩ በሚያወጣው የአሰራር መመሪያ መሰረት ይሆናል፡፡

3. አምራቹ በተሰጠው በማንኛውም የቁጥጥር ውጤት የማይስማማ ከሆነ በድጋሚ ቁጥጥር እንዲደረግለት በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ክፍያ በመፈጸም ለክልል ባለስልጣን ይግባኝ ማለት ይችላል፤ ሆኖም በድጋሚ ቁጥጥሩ ወቅት የማሳው ደረጃ ተቀባይነት ካገኘ ለድጋሚ ቁጥጥር የተከፈለው የአገልግሎት ክፍያ ይመለስለታል፡፡

## 24.የዘር ዝግጅት

1. የማሳ ቁጥጥርን ያለፈ ዘር ለላቦራቶሪ ፍተሻ ከመላኩ በፊት መዘጋጀት አለበት፡፡
2. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የያዘና የተመዘገበ ዘር አዘጋጅ የማሳ ቁጥጥርን ያለፈ ዘር አበጥሮ ያዘጋጃል፡፡

## 25.መጠኑ የታወቀ የዘር ክምችት

1. መጠኑ የታወቀ የዘር ክምችት ዘር ከአንድ ዓይነት ዝርያ ከተሰበሰበ ዘር የዓለም አቀፍ የዘር ምርመራ ማሕበር ያወጣውን ከፍተኛውን ተፈላጊ መስፈርት መጠን መሰረት በማድረግ የሚመሰረት ይሆናል፡፡
2. እያንዳንዱ የዘር መጠኑ የታወቀ የዘር ክምችት ዓለም አቀፋዊ ይዘት ያለውን የኮድ ቅንብር በመከተል የዘር ክምችት ተለይቶ የሚታወቅ መለያ ኮድ ቁጥር ይሰጠዋል፣ ኮዱም የፌደራል ወይም የክልል ባለስልጣንና የተመረተበትን ዓመት ለመለየት እንዲያስችል ፊደሎችን ወይም ቁጥሮችን ያካተተ መሆን አለበት፡፡

## 26.የዘር ናሙና አወሳሰድ

1. ሚኒስቴሩ ወይም የክልል ባለስልጣን እውቅና የሰጣቸው ባለሙያዎች ናሙና መውሰድ የሚችሉ ይሆናል።

2. የዘር ናሙና መጠኑ ከታወቀ የዘር ክምችት ዘር የሚወሰደው በአለም አቀፍ የዘር ምርመራ ማሕበር አሰራር መሰረት ነው።
3. ከሁሉም የተዘጋጁ መጠኑ የታወቀ የዘር ክምችት ዘር ለላቦራቶሪ ፍተሻና ለድህረ ቁጥጥርና ምርመራ የሚወሰደው የዘር ናሙና በነፃ ይሆናል፡፡
4. ማንኛውም ለላቦራቶሪ ትንተና የተወሰደ ናሙና ትክክለኛውን የመለያ ቁጥር መያዝ አለበት።
5. ለናሙና አወሳሰድ የተዘጋጀው መጠኑ የታወቀ የዘር ክምችት ዘር አለም አቀፍ የዘር ምርመራ ማህበር አሰራር ካስቀመጠው ከፍተኛ ክብደት መጠን መብለጥ የለበትም፡፡
6. የዘር አምራችና አከፋፋይ መጠኑ የታወቀ የዘር ክምችት ዘር ናሙና ክብደትን ለማረጋገጥ የተፈተሸ ሚዛን መያዝ አለባቸው፡፡
7. የዘር አምራቹ ለናሙና ፍተሻ ሥራ በመንግስት የተተመነውን የአገልግሎት ክፍያ መፈጸም አለበት፡፡

27.<u>ናሙናን ማሸግና መለያ ምልክት ማድረግ</u>

1. ናሙና እንደተወሰደ እርጥበት በማያስገባ መያዣ ውስጥ ወዲያውኑ በጥብቅ መታሸግ ይኖርበታል፡ አስተሻሸጉም ናሙናውን ለመቀየር የሚደረግን ሙከራ የሚያሳውቅ መሆን አለበት፡፡
2. በናሙና መያዣ ላይ የሚደረገው መለያ ምልክት መያዝ የሚገባውን ዝርዝር መግለጫ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡
3. የሚከማቹ ናሙናዎች መቀመጥ የሚችሉበት የሙቀትና የእርጥበት መጠን፣ የጊዜ ወሰንና ሌሎች አስፈላጊ መስፈርቶች ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወስናሉ።

28.<u>የላቦራቶሪ ፍተሻ</u>

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 23 መሰረት የመስክ ቁጥጥርን ያለፈ ዘር በአለም አቀፍ የዘር ምርመራ ማህበር አሰራር መሰረት የላቦራቶሪ ፍተሻ ይካሄድበታል፡፡
2. የላቦራቶሪው የዘር ፍተሻ ብቃት በሚኒስቴሩ ወይም በክልል ባለስልጣን በየወቅቱ ቁጥጥር ይደረግበታል፡፡

## 29.የዘር ናሙናዎች ፍተሻ

1. የዘር ናሙናዎች ላቦራቶሪ በደረሱ ከሁለት እስከ ሦስት ቀናት ውስጥ በአለም አቀፍ የዘር ምርመራ ማሕበር አሰራር መሰረት የንጽሕና፣ የብቅለት፣ የእርጥበት፣ የዘር ጤና እና ሌሎች አግባብ ያላቸው ሙከራዎች በማድረግ የጥራት ፍተሻ መደረግ አለበት፡፡
2. የዘር ናሙናዎች ፍተሻ ውጤት ፍተሻው ከተጠናቀቀ በኋላ ከ7 እስከ 21 ቀናት ውስጥ መመዝገብና ሪፖርት መደረግ አለባቸው።

## 30.የዘር ጥራት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት

1. በአዋጁ አንቀጽ 13 (1 የተጠቀሱት መስፈርቶች መሟላታቸው በክልል ባለስልጣን ተረጋግጦ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ዘር ባለቤት ለተመሰከረ ዘር ወይም ጥራቱ ለተገለጸ ዘር ለእያንዳንዱ መጠኑ የታወቀ የዘር ክምችት የሚከተሉትን መግለጫዎች የያዘ የዘር መለያ ካርድ ማያያዝ አለበት፡-

   ሀ) የድርጅቱ ስምና አድራሻ፤

   ለ) የሰርተፊኬት ቁጥር፤

   ሐ) የሰብሉ ዓይነትና የዝርያ ስም፤

   መ) የዘር ደረጃ፤

   ሠ) የመለያ ቁጥር፤

   ረ) የተጣራ ዘር ክብደት፤

   ሰ) የተመረተበት ዓመት፤

   ሸ) የታሸገበት ቀን፤

   ቀ) የቆይታው ጊዜ፤ እና

   በ) በመድሃኒት የታከመ ከሆነ የማስጠንቀቂያ ምክልት።

2. የጥራት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ይሆናል።
3. ማንኛውም የጥራት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ ሊራዘም የሚችለው በድጋሚ ፍተሻ ወቅት የዘር መጠኑ የታወቀ የዘር ክምችት ዘር ለፊዚካል ንጽህና፤ ለብቅለት እና ለጤና የተደነገጉትን መስፈርቶች አሟልቶ ሲገኝ ይሆናል፡፡

31.<u>የጸደቀ ዘር ማሸግና መለያ ምልክት ማድረግ</u>

1. የጸደቀ ዘር የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ ባወጣው መስፈርትና የአለም አቀፍ ደረጃዎችን መሰረት በማድረግ መታሸግና መለያ ምልክት ሊኖረው ይገባል፡፡
2. የክልል ባለስልጣን የዘር ፍተሻ አድርጎ የጥራት ማረጋገጫ ውጤት ከመሰጠቱ በፊት መጠኑ የታወቀ የዘር ክምችት ዘር መታሸግና መሰራጨት የለበትም፡፡
3. ከመጨረሻው ተጠቃሚ በስተቀር ማንም ሰው የዘር መለያ ምልክቱን ማንሳት ወይም የተሰፋውን ወይም የታሸገውን የዘር ከረጢት መክፈት የለበትም፡፡
4. ጥራቱ የተረጋገጠ እና የዘር መጠኑ የታወቀ የዘር ክምችት በድጋሚ ሊታሸግ የሚችለው በክልል ባለስልጣን ወይም ሚኒስቴር ሲወሰንና በነሱ ቁጥጥር የተደረገበት ብቻ ሲሆን በድጋሚ የታሸገው ዘር ከዋናው ጋር ተመሳሳይ መሆን አለበት፡፡
5. ለገበያ የሚቀርብ ዘር በዚህ ደንብ አንቀፅ 30 (1 የተመለከተውን መረጃ የያዘ በመደበኛ አጠቃቀም ሂደት በቀላሉ ሊበላሽ በማይችል በዘር መያዣው ላይ የሚጣበቅ ወይም የሚለጠፍ መለያ ምልክት ሊኖረው ይገባል፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5 መሠረት የሚደረግ መለያ ምልክት በቅርጽ ሬክታንግል ሆኖ ለተለያዩ የዘር ደረጃዎች የሚከተሉትን የቀለም ቅንብር የያዘ መሆን ይኖርበታል፡-
   ሀ) አራቢ ዘር ወይም ቅድመ መስራች ዘር መደቡ ነጭ ሆኖ በሠያፍ ሐምራዊ ቀለም የተሰመረ፣
   ለ) መስራች ዘር ነጭ ቀለም፣
   ሐ) የተመሰከረለት ዘር አንደኛ ትውልድ ሰማያዊ ቀለም፣
   መ) የተመሰከረለት ዘር ሁለተኛ ትውልድ ወይም ቀጣይ ትውልዶች ቀይ ቀለም፣
   ሠ) ለሁሉም ዘሮች የመለያው ምልክት አንዱ ጫፍ ከሌላው ጫፍ የመለያ ምልክት ቀለም 3ሴ.ሜ አነስተኛ ርቀት በመጠበቅ በጥቁር ቀለም ይቀለማል፣
   ረ) ለሁሉም ዘሮች የመለያው ምልክት አንዱ ጫፍ ላይ 3ሴ.ሜ አነስተኛ ርቀት በመጠበቅ በጥቁር ቀለም ተቀብቶ ሌላው የመለያ ምልክት ቅብ ያለው ይሆናል፡፡

32.<u>የድህረ ቁጥጥር ሙከራ</u>

1. የዘር ጥራት ምስክር ወረቀት ተሰጥቶት የነበረ መጠኑ የታወቀ የዘር ክምችት ዘር ናሙና ተወስዶበት በአለም አቀፍ የዘር ምርመራ ማህበር የአሰራር ዘዴ መሰረት የድህረ ቁጥጥር ፍተሻ ይደረግበታል፡፡
2. ድህረ ቁጥጥር ሙከራ የሚካሄድበት ማሳ በዘር ኢንዱስትሪው ላይ ፍላጎት ባለዉ ማንኛዉም አካል እንዲጎበኝና ምርመራ እንዲካሄድበት ክፍት ይሆናል፡፡
3. ድህረ ቁጥጥር በኋላ የክልል ባለስልጣን በሙከራ ማሳ ላይ ለታዩ ብክለቶችና ለውጦች ሪፖርት ያዘጋጃል፣ እንዲሁም የችግሩን ምንጭ በመለየት ለቀጣዩ የሰብል ወቅት ተመሳሳይ ችግሮች እንዳይከሰቱ መፍትሄ ሊሆን የሚችል እርምጃ ይወስዳል።

33.<u>የጥራት ደረጃ መስፈርቶችን ስለማያሟላ ዘር</u>

በአዋጁ አንቀጽ 16 (1) መሠረት አንድ የዘር መጠኑ የታወቀ የዘር ክምችት ዘር ከደረጃ ዝቅ በሚደረግበት ወይም በሚወገድበት ጊዜ የክልል ባለስልጣኑ ለአመልካቹ፡-

1. ውሳኔው የተሰጠበትን ምክንያት፤
2. አመልካቹ ለፍርድ ቤት ክስ የማቅረብ መብቱ የተጠበቀ መሆኑን፤ እና
3. እንዲወገድ የተባለውን ዘር ከዘር አገልግሎት ውጪ ለሌላ አገልግሎት በአዋጁ አንቀጽ 16 (2 መሰረት ሊጠቀምበት እንደሚችል፤

በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

## <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>ዘር ከውጭ ስለማስገባትና ወደ ውጭ ስለመላክ</u>

34.<u>ዘር ከውጭ አስገቢ ማሟላት ያለባቸው መስፈርቶች</u>

ዘርን ከውጭ በማስገባት ንግድ የተሰማራ ማንኛውም ሰው፡-

1. ዘርን ወደ አገር ውስጥ ማስገባት የሚያስችል የጸና የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መያዝ፤
2. የዘር ማስገቢያ ፈቃድ ከሚኒስቴሩ ማግኘት፤
3. በዚህ ደንብ በአንቀጽ 35 የተቀመጠውን መስፈርት ማሟላት፤
4. ከጭነቱ ጋር የጤንነት ሰርተፍኬት ማቅረብ፤
5. ስለ ዘሩ ዓይነትና የዝርያ ስም እንዲሁም የዘሩ ምንጭ አገር ስም የያዘ የግዥና የርክክብ ሰነድ ማቅረብ፤ እና

6. ጭነቱ አስፈላጊ የሆኑ የማሸጊያና የመለያ ምልክት አለጣጠፍ መስፈርት ማሟላቱን ማረጋገጥ፤

አለበት፡፡

## 35.ከውጭ የሚገባ ዘር ማሟላት ያለበት መስፈርት

1. የአዋጁ አንቀጽ 17 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዘርን ወደ አገር ዉስጥ ማስገባት የሚቻለው፦
   - ሀ) የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ ከሚኒስቴሩ ጋር በመተባበር ያወጣውን የኢትዮጵያ ዘር ደረጃዎች፤ እና
   - ለ) ሚኒስቴሩ በመመሪያ የወሰነውን ማንኛውንም መስፈርት፣

   አሟልቶ ሲገኙ ይሆናል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1 የተደነገገው ቢኖርም ሚኒስቴሩ አነስተኛ መጠን ያለው ዘር ለግለሰብ ግቢ ማስጌጫ ለማዋል የሚገባ ዘር ከሆነ የመስፈርቱን አፈጻጸም ለመተው ይችላል፡፡

## 36.ዘርን ወደ አገር ውስጥ የማስገቢያ ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ

1. ዘርን ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት ከሚኒስቴሩ ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ ከሚከተሉት መረጃዎች ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፦
   - ሀ) የአስገቢው ስምና አድራሻ፤ዘሩ የሚመጣበት አገር እና የጭነቱ መጨረሻ መድረሻ ቦታ የሚያሳይ መግለጫ፤
   - ለ) በዚህ ደንብ በአንቀጽ 34 እና በአንቀጽ 35 (1) የተመለከቱ አግባብ ያላቸው ሰነዶች፤
   - ሐ) የዘሩ አይነት፣ ዝርያና የዘር መጠን የሚያሳይ መግለጫ፤
   - መ) የማጓጓዣ አይነትና የሚገባበት ወደብ የሚያሳይ መግለጫ፤
   - ሠ) ሌሎች ሚኒስቴሩ በመመሪያዎች የሚወስናቸው መረጃዎች፡፡
2. ዘርን ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት በዚህ ደንብ መሰረት የተሰጠ ፈቃድ ጸንቶ የሚቆየው ለስድስት ወር ይሆናል፡፡

## 37.የድንበር ላይ ቁጥጥር

በሚኒስቴሩ የተመደበ የዘር ኢንስፔክተር በአዋጁ አንቀጽ 23 (2)፣ በዚህ ደንብ አንቀጽ 34 እና አንቀጽ 35 (1) የተመለከቱ መስፈርቶች መሟላታቸውን ለማረጋገጥ ወደ አገር ውስጥ በሚገባ ዘር ላይ የድንበር ላይ ቁጥጥር ያደርጋል፡፡

**38.የጥራት ደረጃ መስፈርት ሳያሟላ ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ዘር**

1. የኢትዮጵያን የዘር ደረጃ ሳያሟላ ወደአገር ውስጥ የገባ ዘር እንደሁኔታው፡-

   ሀ) በአስመጪው ወጪ ወደመጣበት አገር እንዲመለስ፤

   ለ) ለኢንዱስትሪ አገልግሎት እንዲውል፤ ወይም

   ሐ) ቁጥጥር እየተደረገ በአስመጭው ወጪ እንዲወገድ ይደረጋል፡፡

2. ሚኒስቴሩ ደረጃውን ስላላሟላ ዘር አወጋገድ ሌሎች አማራጮችን እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ለተዘረዘሩት አፈጻጸም አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

**39.ዘር ወደ ውጭ ላኪ ማሟላት ያለባቸው መስፈርቶች**

ዘርን ወደ ውጭ በመላክ ንግድ የተሰማራ ማንኛዉም ሰው፡-

1. ዘር ወደ ዉጭ ለመላክ የሚያስችል የጸና ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መያዝ፤
2. ዘር ወደ ዉጭ የመላኪያ ፈቃድ ከሚኒስቴሩ ማግኘት፤
3. የተቀባዩ አገር ዝቅተኛ የዘር ጥራት ደረጃ መስፈርት ማሟላት፤
4. ዘሩ የጤንነት ሰርተፊኬት እንዲያገኝ ማድረግ፣
5. ከኢትዮጵያ ብዝሀ ህይወት ኢንስቲትዩት ፈቃድ ማግኘት፤ እና
6. ሚኒስቴሩ በመመሪያ የወሰናቸው ሌሎች መስፈርቶች ማሟላት፤ይኖርበታል፡፡

**40.የዘር ላኪ ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብ የብቃት ማረጋገጫ ማመልከቻ**

ዘርን ወደ ውጭ አገር ለመላክ ከሚኒስቴሩ ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብ የብቃት ማረጋገጫ ማመልከቻ ከሚከተሉት መረጃዎች ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡-

1. የላኪውና የተቀባዩ አገር ስምና አድራሻ እና የጭነቱ መጨረሻ መድረሻ ቦታ የሚያሳይ መግለጫ፤
2. በዚህ ደንብ በአንቀጽ 39 የተመለከቱ አግባብ ያላቸው ሰነዶች፤
3. የዘሩ ዓይነት፣ ዝርያና የዘር መጠን የሚያሳይ መግለጫ፤
4. የማጓጓዣ ዓይነት የሚያሳይ መግለጫ፤
5. ሌሎች ሚኒስቴሩ በመመሪያ የሚወስናቸው መረጃዎች፡፡

## ክፍል ስድስት

## የብቃት ማረጋገጫ  ምስክር ወረቀት

### 41.የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አስፈላጊነት

ማንኛውም የዘር አምራች፣ አዘጋጅ፣ ጅምላ ሻጭ፣ አከፋፋይ ወይም ቸርቻሪ በአዋጁ አንቀጽ 19 መሠረት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከሚኒስቴሩ ወይም ከክልል ባለሥልጣን ማግኘት አለበት፡፡

### 42.የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስፈርት

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 41 መሠረት የዘር አምራች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚያመለክት ማንኛውም ሰው፡-
   ሀ) የዘር ጥራት ቁጥጥር ለማድረግ ምቹና ተደራሽ የሆነ የእርሻ ማሳ፤ እና
   ለ) ስለዘር አመራረት መሠረታዊ እውቀት እና ልምድ ያላቸው በቂ ባለሙያዎች፤
   ያሉት መሆን ይኖርበታል።
2. በዚህ ደንብ አንቀጽ 41 መሠረት የዘር አዘጋጅ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚያመለክት ማንኛውም ሰው፡-
   ሀ) ተስማሚ የሆነ የዘር ማከማቻ መጋዘን፤
   ለ) ዘር የማዘጋጀት ሥራ ለመሥራት አስፈላጊ የሆነ ማሽነሪ ወይም የሰዉ ኃይል፤ እና
   ሐ) ስለ ዘር አዘገጃጀት መሠረታዊ እውቀት እና ልምድ ያላቸው ሠራተኞች፤
   ያሉት መሆን ይኖርበታል።
3. በዚህ ደንብ አንቀጽ 41 መሠረት የዘር አስመጭ፣ ላኪ ወይም አከፋፋይ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚያመልክት ማንኛውም ሰዉ፡-
   ሀ) ተስማሚ የሆነ የራሱ ወይም የተከራየው የዘር ማከማቻ መጋዘን፤ እና
   ለ) ስለዘር አያያዝ መሠረታዊ ዕዉቀት እና ልምድ ያለው ባለሙያ፤
   ሊኖረው ይገባል፡፡
4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1፣ (2 እና (3 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ሚኒስቴሩ ዝርዝር መስፈርት እና የአፈጻጸም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

43.**የማመልከቻ አቀራረብ**

በዚህ ደንብ በአንቀጽ 41 መሠረት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ ማንኛውም ማመልከቻ የሚከተሉትን ዝርዝር መረጃዎች መያዝ ይኖርበታል፡-

1. የአመልካቹ ሙሉ ስምና አድራሻ፤
2. እንደአግባቡ በዚህ ደንብ አንቀጽ 42 መሠረት የተመለከቱ መስፈርቶች ስለመሟላታቸው ዝርዝር መረጃ፤
3. ሌሎች በሚኒስቴሩ መመሪያ የሚገለጹ መረጃዎች።

44.**የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለመስጠት**

1. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በዚህ ክፍል የተመለከቱት መስፈርቶች ተሟልተው ሲገኙ እና የአገልግሎት ክፍያ ሲፈጸም እንደ አግባቡ በሚኒስቴሩ ወይም በክልል ባለሥልጣን አማካይነት የሚሰጥ ይሆናል፡፡
2. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለሶስተኛ ወገን በማንኛውም መልኩ ሊተላለፍ ወይም ሊሰጥ አይችልም።
3. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ጸንቶ የሚቆይበት እና የሚታደስበት ጊዜ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

**ክፍል ሰባት**

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

45.**የዘር ኢንስፔክሽን**

1. ሚኒስቴሩ፡-
   ሀ) ለዘር ኢንስፔክተሮች ምደባ የሚያገለግል ዝቅተኛ የትምህርት ዝግጅት እና ልምድ በመመሪያ ይወሰናል፣ አቅማቸውን ለማጎልበት ሥልጠና ይሰጣል፤
   ለ) የዘር ኢንስፔክተሮች ሥራቸዉን በአግባቡ ማከናወን እንዲችሉ ደረጃዉን የጠበቀ የአሰራር ሥርዓት መመሪያ ያዘጋጃል።
2. በአዋጁ አንቀጽ 23 (2 የተመለከቱ ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው የዘር ኢንሰፔክተር፡-
   ሀ) በመስክ የዘር ጥራት ፍተሻ በማከናወን በኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ የተቀመጠዉ የኢትዮጵያ ደረጃ ስለመሟላቱ ቁጥጥር ያደርጋል፤
   ለ) የዘሩን ጥራት ለማረጋገጥ በድቃይ ሰብል ላይ ቢያንስ ሦስት ጊዜና በሌሎች ሰብሎች ቢያንስ ሁለት ጊዜ የመስክ ቁጥጥር ያደርጋል፤

ሐ) የመስክ ቁጥጥር ለተደረገበት ለእያንዳንዱ ማሳ ሪፖርት ያዘጋጃል፤

መ) የመስክ ቁጥጥርን ያለፈ ዘር ወደ ዘር ማዘጋጃ ቦታ ከመጓጓዙ በፊት በመያዣ ዕቃዉ ላይ የማይለቅ የቀለም ምልክት በማድረግ ያረጋግጣል፤

ሠ) ለብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ ዓላማ የተመዘገበ ዘር አምራች ማሳን፣ የዘር አዘገጃጀትን እና የዘር ማከማቻ መጋዘንን የጥራት ቁጥጥር ፍተሻ ያደርጋል።

46. <u>ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ደንቦች</u>

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ ደንብ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

47. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ የካቲት 10 ቀን 2008 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስትር**

## የፍትህ ሚኒስቴር

**ደንብ ቁጥር 361/2008**

**የዕጽዋት ዘር ብቃት ማረጋገጫና የተያያዥ አገልግሎቶችን ክፍያ ተመን መወሰኛ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀጽ 5፣ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀጽ 17 (1/ እና በዕጽዋት ዘር አዋጅ ቁጥር 782/2005 አንቀጽ 27 (1 መሠረት የሚከተለውን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የዕጽዋት ዘር ብቃት ማረጋገጫና የተያያዥ አገልግሎቶችን ክፍያ ተመን መወሰኛ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 361/2008" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

   1. "አዋጅ" ማለት የዕጽዋት ዘር አዋጅ ቁጥር 782/2005 ነው፤
   2. በአዋጁ ውስጥ የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ ደንብም ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

3. **ስለአገልግሎት ክፍያ**

   የእርሻና የተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር በአዋጁ በተደነገገው መሠረት ለሚሰጠው አገልግሎት ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ በተመለከተው ተመን መሠረት የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡

4. **ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ታህሳስ 4 ቀን 2008 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሣለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክጠቅላይ ሚኒስትር**

## የእጽዋት ዘር የብቃት ማረጋገጫና የተያያዥ አገልግሎቶች የክፍያ ተመን ሰንጠረዥ

| የአገልግሎት አይነት | | የክፍያ መጠን (በብር |
|---|---|---|
| ለማመልከቻ ምርመራ | ለዘር ንግድ ምዝገባ | 100.00 |
| | ከሌላው የተለየ፣ ወጥነት ያለው እና ሊቀያየር የማይችል የዝርያ ባህርይ ሙከራ | 100.00 |
| | ለግዴታ ፍቃድ | 100.00 |
| | ለብሔራዊ የዝርያ ብቃት ማረጋገጫ ሙከራ | 100.00 |
| | ለዘር መስክ ቁጥጥር | 100.00 |
| | ለላብራቶሪ ሙከራ | 100.00 |
| የዘር ምርመራ | ለብቅለት | 40/ናሙና |
| | ለተትራዞልየም | 47/ናሙና |
| | ለንህጽና | 20/ናሙና |
| | ለእርጥበት | 25/ናሙና |
| | ለጤና | 182/ናሙና |
| የመስክ ቁጥጥር | ለድቃይ በቆሎ | 30/ሄክታር |
| | ለሌሎች ሰብሎች | 20/ሄክታር |
| ናሙና ለመውሰድ | ለሁሉም ሰብሎች | 20/ናሙና |
| የምስክር ወረቀት | ለጸደቀ ዘር | 100.00 |
| | ጥራቱ የተገለጸ ዘር | 100.00 |
| | ለዘር ላብራቶሪ ሙከራ | 100.00 |
| | ከሌላው የተለየ፣ ወጥነት ያለውና ሊቀያየር የማይችል የዝርያ ባህሪ ሙከራ | 100.00 |
| | ለዝርያ ምዝገባ | 100.00 |
| | ለብቃት ማረጋገጫ | 100.00 |
| | የጠፋ ወይም የተበላሸ የምስክር ወረቀት ለመቀየር | 100.00 |

| የፍትህ ሚኒስቴር | | |
|---|---|---|
| | ለዓመታዊ ክፍያ | 200.00 |
| የዝርያ ሙከራ | ከሌላው የተለየ፣ ወጥነት ያለውና ሊቀያየር የማይችል የዝርያ ባህሪ ሙከራ (ዝርያ በቁጥርና በወቅት | 4000.00 |
| | ለብሔራዊ የዝርያ ብቃት ማረጋገጫ (በዝርያ፣ በወቅትና በቦታ | 11000.00 |

**ለ) እንስሳት እና ቆዳና ሌጦ**

## አዋጅ ቁጥር 267/1994

## የእንስሳት በሽታዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ

የሀገሪቱ የእንስሳት ሃብት ለእርሻ ተግባር፣ ለምግብነት፣ ለኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃ፣ ለውጭ ምንዛሬ ማስገኛ በጠቅላላው ለሀገሪቱ ኢግኮኖሚያዊ ዕድገት መሠረት ከሆኑት ዋና ሃብቶች አንዱ መሆኑን በመገንዘብ፤

ከዚህ ሰፊ የእንስሳት ሃብት የሚገኘውን ጥቅም ለማሳደግ በቅድሚያ የእንስሳት በሽታዎችን በሚገባ መከላከልና መቆጣጠር ወሣኝ እየሆነ በመምጣቱ፣

ለዚህም ከውጭ ሀገር ወደ ሀገር ውስጥ፤ ከሀገር ውስጥ ወደ ውጭ እንዲሁም በሀገር ውስጥ ከቦታ ቦታ የእንስሳት፣ የእንስሳት ውጤቶችና ተዋጽኦዎች ዝውውር ሥርዓት በመዘርጋት የእንስሳት በሽታዎችን መቆጣጠር አስፈላጊ በመሆኑ፣

በአጠቃላይ የእንስሳት በሽታዎችን በመቆጣጠርና በዓለም አቀፍ ደረጃ የተደረሱትን የእንስሳት ጤና ስምምነቶች በመጠበቅ የእንስሳት፣ የእንስሳት ውጤቶችና ተዋጽኦዎችን ኤክስፖርት ንግድ ማስፋፋት አስፈላጊ በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55(1 መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ

## አጠቃላይ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የእንስሳት በሽታዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁጥር 267/1994" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

   1. "ሚኒስትር" ወይም "ሚኒስቴር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የግብርና ሚኒስትር ወይም ሚኒስቴር ነው፣
   2. "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47(1 የተመለከቱትን ማለት ሲሆን ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ሲባል የአዲስ አበባና የድሬዳዋ አስተዳደርንም ይጨምራል፣
   3. "እንስሳት" ማለት ለዚህ አዋጅ ዓላማ ሲባል የቤትና የዱር እንሳሳ ሲሆን እንዲሁም የባህር እንስሳትና ንብን ያጠቃልላል፣

4. “የእንስሳት ውጤት” ማለት ሥጋና የሥጋ ውጤቶች፣ወተትና የወተት ውጤቶች፣ እንቁላል፣ ማር፣ እንዲሁም ሚኒስቴሩ ለዚሀ አዋጅ አፈፃፀም ሲባል የእንሳሳት ውጤቶች ብሎ የሚሰይማቸውን ሁሉ ያጠቃልላል፣
5. “የእንስሳት ተዋጽኦ” ማለት ቆዳ፣ ሌጦ፣ ጠጉር፣ ላባ፣ ዝባድ፣ ቀንድ፣ ሰም፣ ሸሆና፣ አጥንት፣ ሞራና ከነዚህ የሚገኙትን መኖን እንዲሁም ሚኒስቴሩ ወደፊት ለዚሀ አዋጅ አፈጻጸም ሲባል የእንስሳት ተዋጽኦ ብሎ የሚሰይማቸውን ሁሉ ይጨምራል፣
6. “በሽታ” ማለት ማንኛውም በሚኒስቴሩ የተመዘገበ ወይም የሚመዘገብ የእንስሳት በሽታ ነው፤
7. “ዓለም አቀፍ የእንስሳት ጤና ድርጅት” ማለት ኢትዮጵያ አባል የሆነችበትና በዓለም አቀፍ ደረጃ የእንስሳት በሽታዎችን ቁጥጥር ለማስተባበር የተቋቋመ ድርጅት ነው፤
8. “ተዛማች የእንስሳት በሽታ” ማለት በእንስሳት ላይ ከፍተኛ እልቂት እና/ወይም በሽታ የሚያስከትል ከእንስሳ ወደ ሰው የሚተላለፍ ከባድ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳት የሚያደርስ ወይም በዓለም አቀፍ የእንስሳት፣ የእንስሳት ውጤቶችና ተዋጽአዎች ንግድ ላይ ተጽእኖ የሚያደርስ የተመዘገበና ባስቸኳይ መገለጽ ያለበት ማንኛውም ተላላፊ የእንስሳት በሽታ ነው፡
9. “ክትባት” ማለት የተዳከመ ወይም ሕይወት የሌለው የበሽታ መንስኤ ተዋህስያን ውጤት ሆኖ እንስሳትን ከበሽታዎች ለመከላከል ለጤነኛ እንስሳት የሚሰጥ ነው፤
10. “ቁስ” ማለት ከበሽተኛ እንስሳት ጋር በሚኖረው ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ባልሆነ ንክኪ በመበከል በሽታን ማስተላለፍ የሚችሉ ማናቸውም የእንስሳት ጉዝጓዝ፣ መኖ፣ ግርግም፣ ውየና የውሃ መጠጫ ገንዳዎች፣ በረቶች፣ ልዩ ልዩ የመገልገያ ቁሳቁሶችን ተሽከርካሪዎችና ሌሎች ከበሽታ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ነገሮች ያጠቀልላል፣
11. “የባዮሎጂካል ውጤት” ማለት ሪኤጀንት፤ የደም ቅራሪ፣ የተዳከመ ወይም የሞተ ክትባትና የጀርምጀነቲከ ውጤት ሆኖ የእንስሳት በሽታን ለመመርመር፣ ለመከላከልና ለማከም ተግባር የሚውል ነው፡

12. “የፓቶሎጂካል ናሙና” ማለት የተፈጥሮ ሂደትን ያልተከተለ የሴል እድገት ወይም በበሽታ አስተላላፊ ወይም ተህዋስ ወይም ጥገኛ ከተበከለ ወይም መበከሉ ከተጠረጠረ ሕይወት ካለው ወይም ከሞተ እንስሳ ተወስዶ ለምርመራ ወደ ላቦራቶሪ የሚላክ ነገር ነው፣
13. “ተሕዋስ” ማለት ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ በበሽታ አስተላላፊ ተሕዋስ ወይም ጥገኛ የተበከለን ቁስ በሚገባ ካጸዱ በኋላ ፀረ ተሕዋስ በመጠቀም የበሽታ መንስኤዎችን የማስወገድ ተግባር ነው፣
14. “የአስተዳደር ባለሥልጣን” ማለት በብሔራዊ ክልላዊ መስተዳድሮች በማናቸውም ደረጃ ሕዝቡን ለማስተዳደር የተመረጠ ኃላፊ ነው፤
15. “የእንስሳት ጤና ተቆጣጣሪ” ማለት የእንስሳት በሽታን ለመቆጣጠር በሚኒስትሩ ወይም በክልል መስተዳድሮች የተመደበና ኃላፊነት የተሰጠው የእንስሳት ጤና ባለሙያ ነው፣
16. “የእንስሳት ጤና ባለሙያ” ማለት በየደረጃው የሚሰጠውን የእንስሳት ሕክምና ትምህርት ተከታትሎ ዲግሪ፣ ዲፕሎማ ወይም ሰርቲፊኬት ያለው ሙያውን ለመተግበር የተፈቀደለት ነው፣
17. “የእንስሳት ጤና ተጠሪ” ማለት በእንስሳት ጤና አጠባበቅ መሠረታዊ የእንስሳት ጤና ክብካቤ ሥልጠና የተሰጠው የገበሬ ማህበር፣ የኅብረት ሥራ ማኅበርወይም የአርብቶ አደሩ ማኅበረሰብ የእንስሳት ጤና ተወካይ የሆነ ሰው ነው፤
18. “የእንስሳት ጠባቂ” ማለት የማንኛውም እንስሳ ባለቤት የሆነ ወይም ለእንስሳው ኃላፊ የሆነ ማንኛውም ሰው ነው፣
19. “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡
20. “የኳራንቲን ጣቢያ” ማለት እንስሳትን እንደአስፈላጊነቱ ለተወሰነ ጊዜ አግልሎ በማቆየት፡ ከሌሎች እንስሳት ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ እንዳይገናኙ በማድረግ ጤንነታቸውን በመከታተል እንዲሁም አንዳስፈላጊነቱ የክትባት ምርመራዎችንና ሕክምና ለማካሄድ አስፈላጊ የሆኑ መሰናዶዎችን ያሟላ የተለየ ስፍራ ነው፣
21. “የመውጪያ ወይም የመግቢያ መቆጣጠሪያ ጣቢያ” ማለት ለዓለም አቀፍ ትራፊክ ክፍት የሆነ ማንኛውም ዓለም አቀፍ የአውሮፕላን ማረፊያ ወይም የባህር ወደብ፡ የየብስ ወይም የባቡር የወሰን ጣቢያ ነው።

22. “ዓለም አቀፍ የሳኒተሪ የምስክር ወረቀት” ማለት ለሰው ምግብነት፣ ለእንስሳት መኖ ወይም ለሌሎች ተግባሮች የሚውሉ የእንስሳት ውጤቶችና ተዋፅኦዎች ጥራትና ሀይጂን ዓለም አቀፍ ደረጃን የጠበቀ መሆኑን በማረጋገጥ በላኪው አገር የእንስሳት ጤና አገልግሎት የሚሰጥ ወይም የገዥውን አገር ፍላጎት ያሟላ የምስክር ወረቀት ነው፣
23. “ዓለም አቀፍ የእንስሳት ጤና የምስክር ወረቀት” ማለት ወደ ውጭ ሀገር የሚላኩ እንስሳትን፣ የእንስሳትን አባላዘር፣ ጽንስና የለማ እንቁላልን ጤንነትና ደህንነት መርምሮ በማረጋገጥ በላኪው አገር የእንስሳት ጤና አገልግሎት የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው፡
24. “የእንስሳት ጤና አገልግሎት አስተዳደር ጽ/ቤት” ማለት በየደረጃው በፌደራልና በክልል የእንስሳት በሽታን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር፣ ክትባትና ሕክምና ለመስጠት፡ በተጨማሪም ሌሎች የእንስሳት ጤና ነክ ሥራዎችን ለመሥራት የተቋቋመ አካል ነው።

## ክፍል ሁለት

## የእንስሳት በሽታዎችን ስለመከላከልና መቆጣጠር

### 3. የእንስሳት በሽታ መከሰቱን ስለማሳወቅ

1. የአንስሳት በሽታ ሲከሰት የእንስሳት ጠባቂው ወዲያውኑ በአካባቢው ለሚገኝ የእንስሳት ጤና ተጠሪ ወይም የአስተዳደር ባለሥልጣን ወይም ለእንስሳት በሽታ ተቆጣጣሪ በቃልም ሆነ በጽሁፍ የማሣወቅ ግዴታ አለበት፡፡
2. ማንኛውም የእንስሳት ጤና ባለሙያ በሥራው ላይ እያለ ተዛማች የእንስሳት በሽታ መኖሩን ሲያረጋግጥ ይህንኑ በአስቸኳይ በአቅራቢያው ለሚገኝ የእንስሳት ጤና አገልገግሎት አስተዳደር ጽ/ቤት ማሳወቅ አለበት፡፡
3. የእንስሳት ጤና ተቆጣጣሪው ሪፖርት የተደረገለት የእንስሳት በሽታ መኖሩን ለማረጋገጥ አስፈላጊውን ማጣራት በማድረግ በሽታው መኖሩን ሲያረጋግጥ ለሚመለከተው የእንስሳት ጤና አገልግሎት አስተዳደር ጽ/ቤት ወዲያውኑ ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡
4. የእንስሳት በሽታ ስለመከሰቱ ሪፖርት የተደረገለት ክልልም በአፋጣኝ ለሚኒስቴሩ ሪፖርት ማድረግ ይኖርበታል፡፡
5. ሚኒስቴሩም ስለተከሰተውተዛማች የእንስሳት በሽታ በዓለም አቀፍ የእንስሳት ጤና ድርጅት አማካይነት ለሌሎች አገሮች መረጃ እንዲደርስ ያደርጋል፡፡

6. የእንስሳት ጤና ተቆጣጣሪው የእንስሳት በሽታ በአካባቢው ሲከሰት ሪፖርት የሚደረግበትን ሥርዓት ለመከታተልና የሚወሰዱ እርምጃዎችን ለማቀናጀት በግንባር ቀደምትነት ኃላፊነትና ተጠያቂነት አለበት፡፡
7. የእንስሳት ጤና ተጠሪ እና የአስተዳደር ባለሥልጣን ለዚህ አዋጅ ተግባራዊነት አስፈላጊውን የመፈፀም ግዴታ አለባቸው።
8. የተዛማች የእንስሳት በሽታዎች ዝርዝርና ስለሚገለጹበት ሁኔታ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ ይገለጻል፡፡

4. <u>**የእንስሳት በሽታ የገባባቸውን አካባቢዎች የማሳወቅ ሥልጣን**</u>
    1. ሚኒስቴሩ አንድ አካባቢ ተዛማች የእንስሳት በሽታ የተከሰተበት መሆኑን በሕዝብ መገናኛ እንዲገለጽ ያደርጋል፡፡
    2. ማስታወቂያውም በሽታው ያለበትን ሥፍራና አለ የተባለውን የበሽታ ዓይነት እንዲሁም መወሰድ የሚገባቸውን እርምጃዎች ለይቶ የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡
    3. ሚኒስቴሩ በሽታው ተከስቶበታል የተባለውን አካባቢ ስፋት እንደበሽታው ስርጭት ሁኔታ መጨመር፣ መለወጥ ወይም መቀነስ ይችላል፡፡

5. <u>**የእንስሳት በሽታ የተከሰተባቸውን አካባቢዎች ስለሚመለከቱ ጉዳዮች**</u>
    1. የእንስሳት ጤና ተቆጣጣሪው በጽሁፍ ካልፈቀደ በስተቀር የእንስሳት በሽታ ከገባበት አካባቢ እንስሳት፣ የእንስሳት ውጤቶችና ተዋጸኦዎች ወደ ሌላ ሥፍራ መጓጓዝ አይኖርባቸውም።
    2. በሽታ አለበት በተባለ ሥፍራ ላይ የሚገኙት እንስሳት ሁሉ በተቻለ መጠን ከሕዝብ መተላለፊያ መንገድ ርቀው መጠበቅ ይኖርባቸዋል።
    3. የእንስሳት ጤና ተቆጣጣሪው በሽታው አለበት በተባለው ሥፍራ የሚገኝን ማንኛውንም በእንስሳት በሽታ የተያዘን ወይም መያዙየተጠረጠረን እንስሳ እንዲለይና ተስማሚ ነው ብሎ የሚያምንበትን ምልክት ሊያደርግ ይችላል፡፡
    4. በሽታው አለበት በተባለው ሥፍራ ዙሪያ ለሚገኙ እንስሳት እንዳስፈላጊነቱ የከበባ ክትባት እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡
    5. በእንስሳት በሽታ ታመው የሞቱ ወይም በበሽታ መያዛቸው የተጠረጠሩ እንስሳት በድን የእንስሳት ጤና ተቆጣጣሪው በሚሰጠው ትዕዛዝ መሠረት መወገድ ይኖርበታል።

6. <u>**የእንስሳት በሽታ የተከሰተበት አካባቢ ከበሽታ ነጻ መሆኑ የሚገለፅበት አኳኋን**</u>

   1. ተዛማች የእንስሳት በሽታ አለበት ተብሎ ማስታወቂያ የወጣበት አካባቢ በሚኒስቴሩ ከበሽታው ነፃ ነው ተብሎ እስካልተገለፀ ድረስ ከበሽታው ነፃ እንደሆነ አይቆጠርም።
   2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4(1) መሠረት የእንስሳት በሽታው ተዛምቶበታል የተባለ አካባቢ ከበሽታው ነፃ መሆኑ በሚኒስቴሩ ሲረጋገጥ ሚኒስቴሩ ቀደም ሲል በሽታው መኖሩን ባስታወቀበት መንገድ አካባቢው ከበሽታው ነፃ መሆኑን ያሳውቃል።

7. <u>**የእንስሳት በሽታዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ስለሚወሰዱ እርምጃዎች**</u>

   በማናቸውም ወቅትና ቦታ የእንስሳት በሽታዎች እንዳይከሰቱና እንዳይዛመቱ እንደአስፈላጊነቱ ሚኒስቴሩ እና/ወይም ጉዳዩ የሚመለከተው ክልል፤

   1. የእንስሳት በሽታ መኖሩ ከተረጋገጠ ወይም ከተጠረጠረ አካባቢ ወይም አገር፡ እንስሳት፡ የእንስሳት ውጤት፡ የእንስሳት ተዋጽኦ እና ቁስ ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ ይከላከላል፤ ይቆጣጠራል
   2. የእንስሳት በሽታ መኖሩ ከተረጋገጠበት ወይም ከተጠረጠረ ክልል እንስሳት፡ የእንስሳት ውጤቶች፣ የእንስሳት ተዋጽኦዎች እና ቁስ ወደ ሌላ ክልል እንዳይዘዋወሩ ይከላከላል፤ ይቆጣጠራል።
   3. የእንስሳት በሽታዎችን ለመከላከል የእንስሳት ውጤቶችና ተዋጽኦዎች አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎችን ሳያሟሉ ድንበርን አቋርጠው እንዳይዘዋወሩ ይቆጣጠራል፡፡
   4. ኢትዮጵያ የገባችባቸውን ዓለም አቀፍና አህጉራዊ የእንስሳት ጤና ስምምነቶች በሀገሪቱ ውስጥ እንዲከበሩ ያደርጋል፡፡
   5. ከሰው ወደ እንስሳትና ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎችን ለመቆጣጠር ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ይሠራል፡፡
   6. ከዱር እንስሳት ወደ ቤት እንስሳት ከቤት እንስሳት ወደ ዱር እንስሳት፣ የሚተላለፉ ተዛማች የእንስሳት በሽታዎችን ለመቆጣጠር አስፈላጊ የሆኑ የመከላከያ እርምጃዎችን ይወስዳል፣
   7. ለእንስሳት፣ ለእንስሳት ውጤቶችና ተዋጽእዎች፣ ኢምፖርተሮች፣ኤክስፖርተሮች፣ አምራቾች፣ ተመጋቢዎችና በአጠቃላይም ለኅብረተሰቡ በየጊዜው ስለእንስሳት በሽታዎች ሁኔታ አስፈላጊውን መረጃ ይሰጣል፡፡

8. የእንስሳት በሽታዎች እንዳይስፋፉና ባዕድ በሽታዎች ወደ አገሪቱ እንዳይገቡ የአጣዳፊ ጊዜ ዝግጁነትና የበሽታ ክትትል ሥርዓት ይዘረጋል፡፡
9. የእንስሳት በሽታዎች በኅብረተሰቡ ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ እና ጤና ላይ የሚያደርሱትን ጉዳት መሠረት በማድረግ ቅደም ተከተል በማውጣት የቁጥጥር ፕሮግራም ያካሂዳል፣
10. አገሪቱን ደረጃ በደረጃ ከተዛማች የእንስሳት በሽታዎች ነጻ ለማድረግና የአገሪቱን የእንስሳት፣ የእንስሳት ውጤቶችና ተዋጽኦዎች የውጭ ንግድን ለማስፋፋት ከበሽታ ነጻ የሆኑ ቀጠናዎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን እንዲቋቋሙ ያደርጋል፡፡

8. <u>የእንስሳት ጤና ተቆጣጣሪ ሥልጣን</u>

የእንስሳት በሽታዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የእንስሳት ጤና ተቆጣጣሪ፤

1. የመከላከያ የህክምና ወይም እንደአስፈለጊነቱ የኳራንቲን እርምጃዎችን ተግባራዊ ለማድረግ እንስሳትን የመመርመር፣
2. እንስሳት ከመጓጓዛቸው በፊት፣ በመጓጓዝ ላይ እንዳሉ፣ ከተጓጓዙም በኋላ የመመርመርና እንዲሁም አንዳስፈላጊነቱ ዝውውራቸውን የመቆጣጠር፤
3. እንስሳት፣ የእንስሳት ውጤቶችና ተዋጽኦዎች ወይም የእንስሳት መኖ የሚገኙባቸውን ማናቸውም ቅጥር ግቢ ወይም አካባቢ ገብተው የመመርመር፣
4. የእንስሳት በሽታን ለመለየት ሲባል ከማንኛውም እንስሳት የእንስሳት ውጤቶች ወይም ተዋጽኦዎች ናሙና የመውሰድ፡
5. አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ በማንኛውም ወቅት እንስሳት እንዲመረመሩ፣ እንዲከተቡ፣ እንዲታከሙ በፀረ ተባይ መድሃኒት እንዲረጩ ወይም በኳራንቲን እንዲቆዩ የማድረግ፣
6. እንስሳት እንዲለዩ፣ እንዲታረዱ ወይም እንዲወገዱ ትእዛዝ የመስጠት፣
7. በመግቢያና በመውጫ የመቆጣጠሪያ ጣቢያዎች ተገቢውን ቁጥጥር የማድረግ፣
8. የሞቱ እንስሳት በድን፣ የበድን ቅሪቶች፡ የተበላሹ የእንስሳት ውጤቶች፣ በእርድ ወቅት የሚወጻድቁ ቅንጥብጣቢዎች፣ አዛባ፣ እበት እና ጉዝጓዝ በተገቢው ሁኔታ መወገዳቸዉን የመከታተል፣
9. ከዚህ በላይ በተዘረዘሩት ሳይወሰን የእንስሳት ጤና ተቆጣጣሪው የእንስሳት ህክምና ሙያ አስፈላጊ የሚያደርጋቸውን ሌሎች እርምጃዎች የመውሰድ፣

ሥልጣን ይኖረዋል።

9. **ስለ እንስሳት ጤና መረጃ ልውውጥ**

1. የእንስሳት በሽታዎችን ለመከላከልና ለመቶጣጠር፣ ውጤታማ የሆኑ የበሽታ ቁጥጥር ፖሊሲና ስልቶችን ለመንደፍ አገሪቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚጠበቅባትን ግዴታዎች ለመወጣት ሚኒስቴሩ አገር አቀፍ የእንስሳት ጤና የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት ይዘረጋል።
2. ሚኒስቴሩ በየጊዜው በዓለም አቀፍ ደረጃ በእንስሳት ሕክምና ሳይንስ በኩል የሚገኙትን አዳዲስ ውጤቶች በሙያው ለተሰማሩ ግለሰቦችና ድርጅቶች ያሳውቃል።
3. ተዛማች የእንስሳት በሽታዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር እያንዳንዱ ክልላዊ መንግሥት ከአጎራባች ክልሎችና ከሚኒስቴሩ ጋር አስፈላጊ መረጃዎችን መለዋወጥ ይኖርበታል።

**ክፍል ሶስት**

**የእንስሳት፣ የእንስሳት ውጤቶችና ተዋጽኦዎች ዝውውር**

10. **የኳራንቲን ጣቢያዎች ስለማቋቋም እና ስለመቆጣጠር**

1. የኳራንቲን ጣቢያ እንስሳትን ለማቆየትና ለማጓጓዝ በሚያመች ቦታ ላይ አስፈላጊ የሆኑ መሰናዶዎችን አሟልቶ መቋቋም ይኖርበታል።
2. የኳራንቲን ጣቢያዎች ስለሚቋቋሙባቸውና ስለሚያሟሏቸው መስፈርቶች በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።
3. ሚኒስቴሩ፡ የሚቋቋሙ የኳራንቲን ጣቢያዎችን ከሚሰጠው የእንስሳት ጤና አገልግሎት አንጻር ይቆጣጠራል፣ እንደ አስፈላጊነቱም ሥልጣኑን ለክልሎች በውክልና ይሰጣል፡፡

11. **የመውጫ እና የመግቢያ መቆጣጠሪያ ጣቢያዎችን ስለማቋቋም**

1. ሚኒስቴሩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ሆኖ እንስሳት፣ የእንስሳት ውጤቶችና ተዋጽኦዎች ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡበትን፣ ከሀገር ውስጥ ወደ ውጭ የሚወጡበትን የመውጫ እና የመግቢያ መቆጣጠሪያ ጣቢያዎች ይወስናል፡፡
2. ከተዛማች የእንስሳት በሽታዎች ቁጥጥርና ከበሽታ ነፃ የሆኑ ቀጠናዎችን ከማቋቋም አንጻር እንስሳት፣ የእንስሳት ውጤቶችና ተዋጽኦዎች ከክልል ወደ ክልል አግባብ ካላቸው ክልሎች ጋር በመሆን ይወስናል።

12. **<u>እንስሳት፣ የእንስሳት ውጤቶችንና ተዋጽኦዎችን ወደ ውጭ ሀገር ስለመላክ</u>**

1. ወደ ውጭ አገር የሚላኩ እንስሳት በቅድሚያ ኳሪንቲን ጣቢያ ውስጥ ገብተው ለተወሰነ ጊዜ እንዲቆዩ መደረግ አለበት፡፡
2. ወደ ኳራንቲን ጣቢያ የሚገቡት እንስሳት ተዛማች የእንስሳት በሽታ ካልተከሰተበት አካባቢ የመጡና የዝውውር ፈቃድ ያላቸው መሆን ይኖርባቸዋል።
3. እንስሳት፡ የእንስሳት ውጤቶችንና ተዋጸኦዎችን ወደ ውጪ ሀገር ለመላክ የሚያጓጓዙ ሰዎች የማጓጓዣ መስፈርቶችን ጠብቀው ማጓጓዝና እንዲሁም የተሰየሙትን የመውጪያ መቆጣጠሪያ ጣቢያዎች መጠቀም ይኖርባቸዋል፡፡

13. **<u>እንስሳት፣ የእንስሳት ውጤቶችንና ተዋጸኦዎችን ወደ ሀገር ውስጥ ስለማስገባት</u>**

1. ማንኛውም ሰው እንሰሳት የእንስሳት ውጤቶችና ተዋጽኦዎችን ወደ ሀገር ውስጥ ከማስገባቱ በፊት በቅድሚያ ስለሚገቡት እንስሳት፡ የእንስሳት ውጤቶችና ተዋጽኦዎች ዓይነትና ዝርያ፡ ብዛት፣ የመጓጓዣ ሁኔታ፤ የመድረሻ ቀን የመግቢያ በር እንዲሁም ከየት ሀገር እንደሚመጡ የሚያቋርጧቸውን ሀገሮች ለሚኒስቴሩ በማሳወቅ የመግቢያ ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1 መሠረት የተፈደላቸው እንስሳት፡ የእንስሳት ውጤቶችና ተዋጽኦዎች ሲገቡ በመግቢያ ጣቢያ ላይ በእንስሳት ጤና ተቆጣጣሪዎች መታየት ይኖርባቸዋል።

14. **<u>ዓለም አቀፍ የእንስሳት ጤናና የሳኒተሪ የምስክር ወረቀት</u>**

1. ማንኛወም እንስሳት፣ የእንስሳ አባለዘር፡ ጽንስ፣ የለማ እንቁላል የእንስሳት ውጤቶች የእንስሳት ተዋጽኦዎች ሲገቡ በመግቢያ ጣቢያ ላይ በእንስሳት ጤና ተቆጣጣሪዎች መታየት ይኖርባቸዋል።
2. የእንስሳት ጤናና የሳኒታሪ የምስክር ወረቀቶች ሊይዟቸው ስለሚገቡ ዝርዝሮች በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

15. **<u>የእንስሳት የዝውውር ፈቃድ</u>**

1. ማንኛውም ሰው እንስሳትን ከወረዳ ወደ ወረዳ እና/ወይም ከክልል ወደ ክልል ለማዘዋወር ከእንስሳቱ መነሻ ቦታ ከበሽታ አንፃር ፈቃድ መያዝ ይኖርበታል።
2. የሚሰጠው የእንስሳት የዝውውር ፈቃድ የእንስሳቱን መነሻና መድረሻ ቦታ፣ የጉዞ አቅጣጫ፣ የእንስሳቱን ዓይነትና ብዛት፣ የእንስሳቱን የጤንነት ሁኔታና ሌሎች አስፈላጊ ዝርዝሮችን የሚገልጽ መሆን ይኖርበታል።

## ክፍል አራት

## ስለ እንስሳት ጤና ባለሞያዎች ምዝገባና አገልግሎት አሰጣጥ

**16.ምዝገባ**

1. የእንስሳት ጤና ባለሞያ ካልተመዘገበና የምዝገባ ምስክር ወረቀት ካላገኘ በስተቀር በእንስሳት ጤና ጥበቃ ሥራ ላይ መሠማራት አይችልም።
2. ሚኒስቴሩ ያልተመዘገቡ የእንስሳት ጤና ባለሙያዎችና ሌሎች ባለሙያ ያልሆኑ ተጠቃሚዎች ሊያከናውኗቸው ስለሚችሉ የእንስሳት ጤና አገልግሎት ሥራዎች መመሪያ ያወጣል።
3. የእንስሳት ጤና ባለሞያዎችን ለመመዝገብና ፈቃድ ለመስጠት የእንስሳት ጤና ባለሙያዎች ምክር ቤት ይቋቋማል፡፡
4. ምዝገባው ስለሚካሄድበትና የእንስሳት ጤና ባለሞያዎች ምክር ቤት ስለሚቋቋምበት ሁኔታ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

**17. የእንስሳት ጤና አገልግሎት ስለመስጠት**

1. ማንኛውም ሰው አስፈላጊዎቹን መስፈርቶች አሟልቶ እስከቀረበ ድረስ የእንስሳት ጤና አገልግሎት መስጫ ጣቢያ፣ ማዕከል ወይም ተቋም ማቋቋም ይችላል፡፡
2. ማንኛውም ሰው ለእንስሳት ጤና አገልግሎት ጣቢያ፣ ማዕከልና ተቋም የንግድ ሥራ ፈቃድ ለማግኘት በቅድሚያ ከሚኒስቴሩ ወይም ጉዳዩ ከሚመለከተው ክልል የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማቅረብ ይኖርበታል።
3. ሚኒስቴሩ የግል የእንስሳት ጤና አገልግሎት እንዲስፋፋ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፡፡
4. ሚኒስቴሩ እንደየአገልግሎቱ ባህርይ የመንግሥትና የግሉ ዘርፍ የእንስሳት ጤና አገልግሎት የሚኖራቸውን ሚናና ኃላፊነት ይለያል።

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**18. ስለ ካሣ**

1. የእንስሳት በሽታ እንዳይዛመት ለመከላከልና ለመቆጣጠር በእንስሳት ጤና ተቆጣጣሪው ትዕዛዝ መሠረት የታመመ እንስሳ የተወገደ ወይም የታረደ ከሆነ ለጠባቂው ምንም ዓይነት ካሣ አይከፈልም፡፡
2. በእንስሳት ጤና ተቆጣጣሪው ትዕዛዝ መሠረት የእንስሳው በድን እንዲቀበር ወይም እንዲቃጠል ከተደረገ የበድኑ ማስወገጃ ወጪ ለጠባቂው አይከፈልም፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1 እና (2 ላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ተዛማች የእንስሳት በሽታን ከመላ ሀገሪቱ ወይም ከተወሰነ የሀገሪቱ ክፍል ለመከላከልና ለመቆጣጠር እንዲቻል ሚኒስቴሩ እንስሳት እንዲታረዱወይም እንዲወገዱ ትእዛዝ ከሰጠ እንደአስፈላጊነቱ ካሣ የሚከፈልበትን ሁኔታ ያመቻቻል።
4. በኳራንቲን ጣቢያ ውስጥ በተዛማች የእንስሳት በሽታ መከሰት ምክንያት ለሚታረዱት እንስሳት ካሣ አይከፈልም፡፡
5. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3 አፈጻጸም የሚረዳ እና ባለሙያው በእንስሳት ጤና አገልግሎት ሥራ ላይ እያለ ለሚደርስበት ጉዳት ስለሚከፈል ካሣ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

19. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማንኛውም የሚመለከተው ሰው ይህን አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን ተግባራዊ ለማድረግ መተባበር ይኖርበታል።

20. <u>የአገልግሎት ክፍያ ስለመሰብሰብ</u>

ሚኒስቴሩ ለሚሰጠው አገልግሎት በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ መሠረት ክፍያዎችን ይሰበስባል፡፡

21. <u>ቅጣት</u>

ይህን አዋጅና በአዋጁ መሠረት የሚወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን የተላለፈ ማንኛውም ሰው በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሠረት ይቀጣል።

22. <u>የተሻሩና ተፈጻሚነት የሌላቸው ሕጎች</u>

1. የከብት በሽታዎችን ስለመከላከል የወጣው አዋጅ ቁጥር 171/1953 በዚህ አዋጅ ተሽሯል።
2. ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

23. <u>ደንብና መመሪያ ስለማውጣት</u>

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለአዋጁ አፈጻጸም የሚረዱ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚረዱ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

24.<u>አዋጁ የሚጸናበት ቀን</u>

ይህ አዋጅ ከጥር 23 ቀን 1994 ዓ ም ጀምሮ የጸና ይሆናል ፡፡

**አዲስ አበባ ጥር 23 ቀን 1994 ዓ ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ**

**ሪፐብሊክ ፕሬዘዳንት**

**አዋጅ ቁጥር 728/2004**

**የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ**

ደህንነቱ፣ ጥራቱና ፈዋሽነቱ የተጠበቀ የእንስሳት መድኃኒት አመራረት፣ አቅርቦትና አጠቃቀም ቁጥጥርን በማሻሻል የእንስሳት ሀብት ልማትንና ጤንነት አጠባበቅን ማሳደግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በአገሪቱ በመካሄድ ላይ የሚገኘውን የእንስሳት ጤና አጠባበቅ መርሃ ግብር በተሻለ ሁኔታ ውጤታማ በማድረግ በእንስሳትና በእንስሳት ውጤቶች ዓለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪ ሆኖ መገኘት በማስፈለጉ፤

የመኖ አስተዳደርና ቁጥጥር በማጠናከርና የመኖ ልማቱን ኢንዱስትሪና የእንስሳት እርባታውን በማሻሻል የሕዝብን ጤንነት መጠበቅ በማስፈለጉ፤

በመኖ ጥራትና ደህንነት ማነስ ምክንያት ሊከሰቱ የሚችሉ የእንስሳት በሽታዎችን በመከላከል የእንስሳት ጤንነት በመጠበቅ ምርታማነትን ማሳደግ በማስፈለጉ፤

የእንስሳት መድኃኒትና መኖ ህገወጥ ምርት፣ ስርጭትና አጠቃቀም መከላከልና መቆጣጠር በማስፈለጉ፤

እነዚህን ዓላማዎች ለማስፈጸም ውጤታማ የሆነ የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55)1/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ**

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ "አዋጅ የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 728/2004" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

   1. "እንስሳ" ማለት ለማዳና የዱር እንስሳትን፣ አዕዋፍን፣ የውሃ ውስጥ እንስሳትን፣ ንብንና የሐር ትልን ያጠቃልላል፤

2. “የእንስሳት መድኃኒት” ማለት የእንስሳት በሽታን ለመመርመር፣ ለማከም ወይም ለመከላከል ጥቅም ላይ የሚውል ማንኛውም ንጥረ ነገር ወይም የንጥረ ነገሮች ውህድ ሲሆን የውስጥና የውጭ ጥገኞችንና በሽታ አስተላላፊ ተባዮችን ማከሚያ ውህዶችን፣ ባዮሎጂካል ውጤቶችን፣ የሳኒተሪ መገልገያዎችንና የእንስሳት ሕክምና መሣሪያዎችን ያካትታል፤
3. “ባዮሎጂካል ውጤት” ማለት ሪኤጀንት፣ የደም ተዋፆ፣ የተዳከመ ወይም የሞተ ክትባት ወይም የጀርም ጄኔቲክ ውጤት ሆኖ የእንስሳት በሽታን ለመመርመር፣ ለመከላከል ወይም ለማከም ተግባር የሚውል ነው፤
4. “የእንስሳት ሕክምና መሣሪያ” ማለት የእንስሳት በሽታን ለመመርመር ወይም ለማከም ጥቅም ላይ የሚውል መሣሪያ ሲሆን የላቦራቶሪ፣ የማዳቀያና የማኮላሻ መሣሪያዎችን ያካትታል፤
5. “ባህላዊ የእንስሳት መድኃኒት” ማለት በልምድ የዳበረ፣ በህብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያገኘ እና በሙከራ የተረጋገጠ የእንስሳት መድኃኒት ነው፤
6. “ተደጋጋፊ ወይም አማራጭ የእንስሳት መድኃኒት” ማለት ከባህላዊ ወይም ከዘመናዊ የእንስሳት ጤና ሥርዓት ጋር ያልተጣመረ ሆኖ በተደጋጋፊነት ወይም በአማራጭነት ጥቅም ላይ የሚውል የእንስሳት መድኃኒት ነው፤
7. “ጀርም” ማለት ማንኛውም የበሽታ መንስኤ ተህዋስያን ሲሆን ቫይረስን ባክቴሪያን፣ ፈንገስን፣ ፕሮቶዞዋንና የውጭና የውስጥ ጥገኞችን ያካትታል፤
8. “ፋርማኮቪጂላንስ” ማለት ከእንስሳት ጤና ባለሙያዎችና ከእንስሳት ባለቤቶች መረጃ በማሰባሰብና በመመራመር የእንስሳት መድኃኒት በታካሚው እንስሳ ላይ የሚያስከትለውን ጉዳት ማጥናት ነው፤
9. “የእንስሳት መድኃኒት ንግድ” ማለት የእንስሳት መድኃኒት ለትርፍ ዓላማ ማምረት፣ እንደገና ማሸግ፣ ከውጭ አገር ማስመጣት ወደውጭ አገር መላክ፣ በጅምላ ማከፋፈል ወይም በችርቻሮ ማደል ሲሆን የእንስሳት መድኃኒት ጥራት ምርመራ ላቦራቶሪ አገልግሎትን እና በንግድ ወኪልነት መሥራትን ይጨምራል፤
10. “መኖ” ማለት ለንግድ ዓላማ የተመረተ ወይም የተዘጋጀ የእንስሳት ምግብ ነው፤
11. “የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር” ማለት በይዘቱ ምግብነት ያለው ወይም የሌለው ሆኖ መኖው በሚዘጋጅበት ጊዜ በመኖ ውስጥ በጥቂት መጠን የሚጨመር ንጥረ ነገር ነው፤

12. “የመኖ ንግድ” ማለት መኖን ለንግድ ማዘጋጀት፣ ማሸግ፣ ከውጭ ማስመጣት፣ ወደ ውጭ መላክ ወይም በጅምላ ወይም በችርቻሮ መሸጥ ሲሆን የመኖ ጥራት ምርመራ ላቦራቶሪ አገልግሎትን እና በንግድ ወኪልነት መስራትን ይጨምራል፤
13. “የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት” ማለት ባለሥልጣኑ ያወጣውን መሥፈርት በማሟላት በእንስሳት መድኃኒት ወይም መኖ ንግድ ለመሰማራት ብቁ መሆንን የሚያረጋግጥ አግባብ ባለው አካል የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው፤
14. “ማሸጊያ” ማለት የእንስሳት መድኃኒትን ወይም መኖ በውስጡ ለመሙላት፣ ለመክተት ወይም ለመጠቅለል የሚያገለግል ማንኛውም መያዣ ነው፤
15. “ገላጭ ፅሁፍ” ማለት ማንኛውም በማሸጊያ ላይ የተፃፈ ወይም የተለጠፈና ስለእንስሳት መድኃኒት ወይም ስለመኖ ተገቢውን መረጃ የሚሰጥ መግለጫ ሲሆን በማሸጊያው ውስጥ በአባሪነት የሚካተተውን ጽሑፍ ይጨምራል፤
16. “አስመስሎ ማቅረብ” ማለት የአንድን አምራች እውነተኛ ምርት ማሸጊያ፣ የንግድ ስም፣ የንግድ ምልክት ወይም ማንኛውንም ዓይነት ልዩ ምልክት በመጠቀም የእንስሳት መድኃኒትን ወይም መኖን በእውነተኛው አምራች እንደተመረተ በማስመሰል አሽጎና ገላጭ ጽሑፍ አድርጎ ማቅረብ ነው፤
17. “መከለስ” ማለት የእንስሳት መድኃኒት ወይም መኖ ከተሰራበት ንጥረ ነገር ውጭ ከሌላ ነገር ጋር በመደባለቅ ወይም የተሰራበትን ንጥረ ነገር በሙሉ ወይም በከፊል በሌላ በመተካት ወይም ንፅህና በጎደለው መንገድ መድኃኒቱን ወይም መኖውን በማዘጋጀት ወይም በማከማቸት በባዕድ ነገሮች እንዲበከል አድርጎ ጥራቱን መቀነስ ነው፤
18. “ቅድመ ክሊኒካል ሙከራ” ማለት የእንስሳት መድኃኒትን፣ መኖን ወይም የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገርን በሚመለከት የሚከናወን የሰነድ ምርመራ አካላዊ ምልከታና የላቦራቶሪ ምርመራ ነው፤
19. “ክሊኒካል ሙከራ” ማለት የእንስሳት መድኃኒት ፈዋሽነትና ደህንነት ለማረጋገጥ በእንስሳት ላይ የሚከናወን ሙከራ ነው፤
20. “የእንስሳት መድኃኒት ባለሙያ” ማለት የእንስሳት ሃኪም ወይም ረዳት የእንስሳት ሃኪም ወይም ከእንስሳት መድኃኒት የተያያዘ የሙያ አገልግሎት የሚሰጥ የእንስሳት ጤና ፋርማሲስት የእንስሳት ጤና ድራጊስት ወይም የእንስሳት ጤና ፋርማሲ ቴክኒሽያን ነው፤

21.“የእንስሳት ሐኪም” ማለት ከታወቀ ዩኒቨርሲቲ በእንስሳት ህክምና ሙያ ዶክትሬት ዲግሪ ወይም ከዚያ በላይ የተመረቀ ነው፤

22.“ሌሎች የእንስሳት ጤና ባለሙያዎች” ማለት ከታወቀ ተቋም በእንስሳት ህክምና ሙያ በቢ.ኤስ ሲ ዲግሪ ወይም ዲፕሎማ ወይም ሰርተፊኬት የተመረቀ ነው፡፡

23.“የሙያ ፈቃድ” ማለት የእንስሳት መድኃኒት ባለሙያ ወይም የእንስሳት መኖ ባለሙያ በሙያው መሥራት እንዲችል አግባብ ባለው አካል የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው፣

24.“የእንስሳት መድኃኒት ቤት” ማለት የእንስሳት መድኃኒት ብቻ የሚሸጥበት ተቋም ነው፤

25.“የእንስሳት መኖ መሸጫ” ማለት የእንስሳት የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገርና የመኖ ዘር ብቻ የሚሸጥበት ተቋም ነው፤

26.“የእንስሳት መኖ ባለሙያ” ማለት ከታወቀ ዩኒቨርሲቲ ወይም ተቋም በእንስሳት ሳይንስ ወይም በእንስሳት መኖና ግጦሽ በዲፕሎማ ወይም በመጀመሪያ ዲግሪ ወይም ከዚያ በላይ የተመረቀና በተጨማሪ በመኖና በእንስሳት ስነ ምግብ ስልጠና የወሰደ ነው፤

27.“ማስታወቂያ” ማለት ማንኛውንም ማስገንዘቢያ፣ ሰርኩለር፣ መግለጫ ጽሑፍ ወይም ሌላ መሰል ሰነድና በቃል፣ በምስል ወይም በድምፅ የተላለፈን መልዕክት ያካትታል፤

28.“ሚኒስቴር” ማለት የግብርና ሚኒስቴር ነው፡፡

29.“ባለስልጣን”[13] ማለት በሚኒስተሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ የሚቋቋም የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ነው፡፡

30. “አግባብ ያለው አካል” ማለት እንደ አግባቡ ባለሥልጣኑ ወይም የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ተግባራትን የማከናወን ስልጣን የተሰጠው የክልል መንግሥት አካል ነው፤

31.“ስልጣን የተሰጠው አካል” ማለት የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ ነው፤

32.“ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47/1/ የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባንና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

[13] የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን በደንብ ቁትር 272)05 ተቋቁሟል፡፡

33.“ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

34. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል።

3. **የተፈፃሚነት ወሰን**

1. ይህ አዋጅ በእንስሳት መድኃኒት፣ በመኖ እና በእንስሳት መድኃኒት ባለሙያ ላይ በሚካሄዱ የቁጥጥር ተግባሮች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ እንደተጠበቀ ሆኖ በፌዴራል ደረጃ የዚህ አዋጅ ተፈጻሚነት የሚከተሉትን በሚመለከት ይሆናል፦

ሀ/ የእንስሳት መድኃኒት፣ የመኖና የእንስሳት መድኃኒት ባለሙያዎች ደረጃማውጣትን፤ እና

ለ/ ክልል ተሻጋሪ የእንስሳት መድኃኒትና መኖ ማምረትን፣ ማከፋፈልን፣ ማከማቸትን፣ ማስተዋወቅንና የጥራት ቁጥጥር ላቦራቶሪዎችን እና መድኃኒትና መኖ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባትንና ወደ ውጭ መላክን መቆጣጠር።

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 20 ለባለሥልጣኑ ከተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት ውጪ ያሉ የቁጥጥር ተግባራት በክልል መንግሥታት ተቆጣጣሪ አካላት የሚፈጸሙ ይሆናሉ።

## ክፍል ሁለት

## የእንስሳት መድኃኒት አስተዳደርና ቁጥጥር

4. **ስለምዝገባ**

1. ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት ደህንነቱ፣ ፈዋሽነቱና ጥራቱ ተገምግሞ በባለሥልጣኑ ሳይመዘገብ በአገር ውስጥ ተመርቶም ሆነ ከውጭ አገር ገብቶ ጥቅም ላይ ሊውል አይችልም።

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ቢኖርም ባለሥልጣኑ በአስገዳጅ ሁኔታዎች ምክንያት ማለትም ከፍተኛ የእንስሳት ፍልሰት የሚያስከትሉ የተፈጥሮ አደጋዎች እንደ ድርቅ፣ ጐርፍና የመሬት ነውጥ የመሳሰሉወይም ባእድ የእንስሳት በሽታ ወረርሽኝ ክስተት ወይም ለእንስሳት ጤናምርምር አገልግሎትና ለቅድመ ምዝገባ የሙከራ አገልግሎት እንዲውል ሊፈቅድ ይችላል።

5. **ስለምዝገባ ምስክር ወረቀት**
   1. የእንስሳት መድኃኒት የምዝገባ የምስክር ወረቀት ለ5 ዓመታት የሚያገለግል ይሆናል።
   2. የእንስሳት መድኃኒት የምዝገባ የምስክር ወረቀት መድኃኒቱ የምዝገባ መስፈርቶችን አሟልቶ እስከ ቀጠለ ድረስ በየአምስት ዓመቱ ሊታደስ ይችላል፡፡
   3. የምዝገባ የምስክር ወረቀት ለማሳደስ የሚቀርብ ማመልከቻ የምስክር ወረቅቱ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ከማብቃቱ ከሦስት ወራት በፊት መቅረብ ይኖርበታል።
6. **የእንስሳት መድኃኒት የጥራት ደረጃዎችና አጠቃቀም**
   1. ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት፣ የመድኃኒቱ ጥሬ ዕቃ ወይም ማሸጊያ ሥልጣን የተሰጠው አካል ባወጣው ወይም በተቀበለው ደረጃ የተካተቱ የጥራት መስፈርቶችን የሚያሟላ መሆን አለበት።
   2. ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት ጥቅም ላይ የሚውለው አግባብነት ያለው የመድኃኒት አጠቃቀምን ለማረጋገጥ ባለሥልጣኑ በሚያወጣቸው የአሰራር መመሪያዎች መሠረት መሆን አለበት፡፡
7. **ድህረ ገበያ ቅኝት**
   1. ባለሥልጣኑ የተመዘገበ የእንስሳት መድኃኒት ከተሰራጨ በኋላ ያስገኘውን ጠቀሜታና ያስከተለውን ጉዳት ለማወቅ የድህረ ገበያ ቅኝት ያደርጋል፡፡
   2. የእንስሳት መድኃኒቱን ያስመዘገበው ሰው በድህረ ገበያ ቅኝት ወቅት መድኃኒቱን በሚመለከት በእጁ የሚገኙ የፋርማኮቪጂላንስ መረጃዎችን ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡
   3. በድህረ ገበያ ቅኝት ውጤት እንደተረጋገጠው ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት፡

      ሀ)ለታቀደለት ዓላማ ጥቅም ላይ እንዲውል ሲደረግ የተጠበቀውን የደኅንነት፣ የፈዋሽነት ወይም ጥራት ባህሪ ይዞ ያልተገኘ እንደሆነ፤

      ለ) የሚያስከትለው ጉዳት ከሚያስገኘው ጥቅም አመዝኖ ሲገኝ፤ ወይም

ሐ) ከታካሚው እንስሳ አካል የሚወገድበት የጊዜ ገደብና የቅሪት መጠን በብሔራዊም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከተቀመጡት መሥፈርቶች ጋር የማይጣጣም ከሆነ፤

በጥቅም ላይ እንዳይውል ተደርጎ ምዝገባው እንዲታገድ ወይም እንዲሰረዝ ይደረጋል፡፡

8. **<u>ቅድመ ክሊኒካልና ክሊኒካል ሙከራ ስለማድረግ</u>**

1. ባለሥልጣኑ በአገር ውስጥ እንዲመረት ወይም ከውጭ አገር እንዲገባ የሚደረግ የእንስሳት መድኃኒትን ደህንነት፣ ፈዋሽነትና ጥራት ለመገምገም ናሙና መውሰድ፣ የሰነድና አካላዊ ምልከታ ማድረግና ቅድመ ክሊኒካል የላቦራቶሪ ሙከራ ማድረግ ይችላል፡፡
2. በእንስሳት ላይ ክሊኒካል ሙከራ ማድረግ የሚቻለው ባለሥልጣኑ በሚሰጠው ፈቃድና በእንስሳው ባለቤት ስምምነት ሲሆን በዱርእንስሳት ላይ ሙከራ ለማድረግ ከባለሥልጣኑ እና ከኢትዮጵያ ዱርእንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን ፈቃድ መገኘት አለበት፡፡
3. ክሊኒካል ሙከራ ሲደረግ ለእንስሳት ደህንነት ተገቢውን ጥበቃ በማድረግ መፈፀም አለበት፡፡

9. **<u>ስለእንስሳት መድኃኒት ማሸጊያና ገላጭ ፅሁፍ</u>**

1. ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት አምራች፣ አስመጪ ወይም አከፋፋይ ወይም የእንስሳት ፋርማሲ መድኃኒቱ በአግባቡ ካልታሸገና ገላጭ ጽሑፍ ካልተደረገበት በስተቀር ለገበያ ሊያቀርበው ወይም በማናቸውም አኳኋን ሊያሰራጨው አይችልም።
2. ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት ገላጭ ጽሑፍ በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተጻፈ ሆኖ ለእንስሳት ሕክምና ጥቅምብቻ የሚውል የሚል በጉልህ የሚታይ መግለጫ ጨምሮ ሊይዝ ይገባል፡፡

10. **<u>መድኃኒት ስለማዘዝና ማደል</u>**

1. የእንስሳት መድኃኒት የሚታዘዘው በእንስሳት ሐኪም ብቻ ይሆናል። የባህላዊ የእንስሳት መድሃኒት የሚታዘዘውና የሚታደለው በባለስልጣኑ በተመዘገበና እውቅና በተሰጠው የባህል እንስሳት መድሃኒት አዋቂ ይሆናል።
2. ማንኛውም የእንስሳት ሐኪም የመድኃኒት አስተዛዘዝ ሥርዓትን በመከተልና ደረጃውን ጠብቆ በተዘጋጀ የመድኃኒት ማዘዣወረቀት ላይ ማዘዝ አለበት።

3. የእንስሳት መድኃኒት የሚታደለው የሙያ ፈቃድ በተሰጠው የእንስሳት መድኃኒት ባለሙያ ይሆናል፡፡
4. ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት ባለሙያ የመድኃኒት እደላ ሥርዓትን መሠረት በማድረግ በቂ መረጃና ግንዛቤ በመስጠት በጥንቃቄ ማደል አለበት፡፡
5. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ እና /2/ ድንጋጌዎች ቢኖሩም ከእንስሳት ሐኪም በተጨማሪ በሌሎች የእንስሳት ጤና ባለሙያዎች ትዕዛዝ ሊታደሉ የሚችሉ እና ያለመድኃኒት ማዘዣ ወረቀት ሊታደሉ የሚችሉ የእንስሳት መድኃኒቶችን ዝርዝር ባለሥልጣኑ በመመሪያ ሊወስን ይችላል፡፡

11. <u>ስለእንስሳት ህክምና ባዮሎጂካል ውጤቶች</u>

የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የእንስሳት ህክምና ባዮሎጂካል ውጤት በሚከተሉት ምክንያቶች በአገር ውስጥ እንዳይመረት፣ ከውጭ እንዳይገባ እና እንዳይሰራጭ በባለሥልጣኑ ሊታገድ ይችላል፡-

1. በኢትዮጵያ ውስጥ የሌለ ባዕድ በሽታ መንስኤ ጀርም ወይም የጀርም ውጤት በውስጡ ከያዘ፤
2. ምርቱ የተዘጋጀው በጀርም ከተበከለ የእንስሳት አካል ሆኖ በአገሪቱ በሽታን ለማስራጨት የስጋት ምንጭ ከሆነ፤
3. ምርቱን በጥቅም ላይ ማዋል በአገሪቱ የእንስሳት ወይም የሕዝብ በሽታ ቁጥጥር ወይም የበሽታ ቅኝት መርሃ ግብር መሠረት ቅድሚያ የማይሰጠው ወይም ተፅዕኖ የሚያሳድር ምርት ከሆነ፤ ወይም
4. ምርቱን በጥቅም ላይ ማዋል በአገሪቱ የእንስሳት፣ የእንስሳት ውጤቶችና ተረፈ ምርቶች ንግድ ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድር ከሆነ።

12. <u>የእንስሳት መድኃኒት ንግድ</u>

1. ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው አካል የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይኖረው በእንስሳት መድኃኒት ንግድ ሊሰማራ አይችልም።
2. ማንኛውም ሰው የሙያ ፈቃድ የተሰጠው የእንስሳት መድኃኒት ባለሙያ በሌለበት የእንስሳት መድኃኒት ቤት ንግድ ሊያካሂድ አይችልም።

13. **ስለባህላዊና ተደጋጋፊ ወይም አማራጭ የእንስሳት መድኃኒት**

1. ማንኛውም በአገር ውስጥ የሚመረት ወይም ከውጭ አገር የሚመጣ ባህላዊ፣ ተደጋጋፊ ወይም አማራጭ የእንስሳት መድኃኒት አግባብ ባለው አካል ተገምግሞ ሳይመዘገብ አገልግሎት ላይ ሊውል አይችልም።
2. ማንኛውም ሰው አግባብ ካለው አካል የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይኖረው ባህላዊ፣ ተደጋጋፊ ወይም አማራጭ መድኃኒት ማምረት፣ ማስመጣት፣ መላክ፣ማከፋፈል ወይም መሸጥ አይችልም።

## ክፍል ሦስት

## የመኖ አስተዳደርና ቁጥጥር

14. **የመኖ ጥራት ደረጃዎች**

ማንኛውም መኖ ወይም የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር ሥልጣን የተሰጠው አካል ያወጣውን ወይም የተቀበለውን የጥራት ደረጃዎችን የሚያሟላ መሆኑ አግባብ ባለው አካል ካልተረጋገጠ በስተቀር ለአገልግሎት ሊውል አይችልም።

15. **የመኖ ደህንነት ቁጥጥር**

1. ማንኛውም መኖ፣ የመኖ ጥሬ ዕቃ ወይም የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር ብክለትንና ብልሽትን በሚከላከል አሰራር መመረት፣ መከማቸትና መጓጓዝ አለበት፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ:-
   ሀ) የመኖ፣ የመኖ ጥሬ ዕቃና የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር የማምረቻ መሳሪያዎች፣ ማከማቻዎችና ማጓጓዣዎች ንፅህና መጠበቅና አግባብነት ያለው የተህዋስያን ቁጥጥር ሥርዓት መተግበር አለበት፤
   ለ) መኖና የመኖ ጥሬ ዕቃና የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር በማምረት፣ በማከማቸት፣ በማጓጓዝ፣ በአያያዝና በመመዘን ሂደት ጥቅም ላይ የሚውሉ መያዣዎችና ዕቃዎች ንፅህና መጠበቅ አለበት፤
   ሐ) የንፅህና አጠባበቁ ዘዴ አስተማማኝና የፀረ ተህዋስያንና የማፅጃ ኬሚካሎችን ቅሪት መጠን ዝቅተኛ የሚያደርግ ሊሆን ይገባል፤
   መ) የመኖ ማምረቻ ድርጅት ከእንስሳት እርባታ ወይም ማድለቢያ ቦታ ወይም ከቄራ በቅርብ ርቀት ላይ መገኘት የለበትም፤
   ሠ) ማንኛውም መኖ ለእንስሳት ደህንነትና ጤንነት ጎጂ ከሆኑ ማዕድናት፣ ንጥረ ነገሮችና ተህዋስያን ነፃ መሆን አለበት፡፡

16. የመኖ ማሸጊያና ገላጭ ጽሑፍ

1. ማንኛውም የመኖ አምራች፣ አስመጪ፣ አከፋፋይ ወይም የእንስሳት መኖ መሸጫ መኖው በአግባቡ ካልታሸገና ገላጭ ጽሑፍ ካልተደረገበት በስተቀር ለገበያ ሊያቀርበው ወይም በማንኛውም አኳኋን ሊያሰራጨው አይችልም።
2. የማንኛውም መኖ ገላጭ ጽሑፍ በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ ቋንቋ በጉልህ የተጻፈ ሊሆን ይገባል፡፡

17. ስለመረጃ አያያዝ

1. የመኖ ግብዓቶችን፣ የማምረት ሂደትና ስርጭትን የሚያሳዩ መረጃዎች ተመዝግበውና በቀላሉ ተደራሽ እንዲሆኑ ተደርገው መያዝ አለባቸው።
2. መረጃዎቹ የምርቱ ጎጂ ጎን ሲከሰት የጥሬ ግብዓቶቹን አቅራቢም ሆነ ያለቀለትን ምርት ተጠቃሚ መለየት የሚያስችሉ ሆነው መደራጀት አለባቸው።

18. መኖ ወደ አገር ውስጥ ስለማስገባትና ወደ ውጭ አገር ስለመላክ

1. ማንኛውም ወደ አገር ውስጥ የሚገባ የመኖ ምርት በላኪው አገር የሚመለከተው አካል የተረጋገጠ የጥራት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያለው መሆን አለበት፡፡
2. ማንኛውም ወደ ውጭ አገር የሚላክ መኖ በባለሥልጣኑ የተሰጠ የጥራት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያለው መሆን አለበት፡፡

19. የመኖ ንግድ

ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው አካል የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይኖረው በመኖ ንግድ ሊሰማራ አይችልም።

## ክፍል አራት

## ስለባለሥልጣኑ እና ስለተቆጣጣሪዎች

20. የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የእንስሳት መድኃኒቶችን ደኅንነት፣ ፈዋሽነትና ጥራት እንዲሁም የመኖና የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮችን ደኅንነትና ጥራት ደረጃዎች አዘጋጅቶ ሥልጣን ለተሰጠው አካል ያቀርባል፣ ሲጸድቁም በተግባር ላይ መዋላቸውንና መከበራቸውን ይከታተላል፣

2. በእንስሳት መድኃኒት ወይም መኖ ንግድ ሥራ ለሚሰማሩ ሰዎች የብቃት መመዘኛ ያዘጋጃል፣ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ (2(ለ ለተመለከቱት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ በዚህ አዋጅና አዋጁን ለማስፈጸም በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት የምስክር ወረቀቱን ያድሳል፣ ያግዳል፣ ይሰርዛል፤
3. አገር ውስጥ የሚመረቱም ሆነ ከውጭ አገር የሚመጡ የእንስሳት መድኃኒቶችንና የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮችን ገምግሞ ይመዘግባል፣ በዚህ አዋጅና አዋጁን ለማስፈጸም በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት ምዝገባውን ያድሳል፣ ያግዳል፣ ይሰርዛል፤
4. የእንስሳት መድኃኒትና መኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር መዘርዝር ያዘጋጃል፣ መድኃኒቶችንና የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮችን በየዓይነታቸው ይመድባል፣ መዘርዝሩንም እንደአስፈላጊነቱ በየጊዜው ይከልሳል፤
5. የእንስሳት መድኃኒቶችንና መኖን በተመለከተ የፖሊሲ ሀሳብ ያመነጫል፣ ረቂቅ ሕጎችን ያዘጋጃል፣ በመንግሥት ሲፀድቁም ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤
6. የእንስሳት መድኃኒትና መኖ ዘርፉን ለማጠናከርና ለማስፋፋት በአገር ውስጥና በውጭ አገር የሚደረጉ ሳይንሳዊ ግኝቶችን በመከታተል ከአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር እንዲጣጣሙ ያደርጋል፤
7. የላቦራቶሪና የክሊኒካል ጥናት በማድረግ የባህላዊ መድኃኒቶቹን ደህንነት፣ ፈዋሽነትና ጥራት ያረጋግጣል፣ በእንስሳት ጤና አገልግሎት ውስጥ ገብተው ጥቅም ላይ እንዲውሉ ይፈቅዳል፤
8. ለእንስሳት መድኃኒትና መኖ የመረጃ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፣ እንደ አስፈላጊነቱ የእንስሳት መድኃኒትና መኖ መረጃዎችን ለባለሙያዎችና ለተጠቃሚው ኅብረተሰብ ያስተላልፋል፣ መረጃ የሚያስተላልፉ ሰዎች መረጃ ትክክለኛነትና አግባብነት ያረጋግጣል፣ አሻሚ ወይም ትክክለኛ ያልሆኑ መረጃዎች እንዳይሰራጩም ያደርጋል፤
9. በእንስሳት መድኃኒቶች ላይ የክሊኒካል ሙከራ እንዲደረግ ፈቃድ ይሰጣል፣ ሂደቱን ይከታተላል፤

10.በእንስሳት ሕክምና ጥቅም ላይ የሚውሉ ናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶችን በተመለከተ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ለኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን ሪፖርት ያደርጋል፤

11.ለሥራው አስፈላጊ የሆኑትን የጥራት ምርመራ ላቦራቶሪዎችን ያደራጃል፤

12. በእንስሳት መድኃኒትና መኖ አያያዝና አጠቃቀም ዙሪያ አግባብ ላላቸው አካላት ስልጠና ይሰጣል፤

13. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 2(2 መሠረት ለእንስሳት የውጭ ጥገኛ ህክምና ወይም ለእንስሳት በሽታ አስተላላፊ ተባዮች መቆጣጠሪያ አገልግሎት የሚውሉ ንጥረ ነገሮችንና ውህዶችን ይመዘግባል፣ ይቆጣጠራል ይህንንም አስመልክቶ በአዋጅ ቁጥር 674/2002 ስልጣን ለተሰጠው አካል ያሳውቃል፤ ዝርዝር አፈፃፀሙ በሚወጣው ደንብ መሠረት ይሆናል፡፡

21. <u>ስለተቆጣጣሪዎች</u>

1. አግባብ ያላቸው አካላት ይህን አዋጅና አዋጁን ለማስፈጸም የሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ የእንስሳት መድኃኒትና መኖ ተቆጣጣሪዎችን ይመደባሉ።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የተመደበ ተቆጣጣሪ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡-

    ሀ) የእንስሳት መድኃኒት ወይም መኖ ንግድ ሥራ ወደሚካሄድበት ወይም የእንስሳት መድኃኒት ወይም መኖ ወደተከማቸበት ግቢ በሥራ ሰዓት በመግባት ወይም የእንስሳት መድኃኒት ወይም መኖ የጫነንማጓጓዣ በማስቆም የቁጥጥር ተግባር የማከናወን፤

    ለ) ከእንስሳት መድኃኒትና መኖ ሥራ ጋር የተዛመደ ማንኛውንም መዛግብት፣ ሰነድ፣ማዘዣና ኮምፒውተር መመልከትና አስፈላጊ ሆኖሲያገኘው ኮፒ ተደርጎ እንዲሰጠው የማድረግ፤

    ሐ) ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ከእንስሳት መድኃኒቶች፣ መኖዎች ወይም የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮች ላይ ናሙናዎችን የመውሰድ፤

መ) የተከለሱ፣ የተበላሹ፣ በማስመሰል የቀረበ፣ የተበከሉ ወይም በማናቸውም ሌላ ምክንያት በተጠቃሚዎች ላይ ጉዳት ያደርሳሉ ተብለው በተጠረጠሩ መድኃኒቶች፣ መኖዎች ወይም የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮች ላይ የጥራት ምርመራ እንዲካሄድ ለማድረግና ውጤቱ እስኪታወቅ ድረስ ተለይተው እንዲቆዩ የማዘዝ፤

ሠ) የእንስሳት መድኃኒቶች፣ መኖዎች ወይም የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮች የአገልግሎት ዘመናቸው ሲያበቃ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት ጥቅም ላይ እንዳይውሉ ሲወሰን በተገቢው መንገድ እንዲወገዱ መደረጋቸውን የመቆጣጠር፡፡

3. ማንኛውም ተቆጣጣሪ የቁጥጥር ስራውን በሚያከናውንበት ወቅት አግባብ ባለው አካል የተሰጠውን የጸና መታወቂያ መያዝና ሲጠየቅም ማሳየት አለበት፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 22.ስለእንስሳት መድኃኒትና መኖ አወጋገድና የንግድ ሥራ ስለማቋረጥ

1. ማንኛውም በእንስሳት መድኃኒት ወይም መኖ ንግድ ሥራ የተሰማራ ሰው የተበላሸ ወይም የአገልግሎት ጊዜው ያለፈበትን የእንስሳት መድኃኒት ወይም መኖ እስከሚወገድ ድረስ ተለይቶ እንዲቀመጥ ማድረግ አለበት፡፡
2. የእንስሳት መድኃኒት ወይም መኖ አወጋገድ ባለሥልጣኑ ያወጣውን መመሪያ ተከትሎና አካባቢን በማይበክል መንገድ በጥንቃቄ መፈፀምአለበት፡፡
3. ማንኛውም የብቃት ምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው የንግድ ሥራውን ሲያቋርጥ በእጁ ስለሚገኝ የእንስሳት መድኃኒት ወይም መኖ እና ስለዚሁምርት የተዘጋጁ ኢንቮይሶች፣ መዝገቦችና ማዘዣ ወረቀቶች ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት አስፈላጊውን መፈጸም አለበት፡

### 23. ስለንግድ ማስታወቂያና መረጃ ስለመስጠት

1. የእንስሳት መድኃኒት ወይም መኖ የንግድ ማስታወቂያ በመገናኛ ብዙሃንወይም በማናቸውም መንገድ የሚተላለፍበት ሁኔታ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወስናል።

2. ማንኛውም የመገናኛ ብዙኃን ወይም ማስታወቂያ አዘጋጅ ባለሥልጣኑ ያወጣውን መመሪያ አክብሮ የመስራት ግዴታ አለበት።
3. በእንስሳት መድኃኒትና መኖ ንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ሰዎች ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ሥራቸውን የሚመለከት መረጃዎችን አግባብ ላለው አካል በየጊዜው የማቅረብ ግዴታ ይኖርባቸዋል።
4. አግባብ ያላቸው የክልል አካላት ስለሰጧቸው፣ ስላገዷቸውና ስለሰረዟቸው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቶች እና የሙያ ፈቃዶች ለባለሥልጣኑ መረጃ የማስተላለፍ ግዴታ አለባቸው።

24.<u>አስተዳደራዊ እርምጃዎች</u>

1. አግባብ ያለው አካል ይህንን አዋጅ ወይም ለአዋጁ አፈጻጸም የወጣን ደንብ ወይም መመሪያ በመተላለፍ ሲሰራ የተገኘ ሰውን የምስክር ወረቀት ወይም የሙያ ፈቃድ ሊያግድ ወይም ሊሰረዝ ይችላል፡፡
2. አግባብ ያለው አካል ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት ወይም መኖ ወይም የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር ለአገልግሎት ብቁ አለመሆኑን ሲያረጋግጥ መድኃኒቱን፣ መኖውን ወይም የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሩን መያዝና በባለቤቱ ወጪ እንዲወገድ ሊያደርግ ይችላል።
3. ማንኛውም ሰው የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሳይኖረው በእንስሳት መድኃኒት ወይም መኖ ንግድ ሥራ ተሰማርቶ ከተገኘ አግባብ ያለው አካል የንግድ ተቋሙን በማሸግ ተገቢውን እርምጃ ሊወሰድ ይችላል፡፡

25.<u>ስለቅሬታ አቀራረብ</u>

1. ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ወይም የሙያ ፈቃድ የተከለከለ፣ የምስክር ወረቀቱ የታገደበት ወይም የተሰረዘበት ሰው እርምጃው ከተወሰደበት ቀን ጀምሮ በ30 የስራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን አግባብ ያለው አካል ላቋቋመው ቅሬታ ሰሚ አካል ማቅረብ ይችላል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሰረት ቅሬታ የቀረበለት አካል በ30 የስራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡
3. ቅሬታ አቅራቢው በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (2 በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ምላሽ ባያገኝ ወይም የተሰጠው ምላሽ አጥጋቢ ሆኖ ሳያገኘው ቢቀር ጉዳዩን ወደ መደበኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል።

26.<u>ቅጣት</u>

1. በወንጀል ሕጉ የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም ሰው፡
   ሀ) በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 21 መሠረት የተሰየመን ተቆጣጣሪ ሥራ የሚያውክ ከሆነ ከ6 ወር በማያንስ ቀላል እስራት እና ከብር 10 ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤
   ለ) የተሰጠውን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ወይም የሙያ ፈቃድ አግባብ ያለውን አካል ሳያስፈቅድ ለሌላ ሰው አሳልፎ ከሰጠ ከአንድ ዓመት በማያንስና ከሦስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት እና ከብር5ሺ በማያንስና ከብር 20ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።
2. ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት ወይም መኖ አምራች፣ አስመጪ ወይም ጅምላ አከፋፋይ ፈቃድ ለሌለው ሰው መድኃኒት ወይም መኖ ካከፋፈለ ከሁለት ዓመት በማያንስና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት እና ከብር 10ሺ በማያንስና ከብር 20ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።
3. ከራሳቸው ፍጆታ የተረፈውን መኖ ከሚሸጡ አነስተኛ አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች በስተቀር ማንኛውም ሰው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይኖረው በእንስሳት መድኃኒት ወይም መኖ ንግድ ሥራ ላይ ከተሰማራከአምስት ዓመት በማያንስና ከሰባት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት እና ከብር 20ሺ በማያንስና ከብር 50ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።
4. ማንኛውም በእንስሳት መድኃኒት ወይም መኖ ጅምላ ወይም ችርቻሮ ንግድ የተሰማራ ሰው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ካልተሰጠው ሰው መድኃኒት ወይም መኖ ከገዛ ከሁለት ዓመት በማያንስና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከብር 10ሺ በማያንስና ከብር 20ሺ በማይበልጥየገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።
5. የእንስሳት መድኃኒት ወይም መኖ አስመስሎ ያቀረበ ወይም የከለሰ ወይም ደረጃውን ያልጠበቀ ወይም የመጠቀሚያ ጊዜው ያለፈበትን መድኃኒት ወይም መኖ ለገበያ ያቀረበ ሰው ከ10 ዓመት በማያንስና ከ20 ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከብር 20ሺ በማያንስና ከብር 50ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።

6. ማንኛውም ሰው የዚህን አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች ወይም አዋጁን ለማስፈፀም የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን የጣሰ እንደሆነ ከሁለት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት እና ከብር 10ሺ. በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።
7. ማንኛውም ከእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ጋር የተገናኙ ሥራዎችን የሚያከናውን አግባብ ያለው አካል ሠራተኛ ወይም ባለሥልጣን መደለያ በመቀበል ወይም በዝምድና ወይም በሌላ ግንኙነት ሳቢያ በዚህ አዋጅ ወይም አዋጁን ለማስፈፀም በወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች ከተደነገገው ውጪ፡-
    ሀ) የእንስሳት መድኃኒት ወይም መኖ ንግድን በተመለከተ የብቃትማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ወይም የሙያ የስራ ፈቃድ የሰጠ ወይምያደሰ ወይም እንዲሰጥ ወይም እንዲታደስ ያደረገ እንደሆነ፤ ወይም
    ለ) የእንስሳት መድኃኒት፣ መኖ ወይም የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር የጥራት፣ የደህንነት እና እንደአግባቡ የፈዋሽነት ደረጃ ግምገማ ሳያልፍ አገልግሎትላይእንዲውል የፈቀደ ወይም እንዲፈቀድ ያደረገ እንደሆ፤ከ10 ዓመት በማያንስና ከ15 ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት እና ከብር 30ሺ. በማያንስና ከብር 50ሺ. በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።
8. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (7) የተጠቀሰው ቅጣት መደለያ በሰጠው ሰው ላይም ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
9. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (7) የተመለከተን ጥፋት በመፈጸም ተግባር የተሳተፈ ሰው ጉዳዩ ወደ ፍርድ ቤት ከመቅረቡ በፊት ስለተፈፀመው ጥፋትና ስለተባባሪዎቹ ሚና በቂ መረጃ ከሰጠ የፍትህ ሚኒስቴር[14] ወይም የፌዴራል ሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ክስ እንዳይመሰረትበት ሊያደርግ ይችላል፡፡

27.**ተፈጻሚ ስለማይሆኑ ሕጎች**

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

[14]በ22/62 (2008) አ.943 መሠረት የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ሆኗል፡፡

28.<u>ደንቦችና መመሪያዎች የማውጣት ሥልጣን</u>

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል።
2. ባለስልጣኑ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

29.<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ጥር 10 ቀን 2004 ዓ ም**

**ግርመ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

## ደንብ ቁጥር 325/2006

## የእንስሳት መድኃኒትና መኖ ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ የአገልግሎት ክፍያን ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በኢትዮጵያ ፌደራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀጽ 17(1 መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የእንስሳት መድኃኒትና መኖ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎቶች ክፍያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 325/2006" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

   1. "አዋጅ" ማለት የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 728/2004 ነው፤
   2. በአዋጁ አንቀጽ 2 የተሰጡ ትርጓሜዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፥
   3. "ባለስልጣን" ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 272/2005 የተቋቋመው የእንስሳት መድሃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ነው፥

3. **ስለአገልግሎት ክፍያ**

   1. ለእንስሳት መድኃኒትና ህክምና መሣሪያዎች ምዝገባና ፈቃድ ለመስጠት ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ አንድ በተመለከተው ተመን መሠረት የአገልግሎት ክፍያ ይፈፀማል፡፡
   2. ለእንስሳት መድኃኒትና መኖ ባለሙያዎች ምዝገባና ፈቃድ ለመስጠት እና የንግድ ማስታወቂያ ምዝገባና ፈቃድ ለመስጠት ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ሁለት በተመለከተው መሠረት የአገልግሎት ክፍያ ይፈፀማል፡፡
   3. በውጭ አገር አምራች ኩባንያዎች ለእንስሳት መድኃኒት የመልካም አመራረት ተሞክሮ ምልከታ ለማድረግ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ሦስት በተመለከተው መሠረት የአገልግሎት ክፍያ ይፈፀማል፡፡
   4. ለእንስሳት መድኃኒትና መኖ ተቋማት ምዝገባና ፈቃድ ለመስጠት ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ አራት በተመለከተው ተመን መሠረት አገልግሎት ክፍያ ይፈፀማል፡፡

4. <u>**ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**ህዳር 12 ቀን 2007 ዓ ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## የፍትህ ሚኒስቴር

**ሠንጠረዥ አንድ**

**የእንስሳት መድኃኒትና ህክምና መሣሪያዎች ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት ክፍያ**

| ተ.ቁ | የአገልግሎት ዓይነት | በአሜሪካን ዶላር | በብር |
|---|---|---|---|
| 1 | የደህንነትና ፈዋሽነት ፍተሻ መረጃ ማቅረብ የሚገባቸው አዳዲስ የእንሰሳት መድኃኒቶች ምዝገባ | 800 | 15,600.00 |
| 2 | ለመጀመሪያ ጊዜ መድኃኒቱን ካገኘው ባለመብት ጋር መድኃኒቶች አቻ ስለመሆናቸው መረጃ ማቅረብ የሚገባቸው አዳዲስ መድኃኒቶች ምዝገባ | 700 | 13,650.00 |
| 3 | ለመጀመሪያ ጊዜ መድኃኒቱን ካገኘው ባለመብት ጋር መድኃኒቶች አቻ ስለመሆናቸው መረጃ ማቅረብ የማይጠበቅባቸው አዳዲስ መድኃኒቶች ምዝገባ | 500 | 9,750.00 |
| 4 | ዳግም የመድኃኒት ምዝገባ (በየአምስት ዓመቱ | 250 | 4,875.00 |
| 5 | መድኃኒቱ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲመዘገብ ከነበረው አጠቃላይ ሁኔታ ላይ ለውጥ ሲኖር እና የላብራቶሪ ፍተሻ የሚያስፈልገው ሲሆን ለመመዝገብ | 200 (ለየምዝገባው) | 3,900.00 (ለየምዝገባው) |
| 6 | መድኃኒቱ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲመዘገብ ከነበረው አጠቃላይ ሁኔታ ላይ ለውጥ ሲኖር እና የላብራቶሪ ፍተሻ የማያስፈልገው ሲሆን ለመመዝገብ | 100 (ለየምዝገባው) | 1,950.00 (ለየምዝገባው) |
| 7 | አዳዲስ የእንስሳት ህክምና መገልገያ መሳሪያዎች ምዝገባ | 500 | 9,750.00 |
| 8 | ለዳግም የእንስሳት ህክምና መገልገያ መሳሪያዎች ምዝገባ | 250 | 4,875.00 |
| 9 | የሀገር ውስጥ የመድኃኒት ድርጅት ውክልና ለማጽደቅና ለተጨማሪ ውክልና ሲጠየቅ | 50 | 975.00 |

| የፍትህ ሚኒስቴር | | | |
|---|---|---|---|
| 10 | በገበያ ውስጥ እጥረት የሚታይባቸው ልዩ ልዩ የእንስሳት መድኃኒቶች አዲስ ምዝገባ | 100 | 1,950.00 |
| 11 | በገበያ ውስጥ እጥረት የሚታይባቸው ልዩ ልዩ የእንስሳት | 75 | 1,462.50 |

## ሠንጠረዥ ሁለት

## የእንስሳት መድኃኒትና መኖ ባለሙያዎች ምዝገባ እና ፈቃድ እና የንግድ ማስታወቂያ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት

| ተ.ቁ | የአገልግሎት ዓይነት | አዲስ በብር | ዕድሳት በብር | ምትክ በብር |
|---|---|---|---|---|
| 1 | እንስሳት ሐኪም ምዝገባ | 54.00 | 27.00 | 18.00 |
| 2 | የእንስሳት ጤና ባለሙያዎች በቢ ኤስ ሲ ዲግሪ ምዝገባ | 54.00 | 27.00 | 18.00 |
| 3 | የእንስሳት ጤና ፋርማሲስት ምዝገባ | 54.00 | 27.00 | 18.00 |
| 4 | ለረዳት የእንስሳት ሐኪም ምዝገባ | 54.00 | 27.00 | 18.00 |
| 5 | የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪ ባለሙያዎች በቢ ኤስ ሲ ዲግሪ ምዝገባ | 54.00 | 27.00 | 18.00 |
| 6 | የእንስሳት ጤና ቴክኒክና ሙያ (TVT ሥልጠና ደረጃ አራት ባለሙያዎች ምዝገባ | 54.00 | 27.00 | 18.00 |
| 7 | ክፍተኛ የእንስሳት መኖ ሙያተኛ ምዝገባ | 54.00 | 27.00 | 18.00 |
| 8 | መለስተኛ የእንስሳት መኖ ሙያተኛ ምዝገባ | 54.00 | 27.00 | 18.00 |
| 9 | የእንስሳት እርባታና ግብይት አስተዳደር ቴክኒክና ሙያ (TVT ሥልጠና ደረጃ አራት ባለሙያዎች ምዝገባ | 54.00 | 27 | 18.00 |
| 10 | የእንስሳት መድኃኒት ወይም የህክምና መሣሪያ ማስታወቂያ ፈቃድ ለማውጣት | 400.00 | 200.00 | 133.3 |
| 11 | እንስሳት መድኃኒት ወይም ህክምና መሣሪያዎች የማስተዋወቅ መታወቂያ ለማውጣት | 200.00 | 100.00 | 66.7 |

## ሠንጠረዥ ሦስት

## ለእንስሳት መድኃኒት የመልካም አመራረት ተሞክሮ ምልከታ በውጭ አገር አምራች ካምፓኒዎች የማድረግ አገልግሎት

| ተ.ቁ | ክፍለ አህጉር | የአገልግሎት አይነት | በአሜሪካን ዶላር (በግምገማ | በኢትዮጵያ ብር (በግምገማ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ምስራቅ አፍሪካ | የፋብሪካውን የመልካም አመራረት ሙሉ ግምገማ ማድረግ | 4,000 | 78,000 |
| 2 | ምስራቅ አፍሪካ | የፋብሪካውን በከፊል የመልካም አመራረት ግምገማ ማድረግ | 3,000 | 58,500 |
| 3 | ከምስራቅ አፍሪካ ውጭ | የፋብሪካውን የመልካም አመራረት ሙሉ ግምገማ ማድረግ | 4,500 | 87,750 |
| 4 | ከምስራቅ አፍሪካ ውጭ | የፋብሪካውን በከፊል የመልካም አመራረት ግምገማ ማድረግ | 4,000 | 78,000 |
| 5 | መካከለኛው ምስራቅ | የፋብሪካውን የመልካም አመራረት ሙሉ ግምገማ ማድረግ | 6,000 | 117,000 |
| 6 | መካከለኛው ምስራቅ | የፋብሪካውን በከፊል የመልካም አመራረት ግምገማ ማድረግ | 5,000 | 97,500 |
| 7 | ሩቅ ምስራቅና እስያ | የፋብሪካውን የመልካም አመራረት ሙሉ ግምገማ ማድረግ | 6,500 | 126,750 |
| 8 | ሩቅ ምስራቅና እስያ | የፋብሪካውን በከፊል የመልካም አመራረት ግምገማ ማድረግ | 6,000 | 117,000 |
| 9 | አውሮፓ፣ ሰሜን አሜሪካ እና ደቡብ አሜሪካ | የፋብሪካውን የመልካም አመራረት ሙሉ ግምገማ ለማድረግ ለሚያስፈልጋቸው ኩባንያዎች | 6,500 | 126,750 |

## ሠንጠረዥ አራት

## ለእንስሳት መዳኃኒት እና መኖ ተቋም ምዝገባና ፍቃድ አገልግሎት ክፍያ

| ተ.ቁ | የተቋማት ዓይነት | አዲስ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማውጣት (በብር | ለብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እድሳት (በብር | ምትክ ለማግኘት (በብር | ለ2ተኛ ዙር ቅድመ ፍቃድ ኢንስፔክሽን (በብር | ለ3ተኛ ዙር ቅድመ ፍቃድ ኢንስፔክሽን (በብር | የባለሙያ ለውጥ (በብር | የቦታ ለውጥ (በብር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የእንስሳት መድኃኒትናሕክምና መሣሪያ አስመጪ | 720 | 360 | 120 | 720 | 1440 | 360 | 360 |
| 2 | የእንስሳትመድኃኒትና ሕክምና መሣሪያ ላኪ | 720 | 360 | 120 | 720 | 1440 | 360 | 360 |
| 3 | የእንስሳትመድኃኒትሕክምና መሣሪያ ጅምላ አከፋፋይ | 600 | 300 | 120 | 720 | 1440 | 360 | 360 |
| 4 | የእንስሳት ሕክምና መሣሪያ አስመጪ፣ | 600 | 300 | 120 | 720 | 1440 | 360 | 360 |
| 5 | የእንስሳት ሕክምና መሣሪያ ጅምላ አከፋፋይ | 600 | 300 | 120 | 720 | 1440 | 360 | 360 |
| 6 | የአገር ውስጥ የመድኃኒት | 800 | 400 | 200 | 800 | 1600 | 400 | 400 |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | አምራች የማምረቻ ፍቃድ | | | | | | | |
| 7 | የሀገር ውስጥ የእንስሳት መኖ፤የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮች፤ ውህዶች፣ የመኖ መሣሪዎች መፈብረኪያ | 1820 | 910 | 303.3 | 1820 | 3640 | 910 | 910 |
| 8 | የእንስሳት መኖ፣ የመኖተጨማሪ ንጥረ ነገሮች፤ ውህዶች፣ የመኖመሣሪዎች፣ አስመጪ፤ | 1450 | 725 | 241.6 | 1450 | 2900 | 725 | 725 |
| 9 | የእንስሳት መኖ፣ የመኖተጨማሪ ንጥረ ነገሮች፤ ውህዶች ላኪ፣ | 885 | 442.5 | 147.5 | 885 | 1770 | 442.5 | 442.5 |
| 10 | የእንስሳት መኖ፣ የመኖተጨማሪንጥረ ነገሮች፤ ውህዶች፣ የመኖ መሣሪዎች፣ ጅምላ አከፋፋይ | 360 | 180 | 60 | 360 | 720 | 180 | 180 |

## አዋጅ ቁጥር 814/2006

## የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት አዋጅ

በቆዳ ኢንዱስትሪ ተወዳዳሪነት ላይ ከፍተኛ ተጽዋ የሚያሳድረው በሥራ ላይ ያለው ኋላቀር፣ የተንዛዛ እና ከፍተኛ የግብይት ወጪ የሚያስከትለው የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት ሥርዓትን ማሻሻል በማስፈለጉ፤

በከፍተኛ ደረጃ የሚታየውን የጥሬ ቆዳና ሌጦ ብክነትን እና የጥራት ጉድለትን ለማስቀረት የሚያስችል የግብይት ስርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፣

የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት በጥራት ደረጃ ላይ የተመሠረተ እንዲሆን የምርቱ አሰባሰብ፣ አዘገጃጀት፣አከመቻቸትና አጓጓዝ ሂደትን የሚያሻሽሉ የአሠራር ሥርዓቶችን መዘርጋት በማስፈለጉ፣

በሥራ ላይ በነበረው የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት ሥርዓት አዋጅ ውስጥ የታዩ ክፍተቶችን በመሙላት የግብይት ሥርዓቱን ዘመናዊ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 55(1 መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት አዋጅ ቁጥር 814/2006" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**[15]

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

   1. "ጥሬ ቆዳ" ማለት ከበሬ፣ ከላም፣ ከወይፈን፣ ከጊደር፣ ከግመል እና ከመሰል እንስሳ የሚገኝ ትኩስ፣ በአየር የደረቀ ወይም በጨው የተዘጋጀ ቆዳ ነው፤
   2. "ጥሬ ሌጦ" ማለት ከበግ፣ ከፍየል፣ ከጥጃ፣ ከአዞ፣ ከጥንቸል፣ ከሰጎን፣ ከዓሳ እና ከመሳሰሉት የሚገኝ ትኩስ፣ በአየር የደረቀ ወይም በጨው የተዘጋጀ ሌጦ ነው፤
   3. "ትኩስ ቆዳ ወይም ትኩስ ሌጦ" ማለት እንስሳው ከታረደ ከስድስት ሰዓት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የቀረበ በጨው ያልተዘጋጀ ወይም በአየር ያልደረቀ እርጥብ ቆዳ ወይም ሌጦ ነው፤

[15] የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (3)፣ (4)፣ (8)፣ (18)፣ (19) እና (20) በ(24)39(2010) አ.1073 አንቀፅ 2(1) መሰረት ተሻሻሉ፡፡

4. “ጨው” ማለት የጥሬ ቆዳና ሌጦን ለማዘጋጀት የሚያገለግል እና ለሰውም ሆነ ለእንስሳት ምግብነት የማይውል ኬሚካል የተጨመረበት ጨው ብሎ የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ የሰየመው ነው፤
5. “የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት” ማለት ጥሬ ቆዳና ሌጦን የመሰብሰብ፣ የማዘጋጀት፣ የማጓጓዝ፣ የማከማችት፣ የመሸጥና የመግዛት ሂደት ነው፤
6. “የመጀመሪያ ደረጃ ግብይት” ማለት አግባብ ባለው አካል በተሰየሙ የግብይት ማዕከላት ውስጥ በዚህ አዋጅ መሠረት የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት የሚፈጸምበት ሂደት ነው፤
7. “ሁለተኛ ደረጃ ግብይት” ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት ሻጭ በሆኑ አቅራቢዎች የኤክስፖርትና ከፍተኛ ቄራዎች እና ገዢ በሆኑ ቆዳ ፋብሪካዎች መካከል በሚደረግ ውል አማካኝነት የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት የሚፈጸምበት ሂደት ማለት ነው፣
8. “የግብይት ተሳታፊ”ማለት በጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት የሚሳተፉ አምራቾችን፣ ሰብሳቢዎችን፣ አቅራቢዎችን፣ባህላዊ ቆዳና ሌጦ አልፊዎችን፣ የቆዳ ፋብሪካዎችን እና አጓጓዦችን ያካትታል፤
9. “አምራች” ማለት አነስተኛ ወይም ከፍተኛ ቄራ፣ የኤክስፖርት ቄራ ወይም ለግል ፍጆታ የእንስሳት እርድ የሚፈጽም ወይም በእርድ አገልግሎትላይ በመሰማራት ጥሬ ቆዳና ሌጦን ለገበያ የሚያቀርብ ሰው ነው፤
10. “አነስተኛ ወይም ከፍተኛ ቄራ” ማለት አግባብ ባለው አካል አነስተኛ ወይም ከፍተኛ ተብሎ የተሰየመ ቄራ ነው፤
11. “የኤክስፖርት ቄራ” ማለት የቁም እንስሳትን በማረድ ለውጭ ገበያ የሚያቀርብ ሥጋና የሥጋ ውጤቶችን የሚያዘጋጅና የሚያቀነባብር ድርጅት ነው፤
12. “አቅራቢ” ማለት ጥሬ ቆዳና ሌጦ ከመጀመሪያ ደረጃ የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት ማዕከል ገዝቶ ለቆዳ ፋብሪካ የሚያቀርብ ሰው ነው፤
13. “የቆዳ ፋብሪካ” ማለት ጥሬ ቆዳና ሌጦን በማልፋት፣ በማለስለስና በማዘጋጀት ወደ አለቀ ቆዳ ምርት ደረጃ የሚያደርስ ፋብሪካ ነው፤
14. “ባህላዊ ቆዳ አልፊ” ማለት ጥሬ ቆዳና ሌጦን በባህላዊ መንገድ በማልፋት ባህላዊ የቆዳ ቁሳቁሶች የሚያመርት ሰው ነው፤
15. “ማጓጓዣ” ማለት ጥሬ ቆዳና ሌጦን ለማጓጓዝ አገልግሎት የሚውል ተሽከርካሪ ሲሆን የጭነት እንስሳንም ያጠቃልላል፤

16.“የማጓጓዝ ፍቃድ” ማለት ጥሬ ቆዳና ሌጦን ከቄራ ወይም ከመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከል ወደ ማዘጋጃና ማከማቻ መጋዘን ወይም ወደ ቆዳ ፋብሪካ ለማጓጓዝ እንዲቻል አግባብ ባለው አካል የሚሰጥ ፈቃድ ነው፤

17.“አሳሳች ድርጊት” ማለት በጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት ሂደት ውስጥ የግብይት ተሳታፊዎችን ወይም የመንግሥት አካልን ሊያሳስት ወይም ሊያታልል የሚችል ማንኛውም ድርጊት ነው፤

18.“የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት”‘የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት’ ማለት በጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት ለመሰማራት አግባብ ያለው አካል በመመሪያ የሚያወጣውን አስፈላጊውን መስፈርት ላሟላ ስው የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው፤

19.“ሚኒስቴር”ማለት የእንስሳትና ዓሳ ሀብት ሚኒስቴር ነው፤

20.“አግባብ ያለው አካል”ማለት እንደአግባቡ ሚኒስቴሩ ወይም የግብይቱን ሥራ የማስተዳደር ሥልጣን የተሰጠው የክልል አካል ነው፤

21.“ሴክተር መስሪያ ቤት” ማለት የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት ስርዓቱን በማስፈፀምና በመደገፍ ሂደት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ትስስር ያላቸውን የፌዴራልና የክልል አስፈፃሚ አካላት የሚያጠቃልል ነው፤

22.“ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ አንቀጽ 47(1 የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፣

23.“ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፣

24.“የጥሬ ቆዳና ሌጦ ሰብሳቢ” ማለት አግባብ ባለው አካል የተመዘገበ ሆኖ ትኩስ ጥሬ ቆዳና ሌጦ ምርት ከሚገኝበት ቦታ ተዘዋውሮ በተመዘገበበት አካባቢ ከግለሰብ አምራች በማሰባሰብ ለጥሬ ቆዳና ሌጦ አቅራቢዎች ወይም ለባህላዊ ቆዳና ሌጦ አልፊዎች በመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ላይ የሚሸጥ ሰው ነው፤[16]

25.“ክምችት” ማለት በማዘጋጃና በማከማቻ መጋዘን ውስጥ ቁጥሩ እንዲኖር ከሚፈቀደው መጠንና ጊዜ በላይ የጥሬ ቆዳና ሌጦ ይዞ መገኘት ነው፤

[16] ንዑስ አንቀፆች (24 ፣(25 ፣(26 እና (27 በ24)39(2010 አ.1073 አንቀፅ 2(2 መሰረት አዲስ የገቡ ሲሆን የቀድሞ ንዑስ አንቀፅ (24 ንዑስ አንቀፅ (28 ሆኖ ተሸጋሽጓል፡፡

26.“ደረጃ” ማለት የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ ለጥሬ ቆዳና ሌጦ ያወጣው የጥራት ማረጋገጫ ነው፤

27.“ግለሰብ አምራች” ማለት ለግል ድርጅት የእንስሳት እርድ በመፈፀም ወይም ቤት ለቤት በመዘዋወር የእርድ አገልግሎት በመስጠት ትኩስ ቆዳ ወይም ሌጦን ለሽያጭ የሚያቀርብ ሰው ነው፤”

28.ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ይጨምራል።

3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅ በአገሪቱ ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት ላይ በሚሳተፍ ማንኛውም ሰው ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት ስርዓት

4. <u>የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት</u>

የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት የሚካሄደው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 ወይም አንቀጽ 6 መሠረት በመጀመሪያ ወይም በሁለተኛ ደረጃ ግብይት ይሆናል፡፡

5. <u>የጥሬ ቆዳና ሌጦ የመጀመሪያ ደረጃ ግብይት</u>[17]

1. የጥሬ ቆዳና ሌጦ የመጀመሪያ ደረጃ ግብይት የሚፈጸምባቸው የገበያ ማዕከላት አደረጃጀት እና አስተዳደር ሚኒስቴሩ በሚያወጣዉ መመሪያ ይወሰናል፡፡
2. በግብይት ማዕከላት ውስጥ የጥሬ ቆዳና ሌጦ የመጀመሪያ ደረጃ ግብይት የሚካሄደው ፤[18]

   ሀ) በግለሰብ አምራቾች እና በአቅራቢዎች

   ለ) በግለሰብ አምራቾች እና በባህላዊ ቆዳ አልፊዎች ወይም

   ሐ) በአነስተኛ ቄራዎች እና በአቅራቢዎች

---

[17] የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (8 በ24)39(2010 አ.1073 አንቀፅ 2(4 መሰረት ተሰርዟል፡፡

[18] የዚህ ንዑስ አንቀፅ ፊደል ተራ (መ እስከ (ረ በ24)39(2010 አ.1073 አንቀፅ 2(3 መሰረት አዲስ የገቡ ናቸው፡፡

መ) በግለሰብ አምራቾች እና በጥሬ ቆዳና ሌጦ ሰብሳቢዎች፤

ሠ) በጥሬ ቆዳና ሌጦ ሰብሳቢዎች እና በባህላዊ ቆዳና ሌጦ አልፊዎች፤ እና

ረ) በጥሬ ቆዳና ሌጦ ሰብሳቢዎች እና አቅራቢዎች፤"

መካከል ይሆናል፡፡

3. በመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከል የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት የሚካሄደው በድርድር ወይም በጨረታ ሊሆን ይችላል፡፡
4. ለመጀመሪያ ደረጃ ግብይት የሚቀርበው ጥሬ ቆዳና ሌጦ ትኩስ በአየር የደረቀ ብቻ ይሆናል፡፡
5. በአቅራቢ የሚፈጸም የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግዢ በአቅራቢው በራሱ ወይም በወኪሉ አማካኝነት መፈፀም አለበት፡፡
6. በአቅራቢ የተገዛው ጥሬ ቆዳና ሌጦ የማጓጓዝ ፍቃድ ወጥቶለት ወደ አቅራቢው ወይም በባህላዊ አልፊው የማዘጋጃና የማከማቻ መጋዘን ይሸኛል።
7. የጥሬ ቆዳና ሌጦ ዋጋ በጥራት ደረጃ ይወሰናል፣

6. <u>**የጥሬ ቆዳና ሌጦ ሁለተኛ ደረጃ ግብይት፤**</u>

1. የጥሬ ቆዳና ሌጦ ሁለተኛ ደረጃ ግብይት የሚፈጸመው፡-

   ሀ) በአቅራቢዎች እና በቆዳ ፋብሪካዎች፤

   ለ) በከፍተኛ ቄራዎች እና በቆዳ ፋብሪካዎች፣ ወይም

   ሐ) በኤክስፖርት ቄራዎች እና በቆዳ ፋብሪካዎች፤

   መካከል ይሆናል፡፡
2. በሁለተኛ ደረጃ የግብይት ማዕከል የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት የሚካሄደው በድርድር ወይም በጨረታ ሊሆን ይችላል፡፡
3. ሁለተኛ ደረጃ ግብይት የሚፈጸምበት ጥሬ ቆዳና ሌጦ ትኩስ በአየር የደረቀ ወይም በጨው የተዘጋጀ ሊሆን ይችላል፡፡
4. በሁለተኛ ደረጃ ግብይት የግብይቱ ውል በፅሁፍ መሆን ያለበት ሆኖ የውሉ ዝርዝር ሁኔታዎች ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሰረትየተመለከቱትን መያዝ አለበት፡፡
5. ግብይት የተካሄደበት ጥሬ ቆዳና ሌጦ ርክክብ የሚፈጸመው በአቅራቢው የማዘጋጃና ማከማቻ መጋዘን ወይም በከፍተኛ ቄራዎች ወይም በኤክስፖርት ቄራዎች ወይም በቆዳ ፋብሪካው ውስጥ ይሆናል፡፡
6. የጥሬ ቆዳና ሌጦ ዋጋ በጥራት ደረጃ ይወሰናል፡፡

7. **የጥሬ ቆዳና ሌጦ ጥራት ቁጥጥር**

   1. የጥሬ ቆዳና ሌጦ የጥራት ደረጃ በኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ ይዘጋጃል።
   2. የጥሬ ቆዳና ሌጦ የጥራት ደረጃ የማረጋገጥና የቁጥጥር ስራ ከመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከል ጀምሮ ሲሆን ዝርዝሩ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡
   3. ጥሬ ቆዳና ሌጦ ለግብይት በሚቀርብበት ወቅት የጥራት ደረጃውን ጠብቆ ስለመቅረቡ አግባብ ባለው አካል ቁጥጥር ይደረግበታል፡፡
   4. ጥሬ ቆዳና ሌጦ ከአቅራቢ ማዘጋጃና ማከማቻ መጋዘን እንዲሁም ከከፍተኛ ቄራዎች እና ኤክስፖርት ቄራዎች ወደ ቆዳ ፋብሪካ ከመጓጓዙ በፊት አግባብ ባለው አካል የጥራት ደረጃውን ጠብቆ ስለመዘጋጀቱ ተረጋግጦና ታሽጎ የማጓጓዝ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡

## ክፍል ሦስት

## የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት ተሳታፊዎች ግዴታዎች

8. **የአምራች ግዴታዎች**

   ማንኛውም የጥሬ ቆዳና ሌጦ አምራች፡-

   1. የጥሬ ቆዳና ሌጦ ጥራትን ጠብቆ የማምረት፣
   2. ያመረተውን ጥሬ ቆዳና ሌጦ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 መሠረት ለግብይት ማዕከል ወይም በአንቀጽ 6 መሠረት ውል ለገባለት የቆዳ ፋብሪካ በወቅቱ የማቅረብ፣ እና
   3. የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎችና አዎጁን ለማስፈጸም የወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን የማክበር፤

   ግዴታዎች አሉበት።

9. **የአቅራቢ ግዴታዎች**[19]

   ማንኛውም የጥሬ ቆዳና ሌጦ አቅራቢ፡-

   1. መስፈርቱን የሚያሟላ የራሱ ወይም የተከራየው የጥሬ ቆዳና ሌጦ ማዘጋጃና ማከማቻ ኖሮት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትና የንግድ ፈቃድ የማውጣት፣
   2. ጥሬ ቆዳና ሌጦን ከመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከላት ብቻ የመግዛት፣

[19] የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (10 በ24)39(2010 አ.1073 አንቀፅ 2(5 መሰረት አዲስ የገባ ሲሆን ቀድሞው ንዑስ አንቀፅ (10 ንዑስ አንቀፅ (11 ሆኖ ተሸጋሽጓል፡፡

3. ጥሬ ቆዳና ሌጦ በክምችት እንዲቀመጥ ከተፈቀደው ጊዜ በላይ ያለማከማቸት፣
4. በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው ደንብ ከተገለፀው መጠን በላይ የተዘጋጀ ጥሬ ቆዳና ሌጦ በክምችት አለመያዝ፤
5. ጥሬ ቆዳና ሌጦን ግብይት ማዕከል ወደ ማዘጋጃና ማከማቻ መጋዘን ወይም ከማዘጋጃና ማከማቻ መጋዘን ወደ ቆዳ ፋብሪካ ለማጓጓዝ አግባብ ባለው አካል የተሰጠ የማጓጓዝ ፈቃድ የመያዝ፣
6. የየዕለቱን የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግዢ እና ሽያጭ መጠን፣ ደረጃ እና ዋጋ መዝግቦ የመያዝ እና አግባብ ባለው አካል ሲጠየቅ ይህንኑ መረጃ የመስጠት፣
7. አግባብ ባለው አካል ሲጠየቅ የጥሬ ቆዳና ሌጦ ማዘጋጃ እና ማከማቻ መጋዘኖቹ እንዲጎበኙ የመፍቀድ፣
8. ለቆዳ ፋብሪካዎች ጥሬ ቆዳና ሌጦ ለመሸጥ በገባው ውል መሠረት ጥራቱን ጠብቆ የማቅረብ፣
9. የአገሪቱን የጥሬ ቆዳና ሌጦ ጥራት እና ግብይት ከሚያጎድፉ ማናቸውም ድርጊቶች የመቆጠብ፣ እና
10. የአካባቢን ብክለት ለመከላከል በወጡ ሌሎች ሕጎች መሠረት ብክለትን በማያስከትል ሁኔታ የመስራት፣የማዘጋጀትና የማስተዳደር፤
11. የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎችና አዋጁን ለማስፈጸም የወጡ ደንቦችንናመመሪያዎችን የማክበር፤

ግዴታዎች አሉበት።

10.**<u>የጥሬ ቆዳና ሌጦ አጓጓዥ ግዴታዎች</u>**

ማንኛውም የጥሬ ቆዳና ሌጦ አጓጓዥ፡-

1. ጥሬ ቆዳና ሌጦ ሲያጓጉዝ አግባብ ባለው አካል የተሰጠ የማጓጓዝ ፈቃድ የመያዝና አግባብ ባለው አካል በተመደበ ተቆጣጣሪ ሲጠየቅ የማሳየት፣
2. የአገሪቱን የጥሬ ቆዳና ሌጦ ጥራት እና ግብይት ከሚያጎድፉ ማናቸውም ድርጊቶች የመቆጠብ፣
3. የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎችና አዋጁን ለማስፈጸም የወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን የማክበር፣

ግዴታዎች አሉበት።

## 11.<u>የቆዳ ፋብሪካ ግዴታዎች</u>[20]

ማንኛዉም የቆዳ ፋብሪካ፡-

1. መስፈርቱን በማሟላት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትና የንግድ ፈቃድ የማውጣት፤
2. ጥሬ ቆዳና ሌጦን በሁለተኛ ደረጃ ግብይት ብቻ የመግዛት፣
3. ከአቅራቢዎችና ከቄራዎች ጋር በገባው ውል መሠረት ጥሬ ቆዳና ሌጦ የመቀበል እና ክፍያ የመፈጸም፣
4. የየዕለቱን የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግዢ መጠን፣ ደረጃ እና ዋጋ መዝግቦ የመያዝ እና አግባብ ባለው አካል ሲጠየቅ ይህንኑ መረጃ የመስጠት፣
5. አግባብ ያለው አካል የጥሬ ቆዳና ሌጦ አያያዝ እና የምርት ሂደትን ለመጎብኘት ሲጠይቅ የመተባበር ፤
6. ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ከተገለፀው የጊዜ ገደብ በላይ ጥሬ ቆዳና ሌጦ ከምርት ሂደት ውጪ በክምችት ያለመያዝ፣
7. የአገሪቱን የጥሬ ቆዳና ሌጦ ጥራት እና ግብይት ከሚያጎድፉ ማናቸውም ድርጊቶች የመቆጠብ፣ እና
8. የአካባቢን ብክለት ለመከላከል በወጡ ሌሎች ሕጎች መሠረት ብክለትን በማያስከትል ሁኔታ የመስራት፣ የማዘጋጀትና የማስተዳደር፤
9. የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎችና አዋጁን ለማስፈጸም የወጡ ደንቦችና መመሪያዎችን የማክበር፤

ግዴታዎች አሉበት።

## 12.<u>የጥሬ ቆዳና ሌጦ ሰብሳቢዎች ግዴታ</u>[21]

ማንኛውም የጥሬ ቆዳና ሌጦ ሰብሳቢ፡-

1. የአካባቢ ብክለትን ለመከላከል በወጡ ሌሎች ሕጎች መሠረት ብክለትን በማያስከትል ሁኔታ የመስራት፣ የማዘጋጀትና የማስተዳደር፤
2. ትኩስ ቆዳና ሌጦን ከግለሰብ አምራቾች ብቻ የመግዛት፤
3. ጥሬ ቆዳና ሌጦን ጥራቱን ጠብቆ የመሰብሰብ፤

[20] የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (8 በ24)39(2010 አ.1073 አንቀፅ 2(6 መሰረት አዲስ የገባ ሲሆን ነባሩ ንዑስ አንቀፅ (8 ንዑስ አንቀፅ (9 ሆኗል፡፡

[21] አንቀፅ 12 እና 13 በ24)39(2010 አ.1073 አንቀፅ 2(7 መሰረት አዲስ የገቡ ሲሆን ነባሮቹ ድንጋጌዎች ከአንቀጽ 12 እስከ አንቀጽ 17 ያሉት እንደቅደም ተከተላቸው ከአንቀጽ 14 እስከ 19 ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

4. አግባብ ባለው አካል ሲጠየቅ ጥሬ ቆዳና ሌጦ እንዲሰበስብ አግባብ ባለው አካል ተመዝግቦ የተሰጠውን ማረጋገጫ የማሳየትም ሆነ የጥሬ ቆዳና ሌጦ የሚያሰባስብበትን ቦታ እንዲጎበኝ የመፍቀድ ግዴታ አለበት
5. የአገሪቱን የጥሬ ቆዳና ሌጦ ጥራትና ግብይት ከሚያጎድፉ ማናቸውም ድርጊቶች የመቆጠብ፤ እና
6. የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎችና አዋጁን ለማስፈፀም የወጡ ደንብና መመሪያዎችን የማክበር፤

   ግዴታዎች አሉበት፡፡

13.**<u>የጥሬ ቆዳና ሌጦ ባህላዊ አልፊዎች ግዴታ</u>**

ማንኛውም የጥሬ ቆዳና ሌጦ ባህላዊ አልፊ :-

1. የአካባቢ ብክለትን ለመከላከል በወጡ ሌሎች ሕጎች መሠረት ብክለትን በመከላከል መስራት፤
2. ከሚመለከተው አካል ሥራውን ለመስራት የሚያስችለው የንግድ ፈቃድ የማውጣት፤
3. ጥሬ ቆዳና ሌጦን ከአምራች ወይም ከጥሬ ቆዳና ሌጦ ሰብሳቢዎች ብቻ የመግዛት፤
4. ጥሬ ቆዳና ሌጦን ያለማከማቸት፤
5. የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግዥና ሽያጭ መጠን፣ ደረጃና ዋጋ መዝግቦ የመያዝና አግባብ ባለው አካል ሲጠየቅ ይህንኑ መረጃ የመስጠት/የማሳየት፤
6. አግባብ ባለው አካል ሲጠየቅ የጥሬ ቆዳና ሌጦ ማልፊያ ቦታውን እንዲጎበኝ የመፍቀድ፤
7. የአገሪቱን የጥሬ ቆዳና ሌጦ ጥራት እና ግብይት ከሚያጎድፉ ማናቸውም ድርጊቶች የመቆጠብ፤ እና
8. የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎችና አዋጁን ለማስፈፀም የወጡ ደንብና መመሪያዎችን የማክበር፤

ግዴታዎች አሉበት፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 14. አግባብ ያለው አካል ሥልጣንና ተግባር

በሌሎች ሕጎችና በዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች የተመለከቱት ሥልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆኖ አግባብ ያለው አካል የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የጥሬ ቆዳና ሌጦ የመጀመሪያ ደረጃ ግብይት የሚፈጸምባቸውን ማዕከላት የመሰየም እና ተፈላጊ መስፈርቶችን ማሟላታቸውን የማረጋገጥ፤
2. ለግብይት የሚቀርብ ጥሬ ቆዳና ሌጦ የጥራት ደረጃውን የጠበቀ መሆኑንለማረጋገጥ ክትትል የማድረግ፣
3. ማንኛውም የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት ተሳታፊ የግብይት ሥርዓቱን የሚያዛባ አሳሳች ድርጊት ፈጽሞ ሲገኝ ተገቢውን አስተዳደራዊ እርምጃ የመውሰድ፣
4. በጥሬ ቆዳና ሌጦ ንግድ ለሚሳተፉና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለያዙ ሰዎች የንግድ ፈቃድ የመስጠት፣
5. በሕገ ወጥ መንገድ ተከማችቶ ወይም ሲጓጓዝ ወይም ግብይት ሲፈጸምበት የተገኘ ጥሬ ቆዳና ሌጦ የመያዝ፤ ጥሬ ቆዳና ሌጦው ትኩስ ከሆነ ከ4 ሰዓት ወይም በአየር የደረቀ ወይም በጨው የተዘጋጀ ከሆነ ከ24 ሰዓት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለአቅራቢዎች ወይም ለቆዳ ፋብሪካዎች በመሸጥ ገንዘቡን በዝግ የባንክ ሂሳብ እንዲቀመጥ የማድረግ፤ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 14 መሠረት እንዲወረስ ሲወሰንም ለመንግሥት ገቢ እንዲሆን የማድረግ፣
6. ሕገ ወጥ የጥሬ ቆዳና ሌጦ ንግድ እንቅስቃሴን ለሚጠቁሙ ሰዎች የኮሚሽን አበል መጠን በማጥናት ለመንግሥት ማቅረብና ሲፀድቅ ተግባራዊ የማድረግ፣
7. ለሚሰጠው አገልግሎት በመንግስት በሚወስነው ተመን መሠረት የአገልግሎት ክፍያ የማስከፈል፡፡

### 15. የመተግበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው ይህን አዋጅ እና አዋጁን ለማሰፈጸም የወጡ ደንብና መመሪያዎችን በማስፈፀም ረገድ ከሚኒስቴሩ እና አግባብ ካለው አካል ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

16.ቅጣት

1. በመጀመሪያ ደረጃ ግብይት እንዲገበያይ ካልተፈቀደለት ሰው ጋር የጥሬ ቆዳ ወይም ሌጦ የመጀመሪያ ደረጃ ግብይት የፈጸመ ማንኛውም ሰው ጥሬ ቆዳ ወይም ሌጦው እንዲወረስ ይደረጋል፣ ሆኖም ለግል ፍጆታው ከሚያመርተው ሰው ውጭ ሆኖ በተገኘ ጊዜ በተጨማሪ ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራትና ከብር 15 ሺ.ህ (አስራ አምስት ሺ.ህ በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡[22]
2. የጥሬ ቆዳ ወይም ሌጦ የመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ለመፈጸም በአንድ የግብይት ማዕከል ከራሱ በተጨማሪ ወኪል ያሰማራ ወይም ከአንድ በላይ ወኪሎች ያሰማራ ማንኛውም አቅራቢ ከስድስት ወር በማይበልጥ ቀላል እስራት እና ከብር 5ሺ. በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡
3. በሁለተኛ ደረጃ ግብይት እንዲገበያይ ካልተፈቀደለት ሰው ጋር የጥሬ ቆዳ ወይም ሌጦ ሁለተኛ ደረጃ ግብይት የፈጸመ ማንኛውም ሰው ጥሬ ቆዳው ወይም ሌጦው እንዲወረስ ተደርጎ ከሶስት ዓመት የማይበልጥ ቀላል እስራት እና ከብር 50ሺ. በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡
4. በቆዳ ወይም ሌጦ የመጀመሪያ ደረጃም ሆነ የሁለተኛ ደረጃ ግብይት በተመሳሳይ ምድብ ከሚገኝ የግብይት ተሳታፊ ጋር ግብይት የፈጸመ ማንኛውም ሰው ከሁለት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት እና ከብር 30ሺ. በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡
5. በጥሬ ቆዳ ወይም ሌጦ ግብይት ሂደት አሳሳች ድርጊት የፈጸመ ማንኛውም ሰው ከአራት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት እና ከብር 60ሺ. በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡
6. በዚህ አዋጅ መሰረት ለገበያ ለማቅረብ በአምራች የሚጓጓዝ ጥሬ ቆዳና ሌጦን ሳይጨምር፣ የማጓጓዝ ፈቃድ ሳይዝ ጥሬ ቆዳ ወይም ሌጦን ከቦታ ቦታ ሲያዘዋውር የተገኘ ማንኛውም ሰው ጥሬ ቆዳና ሌጦው እንዲወረስ ተደርጎ ከስድስት ወር በማይበልጥ ቀላል እስራት እና ከብር 5ሺ. በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡
7. ሕገ ወጥ ግብይት የተፈጸመበትን ጥሬ ቆዳ ወይም ሌጦ ሲያጓጉዝ የተገኘ ማንኛውም አጓጓዥ ከሁለት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት እና ከብር 30 ሺ. በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

[22] በ24/39(2010) አ.1073 አንቀፅ 2(7) ተሻሻለ፡፡

8. ጥሬ ቆዳ ወይም ሌጦ በክምችት እንዲቀመጥ ከተፈቀደው ጊዜና ቦታ ውጪ አግባብ ያለውን አካል ሳያስፈቅድ አከማችቶ የተገኘ ማንኛውም ሰው ጥሬ ቆዳው ወይም ሌጦው እንዲወረስ ተደርጎ ከሁለት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት እና ከብር 30ሺ በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡
9. የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም አዎጁን ለማስፈፀም የሚወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን በመተላለፍ ሌላ ጥፋት የፈጸመ ማንኛውም ሰው ከስድስት ወር በማይበልጥ ቀላል እስራት እና ከብር 5ሺ በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡
10. በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል በወንጀል ሕግ አንቀጽ 34 በተደነገገው መሠረት በዚህ አንቀጽ በተመለከቱ ጥፋቶች ተካፋይ በሚሆንበት ጊዜ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 90 መሠረት ይቀጣል፡፡

17.<u>የተሻሩ ሕጎች</u>

ጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት ስርዓት አዋጅ ቁጥር 457/1997 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

18.<u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የሚያስፈልግ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ሚኒስቴሩ ይህንን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1 መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

19.<u> አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መጋቢት 16 ቀን 2006 ዓ ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ**

**ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**ደንብ ቁጥር 339/2007**

## የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት አዋጅ ቁጥር 814/2006 አንቀጽ 16 /1/ መሰረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 339/2007" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

   1. "አዋጅ" ማለት የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት አዋጅ ቁጥር 814/2006 ነው፤
   2. በአዋጁ አንቀጽ 2 የተሰጠ ትርጓሜ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

### ክፍል ሁለት

### ስለጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት ሥርዓት

3. **የግብይት ማዕከላት ብዛትና ስርጭት**

   አግባብነት ያለው አካል በሕግ ሥልጣን ከተሰጣቸው ሌሎች አካላት ጋር በመሆን የመጀመሪያ ደረጃ የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት ማዕከላትን ብዛትና ሥርጭት ይወስናል።

4. **የመጀመርያ ደረጃ የግብይት ማዕከላትን ስለመሰየም**

   1. አግባብ ያለው አካል በሕግ ሥልጣን ከተሰጣቸው ሌሎች አካላት ጋር በመመካከርየመጀመሪያ ደረጃ የጥሬ ቆዳና ሌጦ የግብይት ማዕከላትን ሲሰይምና ብዛትና ስርጭት ሲወስን የሚከተሉትን መስፈሮቶች ከግምት ማስገባት ይኖርበታል፡፡

      ሀ) ለጥሬ ቆዳና ሌጦ አምራቾችና አቅራቢዎች ያላቸው ቀረቤታ፤

      ለ) ተሽከርካሪን ለማስገባትና ለማስወጣት ያላቸው አመቺነት፤

      ሐ) ለጥሬ ቆዳና ሌጦ የግብይት አገልግሎት ለመስጠት ያላቸው አመቺነት፤

መ) ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ከመኖሪያ ቤቶች፣ ከትምህርት ቤቶች፣ ከጤናና ከእምነት ተቋማት እና ከመደበኛ የመገበያያ ማዕከላት በበቂ ርቀት ላይ መገኘት፤

ሠ) የአካባቢ ብክለትን የማያስከትል መሆን፤

ረ) ጽዳቱ የተጠበቀና ለመረጃ አገልግሎት አሰጣጥ የተመቻቸ መሆን።

2. የግብይት ማዕከሉ ለአጎራባች ወረዳዎች ወይም ቀበሌዎች የሚያገለግል ከሆነ የአጎራባች ወረዳዎቹ ወይም ቀበሌዎቹ አግባብ ያላቸው አካላት ከሴክተር መሥሪያ ቤቶች ጋር በጋራ የሚወስኑት ይሆናል፡፡

5. <u>***የመጀመሪያ ደረጃ የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት ማዕከል ማሟላት ያለበት መስፈርት***</u>

1. የመጀመሪያ ደረጃ የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት ማዕከል እንደ አካባቢው የመሬት አቅርቦት እና የጥሬ ቆዳና ሌጦ ምርት አቅርቦት መጠን የሚወሰን ሆኖ የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟላ መሆን አለበት፦

ሀ) ስፋቱ ከ 1600 ካሬ ሜትር የማያንስ፣

ለ) ዙሪያው ከአካባቢው በሚገኝ ቁሳቁስ የተሰራ አጥር ያለው፣

ሐ) የደረቅ ቆሻሻ ማቃጠያ፣ የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ፣ የጋራ መገልገያዎች እና መፀዳጃ ቤት ያለው፤

መ) የገበያ መረጃ ሠሌዳ ያለውና ለመረጃ አገልግሎት የተመቻቸ፡፡

2. እያንዳንዱ የጥሬ ቆዳና ሌጦ አቅራቢ ወይም ባህላዊ አልፊ በግብይት ማዕከል አንድ ወጥ ሆኖ በተዘጋጀ ዳስ ውስጥ ማጠራቀሚያ ወይም መደብ እንዲኖረው ይደረጋል፡፡

6. <u>***የመጀመሪያ ደረጃ የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት ማዕከላት አስተዳደር***</u>

1. የመጀመሪያ ደረጃ የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት ማዕከል ግብይት ማዕከሉ በሚገኝበት ወረዳ ወይም ከተማ ውስጥ በሚገኝ ማዕከሉን እንዲያስተዳድር ሥልጣን በተሰጠው አካል በበላይነት የሚተዳደር ይሆናል፡፡

2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የመጀመሪያ ደረጃ የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት ማዕከልን የሚያስተዳድር ስልጣን የተሰጠው አካል የሚከተሉት ስልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ) አጠቃላይ የገበያውን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ሚከታተል እና የሚቆጣጠር አካል ይመድባል፣

ለ) የግብይት ማዕከሉ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ መረጃዎችን አደራጅቶ በወቅቱ ለሚመለከተው አካል እንዲቀርቡ ያደርጋል፤

ሐ) የግብይት ማዕከሉ በጥሬ ቆዳና ሌጦ ጥራት ላይ ተጽዕኖ ከሚያሳድሩ የአካባቢው ሁኔታዎች ነጻ እንዲሆን ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፤

መ) ግብይት ለተፈጸመበት ጥሬ ቆዳና ሌጦ የማጓጓዝ ፈቃድ ይሰጣል፤

ረ) የግብይት ማዕከሉ በከተማ የሚገኝ ከሆነ ካርታና ፕላን ወይም በገጠር የሚገኝ ከሆነ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተር እንዲኖረው ያደርጋል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት ተሳታፊዎች ግዴታዎች

7. **የወል ግዴታዎች**

1. ትኩስ ቆዳ ወይም ሌጦ ከመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከል ከተሰበሰበበት ወይም ከከፍተኛ ቄራ ወይም ከኤክስፖርት ቄራ እርድ ከተፈጸመበት ጊዜ ጀምሮ ከ6 ሰዓት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ወደ አቅራቢዎች ማዘጋጃና ማከማቻ መጋዘን ወይም ወደ ቆዳ ፋብሪካዎች መድረስ አለበት፡፡
2. በጨው የተዘጋጀ ወይም በአየር የደረቀ የጥሬ ቆዳ ወይም ሌጦ ከሆነ ከአቅራቢው ማዘጋጃና ማከማቻ መጋዘን፣ ከከፍተኛ ቄራ ወይም ከኤክስፖርት ቄራ ወደ ቆዳ ፋብሪካ ከአንድ ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ መድረስ አለበት፡፡
3. ማንኛውም የግብይት ተሳታፊ አዋጁን፣ የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች እና ደንቡን ለማስፈፀም የወጡትን መመሪያዎች የማክበር ግዴታ አለበት፡፡
4. ማንኛውም የጥሬ ቆዳ ወይም ሌጦን አምራች ለሌላ አምራች መሸጥ የተከለከለ ነው፣ እንዲሁም ማንኛውም ጥሬ ቆዳ ወይም ሌጦ አቅራቢ ወይም ባህላዊ አልፊ ለሌላ አምራች፣ ባህላዊ አልፊ ወይም አቅራቢ መልሶ መሸጥ የተከለከለ ነው።
5. ጥሬ ቆዳና ሌጦን በአዋጁና በዚህ ደንብ መስረት የሚገበያይ አቅራቢ፣ ከፍተኛ ቄራ፣ ኤክስፖርት ቄራ ወይም ቆዳ ፋብሪካ እንደ ቅደምተከተሉ ለሌላ አቅራቢ፣ ከፍተኛ ቄራ፣ ኤክስፖርት ቄራ ወይም ቆዳ ፋብሪካ መልሶ መሸጥ የተከለከለ ነው፡፡
6. የጥሬ ቆዳ ወይም ሌጦ በጨው የሚያዘጋጅ ማንኛውም የግብይት ተሳታፊ የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ የጥሬ ቆዳና ሌጦን ለማዘጋጀት የሚያገለግል ኬሚካል ጨው ብሎ ከሰየመው ጨው ውጭ ሌላ ጨው መጠቀም እና ማዘጋጀት ወይም ጥቅም ላይ የዋለን ጨው በድጋሚ መጠቀም የለበትም፡፡

7. ማንኛውም የግብይት ተሳታፊ በጥሬ ቀዳ ወይም ሌጦ ግብይት እና በጥራት ቁጥጥር ላይ አሳሳች ድርጊት መፈጸም የለበትም፡፡

8. **<u>የአምራች ግዴታዎች</u>**

የአዋጁ አንቀጽ 8 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁሆነው ማንኛውም ጥሬ ቆዳና ሌጦ አምራች ግብርና ሚኒስቴር እና የክልል ግብርና ቢሮ የሚያወጡትን መመሪያ በማክበር ማምረትና በአዋጁ አንቀጽ 5 እና 6 መሠረት ለግብይት ማዕከልየማቅረብ ግዴታዎች አሉበት።

9. **<u>የአቅራቢ ግዴታዎች</u>**

የአዋጁ አንቀጽ 9 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም ጥሬ ቆዳና ሌጦ አቅራቢ፦

1. የጥሬ ቆዳና ሌጦ ማዘጋጃና ማከማቻ መጋዘን ግብርና ሚኒስቴር በሚያወጣው መስፈርት መሰረት መገንባት ወይም የተገነባን መከራየት፤
2. የጥሬ ቆዳና ሌጦን ግብርና ሚኒስቴር በሚያወጣው መስፈርት መሠረት በተገነቡ ማደራጃና ማከማቻ መጋዘኖች ውስጥ ብቻ የማዘጋጀትና የማከማቸት፤
3. ግብይት የተፈጸመበት ጥሬ ቆዳና ሌጦ ትኩስ ከሆነ በ6 ሰዓት ውስጥ ወደ አቅራቢዎች ማዘጋጃና ማከማቻ መጋዘን በማጓጓዝ ማድረስ ወይም የሽያጭ ውል ስምምነት ለገባለት ቆዳ ፋብሪካ የማቅረብ ወይም ግብይት የተፈጸመበት ጥሬ ቆዳና ሌጦ በአየር የደረቀ ወይም በጨው የተዘጋጀ ከሆነ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የሽያጭ ውል ስምምነት ለገባለት ቆዳ ፋብሪካ የማቅረብ፤
4. በማዘጋጃና ማከማቻ መጋዘን ውስጥ በቁጥር ከ5 ሺ በላይ የሆነ ጥሬ ቆዳና ሌጦ ክምችት አለመያዝ፤
5. የጥሬ ቆዳና ሌጦን ጥራት ሊያጎድፉ ከሚችሉ ሌሎች ነገሮች ጋር ቀላቅሎ ያለማከማቸት፤
6. የጥሬ ቆዳና ሌጦን አየር ሊያዘዋውር በሚችል መልኩበተዘጋጀው ርብራብ ላይ በአግባቡ የማስቀመጥ፤
7. ትኩስ ጥሬ ቆዳና ሌጦ ለቆዳ ፋብሪካዎች በጊዜ ማቅረብ በማይቻልበት ወቅት ምርቱን በጨው የማጀል ወይም በአየር የማድረቅ፤
8. ለቆዳ ፋብሪካዎች የሚያቀርበው የጥሬ ቆዳና ሌጦ አቅርቦት የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ በተቀመጠው ደረጃ መሰረት ጥራቱን የጠበቀ መሆኑን የማረጋገጥ፤

9. የአንድ አካባቢ ጥሬ ቆዳና ሌጦን ከሌላ አካባቢ ጥሬ ቆዳና ሌጦ ሳያደባልቅ የማዘጋጀት፤
10. ጥሬ ቆዳና ሌጦን ደረጃውን በጠበቀ የደረቅ ጭነት ተሽከርካሪ ማጓጓዝ የሚገባው ሲሆን ዝርዝሩ የሚመለከተው ሴክተር መሥሪያ ቤት በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የመፈጸም፤
11. የንግድ ፍቃድን በማንኛውም መልኩ ለሶስተኛ ወገን ያለማስተላለፍ ፤
12. አግባብነት ባለው አካል በተመደበ የጥሬ ቆዳና ሌጦ ጥራትና ግብይት ተቆጣጣሪ ተረጋግጦና ታሽጎ ወደ ቆዳ ፋብሪካ እንዲደርስ የተላከውን ጥሬ ቆዳና ሌጦ በወቅቱና በአግባቡ ውል ለገባለት ቆዳ ፋብሪካ መድረሱን የሚገልጽ የግብረ መልስ ሪፖርት ከቆዳ ፋብሪካው የመቀበልና ለጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት ተቆጣጣሪ በወቅቱ የማቅረብ፤

   ግዴታዎች አሉበት።

10. <u>የቆዳ ፋብሪካዎች ግዴታዎች</u>

በአዋጁ አንቀጽ 11 የተመለከቱት ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም የቆዳ ፋብሪካ፦

1. የጥሬ ቆዳና ሌጦ ርክክብ የተፈጸመው ከአቅራቢ፣ ከከፍተኛ ቄራ ወይም ኤክስፖርት ቄራ ማዘጋጃና ማከማቻ መጋዘን ከሆነ ምርቱ ወደ ቆዳ ፋብሪካው በሚጓጓዝበት ወቅት በፕሎምፕ የማሳሸግ፣ የማጓጓዣ ፈቃድ መያዝና በጉዞ ላይ አግባብ ባለው ተቆጣጣሪ ሲጠየቅ የማሳየት፤
2. ጥሬ ቆዳና ሌጦው በሚያጓጉዝበት ወቅት የሚመለከተው ሴክተር መሥሪያ ቤት ስለጭነት ተሽከርካሪ ያወጣውን መመሪያ የማክበርና ተግባራዊ የማድረግ፤
3. በጥሬ ቆዳና ሌጦ ጥራትና ግብይት ተቆጣጣሪ ተረጋግጦና ታሽጎ ወደ ቆዳ ፋብሪካ የተላከው ጥሬ ቆዳና ሌጦ በማጓጓዣ ፈቃዱ ላይ የተገለጸው አይነትና መጠን መሆኑን፣ በወቅቱና በአግባቡ ወደ ፋብሪካው መድረሱን የሚገልጽ የግብረ መልስ ሪፖርት ለአቅራቢው፣ ለከፍተኛ ቄራ ወይም ለኤክስፖርት መጠን ቄራ በወቅቱ አዘጋጅቶ የመስጠት፤

ግዴታዎች አሉበት።

11.**<u>የአጓጓዥ ግዴታዎች</u>**

የአዋጁ አንቀጽ 10 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ጥሬ ቆዳና ሌጦ አጓጓዥ፡-

1. ጥሬ ቆዳና ሌጦን ከማጓጓዙ በፊት በግብይትና ጥራት ተቆጣጣሪ በፐሎምፕ የማሳሸግ፣
2. ጥሬ ቆዳና ሌጦው በሚያጓጉዝበት ወቅት የሚመለከተው ሴክተር መሥሪያ ቤት ያወጣውን መመሪያ ማክበርና ተግባራዊ የማድረግ፣
3. ጥሬ ቆዳንና ሌጦን ጥራት ከሚያበላሹ ባዕድ ነገሮች ጋር ቀላቅሎ ያለማጓጓዝ፤
4. ጥሬ ቆዳና ሌጦን እንዲያጓጉዝ ከተፈቀደለት መሥመር ውጭ ያለመጓጓዝ፣

ግዴታዎች አሉበት።

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ጥሬ ቆዳና ሌጦ ጥራትና ግብይት ቁጥጥር</u>

12.**<u>ጥራት ቁጥጥር</u>**

1. በአዋጁ አንቀጽ 7(2) መሠረት የጥሬ ቆዳና ሌጦ የጥራት ደረጃ የማረጋገጥና የቁጥጥር ሥራ የሚያካሂደው በግብርና ሚኒስቴር እና በክልል ግብርና ቢሮዎች አማካኝነት ሰልጥነው በሚሰማሩ ባለሙያዎች ይሆናል፡፡
2. በአዋጁ አንቀጽ 7 (1) መሠረት በኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ የተዘጋጀውን ደረጃ ለማስፈጸም እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለሚካሄድ የጥሬ ቆዳና ሌጦ የጥራት ደረጃ ቁጥጥር የሚያገለግል መመሪያ ሚኒስቴሩ ያወጣል።
3. ጥሬ ቆዳና ሌጦው ቆዳ ፋብሪካዎች ሲደርስ በወካይ ናሙና መሠረት ምርመራ ተደርጎለት በደረጃ ይመደባል፤ ሆኖም በአቅራቢውና በቆዳ ፋብሪካው መካከል ለሽያጭ በቀረበው ጥሬ ቆዳና ሌጦ ደረጃ አመዳደብ ላይ አለመግባባት ቢፈጠር በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በሚመደብ ሶስተኛ ወገን ባለሙያ አማካኝነት ውሳኔ እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡

13.**<u>የግብይትና የጥራት ተቆጣጣሪዎችን ስለመመደብ</u>**

1. አግባብ ያለው አካል የጥሬ ቆዳና ሌጦ የግብይት ተቆጣጣሪዎችን የሚመድብ ሲሆን የግብርና ሚኒስቴርና በየደረጃው የሚገኙ የክልል ግብርና ቢሮዎች የጥሬ ቆዳና ሌጦ ጥራት ተቆጣጣሪዎችን ይመድባሉ፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1 መሠረት የሚመደቡ የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት እና ጥራት ተቆጣጣሪዎች በመስኩ እውቀት እና መልካም ሥነ ምግባር ያላቸው መሆን ይኖርባቸዋል።

14.የግብይትና የጥራት ተቆጣጣሪ ኃላፊነት

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 13 መሠረት የተመደበ የጥሬ ቆዳና ሌጦ የግብይትና ጥራት ተቆጣጣሪ አዋጁን፣ የዚህን ደንብ ድንጋጌዎችንና ደንቡን ተከትሎ በወጡ መመሪያዎች መሠረት የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት መፈጸሙን ለማረጋገጥ፦

ሀ) በመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከላት እና በሁለተኛ ደረጃ ግብይት የሚካሄደውን የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት፤

ለ) በአቅራቢዎች መጋዘን፣ በከፍተኛ ቄራዎች ወይም በኤክስፖርት ቄራዎች የሚካሄደውን የጥሬ ቆዳና ሌጦ አዘገጃጀትና አከመቻቸት፤

ሐ) በአቅራቢዎች ወይም በአነስተኛ ቄራዎች ወይም በከፍተኛ ቄራዎች ወይም በኤክስፖርት ቄራዎች የሚካሄደውን የጥሬ ቆዳና ሌጦ አጓጓዝ፤

የመቆጣጠር ሀላፊነት ይኖረዋል፡፡

2. የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይትና ጥራት ተቆጣጣሪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1 የተመለከቱትን ኃላፊነቶች ለመወጣት፡-

ሀ) ወደ ማንኛውም የጥሬ ቆዳና ሌጦ ማዘጋጃና ማከማቻ መጋዘን ወይም አገልግሎት መስጫ ግቢ በሥራ ሰዓት መግባትና አግባብነት ያላቸውን ሠነዶች መመልከትና ፎቶ ኮፒ፣ የፎቶግራፍ ወይም ኤሌክትሮኒክስ መረጃዎችን የመውሰድ፤

ለ) የጥሬ ቆዳና ሌጦ የሚያጓጉዝ ተሽከርካሪን በማስቆም መፈተሽና አግባብ ያላቸው ሠነዶች እንዲቀርቡለት የማድረግ፤ እና

ሐ) ከአቅራቢው መጋዘን፣ ከከፍተኛ ቄራዎች ወይም ከኤክስፖርት ቄራዎች ወደ ቆዳ ፋብሪካዎች የሚጓጓዝ ጥሬ ቆዳና ሌጦ ሲጫን በጥራትን በዓይነቱ ላይ የመጀመሪያ ደረጃ ማጣራት ማድረግ፤

ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

3. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይትን ጥራት ተቆጣጣሪ የአዋጁን፣ የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ወይም ይህን ደንብ ለማስፈፀም የሚወጡ መመሪያዎች መጣሳቸውን ሲያረጋግጥ ሕገወጥ ድርጊት የተፈፀመበትን ጥሬ ቆዳና ሌጦ ደረሰኝ ሰጥቶ እንዲያዝ የማድረግ ወይም ጥሬ ቆዳና ሌጦ የተከማቸበትን መጋዘን የማሸግ ሥልጣን ይኖረዋል፡፡
4. የጥሬ ቆዳና ሌጦ የግብይትን ጥራት ተቆጣጣሪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (3) መሠረት ስለተወሰደው እርምጃ ወዲያውኑ በየደረጃው ለሚገኝ አግባብ ላለው አካል ሪፖርት ማድረግና በአዋጁ ወይም በዚህ ደንብ መሠረት መወሰድ ስለአለባቸው ተከታታይ እርምጃዎች አግባብ ካለው አካል የሚሰጠውን መመሪያ የመፈፀም ኃላፊነት አለበት፡፡

15. <u>ሕገወጥ ድርጊቶችን ስለመጠቆም</u>

1. ማንኛውም ሰው የጥሬ ቆዳና ሌጦ አዘገጃጀት፣ አከመቻቸት፣ አጓጓዝ ወይም ግብይት ሂደት ላይ አዋጁን፣ የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ወይም ደንቡን ተከትለው የሚወጡ መመሪያዎችን በመተላለፍ ሕገወጥ ድርጊት መፈፀሙን ሲያውቅ በአካባቢው ለሚገኝ የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት ተቆጣጣሪ ወይም በየደረጃው ለሚገኝ አግባብ ላለው አካል መጠቆም ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ጥቆማ አቅርቦ ሕገወጥ ድርጊት የተፈፀመበትን ጥሬ ቆዳና ሌጦ ያስያዘ ማንኛውም ሰው ከተያዘው ሕገወጥ ጥሬ ቆዳና ሌጦ ሽያጭ ገንዘብ ውስጥ 40% የጠቋሚ አበል ይከፈለዋል፡፡
3. ጠቋሚው በመጠቆሙ ምክንያት ማንኛውንም አይነት ጉዳት እንዳይደርስበት ማንነቱ እንዳይገለጽ ይደረጋል፡፡

16. <u>ስለተያዘ ሕገወጥ ጥሬ ቆዳና ሌጦ</u>

1. በዚህ ደንብ አንቀፅ 14(3) መሠረት የተያዘው ጥሬ ቆዳና ሌጦ ምርት መጠን የያዘ ወይም የአቅራቢ፣ የከፍተኛ ቄራ፣ የኤክስፖርት ቄራ ወይም የቆዳ ፋብሪካ ከሆነ በሁለተኛ ደረጃ የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት ብቻ ቀርቦ በጨረታ እንዲሸጥ ከተደረገ በኋላ ገንዘቡ አግባብ ባለው አካል በተከፈተ ዝግ የባንክ ሂሳብ ገቢ ይደረጋል፡፡
2. ሕገወጥ ድርጊት የተፈጸመበት ጥሬ ቆዳና ሌጦ ለጨረታ ቀርቦ ካልተሸጠ ምርቱን ለሚፈልግ የግብይት ተሳታፊ በድርድር እንዲሸጥ ይደረጋል፡፡

3. በዚህ ደንብ በአንቀጽ 14(3) መሠረት ጥሬ ቆዳና ሌጦ የተያዘበት ወይም መጋዘኑ የታሸገበት ማንኛውም ሰው ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሠረት የጥሬ ቆዳና ሌጦ የተሸጠበት ማንኛውም ሰው በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን አግባብነት ላለው አካል ሊያቀርብ ይችላል፡፡
4. አግባብ ያለው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (3) መሠረት የቀረበለትን ቅሬታ በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፡፡ አግባብ ያለው አካል የሰጠው ውሳኔ፡-

    ሀ) የተቆጣጣሪውን እርምጃ የሚሽር ከሆነ የተያዘው ጥሬ ቆዳና ሌጦ ለመሸጥ የወጣ ወጭ ተቀንሶ ቀሪው የሽያጭ ገንዘብ ወዲያውኑ ለአመልካቹ እንዲመለስ ወይም የጥሬ ቆዳና ሌጦው የተከማቸበት መጋዘን እሽግ ወዲያውኑ እንዲከፈት ይደረጋል፤ ወይም

    ለ) የተቆጣጣሪውን እርምጃ የሚያጸና ከሆነ ሕገወጥ ድርጊት የተፈጸመበት ጥሬ ቆዳና ሌጦ ወይም የመጋዘን ባለቤት ውሳኔውን በጽሁፍ እንዲያውቅ ይደረጋል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) ፊደል ተራ (ለ) የተመለከተውን ውሳኔ የሚቃወም የጥሬ ቆዳና ሌጦ ወይም መጋዘን ባለቤት ውሳኔ በተወሰነ በ15 ቀናት ውስጥ ጉዳዩን የማየት ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ክስ ሊያቀርብ ይችላል፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) መሠረት ጉዳዩን ያየው ፍርድ ቤት አግባብ ያለው አካል የሰጠውን ውሳኔ፡-

    ሀ) ከሻረው ጥሬ ቆዳና ሌጦውን ለመሸጥ የወጣው ወጪ ተቀናሽ ተደርጎ የሽያጩ ገንዘብ ለባለቤቱ ተመላሽ ይደረጋል፤ ወይም

    ለ) ካጸናው ወይም የጥሬ ቆዳና ሌጦው ባለቤት በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ይግባኝ ካላቀረበ ከጥሬ ቆዳና ሌጦው ሽያጭ ገንዘብ ውስጥ አስተዳደራዊ ወጪዎች ተቀንሰው 40 % ለጠቋሚው ወይም ያለጥቆማ የተያዘ ከሆነ ለያዘው የመንግስት ፀጥታ ተቋም ይከፈላል፣ ቀሪው 60% ለመንግስት ገቢ ይደረጋል፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

17. **የመተባበር ግዴታ**

የጥሬ ቆዳና ሌጦ የግብይትና ጥራት ተቆጣጣሪዎች በዚህ ደንብ አንቀጽ 15 መሠረት ሕገወጥ ድርጊትን ለመቆጣጠር ለሚያደርጉት እንቅስቃሴ ማንኛውም ሰው የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

18. **ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ደንቦችና መመሪያዎች**

ይህንን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልምድ በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

19. **ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ የካቲት 6 ቀን 2007 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስትር**

## አዋጅ ቁጥር 819/2006

## የቁም እንስሳት ግብይት አዋጅ

በጥራትና በዋጋ ተወዳዳሪ የሆነ የቁም እንስሳት ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያ በተቀላጠፈ ሁኔታ ለማቅረብ የሚያስችል ዘመናዊ የቁም እንስሳት ግብይት ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የቁም እንስሳት ግብይት በወቅታዊ መረጃ የተደገፈ፣ ቀልጣፋ እና ወጪ ቆጣቢ በማድረግ አርቢው፣ ነጋዴው፣ ሸማቹ እና አገሪቱ ከግብይቱ ተገቢውን ጥቅም የሚያገኙበትን ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 55(1 መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የቁም እንስሳት ግብይት አዋጅ ቁጥር 819/2006" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ አዋጅ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

   1. "የቁም እንስሳ" ማለት የዳልጋ ከብትን፣ በግን፣ ፍየልን፣ ግመልን እና ሚኒስቴሩ የቁም እንስሳ ብሎ የሚሰይማቸውን ሌሎች እንስሳት ይጨምራል፣
   2. "የቁም እንስሳት ግብይት" ማለት የቁም እንስሳት ሽያጭን፣ ግዢን፣ ማጓጓዝን የእንስሳት ማድለቢያ ማከራየትን እና ሌሎች ተመሳሳይ የግብይት ተግባራትን የሚያካትት ሂደት ነው፤
   3. "የመጀመሪያ ደረጃ ወይም ሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከል" ማለት አግባብ ባለው አካል የተሰየመና በዚህ አዋጅ መሠረት የቁም እንስሳት ግብይት የሚከናወንበት ቦታ ነው፡፡
   4. "የግብይት ተሳታፊዎች" ማለት በቁም እንስሳት ግብይትየሚሳተፉ አርቢዎችን፣ አድላቢዎችን፣ ላኪዎችን፣ ቄራዎችን፣ ሉኳንዳ ቤቶችን፣ የሕብረት ሥራ ማህበራትን እና ሸማቾችን ያካትታል፤
   5. "አርቢ" ማለት እንስሳትን የሚያረባ ማንኛውም ሰው ነው፤

6. “አድላቢ” ማለት የቁም እንስሳትን ከመጀመሪያ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት በመግዛት በማድለቢያ ጣቢያ እስከ 4 ወራት በማቆየት አደልቦ ለሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት የሚያቀርብ ሰው ነው፤
7. “ላኪ” ማለት የቁም እንስሳትን ወይም ሥጋንና የሥጋ ውጤቶችን ለውጭ ገበያ የሚያቀርብ ሰው ነው፤
8. “ቄራ” ማለት የቁም እንስሳትን በማረድ ለገበያ የሚቀርብ ሥጋና የሥጋ ውጤቶችን የሚያዘጋጅና የሚያቀነባብር ወይም ለሉካንዳ ቤቶችና ለሸማቾች የእርድ አገልግሎት የሚሰጥ ሰው ነው፤
9. “ሉኳንዳ ቤት” ማለት ሥጋን ለሸማቾች የሚያቀርብ ሰው ነው፤
10. “የህብረት ሥራ ማህበር” ማለት አግባብ ባለው በህብረት ሥራ ማህበራት ሕግ የተሰጠው ትርጓሜ ይኖረዋል፣
11. “ሸማች” ማለት የቁም እንስሳትን ወይም ሥጋን ለግል ፍጆታ የሚገዛ ግለሰብ ሲሆን ምግብ አዘጋጅቶ ለተመጋቢዎች በሽያጭ ወይም በሌላ ሁኔታ የሚያቀርብ ማንኛውንም ሰው ይጨምራል፡፡
12. “ጨረታ” ማለት ሻጮችና ገዢዎች ባሉበት እና በአጫራች አማካኝነት በሚካሄድ ግልፅ ውድድር የቁም እንስሳት ዋጋ የሚወሰንበትና የባለቤትነት ዝውውር የሚፈፀምበት የግብይት ስርዓት ነው፡፡
13. “አጫራች” ማለት ጨረታን እንዲመራ አግባብ ባለው አካል የተሰየመ ገለልተኛ ሰው ነው፡፡
14. “ድርድር” ማለት በሻጭና በገዢ መካከል በቀጥታ በሚካሄድ ክርክር አማካይነት የቁም እንስሳት ዋጋ የሚወሰንበትና የባለቤትነት ዝውውር የሚፈጸምበት የግብይት ሥርዓት ነው፤
15. “ማጓጓዝ” ማለት የቁም እንስሳትን በእግር በመንዳት ወይም ትራንስፖርት በመጠቀም ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ማዘዋወር ነው፤
16. “የማጓጓዝ ፈቃድ” ማለት የቁም እንስሳትን ከእርባታ ወይም ማድለቢያ ጣቢያ ወይም ከቁም እንስሳት ግብይት ማዕከል ወደ ቀጣይ መዳረሻ ለማጓጓዝ አግባብ ባለው አካል የሚሰጥ ፈቃድ ነው፤

17. “የእንስሳት መለያ” ማለት የቁም እንስሳት በሚጓጓዙበት ወቅት በጆሮ መለያ ምልክት ወይም በሌላ መንገድ ለመለየት እንዲያስችል የሚዘረጋ ሥርዓት ነው፤
18. “የኳራንቲን ጣቢያ” ማለት የቁም እንስሳትን በተከለለ ስፍራ ለተወሰነ ጊዜ ከሌሎች እንስሳት ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ እንዳይገናኙ በማድረግ ጤንነታቸውን ለመከታተል እንዲሁም እንደአስፈላጊነቱ የክትባት ወይም የህክምና አገልግሎት ለመስጠት እንዲያስችል ሆኖ የተዘጋጀ የተለየ ሥፍራ ነው፤
19. “ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት” ማለት በፍትሐብሔር ሕጉ ከአቅም በላይ ለሆነ ምክንያት የተሰጠው ትርጓሜ እንደተጠበቀ ሆኖ አገር ውስጥ የእንስሳት በሽታ ወረርሽኝ መከሰትን፣ በገዢ አገራት ማዕቀብ መጣልን እና ሌሎች ተመሳሳይ የሆኑ ምክንያቶችን ያካትታል
20. “አሳሳች ድርጊት” ማለት በቁም እንስሳት ግብይት ሂደት ውስጥ የግብይት ተሳታፊዎችን ወይም የመንግሥት አካልን ሊያሳስት ወይም ሊያታልል የሚችል ማንኛውም ድርጊት ነው፤
21. “የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት” ማለት በቁም እንስሳት ግብይት ተሳታፊነት ንግድ ለመሰማራት የሚያስችሉ በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 686/2002[23] አግባብ ያላቸው ድንጋጌዎች መሠረት የተወሰኑ መስፈርቶችን አሟልቶ ለተገኘ ሰው በሚመለከተው የሴክተር መሥሪያ ቤት የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው፤
22. “ሴክተር መስሪያ ቤት” ማለት የእንስሳት ግብይት ስርዓቱን በማስፈፀምና በመደገፍ ሂደት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ትስስር ያላቸውን የፌዴራልና የክልል አስፈፃሚ አካላትን ያጠቃልላል፤
23. “ሚኒስቴር” ማለት የንግድ ሚኒስቴር[24] ነው፤
24. “አግባብ ያለው” ማለት እንደአግባቡ ሚኒስቴሩ ወይም የንግድ ፈቃድ ለመስጠት ሥልጣን የተሰጠው የክልል አካል ነው፤
25. “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 47(1 የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

[23] በ22)101 (2008 አ. 980 አንቀጽ 51 (1 ተሽሯል፡፡
[24] በ25)08 (2011 አ. 1097 አንቀጽ 9(7 የንግድና ኢንደስትሪ ሚንስቴር ሆኗል፡፡

26.“ሰው” ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

27.ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል።

3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅ በአገሪቱ ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በቁም እንስሳት ግብይት ላይ በሚሳተፍ ማንኛውም ሰው ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የቁም እንስሳት ግብይት ሥርዓት</u>

4. <u>የቁም እንስሳት ግብይት</u>

የቁም እንስሳት ግብይት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 እና አንቀጽ 6 መሠረት በመጀመሪያ ደረጃ እና በሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት ውስጥ የሚከናወን ይሆናል፡፡

5. <u>የመጀመሪያ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት</u>

1. የመጀመሪያ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት አደረጃጀት እና አስተዳደር አግባብ በሚኒስቴሩ በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡
2. በመጀመሪያ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት ግብይት የሚካሄደው፡
   ሀ) በአርቢዎች መካከል፤ ወይም
   ለ) ሻጭ በሆኑ አርቢዎች እና ገዢዎች በሆኑ የህብረት ሥራ ማህበራት፣ አድላቢዎች፣ ላኪዎች፣ ቄራዎች፣ ሉኳንዳ ቤቶችና ሸማቾች መካከል፤ ይሆናል፡፡
3. በመጀመሪያ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት ግብይት የሚካሄደው በድርድር ወይም በጨረታ ይሆናል፡፡
4. በመጀመሪያ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከል ላይ የእንስሳት ዋጋ የሚወስነው እንደ እንስሳቱ ዝርያ፣ ዕድሜ እና አቋም በክብደት ላይ ተመስርቶ ይሆናል፡፡
5. ከሸማች፣ ከአርቢ እና ከህብረት ሥራ ማህበራት በስተቀር በመጀመሪያ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከል ተሳታፊ የሆነ ማንኛውም ሰው በእንስሳት ንግድ ላይ ለመሰማራት የሚያስችል የጸና የንግድ ፈቃድ ያለው መሆን አለበት፡
6. በመጀመሪያ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከል ቀርበው ያልተሸጡ እንስሳት ወደ መጡበት መመለስ አለባቸው።

6. <u>**ሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት**</u>

1. የሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት አደረጃጀት እና አስተዳደር በሚኒስቴሩ በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡
2. በሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት የቁም እንስሳት የሚካሄደው፡-

   ሀ) ሻጭ በሆኑ አርቢዎች እና ገዢዎች በሆኑ ላኪዎች፣ ቄራዎች፣ ሉኳንዳ ቤቶችና ሸማቾች፤

   ለ) ሻጭ በሆኑ አድላቢዎች እና ገዢዎች በሆኑ ላኪዎች፣ ቄራዎች፣ ሉኳንዳ ቤቶችና ሸማቾች፣ ወይም

   ሐ) ሻጭ በሆኑ የህብረት ሥራ ማህበራት እና ገዢዎች በሆኑ ላኪዎች፣ ቄራዎች፣ ሉኳንዳ ቤቶችና ሸማቾች፤

   መካከል ይሆናል፡፡
3. ወደ ሁለተኛ ደረጃ የግብይት ማዕከላት የሚቀርቡ የቁም እንስሳት የደለቡ መሆን አለባቸው።
4. በሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት ግብይት የሚካሄደው በድርድር ወይም በጨረታ ይሆናል፡፡
5. በሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከል የቁም እንስሳት ዋጋ የሚወሰነው እንደቁም እንስሳቱ ዝርያ፣ ዕድሜ እና አቋም በክብደት ላይ ተመስርቶ ይሆናል፡፡
6. በሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከል እንስሳትን ለሽያጭ የሚያቀርብ ማንኛውም የግብይት ተሳታፊ እንስሳቱን፡-

   ሀ) ከተሰጠው የቁም እንስሳት መለያ፣

   ለ) ከእንስሳቱ የጤና ምስክር ወረቀት፤ እና

   ሐ) ከባለቤትነት ማረጋገጫ ስነድ፣

   ጋር ማቅረብ እና ሽያጭ ከተፈጸመ በኃላም እንስሳቱን ከእነዚሁ ሰነዶች ጋር ለገዥው ማስረከብ አለበት፡፡

7. <u>**የቁም እንስሳት ጤና ቁጥጥር**</u>

1. በመጀመሪያ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከል ግብይት የተፈፀመባቸው እንስሳት ጤንነታቸው በገበያ ማዕከሉ በሚገኙ የእንስሳት ጤና ባለሙያዎች ተረጋግጦ መለያ እንዲሰጣቸው ይደረጋል፡፡

2. ከቁም እንስሳት ግብይት ማዕከል እንስሳት ተገዝተው ወደ ቀጣዩ መዳረሻ ከመጓጓዛቸው በፊት የግብርና ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ቅድመ ግዢ የጤና ምርመራ ይደረጋል፡፡
3. አግባብ ያለው አካል ለቁም እንስሳት የግብይት ማዕከል ቀርበው በጤና ምርመራ ወቅት የበሽታ ምልክት በታየባቸው እንስሳት ላይ ቀጣይ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡
4. ወደ ውጭ አገር የሚላክ እንስሳት ደረጃውን በጠበቀ የኳራንታይን ጣቢያ የጤና ክትትል ተደርጎላቸው የእንስሳት ጤና የምስክር ወረቀት እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡

8. <u>የቁም እንስሳትን ስለማጓጓዝ</u>

1. በዝርያ፣ በፆታ ወይም በእድሜ የሚለያዩ የቁም እንስሳት በአንድ ላይ በማይቀላቀሉበት ሁኔታ መጓጓዝ አለባቸው።
2. የቁም እንስሳት የሚጓጓዙበት ሁኔታ፣ በእግር ከተወሰነ ርቀት በላይ እንዳይነዱ የሚደረግበት እና በዋና ዋና ከተሞች በእግር መንዳት የሚከለከልበት ሁኔታ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>የግብይት ተሳታፊዎች መብቶችና ግዴታዎች</u>

9. <u>የአርቢዎች መብቶችና ግዴታዎች</u>

1. ማንኛውም አርቢ ያረባቸውን የቁም እንስሳት ወደ መጀመሪያ ወይም ሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከል አቅርቦ የመሸጥ ወይም በቀጥታ ወደ ውጭ የመላክ መብት ይኖረዋል።
2. ማንኛውም አርቢ፡-
   ሀ) ያረባቸውን የቁም እንስሳት በአገር ውስጥ ለመሸጥ ከወሰነ በቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት ውስጥ ብቻ የመሸጥ እና አግባብ ባለው አካል በተወሰኑት ቦታዎች ርክብክብ የመፈጸም፣
   ለ) የደለቡ የቁም እንስሳትን ወደ ሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት ለማቅረብ የእንስሳት ጤና የምስክር ወረቀት፣ የማጓጓዝ ፈቃድና የእንስሳት መለያ የመያዝና በባለቤትነት ማስተላለፍ ወቅትም እነዚህንሰነዶች ለገዥው የማስረከብ፣

ሐ) ለገበያ ቀርበው የበሽታ ምልክት የታየባቸውን እንስሳት አስመልክቶ አግባብነት ያለው አካል የሚሰጠውን ውሳኔ የማክበርና የመፈጸም፣ እና

መ) ለውጭ ገበያ የሚያዘጋጇቸውን የቁም እንስሳት ወደ ኳራንታይን ጣቢያ የማስገባትና የእንስሳት ጤና የምስክር ወረቀት እንዲያገኙ የማድረግ፣

ግዴታዎች አሉበት።

10.<u>የአድላቢ መብቶችና ግዴታዎች</u>

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2(ለ) ድንጋጌ ቢኖርም የራሱ ሉኳንዳ ቤት ያለው አድላቢ የቁም እንስሳትን ወደ ሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማቅረብ ሳያስፈልገው ለእርድ አገልግሎት የማዋል መብት ይኖረዋል።
2. ማንኛውም የቁም እንስሳት አድላቢ፡-

ሀ) መስፈርቱን የሚያሟላ የራሱ ወይም የተከራየው የቁም እንስሳት ማድለቢያጣቢያ ኖሮት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትና የንግድፈቃድ የማውጣት፣

ለ) ያደለባቸውን የቁም እንስሳት ለሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከል ብቻ የማቅረብ እና አግባብ ባለው አካል በተወሰነው የርክክብ ቦታ የእንስሳቱን ርክክብ የመፈጸም፣

ሐ) የቁም እንስሳቱን ወደ ቁም እንስሳት ግብይት ማዕከል ለማቅረብ የእንስሳት ጤና የምስክር ወረቀት፣ የማጓጓዝ ፈቃድና የእንስሳት መለያ መያዝ እና በባለቤትነት ማስተላለፍ ወቅትም እነዚህን ሰነዶች ለገዥውየማስረከብ፣

መ) ለገበያ ቀርበው የበሽታ ምልክት የታየባቸውን እንስሳት አስመልክቶ አግባብ ያለው አካል የሚሰጠውን ውሳኔ የማክበርና የመፈጸም፣

ሠ) የየእለቱን የቁም እንስሳት ግዢና ሽያጭ ብዛት እና ዋጋ መዝግቦ የመያዝና አግባብ ባለው አካል ሲጠየቅ ይህንኑ መረጃ የመስጠት፤

ረ) የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች እና አዋጁን ለማስፈጸም የወጡደንቦችንና መመሪያዎችን ማክበር፣

ግዴታዎች አሉበት።

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) (ሀ)ድንጋጌ የቁም እንስሳት ማድለቢያ ጣቢያ ኪራይ አገልግሎት ለመስጠትም ተፈጻሚ ይሆናል፡

## 11.የላኪ ግዴታዎች

ማንኛውም ላኪ፡

1. የቁም እንስሳትን የሚልክ ሲሆን መስፈርቱን የሚያሟላ የራሱ ወይም የተከራየው የቁም እንስሳት ማድለቢያ ወይም ማቆያ ጣቢያ ኖሮት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትና የላኪነት ንግድ ፈቃድ የማውጣት፤
2. ሥጋና የሥጋ ውጤት የሚልክ ሲሆን መስፈርቱን የሚያሟላ የራሱ ወይም የተከራየው የኤክስፖርት ቄራ ኖሮት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትና የላኪነት ንግድ ፈቃድ የማውጣት፣
3. የቁም እንስሳት ግዢን ከቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት ብቻ የማካሄድ እና አግባብ ባለው አካል በተወሰነው የርክክብ ቦታ እንስሳቱን የመረከብ፣
4. በግብርና ሚኒስቴር ስለቅድመ ግዢ ጤናና ጥራት ቁጥጥር የወጣውን መመሪያ አክብሮ የቁም እንስሳት ግዢን የመፈጸም፣
5. ለውጭ ገበያ የሚዘጋጁ የቁም እንስሳትን ወደ ኳራንታይን ጣቢያ የማስገባትና የእንስሳት ጤና የምስክር ወረቀት እንዲያገኙ የማድረግ፣
6. የቁም እንስሳትን ከማድለቢያና ከኳራንታይን ጣቢያ ወደ ወደብ በማጓጓዝ ሂደት የእንስሳት ጤና ምስክር ወረቀት እና የማጓጓዝ ፈቃድ የመያዝና አግባብ ባለው አካል ሲጠየቅ የመስጠት፣
7. አግባብ ባለው አካል በልዩ ሁኔታ ካልተፈቀደ በስተቀር በዚህ አዋጅ እና አዋጁን ለማስፈፀም በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት ለውጭ ገበያ የተዘጋጁትን የቁም እንስሳት ለውጭ ገበያ ብቻ የመላክ፣
8. ለውጭ ገበያ የተዘጋጁ የቁም እንስሳትን ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ካላጋጠመ በስተቀር ለአገር ውስጥ ገበያ ያለመሸጥ፣
9. የየእለቱን የቁም እንስሳት ግዢና የውጭ ገበያ ሽያጭ ብዛት እና ዋጋ መዝግቦ የመያዝና አግባብ ባለው አካል ሲጠየቅ ይህንኑ መረጃ የመስጠት፣
10. ትክክለኛ የመሸጫ ዋጋውን የሚገልፅ የውጪ ገበያ ሽያጭ ውል የመፈጸምና ከ72 ሰዓታት ባልበለጠ ጊዜ ወስጥ ውሉን በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የማስመዝገብ እንዲሁም ለሚኒስቴሩና ለሌሎች ለሚመለከታቸው አካላት ከ5 የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የማሳወቅ፣

11. አሳማኝ ምክንያት ኖሮ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እንዲራዘም ካልተፈቀደ በስተቀር ከገዢ ጋር የገባውን የውጭ ገበያ ሽያጭ ውል በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ የመፈጸም፣
12. የአገሪቱን የቁም እንስሳትና የሥጋና የሥጋ ውጤቶች የውጭ ገበያ መልካም ስም ሊያጎድፍ ከሚችል ከማንኛውም ድርጊት የመቆጠብ እና
13. የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች እና አዋጁን ለማስፈጸም የወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን የማክበር ግዴታዎች አለበት።

12. <u>የቁም እንስሳት አጓጓዥ ግዴታዎች</u>

ማንኛውም የቁም እንስሳት አጓጓዥ፡-

1. መስፈርቱን የሚያሟላ የቁም እንስሳት ማጓጓዣ ተሽከርካሪ ኖሮት የብቃት ማረጋገረጫ የምስክር ወረቀትና የንግድ ፈቃድ የማውጣት፤
2. በዚህ አዋጅ መሠረት ለግብይት የሚቀርቡ ወይም ተገዝተው ወደ ቀጣዩ መዳረሻ የቁም እንስሳትን ብቻ የማጓጓዝ፣
3. በዝርያ፣ በፆታና በእድሜ የተለያዩ የቁም እንስሳትን በጉዞ ወቅት በአንድ ላይ ያለመቀላቀል፣
4. የቁም እንስሳትን በሚያጓጉዝበት ወቅት የማጓጓዝ ፈቃድ የመያዝና አግባብ ባለው አካል ሲጠየቅ የማሳየት እና የቁም እንስሳትን የአጫጫን ሁኔታ የማስፈተሽ፣
5. የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች እና አዋጁን ለማስፈጸም የወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን የማክበር፣

ግዴታዎች አለበት።

13. <u>የባለቁራዎች ግዴታዎች</u>

ማንኛውም ባለቁራ፡-

1. መስፈርቱን የሚያሟላ የራሱ ወይም የተከራየው ቁራ ኖሮት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትና የንግድ ፈቃድ የማውጣት፤
2. የቁም እንስሳትን ከራሱ ማድለቢያ ጣቢያ ለእርድ አገልግሎት የማዋል መብቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ከቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት ብቻ የእንስሳት ግዢ የመፈጸም፣

3. የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች እና አዋጁን ለማስፈጸም የወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን የማክበር፤

ግዴታዎች አሉበት።

14. <u>የባለሉኳንዳ ቤቶች ግዴታዎች</u>

ማንኛውም ባለሉኳንዳ ቤት:-

1. መስፈርቱን የሚያሟላ ሉኳንዳ ቤት የማዘጋጀትና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትና የንግድ ፈቃድ የማውጣት፤
2. በቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት ውስጥ ብቻ የቁም እንስሳት ግዢ የመፈጸም፣
3. የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች እና አዋጁን ለማስፈጸም የወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን የማክበር፣

ግዴታዎች አሉበት።

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

15.<u>አግባብ ያለው አካል ሥልጣንና ተግባር</u>

በሌሎች ሕጎችና በዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች የተመለከቱት ሥልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆኖ አግባብ ያለው አካል የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1. የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላትን የመሰየም እና ተፈላጊ መስፈርቶችን ማሟላታቸውን የማረጋገጥ፣
2. የቁም እንስሳት ሽያጭና ግዢ በድርድር ወይም በጨረታ ላይ ተመስርቶ እንዲካሄድ የመፍቀድ እና አጫራች የመሰየም፣
3. ለአገር ውስጥ ወይም ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የቁም እንስሳት የጤና ምርመራ የተደረገላቸውና የምስክር ወረቀት እና የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ የተሰጣቸው መሆኑን የማረጋገጥ፣
4. ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የቁም እንስሳት የጥራት ደረጃቸውን ጠብቀው እንዲዘጋጁ ክትትል የማድረግ፣
5. ማንኛውም የቁም እንስሳት ግብይት ተሳታፊ የግብይት ሂደቱን የሚያዛባ አሳሳች ድርጊት ፈጽሞ ሲገኝ ተገቢውን አስተዳደራዊ እርምጃ የመውሰድ፣

6. በቁም እንስሳት ንግድ ለመሳተፍ የሚያስችል የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለያዙ ሰዎች የንግድ ፈቃድ የመስጠት፣
7. ለቁም እንስሳት መለያ የሚውሉ የአሠራር ሥርዓቶችን የመዘርጋትና ተግባራዊ የማድረግ ፤
8. በሕገ ወጥ መንገድ ሲጓጓዙ ወይም ግብይት ሲፈጸምባቸው የተገኙ የቁም እንስሳትን የመያዝ፤ የቁም እንስሳቱን እንደአግባቡ በመጀመሪያ ወይም በሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከል አቅርቦ በጨረታ በመሸጥ ገንዘቡን በዝግ የባንክ ሂሳብ እንዲቀመጥ የማድረግ፤ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 17 መሠረት እንዲወረስ ሲወሰንም ለመንግሥት ገቢ እንዲሆን የማድረግ፣
9. ሕገወጥ የቁም እንስሳት ንግድ እንቅስቃሴን ለሚጠቁሙ ሰዎች የሚከፈል የኮሚሽን አበል መጠን ለመንግሥት ማቅረብ፣ ሲፀድቅም በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ፣
10. ለሚሰጠው አገልግሎት በመንግሥት በሚወሰነው ተመን መሠረት የአገልግሎት ክፍያ የማስከፈል፡፡

16. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማንኛውም ሰው ይህን አዋጅና አዋጁን ለማስፈፀም የወጡ ደንብና መመሪያ በማስፈፀም ረገድ ከሚኒስቴሩ እና አግባብ ያለው አካል ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

17. <u>ቅጣት</u>

1. ከቁም እንስሳት የግብይት ማዕከላት ውጪ የቁም እንስሳትን የሸጠ ወይም ለሽያጭ ያቀረበ ወይም የገዛ ማንኛውም ሰው የቁም እንስሳቱ እንዲወረስ ይደረጋል፡፡ ሆኖም ለግል ፍጆታው ከሚገዛውና ያረባውን ከሚሸጠው ሰው ውጪ ሆኖ በተገኘ ጊዜ በተጨማሪ ከሁለት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት እና ከብር 30,000.00 በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡
2. የቁም እንስሳት ንግድ ፈቃዱን ለሶስተኛ ወገን አሳልፎ የሰጠ ወይም ለውጭ ዜጎች በቁም እንስሳት ግብይት ከለላ የሰጠና አመቺ ሁኔታ የፈጠረ ማንኛውም ሰው ከቁም እንስሳቱ መወረስ በተጨማሪ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት እና ከብር 150,000.00 በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

3. በእንስሳት አርቢዎች መካከል ከሚፈፀም የእርስ በእርስ ግብይት በስተቀር በማናቸውም የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከል በተመሳሳይ ደረጃ ላይ ከሚገኝ የግብይት ተሳታፊ ጋር ግብይት የፈፀመ ማንኛውም ሰው ከቁም እንስሳቱ መወረስ በተጨማሪ ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት እና ከብር 15,000 በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡
4. የኳራንቲን ጊዜያቸውን ያላጠናቀቁ የቁም እንስሳትን ለውጭ ገበያ ያቀረበ ማንኛውም ሰው ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት እና ከብር 150,000.00 በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡
5. በእርባታ ጣቢያቸው ያረቧቸውን የቁም እንስሳት ለቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት ከማቅረብ ወይም በቀጥታ ወደ ውጭ ከመላክ በስተቀር በቁም እንስሳት ግብይት መስክ ተሰማርቶ የተገኘ የውጭ አገር ዜጋ ከስድስት ወር በማይበልጥ ቀላል እስራት እና ከብር 50,000.00 በማይበልጥ መቀጮ ተቀጥቶ ከአገር እንዲወጣ ይደረጋል፡፡
6. በቁም እንስሳት ግብይት ሂደት አሳሳች ድርጊት የፈጸመ ማንኛውም ሰው ከአራት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት እና ከብር 60,000.00 በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡
7. ሚኒስቴሩ ባወጣው መመሪያ መሠረት በተከለከለ ከተማ የቁም እንስሳትን በእግር የነዳ ወይም እንዲነዱ ያደረገ ማንኛውም ሰው ከቁም እንስሳቱ መወረስ በተጨማሪ ከስድስት ወር በማይበልጥ ቀላል እስራትና ከብር 5,000 በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡
8. ከቁም እንስሳት የግብይት ማዕከል ወይም ከእርባታ ወይም ማድለቢያ ጣቢያ ወደ ቀጣዩ መዳረሻ የሚጓጓዙ የቁም እንስሳትን ከተፈቀደው ርቀት በላይ በእግር የነዳ ወይም እንዲነዱ ያደረገ ማንኛውም ሰው ከስድስት ወር በማይበልጥ ቀላል እስራት እና ከብር 5,000.00 በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡
9. ለግል ፍጆታው ከሚገዛው ሰው ውጪ ከቁም እንስሳት ግብይት ማዕከል ወይም ከእርባታ ወይም ማድለቢያ ጣቢያ ወደ ቀጣዩ መዳረሻ የሚጓጓዙ የቁም እንስሳትን የማጓጓዝ ፈቃድ ሳይዝ ወይም በማጓጓዝ ፈቃዱ ላይ ከተመለከተው አቅጣጫ ውጪ ያጓጓዘ ወይም እንዲጓጓዙ ያደረገ ሰው ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት እና ከብር 15,000.00 በማይበልጥ ይቀጣል፡፡

10. ህገ ወጥ ግብይት የተፈፀመባቸው የቁም እንስሳትን ያጓጓዘ ማንኛውም አጓጓዥ ከሁለት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት እና ከብር 30,000.00 በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡
11. ከቁም እንስሳት ግብይት ማዕከል ወይም ከእርባታ ወይም ማድለቢያ ጣቢያ ወደ ቀጣዩ መዳረሻ የሚጓጓዝ የቁም እንስሳትን በሚመለከት ተደራራቢ ክፍያ የጠየቀ ወይም ያጉላላ ማንኛውም ሰው ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ከብር 15,000.00 በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡
12. የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም አዋጁን ለማስፈፀም የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን በመተላለፍ ሌላ ጥፋት የፈጸመ ማንኛውም ሰው ከስድስት ወር በማይበልጥ ቀላል እስራት እና ከብር 5,000.00 በማያበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡
13. በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል በወንጀል ሕግ አንቀጽ 34 በተመለከተው መሠረት በዚህ አንቀጽ በተመለከቱ ጥፋቶች ተካፋይ በሚሆንበት ጊዜ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 90 መሠረት ይቀጣል፡፡

18. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1 መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

19. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መጋቢት 17 ቀን 2006 ዓ ም**

**ዶ)ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ**

**ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## ደንብ ቁጥር 341/2007 ዓ.ም.

## ስለቁም እንስሳት ግብይት የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በቁም እንስሳት ግብይት አዋጅ ቁጥር 819/2006 አንቀጽ 18 (1) መሰረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የቁም እንስሳት ግብይት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 341/2007" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፦

   1. "አዋጅ" ማለት የቁም እንስሳት ግብይት አዋጅ ቁጥር 819/2006 ነው፤
   2. በአዋጁ አንቀጽ 2 የተሰጠ ትርጓሜ ተፈጻሚ ይሆናል፤
   3. በአዋጁ አንቀጽ 2 (1) ለቁም እንስሳት የተሰጠው ትርጉም የጋማ ከብትንም ይጨምራል፤
   4. "ማቆያ ጣቢያ" ማለት ከዳልጋ ከብት ውጭ የሆኑ የቁም እንስሳት ከመጀመሪያ ደረጃ የቁም እንስሳት የግብይት ማዕከል ተገዝተው ወደ ሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከል ከመጓጓዛቸው በፊት የሚቆዩበት የተከለለ ቦታ ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለቁም እንስሳት የግብይት ማዕከላት

3. **የግብይት ማዕከላት ብዛትና ሥርጭት**

   አግባብ ያለው የክልል አካል በቁም እንስሳት ግብይት ሥልጣን ከተሰጣቸው ሌሎች አካላት ጋር በመመካከር የቁም እንስሳት የግብይት ማዕከላት በአርቢዎች አካባቢ እንዲደራጁ ያደርጋሉ፣ ብዛትና ስርጭታቸውንም ይወስናሉ።

4. **የመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላትን ስለመሰየም**

1. አግባብ ያለው የክልል አካል በቁም እንስሳት ግብይት ሥልጣን ከተሰጣቸው ሌሎች አካላት ጋር በመመካከር የመጀመሪያ ደረጃ የቁም እንስሳት የግብይት ማዕከላትን ሲሰይም፣ ብዛትና ስርጭት ሲወስን የሚከተሉትን መስፈርቶች ከግምት ማስገባት ይኖርበታል፡-

 ሀ) ለቁም እንስሳት አርቢዎች ያላቸውን ቀረቤታ፤

 ለ) ለተሽከርካሪዎች ተደራሽነት ያላቸው አመቺነት፤

 ሐ) ለተጠቃሚዎች ያላቸው ቀረቤታ፤

 መ) ለውሀና መኖ አቅርቦት ያለውን አመቺነት፤

 ሠ) የተለያዩ የቁም እንስሳት ዝርያዎችን፣ እድሜ እና ዓይነት በመለየት ለመገበያየት ያላቸውን አመቺነት፤

 ረ) ለቁም እንስሳት የጤና ጥበቃ ስራዎች፣ የደረጃ ምደባና የጨረታ ግብይት ለመካሄድ ያላቸው አመቺነት፤

 ሰ) ሚኒስቴሩ የሚያወጣውን መመሪያ በመከተል ከመኖሪያ አካባቢዎች፣ ከትምህርት ቤቶች፣ ከጤና ተቋማት፣ ከእምነት እና ከሌሎች ማህበራዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በበቂ ርቀት ላይ መገኘታቸውን፤

 ሸ) የገበያ ማዕከላቱን ለማስፋፋት ያላቸውን አመቺነት፤ እና

 ቀ) ለቁም እንስሳት ግብይት ተሳታፊዎች መሠረታዊ ፍላጎት ማሟያ የአገልግሎት መስጫ ተቋማት በአካባቢው መኖራቸው፡፡

2. የግብይት ማዕከል ለአጎራባች ወረዳዎች እና ቀበሌዎች የሚያገለግል ከሆነ አሰያየሙ አግባብ ያለው የክልል አካል ከአጎራባች ወረዳዎቹ እና ቀበሌዎቹ አስተዳደር አካላት ጋር በጋራ የሚወስኑት ይሆናል፡፡

3. የገበያ ማዕከላቱን እንዲያስተዳድር ሥልጣን የተሰጠው የወረዳ ወይም የቀበሌ አካል የግብይት ማዕከሉ በከተማ ክልል የሚገኝ ከሆነ ካርታና ፕላን ወይም በገጠር የሚገኝ ከሆነ ደግሞ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተር እንዲኖረው ያደርጋል፡፡

5. **የመጀመሪያ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከል ማሟላት ያለበት መስፈርት**

የመጀመሪያ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከል ቦታ ስፋት እንደ አካባቢው የቁም እንስሳት እና የመሬት አቅርቦት የሚወሰን ሆኖ፤ አደረጃጀቱ የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟላ መሆን አለበት፡-

1. ቢያንስ ከ5000 ሜትር ካሬ ስፋት ቦታ ያለው፤
2. በአካባቢው የሚገኝ ቁሳቁስን በመጠቀም የተገነባ አጥር ያለው፤
3. የገበያ መረጃ ሰሌዳን፣ መጫኛ እና ማራገፊያ መደላድል፣ የደረቅ ቆሻሻ ማቃጠያ እና የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ያለው፤
4. ለግብይት ተሳታፊዎች የሚያገለግል የጋራ መገልገያ መዣሪያዎች እና የመጸዳጃ ቤት ያለው፤
5. የተለያዩ ዓይነት የቁም እንስሳት ማስተናገድ እንዲችል የተከፋፈለ ቦታ ያለው፤
6. ለቁም እንስሳት በቂ ውሃ፣ መኖ፣ ህክምና አገልግሎት መስጫ ያለው እና በጤና ችግር ምክንያት ለሚገለሉ የቁም እንስሳት ማግለያ ቦታ ያለው፤ እና
7. ንጽሕናው የተጠበቀና ለመረጃ አገልግሎት የተመቻቸ፡፡

6. <u>የሁለተኛ ደረጃ ግብይት ማዕከላትን ስለመሰየም</u>

1. አግባብ ያለው አካል የሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት የግብይት ማዕከላትን ሲሰይምና ብዛትና ስርጭት ሲወስን የሚከተሉትን መስፈርቶች ከግምት ማስገባት ይኖርበታል፡-
   ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ 4 (1) (ለ)፣ (መ)፣ (ሠ)፣ (ረ)፣ (ሰ)፣ (ሽ)፣ እና (ቀ0 የተገለፁት መስፈርቶች መሟላታቸውን፤
   ለ) ለቁም እንስሳት አድላቢዎች ያላቸውን ቀረቤታ፤
   ሐ) ለኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መረብ አገልግሎት ያላቸውን አመቺነት፤
   መ) የኤሌትሪክ ኃይል አቅርቦት አገልግሎት ለማግኘት ያላቸውን አመቺነት፡፡
2. የግብይት ማዕከሉ ለአጎራባች ወረዳዎች ወይም ቀበሌዎች የሚያገለግል ከሆነ አደረጃጀቱ አግባብ ባለው የክልል አካልና የአጎራባች ወረዳዎቹ ወይም ቀበሌዎቹ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በጋራ ይወሰናል፡፡
3. የገበያ ማዕከላቱን የሚያስተዳድረው አግባብ ያለው አካል የግብይት ማዕከሉ በከተማ ክልል የሚገኝ ከሆነ ካርታና ፕላን ወይም በገጠር የሚገኝ ከሆነ ደግሞ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተር እንዲኖረው ያደርጋል፡፡

7. <u>የሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከል ማሟላት ያለበት መስፈርት</u>

የሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከል ቦታ ስፋት እንደ አካባቢው የእንስሳት እና የመሬት አቅርቦት የሚወሰን ሆኖ አደረጃጀቱ የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟላ መሆን አለበት፡-

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 5 (3)፣ (4)፣ (5)፣ እና (6) የተገለፁት መስፈርቶች፤
2. ቢያንስ 20ሺ ሜትር ካሬ ስፋት ቦታ ያለው፤
3. ዙሪያውን በግንብ ወይም በሽቦ በአስተማማኝ ሁኔታ የታጠረ አጥር ያለው፤
4. የተለያዩ ዓይነት የቁም እንስሳት ማስተናገድ እንዲችል የተከፋፈለ ቦታ ያለው፤
5. የግብይት ተሳታፊ ለሆኑት ኅብረት ስራ ማህበራት፣ አርቢዎች እና አድላቢዎች የቁም እንስሳት መገበያያ ተሸንሽኖ የታጠረ ቦታ ያለው፤
6. በግብይት ማዕከሉ በባለቤትነት የተያዘ በሥነ ልክ ኢንስቲትዩት የተመሰከረለት የቁም እንስሳት ሚዛን ያለው፤ እና
7. የተሟላ የውሀና የመብራት አቅርቦት የመገናኛ መሰረተ ልማት፣ የጥበቃ ማማ እና ግብይት ማካሄጃ ቢሮ ያለው።

8. **<u>የግብይት ማዕከላት አስተዳደር</u>**

1. የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት፦
   ሀ) ከከተማ ክልል ውጭ የተደራጁ ከሆነ የግብይት ማዕከሉ በሚገኝበት አካባቢ ያለው አግባብነት ያለው አካል ወይም ለዚህ ተግባር ስልጣን የተሰጠው አካልየግብይት ማዕከላቱን ያስተዳድራል፤
   ለ) በከተማ ክልል ውስጥ ከሆኑ ግን የከተማው ማዘጋጃ ቤት፣ አግባብነት ያለው አካል ወይም ለዚህ ተግባር ስልጣን የተሰጠው አካል የግብይት ማዕከላቱን ያስተዳድራል።
2. ግብይት ማዕከላትን ለማስተዳደር ስልጣን የተሰጠው አካል ፦
   ሀ) በቁም እንስሳት ግብይት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ከሚያሳድሩ የአካባቢው ሁኔታዎች ነጻ እንዲሆኑ ተገቢውን እርምጃ የመውሰድ፤
   ለ) ለግብይት ሂደት የሚጠየቀው የአገልግሎት ክፍያ ከሚሰጠው አገልግሎት ጋር ተመጣጣኝ እንዲሆን የማድረግ፤
   ሐ) ለግብይቱ መቀላጠፍና መሳለጥ የሚያገለግሉ መሰረተ ልማቶችን የማደራጀትና የማሟላት፤
   መ) የገበያውን የዕለት ተዕለት የግብይት ሂደት፣ የቁም እንስሳቱን ጤና፣ የፀጥታ ሁኔታ እንዲሁም ተያያዥ የግብይት እንቅስቃሴ የሚከታተልና የሚቆጣጠር ሠራተኛ በበቂ ሁኔታ እንዲመደብና እንዲሟላ የማድረግ፤

ሠ) አርቢዎች፣ ህብረት ስራ ማህበራት፣ አድላቢዎች እንደ ግብይት ማዕከሉ ስፋት በሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት መሸጫ ቦታ እንዲኖራቸው የማድረግ፤

ረ) አርቢዎች፣ ህብረት ስራ ማህበራት፣ አድላቢዎች በሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት ያገኙትን መሸጫ ቦታ በተገቢው ሁኔታ አደራጅተው እንዲይዙና ለአገልግሎቱ ተመጣጣኝ ክፍያ እንዲከፍሉ የማድረግ፤

ሰ) በሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት የቁም እንስሳትን በወካይ ናሙና መሰረት የሚሸጥ የግብይት ተዋናይ ለገበያ ያቀረባቸውን የቁም እንስሳት ቁጥር በማድለቢያው ወይም በማቆያ ጣቢያው ስለመኖራቸው የማረጋገጥ፤

ሸ) በሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት በወካይ ናሙና መሰረት የሚፈፀም ግብይት በጽሁፍ ውል መፈፀሙን የማረጋገጥ እና የግብይት ተቆጣጣሪው ካረጋገጠ በኋላ የማጓጓዣ የምስክር ወረቀት የመስጠት፣ ወይም የቁም እንስሳቱን ከማድለቢያ ወይም ከማቆያ ጣቢያ እንዲረከብ የማድረግ፤

ቀ) በሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት ግብይት በድርድር ወይም በጨረታ ሲካሄድ የመቆጣጠር፤

ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

3. የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት አደረጃጀት እና አሠራር እንዲሁም ግብይት ማዕከላትን በመከለል እና በመሰየም የማሳወቂያ ጊዜ ገደብ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው ዝርዝር መመሪያ ይወሰናል፡፡

9. <u>**የግብይት ቀንና ሰዓት**</u>

1. በመጀመሪያ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት ግብይት የሚካሄድበት ቀንና ስዓት የአካባቢውን ተጨባጭ ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት የግብይት ማዕከላቱን በሚያስተዳድረው አካል የሚወሰን ይሆናል፡፡
2. በሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት ግብይት የሚካሄደው ግብይት በሚኖርበት በማንኛውም ቀንና ሰዓት ይሆናል፡፡

10.<u>በመጀመሪያ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከል የሚፈጸም የግብይት ሥርዓት</u>

1. የቁም እንስሳት ግብይት ተሳታፊ በአንድ የመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከል እራሱ ወይም በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አካል የተረጋገጠና የተመዘገበ ውክልና ሥልጣን እና የጸና ንግድ ፈቃድ ባለው በአንድ ሕጋዊ ወኪል ብቻ መገበያየት ይኖርበታል፡፡
2. ወደ መጀመሪያ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከል ቀርበው ያልተሸጡ የቁም እንስሳት በግብይት ማዕከሉ ተቆጣጣሪ ከተረጋገጠ በኋላ ምንም ዓይነት የአገልግሎት ክፍያ ሳይጠየቅባቸው ወደ መጡበት ይመለሳሉ።
3. ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በመጀመሪያ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከል የተፈፀመ ግብይት ሕጋዊ ሥርዓቱን የተከተለ ስለመሆኑ በግብይት ተቆጣጣሪው ከተረጋገጠ በኋላ የቁም እንስሳት የማጓጓዝ ፈቃድ ይሰጣል፡፡

11.<u>በሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከል የሚፈጸም የግብይት ሥርዓት</u>

1. የቁም እንስሳት ግብይት ተሳታፊ በሁለተኛ ደረጃ ግብይት ማዕከል እራሱ ወይም በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አካል የተረጋገጠና የተመዘገበ ውክልና ሥልጣን እና የጸና ንግድ ፈቃድ ባለው በአንድ ሕጋዊ ወኪል ብቻ መገበያየት ይኖርበታል፡፡
2. ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን የቁም እንስሳት ለሁለተኛ ደረጃ ግብይት ማዕከል የሚያቀርብ አርቢ፣ አድላቢ ወይም የኀብረት ሥራ ማህበር ሁሉንም የቁም እንስሳት ወደ ግብይት ማዕከላት ማምጣት ሳያስፈልግ የቁም እንስሳቱን ናሙና ወይም ኤሌክትሮኒክስ ማስረጃ በማቅረብ ግብይት መፈፀም ይችላል፡፡ ዝርዝር አፈጻጸሙ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት የተፈፀመ የቁም እንስሳት ግብይት ሕጋዊነት በግብይት ማዕከሉ ተቆጣጣሪ ከተረጋገጠ በኋላ ተቆጣጣሪው በሚሰጠው ማረጋገጫ መሠረት የእንስሳቱ ርክክብ በማድለቢያው ጣቢያ የሚፈጸም ይሆናል፡፡
4. አግባብነት ያለው አካል እንደ አስፈላጊነቱ በተመረጡ አካባቢዎች በኤሌክትሮኒክስ ሥርዓት የሚታገዝ የሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት የግብይት ማዕከላት ያደራጃል፡፡ ዝርዝር አፈፃፀሙ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

5. ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከል የተፈፀመ ግብይት ሕጋዊ ሥርዓቱን የተከተለ ስለመሆኑ በግብይት ተቆጣጣሪው ከተረጋገጠ በኋላ እንስሳት የማጓጓዝ ፈቃድ ይሰጣል፡፡

## ክፍል ሶስት

## የቁም እንስሳት ግብይት ተሳታፊዎች መብቶችና ግዴታዎች

### 12.የወል ግዴታዎች

ማንኛውም የግብይት ተሳታፊ፦

1. ከመጀመሪያ እና ከሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት ወይም ከማድለቢያ ጣቢያ የተገዙ የቁም እንስሳትን ከ50 ኪ.ሜ በላይ በእግር ማጓጓዝ የለበትም፤
2. ከመጀመሪያ እና ከሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት ወይም ከማድለቢያ ጣቢያ የተገዙ የቁም እንስሳትን በእግርም ሆነ በተሽከርካሪ ከ8 ሰዓት በላይ ያለእረፍት ማጓጓዝ የለበትም፤
3. በጉዞ ወቅት ለቁም እንስሳቱ መኖ፣ ውሃና አስፈላጊ እንክብካቤ ማድረግ አለበት፤
4. በእይታ ከሚለዩ ጉዳቶችና በሽታዎች ነፃ የሆነ የቁም እንስሳ ለገበያ ማቅረብ አለበት፤
5. በቁም እንስሳት ግብይት እና በጤና ቁጥጥር ላይ አሳሳች ድርጊት ከመፈጸም መቆጠብ አለበት፤
6. ከሸማች በስተቀር የቁም እንስሳትን ከመጀመሪያ እና ከሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት ወይም ከማድለቢያ ጣቢያ በመግዛት ሲያጓጉዝ በማጓጓዣ ፈቃድ ላይ የተገለጹት የቁም እንስሳት አይነትና ብዛት ትክክል መሆኑን፣ በወቅቱና በአግባቡ ወደ መዳረሻ ስፍራ ስለማድረሱ የሚገልጽ ማረጋገጫ አግባብ ካለው አካል ማግኘት ይኖርበታል።

### 13.የአድላቢ ግዴታዎች

የአዋጁ አንቀጽ 10 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም በቁም እንስሳት ግብይት ላይ የተሰማራ አድላቢ፦

1. የቁም እንስሳት ከማድለቢያ ጣቢያ ብቻ ለሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ማዕከላት የማቅረብ፤
2. አግባብነት ካለው አካል ያገኘውን ንግድ ፈቃድ ለሶስተኛ ወገን ያለማስተላለፍ፤ ግዴታዎች አሉበት፡፡

14.<u>የላኪ ግዴታዎች</u>

የአዋጁ አንቀጽ 11 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም በቁም እንስሳት ግብይት ላይ የተሰማራ ላኪ፡-

1. የኳራንቲን ጊዜያቸውን ያጠናቀቁ የቁም እንስሳትን ብቻ ለውጪ ገበያ የማቅረብ፤
2. ወደ ውጭ ሀገር የሚልከውን የቁም እንስሳት በኢትዮጵያ ደረጃ መሰረት ማዘጋጀት ወይም የኢትዮጵያ ደረጃ ያልወጣለት በሆነ ጊዜ በገዢው ፍላጎት መሰረት የማዘጋጀት፤
3. በድርጅቱ ውስጥ የሚገኙ ወደ ውጭ ሊላኩ የተዘጋጁ ቁም እንስሳትን በአካል ተገኝቶ ለመቆጣጠር ወይም ስለእንስሳቱ መረጃ ለማግኘት አግባብ ያለው አካል ሲጠይቅ ትብብር የማድረግ፤
4. የንግድ ፈቃዱን በማንኛውም ሁኔታ ለሶስተኛ ወገን አሳልፎ ያለመስጠት፤

ግዴታዎች አለበት ፡፡

15.<u>የአጓጓዡ ግዴታዎች</u>

የአዋጁ አንቀጽ 12 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በቁም እንስሳት ማጓጓዝ ንግድ የተሰማራ አጓጓዥ የቁም እንስሳቱ በጉዞ ወቅት እንዲያርፉ፣ እንዲመገቡ እና ውኃ እንዲያገኙ እንዲሁም አስፈላጊውን እንክብካቤ እንዲያገኙ የማድረግ ግዴታዎች አለበት፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>የቁም እንስሳት ግብይት እና ጤና ቁጥጥር</u>

16.<u>የግብይት ተቆጣጣሪ ስለመመደብ</u>

1. አግባብ ያለው አካል የቁም እንስሳት ግብይት ተቆጣጣሪዎችን ይመድባል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1 መሰረት የሚመደቡ የቁም እንስሳት ግብይት ተቆጣጣሪዎች በመስኩ ዕውቀት እና መልካም ሥነ-ምግባር ያላቸው መሆን ይኖርባቸዋል።

17.<u>የግብይት ተቆጣጣሪ ኃላፊነት</u>

1. ግብይት ተቆጣጣሪ፡-

   ሀ) የቁም እንስሳት ግብይት አዋጁ፣ ይህን ደንብ እና ደንቡን ለማስፈጸም የወጡ መመሪያዎች ተከትሎ መፈጸሙን የማረጋገጥ፤

ለ) ወደ ማንኛውም የቁም እንስሳት ማድለቢያ ወይም ማቆያ ጣቢያ በሥራ ሰዓት የመግባትና የመቆጣጠር፣ መረጃ የማግኘት ወይም ሰነዶችን የመመልከት፤

ሐ) ከግብይት ማዕከላት ተገዝተው ወደ ቀጣይ መዳረሻ የሚጓጓዙ የቁም እንስሳት አግባብ ካለው አካል የተሰጣቸውን የማጓጓዝ ፈቃድ የያዙመሆኑን የማረጋገጥ፤

መ) የቁምእንስሳትን የሚያጓጉዝ ተሽከርካሪዎችን የማስቆም፣ የመፈተሽና አግባብ ያላቸው ሰነዶች እንዲቀርቡለት የማድረግ፤

ኃላፊነት ይኖረዋል።

2. ግብይት ተቆጣጣሪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1 የተመለከተውን ኃላፊነት ለመወጣት በግብይት ማዕከላትና በማጓጓዝ ሂደት እንዲሁም በሌሎች የግብይት ሂደቶች ሕገወጥ ድርጊት የተፈፀመባቸውን የቁም እንስሳት ወይም የቁም እንስሳት የጫነ ማጓጓዣ ተሽከርካሪ የመያዝ ሥልጣን ይኖረዋል።

3. ግብይት ተቆጣጣሪ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (1 እና (2 የተዘረዘሩት ኃላፊነቶችን ሲወጣ አዋጁ፣ ይህ ደንብ ወይም ደንቡን ተከትለው የወጡ መመሪያዎች መጣሳቸውን ሲያረጋግጥ በአስቸኳይ አግባብ ላለው አካል ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡

18.<u>ሕገወጥ ድርጊቶችን ስለመጠቆም</u>

1. ማንኛውም ሰው አዋጁን፣ ይህን ደንብ ወይም ደንቡን ተከትለው የወጡ መመሪያዎችን በመተላለፍ ሕገወጥ የቁም እንስሳት ማጓጓዝ ወይም ግብይት ተፈጽሟል ወይም ሊፈጸም ነው ብሎ ሲያምን በአካባቢው ለሚገኝ የቁም እንስሳት ግብይት ተቆጣጣሪ ወይም አግባብነት ላለው አካል መጠቆም ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት ጥቆማ አቅርቦ ሕገወጥ ድርጊት የተፈጸመበትን የቁም እንስሳ ያስያዘ ማንኛውም ሰው በዚህ ደንብ አንቀጽ 19 (5) (ለ) መሰረት የጠቋሚ አበል ይከፈለዋል፡፡

3. ጠቋሚው በመጠቆሙ ምክንያት ማንኛውም አይነት ጉዳት እንዳይደርስበት ማንነቱ እንዳይገለጽ ይደረጋል፡፡

## 19. ሕገ-ወጥ ድርጊት የተፈጸመበትን የቁም እንስሳ ማድለቢያ ወይም ማቆያ ጣቢያ እና የተያዘ የቁም እንስሳ

1. በዚህ ደንብ በአንቀጽ 17 (3) መሠረት የተቆጣጣሪ ሪፖርት ሲደርስ አግባብ ያለው አካል ሕገወጥ ድርጊት የተፈፀመበትን የቁም እንስሳት ማድለቢያ ወይም ማቆያ ጣቢያ ያግዳል፡፡
2. በዚህ ደንብ በአንቀጽ 17 (2) መሠረት የቁም እንስሳት ወይም የቁም እንስሳት የጫነ ማጓጓዣ ተሽከርካሪ የተያዘበት ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የቁም እንስሳት የማድለቢያ ወይም ማቆያ ጣቢያ የታገደበት ማንኛውም ሰው በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ተቃውሞውን አግባብነት ላለው አካል ሊያቀርብ ይችላል፡፡
3. አግባብ ያለው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የቀረበውን ተቃውሞ ከሰባት ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፣ አግባብ ያለው አካል ውሳኔ፦
   ሀ) የተቆጣጣሪውን እርምጃ የሚሽር ከሆነ ወዲያውኑ የተያዘው ቁም እንስሳ ለአመልካቹ እንዲመለስ ወይም የታገደው ማድለቢያ ወይም ማቆያ ጣቢያ እገዳ እንዲነሳ ይደረጋል፤
   ለ) የተቆጣጣሪውን እርምጃ የሚያጸና ከሆነ ፦
      1. የቁም እንስሳው መወረሱን የሚገልጽ ሕጋዊ ደረሰኝ ለግለሰቡ በመስጠት እንስሳቱ በግልጽ ጨረታ ወይም በግልጽ ጨረታ ካልተሸጠ ለመንግስት ወይም ለግል ተቋማት በድርድር እንዲሸጥ ተደርጎ ገንዘቡ አግባብ ያለው አካል በከፈተው ዝግ የባንክ ሂሳብ ገቢ ይደረጋል፤ ወይም
      2. የታገደው ማድለቢያ ጣቢያ ባለቤት ወይም ተከራይ ላይ በአዋጁ አንቀጽ 15 (5 መሠረት አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል።
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ውሳኔ ያልተሰጠ ከሆነ ወይም በዚሁ ንዑስ አንቀጽ በፊደል ተራ (ለ) መሠረት በተሰጠ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ሰው ውሳኔው በተወሰነ ወይም የጊዜ ገደቡ እንዳለፈ በ30 ቀናት ውስጥ ጉዳዩን የማየት ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ክስ ማቅረብ ይችላል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሰረት ይግባኝ የቀረበለት ፍርድ ቤት አግባብ ያለው አካል የሰጠውን ውሳኔ፡-
   ሀ) ከሻረው የቁም እንስሳውን ለመሸጥ የወጣው ወጪ ተቀናሽ ተደርጎ የሽያጩ ገንዘብ ለባለቤቱ ተመላሽ ይደረጋል፣ አስተዳደራዊ መቀጮው እንዲነሳ ይደረጋል፤ ወይም
   ለ) ካጸናው ወይም የቁም እንስሳቱ ባለቤት በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ይግባኝ ካላቀረበ ከቁም እንስሳቱ ሽያጭ ገንዘብ አስተዳደራዊ ወጪዎች ተቀንሰው 40% ለጠቋሚው ወይም ያለጥቆማ የተያዘ ከሆነ ለያዘው የመንግሥት ፀጥታ ተቋም ይከፈላል፣ ቀሪው 60% ለመንግስት ገቢ ይደረጋል፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የታገደ የቁም እንስሳት ማድለቢያ ወይም ማቆያ ጣቢያ ለሌላ የግብይት ተሳታፊ ሊከራይ ይችላል፡፡

20.<u>የቁም እንስሳት ጤና ቁጥጥር</u>

1. አግባብ ያለው አካል በአዋጁ አንቀጽ 7 (3) መሠረት በቅድመ ግዥ የጤና ምርመራ የጤና ችግር ምልክት የታየባቸውን የቁም እንስሳት በመለየት ህክምና ወይም እንክብካቤ እንዲያገኙ ወይም ሌላ ተገቢ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ያደርጋል፡፡
2. የገበያ ማዕከሉ የእንስሳት ጤና ተቆጣጣሪ የጤና ችግር የሌለባቸውን የቁም እንስሳት ለግብይት እንዲቀርቡ ፈቃድ በመስጠት፣ ግዥና ሽያጭ ከተፈጸመባቸው በኋላ የመለያ ቁጥር፣ የጤና ሰርተፍኬት እና የማጓጓዣ ፈቃድ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

21.<u>የጤና ተቆጣጣሪ ባለሙያ ስለመመደብ</u>

1. የግብርና ሚኒስቴር ወይም የክልል ግብርና ቢሮዎች የቁም እንስሳት ጤና ተቆጣጣሪዎችን ይመድባሉ፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የሚመደብ የቁም እንስሳት የጤና ተቆጣጣሪ በመስኩ በቂ ዕውቀትና መልካም ሥነ ምግባር ያለው መሆን ይኖርበታል።

22.**የቁም እንስሳት ጤና ተቆጣጣሪ ኃላፊነት**

1. የቁም እንስሳት ጤና ተቆጣጣሪ፦
   ሀ) ከመጀመሪያና ከሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት የግብይት ማዕከላት ተገዝተው ወደ ማድለቢያ ጣቢያ እና ወደ ኤክስፖርት ቄራ የሚጓጓዙ እንስሳት ጤና ቁጥጥርን በተመለከተ ግብርና ሚኒስቴር ስለ ቅድመ ግዢ ምርመራ የሚያወጣቸውን መመሪያዎች መከበራቸውን፣
   ለ) በመጀመሪያና በሁለተኛ ደረጃ የግብይት ማዕከላት እና በማጓጓዝ ሂደት የሚታየውን የቁም እንስሳት ጤንነት ሁኔታ፣ እና
   ሐ) በቁም እንስሳት አድላቢዎችና ላኪዎች የሚከናወነውን የቁም እንስሳት የጤና አጠባበቅ ዝግጅት፤

የመቆጣጠር እና የማረጋገጥ ኃላፊነት ይኖረዋል።

2. የቁም እንስሳት ጤና ተቆጣጣሪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1 የተመለከተውን ኃላፊነቱን ለመወጣት ወደ ማንኛውም የቁም እንስሳት ማድለቢያ ወይም የገበያ ማዕከላት በሥራ ሰዓት ለመግባት ያላቸውን ሰነዶች ለመመልከትና አስፈላጊ መረጃዎችን የማጣራት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

23.**የመተባበር ግዴታ**

የግብይት ተቆጣጣሪዎች ይህንን ደንብ ተግባራዊ ለማድረግ ለሚያደርጉት እንቅስቃሴ ማንኛውም ሰው የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

24.**ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ደንቦችና መመሪያዎች**

ይህን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማድ በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

25.**ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ የካቲት 10 ቀን 2007 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስትር**

ሐ) <u>ቡና እና ሻይ</u>

## አዋጅ ቁጥር 1051/2009

## የቡና ግብይት እና ጥራት ቁጥጥር አዋጅ

በዓለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪ የሆነ በጥሬውና እሴት የተጨመረበት የቡና ምርት በጥራትና በከፍተኛ መጠን፣ ቀጣይነት ባለውና የምርት ዱካውን በጠበቀ ሁኔታ ለማቅረብ የሚያስችል የቡና ግብይትና ጥራት ቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፣

የቡና ግብይትን ዘመናዊነት፣ ህጋዊነትና ፍትሃዊነት በማሻሻል የቡና አምራቾች፣ የግብይት ተዋንያንና የሀገሪቱን ተጠቃሚነት በላቀ ደረጃ ማሳደግ የሚያስችል የተለያየ አማራጭ ያለው የግብይት ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት አንቀፅ 55 (1 መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የቡና ግብይትና ጥራት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1051)2009 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

   1. "ቡና" ማለት በማንኛውም ዓይነትና የዝግጅት ደረጃ የሚገኝ የቡና ተክል ፍሬ ወይም የፍሬው ክፍል ነው፤
   2. "ቀይ እሸት ቡና" ማለት በተፈጥሮ የብስለት ደረጃ ላይ ደርሶ የተለቀመ እና ያልተፈለፈለ የቡና ፍሬ ነው፤
   3. "ጀንፈልቡና" ማለት ቀይ እሸት ቡና በወቅቱ ተለቅሞ፤ በማድረቂያ አልጋ ወይም ከሲሚንቶ በተሰራ አውድማ ላይ ወይም በተፈቀደ ሌላ ማድረቂያ ላይ የደረቀና ያልተቀሸረ የቡና ፍሬ ነው፤
   4. "የታጠበ ቡና ከነገለፈቱ" ማለት በባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ባለው የክልል አካል በተፈቀደ የቴክኒክ አሰራር ቀይ እሸት ቡና በመፈልፈል፣ በማቡካት ወይም ሳይቦካ በመዘፍዘፍ፣ በማጠብና በማድረቅ ተዘጋጅቶ ከነ-ሸሚዙ ያለ ቡና ነው፤

5. “የታጠበቡና” ማለት በባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ባለው የክልል አካል በተፈቀደ የቴክኒክ አሰራር ተዘጋጅቶ ገለፈቱና ስስ ልባሱ የወጣለት ቡና ነው፤
6. “በከፊል የታጠበ ቡና” ማለት በባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ባለው የክልል አካል በተፈቀደ የቴክኒክ አሠራር ቀይ እሸት ቡና በመፈልፈል ከነልጋጉ በማድረቅ የተዘጋጀ ቡና ነው፤
7. “ተፈጥሯዊ ወይም ያልታጠበ ቡና” ማለት በባለስልጣኑ ወይም አግባብ ባለው የክልል አካል በተፈቀደ የቴክኒክ አሠራር ጀንፈል ቡናን በመቀሸርና በማበጠር የተዘጋጀ ቡና ነው፤
8. “ልዩ ቡና” ማለት በአመራረቱ፣ በአዘገጃጀቱ እና በጥራቱ የተለየ ስለመሆኑ በመስፈርት አግባብ ባለው አካል ተመስክሮለት ከሌሎች ቡናዎች በተሻለ ዋጋ የሚሸጥ ቡና ነው፤
9. “አቅርቦት ቡና” ማለት በአምራች አካባቢ ባሉ ኢንዱስትሪዎች ተዘጋጅቶ ለኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም ለኤክስፖርት ማዘጋጃ ኢንዱስትሪዎችበቀጥታየሚቀርብ ቡና ነው፤
10. “የወጪ ገበያ ቡና” ማለት የአገሪቱን የወጪ ገበያ ቡና የጥራት ደረጃ መስፈርትና የገዢውን ፍላጎት በጠበቀ መልኩ በጥሬው፣ ተቆልቶ፣ ተፈጭቶ ወይም በሌላ መልኩ እሴት ተጨምሮበት የተዘጋጀ ቡና ነው፤
11. “ተረፈ ምርት ቡና” ማለት ቡናን በማዘጋጀት ሂደት የሚወጡ ያልፈረጠሙ ወይም ልቃሚ ወይም ሰባራ እና ገለባ ያሉበትን ቡና ያጠቃልላል፤
12. “የሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና” ማለት ቡና ሲዘጋጅ የሚወጣ ተረፈ ምርት ቡና ወይም የጥሬና ጣዕም ምርመራ ውጤቱ ከ 15 በመቶ ያልበለጠ ንጹህ ቡና ሆኖ ለወጪ ገበያ የማይላክ ቡና ነው፤
13. “መርቡሽ ቡና” ማለት በሙቀጫ ወይም በድንጋይ ወፍጮ ወይም በሌላ ኋላ ቀር በሆነ መንገድ የተዘጋጀና የኤክስፖርት ደረጃ የማያሟላ ቡና ነው፤
14. “ቡና አቅራቢ” ማለት አግባብ ካለው የክልል አካል የብቃት ማረጋገጫና የቡና ንግድ ፈቃድ የተሰጠው ቀይ እሸት ወይም ጀንፈል ቡና በተፈቀደ የመገበያያ ስፍራ ወይም ህጋዊ የልማትና ግብይት ትስስር ከፈጠሩ አርሶ አደሮች በመግዛት ወይም ከራሱ ማሳ ወይም ህብረት ሥራ ማህበር ከሆነ ከአባላት በመሰብሰብና በማዘጋጀት ለኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም በህግ አግባብ በቀጥታ የግብይት ትስስር ለላኪ ወይም ለውጭ ገበያ የሚያቀርብ ሰው ነው፤

15.“ቡና አልሚ እና ላኪ” ማለት አግባብ ካለው መንግሥታዊ አካል የብቃት ማረጋገጫና የቡና ላኪነት ንግድ ፍቃድ የተሰጠው ሆኖ በማሳው ያመረተውን ወይም በህግ አግባብ የልማትና ግብይት ትስስር ከፈጠሩ አርሶ አደሮች ወይም ከህብረት ሥራ ማህበር አባላት የተሰበሰበን ቡና ለውጪ ገበያ በሚመጥን ደረጃ አዘጋጅቶ የሚልክ ሰው ነው፤

16.“ቡና ላኪ” ማለት አግባብ ካለው መንግስታዊ አካል የብቃት ማረጋገጫና የቡና ላኪ ንግድ ፍቃድ የተሰጠውና በህግ አግባብ በተፈጠረ የግብይት ትስስር ወይም ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ የገዛውን ቡና ለውጪ ገበያ በሚመጥን ደረጃ አዘጋጅቶ የሚልክ ሰው ነው፤

17.“የመጀመሪያ ደረጃ የቡና ግብይት ማዕከል” ማለት በቡና አምራች አካባቢዎች አግባብ ባለው የክልል አካል የተፈቀደ ቀይ የእሸት ወይም የጀንፈል ቡና መገበያያ ሥፍራ ነው፤

18.“ሌሎች የቡና ግብይት አማራጮች” ማለት የቡና ጥራት በማሻሻልና የተሻለ ዋጋ በማስገኘት አምራቾችንና የግብይት ተዋንያንን ተጠቃሚ የሚያደርግ መሆኑ በባለሥልጣኑ ተረጋግጦ የሚፈቀድ ከምርት ገበያው ውጪ የሚካሄድ የቡና ግብይት መድረክ ነው፤

19.“የቡና ግብይት” ማለት ህጋዊ የግብይት ሥርዓትን በመከተል በመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት፣ በምርት ገበያው፣ በውጪ ገበያ ወይም በሌሎች የግብይት አማራጮች በአምራቾች፣ በአቅራቢዎች፣ ላኪዎች፣ እሴት በሚጨምሩ ኢንዱስትሪዎችና የውጭ ቡና ገዢ ኩባንያዎች እንዲሁም በጅምላ ነጋዴና ቸርቻሪ መካከል የሚከናወን የቡና ግዢና ሽያጭ ሂደት ነው፤

20.“የቡና ጥራት ቁጥጥር” ማለት ቡና የተፈጥሮ ባህሪውንና ጣዕሙን እንደጠበቀ ለተጠቃሚው ለማቅረብ ከምርት መሰብሰብ ጀምሮ በግብይት፣ በምርት ዝግጅት፣ በአከመቻቸት፣ በመቁላት ወይም በመቁላትና በመፍጨት፣ በማሸግና በማጓጓዝ ሂደት በተፈቀደ የአሠራር ሥርዓት እና የጥራት ደረጃ መስፈርት መሠረት ስለመከናወኑ በየደረጃው የሚፈጸም የቁጥጥር ተግባር ነው፤

21.“ቡና ማዘጋጀት” ማለት በሀገሪቱ በተፈቀደ የጥራትና ደረጃ የቴክኒክ አሰራር መሰረት በመጀመሪያ ደረጃና በኤክስፖርት ማዘጋጃ ኢንዱስትሪዎች የታጠበ ቡና፣ በከፊል የታጠበ ቡና ወይም ተፈጥሯዊ ወይም ያልታጠበ ቡና በጥሬው የማዘጋጀት ሂደትን ያጠቃልላል፤

22. “እሴት የሚጨምሩ ኢንዱስትሪዎች” ማለት ቡናን ቆልተው ወይም ቆልተውና ፈጭተው ወይም በተለያዩ መልኩ አቀናብረው ለሃገር ውስጥ ወይም ለውጭ ገበያ የሚያቀርቡ ኢንዱስትሪዎች ናቸው፤
23. “እሴት የተጨመረበት ቡና ማዘጋጀት” ማለት በተፈቀደ የቴክኒክ አሰራር መሠረት ጥሬ ቡናን ቆልቶ፣ ቆልቶና ፈጭቶ ወይም ወደ ተለያየ ዓይነት ምርቶች የማቀነባበር ሂደት ነው፤
24. “የቡና አምራቾች” ማለት አነስተኛ ይዞታ ያላቸው ቡና አምራች አርሶ አደሮች፣ የቡና አምራች ህብረት ሥራ ማህበራት እና አልሚ ባለሀብቶች ናቸው፤
25. “የቡና ጥራት ምርመራና ደረጃ ምደባ ማዕከል” ማለት የብቃት ማረጋገጫና የሥራ ፈቃድ በባለሥልጣኑ ተሰጥቷቸው የአቅርቦት ቡና ጥራትና ጣዕም በመመርመር ደረጃ ለመመደብ በቡና አምራች አካባቢዎች አገልግሎት እንዲሰጥ የተቋቋመ መንግስታዊ ወይም የግል ድርጅት ነው፤
26. “የቡና ጥራት ምርመራና ሰርተፊኬሽን ማዕከል” ማለት ለውጭ ሀገር ገበያ በጥሬው፣ ተቆልቶ ወይም ተቆልቶና ተፈጭቶ የሚቀርብ ቡና የጥራት ደረጃ በማረጋገጥ የምስክር ወረቀትና የምርት ሀገር ሰርተፍኬት የሚሰጥ ማዕከል ነው፤
27. “የቡና ግብይት ማዕከላት” የመጀመሪያ ደረጃ ቡና ግብይት ማዕከላት እና የኢትዮጵያ ምርት ገበያን ያጠቃልላል፤
28. “የቡና ንግድ” ማለት አግባብ ካለው የመንግስት አካል የቡና ብቃት ማረጋገጫ እና ንግድ ፈቃድ አግኝቶ ቡና ከአምራቾች በመግዛት ወይም በማምረት አዘጋጅቶ ለኢትዮጵያ ምርት ገበያ ማቅረብን፣ በጥሬው ወይም ቆልቶ ወይም ቆልቶና ፈጭቶ ወደ ውጭ ሀገር መላክን፣ ከምርት ገበያው ገዝቶ ማከፋፈልን፣ መቸርቸርን የሚያጠቃልል ነው፤
29. “የሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና ጅምላ ነጋዴ” ማለት አግባብ ካለው መንግስታዊ አካል የሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና የጅምላ ንግድ የብቃት ማረጋገጫና ፈቃድ አውጥቶ ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ለወጪ ገበያ የማይውል ቡናን በመግዛት በተፈቀደለት አካባቢ ለሚገኙ የቡና ቸርቻሪዎች ብቻ የሚያከፋፍል ሰው ነው፤
30. “ቡና ቸርቻሪ ነጋዴ” ማለት አግባብ ካለው መንግስታዊ አካል የሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና የችርቻሮ ንግድ ብቃት ማረጋገጫና ፈቃድ የተሰጠው ከሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና ጅምላ ነጋዴ ብቻ በመግዛት ለተጠቃሚዎች የሚሸጥ ሰው ነው፤

31. “የወጪ ቡና ቆዪ” ማለት አግባብ ካለው የመንግሥት አካል የወጪ ቡና ቆዪነት የብቃት ማረጋገጫና የንግድ ፈቃድ የተሰጠው ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ፣ ከራሱ ማሳ አምርቶ ወይም በሌሎች የግብይት አማራጮች ቡና በመግዛት ቆልቶ ወይም ቆልቶና ፈጭቶ ለወጪ ገበያ በሚመጥን ደረጃ አዘጋጅቶ የሚልክ ሰው ነው፤

32. “የሀገር ውስጥ ቡና ቆይ” ማለት አግባብ ካለው የክልል አካል የሀገር ውስጥ ቡና ቆይነት የብቃት ማረጋገጫና ንግድ ፈቃድ የተሰጠው ለሀገር ውስጥ ገበያ ሊውል የሚችል ቡና ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ገዝቶ ቆልቶ ወይም ተቆልቶና ፈጭቶ ለሀገር ውስጥ ገበያ የሚያቀርብ ሰው ነው፤

33. “የልማትና ግብይት ትስስር” ማለት የቡና አልሚነት ፈቃድ በተሰጠው ባለሀብት እና ኩታገጠም ወይም በዙሪያው የሚገኙ የቡና አምራች አርሶ አደሮች መካከል የጋራ ፍላጎትና ተጠቃሚነት ላይ የተመሠረተ ሆኖ በኤክስቴንሽን አገልግሎትና የቴክኖሎጂ አቅርቦት ትስስር በማድረግ ምርታማነትና የምርት ጥራት ለማሻሻል እና ለመገበያየት የሚፈጠር ህጋዊ ግንኙነት ነው፤

34. “የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት” ማለት የቡና ግብይትን ለማከናወን፣ ለማዘጋጀት፣ ለማከማቸት፣ ለመቁላት፣ ለመቁላትና ለመፍጨት፣ ለማሸግ እና ለማጓጓዝ የሚያስችል ብቃት ያለው መሆኑን የሚያረጋግጥ አግባብ ባለው የመንግስት አካል የተሰጠ ህጋዊ ሰነድ ነው፤

35. “ቡና የማሸግ ሥራ” ማለት ቡና ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ለማጓጓዝ በባለስልጣኑ ወይም በክልል አካል በተፈቀደ የቴክኒክ አሰራር የተዘጋጀ ቡናን ከብክነትና ጥራት መጓደል ለመጠበቅ ተስማሚነቱ ተረጋግጦ በባለሥልጣኑ በተፈቀደ ማሸጊያ ቁሳቁስ የማሸግ አሠራር ነው፤

36. “የቡና ገለባ” ማለት ቀይ እሸት ቡና በመፈልፈል፣ ጀንፈል ወይም የታጠበ ቡና ከነገለፈቱ በመቀሸርና በማበጠር ከዋናው የቡና ምርት የሚለይ እርጥብ ወይም ደረቅ ሽፋን ሆኖ እስከ አንድ በመቶ ንፁህ ቡና ሊኖርበት የሚችል የቡና ተረፈ ምርት ነው፤

37. “የወጪ ቡና ሽያጭ ውል” ማለት ቡናን በጥሬዉ፣ ቆልቶ ወይም ቆልቶና ፈጭቶ አዘጋጅቶ የሚልክ ቡና ላኪ በተለያዩ መዳረሻ ሀገራት ቡና ሲሸጥ በዋጋ፣ በመጠን፣ በምርት ዓይነትና ጥራት ደረጃ፣ የመላኪያ ጊዜ፣ የክፍያ ሁኔታ ዝርዝር ከውጭ ሀገር ቡና ገዢ ደንበኛው ጋር በመፈራረም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ዕውቅና አግኝቶ የተመዘገበ የተፈጻሚነት ግዴታ ያለው ሰነድ ነው፤

38.“የቅይጥ ቡና ዝግጅት” ማለት ባለስልጣኑ በሚፈቀደው የቴክኒክ አሠራር መሠረት የተለያየ ባህሪ ያላቸው ቡናዎች በማቀላቀል በተለየ ራሱን የቻለ መለያ ስም የሚዘጋጅ በጥሬ ወይም እሴት የተጨመረበት ቡና ነው፤

39.“አገልግሎት ሰጪ” ማለት በባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ባለው የክልል አካል የአገልግሎት ሰጪነት የብቃት ማረጋገጫና የንግድ ፈቃድ ወስዶ በቡና ማጠብ፣ መፈልፈል፣ ማበጠር፣ ውጪ ንግድ ቡና ማዘጋጀት፣ መቁላት፣ መፍጨት፣ ማከማቸት ወይም ማጓጓዝ አገልግሎት የሚሰጥ ሰው ነው፤

40.“አሳሳች ድርጊት” ማለት የቡና ዓይነት፣ ዋጋ፣ መጠን፣ የጥራት ደረጃ፣ ዝግጅት፣ ማከማቸት ወይም ማጓጓዝ በተመለከተ የገበያ ተሳታፊዎችንና መንግሥትን አሳሳች የሆነ ማንኛውም ድርጊት ነው፤

41.“ፕሎምፕ” ማለት ቡናን በጆንያ ወይም በብትን ሆኖ በኮንቴነር ወይም በጭነት መኪና ወይም በባቡር ተሞልቶ ከተጫነ በኋላ ወደ ምርት ገበያ ወይም ወደ ውጪ ምርት ማዘጋጃ ኢንዱስትሪ ወይም እሴት ወደ ሚጨምሩ ኢንዱስትሪዎች ወይም ወደ ጅምላ ነጋዴ ወይም ወደ ወደብ ወይም ከማዘጋጃ ኢንዱስትሪ ወደ ሌላ ማዘጋጃ ኢንዱስትሪ ለመላክ በሽቦ ታስሮ በብረት መጨፍለቅ ወይም ማሽግ ነው፤

42.“ባለሥልጣን”[25] ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት በደንብ የተቋቋመ የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን ነው፤

43.“አስፈጻሚ አካል” ማለት ሚኒስቴሩ፣ ባለሥልጣኑ፣ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም በዚህ አዋጅ የቡና ግብይትና ጥራት ቁጥጥር ሥራን አስመልክቶ የሚወጣውን ደንብና መመሪያ እንዲያስፈጽም በህግ ሥልጣን የተሰጠው የፌደራልና ክልል አካል ነው፤

44.“አግባብ ያለው የክልል አካል” ማለት የክልል የቡናና ሻይ ባለሥልጣን ወይም ተመሳሳይ ሥልጣንና ተግባር የተሰጠው አካል ነው፤

45.“ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47 የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

46.“ሚኒስቴር” ወይም “ሚኒስትር” ማለት እንደቅደም ተከተሉ የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት[26] ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

---

[25] በደንብ ቁጥር 364/08 የተቋቋመው የቡናና ሻይ ልማትና ግብይት ባለስልጣን ነው፡፡

[26] 25/08(2011) አ. 1097 አንቀጽ 9(6) የግብርና ሚንስቴር ሆኗል፡፡

47.“ሰው” ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

48. በዚህ አዋጅ በወንድ ጾታ የተገለጸው ድንጋጌ የሴትንም ፆታ ይጨምራል፡፡

3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅ በኢትዮጵያ የቡና ግብይትና ጥራት ቁጥጥር ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በሚሳተፍ ማንኛውም ሰው ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የቡና ጥራትና ግብይት አሰራር</u>

4. <u>ቡና ጥራት ቁጥጥር አሠራር</u>

1. በክልል ሥልጣን የተሰጠው የቡና ጥራት ተቆጣጣሪ አካል፡-

ሀ በመጀመሪያ ደረጃ ወይም በሌሎች በተፈቀዱ የግብይት አማራጭ ቦታዎች የሚካሄደውን ቀይ እሸት እና የጀንፈል ቡና ግብይት በጥራት ላይ ተመስርቶ መፈጸሙን ክትትልና ቁጥጥር ያካሂዳል፤

ለ ቡና ማዘጋጃ ኢንዱስትሪ አስፈላጊውን ብቃት ያለው ዝግጅት ማድረጉን፣ በተፈቀደ የቴክኒክ አሠራር ቡና ስለመዘጋጀቱ፣ ስለቡና አያያዝና አከመቻቸት ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤

ሐ ቡና ከተመረተበት አካባቢ አዋጁን ለማስፈጸም በሚወጣው በደንብ ወይም መመሪያ በሚወሰነው መሠረት አስፈላጊውን ቅድመ ሽኝት መረጃ አረጋግጦ በፕሎምፕ አሽጎ በመሸኛ ሠነድ አስደግፎ ወደ ህጋዊ መዳረሻው ይሸኛል፤ መድረሱንም ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፡፡

2. የቡና ጥራት ምርመራና ደረጃ ምደባ ማዕከል የደረሰ የአቅርቦት ቡና በአግባቡ ታሽጎ መድረሱን በማረጋገጥና ወካይ ናሙና በመውሰድ አስፈላጊውን የጥራትና የጣዕም ምርመራ በማድረግ ደረጃ ይመድባል፡፡

3. ባለሥልጣኑ የጥራት ደረጃ የተሰጠውንና አስፈላጊው መረጃ የተሟላለትን ቡና የግብይት ሂደቱ ሲጠናቀቅ ወደ የወጪ ቡና ማዘጋጃ ኢንዱስትሪዎች በፕሎምፕ አሽጎ ይሸኛል፣ መድረሱንም ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፡፡

4. ባለሥልጣኑ የውጪ ገበያ ቡና ከአገር ከመውጣቱ በፊት በተመረተበት ሥነ-ምህዳር አካባቢ ባህሪና ስያሜ ወይም በባለስልጣኑ በተፈቀደ የቅይጥ ዝግጅት ምጣኔ መሠረት መዘጋጀቱን ያረጋግጣል፡፡

5. ባለሥልጣኑ የጥራት ደረጃው በቡና ጥራት ምርመራና ሰርተፊኬሽን ማዕከል የተሰጠውን የጥራት ደረጃና የምርት ሀገር የምስክር ወረቀት በመስጠት በፕሎምፕ አሽጎ ወደ ወደብ ይሸኛል፤ መድረሱንም ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡
6. በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም በባለስልጣኑ የተፈቀደለት ሌላ የምርመራ ማዕከል ለሀገር ውስጥ ፍጆታ የሚውል ቡና የተቀመጠውን መስፈርት ማሟላቱን በማረጋገጥ የደረጃ ምደባና የምስክር ወረቀት በመስጠት ወደ ተጠቃሚ አከባቢዎች ይሸኛል፤ መድረሱንም ይከታተላል ይቆጣጠራል፡፡
7. ባለሥልጣኑ ለሀገር ውስጥና ለወጪ ገበያ በተዘጋጀ ቡና በተሰጠ የጥራት፣ ምርመራና የደረጃ ምደባ ላይ በሚቀርቡ ቅሬታዎች ላይ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

## 5. <u>የቡና ግብይት አሠራር</u>

የቡና ግብይት አሠራር በሚከተለው መልክ ይከናወናል:-

1. ቀይ እሸት ወይም የጀንፈል ቡና ግብይት አነስተኛ ይዞታ ባላቸው አርሶ አደሮች ወይም አልሚ ባለሀብቶች ወይም በአቅራቢዎች ወይም በህብረት ሥራ ማህበራት ወይም በልማትና ግብይት ትስስር በፈጠሩ አልሚ ባለሃብቶች ወይም እሴት በሚጨምሩ ኢንዱስትሪዎች መካከል፤
2. የአቅርቦት ቡና ለውጭ ገበያ ለማዘጋጀት የሚውል ከሆነ በአቅራቢና በላኪ መካከል ወይም በአቅራቢ እና በኤክስፖርት ቡና ቆዩ መካከል፤
3. የአቅርቦት ቡና ሆኖ የውጭ ገበያ ደረጃ ካላሟላ በአቅራቢና በጅምላ ነጋዴ ወይም በሀገር ውስጥ ቡና ቆዩ መካከል፤
4. ከወጪ ገበያ ምርት ዝግጅት የሚወጣ ተረፈ ምርት ቡና ከሆነ በላኪ እና በሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና ጅምላ ነጋዴ ወይም በሃገር ዉስጥ ቡና ቆዩ መካከል በግብይት ማዕከላት፤
5. በኢትዮጵያ ምርት ገበያ የሚፈጸም የአቅርቦት ቡና ግብይት በምርት ገበያ ወይም በባለስልጣኑ በተፈቀደላቸው የግል የቡና ጥራት ምርመራና ደረጃ ምደባ ማዕከላት በተሰጠው የጥራት ደረጃና ባለቤትነትን ገላጭ የሆነ በተሟላ መረጃ መሰረት፤
6. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (2 ፤(3 እና (4 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በሌሎች የግብይት አማራጮች የሚፈጸም የአቅርቦት ቡና ግብይት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣው ደንብ በዝርዝር በሚወሰነዉ መሠረት በባለስልጣኑ እየተመዘገበ ይከናወናል፤

7. በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ሆነ በሌሎች የግብይት አማራጮች የተሸጠ የአቅርቦት ቡና ለውጪ ገበያ ዝግጅት ከዝርዝር መረጃው ጋር ወደ ቡና ማዘጋጃ ኢንዱስትሪ ይሸኛል፤
8. የአቅርቦት ቡና ደረጃ ከወጣለት ቀን ጀምሮ በኢትዮጵያ ምርት ገበያው አሰራር በሚፈቀደው የጊዜ ገደብ በመኪና ላይ ወይም ባለቤትነትን ገላጭ በሆነ መንገድ ተከማችቶ ይሸጣል፤
9. በመኪና ላይ በጊዜ ገደቡ ያልተሸጠ የአቅርቦት ቡና በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም የመጋዘን አገልግሎት ለመስጠት በተፈቀደላቸው ድርጅቶች መጋዘን ብቻ ባለቤትነትን ገላጭ በሆነ አግባብ በማቆየት ለገበያ ይቀርባል፤
10. የሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ብቻ ለጅምላ ነጋዴዎች ወይም ለሀገር ውስጥ ቡና ቆዪዎች በጨረታ ይሸጣል፤
11. ቡና አልሚ ባለሃብቶች አነስተኛ ይዞታ ካላቸው ቡና አምራች አርሶ አደሮች ጋር ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣው ደንብ መሠረት የልማትና ግብይት ትስስር በመፍጠር የእሸት ወይም የጀንፈል ቡና ግብይት ማካሄድ ነው፤
12. ቡና ላኪዎች በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም በሌሎች የግብይት አማራጮች የገዙትን ወይም በማሳቸውና በትስስር ያመረቱትን እንዲሁም ቆልተው ወይም ቆልተውና ፈጭተው ያዘጋጁትን ቡና ለውጭ ሀገር ቡና ገዢዎች በመሸጥ የሽያጭ ውል ሰነድ በብሔራዊ ባንክ ያስመዘግባሉ፤ ለባለሥልጣኑ ያሳውቃሉ፤
13. የወጪ ንግድ ደረጃ ያለው እሴት የተጨመረበት ቡና ተፈጥሯዊ ጣዕምና ባህሪውን ለማስተዋወቅ ሲባል በደንብ በሚፈቀደው ቦታና ጊዜ መሠረት በሀገር ውስጥ በውጭ ምንዛሪ ብቻ ለሽያጭ ሊቀርበ ይችላል፡፡
14. የቡና እሴት የሚጨምሩ ኢንዱስትሪዎች ይህንን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ ደንብ መሠረት ከውጭ ሀገር ጥሬ ቡና ማስገባት ይችላሉ፡፡

## 6. <u>የቡና ገለባ ግብይት</u>

1. በባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ባለው የክልል አካል በሚሰጠው የብቃት ማረጋገጫ መሰረት ማንኛውም ቡና አምራች ወይም አዘጋጅ ወይም ከህጋዊ አካል ቡናን የገዛ ሰው በዝግጅት ሂደት የሚወጣውን የቡና ገለባ አዘጋጅቶ ለሀገር ውስጥ ወይም ለውጪ ገበያ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብ ካለው የመንግስት አካል ፈቃድ የወሰደ ሰው የቡና ገለባን በጥሬ ዕቃነት ተጠቅሞ የተፈጥሮ ማዳበሪያ ወይም ወደ ሌሎች ምርቶች ቀይሮ ጥቅም ላይ ማዋል ይቻላል፡፡

## ክፍል ሶስት
## የግብይት ተሳታፊ ግዴታዎች

7. **በቡና ግብይት ሥራ የተሰማራ ሰው ግዴታዎች**

ማንኛውንም በቡና ግብይት የተሠማራ ሰው፡-

1. የቀይ እሸትና ጀንፈል ቡና ግብይት በተፈቀዱ የቡና ማዘጋጃ ኢንዱስትሪዎች ወይም አግባብ ባለው የክልል አካል በተፈቀደ የመገበያያ ስፍራ ብቻ የማካሄድ፤
2. የአቅርቦት ቡና ግብይት በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ውጪ በተፈቀዱ ሌሎች የግብይት አማራጮች የሚፈጸም ከሆነ የቡና ዓይነት፣ መጠን፣ ጥራት ደረጃ፣ ዋጋና ጊዜ በባለስልጣኑ በማስመዝገብ የመፈጸም፤
3. የአቅርቦት ቡና በሀገር ውስጥ ለግብይት ከመቅረቡ በፊት በልዩ ሁኔታ በባለስልጣኑ የተፈቀደለት ካልሆነ በስተቀር በቡና ጥራት ምርመራና ደረጃ ምደባ ማዕከል አስመርምሮ የምስክር ወረቀት የማግኘት፤
4. የአቅርቦት ወይም የውጪ ቡና ከመጫኑ በፊት አሽከርካሪውና ተሽከርካሪውን የብቃት መስፈርት አሟልቶ መሰማራቱን የማረጋገጥ፤
5. በባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ባለው የክልል አካል የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የማቅረብ፤
6. ለግብይት ካዘጋጀው ቡና ለጥራት ምርመራ አገልግሎት የሚውል ናሙና እንዲሰጥ ሲጠየቅ ወካይ ናሙና የመስጠት ወይም የማቅረብ፤
7. ማንኛውንም ቀይ እሸት ወይም ጀንፈል ቡና ከባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ካለው የክልል አካል ከተፈቀደ የመገበያያ ሥፍራ ወደ መፈልፈያ ወይም መቀሸሪያ ኢንዱስትሪ ከማጓጓዙ በፊት ህጋዊ መሸኛ የመያዝ፤
8. ማንኛውንም የአቅርቦት ወይም የወጪ ገበያ ቡና ከማጓጓዙ በፊት በፕሎምፕ ማሳሸግና በተቆጣጣሪው የተሰጠውን መሸኛ የመያዝ፤

9. ዕለታዊ የቡና ግዢና ሽያጭ መጠን፣ደረጃ፣ ዋጋና ሌሎች ዝርዝር መረጃዎች መዝግቦየመያዝና ለባለሥልጣኑ ወይምለሚመለከተው ተቆጣጣሪ የማሳወቅ፣ ወይም በአካል ለመነብኘት ወይም ክምችት ለመቁጠር ሲፈለግ የመተባበር፤
10. የአገሪቱን የቡና ጥራት መስፈርት የማክበርና እና የቡናችንን መልካም ሥም ከሚያጎድፉ ማንኛውም ድርጊቶች የመቆጠብ፤
11. ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚወጡ ደንቦች፣ መመሪያዎች እና የአሠራር ሥርዓቶች የመፈፀምና የማስፈጸም ግዴታዎች አለበት፡፡

8. <u>የቡና አምራች ግዴታዎች</u>

ማንኛውም የቡና አምራች፡-

1. ከአርሶ አደር በስተቀር፣ ከሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የጸና የብቃት ማረጋገጫ እና ንግድ ፈቃድ የመያዝ፤
2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 ንኡስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ያመረተውን የአቅርቦት ቡና በቀጥታ ወደ ውጭ ለመላክ ሲፈልግ ወደ ኤክስፖርት ማዘጋጃ ኢንዱስትሪ አሳሽነ የማሽኘትና የውጪ ምርት ዝግጅት ሲያጠናቀቅ ጥራት ምርመራና ሰርተፊኬሽን ማዕከል አቅርቦ ደረጃ የማረጋገጥና የማሸኘት፤
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም በሌሎች የግብይት አማራጮች በሀገር ውስጥ የሚገበያይ ከሆነ ለቡና ጥራት ምርመራና ደረጃ ምደባ ማዕከል አቅርቦ ደረጃ የማሰጠት፤
4. ቡና አልሚ ባለሀብት አነስተኛ ይዞታ ካላቸው ቡና አምራች አርሶ አደሮች በልማትና ግብይት ትስስር ቡና ለመግዛት የኤክስቴንሽንና የቴክኖሎጂ አቅርቦት ድጋፍ የማድረግ፣ ከወቅቱ የተሻለ ዋጋ የመክፈል ወይም በውል ስምምነታቸው መሠረት ከሽያጭ በኋላ ትርፍ የማከፋፈል፤
5. ተረፈምርት ቡና በቡና ጥራት ምርመራና ደረጃ ምደባ ማዕከል አስመርምሮ ሲፈቀድ ብቻ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ የመሸጥ፤
6. ያመረተውን ወይም በልማትና ግብይት ትስስር የገዛውን ቡና በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም በሌላ ህጋዊ የግብይት አማራጭ የምርት ዘመኑ ሳያልፍ የመሸጥ ወይም ወደ ውጭ አዘጋጅቶ የመላክ ግዴታዎች አለበት፡፡

9. <u>የቡና አቅራቢ ግዴታዎች</u>

ማንኛውንም ቡና አቅራቢ፡-

1. ቀይ እሸት ወይም ጀንፈል ቡና በተፈቀደለት አካባቢ ብቻ የመግዛት፣ የማዘጋጀት፣ የማጓጓዝ፣ የበቀለበትን አካባቢ ቡና ባህሪና ስያሜ የመጠበቅ፣ ከሌላ ሥነ-ምህደር ዓይነት ቡና ጋር ሳይቀይጥ ወይም ከማንኛውም ሌሎች ባዕድ ነገሮች ሳይደባለቅ የማቅረብ፣
2. የገዛውን ቀይ እሸት ቡናን በደንቡ በባለሥልጣኑ በተፈቀደ የቴክኒክ አሠራርና ጊዜ መሠረት የታጠበ ቡና ከነገለፈቱ፣ በከፊል የታጠበ ቡና ወይም ተፈጥሯዊ ቡና የማዘጋጀት፣
3. የሚያዘጋጀውን የአቅርቦት ቡና በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም በሌላ ህጋዊ የግብይት አማራጭ የምርት ዘመኑ ሳያልፍ የመሸጥ ወይም ወደ ውጭ አዘጋጅቶ የመላክ፣
4. ለቡና ጥራት ምርመራና ደረጃ ምደባ ማዕከላት የሚያቀርበው ወይም በቀጥታ ለላኪ የሚሸጠውን ወይም በራሱ አዘጋጅቶ ቀጥታ ወደ ውጭ የሚልከውን የአቅርቦት ቡና ጥራቱን የጠበቀና የእርጥበቱ መጠን ወይም ይዘት ይህንን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣው ደንቡ በሚወሰነው መሠረት መሆኑን የማረጋገጥ፣
5. በቡና ጥራት ምርመራና ደረጃ ምደባ ማዕከል ተመርምሮ ለውጭ ገበያ ብቁ የሆነ የአቅርቦት ቡና በኢትዮጵያ ምርት ገበያ የመሸጥ ወይም
6. አስቀድሞ በሌላ አማራጭ የግብይት ትስስር የተሸጠ ከሆነ ለገዥው የማስረከብ ወይም
7. የተሻለ ዋጋ ለመጠበቅ ያሰበ እንደሆነ በቡና ግብይት ባልተሰማሩ ህጋዊ የማከማቻ አገልግሎት የመስጠት ፍቃድ ባላቸው ድርጅቶች የማከማቸት፣
8. የምርት ዘመኑ የቡና ግብይት ከመጀመሩ በፊት አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት ስለማጠናቀቁ ከሚመለከተው የክልል አካል የብቃት ማረጋገጫ የመያዝ ግዴታዎች አሉበት፡፡

10. <u>የቡና ላኪ ግዴታዎች</u>

ማንኛውም ቡና ላኪ፡-

1. ከሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የፀና የብቃት ማረጋገጫ እና ንግድ ፈቃድ የመያዝ፤

2. ወደ ውጪ የሚልከውን ቡና የአገሪቱን የጥራት ደረጃ መስፈርት ጠብቆ የማዘጋጀት፣
3. በባለስልጣኑ በልዩ ፍቃድ ካስመዘገበው የቅይጥ ቡና ዝግጅት ውጭ ቡናው በተመረተበት አካባቢ ባህሪና ስያሜ ጠብቆ ለውጭ ገበያ የማቅረብ፣
4. የውጪ ቡና ሽያጭ ውል ስምምነት ከፈፀመ 24 ሰዓት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የማስመዝገብ እንዲሁም ለባለስልጣኑ በሦስት የስራ ቀናት ውስጥ የማሳወቅ፣
5. በማናቸውም የግብይት አማራጮች የገዛውን ወይም ያመረተውን ወይም ህብረት ስራ ማህበር ከሆነ የቡና ማሳ ካላቸው አባላቱ የሰበሰበውን ቡና ምንም ሳያባክንና የጥራት ደረጃው ሳይጓደል በምርት ዘመኑ ለውጭ ሀገር ገበያ የመሸጥ፣
6. ለውጪ ገበያ በማዘጋጀት ሂደት የሚወጣ ተረፈ ምርት ቡና ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ በማቅረብ የመሸጥ፣
7. አሳማኝ ምክንያት መኖሩ በባለሥልጣኑ ተረጋግጦ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መራዘሙ እንደተጠበቀ ሆኖ ከገዢዎች ጋር የገባውን ውል በውሉ ጊዜ ውስጥ የመፈጸም፣
8. በቡና ጥራት ምርመራና ደረጃ ምደባ ማዕከል ተመርምሮ ለውጪ ገበያ ብቁ የሆነ ቡና በልዩ ምክንያት በባለሥልጣኑ ካልተፈቀደ በስተቀር በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም በሌላ የግብይት አማራጭ በአገር ውስጥ ለግብይት ያለማቅረብ ግዴታዎች አለበት፡፡

11. <u>የሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና ጅምላ ነጋዴ ግዴታዎች</u>

ማንኛውም የሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና ጅምላ ነጋዴ፡-

1. ከሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የፀና የብቃት ማረጋገጫ እና ንግድ ፈቃድ የመያዝ፤
2. የሀገር ውስጥ ፍጆታ የሚሆን ቡና ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ብቻ የመግዛት፣
3. የውጪ ገበያ ቡና አለመግዛት ወይም አለማጓጓዝ ወይም አለመሸጥ፣
4. የሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡናን በጅምላ ለማከፋፈል ንግድ ፈቃድ በወሰደበት ክልል ወይም ዞን ወይም ከተማ ብቻ የመሸጥ፣

5. የሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡናን ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወደ ተጠቃሚ ክልል ወይም ዞን ወይም ከተማ ሲያጓጉዝ በባለስልጣኑ የሸኝት ሠራተኞች በፕሎምፕ ማሳሸግ፣ የመሸኛ ሠነድ የመያዝና ሲጠየቅ የማሳየት፣ እንደታሸገ መድረሱንም ከሚመለከተው አካል ማረጋገጫ የመውሰድና ለባለስልጣኑ የማቅረብ፣
6. የዘመኑ የቡና ግብይት ከመጀመሩ በፊት አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት ስለማጠናቀቁ ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት የብቃት ማረጋገጫ የመያዝ ግዴታዎች አሉበት፡፡

12.<u>የሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና ቸርቻሪ ነጋዴ ግዴታዎች</u>

ማንኛውም የሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና ቸርቻሪ ነጋዴ፡-

1. ከሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የፀና የብቃት ማረጋገጫ እና ንግድ ፈቃድ የመያዝ፤
2. የሀገር ውስጥ ፍጆታ የሚሆን ቡና ከሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና ጅምላ ነጋዴ ወይም የሀገር ውስጥ ቡና ቆዪ ብቻ የመግዛት፣
3. የወጪ ገበያ ቡና አለመግዛት ወይም አለማጓጓዝ ወይም አለመያዝ ወይም አለመሸጥ፣
4. የሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡናን በችርቻሮ ለመሸጥ ንግድ ፈቃድ በወሰደበት መቸርቸሪያ ሱቅ ወይም ቦታ ብቻ የመሸጥ፣
5. የሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡናን የሚቸረችር ነጋዴ የቡና ግዢና ሽያጭ መረጃ የመያዝና ሲጠየቅ የማቅረብ ግዴታዎች አሉበት፡፡

13.<u>የውጪ ቡና ቆይ ግዴታዎች</u>

ቡና ቆልቶ ወይም ቆልቶና ፈጭቶ ወደ ውጭ ሀገር በመላክ ሥራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው፡-

1. ከሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የፀና የብቃት ማረጋገጫ እና ንግድ ፈቃድ የመያዝ፤
2. ለግብዓትነት የሚጠቀመው ቡና ከራሱ ማሳ ያመረተውን ወይም ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም በቀጥታ ከአቅራቢ ወይም ከአምራች የመግዛት፣
3. ለውጭ ገበያ ቆልቶ ከሚያዘጋጀው ቡና የግብዓትና ውጤት ምጣኔ እንደተጠበቀ ሆኖ በጥሬውና ከተቆላ በኋላ የሚወጣ ተረፈ ምርት ቡና ቆልቶ ወይም ቆልቶ ፈጭቶ ለሀገር ውስጥ ቸርቻሪዎች ወይም የተፈላ ቡና አዘጋጅተው ለሚሸጡ አገልግሎት ሰጪዎች የማቅረብ፣

4. በባለሥልጣኑ ካስመዘገበው የቅይጥ ቡና ዝግጅትና የንግድ ስያሜ መብት ውጭ አንዱን ዓይነት ቡና ከሌላ ዓይነት ጋር ሳይቀይጥ ወይም ሳይደባልቅ ቡናው የተመረተበት አካባቢ ባህሪና ስያሜ ጠብቆ ለውጭ ገበያ የማቅረብ፣
5. ተቆልቶና ተፈጭቶ የተሸጠ ቡና ውል በ24 ሰዓት ውስጥ ለብሔራዊ ባንክ የማስመዝገብ እንዲሁም ለባለስልጣኑ በሦስት የሥራ ቀናት ውስጥ የማሳወቅ፣
6. አስገዳጅ ሁኔታ መፈጠሩ በባለሥልጣኑ ተረጋግጦ ካልተፈቀደ በስተቀር ወደ ውጭ የሚላከው የተቆላ ወይም ተቆልቶ የተፈጨ ቡና በሀገር ውስጥ ገበያ አለመሸጥ፣
7. ተቆልቶ ወይም ተፈጭቶ ወደ ውጭ የሚላከው ቡና እሽግ ላይ የተመረተበት ሀገር፣ የጥራት ደረጃ፣ ይዘት፣ የተመረተበትና የመጠቀሚያ ጊዜ፣ የቡናው ዓይነት እና የንግድ ስያሜ የመገለፅ፣
8. ወደ ውጭ የሚላከው የተቆላ ወይም ተቆልቶ የተፈጨ ቡና እና ማሸጊያው በሀገሪቱ የጥራት ደረጃ መስፈርት እና በቡና ገዥ ኩባኒያ ፍላጎት መሠረት የማዘጋጀት፣
9. አሳማኝና በቂ ምክንያት መኖሩ በባለሥልጣኑ ተረጋግጦ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መራዘሙ እንደተጠበቀ ሆኖ ከገዢዎች ጋር የገባውን የውል ግዴታ የመፈጸም፣
10. የቡና ግዢ፣ ዝግጅትና ሽያጭ መረጃ መዝግቦ የመያዝና በባለሥልጣኑና በሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ሲጠየቅ የማቅረብ፣ እና
11. ይህንን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣው ደንብ መሠረት ጥሬ ቡና ከውጭ ሀገር የማስገባት ግዴታዎች አሉበት፡፡

14.<u>የሀገር ውስጥ ቡና ቆይ ግዴታዎች</u>

የሀገር ውስጥ ቡና ቆልቶ በመሸጥ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው፡-

1. ከሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የፀና የብቃት ማረጋገጫ እና ንግድ ፈቃድ የመያዝ፤
2. ለሀገር ውስጥ ገበያ የተፈቀደውን ቡና ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ገዝቶ ቆልቶ ወይም ቆልቶና ፈጭቶ ለሀገር ውስጥ ገበያ ብቻ የማቅረብ፣
3. ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ የገዛውን የሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና ቆልቶ ወይም ፈጭቶ በወቅቱ ባለው ገበያ ዋጋ በጅምላ የመሸጥ፣
4. የተቆላ ወይም ተቆልቶ የተፈጨ ቡና ከመጠቀሚያው ጊዜው በላይ አለማከማቸት፣
5. ተቆልቶ ወይም ተቆልቶና ተፈጭቶ ለሀገር ውስጥ ፍጆታ የተዘጋጀ ቡና እሽግ ላይ ያመረተው ድርጅት፣ የጥራት ደረጃ፣ ይዘት፣ የተመረተበትና የመጠቀሚያ ጊዜ፣ የቡናው ዓይነት እና የንግድ ስያሜ የመገለፅ፣

6. ከሚመለከተው የመንግስት አካል የብቃት ማረጋገጫ የማግኘት እና በጊዜው የማሳደስ፣
7. ለሀገር ውስጥ ፍጆታ የተቆላ ወይም ተቆልቶ የተፈጨ ቡና እና ማሸጊያው በሀገሪቱ የጥራት ደረጃ መስፈርት መሠረት የማዘጋጀት፣
8. የቡና ግብር፣ ዝግጅትና ሽያጭ መረጃ መዝግቦ የመያዝና በባለስልጣኑና በሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ሲጠየቅ የማቅረብ፣

ግዴታዎች አሉበት፡፡

15. <u>ቡና በምግብነት ወይም በመጠጥነት አዘጋጅቶ የመሸጥ አገልግሎት ሰጪ ግዴታዎች</u>

ቡናን በምግብነት ወይም በመጠጥነት አዘጋጅቶ ለሀገርውስጥ ፍጆታ የመሸጥ አገልግሎት ላይ የተሰማራ ማንኛውም አገልግሎት ሰጪ፡-

1. ከሚመለከታቸው የመንግስት አካል የብቃት ማረጋገጫ የመያዝ እና በጊዜ የማሳደስ፣
2. በባለስልጣኑ በልዩ ሁኔታ ካልተፈቀደ በስተቀር ሕጋዊ ከሆነ ከሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና ጅምላ ነጋዴ ወይም ቸርቻሪ ወይም ቆልቶ ወይም ቆልቶና ፈጭቶ አከፋፋይ ብቻ የመግዛት፣
3. በባለሥልጣኑ በልዩ ሁኔታ ካልተፈቀደ በስተቀር የውጪ ገቢያ ቡና አለመግዛት ወይም አለማጓጓዝ ወይም አለመያዝ ወይም አለመጠቀም፣
4. የቡና ግብር፣ ዝግጅትና ሽያጭ መረጃ መዝግቦ የመያዝና በባለስልጣኑ ወይም በሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ሲጠየቅ የማቅረብ፣

ግዴታዎች አሉበት፡፡

16. <u>የቡና ማዘጋጃና ማከማቻ አገልግሎት ሰጪ ግዴታዎች</u>

በቡና ማዘጋጃና ማከማቻ አገልግሎት በመስጠት ሥራ ላይ የተሰማራ አገልግሎት ሰጪ፡-

1. የሚመለከተው አካል ያወጣውን መስፈርት በማሟላት የብቃት ማረጋገጫ መያዝና በጊዜ የማሳደስ፣
2. የተረከበውን ቡና በሀገሪቱ የጥራት ደረጃ መስፈርትና በውሉ መሠረት አዘጋጅቶ ስለ ቡናው ዓይነት፣ መጠንና ጥራት ደረጃው ከሚገልጽ ማስረጃ ጋር የማስረከብ፣
3. ለማከማቸት የተረከበውን ቡና በገባው የውል ስምምነት መሠረት በአግባቡ የማከማቸት፣

4. በባለስልጣኑ ወይም አግባብነት ባለው አካል ሕጋዊነቱ ተረጋግጦ ያልተሸኘ ቡና ያለመረከብ እና ያለማዘጋጀት፣
5. ቡና በመፈልፈል፣ በማበጠር፣ ለውጪ ንግድ በማዘጋጀት፣ በመቁላት ወይም ቆልቶ በመፍጨት የተሰማራ ከሆነ ከሚመለከተው የአካባቢ ጥበቃ መስሪያ ቤት ከአካባቢ ብክለት ነፃ ስለመሆኑ የምስክር ወረቀት የመያዝ፣ግዴታዎች አለበት፡፡

## 17.<u>ቡና የማጓጓዝ አገልግሎት ሰጪ ግዴታዎች</u>

ቡና የማጓጓዝ አገልግሎት በመስጠት ላይ የተሰማራ ማንኛውም አሽከርካሪ ወይም የተሽከርካሪ ባለቤት ወይም ወኪል እንደአግባቡ፡-

1. ባለሥልጣኑ ከሚመለከተው አካል ጋር በመተባበር በሚያወጣው ደንብና መመሪያ በተመለከተው መስፈርት መሠረት ስለተሽከርካሪው የብቃት ማረጋገጫ የመያዝና የማሳደስ፣
2. ቡና ጭኖ ሲጓዝ ብልሽት ያጋጠመው ወይም ወንጀል የተፈጸመበት እንደሆነ በአካባቢው ለሚገኝ ሥልጣን ላለው አካል በዕለቱ የማመልከትና ማስረጃ የማቅረብ፣
3. ቡናው ከመጫኑ በፊት ቡናው በዚህ አዋጅ መሰረት ለመጓጓዝ የተዘጋጀና ሕጋዊ መሆኑን የማረጋገጥ፣
4. ከቦታ ቦታ እንዲያጓጉዝ የተሰጠውን ቡና ፕሎምፕ ሳይበጠስ፣ ሸራ ሳይቀደድ ጥራቱን ጠብቆ ወደ ተሸኘበት አካባቢ በትክክል የማድረስ፣
5. እንዲያጓጓዝ ከተፈቀደለት ቡና ውጪ በማንኛውም የተሽከርካሪ አካል ላይ ተጨማሪ ቡናና ሌሎች የቡናውን ጥራት ሊያጓድሉ የሚችሉ ነገሮች ያለመያዝ፣
6. ተሽከርካሪውን ለሌላ ወገን በኪራይ ውል ስምምነት ወይም በሌላ አኳኃን ሲያስተላልፍ ተሽከርካሪው በሕገ ወጥ ድርጊት እንዳይሰማራ የመቆጣጠር፣

   ግዴታዎች አለበት፡፡

# <u>ክፍል አራት</u>

# <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

## 18.<u>የባለሥልጣኑ ሥልጣን እና ተግባር</u>

ባለሥልጣኑ በሌሎች ሕጎችና በዚህ አዋጅ የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

1. አግባብ ካላቸው የክልል አካላት ጋር በመተባበር የቡና ግብይትና ጥራት መከታተያና መቆጣጠሪያ ቦታዎች በጥናት የመለየት፣ተቆጣጣሪ በመመደብ የማስተዳደር ወይም ውክልና የመስጠት፣

2. በቡና ግብይት ለሚሳተፉ አካላት በደንብና መመሪያ በሚወጡ መስፈርቶች ላይ ተመስርቶ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የመስጠት፣ የመከታተልና የመቆጣጠር፣
3. ማንኛውም ለውጭ ገበያ የተዘጋጀ ቡና የጥራት ምርመራ፣ የሰርተፊኬሽን፣ የሸኝት አገልግሎት እና የምርት ሀገር ሰርተፊኬት የመስጠት፣
4. ለናሙና ወይም ለንግድ ትርኢት ጉዳዮች ቡና ወደ ውጭ ሀገር እንዲላክ የመፍቀድ፣
5. ይህን አዋጅ ወይም አዋጁን ለማስፈጸም የሚወጡ ደንቦችንና መመሪያዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ ከሚመለከታቸው የፍትህና ፀጥታ አካላት ጋር በመተባበር ሕገ-ወጥ ቡና ሊገኝበት ይችላል ተብሎ በበቂ ሁኔታ በባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ያለው የክልል አካል ሲጠረጠር ማንኛወንም ቦታና ተሽከርካሪ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ወይም አስቸኳይ ሁኔታ ሲኖር ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሠረት የመፈተሽ፣ የማሸግ፣ የማገድ፣ የመያዝ፣ ተጣርቶ ሕገ-ወጥ ሆኖ ሲገኝ የቡናው ባለቤት ለፍርድ ቤት ቅሬታውን የማቅረብ መብቱ እንደተጠበቀ ሆኖ የመውረስና የመሸጥ ውሳኔ የመስጠት፣
6. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (5) የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ባለስልጣኑ ወይም አግባብ ያለው የክልል አካል በማንኛውም ሁኔታ በጥርጣሬ በተያዘ ቡና ከመልቀቁ ወይም ከመወረሱ በፊት አጣርቶ የመጨረሻ ውሳኔ የመስጠት፣
7. በቡና ግብይት የሚሳተፍ አካል የግብይት ሥራውን የሚያዛባ ድርጊት መፈፀሙ ወይም የብቃት ጉድለት ስለመከሰቱ ሲረጋገጥ በሚወጣው ደንብና መመሪያ መሠረት የብቃት ማረጋገጫ በማገድ ወይም በመሰረዝ አገልግሎት እንዳያገኝ ለሚመለከታቸው አካላት የማሳወቅ፣
8. የቡና ሕገ-ወጥ ግብይት፣ ዝውውርና ክምችት ለሚጠቁሙ እና ለሚይዙ አካላት የኮሚሽን አበል ክፍያ መጠንና አፈፃፀም በደንብ የማስወሰንና የማስፈጸም፣

ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

19.<u>ስለተከለከሉ ተግባራትና ቅጣቶች</u>

1. ማንኛውም ቡና አዘጋጅ ቡና ሲያዘጋጅ በባለሥልጣኑ ወይም በክልል አግባብ ያለው አካል ከተፈቀደ የቴክኒክ አሠራር ውጭ በማዘጋጀት በቡናው ጥራት ላይ እና በአካባቢው ማህበረሰብ ላይ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ፣ ማዘጋጃ ኢንዱስትሪው መታሸጉና ምርቱ ለግብይት እንዳይቀርብ መደረጉ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከአንድ ዓመት በማያንስና ከሦስት ዓመት በማይበልጥ እስራት እና ከብር 20 ሺ. እስከ 40 ሺ. (ከብር አስር ሺ. እስከ አርባ ሺ.) በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡
2. ማንኛውም በቡና ግብይት የተሰማራ ሰው ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም ባለሥልጣኑ ከሚወስናቸው ሌሎች የግብይት አማራጮችና ስፍራዎች ውጪ ሲሸጥም ሆነ ሲገዛ የተገኘ እንደሆነ፣ ቡናው መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ ከአንድ ዓመት በማያንስና ከሦስት ዓመት በማይበልጥ እስራት እና ከብር 20ሺ. እስከ 40 ሺ. (ከብር አስር ሺ. እስከ አርባ ሺ.) በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡
3. ማንኛውም በቡና ንግድ የተሰማራ ሰው ቡናን በክምችት እንዲቀመጥ በደንቡ ከተፈቀደው ጊዜና ቦታ ውጪ አከማችቶ የተገኘ እንደሆነ፣ ቡናው መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከአንድ ዓመት በማያንስና ከሦስት ዓመት በማይበልጥ እስራት እና ከብር 20 ሺ. እስከ 40 ሺ. (ከብር አስር ሺ. እስከ አርባ ሺ.) በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡
4. ማንኛውም በቡና ንግድ ሥራ የተሰማራ ሰው ለውጭ ገበያ የሚመጥን ቡናን በሀገር ውስጥ ገበያ በጥሬውም ሆነ ቆልቶ ወይም ቆልቶ በመፍጨት ያለ ባለሥልጣኑ ልዩ ፈቃድ የሸጠ እንደሆነ፣ ቡናው መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከሦስት ዓመት በማያንስና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከብር 60 ሺ. እስከ 100 ሺ. (ከብር ስልሳ ሺ. እስከ መቶ ሺ.) በሚደርስ መቆጮ ይቀጣል፡፡
5. ማንኛውም በቡና ግብይት የተሠማራም ይሁን ከቡና ግብይት ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ግንኙነት ያለው ሰው ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት አለአግባብ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በቡና ጥራትም ይሁን ግብይት ላይ አሳሳች ድርጊት የፈጸመ እንደሆነ ከሶስት ዓመት በማያንስና ከአምስት ዓመት
6. በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከብር 60 ሺ. እስከ 100 ሺ. (ከብር ስልሳ ሺ. እስከ መቶ ሺ.) በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

7. ማንኛውም ሰው ከባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ካለዉ የክልል አካል ከተፈቀደለት ቦታ ውጪ ቡናን አከማችቶ የተገኘ እንደሆነ፣ የቡናው መወረስ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከሶስት ዓመት በማያንስና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከብር 60 ሺ እስከ 100 ሺ (ከብር ስልሳ ሺ እስከ መቶ ሺ) በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡
8. ማንኛውም ሰው ከባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ካለዉ የክልል አካል ከተፈቀደለት አድራሻና የጉዞ መስመር ውጪ ቡና ሲያጓጉዝ የተገኘ እንደሆነ፣ ቡናውና ተሽከርካሪው መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከሶስት ዓመት በማያንስና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከብር 60 ሺ እስከ 100 ሺ (ከብር ስልሳ ሺ እስከ መቶ ሺ) በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡
9. ማንኛውም ቡና ከቦታ ቦታ ለማጓጓዝ የተረከበ አሽከርካሪ የቡናው ፕሎምፕ ተበጥሶ ወይም ሸራ ተቀዶ ጥራቱና ዓይነቱ ተቀይሮ ወይም መጠኑ ተጨምሮ ወይም ተቀንሶ ወደ ተሸኘበት አካባቢ እንዲጓጓዝ ያደረገ እንደሆነ ከሶስት ዓመት በማያንስና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከብር 60 ሺ እስከ 100 ሺ (ከብር ስልሳ ሺ እስከ መቶ ሺ) በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡
10. ማንኛውም አሽከርካሪ እንዲጭን ከተፈቀደለት ቡና ውጪ በየትኛውም የተሽከርካሪው አካል ላይ ተጨማሪ ቡና ወይም ቡና ያልሆነ ሌላ ጭነት ወይም ምርት አዳብሎ የጫነ እንደሆነ፣ በተጨማሪነት የተጫነው ቡናና ሌላው ጭነት ወይም ምርት መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ ከስድስት ወር በማያንስና ከሶስት ዓመት በማይበልጥ እስራት እና ከብር 10 ሺ እስከ 30 ሺ (ከብር አስር ሺ እስከ ሰላሳ ሺ) በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡
11. ማንኛውም ሰው ሕገወጥ ቡና በመሸጥ፣ በመግዛት፣ በማከማቸትና ማዘጋጀት፣ በመቁላትና በመፍጨት፣ በማጓጓዝ ቡና እንዲሠወር ወይም እንዲበላሽ ያደረገ ወይም የተባበረ እንደሆነ ከአንድ ዓመት በማያንስና ከሦስት ዓመት በማይበልጥ እስራት እና ከብር 20 ሺ እስከ 40 ሺ (ከብር አስር ሺ እስከ አርባ ሺ) በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡
12. የታጠበ ቡና ማዘጋጃ ኢንዱስትሪዎች ባሉባቸዉ አካባቢዎች በባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ባለዉ የክልል አካል ሳይፈቀድ ቀይ እሸት ቡናን ለጀንፈል ቡና ዝግጅት የመግዛትና የማበጠር አገልግሎት የሰጠ ማንኛውም ሰው ከአንድ ዓመት በማያንስና ከሦስት ዓመት በማይበልጥ እስራት እና ከብር 10,000 እስከ 40,000 (ከብር አስር ሺ እስከ አርባ ሺ) በሚደርስ መቀጮይቀጣል፡፡

13. ማንኛውም በቡና ግብይት ለመሰማ ራት የብቃት ማረጋገጫ የተሰጠዉ ሰዉ ስራውን ለማከናወን የማያስችል ከአቅም በላይ የሆነ ችግር የገጠመው ስለመሆኑ አሳማኝ ማስረጃ ለባለስልጣኑ ወይም አግባብ ላለው ክልል አካል አቅርቦ ሳያስፈቅድ በውክልና ያሰራ እንደሆነ፣ የብቃት ማረጋገጫ ማስረጃው መሰረዝ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከአንድ ዓመት በማያንስና ከሦስት ዓመት በማይበልጥ እስራት እና ከብር ከብር 20 ሺ. እስከ 40 ሺ. (ከብር አስር ሺ. እስከ አርባ ሺ.) በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡
14. ማንኛውም ሰዉ በውጪ ንግድ ቡና ግብይትና ዝግጅት ላይ በዉክልና ለመስራት የሚያስችል ብቃት ያለው ስለመሆኑ በባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ላለው ክልል አካል ማረጋገጫ ሳይሰጠዉ ውክልና ይዞ በግብይት ላይ የተሰማራ እንደሆነ ከአንድ ዓመት በማያንስና ከሦስት ዓመት በማይበልጥ እስራት እና ከብር 20 ሺ. እስከ 40 ሺ. (ከብር ሀያ ሺ. እስከ አርባ ሺ.) በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡
15. ከመሸኛ ጣቢያ ሕጋዊ የሆነ ቡና ጭኖ ወደ ተሸኘበት ሕጋዊ ቡና ማዘጋጃ ኢንዱስትሪ ወይም የምርት ገበያ መጋዘን ወይም ወደብ ሳያደርስ ቡናው እንዲሰወር ወይም ሆን ብሎ መጠኑ እንዲቀንስ ወይም እንዲጨመር ወይም ጥራትና ዓይነቱ እንዲቀየር ያደረገ ማንኛውም አጓጓዥ፣ ከአምስት ዓመት በማያንስና ከአስር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከብር 100 ሺ. እስከ 200 ሺ. (ከመቶ ሺ. እስከ ሁለት መቶ ሺ.) በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡
16. ማንኛውም በባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ባለው የክልል አካል የተመደበ የሥራ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ ባለው የስራ ኃላፊነቱ ወይም ሰራተኛነቱ ያገኘውን ለህዝብ ያልተገለፀ የቡና ግብይትና ጥራት ማዛባት የሚችል መረጃ ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት የግል ጥቅም ለማግኘት ወይም ለሌሎች ለማስገኘት አሳልፎ የሰጠ ወይም እንዲሰጥ ያደረገ እንደሆነ ከአንድ ዓመት በማያንስና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ እስራት እና ከብር 20 ሺ. እስከ 40 ሺ. (ከብር ሀያ ሺ. እስከ አርባ ሺ.) በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

20. <u>በሕግ የሰውነት መብት በተሰጠው አካል ላይ ስለሚፈጸም ቅጣት</u>

በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል በወንጀል ሕግ አንቀጽ 34 በተመለከተው መሠረት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 19 በተመለከቱ ወንጀሎች ተካፋይ በሚሆንበት ጊዜ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 90 መሠረት ይቀጣል፡፡

**21.<u>የዳኝነት ሥልጣን</u>**

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 19 እና 20 በተመለከቱ የወንጀል ጉዳዮች የዳኝነት ስልጣን ይኖራቸዋል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የቡና የፍትሃብሔር ጉዳዮች የዳኝነት ስልጣን ይኖራቸዋል፡፡

**22.<u>የተሻሩና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች</u>**

1. የቡና ጥራት ቁጥጥር ግብይት አዋጅ ቁጥር 602/2000 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡
2. የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡

**23.<u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>**

1. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም በክርክር ላይ ያሉ ጉዳዮች በቀድሞው አዋጅ መሠረት ፍጻሜ ያገኛሉ፡፡
2. ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት የተሠጠ የብቃት ማረጋገጫ ሠርተፍኬት በዚህ አዋጅ መሠረት ሥልጣን ያለው አካል በሚሰጥ አዲስ የብቃት ማረጋገጫ ሠርተፍኬት እስከሚተካ ድረስ በዚህ አዋጅ እንደተሰጠ ይቆጠራል፡፡

**24.<u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>**

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ባለሥልጣኑ ለዚህ አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚወጣ ደንብ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡
3. ክልሎች ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ሕጎች ሊያወጡ ይችላሉ፡፡
4. በኢትዮጵያ ምርት ገበያ የሚፈፀም የቡና ግብይትን በተመለከተ ለዚህ አዋጅና በዚህ አንቀጽ (1) መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪዎችን የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ቦርድ እና የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን ሊያወጡ ይችላሉ፡፡

**25.<u>አዋጁ የሚፀናበት ቀን</u>**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ -------- ቀን ------2009 ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**ኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዝዳንት**

## ደንብ ቁጥር 433)2011

## የቡና ግብይት እና ጥራት ቁጥጥርን ለመደንገግ የወጣ ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላት ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 (እንደተሻሻለ አንቀጽ 5 እና በቡና ግብይት እና ጥራት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1051/2009 አንቀጽ 24 (1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የቡና ግብይት እና ጥራት ቁጥጥር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 433)2011" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

   1. "አዋጅ" ማለት የቡና ግብይትና ጥራት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1051/2009 ነው፤
   2. "የቡና ክምችት ሚዛን" ማለት ማንኛውም በቡና ማምረት ወይም በንግድ ሥራ የተሠማራ ሰው ያመረተውን ወይም የገዛውን ቡና በማዘጋጀት ለገበያ ያቀረበውን እና በመጋዘን ሊገኝ የሚገባው ቀሪ ክምችት ተሰልቶ የሚገኝ ውጤት ነው፤
   3. "የቡና ናሙና" ማለት ማንኛውም ቡና በሀገር ውስጥ ግብይት እንዲካሄድበት ወይም ወደ ውጭ ከመላኩ በፊት የቡናውን ዓይነትና የጥራት ደረጃ ለመወሰን የሚወሰድ ወካይ ቡና ነው፤
   4. "ጥብቅ የቡና መጋዘን" ማለት ባለሥልጣኑ በሚሰጠው ፈቃድ መሠረት የውጭ ቡና ገገርዎች የገዙትን ወጪ ቡና በሀገር ውስጥ ተረክበው ለተወሰነ ጊዜ የሚያቆዩበት ደህንነቱ የተጠበቀ መጋዘን ነው፤
   5. "የቡና ምርት ዘመን" ማለት የቡና ምርት ከተሰበሰበበት ጊዜ ጀምሮ የአንድ ዓመት ጊዜ ነው፤

6. "የቡና ምርት ግብይት ዘመን" ማለት በተለየ ሁኔታ በባለሥልጣኑ ካልተራዘመ በስተቀር የቡና ምርት ከተሰበሰበበት ጊዜ ጀምሮ የአንድ ዓመት የግብይት ጊዜ ነው፤
7. "የአምራችና ኢንዱስትሪ ትስስር" ማለት በቡና አምራችና በወጪ ቡና ቆይ ኢንዱስትሪዎች መካከል በውል የሚፈጸም የቡና ማምረትና ሽያጭ አሠራር ነው፤
8. "የቡና ምርት ዱካ" ማለት የቡና ምርት ከተመረተበት ጀምሮ እሴት ሰንሰለቱን ተከትሎ ታሪኩን የሚገልጽ መለያ ሰነድ ነው፤
9. "የቡና መሸኛ" ማለት በባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ባለው የክልል አካል የተዘጋጀ አስፈላጊው መረጃ የተሞላበት፣ የተፈረመበትና የመንግሥት ማህተም ያረፈበት የይለፍ ሰነድ ነው፤
10. የአቅርቦት ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ" ማለት አግባብ ያለው የክልል አካል የሚያወጣውን የቴክኒክ መስፈርት አሟልቶ የቀይ እሸት ቡና ተፈልፍሎና ታጥቦ የታጠበቡና ከነገለፈቱ የሚዘጋጅበትና የሚከማችበት እንደሁም ጀንፈል ቡና ተቀሽሮ፣ተለቅሞ ያልታጠበ የአቅርቦት ቡና የሚዘጋጅበትና የሚከማችበት በቡና አመራች አካባቢ የተቋቋመ ኢንዱስትሪ ነው፤
11. "የወጪ ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ" ማለት ባስልጣኑ የሚያወጣውን የቴክኒክ መስፈርት አሟልቶ ከነገለፈቱ ያለውን የታጠበ ቡናን ገለፈቱን በማስወገድ የታጠበቡና ተበጥሮና ተለቅሞ ለወጪ ገበያ የሚዘጋጅበትና የሚከማችበት እንዲሁም ያልታጠበ አቅርቦት ቡና ተበጥሮና ተለቅሞ ለውጪ ገበያ የሚዘጋጅበትና የሚከማችበት ኢንዱስትሪ ነው፤
12. "ለግብይት የሚቀርብ የቡና ቅጠል" ማለት በቡና አምራቾች ተሰብስቦ ለገበያ የሚቀርብ ቡና ለተክሉ ተፈጥሯዊ አግልግሎቱን ያጠናቀቀ የቡና ቅጠል ነው፤
13. በአዋጁ አንቀጽ (2 የተመለከተው ትርጓሜ ለዚህ ደንብም ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

3. <u>**የተፈጻሚነት ወሰን**</u>

ይህ ደንብ በኢትዮጵያ የቡና ግብይትና ጥራት ቁጥጥር ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በሚሳተፍ ማንኛውም ሰው ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የቡና ግብይት አሠራር

4. **የቀይ እሸትና የጀንፈል ቡና ግብይት**

ማንኛውም የቀይ እሸት እና የጀንፈል ቡና ግብይት የሚከናወነው፡-

1. የቡና አምራች አርሶ አደሮች ከግል ቡና አቅራቢዎች ወይም ከመሠረታዊ ህብረት ሥራ ማህበራት ጋር በተፈቀደ የታጠበ እና ያልታጠበቡና ማዘጋጃ ኢንዱስትሪዎች፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የቡና ማዘጋጃ ኢንዱስትሪዎች ተደራሽ ባልሆኑባቸው ወይም በሌሉባቸው አካባቢዎች በሚቋቋሙ በመጀመሪያ ደረጃ ቡና ግብይት ማዕከላት፤
3. የቡና ልማትና ግብይት ትስስር በፈጠሩ ቡና አምራች አርሶ አደሮችና አልሚ ባለሃብቶች መካከል በውል ስምምነቱ በተገለጸ ቦታ፤ እና
4. የወጪ ቡና ቆዩ ኢንዱስትሪዎች ከቡና አምራች አርሶ አደሮች ጋር በምርትና ግብይት ውል ስምምነቱ በተገለጸው ቦታ ነው፡፡

5. የአቅርቦትና ተረፈ ምርት ቡና ግብይት

1. የአቅርቦት ቡና ግብይት በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም በሌሎች አማራጭ የቡና ግብይት ሥርዓት ብቻ ይከናወናል፣
2. ማንኛውም ተረፈ ምርት ቡና ግብይት የሚካሄደው በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ብቻ ነው፡፡
3. በኢትዮጵያ ምርት ገበያ የሚካሄድ የቡና ግብይት፡-
   ሀ) ቡና አቅራቢ ወይም ቡና አምራች የአቅርቦት ወይም የሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና ብቻ በመሸጥ፣
   ለ) ቡና ላኪ ለወጪ ገበያ የሚሆን የአቅርቦት ቡና በመግዛትና ተረፈ ምርት ቡና ብቻ በመሸጥ፣
   ሐ) የወጪ ቡና ቆይ የአቅርቦት ቡና ወይም የሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና በመግዛትና ተረፈ ምርት ቡናን ብቻ በመሸጥ፣
   መ) የሀገር ውስጥ ቡና ጅምላ ነጋዴ የሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና ወይም ተረፈ ምርት ቡናን ብቻ በመግዛት፣ እና
   ሠ) የሀገር ውስጥ ቡና ቆይ የሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና ወይም ተረፈ ምርት ቡናን ብቻ በመግዛት፤ ይከናወናል፡፡

4. ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም ከሌሎች የግብይት አማራጮች የተገዛ የአቅርቦት ቡና በድጋሚ በሀገር ውስጥ ሊሸጥ አይችልም፤
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ቡና ላኪ የቡና ላኪነት ሥራውን ያቋረጠ ከሆነ ወይም የውጭ ገበያ ማጣቱን አሳማኝ ማስረጃ ያቀረበ ከሆነ ወይም ከውጪ ገበያ ሽያጭ ተርፎ ሳይላክ የቀረ አነስተኛ መጠን ያለው ቡና መኖሩ ሲረጋገጥ በባለሥልጣኑ ልዩ ፈቃድ ብቻ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም በስምምነት በሌላ ቡና ላኪ በውጭ ገበያ ሊሸጥ ይችላል፡፡
6. ቡና አምራች አርሶ አደሮች ያመረቱትን የአቅርቦት ወይም ተረፈ ምርት ቡናን አግባብ ባለው የክልል አካል ተረጋግጦ ንግድ ፈቃድ ሳይጠየቁ በሚሰጣቸው ልዩ ፈቃድ ብቻ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ መሸጥ ይችላሉ፡፡

6. <u>አማራጭ የቡና ግብይትና አሠራር</u>

1. ቡና ላኪ ወይም የወጪ ቡና ቆዪ ከቡና አቅራቢ ወይም ከቡና አልሚ ባለሃብት ጋር የቀጥታ የአቅርቦት ቡና ግብይት ትስስር የሚፈጥረው፡-
   ሀ) በተዋዋይ ወገኖች መካከል ቢያንስ ለሁለት ዓመት የሚቆይ ስልጣን ባለው አካል የተመዘገበ የውል ስምምነት ሲኖር፣
   ለ) የተመዘገበው ውል በአስራ አምስት የስራ ቀናት ውስጥ ለባለስልጣኑ ቀርቦ የጸደቀና በሦስት የስራ ቀናት ውስጥ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ቀርቦ የተመዘገበ ሲሆን፣
   ሐ) በውል ስምምነቱ የርክክብ ቦታው የተገለጸና የርክክብ ጊዜው የምርት ዘመኑ ሳያልፍ ስለ መሆኑ በግልጽ የተጠቀሰ ከሆነ፣
   መ) የተዋዋይ ወገኖች የግብይት ዋጋ ስምምነቱ በቡና ጥራትና ደረጃ ምደባ ማዕከል የቡናው ጥራት ደረጃ በተሰጠበት ቀን በኢትዮጵያ ምርት ገበያው በሚኖር ተመሳሳይ ዓይነትና ደረጃ ያለው ቡና አማካይ ዋጋ በላይ ከሆነና ጭማሪውም በመቶኛ በውሉ የተገለጸ ከሆነ፣
   ሠ) ቡና አቅራቢው ወይም ቡና አልሚ ባለሃብቱ ከሚያዘጋጀው ቡና ከ75 በመቶ (ከሰባ አምስት በመቶ) በላይ ጥራቱ ከደረጃ አንድ እስከ ደረጃ አራት በማድረግ ለማስረከብ በውሉ የተስማማ ከሆነ፣
   ረ) ቡና ላኪው ወይም የወጪ ቡና ቆይ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከተመዘገበው ተመሳሳይ የቡና ዓይነት፣ደረጃ እና መዳረሻ ገበያ አማካይ ዋጋ በላይ በውጭ ገበያ ለመሸጥ የተስማማ ከሆነ፣

ሰ) ሁለቱም ወገኖች በውል አፈጻጸም ላይ አለመግባባት ቢከሰት በድርድር ወይም አግባብ ባለው ፍርድ ቤት ለመዳኘት መስማማታቸው በውሉ የተገለጸ ከሆነ፣ እና

ሸ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ሥር ከፊደል ተራ (ሀ) እስከ (ረ) የተመለከቱ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው የተለየ የገበያ ዕድል ወይም የተሻለ ዋጋ ለማግኘት ከሴት ቡና አምራች፣ከሴት ቡና ላኪ ወይም ከሴት የውጪ ቡና ቆዪ ጋር በቀጥታ የቡና ግብይት ለመፈጸም በውል የተስማሙ ከሆነ፤ ነው፡፡

2. ቴቡና አቅራቢ የወጪ ገበያ ቡናን በቀጥታ ወደ ውጭ ሀገር መላክ የሚችለው፡-

ሀ) ከቡና አቅራቢነት በተጨማሪ የቡና አቅራቢ፣ ላኪነት የብቃት ማረጋገጫና የቡና ላኪነት የንግድ ፈቃድ ካለው፤

ለ) በራሱ ኢንዱስትሪ ከሚያዘጋጀው ቡና ከ75 በመቶ (ከሰባ አምስት በመቶ) በላይ የሚሆነው ጥራቱ ከደረጃ አንድ እስከ ደረጃ አራት ከሆነና ዱካውን ጠብቆ ወደ ውጭ ገበያ ለመላክ ከተስማማ፤ እና

ሐ) በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከሚመዘገበው ተመሳሳይ የቡና ዓይነት፣ ደረጃ እና መዳረሻ ገበያ አማካይ ዋጋ በላይ በውጭ ገበያ ለመሸጥ ከተስማማ ነው፡፡

3. ቡና አምራች አርሶ አደር በቀጥታ ቡናን ለውጭ ገበያ መላክ የሚችለው:-

ሀ) የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ያለው፣ በቡና የተሸፈነ መሬት መጠንና በየዓመቱ የሚመረተውን የቡና ምርት ግምት ማስረጃ አግባብ ካለው የክልል አካል የሚያቀርብ ከሆነ፣

ለ) የአቅርቦት እና የወጪ ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ ያለው ወይም የኪራይ ውል ያለው ስለ መሆኑ የሚያቀርብ ከሆነ፣

ሐ) በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የቡና አምራች አርሶ አደሮች በተመሳሳይ ጊዜ ካስመዘገቡት ተመሳሳይ የቡና ዓይነት፣ ደረጃ እና መዳረሻ ገበያ ሽያጭ ተመጣጣኝ በሆነ ዋጋ ለመሸጥ ከተስማሙ፣ እና

መ) ከማሳው ያመረተውን ቡና ብቻ ለመላክ ንግድ ፈቃድ ሳያስፈልገው ከባለሥልጣኑ ቡና የመላክ ልዩ ፈቃድ የተሰጠው ከሆነ፤ ነው፡፡

4. ቡና አልሚና ላኪ ባለሃብት በቀጥታ ቡናን በውጭ ገበያ መላክ የሚችለው:-

ሀ) የኢንቨስትመንት ፈቃድ፣ የመሬት ኪራይ ውል፣ በቡና የተሸፈነ መሬት መጠንና ዓመታዊ የቡና ምርት ግምት አግባብ ካለው የክልል አካል ማስረጃ ካቀረበ፣

ለ) ከቡና አምራች አርሶ አደሮች ጋር የልማትና ግብይት ትስስር የፈጠረ እና ስለዚህ ሁኔታ አግባብ ካለው የክልል አካል ማስረጃ ካቀረበ፣

ሐ) የአቅርቦት እና የወጪ ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ ያለው ወይም የኪራይ ውል ያለው ስለመሆኑ የሚያቀርብ ከሆነ፣ እና

መ) ቡና አልሚና ላኪ ባለሃብቶች በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በተመሳሳይ ጊዜ ካስመዘገቡት ተመሳሳይ የቡና ዓይነትና ደረጃ የመዳረሻ ገበያ አማካይ ዋጋ እና በላይ በውጭ ገበያ ለመሸጥ የተስማሙ ከሆነ፤ ነው፡፡

5. የወጪ ቡና ቆይ በአምራችና ኢንዱስትሪ ትስስር ቡና ገዝቶ ወደ ውጭ መላክ የሚችላው፡-

ሀ) ቀይ እሸት ወይም ጀንፈል ቡና ከአምራች አርሶ አደሮች በአምራችና ኢንዱስትሪ ትስስር ከገዛ፣

ለ) የገዛውን ቡና የጥራት ደረጃና የምርት ዱካ ጠብቆ ቆልቶ ወይም ቆልቶና ፈጭቶ ወደ ውጭ ለመላክ ከተስማማ፣ እና

ሐ) የወጪ ቡና ቆይዎች በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በተመሳሳይ ጊዜ ካስመዘገቡት የቡና ዓይነትና ደረጃ መዳረሻ ገበያ አማካይ ዋጋ በላይ በውጭ ገበያ ለመሸጥ የተስማሙ ከሆነ፣ ነው፡፡

7. <u>የልዩ ቡና ዝግጅትና ግብይት አሰራር</u>

1. የልዩ ቡና ዝግጅትና ግብይት የሚፈጸመው፡-

ሀ) ቀይ እሸት ወይም ጀንፈል ቡና ለልዩ ቡና ዝግጅት ግብዓትነት ለመጠቀምም ሆነ ለማዘጋጀት የባለሥልጣኑን የቴክኒክ መስፈርትና የጥራት ደረጃ ያሟላ ከሆነ፣

ለ) ማንኛውም ቡና አቅራቢ ወይም አምራች ያልታጠበ ልዩ ቡና ለማዘጋጀት አግባብ ካለው የክልል አካል የብቃት ማረጋገጫና ፈቃድ ያገኘ ከሆነ፣

ሐ) የልዩ ቡና የግዢ፣ የዝግጅት፣ የክምችትና የሽያጭ መረጃ በተለየ መልኩ ሲይዝና ሊቀርብ የሚችል ከሆነ፣ እና

መ) በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም በአማራጭ ግብይት ሲፈጸም ልዩ ቡና ተብሎ ከተመዘገበ፣ ነው፡፡

2. ማንኛውም ቡና አቅራቢ ለልዩ ቡና ዝግጅት ከቡና አምራች አርሶ አደሮች ጋር የልዩ ቡና ልማትና ግብይት የትስስር ውል ሲያደርግ፡-
   ሀ) ለቡና አምራች አርሶ አደሮቹ ምርትና ምርታማነትን የሚያሳድጉና ጥራትን የሚያሻሽሉ የኤክስቴንሽን ድጋፍና ቴክኖሎጂ ለማቅረብ መስማማት፤
   ለ) ለቡና አምራች አርሶ አደሮቹ የኤክስቴንሽን ድጋፍ ለመስጠት አግባብ ያለው ባለሙያ በቅጥር ለማሠማራትና የቴክኖሎጂ ድጋፍ ለማድረግ አቅም ያለው ስለመሆኑ አግባብ ካለው የክልል አካል ማስረጃ ማቅረብ፤
   ሐ) ከቡና አምራች አርሶ አደሮቹ ከተረከበው ቡና ከ90 በመቶ (ከዘጠና በመቶ በላይ በልዩ ቡናነት ለማዘጋጀት መስማማት፣ እና
   መ) ለልዩ ቡና ዝግጅት ለሚረከበው ቡና ከአካባቢው ገበያ ዋጋ በላይ ለመክፈል መስማማት አለበት፡፡

8. <u>ከውጭ ሀገር ስለሚገባ ጥሬ ቡና</u>
   1. ከውጭ ሀገር ቡና ለማስገባት የሚቻለው፡-
      ሀ) ጥሬ ቡናን ከውጭ ሀገር ማስገባት የሚኖረው ሀገራዊ ፋይዳ በጥናት ሲረጋገጥ፣
      ለ) ከውጭ ሀገር ተፈቅዶ የሚገባው ጥሬ ቡና የተመረተበት ሀገር የተገለጸ እና ሀገራዊ የዕጽዋት ጤና ማረጋገጫ መስፈርት ሲያሟላ፣
      ሐ) ከውጭ የሚገባው ጥሬ ቡና የተፈቀደለትን የጉዞ መስመር፣መጋዘንና ኢንዱስትሪ ብቻ የሚጠቀም ከሆነ፣
      መ) ከሀገራችን ቡና ጋር በሚታወቅ ምጣኔ ተቀይጦ በተቆላ ወይም ተቆልቶ በተፈጨ ወይም በሌላ መልኩ እሴት ተጨምሮ ሙሉ በሙሉ ወደ ውጭ ገበያ የሚላክ ከሆነ፣ ነው፡፡
   2. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ከውጭ ለሚገባ ጥሬ ቡና ልዩ የጉምሩክ ማስተናገጃ ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

9. <u>ለውጪ ገበያ የተዘጋጀ ቡና በሀገር ውስጥ ስለመሸጥ</u>

   ለውጪ ገበያ በተቆላ ወይም ተቆልቶ በተፈጨ ወይም በሌላ መልኩ የተዘጋጀ ቡና በሀገር ውስጥ ግብይት የሚፈጸመው፡-
   1. የውጪ ቡና ቆዪ ለሀገር ውስጥ ግብይት ከባለሥልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ የተሰጠው እና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተመዘገ በከሆነ፤

2. ሽያጩ በባለሥልጣኑ ተለይተው በሚፈቀዱ አህጉርና አለም አቀፍ ኩነቶች ማካሄጃ፣ የውጪ ሀገር ጎብኚዎች መንገደኞች መተላለፊያና ማዘውተሪያ ቦታ ከሆነ፤
3. በአሜሪካ ዶላር ወይም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በተፈቀደ የውጭ ሀገር ገንዘብ ብቻ ሲፈጸም፤
4. በእሽጉ ላይ የቡናው ዓይነት፣ ስያሜ፣ የንግድ ምልክት፣የተመረተበት ሀገር እና ለውጭ ገበያ የተዘጋጀ በሚል ከተጻፈበት፤
5. የተሸጠው ቡና ዓይነት፣ መጠን፣የገንዘቡ ልክ በውጭ ምንዛሪና መሸጫ ቦታው ተገልጾ በሻጩ ለገዥው ደረሰኝ ሲሰጥ፤ እና
6. በየወሩ መጨረሻ ዝርዝር የቡና ግዢ እና ሽያጭ መግለጫ በሻጩ ተዘጋጅቶ በብሔራዊ ባንክ የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ ሲወራረድ እና ይኸው ለባለሥልጣኑ በሻጩ ሪፖርት ከተደረገ፤ ነው፡፡

10. <u>የቡና ገለባና ቅጠል የግብይት አሠራር</u>

1. ቡና አምራች፣ የቡና ገለባ አቀነባባሪ፣ የቡና ቅጠል አቀነባባሪ ወይም ቡና ላኪ የቡና ገለባ ወይም የቡና ቅጠል በባለስልጣኑ ፈቃድ በቀጥታ ወደ ውጪ መላክ ይችላል፡፡
2. የቡና ገለባ ግብይት የሚፈጸመው ከቡና አምራች ወይም ከቡና አቅራቢ ከቡና ገለባ አቀነባባሪ ወይም ከቡና ላኪ ጋር በሚደረግ ድርድር ይሆናል፡፡
3. ለቡና ተክሉ ተፈጥሯዊ አገልገሎቱን ያጠናቀቀ የቡና ቅጠል ግብይት የሚፈጸመው ከቡና አምራቾች እና ፈቃድ ከተሰጣቸው የቡና ቅጠል አቀነባባሪዎች ወይም ከቡና ላኪዎች ጋር በድርድር ነው፡፡
4. ለሽያጭ የሚውለው የቡና ገለባ በውስጡ ያለው የቡና ፍሬ መጠን ከአንድ በመቶ መብለጥ የለበትም፡፡
5. ማንኛውም የቡና ገለባ ወይም የቡና ቅጠል ከቦታ ወደ ቦታ ለማዘዋወር ከባለስልጣኑ ወይም አግባብ ካለው የክልል አካል የተሰጠ መሸኛ መያዝ አለበት፡፡
6. ማንኛውም የቡና ገለባ ወይም የቡና ቅጠል በተቀነባበረ ወይም በጥሬው ወደ ውጭ የሚላክ ከሆነ የሽያጭ ውል ስምምነት ከተደረገ በኋላ በ24 ሰዓት ውስጥ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ቀርቦ መጽደቅ እና በሦስት የሥራ ቀናት ለባለሥልጣኑ ቀርቦ መመዝገብ አለበት፡፡

7. በማንኛውም መልክ ወደ ውጭ የሚላክ የቡና ገለባ ወይም የቡና ቅጠል የአዘገጃጀትና ጥራት ምርመራ የምስክር ወረቀት መሸኛ ያገኘ መሆን አለበት፡፡

11.<u>የወጪ ቡና የሽያጭ ውልና አሠራር</u>

1. ማንኛውም ለውጭ ገበያ ቡናን የሚያቀርብ ሰው ስለቡና ገገርው ህጋዊነት አረጋግጦ የሽያጭ ውል መፈጸም አለበት፡፡
2. የወጪ ቡና ሽያጭ ውል ሲፈጸም የገገርው ፍላጎት እንደተጠበቀ ሆኖ የውሉ ሰነድ፡-
   ሀ) የቡና ሻጭ እና ገገር ሙሉ ስም እና የሚገኝበት አድራሻ፣
   ለ) የቡናውን ዓይነት፣ መጠን፣ የጥራት ደረጃ፣ እና ውሉ የሚፈጸምበት ጊዜ እና የተሸጠበትን ዋጋ በአሜሪካ ዶላር፣ እና
   ሐ) ሌሎች አግባብነት ያላቸው የውል ቃሎችን መያዝ ያለበት ሲሆን ከውሉ ጋር አስፈላጊ ሰነዶች ተሟልተው ውሉ በተፈጸመ በ24 ሰዓት ውስጥ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ቀርቦ መጽደቅና በሦስት የሥራ ቀናት ውስጥ ለባለስልጣኑ ቀርቦ መመዝገብ አለበት፡፡
3. የወጪ ቡና ሽያጭ ውል መፈጸሚያ ጊዜ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ከ90 ተከታታይ ቀናት መብለጥ የለበትም፡፡
4. ማንኛውም የወጪ ቡና ላኪ የሽያጭ ሂሳብ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማወራረድ አለበት፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3 የተጠቀሰው ቢኖርም ቡና ላኪው ቡና አምራች ከሆነ የውሉ መፈጸሚያ ጊዜ ከዘጠኝ ወራት ያልበለጠ ሆኖ ባመረተው ወይም በሚያመርተው የቡና ምርት ዓይነትና መጠን ልክ እስከ ቡና ምርት ዘመኑ መጨረሻ ድረስ ሊሆን ይችላል፡፡
6. ማንኛውም የወጪ ቡና ሽያጭ በውሉ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ፣ ጥራት፣ መጠን፣ ዋጋና ሁኔታ መሠረት መፈጸም አለበት፡፡
7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6 የተደነገገው ቢኖርም ውሉን ለመፈጸም የማያስችል አስገዳጅ ያልታሰበ ሁኔታ ስለመኖሩ በማስረጃና በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች ስምምነት ከቀረበ ባለሥልጣኑ የውል ጊዜው እንዲራዘም ወይም ዋጋ በመጨመር ውሉ እንዲሻሻል ወይም ወደ ሌላ ላኪ እንዲተላለፍ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

8. ማንኛውም ቡና ላኪ ያለበቂ ምክንያት፣የተዋዋለውን የሽያጭ ውል በሙሉ ወይም በከፊል በተለይ በጊዜ ገደቡ ወይም በጥራት ወይም በሁለቱም ያለመፈጸሙ ሲረጋገጥ በዚህ ደንብና አግባብነት ባላቸው ህጎች አስተዳደራዊ እና ህጋዊ እርምጃ ይወሰዳል፣
9. ውሉን ያልፈጸመ የውጭ ሀገር ቡና ገዥ ሲኖር በውጭ ሀገር ባሉ የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች አማካይነት በድርድር እንዲፈታ ይደረጋል ወይም አግባብነት ባለው ህግ እርምጃ ይወሰዳል፡፡
10. ማንኛውም ቡና ላኪ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከሚወሰነው አማካይ ዋጋ ዝቅተኛ ህዳግ በታች ወይም ብሔራዊ ጥቅምን የሚያሳጣ ተደጋጋሚ የሽያጭ ውል ማስመዝገቡ ሲረጋገጥ በዚህ ደንብና አግባብነት ባላቸው ህጎች አስተዳደራዊ እና ህጋዊ እርምጃ ይወሰዳል፡፡
11. ማንኛውም ቡና አምራች ወይም ቡና ላኪ የኢትዮጵያን ቡና ልዩ ተፈጥሯዊ ጣዕምና ባህሪይ ለማስተዋወቅና የተሻለ ዋጋ ለማስገኘት በውጭ ሀገር የተጠቃሚ ገበያ በቀጥታ ወይም በህጋዊ ሽርክና በገበያ ለመሳተፍ የፈለገ እንደሆነ ሀገራዊ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳው በጥናት ተረጋግጦ ባለሥልጣኑ ሊፈቀድ ይችላል፡፡

12. <u>ለውጭ ሀገር ገዢ የውጪ ቡናን በሀገር ውስጥ ስለማስረከብ</u>

1. ለውጭ ሀገር ቡና ገዢ የተሸጠ የውጪ ቡና በሀገር ውስጥ ርክክብ እንዲፈጸምና ለተወሰነ ጊዜ እንዲከማች ሀገራዊ ፋይዳው በጥናት ሲረጋገጥ በባለሥልጣኑ ሊፈቀድ ይችላል፡፡
2. ማንኛውም የውጭ ሀገር ቡና ግዢ በሀገር ውስጥ የቡና ርክክብ የሚፈጽመው አስቀድሞ በውል ስምምነቱ ከተገለጸነው፡፡
3. የውጭ ሀገር ቡና ገዢ በሀገር ውስጥ የወጪ ገበያ ቡናን ከተረከበበት ቀን ቀጥሎ ባሉት ሦስት የሥራ ቀናት ውስጥ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በተመዘገበ የሽያጭ ውል መሠረት ክፍያ መፈጸም አለበት፡፡
4. የውጭ ሀገር ቡና ገዥ በሀገር ውስጥ የተረከበውን ቡና አስፈላጊውን የሎጀስቲክና የሽኝት ሥነሥርዓት አጠናቆ ወደ ወደብ ሊያጓጓዝ ወይም በተፈቀደለት ጥብቅ የቡና ማከማቻ መጋዘን እስከ ሦስት ወራት አከማችቶ ሊያቆይ ይችላል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (4 የተደነገገው ቢኖርም ማንኛውም የውጭ ሀገር ቡና ገዢ ቡናውን ወደ ወደብ ማጓጓዝ የሚችለው ከባለሥልጣኑ በጽሁፍ የተረጋገጠ ፈቃድ እና የጉምሩክ ሽኝት አገልግሎት ሲያገኝ ብቻ ነው፡፡
6. በማናቸውም ምክንያቶች የውጪ ሀገር ቡና ገዥ የተረከበውን ቡና በሀገር ውስጥ መልሶ መሸጥ አይችልም፡፡

## ክፍል ሦስት

## የቀይ እሸት እና ጀንፈል ቡና መገበያያ ስፍራ እና አስተዳደር

### 13. የመገበያ ያስፍራ እና አሰራር ስለመወሰን

1. አግባብ ያለው የክልል አካል የቀይ እሸትና የጀንፈል ቡና መገበያያ ስፍራን፣ ወሰንን፣ ብዛትንና ስርጭትን ይወስናል፣ ይከልላል፣ የአስተዳደር ሥርዓት ይዘረጋል፡፡
2. አግባብ ያለው የክልል አካል የመገበያ ያስፍራ፣ ወሰን፣ ብዛትና ስርጭት ሲወስንና ሲከልል፡-
   ሀ) የቡና አምራች አርሶ አደሮችን ብዛት፣
   ለ) በቡና የተሸፈነ ማሳመጠንን፣
   ሐ) የህዝቡን አሰፋፈርና የመሬቱን አቀማመጥ፣
   መ) ለአምራች አርሶ አደሮች የቡና ምርታቸውን ለማቅረብ ያላቸውን አንጻራዊ ቀረቤታና ለተገበያዮቹ የግብይት እንቅስቃሴ አመቺነት፣ እና
   ሠ) የቡና ጥራትን ለማስጠበቅ የሚኖራቸውን አስተዋጽኦ፤ ከግምት ውስጥ መግባት ይኖርበታል፡፡
3. የአቅርቦት ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ ለቀይ እሸትና ጀንፈል ቡና መገበያያነት እንዲያገለግል የተወሰነ ከሆነ ለግብይት የተለየ ቦታ፣የቡና ጥራት ጉድለት መልቀሚያ አልጋ፣ ለጋማ ከብቶች ማቆያ የተለየ ቦታ፣ ዕለታዊ የቡና ገበያ ዋጋ ማሳወቂያ ሠሌዳ፣የደረቅ ቆሻሻ ማቃጠያ እና መፀዳጃ ቤት ማሟላት አለበት፡፡
4. የአቅርቦት ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ ተደራሽ ባልሆኑባቸው ወይም በሌሉባቸው አከባቢዎች ለቀይ እሸትና ጀንፈል ቡና መገበያያነት እንዲያገለግል የተወሰነው የመጀመሪያ ደረጃ ቡና ግብይት ማዕከል ከሆነ፡-
   ሀ) ለቡና አምራች አርሶ አደሩ ቀረቤታ፣

ለ) ለግብይቱ የሚሆን ቢያንስ 50 ሜትር በ50 ሜትር ስፋት ያለው የታጠረ ቦታ፣

ሐ) የቡና ጥራት ጉድለት መልቀሚያ አልጋ፣

መ) ለጋማ ከብቶች ማቆያ የተለየ ቦታ፣

ሠ) ዕለታዊ የቡና ገበያ ዋጋ ማሳወቂያ ሠሌዳ፣

ረ) ደረቅ ቆሻሻ ማቃጠያ እና መፀዳጃ ቤት፣ እና

ሰ) በእያንዳንዱ ቡና አቅራቢ ስም ወለሉ በሲሚንቶ የተሠራ የምርት ግዢ መፈፀሚያ ክፍል፣ ያለው መሆን ይኖርበታል፡፡

5. ቡና አምራች አርሶ አደር የተሻለ የቡና ዋጋ በሚያስገኝለት ኢንዱስትሪ ወይም የመጀመሪያ ደረጃ ገበያ መርጦመሸጥ ይችላል፡፡

6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም በልማትና ግብይት የተሳሰሩ አልሚ ባለሃብቶች እና በአምራችና ኢንዱስትሪ የሚተሳሰሩ የወጪ ቡና ቆዩ ኢንዱስትሪዎች ከቡና አምራች አርሶ አደሮች የሚረከቡት ቀይ እሸት ወይም ጀንፈል ቡና በውል ስምምነታቸው በተገለጸው ስፍራ ይሆናል፡

7. አግባብ ያለው የክልል አካል የቀይ  እሸትና ጀንፈል ቡና መገበያ ያስፍራ በቡና ጥራትና ግብይት ሂደቱ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ከሚያሳድሩ ነገሮች ነፃ መሆኑን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ እርምጃ ይወስዳል፡፡

14. የቀይ እሸት እና የጀንፈል ቡና ግብይት ወቅት

1. በአቅርቦት ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪም ሆነ በመጀመሪያ ደረጃ የቡና ግብይት ማዕከላት ግብይቱ የሚጀምርበትና የሚጠናቀቅበት ወቅት አግባብባ ለው የክልል አካል ይወሰናል፡፡

2. በአቅርቦት ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪዎች ሆነ በመጀመሪያ ደረጃ የቡና ግብይት ማዕከላት የሚፈጸመው ግብይት ወይም በውል ስምምነት መሰረት የሚፈጸም ርክክብ ከጠዋቱ 3 ሰዓት እስከ ምሽቱ 12 ሰዓት ብቻ መሆን ይኖርበታል፤

## ክፍል አራት

## የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት

15. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አስፈላጊነት የአዋጁ አንቀጽ8(1 ድንጋጌ እንደ ተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ሰው የቡና ግብይትን ለማከናወን፣ ቡናን ለማዘጋጀት፣ ለማከማቸት፣ እሴት ለመጨመር፣ ለማሸግ፣ ለማጓጓዝ እና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸው አገልግሎቶችን ለመስጠት  በዚህ ደንብ መሰረት የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያለው መሆን ይኖርበታል፡፡

## ንዑስ ክፍል አንድ

## ስለ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ዓይነቶችና መስፈርቶች

16. <u>የቡና ልማትና ግብይት ትስስር ለሚፈጥር አልሚና ላኪ የሚሰጥ የብቃት ማረጋገጫ</u>

ማንኛውም ሰው ለቡና አልሚና ላኪ የልማትና ግብይት ትስስር ለመፍጠር የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው፡-

1. የቡና ልማት ኢንቨስትመንት ፈቃድ እና የመሬት ሊዝ ውል ያለው፤
2. በቡና የተሸፈነ መሬትና ዘመናዊ  የቡና ልማት በማካሄድ  የተሻሻለ ምርታማነትና የምርት ጥራት ደረጃ ስለመድረሱ ማስረጃ ያለው፤
3. ለአምራች አርሶአደሮች ዘመናዊ የቡና አመራረት ዘዴ ለማስፋፋት የቡና ዕውቀትና ክህሎት ያለውን ባለሙያ ማሰማራቱን የሚገልጽ ማስረጃ ያለው፤
4. ለአምራች አርሶአደሮች ዘመናዊ የኤክስቴንሽን አገልግሎት ድጋፍ እና የተሻሻሉ ግብዓቶችን በማቅረብ ምርታማነትና የምርት ጥራት ለማሻሻል የተስማማ፤
5. ከአምራች አርሶአደሮች ለሚረከበው ቡና ከአካባቢው ወቅታዊ የገበያ ዋጋ የተሻለ ለመክፈል የተስማማ፤
6. ከቡና አልሚ ባለሃብት ማሳ ኩታገጠም ወይም በቅርብ ርቀት የሚገኙ ቡና አምራች አርሶአደሮችን ዝርዝርና በእያንዳንዱ አርሶአደር በባለቤትነት የተመዘገበበቡና የተሸፈነ ማሳ መጠንና ከዚሁ የሚገኝ ዓመታዊ የምርት መጠን የሚገልጽ ማስረጃ እና አርሶአደሮቹ ስለመብትና ግዴታቸው ተወያይተው የተፈራረሙበት የቃለጉባኤ ሰነድ ያለው፤እና
7. በባለቤትነት የተያዘ ወይም በተመዘገበ የኪራይ ውል ያገኘው የቡናማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ ያለው ስለመሆኑ ማስረጃ ያለው ፣መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡

17. **የቡና አቅራቢነት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት**

ማንኛውም ሰው የቡና አቅራቢነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው፡-

1. በህግ ሰውነት የተሰጠው አካል ሲሆን የሥራ አድራሻ ያለው፤የተፈጥሮ ሰው ከሆነ ቋሚ ንብረት እና የመኖሪያ አድራሻ ያለው፤
2. በማንኛውም ንግድ ወይም በማህበራዊ አገልግሎት ወይም በተሠማራበት የሙያ መስክ መልካም አፈጻጸም ና ስም ያለው ስለመሆኑ ከሚመለከተው አካል ማስረጃ ማምጣት የሚችል፤
3. አግባብ ባለው የክልል አካል የተዘጋጀውን የቴክኒክ መስፈርት ያሟላበ ባለቤትነት የያዘው ወይም አግባብ ባለው አካል በጸደቀ የኪራይ ውል ያገኘዉ የታጠበ ወይም ያልታጠበ የአቅርቦት ቡና ማዘጋጃ ና ማከማቻ ኢንዱስትሪ ያለው፤
4. አግባብ ባለው የመንግሥት ተቋም በዘመኑ የተመረመረ ሚዛንና  የእርጥበት መለኪያ መሣሪያ ያለው፤
5. ስለ ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱሰትሪው አሠራር ሁኔታ ከሚመለከተው መንግሥታዊ አካል የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ሰነድ ማቅረብ የሚችል፤
6. ከቡና ግብይት፣ ክምችት፣ አዘገጃጀትና ጥራት አያያዝ ጋር በተያያዘ ዕውቀትና ክህሎት ያለው ባለሙያ በቋሚነት የቀጠረ፤
7. የአቅርቦት ቡና አዘገጃጀትን በሚመለከት አግባብ ባለው የክልል አካል በተቀመጡ መስፈርቶች መሠረት ለማዘጋጀት የተስማማ፤
8. ስለ ቡና ግዥ፣ዝግጅት፣ ክምችትና ሽያጭ መረጃ ለማደራጀት እና መረጃውን አግባብ ባለው አስፈጻሚ አካል በተጠየቀ ጊዜ ለመስጠት የተስማማ፤
9. በአቅርቦት ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪው የሚዘጋጅ ቡና ግዥ በህጋዊ ግብይት ብቻ ስለመከናወኑ ሙሉ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ አውቆ የተስማማ፤እና
10. በቡና ንግድ በወንጀል ወይም በአስተዳደር ቅጣት ተወስኖበት ከነበረ ቅጣቱን የፈጸመ ወይም የወንጀል ቅጣቱ የተገደበለት ከሆነ ገደቡን የፈጸመ፤ መሆኑ ሲረጋገጥ ይሆናል፡፡

## 18. <u>የቡና ላኪነት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት</u>

ማንኛውም ሰው የቡና ላኪነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው፡

1. በህግ ሰውነት የተሰጠው አካል ሲሆን የሥራ አድራሻ ያለው፤ የተፈጥሮ ሰው ከሆነ ቋሚ ንብረት እና የመኖሪያ አድራሻ ያለው፤
2. በማንኛውም ንግድ ወይም በማህበራዊ አገልግሎት ወይም በተሠማራበት የሙያ መስክ መልካም አፈጻጸምና ስም ያለው ስለመሆኑ ከሚመለከተው አካል ማስረጃ ማምጣት የሚችል፤
3. በባለስልጣኑ የተዘጋጀውን የቴክኒክ መስፈርት ያሟላ በባለቤትነት የያዘው ወይም ስልጣን ባለው አካል በጸደቀ ውል ከሦስተኛ ወገን ያገኘው ወይም የአገልግሎት ውል ያለው የወጪ ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ ያለው፤
4. አግባብ ባለው የመንግሥት ተቋም በዘመኑ የተመረመረ ሚዛንና የእርጥበት መለኪያ መሣሪያ ያለው፤
5. ስለወጪ ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱሰትሪው አሠራር ሁኔታ ከሚመለከተው መንግሥታዊ አካል የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ሰነድማ ቅረብ የሚችል፤
6. ከቡና ግብይት፣ ክምችት፣ አዘገጃጀትና ጥራት አያያዝ ጋር በተያያዘ ዕውቀትና ክህሎት ያለው ባለሙያ በቋሚነት የቀጠረ፤
7. በህግ የሀገሪቱን የወጪ ቡና የጥራት ደረጃ ለማስጠበቅ የተቀመጡ ግዴታዎችን እና መስፈርቶችን ጠብቆና ብሔራዊ ጥቅምን ከሚጎዳ ተግባር ተቆጥቦ ለመሥራት የተስማማ፤
8. ስለ ቡና ግዥ፣ ዝግጅት፣ ክምችትና ሽያጭ መረጃ በማደራጀት መረጃውን አግባብ ባለው አስፈጻሚ አካል በተጠየቀ ጊዜ ለመስጠት የተስማማ፤
9. የወጪ ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪው የሚዘጋጅ ቡና ግዥ በህጋዊ ግብይት ብቻ መከናወኑን ሙሉ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ አውቆ የተስማማ፤እና
10. በቡና ንግድ በወንጀል ወይም በአስተዳደር ቅጣት ተወስኖ በትክከነበረ ቅጣቱን የፈጸመ ወይም የወንጀል ቅጣቱ የተገደበለት ከሆነ ገደቡን የፈጸመ፤ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

19. **<u>የወጪ ቡና ቆይነት የብቃት ማረጋገጫ</u>**

ማንኛውም ሰው የወጪ ቡና ቆይነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው፡-

1. በህግ ሰውነት የተሰጠው አካል ሲሆን የሥራ አድራሻ ያለው፤የተፈጥሮ ሰው ከሆነቋሚንብረትእናየመኖሪያአድራሻያለው፤
2. በማንኛውም ንግድ ወይም በማህበራዊ አገልግሎት ወይም በተሠማራበት የሙያ መስክ መልካም አፈጻጸምና ስም ያለው ስለመሆኑ ከሚመለከተው አካል ማስረጃ ማምጣት የሚችል፤
3. በባለስልጣኑ የተዘጋጀውን የቴክኒክ መስፈርት ያሟሉ በባለቤትነት የያዛቸው ወይም አግባብ ባለው አካል በጸደቀ ውል በኪራይ ያገኛቸው እሴት የተጨመረበት የወጪ ቡና ማዘጋጃ ኢንዱስትሪ እና የቡና ጥራትና ጣዕም ምርመራ ላብራቶሪ ያለው፤
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በተፈቀዱ መገበያያ ስፍራዎች ቀይ እሸት ወይም ጀንፈል ቡና የሚገዛ ከሆነ በባለቤትነት የያዘው ወይም ከሦስተኛ ወገን በኪራይ ውል ያገኘው የአቅርቦት ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ ያለው፤
5. ስለ ወጪ ቡና እሴት የሚጨምር ማዘጋጃ ኢንዱስትሪውን በሚመለከት በሚመለከተው መንግሥታዊ አካል የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ሰነድ ማቅረብ የሚችል፤
6. በህግ የሀገሪቱን የወጪ ቡና የጥራት ደረጃ ለማስጠበቅ የተቀመጡ ግዴታዎችንና መስፈርቶችን ጠብቆና ብሔራዊ ጥቅምን ከሚጎዳ ተግባር ተቆጥቦለመሥራትየተስማማ፤
7. ከቡና ግብይት፣ ክምችት፣ አዘገጃጀት፣ እሴት ጭመራና ጥራት አያያዝ ጋር በተያያዘ ዕውቀትና ክህሎት ያለው ባለሙያ በቋሚነት የቀጠረ፤
8. ለአዘጋጀው እሴት የተጨመረበት ቡና የራሱ የሆነ ስያሜ እና የንግድ ምልክት ያለው፤
9. እያንዳንዱን የቡና ዓይነት ተፈጥሯዊ ባህሪውን ጠብቆ ወይም በሚታወቅ የቅይጥ ምጣኔ ጥንቅር እሴት የተጨመረበት የወጪ ገበያ ቡና አዘጋጅቶ ወደ ውጭ ለመላክ የተስማማ፤

10. ስለ ቡና ግዥ፣ ክምችት፣ ዝግጅት፣ እሴት ጭመራና ሽያጭ መረጃ ለማደራጀት እና መረጃውን አግባብባለው አስፈጻሚ አካል በተጠየቀ ጊዜ ለመስጠት የተስማማ፤
11. እሴት በሚጨምር የወጪ ቡና ማዘጋጃ ኢንዱስትሪው ውስጥ የሚዘጋጅ ቡና ግዥ በህጋዊ ግብይት ብቻ መከናወኑን ሙሉ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ አውቆ የተስማማ፤እና
12. በ ቡና ንግድ በወንጀል ወይም በአስተዳደር ቅጣት ተወስኖበት ከነበረ ቅጣቱን የፈጸመ ወይም የወንጀል ቅጣቱ የተገደበለት ከሆነ ገደቡን የፈጸመ፤ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

20. <u>**የሀገር ውስጥ ቡና ቆይነት የብቃት ማረጋገጫ**</u>

ማንኛውም ሰው ለሀገር ውስጥ ቡና ቆይነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው፡-

1. በህግ ሰውነት የተሰጠው አካል ሲሆን የሥራ አድራሻ ያለው፤ የተፈጥሮ ሰው ከሆነ ቋሚ ንብረት እና የመኖሪያ አድራሻ ያለው፤
2. በማንኛውም ንግድ ወይም በማህበራዊ አገልግሎት ወይም በተሠማራበት የሙያ መስክ መልካም አፈጻጸምና ስም ያለው ስለመሆኑ ከሚመለከተው አካል ማስረጃ ማምጣት የሚችል፤
3. በባለስልጣኑ የተዘጋጀውን የቴክኒክ መስፈርት ያሟላ በባለቤትነት የያዘው ወይም አግባብ ባለው አካል በጸደቀ ውል በኪራይ ያገኘው እሴት የሚጨምር የሀገር ውስጥ ገበያ ቡና ማዘጋጃ ኢንዱስትሪ እና የቡና ጥራትና ጣዕም ምርመራ ላብራቶሪ ያለው፤
4. ለሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና እሴት የሚጨምር ማዘጋጃ ኢንዱስትሪው ከሚመለከተው መንግሥታዊ አካል የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ሰነድ ማቅረብ የሚችል፤
5. ከቡና ግብይት፣ ክምችት ፣አዘገጃጀት፣ እሴት ጭመራና ጥራት አያያዝ ጋር በተያያዘ ዕውቀትና ክህሎት ያለው ባለሙያ በቋሚነት የቀጠረ፤
6. ለአዘጋጀው እሴት የተጨመረበት ቡና የራሱ የሆነ ስያሜ እና የንግድ ምልክት ያለው፤

7. እያንዳንዱን የቡና ዓይነት ተፈጥሯዊ ባህሪውን ጠብቆ ወይም በሚታወቅ የቅይጥ ምጣኔ ጥንቅር አዘጋጅቶ እሴትየ ተጨመረ ቡና ለሀገር ውስጥ ገበያ ለማቅረብ የተስማማ፤
8. ስለ ቡና ግዥ፣ ክምችት፣ ዝግጅት፣ እሴት ጭመራና ሽያጭ መረጃ ለማደራጀት እና መረጃውን አግባብ ባለው አስፈጻሚ አካል በተጠየቀ ጊዜ ለመስጠት የተስማማ፤
9. እሴት በሚጨምር የሀገር ውስጥ ቡና ማዘጋጀ ኢንዱስትሪው ውስጥ የሚዘጋጅ ቡና ግዥ ሆነ ሽያጭ ቡና በህጋዊ ግብይት ብቻ መከናወኑን ሙሉ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ አውቆ የተስማማ፤እና
10. በ ቡና ንግድ በወንጀል ወይም በአስተዳደር ቅጣት ተወስኖበት ከነበረ ቅጣቱን የፈጸመ ወይም የወንጀል ቅጣቱ የተገደበለት ከሆነ ገደቡን የፈጸመ፤ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

21. <u>**የወጪ ቡና አዘጋጅነትና ማከማቸት አገልግሎት የብቃት ማረጋገጫ**</u>

ማንኛውም ሰው የወጪ ቡና አዘጋጅነትና ማከማቸት አገልግሎት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው፡-

1. በህግ ሰውነት የተሰጠው አካል ሲሆን የሥራ አድራሻ ያለው፤ የተፈጥሮ ሰው ከሆነ ቋሚ ንብረት እና የመኖሪያ አድራሻ ያለው፤
2. በማንኛውም ንግድ ወይም በማህበራዊ አገልግሎት ወይም በተሠማራበት የሙያ መስክ መልካም አፈጻጸምና ስም ያለው ስለመሆኑ ከሚመለከተው አካል ማስረጃ ማምጣት የሚችል፤
3. በባለስልጣኑ የተዘጋጀውን የቴክኒክ መስፈርት ያሟላ በባለቤትነት የያዘው ወይም አግባብ ባለው አካል በጸደቀ ኪራይ ውል ያገኘው የወጪ ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ እና የቡና ጥራትና ጣዕም ምርመራ ላቦራቶሪ ያለው፤
4. ስለ ወጪ ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪው በሚመለከተው መንግሥታዊ አካል የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ሰነድ ማቅረብ የሚችል፤
5. ከቡና ግብይት፣ ክምችት፣ አዘገጃጀትና ጥራት አያያዝ ጋር በተያያዘ ዕውቀትና ክህሎት ያለው ባለሙያ በቋሚነት የቀጠረ፤

6. በህግ የሀገሪቱን የወጪ ቡና የጥራት ደረጃ ለማስጠበቅ የተቀመጡ ግዴታዎችንና መስፈርቶችን ጠብቆና ብሔራዊ ጥቅምን ከሚጎዳ ተግባር ተቆጥቦ ለመሥራት የተስማማ፤
7. የተለያዩ ባህሪ ወይም ደረጃ ያላቸውን የቡና ዓይነቶች ለይቶ ለማዘጋጀትና ለማከማቸት የሚያስችለው አሠራር ያለው፤
8. ስለ ቡና ግዥ፣ ዝግጅት፣ ክምችትና ሽያጭ መረጃ ለማደራጀት እና መረጃውን አግባብ ባለው አስፈጻሚ አካል በተጠየቀ ጊዜ ለመስጠት የተስማማ፤
9. በወጪ ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪው የሚዘጋጅ ቡና በህጋዊ ግብይት ብቻ መከናወኑን ሙሉ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ አውቆ የተስማማ፤ እና
10. በቡና ንግድ በወንጀል ወይም በአስተዳደር ቅጣት ተወስኖበት ከነበረ ቅጣቱን የፈጸመ ወይም የወንጀል ቅጣቱ የተገደበለት ከሆነ ገደቡን የፈጸመ፤ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

22. <u>አቅርቦት ቡና ማዘጋጀትና ማከማቸት አገልግሎት ሰጪነት የብቃት ማረጋገጫ</u>

ማንኛውም ሰው የአቅርቦት ቡና ማዘጋጀትና ማከማቸት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው፡-

1. በህግ ሰውነት የተሰጠው አካል ሲሆን የሥራ አድራሻ ያለው፤የተፈጥሮ ሰው ከሆነ ቋሚ ንብረት እና የመኖሪያ አድራሻ ያለው፤
2. በማንኛውም ንግድ ወይም በማህበራዊ አገልግሎት ወይም በተሠማራበት የሙያ መስክ መልካም አፈጻጸምና ስም ያለው ስለመሆኑ ከሚመለከተው አካል ማስረጃ ማምጣት የሚችል፤
3. በባለስልጣኑ ወይም አግባብ ባለው የክልል አካል የተዘጋጀውን የቴክኒክ መስፈርት ያሟላ በባለቤትነት የያዘው ወይም አግባብ ባለው አካል የጸደቀ ኪራይ ውል ያገኘው የአቅርቦት ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ ያለው እና የቡና እርጥበት መለኪያ ያለው፤
4. ለቡና አምራቾች ብቻ ቡና የማዘጋጀትና የማከማቸት አገልግሎት ውል ለመስጠት የተስማማ፤
5. በሚመለከተው መንግሥታዊ አካል የተረጋገጠ ስለማዘጋጃ ኢንዱስትሪው የሥራ እንቅስቃሴ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ሰነድ ማቅረብ የሚችል፤

6.ከቡና ግብይት፣ ክምችት፣ አዘገጃጀትና ጥራት አያያዝ ጋር በተያያዘ ዕውቀትና ክህሎት ያለው ባለሙያ በቋሚነት የቀጠረ፤

7.በህግ የሀገሪቱን የወጪ ቡና የጥራት ደረጃ ለማስጠበቅ የተቀመጡ ግዴታዎችንና መስፈርቶችን ጠብቆና ብሔራዊ ጥቅምን ከሚጎዳ ተግባር ተቆጥቦ ለመሥራት የተስማማ፤

8.የተለያዩ ባህሪ ወይም ደረጃ ያላቸውን የቡና ዓይነቶች ለይቶ ለማዘጋጀትና ለማከማቸት የሚያስችለው አሠራር ያለው፤

9.ስለ ቡናግዥ፣ ዝግጅት፣ ክምችትና ሽያጭ መረጃ ለማደራጀት እና መረጃውን አግባብ ባለው አስፈጻሚ አካል በተጠየቀ ጊዜ ለመስጠት የተስማማ፤

10.የአቅርቦት ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪው የሚዘጋጅ ቡና ግዥ ሆነ ሽያጭ በህጋዊ ግብይት ብቻ መከናወኑን ሙሉ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ አውቆ የተስማማ፤ እና

11.በቡና ንግድ በወንጀል ወይም በአስተዳደር ቅጣት ተወስኖበት ከነበረ ቅጣቱን የፈጸመ ወይም የወንጀል ቅጣቱ የተገደበለት ከሆነ ገደቡን የፈጸመ፤ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

23.<u>የቡና ገለባ አቀነባባሪነት የብቃት ማረጋገጫ</u>

ማንኛውም ሰው የቡና ገለባ አቀነባባሪነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው፡-

1.በህግ ሰውነት የተሰጠው አካል ሲሆን የሥራ አድራሻ ያለው፤የተፈጥሮ ሰው ከሆነ ቋሚ ንብረት እና የመኖሪያ አድራሻ ያለው፤

2.በማንኛውም ንግድ ወይም በማህበራዊ አገልግሎት ወይም በተሠማራበት የሙያ መስክ መልካም አፈጻጸምና ስም ያለው ስለመሆኑ ከሚመለከተው አካል ማስረጃ ማምጣት የሚችል፤

3.በባለስልጣኑ የተዘጋጀውን የቴክኒክ መስፈርት ያሟላ በባለቤትነት የያዘው ወይም አግባብ ባለው አካል በጸደቀ የኪራይ ውል ያገኘው የቡና ገለባ ማቀነባበሪያና ማከማቻ ያለው፤

4.በሚመለከተው መንግሥታዊ አካል የተረጋገጠ ስለማዘጋጃ ኢንዱስትሪ የሥራ እንቅስቃሴ የአከባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ሰነድ ማቅረብ የሚችል፤ እና

5.ከቡና ገለባ አዘገጃጀትና ጥራት አያያዝ ጋር በተያያዘ ዕውቀትና ክህሎት ያለው ቋሚ ባለሙያ የቀጠረ፤ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

24. **የቡና ቅጠል አቀነባባሪነት የብቃት ማረጋገጫ**

ማንኛውም ሰው የቡና ቅጠል አቀነባባሪነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው፡-

1. በህግ ሰውነት የተሰጠው አካል ሲሆን የሥራ አድራሻ ያለው፤ የተፈጥሮ ሰው ከሆነ ቋሚ ንብረት እና የመኖሪያ አድራሻ ያለው፤
2. በማንኛውም ንግድ ወይም በማህበራዊ አገልግሎት ወይም በተሠማራበት የሙያ መስክ መልካም አፈጻጸምና ስም ያለው ስለመሆኑ ከሚመለከተው አካል ማስረጃ ማምጣት የሚችል፤
3. በባለቤትነት የያዘው ወይም አግባብ ባለው አካል በጸደቀ የኪራይ ውል ያገኘው የቴክኒክ መስፈርት ያሟላ የቡና ቅጠል ማቀነባበሪያና ማከማቻ ያለው፤
4. በሚመለከተው መንግሥታዊ አካል የተረጋገጠ ስለማዘጋጃ ኢንዱስትሪ የሥራ እንቅስቃሴ የአከባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ሰነድ ማቅረብ የሚችል፤ እና
5. ከቡና ቅጠል አዘገጃጀትና ጥራት አያያዝ ጋር በተያያዘ ዕውቀትና ክህሎት ያለው ቋሚ ባለሙያ የቀጠረ፤ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

25. **የጥብቅ የወጪ ቡና ማከማቸት አገልግሎት ሰጪነት የብቃት ማረጋገጫ**

ማንኛውም ሰው የጥብቅ የወጪ ቡና ማከማቸት አገልግሎት ሰጪነት የብቃት ማረጋጋጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው፡-

1. በህግ ሰውነት የተሰጠው አካል ሲሆን የሥራ አድራሻ ያለው፤የተፈጥሮ ሰው ከሆነ ቋሚ ንብረት እና የመኖሪያ አድራሻ ያለው፤
2. በማንኛውም ንግድ ወይም በማህበራዊ አገልግሎት ወይም በተሠማራበት የሙያ መስክ መልካም አፈጻጸምና ስም ያለው ስለመሆኑ ከሚመለከተው አካል ማስረጃ ማምጣት የሚችል፤
3. በባለስልጣኑ የተዘጋጀውን የቴክኒክ መስፈርት ያሟላ በባለቤትነት የያዘው ወይም ስልጣን ባለው አካል በጸደቀ የኪራይ ውል ያገኘው ጥብቅ የወጪ ገበያ ቡና ማከማቻ ያለው፤
4. የተለያየ ባህሪ ወይም ደረጃ ያላቸውን የቡና ዓይነቶች ለይቶ ለማከማቸት የሚያስችለው አሠራር ያለው፤

5.በህግ የሀገሪቱን የወጪ ቡና የጥራት ደረጃ ለማስጠበቅ የተቀመጡ ግዴታዎችንና መስፈርቶችን ጠብቆና ብሔራዊ ጥቅምን ከሚጎዳ ተግባር ተቆጥቦ ለመሥራት የተስማማ፤

6.ስለ ቡና ግዥ፣ ክምችትና ጭነት መረጃ ለማደራጀት እና መረጃውን አግባብ ባለው አስፈጻሚ አካል በተጠየቀ ጊዜ ለመስጠት የተስማማ፤

7.በጥብቅ የወጪ ቡና ማከማቻ መጋዘኑ ስለሚከማች ቡና እና የጭነት እንቅስቃሴ በህጋዊ መንገድ ብቻ መከናወኑን አስመልክቶ ሙሉ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ አውቆ የተስማማ፤ እና

8.በቡና ንግድ በወንጀል ወይም በአስተዳደር ቅጣት ተወስኖበት ከነበረ ቅጣቱን የፈጸመ ወይም የወንጀል ቅጣቱ የተገደበለት ከሆነ ገደቡን የፈጸመ፤ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

26.<u>የሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና ጅምላ ነጋዴነት የብቃት ማረጋገጫ</u>

ማንኛውም ሰው የሀገር ውስጥ ፍጆታ የቡና ጅምላ ነጋዴነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው፡ -

1.በህግ ሰውነት የተሰጠው አካል ሲሆን የሥራ አድራሻ ያለው፤የተፈጥሮ ሰው ከሆነ ቋሚ ንብረት እና የመኖሪያ አድራሻ ያለው፤

2.በማንኛውም ንግድ ወይም በማህበራዊ አገልግሎት ወይም በተሠማራበት የሙያ መስክ መልካም አፈጻጸምና ስም ያለው ስለ መሆኑ ከሚመለከተው አካል ማስረጃ ማምጣት የሚችል፤

3.አግባብ ባለው የክልል አካል የተዘጋጀውን የቴክኒክ መስፈርት ያሟላ በባለቤትነት የያዘው ወይም አግባብ ባለው አካል በጸደቀ የኪራይ ውል ያገኘው የሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና ማከማቻ መጋዘን ያለው፤

4.ቡናን ለማከፋፈል ንግድ ፈቃድ በሚጠይቅበት ዞን፣ ከተማ ወይም ወረዳ የሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና አከፋፋይ ስላለመኖሩ ወይም በቂ ስላለመሆኑ ከሚመለከተው የመንግሥት አካል ማረጋገጫ ሰነድ የሚያቀርብ፤

5.የሀገሪቱን የቡና ጥራት መስፈርት አክብሮ ቡና ለመያዝና ለማከፋፈል የተስማማ፣

6.ስለቡና ግዥ፣ ክምችትና ሽያጭ መረጃ ለማደራጀት እና መረጃውን አግባብ ባለው አስፈጻሚ አካል በተጠየቀ ጊዜ ለመስጠት የተስማማ፤ እና

7.በቡና ንግድ በወንጀል ወይም በአስተዳደር ቅጣት ተወስኖበት ከነበረ ቅጣቱን የፈጸመ ወይም የወንጀል ቅጣቱ የተገደበለት ከሆነ ገደቡን የፈጸመ፤ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

27.<u>የሀገር ውስጥ ፍጅታ ቡና ቸርቻሮ ነጋዴነት የብቃት ማረጋገጫ</u>

ማንኛውም ሰው የሀገር ውስጥ የቡና ፍጆታ የቡና ቸርቻሮ ነጋዴነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው፡-

1.በህግ ሰውነት የተሰጠው አካል ሲሆን የሥራ አድራሻ ያለው፤ የተፈጥሮ ሰው ከሆነ ቋሚ ንብረት እና የመኖሪያ አድራሻ ያለው፤

2.በባለቤትነት የያዘው ወይም አግባብ ባለው አካል በጸደቀ የኪራይ ውል ያገኘው የንግድ መደብር ያለውና መደብሩ ለቡና ማስቀመጫ የተለየ ስፍራ ያለው፤

3.የሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና ለመያዝና ለመቸርቸር ህጋዊ ሥርዓት ጠብቆ ለመሥራት የተስማማ፤ እና

4.ስለቡና ግዥ፣ ክምችት ሽያጭ መረጃ ለማደራጀት እና መረጃውን አግባብ ባለው አስፈጻሚ አካል በተፈለገ ጊዜ ሲጠየቅ ለመስጠት የተስማማ፤ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

28.የቡና የንግድ ሥራ ወኪልነት የብቃት ማረጋገጫ ማንኛውም ሰው የቡና ንግድ ሥራ ወኪልነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው፡-

1.በህግ ሰውነት የተሰጠው አካል ሲሆን የሥራ አድራሻ ያለው፤ የተፈጥሮ ሰው ከሆነ ቋሚ ንብረት እና የመኖሪያ አድራሻ ያለው፤

2.በማንኛውም ንግድ ወይም በማህበራዊ አገልግሎት ወይም በተሠማራበት የሙያ መስክ መልካም አፈጻጸምና ስም ያለው ስለመሆኑ ከሚመለከተው አካል ማስረጃ ማምጣት የሚችል፤

3.በዘርፉ ዕውቀትና ክህሎት ያለው ስለመሆኑ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፤

4.ስለቡና ግዥ፣ ክምችት፣ ሽያጭና ጭነት መረጃ ለማደራጀት እና መረጃውን አግባብ ባለው አስፈጻሚ አካል በተጠየቀ ጊዜ ለመስጠት የተስማማ፤ እና

5.በቡና ንግድ በተያያዘ በወንጀል ወይም በአስተዳደር ቅጣት ተወስኖበት ከነበረ ቅጣቱን የፈጸመ ወይም የወንጀል ቅጣቱ የተገደበለት ከሆነ ገደቡን የፈጸመ፤ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

29.<u>ቡና የማጓጓዝ አገልግሎት ሰጪነት የብቃት ማረጋገጫ</u>

ማንኛውም ሰው ቡና የማጓጓዝ አገልግሎት ሰጪነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው፡-

1. በህግ ሰውነት የተሰጠው አካል ሲሆን የሥራ አድራሻ ያለው፤የተፈጥሮ ሰው ከሆነ ቋሚ ንብረት እና የመኖሪያ አድራሻ ያለው፤
2. ከሚመለከተው የመንግሥት አካል የጭነት ትራንስፖርት ንግድ ፈቃድ የሚያቀርብ፤
3. ባለስልጣኑ ወይም አግባብ ያለው የክልል አካል ከሚመለከተው ትራንስፖርት ተቆጣጣሪ አካል ጋር በመሆን የሚያወጣውን የቡና ማጓጓዝ ወይም የጭነት የቴክኒክ መስፈርት የሚያሟላ በባለቤትነት የያዘው ወይም አግባብ ባለው አካል በጸደቀ የኪራይ ውል የተገኘው የጭነት ተሽከርካሪ ያለው፤
4. ቡና ሲያጓጉዝ የሚደርሰውን አደጋ ለመካስ የሚያስችል የመድህን ዋስትና ያለው ስለመሆኑ ማስረጃ የሚያቀርብ፤ እና
5. ስለሚያጓጉዘው ወይም ስለሚጭነው ቡና ህጋዊነት የማረጋገጥ ሙሉ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ አውቆ የተስማማ፤ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

30.<u>ቡና የመጫንና የማራገፍ አገልግሎት ሰጪነት የብቃት ማረጋገጫ</u>

ማንኛውም ሰው ቡና በመጫንና በማራገፍ አገልግሎት ሰጪነት ለመሰማራት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው፡-

1. በዘመኑ የታደሰ የቀበሌ የነዋሪነት መታወቂያ የሚያቀርብ፤
2. ከአከባቢው አስተዳደር የመጫንና የማራገፍ አገልግሎት ለመስጠት በማህበር ተደራጅቶ ፈቃድ ያለው ወይም በግል ለመሰማራት የሚያስችል ማስረጃ የሚያቀርብ፤ እና
3. ስለሚጫነው ወይም ሰለሚያራግፈው ቡና ህጋዊነት የማረጋገጥ ሙሉ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ አውቆ የተስማማ፤ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

31.<u>የቡና ጥራት ምርመራና ደረጃ ምደባ አገልግሎት ሰጪነት የብቃት ማረጋገጫ</u>

ማንኛውም ሰው የቡና ጥራት ምርመራ እና ደረጃ ምደባ ላቦራቶሪ አግልግሎት ሰጪነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው፡-

1. በህግ ሰውነት የተሰጠው አካል ሲሆን የሥራ አድራሻ ያለው፤ የተፈጥሮ ሰው ከሆነ ቋሚ ንብረት እና የመኖሪያ አድራሻ ያለው፤

2.የባለሥልጣኑን አሠራርና የአደረጃጀት የቴክኒክ መስፈርት የሚያሟላ የቡና ጥራት ምርመራና ደረጃ ላቦራቶሪ ያለው፤

3.በቡና ጥራት ምርመራና ደረጃ ምደባ ልዩ ስልጠና የወሰደ ባለሙያ በቋሚነት የቀጠረ፤

4.ስለቡና ጥራት፣ ደረጃና መጠን በእያንዳንዱ የቡና ዓይነት ከነባለቤቱ መረጃ ለማደራጀት እና መረጃውን አግባብ ባለው አስፈጻሚ አካል በተጠየቀ ጊዜ ለመስጠት የተስማማ፤

5.በህግ የሀገሪቱን የቡና ጥራት ደረጃ ለማስጠበቅ የተቀመጡ ግዴታዎችንና መስፈርቶችን ጠብቆ ብሄራዊ ጥቅምን ከሚጎዳ ተግባር ተቆጥቦ ለመሥራት የተስማማ፤ እና

6.በቡና ንግድ በወንጀል ወይም በአስተዳደር ቅጣት ተወስኖበት ከነበረ ቅጣቱን የፈጸመ ወይም የወንጀል ቅጣቱ የተገደበለት ከሆነ ገደቡን የፈጸመ፤መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥና አስተዳደር

### 32.የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ

1.የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው፡-

ሀ) በወጪ ቡና ማዘጋጀትና ማከማቸት፣ ቡና ላኪነት፣ የወጪ ቡና ቆይነት፣ የጥብቅ ቡና ማከማቸት፣ በወጪ ቡና ንግድ ሥራ ወኪልነት፣ በጥራት ምርመራና ደረጃ ምደባ አገልግሎት ሰጪነት ሥራ የሚሰማራ ከሆነ ማመልከቻውን ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

ለ) የቡና አቅራቢነት፣ የሀገር ውስጥ ቡና ቆይነት፣ በአቅርቦት ቡና ማዘጋጀትና ማከማቸት፣ በቡና ገለባ አቀነባባሪነት፣ በቡና ቅጠል አቀነባባሪነት፣ በሀገር ውስጥ ቡና ፍጆታ ጅምላ ነጋዴነት፣ በሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና ችርቻሪ ነጋዴነት፣ በሀገር ውስጥ ቡና ንግድ ወኪልነት፣ የቡና ማጓጓዝ አገልግሎት ሰጪነት፣ የቡና መጫንና ማራገፍ አገልግሎት ሰጪነት ከሆነ፣ ማመልከቻውን አግባብ ላለው የክልል አካል ማቅረብ አለበት፡፡

ሐ) ከማመልከቻው ጋር የተጠየቀውን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት በዚህ ደንብ የተደነገጉት መስፈርቶች መሟላታቸውን የሚያሳዩ ማስረጃዎችንና ባለስልጣኑ ወይም አግባብ ያለው የክልል አካል በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የሚጠየቁ ሌሎች መረጃዎችን አሟልቶ ማቅረብ አለበት፡፡

2.ባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ያለው የክልል አካል ማመልከቻው ከቀረበለት ቀን ጀምሮ በ15 የሥራ ቀናት ውስጥ አጣርቶ የብቃት ማረጋገጫ መስጠት ወይም የማይገባው መሆኑ የሚገልፅ ውሳኔ መስጠት ይኖርበታል፤

3.ባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ያለው የክልል አካል አመልካቹ የብቃት ማረጋገጫው የማይገባው መሆኑን በወሰነ ጊዜ የክልከላውን ምክንያት በውሳኔው ላይ በዝርዝር በማስቀመጥ ለአመልካቹ በጽሁፍ መስጠት ይኖርበታል፤

4.ባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ያለው የክልል አካል በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ አመልካች ውሳኔው በተሰጠው በ30 የሥራ ቀናት ውስጥ ለሚመለከተው ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

33.<u>የብቃት ማረጋገጫ ስለ ማሳደስ</u>

1.በዚህ ደንብ መሠረት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ማንኛውም ሰው በሚቀመጥ የጊዜ ገደብ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱን በየአመቱ ማሳደስ ይኖርበታል፡፡

2.በተቀመጠው የጊዜ ገደብ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱን ያላሳደሰ እንደሆነ ይህን ደንብ ተከትሎ በሚወሰን መመሪያ በሚወሰን ተጨማሪ ጊዜ እና በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ በሚወሰን የቅጣት መጠን በገንዘብ ቅጣት ማሳደስ ይችላል፡፡

34.<u>የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለ ማገድ እና መሰረዝ</u>

1.በዚህ ደንብ መሠረት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ማንኛውም ሰው፡-

ሀ) የምስክር ወረቀቱ የተሰጠባቸውን መስፈርቶች አጓድሎ ሲገኝ፣

ለ) በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱን ያላሳደሰ እንደሆነ፣ ወይም

ሐ) የአዋጁን ወይም የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ወይም አዋጁንና ይህን ደንብ ለማስፈጸም የወጡ መመሪያዎችን ተላልፎ ሲገኝ፤

ባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ያለው የክልል አካል ጉድለቱን እንዲያስተካክል በማዘዝ የምስክር ወረቀቱን አግዶ ሊያቆየው ይችላል፤ መታገዱንም ለሚመለከታቸው አካላት በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡

2.በዚህ ደንብ መሠረት የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የያዘ ሰው፡-

ሀ) የምስክር ወረቀትቱን ያገኘው ሀሰተኛ ማስረጃ በማቅረብ ሆኖ ከተገኘ፣

ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለምስክር ወረቀቱ መታገድ ምክንያት የሆነውን ጉድለት በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማስተካከል ካልቻለ፣ ወይም

ሐ) በአዋጁ አንቀጽ 19 የተደነገገውን በመተላለፍ በወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ ከተፈረደበት፤ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ በባለሥስልጣኑ ወይም አግባብነት ባለው የክልል አካል ይሰረዛል፡፡

3.በባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ባለው የክልል አካል የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የታገደበት ወይም የተሰረዘበት ሰው ቅሬታ ካለው ውሳኔው ከደረሰው ቀን ጀምሮ ባሉት 60 የሥራ ቀናት ውስጥ ለሚመለከተው ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

35.<u>የእግድ ወይም የመሠረዝ ውጤት</u>

1.በዚህ ደንብ አንቀጽ 34 መሠረት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የታገደበት ወይም የተሰረዘበት ሰው በዕገዳው ወይም በመሰረዙ ላይ የቀረበው ይግባኝ በመታየት ላይ እያለ በቡና ግብይት ወይም በአገልግሎት ሰጪነት ላይ ሊሠማራ አይችልም፡፡

2.የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1 ድንጋጌ ቢኖርም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የታገደበት ወይም የተሰረዘበት ሰው በዚህ ደንብ የተቀመጠውን መስፈርት የሚያሟሉ መገልገያዎቹን፣መሳሪያዎቹንና ዕቃዎቹን የጸና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያለው ሌላ ሰው እንዲጠቀምባቸው ሊፈቅድ ይችላል፡፡

## ክፍል አምስት

## የቡና ጥራት እና ግብይት ቁጥጥር አሠራር

### 36.የቡና ጥራት ቁጥጥር አሠራር

1.ቡና ሲለቀም፣ ሲዘጋጅ፣ ሲከማች፣ ሲጓጓዝ ተፈጥሯዊ ጥራት ተጠብቆ ለገበያ እንዲቀርብ ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፡፡

2.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ቀይ እሸት እና ጀንፈል ቡና ወደ ግብይት ማዕከላት ሲቀርብ የቀይ እሸት ወይም የጀንፈል ቡና ጥራት ደረጃ መሠረት ስለመቅረቡ ቁጥጥር ይደረጋል፡፡

3.የቀይ እሸት ቡና በተለቀመበት ዕለት ወደ የታጠበ የአቀርቦት ቡና ማዘጋጃ ኢንዱስትሪ ገብቶ በጥራት ስለመዘጋጀቱ ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፡፡

4.ጀንፈል ቡና በተዘጋጀው የአደራረቅ የቴክኒክ መስፈርት መሠረት ስለመዘጋጀቱና ስለመከማቸቱ ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፡፡

5.የአቅርቦት ቡና ወደ ወጪ ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ ገብቶ በጥራት ስለመዘጋጀቱና ስለመከማቸቱ፣ በቃጫ ጆንያ ወይም በሌላ በባለሥልጣኑ በተፈቀደ መያዣ ታሽጎ ስለመያዙ ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፡፡

6.የአቅርቦት ቡና ከተመረተበት አካባቢ ታሽጎ ከመሸኘቱ በፊት ለባለቤቱ የሚመለስ ወካይ ናሙና ተወስዶ የጥሬ ቡና ምርመራ ይደረጋል፡፡

7.የአቅርቦት ቡና ለወጪ ገበያ ወይም ለሀገር ውስጥ ፍጆታ ወደ ገበያ ከመቅረቡ በፊት በወጣው የቡና ጥራትና ጣዕም ምርመራ የቴክኒክ መስፈርት መሠረት ወካይ ናሙና ተወስዶ የጥራት ደረጃው እንዲመደብ ይደረጋል፡፡

8.የተቆላ ወይም ተቆልቶ የተፈጨ ቡና ወይም በሌላ መልኩ እሴት የተጨመረበት ቡና በተቀመጠው የቴክኒክ መስፈርት መሠረት በጥራት ስለመቀነባበሩ፣በሚፈለገው ደረጃ ስለመታሸጉና ስለመከማቸቱ ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፡፡

9.በማንኛውም መልኩ ቡና የሚጫንበት የጭነት ተሽከርካሪ ወይም ኮንቴነር ቡናን ለመጫን አስፈላጊውን የጥራት ደረጃ ስለማሟላቱ ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፡፡

37.<u>የቡና ግብይት ቁጥጥር</u>

1. በማንኛውም የቡና አምራች የቀይ እሸት ቡና ለታጠበቡና ዝግጅት የሚቀርብ ከሆነ ከተለቀመበት ጊዜ ጀምሮ ከስምንት ሰዓት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ወደ የመጀመሪያ ደረጃ ቡና ግብይት ማዕከላት ስለመግባቱ ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፡፡
2. በማንኛውም የቡና አምራች የሚዘጋጅ የጀንፈል ቡና ባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ያለው የክልል አካል በሚያወጣው የቴክኒክ መስፈርት መሠረት ጥራቱን በጠበቀ ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ እንዲከማች እና ስለመከማቸቱ ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀት (2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ቡና አምራች አርሶ አደር ጀንፈል ቡና ከአንድ የምርት ዘመን በላይ እንዳይከማች ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፡፡
4. ማንኛውም የታጠበ የአቅርቦት ቡና በምርት ዘመኑ እስከ ነሐሴ 30 ቀን ድረስ ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም በአማራጭ ግብይት ውል መሠረት ለቡና ላኪው ስለመቅረቡ ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፡፡
5. ማንኛውም ያልታጠበ የአቅርቦት ቡና በምርት ዘመኑ እስከ ጥቅምት 30 ቀን ድረስ ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም በአማራጭ ግብይት ውል መሠረት ለቡና ላኪው ስለመቅረቡ ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፡፡
6. ማንኛውም ቡና አዘጋጅቶ ለወጪ ገበያ የሚያቀርብ ሰው ለወጪ ገበያ ያዘጋጀውን የታጠበ ቡና የምርት ዘመኑ ማጠናቀቂያ ጊዜ እስከሆነው ጥቅምት 30 ቀን ድረስ በወጪ ገበያ ስለ መሸጡ ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፡፡
7. ማንኛውም ቡና አዘጋጅቶ ለወጪ ገበያ የሚያቀርብ ሰው ለወጪ ገበያ ያዘጋጀውን ያልታጠበ ቡና የምርት ዘመኑ ማጠናቀቂያ ጊዜ እስከ ሆነው ጥር 30 ቀን ድረስ ስለመሸጡ ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፡፡

8.በባለስልጣኑ የተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ያለበቂ ምክንያት ማለፉን ሲያረጋግጥ የጊዜ ገደቡ ከተጠናቀቀ በኋላ ባለው አንድ ወር ውስጥ የቡናውን ጠቅላላ ዋጋ ሁለት በመቶ ቅጣት ለመንግሥት ገቢ ከተፈጸመ እንዲሁም የጊዜ ገደቡ ከተጠናቀቀ በኋላ ባለው በሁለተኛ ወር ውስጥ የቡናውን ጠቅላላ ዋጋ 5 በመቶ (አምስት በመቶ ቅጣት ለመንግሥት ገቢ ከተፈጸመ በኋላ እንዲሸጥ ይፈቅዳል፡፡

9.በአቅርቦትና በወጪ ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ የሚኖረውን የቡና ክምችት እንደአግባብነቱ በባለስልጣኑ ወይም አግባብ ባለው የክልል አካል በሚወጣው መርሐ ግብር መሠረት በዓመት አንድ ጊዜ የቡና ክምችት ቆጠራ ይደረጋል፡፡

10.የቡና ክምችት ቆጠራ ተደርጎ በቡና ግብይት ሂደት በቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪው ሊኖር የሚገባው የቡና ክምችት መጠን ተሰልቶ በማነስም ሆነ በመብለጥ በሚለየው የቡና ክምችት ላይ እንደአግባብነቱ በባለስልጣኑ ወይም አግባብ ባለው የክልል አካል በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ሕጋዊና አስተዳዳራዊ እርምጃ እንዲወሰድ ይደረጋል፡፡

11.ማናቸውም የአቅርቦትና የወጪ ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ ከተገልጋዩ ጋር በገባው ውል መሠረት ላዘጋጀው ቡና በኢንዱስትሪው ስለመዘጋጀቱ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለመሰጠቱ ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፡፡

12.ቡናው የተመረተበት አካባቢ ወይም የአቅርቦት ቡና ማዘጋጃ ኢንዱስትሪ ወይም የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም የወጪ ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ ወይም የሀገር ውስጥ ቡና ሸማች አካባቢ በአግባቡ ስለመሸኘቱና ስለመድረሱ ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፤ ማንኛውም ሰው ማጓጓዝ የሚችለው የግል ፍጆታ የቡና መጠን ባለስልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

13.የወጪ ገበያ ቡና አስፈላጊውን መስፈርት አሟልቶ ከተሸኘ በኋላ ከሀገር ስለመውጣቱ በሀገሪቱ ህጋዊ መውጫ በሮች ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፡፡

38.የተከለከሉ አሰራሮች

በአዋጁ የተከለከሉ ተግባራትና አሠራሮች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም ቡና አምራች ወይም አዘጋጅ ወይም የግብይት ተሳታፊ በቡና ልማት፣ ለቀማ፣ ዝግጅት፣ ግብይት፣ ማከማቸት እና ማጓጓዝ ሂደት ላይ:-

1.አረንጓዴ ቡና መልቀም፣ ቡናን መሸምጠጥ ወይም የተለያየ ብስለት ደረጃ ያለው ቡና መቀላቀል፤

2.ቡናን ክብደቱ እንዲጨምር በአፈር ማሸት፣ ከባዕድ አካላት ጋር ማደባለቅ ወይም በውሃ መዘፍዘፍ፤

3.ቡናን በመንገድ ወይም በመሬት ላይ መጨፍለቅ ወይም ለማድረቅ ማስጣት ወይም መርቡሽ ቡና ማዘጋጀት ወይም በማንኛውም ሁኔታ የቡናውን ጣዕምና ጥራት ከሚያበላሽ ባዕድ ነገር እንዲነካካ ማድረግ፤

4.ለቡና ተክሉ አገልገሎቱን ያላጠናቀቀ ቅጠል ሽምጥጦ ለገበያ ማቅረብ፤

5.ባለስልጣኑ ወይም አግባብ ያለው የክልል አካል አገልግሎት ላይ እንዲውል ከሚፈቅደው የቃጫ ጆንያ ወይም ሌላ የቡና መያዣ ውጪ መጠቀም፤

6.በቡና ማሳው ላይ በባለሙያ ያልተመሰከረለትና ጥቅም ላይ እንዲውል ያልተፈቀደ ኬሚካል መጠቀም፤

7.በልዩ ሁኔታ ካልተፈቀደ በስተቀር ከውጭ እንዲገባ የተፈቀደውን ቡና በማንኛውም መልኩ ለሀገር ውስጥ ፍጆታ ማዋል እና በጥሬው መልክ መልሶ ወደ ወጪ መላክ፤

8.ቡና አምራች አርሶ አደር ቡናን ወደ መጀመሪያ ደረጃ ቡና ግብይት ማዕከል ሲያጓጉዝ ካልሆነ በስተቀር ባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ያለው የክልል አካል ሳይፈቅድ የቡና ምርትን በማንኛውም ተሽከርካሪ፣ ጋሪ እና በጋማ ከብት ከቦታ ቦታ ማዘዋወር፤

9.ከባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ካለው የክልል አካል ፈቃድ ውጪ የወጪ ቡና በማንኛውም መደብር ወይም ቦታ ማከማቸት ወይም መገበያየት፤

10.ለውጪ ገበያ የተዘጋጀ ቡና ለመሸጥ በሚፈቀዱ ቦታዎች ለሀገር ውስጥ ፍጆታ የተዘጋጀ ቡና መሸጥ፤ እና

11.አግባብ ካለው የክልል አካል ህጋዊ ፈቃድ ሳይሰጠው በመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከል ገብቶ መገበያየት፤ የተከለከለ ነው፡፡

39.<u>የቡና ጥራትና ግብይት ተቆጣጣሪዎችን ስለ መመደብ</u>

1.እንደ አግባብነቱ ባለሥልጣኑና አግባብ ያለው የክልል አካል የቡና የጥራት ተቆጣጣሪ እና የቡና ግብይት ተቆጣጣሪ ይመድባሉ፡፡

2.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ መሠረት የሚመደብ የቡና ጥራት እና የቡና ግብይት ተቆጣጣሪ በቂ ዕውቀት፣ ክህሎት እና መልካም ስነምግባር ያለው መሆን አለበት፡፡

40.<u>የቡና ጥራት ተቆጣጣሪ ሥልጣንና ተግባር</u>

1.በዚህ ደንብ አንቀጽ 39 መሠረት የተመደበ የቡና ጥራት ተቆጣጣሪ ስለ ቡና ጥራት ቁጥጥር የተደነገጉ ድንጋጌዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ የሚከተለው ስልጣን ይኖረዋል:-

ሀ) በመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከላት እና በቡና ማዘጋጃ ኢንዱስትሪዎች የሚቀርበውን ቡና ጥራት ሁኔታ መከታተል፣ መቆጣጠር፤

ለ) አነስተኛ ይዞታ ባላቸው ቡና አምራች አርሶ አደሮችና ቡና አልሚ ባለሃብቶች የሚካሄደውን የቡና አዘገጃጀት፣ አከመቻቸት እና የማጓጓዝ ሂደት መከታተል መቆጣጠር፤

ሐ) በቡና አቅራቢዎች፣ በቡና ላኪዎች፣ በኅብረት ሥራ ማህበራት፣ በቡና ቆይዎች እና በቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪዎች የሚከናወነውን የቡና ክምችትና ዝግጅት መከታተል፣ መቆጣጠር፤ እና

መ) ከውጭ በግዢ የሚገባውን የጥሬ ቡና ጥራትና ዝግጅት ሂደት መቆጣጠር፡፡

2.የቡና ጥራት ተቆጣጣሪ የጥራት ቁጥጥርን በሚመለከት ለሚመለከተው አካል ወቅታዊ ሪፖርት ማቅረብ፡፡

41.<u>የቡና ግብይት ተቆጣጣሪ ሥልጣንና ተግባራት</u>

1.የቡና ግብይት ተቆጣጣሪ በአዋጁ፣በዚህ ደንብ እና ለወደፊት በሚወጣ መመሪያ ስለቡና ግብይት ቁጥጥር የተደነገጉ ድንጋጌዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

ሀ) ወደ ማንኛውም የቡና ማዘጋጃና ማዘጋጃ ኢንዱስትሪ ወይም የአገልግሎት ሰጪ መሥሪያ ቦታ በሥራ ሰዓት የመግባት፣ ወካይ የቡና ናሙና የመውሰድ፣ የማጣራት፣ ሰነዶችን የመመልከትና ኮፒ የመውሰድ፣ ፎቶግራፍ የማንሳት፣

ለ) ከቡና አቅራቢ ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም ወደ ወጪ ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ የሚጓጓዝ ቡና ሲጫን በጥራት፣ በእርጥበት መጠኑ እና በቡና ዓይነቱ መዘጋጀቱን የማጣራት፣

ሐ) በቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪዎች እና በመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከላት የሚቀርበውን ቡና ግብይት የመቆጣጠር፣

መ) የአቅርቦትና የወጪ ቡና ክምችት መጠን፣ አያያዝ፣ አስተሻሸግና ማጓጓዝ ሂደት የመከታተልና መቆጣጠር፣

ሠ) አስፈላጊ በሆነበት ጊዜና ወቅት በቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪዎች ተገኝቶ የቡና ክምችት ቆጠራ የማካሄድ፣

ረ) የወጪ ቡና ሽያጭ በውሉ መሠረት መፈጸሙን የመቆጣጠር እና በውሉ መሠረት በአልተፈጸመ ጊዜ አጣርቶ እርምጃ እንዲወሰድ የማድረግ፣

ሰ) በልማትና ግብይት ትስስር የሚፈጸመውን የቡና ግብይት ሂደትና አፈጻጸም የመከታተልና የመቆጣጠር፣

ሸ) የሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና ጅምላና ችርቻሮ ንግድን የመቆጣጠር፣

ቀ) በየደረጃው የሚጓጓዝ የአቅርቦት፣ የሀገር ውስጥ ፍጆታና የወጪ ንግድ ቡና አጣርቶ በፕሎምፕ በማሸግ የመሸኘት፣

በ) ቡና የሚያጓጉዝ ተሽከርካሪ በማስቆም መፈተሽና አግባብነት ያላቸው ሠነዶች እንዲቀርቡለት የመጠየቅ፣ እና

ተ) በኬላ ላይ የህገወጥ ቡና ንግድና ዝውውር ቁጥጥር የማካሄድ፣

2.የቡና ግብይት ተቆጣጣሪ ህጉን በመጣስ ህገወጥ የቡና ግብይት ድርጊት ተፈጽሟል ብሎ በበቂ ሁኔታ ሲጠረጠር አግባብነት ባለው ህግ መሠረት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ወይም አስቸኳይ ሁኔታ ሲኖር ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ ከፍትህ አካላት ወይም ከፀጥታ አካላት ጋር በመተባበር ደረሰኝ ሰጥቶ ቡናውን ይይዛል ወይም የቡናውን ናሙና ወስዶ ቡናው የተከማቸበትን ቦታ ያሽጋል፡፡

3. የቡና ግብይት ተቆጣጣሪ ከጠቅላላ የመጫን ክብደቱ መጠን ግማሽና ከዚያ በላይ ቡና በመጫን ተሽከሪካሪው ህገወጥ ተግባር መፈፀሙን በበቂ ምክንያት ሲያምን እና አግባብነት ባለው የወንጀል ሥነ ሥርዓት ህግ መሠረት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ወይም አስቸኳይ ሁኔታ ሲኖር ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ ከፍትህ አካላት ወይም ከፀጥታ አካላት ጋር በመተባበር የመረከቢያ ደረሰኝ በመስጠት ተሽከርካሪውን ይይዛል፤
4. የቡና ግብይት ተቆጣጣሪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2 እና (3 መሠረት ስለወሰደው እርምጃ ወዲያውኑ ለባለስልጣኑ ወይም አግባብ ላለው የክልል አካል ሪፖርት ያድርጋል፤ በዚህ ደንብ መሠረት መወሰድ ስላለባቸው ተከታይ እርምጃዎች ከባለስልጣኑ ወይም አግባብነት ካለው የክልሉ አካል የሚሰጠውን መመሪያ ይፈጽማል፡፡
5. የቡና ግብይት ተቆጣጣሪ የቡና ግብይት ቁጥጥርን በሚመለከት ለሚመለከተው አካል ወቅታዊ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

42. <u>ህገ ወጥ ድርጊቶችን ስለ መጠቆም</u>

1. ማንኛውም ሰው በቡና አዘገጃጀት፣ ክምችት፣ ማጓጓዝ ወይም ግብይት ሂደት ህገወጥ ድርጊት መፈጸሙን ሲያውቅ በአካባቢው ለሚገኝ የቡና ግብይት ተቆጣጣሪ ወይም ለባለስልጣኑ ወይም አግባብነት ላለው የክልል አካል ወይም የጸጥታ አካላት በአካል፣ በጽሁፍ፣ በኤሌክትሮኒክስ መልዕክት መጠቆም ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ጥቆማ አቅርቦ ሕገወጥ ድርጊት የተፈጸመበትን ቡና ያስያዘ እና የያዘ ማንኛውም ሰው በዚህ ደንብ አንቀጽ 43 (11) (ለ) መሠረት የጠቋሚ ወይም የያዥ አበል ይከፈለዋል፡፡

43. <u>ስለተያዘ ቡና</u>

1. በበቂ ጥርጣሬ ህገወጥ ነው ተብሎ የተያዘ ቡና ተጣርቶ ውሳኔ እስከሚያገኝ ድረስ:-
   ሀ) ቀይ እሸት ቡና ከሆነ በ60 ሰዓት ውስጥ በአቅራቢያው ወደ ሚገኝ የመጀመሪያ ደረጃ የቡና ግብይት ማዕከል ቀርቦ በዕለቱ መሸጫ ዋጋ ተሸጦ በወረዳው በሚገኝ አግባብ ባለው የክልል አካል ለዚሁ ተብሎ በተከፈተ ዝግ የባንክ ሒሳብ መቀመጥ አለበት፡፡

ለ) ጀንፈል ቡና ከሆነ በወረዳው ወይም በከተማ አስተዳደሩ በሚገኝ አግባብ ባለው የክልል አካል በተዘጋጀ መጋዘን መጠኑ ታውቆ መቀመጥ አለበት፡፡

ሐ) የአቅርቦት ወይም የወጪ ገበያ ቡና ከሆነ በ48 ሰዓት ውስጥ በአቅራቢያው ወደሚገኝ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ መጋዘን መጠንና ደረጃው ተለይቶ በህጋዊ ደረሠኝ ገቢ ሆኖ መቀመጥ አለበት፡፡

መ) ለቡናው ባለቤት ወይም ተወካይ የተያዘው ቡና ዓይነትና መጠን ተገልጾ እንደዚሁም የአቅርቦት ወይም የወጪ ገበያ ቡና ከሆነ የቡናው ደረጃም ጭምር ተገልጾ ህጋዊ ደረሰኝ መሰጠት አለበት፡፡

2.በህገወጥ መንገድ ቡና በመጫን ወይም በማጓጓዝ በበቂ ሁኔታ ተጠርጥሮ የተያዘ ተሽከርካሪ ተጣርቶ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ በአቅራቢያው በሚገኝ የሚመለከተው የፖሊስ አካል ተይዞ መቆየት አለበት፡፡

3.ማንኛውም አሽከርካሪ እንዲጭን ከተፈቀደለት ቡና ውጪ በየትኛውም የተሽከርካሪው አካል ላይ ተጨማሪ ቡና ወይም ቡና ያልሆነ ሌላ ጭነት ወይም ምርት አዳብሎ ጭኖ የተያዘ እንደሆነ በተጨማሪነት ለተጫነው ቡና ምርት እንደ አግባብነቱ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 (ለ) እና (ሐ) በተደነገገው መሰረት ይፈጸማል፡፡

4.ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ በተደነገገው መሠረት ህገወጥ ተግባር የተፈጸመበት ቡና ወይም ተሽከርካሪ የያዘ ሰው ለባለስልጣኑ ወይም አግባብ ላለው የክልል አካል ለውሳኔ አስፈላጊ የሆነ መረጃና ማስረጃ አያይዞ በ48 ሰዓት ውስጥ ማቅረብ አለበት፡፡

5.በዚህ ደንብ መሠረት ስለተያዘ ቡና፣ ተሽከርካሪ፣ ተጨማሪ ጭነት ወይም ምርት በሚመለከት ቅሬታ ያለው ማንኛውም ሰው ቅሬታውን በማስረጃ አስደግፎ በሚከተለው አግባብ ሊያቀርብ ይችላል:-

ሀ) ቀይ እሸት ወይም ጀንፈል ቡና ወይም ከዚህ ጋር የተያያዘ ተሽከርካሪ፣ ተጨማሪ ጭነት ወይም ምርት ሲሆን ደረሰኝ ከተቀበለበት ቀን ጀምሮ በሦስት የሥራ ቀናት ውስጥ በወረዳ ወይም በከተማ አስተዳደር ደረጃ ላለ ባለስልጣን ወይም አግባብ ላለው የክልል አካል ሊያቀርብ ይችላል፣

ለ) የአቅርቦት ወይም የወጪ ገበያ ቡና ወይም ከዚህ ጋር የተያያዘ ተሽከርካሪ፣ ተጨማሪ ጭነት ወይም ምርት ሲሆን ደረሰኝ ከተቀበለበት ቀን ጀምሮ በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ለዞን ወይም በዞን ደረጃ ለሚገኝ የከተማ አስተዳደር ባለስልጣን ወይም አግባብ ላለው የክልል አካል ቅሬታውን ሊያቀርብ ይችላል፣

6. የተያዘ ቡናን፣ ተሽከርካሪን፣ ተጨማሪ ጭነትን ወይም ምርትን አስመልክቶ የሚሰጥ ውሳኔ በባለስልጣኑ ወይም አግባብ ባለው የክልል አካል የበላይ ኃላፊ በሚመራ ኮሚቴ ይሆናል፡፡

7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5 (ሀ) እና (ለ) መሠረት ቅሬታ የቀረበለት አካል የቀረቡለትን መረጃዎችና ማስረጃዎች መርምሮ:-

ሀ) ቀይ እሸት ወይም ጀንፈል ቡና ወይም ከዚህ ጋር የተያያዘ ተሽከርካሪ፣ ተጨማሪ ጭነት ወይም ምርት ሲሆን የቅሬታ ማቅረቢያው ቀን በተጠናቀቀ በሁለት የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠትና ወዲያውኑ ለተያዘበት ሰው በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፣

ለ) የአቅርቦት ወይም የወጪ ገበያ ቡና ወይም ከዚህ ጋር የተያያዘ ተሽከርካሪ፣ ተጨማሪ ጭነት ወይም ምርት ሲሆን የቅሬታ ማቅረቢያው ቀን በተጠናቀቀ ሦስት የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠትና ወዲያውኑ ለተያዘበት ሰው በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፣

ሐ) የውሳኔውን ግልባጭ ከነማስረጃው ለባለስልጣኑ ወይም አግባብ ላለው የክልል አካል በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ማድረስ አለበት፡፡

8. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (7) በተሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ያለው ሰው:-

ሀ) ቀይ እሸት ወይም ጀንፈል ቡና ወይም ከዚህ ጋር የተያያዘ ተሽከርካሪ፣ ተጨማሪ ጭነት ወይም ምርት ከሆነ በዞን ደረጃ ላለው አግባብ ያለው የክልል አካል፣

ለ) የአቅርቦት ቡና ሆኖ ቅሬታ አቅራቢው ቡና አቅራቢ ከሆነ አግባብ ላለው የክልል አካል፣

ሐ) የአቅርቦት ወይም የወጪ ገበያ ቡና ሆኖ ቅሬታ አቅራቢው ቡና ላኪ ከሆነ ለባለስልጣኑ፤ በአምስት የሥራ ቀናት ቅሬታውን ማቅረብ አለበት፡፡

9.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (8 መሠረት ቅሬታ የቀረበለት ባለሥልጣን ወይም አግባብ ያለው የክልል አካል አቤቱታውን በአምስት የስራ ቀናት ውስጥ መርምሮ:-

ሀ) የተሰጠውን ውሳኔ የሚሽር ከሆነ ወዲያው የተያዘውን ቡና፣ ተሸከርካሪ፣ ተጨማሪ ጭነት ወይም ምርት ወይም የተሸጠበትን ገንዘብ ለአመልካቹ እንዲመለስ ማድረግ አለበት፣

ለ) የተሰጠውን ውሳኔ ካጸናው ወይም ቅሬታ በጊዜ ገደቡ ያልቀረበ እንደሆነ የተሰጠውን ውሳኔ አጽንቶ ለቅሬታ አቅራቢው በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፤

ሐ) በዚህ ንኡስ አንቀጽ (ለ) መሠረት ውሳኔውን ያጸናው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (10) መሠረት በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ለፍርድ ቤቱ አቤቱታ ያልቀረበ ከሆነ የተያዘው ቡና በኢትዮጵያ ምርት ገበያ፤ ተሸከርካሪው ወይም ተጨማሪ ጭነቱ ወይም ምርቱ በግልጽ ጨረታ ተሽጦ ከእነዚህ የሚገኝ ገንዘብ በዝግ የባንክ ሂሳብ እንዲቀመጥ ማድረግ አለበት፡፡

10.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (9) (ለ) የተመለከተውን ውሳኔ የሚቃወም የቡና፣ የተሽከርካሪ፣ የተጨማሪ ጭነት ወይም የምርት ባለቤት ውሳኔው በደረሰው በ60 (ስልሳ የሥራ ቀናት ውስጥ ለሚመለከተው ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ አለበት፡፡

11.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (10) መሠረት አቤቱታ የቀረበለት ፍርድ ቤት እንደ አግባቡ የባለስልጣኑ ወይም አግባብ ያለው የክልል አካል የሰጠውን ውሳኔ:-

ሀ) የሻረው እንደሆነ ቡናውን፣ ተሽከርካሪውን፣ ተጨማሪ ጭነቱን ወይም ምርቱን ወይም የሽያጩን ገንዘብ ለማጓጓዣና ከሽያጭ ጋር የተያያዙ ወጪዎች እንዲቀነሱ ተደርጎ ለባለቤቱ እንዲመለስ ይደረጋል፤

ለ) ያጸናው ወይም ባለቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (10 በተቀመጠ የጊዜ ገደብ ውስጥ አቤቱታ ያላቀረበ እንደሆነ ባለስልጣኑ ወይም አግባብ ያለው የክልል አካል ከማጓጓዝና ከሽያጭ ጋር የተያያዙ ወጪዎችን ተቀናሽ አድርጎ የሽያጭ ገንዘቡ ለማበረታቻነት 20 በመቶ (ሃያ በመቶ) ለጠቋሚ፣ 20 በመቶ (ሃያ በመቶ) ለያዥ እና 20 በመቶ (ሃያ በመቶ) ለባለስልጣኑ ወይም አግባብ ላለው የክልል አካል ለሎጀስቲክስና ለቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ፣ 20 በመቶ (ሃያ በመቶ) ለህገ ወጥ ቡና በመቆጣጠር በቀጥታ ለሚሳተፉ ተቋማት አቅም ግንባታ እና ቀሪው 20 በመቶ (ሃያ በመቶ) ቡናው በተያዘበት አስተዳደር እርከን ለአካባቢ ልማት እንዲውል ያደረጋል፤

ሐ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ለ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ጠቋሚ በሌለበት ሲሆን የሽያጭ ገንዘቡ 30 በመቶ (ሰላሳ በመቶ) ለያዥ፣ 30 በመቶ (ሰላሳ በመቶ) ህገ ወጥ የቡና ንግድና ዝውውር ለመቆጣጠር በቀጥታ ለሚሳተፉ ተቋማት አቅም ግንባታ እንዲውል ይደረጋል፤ አፈጻጸሙ ይህን ደንብ ተከትሎ በሚወጡ መመሪያዎች መሠረት ይሆናል፡፡

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 44.የመተባበር ግዴታ

1.ማንኛውም ሰው ይህን ደንብ በማስፈጸም ረገድ ከባለስልጣኑ ወይም አግባብ ካለው የክልል አካል ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

2.ቡና ግብይት ተቆጣጣሪ በዚህ ደንብ መሠረት ህገወጥ ድርጊት የተፈጸመበትን ቡና ለመያዝ በሚያደርገው እንቅስቃሴ በየደረጃው የሚገኙ የጸጥታ አካላት እንዲሁም የሚመለከታቸው የመስተዳድር አካላት የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

**45.<u>ተሻሩና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ህጎች</u>**

1. የቡና ጥራት ቁጥጥርና ግብይት ደንብ ቁጥር 161/2001 በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡
2. የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ ደንብ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**46.<u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች</u>**

ማንኛውም በቡና ንግድ ወይም በአገልግሎት ሰጪነት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ያለው ሰው ይህ ደንብ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ስድስት ወራት ከባለስልጣኑ ወይም አግባብ ካለው የክልል አካል በዚህ ደንብ መሠረት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማግኘት ያለበት ሲሆን ይህን እስኪያገኝ ድረስ ባለው የጸና የንግድ ፍቃድ ሥራውን ማካሄድ ይችላል፡፡

**47.<u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥቅምት 23 ቀን 2011 ዓ.ም**

**ዶ)ር አብይ አህመድ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**መ) የዱር እንስሳት እና ደኖች**

## አዋጅ ቁጥር 541/1999

## የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ

የዱር እንስሳት ሀብት ባልተቀናጀና አለአግባብ በሆነ አጠቃቀም ምክንያት እየተመናመነ በመምጣቱና ህልውናው አደጋ ላይ በመዉደቁ፤

እስከዛሬ ለዱር እንስሳት እየተደረገ ያለው ጥበቃና እንክብካቤ ውጤታማ ሆኖ ባለመገኘቱ፤

በጥበቃ ቦታዎች አካባቢ የሚኖረውን ሕብረተሰብና የግል ባለሃብቶችን በዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ላይ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ ጠቀሜታው የጎላ ስለሆነ፤

ቀደም ብለው የወጡትና እስከዛሬ የሚሠራባቸው አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች የጊዜውን ተጨባጭ ሁኔታ ያላገናዘቡና አሁን ያለውን ፌዴራላዊ ሥርዓት የተከተሉ ባለመሆናቸው፤

ከዱር እንስሳት ሀብት የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጥቅም በማጎልበት ለድህነት ቅነሳው ስትራቴጂ የሚኖረውን ሚና ማሳደግ የተገባ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገመንግሥት አንቀጽ 55)1)መሠረት የሚከተለው ታዉጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ “የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 541)1999” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

   1. “የዱር እንስሳት” ማለት ከቤት እንስሳ በስተቀር በሕይወት ያለ ወይም የሞተ የጀርባ አጥንት ያለው ወይም የሌለው እንስሳ ነው፡፤

2. "የዱር እንስሳት ሀብት" ማለት በኢትዮጵያ የሚገኙ የዱር እንስሳት ማለት ሲሆን ከአገር ወደ አገር የሚሰደዱና በጊዜያዊ መልክ በኢትዮጵያ የሚኖሩትን ዝርያዎች ይጨምራል፤
3. "የዱር እንስሳ ውጤት" ማለት የማንኛውም የዱር እንስሳ ናሙና ወይም የእንስሳው አካል፣ እንቁላል፣ እጭ፣ ዝባድ፣ ቀንድ፣ ጥርስ፣ ጥፍር፣ ቆዳ፣ ሥጋ፣ ጠጉር፣ ላባ ወይም ጎፍላው ሲሆን ከእነዚህ የተሠሩ ውጤቶችንና ከእንስሳው መኖሪያ አካባቢ የተገኙትን የወፍ ጎጆ፣ እንጨት፣ ሣር፣ ልጣጭ፣ አበባ፣ ማርና የመሳሰሉትን ይጨምራል፤
4. "የዱር እንሰሳ የመኖሪያ አካባቢ" ማለት የየብስ፣ የውሃ አካል ወይም ሁለቱንም የሚያካትት ሆኖ የዱር እንስሳት የሚኖሩበት የዱር እንስሳት የጥበቃ ቦታ ወይም ከጥበቃ ቦታ ውጭ ያለ ስፍራ ነው፤
5. "ሰዉ" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ መሠረት ሕጋዊ ሰውነት የተሰጠው ሰው ነው፤
6. "ራንች" ማለት በግዥ የተገኙ ወይም ከዱር የተሰበሰቡ የዱር እንስሳትን ተንክባክቦ በማሳደግ ጥቅም ላይ ለማዋል የተከለለ ሥፍራ ነው፤
7. "የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታ" ማለት ለዱር እንስሳት ጥበቃ የተከለለ ሥፍራ ሲሆን ብሔራዊ የዱር እንስሳት ጥበቃ ፓርክን፣ የዱር እንስሳት መጠለያዎችን፣ የዱር እንስሳት ጥበቃ ክልሎችን እና የዱር እንስሳት የቁጥጥር አደን ቀበሌዎችን ይጨምራል፤
8. "ብሔራዊ ፓርክ" ማለት የዱር እንስሳትንና ከነዚሁ ጋር የተያያዙትን ሐይቆችንና ሌሎች በውሃ የተሸፈኑ ሥፍራዎችን ጨምሮ ለአካባቢው ውበትና ለሳይንሳዊ እውቀት የሚረዱትን የተፈጥሮ ሃብቶች ለመጠበቅ የሚከለል ቦታ ነው፤
9. "የዱር እንስሳት መጠለያ" ማለት አንዱ ወይም ከዚያ በላይ ለሆኑ ከፍተኛ ትኩረት የተሰጣቸው የዱር እንስሳት ጥበቃ የሚከለል ሥፍራ ነው፤
10. "የዱር እንስሳት ጥብቅ ክልል" ማለት ለዱር እንስሳት ጥበቃ የሚከለል ሥፍራ ሆኖ ስፍራው ለዱር እንስሳት ጥብቃ ከመከለሉ በፊት በክልሉ ውስጥ ሰፍረው የነበሩ ሰዎች የዱር እንስሳቱን እየተንከባከቡ በቦታው እንዲኖሩ የሚፈቀድበት የጥበቃ ቦታ ነው፤

11. “የዱር እንስሳት የቁጥጥር አደን ቀበሌ” ማለት ለዱር እንስሳት ጥበቃ የሚከለልና ቁጥጥር እየተደረገ ሕጋዊ አደን የሚካሄድበት ሥፍራ ነው፤
12. “የዱር እንስሳት ንግድ” ማለት የዱር እንስሳትን ወይም የዱር እንስሳት ውጤቶችን ወደውጭ መላክ ወደአገር ውስጥ ማስገባት መልሶ ወደውጭ መላክ ወይም እነዚህኑ የሚመለከት ማንኛውም ዓይነት የንግድ ልዉዉጥ ነዉ፤
13. “የዱር እንስሳት ቁጥጥር ሠራተኛ” ማለት የዱር እንስሳትና የዱር እንስሳት ውጤቶችን በሚመለከት የሚፈጸሙ ሕገ ወጥ ድርጊቶችን እንዲቆጣጠር በባለስልጣኑ ወይም በሚመለከተው የክልል መንግሥት አካል የተመደበ ሠራተኛ ነው፤
14. “ማደን”ማለት የዱር እንስሳትን ለመግደል፣ ለማቁሰል፣ ለማጥፋት፣ ለማስፈራራት፣ ለማባረር፣ ለመያዝ፣ ለማጥመድ ወይም የዱር እንስሳት ላባ ወይም እንቁላል ለመውሰድ የሚወሰድ እርምጃ ወይም እንቅስቃሴ ነው፤
15. “መሣሪያ” ማለት የዱር እንስሳትን ለመግደል፣ ለመያዝ ወይም እንዳያመልጡ ለማድረግ የሚጠቀሙበት ጥይት የሚተኩስ መሣሪያ፣ ዳርትጋን፣ ወርዋሪ ሚሳየል፣ ፈንጂ፣ ቀስት፣ ዱላ፣ ስለት፣ ወጥመድ፣ መረብ፣ ጉድጓድ፣ መርዝ፣ ኬሚካል፣ወይም ሌላ ማንኛውም ለዚህ ተግባር የሚውል መገልገያ ነው፣
16. “አየር መንኮራኩር” ማለት በሰው ወይም ያለ ሰው የሚንቀሳቀስ ሆኖ በሞተር ኃይል በአየር ላይ በሚነዳ አካል ብቻ ሳይወሰን ማናቸውም አይሮፕላን፣ ሄሊኮፕተር፣ በአየር ላይ ተንሳፋፊ አካል፣ ነው፤
17. “ባለስልጣን” ማለት የኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን ነው”[27]
18. “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47 የተመለከተውን ማንኛውንም ክልል እና አዲስ አበባንና የድሬዳዋ መስተዳድርን ይጨምራል፡፡

3. **ዓላማ**

የዚህ አዋጅ ዋና ዋና ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

1. የኢትዮጵያን የዱር እንስሳት ሀብት መጠበቅ፣ መንከባከብ፣ ማልማትና በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋል፤

[27] በ14)31 (2000 አ. 575 አንቀፅ 11(1 ተሻሻለ፡፡

2. የዱር እንስሳት ሀብትን አጠባበቅ፣ እንክብካቤና አጠቃቀም በሚመለከት መንግሥት በዓለም ዓቀፍ ስምምቶች መሠረት የገባቸውን ግዴታዎች ለመፈጸም እንዲችል ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤
3. በዱር እንስሳት ሀብት ላይ የተመሠረተ ቱሪዝም እንዲስፋፋና ኢንቨስትመንት እንዲበረታታ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፡፡

## ክፍል ሁለት

## የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎችና የሕጋዊ አደን እንቅስቃሴዎች

4. <u>በፌዴራል መንግሥት የሚሰየሙና የሚተዳደሩየዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች</u>
   1. የሚከተሉት የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች በፌዴራል መንግሥት የሚሰየሙና የሚተዳደሩ ይሆናሉ፤
      ሀ) ከፍተኛ የዱር እንስሳት ብዝሀ ሕይወት ስብጥር ኖሯቸው አገራዊና ዓለም አቀፋዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ወካይ ምህዳረ ቀጠናዎች የያዙ ብሔራዊ ፓርኮች፤
      ለ) አገሪቱ በብቸኛ ባለቤትነት የምትታወቅባቸውና ለአልቂት የተቃረቡ ዝርያዎች መኖሪያ የሆኑ ብሔራዊ ፓርኮችና የዱር እንስሳት መጠለያዎች፤
      ሐ) በመልክአ ምድር አቀማመጣቸው በሁለትና ከዚያም በላይ ባሉ ክልሎች ውስጥ የሚገኙ ማናቸውም የዱር እንስሳት የጥበቃ ቦታዎች፤ እና
      መ) ከጎረቤት አገሮች ጋር በስምምት የሚቋቋሙ ማናቸውም የድንበር ዘለል የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች፡፡
   2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ )1) የተመለከቱት የዱር እንስሳት የጥበቃ ቦታዎች የሚሰየሙት የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በሚያቀርበዉ ሃሳብ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይሆናል፡፡[28]
5. <u>በክልሎች የሚሰየሙና የሚተዳደሩ የዱር እንስሳት የጥበቃ ቦታዎች</u>
   1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በፌዴራል መንግሥት እንዲሰየሙና እንዲተዳደሩ ከሚደረጉት በስተቀር ብሔራዊ ፓርኮች፣ የዱር እንስሳት መጠለያዎች የዱር እንስሳት፣ ጥብቅ ክልሎች፣ እና የዱር እንስሳት የቁጥጥር አደን ቀበሌዎች፣ የሚሰየሙትና የሚተዳደሩት በክልሎች ይሆናል፡፡

[28] በ14)31 (2000 አ. 575 አንቀፅ 11(2 መሰረት ተሻሻለ፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከቱት የዱር እንስሳት የጥበቃ ቦታዎች የሚሰየሙት ክልሎች በሚያወጧቸው ሕጎች ይሆናል፡፡

6. <u>በግል ባለሃብቶች የሚተዳደሩ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች</u>

የግል ባለሃብቶች ከፌደራል መንግሥትና ከሚመለከታቸዉ ክልሎች ጋር በሚያደርጓቸዉ የኮንሴሽን ዉሎች መሠረት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 እና 5 የተመለከቱትን የዱር እንስሳት የጥበቃ ቦታዎች እንዲያስተዳድሩ ሊፈቀድላቸዉ ይችላል፡፡

7. <u>በአካባቢ ሕብረተሰብ የሚተዳደሩ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች</u>

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4፣ 5 እና 6 ከተመለከቱት የጥበቃ ቦታዎች ውጭ የሚገኙ የዱር እንስሳት መኖሪያ አካባቢዎች በአካባቢው ሕብረተሰብ እንዲተዳደሩ በሚመለከታቸው ክልሎች ሊፈቀድ ይችላል።

8. <u>የአደን ፈቃድ</u>

1. ባለስልጣኑ ወይም የሚመለከተው የክልል አካል ተግባሩን ለማከናወን በሚያደርገው ሂደት ምክንያት ከሚፈጽመዉ አደን በስተቀር ማንኛውም ሰው የአደን ፈቃድ ሳይዝ የዱር እንስሳትን ማደን የተከለከለ ነው።
2. የአደን ፈቃድ የሚሰጥበት፣ የሚታደስበት፣ የሚታገድበትና የሚሠረዝበት ሁኔታ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት የሚወሰን ይሆናል፡፡
3. ባለስልጣኑ አደንንና የአደን ዘዴዎችን በሚመለከት ደንብ ያወጣል።

9. <u>ለሳይንሳዊ ተግባር የዱር አንስሳትን ወይም ውጤቶቻቸውን የመሰብሰብ ፈቃድ</u>

1. ከታወቀ የሳይንስ ተቋም የተጻፈ የድጋፍ ደብዳቤ በመያዝ የዱር እንስሳት ወይም ዉጤት ለመሰብሰብና ለሳይንሳዊ ተግባር ወይም ትምህርት ለማዋል ለሚጠይቅ አመልካች ባለስልጣኑ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፡፡
2. ባለስልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ )1) የተመለከተውን ፈቃድ የሚሰጠው ከዚህ አዋጅና የዱር እንስሳት ጥበቃን ከሚመለከቱ ሌሎች ሕጎችና ደንቦች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይሆናል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎችና ጥቅሞች

### 10. ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ

1. በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታ ውስጥ የሚደረግ ማንኛውም ኢኮኖሚያዊ የሥራ እንቅስቃሴ የዚህን አዋጅና አዋጁን ለማስፈጸም የሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎችን ድንጋጌዎች በማይቃረን ሁኔታ መካሄድ አለበት፡፡
2. ከዱር እንስሳት ሃብት አጠቃቀም የሚገኘውን ገቢ የፌዴራልና የክልል መንግሥታት የሚጋሩበት መንገድና የአካባቢው ሕብረተሰብ ተጠቃሚ የሚሆንበት ስልት በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

### 11. በዱር እንስሳት ሀብት ላይ የተመሠረተ ቱሪዝም

1. ባለስልጣኑና ክልሎች አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በዱር እንስሳት ሀብት ላይ የተመሠረተ የቱሪዝም ኢንቨስትመንቶችን ያበረታታሉ፡፡
2. ባለስልጣኑ፣ ለክልሎችና ለሌሎች የሚመለከታቸው አካላት በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ውስጥም ሆነ ከእነሱ ዉጪ የሚከናወን የኢኮ-ቱሪዝም ልማት የአካባቢውን ሥነምህዳራዊ ደህንነት እንዳይናጋ ያደርጋሉ።

### 12. በዱር እንስሳትና ውጤቶቻቸው ስለመነገድ

1. እንደአግባቡ ከባለስልጣኑ ወይም ከሚመለከተው የክልል አካል በተገኘ ፈቃድ መሠረት ካልሆነ በስተቀር፣

   ሀ) በዱር አንስሳትና በዱር እንስሳት ውጤት የመነገድ ተግባር ማካሄድ፣

   ለ)ማንኛውንም የተዘጋጀ ወይም ያልተዘጋጀ የዱር እንስሳት ዉጤት በባለቤትነት መያዝ፣ መሸጥ፣ ማስተላለፍ፣ ወደሌላ አገር መላክ ወይም ወደ አገር ውስጥ ማስገባት፣ የተከለከለ ነው።
2. ባለስልጣኑና የሚመለከታቸው የክልል አካላት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ )1) የተጠቀሰውን ፈቃድ የሚሰጡት በዚህ አዋጅና አዋጁን ለማስፈጸም በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች እንዲሁም አገሪቱ አባል በሆነችባቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የተደነገጉትን በመከተል ይሆናል።

## ክፍል አራት

## የባለስልጣኑ ሥልጣንና ተግባር[29]

### 13.የክልሎች ሥልጣንና ተግባር

ክልሎች በዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች ከተሰጧቸው በተጨማሪ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሯቸዋል፤

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 መሠረት የተቋቋሙትን የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ያለማሉ፣ ያስተዳድራሉ፤
2. በሚያስተዳድሯቸው የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎችና ከዱር አንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ውጭ የሚገኙት የዱር እንስሳት ሕገ ወጥ ተግባራት እንዳይፈጸሙባቸው ይከላከላሉ፤ በፌዴራል መንግሥት በሚተዳደሩ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ሕገ ወጥ ተግባራት እንዳይፈጸሙ በመከላከል ረገድም አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋሉ፤
3. በግል ባለሀብቶችና በአካባቢ ሕብረተሰብ የሚተዳሩትን የዱር እንስሳት የጥበቃ ቦታዎች ይቆጣጠራሉ፤
4. በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎችም ሆነ ከጥበቃ ቦታዎች ውጪ በሚገኙ የዱር እንስሳት ሊደርሱ የሚችሉ በሽታዎችን ይከላከላሉ፣ ይቆጣጠራሉ ከአቅም በላይ ሲሆን ለባለስልጣኑ ያሳውቃሉ፤
5. የዱር እንስሳት እርባታና ራንች ፈቃድ ይሰጣሉ፣ ይቆጣጠራሉ፤
6. በሰው ሕይወትና ንብረት ላይ አደጋ በሚያደርሱ የዱር እንስሳት ላይ ተገቢውን ጥናት በማካሄድ ችግሩ የሚቃለልበትንና የሚወገድበትን እርምጃ ይወስዳሉ፣ ከአቅም በላይ ሲሆን ለባለስልጣኑ ያቀርባሉ፤
7. ከውጭ ቱሪስቶች በስተቀር በሌሎች ሰዎች ለሚካሄድ አደን ፈቃድ ይሰጣሉ፤
8. የዱር እንስሳትና የዱር እንስሳት ውጤቶች በባለቤትነት ለመያዝ፣ ለማስተላለፍና በአገር ውስጥ ለመሸጥ የሚያስችል ፈቃድ ይሰጣሉ።

### 14.የዱር እንስሳት ቁጥጥር ሠራተኛ ሥልጣን

የዱር እንስሳት ቁጥጥር ሠራተኛ የሚከተለው ሥልጣን ይኖረዋል፣

1. የዱር እንስሳት ወይም የዱር እንስሳት ውጤት ይዞ የተገኘውን ማንኛውንም ሰው እነዚህኑ ለመያዝ ያስቻለውን ሕጋዊ ፈቃድእንዲያሳይ የመጠየቅ፤

[29]ነባሩ አንቀጽ 13 በ14)31 (2000 አ. 575አንቀፅ 11(4 መሰረት ተሰርዞ ነባሮቹ አንቀጽ 14፣15፣16፣17፣18፣ 19 እና 20 እንደቅደም ተከተላቸው አንቀጽ 13፣14፣15፣16፣17፣18 እና 19 ሆነዋል፡፡

2. ሕግን በመተላለፍ በይዞታ ሥር የተደረጉ የዱር እንስሳት ወይም የዱር እንስሳት ውጤቶች ተደብቀዋል ብሎ ለማመን በቂ ምክንያት ሲኖር ያለፍርድ ቤት ማዘዣ ወደ ማንኛውም ሰው መሬት፣ ሕንፃ፣ ድንኳን፣ ተሽከርካሪ፣ የአየር መንኩራኩር ወይም ጀልባ ውስጥ የመግባትና የመፈተሽ እንዲሁም ሻንጣ ወይም እሽግ የመበርበር፤
3. ሕግን በመተላለፍ በይዞታ ሥር የተደረጉ የዱር እንስሳትና የዱር እንስሳት ውጤቶችን እንዲሁም ጥፋቱ የተፈጸመባቸውን መሣሪያዎች በዚህ አዋጅ አንቀጽ 16)2) መሠረት እንዲወረሱ ለማድረግ እንዲቻል በቁጥጥር ሥር የማድረግና ባለስልጣኑ ወይም የሚመለከተው የክልል አካል ባወጣው የመመዝገቢያ ቅጽ መሠረት ተገቢውን ደረሰኝ ሰጥቶ የመረከብ፤
4. የዚህን አዋጅ አንቀጽ 16 ድንጋጌዎች በመተላለፍ ጥፋት ሲፈጽም ያገኘውን ሰው ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ ይዞ ለሚመለከተው ሕግ አስከባሪ አካል ማቅረብ፡፡
5. ማንኛውም ሰው ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

15. <u>ቅጣት</u>

1. በወንጀለኛ ሕግ መሠረት የበለጠ ቅጣት የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር፣

   ሀ) ማንኛውም ሰው፣

   (i) ሕገወጥ የዱር እንስሳት አደን ወይም ንግድ ድርጊት ከፈጸመ፣

   (ii) በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ውስጥ ያልተፈቀዱ ተግባሮች ካከናወነ ወይም በማናቸውም አኳኋን በነዚሁ ላይ ጉዳት ካደረሰ፣ ወይም

   (iii) የዱር እንስሳትን ወይም የዱር እንስሳት ውጤቶችን ያለፈቃድ ይዞ ከተገኘ፣

   ከብር 5000 ሺ. በማያንስና ከብር 30,000 ሺ. በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከአንድ ዓመት በማያንስና ከአምስት ዓመት በማይበይልጥ እስራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

ለ) የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም አዋጁን ለማስፈጸም የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን በመተላለፍ ሌሎች ጥፋቶችን የፈጸመ ማንኛውም ሰው ከብር 500 በማያንስና ከብር 3000 በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከአንድ ወር በማያንስና ከስድስት ወር በማይበልጥ እስራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1 መሠረት ፍርድ ቤት ቅጣት ሲወስን ከቅጣቱ በተጨማሪ ከጥፋቱ የተገኘው የዱር እንስሳ ወይም የዱር እንስሳ ውጤት እንዲሁም ጥፋቱ የተፈጸመበት መሣሪያ ውርስ እንዲሆን ይወሰናል፡፡
3. ባለስልጣኑ ወይም የሚመለከተው የክልል አካል፣
   ሀ) የተወረሰውን የዱር እንስሳ ወይም የዱር እንስሳ ውጤት እንደአግባቡ መሸጥ፣ ለሳይንስ ተግባር፣ ለትምህርት ተቋም ማስተላለፍ ወይም ከጥቅም ውጭ እንዲሆን ማድረግ ይችላል፡፡
   ለ) የተወረሰውን መሣሪያ እንደአግባቡ ለሚመለከተው መንግሥታዊ አካል ማስተላለፍ ወይም ከጥቅም ውጭ እንዲሆን ማድረግ፣ይችላል፡፡

16.<u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ባለስልጣኑ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

17.<u>የተሻሩና ጸንተው የሚቆዩ ሕጎች</u>

1. የሚከተሉት ሕጎች በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፤
   ሀ) የደንና ዱር እንስሳት ጥበቃና ልማት አዋጅ ቁጥር 192/1972 (እንደተሻሻለ)፤
   ለ) የዱር እንስሳት ጥበቃ ደንብ ቁጥር 416/1964 (እንደተሻሻለ)፡፡
2. የሚከተሉት ሕጎች በዚህ አዋጅ መሠረት እንደወጡ ተቆጥረው የጸኑ ይሆናሉ፤[30]
   ሀ) የአዋሽ ብሔራዊ የዱር እንስሳት ጥበቃ ፓርክ ማቋቋሚያ ትዕዛዝ ቁጥር 54/1961
   ለ) የሰሜን ብሔራዊ የዱር እንስሳት ጥበቃ ፓርክ ማቋቋሚያ ትዕዛዝ ቁጥር 59/1962፡፡

18.<u>ተፈጻሚ ስለማይሆኑ ሕጎች</u>

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸዉም ሕግ፣ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተመለከቱ ጉዳዮች አይኖረውም፡፡

[30]ይህ ንዑስ አንቀፅ የአዋሽ እና የሰሜን ብሔራዊ ፓርኮች ማቋቋሚያ ህጎችበ21/27 (2007) ደ. 337 እና21/12 (2007) ደ. 329 መሰረትበየራሳቸውማቋቋሚያህግ የወጣላቸው ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

19.<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ቀን 1999 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**ደንብ ቁጥር 163)2001**

## የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባርን ለመወሰን በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 471/1998 አንቀጽ 5 እና በዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 541/1999 አንቀጽ 17(1) መሠረት ይህንን ደንብ አዉጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 163/2001" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠዉ ካልሆነ በቀር በዚህ ደንብ ዉስጥ፤

   1. "አዋጅ" ማለት የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 541/1999 ነዉ፡፡
   2. በአዋጁ አንቀጽ 2 ሥር ለተመለከቱት ቃላት የተሰጠው ትርጓሜ ተፈጻሚ ይሆናል፤
   3. "ሥልጣን የተሰጠው ሰራተኛ" ማለት የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር፣ የመምሪያ ኃላፊ፣ የዱር እንስሳት የጥበቃ ቦታዎች ኃላፊ፣ የዱር እንስሳት ኤክስፐርት፣ የዱር እንስሳት ጥበቃ ስካዉት፣ የዱር እንስሳትና ዉጤቶቻቸዉ ዝዉዉር ቁጥጥር ሠራተኛ፣ የዱር እንስሳት ስካዉት ረዳት ወይም በዚህ ደንብ ዉስጥ የተመለከቱትን ተግባራት እንዲሠራ ባለሥልጣኑ በጽሑፍ የመደበዉ ሌላ ሰው ነው፤
   4. "የአካባቢ ሕብረተሰብ የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ቦታ" ማለት በባለሀብት በኮንሴሽን ወይም በመንግሥት ያልተያዘ በአካባቢው ሕብረተሰብ የዱር እንስሳት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም ሥራ የሚሠራበት ሥፍራ ነው፤

5. “ፈቃድ” ማለት በዱር እንስሳትና ውጤቶቻቸው ላይ ለሚደረግ ማንኛውም ሕጋዊ ንግድ ወይም ለባለቤትነት የሚሰጥ ፈቃድ የዱር እንስሳትን የማደን፣ የማሳደን፣ የማርባት የመያዝ፣ የጉፍላ ሥራ የመሥራት፣በባለቤትነት የመያዝ፣ የዱር እንስሳትን በህይወት የመነገድ፣የዱር እንስሳትን ፊልም የመቅረጽ ፈቃድን ያካትታል፤
6. “ነጋዴ” ማለት በዱር እንስሳት ውጤትና ከዱር እንስሳት ውጤት በተሠሩ ዕቃዎች የንግድ ተግባር እንዲያከናውን ባለሥልጣኑ የፈቀደለት ሰው ሲሆን በዱር እንስሳት ውጤት ልዩ ልዩ ቅርጾች የሚያዘጋጅ፣ ለትርኢት የሚያሰናዳ ወይም ከአደን ውጤቶች ዕቃን የሚያዘጋጅ ወይም በሌላ መንገድ የሚሠራን ሰው ይጨምራል፤
7. “ሳይተስ” ማለት ህልውናቸው ለአልቂት አደጋ የተጋለጡ የዱር እንስሳትና እፅዋት ንግድ ዓለም አቀፍ ስምምነት ነው፤
8. “ዝርያ” ማለት በተፈጥሮአዊ ሥነ አካልና ዘረመል አመዳደብ መሠረት በአንድ ሥነ-ሕይወት ምድብ ውስጥ አባል ሆኖ የተመደበ የዱር እንስሳ ዓይነት ሲሆን ንዑስ ዝርያዎችንም ይጨምራል፤
9. “ባለሥልጣን” ማለት የኢትዮጵያ ዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን ነው፤
10. “ገቢ” ማለት ከዱር እንስሳት አደን፣ ከፊልም ቀረጻ፣ ከዱር እንስሳትና ከዱር እንስሳት ውጤት ንግድ፣ ከዱር እንስሳት ጥናትና ምርምር፣ ከጥበቃ ቦታዎች ጉብኝትና ካምፕ፣ ከልዩ ልዩ ፈቃዶችና የፈቃድ ዕድሳት የሚሰበሰብ ገቢ ነው፤
11. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል።

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የዱር እንስሳት የጥበቃ ቦታዎች አስተደደር</u>

### 3. <u>የዱር የጥበቃ ቦታዎች ዳር ድንበር</u>

ብሔራዊ ፓርኮች፣ የዱር እንስሳት ጥብቅ ክልሎች፣ የዱር እንስሳት መጠለያዎች፣ ቀበሌዎች እና የቁጥጥር አደን የሕብረተሰብ የዱር እንስሳት ልማት፣ጥበቃና አጠቃቀም ቦታዎች ዳር ድንበር ቀደም ሲል የነበራቸውን ዳር ድንበር መሠረት ያደረገ ወይም ካለው ነባራዊ ሁኔታ አንጻር ሥርዓት አያያዛቸውን ለማሻሻል በፌዴራል መንግሥትና በክልሎች የሚዘጋጁ ዳር ድንበሮችን መሠረት ያደረገ ይሆናል፡፡

4. **<u>በፌደራልና በክልል መንግስት የሚተዳደሩ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች</u>**

   1. በአዋጁ አንቀጽ4 ንዑስ አንቀጽ (1) በተደነገገው መሥፈርት መሠረት የሰሜን ተራራዎች ብሔራዊ ፓርክ፣ የባሌ ተራራዎች ብሔራዊ ፓርክ፣ የነጭሣር ብሔራዊ ፓርክ፣ የኦሞ ብሔራዊ ፓርክ፣ የአብያታ ሻላ ሐይቆች ብሔራዊ ፓርክ፣ አዋሽ ብሔራዊ ፓርክ፣ የሰንቀሌ ቀርኬዎች መጠለያ፣ ባቢሌ የዝሆኖች መጠለያ፣ ጋምቤላ ብሔራዊ ፓርክ፣ አላጥሽ ብሔራዊፓርክ፣ ቃፍታ ሽራሮ ብሔራዊ ፓርክ እና ገራይሌ ብሔራዊ ፓርክ በባለሥልጣኑ የሚተዳደሩ ይሆናሉ፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ባለሥልጣኑ ስልጣኑን በውክልና አግባብ ላላቸው የክልል አካላት ሊሰጥ ይችላል፡፡
   2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተመለከቱት ውጭ የሆኑ የዱር እንስሳት የጥበቃ ቦታዎች በክልሎች ወይም በአካባቢው ሕብረተሰብ የሚተዳደሩ ይሆናሉ።

5. **<u>በብሔራዊ ፓርኮች፣ በዱር እንስሳት መጠለያዎችና በዱር እንስሳት ጥብቅ ክልሎች ዉስጥ እንዳይከናወኑ ስለተከለከሉ ተግባራት</u>**

   1. በዚህ ደንብ ውስጥ በተመለከተው መሠረት ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም ሰው በብሔራዊ ፓርክ፣የዱር እንስሳት መጠለያ ወይም በዱር እንስሳት ጥብቅ ክልል ውስጥ ቀጥሎ የተመለከቱትን ድርጊቶች መፈፀም የተከለከለ ነው፤

      ሀ) ማናቸውንም የጦር መሣሪያ ይዞ መገኘት ወይም ማስተላለፍ፤

      ለ) ማደን ወይም ዓሣ ማጥመድ፤

      ሐ) ማናቸውንም ተሽከርካሪ፣ የአየር መንኮራኩር ወይም ጀልባ ማንቀሳቀስ፤

      መ) ማናቸውንም ተፈጥሮአዊ፣ ወይም ሰው ሠራሽ ነገር ማንሣት፣ ማወክ፣ ማበላሸት ወይም ማጐሳቆል፤

      ሠ) የግብርና ሥራ ማካሄድ ወይም መሬት ለእርሻ ተግባር ማዘጋጀት፤

      ረ) የቤት እንስሳትን ለግጦሽና ለውሃ ማሠማራት፤

      ሰ) ማናቸውንም የቤት እንስሳት ወይም የዱር እንስሳ ወደ ቦታው ማስገባት፣ ማሳለፍ ወይም እንዲሠማራበት ማድረግ፤

      ሸ) የማዕድን ፍለጋ ወይም ቁፋሮ ማካሄድ፤

      ቀ) ማናቸውንም እፅዋት መትከል፣ መቁረጥ፣ መፍለጥ፣ ማንሣት፣ መውሰድ፣ ማበላሸት ወይም ማስተላለፍ፤

      በ) እሳት ማቀጣጠል ወይም ለማቀጣጠል ሙከራ ማድረግ፤

ተ) የንብ እርባታ ማካሄድ፣ማር መቁረጥ ወይም የዱር እንስሳት ውጤት መውሰድወይም ለመውሰድ መሞከር፤

ቸ) የመንገድ ወይም የሌላ ግንባታ ሥራ ማካሄድ ወይም የነበረውን የተፈጥሮ አቀማመጥ ማበላሸት ወይም መረበሽ፤

ኀ) ማናቸውንም ፀረ-ተባይ ወይም ፀረ-አረም ኬሚካል መጠቀም፣ መርጨት፣ መጣልወይም ይዞ መገኘት፤

ነ) ማንኛውም እቃ መሸጥ ወይንም ለሽያጭ ማቅረብ ወይም አገልግሎት መስጠት፤

ኘ) ማንኛውንም መግለጫ ወይም ማስታወቂያ መለጠፍ፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1 የተደነገገው ቢኖርም ባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው የክልል መንግሥት አካል በጽሁፍ በሚፈቅደው መሠረት ቀጥሎ የተዘረዘሩት ድርጊቶች በብሔራዊ ፓርክ ወይም በዱር እንስሳት መጠለያ ውስጥ ሊከናወኑ ይችላሉ፤

ሀ) የተፈቀደላቸው አስጎብኚዎችና ቱሪስቶች ወደ ብሔራዊ ፓርክ ወይም የዱር እንስሳት መጠለያ ውስጥ ለመግባትና ለመቆየት እንዲሁም በዚህ ደንብ መሠረት በወጣ መመሪያ የተፈቀዱ ድርጊቶችን ለመፈጸም ይችላሉ፤

ለ) የተፈቀደላቸው ባለሙያ ፎቶግራፍ አንሺዎች፣ ደራሲዎችና ሠዓሊዎች ወደ ብሔራዊ ፓርክ ወይም የዱር እንስሳት መጠለያ ውስጥ ለመግባትና ለመቆየት እንዲሁም በየሙያቸው የሚፈልጉትን ተግባር ለማከናወን ይችላሉ፤

ሐ) ሥልጣን የተሰጣቸው ሠራተኞች ኃላፊነታቸውን ለመወጣት ከነቤተሰቦቻቸው ወደ ብሔራዊ ፓርክ ወይም የዱር እንስሳት መጠለያ ውስጥ ለመግባትና ለመኖር ይችላሉ፤

መ) ሥልጣን የተሠጣቸው ሠራተኞችና የተፈቀደላቸው ተመራማሪ ሳይንቲስቶች በዚህ ደንብና በደንቡ መሠረት በወጡ መመሪያዎች መሠረት የዱር እንስሳት ሀብት ውጤትን መውሰድ፣ እጽዋት መቁረጥ ወይም ማቃጠል፣ ተሽከርካሪዎች ማንቀሳቀስና የግንባታ ሥራ ማካሄድ ይችላሉ፤

ሠ) በብሔራዊ ፓርኮች እና በዱር እንስሳት መጠለያዎች አካባቢ በሚኖረው ሕብረተሰብና በፓርኩ ወይም መጠለያው ማኔጅመንት መካከል በሚደረግ ስምምነት መሠረት እንደ ንብ ማነብና ማር መቁረጥ፣ ሣር አጭዶ መውሰድ እና ለባህላዊ መድኃኒትየሚውል ዕፅዋት መሰብሰብ የመሰለ የተፈጥሮ ሀብት ወቅታዊ አጠቃቀም ቁጥጥር እየተደረገበት እንዲከናወን ሊፈቀድ ይችላል፤

ረ) አገራዊ ጠቀሜታ ያላቸው የማዕድን ፍለጋና ሌሎችም የልማት ሥራዎች አስፈላጊ ሆነው ሲገኙ ከዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ተግባራት ጋር ተጣጥመው ሊከናወኑ ይችላሉ፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው የክልል መንግሥት አካል፣

ሀ) በጥብቅ ክልል ውስጥ ለሥራ የተሠማሩ የመንግስት ሠራተኞች ከነቤተሰቦቻቸው እና ሳይንሳዊ ምርምር የሚያካሂዱ ሰዎች በዱር እንስሳት ጥብቅ ክልሉ ውስጥ በጊዜያዊነት ለመኖር እንዲችሉ፣ እና

ለ) ሥፍራው የዱር እንስሳት ጥብቅ ክልል ከመሆኑ በፊት በቦታው ላይ ሠፍረው የነበሩት ሰዎች በዚያው መኖር እንዲችሉ፣ መፍቀድ ይችላል፡፡

4. በዱር እንስሳት ጥብቅ ክልል ውስጥ ለመኖር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 (ለ መሠረት የተፈቀደላቸው ሰዎች በክልሉ ውስጥ የቀድሞ ይዞታቸውን ሳያስፋፉ ለማረስ፣ ከብቶቻቸውን ለማስጋጥና ውሃ ለማጠጣት እና ንብ ለማርባት ይችላሉ፡ ፡ ሆኖም የዱር እንስሳት ጥብቅ ክልሉን የሚያስተዳድረው አካል ክልሉን ለተሻለ አያያዝ ከፈለገው ሌላ ምትክ ቦታ ተዘጋጅቶላቸው እንዲሰፍሩ ይደረጋል፡፡

6. <u>የዱር እንስሳትን ስለማደን</u>

1. በዚህ ደንብ መሰረት የቁጥጥር አደን ቀበሌውን በመጥቀስ በሚሰጥ ፈቃድ መሠረት ካልሆነ በስተቀር በቁጥጥር በሚታደንበት ቀበሌም ሆነ በአካባቢ ህብረተሰብ የዱር እንስሳት ልማት፣ አጠቃቀም ቦታ ወይም በሌላ ማናቸውም የዱር እንስሳት መከማቻ ቦታ የዱር እንስሳትን ማደን የተከለከለ ነው፡፡

2. ባለሙያ አሳዳኝና የባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው ክልል የአደን ተቆጣጣሪ በሌሉበት አደን ማከናወን የተከለከለ ነው፡፡

3. ክልሎች እና ባለሥልጣኑ የቁጥጥር አደን ቀበሌዎችን ዳር ድንበር በመከለል በግልጽ ጨረታ አወዳድረው ለአሳዳኝ ድርጅቶች ከአምስት ዓመት ለማይበልጥ ጊዜ በኮንሴሽን ሊሰጡ ይችላሉ፡፡

4. ለአንድ አሳዳኝ ድርጅት በኮንሴሽን በተሰጠ የቁጥጥር አደን ቀበሌ ውስጥ ከባለይዞታው ፈቃድ ውጪ ሌላ አሳዳኝ ድርጅት እንዲያሳድን አይፈቀድለትም፡
5. የአሳዳኝ ድርጅት ፈቃድ በየዓመቱ ከሐምሌ 1 እስከ 30 ባሉት ቀናት ውስጥ መታደስ አለበት፡፡
6. የቁጥጥር አደን ቀበሌ ኮንሴሽን ስምምነት ከሚከተሉት ምክንያቶች ባንዱ ሊቋረጥ ይችላል፤
   ሀ) ለተጨማሪ ጊዜ ካልተራዘመ በስተቀር የኮንሴሽን ዘመኑ ሲያበቃ፤
   ለ) አሣዳኝ ድርጅቱ ያልተፈቀደለትን ወይም ከተሰጠው ኮታ በላይ የዱር እንስሳ አሣድኖ ከተገኘ፤
   ሐ) አሣዳኝ ድርጅቱ በኮንሴሽን ስምምነቱ መሠረት መክፈል የሚገባውን ዓመታዊ ክፍያ በወቅቱ ሳይፈጽም ከቀረ፤
   መ) አሣዳኝ ድርጀቱ የኮንሴሽን ስምምነቱን ግዴታዎች በተለይም በያዘው የቁጥጥር አደን ቀበሌ ውስጥ ለተፈጥሮ ሀብት መደረግ ያለበትን እንክብካቤ ካላደረገና ግዴታዎቹን ሳያከብር ከቀረ፡፡

7. <u>**የአካባቢ ሕብረተሰብ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች**</u>

1. የአካባቢ ሕብረተሰብ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎችን ሕብረተሰቡ ያስተዳድራል፣ ያለማል፣ ይጠቀማል፡፡
2. የአካባቢው ሕብረተሰብ በኢኮቱሪዝም ሥራዎች ይሳተፋል፤ የሚገኘውን ገቢ ለሕብረተስቡ ጥቅም ያውላል።
3. የአካባቢው ሕብረተሰብ ዓመታዊ ኮታን በሚመለከተው አካል በማፀደቅ በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታው ውስጥ የሚገኙትን የዱር እንስሳት ለሕጋዊ አዳኝ ሊሸጥ ይችላል፤ ገቢውንም የሕብረተሰቡን መሠረታዊ ፍላጐት ለማሟላት ያዉላል፡፡
4. የአካባቢው ሕብረተሰብ ፣
   ሀ) የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታውን ለማሻሻል የሚረዱ የልማት ሥራዎችን ከራሱ ወይም ከሌሎች ምንጮች በሚገኝ ገቢ ያከናውናል፤
   ለ) ለዱር እንስሳት ጥበቃ የሚያግዙ ሠራተኞችን ያሰለጥናል፤
   ሐ) የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታውን የተፈጥሮ ሀብት ይዘት የማይጐዱ የልማት ሥራዎችን ያከናውናል፤
   መ) የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታውን ልማት ለማጠናከር የገንዘብና የጉልበት አስተዋጽኦ ያደርጋል፤

ሠ) በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታው ውስጥ የሚከናወነውን የአጠቃቀም ዓይነት ከሚመለከተው የክልሉ አካል ጋር በመመካከር ይወስናል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ስለፈቃዶች

### 8. የፈቃድ አስፈላጊነት

በዚህ ደንብ መሠረት ፈቃድ ያልተሰጠው ሰው ማንኛውንም ዓይነት የዱር እንሰሳ ለማደን ወይም በህይወት ለመያዝ፣የዱር እንስሳት ውጤቶች ለመውሰድ፣በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ውስጥም ሆነ ውጭ የዱር እንስሳትን በፊልም ለመቅረጽ ወይም በዱር እንስሳትና አካባቢያቸው ላይ ጥናት ለማካሄድ አይችልም።

### 9. የፈቃድ ቅደመ ሁኔታዎች

1. ፈቃድ እንዲሰጠው ከማመልከቱ በፊት በነበሩት አምስት ዓመታት ውስጥ የዱር እንስሳት ጥበቃ ሕግን በመተላለፍ ጥፋት ፈጽሞ የተፈረደበት ወይም የተሰጠው ፈቃድ የተሠረዘበት ሰው በዚህ ደንብ መሠረት ለሚሰጥ ማንኛውም ዓይነት ፈቃድ ብቁ አይሆንም።
2. እድሜው 18 ዓመት ያልሞላ ወይም የአካልብቃቱ በባለሙያ ያልተረጋገጠ ማንኛውም ሰው ለባለሙያ አሳዳኝነት ፈቃድ ብቁ አይሆንም።
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ፈቃድ ለማግኘት መሟላት ያለባቸው ሌሎች ቅድመ ሁኔታዎች ባለሥልጣኑ ከክልሎች ጋር በመመካከር በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናሉ።
4. በዚህ ደንብ መሠረት የሚሰጥን ማንኛውንም ዓይነት ፈቃድ ለማግኘት የሚፈልግ ሰው ማመልከቻውን እንደአግባቡ ባለሥልጣኑ ለዚሁ ተግባር ባዘጋጀው ፎርም ላይ ሞልቶና የፈቃድ ቅድመ ሁኔታዎችን ማሟላቱን ከሚያሳዩ ማስረጃዎች ጋር አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡

### 10. ፈቃድን ስለመስጠት

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 9(4 መሠረት የቀረበ የፈቃድ ማመልከቻ ተቀባይነት ሲያገኝ አመልካቹ ተገቢውን የፈቃድ ክፍያ እንዲፈጽም ተደርጎ የጠየቀው ፈቃድ ይሰጠዋል።
2. ማንኛውም ፈቃድ የዚህን ደንብ ድንጋጌዎችና በፈቃዱ ላይ የሠፈሩትን ግዴታዎችና ገደቦችን በመጠበቅ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 11.ፈቃድን ስለማሳደስ

1. ማንኛውም ፈቃድ በየዓመቱ ከሐምሌ 1 እስከ 30 ባሉት ቀናት ውስጥ መደበኛው የፈቃድ ክፍያ ወይም ከዚያ በኋላ ተጨማሪ ክፍያ ተፈጽሞ መታደስ አለበት፡፡
2. የፈቃድ እድሳት ማመልከቻ ፈቃዱ በዚህ ደንብ አንቀጽ 17 መሠረት መታገድ ወይም መሠረዝ ያለበት ከሆነ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡
3. ማንኛውም ባለፈቃድ የዓመቱን አስፈላጊ የመንግሥት ግብር ስለመክፈሉ ማረጋገጫ ማቅረብ ይኖርበታል።

## 12.የፈቃድ ክፍያ

1. በዚህ ደንብ መሠረት የሚሰጡ ፈቃዶችን ለማውጣት ወይም ለማሳደስ የሚጠየቁ ክፍያዎች በዚህ ደንብ ሠንጠረዥ ሁለት በተመለከተው መሠረት ይሆናል፡፡
2. ማንኛውም ባለፈቃድ ፈቃዱን ለማሳደስ፣

   ሀ) እስከ ነሐሴ 30 ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ ዘግይቶ ከቀረበ የማሳደሻ ክፍያውን 30% በተጨማሪነት ይከፍላል፤

   ለ) ከነሐሴ 30 በኋላ ዘግይቶ ከቀረበ የማሳደሻ ክፍያውን 50% በተጨማሪነት ይከፍላል።

## 13.የአደን ክፍያና የዱር እንስሳት ዉጤቶች ዋጋ ተመን

1. የዱር እንስሳት አደን ክፍያዎችና የዱር እንስሳት ውጤቶች ዋጋ ተመን ከዚህ ደንብ ጋር ተያይዘው በሚገኙት ሠንጠረገዥ ላይ በተመለከተው መሠረት ይሆናል፤ ሆኖም በሠንጠረገዡ ላይ ያልተመለከቱ የዱር እንስሳትን በሚመለከት የሚጠየቀውን ክፍያ ተመን ባለሥልጣኑ ከሚመለከታቸው ክልሎች ጋር በመመካከር ይወስናል፡፡
2. የዱር እንስሳ ለማደን የተፈጸመ የቅድሚያ ክፍያ ተመላሽ አይሆንም።

## 14.ፈቃድን ይዞ ስለመገኘት

1. ማንኛውም ሰው ፈቃድ የተሰጠበትን ተግባር በሚያከናውንበት ጊዜ ፈቃዱን ይዞ መገኘት አለበት፡፡
2. ማንኛውም ባለፈቃድ ያደናቸውን የዱር እንስሳት የሚመለከት መረጃ ከፈቃዱ ጋር በተሰጠው የአደን ቅጽ መሠረት መዝግቦ መያዝ አለበት፡፡ የፈቃዱ የአገልግሎት ጊዜ እንዳለቀ ወይም ባለፈቃዱ ኢትዮጵያን ለቆ በሚሄድበት ጊዜ የአደን ቅጹን ከነፈቃዱ ለሰጠው አካል ያስረክባል።

3. ባለፈቃዱ የአደነውን የዱር እንስሳ ውጤት ከሥፍራው ከማንቀሳቀሱ በፊት በአደን ቅጹ ላይ መመዝገብ አለበት፡፡ የዱር እንስሳው ቆስሎ ያመለጠ ከሆነም ይኸው ሁኔታ በዝርዝር በአደን ቅጹ ውስጥ መመዝገብ አለበት፡፡

15. <u>ስለተገደሉ ወይም ስለቆሰሉ የዱር እንስሳት</u>

1. የአደን ፈቃድ የያዘ አዳኝ በማንኛውም ሁናቴ የገደለው ወይም ያቆሰለው የዱር እንስሳ በአዳኙ ላይ ይቆጠርበታል፡፡
2. የአደን ፈቃድ የያዘ አዳኝ፣

ሀ) ከተወሰነው የማርጣ መጠን በታች የሆነ የዱር እንስሳ አድኖ ከተገኘ የእንስሳውን የነፍስ ወከፍ ዋጋ በእጥፍ ይከፍላል፤

ለ) እንስት የዱር እንስሳ አድኖ ከተገኘ የወንዱን የነፍስ ወከፍ ዋጋ እጥፍ ይከፍላል።

16. <u>ፈቃድን ስለማስተላለፍ</u>

1. ማንኛውም ሰው የተሰጠውን ፈቃድ ለሌላ ሰው ማስተላለፍ ወይም የራሱ ባልሆነ ፈቃድ ሊጠቀም አይችልም፤ ሆኖም አዳኝ ቱሪስት ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት አደኑን ማከናወን ካልቻለ ከስድስት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በአደን ክፍያው ላይ 25 % ተጨማሪ ገንዘብ በመክፈል ፈቃዱን ለህጋዊ ወኪሉ ማስተላለፍ ይችላል፡፡
2. የአደን ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የአደን ወቅቱን ሳይጀምር ወይም ሳያጠናቅቅ አደን ቢያቋርጥ ከስድስት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እንደገና አደኑን ያለተጨማሪ ክፍያ ማካሔድ ይችላል፡፡

17. <u>ፈቃድን ስለማገድና ስለመሰረዝ</u>

1. ማንኛውም ባለፈቃድ የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ወይም የፈቃዱን ግዴታዎች ጥሶ ሲገኝ ኃላፊነት የተሰጠው የፈቃድ ሰጪው አካል ሠራተኛ ፈቃዱን ለማገድ ይችላል፡፡ የፈቃድ ሰጪው አካል የበላይ ኃላፊ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ እግዱን ሊያነሳ ወይም ሊያፀድቅ ወይም ፈቃዱን ሊሠርዝ ይችላል፡፡
2. ይህን ደንብ በመተላለፍ በፈጸመው ጥፋት ተከስሶ የተፈረደበት ማንኛውም ሰው ፍርድ ቤቱ በሌላ አኳኋን ካልወሰነ በስተቀር የተሰጠው ማንኛውም ፈቃድ ወዲያውኑ እንደተሠረዘ ይቆጠራል።
3. ፈቃድ የተሠረዘበት ሰው የፈቃዱን ወረቀት በአምስት ቀናት ውስጥ ፈቃዱን ለሰጠው አካል መልሶ ማስረከብ አለበት፡፡

18.**<u>የዉጪ ቱሪስት የአደን ፍቃድ</u>**

1. የዉጪ ቱሪስት የአደን ፈቃድ ከዚህ ደንብ ጋር ተያይዞ በሚገኘው ሠንጠረዥ 4 የተመለከቱትን የዱር እንስሳት ለማደን ለዉጪ ቱሪስት አዳኞች በባለሥልጣኑ የሚሰጥ ፈቃድ ነው፡፡
2. በአንድ የውጪ ቱሪስት አደን ፈቃድ ሊታደኑ የሚችሉ ታዳኝ የዱር እንስሳት ብዛት ፈቃዱን በሚሰጠው አካል ለበጀት ዓመቱ በሚያፀድቀው ኮታ መሠረት ሆኖ ከየዝርያው አንድ የዱር እንሰሳ ብቻ ይሆናል፡፡
3. የቱሪስት የአደን ፈቃድ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ለሁለት ወር ጊዜ የጸና ይሆናል፡፡
4. በዱር እንስሳቱና የመኖሪያ አካባቢው ዙሪያ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ በየጊዜው በማጥናትና በመገምገም በሠንጠረዥ 4 ከተመለከቱት የዱር እንስሳት ዝርዝር ላይ ሊቀነስ ወይም ሌላ ያልተካተተ ዝርያ ካለ ሊጨመር ይችላል፡፡

19.**<u>የአገር ዉስጥ አደን ፍቃድ</u>**

1. የአገር ውስጥ ነዋሪ የአደን ፈቃድ ከዚህ ደንብ ጋር ተያይዞ በሚገኘው ሠንጠረዥ 5 ላይ የተመለከቱትን የዱር እንስሳት ለማደን በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚኖሩ የውጪ አገር ዜጎች ወይም ለኢትዮጵያውያን በሚመለከተው የክልል አካል የሚሰጥ ፈቃድ ነው፡፡
2. የሀገር ውስጥ ነዋሪ አደን ፈቃድ ጸንቶ የሚቆየው ለ 15 ቀናት ይሆናል፡፡

20.**<u>የአእዋፍ አደን ፍቃድ</u>**

1. የአእዋፍ አደን ፈቃድ ከዚህ ደንብ ጋር ተያይዞ በሚገኘው ሠንጠረዥ 6 የተመለከቱትን አእዋፍ ለማደን በሚመለከተው የክልል አካል የሚሰጥ ፈቃድ ነው፡፡
2. የአእዋፍ አደን ፈቃድ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ለአንድ ወር የፀና ይሆናል፡፡
3. የአደን አካባቢዎችን የዝናብ ሥርጭትና የአእዋፍ መራቢያ ወቅትን ግምት ውስጥ በማስገባት፣

   ሀ) ለመካከለኛ የሀገሪቱ ከፍተኛ ቦታዎች ከሰኔ 1 ቀን እስከ ሕዳር 30 ቀን፣

   ለ) ለደቡብና ምሥራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ከመጋቢት 1 ቀን እስከ ነሐሴ 30 ቀን፣ የአእዋፍ አደን ዝግ ይሆናል፡፡

21.<u>የፎፍዬ አደን ፈቃድ</u>

1. የፎፍዬ አደን ፈቃድ ለቱሪስት አዳኞች ወይም ለሀገር ውስጥ አዳኞች በሚመለከተው የክልል አካል የሚሰጥ ፈቃድ ነው፡፡
2. ለአደን የሚፈቀዱት የፎፍዬ ዝርያዎች ትልቁ ፎፍዬና ተራው ፎፍዬ ብቻ ይሆናሉ።
3. የፎፍዬ አደን ከነሐሴ 1 ቀን እስከ ጥቅምት 30 ቀን ብቻ የሚካሄድ ይሆናል፡፡

22.<u>ለሳይንስ ጥናት የሚሰጥ ልዩ የአደን ፍቃድ</u>

1. ማንኛውንም የዱር እንሰሳ ለሳይንስ ጥናት አገልግሎት እንዲውል በሚያስፈልግበት ጊዜ ባለሥልጣኑ ልዩ የአደን ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፡፡
2. ልዩ የአደን ፈቃድ ጸንቶ የሚቆየው በፈቃዱ ላይ ለተወሰነው ጊዜ ይሆናል፡፡
3. ልዩ የአደን ፈቃድ የተሰጠው ሰው የተፈቀደለትን የዱር እንስሳ ለማደን የሚያስችል በቂ ችሎታ የሌለው ከሆነ ከባለሥልጣኑ በሚመደብ ባለሙያ እገዛ ማደን አለበት፡፡

23.<u>የዱር እንስሳ የመያዝ ፈቃድ</u>

1. የዱር እንስሳ የመያዝ ፈቃድ የሚሰጠዉ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘዉ ሠንጠረዥ 8 ላይ የተመለከተ የዱር እንስሳ ለመያዝ ይሆናል፡፡
2. ባለስልጣኑ የዱር እንስሳት የመያዝ ፈቃድ ከመስጠቱ በፊት አመልካቹ የዱር እንስሳትን ከነነፍሳቸዉ ለመያዝና ለማቆየት ያለዉን ልምድ፣ የሚይዘዉ የዱር እንስሳ ለምን እንደተፈለገ፣የሚያዝበትን ዘዴና ወደተፈለገበት ቦታ ለማድረስ የሚጠቀምበት መንገድ የሚያሳይ አጥጋቢ ማስረጃ እንዲያቀርብ ማድረግ አለበት፡፡
3. የዱር እንስሳ የመያዝ ፈቃድ ጸንቶ የሚቆየዉ በፈቃዱ ላይ ለተመለከተዉ ጊዜ ይሆናል፡፡
4. የዱር እንስሳዉ በሚያዝበት ጊዜ ወይም ከዚያ በኃላ ቢሞት በባለፈቃዱ ላይ ይቆጠርበታል፡፡
5. የዱር እንስሳ የመያዝ ፈቃድ የተሰጠዉ ሰዉ የተፈቀደለትን እንስሳ ለመያዝ በብረት ወጥመድ፣በመርዝ ወይም በመርዛማ መሣሪያ መጠቀም ወይም የራሱን ወይም የሌላዉን ሰዉ ህይወት ለማዳን ካልተገደደ በቀር በማናቸዉም የዱር እንስሳ ላይ መተኮስ አይችልም፡፡ ሆኖም በፈቃድ ሰጪዉ አካል ሲፈቀድለት በማደንዘዣ ጠብመንጃ መጠቀም ይችላል፡፡

6. ማንኛውም የተያዘ የዱር እንስሳ በሰው ወይም በንብረት ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት ባለፈቃዱ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

**24.** **<u>ለአደን የተከለከሉ የዱር እንስሳት</u>**

ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘዉ ሠንጠረዥ 10 ላይ የተዘረዘሩትን የዱር እንስሳት በዚህ ደንብ አንቀጽ 22 መሠረት ካልሆነ በቀር ማደን ፈጽሞ የተከለከለ ነዉ፡፡

**25.** **<u>ስለተከለከሉ የማደኛ ዘዴዎች</u>**

1. ለማንኛዉም ሰዉ የዱር እንስሳ ለማደን በሚከተሉት ዘዴዎች መጠቀም የተከለከለ ነዉ፤
   ሀ) ከሁለት መቶ ሜትር ባነሰ ርቀት በተሽከርካሪ፣ በጀልባ ወይም አውሮፕላን ወደ ዱር እንስሳ መጠጋት፤
   ለ) እሳት ማስነሳት ወይም የዱር እንስሳትን በእሳት ማባረርና መክበብ፤
   ሐ) ከታዳኝ የሌሊት ተንቀሳቃሽ የዱር እንስሳት በስተቀር በጨለማ ማደን፤
   መ) ከወፍ በቀር ማንኛውንም የዱር እንስሳ በውሻ ማደን፤
   ሠ) የክበቡ ስፋት ስምንት ሴንቲ ሜትር ወይም ከዚህ በላይ ስፋት ያለዉ ወጥመድ ወይም ተመሳሳይ የሆነ ስፋት ያለዉ ወጥመድ ወይም ተመሳሳይ የሆነ በሽቦ የተሠራ ወጥመድ መጠቀም፤
   ረ) በተጠመደ ጠብመንጃ፣ በጉድጓድ፣ በቦይ፣ በመረብ፣ በአጥር፣ በወጥመድ፣ በመርዝ ወይም ይህን በመሠለ ጎጂ ነገር ወይም በአዉቶማቲክ መሣሪያመጠቀም፤
   ሰ) ለወፍ፣ለኢንሹ፣ለሚዳቋ፣ለጥንቸል፣ለቀበሮዎችና ለመሳሰሉት ትናንሽ የዱር እንስሳት ካልሆነ በስተቀር ካሊበሩ ዜሮ ነጥብ ሃያ ሁለት በሆነ መሣሪያ መጠቀም፤
   ሸ) ለትናንሽ ሣር በል የዱር እንስሳት ካልሆነ በስተቀር በነፋስ ጠብመንጃ ወይም በሽጉጥ መጠቀም፤
   ቀ) ለሜዳ ፍየል፣ ለብሆር፣ለድኩላ፣ ለአምባራይሌና ለመሳሰሉት መካከለኛ የዱር እንስሳት ካልሆነ በስተቀር ካሊበሩ ከዜሮ ነጥብ ሁለት መቶ አርባ እሰከ ዜሮ ነጥብ ሦስት መቶ ባልሆነ መሣሪያ መጠቀም፣
   በ) ለሣላ፣ ለቆርኬ፣ ለድፋርሣና ለመሳሰሉት ትላልቅ የዱር እንስሳት ካሊበሩ ከዜሮ ነጥብ ሦስት መቶ እስከ ዜሮ ነጥብ ሦስት መቶ ሰባ ስምንት ባልሆነ መሣሪያ መጠቀም፤

ተ) ለጎሽ፣ ለጉማሬ፣ ለአንበሣ፣ ለነብርና ለመሳሰሉት በጣም ትላልቅና ኃይለኛ የዱር እንስሳት ካሊበሩ ከዜር ነጥብ ሦስት መቶ ሰባ አምስት እሰከ ዜሮ ነጥብ ስድስት መቶ ባልሆነ መሣሪያ መጠቀም፤

ቸ) በማንኛዉም ዓይነት ተወርዋሪ ፈንጂ ወይም የእጅ ቦንብ መጠቀም፤

ኀ) ፈቃድ ሰጪዉ አካል በጽሑፍ ካልፈቀደ በስተቀር ማንኛዉንም የዱር እንስሳ ለማደንዘዝ፣ ሽባ ለማድረግ፣ ለማፍዘዝ ወይም በከፊልም ሆነ በሙሉ ለመሰንከል የሚችል መድኃኒት ባለዉ ማንኛዉም ዓይነት ተወርዋሪ መሣሪያ መጠቀም፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌዎች ሥልጣን በተሰጣቸዉ ሠራተኞችና የተወሰነ ተግባር ለመፈጸም በፈቃድ ሰጪው አካል በጹሑፍ በተፈቀደላቸዉ ሰዎች ላይ ተፈጻሚ አይሆኑም፡፡

## ክፍል አራት

## የዱር እንስሳትና የዱር እንስሳት ዉጤቶች ሕጋዊ ባለይዞታነት

### 26.የባለቤትነት የምስክር ወረቀት

1. ፈቃድ ሰጪዉ አካል በተወሰነዉ ፎርማት መሠረት ተሞልቶ ማመልከቻ ሲቀርበለት በሕጋዊ መንገድ የተገኘ የዱር እንስሳ ወይም የዱር እንስሳት ዉጤት ባለይዞታ ለሆነ ሰዉ የባለቤትነት የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡ በሳይተስ ለተመዘገበ ዝርያ በተጨማሪ የሳይተስ የምሥክር ወረቀት እንዳስፈላጊነቱ ይሰጣል፡፡
2. ማንኛዉም ሰዉ በህጋዊ መንገድ የተገኘን የዱር እንስሳ ወይም የዱር እንስሳት ዉጤት ለሌላ ሰዉ ሲሸጥ ወይም ሲያስተላልፍ የባለቤትነት የምስክር ወረቀቱን ለገዢዉ ወይም ለተቀባዩ ማዘወርና የባለቤትነቱ መብት መተላለፉንና ቀኑን በምስክር ወረቀቱ ላይ ማስፈር አለበት፡፤

### 27.የዱር እንስሳት ንግድ ፈቃድ

1. የዱር እንስሳት ንግድ ፈቃድ ካልያዘ በስተቀር ማንኛዉም ሰዉ በዱር እንስሳት፣ በዱር እንስሳት ዉጤቶች ወይም በዱር እንስሳት ዉጤት በተሠሩ ዕቃዎች ንግድ መሰማራት ወይም የዱር እንስሳት ዉጤት በመጠቀም ልዩልዩ ቅርጾችን ማዘጋጀት፣ ትርኢት ማሳየት ወይም ሌሎች ቁሳቁሶች ማዘጋጀት አይችልም፡፡

2. የዱር እንስሳት ንግድ ፈቃድ የተሰጠዉ ሰዉ በፈቃዱ መሠረት የሚያከናዉናቸዉን ተግባራት ሁሉ ፈቃድ ሰጪዉ አካል በሚሰጠዉ መመሪያ መሠረት በመዝገብ እየጻፈ በተጠየቀ ጊዜ ለቁጥጥር ያቀርባል፡፡
3. የዱር እንስሳት ንግድ ፈቃድ ተገቢዉ የማሳደሻ ክፍያ ተከፍሎ በየዓመቱ መታደስ አለበት፡፡

28.<u>የዱር እንስሳትንና የዱር እንስሳት ዉጤቶችን ወደ አገር ዉስጥ ስለማስገባት</u>

1. የዱር እንስሳትንና የዱር እንስሳት ዉጤቶችን ወደ አገር ዉስጥ ማስገባት የሚቻለዉ በተፈቀዱ የጉምሩክ መግቢያ በሮች ብቻ ሆኖ ከመጡበት አገር በሕጋዊ መንገድ መዉጣታቸዉን የሚያሳይ አጥጋቢ ማስረጃና የጤና ማረጋገጫ ሠርተፍኬት ሲቀርብ ነዉ፡፡
2. በሳይተስ እዝል የተመዘገቡ የዱር እንስሳትን ወይም ዉጤቶቻቸውን ወደ አገር ዉስጥ ለማስገባት ከመጡበት አገር የተሰጠ የሳይተስ ማዉጫ ፈቃድ እንዲሁም በሳይተስ እዝል አንድ የተመዘገቡ ሲሆን በተጨማሪ ከባለሥልጣኑ የተሰጠ የሳይተስ ማስገቢያ ፈቃድ መቅረብ አለበት፡፡

29.<u>የዱር እንስሳትንና የዱር እንስሳት ዉጤቶችን ወደ ዉጪ አገር ስለመላክ</u>

1. ማንኛዉም ሰዉ የዱር እንስሳትን ወይም የዱር እንስሳት ዉጤቶችን ወደ ዉጪ አገር ለመላክ፤
   ሀ) የሕጋዊ ባለቤትነት ምስክር ወረቀት በማቅረብ ከባለሥልጣኑ የማዉጫ ፈቃድ ማግኘት፣
   ለ) ከባለሥልጣኑ በተሰጠዉ የመላኪያ ፈቃድ ላይ የተዘረዘሩትን ግዴታዎች መጠበቅ፤
   ሐ) በህግ የተወሰነ ማናቸዉንም ተፈላጊ ግብርና ቀረጥ መክፈል፤
   መ) የዱር እንስሳዉ በሳይተስ ዝርያነት የተመዘገበ ከሆነ ከባለሥልጣኑ የሳይተስ ማዉጪያ ፈቃድእንዲሁም በሳይተስ ዕዝል አንድ የተመዘገበ ከሆነ ከሚደርስበት አገር የሳይተስ ማስገቢያ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡
2. የዱር እንስሳት ወይም የዱር እንስሳት ዉጤት ወደ ዉጪ ሀገር ለመላክ የሚሰጥ ፈቃድ የሚያገለግለዉ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ለስድስት ወራት ብቻ ይሆናል፡፡

30.<u>ወደ ሌላ አገር እንዲተላለፉ ስለሚደረጉ የዱር እንስሳትና የዱር እንስሳት ዉጤቶች</u>

1. የዱር እንስሳትና የዱር እንስሳት ዉጤቶች የኢትዮጵያን ድንበር በማቋረጥ ወደ ሌላ አገር እንዲተላለፍ ለማድረግ፡
   ሀ) የዱር እንስሳዉ ወይም የዱር እንስሳት ዉጤቱ ከተላከበት አገር የመተላለፍ መብት የሚሰጥ ማረጋገጫና የጤና ማረጋገጫ ሠርተፍኬት ማቅረብ፤ እና
   ለ) የዱር እንስሳዉ ወይ የዱር እንስሳዉ ዉጤት የሳይተስ ዝርያ ከሆነ የሳይተስ ፈቃድ ማቅረብ ያስፈልጋል፡፡
2. የሳይተስ ስምምነትን ካልፈረመ አገር የሚመጣ የሳይተስ ዝርያ የዱር እንስሳ ወይም የዱር እንስሳ ዉጤት የኢትዮጵያን ድንበር አቋርጦ እንዲያልፍ ለማድረግ አይፈቀደም፡፡

31.<u>በሕገ ወጥ መንገድ ተይዘዉ ስለሚገኙ የዱር እንስሳትና የዱር እንስሳት ዉጤቶች</u>

1. ማንኛዉም ሰዉ በሕገ ወጥ መንገድ የተገኘን የዱር እንስሳ ወይም የዱር እንስሳት ዉጤት ይዞ መገኘት፣ መነገድ፣ ወደ ዉጪ አገር መላክ ወይም ወደ አገር ዉስጥ ማስገባት አይችልም፡፡
2. በሕገ ወጥ መንገድ ተይዞ የተገኘ የዱር እንስሳ ወይም የዱር እንስሳት ዉጤት በቁጥጥር ሥር እንዲዉል ተደርጎ ሥልጣን ባለዉ ፍርድ ቤት እንዲወረስ ሲወሰን የፈቃድ ሰጪዉ አካል ንብረት ይሆናል፡፡
3. በሕገ ወጥ መንገድ ተይዞ የተገኘ የዱር እንስሳ ወይም የዱር እንስሳት ዉጤት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት እንዲወረስ ሲደረግ የዋጋው ሠላሳ በመቶ ጠቁሞ ላስያዘዉ፣ አሥር በመቶ ለያዘዉ ወይም አርባ በመቶዉ ለጠቆመዉና ለያዘዉ ሰዉ ይከፈላል፡፡

32.<u>የዱር እንስሳት ዉጤት አወጋገድ</u>

1. ማንኛዉም የዱር እንስሳት ዉጤት ከጥቅም ዉጭ መሆኑ ሲረጋገጥ በአካባቢዉ ሕብረተሰብና ሥነ ምህዳር ላይ ምንም ዓይነት ተጽዕኖ በማያስከትል መንገድ እንዲወገድ ይደረጋል፡፡
2. የዱር እንስሳት ዉጤት አወጋገድ ሂደት በፈቃድ ሰጪዉ አካል የተወከሉ ታዛቢዎች በተገኙበት መፈጸም አለበት፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 33.በሰዉ ሕይወትና በንብረት ላይ ጉዳት ስለሚያደርሱ የዱር እንስሳት

1. የሰውን ሕይወት ለማዳን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የዱር እንስሳ መግደል ወይም ማቁሰል ይህን ደንብ እንደመተላለፍ አያስቆጥርም፣ ሆኖም የተገደለው ወይም የቆሰለው የዱር እንስሳለሰው ሕይወት አደገኛ ለመሆን የቻለው ይህን፣ደንብ በመተላለፍ በተፈጸመው ተግባር ምክንያት ሆኖ ከተገኘ ይህን ደንብ የተላለፈው ሰው ከተጠያቂነት ነጻ ሊሆን አይችልም።
2. ማንኛውም ባለንብረት በንብረቱ ላይ ጉዳት የሚያደርሱትን የዱር፣ እንስሳት በመርዝከመጠቀም በስተቀር በዚህ ደንብ በተከለከሉ ዘዴዎች ጭምር ለመከላከል ይችላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የዱር እንስሳ ለማደን ያቀደ ሰው የሚችል እስከሆነ ድረስ አስቀድሞ ለሚመለከተው ፈቃድ ሰጪ አካል ማስታወቅ አለበት፡፡ ፈቃድ ሰጪ አካሉም ማስታወቂያው ሲደርሰው የታቀደው የማደን ተግባር እንዲታገድ በማድረግ በንብረቱ ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ራሱ በሌላ መንገድ ለመከላከል ወይም ይህንኑ ባለንብረቱ እንዲፈጽም ለማዘዝ ይችላል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ መሠረት የዱር እንስሳ የገደለ ወይም ያቆሰለ ሰው ይህንኑ በተቻለ ፍጥነት ለፈቃድ ሰጪው አካል ወይም በአቅራቢያው ለሚገኝ የአስተዳደር ወይም የፖሊስ አካል ማስታወቅ አለበት፡፡ ከአደን የተገኘው የዱር እንስሳት ውጤትም የሚመለከተው ፈቃድ ሰጪ አካል ንብረት ይሆናል፡፡
5. ሥልጣን የተሰጠው ሠራተኛ የኅብረተሰቡን ጥቅም ለማስጠበቅ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ማንኛውንም ዓይነት የዱር እንሰሳ አግባብ ባለው ዘዴ ለመግደል ይችላል፡፡

### 34.ስለ ቱሪስት አዳኝ ረዳቶች

1. ማንኛውም ሰው ቱሪስት አዳኝ ለመርዳት በዚህ ደንብ መሠረት የተሰጠው ፈቃድ ከሌለው በቀር ቱሪስት አዳኙ አስቀድሞ ያቆሰለውን የዱር እንስሳ ለማቁሰል፣ ለመግደል፣ ለመያዝ ወይም በዱር እንስሳዉ ላይ ለመተኮስ አይፈቀድለትም፡፡

2. የቱሪስት አዳኝ ረዳት ያቆሰለው፣ የገደለው ወይም የያዘው የዱር እንስሳ ቱሪስት አዳኙ እንዳቆሰለው፣ እንደገደለው ወይም እንደያዘው ይቆጠራል።

35.<u>**የቆሰለ የዱር እንስሳን ስለመከታተልና ሊደርስ የሚችል አደጋን ስለማስታወቅ**</u>

1. የዱር እንስሳ ያቆሰለ ሰው የዱር እንስሳውን ለመግደል የተቻለውን ሁሉ ጥረት ማድረግ አለበት፤ ሆኖም የቆሰለውን የዱር እንሰሳ ለማደን ፈቃድ የሌለው ሰው ከሆነ እንስሳውን ተከትሎ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታ ውስጥ ለመግባት አይፈቀድለትም፡፡
2. ጐሽ፣ ዝሆን፣ ጉማሬ፣ ነብር ወይም አንበሳ ያቆሰለ ማንኛውም ሰው የሚከተሉትን ዝርዝር ሁኔታዎች በመግለጽ በተቻለ ፍጥነት በፈቃድ ሰጪው አካል ወይም በአቅራቢያው ለሚገኝ የአስተዳደር ወይም የፖሊስ አካል ሪፖርት ማድረግ አለበት፤

   ሀ) የቆሰለውን የዱር አንስሳ ዓይነት፤

   ለ) እንስሳው የቆሰለበትን ቀን፣ሰዓትና ሥፍራ፤

   ሐ) እንስሳው የተመታበትን ብልትና የቆሰለበትን የመሣሪያ ዓይነት፤

   መ) የቆሰለውን የዱር እንስሳ ለመከታተል የተደረገውን ሙከራ፤ እና

   ሠ) እንስሳውን ለማግኘትና ለመለየት የሚያስችሉ ሌሎች  መግለጫዎችን፡፡

36.<u>**የገቢ ክፍፍል**</u>

ባለሥልጣኑ ከዱር እንስሳት አደን፣ ከዱር እንስሳት በህይወት ንግድና ከፊልም ቀረፃ ከሚሰበሰበው ገቢ ላይ 85% የሚሆነውን ድርሻ ለሚመለከታቸው ክልሎች ያስተላልፋል፡፡

37.<u>**ቅጣት**</u>

የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች የተላለፈ ማንኛዉም ሰው በአዋጁና በወንጀል ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ይቀጣል፡፡

38.<u>**ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ የካቲት 11 ቀን 2001 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

W”Ö[» ›”É

¾û`¡“ ¾SÖKÁ ÑAw˜-‹ SÓu=Á ªÒ }S”

G. uÔw—>-‹ ¯A’ƒ“ u°ÉT@ LA ¾}S[¢²

| }.l | ¾Ôw—> ¯A’ƒ | w` |
| --- | --- | --- |
| 1 | ›=ƒÄåÁ© | |
| | 1.1 12 ¯Sƒ“ Ÿ²=Á uLA | 20.00 |
| | 1.2 Ÿ12 ¯Sƒ u•‹ | 10.00 |
| | 1.3 K}T]-‹ | 10.00 |
| 2 | ’ª] ¾¨<ß ›Ñ` ²?Ò | |
| | 2.1 12 ¯Sƒ“ Ÿ²=Á uLA | 50.00 |
| | 2.2 Ÿ12 ¯Sƒ u•‹ | 10.00 |
| 3 | ¾¨<ß GÑ` ~]eƒ | |
| | 3.1 12 ¯Sƒ“ Ÿ²=Á uLA | 90.00 |
| | 3.2 Ÿ12 ¯Sƒ u•‹ | 10.00 |

K. u}iŸ`"] ¾SkSÝ w³ƒ LA ¾}S[¢²

| }.l | ¾}iŸ`"]¨< SkSÝ SÖ” | w` | | |
| --- | --- | --- | --- | --- |
| | | K›=ƒÄåÁ© | K’ª] ¨<ß ²?Ò | K¨<ß ~]eƒ |

| }.l | ¾}iŸ`"]¨< SkSÝ SÖ” | w` | | |
|---|---|---|---|---|
| | | K›=ƒÄåÁ© | K’ª] ¨<ß ²?Ò | K¨<ß ~]eƒ |
| 1 | •eŸ 12 SkSÝ | 10.00 | 15.00 | 20.00 |
| 2 | Ÿ12 SkSÝ uLA | 15.00 | 30.00 | 40.00 |

N.KT[òÁ Yõ^ ¾T>Å[Ó ¾24 c¯ƒ ¡õÁ

| }.l. | ¾Ôw—> ²?Ó’ƒ | w` |
|---|---|---|
| 1 | ›=ƒÄåÁ© ²?Ò | |
| | 1.1 •eŸ 4 c¨< KT>A´ É”"D” | 10.00 |
| | 1.2 Ÿ4 c¨< uLA KT>A´ É”"D” | 15.00 |
| 2 | ’ª] ¾¨<ß HÑ` ²?Ò | |
| | 2.1 •eŸ 4 c¨< KT>A´ É”"D” | 30.00 |
| | 2.2 Ÿ4 c¨< uLA KT>A´ É”"D” | 40.00 |
| 3 | ¾¨<ß GÑ` ~]eƒ | |
| | 3.1 •eŸ 4 c¨< KT>A´ É”"D” | 40.00 |
| | 3.2 Ÿ4 c¨< uLA KT>A´ É”"D” | 60.00 |

S. ¾›¨<a—L” T[òÁ

| }.l | ¾qA• Ñ>²? | w` |
|---|---|---|
| 1 | K›”É Ñ>²? ›`ö KS’dƒ | |
| | 1.1 vK ›”É V}` | 500 |
| | 1.2 vK G<Kƒ V}` | 900 |
| 2 | K48 c¯•ƒ qA• | |
| | 2.1 vK ›”É V}` | 500 |
| | 2.2 vK G<Kƒ V}` | 900 |

W”Ö[» G<Kƒ

¾M¿ M¿ ðnÊ‹ T¨<Ý“ TdÅh ¡õÁ }S”

| }.l | ¾ðnÉ ¯A’ƒ | w` | ¾›T@]" ÊL` |
|---|---|---|---|
| 1 | ¾›dÇ˜ É`Ïƒ ðnÉ | 4000 | |
| 2 | ¾vKS<Á ›dÇ˜ ðnÉ | 2500 | |
| 3 | ¾[Çƒ vKS<Á ›dÇ˜ ðnÉ | 1500 | |
| 4 | ¾›Å” ðnÉ (Ÿ›•ªõ ›Å” ue}k` | 200 | |
| 5 | ŸöòÂ ¨ö‹ue}k`¾›•ªõ ›Å” ðnÉ (K›Ñ`¨<eØ ›Ç™‹ | 1000 | |
| 6 | ŸöòÂ ¨ö‹ue}k`¾›•ªõ ›Å” ðnÉ (K¨<ß ~¶ST xÄ®C | | 1000 |
| 7 | ¾ööÂ ¨ö‹xdN f”D (K›Ñ`¨<eØ ›Ç™‹ | 3000 | |
| 8 | ¾ööÂ ¨ö‹xdN f”D (K¨<ß ~¶ST xÄ®C | | 3000 |

| }.l | ¾ðnÉ ¯A'ƒ | w` | ¾›T@]" ÊL` |
|---|---|---|---|
| 9 | ¾Æ` •"edƒ ÖSÇ vKS<Á ¾S<Á ðnÉ | 1500 | |
| 10 | K¨<ß }S^T]-‹ KdA"d© Ø"ƒ ¾T>cØ ¾'õe ¨Ÿõ ¡õÁ u›Sƒ | | 1000 |
| 11 | ŸUÉ` òMU k[í ðnÉ | | 9000 |
| 12 | Ÿ›¾` LA òMU k[í ðnÉ | | 15®®® |
| 13 | ¾Æ` •"edƒ uQA¨ƒ "ÓÉ ðnÉ | 3000 | |
| 14 | ¾Æ` •"edƒ ¨<Ö?„‹ "ÓÉ ðnÉ | 25®® | |
| 15 | ¾Æ` •"edƒ •¡c= Å`T> Y^ ðnÉ | 3000 | |
| 16 | ¾Ø`˜ ÖSÇ ðnÉ (K›`f ›Å`)›`w„ ›Å` | 200 | |
| 17 | ¾›µ •`v• ðnÉ | 4000 | |
| 18 | ¾cÑA" •`v• ðnÉ | 4000 | |
| 19 | ¾´vÉ LŸ='ƒ ðnÉ | 1200 | |
| 20 | ¾~]eƒ ›Å" SX]Á ðnÉ | | 100 |
| 21 | ¾~]eƒ ›Ç˜ ¡õÁ KqA• uk")¾¢"c`y?i") | | 100 |
| 22 | ¾›Å" •³u= ¡õÁ uk" | | 100 |
| 23 | ¾›Ñ` ¨<eØ 'ª] ›Å" ðnÉ | 2000 | |
| 24 | ¾vKS<Á ›dÇ˜<br>G) Ÿ7-15 k"ƒ | 900 | |

| }.l | ¾ðnÉ ¯A’ƒ | w` | ¾›T@]" ÊL` |
|---|---|---|---|
| | K) Ÿ15-21 k“ƒ“ uLA | 2,000 | |
| 25 | ¯S•© ¾›Å” x•)¾¢”c?i” ¡õÁ | 100,000 | |

**W”Ö[» Zeƒ**

**¾›µ’ ¾Ø`~“ ¾cÑA” ¾’õe ¨Ÿõ ªÒ }S”**

| }.l | ¾Æ`  ”ed~ ¯A’ƒ | ¾ªÒ }S” | |
|---|---|---|---|
| | | w` | ¾›T@]"” ÊL` |
| 1 | Ø`~ ("”É | | |
| | 1.1 K¨<ß ²?Ò ›=”ye}` | | 15 |
| | 1.2 K›=ƒÄåÁ© ›=”ye}` | 2® | |
| | 1.3 K›`f›Å`)K›`w„ ›Å` | | |
| | 1.3.1 Ÿ11  eŸ 5® Ø`~ | 2 | |
| | 1.3.2 ከ51  eŸ 1®® Ø`~ | 5 | |
| 2 | ¾›µ ÝÛƒ | | |
| | 2.1 K¨<ß ²?Ò ›=”ye}` | | 2 |
| | 2.2 K›=ƒÄåÁ© ›=”ye}` | 15 | |
| | 2.3 K›`f›Å`)K›`w„ ›Å`<br>Ÿ100 ŸuKÖ | 5 | |

| }.l | ¾Æ`  ”ed~ ¯A’ƒ | ¾ªÒ }S” | |
|---|---|---|---|
| | | w` | ¾›T@]"” ÊL` |
| 3 | ¾›µ  ”lLM | | |
| | 3.1 K¨<ß ²?Ò ›=”ye}` | | 1 |
| | 3.2 K›=ƒÄåÁ© ›=”ye}` | 10 | |
| | 3.3 K›`f›Å`)K›`w„ ›Å`<br>Ÿ100 ŸuKÖ | 3 | |
| 4 | ¾cÔ” ÝÛƒ | | |
| | 4.1 K¨<ß ²?Ò ›=”ye}` | | 10 |
| | 4.2 K›=ƒÄåÁ© ›=”ye}` | 50 | |
| | K›`f›Å`)K›`w„ ›Å`<br>Ÿ100 ŸuKÖ | 10 | |
| 5 | ¾cÔ”  ”lLM | | |
| | 5.1 K¨<ß ²?Ò ›=”ye}` | | 1 |
| | 5.2 K›=ƒÄåÁ© ›=”ye}` | 10 | |
| | 5.3 K›`f›Å`)K›`w„ ›Å`<br>Ÿ100 ŸuKÖ | 5 | |

W”Ö[» ›^ƒ

u¨<Ü GÑ` ~]eƒ ›Ç™‹ •”Ç=•Å’< ¾T>ðkÆ

¾Æ` •”edƒ ^^“ ¾’õe ¨Ÿõ ªÒ }S”

| }.l | ¾›T`– SÖ]Á | ¾dA”e SÖ]Á | ¾›T@]"” ÊL` |
|---|---|---|---|
| 1 | ´”Ëa (}^ | ûúÄ ›’<u=e | 100 |
| 2 | ´”Ëa (ßLÇ | ûúÄ Ñ>LÇ | 3000 |
| 3 | ´”Ëa (’Û | ûúÄ GTÉ`Ác | 1000 |
| 4 | ÉŸ<L (}^ | ƒ^Í=Lóe e¡]—}e | 700 |
| 5 | ÉŸ<L (¾U’>K=¡ | ƒ^Í=Lóe e¡]—„e S”K=Ÿ= | 6000 |
| 6 | Ôi | c=”c?\e "ð` | 3000 |
| 7 | ÇMÒ ›”uX | òK=e "^"M | 400 |
| 8 | ¾Æ` ÉSƒ | ôK=e c=My?e}]e | 200 |
| 9 | Ñ<_³ | ¢KAue Ñ<_³ | 600 |
| 10 | ›µ | ¡a¡Ç=KAe “AKA+¡e | 2000 |
| 11 | ›=”g< (¾Ñ<”}` | TÊ" Ñ<”}] | 200 |
| 12 | ›=”g< (¾fMƒ | TÊ" dM+“ | 340 |
| 13 | T>Çs (}^ | c=My="ý^ Ó]T | 360 |
| 14 | kua (Ða cò | *„eÄ” T@ÒKA+e | 300 |
| 15 | ¾T@Ç õ¾M (¾Ó^”ƒ | Ò²?L Ó^”+ | 440 |

| }.l | ¾›T`– SÖ]Á | ¾dA”e SÖ]Á | ¾›T@]"” ÊL` |
|---|---|---|---|
| 16 | ¾T@Ç õ¾M (¾cS]”Ó | Ò²?L cS]”Ó | 2600 |
| 17 | óa ÉSƒ (}^ | Ë'@• Ë'@• | 200 |
| 18 | óa ÉSƒ (ÖnÖq | Ë'@• \u=Ó•d | 200 |
| 19 | ›”Ñ} [ÏT@ | K=„¡^'>Äe ªK] | 3000 |
| 20 | Ø”†M | K=ùe Gwc='>Ÿe | 60 |
| 21 | q`Ÿ? (K?M«M | ›Mc=Lóe u<c?Lóe K?K=©M | 4000 |
| 22 | Ñ<T_ | H@þþ•S<e ›Uòu=Äe | 1200 |
| 23 | ¾Æ` ›dT (ƒMl | H>KAŸ<[e T>¾'` ƒ³IÑ'> | 1000 |
| 24 | Ïw ÖnÖq | ¡aŸA• ¡aŸ<• | 180 |
| 25 | kua (Ë`v Øl` | "'>e T>fT>Le | 100 |
| 26 | kua (}^ | Ÿ'>e ›<]e | 160 |
| 27 | kua (vK Ô” SeS` | "'>e ›Æe}e | 100 |
| 28 | ce | ›_Äƒ^ÑAe *_Äƒ^ÑAe | 1400 |
| 29 | ƒMl ›Ò²” (¾qL | ƒ^Í=Lóe eƒ_—c=c=ae | 2700 |
| 30 | ›Uv^AK? | ƒ^Í=Lóe ›=Uu`u=e | 3000 |
| 31 | 'w` | û” ‚^ þ`Í=e | 4600 |
| 32 | ›”uX | û” ‚^ K?- | 4000 |
| 33 | gKSØTØ (¾Ówî | N`üe}e ›”ˆ”Ä” | 60 |

| }.l | ¾›T`– SÖ]Á | ¾dA”e SÖ]Á | ¾›T@]"” ÊL` |
|---|---|---|---|
| 34 | gKSØTØ (i”Ö [ÏU | N?`üc}e d”Ñ>’e | 60 |
| 35 | gKSØTØ (¾Åu<w É”¡Â | N?KAÒK? û`y<L | 60 |
| 36 | Ú• | c?`¢ú+Ÿe T>+e | 140 |
| 37 | Ù× (Ó_y?ƒ | c=`²ú+"e ›=ƒ¿—e | 80 |
| 38 | Ù× (y`y?ƒ | c`¢ú+Ÿe ûAÑ]ƒ[e | 80 |
| 39 | ¾ÅÒ ›Ò²” | ƒ^Í=Lðe v¡c„’> | 15000 |
| 40 | ôq | ›_u=Á *_u=Á | 240 |
| 41 | dL | ›]¡e u?AX | 2000 |
| 42 | cÔ” | c~`+Ä "T@K<c | 1600 |
| 43 | ¾Æ` ›dT | û•V†\e û`Ÿ<e | 400 |
| 44 | Í`ƒ | HAe}]¡e ¡]e•• | 50 |
| 45 | kö Åò | TKI^ "ú”c=e | 300 |
| 46 | wJ` }^ | _Æ”" _Æ”" | 700 |
| 47 | wJ` ¾ÅÒ | _Æ”" ñMl`ñL | 1000 |
| 48 | ›’` | ôK=e c`zM | 360 |
| 49 | q`Ÿ? (SÒL¨< | ÅTK=eŸe K<“}e +Á”Ó | 1100 |
| 50 | Ÿ`Ÿa | óŸ<†›\e ›=ƒÄú¡e | 400 |
| 51 | Éó`d | Ÿu<e ›=K=—c=—]U’<e | 1000 |

**የፍትህ ሚኒስቴር**

| }.l | ¾›T`– SÖ]Á | ¾dA”e SÖ]Á | ¾›T@]"” ÊL` |
|---|---|---|---|
| 52 | óa | ›=¡„’>¡e eƒ]Á}e | 100 |
| 53 | ÂYL l@Cê& | ¢ue T@ÒKAc=[e | 7000 |
| 54 | n+ íé ቆRk@ | ¢ue ¢ue K=¢+e | 4000 |

<u>W”Ö[» ›Ueƒ</u>

<u>u›Ñ` ¨<eØ ›Ç™‹ •”Ç=•Å’< ¾T>ðkÆ ¾Æ` •”edƒ</u>

<u>^^“ ¾’õe ¨Ÿõ ªÒ }S”</u>

| }.l | ¾›T`– SÖ]Á | ¾dA”e SÖ]Á | ¾›T@]"” ÊL` |
|---|---|---|---|
| 1 | Ÿ`Ÿa | óŸ<†›\e ›=ƒÄú¡e | 240 |
| 2 | ›XT | û• V†\e û`Ÿ<e | 240 |
| 3 | Ø”†M | K=ùe Gwc=’>Ÿe | 36 |
| 4 | ›=”g< ¾Ñ<”}`e | TÊ" Ñ<”}] | 120 |
| 5 | Ù× Ó]y?ƒ | c=`¢ú+"e ›=ƒ¿—e | 32 |
| 6 | ´”Ëa }^ | ûúÄ ›’<u=e | 40 |
| 7 | Ïw ÖnÖq | ¡aŸA• ¡aŸ<• | 72 |
| 8 | Í`ƒ | HAe}]¡e ¡]e•• | 20 |

## የፍትህ ሚኒስቴር

**W”Ö[» eÉeƒ**

**u¨<ß ~]eƒ“ u›Ñ` ¨<eØ ›Ç™‹ •”Ç=•Ç’<¾T>ðkÆ ›•ªõ ^^**

| }.l. | ¾›T`– SÖ]Á | ¾dA”e SÖ]Á |
|---|---|---|
| 1 | ›A’ kA ª’@ | eƒaý„üK=Á cTA„`"• |
| 2 | ›”Ñ} kKuƒT ª’@ | eƒaý„üK=Á "ú¢L |
| 3 | Ç¡Â | ›“e eû`d |
| 4 | Ç¡Â | È”Éac=Ó“ vAŸK` |
| 5 | ƒ”g< u<“T Ç¡Â | ›¡c=¨<^ TŸ<ª |
| 6 | S”l[ kA Ç¡Â | ›“e •^Aƒa^H>’@Je |
| 7 | vKl”à Ç¡Â | ›A+Á óK=ÔL |
| 8 | ’ß Ë`v Ç¡Â | •Lc`’>e K=¨<¢”+e |
| 9 | Ç¡Â | È”ÉaAÓ“ y=Æª• |
| 10 | S”l[ u=Ý Ç¡Â | ›“e ›<”ÆL• |
| 11 | qp | õ^”¢K=’e ¡Lü„`„’> |
| 12 | Å[} u<L qp | õ^”¢K=’e "e•’>Ÿ<K=e |
| 13 | ¾¢Ÿ= qp | õ^”¢K=’e ¢Ÿ= |
| 14 | vKl”Ýqp | õ^”¢K=’e c?ô“ |
| 15 | ¾›?`Ÿ?M qp | õ^”¢K=’e ›?`¢K= |
| 16 | vKÑKò”ƒ qp | õ^”¢K=’e e"DT}e |

| }.l. | ¾›T`– SÖ]Á | ¾dA”e SÖ]Á |
|---|---|---|
| 17 | u<LT Ç¡Â | ›“e eƒ_û^ |
| 18 | ƒ”g< Ç¡Â | ›“e £`"ÆL |
| 19 | vKÓ^Ý ¡”õ qp | õ^”¢K='e c=KAK?Se |
| 20 | vKÓ^Ý ¡”õ qp | õ^”¢K='e K?yAL”„AÇ=e |
| 21 | ¾Ówî ´A | ›KAûŸ” ›?Ïý+ÁŸe |
| 22 | ´A | d`Ÿ=Ç=Ä`’>e T@L•• |
| 23 | ´A | ýK?¡ƒaý,[e ÒUu?”c=e |
| 24 | ÏÓ^ (vKl”à | ’<T>Ç T@K?Ó]e |
| 25 | Ç¡Â | ›“e ýL,`Ÿ<e |
| 26 | ¾›gª ª•e | ›Vü`Ç= H@A |
| 27 | ¾sØ˜ ª•e | +KAûŸe üƒace |
| 28 | ’Öw×vT •`Ów | ¢K<Uv Ñ>’>Á |
| 29 | Ï^} [ÏU Ç¡Â | ›“e ›Ÿ<• |
| 30 | U<“T Ç¡Â | ›A+Á ô]“ |
| 31 | U<“T Ç¡Â | ’@• ›=]ƒaõ•MT |
| 32 | ›A’ ’ß Ç¡Â | ›A• “Aa" |
| 33 | cTÁ© É`ßƒ | ¢~`’>e ‰A’@”c=e |
| 34 | ¾›¨<aû É`ßƒ | ¢~`’>e ¢~`’>¡e |
| 35 | ¾H`K?Ÿ=” É`ßƒ | ¢~`’>¡e ÈK?Ô`Ñ> |

| }.l. | ¾›T`– SÖ]Á | ¾dA"e SÖ]Á |
|---|---|---|
| 36 | O} Øl` ¾›gª É`ßƒ | ‚a¡K?e È¢^}e |
| 37 | Å[} u<L ¾›gª É`ßƒ | ‚a¡K?¡e ›?¡c<e}e |
| 38 | vK ›^ƒ kKuƒ ¾›gª É`ßƒ | ‚a¡K?e "DÉ]c="¡}e |
| 39 | ¾M‹"e‚A" ¾›gª É`ßƒ | ‚a¡K?e K?‹"e•A'> |
| 40 | vK'Öw×w ¾›gª É`ßƒ | ‚a¡K?e c?'@ÒK<e |
| 41 | ›"Ñ} u=Ý ¾›gª É`ßƒ | ‚a¡K?e ›?Ñ<~^K=e |
| 42 | Aw^ | ›"e ¡K=úÁ+ |
| 43 | vKu=Ý ›"Ñ} qp | õ^"¢K='e K=¨<¢c?øe |
| 44 | ƒ"g< Ç¡Â | ›"e ¡_" |
| 45 | ƒ"g< Ç¡Â | ›"e J"„• |
| 46 | ƒ"g< Ç¡Â | ›"e ü'@KAü |
| 47 | ƒ"g< Ç¡Â | ›"e "ü"c=e |

<u>W"Ö[» cvƒ</u>

<u>u¨<ß ~]eƒ" u›Ñ` ¨<eØ ›Ç™‹</u>

<u>•"Ç=•Å'< ¾T>ðkÆ öòÂ ¨ö‹</u>

| t.q$ | ¾›T`– SÖ]Á | ¾dA"e SÖ]Á |
|---|---|---|
| 1 | ƒMI öõÂ | ÒK="Ô T>Ç=Á |

| t.q$ | ¾›T`– SÖ]Á | ¾dA”e SÖ]Á |
|---|---|---|
| 2 | }^¨< öõÂ | ÒK=“Ô ÒK=“Ô |

**W”Ö[» eU”ƒ**

**uQA¨ƒ •”Ç=’ÑÆ ¾T>ðkÆ ¾Æ`  ”edƒ ^^“**

**¾’õe ¨Ÿõ“ T¨<Ý ªÒ**

G.Ö<ƒ ›Øu=

| }.l | ¾›T`– SÖ]Á | ¾dA”e SÖ]Á | ªÒ (w` | T¨<Ý ªÒ (w` |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ´”Ëa (}^ | ûúÄ ›’<u=e | 100 | 10 |
| 2 | ´”Ëa (NTÉ`Áe | ûúÄ GTÉ`Ác | 1200 | 120 |
| 3 | ¾Æ` ÉSƒ | ôK=e c=My?e}]e | 240 | 24 |
| 4 | Ñ<_³ | ¢KAue Ñ<_³ | 720 | 72 |
| 5 | ›=”g< (¾Ñ<”}` | TÊ" Ñ<”}] | 240 | 24 |
| 6 | ›=”g< (¾fM}e | TÊ" dM+“ | 400 | 40 |
| 7 | T>Çs (}^ | c=y="ý^ Ó]T | 440 | 44 |
| 8 | kua (Ða cò | *„eÄ” T@ÒKA+e | 360 | 36 |
| 9 | gKSØTØ (}^ | Ë’@• Ë’@• | 200 | 20 |
| 10 | gKSØTØ (ÖnÖq | Ë’@• \u=Ó•d | 200 | 20 |

| }.l | ¾›T`– SÖ]Á | ¾dA”e SÖ]Á | ªÒ (w` | T¨<Ý ªÒ (w` |
|---|---|---|---|---|
| 11 | Ø”†M | K=ùe Gwc=’>Ÿe | 120 | 12 |
| 12 | Ïw (ÖnÖq | ¡aŸA• ¡aŸ<• | 220 | 22 |
| 13 | kua (Ë`v ØI` | "’>e T>fT>Le | 120 | 12 |
| 14 | kua (}^ | Ÿ’>e ›<]e | 120 | 12 |
| 15 | kua (vKÑA” SeS` | "’>e ›Æe}e | 120 | 12 |
| 16 | ›”uX (Ÿ*ÒÈ” ^Á ue}k` | û”‚^ K?- | 4800 | 480 |
| 17 | óa (¾Ówê | N`üe}e ›”"”Ä” | 200 | 20 |
| 18 | óa (i”Ö [ÏU | N?`üc}e d”Ñ>’e | 200 | 20 |
| 19 | óa (¾Åu<w É”¡Â | N?KAÒK? û`y<L | 200 | 20 |
| 20 | Ù× (Ó]y?ƒ | c=`¢ú+"e ›=ƒ¿—e | 80 | 8 |
| 21 | Ù× (y`y?ƒ | c`¢ú+Ÿe ûAÑ]ƒ[e | 80 | 8 |
| 22 | ¾Æ` ›XT | û•V†\e û`Ÿ<e | 200 | 20 |
| 23 | Í`ƒ | HAe}]¡e ¡]e•• | 80 | 8 |
| 24 | kö Åò | TKI^ "ú”c=e | 400 | 40 |
| 25 | Ÿ`Ÿa | óŸ<†›\e ›=ƒÄú¡e | 400 | 40 |
| 26 | µ]L | c=„’>¡e eƒ]Á}e | 200 | 20 |

<u>K. ›ªõ</u>

| የፍትህ ሚኒስቴር | | | | |
|---|---|---|---|---|
| }.<br>l | ¾›T`– SÖ]Á | ¾dA”e SÖ]Á | ¾’ÖL ªÒ<br>u›T@]"<br>ÊL` | ¾T¨<Ý ªÒ<br>u›T@]"<br>ÊL` |
| 1 | S”q[ [ÏU K?Ù | ]Ÿ`y?ae• ›le• | 10 | 1.00 |
| 2 | S”q[ ØI` Ò`ÅU | LAu=¿e ›<”Ç}e | 6 | 0.60 |
| 3 | Ò`ÅU É`w Ø`e | LAu=¿e u?È”•~e | 6 | 0.60 |
| 4 | Å[} cTÁ© ”uuM | T@`ûe Lõ_e“A | 8 | 0.80 |
| 5 | kÁT ”uuM | T@`ûe ’<u=Ÿe | 8 | 0.80 |
| 6 | ¾›¨<aþ ”uuM | T@`ûe ›eúÁe}` | 8 | 0.80 |
| 7 | ›”Ñ} ’ß ”uuM | T@`ûe ›Mu=¢K=e | 8 | 0.80 |
| 8 | ¾SekM ¨õ | ›=¿ýKŸ}e J`Çc?eÄe | 6 | 0.60 |
| 9 | ¾SekM ¨õ | ›=¿ýKŸ}e õ^”c="’<e | 6 | 0.60 |
| 10 | ¾SekM ¨õ | ›=¿ýKŸ}e Ÿ?ü”c=e | 6 | 0.60 |
| 11 | ¾SekM ¨õ | ›=¿ýKŸ}e›ð` | 6 | 0.60 |
| 12 | Å[} ’ß u<K? | ûA¢”}e v^v}e | 4 | 0.40 |
| 13 | É”u=Ø | ¿^Ñ@’>”}e u?”ÒKAKe | 2 | 0.20 |
| 14 | Ÿ<¢ (•”l›T | ¡^Af¢c=A¡e Ÿ<ý[e | 8 | 0.80 |
| 15 | Ÿ<¢ (ÉÉ]Ÿ | ¡^Af¢c=A¡e "ý]¾e | 8 | 0.80 |
| 16 | Ÿ<¢ ¡Le | ¡^Af¢c=A¡e¡Le | 8 | 0.80 |
| 17 | É”u=Ø | ›TÇ=“ óg=Á• | 2 | 0.80 |

| የፍትህ ሚኒስቴር | | | | |
|---|---|---|---|---|
| }. l | ¾›T`– SÖ]Á | ¾dA”e SÖ]Á | ¾’ÖL ªÒ u›T@]" ÊL` | ¾T"<Ý ªÒ u›T@]" ÊL` |
| 18 | S”l[ Øl` ª’@ | ~`~` ›u=c='>Ÿe | 6 | 0.60 |
| 19 | cTÁ© ’Öw×vT ª’@ | ~`~`›ð` | 6 | 0.60 |
| 20 | ›[”ÕÈ ’Öw×vT ª’@ | }`}`‰KAeûAKe | 6 | 0.60 |
| 21 | dm• ¨’@ | eƒ_ý„üMÁ c?’@ÒK?”c=e | 6 | 0.60 |
| 22 | ›[”ÕÈ ª’@ | ›ûKAüLA L`z• | 6 | 0.60 |
| 23 | S<`’>”Ó ª’@ | eƒ_ý„üK=Á Åc=ûA”e | 6 | 0.60 |
| 24 | ¾“Tኋ ª’@ | *“ "ü’K=e | 6 | 0.60 |
| 25 | Å[} HU^© ª’@ | eƒ_ý„üMÁ K?Ñ”e | 6 | 0.60 |
| 26 | Å[} kA ª’@ | eƒ_ý„üMÁaµÓ]c?Á | 6 | 0.60 |
| 27 | ¯A’ kA ª’@ | eƒ_ý„üMÁ cT>„`£• | 6 | 0.60 |
| 28 | ›”Ñ} kKuƒT ª’@ | eƒ_ý„üMÁ "ú¢L | 6 | 0.60 |
| 29 | ¾•Ux]” ª’@ | ƒ\~` ƒAû’>¡ƒ]Á | 6 | 0.60 |
| 30 | ›?K= ScM ª’@ | eƒ_ý„üMÁ ~`~` | 6 | 0.60 |
| 31 | ¾y=“eÄe ª’@ | eƒ_ý„üMÁ g=“MÁ | 10 | 0.60 |
| 32 | Ç¡Â | ›“e eû`d | 10 | 1.00 |
| 33 | Ç¡Â | È”Éac=Ó“ v¾¡K` | 10 | 1.00 |
| 34 | ƒ”g< u<“T Ç¡Â | *¡c=^ T¢› | 10 | 1.00 |

| የፍትህ ሚኒስቴር | | | | |
|---|---|---|---|---|
| }.l | ¾›T`– SÖ]Á | ¾dA”e SÖ]Á | ¾'ÖL ªÒ u›T@]" ÊL` | ¾T"<Ý ªÒ u›T@]" ÊL` |
| 35 | S”q[ kA Ç¡Â | ›“e ›?`Aƒa^A”Œe | 10 | 1.00 |
| 36 | vKl”à Ç¡Â | ›A}Á óK=Ñ<L | 10 | 1.00 |
| 37 | ’ß Ë`v Ç¡Â | •LfA’>e K=¨<¢•}e | 10 | 1.00 |
| 38 | Ç¡Â | È”Éac=Ó“ y=Æ›• | 10 | 1.00 |
| 39 | S”l[ u=Ý Ç¡Â | ›“e ›<”ÆL• | 10 | 1.00 |
| 40 | É”u=Ø | KAÔ•e+Ÿ• c?’@ÒKe | 2 | 0.20 |
| 41 | ¾Ñ’ƒ ´Uu uM | ‚`ýc=ö” zA]Ç=e | 8 | 0.80 |
| 42 | qp (Å[} u<L | õ^”¢K='e "e•’>¢K=e | 10 | 1.00 |
| 43 | fp | õ^”¢K='e ¡Lý„`’> | 10 | 1.00 |
| 44 | ¢Ÿ= qp | õ^”¢K='e ¢Ÿ= | 10 | 1.00 |
| 45 | vKl”à qp | õ^”¢K='e c?ó“ | 10 | 1.00 |
| 46 | ¾›?`Ÿ?M qp | õ^”¢K='e•`ŸLA | 10 | 1.00 |
| 47 | vKÑKð”ƒ qp | õ^”¢K='ee¢T}e | 10 | 1.00 |
| 48 | u<LT Ç¡Â | ›“e eƒ_ü^ | 10 | 1.00 |
| 49 | ƒ”g< Ç¡Â | ›“e Ÿ<¨`Ÿ<ÉL | 10 | 1.00 |
| 50 | vKÓ^Ý ¡”õ qp | Õ^”¢K='e c=KALS<e | 10 | 1.00 |
| 51 | vKÓ^Ý ¡”õ qp | õ^”¢K='e K?z”„AÉe | 10 | 1.00 |

| የፍትህ ሚኒስቴር | | | | |
|---|---|---|---|---|
| }.l | ¾›T`– SÖ]Á | ¾dA"e SÖ]Á | ¾'ÖL ªÒ u›T@]" ÊL` | ¾T"<Ý ªÒ u›T@]" ÊL` |
| 52 | ¨ÝK? )S"l[ 'ß) | ¢+•¡cAÉ K="<¢Òe}` | 14 | 1.40 |
| 53 | ´A | ›KAþ+" ›=Í=ý+Ÿe | 12 | 1.20 |
| 54 | ´A | d`Ÿ=Ç=›`'>e T@L•• | 16 | 1.60 |
| 55 | ´A | ýLeƒa'[e ÒUu?'c=e | 16 | 1.60 |
| 56 | É"u=Ø | ¿^Ñ>'>"}e ›=¾"+›•Òe}` | 10 | 1.00 |
| 57 | ÏÓ^ (vKl"à | '<T@Ç T@K?Ó]e | 10 | 1.00 |
| 58 | ƒMl ÏÓ^ | ›¡]K=¾U y<M†^A" | 20 | 2.00 |
| 59 | k[\ | ¿ùû ›=þýe | 12 | 1.20 |
| 60 | kA ›õ gKq | „Ÿe ›?`AƒaH>"Ÿe | 16 | 1.60 |
| 61 | Ñ<"Ú w^T gKq | vA"'>e}e w_y=e | 16 | 1.60 |
| 62 | ¾y"È`Ç=Ÿ"e gKq | „Ÿ<e Ç?Ÿ?'> | 16 | 1.60 |
| 63 | ÒÒ• | ýK=ÒÇ=e óMc='@K<e | 10 | 1.00 |
| 64 | e"²]ƒ | ›¡„òKA`'>e ›õ]"" | 10 | 1.00 |
| 65 | ƒMl ¾›X ›S, | W`AK? T¡c=T | 12 | 1.20 |
| 66 | ^c Ó^Ý ¾›X ›S, | GMc=Ä" K="<¢c?óL | 12 | 1.20 |
| 67 | ƒ"g< ¾›X ›S, | ›Mc=Ê ¡]e•• | 12 | 1.20 |
| 68 | ´"Ñ<`Ñ<` ¾›X ›S, | W`AK? \Ç=e | 10 | 1.00 |

| የፍትህ ሚኒስቴር | | | | |
|---|---|---|---|---|
| }.<br>l | ¾›T`– SÖ]Á | ¾dA”e SÖ]Á | ¾’ÖL ªÒ<br>u›T@]"<br>ÊL` | ¾T"<Ý ªÒ<br>u›T@]"<br>ÊL` |
| 69 | ¾¨<ÉL”É ›X ›S, | GMc=Ä” c?’@ÒK’c=e | 10 | 1.00 |
| 70 | Ç¡Â | ›“e ýL+]”Ÿe | 10 | 1.00 |
| 71 | É”u=Ø | KA”†^ Ÿ<Ÿ<L• | 2 | 0.20 |
| 72 | SÔØ ¨õ | ¢K=¾e T¡a]e | 8 | 0.80 |
| 73 | ò} ØI` Ú[v | *]*Ke L`z}e | 10 | 1.00 |
| 74 | JÅ w`~"" ukk” | þAc?óKAe \òy?”ƒ]e | 12 | 1.20 |
| 75 | ¾›gª ª•e | ›Uý`Ç= H@A | 10 | 1.00 |
| 76 | ¾sØ˜ ª•e | ‚K?û‡e üƒ\Ÿe | 10 | 1.00 |
| 77 | ¾w\e `Ów | ƒ^a” ªK=Á | 12 | 1.20 |
| 78 | ›[”ÕÈ •`Ów | ƒ^a”›¨<eƒ^K=e | 12 | 1.20 |
| 79 | ¨A^T `Ów | ¢K<Uv ›`Ÿ<<›ƒ]¡e | 12 | 1.20 |
| 80 | ¾sØ˜ `Ów | ¢K<UvK=y=Á | 10 | 1.00 |
| 81 | ’Öw×w `Ów | ¢K<UvÑ>’>Á | 8 | 0.80 |
| 82 | Ï^} [ÏU Ç¡Â | ›“e ›Ÿ<• | 10 | 1.00 |
| 83 | Ÿ<K=K=ƒ | z’@K<e eûA•ce | 6 | 0.60 |
| 84 | u<“T Ç¡Â | ›A+Á ô]“ | 10 | 1.00 |
| 85 | u<“T Ç¡Â | ’• ›?aAƒaõ•MT | 10 | 1.00 |

| የፍትህ ሚኒስቴር | | | | |
|---|---|---|---|---|
| }. l | ¾›T`– SÖ]Á | ¾dA"e SÖ]Á | ¾'ÖL ªÒ u›T@]" ÊL` | ¾T"<Ý ªÒ u›T@]" ÊL` |
| 86 | ¯A' 'ß Ç¡Â | ›A}Á "Aa" | 10 | 1.00 |
| 87 | cTÁ© É`ßƒ | ¢~]'>¡e ‰A'c=e | 8 | 0.80 |
| 88 | ¾›¨<aþ É`ßƒ | ¢~]'>¡e¢ƒ`'>¡e | 8 | 0.80 |
| 89 | ¾N?`K?Ÿ?" É`ßƒ | ¢~]'>¡eÇ=MÔ`'> | 8 | 0.80 |
| 90 | ¾›u=c='>Á Ùa | ¢^c=Áe ›u=c='>" | 12 | 1.20 |
| 91 | Å[} ¨A" ÖÏ Ùa | ¢^c=Áe"¨<Ç• | 12 | 1.20 |
| 92 | ò} ØI` ¾›gª É`ßƒ | ‚a¡Ke Ç¢^}e | 6 | 0.60 |
| 93. | Å[} u<L ¾›gª É`ßƒ | ‚a¡Ke›?¡c<e}e | 6 | 0.60 |
| 94. | vK ›^ƒ kKuƒ ¾›gª É`ßƒ | ‚a¡Ke"DÉ]c=•¡}e | 6 | 0.60 |
| 95. | ¾M†"e‚A" ¾›gª É`ßƒ | ‚a¡KeK=‹"e‚'> | 6 | 0.60 |
| 96. | vK'Öw×w ¾›gª É`ßƒ | ‚a¡Kec?'@ÒK<e | 6 | 0.60 |
| 97. | ›"Ñ} u=Ý ¾›gª É`ßƒ | ‚a¡Ke›Ñ<~^K=e | 6 | 0.60 |
| 98. | Aw^ | ›"e ¡K=Aü• | 10 | 1.00 |

| የፍትህ ሚኒስቴር | | | | |
|---|---|---|---|---|
| }.<br>l | ¾›T`– SÖ]Á | ¾dA"e SÖ]Á | ¾'ÖL ªÒ<br><br>u›T@]"<br>ÊL` | ¾T"<Ý ªÒ<br><br>u›T@]"<br>ÊL` |
| 99 | g<hA | L'>¾e ›?¡eŸ<u=„]e | 6 | 0.60 |
| 100 | g<hA | L'>¾e ¢L]e | 4 | 0.40 |
| 101 | Ú[v | ûc` Ó]cÄe | 2 | 0.20 |
| 102 | Ú[v | ûc`eªA"f'> | 2 | 0.20 |
| 103 | Ú[v | ýKAc?ûc` THK= | 4 | 0.40 |
| 104 | qp (vKu=Ý ›"Ñƒ | õ^"¢K='e K="<¢c?øe | 10 | 1.00 |
| 105 | "TA | LUýa„`'>e ‰Mu?Ae | 6 | 0.60 |
| 106 | Ï^} [ÏU "TA | LUýa„`'>eù`‡aeý‚\e | 6 | 0.60 |
| 107 | "TA | eüa c<ø`u<e | 6 | 0.60 |
| 108 | "TA | c='>^c="¡Le K?¢Òe}` | 6 | 0.60 |
| 109 | "TA | ¡^„õ^ c='^ | 8 | 0.80 |

| የፍትህ ሚኒስቴር | | | | |
|---|---|---|---|---|
| }. l | ¾›T`– SÖ]Á | ¾dA”e SÖ]Á | ¾’ÖL ªÒ u›T@]" ÊL` | ¾T¨<Ý ªÒ u›T@]" ÊL` |
| 110 | vKØl` ¡”õ gSK? | H>T”„ýe H>T”„ýe | 10 | 1.00 |
| 111 | Å[} kA ¾›uv kdT> | ’@¡•]'>Á ùMŠL | 8 | 0.80 |
| 112 | Å[} kA ¾›uv kdT> | ’@¡•]'>Ác?’@ÒK'c=e | 8 | 0.80 |
| 113 | Å[} kA ¾›uv kdT> | ’@¡•]'>Á•"²? | 8 | 0.80 |
| 114 | Å[} kA ¾›uv kdT> | ’@¡•]'>Áy?’<e• | 8 | 0.80 |
| 115 | ƒ”g< Ç¡Â | ›“e c?`" | 10 | 1.00 |
| 116 | ƒ”g< Ç¡Â | ›“eJ}”„• | 10 | 1.20 |
| 117 | Ñ<”Ú ’ß µ]ƒ | ~^¢ K=¨<¢+e | 12 | 1.20 |
| 118 | É”u=Ø | eƒ]MÇ ›eƒ]É | 2 | 0.20 |
| 119 | NU^© É”u=Ø | eƒ]MÇaÊúAÒ | 2 | 0.20 |
| 12 | É”u=Ø | eƒ]MÇT@L•+e | 2 | 0.20 |

| የፍትህ ሚኒስቴር | | | | |
|---|---|---|---|---|
| }. l | ¾›T`– SÖ]Á | ¾dA”e SÖ]Á | ¾’ÖL ªÒ<br>u›T@]"<br>ÊL` | ¾T¨<Ý ªÒ<br>u›T@]"<br>ÊL` |
| 0 | | | | |
| 121 | Ú[v | ýKAcÄe vÓLõ†ƒ | 4 | 0.40 |
| 122 | Ú[v | ýKAcÄeŸ<Ÿ<L}e | 4 | 0.40 |
| 123 | Ú[v | ýKAcÄeÒMu<L | 4 | 0.40 |
| 124 | Ú[v | ýKAcÄe›=”}`T>Åe | 4 | 0.40 |
| 125 | mMd | µe+aýe ›u=c=’>" | 2 | 0.20 |
| 126 | ¾SekM ¨õ | ›=¨<ýK?¡}e ›¡c=L]e | 6 | 0.60 |
| 127 | ¾SekM ¨õ | ›=¨<ýK?¡}eT¡a]e | 6 | 0.60 |
| 128 | ƒ”g< Ç¡Â | ›“e ü’@KAý | 10 | 1.00 |
| 129 | ƒ”g< Ç¡Â | ›“eŸ?ý’c=e | 10 | 1.00 |
| 130 | Ó”Å q`l` | T@fú¢e Ô`, | 8 | 0.80 |

| የፍትህ ሚኒስቴር | | | | |
|---|---|---|---|---|
| }. l | ¾›T`– SÖ]Á | ¾dA”e SÖ]Á | ¾’ÖL ªÒ u›T@]" ÊL` | ¾T"<Ý ªÒ u›T@]" ÊL` |
| 131 | ¾’<u=Á Ó”Å q`l` | "Uü‚^ ’<u=" | 8 | 0.80 |

## N. XÆB

| }. l | ¾›T`– SÖ]Á | ¾dA”e SÖ]Á | ¾’ÖL ªÒ u›T@]" ÊL` | ¾T"<Ý ªÒ u›T@]" ÊL` |
|---|---|---|---|---|
| 1 | XÆB | ]•• AýKAýe ûK=Åe | 2.00 | 0.20 |
| 2 | XÆB | ]•• AýKAýeeŸKÑK= | 2.00 | 0.20 |
| 3 | XÆB | ]•• AýKAýe¿’>•’>Á}e | 2.00 | 0.20 |
| 4 | XÆB | • AýKAýe Ÿ<’>ae ƒ]e | 2.00 | 0.20 |
| 5 | XÆB | • AýKAýeK=•L}e | 2.00 | 0.20 |
| 6 | XÆB | K?ý„• AýKAýe Ÿ?] | 2.00 | 0.20 |
| 7 | XÆB | K?ý„• AýKAýeT¡a]A”Ÿe | 2.00 | 0.20 |
| 8 | XÆB | K?ý„• AýKAýe’>Ó]”" | 2.00 | 0.20 |
| 9 | XÆB | ›?]¡e ¢KAw]’e | 2.00 | 0.20 |
| 10 | XÆB | ›?]¡efTK=Ÿe | 2.00 | 0.20 |
| 11 | XÆB | ûA}” c?v | 10 | 1.00 |

| }. l | ¾›T`– SÖ]Á | ¾dA”e SÖ]Á | ¾’ÖL ªÒ u›T@]" ÊL` | ¾T¨<Ý ªÒ u›T@]" ÊL` |
|---|---|---|---|---|
| 12 | XÆB | ›?K<aÓK<“ Ÿ<Ÿ<L• | 2.00 | 0.20 |
| 13 | XÆB | ›û^¡•eúe Í¡f’> | 2.00 | 0.20 |
| 14 | XÆB | ›û^¡•eúe›=_Ñ<L]e | 2.00 | 0.20 |
| 15 | XÆB | › ƒ^¡•eúe óL¡e | 2.00 | 0.20 |
| 16 | XÆB | › ƒ^¡•eúe›=aÑ<L]e | 2.00 | 0.20 |
| 17 | XÆB | › ƒ^¡•eúeTÑ_+ | 2.00 | 0.20 |
| 18 | XÆB | › ƒ^¡•eúeTA¡aK?úÊ• | 2.00 | 0.20 |
| 19 | XÆB | › ƒ^¡•eúee¢`,c= | 2.00 | 0.20 |
| 20 | XÆB | ¢K<u` w_y=e | 2.00 | 0.20 |
| 21 | XÆB | ¢K<u`õKA\L”}e | 2.00 | 0.20 |
| 22 | XÆB | ¢K<u`aÊ^ˆe | 2.00 | 0.20 |
| 23 | XÆB | ¢K<u`eT>´ | 2.00 | 0.20 |
| 24 | XÆB | ¢K<u`•AKA] | 2.00 | 0.20 |
| 25 | XÆB | ¢K<u` | 2.00 | 0.20 |
| 26 | XÆB | ¡a•öýL+e ÅÑ’> | 2.00 | 0.20 |
| 27 | XÆB | ¡a•öýL+eJ•Uw•› | 2.00 | 0.20 |
| 28 | XÆB | ÇeüK+e e"w^ | 1.50 | 0.15 |

| }. l | ¾›T`– SÖ]Á | ¾dA”e SÖ]Á | ¾’ÖL ªÒ u›T@]" ÊL` | ¾T¨<Ý ªÒ u›T@]" ÊL` |
|---|---|---|---|---|
| 29 | XÆB | Ç=eûK=Åe •Aýe | 1.60 | 0.16 |
| 30 | XÆB | ÉaVòe K="}e | 2.00 | 0.20 |
| 31 | XÆB | Æu[ K<ƒ]¡e | 2.00 | 0.20 |
| 32 | XÆB | ›A['>e ›õ]"" | 2.00 | 0.20 |
| 33 | XÆB | Ó^Á „KA'> | 2.00 | 0.20 |
| 34 | XÆB | H@T^Ñ]e Ÿ?K] | 2.00 | 0.20 |
| 35 | XÆB | H@T^Ñ]e•„•'>› | 2.00 | 0.20 |
| 36 | XÆB | LUýaúe óK=Ó•ce | 2.00 | 0.20 |
| 37 | XÆB | LA¢òÊ" Ÿ?ý'e | 2.00 | 0.20 |
| 38 | XÆB | LA¢òÊ"Ç=ý[c=ae}` | 2.00 | 0.20 |
| 39 | XÆB | LA¢òÊ"• AKA] | 2.00 | 0.20 |
| 40 | XÆB | SIMÁ Ÿ?ý'c=e | 2.00 | 0.20 |
| 41 | XÆB | SµÊ" ýK<SvAWýe | 2.00 | 0.20 |
| 42 | XÆB | SµÊ"_Ñ<L]e | 2.00 | 0.20 |
| 43 | XÆB | SµÊ"WT>›^"}e | 2.00 | 0.20 |
| 44 | XÆB | T>c`Lýe x}Ñ] | 2.00 | 0.20 |
| 45 | XÆB | "ƒ]c=ƒ[e ›K=zc? | 2.00 | 0.20 |

| }. l | ¾›T`– SÖ]Á | ¾dA”e SÖ]Á | ¾’ÖL ªÒ u›T@]" ÊL` | ¾T¨<Ý ªÒ u›T@]" ÊL` |
|---|---|---|---|---|
| 46 | XÆB | òKA•S’e v}`evA | 2.00 | 0.20 |
| 47 | XÆB | òKA•S’eu?Ÿ<›`} | 2.00 | 0.20 |
| 48 | XÆB | òKA•S’eH@ ƒaK?úÊ}e | 2.00 | 0.20 |
| 49 | XÆB | òKA•S’eù”•}e | 2.00 | 0.20 |
| 50 | XÆB | òKA•S’eWT>z]Í}e | 2.00 | 0.20 |
| 51 | XÆB | ýac=AU“ T@LÓ]e | 2.00 | 0.20 |
| 52 | XÆB | ýac=AU“fTK=" | 2.00 | 0.20 |
| 53 | XÆB | ýac=AU“\eûK= | 2.00 | 0.20 |
| 54 | XÆB | dVòe ›”ÔK?”c=e | 2.00 | 0.20 |
| 55 | XÆB | dVòevAc?]Á}e | 2.00 | 0.20 |
| 56 | XÆB | dVòeùM†` | 2.00 | 0.20 |
| 57 | XÆB | dVòeù”Ÿ<L}e | 2.00 | 0.20 |
| 58 | XÆB | dVòee¢"] | 2.00 | 0.20 |
| 59 | XÆB | dVòeK=u=L’e | 2.00 | 0.20 |
| 60 | XÆB | dVòe•”Ò’>Ÿe | 2.00 | 0.20 |
| 61 | XÆB | dVòK=¡e z]Áu=Ke | 2.00 | 0.20 |
| 62 | XÆB | ^Uò*ðe *¡c=]”Ÿe | 2.00 | 0.20 |

| }. l | ¾›T`– SÖ]Á | ¾dA”e SÖ]Á | ¾'ÖL ªÒ u›T@]" ÊL` | ¾T¨<Ý ªÒ u›T@]" ÊL` |
|---|---|---|---|---|
| 63 | XÆB | ^Uò*ðe\waù”•}e | 2.00 | 0.20 |
| 64 | XÆB | e"ò*òe ›Mxù“¡•}e | 2.00 | 0.20 |
| 65 | XÆB | ‚K?e¢øe Ç^ | 2.00 | 0.20 |
| 66 | XÆB | ‚K?e¢øeùM†` | 2.00 | 0.20 |
| 67 | XÆB | Å”Éaeúe ýLAK?úe | 2.00 | 0.20 |
| 68 | XÆB | ›=LýfAÉÉ Kay`Ç=Ñ@ | 2.00 | 0.20 |
| 69 | XÆB | “Í HÎ | 2.00 | 0.20 |
| 70 | XÆB | “ÍT@L•K<" | 2.00 | 0.20 |
| 71 | XÆB | “Í’>Ó]¢K=e | 2.00 | 0.20 |
| 72 | XÆB | “ÍûK=Ç | 2.00 | 0.20 |
| 73 | XÆB | u=+e *]•”e | 2.00 | 0.20 |
| 74 | XÆB | "¨<ce TŸ<L}e | 2.00 | 0.20 |
| 75 | XÆB | "¨<ce_c=Se | 2.00 | 0.20 |
| 76 | XÆB | "¨<ceaUu?}e | 2.00 | 0.20 |
| 77 | XÆB | ›?Ÿ=e ú^T>ÅU | 2.00 | 0.20 |
| 78 | XÆB | ›?Ÿ=ez]› | 2.00 | 0.20 |

S. ¾•"iLK=ƒ" ¾ÑuKA ^Á

| }.l | ¾›T`– SÖ]Á | ¾dA"e SÖ]Á | ¾'ÖL ªÒ u›T@]" ÊL` | ¾T¨<Ý ªÒ u›T@]" ÊL` |
|---|---|---|---|---|
| 1 | •"iLK=ƒ | '@Teúe Ç=¡[f'> | 1.60 | 0.16 |
| 2 | •"iLK=ƒ | dA„Ç¡+Ke e"u` | 1.60 | 0.16 |
| 3 | •"iLK=ƒ | H@T>Ç¡+Ke ›Mxù"¡}e | 1.60 | 0.16 |
| 4 | •"iLK=ƒ | H@T>Ç¡+Ke vaÇ"e | 1.60 | 0.16 |
| 5 | •"iLK=ƒ | H@T>Ç¡+Ke waŸ= | 1.60 | 0.16 |
| 6 | •"iLK=ƒ | H@T>Ç¡+Ke Ÿ`K= | 1.60 | 0.16 |
| 7 | •"iLK=ƒ | H@T>Ç¡+Ke õLy=y=]Ç=e | 1.60 | 0.16 |
| 8 | •"iLK=ƒ | H@T>Ç¡+Ke ›AfK=úe | 1.60 | 0.16 |
| 9 | •"iLK=ƒ | H@T>Ç¡+Ke Ìu'>c=e | 1.60 | 0.16 |
| 10 | •"iLK=ƒ | H@T>Ç¡+Ke L+"¨<Ç}e | 1.60 | 0.16 |
| 11 | •"iLK=ƒ | H@T>Ç¡+Ke Tx› | 1.60 | 0.16 |
| 12 | •"iLK=ƒ | H@T>Ç¡+Ke T¡aò*K=e | 1.60 | 0.16 |
| 13 | •"iLK=ƒ | H@T>Ç¡+Ke *òK?úe | 1.60 | 0.16 |
| 14 | •"iLK=ƒ | H@T>Ç¡+Ke û`Ÿ] | 1.60 | 0.16 |

| }.l | ¾›T`– SÖ]Á | ¾dA”e SÖ]Á | ¾’ÖL ªÒ u›T@]" ÊL` | ¾T¨<Ý ªÒ u›T@]" ÊL` |
|---|---|---|---|---|
| 15 | •”iLK=ƒ | H@T>Ç¡+Ke aue}e | 1.60 | 0.16 |
| 16 | •”iLK=ƒ | H@T>Ç¡+Ke \eûK= | 1.60 | 0.16 |
| 17 | •”iLK=ƒ | H@T>Ç¡+Ke dA“}e | 1.60 | 0.16 |
| 18 | •”iLK=ƒ | H@T>Ç¡+Ke eT>²= | 1.60 | 0.16 |
| 19 | •”iLK=ƒ | H@T>Ç¡+Ke ƒaúÊMúe | 1.60 | 0.16 |
| 20 | •”iLK=ƒ | H@T>Ç¡+Ke fTK=Ÿe | 1.60 | 0.16 |
| 21 | •”iLK=ƒ | H@T>Ç¡+Ke •AKA] | 1.60 | 0.16 |
| 22 | •”iLK=ƒ | H@T>Ç¡+Ke ›õ]"”e | 1.60 | 0.16 |
| 23 | •”iLK=ƒ | JVöK=e óc=Á• | 1.60 | 0.16 |
| 24 | •”iLK=ƒ | K=AÔÇ¡•AKe Ñ<~^K=e | 1.60 | 0.16 |
| 25 | •”iLK=ƒ | K=AÔÇ¡•AKe Ÿ?’>’c=e | 1.60 | 0.16 |
| 26 | •”iLK=ƒ | K=AÔÇ¡•AKe e¢`,c= | 1.60 | 0.16 |
| 27 | •”iLK=ƒ | K=AÔÇ¡•AKe fTK=Ÿe | 1.60 | 0.16 |
| 28 | •”iLK=ƒ | K=AÔÇ¡•AKe c<Ç’@”c=e | 1.60 | 0.16 |
| 29 | •”iLK=ƒ | ]e~[e ¡\c=ð` | 1.60 | 0.16 |

| }.l | ¾›T`– SÖ]Á | ¾dA"e SÖ]Á | ¾'ÖL ªÒ u›T@]" ÊL` | ¾T"<Ý ªÒ u›T@]" ÊL` |
|---|---|---|---|---|
| 30 | •"iLK=ƒ | ]e~[e òK=úc= | 1.60 | 0.16 |
| 31 | •"iLK=ƒ | ]e~[e \ýeƒ]e | 1.60 | 0.16 |
| 32 | •"iLK=ƒ | ]e~[e õLy=ù"¡•}e | 1.60 | 0.16 |
| 33 | •"iLK=ƒ | •¿Ç¡+Ke GcMŸ<e+ | 1.60 | 0.16 |
| 34 | •"iLK=ƒ | e,•Ç¡+Ke e,•Ç¡+Ke | 1.60 | 0.16 |
| 35 | •"iLK=ƒ | •["„L ›'<L]e | 1.60 | 0.16 |
| 36 | ÑuKA | ›ÒT ›ÒT | 1.60 | 0.16 |
| 37 | ÑuKA | ›ÒT ¢`'> | 1.20 | 0.12 |
| 38 | ÑuKA | ›ÒT Ê_A | 1.20 | 0.12 |
| 39 | ÑuKA | ›ÒT G`ƒT'> | 1.20 | 0.12 |
| 40 | ÑuKA | ›ÒT ø`c=T>K=e | 1.20 | 0.12 |
| 41 | ÑuKA | ›ÒT \üK= | 1.20 | 0.12 |
| 42 | ÑuKA | ›ÒT c="A• | 1.20 | 0.12 |
| 43 | ÑuKA | ›ÒT eú•d | 1.20 | 0.12 |
| 44 | ÑuKA | ›ÒT ›'@¡,"e | 1.20 | 0.12 |
| 45 | ÑuKA | e,K=* ›ƒ]¢K=e | 1.20 | 0.12 |
| 46 | ÑuKA | e,K=* dÁ•Òe}` | 1.20 | 0.12 |
| 47 | ÑuKA | e,K=* òK=ýc= | 1.20 | 0.12 |

| }.l | ¾›T`– SÖ]Á | ¾dA”e SÖ]Á | ¾’ÖL ªÒ u›T@]" ÊL` | ¾T¨<Ý ªÒ u›T@]" ÊL` |
|---|---|---|---|---|
| 48 | ÑuKA | e,K=* µ’<^ | 1.20 | 0.12 |
| 49 | ÑuKA | ¿aTeƒ]¡e *c=L• | 1.20 | 0.12 |
| 50 | gblÖ | ²?“ÒT v+K=ð^ | 1.20 | 0.12 |
| 51 | ÑuKA | ²?“ÒT •AKA] | 1.20 | 0.12 |
| 52 | •eeƒ | "T@M* ›ò’>e | 2.60 | 0.26 |
| 53 | •eeƒ | "T@M* ›õ]"’e | 2.60 | 0.26 |
| 54 | •eeƒ | "T@M* u=•’>›}e | 2.60 | 0.26 |
| 55 | •eeƒ | "T@M* "M"]"`’e | 2.60 | 0.26 |
| 56 | •eeƒ | "T@M* ÇAK?úe | 2.60 | 0.26 |
| 57 | •eeƒ | "T@M* Ó^c=Ke | 2.60 | 0.26 |
| 58 | •eeƒ | "T@M* \eûK= | 2.60 | 0.26 |
| 59 | •eeƒ | "T@M* c?’@ÒK’c=e | 1.20 | 0.12 |
| 60 | •eeƒ | ^SöM›” Ÿ`e,’> | 1.20 | 0.12 |
| 61 | •”iLK=ƒ | ‰Mc=Åe *c=L}e | 1.20 | 0.12 |
| 62 | •”iLK=ƒ | ‰Mc=Åe ^Ò²= | 1.20 | 0.12 |
| 63 | •”iLK=ƒ | K?AÔfT ›õ[U | 1.20 | 0.12 |
| 64 | •”iLK=ƒ | K?AÔfT üÊ"`’>›}U | 1.20 | 0.12 |
| 65 | •”iLK=ƒ | K?AÔfT W”ÉzK= | 1.20 | 0.12 |

| }.l | ¾›T`– SÖ]Á | ¾dA”e SÖ]Á | ¾’ÖL ªÒ u›T@]" ÊL` | ¾T¨<Ý ªÒ u›T@]" ÊL` |
|---|---|---|---|---|
| 66 | •”iLK=ƒ | K?AÔfT y=”c=Ñ<^_ | 1.20 | 0.12 |
| 67 | •”iLK=ƒ | Tu?Á wóy=¢K=e | 1.20 | 0.12 |
| 68 | •”iLK=ƒ | Tu?Á H>MÅw^”Ç=+ | 1.20 | 0.12 |
| 69 | •”iLK=ƒ | Tu?Á ›=eK= | 1.20 | 0.12 |
| 70 | •”iLK=ƒ | Tu?Á TŸ<K=›w]e | 1.20 | 0.12 |
| 71 | •”iLK=ƒ | Tu?Á T@ÒK<^ | 1.20 | 0.12 |
| 72 | •”iLK=ƒ | Tu?Á ýL’>õa”e | 1.20 | 0.12 |
| 73 | •”iLK=ƒ | Tu?Á Ÿ<’Ÿ<•’@ƒ | 1.20 | 0.12 |
| 74 | •”iLK=ƒ | Tu?Á e}]›• | 1.20 | 0.12 |
| 75 | •”iLK=ƒ | Tu?Á z]› | 1.20 | 0.12 |
| 76 | •”iLK=ƒ | Tu?Á ©’Ò+ | 1.20 | 0.12 |
| 77 | •”iLK=ƒ | û“eúe •’¡_Ç= | 1.20 | 0.12 |
| 78 | •”iLK=ƒ | û“eúe ªKu`Ñ> | 1.20 | 0.12 |
| 79 | •”iLK=ƒ | ›c”„Ç¡+Ke xeŸ=Á’e | 1.20 | 0.12 |
| 80 | •”iLK=ƒ | H@M*xKe eüŸ= | 1.20 | 0.12 |
| 81 | •”iLK=ƒ | H@M*xKe ’>¨<T’> | 1.20 | 0.12 |
| 82 | •”iLK=ƒ | L•e+› xc=Á | 1.20 | 0.12 |
| 83 | •”iLK=ƒ | L•e+› "\K=*ù”¡•• | 1.20 | 0.12 |

| }.l | ¾›T`– SÖ]Á | ¾dA”e SÖ]Á | ¾’ÖL ªÒ u›T@]" ÊL` | ¾T¨<Ý ªÒ u›T@]" ÊL` |
|---|---|---|---|---|
| 84 | •”iLK=ƒ | L•e+› Ê]* | 1.20 | 0.12 |
| 85 | •”iLK=ƒ | L•e+› KA”Ñ>"¨<Ç• | 1.20 | 0.12 |
| 86 | •”iLK=ƒ | c=ÊÅ`T>Áe w_’] | 1.20 | 0.12 |
| 87 | •”iLK=ƒ | c=ÊÅ`T>Áe S<¡a“• | 1.20 | 0.12 |
| 88 | •”iLK=ƒ | c=ÊÅ`T>Áe eT>´ | 1.20 | 0.12 |
| 89 | •”iLK=ƒ | c=ÊÅ`T>Áe eƒ]›• | 1.20 | 0.12 |
| 90 | •”iLK=ƒ | òKA¢`}e H`ÅÑ] | 1.20 | 0.12 |
| 91 | •”iLK=ƒ | c=ÊÅ`T>Áe ›=”}`T>Ç=e | 1.20 | 0.12 |
| 92 | •”iLK=ƒ | òKA¢`}e òK=ýc= | 1.20 | 0.12 |
| 93 | •”iLK=ƒ | òKA¢`}e eú“K=e | 1.20 | 0.12 |
| 94 | •”iLK=ƒ | ¢`Ç=Ke ƒaúÊe}`’U | 1.20 | 0.12 |
| 95 | •”iLK=ƒ | Ñ[Jd[e õLy=Ñ<L]e | 1.30 | 0.130 |
| 96 | •”iLK=ƒ | Ñ[Jd[e T@Ë` | 1.50 | 0.150 |

W. xR©ñ

| }.l | ¾›T`– SÖ]Á | ¾dA”e SÖ]Á | ¾’ÖL ªÒu›T@]" ÊL` | ¾T¨<Ý ªÒu›T@]" ÊL` |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ›`Í• | z^’e ›Mu=Ñ<L]e | 3.60 | 0.36 |
| 2 | ›`Í• | z^’e ›?¡d}T+Ÿe | 1.50 | 0.15 |
| 3 | ›`Í• | z^’e ’>KA+Ÿe | 3.00 | 0.30 |
| 4 | ›`Í• | ›”c=KA¡^’>¾U fTK=ŸU | 0.12 | 0.012 |

[. •”l^]ƒ“ Ñ<`Ø

| }.l | ¾›T`– SÖ]Á | ¾dA”e SÖ]Á | ¾’ÖL ªÒu›T@]" ÊL` | ¾T¨<Ý ªÒ u›T@]" ÊL` |
|---|---|---|---|---|
| 1 | Ñ<`Ø | u<ö _Ñ<L]e | 1.20 | 0.12 |
| 2 | Ñ<`Ø | u<ö Ò`T’> | 1.20 | 0.12 |
| 3 | Ñ<`Ø | u<ö ²?ae | 1.20 | 0.12 |
| 4 | Ñ<`Ø | u<ö ÆÉf’> | 1.20 | 0.12 |
| 5 | Ñ<`Ø | u<ö wL”ö`Ç= | 1.20 | 0.12 |
| 6 | Ñ<`Ø | u<ö L”Ò•’c=e | 1.20 | 0.12 |
| 7 | Ñ<`Ø | u<ö Ÿ`’>ÁÑ@ | 1.20 | 0.12 |
| 8 | Ñ<`Ø | u<ö ›eT_ | 1.20 | 0.12 |
| 9 | Ñ<`Ø | u<ö ü”„’> | 1.20 | 0.12 |

| }.l | ¾›T`– SÖ]Á | ¾dA”e SÖ]Á | ¾’ÖL ªÒu›T@]" ÊL` | ¾T¨<Ý ªÒ u›T@]" ÊL` |
|---|---|---|---|---|
| 10 | Ñ<`Ø | u<ö K<Ñ”c=e | 1.20 | 0.12 |
| 11 | Ñ<`Ø | u<ö e,’Ç†’] | 1.20 | 0.12 |
| 12 | Ñ<`Ø | u<ö TŸ<L}e | 1.20 | 0.12 |
| 13 | •”l^]ƒ | K?ý„úK=e x”Í= | 1.20 | 0.12 |
| 14 | •”l^]ƒ | ›õ]³Ke "DÉ]y=•}e | 1.20 | 0.12 |
| 15 | •”l^]ƒ | ›õ]³Ke y=+Ñ` | 1.20 | 0.12 |
| 16 | •”l^]ƒ | GAýaK=¾e “c<}e | 1.20 | 0.12 |
| 17 | •”l^]ƒ | GAýaK=¾e y=]Ç=õL›e | 1.20 | 0.12 |
| 18 | •”l^]ƒ | "c=• c?’@ÒK’c=e | 1.20 | 0.12 |
| 19 | •”l^]ƒ | ÓA]A•T@[e u=óc=Á}e | 1.20 | 0.12 |
| 20 | •”l^]ƒ | ˆaT”+e ü}`c= | 1.20 | 0.12 |
| 21 | •”l^]ƒ | H@T>ce T`V^}e | 1.20 | 0.12 |
| 22 | •”l^]ƒ | H>MÅw^”+› T¡a• Aû’U | 1.20 | 0.12 |
| 23 | •”l^]ƒ | HAL[“ ÒLT’c=e | 1.20 | 0.12 |
| 24 | •”l^]ƒ | ^“ ›”ÔK?K’c=e | 1.20 | 0.12 |
| 25 | •”l^]ƒ | ^“ *¡eú•K=e | 1.20 | 0.12 |
| 26 | •”l^]ƒ | ^“ ©+ | 1.20 | 0.12 |
| 27 | •”l^]ƒ | „V}`“ ¡]ý„+e | 1.20 | 0.12 |

| }.l | ¾›T`– SÖ]Á | ¾dA”e SÖ]Á | ¾’ÖL ªÒu›T@]" ÊL` | ¾T¨<Ý ªÒ u›T@]" ÊL` |
|---|---|---|---|---|
| 28 | •”l^]ƒ | +Ÿ=Ç=“ ›”ˆ‚ | 1.20 | 0.12 |
| 29 | •”l^]ƒ | +Ÿ=Ç=“ TeŸ['c=e | 1.20 | 0.12 |
| 30 | •”l^]ƒ | +Ÿ=Ç=“ ùT>KA | 1.20 | 0.12 |
| 31 | •”l^]ƒ | +Ÿ=Ç=“ ûac=c=T | 1.20 | 0.12 |
| 32 | •”l^]ƒ | +Ÿ=Ç=“ eˆK<¢[U | 1.20 | 0.12 |
| 33 | •”l^]ƒ | ñ]•vƒ]Ÿe x}Ñ> | 1.20 | 0.12 |
| 34 | •”l^]ƒ | ñ]•vƒ]Ÿe “•K’c=e | 1.20 | 0.12 |
| 35 | •”l^]ƒ | ñ]•vƒ]Ÿe ›¡]ÊAÉe | 1.20 | 0.12 |
| 36 | •”l^]ƒ | ñ]•vƒ]Ÿe ø`þMT}e | 1.20 | 0.12 |
| 37 | •”l^]ƒ | ñ]•vƒ]Ÿe T’>¨<}e | 1.20 | 0.12 |
| 38 | •”l^]ƒ | ñ]•vƒ]Ÿe u•Ñ] | 1.20 | 0.12 |

W"Ö[´ ²Ö˜

¾Æ` •"edƒ ¨<Ö?„‹" ¨Å ¨<Ü ¾SLŸ=Á ¡õÁ }S"

| }.l. | ¾ "ed¨<eU | 'ÖL qÇ | U"×õ 'ÖL | ŸI`Ø^ß ¾}W^ U"×õ | | | Ÿß" pLƒ ¾} W^ | S<K< uÉ" | k"É | Ø`e | ¾^e ›Ø" ƒ | "IL M |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ƒ"i | S"ŸK – | ƒMp | | | | | | |
| | | w` | w` | w` | w` | w` | w` | w` | w` | w` | w` | w` |
| 1 | ´"Ëa (}^ | 20 | 10 | 20 | 30 | 50 | 30 | 50 | - | - | 20 | - |
| 2 | ´"Ëa (ßLÇ | 40 | 10 | 60 | 80 | 90 | 80 | 110 | - | - | 50 | - |
| 3 | ´"Ëa)NTÉ`Áe | 40 | 10 | 50 | 60 | 80 | 60 | 90 | - | - | 40 | - |
| 4 | ÉŸ<L (}^ | 20 | 10 | 30 | 50 | 70 | 70 | 120 | 30 | - | 30 | - |
| 5 | ÉŸ<L (¾U'>M¡ | 30 | 20 | 50 | 80 | 110 | 110 | 180 | 40 | - | 40 | - |
| 6 | Ôi | 30 | - | - | - | 30 | 50 | 100 | 30 | - | 30 | - |
| 7 | ÇMÒ ›"uX | 30 | 20 | 50 | 60 | 80 | 80 | 110 | - | - | 40 | - |
| 8 | ¾Æ` ÉSƒ | 40 | 20 | 80 | 110 | 180 | 80 | 180 | - | - | 40 | - |
| 9 | Ñ<_³ | 20 | 10 | 80 | 110 | 150 | 60 | 110 | - | - | 20 | - |
| 10 | ›µ | 150 | - | - | - | 100 | 180 | 110 | - | - | 50 | - |
| 11 | ›="g< (¾Ñ<"}` | 10 | 10 | 30 | 40 | 60 | 50 | 70 | 10 | - | 20 | - |
| 12 | ›="g<)¾fMƒ) | 10 | 10 | 30 | 40 | 60 | 50 | 70 | 10 | | 20 | - |
| 13 | T>Çs }^ | 10 | 10 | 30 | 40 | 60 | 50 | 70 | 10 | | 20 | - |
| 14 | kua (Ða cò | 30 | 10 | 40 | 50 | 70 | 50 | 70 | - | | 20 | - |

| }.l. | ¾ ”ed¨<eU | ’ÖL qÇ | U”×õ ’ÖL | ŸI`Ø^ß ¾}W^ U”×õ | | | Ÿß” pLƒ ¾} W^ | S<K < uÉ” | k”É | Ø`e | ¾^e ›Ø” ƒ | ” ìL M |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ƒ”i | S"ŸK _ | ƒMp | | | | | | |
| | | w` | w` | w` | w` | w` | w` | w` | w` | w` | w` | w` |
| 15 | ¾T@Ç õ¾M (¾Ó^”ƒ | 20 | 10 | 30 | 50 | 70 | 170 | 120 | 30 | | 30 | |
| 16 | ¾T@Ç õ¾M (¾cS]”Ó | 20 | 10 | 30 | 50 | 70 | 170 | 120 | 30 | - | 30 | |
| 17 | óa ÉSƒ (}^ | 20 | 10 | 30 | 40 | 50 | 50 | 70 | - | - | 30 | |
| 18 | óa ÉSƒ ÖnÖq | 20 | 10 | 30 | 40 | 50 | 50 | 70 | - | - | 30 | |
| 19 | ›”Ñ} [ÏT@ | 30 | 10 | 30 | 40 | 50 | 50 | 70 | 30 | - | 30 | |
| 20 | Ø”†M | 20 | 10 | 30 | 50 | 70 | 30 | 50 | - | - | 20 | |
| 21 | q`Ÿ? (K?M«M | 30 | 10 | 30 | 40 | - | 40 | 70 | 30 | - | 30 | |
| 22 | Ñ<T_ | 20 | - | 10 | 20 | - | 110 | 220 | - | 40 | 40 | |
| 23 | ¾Æ` ›XT (ƒMl | 20 | - | - | - | - | 40 | 60 | - | 30 | 30 | |
| 24 | Ïw | 30 | 10 | 30 | 50 | 70 | 50 | 70 | - | - | 30 | |
| 25 | i¢¢ | 10 | 10 | 30 | 50 | 70 | 30 | 50 | - | - | 20 | |
| 26 | kua (Ë`v Øl` | 30 | 10 | 40 | 50 | 70 | 50 | 70 | - | - | 20 | |
| 27 | kua (}^ | 30 | 10 | 40 | 50 | 70 | 50 | 70 | - | - | 20 | |
| 28 | kua (vKÑA” SeS` | 30 | 10 | 40 | 50 | 70 | 40 | 70 | - | - | 20 | |

| }.l. | ¾ ”ed¨<eU | ’ÖL qÇ | U”×õ ’ÖL | Ÿl`Ø^ß ¾}W^ U”×õ | | | Ÿß” pLƒ ¾} W^ | S<K< uÉ” | k”É | Ø`e | ¾^e ›Ø”ƒ | ”lM |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ƒ”i | S"ŸK — | ƒMp | | | | | | |
| | | w` | w` | w` | w` | w` | w` | w` | w` | w` | w` | w` |
| 29 | ce | 20 | 10 | 30 | 30 | 50 | 40 | 50 | 20 | - | 20 | |
| 30 | ›Ò²” (¾qL | 40 | 20 | 30 | 50 | 70 | 60 | 120 | 30 | - | 30 | |
| 31 | ›Uv^AK? | 40 | 20 | 30 | 50 | 70 | 60 | 120 | 30 | - | 30 | |
| 32 | ’w` | 730 | 550 | 550 | 730 | 1090 | 900 | 1090 | - | - | 40 | |
| 33 | ›”uX | 220 | 180 | 110 | 150 | 180 | 290 | 510 | - | - | 40 | |
| 34 | gKUØTØ (¾Ówê | 20 | 10 | 30 | 40 | 50 | 50 | 70 | - | - | 30 | |
| 35 | gKUØTØ ([ÏU | 20 | 10 | 30 | 40 | 50 | 50 | 70 | - | - | 30 | |
| 36 | gKUØTØ (É”¡Â | 20 | 10 | 30 | 40 | 50 | 50 | 70 | - | - | 30 | |
| 37 | Ú• | 20 | 10 | 50 | 60 | 80 | 40 | 60 | - | - | 20 | |
| 38 | Ù× (Ó_y?ƒ | 20 | 10 | 50 | 60 | 80 | 40 | 60 | - | - | 20 | |
| 39 | Ù× (y`y?ƒ | 20 | 10 | 50 | 60 | 80 | 40 | 60 | - | - | 20 | |
| 40 | ¾ÅÒ ›Ò²” | 60 | 20 | 50 | 80 | 110 | 90 | 180 | 40 | - | 40 | |
| 41 | ôq | 30 | 10 | 40 | 50 | 70 | 50 | 70 | 20 | - | 20 | |
| 42 | dL | 40 | 20 | 30 | 50 | 70 | 60 | 120 | 30 | - | 30 | |
| 43 | ¾¨<• uÓ | 20 | 10 | 40 | 50 | 70 | 30 | 50 | - | | 20 | |

| }.l. | ¾ ”ed¨<eU | ’ÖL qÇ | U”×õ ’ÖL | ŸI`Ø^ß ¾}W^ U”×õ | | | Ÿß” pLƒ ¾} W^ | S<K< uÉ” | k”É | Ø`e | ¾^e ›Ø”ƒ | ” ïL M |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ƒ”i | S"ŸK – | ƒMp | | | | | | |
| | | w` | w` | w` | w` | w` | w` | w` | w` | w` | w` | w` |
| 44 | cÔ” | 150 | - | - | - | 100 | - | 110 | 25* | 50** | - | 18 |
| 45 | ¾Æ` ›dT | 20 | | - | - | - | 40 | 60 | - | 30 | 30 | |
| 46 | Í`ƒ | - | | - | - | - | 20 | 30 | - | - | 20 | |
| 47 | kö Åò | 20 | 10 | 40 | 50 | 70 | 50 | 70 | - | | 20 | |
| 48 | wJ` (G<K~U ¨Á-‹ | 20 | 10 | 30 | 40 | 50 | 40 | 50 | 20 | | 20 | |
| 49 | ›”` | 40 | 20 | 80 | 110 | 180 | 80 | 180 | - | | 40 | |
| 50 | q`Ÿ? (SÒL¨< | 30 | 10 | 30 | 40 | 50 | 40 | 70 | 30 | | 30 | |
| 51 | Ÿ`Ÿa | 20 | - | - | - | - | 40 | 60 | - | 30 | 90 | |
| 52 | óa | 30 | 10 | 40 | 50 | 70 | 50 | 70 | - | - | 20 | |
| 53 | ¨<É”u= | 40 | 20 | 30 | 50 | 70 | 60 | 180 | 30 | - | 30 | |
| 54 | ÚK? vKÒT@ | 40 | 20 | 30 | 50 | 70 | 60 | 120 | 30 | | 30 | |
| 55 | ›x gT’@ | 730 | 550 | 550 | 730 | 1090 | 910 | 1090 | - | | 40 | |
| 56 | ¾T@Ç ›IÁ (G<Kƒ ¨Á-‹ | 180 | 220 | 220 | 290 | 360 | 290 | 440 | - | | 40 | |
| 57 | u `v ¾}S[} ¾›µ qÇ | 7.50 | - | - | - | - | - | - | - | - | - | |

| }.l. | ¾ ”ed¨<eU | 'ÖL qÇ | U”×õ 'ÖL | ŸI`Ø^ß ¾}W^ U”×õ | | | Ÿß” pLƒ ¾} W^ | S<K < uÉ” | k”É | Ø`e | ¾^e ›Ø” ƒ |  ”lL M |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ƒ”i | S"ŸK – | ƒMp | | | | | | |
| | | w` | w` | w` | w` | w` | w` | w` | w` | w` | w` | w` |
| 58 | ß^ | 10 | - | - | - | - | - | - | - | - | - | |

* Øõ`

**›Ø”ƒ Lv)Ÿ=Ó

<u>W”Ö[» ›Y`</u>

<u>K›Å” ¾}ŸKŸK< ¾Æ` •”edƒ</u>

| }.l | ¾›T`– SÖ]Á | ¾dA”e SÖ]Á |
|---|---|---|
| 1. | ›ªMÉÑ@X | ›]eƒaøe ›ð` |
| 2. | ¾kS` Ïw | —a,Ke ¡]e•~e |
| 3. | u=¾^ q`Ÿ? | Ê`"ƒ^Ñ<e T@ÒKA+e |
| 4. | ÚK? vKÒT | H@þƒ^Ñ<e ›Ÿ<©”e |
| 5. | ¾Æ` ›lÁ | ›?Ÿ<e ›c='<e ›õ]"'e |
| 6. | nn' ¾›u=c='>Á ¾lØsÙ l^ | ³z•] É`'>e eƒ]cT@'> |
| 7. | ›xgT'@ | ›c=•'>¡e Ìv}e |
| 8. | ¨õ (¡_¡ ¢`” | c?]¡e c?]¡e |
| 9. | l`Â vK•”ØMØM | Ó\e "\”Ÿ<L}e |
| 10. | Ç=v•Ó | ›VÊ`"e ¡K`Ÿ= |

| }.l | ¾›T`– SÖ]Á | ¾dA"e SÖ]Á |
|---|---|---|
| 11. | Ç¡Â | ›A+Á "Aa" |
| 12. | "e` vKÖnÖq | ›Ÿ<©L ¡L'Ò |
| 13. | "e` ›=Uü]ÁM | ›Ÿ<¨L H>K=Á" |
| 14. | ¨<É"u= | ƒ^Î>Lðe *]¡e |
| 15. | ›Ç˜ ßMòƒ | óM¢ óc='<‰ |
| 16. | ¡"ð 'ß ¨õ | daƒ\^ ›¾`c= |
| 17. | ¾G¨<É qp)f['@) | õ^"¢K='<e G`¨<Ç= |
| 18. | ¾T@Ç õ¾M)üM²") | Ò³L úM²=M'> |
| 19. | ¾eü¡ T@Ç õ¾M | Ò²?L eüŸ= |
| 20. | kß'@ | Í=^õ "T@KAû`ÇK=e |
| 21. | ¾e«A" q`Ÿ? | ›c=Lðe u<c=Lðe c«A'> |
| 22. | }^ q`Ÿ? | ›c=Lðe u<c=Lðe „^ |
| 23. | }Ÿ<L | LAŸ" ú¡}e |
| 24. | Ïw iMUMU | GA" GA" |
| 25. | ªMÁ ›Au?¡e | "—^ ªMÁ |
| 26. | ƒ"g< Ÿ?e}[M | óM¢ ""<T'> |
| 27. | ¾Ç=ÔÇ= ¾c"ÅÊ ¨õ | T>^õ^ Ç=ÔÈ"c=e |
| 28. | ¾c=ÇV ¾e"ÅÊ ¨õ | H@ƒaT>^õ^ c=ÇV¾"c=e |
| 29. | ¾Ú• Ù× | c=`¢ú+Ÿe '@ÓK?¡}e |

| }.l | ¾›T`– SÖ]Á | ¾dA”e SÖ]Á |
|---|---|---|
| 30. | kA Ù× | ›?`+ac=ue û•e |
| 31. | UeÖ uM | eS<ƒc=Á ‚T>’@Ÿ= |
| 32. | ›¨<^]e | Ç=c?ae ÇA¢`’>e |
| 33. | ¾›”¢u` ²[ uM | c?]’e ›”¢u_”c=e |
| 34. | ¾dMzÊ] ²[uM | c?]’e ³”„K=T |
| 35. | T”l`} u=Ý ²[uM | c?]’e õLy=Ñ<L |
| 36. | ß^ ’ß ¨”ßõƒ | GA\”Ê T@Ò¾”c=e |
| 37. | ¨õ)²]ƒ ²^eþ^) | ~^ŸA \eþK=e |
| 38. | ¾cT@” kua)kA kua) | "’>e eT@”c=e |
| 39. | ¾T@Ç ›lÁ)u`†M) | ›=Ÿ<©e u<`ŠK= |
| 40. | ¾T@Ç ›lÁ )¾Ó_{) | ›=Ÿ<©e Ó_y= |
| 41. | ¾vQ` LU | ÆÑ<”Ó Ç=Ñ<”Ó |
| 42. | UeÖ uM | û•Ñ>’e ‚T@’>Ÿ=A |
| 43. | Ö=TU Ðò | Í=úÅ}e v`v~e |
| 44. | ¨õ (²ªMÉ^— | Óa”+Ÿe ›?[T>• |
| 45. | vK’ß ¡”õ `Ów | e„[—„úK=Á ]¡“© |
| 46. | ¨õ ð×’< | *úe T>¿úƒKe |
| 47. | c?ƒ •”edƒ“ ÓMÑKA‹ | ¾T”–¨<U •”ed |
| 48. | ´J” | KA¡eÅ”• ›õ]"“ |

## አዋጅ ቁጥር 1065/2010

## የደን ልማት፣ ጥበቃ እና አጠቃቀም አዋጅ

የደን ዘርፉ የአየር ንብረት ለውጥ የሚያደርሰውን አሉታዊ ተፅዕኖ ለመቋቋም ትልቅ ሚና የሚጫወት በመሆኑና በሀገራችን በከፍተኛ ደረጃ በደን መመናመን ምክንያት እየተከሰተ ያለውን አካባቢያዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለመግታት ዘላቂ የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ወሳኝ ሚና ያለው በመሆኑ፤

እየተከሰተ ያለውን የአፈር መከላት፣ የበረሃማነት መስፋፋትና የብዝሐ ሕይወት መመናመን ለመግታት የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ያለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ በመሆኑ፤

የደን ዘርፉ የህብረተሰቡን የደን ውጤት ፍላጎትና አቅርቦት ልዩነት ለመሙላት፣ የግብርና ምርት እድገትን በማስቀጠል የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ወሳኝ ድርሻ ያለው በመሆኑ፤

መንግስት ለዘላቂ የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ያወጣቸውን ፖሊሲዎችና እና ስትራቴጂዎች ለማስፈጸም በመንግስት እና በግል ባለቤትነት ከሚለማው ደን በተጨማሪ የማህበረሰብና የማህበራት ባለቤትነትን በማረጋገጥ በህብረተሰብ ተሳትፎ ደንን ማልማት ከፍተኛሚና ያለው መሆኑ ስለታመነበት፣

ለዘላቂ የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ደን ከአካባቢያዊ፤ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎች አንፃር በምርት ሰጪነት፤ በጥብቅ እንዲሁም በፍፁም ጥብቅ ደንነት መለየትና ማስተዳደር አስፈላጊ በመሆኑ፤

ከዘርፉ ብዙ እና ከሁለትዮሽ ስምምነቶች የደን ዘርፍ ሊያስገኝ የሚያስችላቸውን አካባቢያዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎች ይበልጥ ማሳደግ በማስፈለጉ፤ በደን ዘርፉ የምርምር፤ የትምህርት፤ የኢንቨስትመንት፣ የግብይት እና የመረጃ ሥርዓትን ማጠናከር አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 51/5 እና አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ “የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 1065/2010” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

1. "ደን" ማለት በደን መሬት፣ በመንገዶች ዳርቻ፣ ወንዝ ዳርቻ፣ በእርሻና የግጦሽ መሬቶች ውስጥና በዙሪያቸው እንዲሁም በመኖሪያ አካባቢዎችና ፓርኮች ውስጥ በተፈጥሮ የበቀሉ ወይም ተተክለው ወይም በሌላ ዘዴ የለሙ የዛፎችና የዕፅዋቶች እንዲሁም ሌሎች ብዝሃ-ሕይወቶች ክምችት ነው፤
2. "የደን ብዝሀ-ሕይወት" ማለት በደን ውስጥ ወይም በደን መሬት ላይ ያለ የዕፅዋት፣ የእንስሳትና የደቂቅ ሕያውን ዝርያዎች ክምችትና ስብጥር በተደጋጋፊነትና በአንድነት የሚገኙበትን ሥርዓተ ምህዳርን የሚያጠቃልል ነው፤
3. "ዛፍ" ማለት ዕድሜና መጠን ሳይለይ ማንኛውም የእንጨትነት ባህሪ ያለው ተክል የሚያጠቃልል ሲሆን ቀርከሃ፣ ሸመል፣ ዘንባባና ሚኒስቴሩ የሚሰይማቸውን ሌሎች ተመሳሳይ ባህሪ ያላቸውን ተክሎችን ይጨምራል፤
4. "የደን መሬት" ማለት ለደን ልማትና ጥበቃ ተብሎ የተከለለ ወይም የተሰየመ ማንኛውም መሬት ነው፤
5. "የመንግሥት ደን" ማለት በፌደራል እና በክልል መንግሥት ሥር የሚገኝ ማንኛውም ፍጹም ጥብቅ፣ ጥብቅ ወይም ምርት ሰጪ ደን ነው፤
6. "የግል ደን" ማለት የመንግስት እና የማህበረሰብ ያልሆነ በማንኛውም የግልና የተቋማት ይዞታ ላይ የሚገኝ ደን ነው፤
7. "የማሕበረሰብ ደን" ማለት የአንድ አካባቢ ህብረተሰብ የግል ወይም የወል ይዞታቸውን በጋራ በሚያወጡት ዕቅድ እና ሕገ-ደንብ መሠረት የለማ፣ የተጠበቀ፣ በጥቅም ላይ የሚውል እና የሚተዳደር ደን ነው፤
8. "የማሕበራት ደን" ማለት የደን አልሚዎች በማሕበር በመደራጀት የሚያለሙት፣ የሚጠብቁት፣ የሚጠቀሙበት እና የሚያስተዳድሩት ደን ነው፤
9. "አሳታፊ የደን አያያዝ" ማለት በመንግስት ደን ውስጥ ወይም ዙሪያ በሚኖሩ ማህበረሰብና መንግስት መካከል በሚደረግ ስምምነት መሠረት የደን ሀብቱን የማልማት፣ የመንከባከብ፣ የመጠበቅና የመጠቀም መብትን አስመልክቶ የደኑን አስተዳደር የኃላፊነት ሚናን በመለየት ከደኑ የሚገኘን ጥቅም በሚጋሩበት ሥርዓት ላይ በጋራ የሚሰሩበት የደን አስተዳደር ስልት ነው፤

10. “ኮንሴሽን” ማለት አንድን የመንግሥት ደን ሀብት ለማልማት፣ ለመጠበቅ ወይም በጥቅም ላይ ለማዋል ለተወሰነ ጊዜ በውል ህጋዊ ሰውነት ላለው አካል ማስተላለፍ ማለት ነው፤
11. “ጥብቅ ደን” ማለት ለተለያዩ የሥርዓተ ምህዳር ግልጋሎት የሚውል ደን ሲሆን በሚመለከተው አካል በሚዘጋጅለት የደን ማኔጅመንት ዕቅድ መሠረት የደኑን ዘላቂ ሥርዓተ- ምህዳራዊ ዕሴቶች በማይጎዳ መልኩ በጥቅም ላይ እንዲውል የተለየ ደን ነው፤
12. “ፍፁም ጥብቅ ደን” ማለት ደኑን ከአደጋ ለመጠበቅ ካልሆነ በስተቀር ከማንኛውም የሰውና የቤት እንስሳት ጣልቃ ገብነት የተጠበቀ ደን ሲሆን ለብዝሀ ህይወት ጥበቃ፣ ለታሪካዊና ለምርምር የተለየ ደን ነው፤
13. “ምርት ሰጪ ደን” ማለት በዋናነት ለኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶች የለማ ደን ነው፤
14. “ሰው ሰራሽ ደን” ማለት በሰው አማካኝነት የለማ ደን ነው፤
15. “የተፈጥሮ ደን” ማለት በአብዛኛው በተፈጥሮ የበቀሉ ዛፎች፣ ቁጥቋጦና ሌሎች የእንጨትነት ባህሪ ያላቸውና የሌላቸው ተክሎችና ዕፅዋቶች ያሉበት ደን ነው፤
16. “ጥምር እርሻ ደን” ማለት ሰብልንና ዛፍን ወይም የእንስሳት መኖንና ዛፍን ወይም ሶስቱንም በአንድ መሬት ላይ በተመሳሳይ ጊዜ ወይም በማፈራረቅ በቅንጅት በማልማት የሚከናወን የተቀናጀ የመሬት አጠቃቀም ስልት በመጠቀም የሚለማ ወይም የለማ ደን ነው፤
17. “የደን አያያዝ ዕቅድ” ማለት በተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ ደን ውስጥ የሚገኘውን ማንኛውንም የደን ሀብት በዝርዝር በማጥናት ለሀብቱ ጥበቃ፣ ልማትና አጠቃቀም የሚወጣ ዕቅድ ነው፤
18. “የደን ውጤት” ማለት ማንኛውም ከደን የሚገኝ የእንጨትነት ባህርይ ያለውና የሌለው ምርት እንዲሁም የደን ካረበንን ጨምሮ ማንኛውንም የደን ሥርዓተ- ምህዳራዊ ግልጋሎት የሚያካትት ነው፤
19. “የደን ውጤቶች እንቅስቃሴ ፈቃድ" ማለት የደን ውጤቶችን ወደ ሀገር ለማስገባት፣ ወደ ውጭ ለመላክ፣ ለማጓጓዝ፣ ለማከማቸት፣ ለመሸጥ እና፣ ለማምረት በሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ባለው የክልል ባለስልጣን የሚሰጥ ፍቃድ ነው፤
20. “የደን ኬላ" ማለት የደን ምርት ውጤቶችን እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር የተቋቋመ ጣቢያ ነው፤

21.“የደን ውጤቶች ተቆጣጣሪ” ማለት የደን ምርቶችን እንቅስቃሴን ለመቆጣጠር በሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ባለው የክልል ባለስልጣን የሚመደብ ባለሙያ ነው፤

22.“ካርበን” ማለት ህይወት ባላቸው እንዲሁም በሌላቸው አካላት ውስጥ የሚገኝ ከኦክስጅን ጋር ሲዋሃድ ሙቀት የማመቅ ባህሪይ ያለው ጋዝ የሚፈጥርና በከባቢ አየር ውስጥ ያለው ተፈጥሮዊ ክምችት በሰው ሰራሽ ምክንያቶች ሲጨምር የምድር ሙቀት መጨመርን የሚያስከትል ንጥረ-ነገር ነው፤

23. “ካርበን ማከማቸት” ማለት አረንጓዴ ዕፅዋት ምግባቸውን በሚያዘጋጁበት የተፈጥሮ ሂደት ካርበንዳይ ኦክሳይን በመጠቀም ካርበንን ለረጅም ጊዜ በተለያዩ ክፍሎቻቸው መያዝ ነው፤

24.“የደን ካርበን ንግድ” ማለት የደን ምንጣሮና መመናመንን በመቀነስ ወይም የደን ሽፋንን በማሳደግ የካርበን ክምችትን በመጨመር ለካርበን ልቀት ቅነሳ ክፍያ የሚፈጸምበት ግብይት ሥርዓት ነው፤

25.“የደን ካርበን ልቀት” ማለት በደን ውስጥ የተከማቸ ካርበን በተለያዩ ሰው ሰራሽ ምክንያቶች ወደ ከባቢ አየር መለቀቅ ነው፤

26.“አግባብ ያለው ባለስልጣን” ማለት ለደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም በክልል መንግሥት ሥልጣንና ኃላፊነት የተሰጠው ማንኛውም የክልል መንግስት አስፈፃሚ አካል ነው፤

27. “የሮያሊቲ ክፍያ” ማለት ማንኛውም በደን ውጤት ንግድ ስራ ላይ የተሰማራ ሰው ምርቱን ከቦታ ቦታ ለማንቀሳቀስ የሚከፍለውና ቀጣይነት ላለው የደን ልማት አገልግሎት የሚውል ክፍያ ነው፤

28.“የደን ኤክስቴንሽን” ማለት በደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ምርጥ ተሞክሮዎች እና ቴክኖሎጅዎችን በመቀመር፣ በማዘጋጀትና በማሰራጨት የደን አልሚው እውቀትና ክህሎት ማሳደጊያ መንገድ ነው፣

29. “የደን ስርዓተ ምህዳር አገልግሎት” ማለት ከዘላቂ የደን ልማትና ጥበቃ የሚገኝ ማንኛውም የስርዓተ ምህዳር አገልገሎት ነው፤

30. "ኳራንታይን” ማለት የደን ውጤት ከውጭ ወደ ሃገር ውስጥ ሲገባና ከሃገር ውስጥ ወደ ውጭ ሲወጣ ከተባይ፣ ከበሽታ ነጻ መሆኑንና የደን ውጤት ደረጃ መስፈርት ማሟላቱን ለማረጋገጥ የሚከናወን የቁጥጥር ሂደት ነው፤

31.“የጥቅም ተጋሪነት” ማለት በመንግስትና በማህበረሰቡ እንዲሁም በማህበረሰቡ አባላት መካከል ከሚያለሙት ደን የሚገኘን ማንኛውንም ጥቅም መጋራት ማለት ነው፤

32.“ሰው” ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

33.“ሚኒስቴር” ወይም “ሚኒስትር” ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የአካባቢ የደን እና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር[31] ወይም ሚኒስትር ነው፤

34. “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት በአንቀጽ 47 (1 የተመለከቱት ክልሎችን እና የአዲስ አበባና የድሬደዋ የከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

35.በዚህ አዋጅ በወንድ ጾታ የተገለፀው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

3. **<u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>**

ይህ አዋጅ በመላ ሀገሪቱ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

4. **<u>የደን ባለቤትነት</u>**

የሚከተሉት የደን ባለቤትነት ዓይነቶች ይኖራሉ፤

1. የግል ደን፤
2. የማሕበረሰብ ደን፤
3. የማህበራት ደን፤
4. የመንግሥት ደን፡፡

**<u>ክፍል ሁለት</u>**

**<u>ስለ ግል ደን</u>**

5. **<u>የግል ደን አልሚ መብቶች እና ማበረታቻዎች</u>**

1. የግል ደን አልሚ የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፤

ሀ ለደን ልማት የሚውል መሬት የማግኘትና ባለው የግል የመሬት ይዞታ ላይ ደን የማልማት፤

ለ ላለማውና ለሚያለማው ደን የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር የማግኘት፤

ሐ በደን ልማት የሚያገኛቸውን የደን ውጤቶች የመጠቀም፣ በሀገር ውስጥና በውጪ ሀገር ገበያ የመሸጥ፤

[31] 25/08 (2011) አ. 1097 አንቀጽ 36(17) የአካባቢ የደን እና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ሆኗል፡፡ በአዋጁ ውስጥ ሚንስቴር የሚለው ኮሚሽን በሚል ተተክቶ ይነበብ፡፡

መ በደን ልማት፣ ጥበቃ፣ አጠቃቀምና ንግድ ላይ ከመንግሥት ሙያዊ ድጋፍ የማግኘት፤

ሠ የይዞታ መብቱን የማስተላለፍ፤

ረ ከሚያለማውና በይዞታው ሥር ከሚገኝ ደን ካርበን ሽያጭና ከሥነ-ምህዳራዊ ግልጋሎቶች ከሚገኘው ገቢ ተጠቃሚ የመሆን፤

ሰ በሕዝብ ጥቅም ምክንያት ይዞታውን እንዲለቅ ሲደረግ ካሳ የማግኘት

ሸ በደን ልማቱ በማምረት ወይም አገልግሎት በመስጠት ወይም በማምረት እና አገልግሎት በመስጠት ላይ እንዲሁም የደን ውጤቶች ላይ እሴት በመጨመር ወይም ባሉበት ሁኔታ የንግድ ስራ ላይ የመሰማራት፤

2. ለግል ደን አልሚ የሚከተሉት ማበረታቻዎች ይሰጣሉ፤

ሀ ከመሬት ሊዝ ክፍያ ነፃ የመሆንና የመጀመሪያውን አንድ የምርት ዘመን ከማንኛውም ግብር ነፃ የመሆን፤

ለ አግባብ ያለውን መስፈርት አሟልቶ ሲገኝ የብድር አገልግሎት የማግኘት፤

ሐ በዚህ አንቀጽ (2) ሀ እና ለ ለተዘረዘሩት ማበረታቻዎች ዝርዝር አፈጻጸም በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

6. <u>**የግል ደን አልሚ ግዴታዎች**</u>

የግል ደን አልሚ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፡-

1. ደኑን ከቃጠሎ፣ ከተባይ፣ ከበሽታ እና ከወራሪ ዝርያዎች እንዲሁም ከሌሎች ጉዳቶች የመጠበቅ እና የመከላከል፤
2. ባለማው ደን ውስጥ ቃጠሎ፣ ተባይ፣ ወራሪ ዝርያ ወይም በሽታ ሲከሰት አግባብ ላለው አካል በአፋጣኝ ሪፖርት የማድረግ፤
3. በደኑ ውስጥ ያልተፈቀዱ ወይም ያልታወቁ ለሰው፣ ለእንስሳት ወይም ለሥነ-ምህዳር ጎጂ የሆኑ ዕፅዋትን፣ እንስሳትን፣ ደቂቅ አካላትን ወይም ነፍሳትን ያለማስገባት ወይም ያለማራባት፤
4. የአካባቢ ደህንነትን፣ የተፋሰስና የብዝሀ-ሕይወት ጥበቃ፣ ልማትና አጠቃቀም በተመለከተ የወጡ ሕጎችን የማክበር፤
5. የአካባቢውን ጠቃሚ ባሕል፣ ልማድ እና ዕውቀት የማክበር፤
6. አግባብ ላለው አካል ደኑን በተመለከተ መረጃ የመስጠት፤
7. ለደን ልማት የተረከበውን መሬት ለተፈቀደለት ዓላማ ብቻ የማዋል፤

8. በደን ካርበን ሽያጭና በደን ሥርዓት-ምህዳራዊ ግልጋሎቶች ከሚገኘው ገቢ ተጠቃሚ ለመሆን የግብይት ሥርዓቱ የሚፈልገውን መስፈርት የማሟላትና የማክበር፡፡

## ክፍል ሦስት

## ስለማሕበረሰብ ደን

### 7. የማሕበረሰብ ደን አልሚዎች መብቶችና ማበረታቻዎች

1. የማሕበረሰብ ደን አልሚዎች የሚከተሉት መብቶች ይኖራቸዋል፦

   ሀ) በአሳታፊ የደን አስተዳደር በፈቃደኝነት የመታቀፍ እና መንግስት የደን መሬት ብሎ በሚሰይመው ሥፍራ ወይም በወል ይዞታቸው ላይ የማህበረሰብ ደን ለማልማት ድጋፍ የማግኘት፤

   ለ) ለሚያለሟቸው ደኖች የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር የማግኘት፤

   ሐ) በአካባቢያቸው በሚገኘው የተፈጥሮ ደን ላይ የደኖቹን ዘላቂነትና ህልውና በማይጎዳ መልኩ የመጠቀም፤

   መ) መንግስት በኮንሴሽን በሚሰጠው ደን ተጠቃሚ ለመሆን እንደ ሁኔታው ቅድሚያ የማግኘት፤

   ሠ) በሚያመነጩት ገቢ መደገፈ እስኪችሉ ድረስ ከመንግስት የሙያ፣ የቴክኒክ፣ የግብዓት ድጋፍ እና የሕግ አገልግሎት የማግኘት፤

   ረ) በሚያዘጋጁት የአያያዝ ዕቅድ መሠረት የደን ውጤቶችን የመጠቀም፤ የማንቀሳቀስ እና እሴት የመጨመር፤

   ሰ) አባላቱ በጋራ በሚያዘጋጁት ውስጠ ደንብ መሠረት ከሚያለሙት ደን ከሚገኝ ማንኛውም ጥቅም የመጋራት፤

   ሸ) በሕዝብ ጥቅም ምክንያት የደን ይዞታቸውን እንዲለቁ ሲደረጉ ካሣ የማግኘት፡፡

2. ለማሕበረሰብ ደን አልሚዎች የሚከተሉት ማበረታቻዎች ይሰጣሉ፦

   ሀ) ለመጀመሪያ ሁለት የምርት ዓመታት ከማንኛውም የደን ልማት ገቢ ግብር ነፃ የመሆን፤

   ለ) አግባብ ያለውን መስፈርት አሟልተው ሲገኙ የብድር አገልግሎት የማግኘት፤

   ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2 ሀ እና ለ ለተዘረዘሩት ማበረታቻዎች ዝርዝር አፈጻጸም በሚወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

8. **የማሕበረሰብ ደን አልሚዎች ግዴታዎች**

የማሕበረሰብ ደን አልሚዎች የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖራቸዋል፦

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 የተመለከቱ ግዴታዎች በማሕበረሰብ ደን አልሚዎች ላይም ተፈጻሚ ይሆናሉ፤
2. የደን አያያዝ ዕቅድ እና የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ አግባብነት ባለው የመንግስት መስሪያ ቤት ዘንድ ማስቀመጥ አለባቸው፡፡

**ክፍል አራት**

**ማህበራት ደን**

9. **የማህበራት ደን አልሚዎች መብቶች**

1. የማህበራት ደን አልሚዎች የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፦
   ሀ) በአንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሱት መብቶች ለማህበራት ደን አልሚዎችም ተፈፃሚ ይሆናሉ፤
   ለ) አግባብ ባለው የመንግስት አካል የመመዝገብ፤
2. የማህበራት ደን አልሚዎች የሚከተሉት ማበረታቻዎች ይኖሩታል፦
   ሀ) ለመጀመሪያው አንድ የምርት ዘመን ከማንኛውም ግብር ነፃ የመሆን፤
   ለ) አግባብ ያለውን መስፈርት አሟልቶ ሲገኝ የብድር አገልግሎት የማግኘት፤
   ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 (ሀ) እና (ለ) ለተዘረዘሩት ማበረታቻዎች ዝርዝር አፈጻጸም በሚወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

10. **የማህበራት ደን አልሚ ግዴታዎች**

1. የማህበራት ደን አልሚ የሚከተሉት ግዴታዎችን ይኖሩታል፤-
   ሀ) በዚህ አዋጅ በክፍል ሁለት አንቀጽ 6 የተጠቀሱት የግል ደን አልሚዎች ግዴታዎችን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች በሙሉ በማህበራት ደን አልሚዎች ላይ ተግባራዊ ይሆናሉ፤
   ለ) አባላትን በማስተማርና በማስልጠን በደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ያላቸውን እውቀትና ክህሎት በማዳበር ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ባህልን የማጎልበት ሃላፊነት ይኖባቸዋል፤
   ሐ) ማህበሩ ከሁለት የምርት ዘመን በኋላ የገቢ ግብር የመክፈል፤

## ክፍል አምስት

## ስለመንግስት ደን

**11.የመንግስት ደን**

የመንግስት ደን እንደሚከተለው ይከፈላል፤-

1. ምርት ሰጪ ደን
2. ጥብቅ ደን
3. ፍጹም ጥብቅ ደን

**12.ምርት ሰጪ የመንግሥት ደን**

ምርት ሰጪ የመንግስት ደንን በተመለከተ መንግስት የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፤

1. ደኑ የራሱ አስተዳደርና አመራር እንዲኖረው በማድረግ፣ በተገቢው በጀት፣ የሰው ኃይልና ቁሳቁስ እንዲሟሉ ያደርጋል፤
2. ደኑ በአግባቡ እንዲለማ፣ እንዲጠበቅና በጥቅም ላይ እንዲውል ያደርጋል፤
3. የአካባቢው ህብረተሰብ በመንግስት ምርት ሰጪ ደኖች ልማትና ጥበቃ ላይ እንዲሳተፉ፣ የልማቱም ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያስችል የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም መርሐ-ግብር ይቀይሳል፤
4. ደኑን የወራሪነት ባህሪይ ካላቸው አረሞች፣ ከተባይ እና ከበሽታ ይከላከላል፤ ሲከሰትም በቁጥጥር ሥር እንዲውል ያደርጋል፤
5. የደን ሀብቱ ከተፈጥሮም ሆነ ሰው ሰራሽ አደጋዎችና ጥፋቶች እንዲጠበቅ ያደርጋል፤
6. ለደኑ ልማት የሚያገለግሉ መንገዶችና ሌሎች አገልግሎት መስጫ ተቋሞችን ይሰራል፤
7. ከደኑ የሚገኘውን ዘላቂ ጥቅም ለማረጋገጥ የሚያስችል የደን አስተዳደር ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ይጠብቃል፤ ያስተዳድራል፤
8. የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀምን ዘላቂነት ለማረጋገጥ በፌደራልና በክልል አካላት ዘንድ የተጠናከረ ቅንጅታዊ የአሰራር ሥርዓት እንዲኖር ያደርጋል፤
9. በተለዩ የደን መሬቶች ላይ አዳዲስ ምርት ሰጪ ደኖች እንዲለሙ ያደርጋል፤
10. ደኖቹ በካርታ የተደገፈ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡

13.**ጥብቅ ደኖች**

መንግስት ጥብቅ ደኖችን በተመለከተ የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፤

1. አሳታፊ የደን አያያዝ እቅድ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ያደርጋል፤
2. በጥብቅ ደንነት የተሰየሙና ዕፅዋት የማይገኝባቸው ወይም በበቂ ደረጃ በእፅዋት ያልተሸፈኑ የደን መሬቶች በሚወጣላቸው የልማት ዕቅድ መሠረት እንክብካቤና ጥበቃ እንዲደረግላቸው እንዲሁም አስፈላጊ ሲሆን ደን እንዲለማባቸው ያደርጋል፤
3. በደኖች ዙሪያ የደኑን ዳር ድንበር የሚያመለክቱና ለአካባቢው ሕብረተሰብ ለማገዶና ለግንባታ አገልግሎት የሚውሉ ፈጣን ዕድገት ያላቸው የዛፍ ዝርያዎች እንዲለሙ ያደርጋል፤
4. ደኖቹ በካርታ የተደገፈ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡

14.**ፍፁም ጥብቅ ደኖች**

መንግስት ፍጹም ጥብቅ ደኖችን በተመለከተ የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፤

1. ደኖቹ ወሰናቸው ታውቆ ተከልለው እንዲጠበቁ ያደርጋል፤
2. ለምርምር፣ ለትምህርት እና ከማንኛውም ውድመትና ጥፋት ለመጠበቅ ከሚወሰዱ ተግባራት ውጭ ከማንኛውም ዓይነት የሰውም ሆነ የቤት እንስሳት ንክኪ ነፃ እንዲሆኑ ያደርጋል፤
3. ደኖቹ በካርታ የተደገፈ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡

15.**የመንግሥት ምርት ሰጪ ወይም ጥብቅ ደን አስተዳደር እና አጠቃቀም**

1. ደኑ በጥቅም ላይ ሊውል የሚችለው በተዘጋጀውና ኃላፊነት ባለው አካል በፀደቀ የደን የአያያዝ ዕቅድ መሰረት መሆን አለበት፣
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1 መሠረት ደኑ ጥቅም ላይ የሚውለው በመንግሥታዊ ድርጅቶች ወይም ደኑ በኮንሴሽን በተሰጣቸው አካላት ይሆናል፡፡ ዝርዝሩ በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፣
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1 እና (2 እንደተጠበቁ ሆነው ደኑ አስቀድሞ በተዘጋጀ የደን አያያዝ ዕቅድ መሠረት በደኑ ዙሪያ ወይም በደኑ ውስጥ የሚኖሩ የህብረተሰብ አባላት አካባቢያዊ፣ ማህበራዊና፣ ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶችን እንደየአካባቢው ሁኔታ አግባብ ባለው ባለስልጣን ሲፈቀድ ሊያገኙ ይችላሉ፤
4. የደኑ አስተዳደር ሥርዓት ከኤኮ-ቱሪዝም፣ ከካርበን ንግድ እና ሌሎች ተጓዳኝ የሥርዓተ-ምህዳር ግልጋሎቶች ገቢ እንዲያስገኝ መደረግ ይኖርበታል፣

## ክፍል ስድስት

## የአስፈፃሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር

### 16. የሚኒስቴሩ ሥልጣንና ተግባር

ሚኒስቴሩ፡-

1. ይህን አዋጅ ከሚመለከታቸው የክልል ተቋማት ጋር በመቀናጀት ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤
2. የደረጃ ልውውጥ ሥርዓት በመዘርጋት የሀገሪቱን ደን መረጃ ለተጠቃሚዎች ተደራሽ ያደርጋል፤
3. የደን አልሚዎች ዕውቀትና ክህሎት እንዲያድግ የሙያ ድጋፍ ይሰጣል፤
4. ጥቃቅንና አነስተኛ፣ መካከለኛና ከፍተኛ የደን ኢንዱስትሪዎች እንዲስፋፉ እና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ድጋፍ ያደርጋል፤
5. የደን ውጤት ደረጃዎች እንዲወጣ ያደርጋል፤
6. ዘላቂ እና ዘመናዊ የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ሥርዓት በመዘርጋት ለክልሎች የቴክኒክና የማቴሪያል ድጋፍ ያደርጋል፤
7. በደን ውጤቶች ላይ የጥቅም ተካፋይነትን ለመወሰን የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤
8. በደን ሀብት ላይ አደጋ እንዳይከሰት የቅድመ ማስጠንቀቂያ፣ የመከላከያ እና የመቆጣጠሪያ ሥርዓት ያዘጋጃል፤ ሲከሰቱም ክልሎችንና ሌሎች የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትን በማስተባበር አፋጣኝ እርምጃ ይወስዳል፤
9. የኳራንታይን ሥርዓት ያዘጋጃል፤ መተግበሩንም ይቆጣጠራል፤
10. የደን ሙያ፣ የደን ልማትና የደን ውጤቶች ንግድ ብቃት ማረጋገጫ ፍቃድ ይሰጣል፤
11. በህብረተሰብ ተሳትፎ ተፋሰስን መሰረት ያደረገ የደን ልማት ስራን ባለቤት እንዲኖራቸው ይከታተላል፣ ለክልሎች የቴክኒክ ድጋፍ ያደርጋል፤
12. የደን ምርምር እና የስልጠና ተቋማትን በማቋቋም ሀገር በቀል ዕውቀቶች እንዲያድጉ ያደርጋል።

13.እያንዳንዱ ክልል በክልሉ ውስጥ የሚገኝን ማንኛውንም የመንግሥት ደን በዚህ አዋጅ መሠረት የማስተዳደር ሥልጣን ያለው ቢሆንም፦

ሀ) ደኑ በሚገኝባቸው አጎራባች ክልሎች በጋራ በአግባቡ ሊለማና ሊጠበቅ የማይችል ሆኖ ሲገኝ፤

ለ) ደኑ ወይም የደን መሬቱ ከሀገራዊ፣ አህጉራዊ እና ዓለም ዓቀፋዊ ጠቀሜታው አንፃር በፌደራል መንግስት ሥር ሆኖ መተዳደር አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፤ የፌደራል መንግስት ሊያስተዳድር ይችላል፡፡

17.<u>የክልል አስፈፃሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር</u>

የክልል አስፈጻሚ አካል፤-

1. በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 16 ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በክልሉ ውስጥ የሚገኝ ማንኛውንም የደን መሬት እና የመንግስት ደን ያስተዳድራል፤ የግል፣ የማህበራት እና የማህበረሰብ ደኖች በዚህ አዋጅ መሠረት መልማታቸውን፣ መጠበቃቸውን እና መተዳደራቸውን ይቆጣጠራል ይደግፋል፤
2. ደን እና የደን መሬቶችን ሕጋዊ ዕውቅና እንዲያገኙ ያደርጋል፤
3. ህብረተሰቡን ያሳተፈ የደን ልማት ፕሮግራም እንዲስፋፉ ያበረታታል፣ የሙያ ድጋፍ ይሰጣል፤
4. ለደን ልማት በመሬት ይዞታ የመጠቀም መብት የተሰጠው ማንኛውም ደን አልሚ መሬቱን ለደን ልማት ዓላማ ማዋሉንና በሚያዘጋጀው የደን አያያዝ እቅድ መሠረት መተግበሩን በየጊዜው ክትትልና ግምገማ ያደርጋል፤
5. የደን ውጤቶች ሮያሊቲ ክፍያ ተመን ለክልሉ መንግሥት አቅርቦ ያስወስናል ይሰበስባል፤
6. ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስችል አደረጃጀት ይፈጥራል፤ በጀት ይመድባል፣ የሰው ሀይል ያሟላል፤
7. በደን ሀብት ላይ አደጋ እንዳይከሰት የቅድመ ማስጠንቀቂያ፣ የመከላከያ እና የመቆጣጠሪያ ሥርዓት ያዘጋጃል፤ አደጋ ሲከሰትም ህብረተሰቡንና ሌሎች የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትን በማስተባበር አፋጣኝ እርምጃ ይወስዳል፤ እንደስፈላጊነቱ የሚኒስቴሩን ድጋፍ ይጠይቃል፤
8. በህብረተሰብ ተሳትፎ ተፋሰስን መሰረት ያደረጉ የደን ልማት ስራዎችን ባለቤት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡

## ክፍል ሰባት

## የደን ኤክስቴንሽንና ገበያ ማስፋፋት

18.**የደን ኤክስቴንሽን መንግስት፣**

1. በደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ምርጥ ተሞክሮዎች እና ቴክኖሎጅዎችን በመቀመር፣ በማዘጋጀትና በማሰራጨት የደን አልሚው እውቀትና ክህሎት እንዲያድግ፣
2. የደን ልማት ግብአት አቅርቦት ሥርዓት እንዲዘረጋ፣
3. በደን ልማት ለተሰማሩ ሰዎች ዘመናዊ የደን ልማት፣ አያያዝ፣ ቴክኖሎጂ እና የገበያ እውቀት እንዲኖራቸው ሥልጠና እንዲያገኙ፣
4. የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የኤክስቴንሽን ፓኬጅ በማዘጋጀት እንዲተገበር ያደርጋል፡፡

19.**የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም**

1. መንግስት የመንግስት የደን ሀብት በጥብቅ፣ ፍፁም ጥብቅና በምርት ሰጪ ደንነት ተለይተው እንዲመዘገቡ፣ እንዲጠበቁ፣ እንዲለሙና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤
2. መንግስት ለካርበን ንግድ የሚሆን የደን መሬት ወይም ደን ሊከልል ይችላል፤
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሠረት የሚፈጸሙ ደን የመለየትና የመከለል ተግባራትን የአካባቢውን ህብረተሰብ በማሳተፍ የሚከናወኑ ይሆናል፤
4. በዚህ አንቀጽ (1) እና (2) መሠረት የተለየና የተከለለ የመንግሥት ደን ደኑ በሚገኝበት ክልል መንግሥት ዕውቅና ያገኛል፤
5. መንግስት የአካባቢው ሕብረተሰብ በመንግሥት ደኖች ልማትና ጥበቃ ላይ እንዲሳተፉ፣ የልማቱም ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያስችል የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም መርሐ-ግብር ይቀይሳል፤
6. መንግስት በደን ልማት ዘርፍ ኢንቨስት በማድረግ በልማቱ ይሳተፋል
7. መንግስት በይዞታው ስር ካሉ ደኖች በኮንሴሽን ሊለሙ የሚችሉ የደን ቦታዎችን በመለየት በኮንሴሽን ውል እንዲለሙ ሊያደርግ ይችላል፤
8. መንግሥት በጥብቅ ወይም በምርት ሰጪ ደንነት የተከለሉ ደኖችን የአካባቢው ነዋሪዎች፣ ግለሰቦች፣ ማህበራት ወይም ባለሀብቶች በሚመለከተው አካል በሚወጣ መመሪያ መሠረት የአካባቢውን ሕብረተሰብ በማሳተፍ የአያያዝ ዕቅድ አዘጋጅተው፤ ጠብቀውና አልምተው እንዲጠቀሙ ያደረጋል፤

9. መንግስት በደኑ መኖር ተጠቃሚ የሆኑ አካላትን ለደን ልማትና ጥበቃ አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ ስርዓት ይዘረጋል፤
10. መንግስት የጥምር እርሻ ደን ዘዴ በይበልጥ በአርሶ አደሩ፣ በከፊል አርብቶ አደሩና አርብቶ አደር ዘንድ እንዲሰርጽ ለማድረግ ልዩ ልዩ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸውን የዕፅዋት ዘርና ችግኝ በበቂ ሁኔታ እንዲያገኙ ያደረጋል፤
11. መንግስት በደን እና የደን መሬት ውስጥ የሰፈሩ ሰዎች ለልማቱ እንቅፋት በማይሆኑበት መንገድ ኑሮአቸውን የሚመሩበትና በልማቱና በጥበቃው ተግባር እንዲሳተፉ በማድረግ ተጠቃሚ የሚሆኑበት መንገድ ወይም በጥናት ላይ በመመስረት ከደኑና ከደን መሬቱ ውስጥ ወጥተው ሕይወታቸውን ሊመሩ በሚችሉባቸው ስፍራዎች እንዲሰፍሩ አግባብ ካለው አካል ጋር በመወያየት ሁኔታዎች እንዲመቻቹ ያደረጋል፤
12. መንግስት የግልና የማህበረሰብ ደን ልማትን ለማስፋፋት ለደን ልማትና የደን ውጤቶች ማምረቻ የሚውሉ መሣሪያዎች እና ቴክኖሎጂዎች እንደአስፈላጊነቱ ከታክስ ነፃ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡበት እና ሌሎች የድጋፍና የማበረታቻ ሥርዓቶች ያዘጋጃል፤
13. መንግስት የከተማ ደን ልማት እንዲስፋፋ ያደርጋል፡፡

20. <u>የደን ውጤቶች ገበያ ማስፋፋት መንግስት፤-</u>

1. ደን አልሚዎች ጥራቱን የጠበቀና ለገበያ ተወዳዳሪ የሆኑ የደን ውጤቶችን በማምረት ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ እንዲያቀርቡ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፤
2. በደን የአያያዝ ዕቅድ መሠረት የደን ውጤቶች ለንግድና ለኢንዱስትሪ ልማት እንዲውሉ እገዛ ያደርጋል፤
3. ለደን ውጤቶች ንግድ የሚሰጠው ፈቃድ የሀገሪቱን ውስን የደን ሀብት ዘለቄታዊ አጠቃቀም ባገናዘበና የአካባቢውን የተፈጥሮ ሀብት መዛባት በማያስከትል መንገድ በሚዘጋጅ የአያያዝ ዕቅድ መሠረት መሆኑን ያረጋግጣል፤
4. በገበያ ተፈላጊ ለሆኑ የዛፍ ዝርያዎች ተገቢውን እንክብካቤ በማድረግ ምርትና ምርታማነትን በዘላቂነት ለማሳደግ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤
5. በደን ልማት ተግባር ላይ ለተሰማሩ ሰዎች በደን ውጤቶች ግብይት ላይ ተከታታይ ሥልጠና እንዲሰጥ ያደርጋል፤

6. የደን አልሚዎችን በደን ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት ለማሳተፍ የሚያስችሉ ምቹ የኢንቨስትመንት አማራጮችና ማበረታቻዎች እንዲያገኙ ያደርጋል፤
7. የደን ውጤቶች ገበያ መረጃ በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች ለደን አልሚና ተጠቃሚ ህብረተሰብ እንዲደርስ ያደርጋል፡፡

## ክፍል ስምንት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 21. የደን አደጋዎችን መከላከል

1. አግባብነት ያላቸው የመንግስት አካላት የደን ቃጠሎን አስቀድሞ ለመከላከል የሚያስችል ተከታታይ ሥልጠና የመስጠትና የቅድመ-ማስጠንቀቂያ ሥርዓት የመዘርጋት ኃላፊነት አለባቸው፡፡
2. በደን ውስጥ ወይም በአካባቢው የሚኖር፣ የሚሰራ ወይም የሚተላለፍ ማንኛውም ሰው የደን ቃጠሎ እንዳይነሳ ተገቢውን ጥንቃቄ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡
3. የደን ቃጠሎ መነሳቱን የተረዳ ማንኛውም ሰው ወዲያውኑ በአቅራቢያው ለሚገኝ የመንግሥት አካልና ማኅበረሰብ ወይም ለሚኒስቴሩ ማሳወቅ አለበት፡፡
4. የደን ቃጠሎ ሲነሳ በየደረጃው ያለው የአስተዳደር አካላት፣ መንግሥታዊ፣ መንግሥታዊ ያልሆኑና የግል ተቋማትን እንዲሁም የአካባቢውን ሕብረተሰብ በማስተባበርና በማንቀሳቀስ እሳቱን ለማጥፋት ተገቢውን እርምጃ የመውሰድ ግዴታ አለባቸው፡፡
5. በአካባቢው የሚገኙ የሚመለከታቸው መንግሥታዊ፣ መንግሥታዊ ያልሆኑና የግል ተቋሞች እንዲሁም የአካባቢው ህብረተሰብ አባላት የተነሳውን የደን ቃጠሎ ለማጥፋት በሚደረገው እንቅስቃሴ የመሣተፍ ግዴታ አለባቸው፡፡
6. ከክልል አቅም በላይ የሆነ ከፍተኛ የደን ቃጠሎ አደጋ ሲከሰት ሚኒስቴሩ የማስተባበር ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡
7. የደን ባለቤቶች በይዞታቸው ሥር ባለ ደን ውስጥ ተባይና በሽታ ሲከሰት፣ ተስፋፊነት ያላቸው አረሞች ሲከሰቱ አግባብ ላለው ባለሥልጣን በአፋጣኝ ሪፖርት ማድረግ አለባቸው፡፡
8. ማንኛውም ሰው በደን ውስጥ ያልተፈቀዱ ወይም ያልታወቁ ለሰው፣ ለእንስሳት ወይም ለሥነ-ምህዳር ጎጂ የሆኑ ዕፅዋትን፣ እንስሳትን ወይም ደቂቅ አካላትና ነፍሳትን ማስገባት ወይም ማራባት አይቻልም፡፡

22.**የደን ውጤቶችን ማምረትና ማንቀሳቀስ**

1. ማንኛውም ሰው ከራሱ ይዞታ ካልሆነ በስተቀር ከሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ካለው የክልል አካል ወይም ከሚመለከተው የባለይዞታ ፈቃድ ሳያገኝ ከማንኛውም ደን ውስጥ የደን ውጤቶችን ማምረትና ማንቀሳቀስ አይችልም፡፡
2. ማንኛውም ሰው በግል ካለማው የሰው ሰራሽ ደን በስተቀር የደን ውጤት ከቦታ ቦታ ከማጓጓዙ በፊት የደን ሀብቱ በሚገኝበት አካባቢ አግባብ ላለው የመንግስት ባለሥልጣን በቅድሚያ በማሳወቅ የደን ውጤቶች እንቅስቃሴ ፈቃድ መያዝ ይኖርበታል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተመለከተውን በመተላለፍ የተያዘ የደን ውጤት ሊበላሽ የሚችል ከሆነ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው የክልል አካል የደን ውጤቱን በወቅቱ የገበያ ዋጋ ሸጦ ገንዘቡን በጉዳዩ ላይ የፍርድ ቤት ውሣኔ እስከሚሰጥ ድረስ አግባብ ባለው የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ጽሕፈት ቤት ዘንድ በአደራ ያስቀምጣል፡፡

23.**የደን ጠባቂዎች እና የደን ውጤት ተቆጣጣሪዎች**

1. የመንግሥት ደን ጠባቂዎች ከሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ካለው የክልል አካል በሚሰጣቸው መመሪያ መሠረት ደኖችን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 23 የተደነገጉትን በመተላለፍ ከሚፈፀሙ ድርጊቶች የመጠበቅ ሥልጣን ይኖራቸዋል፡፡
2. የደን ውጤት ተቆጣጣሪዎች ከሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ካለው የክልል አካል በሚሰጣቸው መመሪያ መሠረት፤

   ሀ) ሕገወጥ የደን ውጤቶችን የጫነ ወይንም ለመጫኑ የሚጠረጠርን ማናቸውንም ማጓጓዣ በደን ክልል መግቢያና መውጫዎች እንዲሁም እንደ አስፈላጊነቱ በሚመረጡ የሀገር ውስጥ እና የድንበር ኬላዎች ላይ አስቁሞ የመፈተሽ፤

   ለ) የደን ውጤቶችን ሲያጓጉዝ፣ ሲያዘጋጅ ወይም አከማችቶ የተገኘ ሰው የደን ውጤቶቹን መጠን፣ መነሻና መድረሻ የሚያሳይ የምስክር ወረቀት ወይም ማናቸውንም ሌላ ሕጋዊ ማስረጃ እንዲያቀርብ የመጠየቅ፤

   ሐ) የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች በመተላለፍ ተዘጋጅተው ሲጓጓዙ ወይም ተከማችተዉ የተገኙ የደን ውጤቶችን በመያዝ የድርጊቱ ተጠያቂዎችን ወዲያውኑ ለሚመለከተው ፍትሕ አካል ማቅረብ፤

መ) ስለተያዙ የደን ውጤቶች ዝርዝር ሁኔታ ወዲያውኑ ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ላለው የክልል ባለሥልጣን ሪፖርት የማድረግ ሃላፊነት አለባቸው ሃላፊነት አለባቸው

3. የደን ጠባቂዎችና የደን ውጤቶች ዝውውር ተቆጣጣሪዎች በሥራቸው ላይ በሚሆኑበት ጊዜ በሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ባለው የክልል አካል በሚወሰነው መሠረት የደንብ ልብስ የመልበስና መታወቂያ ወረቀት የመያዝ፣ በተጠየቁም ጊዜ ማሳየት አለባቸው፡፡

24.<u>የመጠቆም ግዴታና ማበረታቻ</u>

1. ማንኛውም ሰው ማናቸውንም ሕገወጥ የደን ውጤቶች ዝግጅትን፣ ዝውውርን፣ ወይም ክምችትን የተመለከተ እንደሆነ ለሚመለከተው አካል መጠቆም አለበት፤

2. ሕገ ወጥ የደን ውጤቶች በሚመለከት ጥቆማ ሚያቀርቡ ወይም ለሚይዙ ሰዎች ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ክልል ባለሥልጣን በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ማበረታቻ ይሰጣል፡፡

25.<u>የተከለከሉ ድርጊቶች</u>

1. ማንኛውም ሰው በመጥፋት ላይ የሚገኙ በተፈጥሮ የበቀሉ ሀገር በቀል ዛፎችን ከመንግሥት ደን ውስጥ እንዲሁም በተፈጥሮ በቅለው የሚገኙና በማህበረሰብ ይዞታነት ሥር ካሉ ደኖች መቁረጥ አይችል፡፡

2. በተፈጥሮ የበቀሉና ለመጥፋት የተጋለጡ ሀገር በቀል ዝርያዎችን በተመለከተ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ባለይዞታው በባለቤትነት ራሱ ተክሎ ያለማቸውን በመጥፋት ላይ የሚገኙ የዛፍ ዝርያዎች የሚመለከተው አካል አረጋግጦ በሚሰጠው ፍቃድ መሰረት ሊጠቀም ይችላል፡፡

4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1 እና (2 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም ሰው ከሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ካለው የክልል አካል ወይም ከባለ ይዞታው የጽሁፍ ፈቃድ ካልተሰጠው ወይም በራሱ ይዞታ ላይ ካልሆነ በስተቀር ከማንኛውም ደን ውስጥ፣

ሀ) ዛፍ መቁረጥ፣

ለ) በጊዜያዊነት ወይም በቋሚነት መስፈር፣

ሐ) የቤት እንስሳትን ለግጦሽ ማሰማራት፣

መ) አደን ማካሄድ፣

ሠ) የእንጨት መሰንጠቂያ መጋዞችና ሌሎች ለደን ጭፍጨፋ የሚረዱ መሣሪያዎች ይዞ መገኘት፣

ረ) ቀፎ መስቀል ወይም ማር መቁረጥ ወይም ሌሎች ተመሳሳይ ተግባራትን መፈጸም አይችልም፡፡

5. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም በደን የተሸፈነወይም የደን መሬት ለልማት ፕሮጀክቶች እንዲሰጥ ሲወሰን የአካባቢና ማህበራዊ ተፅእኖ ግምገማ ጥናት ቀርቦ በሚኒስቴሩ ወይም በሚመለከተው የክልል አካል ይሁንታ ማግኘት ይኖርበታል፡

26.<u>ቅጣት</u>

1. በዚህ አዋጅና አዋጁን ለማስፈፀም በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት ካልሆነ በስተቀር ከመንግሥት፤ ከማህበረሰብ እና ከግል ደኖችና የደን መሬቶች ዛፎችን ከባለ ይዞታው ፈቃድ ውጭ የቆረጠ ወይም የደን ውጤቶችን የወሰደ ፤ ለዚህ ተግባር የተባበረ ወይም በማንኛውም በሕገ ወጥ መንገድ የተገኘ የደን ውጤት ይዞ የተገኘ ወይም የተጠቀመ ማንኛውም ሰው የደን ውጤቱ መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ ከአንድ ዓመት በማያንስና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከ10,000 (አስር ሺ) ብር እስከ 20,000 (ሀያ ሺ) ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

2. የደን የወሰን ምልክቶችን ያጠፋ፣ ያበላሸ ወይም ያዛባ ማንኛውም ሰው ከአንድ ዓመት በማያንስ እና ከሦስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከ10 (አስር) ሺ ብር እስከ 30 (ሰላሳ) ሺ.ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡

3. ሆነ ብሎ እሳት በመለኮስ ወይም በማናቸውም ሌላ ሁኔታ በደን ላይ ጉዳት ያደረሰ ማንኛውም ሰው ከ 10 (አስር) ዓመት በማያንስና ከ15 (አስራ አምስት) ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል፤ ጉዳቱ የደረሰው በቸልተኝነት ከሆነ ከአንድ ዓመት በማያንስና ከሁለት አመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም ከ5 (አምስት) ሺ ብር እስከ 10 (አስር) ሺ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

4. ደን እና የደን መሬት ተብሎ በተከለለ ስፍራ የሰፈረ ወይም የእርሻ ቦታ ያስፋፋ ወይም ማንኛውንም ግንባታ ያካሄደ ማንኛውም ሰው ከሁለት ዓመት በማያንስና ከአራት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከ10 (አስር) ሺ እስከ 40 (አርባ) ሺ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

5. ያልተፈቀደ የደን ውጤት ያጓጓዘ ማንኛውም ሰው ከስድስት ወር በማያንስና ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት እና ከብር 5 (አምስት) ሺ. እስከ ብር 10 (አስር) ሺ. በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡
6. ማንኛውም የደን ባለቤት በደን ውስጥ ተባይ፣ ተስፋፊነት ያላቸው አረሞችና በሽታ መከሰቱን እያወቀ አግባብ ላለው አካል በአፋጣኝ ያላሳወቀ እንደሆነ ከስድስት ወር በማያንስና ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት እና ከብር 1 (አንድ) ሺ. እስከ 5 (አምስት) ሺ. በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡
7. ማንኛውም የደን ባለቤት በደን ውስጥ ያልተፈቀዱ ዕፅዋትን፣ እንስሳትን ወይም ደቂቅ ነፍሳትን ያስገባ እንደሆነ ከአንድ ዓመት በማያንስና ከሦስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከብር 10 (አስር) ሺ. እስከ 30 (ሰላሣ) ሺ. በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡
8. ዝርያቸው በመጥፋት የሚገኙ የዛፍ አይነቶችን በህገወጥ መንገድ ከመንግስት፣ ከማህብራት፣ ከማህበረሰብና ከግል ይዞታ ላይ የቆረጠ፣ ያጓጓዘ፣ ያከማቸና ለሽያጭ ያቀረበ ከ5 (አምስት) ዓመት በማያንስና ከ8 (ስምንት) ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራትና ከ15 (አስራ አምስት) ሺህ ብር እስከ 20 (ሀያ) ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

27.<u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ደንብ እና መመሪያ እንደ ቅደም ተከተላቸው የሚኒስትሮች ምክር ቤት እና ሚኒስቴሩ ያወጣሉ፤ እንዳስፈላጊቱ ክልሎች ተጨማሪ ደንብና መመሪያ ሊያወጡ ይችላሉ፤

28.<u>የተሻሩና ተፈጻሚነት የሌላቸው ሕጎች</u>

1. የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 542/1999 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡
2. ይህንን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን ጉዳዮች በተመለከተ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

29.<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥር 15 ቀን 2010 ዓ.ም**

**ሙላቱ ተሾመ (ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊ ፕሬዚዳንት**

**ሠ) የውሀና የዓሳ ሀብት**

**አዋጅ ቁጥር 197/1992**

**የኢትዮጵያ የውሃ ሀብት አስተዳደር አዋጅ**

የኢትዮጵያ የውሃ ሀብት በአግባቡ ተጠብቆና በተገቢው አስተዳደር ሥር ሆኖ ለሕዝቦቿ ለላቀ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም እንዲውል ለማድረግ የውሃ ሀብት ጥበቃ፣ አጠቃቀምና አስተዳደር አዋጅ ማውጣት በማስፈለጉ፣

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 55(1) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ ድንጋጌዎች**

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ የውሃ ሀብት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 197/1992" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

   1. "የውሃ መመናመን" ማለት በሰው ሰራሽ ወይም በተፈጥሮአዊ ምክንያት የውሃ ሀብት መጠን በአንድ የተወሰነ ወቅት መገኘት ከሚገባው መደበኛ ደረጃ እየቀነሰ መምጣት ነው፣
   2. "የቤት ውስጥ ግልጋሎት" ማለት ለመጠጥ፣ ምግብ ለማብሰል፣ ለጽዳት ወይም ለሌላ የቤት ወስጥ ሥራ ማዋል ነው፣
   3. "ከአቅም በላይ የሆነ ኃይል" ማለት በኢትዮጵያ የፍትሐ ብሄር ሕግ እንደተደነገገው ነው፣
   4. "የከርሰ ምድር ውሃ" ማለት ከመሬት በታች የሚገኝ ውሃ ነው፣
   5. "የገጸ ምድር ውሃ" ማለት የረጋ ወይም የሚፈስ በመሬት ላይ የሚገኝ ውሃ ነው፣
   6. "የውሃ ሀብት" ማለት የገጸ ምድር እና የከርሰ ምድር ውሃ ሲሆን በማዕድን አዋጅ ቁጥር 52/1985[32] መሠረት የማዕድን ውሃንና የጂኦተርማል ክምችቶችን አይጨምርም፣

[32]በ16/45 (2002) አ. 678 ተሻሯል፡፡

7. “ተቆጣጣሪ አካል” ማለት የማዕከል የውሃ ሀብትን በሚመለከት ሚኒስቴሩ ወይም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ከሚኒስትሩ ውክልና የተሰጠው አካል ነው፣
8. “የመንግስት አካል” ማለት ማንኛውም የፌዴራል መንግስት ወይም የክልል መስተዳድር ወይም የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ወይም የድሬዳዋ አስተዳደር አካል ነው፣
9. “ባህላዊ መስኖ” ማለት መሬትን ለማልማት በአንድ ሴኮንድ ውስጥ ከአንድ ሊትር የማይበልጥ ውሃን በመውሰድ ወይም አንድ አርሶ አደር ከአንድ ሄክታር የማይበልጥ መሬትን የሚያለማበት በአርሶ አደር የሚካሄድመስኖ ነው፣
10. “ቆሻሻ” ማለት ማናቸውም በጠጣር ፣ በፈሳሽ ወይም በተናኝ ጋዝ መልክ ወደ ማናቸውም የውሃ ሀብት አካል የሚጨመር ፣ የሚለቀቅ ወይም የሚደፋ ጐጂ ነገር ነው፣
11. “የተበከለ ውሃ” ማለት ፍሳሽና ከፋብሪካዎች የሚወጣ ቆሻሻ ውሃ እንዲሁም መርዛማ ውሃ ነው፣
12. “የውሃ ብክለት” ማለት ኦርጋኒክ ወይም ኢንኦርጋኒክ ይዘት ያላቸውን ነገሮች በመጠቀም ወይም በውሃው የሙቀት መጠን ለውጥ ምክንያት ውሃው በመበከሉ ሊከሰት የሚችል ጉዳት ነው፣
13. “የውሃ ጥራት” ማለት በፊዚካል፣ በኬሚካል፣ በማይክሮ ባዮሎጂካል፣ በባክቴሪዮሎጂካል እና ሬዲዮሎጂካል ገጽታው በሚታወቀው መሰረት የውሃ ጥራት መግለጫ ነው፣
14. “የውሃ ጥራት ደረጃዎች” ማለት ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 13 ውስጥ ከተጠቀሱት ገጽታዎች አኳያ ሊጠበቁ የሚያስፈልጉትንና የሚፈቀዱትን ደረጃዎች በመወሰን የሚደረግ መለኪያና የጥራት አወሳሰን ነው፣
15. “ተፋሰስ” ማለት ወደ አንድ መልክአ ምድራዊ አቅጣጫ የሚፈሱ የገጸ ምድርን የከርሰ ምድር ውኃዎች የሚያካልሉት አካባቢ ነው፣
16. “የውሃ አካላት ዳርቻ” ማለት ክልሉ እና)ወይም ርቀቱ በተቆጣጣሪው አካልና አግባብ ባለው የመንግስት አካል አማካኝነት የሚወሰን መሬትና ማናቸውም የውሃ አካል የሚገናኝበት ሥፍራ ነው፣
17. “የውሃ መሄጃ” ማለት ውሃ ሁልጊዜ ወይም አንዳንድ ጊዜ የሚሄድበት የተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ ወንዝ ፣ ጅረት፣ ቦይ ወይም ማንኛውም የውሃ መውረጃ ነው፣

18.“የውሃ ስራዎች” ማለት የውሃ ሀብትን ጠቀሜታ ላለው ተግባር ለማዋል የተገነቡ ወይም የሚገነቡ ማናቸውም ሰው ሰራሽ ስራዎች ሲሆኑ ይህም መጥለፍን፣ መገደብን፣ መቆፈርን ወይም መሰርሰርን፣ መጥረግን፣ መመርመርን፣ መቆጣጠርን፣ ማጣራትን፣ መለካትን፣ ማጓጓዝን፣ ማስተላለፍን ጨው አልባ ማድረግን ጎርፍ መከላከያ መገንባትንና ሌሎች ተዛማጅና የመሳሰሉ ሥራዎችን ማከናወንን ያጠቃልላል፤

19.“የውሃ ሀብት አስተዳደር” ማለት የውሃ ሀብትን ማልማትን፣ አጠቃቀምን፣ መንከባከብን፣ መጠበቅንና መቆጣጠርን የሚመለከቱ ተግባራትን ያካተተ ነው፣

20. “ሚኒስቴር” ወይም “ሚኒስትር” ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የውሃ ሀብት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፣[33]

21.“ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም የሕግ ሰውነት መብትና ግዴታ የተሰጠው አካል ነው፣

22.“የንብረት አገልግሎት” ማለት በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 1359 መሰረት የተተረጎመው የንብረት አገልግሎት ነው፡፡

3. <u>ዓላማ</u>

የአዋጁ አላማ የአገሪቱ የውሃ ሀብት በአግባቡ ተጠብቆ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ለላቀ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም መዋሉን፣ በሚገባ መጠበቁን መከታተልና መቆጣጠር፣ የውሃ ጎጂ ገፅታዎችን መከላከል፣ እንዲሁም የውሃ ሀብት ጠቅላላ አስተዳደር በሚገባ መካሄዱን ማረጋገጥ ይሆናል፡፡

4. <u>የአፈጻጸም ወሰን</u>

ይህ አዋጅ የውሃ ሀብት አስተዳደርን በተመለከተ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኝ በማናቸውም የውሃ ሀብት ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

5. <u>የውሃ ሃብት የሕዝብ ስለመሆኑ</u>

ሁሉም የአገሪቱ የውሃ ሀብት የመንግሥትና የሁሉም የኢትየጵያ ህዝብ የጋራ ሀብት ነው፣

6. <u>መሠረታዊ መርሆዎች</u>

1. የተቀናጁ የተፋሰስ ማስተር ፕላን ጥናቶች እና የውሃ ሃብት ሕጎች ማንኛውም የውሃ ሃብት ለሁሉም የኢትየጵያ ሕዝብ ከሁሉም ለላቀ ማኀበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም መዋሉን የሚመሠርቱና የሚያረጋግጡ ይሆናሉ፡፡

[33] በ25/08 (2011)አ. 1097 አንቀጽ 9(11) መሰረት የውሃ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር ሆኗል፡፡

2. የማኛውም ሰው ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ የልማት መርሃ ግብሮች፣ የኢንቨስትመንት ዕቅዶችና የውሃ ሃብት ልማት ሥራዎች የኢትዮጵያን የውሃ ሃብት አስተዳደር ፖሊሲ፣ አግባብነት ያላቸውን የተፋሰስ ማስተር ፕላን ጥናቶች እንዲሁም የውሃ ሃብት አስተዳደር ሕጎችን የተከተሉና መሠረት ያደረጉ መሆን አለባቸው፡፡
3. ተቆጣጣሪው አካል ማንኛውም የውሃ ሃብት ለሁሉም የኢትየጵያ ሕዝብ ለላቀ ማኀበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም መዋሉን የኢትዮጵያን የውሃ ሃብት አስተዳደር ፖሊሲን፣ የተፋሰስ ማስተር ፕላን ጥናቶችን እና የውሃ ሃብት ሕጎችን መሰረት በማድረግ ያረጋግጣል፣ ያስተዳድራል።
4. የኢትዮጵያን የውሃ ሃብት አስተዳደር በፈቃድ ሥርዓት ላይ የተመሰረተ ይሆናል፡፡

## 7. የአገልግሎት ቅድሚያ ስለመስጠት

1. ለቤት ውስጥ ግልጋሎት የሚውል ውሃ ለሌላ ለማናቸውም ግልጋሎት ከሚውል ውሃ ቀደምትነት ይኖረዋል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1 እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የውሃ ሀብቱ አስቀድሞ ለአንድ ለተወሰነ አገልግሎት በመዋሉ ወይም እንዲውል በመታቀዱ ብቻ ግልጋሎቱን ከሌሎች የውሃ ግልጋሎቶች ሁሉ ሊያስበልጠው ወይም የቅድሚያ መብት ሊያሰጠው አይችልም።

## ክፍል ሁለት

## ስለተቆጣጣሪ አካል

## 8. ስለተቆጣጣሪው አካል ስልጣንና ተግባር

1. ተቆጣጣሪው አካል ስለውሃ ሀብት ዕቅድ፣ አሰተዳደር፣ አጠቃቀም እና ጥበቃ ኃላፊ ይሆናል። እንዲሁም በአዋጁ መሠረት ሥራውን ለማከናወን የሚያስፈልገው ሥልጣን ይኖረዋል። ከዚህ በላይ የተነገረው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ተቆጣጣሪው አካል የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፣
   ሀ) ፈቃድና የሙያ ብቀት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣
   ለ) የውሃ ሀብትን ልማት ጥበቃ አጠቃቀም እና ቁጥጥር በሚመለከት ጥናቶች መካሄዳቸውን ያረጋግጣል፣
   ሐ) በተለያዩ ግልጋሎቶች ወይም ተገልጋዮች መካከል የውሃ ሀብት ክፍፍልንና የአጠቃቀም ሁኔታዎችን ይወስናል፣

መ) የውሃ ሥራዎች ለማከናወን የሚያስችል ፈቃድ ማናቸውም ሰው ሲጠይቅ ስለሥራዎቹ የተዘጋጁ እቅዶችና ሃሣቦች እንዲቀርቡለት ይጠይቃል፣ የቀረበለትንም ያጸድቃል፣ ውድቅ ያደርጋል ወይም ያሻሽላል ፣

ሠ) የቅየሳዎችን፣ የንድፎችን (የዲዛይን እና የውሃ ሥራዎች ዝርዝሮችን )ስፔስፊኬሽን) እንዲሁም ለውሃ ሀብት ልማት የሚፈለጉትን የውሃ ሥራዎች ግንባታ የጥራት ደረጃ ይመሠርታል፣ የውሃ ሥራዎች ተገቢውን ደረጃ የጠበቁ መሆናቸውን ይቆጣጠራል፣

ረ) የውሃ ሀብት እንዳይበከል እና ለጤናና ለአካባቢ የጤና ጠንቅ አለመሆኑን ለማረጋገጥ አግባብነት ካላቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመመካከር መመሪያ ያዘጋጃል፣

ሰ) የግድብ ውሃ በግድቦች እና በሰዎች በንብረትና በሰብል ላይ ጉዳት እንዳያደርስ ለመከላከል እንዲቻል ለሃይድሮሊክ ስትራክቸር የደኅንነት መመሪያ ያወጣል፣

ሸ) አግባብነት ካላቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመመካከር የተበከለ ውሃ ወደ ውሃ ሀብት ለመልቀቅ ወይም ለመድፋት የሚቀርብ የፈቃድ ማመልከቻን ለመቀበል የሚያስችል የጥራት ወይም የጤናማነት ደረጃ እንዲወጣ ያደርጋል፣

ቀ) ከኢትዮጵያ የውሃ ሀብት ፖሊሲ፣ አግባብነት ካለው የተፋሰስ ማስተር ፕላን እና የውሃ ሀብት ሕጎች ጋር የማይራመዱ ወይም የማይስማሙ የውሃ ሥራዎች
እንዲስተካከሉ ወይም እንዲታገዱ ትዕዛዝ ይሰጣል፣ ተግባራዊ መሆኑንም ያረጋግጣል፣

በ) በማናቸውም አካባቢ አስቸኳይ የውሃ እጥረት በሚከሰትበት ወቅት በውሃ አጠቃቀም ላይ ሊደረግ ስለሚገባው ገደብ መመሪያ ያወጣል፣ አፈጻጸሙንም ይቆጣጠራል፡፡

2. ተቆጣጣሪው አካል የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር በተቀላጠፈ ሁኔታ ለማከናወን ሲል እንደአስፈላጊነቱ አግባብነት ላለው አካል የውክልና ሥልጣን ሊሰጥ ይችላል፡፡

9. <u>ስለክርክሮች አወሳሰን</u>

1. ተቆጣጣሪው አካል ከፈቃዱ ጋር የተያያዙ መብቶችን ወይም ግዴታዎችን በተመለከተ በባለፈቃዶች መካከል ወይም በባለፈቃድና በሦስተኛ ወገኖች መካከል የሚነሱ ማናቸውም ክርክሮችን ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ በሚወሰን ሥነ ሥርዓትመሠረት አይቶ መወሰን ይችላል፡፡ እንዲሁም ተቆጣጣሪው አካል አንደኛው ተከራካሪ ወገን ለሌላኛው ተገቢውን ካሣ እንዲከፍል ለመወሰን እና ውሣኔዎቹን ለማስፈጸም አስፈላጊውን ትዕዛዝ ለመስጠት ሥልጣን ይኖረዋል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ተቆጣጣሪው አካል በሚሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን ውሳኔው በደረሰው በ60 ቀናት ውስጥ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ ሊያቀርብ ይችላል። ሆኖም ከ60 ቀናት በኋላ የሚቀርብ ይግባኝ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡
3. በተቆጣጣሪው አካልና በባለፍቃዱ መካከል፣ ከፈቃዱ ጋር በተያያዙ ምክንያቶች የሚፈጠር ማንኛውም ክርክርና አለመግባባት ወይም የይገባኛል ጥያቄ በተቻለ መጠን በጋራ ውይይት ይፈታል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (3) መሰረት ጉዳዩ በጋራ ውይይት ሊፈታ ካልቻለ በሽምግልና ዳኝነት ታይቶ ይወሰናል፡፡ ዝርዝሩ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>ስለውሃ ሀብት ዝርዝር ሁኔታና የተወሰዱትን እርምጃዎች ስለመመዝገብ</u>

10. <u>የውሃ ሀብት ዝርዝር ሁኔታ እና የተወሰዱ እርምጃዎችን ስለመመዝገብ</u>

1. ተቆጣጣሪው አካል የውሃ ሀብትን ጥቅም ላይ ለማዋል እንዲቻል ይኸው ሀብት ስለመኖሩ በቂ እውቀት መኖሩን የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለበት በመሆኑ በአገሪቱ ውስጥ ያለውን የውሃ ሀብት ዝርዝር ያዘጋጃል ወይም እንዲዘጋጅ ያደርጋል። ዝርዝሩንም ይይዛል፡፡ ዝርዝሩም፤

   ሀ) በአመት ውስጥ በማናቸውም አስፈላጊ ወቅት የውሃ ሀብት ስለመገኘቱ፣ ስለመኖሩ፣ የሚገኝበትን ሥፍራ፣ ስለመጠኑና ስለጥራቱ መለያ እና መግለጫ፤

   ለ) የውሃውን አቅርቦት በሚመለከት በየክፍለ ዓመቱ የሚጠበቀው ፍላጎት መለያና መግለጫ፤

ሐ) ፍጆታዊ እና ፍጆታዊ ያልሆነ የውሃ ግልጋሎትን በሚመለከት በየጊዜው የተጠናቀሩ መረጃዎችን ይጨምራል።

2. ተቆጣጣሪው አካል በውሃ ሀብት መጠቀምን፣ ቆሻሻን ውሃ ሀብት ውስጥ መልቀቅን ወይም መድፋትን እንዲሁም የውሃ ሥራዎች ግንባታን በሚመለከት በቀረቡለት ማመልከቻዎች ላይ የተወሰደውን እርምጃ የሚያሳዩ መዝገቦችን በሁሉም ደረጃዎች አቋቁሞ ይይዛል፡፡ መዝገቡም በዚህ አዋጅ መሠረት ሚኒስቴሩ የሚያወጣው መመሪያ የሚጠይቀውን መረጃ የሚያካትት ይሆናል፡፡

3. የሀገሪቱን ጠቅላላ የውሃ ሀብት ዝርዝር በማዕከላዊነት ለማወቅ እንዲረዳና ሀብቱ በተገቢው ሁኔታ ጥቅም ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ አግባብነት ያላቸው የመንግሥት አካላት ሚኒስቴሩ በሚወስነው አኳኋን በየክልላቸው ስለሚገኘው የውሃ ሀብት ዝርዝር እና የውሃ ሀብቱን ጥቅም ላይ ለማዋል ስለተፈጸሙ ድርጊቶች መረጃዎችን ለሚኒስትሩ መስጠት አለባቸው፣

4. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (3) የተጠቀሱት መረጃዎችም ሚኒስቴሩ የሚይዛቸው የውሃ ሀብት መረጃ ማዕከል አካል ይሆናሉ፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ስለፈቃዶች እና የሙያ ፈቃድ</u>

### 11.<u>ስለፈቃድ አስፈላጊነት</u>

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12 የተጠቀሱት ልዩ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንም ሰው ከተቆጣጣሪው አካል ፈቃድ ሳያገኝ የሚከተሉትን ተግባራት ሊፈጽም አይችልም፤

   ሀ) የውሃሥራዎችን መገንባት፤

   ለ) ለራስ ግልጋሎትም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ውሃ ማቅረብ፤

   ሐ) ራሱ ከውሃ ሀብት የወሰደውንም ሆነ ከሌላ አቅራቢ የተቀበለውን ውሃ ለሌላ ማስተላለፍ፤

   መ) ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣው ደንብ መሰረት በሌላ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ማናቸውንም ቆሻሻ በውሃ ሀብት ውስጥ መልቀቅ ወይም መድፋት፡፡

2. ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ለተጠቀሱት ተግባራት ፈቃድ እንዲሰጠው ከመጠየቁ በፊት ስለዕቅዱ በቅድሚያ ከተቆጣጣሪው አካል ጋር መመካከር አለበት፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

12.<u>ፈቃድ ስለማያስፈልጋቸው የውሃ ግልጋሎት ዓይነቶች</u>

1. ማንኛውም ሰው ከተቆጣጣሪው አካል የተሰጠ ፈቃድ ሳይኖረው የውሃ ሀብትን ለሚከተሉት ተግባራት ሊያውል ይችላል፡-
   ሀ) በእጅ የውሃ ጉድጓድ ለመቆፈር ወይም በእጅ ከተቆፈረ ጉድጓድ ውሀ ለመጠቀም፤
   ለ) በባሕላዊ የመስኖ እርሻ፣ ለባሕላዊ የማዕድን ማውጣት ተግባር እና ለባሕላዊ የእንስሳትእርባታ ሥራ እንዲሁም በውሃ ለሚሠራ የእህል ወፍጮ አገልግሎት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሀ) እና (ለ) ለተጠቀሱት ግልጋሎቶች የሚውል ውሃ ያለአግባብ ጥቅም ላይ እንዳይውልና እንዳይባክን ለማድረግ ተቆጣጣሪው አካል እንደ አስፈላጊነቱ አግባብነት ያላቸውን መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

13.<u>ስለፈቃድ ማመልከቻ፤</u>

1. በውሃ ሃብት ለመጠቀም፣ ቆሻሻን ውሃ ሀብት ውስጥ ለመልቀቅ ወይም ለመድፋት እና የውሃ ሥራዎች ግንባታን ለማከናወን የፈቃድ መጠየቂያ ማመልከቻ ለተቆጣጣሪው አካል መቅረብ ይኖርበታል። ማመልከቻውም ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣው ደንብ የተመለከተውን ዝርዝር መረጃ ያካተተ ይሆናል፡፡
2. ለሰው ሕይወት፣ ለእንስሳት፣ ለዕጽዋትና ሕይወት ላላቸው ማናቸውም ነገሮች አደገኛ የሆነ ቆሻሻን በውሃ ሀብት ውስጥ ለመልቀቅ ወይም ለመድፋት የሚቀርብ ማመልከቻ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ ሆኖም ተቆጣጣሪው አካል አመልካቹ በካዩን ቆሻሻ አስቀድሞ እንዲያክም ካደረገ ወይም ካሳከመ በኋላ እንዲለቅ ወይም እንዲደፋ በመጠየቅ ማመልከቻውን ሊቀበለው ይችላል፡፡ ዝርዝሩ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

14.<u>ስለፈቃድ አሰጣጥ</u>

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ (3) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የታቀደው የውሃ ግልጋሎት፤
   ሀ) በውሃ ሁብቱ የመጠቀም ሕጋዊ መብት ያለውን ሰው ጥቅም በማናቸውም መልኩ የማይነካ ከሆነ፤
   ለ) በውሃ ሀብትና በአካባቢው ላይ ጎጂ ውጤትን ወይም ብክለትን የማያስከትል ከሆነ፣

ተቆጣጣሪው አካል ከዚህ በላይ በአንቀጽ 13 መሠረት ማመልከቻው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ በስልሣ ቀኖች ውስጥ ለጠያቂው ፈቃዱን ይሰጠዋል።

2. ዝርዝሩ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣው ደንብ የሚወሰን ሆኖ ተቆጣጣሪው አካል በፈቃዱ ውስጥ ሊጠቀሱ የሚገባቸውን መረጃዎች፣ ሁኔታዎችና ገደቦች በፈቃድ መስጫው ቅጽ ላይ ያሰፍራል፣
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሱት ምክንያቶች ሳይሟሉ በመቅረታቸው ማመልከቻው በተቆጣጣሪው አካል ውድቅ የሚደረግ ሲሆን፣ ተቆጣጣሪው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ማመልከቻው ውድቅ መደረጉንና ምክንያቶቹን በጽሁፍ ለአመልካቹ ያስታውቃል፡፡

15.<u>ፈቃዱ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜና እድሳት</u>

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 14 መሠረት የተሰጠ ፈቃድ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ እና ፈቃዱ የሚታደስበት ተገቢው የጊዜ ገደብ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣው ደንብ መሠረት ይወሰናል፡፡
2. ፈቃድ ያገኘ በፈቃዱ ውስጥ የተጠቀሱትን ሁኔታዎች፣ ግዴታዎችና ገደቦች እንዲሁም በዚህ አዋጅና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣው ደንብ ውስጥ የተመለከቱትን አስፈላጊ ሁኔታዎች ማክበሩን ተቆጣጣሪው አካል ሲያረጋጥ ፈቃዱን ያድሳል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ፈቃዱ በጊዜ ገደቡ ሳይታደስ ከቀረ እንደተሰረዘ ይቆጠራል።

16.<u>ፈቃዱን ስለማሻሻልና ማስተላለፍ</u>

1. ፈቃድ ያገኘ የተፈቀደለት የውሃ መጠን እንዲቀነስበት ወይም እንዲጨመርለት ወይም ውሃውን ጠቀሜታ ላለው ለሌላ ተግባር እንዲያውል ፈቃዱ እንዲሻሻልለት ሊያመለክት ይችላል፡፡
2. ተቆጣጣሪው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው ማመልከቻ ሲቀርብለት በአሥር ቀኖች ውስጥ ውሳኔ ይሰጥበታል፡፡

3. ተቆጣጣሪው አካል የአካባቢ ሁኔታዎች በመለወጣቸው ወይም በውሀ ለመጠቀም ያለው ፍላጎት በመጨመሩ ወይም በማናቸውም ሌላ በቂ ምክንያት የውሀውን ክፍፍል እንደገና ማስተካከል አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ይንኑ ለፈቃድ ያገዙ ከስልሳ ቀኖች በፊት በጽሁፍ በማስታወቅ ፈቃዱን ሊያሻሽል ይችላል፡፡ ሆኖም ማሻሻያው በአካባቢው ላይ በደረሰው ተፈጥሮአዊ ለውጥ ምክንያት ካልተደረገ በስተቀር፣ ማሻሻያ በመደረጉ ምክንያት በፈቃድ ያገዙ ላይ ለሚደርስ ጉዳት በፍትሐብሔር ሕግ መሰረት በጉዳት አድራሹ ካሳ ይከፈለዋል፡፡
4. ፈቃድ ያገዙ ሲጠይቅ እና በተቆጣጣሪው አካል ሲፈቀድ በውሃ ሀብት የመጠቀም ፈቃድ ለሌላ ሰው በሕጋዊ መንገድ ሊተላለፍ ይችላል፡፡

17.<u>ስለፈቃድ መሠረዝ ወይም መታገድ</u>

ፈቃድ ያገዙ የሚጠበቅበትን ግዴታዎች የማያሟላ ወይም የማያከብር ሆኖ ሲገኝ ተቆጣጣሪው አካል በማናቸውም ጊዜ ፈቃዱን በሙሉ ወይም በከፊል ሊያግድ ወይም ሊሠርዝ ይችላል፡፡ ዝርዝሩ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣው ደንብ መሠረት ይወሰናል፡፡

18.<u>ስለቅሬታ</u>

1. የሚመለከቱትን ጉዳዮች የሚመለከቱ ማመልከቻዎች በመጀመሪያ ደረጃ ለተቆጣጣሪው አካል ይቀርባሉ፣
   ሀ) በውሃ ሀብት ለመጠቀም ወይም በውሃ ሀብት ውስጥ ቆሻሻ ለመድፋት ወይም ለመልቀቅ፣ ወይም
   ለ) የውሃ ስራዎች ግንባታ ለማካሄድ፣ ወይም
   ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሀ) እና (ለ) የተመለከቱትን ተግባራትለማከናወን የተሰጠ ፈቃድ እንዲሻሻል ወይም እንዲተላለፍ፣ ወይም
   መ) የውሃ ሀብት አጠቃቀምን አስመልክቶ በውሃ ሀብቱ ለመጠቀም ሕጋዊ መብት ባላቸው ሰዎች መካከል የሚነሱ አለመግባባቶች፡፡
2. ተቆጣጣሪው አካል በዚህ አዋጅና አዋጁን ለማስፈጸም በሚወጣው ደንብ መሠረት በቀረበለት ማመልከቻ ላይ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጣል፣ አስፈላጊውን እርምጃም ይወስዳል።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተቆጣጣሪው አካል በሰጠው ውሳኔ ወይም በወሰደው እርምጃ ቅር የተሰኘ ወገን ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን አንስቶ በስልሳ (60) ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ሊያቀርብ ይችላል፡፡

19.<u>ስለሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት</u>

ማንኛውም ሰው ከተቆጣጣሪው አካል የተሰጠ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይኖረው ለንግድም ሆነ ለሌላ ዓላማ የገፀ ምድር የውሃ ሥራዎች ግንባታ ለማካሔድ ወይም ጥልቅ ጉድጓድ ቁፋሮ ፣ ስርሰራ ወይም ጠረጋ ለማካሔድ ወይም ከነዚሁ ጋር የተያያዘ የአማካሪነት አገልግሎት ለመስጠት አይችልም። ዝርዝሩ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣው ደንብ መሠረት ይወሰናል፡፡

## <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>ስለፈቃድ ክፍያ እና የውሃ ግልጋሎት ዋጋ</u>

20.<u>ስለፈቃድ አገልግሎት ክፍያ</u>

1. ለሚከተሉት ጉዳዮች የፈቃድ አገልግሎት ክፍያ ይፈጸማል፣
   ሀ) የውሃ ሥራዎችን ለመገንባት ፈቃድ ለማግኘት፣
   ለ) በውሃ ግልጋሎት ለመጠቀም ፈቃድ ለማግኘት፣
   ሐ) ቆሻሻን በውሃ ሀብት ውስጥ ለመልቀቅ ወይም ለመድፋት ፈቃድ ለማግኘት፣
   መ) ውሃ ነክ ለሆነ ጉዳይ ማናቸውንም ፈቃድ ለማግኘት፣ ለማደስ፣ ለማሻሻል ወይም ለማስተላለፍ፡፡
2. ማንኛውም ሰው የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት፣ ለማሳደስ ወይም ለማሻሻል የአገልግሎት ክፍያ ይከፍላል።
3. የክፍያው መጠን ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣው ደንብ መሠረት ይሆናል፡፡
4. ተቆጣጣሪው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)-(3) መሠረት የተወሰነውን የአገልግሎት ክፍያ የመሰብሰብ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡
5. ተቆጣጣሪው አካል ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣው ደንብ መሠረት ሕዝባዊ ጠቀሜታ ያላቸው የተወሰኑ ግልጋሎቶች ከአገልግሎት ክፍያ ነጻ እንዲሆኑ ማድረግ ይችላል፡፡

21.<u>ስለውሃ ግልጋሎት ዋጋ</u>

1. በዚህ አዋጅ መሠረት የውሃ ሀብትን ለማንኛውም ለተፈቀደ ግልጋሎት ለማዋል የውሃ ግልጋሎት ዋጋ ይከፈላል፡፡ የሚከፈለው የክፍያ ተመን ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣው ደንብ መሠረት ይሆናል፡፡
2. ተቆጣጣሪው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተወሰነውን ዋጋ የመሰብሰብ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡
3. ተቆጣጣሪው አካል ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣው ደንብ መሰረት የተወሰኑ ሰዎችን ከውሃ ግልጋሎት ዋጋ ክፍያ ነጻ ሊያደርግ ይችላል፡፡

22.<u>በውሃ ሀብት ውስጥ ቆሻሻን ለመልቀቅ ወይም ለመድፋት ስለሚደረግ ክፍያ</u>

1. ቆሻሻን በውሃ ሀብት ውስጥ ለመድፋት ወይም ለመልቀቅ ፈቃድ በተሰጣቸው ሰዎች ቆሻሻን ለመድፋት የተወሰነ ክፍያ ይከፈላል። የሚከፈለው ክፍያ አዋጁን ለማስፈጸም በሚወጣው ደንብ መሠረት ይሆናል፡፡
2. ተቆጣጣሪው አካል በደንቡ የተወሰነውን ክፍያ የመሰብሰብ ስልጣን ተሰጥቶታል፡

## <u>ክፍል ስድስት</u>

## <u>ስለንብረት አገልግሎት</u>

23.<u>ስለንብረት አገልግሎት</u>

1. ማናቸውንም የተፈቀዱ የውሃ ሥራዎች ተግባራዊ ለማድረግና ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ የንብረት አገልግሎቶች እና የመተላለፍ መብቶች በመሬት ባለይዞታዎች ላይ ግዴታ ይሆናሉ።
2. የንብረት አገልግሎቱ የሚመሰረትባቸው ልዩ ልዩ ሁኔታዎች ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣው ደንብ መሠረት ይወሰናል፡፡
3. የንብረት አገልግሎቱ መብት የሚገኘው ደንቡን መሰረት በማድረግ ተቆጣጣሪው አካል በሚያጸድቀው ሁኔታ ብቻ ነው፡፡
4. ማንኛውም የንብረት አገልግሎት መብት ያገኘ ሰው በተቆጣጣሪው አካል የጸደቁትን የንብረት አገልግሎቱ የተመሰረተባቸውን ሁኔታዎች ሊለውጥ ወይም ሊያሻሽል አይችልም።
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የንብረት አገልግሎት ሰጪው መሬት ባለይዞታ የንብረት አገልግሎት ጥቅም ከሚያገኘው ሰው ተገቢ ካሣ የማግኘት መብት አለው፡፡

24.<u>የንብረት አገልግሎት መቋረጥ</u>

የንብረት አገልግሎት መብት ከዚህ በታች በተጠቀሱት ምክንያቶች ይቋረጣል፣

1. ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣው ደንብ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ወስጥ የንብረት አገልግሎቱ መብት በተሰጠው ሰው ወይም በወራሹ ወይም በተተኪው ተግባራዊ አለመደረጉን የንብረት አገልግሎት ሰጪው መሬት ባለይዞታ ለተቆጣጣሪው አካል ያስረዳ እንደሆነ መብቱ ቀሪ ይሆናል፡፡
2. በመብቱ መጠቀም ያልተቻለው ከአቅም በላይ በሆነ ኃይል ምክንያት መሆኑን ባለመብቱ ለተቆጣጣሪው አካል ማስረዳት የቻለ እንደሆነ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

<u>ክፍል ሰባት</u>

<u>ስለ ውሃ አካላት ዳርቻዎችና ስለ ውሃ ጉጂ ገጽታዎች</u>

25.<u>የውሃ አካላት ዳርቻዎችን ስለመጠበቅ</u>

ተቆጣጣሪው አካል አግባብ ካለው የመንግሥት አካል ጋር በመመካከር እና በመተባበር

1. የተወሰኑ የውሃ አካላት ዳርቻዎችን ወሰን መከለል፣
2. በተከለሉ የውሃ አካላት ዳርቻዎች ክልል ውስጥ ያሉ የዕጽዋት ሽፋኖች ወይም ዛፎች እንዳይመነጠሩ ወይም እንዳይቆረጡ እንዲሁም የመኖሪያ ቤቶች እንዳይገነቡ መከልከል ይችላል፡፡ ዝርዝሩ በሚኒስቴሩበሚወጣው መመሪያ መሰረት ይወሰናል፡፡

26.<u>የውሃ ጎጂ ገጽታዎችን ስለመቆጣጠር</u>

አግባብ ያላቸው የመንግስት አካላት፣ ከተሞች እንዲቆረቆሩ ወይም መንደሮች እንዲመሠረቱ ከማድረጋቸው በፊት በጐርፍና ሌሎችም ከውሃ ጋር በተያያዙ ምክንያቶች ሊደርሱ የሚችሉ ጉዳቶችን ተጽዕኖዎችን ወይም አደጋዎችን ለመከላከል ወይም ጉዳቶቹ፣ ተጽዕኖዎቹ ወይም አደጋዎቹ እንዳይደርሱ ለማድረግ እንዲቻል ከተቆጣጣሪው አካል ሙያዊ ምክር መጠየቅ አለባቸው።

## ክፍል ስምንት

## ስለውሃ ተገልጋዮች ማኅበራት

27.አደረጃጀት

1. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተቆጣጣሪው አካል አግባብነት ካላቸው የመንግስት አካላት ጋር በመመካከር ውሃን ጠቀሜታ ላለው ግልጋሎት ለማዋል የውሃ ተጠቃሚዎች ማኅበራት እንዲቋቋሙ ያበረታታል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1 እንደተጠበቀ ሆኖ የውሃ ተገልጋዮች ማኅበራት በተጠቃሚዎቹ አነሳሽነት እና ፈቃደኝነት ሊቋቋሙ ይችላሉ፡፡
3. የውሃ ተግልጋዮች ማኅበራት አደረጃጀት ዝርዝር አፈጻጸም ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣው ደንብ መሰረት ይሆናል፡፡
4. ስለማኅበራቱ አደረጃጀት አግባብነት ያላቸው የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ።

## ክፍል ዘጠኝ

## የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

28.የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

1. ይህ አዋጅ ከመውጣቱ፣ በፊት በማንኛውም የመንግሥት አካል በተሰጠ ፈቃድ ወይም ያለፈቃድ፣
   
   ሀ) የውሃ ሥራዎችን ግንባታ ያካሄደ ወይም የሚያካሄድ፣
   
   ለ) በውሃ ሀብት ራሱ በመጠቀም ወይም ለሌሎች ሰዎች ውሃን በማቅረብ ላይያለ፣
   
   ሐ) ቆሻሻን በውሃ ሀብት ውስጥ በመልቀቅ ወይም በመድፋት ላይ ያለ፤
   
   ማንኛውም ሰውይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚወጣው ደንብ ከሚጸናበት ቀን ጀምሮ በ12 ወራት ጊዜ ውስጥ በውሃ ሥራዎቹ ወይም በውሃው መጠቀም ለመቀጠል ወይም ቆሻሻን በውሃ አካላት ውስጥ ለመልቀቅ ወይም ለመድፋት ፈቃድ እንዲሰጠው ለተቆጣጣሪው አካል ማመልከት አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ፈቃድ እንዲሰጠው የሚጠይቅ አመልካች ለተጠቀሱት ተግባራት ፈቃድ ለማግኘት ሊያሟላ የሚገባው ቅድመ ሁኔታና ሊያቀርብ የሚገባው መረጃ አዋጁን ለማስፈጸም በሚወጣጡ ደንብ በሚወሰነው መሠረት ይሆናል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ያላመለከተ የውሃ ሀብት ተጠቃሚ በተመደበው መደበኛ የፈቃድ አገልግሎት ክፍያ ላይ 50 ፐርሰንት (ሃምሣ በመቶ) መቀጫ ከፍሎ በሚቀጥሉት 60 ቀናት ውስጥ ሊያመለክት ይችላል፡፡
4. ተጠቃሚው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ወይም ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት ያላመለከተ እንደሆነ ተቆጣጣሪው አካል፣ በውሃ ሀብቱ እንዳይገለገል ሊያግደው ይችላል፡፡
5. ተቆጣጣሪው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (3) መሠረት ማመልከቻው ሲቀርብለት የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም አዋጁን ለማስፈጸም የሚወጣውን ደንብ በግልጽ የማይቃረን እስከሆነ ድረስ የጠየቀውን ፈቃድ በ60 ቀናት ውስጥ ይሰጣል፣ ማመልከቻው የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም አዋጁን ለማስፈጸም የሚወጣውን ደንብ የሚቃረን ከሆነ በዚህ ንዑስ አንቀጽ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ማመልከቻው ውድቅ መደረጉንና ምክንያቶቹን በጽሁፍ ለአመልካቹ ያስታውቃል፡፡
6. ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በማንኛውም የመንግሥት አካል በተሰጠው የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መሠረት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 19 በተመለከተው የሙያ መስክ የተሰማራ ማንኛውም ሰው ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚወጣው ደንብ ከሚጸናበት ቀን ጀምሮ በስልሣ ቀናት ውስጥ ተቆጣጣሪው አካል ዘንድ ቀርቦ መመዝገብ እና የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መያዝ አለበት፡፡
7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) መሠረት አመልካቹ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት ሊያሟላው የሚገባው ቅድመ ሁኔታና ሊያቀርብ የሚገባው መረጃ አዋጁን ለማስፈጸም በሚወጣው ደንብ በሚወሰነው መሠረት ይሆናል፡፡
8. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ቀርቦ ባላመለከተ ሰው ላይ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ድንጋጌ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
9. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ካላመለከተ ቀድሞ የተሰጠው የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንደተሰረዘ ይቆጠራል።

29.<u>ስለቅጣት</u>

ይህን አዋጅ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጣውን ደንብ የተላለፈ ማንኛውም ሰው፣ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በተደነገገው መሠረት ይቀጣል፡፡

30.<u>ደንብ የማውጣት ሥልጣን</u>

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ለማስፈጸም የሚረዳ ዝርዝር የአፈጻጸም ደንብ ያወጣል።

31.<u>መመሪያዎች</u>

ሚኒስትሩ ይህን አዋጅ ተግባራዊ ለማድረግ የሚረዱ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

32.<u>ስለተሻሩና ተፈጻሚ ስለማይሆኑ ሕጐች</u>

1. የውሃ ሀብት አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 92/1986 በዚህ አዋጅ ተሽሯል።
2. ይህን አዋጅ የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ የተሸፈኑትን ጉዳዮች በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖረውም፡

33.<u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከየካቲት 30 ቀን 1992 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**አዲስ አበባ የካቲት 30 ቀን 1992 ዓ.ም**

**ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ**

**ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**ደንብ ቁጥር 115/1997**

**ስለውሃ ሀብት አስተዳደር የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 4/1987 አንቀጽ 5 እና በኢትዮጵያ የውሃ ሀብት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 197/1992 አንቀጽ 30 መሰረት ይህን ደንብ አዉጥቷል።

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ**

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ የውሃ ሀብት አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 115/1997" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

   1. በኢትዮጵያ የውሃ ሀብት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 197/1992 ለተዘረዘሩት ቃላት የተሰጡት ትርጓሜዎች በተመሳሳይ ሁኔታ በዚህ ደንብ ላይም ተፈጻሚ ይሆናሉ።
   2. "ፖሊሲ" ማለት የኢትዮጵያ የውሃ ሀብት አስተዳደር ፖሊሲ ነው፡፡
   3. "አዋጅ" ማለት የኢትዮጵያ የውሃ ሀብት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 197/1992 ነው።
   4. "የውሃ ጉድጓድ" ማለት በእጅ ከሚቆፈሩ የውሃ ጉድጓዶች በስተቀር ለተለያዩ አገልግሎቶች የተለያዩ መሣሪያዎችን (ሪግ) በመጠቀም የከርሰ ምድር ውሃ አመንጪ ወይም አስተላላፊ አካሎችን በመዝለቅ የሚቆፈር ጉድጓድ ነው።
   5. "የውሃ አቅርቦት ጉድጓድ" ማለት ለመጠጥ ለእርሻም ሆነ ለኢንዱስትሪ ወይም ለሌሎች ግልጋሎቶች የሚቆፈር ጉድጓድ ነው።
   6. "የውሃ አጠቃቀም" ማለት ውሃን ለመጠጥ፣ ለመስኖ ለእርሻ፣ ለኢንዱስትሪ ፥ ለኃይል ምንጭነት፡ ለትራንስፖርት፣ ለቱሪዝም፣ ለእንስሳት እርባታ ለዓሣ ማስገር ወይም ለሌሎች ግልጋሎቶች መጠቀም ማለት ነው።
   7. "ተቆጣጣሪ አካል" ማለት የውሃ ሀብት ሚኒስቴር[34]ወይም በአዋጁ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ከሚኒስቴሩ ውክልና የተሰጠው አካል ነው።

[34] በ25/08 (2011)አ. 1097 አንቀጽ 9(11) መሰረት የውሃ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር ሆኗል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የውሃ ሀብት አጠቃቀም

### 3. የፈቃድ ማመልከቻ

በአዋጁ አንቀጽ 13 ድንጋጌ መሠረት በውሃ ሀብት ለመጠቀም ፈቃድ እንዲሰጥ ለተቆጣጣሪ አካል የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፣

ሀ) የአመልካቹን ስምና ቋሚ አድራሻ፣

ለ) የውሃ ሀብቱ የሚገኝበትንና ጥቅም ላይ የሚውልበትን ክልል ልዩ ቦታ፣

ሐ) የውሃ ሀብቱ ጥቅም ላይ እንዲውል የታቀደበት የግልጋሎት ዓይነት፣

መ) በየወሩና በየዓመቱ ሊወሰድ የታቀደው የውሃ መጠን፣

ሠ) በምን ዓይነት ዘዴ ወይም ሁኔታ ውሃን ወስዶ ለመጠቀም እንደታቀደ፣

ረ) እንደአግባቡ የኢንቨስትመንት ሠርቲፊኬት፣

ሰ) ተቆጣጣሪው አካል ያስፈልጋሉ ብሎ የሚጠይቃቸው ዝርዝር ጥናቶችና ካርታዎች፣

### 4. የተቆጣጣሪው አካል ተግባራት

1. በውሃ ሀብት የመጠቀም ፈቃድን የሚመለከት ማመልከቻ ተቆጣጣሪው አካል ሲደርሰው ማመልከቻው የደረሰው መሆኑን ወዲያውኑ ለአመልካቹ በጽሑፍ ያረጋግጣል፣
2. ተቆጣጣሪው አካል በውሃ ሀብት ለመጠቀም ፈቃድ ለማግኘት የቀረበ ማመልከቻን በሚያይበት ጊዜ፣ በአመልካቹ የቀረበው በውሃ ሀብት የመጠቀም ጥያቄ ፖሊሲውን፣ የተፋሰስ ማስተር ፕላኖችን፣ አዋጁን፥ ይህ ደንብ እና መመሪያዎችን መሠረት ያደረገ መሆኑን ያረጋግጣል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ተቆጣጣሪው አካል የቀረበውን ማመልከቻ አስመልክቶ የሚሰጠውን ውሣኔ ለአመልካቹ ማስታወቅ አለበት፡፡
4. ተቆጣጣሪው አካል በውሃ ሀብት የመጠቀም ማመልከቻን አስመልክቶ የሰጠውን ውሣኔ፣ በአዋጁ አንቀጽ 10 (2) መሠረት መዝግቦ መያዝ አለበት፡፡

### 5. ጥቅም ላይ የዋለ ውሃን ስለመልቀቅ

የአዋጁ አንቀጽ 13)2 እና የዚህ ደንብ አንቀጽ 11 እንደተጠበቁ ሆነው በውሃ የመጠቀም ፈቃድ ጥቅም ላይ የዋለ ውሃን በአግባቡ አክሞ ወደ ውሃ ሀብት የመልቀቅ መብትን ጨምሮ ሊሰጥ ይችላል፡፡

6. **በዉሃ የመጠቀም ፍቃድን ስለመሰረዝ፣ማገድ፣ማስተላለፍና መለወጥ**

1. በአዋጁ አንቀጽ 17 መሠረት በውሃ የመጠቀም ፈቃድ በተቆጣጣሪው አካል በሙሉ ወይም በከፊል ሊታገድ ወይም ሊሰረዝ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ፈቃዱን በሙሉ ወይም በከፊል ሊያሳግዱ የሚችሉ ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡
   ሀ) በፈቃዱ ውስጥ የተጠቀሱትን ገደቦችና ግዴታዎች አለመጠበቅ ወይም አለማክበር፤
   ለ) ከተፈቀደ አገልግሎት ውጪ በውሃ መጠቀም፤
   ሐ) የውሃ ግልጋሎት ዋጋ ማስታወቂያ በደረሰ በስድሳ (60) ቀናት ውስጥ የውሃ ግልጋሎት ዋጋ ያለመክፈል።
   መ) የውሃ ሀብቱ ጊዜያዊ በሆነ መልክ እየመነመነ መሆኑን ተቆጣጣሪው አካል ሲደርስበት፤
   ሠ) የውሃ ጥራት ደረጃዎችን አለመጠበቅ፤
3. ተቆጣጣሪው አካል ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ምክንያቶች የሰጠውን ፈቃድ ሊሰርዝ ይችላል፤
   ሀ) በፈቃድ ውስጥ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ በተፈቀደው ውሃ በገዛ ፈቃድ ሳይጠቀሙ መቅረት፤
   ለ) ተቆጣጣሪው አካል ሳይፈቀድ በውሃ የመጠቀም ፈቃድን ለሌላ ሰው ማስተላለፍ፤
   ሐ) ባለፈቃዱ ፈቃዱን ሊያገኝ የቻለው የሀሰት ማስረጃ በመስጠት መሆኑ በተቆጣጣሪው አካል ሲረጋገጥ፤
   መ) የውሃ ሀብቱ ዘለቄታዊ በሆነ መልክ እየመነመነ መሆኑን ሲያረጋግጥ፤
   ሠ) የባለፈቃዱ የውሃ አጠቃቀም በአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ አዋጅ ቁጥር 299)1995 በተደነገጉት ድንጋጌዎች መሠረት በአካባቢው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳደሩ ሲረጋገጥ፤
4. ተቆጣጣሪው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ከተዘረዘሩት ምክንያቶች ማናቸውም መፈጸማቸውን ሲያረጋግጥ ለፈቃድ ያገዙ በሚሰጠው የአሥራ አምስት ቀናት የጽሑፍ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ውስጥ ባለፈቃዱ ሁኔታውን በማስረጃ ካላስተባበለ በስተቀር ፈቃዱን በከፊል ወይም በሙሉ ሊያግድ ይችላል፡፡

5. ተቆጣጣሪው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3(ሐ) ከተመለከተው ምክንያት በስተቀር በንዑስ አንቀጽ 3 (ሀ) (ለ) (መ) ወይም (ሠ) የተዘረዘሩት ምክንያቶች መፈጸማቸውን ሲያረጋግጥ ለፈቃድ ያገዞ፡ በሚሰጠው የአሥራ አምስት ቀናት የጽሑፍ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ውስጥ ባለፈቃዱ ሁኔታውን በማስረጃ ካላስተባበለ በስተቀር ፈቃዱን ሊሰርዝ ይችላል፡፡
6. በውሃ የመጠቀም ፈቃድ እንዲለወጥለት ወይም በሙሉ ወይም በከፊል እንዲተላለፍለት ፈቃድ ያገዞ ለተቆጣጣሪው አካል ሊያመለከት ይችላል፡፡ ማመልከቻውም በውሃ የመጠቀም ፈቃዱ እንዲለወጥ ወይም እንዲተላለፍ የተፈለገበትን ምክንያትና መለወጡን ወይም መተላለፉን ለመፈጸም እንዲሚሉ የሚያስፈልጉትን ሁኔታዎችና ገደቦች መግለጽ አለበት።
7. ተቆጣጣሪው አካል በዚህ አንቀጽ መሠረት የተወሰደ ማንኛውንም እርምጃ በውሃ የመጠቀም ፈቃድ መዝገብ ውስጥ እንዲመዘገብ ያደርጋል።

<u>**ክፍል ሦስት**</u>

<u>**የውሃ ሥራ ፈቃድ**</u>

7. <u>**ማመልከቻዎችና አፈጻጸማቸው**</u>
   1. የውሃ ሥራዎች የመሥራት፣ የማደስ ወይም የመለወጥ ፈቃድን የሚመለከት ማመልከቻ ለተቆጣጣሪው አካል መቅረብ አለበት፡፡
   2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚቀርበው ማመልከቻ የውሃ ሥራውን ዲዛይን፣ ደህንነትና አደጋ አልባነትን ያካተተ ሙሉ ዝርዝር ጥናት የያዘ መሆን አለበት፡፡
   3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የውሃ ሥራዎችን ለመሥራት ለማደስ ወይም ለመለወጥ በሚቀርቡ ጥያቄዎች ላይ የዚህ ደንብ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 1፣ 2፣ 3፣ እና 4 ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ።
8. <u>**ፈቃዱ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜና የሚራዘምበት ሁኔታ**</u>
   1. የውሃ ሥራዎች ፈቃድ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ የውሃ ሥራውን የአገልግሎት ዘመን ታሳቢ በማድረግ በተቆጣጣሪው አካል ይወሰናል፡፡
   2. የውሃ ሥራውን ለመሥራት በፈቃዱ ውስጥ ተወስኖ የተጠቀሰው የፈቃድ ጊዜ የውሃ ሥራውን ፕሮጀክት ባህሪ መሠረት በማድረግ በተቆጣጣሪው አካል ሊራዘም ይችላል፡፡

9. **በፈቃድ ያዡና በተቆጣጣሪዉ አካል መፈጸም ስላለባቸው ተግባራት**

1. የውሃ ሥራውን ለመሥራት በተወሰነው ወይም በተራዘመው የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲሠራ የተፈቀደው ሥራ እንደተጠናቀቀ ወይም ከመጠናቀቁ በፊት ወዲያውኑ እንደነገሩ ሁኔታ ፈቃድ ያገኙ ለተቆጣጣሪው አካል ሥራው መጠናቀቁን ወይም ይጠናቀቃል ተብሎ የሚጠበቀውን ጊዜ በጽሑፍ ማስታወቅ አለበት፡፡
2. ተቆጣጣሪው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ስለሥራው መጠናቀቅ ማስታወቂያ ሲደርሰው ሥራው የተሠራው በፈቃዱ ውስጥ በተመለከቱት ገደቦች እና ሁኔታዎች መሠረት መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

10. **በውሃ መውረጃዎች ወይም በውሃ ሥራዎች ጣልቃ ስለሚገቡ ሥራዎች**

1. ከተቆጣጣሪው አካል ፈቃድ ሳይሰጠው ማንኛውም ሰው በውሃ ጉዞ ላይ ችግር የሚያስከትል፣ የውሃ መውረጃን አቅጣጫ የሚቀይር፣ በውሃ መውረጃው የሚፈሰውን የውሃ አፈሳሰስ፣ ፍጥነትንና ኃይል የሚለውጥ ወይም የማንኛውንም የውሃ ነክ ሥራ ትክክለኛ እንቅስቃሴ የሚገታ መሰናክል ሊሰራ ወይም ሊያስቀም አይችልም።
2. ተቆጣጣሪው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የቀረበውን ማመልከቻ እንደተቀበለ በእቅዱና በሃሳቡ የታቀፈውን ሥራ ዓላማ፣ እቅዱና ሀሳቡ የሚመለከተው የውሃ መውረጃ በመስጠት ላይ ያለውን ግልጋሎት ሁኔታ የመጠበቅና የመንከባከብ አስፈላጊነትን ግምት ውስጥ በማስገባት ሥራው እንዲሠራ ሊፈቅድ ወይም ለውሃ መውረጃ ደህንነት በቂ ዋስትና ካልተሰጠ በስተቀር ላይፈቅድ ይችላል፡፡

## **ክፍል አራት**

## **የውሃ ጥራት ቁጥጥር**

11. **የታከመ ቆሻሻ ውሃ የመልቀቅ ፈቃድ**

1. በአዋጁ አንቀጽ 13(2) እና በዚህ ደንብ አንቀጽ 5 ድንጋጌዎች መሠረት ማንኛውም ሙያ ነክ ወይም ኢንዱስትሪ ነክ ፍሣሽን ወይም የተበከለ ፍሳሽን ወይም ማንኛውንም መርዛማ፣ ጐጂ ወይም በካይ ነገርን አክሞ በየብስ ውሃ ወይም በከርሰምድር ውሃ ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለመልቀቅ

የሚያስችል ፈቃድን ለማግኘት ማመልከቻ ለተቆጣጣሪው አካል መቅረብ አለበት።

2. ተቆጣጣሪው አካል ውሃ ሀብት ውስጥ የታከመ ቆሻሻ የመልቀቅ ፈቃድ ለመስጠት ወይም ለመከልከል ከሌሎች ሁኔታዎች በተጨማሪ የፍሣሽ እና የጅረት ውሃ ጥራት ደረጃን ግምት ውስጥ ያስገባል።
3. ከዚህ በላይ የተመለከቱት የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጾች እንደተጠበቀ ሆነው በዚህ ደንብ አንቀጽ 4 ውስጥ የተደነገጉት ሁኔታዎች የታከመ ቆሻሻ ለመልቀቅ ፈቃድ ለመጠየቅ በሚቀርቡ ማመልከቻዎችም ላይ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።

12.<u>የታከመ ቆሻሻ ውሃ የሚለቁ ሰዎች ግዴታ</u>

1. ማንኛውም ውሃን ለኢንዱስትሪ ወይም ብክለትን ሊያስከትል ለሚችል ማንኛውም ሥራ ወይም አገልግሎት የሚጠቀም ሰው፤
   ሀ) የቆሻሻ ማጣሪያ ዘዴዎችን ወይም መሣሪያዎችን የመትከልና የመጠቀም ግዴታ አለበት፤
   ለ) እንዲለቅ የተፈቀደለትን የታከመ ቆሻሻ ዓይነትና መጠን ብቻ መልቀቅ አለበት፤
   ሐ) ተቆጣጣሪው አካል በማናቸውም ጊዜ የሚለቀውን የታከመ ቆሻሻ ናሙና እንዲወስድ የመፍቀድ ግዴታ አለበት፣
2. የዚህን አንቀጽ ድንጋጌዎች ለማስፈፀም ሚኒስቴሩ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፣

13.<u>ታከመ ቆሻሻ የመልቀቅ ፈቃድ እድሳት</u>

1. የታከመ ቆሻሻ ወደ ውሃ ሀብት የመልቀቅ ፈቃድ በተቆጣጣሪው አካል ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በየሁለት ዓመቱ መታደስ አለበት።
2. የታከመ ቆሻሻ የመልቀቅ ፈቃድ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ከማለቁ ከአንድ ወር በፊት እንዲታደስ ፈቃድ ያገኙ ለተቆጣጣሪው አካል ማመልከት ይኖርበታል።
3. ተቆጣጣሪው አካል የታከመ ቆሻሻ የመልቀቅ የፈቃድ ማሳደሻ ማመልከቻውን በተቀበለ በአምስት ቀናት ውስጥ በማመልከቻው መሠረት ፈቃዱ ባለበት ሁኔታ መታደሱን ወይም በፈቃዱ ላይ ማሻሻያ ተደርጐ መታደሱን ወይም ማመልከቻው ውድቅ መደረጉን ለአመልካቹ በጽሑፍ ያሳውቃል።
4. ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ንዑስ አንቀጽ መሠረት ተቆጣጣሪው አካል ማመልከቻውን ውድቅ ካደረገ ወይም በፈቃዱ ላይ ማሻሻያዎች ካደረገ ውሳኔው የተመሠረተባቸውን ምክንያቶች ጨምሮ በጽሑፍ ለአመልካቹ ማሳወቅ አለበት።

5. ተቆጣጣሪው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የወሰዳቸውን ማናቸውንም ዓይነት እርምጃዎች በውሃ የመጠቀም ፈቃድ መዝገብ ውስጥ ይመዘግባል።

14.<u>የታከመ ቆሻሻ ውሃ የመልቀቅ ፈቃድ መሰረዝ ወይም መታገድ</u>

1. በአዋጁ አንቀጽ 17 ለተቆጣጣሪው አካል በተሰጠው ስልጣን የታከመ ቆሻሻ ውሃ የመልቀቅ ፈቃድን በሙሉ ወይም በከፊል ሊያሳግዱ የሚችሉ ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡
   ሀ) በፈቃዱ ውስጥ የተጠቀሱ ገደቦችና ሁኔታዎችን አለመጠበቅ ወይም አለማክበር፤
   ለ) በዚህ ደንብ አንቀጽ 12 የተደነገጉትን ድንጋጌዎች መተላለፍ፣
2. ባለፈቃዱ ፈቃዱን ሊያገኝ የቻለው የሀሰት ማስረጃ በመስጠት መሆኑ በተቆጣጣሪው አካል ሲረጋገጥ ፈቃዱ ሊሰርዝ ይችላል።
3. ተቆጣጣሪው አካል በዚህ አንቀጽ መሠረት የተወሰደ ማንኛውንም እርምጃ የታከመ ቆሻሻ የመልቀቅ ፈቃድ መዝገብ ውስጥ እንዲመዘገብ ማድረግ አለበት፡

15.<u>የውሃ አቅርቦት ጉድጓዶች የሚቆፈሩበት ቦታ</u>

የውሃ አቅርቦት ጉድጓድ የሚቆፈርበት ቦታና ሁኔታ በሚኒስቴሩ በሚወጣ መመሪያ መሠረት ይወሰናል፡፡

16.<u>የከርሰ ምድር ውሃ ጥራት ምርመራ</u>

1. የውሃ አቅርቦት ጉድጓድ ቁፋሮ ተጠናቆ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የጉድጓድ ውሃ ናሙና ሕጋዊ ፈቃድ ላለው ላቦራቶሪ ቀርቦ ለመጠጥነት የሚውል መሆኑ መረጋገጥ አለበት፡፡
2. የማንኛውም የውሃ አቅርቦት ጉድጓድ ጠረጋ ሥራ ከተካሄደ በኋላ ከጉድጓዱ እድሜ አንጻር ወይም በጠረጋው ሥራ ምክንያት በውሃው ጥራት ላይ ሊደርሱ የሚችሉ የባክቴሪዎሎጂካልና የኬሚካል ለውጦች መኖራቸውን ወይም አለመኖራቸውን ለማረጋገጥ ሕጋዊ ፈቃድ ባለው ላቦራቶሪ የውሃው ናሙና ቀርቦ ምርመራ መደረግ አለበት።

17.<u>ስለ ውሃ አቅርቦት ጉድጓዶች አያያዝ</u>

1. የውሃ አቅርቦት ጉድጓድ ውስጥ ማንኛውም በካይ ፍሳሽ ሰርጎ እንዳይገባ በጉድጓዱ ቀፎና በጉድጓዱ መካከል ያለ ክፍት ቦታ መታሸግ አለበት።

2. ማንኛውም የውሃ ጉድጓድ በቁፋሮና በግንባታ ወቅት በሚያጋጥሙ ችግሮች ሥራው ሳይጠናቀቅ ቢቀር በሰውና በእንስሳት ላይ አደጋ እንዳይደርስና የከርሰ ምድር ውሃ አዘል አካል እንዳይበክል ቁፋሪው ጉድጓዱን በጥንቃቄ መድፈን አለበት፡፡

18. <u>ዘገባ የማቅረብ ግዴታ</u>

በዚህ ደንብ በተገኘ ፈቃድ መሠረት ሥራቸው ስለተጠናቀቀ ወይም ስላልተጠናቀቀ የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ሥራዎች አፈፃፀም ቆፋሪው ሥራው ከተጠናቀቀ ወይም ከተቋረጠበት ጊዜ ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ ለተቆጣጣሪው አካል ዘገባ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

<u>ክፍል አምስት</u>

<u>ስለ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እና ስለ ደረጃ አመዳደብ</u>

19. <u>ስለውሃ ሥራዎች ግንባታ</u>

1. በማንኛውም የውሃ ሥራዎች መስክ መሰማራት የሚፈልግ ባለሙያ ከተቆጣጣሪው አካል የተሰጠ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እስከሌለው ድረስ በአዋጁ አንቀጽ 11 መሠረት የውሃ ሥራዎች ግንባታ ሥራ ማከናወን አይችልም።
2. ማንኛውም ሕጋዊ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያለው የውሃ ሥራዎች ተቋራጭ የውሃ ሥራዎች ግንባታን በተመለከተ ከማንኛውም ሰው ጋር ውል ከመፈጸሙ በፊት የውሃ ሥራው እንዲሠራ በተቆጣጣሪው አካል የተፈቀደ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡
3. የዉሃ ስራዎች ግንባታ እንዲሰራለት የሚፈልግ ማንኛዉም ሰዉ ከዉሃ ሥራዎች ተቋራጭ ጋር ዉል ከመፈፀሙ በፊት የስራ ተቋራጩ ድርጅት ህጋዊ የስራ ፈቃድ ያለዉ መሆኑን እና ባለሙያዎችም የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ያላቸዉ መሆኑንን ማረጋገጥ አለበት፡፡

20. <u>አስፈላጊዎች</u>

1. ማንኛዉም የዉሃ ስራዎች ተቋራጭ ሚኒስቴሩ በሚያወጣዉ መመሪያ ዉስጥ የሚዘረዘሩ መሳሪያዎችና ባለሙያ ያሉት ወይም የእነዚህኑ መሳሪያዎችና ባለሙያዎች አገልግሎት ሊያገኝ የሚችል መሆን አለበት፡፡

2. የዉሃ ስራዎች ተቋራጭ ለመሆን ያመለከቱ በዚህ አንቀጽ )1) መሰረት በመመሪያዉ ተዘርዝሮ የተቀመጠዉን መመዘኛ አሟልተዉ ሲገኙ በሚመጥኑት ደረጃ በተቆጣጣሪዉ አካል ይመደባል፡፡

21. **ስለደረጃ አመዳደብ**

1. ተቆጣጣሪው አካል የውሃ ሥራዎች ባለሙያ ለመሆን የቀረበ ማመልከቻን በመገምገም፣
   ሀ) አመልካቹ አዋጁ፣ ደንቡ እና መመሪያው የሚጠይቃቸውን ሁኔታዎች የሚያሟላ ሆኖ ሲያገኘው ደረጃውን በመመደብ አመልካቹ በአለው ደረጃ ለመሥራት የሚችል መሆኑን የሚያረጋግጥ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል።
   ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1)ሀ) መሠረት የቀረበ ማመልከቻን ተቆጣጣሪው አካል ሲመረምር አዋጁ፣ ደንቡና መመሪያው የሚጠይቃቸውን ሁኔታዎች የማያሟላ ሆኖ ሲያገኘው የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱን ይከለክላል፤ የከለከለበትንም ምክንያት በጽሑፍ ለአመልካቹ ያሳውቃል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የተሰጠ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱን በየዓመቱ ለተቆጣጣሪው አካል ቀርቦ መታደስ አለበት።
3. ተቆጣጣሪው አካል የሰጠውን የውሃ ሥራዎች ተቋራጭነት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱን ተቋራጩ በምስክር ወረቀቱ የተዘረዘሩ ግዴታዎችን ባለመፈፀሙ ምክንያት በማንኛውም ጊዜ ለመሰረዝ ይችላል፡፡

## ክፍል ስድስት

## ስለአማካሪነት አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት

22. **የአማካሪነት አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አስፈላጊነት**

በአዋጁ አንቀጽ 19 እንደተደነገገው ማንኛውም ሰው ከተቆጣጣሪው አካል የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳያኖረው ለንግድም ሆነ ለሌላ ዓላማ ከውሃ ሀብት ጥናት፣ ዲዛይን፣ ቁጥጥር እና ግንባታ ጋር የተያያዘ የአማካሪነት አገልግሎት ለመስጠት አይችልም።

23.<u>የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማዉጣት ስለሚቀርብ ማመልከቻ</u>

የአማካሪነት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማውጣት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በሚኒስትሩ በሚወጣ መመሪያ መሠረት የሚጠየቁ አግባብ ያላቸው መረጃዎችን የያዘ ማመልከቻ ለተቆጣጣሪው አካል ማቅረብ አለበት።

24.<u>የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለመስጠት</u>

በዚህ ደንብ አንቀጽ 23 መሠረት ለተቆጣጣሪው አካል ማመልከቻ በደረሰው አስር ቀናት ውስጥ አመልካቹ በመመሪያ የወጣውን ደረጃ ያሟላ መሆኑን በመገምገምና ብቁነቱን በማረጋገጥ የተጠየቀውን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል ወይም ማመልከቻውን ያልተቀበለው ከሆነ ያልተቀበለበትን ምክንያት በጽሑፍ ለአመልካቹ ያሳውቃል።

25.<u>ስለ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እድሳት</u>

1. የአማካሪነት አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በተቆጣጣሪው አካል በተሰጠ በየአመቱ መታደስ አለበት።
2. ተቆጣጣሪው አካል የእድሳት ጥያቄ ሲቀርብለት የአማካሪ አገልግሎቱ የሚጠበቅበትን ግዴታ አክብሮና ደረጃውን ጠብቆ የሠራ መሆኑን አረጋግጦ የምስክር ወረቀቱን ያድሳል፡፡
3. ተቆጣጣሪው አካል የምስክር ወረቀት እድሳት ጥያቄውን ያልተቀበለው ከሆነ ያልተቀበለበትን ምክንያት በአስር ቀን ውስጥ በጽሑፍ ለአመልካቹ ያሳውቃል።

26.<u>ስለ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ክፍያ</u>

የአማካሪነት አገልግሎት የምስክር ወረቀት ለማውጣትና ለማሳደስ የሚደረገው ክፍያ በሕግ በሚወሰነው መሠረት ይሆናል፡፡

27.<u>ስለ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መሰረዝ</u>

1. ተቆጣጣሪው አካል የአማካሪነት ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከሚከተሉት ምክንያቶች ባንዱ ሊሰርዝ ይችላል፡፡

   ሀ) የምስክር ወረቀቱ የተሰጠው ሀሰተኛ መረጃ በማቅረብ መሆኑ ሲረጋገጥ፤

   ለ) የአማካሪነት አገልግሎቱ የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች እና ይህን ደንብ ለማስፈጸም የወጡ መመሪያዎችን ባለማክበሩ በተቆጣጣሪው አካል የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በተሰጠው የአንድ ወር የጊዜ ገደብ ውስጥ ጉድለቶቹን ያላስተካከለ ከሆነ፤

2. የምስክር ወረቀት የተሰረዘበት ወይም ሥራውን ያቋረጠ ማንኛውም የአማካሪነት አገልግሎት ሰጪ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱን ለተቆጣጣሪው አካል መመለስ አለበት፡፡

## ክፍል ሰባት

## የውሃ ተገልጋዮች ማህበራት

### 28.ስለ ማህበሮች መቋቋም

1. በአዋጁ አንቀጽ 27/2 መሠረት በውሃ የመጠቀም ፈቃድ ያላቸው ወይም ከፍቃድ አስፈላጊት ነጻ የሆኑ ሰዎች የውሃ ተገልጋዮች ማህበር ማቋቋም ይችላሉ፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት በሚቋቋሙ የውሃ ተገልጋዮች ማኅበራት ላይ የኅብረት ሥራ ማኅበራት አዋጅ ቁጥር 147/1991[35] ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

### 29.ስለማኅበራት ምዝገባ

1. የሚቋቋመው የውሃ ተገልጋዮች ማኅበር የመለስተኛ ወይም ከፍተኛ መስኖ ልማትን የሚመለከት ከሆነ በተቆጣጣሪው መመዝገብ አለበት፡፡
2. የሚቋቋመው የውሃ ተገልጋዮች ማኅበር የአነስተኛ መስኖ ልማትን የሚመለከት ከሆነ በክልሉ ወይም በከተማ መስተዳድሩ የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ለማደራጀት በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል መመዝገብ አለበት፡፡
3. በየክልሉ ወይም በከተማ መስተዳድር ደረጃ የኅብረትሥራ ማኅበራትን ለማደራጀት በሕግ ሥልጣን የተሰጣቸው አካላት የውሃ ተገልጋዮች ማኅበራትን የሚመለከቱ መረጃዎችን ለተቆጣጣሪው አካል የማስተላለፍ ግዴታ አለባቸው፡፡

## ክፍል ስምንት

## ስለፈቃድ ክፍያ እና የውሃ ግልጋሎት ዋጋ

### 30.ስለፈቃድ አገልግሎት ክፍያ

በአዋጁ እና በዚህ ደንብ መሠረት የሚሰጡ ፈቃዶችን ለማግኘትና እነዚሁ ፈቃዶች እንዲታደሱ፣ እንዲሠረዙ ፡እንዲለወጡ ወይም እንዲተላለፉ ማመልከቻዎች ሲቀርቡ በዚህ ደንብ በሠንጠረዥ 1 ላይ የተወሰኑ የአገልግሎት ክፍያዎች ለተቆጣጣሪው አካል መክፈል አለባቸው፡፡

---

[35] በ23/7 (2009) አ. 985 ተሻረ፡፡

## 31.ስለ ውሃ አገልግሎት ዋጋ

1. በአዋጁ እና በዚህ ደንብ መሠረት የውሃ ሀብትን ለማንኛውም ለተፈቀደ ግልጋሎት ለማዋል የውሃ ግልጋሎት ዋጋ ለተቆጣጣሪው አካል መከፈል አለበት፡
2. በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚከፈሉ የውሃ አገልግሎት ዋጋዎች በተቆጣጣሪው አካል ተተምነው በክፍያ መጠየቂያ በዓመት አንድ ጊዜ ወይም እንደ ሁኔታው ከዚህ ባጠረ ጊዜ ውስጥ መከፈል አለባቸው።
3. የውሃ አገልግሎት ዋጋ በዋጋ መጠየቂያ ማስታወቂያ ውስጥ ከሚጠቀሰው ቀን ጀምሮ በ60 ቀናት ውስጥ መከፈል አለበት፡፡
4. የውሃ አገልግሎት ዋጋ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ይወሰናል፡፡

## 32.በውሃ ሀብት ውስጥ የታከመ ቆሻሻን ለመልቀቅ ወይም ለመድፋት ስለሚደረግ ክፍያ

1. በአዋጁ እና በዚህ ደንብ መሠረት በውሃ ሃብት ውስጥ የታከመ ቆሻሻን ለመልቀቅ ወይም ለመድፋት ፈቃድ የተሰጣቸው ሰዎች በሕግ የተወሰነ ክፍያ ለተቆጣጣሪው አካል መክፈል አለባቸው።
2. በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚከፈሉ ክፍያዎች በየዓመቱ በክፍያ መጠየቂያ ማስታወቂያ ውስጥ ከሚጠቀሰው ቀን ጀምሮ በ60 ቀናት ውስጥ መከፈል አለባቸው፡፡

## 33.ከመንግሥት ፕሮጀክት ለተወሰደ ውሃ ስለሚፈጸሙ ክፍያዎች

1. በዚህ ደንብ በተሰጠ ፈቃድ መሠረት ከመንግሥት ፕሮጀክት ለተወሰደ ውሃ የሚከፈለው ክፍያ መዋዕለ ወጪውን ተመላሽ በማስደረግ መሠረት ሂሣብ ላይ ተመሥርቶ በተቆጣጣሪው አካል በሚሰላ ተመን መሠረት ይሆናል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚከፈሉ ክፍያዎች በየዓመቱ በክፍያ መጠየቂያ ማስታወቂያ ውስጥ ከሚጠቀሰው ቀን ጀምሮ በ60 ቀናት ውስጥ መከፈል አለባቸው፡፡

## 34.የውሃ ግልጋሎት ዋጋን ሳይፈጽሙ መቅረት ስለሚያስከትለው ውጤት

ተቆጣጣሪው አካል የውሃ ግልጋሎት ዋጋ መከፈል ከነበረበት የመጨረሻ ቀን ጀምሮ በሚቆጠር ሥልሣ (60) ተጨማሪ የችሮታ ቀናት ውስጥ ካልተከፈለ የውሃውን አገልግሎት ማቋረጥ ይችላል፡፡

## ክፍል ዘጠኝ

## ስለ ክርክሮች አወሳሰን

### 35.ስለክርክር አወሳሰን ሥነሥርዓት

1. በአዋጁ አንቀጽ 9 (1) መሠረት ከፈቃድ ጋር የተያያዙ መብቶችን ወይም ግዴታዎችን በተመለከተ በባለፈቃዶች መካከል ወይም በባለፈቃድና በሦስተኛ ወገኖች መካከል የሚነሱ ማናቸውም ክርክሮች የሚታዩበትና የሚወሰኑብት ሥነ-ሥርዓት እንደሚከተለው ይሆናል፡-
   ሀ) አቤት ባዩ የክርክሩን ፍሬ ሃሣብና ማስረጃውን በማመልከቻ ለተቆጣጣሪው አካል ያቀርባል፡፡ ማመልከቻው የአቤት ባዩን ቅሬታና እንዲሰጥለት የሚፈልገውን ውሣኔ መግለጽ አለበት፡፡
   ለ) ተቆጣጣሪው አካል ማመልከቻውን እንደተቀበለ ተከሣሹ መጥሪያና የማመልከቻ ቅጂ እንዲደርሰው ያደርጋል፡፡ ክርክር የሚሰማበትን ጊዜና ቦታም ለሁለቱም ወገኖች ያሳውቃል፡፡
   ሐ) ባለጉዳዮቹ በቀጠሮ ሰዓትና ቦታ ተገኝተው ጉዳያቸውን ለተቆጣጣሪው አካል ያስረዳሉ፤ ማስረጃዎችንም ያቀርባሉ፡፡ ተቆጣጣሪው አካልም የቀረቡለትን ማስረጃዎች ይመዘግባል፡፡ ተቆጣጣሪው አካል ጉዳዩ በሌላ ጊዜና ቦታእንዲታይ በቀጠሮሊያስተላልፍ እንዲሁም በመጀመሪያውም ሆነ ከዚህ በኋላ በተያዘው ቀጠሮ ከባለጉዳዮቹ አንዱ በሌለበት ጉዳዩን ማየት ሊቀጥል ይችላል፡፡
   መ) ተቆጣጣሪው አካል በጉዳዩ ላይ የሰጠውን ውሣኔ ባለጉዳዮቹ እንዲያውቁት ማድረግና ለእያንዳንዱ ባለጉዳይ የውሣኔውን መዝገብ ግልባጭ መስጠት አለበት፡፡
   ሠ) የዚህ ንዑስ አንቀጽ ሌሎች ድንጋጌዎች እንዲጠበቁ ሆነው በመጀመሪያ ደረጃ የማየት ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት በሚታዩ የፍትሐብሔር ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚ የሚሆኑ የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎችበተቆጣጣሪው አካል ዘንድ በሚታዩ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡
2. ተቆጣጣሪው አካል የቀረቡለትን ክሶች የክርክሩን ሂደትና የሰጣቸውን ውሣኔዎች መዝገቦ ይይዛል፡፡

**36.ስለ ሽምግልና ዳኝነት**

1. በአዋጁ አንቀጽ 9(4) ላይ በተደነገገው መሠረት በተቆጣጣሪው አካልና በባለፈቃዱ መካከል የተፈጠረ አለመግባባት በ60 ተከታታይ ቀናት ውስጥ በጋራ ውይይት ሊፈታ ካልቻለ አንደኛው ወገን ልዩነቶቹ ወይም አለመግባባቶቹ በሽምግልና ዳኞች እንዲታዩለቱ መጠየቅ ይችላል፡፡ይኸውም፡-
   ሀ) እያንዳንዱ ወገን ሁለት የግልግል ዳኞች በመምረጥ ለሌላኛው ያሳውቃል፤
   ለ) በሁለቱ ወገኖች የተመረጡት የግልግል ዳኞች ሰብሳቢ የሚሆን ሦስተኛ የግልግል ዳኛ ይመርጣሉ። በስምምነት ሰብሳቢውን መምረጥ ካልቻሉ አፈጻጸሙ በኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሕግ በተደነገገው መሠረት ይሆናል፣
   ሐ) የሽምግልና ዳኞች አግባብነት ባላቸው የፌዴራልና የክልል ሕጎች ይመራሉ፣
   መ) ተከራካሪዎቹ በሽምግልና ዳኞች የሚጠየቁትን መረጃዎች የማቅረብና የመተባበር ግዴታ አለባቸው፤
   ሠ) በሽምግልና ዳኞች የተወሰነበት አካል ውሣኔውን የመቀበል ግዴታ አለበት፡ ሆኖም መብቱ ለሚፈቅድለት ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. የሽምግልና ዳኝነቱ የሚካሄድበትና ውሳኔ የሚሰጥበት ቦታ የተቆጣጣሪው አካል ዋና መ)ቤት በሚገኝበት ከተማ ይሆናል።
3. ለሽምግልና ዳኞች አስፈላጊ የሆኑ ወጪዎችን ግራ ቀኞቹ በጋራ የመሸፈን ግዴታ አለባቸው፤
4. በዚህ አንቀጽ ያልተሸፈኑ ጉዳዮችን አስመልክቶ የኢትዮጵያ ፍትሐብሔር ሕግ እና የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

**ክፍል አሥር**

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

**37.*መረጃዎችን የመጠየቅ ሥልጣን***

ተቆጣጣሪው አካል ከዚህ በታች የተመለከቱት ሰዎች በያዙት ፈቃድ መሠረት ወይም ሕጉ በሚያዘው መሠረት ስለሚያካሂዱት ተግባር መረጃ እንዲሰጡት በዝርዝር ሊጠይቅ ይችላል፡፡

እነዚህም፡-

ሀ) በዚህ ደንብ ክፍል 2 ፣ 3፣ 4፣ 5 ፣ 6 እና 7 ድንጋጌዎች መሠረት ፈቃድ የያዘ ሰው፣ ወይም

ለ) በአዋጁ አንቀጽ 12 መሠረት የውሃ ጉድጓድ የሚቆፍር ወይም ከዚሁ ጉድጓድ ውሃ የሚወስድ ማንኛውም ሰው፡፡

38. <u>የመግባት ፣ የመመርመርና ናሙናዎችን የመውሰድ ሥልጣን</u>

ተቆጣጣሪው አካል የፈቀደለት ወይም ሥልጣን የሰጠው ማንኛውም ሰው ሥልጣኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ በመያዝ በማንኛውም መሬት ወይም ቦታ ተገኝቶ፣

ሀ) የአዋጁና የደንቡ ድንጋጌዎች እንደዚሁም በተሰጠው ፈቃድ ውስጥ የተዘረዘሩት ገደቦችና ሁኔታዎች የተጠበቁ መሆኑን ለመከታተል፣

ለ) የውሃ ጥራት ሁኔታዎችን ለመመርመርና ለማጥናት፣

ሐ) ለአዋጁና ለዚህ ደንብ ዓላማዎች አስፈላጊ የሆኑ ማንኛቸውንም መሣሪያዎች ለመትከል ለመጠገን ለማንበብ ወይም ለመፈተሽ፣

መ) በውሃ ጉድጓድ ውስጥ ተቆፍረው የወጡትን ነገሮች ለመመርመር፣

ሠ) በማንኛውም ዓይነት ዘዴ የተወሰደውን ወይም ሊወሰድ የሚችለውን የውሃ መጠን ለማረጋገጥ፣

ረ) በዚህ ደንብ መሠረት የተያዙ መዝገቦችን ለመመርመር፣

ሰ) የማንኛውንም ውሃ ናሙና ወይም ፍሳሽ ወይም የውሃ ጥራትን ሊነካ ይችላል ብሎ የሚገመተውን ማንኛውንም ነገር ለመውሰድ፣ ሥልጣን ይኖረዋል።

39. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ ከመጋቢት 20 ቀን 1997 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መጋቢት 20 ቀን 1997 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ**

**ሪፑብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**ሠንጠረዥ 1**

**የፈቃድ አገልግሎት በክፍያ ተመን**

| ተ.ቁ. | የፈቃድ አገልግሎት | ተመን |
|---|---|---|
| 1 | የውሃ ባለሙያዎች የምስክር ወረቀት ለማውጣት | 60.00 |
| 2 | የውሃ ኮንስትራክሽን ባለሙያ የምስክር ወረቀት ለማውጣት | 67.00 |
| 3 | የዲዛይን የረዥም ጊዜ ባለለምድ ባለሙያ የምስክር ወረቀት ለማውጣት | 85.00 |
| 4 | የአማካሪነት አገልግሎት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማውጣት | 151.00 |
| 5 | የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ እና)ወይም ጠረጋ ሥራ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት | 72.00 |
| 6 | የውሃ ሥራዎች ተቋራጭነት የብቃት ምስክር ወረቀት ለማውጣት | 162.00 |
| 7 | የታከመ ቆሻሻ ወደ ውሃ አካል ለመልቀቅ ፈቃድ ለማውጣት | 81.00 |
| 8 | የውሃ ለመጠቀም ፈቃድ ለማውጣት | 87.00 |
| 9 | የውሃ ሥራዎችን ለመሥራት ወይም ለመለወጥ | 94.00 |
| 10 | ባልቃ ገብ ሥራዎችን መስራት ወይም ለመለወጥ | 88.00 |
| 11 | በውሃ ለመጠቀም የተሰጠ ፈቃድን ለማስረዝ፣ ለማስተላለፍ ወይም ለመለወጥ | 55.00 |
| 12 | የውሃ ሥራዎችን ለመስራት ወይም ለመለወጥ የተሠጠ ፈቃድን ለማራዘም፣ ለማሰረዝ፣ ለማስተላለፍ ወይም ለመለወጥ | 54.00 |
| 13 | ቆሻሻን ወደ ውሃ አካል ለመልቀቅ የተሠጠ ፈቃድን ለመለወጥ ወይም ለማሠረዝ | 41.00 |
| 14 | የውሃ ተጠቃሚዎች ማኅበራት እውቅና ለማግኘት | 54.00 |
| 15 | የውሃ ባለሙያ የምስክር ወረቀት ለማደስ | 44.00 |
| 16 | የውሃ ኮንስትራክሽን ባለሙያ የምስክር ወረቀት ለማደስ | 52.00 |
| 17 | የዲዛይን የረዥም ጊዜ ልምድ ባለሙያ የምስክር ወረቀት ለማደስ | 74.00 |

| የፍትህ ሚኒስቴር | | |
|---|---|---|
| 18 | የአማካሪነት አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማደስ | 91.00 |
| 19 | የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ እና ወይም ጠረጋ ሥራ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማደስ | 63.00 |
| 20 | የውሃ ሥራዎች ተቋራጭነት የብቃት ምስክር ወረቀት ለማደስ | 102.00 |
| 21 | የታከመ ቆሻሻ ወደ ውሃ አካል ለመልቀቅ የተሠጠ ፈቃድን ለማደስ | 74.00 |

## አዋጅ ቁጥር 315/1995

## የዓሣ ሀብት ልማትና አጠቃቀም አዋጅ

ኢትዮጵያ ለምግብና ለኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የሚውል የዓሣ ሀብት ክምችት ያላት ሀገር በመሆኗ፣

ይህ የሀገሪቱ የዓሣ ሀብት ትኩረት ተሰጥቶት እንዲለማና በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ በማስፈለጉና ቀደም ሲል የወጣ የዓሣ ሀብት ሕግ ባለመኖሩና ሀብቱን በዘላቂነት ለማልማትና ለመጠበቅ ሕግ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55/1 መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የዓሣ ሀብት ልማትና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 315)1995" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

   1. "ዓሣ" ማለት ማንኛውም የዓሣ ዝርያ፣ ሽርጠን፣ አስተኔ (ክሩስተሺያን፣ ዛጐል ለበስ ) ሞለስክ እንዲሁም እነሱ የጣሉትን እንቁላል፣ የተፈለፈለ ወይም ታዳጊ ጫጩትን ያጠቃልላል፤
   2. "የዓሣ ሀብት" ማለት በተፈጥሮና በሰው ሠራሽ የውሃ አካላት ውስጥ የሚገኝ የዓሣ ክምችት ነው፣
   3. "የዓሳ ግብርና" ማለት ቁጥጥር በሚደረግበት ሁኔታ በተፈጥሮና በሰው ሠራሽ የውሃ አካላት ዓሣን ማርባት እና/ወይም ማምረትና ከዚህ ጋር የተያያዙ ሌሎች ሥራዎችንም የሚጨምር ነው፣
   4. "የዓሣ ግብርና ተቋም" ማለት የዓሣ ግብርና ሥራ የሚካሄድበት ማንኛውም የተወሰነ ቦታ ወይም አካባቢ ሲሆን ለግል መዝናኛነት የሚዘጋጀውን መርዕየ ገንዳን አይጨምርም፣
   5. "ዓሣ ማስገር" ማለት ማንኛውንም ዘዴ በመጠቀም ከማንኛውም የውሃ አካል ለተለያየ ዓላማ ዓሣ የመያዝ፣ የመግደል ወይም የማውጣት ተግባር ነው፤

6. "ለግል ፍጆታ ዓሣ ማስገር" ማለት ዓሣ አስጋሪው ለራሱና ለቤተሰቡ ፍጆታ ብቻ የሚያካሂደው የዓሣ ማስገር ሥራ ነው፣
7. "ለንግድ ዓሣ ማስገር" ማለት በሙሉ ወይም በከፊል ለመሸጥ ወይም ለመለወጥ ዓሣ ማስገር ነው፣
8. "ለመዝናኛ ዓሣ ማስገር" ማለት ለመዝናኛ ተብሎ ልሙጥ የሆነ ነጠላ መንጠቆና የናይለን ክር በመጠቀም የሚካሄድ ዓሣ ማስገር ነው፣
9. "ለምርምር ዓሣ ማስገር" ማለት ለሳይንሳዊ ምርምር፣ ለሙከራ፣ ለሌሎች ጥናታዊ ሥራዎች ወይም ዓሣን በማንኛውም የውሃ አካል ለመጨመር መያዝንና ለመርዐየ ገንዳና ለቤተመዘክር ዓሣ መሰብሰብን ይጨምራል፤
10. "ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት ነው፤
11. "ዓሣ አስጋሪ" ማለት የዓሣ ማስገር ሥራ የሚያካሂድ ሰው ነው፣
12. "ጥብቅ የዓሣ ሀብት ክልል" ማለት በማንኛውም የውሃ አካል ውስጥ የዓሣውን ዝርያ ለመጠበቅ ወይም ለሌላ ተግባር ሲባል በሙሉ ወይም በከፊል የተከለለና ለምርምር ካልሆነ በስተቀር ለማንኛውም የዓሣ ማስገር ሥራ የተከለከለ አካባቢ ነው፣
13. "የዓሣ ማስገሪያ ጀልባ" ማለት ለዓሣ ማስገር ሥራ ከብረት፣ ከጣውላ፣ ከእንጨት፣ ከቀርከሃ፣ ከደንገል ወይም ከመሳሰሉት የተሠራ ማንኛውም ተንሳፋፊ አካልነው፣
14. "የዓሣ ማስገሪያ መሣሪያ" ማለት ለዓሣ ማስገር ሥራ የሚያገለግል ማንኛውም መረብ፣ ወጥመድ፣ ወንፊት፣ ነጠላ የናይለን ክር፣ መንጠቆና እንዲሁም ሌላ ተመሣሣይ መሣሪያ ነው፣
15. "ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የግብርና ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፣
16. "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47(1 መሠረት የተመለከተ ማንኛውም የክልላዊ መስተዳድር ሲሆን ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም የአዲስ አበባና የድሬዳዋ አስተዳደሮችንም ይጨምራል፣
17. "የዓሣ ሀብት ተቆጣጣሪ" ማለት ይህን አዋጅና በአዋጁ መሠረት የሚወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን ካለባቸው ኃላፊነት አንፃር ለማስፈፀም እንደአግባቡ በሚኒስቴሩ ወይም በሚመለከተው የክልል ባለሥልጣን ሥልጣን የተሰጠው አግባብ ያለው ማንኛውም ሰው ነው፣

3. **<u>ዓላማ</u>**

የዚህ አዋጅ ዓላማዎች፡-

1. የዓሣ ብዝሀ-ሕይወትና አካባቢው እንዲጠበቅ፣ ዓሣ ሀብቱ ከሚገባው በላይ እንዳይመረት መከላከልና መቆጣጠር፣
2. ጥራቱና ንጽሕናው የተጠበቀ የዓሣ ምርት አቅርቦትን ማሳደግና ለምግብ ዋስትና የሚያበረክተውን አስተዋጽዖ በዘላቂነት ማረጋገጥ እና፣
3. የዓሣ ግብርና ልማትን ማስፋፋት፣

ናቸው፡፡

4. **<u>የአፈጻጸም ወሰን</u>**

ይህ አዋጅ በኢትዮጵያ ውስጥ ዓሣ በሚረባባቸውና በሚመረትባቸው የውሃ አካላት ሁሉ ማለትም በሐይቆች፣ በወንዞች፣ በጅረቶች፣ በግድቦች፣ በኩሬዎችና በረግረጋማ ቦታዎች እንዲሁም የዓሣ ምርት ዝግጅትና ግብይት በሚካሄድባቸው ቦታዎች ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የዓሣ ሀብት አጠቃቀም</u>

5. **<u>ከተፈጥሮና ሰው ሠራሽ የውሃ አካላት የሚገኝ የዓሣ ሀብት</u>**

1. ለንግድ ሥራ ከተፈጥሮ እና ከሰው ሠራሽ የውሃ አካላት ዓሣ ለማስገር የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ሕጋዊ የዓሣ ማስገር ፈቃድ መያዝ አለበት፡፡
2. የዓሣ ማስገር ፈቃድን በማንኛውም መልኩ ለሌላ ሰው አሳልፎ መስጠት የተከለከለ ነው።
3. ማንኛውም ሰው ከብሔራዊ ዱር እንስሳት ፓርክ ወይም ጥብቅ ቦታ ለፍጆታ፣ ለንግድ ወይም ለመዝናኛ ዓሣ ለማስገር ፓርኩን ለማስተዳደር ሥልጣን ከተሰጠው አካል የተሰጠ የፅሑፍ ፈቃድ መያዝ አለበት።
4. ከጥብቅ የዓሣ ሀብት ክልል ለፍጆታ፣ ለንግድ ወይም ለመዝናኛ ዓሣ ለማስገር የፈለገ ማንኛውም ሰው ከሚኒስቴሩ ወይም ከሚመለከተው የክልል ባለሥልጣን የፅሑፍ ፈቃድ ማግኘት አለበት።
5. ለመዝናኛ ዓሣ ለማስገር የሚፈልግ ማንኛውም የውጭ ሀገር ዜጋ እንደአግባቡ ከሚኒስቴሩ ወይም ከሚመለከተው የክልል ባለሥልጣን የፅሑፍ ፈቃድ ማግኘት አለበት።

6. ማንኛውም ሰው ለፍጆታ፣ ለንግድ ወይም ለመዝናኛ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 በተደነገገው መሠረት በኮንሴሽን ከተሰጠ የዓሣ ሀብት ዓሣ ለማስገር ኮንሴሽን ከተሰጠው ሰው ፈቃድ ማግኘት አለበት።
7. ለምርምር ሥራ ካልሆነ በስተቀር ሕጋዊ ከሆኑ የማስገሪያ መሣሪያዎች ውጭ በፈንጂ፣ ጦር መሣሪያ፣ በመርዝ፣ ዓሣውን በሚያደነዝዝ ዕፅ ወይም በኤሌክትሪክ ሞገድ ከማንኛውም የውኃ አካል ዓሣ ማስገርና እነዚህን ነገሮች በውሃ አካላት ላይና ዳርቻ ይዞ መገኘት የተከለከለ ነው፣
8. ከማንኛውም የውሃ አካል ውሃውን በማጠንፈፍ ዓሣን ማስገር የተከለከለ ነው።
9. በሀገሪቱ የውኃ አካላት ለምርምር ዓሣ ማስገር የሚፈልግ ማንኛውም ሰው የምርምር ሥራን ለመምራት እና እንደአስፈላጊነቱ ውሃን ለማስተዳደር ሥልጣን ከተሰጠው የፌዴራል ወይም የክልል መንግሥት አካል ፈቃድ ማግኘት አለበት።
10. ማንኛውም ሰው ከውጭ ሀገር ማንኛውንም ዓይነት ሕይወት ያለው የዓሣ ዝርያ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት ወይም ከሀገር ለማስወጣት፣ከሚኒስቴሩ የጽሑፍ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡
11. ማንኛውም ሰው ከውጭ ሀገር በፈቃድ ወደ ሀገር ውስጥ የገባውን ወይም በሀገር ውስጥ የሚገኝን ማንኛውም ሕይወት ያለው ዓሣ ከአንዱ ክልል የውሃ አካል ወደ ሌላ ክልል ለማዘዋወር ከሚኒስትሩ የጽሑፍ ፈቃድ ማግኘት አለበት።
12. ማንኛውም ሰው ሙሉ በሙሉ በክልሉ ውስጥ በሚገኙና ወደ ውጭ የመፍሰስ ባህርይ በሌላቸው የውሃ አካላት መካከል ካንዱ የውሃ አካል ወደ ሌላ የውሃ አካል የዓሣ ዝርያ ለማዘዋወር ከሚመለከተው የክልል ባለሥልጣን የጽሑፍ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡

6. **የዓሣ ግብርና**

1. ማንኛውም ሰው ለንግድ የዓሣ ግብርና ተቋም ለማቋቋም ወይም የዓሣ ግብርና ለማካሄድ እንደአግባብነቱ ከፌዴራል ወይም ከክልል ባለሥልጣን ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡
2. ለንግድ የዓሣ ግብርና ተቋም ለማቋቋም ወይም ለማካሄድ ለሚፈልግ ማንኛውም ሰው ፈቃድ የሚሰጠው፡-
   ሀ) በቂ መሬት ያለውና ለሥራው የሚያስፈልገውን የውኃ መጠን ለመጠቀም ወይም ከመሬት ውስጥ ለማውጣት ወይም በተፈጥሮ የውሃ አካላት ላይ ለመጠቀም ሥልጣን ካለው አካል ፈቃድ የተሰጠው፣ እና

ለ) የሚቋቋመው የዓሣ ግብርና ተቋም አካባቢን የማይበክል ወይም በተፋሰሱ ባሉ የውሃ አካላት በሚገኙ የዓሣ ዝርያዎች ላይ ጉዳት የማያደርስ፣

መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው።

3. የዓሣ በሽታ ከዓሣ ግብርና ተቋም ወደ አካባቢው ወይም ተፋሰሱ ሊዛመት ይችላል ብሎ ሲያምን ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው የክልል ባለሥልጣን አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል፣
4. የዓሣ ግብርናና የዓሣ ግብርና ተቋም ግንባታና አጠቃቀም ደረጃዎችን በተመለከተ ሚኒስቴሩ እንደ አስፈላጊነቱ መመሪያ ያወጣል።

7. <u>**የዓሣ ሀብትን በኮንሴሽን ስለመስጠት**</u>

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ወይም ክልላዊ መንግሥታት የአንድ የውሃ አካል ዓሣ ሀብትን ለአንድ ወይም ለብዙ ሰዎች በኮንሴሽን የሚሰጡበትና የዓሣ ሀብቱ በዘላቂነት መልማቱን የሚቆጣጠሩበት ሕግ ማውጣት ይችላሉ፡፡

8. <u>**አካባቢን ስለመጠበቅ**</u>

በማናቸውም ተፋሰስ ለማካሄድ የሚታቀዱ የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በተፋሰሱ በሚገኝ የዓሣ ሀብት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የማያደርሱ መሆናቸውን በሚመለከተው የፌዴራል ወይም የክልል መንግሥት አካል መረጋገጥ አለበት፡፡

9. <u>**ወሰን እና ክልል ተሻጋሪ የዓሣ ሀብት ልማት**</u>

1. ወሰን ተሻጋሪ የዓሣ ሀብት ልማትን በተመለከተ ሚኒስቴሩ ከሚመለከታቸው ጐረቤት ሀገሮች ጋር መደራደርና ስምምነት ማድረግ ይችላል፣
2. እያንዳንዱ ክልል ከሌሎች ክልሎች ጋር በሚያዋስኑ የውሃ አካላት ውስጥ የሚገኝ የዓሣ ሀብት በዚህ አዋጅ በተደነገጉት መርሆዎች መሠረት መጠበቁን ለማረጋገጥ መተባበር ይኖርበታል፣
3. ክልሎችን በሚያዋስኑ የውሃ አካላት የሚገኝ የዓሣ ሀብት በሚመለከታቸው ክልሎች መካከል ሀብቱን በጋራ ለማልማት በሚደረግ ስምምነት መሠረት አለመካሄዱ ሲረጋገጥ የዓሣ ሀብቱን በአግባቡ ለማልማት የሚያስችል ደንብ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሊያወጣ ይችላል፡፡

10.<u>የዓሣ ምርት አያያዝ</u>

የዓሣና የዓሣ ውጤት አያያዝ፣ ዝግጅት፣ ክምችት ፣ማጓጓዝና ንግድ ሥራዎች ተገቢውን የጥራትና የንግድ ደረጃዎችንና ሥርዓቶችን የጠበቀ መሆን አለበት፡፡ ዝርዝሩም በዚህ አዋጅመሠረት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

11.<u>የዓሣ ሀብት መረጃ ልውውጥ</u>

1. ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም እንዲረዳ ክልላዊ መስተዳድሮች የዓሣ ሀብት መረጃዎችን በመሰብሰብና በማጠናቀር ለሚኒስቴሩ ይልካሉ፤
2. ሚኒስቴሩ ከተለያዩ ምንጮች ስለ ዓሣ ሀብት የሚሰበስባቸውን መረጃዎችና የምርምር ውጤቶች በመገምገምና በማዘጋጀት ለክልል መስተዳድሮችና ለሌሎች ተጠቃሚዎች እንዲደርሱ ያደርጋል፣

12.<u>የዓሣ ሀብት ልማት እና አጠቃቀም ሕግ መሠረታዊ ጉዳዮች</u>

በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጣ ማንኛውም የዓሣ ሀብት ሕግ ጥብቅ የዓሣ ሀብት ክልልን፣ ዓመታዊ የዓሣ ምርት መጠንን፣ የማስገሪያ መሣሪያ ዓይነትንና ብዛትን፣ የማስገሪያ ወቅትን፣ የማስገር ፈቃድ አሰጣጥን፣ እድሳትንና እገዳን፣ የዓሣ ዝውውርን፣ የዓሣ ግብርናን፣ የዓሣ ንግድን፣ የዓሣ ውጤቶች ጥራትና የንጽሕና ደረጃን፣ የተከለከሉ ተግባሮችን፣ የኅብረተሰብ ተሳትፎን፣ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማንና ሌሎች ተጓዳኝ ጉዳዮችን በግልጽ ያስቀመጠ መሆን አለበት።

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>አዋጁን ስለማስፈጸም</u>

13.<u>የዓሣ ሀብት ተቆጣጣሪ ሥልጣንና ኃላፊነት</u>

ይህን አዋጅና በአዋጁ መሠረት የሚወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን ተግባራዊነት ለማረጋገጥ የዓሣ ሀብት ተቆጣጣሪ ሥልጣን የተሰጠው መሆኑን የሚገልጽ መታወቂያ በማሳየት ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ፡-

ሀ) በማንኛውም የውኃ አካል ላይ የሚገኝ ዓሣ አስጋሪን አስቁሞ መፈተሽ ጀልባውን ወይም የማስገሪያ መሳሪያውን መመርመር፤

ለ) ይህን አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡትን ደንቦችና መመሪያዎች ጥሷል ተብሎ አጥጋቢ በሆነ ሁኔታ የተጠረጠረ ማንኛውንም ሰው ስሙንና አድራሻውን እንዲነግር፣ መታወቂያውንና ሌሎች ከዚህ ጋር አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች እንዲያሳየው ወይም እንደአስፈላጊነቱ እንዲሰጠው መጠየቅ፤

ሐ) ማንኛውም ዓሣ የተያዘው፣የተጓጓዘው፣ ለገበያ የቀረበው፣ ወደ ሀገር እንዲገባ የተደረገው ወይም ከሀገር እንዲወጣ የተዘጋጀው ይህን አዋጅ በመጣስ ነው ብሎ አጥጋቢ በሆነ ምክንያት ሲያምን ዓሣውን መያዝ፣

መ) ማንኛውም የዓሣ ማስገሪያ ጀልባና መሣሪያ ይህን አዋጅ እና፣ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡትን ደንቦችና መመሪያዎች በተፃረረ ሁኔታ ጥቅም ላይ መዋሉን አጥጋቢ በሆነ ሁኔታ ሲያረጋግጥ እነዚህን መሣሪያዎች መያዝ፤

ሠ) ማንኛውንም ሰው ይህን አዋጅ በመተላለፍ ወንጀል ፈጽሟል ብሎ አጥጋቢ በሆነ ምክንያት ሲያምን በተቻለ ፍጥነት ሥልጣን ባለው አካል ክስ እንዲመሠረት ማድረግ፤

ረ) ማንኛውም ዓሣ መታመሙን፣ መበከሉን ወይም መበላሸቱን አጥጋቢ በሆነ መንገድ ሲያረጋግጥ ዓሣው እንዲወገድ ወይም ጉዳት እንዳያደርስ ማድረግ፣

ሰ) ማንኛውንም ዓሣ አስጋሪ ስለተጠቀመበት ማስገሪያ መሣሪያ፣ ስለያዘው ዓሣ ዓይነትና መጠን፣ እንዲሁም ዓሣውን ያሰገረበትን አካባቢ መረጃ እንዲሰጠው መጠየቅ፤

ሸ) ማንኛውንም የዓሣ ግብርና፣ የዓሣ ማደራጃ፣ ማከማቻ፣ ማጓጓዣና መሸጫ ተቋማትንና መሳሪያዎችን መፈተሽና ተፈላጊውን ደረጃ አሟልተው በማይገኙበት ጊዜ ማሸግ ወይም ማገድ፤

ይችላል።

14.<u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማንኛውም ሰው የዓሣ ሀብት ተቆጣጣሪ ለሥራው የሚፈልጋቸውን መረጃዎች በመስጠት የመተባበር ግዴታ አለበት።

15.<u>ስለተያዘ ዓሣ፣ የማስገሪያ መሳሪያና ሌሎች ዕቃዎች</u>

1. የዓሣ ሀብት ተቆጣጣሪ፡-

ሀ) በዚህ አዋጅ መሠረት የተያዘና ለገበያ መቅረብ የሚችል ማንኛውንም ዓሣ እንዳይበላሽ ለመከላከል ዓሣው የተያዘበት ሰው ባለበት በህጋዊ መንገድ እንዲሸጥ ያደርጋል፤

ለ) በዚህ አዋጅ መሠረት የተያዘ የማስገሪያ መሳሪያን ወይም የማጓጓዣና ሌሎች እቃዎችን ፍርድ እስኪሰጥባቸው ድረስ በጥንቃቄ እንዲቆዩ ማድረግ ይኖርበታል፤

ሐ) የተያዘ ዓሣ፡ የማስገሪያ መሣሪያ ወይም ሌላ እቃ ዓይነትና መጠን፡ የተያዘበትንና ዓሣው የተሸጠበትን ወይም የተወገደበትን ቀን እንዲሁምከሽያጭ የተኘውን ገንዘብ መጠን የሚገልጽ ህጋዊ ደረሰኝ ለተያዘበት ሰው ይሰጣል።

2. በዚህ አዋጅ መሠረት ዓሣ የተያዘበት ሰው በወንጀል የመጠየቁ ሁኔታ እንደተጠበቀ ሆኖ፡ ከዓሣ ሽያጭ የተገኘው ገንዘብ ለመንግሥት ገቢ ይደረጋል፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 16.ወንጀልና ቅጣት

ማንኛዉም ሰዉ፡-

1. ያለፍቃድ ወይም ከተሰጠዉ ፍቃድ ተቃራኒ በሆነ ሁኔታ ህይወት ያለዉ ዓሳ ከዉጭ ሀገር ካስገባ፣ በኢትዮጵያ የዉሃ አካላት ከጨመረ፣ ከሀገር ካስወጣ፣ ወይም ከአንድ የዉሃ አካል ወደ ሌላ የዉሃ አካል ካዛወረ ከአንድ አመት በማያንስ እና ከሶስት ዓመት በማይበልጥ አስራት ወይም እስከ ብር 10 ሺ በሚደርስ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ ከተጠቀሰዉ ወንጀል ዉጪ ይህንን አዋጅና በዚህ አዋጅ መሰረት የሚወጡ ደንቦችንና መመሪያዎች ከተላለፈ በኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ህግ መሰረት ይቀጣል፡፡

### 17.ሌሎች እርምጃዎች

1. ማንኛዉም ሰዉ ይህን አዋጅ በመተላለፍ ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ ጥፋተኛነቱ ሲረጋገጥ በተከሣሹ ላይ ከሚሰጠው ማንኛውም ዓይነት ቅጣት በተጨማሪ ፍርድ ቤቱ፣

   ሀ) ለወንጀል ተግባር የዋሉትን ማናቸውንም የዓሣ ማስገሪያ ጀልባና የዓሣ ማስገሪያ መሣሪያ እንዲወረስ፤

   ለ) ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ የዓሣ ማስገር ሥራ ለማካሄድ የዋለን ማናቸውንም መርዝ ወይም ፈንጂ ወይም ሌላ ዓይነት መሣሪያ እንዲወረስ፤

   ሐ) የዓሣ ማስገር ሥራው ወይም የንግድ ፈቃዱ እንዲታገድ፣ እንዲሰረዝ፤

   ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡
2. የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ የተያዙት ዕቃዎች እንዲወረሱ ትዕዛዝ ካልተሰጠ በስተቀር ውሳኔው በተሰጠ በ30 ቀናት ውስጥ የገንዘብ ቅጣቱ ካልተከፈለ የተያዙት ዕቃዎች ተሸጠው ከሽያጩ በሚገኘው ገንዘብ የገንዘብ ቅጣቱ እንዲሸፈን ይደረጋል፡

3. የወንጀል ክስ ከተመሠረተ በኋላ ተከሳሹ በነጻ ቢለቀቅ የተያዘው የማስገሪያ መሳሪያ ወይም ሌላ እቃ ለተከሣሹ ይመለሳል፡፡ የተያዘው ዓሣ ከሆነ ግን ዓሣው የተሸጠበት ዋጋ ለግለሰቡ ተመላሽ ይሆናል፡፡

18.<u>**ወንጀል እንደተፈጸመ የሚያስቆጥሩ ሁኔታዎች**</u>

1. ማንኛውም ሰው አግባብነት በሌለው ሁኔታ በኢትዮጵያ የውኃ አካላት ወይም ዳርቻ ላይ ፈንጂ፣ የጦር መሣሪያ፣ የኤሌክትሪክ ንዝረት የሚሰጥ መሳሪያ፣ መርዝ ወይም ዓሣን የሚያደነዝዝ ዕፅ ይዞ ቢገኝ የዚህን አዋጅ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀፅ (7 ድንጋጌ በመተላለፍ ሕገ ወጥ ድርጊት እንደፈጸመ ይቆጠራል።
2. ማንኛውም ሰው ፈቃድ ሳይኖረው ሕይወት ያለው ዓሣ ሲያዘዋውር ቢገኝ የዚህን አዋጅ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (1(11 እና (12 ድንጋጌዎች በመተላለፍ በሕገ ወጥ ሥራ ላይ እንደተሰማራ ይቆጠራል።

19.<u>**ከሌሎች ሕጐች ጋር ስላለው ግንኙነት**</u>

ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያና ልምድ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

20.<u>**አዋጁን ለማስፈጸም የሚረዱ ሕጎችን ስለማውጣት**</u>

ይህን አዋጅ ተግባራዊ ለማድረግ እንዲረዳ፡-

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ፤
2. ክልሎች የየራሳቸውን ሕግ፤
3. ሚኒስቴሩ መመሪያ፤

ሊያወጡ ይችላሉ፡፡

21.<u>**አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**</u>

ይህ አዋጅ ከጥር 27 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥር 27 ቀን 1995 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ**

**ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

# አዋጅ ቁጥር 534/1999

## የተፋሰስ ምክር ቤቶችና ባለሥልጣናት አዋጅ

የኢትዮጵያ የውሃ ሀብት ሥርጭቱ በቦታና በወቅት የተዛባ ከመሆኑም በላይ የአገሪቱ ኢኮኖሚ ባደገ መጠን የውሃ አጠቃቀም ፍላጎት በመጠንም ሆነ በጥራት እንዲጨምር የማድረግ ውጤት የሚያስከትል በመሆኑ፣

የኢትዮጵያ የውሃ ሀብት አስተዳደር ፖሊሲ፣ የፖሊሲው ምሰሶ የሆነውን የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር መርህን ተግባራዊ ለማድረግ የተፋሰስ ምክር ቤቶችና ባለሥልጣናት ማቋቋምን እንደ አንዱና ዋነኛ መሣሪያ አድርጎ የተቀበለው በመሆኑ፣

የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር፣ ውሃ እንደ ኢኮኖሚያዊና አካባቢያዊ ሀብትነቱ ልማቱ ሚዛናዊና ቀጣይነት ያለው እንዲሆን በተፋሰስ ውስጥ ያሉ አጠቃቀሞች በአጠቃላይ የሚጣጣሙበትን ሥርዓት መዘርጋትን የሚጠይቅ በመሆኑ፤

የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር፣ በተፋሰስ ውስጥ የሚገኙ አግባብ ያላቸው አካላት ውሳኔዎቻቸው፣ ዕቅዶቻቸውና ተግባሮቻቸው በውሃው ዑደትና በሌሎች ተጠቃሚዎች ላይ በሚያስከትሏቸው ውጤቶች ላይ የአመለካከት፣ የፍላጎትና የግንዛቤ ልዩነት ቢኖራቸውም ተባብረው እንዲሠሩ የሚጠይቅ በመሆኑ፣

የተፋሰስ ምክር ቤቶችና ባለሥልጣናት መቋቋም የተፋሰስ የውሃ ሀብት ዕቅድን መሠረት በማድረግና አግባብነት ባላቸው አካላት ዘንድ ውጤታማና ቀጣይነት ያለው የጋራ አመራር በማስፈን የኢትዮጵያ የውሃ ሀብት አስተዳደር ፖሊሲን በመተግበር ረገድ ብቃት ያለው የተረጋጋ አሠራር እንዲኖር ለማስቻል ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያለው በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የተፋሰስ ምክር ቤቶችና ባለሥልጣናት አዋጅ ቁጥር 534/1999" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

1. "ተፋሰስ" ማለት ወደ አንድ መልክዓ ምድራዊ አቅጣጫ የሚፈሱ የገፀ ምድርና የከርሰ ምድር ውሃዎች የሚያካልሉት አካባቢ ሆኖ የሚከተሉትን የኢትዮጵያ ዋና ዋና ተፋሰሶች ከነንዑስ ተፋሰሳቸው ያጠቃልላል፣
   ሀ) የአባይ ተፋሰስ፣
   ለ) የአይሻ ተፋሰስ
   ሐ) የአዋሽ ተፋሰስ
   መ) የባሮ አኮቦ ተፋሰስ
   ሠ) የደናኪል ተፋሰስ
   ረ) የገናሌ ዳዋ ተፋሰስ
   ሰ) የመረብ ተፋሰስ
   ሸ) የኦጋዴን ተፋሰስ
   ቀ) የኦሞ ጊቤ ተፋሰስ
   በ) የተከዜ ተፋሰስ
   ተ) የስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ፣ እና
   ቸ) የዋቢ ሸበሌ ተፋሰስ፡፡
2. "ክልል" ማለት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 47)1)ሥር የተመለከተ ማንኛውም ክልል ሲሆን፣ የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችን ይጨምራል፤
3. "አግባብ ያለው አካል" ማለት በተፋሰስ የውሃ ሀብት አስተዳደር ፈልጎም ይሁን ሳይፈልግ የሚሳተፍ ወይም በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ጥቅሙ የሚነካ ማንኛውም ሰው ነው፤
4. "የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር" ማለት ውሃ እንደ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና አካባቢያዊ ሀብትነቱ በተፋሰስ ውስጥ ካሉ የተለያዩ አጠቃቀሞች ጋር ሙሉ በሙሉ የተጣጣመ ሆኖ ሚዛናዊና ቀጣይነት ያለው የውሃ ሀብት ልማት እንዲኖር የሚያስችል ሥርዓት ነው፤
5. "የውሃ ሀብት" ማለት መጠንና ጥራትን ባካተተ ሁኔታ በተፋሰስ ውስጥ የሚገኝ የገፀምድርና የከርሰ ምድር ውሃ ሲሆን የውሃ የተፈጥሮ ሥነ ምህዳርንና ረግረጋማ መሬትን ያጠቃልላል፤

6. “የውሃ ምደባ” ማለት የተፋሰስን የውሃ ሀብት በውሃ የመጠቀም ፈቃድ ሥርዓትን በመተግበር ለልዩ ልዩ ግልጋሎቶች ማከፋፈል ነው፤
7. “የውሃ ግልጋሎት” ማለት በውሃ ሀብቱ ወይም ውሃው ሊሰጠው በሚችለው ግልጋሎት ወይም በውሃው የተፈጥሮ ሥነ ምህዳር ላይ ተጽዕኖ ሊያስከትል የሚችል ማንኛውም የውሃ አጠቃቀም ሲሆን ውሃውን መውሰድን፣ የውሃውን ተፈጥሮአዊ መሄጃ ማሻሻልንና የታከመ ቆሻሻን ለመድፋት፣ ለመዝናኛ፣ ለዓሣ እርባታ፣ ለውሃ ላይ ትራንስፖርትና ለሌሎች አገልግሎቶች ማዋልን ያጠቃልላል፤
8. “የተፋሰስ ዕቅድ” ማለት በውሃ ሀብት አጠቃቀም ፍትሐዊነትንና ቀጣይነትን በማረጋገጥ ዓላማ ላይ የተመሠረተና የረዥም ጊዜ ራዕይ ያለው ስትራቴጂክ የተፋሰስ የውሃ ሀብት ዕቅድ ነው፤
9. “ሚኒስቴር” ወይም “ሚኒስትር” ማለት እንደቅደም ተከተሉ የውሃ ሀብት ሚኒስ ቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤[36]
10. “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለተፋሰስ ከፍተኛ ምክር ቤቶችና ባለሥልጣናት

3. ***መቋቋም***
   1. የተፋሰስ ከፍተኛ ምክር ቤቶችና ባለሥልጣናት በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጡ ደንቦች ይቋቋማሉ፡፡
   2. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ተፋሰሶች በአንድ ከፍተኛ የተፋሰስ ምክር ቤትና ባለሥልጣን ሥር ሊጠቃለሉ ይችላሉ፡፡
4. ***ዓላማ***

   የተፋሰስ ከፍተኛ ምክር ቤቶችና ባለሥልጣናት አጠቃላይ ዓላማ የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር ሂደትን ፍትሐዊና አሳታፊ በሆነ መንገድ ለሕዝብ የሶሺዮ ኢኮኖሚ ብልጽግና በሚያመጣና የውሃ የተፈጥሮ ሥነ ምህዳር ቀጣይነትን ባረጋገጠ ሁኔታ የሥልጣን ክልላቸው በሆነው ተፋሰስ ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆን ማበረታታትና መቆጣጠር ይሆናል፡፡

[36] በ25/08 (2011) አ. 1097 አንቀጽ 9(11) መሰረት የውሃ፣ መስኖ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር ሆኗል፡፡

5. **<u>የተፋሰስ ከፍተኛ ምክር ቤት አባላት</u>**
   1. የተፋሰስ ከፍተኛ ምክር ቤት አባላት በመንግሥት ይመደባሉ፡፡
   2. የተፋሰስ ከፍተኛ ምክር ቤት ተጠሪነት በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡
6. **<u>የተፋሰስ ከፍተኛ ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባራት</u>**

   የተፋሰስ ከፍተኛ ምክር ቤት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣
   1. በተፋሰሱ ውስጥ አግባብ ባላቸው አካላት መካከል በተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር አተገባበር ረገድ ከፍተኛ ቅንጅታዊ አሠራር መኖሩን ማረጋገጥ የሚያስችል የፖሊሲ አቅጣጫና በዕቅድ ችግሮች ላይ አመራር ይሰጣል፤
   2. የተፋሰሱን ዕቅድ ዝግጅት ይመራል፣ ለመንግሥት አቅርቦ ያስጸድቃል፤
   3. በተፋሰሱ ውስጥ የሚገኙ የውሃ ተጠቃሚዎች ሊከፍሉት የሚገባውን የክፍያ መጠን በተመለከተ ለመንግሥት ሃሣብ ያቀርባል፤
   4. በተፋሰሱ ውስጥ ከፍተኛ የውሃ ነክ ሥራዎች ግንባታንና የቅደም ተከተሉን አግባብነት በመመርመር ይወስናል፤
   5. በተፋሰሱ የውሃ እጥረት በሌለበትና ባለበት እንዲሁም በድርቅ ወይም በጎርፍ ጊዜ ሊኖር የሚገባውን የውሃ ምደባ ሥርዓትና መርህ ተገቢነት በመመርመር ይወስናል፤
   6. ተፋሰሱን በሚጋሩ ክልሎች መካከል የውሃ ሀብት አጠቃቀምን በሚመለከት ለሚነሱ አለመግባባቶች መፍትሄ ይሰጣል፤
   7. ተፋሰሱ የወሰን ተሻጋሪ  ተፋሰስ አካል ከሆነ ከጎረቤት አገሮች ጋር ይህን በሚመለከት የመወያየት ኃላፊነት ላለበት አግባብ ያለው አካል የመረጃና የምክር ድጋፍ ይሰጣል፤
   8. የተወሰነ ዓላማን ለማስፈፀም የሚረዱ ቋሚ ወይም ጊዜያዊ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፡፡
7. **<u>የተፋሰስ ከፍተኛ ምክር ቤት ስብሰባዎች</u>**
   1. የተፋሰስ ከፍተኛ ምክር ቤት በዓመት ቢያንስ ሁለት ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል፣ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሰብሳቢው በራሱ አነሳሽነት ወይም በ$^{1}$)$_{3}$ኛ የምክር ቤቱ አባላት በጋራ ጥያቄ ሲቀርብ በማንኛውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ ሊያደርግ ይችላል፡፡

2. ከግማሽ በላይ የሚሆኑ የምክር ቤቱ አባላት በስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡፡
3. ምክር ቤቱ ውሳኔ የሚያሳልፈው በድምጽ ብልጫ ይሆናል፣ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወገን ሃሣብ የምክር ቤቱ ውሳኔ ሆኖ ያልፋል፡፡
4. የምክር ቤቱ ሰብሳቢ በማይኖርበት ጊዜ ምክትል ሰብሳቢው የምክር ቤቱን ስብሰባ ይመራል፡፡
5. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

8. **<u>የተፋሰስ ከፍተኛ ምክር ቤት ሴክሬታሪያት</u>**

የተፋሰስ ባለሥልጣን የተፋሰሱ ከፍተኛ ምክር ቤት ሴክሬታሪያት ሆኖ ያገለግላል፡፡

9. **<u>የተፋሰስ ባለሥልጣን ሥልጣንና ተግባር</u>**[37]

የተፋሰስ ባለሥልጣን የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

1. የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደርን በተፋሰሱ ውስጥ ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር የሚረዱ የፖሊሲ ሃሳቦችን በማመንጨት ለምክር ቤቱ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣
2. በተፋሰሱ ውስጥ የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር ሂደትን ለማስፈፀም የሚረዱ ተግባራትን ያከናውናል፣ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣
3. በተፋሰሱ ውስጥ ከውሃ ጋር የተገናኙ ፕሮጀክቶች፣ ተግባሮችና መስተጋብሮች በይዘታቸው፣ በጊዜ ሠሌዳቸው፣ በውጤታቸውና በአመራራቸው ከተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር ሂደቶች ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ያረጋግጣል፣
4. የተፋሰስ ዕቅድ በማዘጋጀት ለተፋሰሱ ከፍተኛ ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣
5. ለክልሎች በሕግ የተሰጠ ሥልጣን እንደ ተጠበቀ ሆኖ በተፋሰሱ ውስጥ በውሃ ለመጠቀምና ውሃ ነክ ሥራዎች ለመሥራት የሚያስችል ፈቃድ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 15 መሠረት ይሰጣል፣ በፈቃዱ የተመለከቱ ሁኔታዎች መከበራቸውን ያረጋግጣል፤

---

[37] በአዋጅ ቁጥር 1097/11 አንቀጽ 32/5 በተቋቋመው ተፋሰሶች ልማት ባለስልጣን እና በደንብ ቁጥር 441/11 አንቀጽ 5 በተሰጠው ስልጣንና ተግባር የተፋሰሶች ባለስልጣን ስልጣንና ተግባር በግልጽ ሳይነገር ለተፋሰሶች ልማት ባለስልጣን ተሰጥቷል፡

6. በተፋሰሱ የሚገኘውን የውሃ ሀብት በተገቢው ሁኔታ ለማቀድ፣ ለማስተዳደርና ለማንቀሳቀስ የሚጠቅሙ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል፣ ይተነትናል፣ ያሠራጫል፣
7. የተፋሰሱን ውሃ ሀብት ስትራቴጂክ ዕቅድና የውሃ አስተዳደር ተግባራትን ለመምራትና ለመደገፍ እንዲያስችል የተፋሰስ ሞዴል ያዘጋጃል፣ ይጠቀማል፣
8. የውሃ ምደባንና አጠቃቀምን ስለሚመለከቱ አለመግባባቶች አፈታት ለተፋሰሱ ከፍተኛ ምክር ቤትና ለሚኒስቴሩ የምክርና የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፤
9. አግባብ ባላቸው አካላት መካከል ውጤታማ የግንኙነት መድረክ በመፍጠር ቀጣይነት ባለው ሁኔታ እንዲካሄድ ያደርጋል፤
10. ከተጠቃሚዎች የውሃ ክፍያ ይሰበስባል፤
11. ከሌሎች አገሮች ጋር ድንበር ዘለል ወንዞችን በሚመለከት ለመወያየት አግባብ ላለው አካል በተፋሰሱ ከፍተኛ ምክር ቤት መመሪያ መሠረት አስፈላጊ መረጃዎችን አዘጋጅቶ ይሰጣል፤
12. ተግባሮቹን ለማከናወን የሚረዱ ጥናቶችን፣ ቅኝቶችንና ምርምሮችን ያካሂዳል፤
13. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በራሱ ስም ይከሳል፣ ይከሰሳል፤
14. ዓላማውን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

10.**<u>የተፋሰስ ባለሥልጣን ተጠሪነት</u>**

የተፋሰስ ባለሥልጣን ተጠሪነት፣

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ድንጋጌዎች የሚሸፈኑ ጉዳዮችን በተመለከተ ለተፋሰሱ ከፍተኛ ምክር ቤት፣ እና
2. በሥልጣንና ተግባሩ ሥር የሚወድቁ ሌሎች ጉዳዮችን በሚመለከት ለሚኒስቴሩ፣

ይሆናል፡፡

11.**<u>የተፋሰስ ባለሥልጣን አቋም</u>**[38]

የተፋሰስ ባለሥልጣን፣

1. በሚኒስትሩ አቅራቢነት በመንግሥት የሚሾም አንድ ዋና ዳይሬክተር፣ እና
2. አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች፣

ይኖሩታል፡፡

---

[38] በደንብ ቁጥር 441/11 አንቀጽ 6 በግልጽ ሳይነገር ተሽሯል፡፡

## 12.የዋና ዳይሬክተር ሥልጣንና ተግባር[39]

1. የተፋሰስ ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር የባለ ሥልጣኑ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን የባለ ሥልጣኑን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ዋና ዳይሬክተሩ፣
   ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 ላይ የተመለከቱትን የባለሥልጣኑን ሥልጣንና ተግባሮች ሥራ ላይ ያውላል፤
   ለ) የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕግን መሠረታዊ ዓላማዎች ተከትሎ መንግሥት በሚያፀድቀው መመሪያ መሠረት የባለሥልጣኑን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤
   ሐ) ለባለሥልጣኑ በተፈቀደለት በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤
   መ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ባለሥልጣኑን ይወክላል፤
   ሠ) የባለሥልጣኑን ዓመታዊ የሥራ አፈፃፀምና የሂሣብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለተፋሰሱ ከፍተኛ ምክር ቤትና ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤
   ረ) በተፋሰሱ ከፍተኛ ምክር ቤትና በሚኒስቴሩ በየጊዜው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ይፈጽማል፡
3. ዋናዳይሬክተሩ ለባለሥልጣኑ የሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልገው መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለባለሥልጣኑ ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

## 13.በጀት[40]

የተፋሰስ ባለሥልጣን በጀት በፌደራል መንግሥት ከሚመደብ ገንዘብና በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9)10) መሠረት ከሚሰበሰብ የውሃ ክፍያ የተውጣጣ ይሆናል፡፡

## 14.የሂሣብ መዛግብት

1. የተፋሰስ ባለሥልጣን የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል፡፡
2. የተፋሰስ ባለሥልጣን የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሠነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም በዋናው ኦዲተር በሚሰየም ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡

[39] በደንብ ቁጥር 441/11 አንቀጽ 7 በግልጽ ሳይነገር ተሽሯል፡፡
[40]በደንብ ቁጥር 441/11 አንቀጽ 9 በግልጽ ሳይነገር ተሽሯል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የውሃ መጠቀሚያ ፈቃድ፣ የመረጃ ሥርዓትና

## የተፋሰስ ዕቅድ

15. **የውሃ መጠቀሚያ ፈቃድ**

1. የተፋሰስ ባለሥልጣን በውሃ የመጠቀምና የውሃ ነክ ሥራዎችን በሚመለከት ፈቃድ የሚሰጠው የኢትዮጵያ የውሃ ሀብት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 197/1992 እና የደንብ ቁጥር 115/1997 ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ ይሆናል፡፡
2. የተፋሰስ ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 91) መሠረት የሰጣቸውን ፈቃዶች በሚመለከት የተጠናቀረ መረጃ ለሚኒስቴሩ የማስተላለፍ ግዴታ አለበት፡፡
3. በውሃ ለመጠቀም ወይም ውሃ ነክ ሥራ ለመሥራት የሚያስችል ፈቃድ አሠጣጥ ከተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር ሂደት አንፃር የተፋሰሱን የወደፊት ሁኔታ ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት፡፡

16. **የተፋሰስ የመረጃ ሥርዓት**

1. ማንኛውም የተፋሰስ ባለሥልጣን የተፋሰሱን የውሃ ሀብት ስትራቴጅክ ዕቅድንና የውሃ ሀብት አስተዳደር ተግባራትን ሊመራና ሊደግፍ የሚችል አስተዳደር ተኮር የተፋሰስ መረጃ ሥርዓት ማደራጀትና መጠቀም አለበት፡፡
2. የተፋሰስ የመረጃ ሥርዓት ቢያንስ የሚከተሉትን ቁልፍ አመልካቾች ማካተት ይኖርበታል፤
   ሀ) የተፋሰሱን የውሃ ሀብት መጠንና ጥራት፤
   ለ) የተፋሰሱን የውሃ የተፈጥሮ ሥነ ምህዳር፤
   ሐ) በተፋሰሱ ውስጥ ያለውን የውሃ ፍላጎት መጠን፤
   መ) ነባርና ለወደፊቱ የታቀዱ ዋና ዋና መሠረተ ልማቶችን፤
   ሠ) በውሃ ሀብቱ ላይ ተጽዕኖ ሊያስከትሉ የሚችሉ ዋና ዋና ጣልቃ ገብ ሥራዎችን ወይም ፕሮጀክቶችን፣
   ረ) በሥራ ላይ ያለውን የውሃ አጠቃቀም፣ እና
   ሰ) የተፋሰሱን አግባብ ያላቸው አካላት፡፡
3. የተፋሰስ ባለሥልጣን የተፋሰስ የመረጃ ሥርዓት ሲያደራጅም ሆነ ሲጠቀም በፌደራል ደረጃ ሊኖር ስለሚገባው የመረጃ መጣጣም ጉዳይ ተገቢ ትኩረት መስጠት አለበት፡፡

17.<u>የመረጃ ልውውጥ</u>

1. የተፋሰስ ባለሥልጣን በተፋሰስ የመረጃ ሥርዓት ውስጥ የሚገኝ መረጃን አግባብ ላላቸው ሁሉ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት መስጠት አለበት፡፡
2. ማንኛውም ሰው ለተፋሰስ ባለሥልጣን የመረጃ ሥርዓት የሚጠቅሙ ከውሃ ጋር ተያያዥነት ያላቸው መረጃዎችን ለባለሥልጣኑ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡
3. የተፋሰስ ባለሥልጣን በተፋሰሱ ውስጥ ብቃት ያለው የመረጃ ቁጥጥር መረብ ለመዘርጋትና ለማሻሻል አግባብ ካላቸው የፌደራልና የክልል አካላት ጋር ተባብሮ መሥራት አለበት፡፡
4. የተፋሰስ ባለሥልጣን የራሱን የመረጃ ቁጥጥር መረብ ለማቋቋምና ለማካሄድ ይችላል፡፡

18.<u>የተፋሰስ ዕቅድ</u>

1. የተፋሰስ ባለሥልጣን በተፋሰሱ ውስጥ ፍትሐዊ የውሃ ክፍፍልን፣ ቀጣይነት ያለው ልማትንና የውሃ የተፈጥሮ ሥነ ምህዳርን የማያዛባ የውሃ ሀብት አጠቃቀምን የሚያረጋግጥ ለረዥም ጊዜ የሚያገለግል የውሃ ሀብት አስተዳደር ማዕቀፍ እንዲኖር የሚያስችል የተፋሰስ ዕቅድ ሊኖረው ይገባል፡፡
2. የተፋሰስ ዕቅድ፣

   ሀ) የተፋሰሱን የውሃ ሀብት፣

   ለ) የተፋሰሱን እንክብካቤ፣

   ሐ) በውሃ ሀብቱ ላይ ከፍተኛ ጫና የሚያሳድሩ ሁኔታዎችን፣

   መ) በተፋሰሱ ውስጥ ያለውን የውሃ አጠቃቀም ደረጃ የሚያሳይ አኃዛዊ መግለጫ፣

   ሠ) የተፋሰሱን የወደፊት ሁኔታ አቅጣጫ ሊያሳይ የሚችል ትንታኔ፣

   ረ) በሁኔታዎች ግምገማ ላይ የተመሠረተና የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር ሂደት አተገባበርን ዕውን ለማድረግ የሚረዱ ስትራቴጂዎችን፣ እና

   ሰ) ዕቅዱን የሚተገብሩ አካላትን፣ የድርጊት መርሐ ግብርንና የሚያስፈልገው በጀትን ጨምሮ ዕቅዱን ተግባራዊ የማድረጊያ ዘዴዎችን፣

   ማካተት ይኖርበታል፡፡
3. በተፋሰሱ ውስጥ አግባብ ባላቸው አካላት የሚከናወኑ ከውሃ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተግባራት ከተፋሰስ ዕቅዱ ጋር እንዲጣጣሙ መደረግ አለባቸው፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

19.**የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው የዚህን አዋጅ አፈፃፀም በተመለከተ ከተፋሰስ ባለስልጣን ጋርየመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

20.**ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች**

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ በዚህ አዋጅ በተደነገጉ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

21.**ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ያወጣል፡፡
2. ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ያወጣል፡፡

22.. **አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ 06 ቀን 1999 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ**

**ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## አዋጅ ቁጥር 841/2006

## የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማኅበራት አዋጅ

በመስኖ እርሻ የውሃ ሀብትን ጥቅም ላይ ማዋል ለምግብ ዋስትናና ለኢኮኖሚ ልማት መረጋገጥ የላቀ አስተዋጽኦ የሚኖረው በመሆኑ፤

በአርሶ አደር ደረጃ በሚመሩ የመስኖ እና የድሬኔጅ ሥራዎች ተስማሚ የሆነ የሕገ ማዕቀፍ ማውጣት አስፈላጊ በመሆኑ፤

ለትርፍ ሳይሆን ራሳቸውን በራሳቸው የሚያስተዳድሩና ለሕዝብ ጥቅም በገጠር አካባቢዎች የመስኖና የድሬኔጅ አገልግሎቶችን የሚሰጡ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማኅበራት የሚደራጁበትን ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

በመንግስት ወጪ የተገነቡ የመስኖና ድሬኔጅ አውታሮችን ለማህበራት ማስተላለፍ የሚያስችል የሕግ መሠረት በመጣል በማህበራቱና በአገልግሎት ሰጪዎች መካከል ያለውን የአገልግሎቶች አቅርቦት በመቆጣጠር የተሻለ የውሃ ሀብት አስተዳደር ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55(1 መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ “የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማኅበራት አዋጅቁጥር 841/2006” ተብሎ ሊጠቀስይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ አዋጅ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉምየሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

   1. “ማኅበር” ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የተደራጀና የተመዘገበ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማኅበር ነው፤
   2. “የመስኖ እና የድሬኔጅ አውታር” ማለት ወደተወሰነ መሬት አካባቢ የመስኖ ውሃን ለማጓጓዝ ጥቅም ላይ የሚውል ቦይ ወይም የቱቦዎች ወይም የመስኖዎች አዉታር ሲሆን ከእነዚሁ ጋርተያያዥነት ያላቸውን ማንኛውንም የውሃ መጥለፊያን፣ ግድብን ወይም የውሃ ማግለያ ውቅርን፣ ማጠራቀሚያን ወይም ኩሬን እንዲሁም ማናቸውንም

የመስኖ ውሃ መተላለፊያ በሮችን፣ፓምፖችን፣ መሬትን፣ ሕንፃዎችን፣ መሣሪያዎችን መጋቢ መንገዶችን እንዲሁም የመስኖ አውታሩን ከእነድሬኔጁ ጥቅም ላይ ለማዋል፣ ለመጠገን ወይም ለማደስ አስፈላጊ የሆኑ ውቅሮችን ሁሉ ያካትታል፣

3. “የአገልግሎት ክልል” ማለት ማኅበሩ የሚገለገልበትየተወሰነ የመሬት ክልል ነው፤
4. “የዉሃ አቅርቦት መገኛ ቦታ” ማለት አንድ ማኅበርለመስኖ የሚውል ውሃን በኃላፊነት ማስተዳደር የሚጀምርበት የውሃ መገኛ ቦታ ሲሆን የውሃ ግድብን፣ መጥለፊያን፣ የማግለያ ውቅርን፣ በዋናው የመስኖና ድሬኔጅ አውታር ውስጥ የሚገኙ በሮችን ወይም ውሃ ማስተላለፊያዎች፣ ካናልን፣ የውሃ ጉድጓድን፣ ምንጭን ወይም የፓምፕ ጣቢያን ሊያካትት ይችላል፤
5. “ዘመናዊ የመስኖና ድሬኔጅ አውታር” ማለትበመደበኛ ጥናትና ዲዛይን ላይበመመሥረትየተገነባ ወይም ዘመናዊ እንዲሆን የተደረገ የመስኖና ድሬኔጅ አውታር ነው፤
6. “ባህላዊ የመስኖና ድሬኔጅ አውታር” ማለት አርሶአደሮች በልምድ ባካበቱት ዕውቀትእና በአካባቢየሚገኙ ቁሳቁሶችን በመጠቀም የገነቡት የመስኖና ድሬኔጅ አውታር ነው፤
7. “አሃድ” ማለት የአንድ ማኅበር የአገልግሎት ክልል የተወሰነ ክፍል ነው፤
8. “የአሃድ ተጠሪ”ማለት አንድን አሀድ በመወከል በጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ ላይ የተመረጠአባል ነው፤
9. “ጠቅላላ ጉባዔ” ማለት የአንድ ማኅበር ከፍተኛ የውሳኔ ሰጪ አካል ነው፤
10. “የሥራ አመራር” ማለት የአንድ ማኅበርን የሥራ እንቅስቃሴ እንዲከታተልና እንዲቆጣጠር በጠቅላላ ጉባዔ የተመረጠ አካል ነው፤
11. “ዋና የመስኖና ድሬኔጅ አውታር”ማለት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ወደሆኑ የማኅበራት የአገልግሎት ክልሎች የመስኖ ውሃ ለማጓጓዝ የሚያገለግል የመስኖና ድሬኔጅ አውታር ነው፤
12. “ፌዴሬሽን”ማለት የዋናውን የመስኖና የድሬኒጅ አውታር የማስተዳደርና የመጠገን ኃላፊነት ያለበት በዚህ አዋጅ መሠረት የተቋቋመ የውሃ ተጠቃሚዎች ማኅበራት ፌዴሬሽንነው፤
13. “አገልግሎት ሰጪ”ማለት ከፌዴሬሽን ሌላ ዋናየመስኖና ድሬኔጅ አውታርን የማስተዳደር የማሰራትና የመጠገን ሥራ የሚሰራ ማንኛውም የመንግሥት ወይም የግል ድርጅት ነው፤

14.“ሚኒስቴር”ወይም“ሚኒስቲር” ማለት እንደቅደም ተከተሉ የዉሃ፣ የመስኖና የኢነርጂ ሚኒስቴርወይም ሚኒስትር ነው፤

15. “ክልል”ማለት በኢትየጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንገስት አንቀጽ 47(1) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባእና የድሬዳዋ ከተሞችአስተዳደሮችን ይጨምራል፡፡

16.“ተቆጣጣሪ አካል”ማለት በፌዴራል መንግሥት በጀት የተገነቡ የመስኖ መሠረተ ልማቶችን በተመለከተ ሚኒስቴሩ ሲሆን በክልል በጀት የተገነቡ የመስኖ መሠረተ ልማቶችን በተመለከተ ማኀበራትን ለማደራጀትና ለመመዝገብ ሥልጠን እና ሌሎች የቴክኒክ ድጋፍ ለማኀበራት ለመስጠት ወይም በዚህ አዋጅ ውስጥ የተዘረዘሩ ሌሎች ተግባራትን ለማከናወን በክልል መንግሥት የተሰየመ አካል ነው፤

17.“የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማኀበራት መዝገብ” ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 40 መሠረት በተቆጣጣሪአካል የሚያዝ መዝገብ ነው፤

18.“የመሠረተ ልማት አካል” ማለት የመስኖ መሠረተ ልማቱ የተገነባው በፌዴራል መንግሥት በጀት ከሆነ ሚኒስቴሩ ሲሆን የመስኖ መሰረተ ልማቱ የተገነባው በክልል መንግስት በጀት ሲሆን የመስኖ መሰረተ ልማት የመገንባት ኃላፊነት ያለበት የክልል አካል ነው፤

19.“ሰዉ”ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

20.ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ያካትታል።

3. <u>**የተፈፃሚነት ወሰን**</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል መንግስት በተገነቡ የመስኖ መሰረተ ልማቶች ላይ የተደራጁ የመስኖ ተጠቃሚዎች ማህበራትን በሚመለክት በመላው ኢትዮጵያ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

4. <u>**የማህበር ዓላማዎች**</u>

በዚህ አዋጅ መሠረት የሚመሠረት ማኀበር የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል።

1. በራሱ በአገልግሎት ክልሉ ያለውን የመስኖና ድሬኔጅ አውታርን ሙሉ በሙሉወይም በከፊል በመምራትና በማስተዳደር ለአባላቱ ለግብርና አገልግሎት የሚውል ፍትሀዊ ውሃ የማቅረብ፣
2. ለአባላቱ የመስኖ ውሃ እና የድሬኒጅ አገልግሎቶችን ለመስጠት በአገልግሎት ክልሉ ውስጥ የሚገኘውን የመስኖና ድሬኔጅ አውታር የማስተዳደርና የመምራት፤

3. በአገልግሎት ክልል ውስጥ የሚገኘውን የመስኖና ድሬኔጅ አውታር መጠገን፣ ማደስአና ማሻሻል፣ እንደአስፈላጊነቱም የግንባታና የመልሶ ግንባታ ሥራዎችን የማካሄድ፣
4. የአፈር መሸርሸርን፣ ጨዋማነትንና ብክለትን ለመከላከል ተገቢውን እርምጃየመውስድ፣
5. የመስኖ ውሃ ፍጆታን በተመለከተ የውስጥ ደንቦችን ማውጣትና ለተሰጡ አገልግሎቶች ከአባላት ክፍያዎችን የመሰብሰብ ፣
6. የመስኖ መሣሪያዎችን መግዛት፣ መተካት፣ መጠገንና ሥራ ላይ የማዋል፣
7. ለአባላት ስለመስኖ ዘዴዎች፣ ስለመስኖ እርሻ አስተራረስ ዘዴዎች፣ ስለውሃ ቁጠባ ዘዴዎችና አዳዲስ የመስኖ ቴክኖሎጂዎች ሥልጠና የመስጠት።

5. **ማህበራት የሚኖሩባቸዉ መሠረታዊ መርሆዎች**

እያንዳንዱ ማኅበር በሚከተሉት መርሆዎች ላይተመሥርቶ መሥራት አለበት፡-

1. ሚዛናዊ የውሳኔ አሠጣጥና ፍትሃዊ የመስኖ ውሃክፍፍል ፣
2. የውሃ ብክነትንና ብክለትን፣ የአፈር መሸርሸርንና ጨዋማነትን የመከላከል፣ እንዲሁምየአካባቢእንክብካቤንና ጥበቃን ለማጠናከር በአገልግሎት ክልል ውስጥ የሚገኘውንየመስኖና ድሬኔጅአውታር መጠበቅና ማስተዳደር፣
3. በውሃ አጠቃቀም ረገድ በአባላት መካከል ብሔርን፣ ፆታን፣ ኃይማኖትን ወይም በማናቸውም ሌሎችተመሳሳይ ምክንያቶች ልዩነት አለማድረግ፣
4. በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ግልጽነትና አሳታፊነት ያለውየአሠራር ሥርዓት መከተል፣
5. ወጪን የመሸፈንና ሀብት በቁጠባ የመጠቀምሥርዓትን መከተል።

6. **የአገልግሎት ክልል**

1. እያንዳንዱ ማኅበር ተለይቶ በታወቀ የአገልግሎትክልል ውስጥ መንቀሳቀስ አለበት።
2. የእያንዳንዱ ማኅበር የአገልግሎት ክልል የተለየና ራሱን የቻለ የመስኖ እናየድሬኒጅ አውታሮች አሀድን ያቀፈ እና ማኅበሩ በሚያካሂደው የመስኖና ድሬኔጅ አውታር አማካኝነት አንድ ወይም ከአንድ በላይ ከሆኑ የውሃ አቅርቦት መገኛ ቦታዎች የመስኖውሃ መቀበል የሚችል መሆን ይኖርበታል።
3. የአንድ ማኅበር የአገልግሎት ክልል ከሌላ ማኅበር የአገልግሎት ክልል ጋር መደራረብ የለበትም፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለማህበር አመሰራረትና ምዝገባ

### 7. ስለማህበር አመሰራረት

አንድ ማኅበር፡-

1. ፍላጎት ባላቸው ሰዎች በፈቃደኝነት፤ ወይም
2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12(1) መሰረት ውሃን ዘላቂ ፍትሃዊና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመጠቀምና ለማስተዳደር እንዲቻል በተቆጣጣሪው አካል፤

ሊመሰረት ይችላል፡፡

### 8. ስለማህበር ስያሜ

1. እያንዳንዱ ማኅበር ከሚሠራበት ቦታ መጠሪያ ጋር የተያያዘ ወይም ሌላ ስም ይኖረዋል።
2. በማንኛውም ማኅበር ስም ውስጥ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማኅበር የሚል ሀረግ መኖር አለበት፡፡
3. አንድ ማኅበር የተመዘገበበትንስም ሌላ ማኅበርመጠቀም የተከለከለ ነው፡፡
4. የማንኛውምማኅበር ስም በጉልህ ተጽፎ የማኅበሩሥራ በሚካሄድበት በማንኛውምሥፍራ መለጠፍ አለበት፡፡እንዲሁም በማኅበሩ ማስታወቂያዎች፣ ደብዳቤዎች፣ በማኅበሩ ስም በሚፈረም ሠነድ ላይ መጻፍ ወይም ማኅተም መደረግ ይኖርበታል።

### 9. በአባላት ፍላጎት ስለሚመሰረት ማህበር

1. አንድን ማህበር፡-
   ሀ) በመሬት የይዞታ መብት መሠረት ከባህላዊየመስኖና ድሬኔጅ አውታር ውሃበሚያገኝመሬት የሚጠቀሙ፣ ወይም
   ለ) በመሬት የይዞታ መብት መሠረት በዚህ አዋጅመሠረት ተቆጣጣሪው አካልማኅበር እንዲመሰርቱ ውሳኔ ያላደረሳቸው ከዘመናዊ የመስኖና ድሬኔጅ አውታሮች ውሃ በሚያገኝመሬት የሚጠቀሙ፤

   ሰዎች በፍላጎት ሊመሰርቱት ይችላሉ፡፡
2. በባህላዊ የመስኖና ድራኔጅ አውታር ለመጠቀምበዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (1) መሠረት የተመሠረተ ማኅበር በኢትዮጵያ የውሃ ሀብት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር197/1992 መሠረት በውሃ ለመጠቀም ፈቃድ የመጠየቅና የማግኘትመብት ይኖረዋል።

## 10.በአባላት ፍላጎት ማህበር የመመስረቻ ስነ-ስርአት

1. ከአምስት የማያንሱ የመስኖ ተጠቃሚዎች በፍላጎታቸው ማኅበር ሊመሰርቱ ይችላሉ፤ለታሰበው ማኅበር የአገልግሎት ክልሉን የሚለዩ ጊዜያዊ አነሳሽ ቡድን በመመስረት እንዲሁም ከአሥራ ሁለት የማይበልጡ የማኅበር አባል ለመሆን የሚችሉ ሰዎች የሚይዝ የመሥራች ኮሚቴ ማደራጀት አለባቸው።
2. ለታሰበው ማኅበር የተሟላ ውክልና እንዲኖር የመስራች ኮሚቴ አባላት ማህበር ለመመስረት ከታሰበው የአገልገሎት ክልል ከተለያዩ አሀዶች የተውጣጡ ሰዎችን የሚያካትት መሆን አለበት፡፡
3. መሥራች ኮሚቴው የራሱን ሊቀመንበር በመምረጥ ከማኅበሩ ምሥረታ በፊት ለሚከናወኑ ተግባራት የሚያገለግሉ የራሱን የሥነ-ሥርዓት ደንብ ያዘጋጃል።
4. መሥራች ኮሚቴው እንዲቋቋም ስለታሰበው ማኅበር ከተቆጣጣሪው አካል ጋር ምክክር በማድረግ የሚከተሉትን ሰነዶች ያዘጋጃል፡-
   ሀ) እንዲቋቋም ለታሰበው ማኅበር ረቂቅ የመመሥረቻ ሰነድና መተዳደሪያ ደንብ፤
   ለ) እንዲቋቋም የታሰበውን ማኅበር የአገልግሎት ክልልና አሀዶች ካሉም የሚገኙበትን ቦታና መጠናቸውን የሚያሳይ ካርታ፣
   ሐ) የታሰበውን ማኅበርለመመስረት አባላትየሚያቀርቡትን ማመልከቻ፣ እና
   መ) የማኅበሩ አባላት ለመሆን የሚሹ ሰዎችን ስም፣አድራሻ፣ ፊርማ እናየእያንዳንዱን አባል የመሬት ይዞታ መግለጫ፣ ያላቸው ከሆነም የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ቁጥር፣ እንዲሁም የታሰበው ማኅበር ረቂቅ በጀትና የሥራ መርሐግብር ሰነድ።
5. መሥራች ኮሚቴው፡-
   ሀ) የታሰበው ማኅበር አባላት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) የተዘረዘሩትን ሠነዶች ተመልከተው አስተያየት እንዲሰጡባቸው፤ እና
   ለ) ማኅበር ለመመስረት አባላት የሚያዘጋጁትን ማመልከቻ አቀናጅቶ እንዲፈረም፤ ያደርጋል።
6. የመስራች ኮሚቴው ሊመሰረት የታሰበው ማኅበር አባላት ሊሆኑ ከሚችሉት ውስጥ ቢያንስ ግማሾቹ ማኅበር ለመመስረት በተዘጋጀው ማመልከቻ ላይ ከፈረሙበት እና በረቂቅ መተዳደሪያ ደንቡ፣ በበጀትና በሥራ መርሐ ግብር ላይ አስተያየት መስጠታቸው ከተረጋገጠ፡-
   ሀ) የማህበሩን ረቂቅ መመስረቻ ሰነድ፣ መተዳደሪያ ደንብ፣ የበጀት እና የሥራ መርሐ ግብር ላይ ተወያይቶ ለማፅደቅ፣ እና

ለ) ጊዜያዊ የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት እና 5 ሌሎች የማኅበሩን የሥራ ኃላፊዎች ለመምረጥ፣

የመሥራቾችን ስብሰባ እንዲጠራ ያደርጋል፡፡

7. የታሰበው ማኅበር አባላት ከሚሆኑት መካከል ከግማሽ በላይ የሆኑት ከተገኙ የመሥራቾች ስብሰባ ምልአተ ጉባዔ ይሆናል፤ የማኅበሩ መመሥረት እና መመስረቻ ሰነድና የመተዳደሪያ ደንብ መፅደቅ በስብሰባው ላይ በተገኙ አባላት አብላጫ ድምጽ ይወሰናል፡፡

8. ጊዜያዊ የሥራ አመራር ኮሚቴ ማኅበሩን ለማስመዝገብ የሚከተሉትን የያዘ ማመልከቻ ለተቆጣጣሪው አካል ያቀርባል።

ሀ) የመሥራቾች ስብሰባ ቃለ ጉባዔ፣

ለ) በሦስት ቅጂዎች የተዘጋጀ የማኅበሩን መመስረቻ ሰነድ እና መተዳደሪያ ደንብ፣

ሐ) የታሰበው የአገልግሎት ክልል እና ካለም የአህዶቹን አቀማመጥ የሚያሳይ ካርታ፣

መ) የታሰበውን ማኅበር ለመመስረት አባላት የጻፉትን ማመልከቻ፣

ሠ) የበጀትና የሥራ መርሐግብር ረቂቅ፤ እና

ረ) ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም በሚወሉ ደንቦች ወይም መመሪያዎች የተዘረዘሩ ሌሎች ሰነዶች።

9. ተቆጣጣሪው አካል ማመልከቻውንና ተያይዘው የቀረቡ ሰነዶችን በ15 ቀናት ውስጥ በመመርመር ማኅበሩ ለምዝገባ የሚያበቃውን መስፈርት ያሟላ መሆኑን በማረጋገጥ በመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማኅበር መዝገብ ውስጥ በመመዝገብ ለማኅበሩ የምዝገባ የምሥክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

10. ተቆጣጣሪ አካሉ ማኅበሩ ለመመዝገብ ያቀረበውን ማመልከቻ ያልተቀበለው እንደሆነ ያልተቀበለበትን ምክንያት በዝርዝር ለጊዜያዊ የሥራ አመራር ኮሚቴው በ15 ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ያሳውቃል።

11. <u>በተቆጣጣሪዉ አካል ስለሚመሰረት ማህበር</u>

ተቆጣጣሪው አካል ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ ዘመናዊ የመስኖና ድሬኔጅ አውታሮችን ወይም ዘመናዊ የተደረጉ ባሕላዊ የመስኖና የድሬኔጅ አውታሮች የመስኖ ውሃ የሚጠቀሙ ማኅበራት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12(1) መሰረት እንዲመሠረቱ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## 12.በተቆጣጣሪዉ አካል የሚመሰረት ማህበር የመመስረቻ ስነ-ስርአት

1. ተቆጣጣሪው አካል ስለሚመሰረተው ማኅበር አባላት ሊሆኑ ከሚችሉት ሰዎች እና አግባብ ካላቸው አካላት ጋር ከተመካከረ እና ሐሣቡ ተቀባይነት ካገኘ በኋላ ማኅበር እንዲመሰረት ውሳኔ የተሰጠ መሆኑን ያሳውቃል።
2. ማስታወቂያውም በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 10(4) ላይ ከተዘረዘሩ ረቂቅ ሠነዶች ቅጅዎች ጋር ተያይዞ እንዲመሰረት ለተወሰነው ማኅበር አባል ለሚሆኑ ሰዎች ለምርመራ እንዲቀርብ ይደረጋል፡፡
3. ተቆጣጣሪው አካል እንዲመሰረት ለተወሰነው ማኅበር አባል ከሚሆኑት ሰዎች ጋር ተከታታይ ውይይት በማካሄድ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 10(4) የተመለከቱት ረቂቅ ሠነዶች የመጨረሻ ቅርፃቸውን እንዲይዙ ያደርጋል።
4. ተቆጣጣሪው አካል የታሰበውን ማኅበር የበጀትና የሥራ መርሐ ግብር የሚያፀድቅና ጊዜያዊ የሥራ አመራር ኮሚቴና ሌሎች የሥራ ኃላፊዎችን የሚመርጥ የመሥራቾች ስብሰባ የሚካሄድበትን ቀን ያሳውቃል።
5. ጊዜያዊ የሥራ አመራር ኮሚቴው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10(8) የተመለከቱትን ሠነዶች ለማኅበሩ ምዝገባ ያቀርባል።
6. አመዘጋገብን በተመለከተ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 10(9) ድንጋጌ በዚህ አንቀጽ መሠረት ለሚመሠረቱ ማኅበራትም በተመሳሳይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 13.ስለህጋዊ ሰዉነትና ሃላፊነት

1. በዚህ አዋጅ መሠረት ተመስርቶ የተመዘገበ ማኅበር ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ሕጋዊ ሰውነት ይኖረዋል።
2. በዚህ አዋጅ መሠረት የተመሠረተ ማንኛውም ማኅበር ኃላፊነቱ የተወሰነ ሲሆን ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም።

## 14.ስለማህበሩ መተዳደሪያ ደንቦች

1. ማንኛውም ማኅበር የራሱ መተዳደሪያ ደንብ ይኖረዋል።
2. የመተዳደሪያ ደንቡ ይዘት የሚከተሉትን ዝርዝሮች ያካትታል፡-

   ሀ) የማኅበሩን ስምና አድራሻ፣

   ለ) የማኅበሩን ዓላማና ተግባር ፤

   ሐ) የማኅበሩን የአገልግሎት ክልል ፕላን ወይም ካርታ፣

   መ) የማኅበሩ አባል ለመሆን የሚያበቁ መስፈርቶች፤

   ሠ) የማኅበሩን አባላት መብቶችና ግዴታዎች፣

ረ) የማኅበሩን አመራር አካላት ሥልጣን፣ ኃላፊነት እና ተግባር፣

ሰ) የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ የሚጠራባቸው እና የሚመራባቸው ሥነ ሥርዓቶች፣

ሸ) የማኅበሩን የሥራ አመራር ኮሚቴና ሌሎች አካላትን ምርጫ፣ የሥራ ዘመንና ከኃላፊነት ስለሚታገዱበት ወይም ስለሚነሱባቸው ሁኔታዎች፣

ቀ) ክፍያዎች የሚወሰኑባቸው ደንቦች፣ እና

በ) የማኅበሩ ተግባራት የሚቋረጥባቸው ሁኔታዎች።

3. የማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ በጠቅላላ ጉባዔ ልዩ ውሳኔ ሊሻሻል ይችላል፤ ሆኖም ማንኛውም የመተዳደሪያ ደንብ ማሻሻያ ተግባራዊ የሚሆነው በተቆጣጣሪው አካል ፀድቆ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ይሆናል።

## ክፍል ሦስት

## ስለማህበር አባልነትና ስለአባላት መብትና ግዴታ

### 15.ስለማህበር አባልነት

1. በዚህ አዋጅ መሠረት በተቋቋመ በአንድ ማህበር የአገልግሎት ክልል ውስጥ የሚገኝን መሬት አግባብ ባለው የመሬት ባለይዞታነት ሥርዓት መሠረት ይዞ የሚጠቀም ማንኛውም ሰው የዚሁ ማኅበር አባል መሆን አለበት።
2. በውርስ ወይም በሌላ ሕጋዊ መንገድ በአንድ ማኅበር የአገልግሎት ክልል ውስጥ በሚገኝ መሬት የመጠቀም መብት ያገኘ ማንኛውም ሰው ቀደም ሲል የዚያ መሬት ተጠቃሚ የነበረው ሰው ለማኅበሩ አጠናቆ ያልከፈላቸውን መዋጮዎች እና ክፍያዎች በመክፈል የማኅበሩ አባል ይሆናል፡፡
3. ከአንድ ማኅበር መቋቋም ጋር ተያይዘው የሚመነጩ መብቶችና ግዴታዎች በማኅበሩ የአገልግሎት ክልል ውስጥ ከሚገኙ ማሳዎች ጋር በቋሚነት የተያያዙና ማኅበሩ እስካልፈረሰ ወይም የማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሻሻልን ተከትሎ ማሳዎቹ ከማኅበሩ የአገልግሎት ክልል ውጭ እስካልሆኑ ድረስ ከማሳዎቹ ሳይነጠሉ የሚተላለፉ ናቸው።
4. በማኅበሩ የአገልግሎት ክልል ውስጥ የሚገኝን መሬት ከሦስት ዓመት በላይ በኪራይ ውል የሚጠቀም ሰው የኪራዩ ዘመን እስከሚቋረጥበት ወይም እስከሚጠናቀቅበት ጊዜ ድረስ የማኅበሩ አባል እንደሆነ ይቆጠራል።

5. በማኅበሩ የአገልግሎት ክልል ውስጥ የሚገኝ መሬት ሦስትና ከሦስት ዓመታት ላነሰ ጊዜ በኪራይ ውል የሰጠ አከራይ የማኅበሩ አባል ሆኖ ይቆያል፤ ሆኖም መሬቱን የተከራየው ሰዉ፡-
   ሀ) የማኅበሩን ሕግጋት የማክበር ግዴታ አለበት፤
   ለ) ከአከራዩ በሚሰጥ የጽሑፍ ፈቃድ ተከራዩ በአከራዩ የማኅበርተኝነት መብቶች መገልገል ይችላል፡፡

16.<u>የአባላት መብትና ግዴታ</u>

1. ማንኛውም የማኅበር አባል የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፡-
   ሀ) ማኅበሩ ከሚያከፋፍለው የመስኖ ውሃ ተገቢ ድርሻውን የማግኘት፣
   ለ) በማኅበሩ ከሚሰጡ ወይም በማኅበሩ በኩል ከሚገኙ ሌሎች አገልግሎቶች የመጠቀም፤
   ሐ) የሚፈለግበት ተገቢ የአገልግሎት ክፍያዎችን በማጠናቀቅ ለማኅበሩ የተለያዩ አካላት የመምረጥና የመመረጥ፤
   መ) ለጠቅላላ ጉባዔው ስብሰባዎች የመወያያ አጀንዳ የማስያዝ፤
   ሠ) ለማኅበሩ ልዩ ልዩ አካላት የሚወዳደሩ ዕጩዎችን የመጠቆም፣
   ረ) ማኅበሩ በቀጠረው ሠራተኛ ወይም ማኅበሩ በመሬቱ ላይ በሚያከናውናቸው የጥገና ሥራዎች ምክንያት ሆን ተብሎ ወይም በቸልተኝነት በሰብሉ ወይም በመሬቱ ላይ ለደረሰ ጉዳት ከማኅበሩ ካሣ የማግኘት፣
   ሰ) በሥራ ሰዓት የማኅበሩን ጽ)ቤት የመጎብኘት፣ የማኅበሩን መዛግብት የመመልከት፣ እንዲሁም በሚያቀርበው ጥያቄ መሠረት የማኅበሩን የሂሣብ አያያዝና የሥራ አመራር ዕቅዶችን የሚመለከት መረጃ የማግኘት።
2. ማንኛውም የማኅበር አባል የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-
   ሀ) የማኅበሩን መተዳደሪያ ደንብ መመሪያዎችንና ውሳኔዎችን የማክበር፣
   ለ) የማኅበሩን ክፍያዎች የመፈጸም፣
   ሐ) የመስኖ ውሃን ማኅበሩ በሚያወጣው የውሃ ክፍፍል መርሐ ግብር መሠረት ብቻ የመጠቀም፣
   መ) በቸልተኝነት ወይም ሆን ብሎ በማኅበሩ መሣሪያ ወይም መሠረተ ልማት ላይ ያደረሰውን ጉዳት የመጠገን ወይም ለመተካት የሚያስፈልገውን ወጪ የመክፈል፤

ሠ) በማኅበሩ ሲጠየቅ ስለራሱ መሬትና ውሃ አጠቃቀም ተፈላጊ የሆነውን መረጃ የመስጠት፣

ረ) የማኅበሩ ሠራተኞች ወይም ከማኅበሩ ጋር የተዋዋሉ አገልግሎት ሰጪዎች የመስኖና የማፍሰሻ አውታሩን ለመሥራት ወይም ጥገና ሥራ ለማካሄድ እንደአስፈላጊነቱ መሣሪያዎችና ዕቃዎችን ይዘው ሲመጡ ይዞታው ወደሆነው መሬት እንዲገቡ የመፍቀድ፣

ሰ) የመስኖና ድሬኔጅ አውታሮችን ከማጽዳትና ከመጠገን ጋር የተያያዙ ተግባራትን የማከናወን፤

ሸ) የመስኖና ድሬኔጅ አዉታሩን አሠራርና ጥገና የሚመለከቱ ቴክኒካዊ ደንቦችን የማክበር፡፡

## 17. አባልነትን ስለማቋረጥ

1. በማኅበሩ የአገልግሎት ክልል ውስጥ በሚገኝ መሬት የመጠቀም መብቱን ያቆመ ማንኛውም አባል በመሬቱ የመጠቀም መብቱን ማቆሙን ለማኅበሩ በጽሑፍ በማስታወቅ ከአባልነቱ ሊወጣ ይችላል።
2. ማንኛውም የማኅበር አባል ከማኅበሩ አባልነት እስከሚወጣበት ቀን ድረስ ላላጠናቀቀው ክፍያ ተጠያቂነት አለበት፡፡

## 18. ስለድምጽ አሰጣጥ

1. ማንኛውም አባል በአሀድ ተወካዮች ምርጫ ወይም በጠቅላላ ጉባዔው ስብሰባዎች ላይ አንድ ድምጽ ይኖረዋል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም በማኅበሩ አባላት መካከል በያዙት መሬት ስፋት ወይም በሚጠቀሙት የውሃ መጠን ላይ ከፍተኛ የሆነ ልዩነት ካለ ተቆጣጣሪው አካል ከሚከተሉት በአንዱ ላይ ተመሥርቶ የድምጽ ድልድል እንዲኖር ሊፈቅድ ይችላል፦

   ሀ) በአገልግሎት ክልል ውስጥ ካለው የማሳ ስፋት ጋር ተመጣጣኝ የሆኑ ድምጽ እንዲኖረው በማድረግ ወይም

   ለ) ለማኅበሩ ከከፈለው መዋጮ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ድምጽ እንዲኖረው በማድረግ፡፡

3. የድምጽ ድልደላው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት እንዲሆን ከተፈቀደ እያንዳንዱ አባል ቢያንስ አንድ ድምጽ ይኖረዋል፤ ሆኖም ማንኛውም አባል በአንድ አሀድ ወይም በጠቅላላ ጉባዔ 20 ከመቶ በላይ የሆነ ድምጽ አይኖረውም።

## ክፍል አራት

## ስለአመራር አካላት

### 19.ስለማህበሩ አመራር አካላት

1. የአንድ ማኅበር የአመራር አካላት፡-
   ሀ) ጠቅላላ ጉባዔ፤
   ለ) የሥራ አመራር ኮሚቴ፤
   ሐ) የቁጥጥር ኮሚቴ፤ እና
   መ) የክርክር አወሳሰን ኮሚቴ፤
   ናቸው፡፡
2. አንድ ማኅበር በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች ኮሚቴዎች እንዲቋቋሙ ሊፈቅድ ይችላል።
3. የአንድ ማኅበር የአመራር አካላት ሥልጣንና ተግባር በዚህ አዋጅና በማኅበሩ የመተዳደሪያ ደንብ በሚወሰነው መሠረት ይሆናል፡፡

### 20.ስለጠቅላላ ጉባኤ

1. የማኅበሩ አባላት ቁጥር በጣም አነስተኛ ከመሆኑ የተነሳ ሁሉም በጠቅላላ ጉባዔው እንዲገኙ መተዳደሪያ ደንቡ የሚፈቅድ ካልሆነ በስተቀር የጠቅላላ ጉባዔው አባላት ከእያንዳንዱ አህድ የሚወከሉ የአህድ ተጠሪዎች ይሆናሉ። ሆኖም የአህድ ተጠሪዎች ያልሆኑ የማኅበሩ አባላት ድምጽ የመስጠት መብት ሳይኖራቸው በጠቅላላ ጉባዔው ስብሰባዎች ላይ የመሳተፍ መብት ይኖራቸዋል።
2. በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ፦
   ሀ) የእያንዳንዱን የአህድ ተጠሪ የአገልግሎት ዘመን፤
   ለ) ከአህዱ ስፋት አንፃር ከእያንዳንዱ አህድ የሚወከሉ ተጠሪዎች ብዛት፣
   ሐ) የአህድ ተጠሪዎችን ለመምረጥ፣ ለመተካት እና ለማንሳት የሚያስፈልጉ ሥነ ሥርዓቶች፤
   መ) የአህድ ተጠሪዎች የወከሏቸውን አባላት ሐሳብ ለጠቅላላ ጉባዔ የሚያቀርቡበትን እና የጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ ውጤትን ለአባላቱ ሪፖርት የሚያደርጉበት ሥርዓት፣ እና
   ሠ) እያንዳንዱ የአህድ ተጠሪ በጠቅላላ ጉባዔው ስብሰባዎች ላይ የሚሰጣቸው የድምጽ መጠን፤
   የሚወሰን ይሆናል።

## 21.የጠቅላላ ጉባኤ ስልጣንና ተግባር

1. የማንኛውም ማኅበር ከፍተኛ የሥልጣን አካል የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባዔ ይሆናል፡፡
2. የጠቅላላ ጉባዔ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።
   ሀ) የማኅበሩን ዓመታዊ የሥራ እቅድና በጀት የማፅደቅ፣
   ለ) የማኅበሩን የሥራ አመራር አካላት፣ የቁጥጥር ኮሚቴ፣ የክርክር አወሳሰን ኮሚቴ እና ሌሎች የንዑሳን ኮሚቴዎች አባላትን የመምረጥ እና የመሻር፣
   ሐ) የማኅበሩን መተዳደሪያ ደንብና የውስጥ ደንብ የማጽደቅ እና የማሻሻል፤
   መ) በማኅበር አባላት የሚከፈል የመዋጮ እና የቅጣት መጠንን የመወሰን ፤
   ሠ) የማኅበሩን ዓመታዊ ገቢና ወጪ መግለጫ እና የሀብትና የዕዳ መግለጫ እንዲሁም የሥራ አመራር አካላት ዓመታዊ ሪፖርት የማፅደቅ፣
   ረ) ማኅበሩን እንደገና የማደራጀት ወይም የማኅበሩን ሂሣብ ማጣራትን የሚመለከቱ ውሳኔዎችን የመወሰን፣
   ሰ) ማናቸውንም የማኅበሩን ንብረቶች መሸጥን፣ መግዛትን በመያዣነት መስጠትን፣ ኢንቨስትመንትን፣ ብድር መበደርን ወይም ማኅበሩ ያለበትን ዕዳ ወይም እነዚህን የሚመለከቱ ገደቦችን የመወሰን፤
   ሸ) በማኅበሩ ውስጠ ደንብ መሠረት ከተወሰነ ዋጋ በላይ ያላቸውን ወይም ለማኅበሩ ከፍተኛ ፋይዳ ያላቸውን ውሎችን የማፅደቅ፣
   ቀ) በሥራ አመራር ኮሚቴ እና በሌሎች ኮሚቴዎች የሚቀርቡለትን ማናቸውንም ጉዳይ የመወሰን።

## 22.ስለ ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባዎች

1. የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባዔ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፡፡
2. የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባዔ ምልዓተ ጉባዔ በመተዳደሪያ ደንቡ ይወሰናል፡፡
3. የሥራ አመራር ኮሚቴው የማኅበሩ የቁጥጥር ኮሚቴ ወይም ከማኅበሩ አባላት አንድ ሦስተኛ የሚሆኑት ወይም የአሀድ ተጠሪዎቻቸው በሚያቀርቡት የጽሁፍ ጥያቄ መሠረት የማኅበሩን አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ሊጠራ ይችላል፡፡
4. ስለጠቅላላ ጉባዔው ስብሰባ አጠራር አጀንዳ አያያዝ፣ ተጨማሪ አጀንዳዎችን ስለማቅረብ እና አጀንዳዎቹ ለአሀድ ተጠሪዎቻቸውና ለማኅበሩ አባላት የሚገለጽበት ሥነ ሥርዓት በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ ይወሰናል፡፡
5. የጠቅላላ ጉባዔው ስብሰባዎች የሚመሩት በሥራ አመራር ኮሚቴው ሊቀመንበር ወይም ሊቀመንበሩ በሌለበት ጊዜ በምክትል ሊቀመንበሩ ይሆናል።

6. ማኅበሩን ለማፍረስ፣ ሂሣብ ለማጣራትና ዕዳን ለመክፈል ወይም ማኅበሩን እንደገና ለማደራጀት፣ መተዳደሪያ ደንቡን ለማሻሻል ወይም በመተዳደሪያ ደንቡ ሁለት ሦስተኛ ደምጽ እንዲሰጥባቸው በግልጽ ከተመለከቱ ጉዳዮች በስተቀር የማኅበሩ የጠቅላላ ጉባዔው ውሳኔዎች በአብላጫ ድምጽ ያልፋሉ።
7. የድምጽ አሠጣጥ ሥነ ሥርዓት በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ መገለጽ አለበት፡፡
8. የጠቅላላ ጉባዔው ቃለጉባዔዎች በሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት ተፈርሞ እና በጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ የተገኙ አባላት ስም ዝርዝርና ፊርማ የያዘ ሰነድ አባሪ ተደርጎ እና ማህተም ተደርጎበት መቀመጥ አለበት፡፡

23. <u>ስለስራ አመራር ኮሚቴ</u>

1. እያንዳንዱ ማኅበር ቁጥራቸዉ ከአምስት ያላነሱ ወይም ከአሥራ አንድ ያልበለጡ እና በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት የሚመረጡ አባላትን የያዘ ለጠቅላላ ጉባዔ ተጠሪ የሆነ የሥራ አመራር ኮሚቴ ይኖረዋል።
2. የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል፤ ሆኖም ግን በአንድ ወቅት የተመረጡ የኮሚቴ አባላት የሥራ ዘመን በአንድ ላይ እንዳያበቃ የሦስት ኮሚቴ አባላት የሥራ ዘመን ማብቂያ በፈረቃ እንዲሆን በመተዳደሪያ ደንቡ ይወስና፣
3. የሥራ አመራር ኮሚቴ አባል ከሁለት ተከታታይ የሥራ ዘመን በላይ ሊመረጥ አይችልም።
4. የማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ የሥራ አመራር ኮሚቴ አባል በአገልግሎት ክልል ውስጥ ከሚገኝ አንድ ወይም ከአንድ በላይ አህዶችን እንዲወክል ተደርጎ ከእነዚህ ከተወከሉ አባላት መካከል እንዲመረጥ ሊደረግ ይችላል፡፡
5. ማንኛውም የሥራ አመራር ኮሚቴ አባል የጥቅም ግጭት ሊያስከትል የሚችል ሁኔታ ሲከሰት ይህንኑ ማሳወቅና በሥራ አመራር ኮሚቴ ውይይቶችና ውሳኔዎች መሳተፉን ማቆም አለበት።
6. የገንዘብ መቀጫዎችን ጨምሮ ያልተከፈለ የማኅበሩ ዕዳ ያለበት ማንኛውም አባል ለሥራ አመራር ኮሚቴው አባልነት ምርጫ የመቅረብ መብት አይኖረውም፡፡
7. ለሥራ አመራር ኮሚቴ አባልነት የተመረጡ አባላት ከመካከላቸው ሊቀመንበር፣ ጸሐፊ እና ገንዘብ ያዥ ይመርጣሉ።

## 24.የሥራ አመራር ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር

የሥራ አመራር ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ የሚወሰን ሆኖ በተለይ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራትን ይጨምራል፦

1. በጠቅላላ ጉበዔዉ የተወሰኑ ውሳኔዎችን የማስፈጸም፤
2. የማኅበሩን ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና በጀት የማዘጋጀትና ሲፈቀድም ተግባራዊ የማድረግ፣
3. የጠቅላላ ጉባዔውን የስብሰባ አጀንዳ የማዘጋጀት፤
4. በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት የጠቅላላ ጉባዔውን ስብሰባ የመጥራት፤
5. የማኅበሩን ጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ ቃለ ጉባዔዎችን በጽሁፍ የመያዝ፣
6. ዓመታዊ የሥራ እንቅስቃሴ እና የበጀት ሪፖርት ለጠቅላላ ጉባዔው የማቅረብ፣
7. የማኅበሩን መዛግብትና ሂሣብ በሚገባ የመያዝ፣
8. በዚህ አዋጅ ወይም በመተዳደሪያ ደንቡ የተደነገጉ ወይም በጠቅላላ ጉባዔው የተወሰኑ ሌሎች ተግባራትን የመፈጸም።

## 25.ስለ ስራ አመራር ኮሚቴ ስብሰባዎች

1. የሥራ አመራር ኮሚቴ በየወሩ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም በማንኛውም አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፡፡
2. የሥራ አመራር ኮሚቴ ስብሰባ ምልዐተ ጉባዔ በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ የተወሰነው ይሆናል፡፡
3. የሥራ አመራር ኮሚቴው ውሳኔዎች በስምምነት ያልፋሉ፣ ሆኖም ስምምነት ላይ መድረስ ያልተቻለ እንደሆነ በድምጽ ብልጫ መወሰን እንዲቻል መተዳደሪያ ደንቡ ሊፈቅድ ይችላል፡፡
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የሥራ አመራር ኮሚቴው የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 26.ስለስራ አመራር ኮሚቴዉ ሊቀመንበር

1. የሥራ አመራር ኮሚቴው ሊቀመንበር የማኅበሩም ሊቀመንበር ነው።
2. ሊቀመንበሩ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።
   ሀ) የሥራ አመራር ኮሚቴውን ስብሰባ የመጥራትና ስብሰባውን በሊቀመንበርነት የመምራት፤ እንዲሁም የጠቅላላ ጉባዔውን ስብሰባዎች የመምራት፣
   ለ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ማኅበሩን የመወከል፤

ሐ) በሥራ አመራር ኮሚቴው ውሳኔዎች መሠረት ውሎችንና ሌሎች ሕጋዊ ሠነዶችን የመፈረም፤

መ) በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ የተዘረዘሩ ሌሎች ተግባራትን የማከናወን።

3. ሊቀመንበሩ ተግባሩን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ምክትል ሊቀመንበሩ ተክቶ ይሰራል።

27.**<u>የጸሃፊዉ ስልጣንና ተግባር</u>**

የማህበሩ ጸሃፊ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1. የማህበሩን ጽህፈት ቤት ያደራጃል፣
2. የማህበሩን ሰነዶች በአግባቡ ይይዛል፤
3. የማህበሩ ቃለ ጉባዔ በሚገባ መያዙን ያረጋግጣል፣
4. የማህበሩን የጽህፈት ሥራዎች በኃላፊነት ይመራል፣
5. በሊቀመንበሩና በሥራ አመራር ኮሚቴው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትያከናውናል።

28.**<u>ስለ ቁጥጥር ኮሚቴ</u>**

1. እያንዳንዱ ማኅበር በጠቅላላ ጉባዔዉ የሚመረጡ ከሦስት የማያንሱ አባላትን የያዘ የቁጥጥር ኮሚቴ ይኖረዋል።
2. የቁጥጥር ኮሚቴ አባላት የሥራ ዘመን ሦስት ዓመት ይሆናል፡፡
3. በአንድ ወቅት የተመረጡ የቁጥጥር ኮሚቴ አባላት የሥራ ዘመን በአንድ ላይ እንዳያበቃ የኮሚቴው አባላት የሥራ ዘመን ማብቂያ ጊዜ የተለያየ እንዲሆን በመተዳደሪያ ደንቡ ይወሰናል፡፡
4. አንድ የቁጥጥር ኮሚቴ አባል በተመሳሳይ ጊዜ የሥራ አመራር ኮሚቴው አባል ሆኖ ማገልገል አይችልም ።
5. የቁጥጥር ኮሚቴው ተጠሪነት ለጠቅላላ ጉባዔው ይሆናል፡፡

29.**<u>የቁጥጥር ኮሚቴው ሥልጣንና ተግባር</u>**

የቁጥጥር ኮሚቴው ሥልጣንና ተግባር በመተዳደሪያ ደንቡ የሚወሰን ሆኖ በተለይ የሚከተሉትን ሥልጣንና ተግባሮች ይጨምራል፣

1. የሥራ አመራር ኮሚቴ ኃላፊነቱን በትክክል መወጣቱን ይከታተላል፣
2. የማኅበሩ ገንዘብና ንብረት በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፤

3. የማኅበሩ የሂሣብ እና ልዩ ልዩ እንቅስቃሴ በማኅበሩ መተዳደሪያ እና በውስጠ ደንብ መሠረት መከናወናቸውን ይከታተላል፣ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ የኦዲት ምርመራ ያካሂዳል፣
4. ዓመታዊ የኦዲት ሪፖርት ለጠቅላላ ጉባዔ ያቀርባል።

## 30. ስለአመራር አካላት የዉል ድንጋጌዎች

1. የሥራ አመራር፣ የቁጥጥር እና የክርክር አወሳሰን ኮሚቴ አባላት የማኅበሩ ተቀጣሪዎች ስላልሆኑ ደመወዝ አይከፈላቸውም፣ ሆኖም ተግባራቸዉን ሲያከናውኑ ያወጧቸው ተገቢነት ያላቸው ወጪዎች እና በኮሚቴ ሥራ ላይ በሚገኙበት ጊዜ አነስተኛ የሆነ አበል በማኅበሩ በጀት መሠረት ሊከፈላቸው ይችላል፡፡
2. የሥራ አመራር፣ የቁጥጥር ወይም የክርክር አወሳሰን ኮሚቴ አባል፡-
   ሀ) ተግባሩን መወጣት ካልቻለ፤
   ለ) በፕሮግራም በተያዙ ስብሰባዎች ላይ ያለበቂ ምክንያት ከሁለት ጊዜ በላይ ካልተገኘ ወይም
   ሐ) ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ከአንድ ወር በላይ ለሆነ ጊዜ በኮሚቴ ስብሰባ ላይ፤

   መገኘት የማይችል ከሆነ፤ በጠቅላላ ጉባዔው ውሳኔ ከኃላፊነት ሊነሳ ይችላል፡፡
3. የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባዔ አንድን ተመራጭ ከኃላፊነቱ በሚያነሳበት ወቅት በምትኩ ሌላ መምረጥ አለበት።

## 31. ስለማህበሩ ሰራተኞች

1. አንድ ማኅበር ዳይሬክተርና ሌሎች የአስተዳደር ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችን ሊቀጥር ይችላል፡፡
2. ዝርዝሩ በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ የሚወሰን ሆኖ ተቀጣሪ ዳይሬክተር በመስኖ ሥራ አመራር ተስማሚ ሙያና በቂ ልምድ ያለው እና የማኅበሩ አባል ያልሆነ ሰው መሆን ይኖርበታል።
3. ዳይሬክተሩ ለሥራ አመራር ኮሚቴው ተጠሪ ሆኖ ምክር ይሰጣል፣ ሲጠየቅም በስብሰባዎች ላይ ይገኛል፤ ሆኖም በውሳኔና በድምጽ አሠጣጥ ላይ አይሳተፍም።
4. የዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር በመተዳደሪያ ደንቡ የሚወሰን መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የሥራ አመራር ኮሚቴው በተወሰነ የገንዘብ መጠን የተገደቡ አነስተኛ ውሎችን እንዲፈርም ለዳይሬክተሩ ሥልጣን ሊሰጥ ይችላል፡፡

5. የማኅበሩ የአስተዳደር ሠራተኞች ቅጥር በማኅበሩ መተዳደሪያ እና የውስጥ ደንብ መሠረት ይሆናል።
6. የአንድ ማኅበር ተቀጣሪ ሠራተኛ በተመሳሳይ ጊዜ የአሀድ ተጠሪ ወይም የማኅበሩ ተመራጭ የሥራ ኃላፊ ሆኖ ማገልገል አይችልም።

## ክፍል አምስት

## ስለማህበራት ገቢ

### 32.ስለማህበር ገቢ ምንጮች

1. የአንድ ማኅበር የገቢ ምንጮች፡-

   ሀ) የማኅበሩ አባላት ዓመታዊ የአባልነት መዋጮ፣

   ለ) የማኅበሩ አባላት የውሃ አገልግሎት ክፍያ፣

   ሐ) ስጦታ ወይም እርዳታ፣

   መ) ለማኅበሩ ሳይከፍሉ ከዘገዩ ክፍያዎች ከሚገኝ ወለድ፣

   ሠ) በባንክ ካስቀመጣቸው ገንዘቦች ወይም ከሌሎች ተመሳሳይ ምንጮች የሚገኝ ወለድ፤

   ረ) ከአባላት መቀጫና ሌሎች ቅጣቶች የተሰበሰቡ ገቢዎች፤እና

   ሰ) ማኅበሩ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሚከፈሉ ክፍያዎች፣

   ናቸው።
2. እያንዳንዱ ማኅበር ለአስቸኳይ ጥገናዎች፣ ማኅበሩ የሚገለገልበትን የመስኖና ድሬኔጅ አውታር ለማሻሻል ወይም አድሶ በጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስፈልገው ወጭ ለመሸፈን የሚውል የመጠባበቂያ ገንዘብ ማስቀመጥ ይኖርበታል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተው የመጠባበቂያ ገንዘብ ወጪ እስከሚደረግበት ጊዜ ድረስ ወለድ በሚያስገኝ የባንክ ሂሣብ ውስጥ መቀመጥ ይኖርበታል።

### 33.ስለዓመታዊ የአባላት መዋጮ

1. ማንኛውም ማኅበር ወጪዎችን ለመሸፈን አባሉ በአገልግሎት ክልል ውስጥ የያዘውን የማሳ ስፋት መሠረት ያደረገ ዓመታዊ የአባልነት መዋጮ ማስከፈል አለበት፡፡
2. እያንዳንዱ አባል የሚከፍለው ዓመታዊ የአባልነት መዋጮ፡-

   ሀ) የመስኖና ድሬኔጅ አውታሩን ለማካሄድና ለመጠገን እና የውሃ መተላለፊያ ማንኛውንም ቦይ ለማፅዳት የሚያስፈልገውን ወጪ ለመሸፈን፤

ለ) የመስኖና ድሬኔጅ አውታሩን ሥራ የማካሄድ ወይም የውሃውን መተላለፊያ መንገድ የመክፈት አገልግሎት ለሚሰጡ ሌሎች ሰዎች የሚደረጉ ክፍያዎችን ለመሸፈን፣

ሐ) የማኅበሩን ሠራተኞች ደመወዝ እና ሌሎች የማኅበሩን ወጪዎች ለመሸፈን፤ እና

መ) ለማኅበሩ የመጠባበቂያ ገንዘብን ተቀማጭ ለማድረግ፣

የሚውል ይሆናል፡፡

3. አነስተኛ የገንዘብ ወጪ ያለበት ማኅበር አባላት በስምምነት ዓመታዊ የአባላት መዋጮውን በከፊል ወይም በሙሉ የጉልበት አስተዋፅዖን ጨምሮ በዓይነት እንዲሆን ማድረግ ይችላሉ፡፡

34.<u>ስለ ዉሃ አገልግሎት ክፍያ</u>

አንድ ማኅበር እያንዳንዱ አባል ለመስኖ እርሻው በሚጠቀመው የውሃ መጠን ወይም በሚያለማው መስኖ መሬት መጠን ላይ የተመሠረተ የአገልግሎት ክፍያ እንዲፈጽም ማድረግ ይችላል፡፡

<u>ክፍል ስድስት</u>

<u>ስለ ቁጥጥር ስረአት</u>

35.<u>ስለተቆጣጣሪ አካል</u>

1. ተቆጣጣሪው አካል የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

   ሀ) ከማኅበራት መቋቋምና ተግባራቸውን ከማከናወን ጋር በተያያዘ የግንዛቤ መፍጠሪያ ሥልጠና የመስጠት፣

   ለ) የውሃ ሀብት አስተዳደርን፣ የሂሣብ አያያዝን፣ የፋይናንስ ዕቅድ ማውጣትን፣ የመስኖ ቴክኒኮችንና ልምዶችን፣ ጥገናንና ሥርዓት ፆታን ጨምሮ ለማኅበራት የቴክኒክ ዕርዳታና ድጋፍ የመስጠት፣

   ሐ) በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረተ አዳዲስ ማኅበራትን የመመስረት፣

   መ) የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማኅበራት መዝገብን የማቋቋምና የመያዝ ፤

   ሠ) በዚህ ክፍል ድንጋጌዎች መሠረት የሕግና የፋይናንስ ቁጥጥር የማድረግ።

2. ተቆጣጣሪው አካል የማኅበራትን የሕግና የፋይናንስ ቁጥጥር ሲያካሂድ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎችና በሥራ የዋሉ የሂሣብ አሠራር ደንቦችን ማክበራቸውን በማረጋገጥ ላይ የተወሰነ ይሆናል፡፡

3. ተቆጣጣሪው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1 ፊደል ተራ (ሀ ፣ (ለ እና (ሠ የተመለከቱትን ሥልጣንና ተግባር በሙሉ ወይም በከፊል አግባብ ላላቸው አካላት በውክልና መስጠት ይችላል፡፡

36.**ስለአመታዊ ሪፖርቶች**

1. ማንኛውም ማኀበር የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ 120 ቀናት ውስጥ ዓመታዊ ሪፖርቱን ከሂሣብ መግለጫ ኮፒ ጋር በማያያዝ በተፈቀደው የሪፖርት አቀራረብ ቅፅ መሠረት ለተቆጣጣሪው አካል ማቅረብ አለበት፡፡
2. የማኀበሩ ዓመታዊ የሀብትና የዕዳ እና የገቢና የወጪ መግለጫዎች በጠቅላላ ጉባዔው መጽደቅ አለባቸው።

37.**ስለ ህግና ፋይናንስ ቁጥጥር**

1. የማኀበሩ መዝገብ፡-
   ሀ) የማኀበሩ አሠራር ትክክል ወይም ተገቢ አይደለም በማለት ሁለት አምስተኛ የማኀበሩ አባላት በጽሑፍ ሲጠይቁ፤ ወይም
   ለ) የሕግና የፋይናንስ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ተገቢነት የሌላቸው አሠራሮች ለመኖራቸው ማስረጃ የተገኘ እንደሆነ፤

   በተቆጣጣሪው አካል ሊመረመር ይችላል።
2. ተቆጣጣሪው አካል የማኀበሩን መዛግብት መርምሮ አግባብ ያልሆነ የፋይናንስ አጠቃቀም ለመኖሩ ወይም ማኀበሩ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም በመተዳደሪያው እና በውስጠ ደንቡ መሠረት እየሠራ አለመሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ካገኘ የሥራ አመራር ኮሚቴው የምርመራ ውጤቱን ለማኀበሩ አባላት የሚያቀርብበት አስቸኳይ የጠቅላላ ጉባዔ ስብስባ በ30 ቀናት ውስጥ እንዲጠራ ማዘዝ ይችላል፡፡
3. የሥራ አመራር ኮሚቴው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የጠቅላላ ጉባዔውን ስብሰባ ሳይጠራ የቀረ እንደሆነ ተቆጣጣሪው አካል ራሱ የማኀበሩን አስቸኳይ የጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ መጥራት ይችላል፡፡
4. ተቆጣጣሪው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት የማኀበሩን ጠቅላላ ጉባዔ ስብስባ የጠራ እንደሆነ የአሰራር ችግሩን ለጠቅላላ ጉባዔው ሪፖርት በማድረግ የአሠራር ችግር ያስከተሉትን የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት ከኃላፊነት የሚነሱበትን እና አዲስ የሥራ አመራር ኮሚቴዉ አባላት የሚመረጡበትን ሁኔታ የማመቻቸት ሥልጣን ይኖረዋል።

38.**የተቆጣጣሪዉን አካል ፈቃድ የሚሹ ጉዳዮች**

1. ማንኛውም ማኅበር የሚከተሉትን ተግባራት ለማከናወን ከተቆጣጣሪው አካል በቅድሚያ የጽሑፍ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡-

   ሀ) የማኅበሩን መተዳደሪያ ደንብ ለማሻሻል፤

   ለ) የማኅበሩን የአገልግሎት ክልል ለማሻሻል፣

   ሐ) ፌዴሬሽን ለመመስረት፣

   መ) የማኅበሩን ንብረቶች በመያዣነት ለመስጠት፣

   ሠ) በዚህ አዋጅ መሠረት የአንድን ማኅበር አባል የውሃ ተጠቃሚነት መብት እንዲሠረዝ ለፍርድ ቤት ማመልከቻ ለማቅረብ፡፡

2. ተቆጣጣሪው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በቀረበ የፈቃድ ጥያቄ ላይ ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣው ደንብ በሚወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት።

39.**ማህበራት መያዝ ስላለባቸዉ መዛግብት**

የማንኛውም ማኅበር፡-

1. የአገልግሎት ክልሉን የሚያሳይ ካርታ፤
2. እንደአስፈላጊነቱ በየሦስት ወሩ የሚታደስ የአባላትን ዝርዝር እና የእያንዳንዱን አባል የመሬት ይዞታ ስፋት እና የሚገኝበትን ቦታ በዝርዝር የያዘ የአባላት መዝገብ፤
3. ማኅበሩ የሚቀበለውን ወይም የሚያወጣውን የውሃ መጠን የሚገልጽ መዝገብ
4. አባላት ያገኙትን የውሃ መጠን የሚያሳይ መዝገብ፤
5. አባላት ያሉባቸውንና የፈጸሟቸውን ክፍያዎች የሚያሳይ መዝገብ፤
6. የጠቅላላ ጉባዔና የሥራ አመራር ኮሚቴ ስብሰባዎች ቃለጉባዔዎችን የያዘ መዝገብ፤
7. የተፈፀሙ ግብይቶችንና ውሎችን የያዘ መዝገብ፤
8. የንብረት ቆጠራ የተደረገበት መዝገብ ፤
9. ማኅበሩ በሚጠቀምበት የመስኖና ድሬኔጅ አውታር ላይ የተደረጉ ቁጥጥሮች ጥናቶችን እና ቅያሶችን የያዘ መዝገብ፤
10. የተካሄዱ ጥገናዎችን የሚያሳይ መዝገብ፤
11. ትክክለኛና የተሟሉ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች፤ እና
12. በማህበሩ ውስጥ ደንብ የተዘረዘሩ ሌሎች መዝገቦች፤

መያዝ አለበት፡፡

40.<u>ተቆጣጣሪው አካል መያዝ ስላለበት መዝገብ</u>

1. ተቆጣጣሪው አካል የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማኅበራትን መዝገብ ያቋቁማል፣ ይይዛል፡፡
2. በተቆጣጣሪው አካል የሚያዘው መዝገብ ስለእያንዳንዱ ማኅበር የሚከተሉትን ዝርዝር መረጃዎች መያዝ አለበት፡-
   ሀ) የማኅበሩን ስምና አድራሻ፤
   ለ) እያንዳንዱ ማኅበር የተመዘገበበትን ቀን፤
   ሐ) የአገልግሎት ክልሉን ስፋትና የሚገኝበትን ቦታ፤
   መ) የአባላቱን ቁጥር፤
   ሠ)የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላትንና የሒቀመንበሩን ስም፣ አድራሻና የስልክ ቁጥር፤
   ረ) ያለም ከሆነ ለማኅበሩ የተላለፈ የመንግሥት መሠረተ ልማትን ይዞታ የሚያሳይ ዝርዝር።
3. የኅብረተሰቡ አባላት በተቆጣጣሪው አካል ዘንድ የተቋቋመውን መዝገብ በማናቸውም መደበኛ የሥራ ሰዓቶች የማየት መብት ይኖራቸዋል።

41.<u>ክልል ተሻጋሪ የመስኖ ዉሃ ተጠቃሚዎች ማህበራት</u>

የአንድ ማኅበር የአገልግሎት ክልል ሁለትና ከሁለት በላይ የክልል መንግሥታትን የሚያካልል ሲሆን ስለማኅበሩ መመስረትና የሥራ ክንውን በሚመለከት ሚኒስቴሩ እንደተቆጣጣሪ አካል ሆኖ ይሠራል።

<u>ክፍል ሰባት</u>

<u>ስለማህበራት መፍረስ እና ሂሳብ ማጣራት</u>

42.<u>ስለማህበር መፍረስ</u>

አንድ ማኅበር፡-

1. የተመሠረተበት ዓላማ ሲቀር፤
2. የተመሠረተበትን ዓላማ ለመተግበር የማይችል ሆኖ ሲገኝ፤ ወይም
3. በማናቸውም ሌሎች ምክንያቶች የማኅበሩ ቀጣይነት የማያስፈልግ ሆኖ ሲገኝ፤

የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባዔ በሁለት ሦስተኛ ድምፅ እንዲፈርስ ሲወስንና ይኸው ውሳኔ ለተቆጣጣሪው አካል ቀርቦ ሲፀድቅ ሊፈርስ ይችላል።

43.<u>የማህበርን ሂሳብ ስለማጣራት</u>

1. በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 42 መሠረት አንድ ማኅበር እንዲፈርስ ሲወሰን የሥራ አመራር ኮሚቴው ወይም ተቆጣጣሪው አካል ሂሳብ አጣሪ መመደብ አለበት።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተመደበ ሂሳብ አጣሪ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-
   ሀ) የማኅበሩን መዛግብት፣ ሰነዶችና ንብረት በመረከብ ጉዳት እንዳይደርስ ያደርጋል፤
   ለ) የማኅበሩን ሀብትና ንብረት ይሰበሰባል፤
   ሐ) ከማኅበሩ ገንዘብ ጠያቂ የሆኑ ሰዎችን ይጠራል፤
   መ) የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባዔ በወሰነው እና በተቆጣጣሪው አካል በፀደቀው ውሳኔ መሠረት የማኅበሩን ሀብትና ንብረት ያከፋፍላል፤
   ሠ) የሂሳብ ማጣራቱን ሥራ በሚገባ ለማከናወን በሚያስፈልግ መጠን የማኅበሩን ሥራ ያንቀሳቅሳል፤
   ረ) ማኅበሩን የሚመለከቱ ክርክሮችን ያካሂዳል።
3. የማህበሩ የመፍረስ ሂደት እስኪጠናቀቅ ድረስ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች፣ የማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብና ውስጠ ደንብ በማኅበሩና በአባላቱ ላይ ተፈጻሚ መሆናቸው ይቀጥላል።
4. የሂሳብ አጣሪው የአገልግሎት ዋጋ ከማኅበሩ ሂሳብ የሚከፈል ይሆናል፡፡

44.<u>ማህበርን ከመመዝገብ ስለመሰረዝ</u>

1. የሂሳብ ማጣራቱ ሥራ እንደተጠናቀቀ ተቆጣጣሪው አካል ማኅበሩን ከመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማኅበራት መዝገብ ይሰርዛል።
2. ማኅበሩ ከመስኖ ዉሃ ተጠቃሚዎች ማኅበራት መዝገብ ከተሰረዘበት ቀን ጀምሮ እንደፈረሰ ይቆጠራል።

## <u>ክፍል ስምንት</u>
## <u>ስለፌዴሬሽኖች</u>

45.<u>ስለፌዴሬሽኖች መመስረት</u>

1. ዋናውን የመስኖና ድሬኔጅ አውታር በሙሉ ወይም በከፊል የሚያስተዳድር እና የመስኖ ውሃ ለተጠቃሚዎች የሚያቀርብ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማኅበራት ፌዴሬሽን ሊመሰረት ይችላል፡፡
2. የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማኅበራት ፌዴሬሽን በተቆጣጣሪው አካል ውሳኔ ወይም ፌዴሬሽኑ ያስተዳድረዋል ተብሎ ከሚጠበቀው ዋና የመስኖና ድሬኒጅ አውታር የመስኖ ውሃ ከሚጠቀሙ ማኅበራት በአብላጫዎቹ ውሳኔ ሊመሠረት ይችላል፡፡

3. ከአንድ ዋና የመስኖና የድሬኔጅ አውታር ውሃ ሊያገኙ የሚችሉ ማኅበራት ሁሉ ዋናውን የመስኖና የድሬኔጅ አውታር የሚያስተዳድረው ፌዴሬሽን አባል መሆን አለባቸው።
4. አንድ ፌዴሬሽን አባላት ከሆኑት ማኅበራት በስተቀር ለሌላ ለማንም የመስኖ ውሃ አያቀርብም፤ እንዲሁም ማኅበሩ በጽሑፍ ካልፈቀደ በስተቀር በማኅበሩ የአገልግሎት ክልል ውስጥ ማንኛውንም ተግባር ማከናወን አይፈቀድም።

46.<u>ስለፌዴሬሽን አሰያየም ስልጣንና ተግባር</u>

1. ማንኛውም ፌዴሬሽን የሚያስተዳድርበትን ቦታ ስም ወይም ሌላ የተለየ መጠሪያ ቀጥሎ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማኅበራት ፌዴሬሽን የሚል ቃላትን የያዘ የራሱ ልዩ ስም ይኖረዋል።
2. ፌዴሬሽን የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-
   ሀ) ዋና የመስኖና ድሬኔጅ አውታሩን ማስተዳደር፣ ሥራውን ማንቀሳቀስ፣ መጠገንና እንደአስፈላጊነቱም ለማሻሻል የሚያስፈልጉ ግንባታ ነክ ሥራዎችን ማካሄድ፤
   ለ) የመስኖ ውሃ ፍጆታን የሚመለከቱ የውስጥ ደንቦችን ማውጣትና ለአባል ማኅበራት ለሰጠው አገልግሎት ክፍያዎችን መሰብሰብ፤
   ሐ) አባላቱን በመወከል የመስኖ መሣሪያዎችን መግዛት፣ መተካት፣ ማንቀሳቀስና መጠገን፤
   መ) በአቅም ግንባታ ሥራዎች አባላቱን መደገፍ፡፡
3. ፌዴሬሽን ሕጋዊ ሰውነት ይኖረዋል። በዚህ ክፍል የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለማኅበራት ተፈፃሚ የሚሆኑ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች በፌዴሬሽኖችም ላይ ተፈፃሚዎች ይሆናሉ።
4. የፌዴሬሽን አባላት በፌዴሬሽኑ መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ እያንዳንዱ ማኅበር በማኅበሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ ውስጥ የሚሠሩ የተወሰነ ቁጥር ያላቸው አባላትን በመወከልና እነዚህ የኮሚቴ አባላትም የፌዴሬሽኑ ጠቅላላ ጉባዔ አባላት ሆነው እንዲሠሩ ሊስማሙ ይችላሉ።

## ክፍል ዘጠኝ

## ስለመስኖና ድሬኔጅ

### 47.ዘመናዊ የመስኖና ድሬኔጅ አዉታሮችን ስለማስተላለፍ

1. የመሠረተ ልማት አካሉ አንድ ዘመናዊ የመስኖ ድሬኔጅ አውታር በመንግስት ወጪ ከተገነባ ወይም መልሶ ከታደሰ የዚህ መስኖና ድሬኔጅ አውታር የተወሰነ ክፍል በአንድ ማኅበር አገልግሎት ክልል ውስጥ የሚገኝ ከሆነ ወጪን የማስመለስ መርህን ተከትሎ ከማኅበሩ ጋር በሚደረስ ስምምነት የተጠቃሚነት መብቱን ለማኅበሩ ሊያስተላልፍ ይችላል።
2. አንድ ማኅበር በአገልግሎት ክልሉ ውስጥ በመንግስት ወጪ የተገነባ ወይም መልሶ የታደሰ ዘመናዊ የመስኖና ድሬኔጅ አውታር የተወሰነ ክፍል የተጠቃሚነት መብት ላልተወሰነ ጊዜ ተላልፎ እንዲሰጠው አግባብ ላለው መሠረተ ልማት አካል ማመልከት ይችላል፡፡
3. የውሃ አቅርቦት መገኛ ቦታ ግድብ፣ የውሃ መጥለፊያ ውቅር፣ የፓምፕ ጣቢያ ወይም ሌላ ዓይነት መሠረተ ልማት በአንድ ማኅበር የአገልግሎት ክልል ውስጥ የሚገኝ የሆነ እንደሆነ ውሃውን ከወንዝ፣ ከጅረት፣ ከማጠራቀሚያ ከኩሬ ወይም ከሌላ ተፈጥሯዊ መገኛ ለመውሰድ የሚያገለግለው መሠረተ ልማት ለማኅበሩ አገልግሎት መስጠት እንዲችል ሊተላለፍ ይችላል፡፡
4. የመስኖና ድሬኔጅ አውታር ማስተላለፊያ ስምምነት ሰነድ በተወሰነ ቅጽ ሆኖ፡-
   ሀ) የሚተላለፈው የመስኖና የድሬኔጅ አውታር ያለበትን ሁኔታ ዝርዝር መረጃ፣ እና
   ለ) የመሠረተ ልማቱን ጥገና አስመልክቶ ስምምነት ያደረጉት ወገኖች ያላቸውን መብቶችና ግዴታዎች፣

   የሚያካትት መሆን አለበት፡፡
5. የመሠረተ ልማት አካሉ ለማኅበሩ ያልተላለፈና በራሱ ቁጥጥር ሥር የሚገኙ የመስኖና ድሬኔጅ አውታር የተወሰኑ ክፍሎችን በሚገባ ተጠብቀውና ተጠግነዉ መያዛቸዉን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡

### 48.ለባህላዊ መስኖና ድሬኔጅ አዉታሮች መጠቀሚያ የምስክር ወረቀት

1. አንድ ማኅበርበአገልግሎት ክልሉ ውስጥ ስለሚገኝ ባህላዊ የመስኖና ድሬኔጅ አውታር በሚመለከት የመጠቀሚያ ምስክር ወረቀት እንዲሰጠው አግባብ ላለው የመሠረተ ልማት አካል ማመልከት ይችላል፡፡

2. የመጠቀሚያ ምስክር ወረቀቱ የባህላዊ መስኖና ድሬኔጅ አውታሩን ዋና ዋና የሆኑ መግለጫዎችን የሚይዝና ማኅበሩ በአውታሩ ለመጠቀም ያለውን መብት የሚያረጋግጥ ይሆናል፡፡

## 49.<u>መረጃን ስለማስተላለፍና ስለቴክኒክ ቁጥጥር</u>

1. አንድ ማኅበር ስለተላለፈለት የመስኖና የድሬኔጅ አውታር ጥገናና ስለሚገኝበት ሁኔታ ወቅታዊ መረጃ አግባብ ላለው መሠረተ ልማት አካል መስጠት አለበት፡፡
2. ከመሠረት ልማት አካሉ ሥልጣን የተሰጠዉ ሰራተኛ ወደ አገልግሎቱ ክልሉ በመግባት ለማህበሩ የተላለፈዉ የመስኖና የድሬኔጅ አውታር ያለበትን ሁኔታ ቁጥጥር ማድረግ ይችላል፡፡
3. በመሠረተ ልማት አካሉ የተወከለው ሠራተኛ ቁጥጥር ካደረገ በኋላ በተገኘው መረጃ መሠረት፡-
   ሀ) በመስኖና የድሬኔጅ አውታሩ ላይ ጉዳት ወይም ጥፋት እንዳይደርስ ወይም
   ለ) በመስኖና ድሬኔጅ አውታሩ አጠቃቀም ምክንያት በመንግሥት ወይም በሦስተኛ ወገን ንብረት ላይ ጉዳት እንዳይደርስ፣

   አንደጉዳዩ አስቸኳይነት የተወሰኑ ሥራዎች እንዲሰሩ ማኅበሩን ማዘዝ ይችላል፡፡

## 50.<u>ስለንብረት አገልግሎት</u>

አንድ ማኅበር ለማኅበርተኞች ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የመስኖና ድሬኔጅ አውታር ለማደስ ወይም ለማልማት የአንድን መሬት አገልግሎት ማግኘት አስፈላጊ ሲሆን በተቆጣጣሪው አካል ተቀባይነት ሲያገኝና አግባብ ባለው ህግ መሠረት ለባለመሬቱ ካሣ አስቀድሞ ሲከፍል ይፈቀድለታል።

## <u>ክፍል አስር</u>

## <u>ለማህበራት ስለሚሰጡ አገልግሎቶች</u>

## 51.<u>ስለ አገልግሎት ሰጪዎች</u>

1. አንድ ማኅበር ለአገልግሎት ክልሉ የሚውል ውሃ የሚያገኘው በፌዴሬሽን ከማይተዳደር የዉሃ ማስተላለፊያ በር፣ የፓምፕ ጣቢያ ወይም በአንድ ዋና የመስኖና ድሬኔጅ አውታር ላይ ከሚገኝ ሌላ መሠረተ ልማት ሲሆን፣ የመስኖ ውሃን ወይም ተዛማጅ አገልግሎቶችን ለማኅበሩ የሚያቀርበው ዋና የመስኖና ድሬኔጅ አውታሩን ኦፕሬሽንና ጥገና የሚያካሂደው አገልግሎት ሰጪ ይሆናል፡፡

2. መንግስታዊ አገልግሎት ሰጪዎች የሚቋቋሙበት ሁኔታ እና ለግል የአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ፈቃድ የሚሰጥበት ሁኔታ ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።
3. አገልግሎት ሰጪው ለአንድ ማኅበር የመስኖ ውሃና ሌሎች ተዛማጅ አገልግሎቶችን የሚሰጠው ከማኅበሩ ጋር በተዋዋሉት ስምምነት መሠረት ይሆናል፡፡

## 52.ስለአገልግሎት አቅርቦት ስምምነት

1. ማንኛውም የአገልግሎት አቅርቦት ስምምነት የቆይታ ጊዜ ከአሥር ዓመት ማነስ የለበትም፤ ሆኖም በአገልግሎት ተቀባይ ጥያቄ መሠረት ከአምስት ዓመት የማያንስ ነገር ግን ከአሥር ዓመት በታች ለሆነ ጊዜ መሰማማት ይቻላል።
2. ማንኛውም የአገልግሎት ስምምነት ወጥነት ያለው ሆኖ በተለይ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፡-
   ሀ) የውሃ መገኛውን ቦታ መረጃ፤
   ለ) በዓመት የመስኖ ውሃ አገልግሎት የሚሰጥበት ወቅት፤
   ሐ) በመስኖ ወቅት ውሃ ለማግኘት የሚቀርብ የጥያቄ አቀራረብ ሥነ ሥርዓት፤
   መ) አገልግሎት ሰጪው ውሃ በሚያቀርብበት ሁኔታ ላይ በሌሎች አግባብ ባላቸው አካላት የሚደረግበት ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በየወሩ በሚወጣው መርሐ ግብር መሠረት ማኅበሩ በእያንዳንዱ የመስኖ ወቅት የሚያስፈልገውን ከፍተኛ የውሃ መጠን፤
   ሠ) የውሃ ብክነትን፣ ብክለትንና ጨዋማነትን ለመቀነስ የሚወሰዱ እርምጃዎች፤
   ረ) የውሃ አገልግሎት ክፍያን እና የአከፋፈሉን ሁኔታ፤
   ሰ) ኃላፊነትንና በውሃ አጠቃቀም ላይ የተጣሉ ገደቦችን፤
   ሸ) የውል ግዴታዎችን ባለመፈፀም የሚወስኑ ቅጣቶችን፤ እና
   ቀ) ውጤታማ የውሃ አጠቃቀምን ተግባራዊ ለማድረግ ወይም ውሃ ማቅረብን አስመልክቶ በአገልግሎት አቅራቢው የውሃ ማቅረብ ፈቃድ ውስጥ የተመለከቱ ሌሎች ግዴታዎችን ለማስፈፀም አስፈላጊ የሆኑ ሁኔታዎች፡፡

## 53.ስለ አገልግሎት ዉሎች መሻሻል

1. የአገልግሎት ውሎች የሚሻሻሉት ወይም የሚለወጡት በሁለቱ ወገኖች ስምምነት መሠረት ይሆናል፡፡

2. በአገልግሎት አቅርቦት ስምምነቱ መሠረት አገልግሎት ሰጪው የውሃ እና ሌሎች አገልግሎቶችን አግዶ ሊያቆይ የሚችለው ማኅበሩ ያለበትን ክፍያ ከ120 ቀናት በላይ ሳይፈጽም የዘገየ እንደሆነ ብቻ ነው።
3. በዚህ አዋጅ መሠረት የተፈፀመ የአገልግሎት ስምምነት ሊሠረዝ የሚችለው፡-
   ሀ) ከሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች መካከል አንዱ ስምምነቱን በተደጋጋሚ ባለማክበሩበፍርድ ቤት የተወሰነ፤ ወይም
   ለ) ማኅበሩ የፈረሰ፤ እንደሆነ ነው፡፡

## 54.የአገልግሎት ሰጪዉ ሃላፊነት

1. አንድ አገልግሎት ሰጪ በአገልግሎት ስምምነቱ መሠረት የውሃ መጠን ባለማቅረቡ፣ ወይም በስምምነቱ የጊዜ መርሐ ግብር መሠረት ውሃ ባለማቅረቡ ማኅበሩ ለደረሰበት ጉዳት ተመጣጣኝ ካሣ የመክፈል ኃላፊነት አለበት፡፡
2. አገልግሎት ሰጪው ለማኅበሩ የመስኖ ውሃ ለማቅረብ ካለመቻሉ የተነሳ ኪሣራ የደረሰበት ማንኛውም የማኅበር አባል ከአገልግሎት ሰጪው ላይ ካሣ ለመጠየቅ የሚሰላውን የካሳ መጠን ለማስላት እንደ አንድ የውሉ ተካፋይ ሆኖ ይቆጠራል።
3. አገልግሎት አቅራቢው የመስኖ ውሃውን ለማቅረብ ያልቻለው በኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ሕግ እንደተመለከተው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የሆነ እንደሆነ ለተጎጂው ካሣ ሊከፈል አይችልም።

## 55.ስለ ዉሃ አቅርቦት ዋጋ አወሳሰን

1. አንድ ማኅበር ለአንድ አገልግሎት ሰጪ የሚከፍለው የውሃ አቅርቦት ዋጋ መጠን በተቆጣጣሪ አካል ይወሰናል፡፡
2. ተቆጣጣሪው አካል አንድ ማኅበር ለአገልግሎት ሰጪ የሚከፍለውን የውሃ አቅርቦት ዋጋ መጠን የሚወሰነው፡-
   ሀ) የማኅበሩ አባላት ለአስፈላጊ ጥገና ማስቀመጥ ያለባቸውን ገንዘብ፤
   ለ) የማኅበሩ አባላት ለመስኖ ውሃ አቅርቦት ለመክፈል ያላቸውን አቅም፤ እና
   ሐ) አገልግሎት ሰጪው ለኢንቨስትመንት ካዋለው ገንዘብ የተመጣጠነ ጥቅም የሚያገኝበትን ሁኔታ፤

   በማመዛዘን ይሆናል፡፡

## ክፍል አስራ አንድ

## ስለክርክር አወሳሰን

### 56.ስለክርክር አወሳሰን ኮሚቴ

1. እያንዳንዱ ማኀበር በጠቅላላ ጉባዔ የሚመረጡ መልካም ስም ያላቸው እና የማያዳሉ ከአምስት የማይበልጡ አባላት ያሉበት የክርክር አወሳሰን ኮሚቴ ይኖረዋል።
2. የክርክር አወሳሰን ኮሚቴ አባላት የስራ ዘመን አራት ዓመት ይሆናል፤ የኮሚቴ አባላት በተከታታይ ከሁለት የሥራ ዘመን በላይ ሊመረጡ አይችሉም።
3. ለክርክር አወሳሰን በጠቅላላ ጉባዔ የተመረጡ አባላት ከመካከላቸው አንዱን አባል የኮሚቴዉ ሊቀመንበር አድርገው ይመርጣሉ።
4. አንድ የሥራ አመራር ኮሚቴ አባል በተመሳሳይ ጊዜ የክርክር አወሳሰን ኮሚቴ አባል ሆኖ ማገልገል አይችልም።

### 57.የክርክር አወሳሰን ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር

1. የክርክር አወሳሰን ኮሚቴ፡-
   ሀ) በውሃ አጠቃቀም እና ድልደላ ምክንያት በማኀበሩ አባላት መካከል የሚነሱ ክርክሮችን፤
   ለ) መተዳደሪያ ወይም የውስጥ ደንቦች በመጣሳቸው ምክንያት የሚቀርቡ አቤቱታዎችን፤
   ሐ) የውሃ ክፍፍል መርሀ ግብር አለማክበርን፤ እና
   መ) በሥራ አመራር ኮሚቴ በሚሰጡ አስተዳደራዊ ውሳኔዎች ላይ የሚቀርቡ ይግባኞችን፤

   የሚመለከቱ ጉዳዮችን ሰምቶ ውሳኔ የመስጠት ስልጣንና ተግባር ይኖረዋል።
2. የክርክር አወሳሰን ኮሚቴ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከፊደል ተራ (ሀ) እስከ (ሐ) ከተመለከቱ ምክንያቶች በአንዱ አቤቱታ በጽሁፍ ወይም በቃል ሲቀርብለት፡-
   ሀ) መጀመሪያ የክርክሩን ምንጭ በሊቀመንበሩ አማካይነት በአስቸኳይ ያጣራል፤
   ለ) አቤቱታው የቀረበው በጽሁፍ እንደሆነ ለተከሰሰው ሰው እንዲደርሰው እና በቀጠሮ ቀን መልስ ይዞ ቀርቦ እንዲከራከር መጥሪያ ይልካል፤
   ሐ) የኮሚቴው ሊቀመንበር በሁለት ቀናት ውስጥ ጉዳዩን ለማየት ለክርክር አወሳሰን ኮሚቴ አባላት ጥሪ ያስተላልፋል፤

መ) በተያዘው ቀን ቀጠሮ ሁለቱንም ተከራካሪ ወገኖች ይሰማል፣ የጽሁፍ ማስረጃዎቻቸውን ይመረምራል፣ አስፈላጊም ሲሆን ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቦታ ድረስ በመሄድ ጉዳዩን ያጣራል፤

ሠ) ከሁለት ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ውሳኔ በመስጠት ለተከራካሪ ወገኖች ያሳውቃል።

## 58. አፈፃፀም

በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠ ማንኛውም ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ በፍትሐብሔር ችሎት እንደተሰጠ ውሳኔ ተቆጥሮ በይግባኝ እስካልተሻረ ድረስ የሚፈፀም ይሆናል፡፡

## 59. ስለይግባኝ

በክርክር አወሳሰን ኮሚቴ ታይቶ በተሰጠ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ማንኛውም ወገን ለክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

# ክፍል አስራ ሁለት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 60. አስተዳደራዊ ቅጣቶች

1. አንድ አባል፡-

ሀ) የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባዔ ያፀደቀውን መተዳደሪያ ደንብ ወይም ማናቸውንም የውስጥ ደንቦች ያላከበረ እንደሆነ፤

ለ) በመተዳደሪያ ደንቡና በዚህ አዋጅ መሠረት የተወሰኑትን ክፍያዎች በወቅቱ ያልከፈለ እንደሆነ፣ ወይም በሚያስፈልግ ጊዜ የጉልበት ሥራ አስተዋጽዖ ያላደረገ እንደሆነ፤

ሐ) የመስኖ ውሃን ማኅበሩ ባወጣው መርሐ ግብር መሠረት የማይጠቀም ከሆነ፤

መ) ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት በማንኛውም የማኅበሩ ንብረት ወይም መሣሪያ ላይ ላደረሰው ጉዳት የማስጠገኛ ወይም የመተኪያ ወጪ ለመክፈል ፈቃደኛ ካልሆነ፤

ሠ) ስለመሬቱ ወይም ስለውሃ አጠቃቀሙ ለማኅበሩ ተገቢውን መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆነ፤

ረ) የማኅበሩን ሠራተኞች ወይም በማኅበሩ የታዘዙ ሌሎች ሰዎች የመስኖ መስመሩን የኦፕሬሽንና ጥገና ስራ ለማካሄድ እንደአስፈላጊነቱ ተሽከርካሪ ወይም መሳሪያ ይዘዉ ሲሄዱ ወደ መሬቱ እንዳይገቡ የተከለከለ ከሆነ፤ ወይም

ሰ) የመስኖና ድሬኔጅ አዉታሩን ኦፕሬሽን የሚመለከቱ ቴክኒካዊ ደንቦችን ለማክበር ፈቃደኛ ካልሆነ፣

ማኅበሩ አስተዳደራዊ ቅጣት መጣል ይችላል።

2. የቅጣት ዓይነትና መጠን በእያንዳንዱ ማኅበር መተዳደሪያ ደንብ የሚወሰን ሲሆን በዋናነት የገንዘብ ቅጣት ወይም የመስኖ ውሃ አቅርቦትን ጨምሮ አገልግሎትን ማቋረጥ ሊሆን ይችላል፡፡
3. ቅጣት የሚጣለው በሥራ አመራር ኮሚቴው ሲሆን ለክርክር አወሳሰን ኮሚቴ ይግባኝ ሊቀርብበት ይችላል፡፡

61. <u>ቅጣትን ለማስፈጸም የሌሎች አካላት ትብብር</u>

ጥፋት በፈፀመው አባል ላይ የተጣለውን ቅጣት በማስፈፀም ረገድ የወረዳና የቀበሌ መስተዳድር የሥራ ኃላፊዎች ለማኅበሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ ድጋፍ መስጠት አለባቸው።

62. <u>ማህበራት ከአካባቢ አስተዳደር አካላት ጋር ስለሚኖራቸዉ ግንኙነት</u>

1. የክልል መንግሥታት ወይም በወረዳና በቀበሌ ደረጃ የሚገኙ የሥራ ኃላፊዎች ከማኅበራቱ የሥራ አመራር ኮሚቴዎች የጽሑፍ ጥያቄ ካልቀረበላቸው በስተቀር ማኅበራቱ በሚቋቋሙበት ጊዜም ሆነ ሥራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት ጣልቃ መግባት የለባቸውም፡፡
2. የወረዳና የቀበሌ መስተዳድር መዋቅሮች በሥልጣን ክልላቸው ውስጥ ለሚገኙ ማኅበራት የአሠራር ነጻነታቸውን በማክበር ለሥራ እንቅስቃሴያቸው ተገቢነት ያለው ድጋፍ መስጠት አለባቸው።
3. የአንድ ማኅበር የአገልግሎት ክልል የውሃዉን የተፈጥሮ አወራረድ ተከትሎ ከአንድ ክልል፣ ወረዳ ወይም ቀበሌ አስተዳደር ወሰን ወደ ሌላው ክልል፣ ወረዳ ወይም ቀበሌ አስተዳደር ወሰን የሚሻገር ከሆነ ከእያንዳንዱ አስተዳደር አካል የሚወከሉ አባላት ያሉበት ኮሚቴ የማኅበሩን ጉዳይ በተመለከተ ከአስተዳደር መዋቅሩ ጋር አገናኝ ሆነው ይሰራሉ፡፡

63.**የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

1. በኅብረት ሥራ ማኅበራት አዋጅ ቁጥር 147/1991 (በአዋጅ ቁጥር 402/1996 እንደተሻሻለው[41] የተቋቋመ የመስኖ የኅብረት ሥራ ማኅበር ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ በሁለት ዓመታት ውስጥ በዚህ አዋጅ መሠረት የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማኅበር ሆኖ እንደገና ይመዘገባል።
2. የመስኖና ድሬኔጅ ሥራ ሲያካሂድ የነበረው የኅብረት ሥራ ማኅበር የመስኖና የድሬኔጅ ውሃ አውታር ሥራዎችን የሚያካሂድና ኃላፊነት የሚቀበል ማኅበር ስለሚመሠረትበት ሁኔታ ድጋፍ ይሰጣል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት አንድ ማኅበር ከተመሰረተ በኋላ ድጋፍ ሲሰጥ የነበረው ነባሩ የኅብረት ሥራ ማኅበር፡-
   ሀ) በመስኖና ድሬኔጅ አውታሩ ላይ ያሉትን መብቶቹንና ግዴታዎቹን አዲስ ለተመሰረተው ማኅበር በነፃ ያስተላልፋል፣
   ለ) አዲስ ከተመሰረተው ማኅበር ጋር በማኅበሩ አገልግሎት ክልል ውስጥ ለሚካሄድ የመስኖ ግብርና ድጋፍ ለማድረግ በትብብር ይሰራሉ፡፡

64.**ተፈጻሚ የማሆኑ ህጎች**

ይህንን አዋጅ የሚቃረን ማናቸውም ሕግ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ የተሸፈኑ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈፈሚነት አይኖረውም።

65.**ደንቦችና መመሪያዎችን የማዉጣት ስልጣን**

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህንን አዋጅ በሚገባ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል።
2. ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1 )መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

66.**አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ መስከረም 17 ቀን 2006 ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ**

**ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

[41] በ23/7 (2009) አ. 985 ተሸሯል፡፡

ረ) የአከባቢ ጥበቃ

## አዋጅ ቁጥር 295/ 995

## የአካባቢ ጥበቃ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ

በአንድ በኩል የአካባቢ ልማትና አያያዝ የሥራ እንቅስቃሴዎችን፣ በሌላ በኩል የአካባቢ ጥበቃ፣ ቁጥጥርና ክትትል ተግባራትን ለተለያዩ አካላት መስጠት የሥራ ኃላፊነቶች አለመጣጣምንና የሥራ ድግግሞሽን በማስወገድ በአካባቢያዊ ሀብቶች በዘላቂነት ለመጠቀም የሚረዳ በመሆኑ፣

በፌዴራልና በክልል የአካባቢ ጥበቃ መሥሪያ ቤቶች መሀል የተቀናጀ፣ ነገር ግን የየቅሉ የሆነ ኃላፊነትን የሚያጠናክር ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55(1 መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የአካባቢ ጥበቃ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 295)1995" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

   1. ‹‹ባለሥልጣን›› ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 መሠረት እንደገና የተቋቋመው የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ነው፤[42]
   2. ‹‹አግባብ ያለው መሥሪያ ቤት›› ማለት ቃሉ የተጠቀሰበት ድንጋጌ በሚነካው ጉዳይ ላይ በሕግ የተሰጠ ኃላፊነት ያለው የፌዴራል ወይም የክልል መንግሥት አካል ነው፤

[42] በ25)08 (2011) አ. 1097 አንቀጽ 36/17 መሰረት የአካባቢ፣ የደን እና አየር ለውጥ ኮሚሽን ሆኗል፡፡

3. ‹‹አካባቢ›› ማለት በመሬት በከባቢ አየር፣ በአየር ሁኔታ እና በአየር ንብረት፣ በውሃ፣ በሕያዋን፣ በድምፅ በሽታ፣ በጣዕም፣ በማኅበራዊ ጉዳዮች እና በሥነ ውበት ሳይወሰን፣ በተፈጥሮአዊ ሁኔታቸው ወይም በሰው አማካኝነት ተሻሽለው ወይም ተለውጠው የሚገኙ ነገሮች በሙሉ ያሉበት ቦታ፣ እንዲሁም መጠናቸውን ወይም ሁኔታቸውን ወይም ደግሞ የሰው ወይም የሌሎች ሕያዋን በጎ ሁኔታን የሚነኩ ተስተጋብሮቶቻቸው ድምር ነው፤
4. ‹‹የአካባቢ ጥበቃ አካላት›› ማለት ባለሥልጣኑ፣ ምክር ቤቱና በዚህ አዋጅ አንቀጽ 14 እና 15 ድንጋጌዎች የተጠቀሱት የዘርፍ የአካባቢ አሃዶችና የክልል የአካባቢ መ)ቤቶች ናቸው፤
5. ‹‹አደገኛ ነገር›› ማለት በሰው ጤና ወይም በአካባቢ ላይ ጉዳት የሚያደርስ ጠጣር፣ ፈሳሽ ወይም የጋዝነት ባህሪይ ያለው ነገር ወይም ተክል፣ እንስሳ ወይም ረቂቅ ሕዋስ ነው፤
6. ‹‹ጥበቃ››ማለት የተፈጥሮ ባህርይ እንዳይናጋ በመጠበቅና የተፈጥሮ ሀብቶች ምንጭ አቅምን በማጎልበት፣ የአሁኑን ትውልድ ፍላጎት የማርካቱ ሂደት የመጪውን ትውልድ ዕድል ሳያሰናክል እንዲሟላ ማስቻል ነው፤
7. ‹‹ሰዉ››ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
8. ‹‹ክልል›› ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47/1 የተመለከቱት የአገሪቷ ክፍሎች ማለት ሲሆን፣ ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ አስተዳደሮችንም ይጨምራል፤
9. ‹‹የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት›› ማለት ለአካባቢና ለተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ወይም ቁጥጥር በክልሉ ኃላፊነት የተሰጠው ማንኛውም የክልል የመንግሥት አካል ነው።

## ክፍል ሁለት[43]

## ክፍል ሦስት

## የዘርፍ፣ የአካባቢ አሀዶችና የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤቶች

### 14. የዘርፍ የአካባቢ አሀዶች

እያንዳንዱ አግባብ ያለው መሥሪያ ቤት የሥራ እንቅስቃሴዎቹ ከዚህ አዋጅና ከሌሎች የአካባቢ ጥበቃ ግዴታዎች ጋር ተጣጥመው መካሄዳቸውን የመከታተልና የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለው የአካባቢ አሀድ በሥሩ ያቋቁሟል ወይም ይሰይማል፡፡

### 15. ስለክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤቶች

1. እያንዳንዱ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በኢትዮጵያ የአካባቢ ፖሊሲና እንክብካቤ ስልት በመመስረትና በውሳኔ ሂደት ሕዝቡን በማሳተፍ፣
   ሀ) የክልሉን የአካባቢ ስልት የሚያዘጋጅ፣እንዲሁም የአተገባበር፣ የግምገማና የክለሳ ሥራዎችን የሚያስተባብር፤
   ለ) የክልሉን የአካባቢ ሁኔታ ክትትል፣ ጥበቃና ቁጥጥር ተግባር የሚያከናውን፤ ራሱን የቻለ የአካባቢ መሥሪያ ቤት ያቋቁማል ወይም ከነባር መሥሪያ ቤቶች መካከል አንዱን ለዚሁ ተግባር ይሰይማል፡፡
2. የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤቶች የፌዴራል የአካባቢ ደረጃዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣሉ እንደአስፈላጊነቱም ከፌደራሉ የጠበቁ ደረጃዎችን በማውጣት ሥራ ላይ ሊያውሉ ይችላሉ፡፡
3. የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤቶች የየክልላቸውን የአካባቢና የዘላቂ ልማት ሁኔታ በተመለከተ ዘገባ በማዘጋጀት ለባለሥልጣኑ ያቀርባሉ፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 16 የተሻሩ ህጎች

1. የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 9)1987 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡
2. ከዚህ አዋጅ ጋር ተቃራኒ የሆኑ ሕጎች በዚህ አዋጅ ዉስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸዉም፡፡

---

[43] በዚህ ክፍል ውስጥ ከአንቀፅ 3 እስከ 13 ድረስ ያሉ ድንጋጌዎች በ19)61 (2005 አ. 803አንቀፅ 2(5 መሰረት ተሰርዘዋል፡፡

17 **<u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ ከጥቅምት 21 ቀን 1995 ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥቅምት 21 ቀን 1995 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌደረላዊ ዲሞክራሲያዊ**

**ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## አዋጅ ቁጥር 299/1995

## የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ አዋጅ

የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ፣ የልማት ሃሣብ ንድፍ ሲዘጋጅ ቦታው ሲመረጥ፣ ሲገነባ ወይም ሲተገበር እንደዚሁም በመተግበር ላይ ያለ እንቅስቃሴ ሲሻሻል ወይም ሲቋረጥ የሚያስከትለውን ተፅዕኖ በመተንበይና አስቀድሞ በማረም በውል የታሰበበትን ልማት ለማምጣት የሚያግዝ በመሆኑ፣

መንግሥታዊ ሰነድ በአካባቢ ላይ ሊያስከትለው የሚችለውን ተፅዕኖ ለመለየት ገናከመፅደቁ በፊት መገምገም፣ የመፅደቂያው ውሳኔ በሚሰጥበት ወቅት አካባቢያዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊናማህበራዊ ታሳቢዎችንና ግቦችን ዘላቂ ልማትን ለማምጣት በሚያመች ሁኔታ እንዲዋሃዱና እንዲቀናጁ ለማድረግ የሚያስችል በመሆኑ፣

አሉታዊ የአካባቢ ተፅዕኖዎችን መተንበይ፣ የመፍትሔ እርምጃዎችን መውሰድና ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቃሚነታቸውን ማዳበር በሕገ መንግሥት የተደነገጉትን የአካባቢ ደህንነት መብቶችንና ዓላማዎችን የመተግበርን ሂደት የሚያግዝ በመሆኑ፣ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አስተዳደራዊ ግልፅነትና በኃላፊነት ተጠያቂነት እንዲኖር ለማድረግ፣ በአጠቃላይ ራሱንና አካባቢውን በሚመለከቱ የልማት እቅዶች አወጣጥና ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ሕዝቡን፣ በተለይም ደግሞ ማሕበረሰቦችን ለማሳተፍ የሚረዳ በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55 (1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### ክፍል አንድ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ"የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አዋጅ ቁጥር 299/1995" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

   1. "ባለሥልጣን›› ማለት የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ማለት ነው፤[44]

[44] በ25)08 (2011 አ.1097 አንቀጽ 36(17 መሰረት የአካባቢ፣ የደን እና አየር ለውጥ ኮሚሽን ስለሆነ በአዋጁ ውሰጥ ባለስልጣኑ የሚለው በዚሁ ተተክቶ ይነበብ፡፡

2. ‹‹አካባቢ›› ማለት በመሬት፣ በከባቢ አየር፣ በአየር ሁኔታ እና በአየር ንብረት፤ በውሃ፤ በህያዋን፤ በድምፅ፤ በሽታ፣ በጣእም፤ በማህበራዊ ጉዳዮች እና በስነ ውበት ሳይወሰን፣ በተፈጥሮአዊ ሁኔታቸው ወይም በሰው አማካኝነት ተሻሽለው ወይም ተለውጠው የሚገኙ ነገሮች በሙሉና ያሉበት ቦታ፣ እንዲሁም መጠናቸውን ወይም ሁኔታቸውን ወይም ደግሞ የሰው ወይም የሌሎች ሕያዋን በጎ ሁኔታን የሚነኩ ተስተጋብሮቶቻቸው ድምር ነው፤
3. ‹‹የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ›› ማለት አንድ ፕሮጀክት ወይም መንግሥታዊ ሠነድ ተግባራዊ ሲሆን የሚያስከትለውን ገንቢም ሆነ አፍራሽ ውጤት በቅድሚያ ለይቶ የማወቂያና የመመዘኛ ዘዴ ነው፤
4. ‹‹ተፅዕኖ›› ማለት በአካባቢ ወይም በንዑሳን ክፍሎቹ ላይ በሚፈጠር ለውጥ ምክንያት ማንኛውም በሰው ጤና ወይም ደህንነት፣ በዕፅዋት፤ በእንስሳት፣ በአፈር፣በአየር፣ በውሃ፣ በአየር ንብረት፣ በተፈጥሮአዊ ወይም በባህላዊ ቅርስ፣ በሌላ ቁሳዊ ቁም አካል፣ወይም በአጠቃላዩ ሲታይ በአካበቢያዊ፣ በማሕበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊ ወይም በባሕላዊ ገፅታዎች ላይ የሚከሰት ተከታይ ለውጥ ነው፤
5. ‹‹የፈቃድ ሰጪ መሥሪያ ቤት›› ማለት እንደሁኔታው የኢንቨስትመንት፤ የንግድ ወይም የሥራ ፈቃድ ለመስጠት ወይም፤የንግድ ድርጅት ለመመዝገብ በሕግ ሥልጣን የተሰጠው ማንኛውም የመንግሥት አካል ነው፤
6. ‹‹ሰው›› ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
7. ‹‹በካይ›› ማለት ፈሳሽ፤ ጠጣር ወይም ጋዝ የሆነ፣ በቀጥታም ሆነ ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ፤
   ሀ) ያረፈበትን የአካባቢ ክፍል ጥራት በመለወጥ ጠቀሜታ የመስጠት አቅሙን የሚያጓድል፣ ወይም
   ለ) በሰው ጤና ወይም በሌሎች ሕያዋን ላይ ጉዳት የሚያደርስ ወይም ሊያደርስ የሚችል መርዝን፣በሽታን፣ ክርፋትን፣ ጨረርን፣ ድምፅን፣ ንዝረትን፣ ሙቀትን ወይም ሌላ ክስተትን የሚያመነጭ፣ ማንኛውም ነገር ነው፤
8. ‹‹ፕሮጀክት›› ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ በማንኛውም መመሪያ ውስጥ በተጠቀሰ ርዕስ የሚካተት ማንኛውም አዲስ የልማት እንቅስቃሴ፣ ወይም በነባር ድርጅት ላይ የሚደረግ ጉልህ መስፋፋት ወይም ለውጥ፣ ወይም ደግሞ ተቋርጦ የነበረ ሥራን መልሶ ለመጀመር የሚደረግ እንቅስቃሴ ነው፤

9. ‹‹የፕሮጀክት ባለቤት›› ማለት ፕሮጀክቱ በመንግሥት የተወጠነ ሲሆን የሚመለከተው የመንግሥት አካል፣ ወይም በግሉ ዘርፍ የተወጠነ ሲሆን ባለሀብት የሆነው ሰው ነው፤
10. ‹‹መንግሥታዊ ሠነድ›› ማለት ፖሊሲ፣ ስልት፣ መርሐ ግብር፣ ሕግ ወይም የዓለም አቀፍ ስምምነት ነው፤
11. ‹‹ክልል›› ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47)1)የተመለከቱት የአገሪቱ ክፍሎች ማለት ሲሆን፤ ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ አስተዳደሮችንም ይጨምራል፤
12. ‹‹የክልል የአካባቢ መ)ቤት›› ማለት ለአካባቢና ለተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ወይም ቁጥጥር በክልሉ ኃላፊነት የተሰጠው ማንኛውም የክልል የመንግሥት አካል ነው።

## ክፍል ሁለት

### 3. ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. ማንም ሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 በወጣ መመሪያ መሠረት የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ የሚያስፈልገውን ማንኛውንም ፕሮጀክት፣ ከባለሥልጣኑ ወይም ከሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት ይሁንታ ሳያገኝ ተግባራዊ ለማድረግ አይፈቀድለትም፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ከሚያስፈልገው ማንኛውም ፕሮጀክት የሚከተለውን ተፅዕኖ ኢምንት ነው ብሎ ከገመተ የፕሮጀክቱን ባለቤት የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ እንዲያካሂድ ላያስገድደው ይችላል፡፡
3. ማንኛውም ፈቃድ ሰጪ መሥሪያ ቤት የኢንቨስትመንት፣ የንግድ ወይም የሥራ ፈቃድ ከመሥጠቱ በፊት ከባለሥልጣኑ ወይም ከሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት ፕሮጀክቱ ተግባራዊ እንዲሆን ይሁንታ መስጠቱን ማረጋገጥ አለበት፡፡
4. የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ዘገባ ተቀባይነት ማግኘቱና ከባለሥልጣኑ ወይም ከሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት ይሁንታ መስጠቱ የፕሮጀክቱን ባለቤት ጉዳት በማድረስ ከሚከተል ኃላፊነት ነፃ አያደርገውም።

5. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከተጠያቂነት ነፃ መሆን የሚቻለው ጉዳቱ በተጎጂው በራሱ ወይም ደግሞ የፕሮጀክቱ ባለቤት ኃላፊነት በሌለበት በሦስተኛ ወገን መድረሱ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡

4. <u>የተፅዕኖ መወሰኛ ታሳቢዎች</u>

1. የፕሮጀክት ተጽዕኖ ከፕሮጀክቱ መጠን፣ ከመካሄጃ ሥፍራዉ፣ከባህሪዉ፣ከክልል ተሻጋሪነቱ፣ ከሌሎች ተጽእኖወች ወይም ክስተቶች ጋር ከሚኖረዉ ተደማሪነት፣ ከቆይታው፣ ወደ ነበረበት ሁኔታ ለመመለስ ከመቻሉ ወይም ካለመቻሉ፣ እንደዚሁም ከሌላ ተዛማጅ ገጽታዎች አኳያ መገምገም አለበት፡፡
2. ጠቃሚና ጎጂ ውጤቶች ካሉት፣ ነገር ግን ጠቃሚ ጎኑ በትንሹ ብቻ ከሚያመዝን ወይም መብለጥ አለመብለጡ ከሚያወዛግብ አንድ ፕሮጀክት ሊከተል የሚችልን አሉታዊ ተፅዕኖ ሲወስን ባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት ወደ ጥንቃቄ እርምጃ በማዘንበል ፕሮጀክቱ ጉልህ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያስከትል ይችላል በማለት መወሰን አለበት፡፡

5. <u>የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ስለሚያስፈልጋቸው ፕሮጀክቶች</u>

1. በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ በማንኛውም መመሪያ ውስጥ በተጠቀሰ ርዕስ በሚካተት በማንኛውም ፕሮጀክት ሁሉ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ መካሄድ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(1) የተጠቀሰው መመሪያ፡
   ሀ) አሉታዊ ተፅዕኖ ያስከትሉ ይሆናል ተብለው ስለማይታሰቡ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ የማያስፈልጋቸውን ፕሮጀክቶች፡ እና
   ለ) አሉታዊ ተፅዕኖ ያስከትሉ ይሆናል ተብለው ስለሚታሰቡ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ የሚያስፈልጋቸውን ፕሮጀክቶች፣
   ለይቶ ማመልከት አለበት፡፡

6. <u>ክልል ተሻጋሪ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ</u>

1. አንድ የፕሮጀክት ባለቤት ክልል ተሻጋሪና ተፅዕኖ ሊያስከትል የሚችል ፕሮጀክት የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሲያካሂድ፡ ጉዳት ይደርስባቸው ይሆናል ተብለው የሚገመቱ በየትኛውም ክልል የሚገኙ ማሕበረሰቦችን ማሳተፍ አለበት፡
2. ክልል ተሻጋሪ ተፅዕኖ ሊያስከትል የሚችል ፕሮጀክት በሚካሄድበት ክልል ውስጥ የሚገኝ የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት፡ የፕሮጀክቱን የአካባቢ ተፅዕኖ የጥናት ዘገባ ለባለሥልጣኑ እንዲቀርብ ማድረግ አለበት።

3. ባለሥልጣኑ ክልል ተሻጋሪ የአካባቢ ተፅዕኖ ሊያስከትል የሚችል ፕሮጀክት የአካባቢ ተፅዕኖ የጥናት ዘገባን መመርመር ከመጀመሩ በፊት ጉዳት ይደርስባቸው ይሆናል የሚባሉት በየሚመለከተው ክልል የሚገኙት ማሕበረስቦች አስተያየት ተጠይቆ የተካተተ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

## ክፍል ሦስት

7. **የፕሮጀክት ባለቤት ግዴታዎች**

1. አንድ የፕሮጀክት ባለቤት የፕሮጀክቱን የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አካሂዶ፣ የፕሮጀክቱን አሉታዊ ተፅዕኖዎች በቅድሚያ ለይቶና ተፅዕኖዎቹን የማስቀሪያ ወይም የመቋቋሚያ ዘዴን በጥናቱ ውስጥ አካትቶ ባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት ተገቢነታቸውን ከወሰነባቸው ሠነዶች ጋር የአካባቢ ተፅዕኖ የጥናት ዘገባውን ለባለሥልጣኑ ወይም ለሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት ማቅረብ አለበት፡፡
2. በፕሮጀክቱ ላይ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ የሚካሄደው የአካባቢ ተፅዕኖ የጥናት ዘገባም የሚዘጋጀው ባለሥልጣኑ በሚያወጣው ማንኛውም መመሪያ የተዘረዘሩ መስፈርቶችን በሚያሟሉ ባለሙያዎች መሆኑን የፕሮጀክት ባለቤቱ ማረጋገጥ አለበት፡፡
3. የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማን ለማካሄድና የአካባቢ ተፅዕኖ የጥናት ዘገባን ለማዘጋጀት የሚያስፈልገውን ወጪ የፕሮጀክቱ ባለቤት መሸፈን አለበት።
4. አንድ የፕሮጀክት ባለቤት ፕሮጀክቱን ሲተገብር በተሰጠው ፈቃድ ውስጥ የተዘረዘሩ ግዴታዎችን ማሟላት አለበት፡፡

8. **የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ዘገባ**

1. የአካባቢ ተፅዕኖ የጥናት ዘገባ፡ ባለሥልጣኑ ወይም የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት የፕሮጀክቱን መካሄድ ወይም አለመካሄድ ተገቢነት፡ እንዲሁም ሲካሄድ ሊኖረው የሚገባውን ሁኔታ ለመወሰን የሚያስችለውን በቂ መረጃ የያዘ መሆን አለበት፡፡
2. የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ዘገባ ቢያንስ የሚከተሉትን ዝርዝሮች የያዘ መሆን አለበት፡

ሀ) የፕሮጀክቱን ባህሪ፡ በጥቅም ላይ የሚውለውን ቴክኖሎጂና አጠቃቀም፡

ለ) ፕሮጀክቱ ሲተገበር እንዲሁም ቋሚ ሥራው ሲከናወን ወደ አካባቢ የሚለቀቀውን የበካይ ይዘትና መጠን፡

ሐ) የሥራው እንቅስቃሴ የሚጠይቀውን የኃይል ፍጆታና ምንጭ፣

መ) ሊከተል ስለሚችል ክልል ተሻጋሪ የአካባቢ ተፅዕኖ መረጃ፣

ሠ) በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ይከተላሉ ተብለው የተተመኑ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተፅዕኖዎች ባህሪያትና የሚቆዩበት ጊዜ፣

ረ) አሉታዊ ተፅዕኖን ለማስወገድ፣ ለመቀነስ ወይም ለማቃለል የታቀዱ እርምጃዎች፣

ሰ) የአካባቢ አያያዝ ችግርን ለማቃለል የተነደፉ እቅዶች፣ የአደጋ መከላከያ ዝግጁነት፣ እና

ሸ) ፕሮጀክቱ በሚተገበርበትና እንደዚሁም ቋሚ ሥራው በሚከናወንበት ወቅት የውስጥ የቁጥጥርና የክትትል ሥራዎች የሚካሄዱባቸውን መንገዶች፡፡

3. ባለሥልጣኑ የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ዘገባን ለማዘጋጀትና ዘገባውን ለመመርመር የሚረዱ ሃሳቦችን የሚዘረዝሩ መመሪያዎችን ማውጣት አለበት፡፡

9. <u>የአካባቢ ተጽዕኖ ጥናት ዘገባ ምርመራ</u>

1. ምርመራ እንዲካሄድበት ለባለሥልጣኑ ወይም ለሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት በሚቀርብ የአካባቢ ተፅዕኖ የጥናት ዘገባ፣ ማንም ሊረዳው በሚችል ቋንቋ በአጭሩ የተዘጋጀ የጥናቱን መግለጫ የያዘና እንደዚሁም የጥናቱ መረጃ መሟላትንና ትክክለኛነቱን የሚያመላክት፣ አጭር መግለጫ መያዝ አለበት።

2. ባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት በ15 የሥራ ቀናት ውስጥ፣ የሕዝብ አስተያየትንና የባለሙያዎች አስተሳሰብን በማመዛዘን የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናቱን ዘገባ ከመረመረ በኋላ፣

ሀ) ጎጂ ተፅዕኖ የማያስከትል መሆኑን ካመነ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ፕሮጀክቱን ይቀበላል፣ እንዲተገበርም ይሁንታውን ይሰጣል፣

ለ) ጎጂ ተፅዕኖዎቹን ለማስቀረት ወይም በበቂ ሁኔታ ለመቋቋም የሚቻል መሆኑን ካመነ ለማስቀረት ወይም ወደ ኢምንትነት ለመቀነስ የሚያስፈልጉትን ቅድመ ሁኔታዎች ዘርዝሮ እንዲሟሉ በማዘዝ ፕሮጀክቱ እንዲተገበር ይሁንታ ይሰጣል፣ ወይም

ሐ) ፕሮጀክቱ ተግባራዊ በሚሆንበት ጊዜ በአካባቢ ላይ የሚከተለውን አሉታዊ ተፅዕኖ በአጥጋቢ ሁኔታ ለማስቀረት እንደማይቻል ካመነ ትግበራውን ይከለከላል።

10.**የፀደቀ የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ዘገባ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ**

1. እንዲተገበር ይሁንታ የተሰጠው የፕሮጀክት የአካባቢ ተፅዕኖ የጥናት ዘገባ፣ ይኸው ይሁንታ ሲሰጥ አብሮ የተመለከተውን የጊዜ ገደብ ተከትሎ ካልተተገበረ ተቀባይነቱ ይቀራል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ አተገባበር ተገቢ አለመሆኑን ሊያስረዳ የሚፈልግ የፕሮጀክት ባለቤት እንደአግባቡ ለባለሥልጣኑ ወይም ለሚመለ ከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት ማመልከት ይችላል፡፡
3. ልዩ ሁኔታ ካላስገደደው በስተቀር፣ ባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ማመልከቻውን ከተቀበለበት ዕለት ጀምሮ በሰላሣ ቀናት ውስጥ የዘገባው ተቀባይነት ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ እንዲራዘም፡ ወይም የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማው እንዲከለስ ወይም እንደገና እንዲካሄድ፡ መወሰን አለበት፡፡

**ክፍል አራት**

11.**የአዲስ ሁኔታ መከሰት**

የአካባቢ ተፅዕኖ የጥናት ዘገባ ከቀረበ በኋላ ከባድ እንድምታ ያለው ቀደም ሲል ያልተጤነ እውነታ ቢከሰት ባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት እንድምታውን ለማጤን እንዲቻል የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማው እንደአስፈላጊነቱ እንዲከለስ ወይም እንደገና እንዲካሄድ ማዘዝ ይችላል፡፡

12.**የትግበራ ክትትል**

1. የፕሮጀክቱ ባለቤት፣ ፕሮጀክቱን በመተግበር ላይ የሚገኘው ለፕሮጀክቱ ትግበራ ይሁንታ በተሰጠበት ወቅት በገባው ቃል እና በተጣለበት ግዴታ ሁሉ መሠረት መሆኑን ለመገምገም ባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት በፕሮጀክቱ አተገባበር ላይ ክትትል ማድረግ አለበት፡፡
2. አንድ የፕሮጀክት ባለቤት እንዲተገብረው ይሁንታ የተሰጠውን ፕሮጀክት በገባው ቃል ወይም በተጣለበት ግዴታ መሠረት ካልተገበረ፣ ባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት መወሰድ ያለበትን የእርምት እርምጃ በመግለጽ ማስጠንቀቂያ ሊሰጠው ይችላል፡፡

3. እንደአግባቡ ባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት ማንኛውንም ፕሮጀክት እንዲተገበር በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9(2) (ሀ) ወይም (ለ) መሠረት የሰጠውን ይሁንታ ሲያግድ ወይም ሲሰርዝ ሌላ ማንም ፈቃድ ሰጪ መሥሪያ ቤት ለፕሮጀክቱ ትግበራ የሰጠውን ፈቃድ ይህንኑ ውሳኔ ተከትሎ ማገድ ወይም መሠረዝ አለበት፡፡

13.<u>የመንግሥት ሠነድ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ</u>

1. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት በወጣ በማንኛውም መመሪያ በሚገለጽ መደብ ውስጥ የሚካተት ማንኛውም የመንግሥት ሠነድ ከመፅደቁ በፊት የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ እንዲካሄድበት መደረግ አለበት፡፡
2. በባህሪያቸው ቸልሊባል የማይችል አካባቢያዊ ተፅዕኖ ያስከትሉ ይሆናል ተብለው የሚገመቱ የመንግሥት ሠነዶች መደብን ለመለየትና የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ እንዲካሄድባቸው ለማድረግ የሚያስችል መመሪያ ባለሥልጣኑ ማውጣት አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በወጣ በማንኛውም መመሪያ መሠረት የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ በሚያስፈልገው መደብ የሚካተትን ማንኛውም የመንግሥት ሠነድ የሚያዘጋጅ የመንግሥት አካል በሠነዱ ላይ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ የተካሄደበት መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡
4. ማንኛውም የመንግሥት አካል የሚያዘጋጀው ማናቸውም የመንግሥት ሠነድ ሊያስከትለው የሚችለው ተፅዕኖ እንዲገመገም ለማስቻል ከባለሥልጣኑ ጋር መተባበር አለበት፡፡

14.<u>የኃላፊነት ክፍፍል</u>

1. ፈቃድ የመስጠቱ፣ የመተግበሩ ወይም የአተገባበር ቁጥጥሩ ድርሻ የፌዴራል መንግሥት አካል ከሆነ ወይም ፕሮጀክቱ ክልል ተሻጋሪ የአካባቢ ተፅዕኖ ያስከትል ይሆናል ተብሎ የሚታሰብ ከሆነ፣ የአካባቢ ተፅዕኖ የጥናት ዘገባውን የመመርመር፣ ፕሮጀክቱ እንዲተገበር ይሁንታ የመስጠትና ክትትል የማካሄድ ኃላፊነት የባለሥልጣኑ ነው፡፡

2. ፈቃድ የመስጠቱ፣ የመተግበሩ ወይም የአተገባበር ቁጥጥር ድርሻ የክልል መንግሥት አካል ከሆነና ፕሮጀክቱ ክልል ተሻጋሪ የአካባቢ ተፅዕኖ ያስከትል ይሆናል ተብሎ የማይታሰብ ከሆነ፣ የአካባቢ ተፅዕኖ የጥናት ዘገባውን የመመርመር፣ ፕሮጀክቱ እንዲተገበር ይሁንታ የመስጠትና አተገባበሩን የመከታተል ኃላፊነት የክልሉ የአካባቢ መሥሪያ ቤት ነው፡፡

## ክፍል አምስት

### 15.ስለሕዝብ ተሳትፎ

1. ባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት ማንኛውንም የአካባቢ ተፅዕኖ የጥናት ዘገባ ለሕዝብ ይፋ በማድረግ በዘገባው ላይ አስተያየት መጠየቅ አለበት፡፡
2. ባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት በአጠቃላዩ የሕዝብ፣ በተለይም ደግሞ የፕሮጀክቱ አተገባበር ጉዳት ያስከትልባቸው ይሆናል ተብለው የሚገመቱ ማኅበረሰቦች አስተያየት፣ በአካባቢ ተፅዕኖ ጥናቱ ውስጥ መካተቱን፣ እንደዚሁም ምርመራው በሚካሄድበት ወቅት መጤኑን፡ማረጋገጥ አለበት፡፡

### 16.ስለማበረታቻ

1. ባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት የተጎዳ አካባቢን መልሶ እንዲያገግም ለማስደረግ የተዘጋጀ ፕሮጀክት አተገባበርን አቅሙ በሚፈቅደው መሠረት ማገዝ አለበት፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የተጎዳ አካባቢን እንዲያገግም ለማድረግ ወይም ብክለትን ለማስቀረት ወይም የተበከለን ለማጽዳት ለተዘጋጀ ፕሮጀክት ባለሥልጣኑ አቅሙ በፈቀደ መጠን ተጨማሪ ወጪዎችን ለመሸፈኛ የገንዘብና የቴክኒክ ድጋፎች ማድረግ ይችላል፡፡

### 17.የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት

1. ለፕሮጀክት ትግበራ በተሰጠ ይሁንታ ወይም በክትትል፤ ወይም ፕሮጀክቱን በሚመለከት ከባለሥልጣኑ ወይም ከክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት በተሰጠ በማንኛውም ሌላ ውሣኔ ላይ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው ቅሬታውን እንዳግባቡ ለባለሥልጣኑ ወይም ለሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት ኃላፊ ማቅረብ ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተደነገገው መሠረት፡ የባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው የአካባቢ መሥሪያ ቤት የሥራ ኃላፊ ቅሬታው በደረሰው በሰላሣ ቀናት ውስጥ ውሣኔ መስጠት አለበት፡፡

## ክፍል ስድስት

### 18. ስለ ጥፋትና ቅጣት

1. የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ፣ ይህን አዋጅ ወይም ሌላ አግባብ ያለውን ሕግ ወይም መመሪያ የሚተላለፍ ማንኛውም ሰው ጥፋት ፈጽሞአልና ቅጣት ይጣልበታል፡፡
2. ማንኛውም የፕሮጀክት ባለቤት የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ እንዲካሄድበት የተደነገገበትን ማንኛውም ፕሮጀክት፣ ከባለሥልጣኑ ወይም ከሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት ይሁንታ ሳያገኝ ተግባራዊ ያደረገ እንደሆነ ወይም በአካባቢ ተፅዕኖ የጥናት ዘገባው ውስጥ ሀሰተኛ መግለጫ ያቀረበ እንደሆነ ጥፋት ፈጽሟልና ከ ሃምሣ ሺ ብር በማያንስና ከአንድ መቶ ሺ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡
3. ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት ፈቃድ ሲሰጠው የተጣለበትን ግዴታ ካልተወጣ፣ ወይም ተፈላጊ ዝርዝሮችን በመዝገብ ሳያሰፍር ከቀረ ጥፋት ፈፅሞአልና ከአስር ሺ ብር በማያንስና ከሃያ ሺ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡
4. በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት ጥፋት ሲፈጽም ድርጅቱ እንዲከፍለው ከተፈረደበት መቀጮ በተጨማሪ የሕጉን መከበር ለማረጋገጥ መፈጸም የሚገባውን ተግባር በትጋት ያልተወጣ በመሆኑ የሥራ መሪው ከአምስት ሺ ብር በማያንስና ከአሥር ሺ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡
5. ይህን አዋጅ ወይም በሥሩ የሚወጣውን ማንኛውም ደንብ ወይም መመሪያ በመጣስ ጥፋተኛነቱ የተረጋገጠበትን ሰው፣ ከሚወሰንበት ከማንኛውም ቅጣት በተጨማሪ የደረሰውን ጉዳት በሙሉ በራሱ ወጪ እንዲያስተካክል ወይም እንዲተካ ፍርድ ቤቱ ማዘዝ ይችላል፡፡

## ክፍል ሰባት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

19. **ደንቦችን የማዉጣት ስልጣን**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ አስፈላጊ የሆኑ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

20. **መመሪያዎችን የማውጣት ሥልጣን**

ባለሥልጣኑ ይህን አዋጅ በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

21. **የመተባበር ግዴታ**

ለዚህ አዋጅ አተገባበር ማንኛውም ሰው የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

22. **ተፈጻሚነት የሌላቸው ሕጎች**

ከዚህ አዋጅ ጋር ተቃራኒ የሆነ ሕግ ወይም አሠራር በዚህ አዋጅ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፣

23. **አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ ከኅዳር 24 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ኅዳር 24 ቀን 1995 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ**

**ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## አዋጅ ቁጥር 300/1995

## የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ

አንዳንድ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ የልማት ጥረቶች ልማቱን የሚቀለብስ ጎጂ አካባቢያዊ ተፅዕኖ ሊያስከትሉ የሚችሉ በመሆናቸው ፣

በአጠቃላዩ አካባቢን መጠበቅ ፣ በተለይም የሰውን ጤንነትና በጎ ሁኔታ እንደዚሁም የሕያዋንን ደሕንነትና የተፈጥሮን ሥነውበት ማቆየት የሁሉም ተግባርና ኃላፊነት በመሆኑ፣

የመከላከያ ወይም የማስወገጃ እርምጃዎችን በመውሰድ በማሕበራዊና በኢኮኖሚያዊ ልማት ጥረቶች ሂደት የሚከሰተውንና የማይፈለገውን ብክለት ማስወገድ ሳይቻል መከላከል ተገቢ በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55(1 መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

## ክፍል አንድ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 300/1995" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ አዋጅ ውስጥ ፣

   1. "ባለሥልጣን"ማለት የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ነው፤[45]
   2. "ኬሚካል" ማለት ኤለመንት፣ ወይም ያልተቀላቀለም ይሁን የተቀላቀለ ውሁድ፣ ወይም ተቀምሞ በሰው የተሠራ፣ ወይም ደግሞ ከተፈጥሮ የተገኘ፣ ቁስአካል ነው፤
   3. "አግባብ ያለው መሥሪያ ቤት" ማለት ይህ ስያሜ የተጠቀሰበት ድንጋጌ በሚነካው ጉዳይ ላይ በሕግ የተሰጠ ኃላፊነት ያለው የፌዴራል ወይም የክልል የመንግሥት አካል ነው፤
   4. "ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት"› ማለት በፌዴራል መንግሥት ሲሆን የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፣ እንዲሁም በብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሲሆን በክልሉ ሕግ መሠረት የሚሰየም ፍርድ ቤት ነው፤

[45] በ25/08 (2011) አ. 1097 አንቀጽ 36/17 መሰረት የአካባቢ፣ የደን እና አየር ለውጥ ኮሚሽን ስለሆነ በአዋጁ ውሰጥ ባለስልጣኑ የሚለው ኮሚሽኑ በሚል ተተክቶ ይነበብ፡፡

5. “ፍሳሽ” ማለት ተጣርቶ ወይም ሳይጣራ ፣ በቀጥታ ወይም ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ወደ አካባቢ የሚለቀቅ ቆሻሻ ውሃ ወይም ሌላ ቆሻሻ ፈሳሽ ወይም ጋዝ ነው፡፡
6. “አካባቢ” ማለት በመሬት፣ በከባቢ አየር፣ በአየር ሁኔታ እና በአየር ንብረት፣ በውሀ፣ በህያዋን ፣በድምፅ በሽታ፣ በጣእም፣ በማህበራዊ ጉዳዮች እና በስነ ውበት ሳይወሰን፣ በተፈጥሮአዊ ሁኔታቸው ወይም በሰው አማካኝነት ተሻሽለው ወይም ተለውጠው የሚገኙ ነገሮች በሙሉና ያሉበት ቦታ፣ እንዲሁም መጠናቸውን ወይም ሁኔታቸውን ወይም ደግሞ የሰው ወይም የሌሎች ሕያዋን በጎ ሁኔታን የሚነኩ ተስተጋብሮቶቻቸው ድምር ነው፣
7. “የአካባቢ ተቆጣጣሪ ወይም ተቆጣጣሪዎች” ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 (1) መሠረት የሚሰየመው አካል ነው፤
8. “አደገኛ ነገር” ማለት በሰው ጤና ወይም በአካባቢ ላይ ጉዳት የሚያደርስ ጠጣር ፣ ፈሳሽ ወይም ጋዝ ወይም ተክል፣ እንስሳ ወይም ረቂቅ ሕዋስ ነው ።
9. “አደገኛ ቆሻሻ” ማለት ተፈላጊነት የሌለው ሆኖ በአካባቢ ወይም በሰው ደህንነት ወይም ጤና ላይ ጉዳት ያደርሳል ተብሎ የሚታመን ማንኛውም ነገር ነው፡፡
10. “ሰዉ” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡ ፣
11. “በካይ” ማለት ፈሳሽ፣ ጠጣር ወይም ጋዝ የሆነ፡ ፣በቀጥታም ሆነ ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ፣
    ሀ) ያረፈበትን የአካባቢ ክፍል ጥራት በመለወጥ ጠቀሜታ የመስጠትአቅሙን የሚያጓድል፣ ወይም
    ለ) በሰው ጤና ወይም በሌሎች ሕያዋን ላይ ጉዳት የሚያደርስ ወይም ሊያደርስ የሚችል መርዝን፣ በሽታን፣ ከርፋትን፣ ጨረርን፣ ድምፅን፣ ንዝረትን፣ ሙቀትን ወይም ሌላ ክስተትን የሚያመነጭ፣

    ማንኛውም ነገር ነው፤
12. “ብክለት” ማለት በዚህ አዋጅ ወይም አግባብ ባለው ሌላ ሕግ የተደነገገን ማንኛውንም ግዴታ፣ ማዕቀብ ወይም ገደብ ጥሶ የማንኛውንም አካባቢ ክፍል ቁሳዊ፣ ጨረራዊ፣ ሙቀታዊ፣ ንጥረ ነገራዊ፣ ሥነ-ሕይወታዊ ወይም ሌላ ባህርይን በመለወጥ የተፈጠረ፣ በሰው ጤና ወይም በጎነት ወይም ደግሞ በሌሎች ሕያዋን ላይ አደገኛ የሆነ ወይም አደገኛ ሊሆን የሚችል ሁኔታ ነው፤

13.“ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ47)1) የተመለከቱት የአገሪቷ ክፍሎች ማለት ሲሆን፣ ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የአዲስ አበባ እንደዚሁም የድሬዳዋ አስተዳደሮችንም ይጨምራል።

14.“የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት” ማለት ለአካባቢና ለተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ወይም ቁጥጥር በክልሉ መንግሥት ኃላፊነት የተሰጠው ማንኛውም የክልል መንግሥት አካል ነው፤

15.“መልቀቅ” ማለት በውል ታስቦም ይሁን ሳይታሰብ በካይን ወደ ማንኛውም የአካባቢ ክፍል መጨመር ነው።

## ክፍል ሁለት

## የብክለት ቁጥጥር

### 3. የብክለት ቁጥጥር

1. ማንም ሰው ተገቢን የአካባቢ ደረጃ በመተላለፍ አካባቢን ሊበክል ወይም በሌላ ሰው በኩል እንዲበክል ሊያደርግ አይፈቀድለትም፡፡
2. ሕግ በመተላለፍ ማንኛውንም በካይ ወደ አካባቢ በሚለቅ ሰው ላይ ባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት አስተዳደራዊ ወይም ሕጋዊ ዕርምጃ መውሰድ ይችላል።
3. ብክለትን ወይም ሌላ አካባቢያዊ ጉዳትን ሊያስከትል በሚችል የተግባር መስክ የተሰማራ ማንም ሰው፣ የቆሻሻ መመንጨትን ለማስወገድ ወይም ወደተፈላጊው መጠን ለመቀነስ በባለሥልጣኑ ወይም በሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት ትዕዛዝ መሠረት በተገቢ ቴክኖሎጂና ሲቻልም ቆሻሻን መልሶ በጥቅም ላይ ለማዋል በሚያስችሉ ዘዴዎች መጠቀም አለበት፡፡
4. ብክለትን ያደረሰ ማንኛውም ሰው፣ ባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት በሚወሰነው ሁኔታና የጊዜ ገደብ መሠረት አካባቢውን ከበካይ ማፅዳት፣ ወይም ለማፅጃ የወጣውን ወጪ መሸፈንአለበት፡፡
5. በጤና ወይም በአካባቢ ላይ አደጋ እንዳያስከትል ከሚያሰጋ የሥራ እንቅስቃሴ ሊመጣ የሚችል ጉዳትን ለመከላከል ባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት ድርጅትን እስከ መዝጋት ወይም ወደ ሌላ ቦታ እስከ ማዛወር የሚደርስ ማንኛውንም አስፈላጊ እርምጃ መውሰደ ይችላል፡፡

4. **ስለአደገኛ ቆሻሻ፡ ኬሚካልና ጨረር አመንጪ ቁስ አያያዝ**

1. ከባለሥልጣኑ ወይም ከሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት ፈቃድ ሳይያዝ ማንኛውንም አደገኛ ቆሻሻን ማመንጨት፣ ማስቀመጥ፣ ማከማቸት፣ ማጓጓዝ፣ ማምከን ወይም ማስወገድ የተከለከለ ነው።
2. ማንኛውንም አደገኛ ቆሻሻ በመሰብሰብ፣ መልሶ በጥቅም ላይ በማዋል፣ በማጓጓዝ፣ በማምከን ወይም በማስወገድ ሥራ የተሰማራ ማንኛውም ሰውበአካባቢ ወይም በሰው ጤና ወይም በነ ሁኔታ ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ተገቢውን የጥንቃቄ እርምጃ መውሰድ አለበት።
3. ጨረር አመንጪ ቁስን ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት፣ ከከርሰ ምድር ለማውጣት፣ ለማጣራት፣ ለማስቀመጥ፣ እንደዚሁም በአገር ውስጥ ለማሰራጨት፡ ለማከማቸት፡ ለማጓጓዝ፡ በጥቅም ላይ ለማዋል ወይም ለማስወገድ፡ አግባብ ካለው መሥሪያ ቤት ፈቃድ መገኘት አለበት፡፡
4. አደገኛ ተብሎ የተመደበን ወይም ለተወሰነ አገልግሎት ብቻ እንዲውል የተወሰነን ኬሚካል ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት፡ ለመቀመም፡ ለማስቀመጥ፣ በአገር ውስጥ ለማሰራጨት፣ ለማከማቸት፣ ለማጓጓዝ፣ ወይም በጥቅም ላይ ለማዋል፣ ከባለሥልጣኑ ወይም ደግሞ ከሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት ወይም አግባብ ካለው ከሌላ መሥሪያ ቤት ፈቃድ መገኘት አለበት፡፡
5. አደገኛ የሆነ ወይም ለተወሰነ አገልግሎት የሚውል ኬሚካልን በመቀመም፣ በማምረት ወይም በማጓጓዝ ወይም በኬሚካሉ በመነገድ ሥራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው ኬሚካሉ በተገቢዎቹ ደረጃዎች መሠረት መመዝገቡን መታሸጉንና ምልክት የተለጠፈበት መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

5. **የከተማ ቆሻሻ አያያዝ**

1. የከተማ አስተዳደሮች የተቀናጀ የከተማ ቆሻሻ አያያዝ ሥርዓትን በማውጣት፣ የከተማ ቆሻሻ መሰብሰቡን፣ መጓጓዙን፣ እንደተገቢነቱም በጥቅም ላይ መዋሉን፣ መምከኑን ወይም ጉዳት እንዳያመጣ ተደርጎ መወገዱን ማረጋገጥ አለባቸው፡
2. ከሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት ጋር በመተባበር፡ ባለሥልጣኑ የከተሞች የቆሻሻ አያያዝ እና አጠቃቀም ሥርዓቶችን ብቃት መመዘንና የአተገባበራቸውንም ውጤታማነት መገምገም፡ መከታተልና ማረጋገጥ አለበት፡፡

3. ለሕዝብ ክፍት የሆነ ቦታን የሚያስተዳድር ማንም ሰው፣ ምንጊዜም በቂና ተስማሚ የመፀዳጃ ቤት፡ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ዕቃዎችና አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች መገልገያዎች በቦታው መዘጋጀታቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡
4. ባለሥልጣኑ ከየሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት እንዲሁም አግባብ ካላቸው ሌሎች መሥሪያ ቤቶች ጋር በመተባበር፡ የከተሞች የቆሻሻ ማስወገጃ መገልገያዎችን መገምገምና በአጥጋቢ ሁኔታ መሟላታቸውን ለማረጋገጥ አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን መውሰድ አለበት።

## ክፍል ሶስት

## ስለአካባቢ ደረጃዎች

6. ስለአካባቢ ደረጃዎች

1. አግባብ ካላቸው መሥሪያ ቤቶች ጋር በመመካከር፣ ባለሥልጣኑ በሣይንሳዊና በአካባቢያዊ መርሆዎች ላይ የተመሠረቱና ተግባራዊ ለመሆን የሚችሉ የአካባቢ ደረጃዎችን ያዘጋጃል። እነዚህም ደረጃዎች ቢያንስ የሚከተሉትን ማካተት አለባቸው፡
   ሀ) ወደ ውሃ አካላትና ወደ ፍሳሽ መቀበያ መስመሮች የሚለቀቁ ፍሳሾችደረጃዎች፤
   ለ) የአካባቢ አየር ጥራትን የሚገልጹና ለማይንቀሳቀሱና ለሚንቀሳቀሱ የአየር ብክለት ምንጮች የተፈቀዱትን የልቀት መጠኖች የሚወስኑ የአየር ጥራት ደረጃዎች፤
   ሐ) ወደ አፈር የሚጨመሩ ኬሚካሎችን ወይም በአፈር ላይ ወይም ውስጥ የሚወገዱ ቁሶችን ዓይነትና መጠን የሚወስኑ የአፈር ጥራት ደረጃዎች፤
   መ) የአሰፋፈር ሁኔታንና የአገሪቱ የሣይንስና የቴክኖሎጂ አቅምን በማገናዘብ የሚፈቀደውን ከፍተኛ የድምፅ መጠን የሚወስኑ የድምፅ ልቀት ደረጃዎች፡
   ሠ) ለተለያዩ የቆሻሻ ዓይነቶች አመነጫጨት፣ አያያዝ፣ አከመቻቸት አመካከን፣ አጓጓዝና አወጋገድ የሚያገለግሉ የመጠንና የአተገባበር ደረጃዎች፡፡
2. የሚያስከትለውን ጠንቅ ለመግታት በሚከረፋ ሽታ ምንጮች ላይ ቁጥጥር መካሄድ አለበት፡፡
3. ባለሥልጣኑ አካባቢን ለመጠበቅ ወይም መልሶ እንዲያገግም ለማድረግ እንደአስፈላጊነቱ ለተለያዩ ሥፍራዎች የተለያዩ የአካባቢ ደረጃዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

4. ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት በየራሳቸው ልዩ ሁኔታ በመመሥረት በፌዴራሉ እርከን ከተወሰኑት የጠበቁ ደረጃዎችን አውጥተው በሥራ ላይ ሊያውሉ ይችላሉ፡ ፡በፌዴራሉ እርከን ከተወሰኑት የላሉ ደረጃዎች እንዲያወጡ ግን አይፈቀድላቸውም፡፡
5. የሕዝብ ጥቅምን ለማጎልበት ሲባል አግባብ ያለውን የአካባቢ ደረጃ እንዲያሟሉ የሚጠበቅባቸውን የተወሰኑ ተፈላጊ ሁኔታዎችን ተፈፃሚነት ባለሥልጣኑ ለተወሰነ ጊዜ እንዲታለፉ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

**ክፍል አራት**

**ስለአካባቢ ተቆጣጣሪዎች**

7. **ስለአካባቢ ተቆጣጣሪዎች**

1. የአካባቢ ተቆጣጣሪዎች )ከዚህ በኋላ“ተቆጣጣሪዎች” እየተባሉ የሚጠሩ) በባለሥልጣኑ ወይም በሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት ይሰየማሉ፤
2. ተቆጣጣሪዎች በዚህ አዋጅ መሠረት ሥልጣንና ተግባራቸውን ሲወጡ ሥራቸውን በትጋትና ያለአድልዎ መፈፀም አለባቸው።

8. **የተቆጣጣሪዎች ሥልጣንና ተግባር**

1. የአካባቢ ተቆጣጣሪዎች የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሯቸዋል፤
   ሀ) የአካባቢ ደረጃዎችና ተዛማጅ ግዴታዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ፣
   ለ) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3 እና (6 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ፤ ሳያሳውቁ ወይም ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሳይዙ በማንኛውም ተገቢ መስሎ በሚታያቸው ጊዜ ወደ ማንኛውም ቦታ ወይም ቅጥር ግቢ መግባት፤
   ሐ) ማንኛውንም ሰው ብቻውን ወይም በምስክር ፊት መጠየቅ፣
   መ) ከብክለት ጋር ግንኙነት ያለውን ማንኛውንም ወረቀት፣ ማሕደር ወይም ሌላ ሠነድ መፈተሽ፣ መገልበጥ ወይም ለይቶ መቅዳት፣
   ሠ) የማንኛውንም ቁስ ናሙናዎች እንደአስፈላጊነቱ ያለክፍያ መውሰድና በአካባቢ ወይም በሕይወት ላይ ጉዳት የሚያደርስ መሆን አለመሆኑን ለመወሰን መመርመር ወይም ማስመርመር፣
   ረ) ይህ አዋጅ እና አግባብ ያለው ማንም ሌላ ሕግ መከበሩን ለማረጋገጥ ሸቀጥን፣ የአመራረት ሂደትን ወይም መገልገያን በፎቶግራፍ ማንሣት፣ መለካት፣ መሳል ወይም መፈተሽ፣

ሰ) ይህን አዋጅ ወይም አግባብ ያለውን ሌላ ሕግ በመተላለፍ ጥፋት ተፈጽሞበታል የተባለ መሣሪያን ወይም ሌላ ነገርን መያዝ፣ ,

2. የተመደበው ተቆጣጣሪ የዚህን አዋጅ ወይም ማንኛውንም አግባብ ያለውን ሕግ ድንጋጌ ለተላለፈ ሰው የመተላለፉን ምንነት ይዘረዝርለታል፣ ይህንኑ መተላለፍ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ለማስቀረት መውሰድ ያለበትን እርምጃ በመግለጽም እርምጃው እንዲወስድ ሊያዝ ይችላል፡፡

3. የተመደበው ተቆጣጣሪ ማንኛውም እንቅስቃሴ በአካባቢ ላይ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል ብሎ ሲጠረጥር እንቅስቃሴውን እስከ ማስቆም የሚደርስ የእርምት እርምጃ እንዲወስድ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡

4. ማንኛውም የተመደበ ተቆጣጣሪ በባለሥልጣኑ ወይም በሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት የተሰጠ፣ የመሥሪያ ቤቱ ማህተም ያለበት መታወቂያ መያዝ፣ ሲጠየቅም ማሳየት አለበት፡፡

5. ናሙና ሲወሰድ ባለንብረቱ የመገኘት ወይም ወኪል የመላክ መብት ስላለው ይህንኑ መብት እንዲያውቀው መደረግ አለበት፡፡

6. የሥራ አፈፃፀም ቅልጥፍናውን የሚበድልበት ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም የተመደበ ተቆጣጣሪ ወደ ማንም ድርጅት ቅጥር ግቢ ወይም ቦታ ሲገባ ለባለንብረቱ ማስታወቅ አለበት፡፡

9. <u>ስለይግባኝ</u>

1. ተቆጣጣሪው በወሰደው ማንኛውም እርምጃ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው፣ እርምጃው ከተወሰደበት ቀን አንስቶ በአሥር ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ ወይም ለሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊይግባኝ ማለት ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ውሳኔ ያልተሰጠ በመሆኑ ወይም የተሰጠው ውሣኔ ተገቢ ባለመሆኑ ቅር የተሰኘ ሰው ውሣኔው ከተሰጠበት ወይም የሚሰጥበት የጊዜ ገደብ ካለፈበት ቀን አንስቶ በሰላሣ ቀናት ውስጥ ክስመመስረት ይችላል፣

10. <u>ስለ ማበረታቻ</u>

1. ብክለትን ለመከላከል ወይም መጠኑን ለመቀነስ በሚያስችል በማንኛውም ዘዴ መጠቀም ለሚጀምር ለማንኛውም ነባር ድርጅት የሚሰጥ ማበረታቻ በዚህ አዋጅ ሥር በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

2. በባለሥልጣኑ ሲረጋገጥ ብክለትን ለመከላከል ሲባል ወደ አገር ውስጥ የሚገባ መሣሪያ ከገቢ ዕቃዎች የጉምሩክ ቀረጥ ክፍያ ነፃ ይሆናል፡፡

## 11. ስለመክሰስ መብት

1. ነገሩ የሚመለከተው መሆኑን ማስረዳት ሳይጠበቅበት፣ ማንኛውም ሰው በአካባቢ ላይ ጉዳት አድርሷል ወይም ጉዳት ሊያስከትል የሚችል ተግባር እየፈጸመ ነው በሚለው በማንኛውም ሰው ላይ ለባለሥልጣኑ ወይምለሚመለከተው የክልል መሥሪያ ቤት ቅሬታ የማቅረብ መብት አለው፡፡
2. ባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት በሰላሳ ቀናት ውስጥ ውሣኔ ካልሰጠ ወይም ቅሬታ አቅራቢው በውሳኔው ካልተስማማ፣ ውሳኔው ከተሰጠበት ወይም የሚሰጥበት የጊዜ ገደብ ካለፈበት ቀን አንስቶ በስድሳ ቀናት ውስጥ በፍርድ ቤት ክስ መመሥረት ይችላል።

## ክፍል አምስት

## ጥፋትና ቅጣት

## 12. ጠቅላላ

1. ይህን አዋጅ ወይም አግባብ ያለውን ሌላ ሕግ የተላለፈ፣ነገር ግን ጥፋቱ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግም ሆነ በዚህ አዋጅ ቅጣት ያልተመደበለት ሆኖ የተገኘ ማንም ሰው ጥፋተኛነቱ ሲረጋገጥ፣
   ሀ) የተፈጥሮ ሰው ሲሆን፣ ከአምስት ሺህ ብር በማያንስና ከአስር ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ወይም ከአንድ ዓመት በማይበልጥ እሥራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል፤
   ለ) በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ሲሆን ከአሥር ሺህ ብር በማያንስና ከሃያ ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ጥፋተኛነቱ ሲረጋገጥ የተፈፀመውን ጥፋት ማወቅ የነበረበትና ኃላፊነቱን በብቃት ያልተወጣው የሥራ ኃላፊ ከአምስት ሺህ ብር በማያንስና ከአስር ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ወይም ከሁለት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል፣
3. በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሠረት የከበደ ቅጣት የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር፣ በዚህ አዋጅ የተደነገጉት ቅጣቶች ተፈፃሚ ይሆናሉ።

13.<u>ከተቆጣጣሪዎች ጋር በተያያዘ ስለሚፈፀሙ ጥፋቶች</u>

1. የተመደበ ተቆጣጣሪን ሥራውን እንዳያከናውን ያደናቀፈ ወይም ያሰናከለ ፣ ተቆጣጣሪው በሕግ መሠረት የጠየቀውን ወይም ያዘዘውን ያልፈፀመ ፣ በማስመሰል ተቆጣጣሪ ነው ሊባል የሞከረ ፣ ተቆጣጣሪው ወደ ማንኛውም ቦታ ወይም ቅጥር ግቢ እንዳይገባ ወይም መዛግብት እንዳይመረምር ያደናቀፈ ማንኛውም ወረቀት፣ ማሕደር ፣ ወይም ሌላ ሰነድ እንዳይፈትሽ፣ እንዳይገለብጥ፣ ወይም ለይቶ እንዳይቀዳ የከለከለ ፣ ለተቆጣጣሪ መረጃ የከለከለ፣ ያሳሳተ ወይም የተሳሳተ መረጃ የሰጠ ማንም ሰው ጥፋት ፈጽሟል፣
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ጥፋት የፈፀመ የተፈጥሮ ሰው ጥፋተኛነቱ ሲረጋገጥ ከሶስት ሺህ ብር በማያንስና ከአሥር ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤ ጥፋቱን የፈፀመው በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ከሆነ ደግሞ ጥፋተኛነቱ ሲረጋገጥ ከብር አሥር ሺህ በማያንስና ከብር ሃያ ሺህ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤ የሥራ ኃላፊውም ከአንድ ዓመት በማያንስ እና ከሁለት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ወይም ከአምስት ሺህ ብር በማያንስና ከአስር ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

14.<u>መዛግብትን በተመለከተ ስለሚፈፀሙ ጥፋቶች</u>

አንድ ሰዉ በዚህ አዋጅ ወይም በሥሩ በሚወጡ ደንቦች መሠረት በመዝገብ እንዲያሰፍር የተጠየቁን የእንቅስቃሴ፣የምርት፣የቆሻሻ ዓይነት ባሕርይ ወይም መጠን ወይም ሌላ ተፈላጊ መረጃ በተገቢዉ ሳይመዘግብ ከቀረ ወይም በመዝገብ የሰፈረዉን ከለወጠ፣ ከአስር ሺህ ብር በማያንስና ከሃ ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

15.<u>አደገኛ የሆነ ቆሻሻንና ሌላ ቁስን በተመለከተ ስለሚፈፀም ጥፋት</u>

1. አንድ ሰው አደገኛ ቆሻሻን ወይም አደገኛ ነገርን አግባብ ባላቸው ሕጎች መሠረት ካልያዘ፤ መለጠፍ ያለበት ዝርዝርን አሳስቶ ከለጠፈ ወይም ጭራሹን ካልለጠፈ፣ወይም ደግሞ ማንኛውንም አደገኛ ቆሻሻን፣ ወይም ሌላ ነገርን በተመለከተ መረጃ ከነፈገ ወይም ያልተፈቀደ የአደገኛ ቆሻሻ ዝውውርን ለማካሄድ ከሞከረ ወይም ካካሄደ ወይም ደግሞ እንዲካሄድ ለመርዳት ከሞከረ ወይም ከረዳ ጥፋተኛ ነው።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ )1) መሠረት ጥፋት የፈፀመ የተፈጥሮ ሰው ጥፋተኛነቱ ሲረጋገጥ ከሃያ ሺህ ብር በማያንስና ከሃምሳ ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ፣ ጥፋቱን የፈፀመው በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ከሆነ ደግሞ ከሃምሳ ሺህ ብር በማያንስና ከአንድ መቶ ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል። የሥራ ኃላፊውም ከሦስት ዓመት በማያንስና ከስድስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ወይም ከሰላሳ ሺህ ብር በማያንስና ከሰባ ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል።

16. <u>ብክለትን በሚመለከት ስለሚፈፀም ጥፋት</u>

አንድ የተፈጥሮ ሰው የዚህን አዋጅ ወይም በሥሩ የሚወጡትን ደንቦች በመተላለፍ በካይን ወደ አካባቢ በመልቀቅ ጥፋተኛ ሆኖ ሲገኝ፣ ከአንድ ሺህ ብር በማያንስና ከአምስት ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ወይም ከአንድ ዓመት በማያንስና ከአሥር ዓመት በማይበልጥ እሥራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል። ጥፋቱን የፈፀመው በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ከሆነ ከአምስት ሺህ ብር በማያንስና ከሃያ አምስት ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፣ የሥራ ኃላፊውም ከአምስት ዓመት በማያንስና ከአስር ዓመት በማይበልጥ እሥራት ወይም ከአምስት ሺህ ብር በማያንስና ከአስር ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

17. <u>ስለመውረስ እና ወደ ነበረበት ሁኔታ ስለመመለስ</u>

ይህን አዋጅና በሥሩ የሚወጡትን ደንቦች በመጣስ ጥፋተኛነቱ በተረጋገጠበት ሰው ላይ ከሚወሰንበት ማንኛውም ቅጣት በተጨማሪ ፍርድ ቤቱ ፣

ሀ) ለጥፋቱ ተግባር የዋለ ማንኛውም ነገር ተወርሶ ለመንግሥት ገቢ እንዲሆን ወይም በሌላ መንገድ እንዲወገድ፣

ለ) አካባቢውን የማፅጃ ወይም መሣሪያውን፣ ኬሚካሉን ወይም ዕቃውን የማስወገጃ ወጪ ተከሳሹ እንዲከፍል፣ እንደዚሁም

ሐ) ጉዳት የደረሰበትን አካባቢ ተከሳሹ በራሱ ወጪ ወደ ነበረበት ሁኔታ እንዲመልስ ወይም ደግሞ ይህ የማይቻል ከሆነ ተገቢ ካሣ እንዲከፍል ማዘዝ ይችላል፡፡

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

18.**የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

በሥራ ላይ ያሉ ተቋማት ይህን አዋጅ እንዴት ተፈፃሚ እንደሚያደርጉት በዚህ አዋጅ ሥር በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

19.**መረጃ የመስጠት ግዴታ**

1. የዚህን አዋጅ ወይም ከዚህ አዋጅ ጋራ ግንኙነት ያለውን የሌላ ሕግ ድንጋጌ የሚመለከት ተግባርን የሚያከናውን ማንኛውም ሰው ባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት በሚፈልገው መሠረት የሥራ እንቅስቃሴውን መረጃ ማቅረብ አለበት፡፡
2. ባለሥልጣኑ ማንኛውንም አካባቢን የሚመለከት መረጃ የማግኘት መብት አለው፡

20.**ደንብ የማዉጣት ሥልጣን**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህንን አዋጅ በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ አስፈላጊ የሆኑ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

21.**ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጎች**

ከዚህ አዋጅ ጋር ተቃራኒ የሆነ ሕግ ወይም አሠራር በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረዉም፡፡

22.**አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ ከህዳር 24 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ህዳር 24 ቀን 1995 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ**

**ሪፐብሊክ ፕሬዘዳንት**

**ደንብ ቁጥር 159)2001**

## የኢንዱስትሪ ብክለት መከላከያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 471/1998 አንቀጽ 5 እና በአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 300/1995 አንቀጽ 20 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የኢንዱስትሪ ብክለት መከላከያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 159/2001" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፤

   1. "ሥልጣን የተሰጠው ፈቃድ ሰጪ መሥሪያ ቤት" ማለት የሥራ ፈቃድ ለመስጠት በሕግ ሥልጣን የተሰጠው ማንኛውም የፌዴራል ወይም የክልል የመንግሥት አካል ነው፤
   2. "ሥልጣን የተሰጠው የአካባቢ መሥሪያ ቤት" ማለት እንደ ሁኔታው የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ወይም የክልል የአካባቢ ጥበቃ መሥሪያ ቤት ነው፤
   3. "ባለሥልጣን" ማለት በአዋጅ ቁጥር 295/1995 መሠረት የተቋቋመው የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ነው፤[46]
   4. "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 47 የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባንና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችንም ይጨምራል፣
   5. "ነባር ፋብሪካ" ማለት ይህ ደንብ ከፀናበት ቀን በፊት ወይም በፀናበት ቀን እየሰራ የነበረ ፋብሪካ ወይም ፋብሪካ ለመስራት የሥራ ፈቃድ ጥያቄ አቅርቦ የነበረ ፕሮጀክት ነው፣

[46] በ25)08 (2011 1097 አንቀጽ 36(17 መሰረት የአካባቢ፣ የደን እና አየር ለውጥ ኮሚሽን ስለሆነ በደንቡ ውሰጥ ባለስልጣኑ የሚለው ኮሚሽኑ በሚል ተተክቶ ይነበብ፡፡

6. “ብክለት” ማለት በዚህ ደንብ ፤ አግባብነት ባለው የአካባቢ ደረጃ ወይም አግባብነት ባለው ሌላ ሕግ የተደነገገ ማንኛውንም ግዴታ ፤ ማዕቀብ ወይም ገደብ ጥሶ የማንኛውንም አካባቢ ክፍል ቁሳዊ ፤ ጨረራዊ፣ ሙቀታዊ፣ ንጥረ ነገራዊ፣ ሥነ-ሕይወታዊ ወይም ሌላ ባሕሪይን በመለወጥ የተፈጠረ በሰው ጤና ወይም በጎነት ወይም ደግሞ በሌሎች ሕያዋን ላይ አደገኛ የሆነ ወይም አደገኛ ሊሆን የሚችል ሁኔታ ነው፤
7. “ሰዉ” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ተቋም ነው፤
8. በወንድ ጾታ የተነገረው ማንኛውም አገላለጽ ሴትንም ይጨምራል ፡፡

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች በዚህ ደንብ መሠረት በሚወጣ መመሪያ በተዘረዘረ የኢንዱስትሪ ዘርፍ ውስጥ የሚካተት ፋብሪካን ወይም ሥልጣን የተሰጠው የአካባቢ መሥሪያ ቤት በዚህ ደንብ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (5) መሠረት ያሳወቀው ፋብሪካን በሚመለከት ፋብሪካው እስከሚዘጋበት ወይም ከተዘጋ በኋላም ቢሆን ሥልጣን ያለው የአካባቢ መሥሪያ ቤት እስከወሰነው ተጨማሪ ጊዜ ማብቂያ ድረስ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

4. <u>አጠቃላይ ግዴታ</u>

1. የዚህ ደንብ ድንጋጌ የሚመለከተው ፋብሪካ በካይ ነገር እንዳይመነጭ የማድረግ፣ የማይቻል ከሆነም በሚመለከተው የአካባቢ ደረጃ ከተፈቀደው ጣራ ሳያልፍ አመንጭቶ አካባቢያዊ ተቀባይነት ባለው መንገድ የማስወገድ ግዴታ አለበት፡፡
2. ማንኛውም ፋብሪካ መሣሪያው፣ ግብአቱና ምርቱ በአካባቢና በሰውና በእንስሳት ጤንነት ላይ ጉዳት እንዳይከተል የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡
3. ማንኛውም ፋብሪካ በይዞታው ያለን ማንኛውም አደገኛ በካይ ቆሻሻ፣ ግብዓት ወይም ምርት ሥልጣን ለተሰጠው የአካባቢ መሥሪያ ቤት ማሳወቅ አለበት፡፡
4. ማንኛውም ፋብሪካ አደገኛ በካይ ቆሻሻ፣ ግብዓት ወይም ምርት ቢጠፋበት ወዲያውኑ ሥልጣን ለተሰጠው የአካባቢ መሥሪያ ቤት ማሳወቅ አለበት፡፡
5. በዚህ ደንብ የማይሸፈን የፋብሪካ ዓይነትም ቢሆን ከፋብሪካው እንቅስቃሴ ሊከተል የሚችል ጠንቅን የሚያስቀር እርምጃ እንዲወስድ ሥልጣን ያለው የአካባቢ መሥሪያ ቤት ሊወስን ይችላል፡፡

6. ሥልጣን የተሰጠው የአካባቢ መሥሪያ ቤት በአካባቢ ደረጃ የተደነገገውን የብክለት ጣራ በማለፍ ከፍተኛ አደጋ ማስከተሉ እንደማይቀር ላመነበት ፋብሪካ የአስጊ ሁኔታውን መከሰት የሚያስቀር እርምጃ እንዲወስድ የጽሑፍ ትዕዛዝ መስጠት አለበት፡፡

5. <u>የሥራ ፈቃድ ስለመስጠት</u>

ሥልጣን የተሰጠው ፈቃድ ሰጪ መሥሪያ ቤት ለፋብሪካ የሥራ ፈቃድ የሚሰጠው ልቀቱ በካይ አለመሆኑን፣ ከሆነም በአካባቢ ደረጃ ከተፈቀደው ጣራ የማይበልጥ እና ልቀቱ ወደ አካባቢ ቢለቀቅ አደጋ የማያስከትል መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ መሆን አለበት ፡፡

6. <u>የፈቃድ ግዴታን ስለመለወጥ</u>

1. ሥልጣን የተሰጠው የአካባቢ መሥሪያ ቤት ተሰጥቶ በነበረ ፈቃድ የተመለከቱ ግዴታዎችን ለመለወጥ ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚችለው፤

   ሀ) ፋብሪካው የአመራረት ዘዴውን ሲለውጥ ወይም መስፋፋት ሲያደርግ፤

   ለ) ፋብሪካው ሥራውን በተፈቀደለት የጊዜ ገደብ ሳይጀምር ሲቀር ወይም

   ሐ) ከባድ አንድምታ ያለው ቀደም ሲል ያልተጤነ እውነታ ሲከሰት ነው፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚሰጥ ትዕዛዝ ትዕዛዙ የተሰጠበትን ምክንያትና ተፈጻሚ የሚሆንበትን የጊዜ ገደብ ማመልከት አለበት፡፡

3. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የተሰጠውን ትዕዛዝ ተገቢነት የሚቃወም የፋብሪካ ባለቤት ወይም ሕጋዊ ወኪል ትዕዛዙ ከደረሰው ዕለት አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ ተቃውሞውን ሥልጣን ለተሰጠው የአካባቢ መሥሪያ ቤት በጽሑፍ ለማቅረብ ይችላል፡፡

4. ሥልጣን የተሰጠው የአካባቢ መሥሪያ ቤት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት በቀረበለት ተቃውሞ ላይ በ30 ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

7. <u>ፈቃድን ስለማገድ ወይም ስለመሰረዝ</u>

1. ሥልጣን የተሰጠው የአካባቢ መሥሪያ ቤት በዚህ ደንብ መሠረት እንዲሟላ የተዘረዘረ የፈቃድ ግዴታ አለመከበሩን ሲያወቅ የፋብሪካው የሥራ ፈቃድ እንዲታገድ ወይም እንዲሰረዝ መወሰን አለበት፡፡

2. በዚህ ደንብ ድንጋጌዎች የተመለከቱትን ግዴታዎች ያልተላለፈ ቢሆንም የፋብሪካው የሥራ እንቅስቃሴ መቀጠል ከፍተኛ ብክለት እንደሚያስከትል ሥልጣን የተሰጠው የአካባቢ መሥሪያቤት ሲያምን የሥራ ፈቃዱ እንዲታገድ ወይም እንዲሰረዝ መወሰን አለበት፡፡
3. ሥልጣን የተሰጠው የአካባቢ መሥሪያ ቤት በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1ወይም (2መሠረት የሥራ ፈቃድ እንዲታገድ ወይም እንዲሰረዝ የወሰነበትን ምክንያትና ከመቼአንስቶ ተፈጻሚ እንደሚሆን ሥልጣን ለተሰጠው የፈቃድ ሰጪ መሥሪያ ቤት ማሳወቅ አለበት፡፡ ፈቃድ ሰጪ መሥሪያ ቤቱም ውሳኔውን ማስተግበር አለበት፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት የተላለፈው ውሳኔ ተገቢ አለመሆኑን የሚቃወም ፋብሪካ ውሳኔው ከደረሰው ዕለት አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ ተቃውሞውን ሥልጣን ለተሰጠው የአካባቢ መሥሪያ ቤት በጽሑፍ ማቅረብይችላል፡፡
5. ሥልጣን የተሰጠው የአካባቢ መሥሪያ ቤት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት የቀረበለትን የቅሬታ ማመልከቻ ከተቀበለበት ዕለት አንስቶ በ30 የሥራ ቀናት ውስጥ አሳልፎት የነበረውን ውሳኔ እንዲሻሻል፣ እንዲሰረዝ ወይም እንዲፀና ማድረግ አለበት፡፡

8. <u>አደጋ የመከላከያ ሥርዓት</u>
   1. ይህ ደንብ የሚመለከተው ማንኛውም ፋብሪካ የአደጋ መከላከያ ዘዴ አዘጋጅቶ መተግበር አለበት፡፡
   2. ፋብሪካው በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተዘጋጀውን የአደጋ መከላከያ ዘዴሥልጣን የተሰጠው የአካባቢ መሥሪያ ቤቱ እንዲያውቀው ማድረግ አለበት፡፡

9. <u>የአካባቢ ደህንነት ክትትል</u>
   1. ይህ ደንብ የሚመለከተው ፋብሪካ የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች መከበራቸውን የሚያረጋግጥበትን የራሱን የውስጥ የአካባቢ አያያዝ መቆጣጠሪያ ዘዴ አዘጋጅቶ መተግበር አለበት፡፡
   2. ሥልጣን የተሰጠው የአካባቢ መሥሪያ ቤት አስፈላጊነቱን ካመነበት በዚህ ደንብ አንቀጽ 3 መሠረት በወጣው መመሪያ ባልተጠቀሰ ዘርፍ በተሰማራ ፋብሪካም ላይ የዚህን አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1 ) ድንጋጌ ተፈፃሚ ለማድረግ ይችላል፡፡

10. <u>የሕዝብ ቅሬታ</u>

1. ሥልጣን የተሰጠው የአካባቢ መሥሪያ ቤት ማንኛውም ሰው ጉዳዩ እንደሚመለከተው ማስረዳት ሳይጠበቅበት ብክለትን አስመልክቶ የሚያቀርበው ቅሬታ የሚስተናገድበትን ዘዴ ያዘጋጃል።
2. ብክለትን አስመልክቶ ቅሬታ የቀረበለት ሥልጣን የተሰጠው የአካባቢ መሥሪያ ቤት ጉዳዩን በማጣራት የወሰደውን እርምጃ በ90 ቀናት ውስጥ ለአቤቱታ አቅራቢው ማሳወቅ አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት በተወሰደ እርምጃ ቅር የተሰኘ ሠው ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ሥልጣን ለተሰጠው የአካባቢ መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ በጽሑፍ ለማቅረብ ይችላል፡፡ የበላይ ኃላፊውም ቅሬታው በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ በቀረበው ቅሬታ ላይ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

11. <u>የብክለት አያያዝ መረጃ</u>

1. ይህ ደንብ የሚመለከተው ማንኛውም ፋብሪካ የሚገለገልበትን መሣሪያና የተጠቀመበትን ግብዓት፣ ያመረተውን ምርት፣ ያመነጨውን በካይነገር ፣ በካይ ነገሩን ያስወገደበትን መንገድና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮችን የሚገልጽ መረጃ መዝግቦ መያዝ አለበት፡፡
2. ማንኛውም ፋብሪካ የዚህ ደንብ ድንጋጌዎችን እንዴት እየተገበረ እንደሆነ የሚገልጽ መረጃ ሥልጣን ለተሰጠው የአካባቢ መሥሪያ ቤት በየዓመቱ ማቅረብ አለበት፡፡
3. ባለሥልጣኑ የኢትዮጵያ የበካይ ነገሮች መጠንን፣ ምንጭን፣ ዝውውርንና አወጋገድን የሚያመለክት ዘገባ ቢያንስ በየአምስት ዓመቱ ማውጣት አለበት፡፡

12. <u>ስለ ነባር ፋብሪካዎች</u>

1. በዚህ ደንብ መሠረት በወጣ መመሪያ በተዘረዘረ የኢንዱስትሪ ዘርፍ ውስጥ የሚካተት ማንኛውም ነባር ፋብሪካ በ5 ዓመታት ውስጥ የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ሙሉ በሙሉ ማክበር አለበት ፡፡
2. በዚህ ደንብ መሠረት በወጣ መመሪያ በተዘረዘረ የኢንዱትሪ ዘርፍ ውስጥ የሚካተት ማንኛውም ነባር ፋብሪካ የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች የሚያሟላበትን ሁኔታ ለመወሰን የአካባቢ ኦዲት ማካሄድና የአካባቢ አያያዝ ዕቅድ አዘጋጅቶ መተግበር አለበት፡፡

3. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1 በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ከፋብሪካው እንቅስቃሴ የሚከተለው አሉታዊ ተፅዕኖ ሊወገድ የማይቻል ሆኖ ከተገኘ ሥልጣን የተሰጠው የአካባቢ መሥሪያ ቤት ይህንኑ አሉታዊ ተፅዕኖ ለማስወገድ ያስችላል ብሎ ያመነበትን እርምጃ መውሰድ አለበት፡፡ ይህም እርምጃ ፋብሪካውን ወደ ሌላ ሥፍራ እንዲዛወር ወይም ደግሞ እንዲዘጋ መወሰንን ሊጨምር ይችላል፡፡

13.<u>የኃላፊነት ድርሻ</u>

1. የሥራ ፈቃድ የመስጠቱ ድርሻ የፌዴራል መንግሥት አካል የሆነን ፋብሪካ በተመለከተ ይህንን ደንብ የማስፈፀም ኃላፊነት የባለሥልጣኑ ይሆናል ፡፡
2. የሥራ ፈቃድ የመስጠቱ ድርሻ የክልል መንግሥት አካል የሆነን ፋብሪካ በተመለከተ ይህንን ደንብ የማስፈፀም ኃላፊነት የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት ይሆናል፡፡

14.<u>ቅጣት</u>

በወንጀል ሕግ የአካባቢ ብክለትን በሚመለከት የተደነገጉት የቅጣት ድንጋጌዎች ይህንን ደንብ ለማስተግበር ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

15.<u>ድንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ታኅሣሥ 29 ቀን 2001 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**ደንብ ቁጥር 207/2003**

**የአበባ ልማት ዘርፍ የአሠራር ሥነ ምግባር ስርዓት የሚኒስትሮች**

**ምክር ቤት ደንብ**

የማይፈለጉ አካባቢያዊና ማሕበራዊ ተፅዕኖዎችን ለማስቀረት የሚያስችሉ የግብርና አሠራሮችን በአበባ ልማት ዘርፍ መተግበር አስፈላጊ በመሆኑ፤

አካባቢያዊ አዛላቂነት እና ማሕበራዊ ተቀባይነት ያለው የግብርና አሠራርን ምንነት መግለፅ እና መደንገግ የአበባ ኢንዱስትሪን አዛላቂነት ስለሚያጎለብት፤

የኢትዮጵያ የአበባ ኢንዱስትሪን መልካም ዝና ከፍ ለማድረግ እንዲቻል የማሕበራዊ እና የአካባቢ የኃላፊነት ደረጃዎችን የሚወስን የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀፅ 5 እና በአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 300/1995 አንቀጽ 20 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ**

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ ‹‹የአበባ ልማት ዘርፍ የአሠራር ሥነ ምግባር ሥርዓት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 207)2003›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

   1. “ባለሥልጣን” ማለት በአዋጅ ቁጥር 295/1995 አንቀጽ 3 መሰረት የተቋቋመው የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ነው፤[47]
   2. “የምስክር ወረቀት” ማለት የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች ለሚያሟላ እርሻ ባለሥልጣኑ የሚሰጠው በነሐስ፣ በብር ወይም በወርቅ ደረጃ የተመደበ የማሕበራዊና አካባቢያዊ ኃላፊነት ደረጃ ማረጋገጫ ሠነድ ነው፤

[47] በበ25)08 (2011 ኢ.1097 አንቀጽ 36(17 መሰረት የአካባቢ፣ የደን እና አየር ለውጥ ኮሚሽን ስለሆነ በደንቡ ውሰጥ ባለስልጣኑ የሚለው ኮሚሽኑ በሚል ተተክቶ ይነበብ፡፡

3. “እርሻ” ማለት ተቆርጦ ለገበያ የሚውል አበባን፣ ለማስዋብ የሚውል ተክልን ወይም የአበባ ዘርን በማምረት ላይ የተሰማራ ኩባንያ ነው፤
4. “ሰዉ” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
5. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል።

3. <u>ዓላማ</u>

የዚህ ደንብ ዓላማ የማሕበራዊና አካባቢያዊ አዛላቂነት ግዴታዎችን የማስተግበር እና የእርሻዎችን አመራረት፣የምርት ጥራትና የገበያ ተወዳዳሪነት ማሻሻል ነው፡፡

4. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

1. በዚህ ደንብ ድንጋጌዎች መሠረት የማሕበራዊና አካባቢያዊ ኃላፊነቱን ስለመወጣቱ የምሥክር ወረቀት ያልተሰጠው እርሻ በአበባ ልማት ዘርፍ መሰማራት አይችልም።
2. ይህ ደንብ ተቆርጦ ለገበያ የሚውል አበባን፣ እንዲሁም የአበባ ዘር ማባዛትን ጨምሮ ለማስዋብ የሚውል ተክልን በሚያመርት እርሻ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የማሕበራዊ እና የአካባቢያዊ ኃላፊነት ደረጃዎች</u>

5. <u>የነሐስ ደረጃ</u>

በዚህ ደንብ መሠረት በምርት ሂደት ለመቀጠል የሚፈለገውን የነሐስ የማሕበራዊና የአካባቢያዊ የኃላፊነት ደረጃ ስለማክበሩ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው የሚፈልግ እርሻ፡-

1. በጥቅም ላይ እንዳይውሉ በተከለከሉም ሆነ ባልተመዘገቡ የግብርና ንጥረ ነገሮች አለመጠቀም፤
2. ከአካባቢ ጋር ተስማሚ የሆነ የቆሻሻ አያያዝ ሥርዓትን መከተል፤
3. የአካባቢና የሥራ ቦታ ደህንነት ጠንቆችን መገምገም፤
4. ደህንነትን በሚያረጋግጥ ሁኔታ ንጥረ ነገሮችን ማከማቸትና መጠቀም፤
5. በእርሻ ቦታው ወይም ከአካባቢው አገልግሎትሰጪዎች ጋር በመተባበር የሕክምና ግልጋሎት ለሠራተኞች ማቅረብ፤ የስራ አካባቢ ጤናማነትን ማረጋገጥ፤

6. የሠራተኞች የመደራጀት መብትን፣ በሕብረት የመደራደርን እና ከሥራ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሌሎች መብቶችን የሚያራምድ ተገቢ የሥራ ሁኔታ መኖሩን ማረጋገጥ፤
7. ተባይ ተቆጣጣሪ ሠራተኞች በግብርና ንጥረ ነገሮች አያያዝ እንዲሁም በመከላከያና በእጥበት መሣሪያዎች አጠቃቀም የሰለጠኑ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤
8. አካባቢያዊ፣ ማሕበራዊና የጤና ግዴታ መሟላቱን ለመገምገም የሚያስችለውን የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋት፤
9. የውሃ ፍጆታውን፣ በግብርና ንጥረ ነገሮች አጠቃቀሙን፣ የቆሻሻ አያያዙንና የሃይል ፍጆታውን መለካት፣ መገምገምና ዘገባ ማቅረብ፤
10. የአደጋና የአስቸኳይ ጊዜ ስርዓት መዘርጋቱንና መተግበሩን ማረጋገጥ፤
11. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (3)፤(8)፤(9)፣ እና(10) መሠረት በተካሔደው ቁጥጥር መሠረት ተገቢውን የእርምት እርምጃ መውሰድ፤
12. ሠራተኞቹን በአዛላቂ አካባቢያዊና ማሕበራዊ ጉዳዮች ላይ ማሰልጠን፤
13. አግባብነት ባላቸው የመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚወስኑ ማናቸውም ተጨማሪ አካባቢያዊ፣ ማህበራዊና የጤና መስፈርቶችን ማሟላት፤

አለበት፡፡

6. <u>የብር ደረጃ</u>

1. የብር ደረጃን ለማገኘት የሚፈልጉ እርሻዎች ለዚህ ደረጃ ኦዲት በሚደረጉበት ጊዜ የነሐስ ደረጃ መስፈርቶችን ያሟሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለባቸው።
2. የብር ደረጃ ተፈላጊ ሁኔታዎችን ለማሟላት ከነሐስ ደረጃ መስፈርቶች በተጨማሪ በእርሻው የማሕበራዊ እና የአካባቢ አያያዝ ዕቅድ፡-
   ሀ) በዓለም አቀፍ ገበያ በወቅቱ የሚፈለጉ ተገቢ የግብርና አሰራር ግዴታዎችን የማክበር፤
   ለ) የማሕበራዊ እና የአካባቢያዊ አያያዝ የአሰራር ብቃቱን በየጊዜው ለመገምገም የሚያስችል ተቀባይነት ያለው የኦዲት ሥርዓትን የመዘርጋት፤
   ሐ) አዋጪ የውኃ አጠቃቀም በጎ ተሞክሮዎችን ተፈጻሚ የማድረግ፤
   መ) የድህረ ምርት አያያዝ በጎ ተሞክሮዎችን እና ተቀባይነት ያለው የፀረ ተባይ የመጠን ደረጃዎችን የማክበር፤

ሠ) ለኅብኘዎች እና ለሌሎች ባለድርሻዎች የቅሬታ ማቅረቢያ እና ምላሽ መስጫ ሥርዓት የመዘርጋት፤

ተጨማሪ ግዴታዎችን ማሟላቱ መረጋገጥ አለበት፡፡

7. **<u>የወርቅ ደረጃ</u>**

1. የወርቅ ደረጃን ለማግኘት የሚፈልጉ እርሻዎች ለዚህ ደረጃ ኦዲት በሚደረጉበት ጊዜ የብር ደረጃ መሥፈርቶችን ያሟሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለባቸው።
2. የወርቅ ደረጃ ተፈላጊ ሁኔታዎችን ለማሟላት ከብር ደረጃ መሥፈርቶች በተጨማሪ በእርሻዉ የማሕበራዊና አካባቢያዊ አያያዝ ዕቅድ፡-

ሀ) በገጠር ወይም በከተማ ማህበረሰቦች ፍላጎት ላይ የተመሰረቱ የክህሎት ማጎልበቻ ፕሮግራሞችን፤

ለ) የማህበረሰቦችን፣ የትምህርት ቤት የአካባቢ ክበቦችን እና ሌሎች የአፈር መከላትን ለመከላከል፣ የእጽዋት ሽፋን እንዲጨምር ለማድረግ፣ የውሃ አዘል መሬቶችን እና ሃይቆችን አቅም ለማጎልበት፣ ብዝሃ ሕይወትን ለመንከባከብ እንዲሁም የወንዞችን የከርሰ ምድር ውሃንና የአየርን ጥራትለማሻሻል የታለሙ ተግባራትን፤

በገንዘብ የማገዝ ተጨማሪ ግዴታዎችን ማሟለት አለባቸው።

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>አረጋጋጮችን ስለመሰየም</u>

8. **<u>በአረጋጋጭነት ለመሰየም ማመልከቻ ስለማቅረብ</u>**

አረጋጋጭ ለመሆን የሚፈልግ ማንኛውም ድርጅት የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች የማስፈፀም ብቃቱ ተገምግሞ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ እንዲሰጠው፡-

1. በዚህ ደንብ መሠረት አገልግሎት ለመስጠት የሚችሉ ብቃት ያላቸው ሠራተኞች ያሉት መሆኑን፤
2. የሥራ ማከናወኛ የውስጥ የአሰራር ስርዓትን መዘጋጀቱን፤
3. እንዲያከናውነው ከተሰጠው ተግባር ጋር የጥቅም ግጭት የሌለው መሆኑን፤
4. ባለስልጣኑ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመማከር ከሚወስነው የአገልግሎት ክፍያ ጣሪያ ሳያልፍ አገልግሎት ለመስጠት ፍቃደኛ መሆኑን፤

የሚያረጋግጡ ሰነዶችን ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

9. <u>የአረጋጋጭ ተግባራት</u>

1. በዚህ ደንብ ድንጋጌዎች መሠረት በባለሥልጣኑ የተመዘገበ አረጋጋጭ፡-
   ሀ) የምስክር ወረቀት ለማግኘት ለባለሥልጣኑ በሚቀርቡ ሠነዶች የተዘረዘሩ ጉዳዮችን በመመርመር አካባቢያዊ አዛላቂነታቸዉንና ማሕበራዊ ተቀባይነታቸዉን የማረጋገጥ፤
   ለ) የምስክር ወረቀት ለማግኘት አመልካቹ ያቀረበዉን የማሕበራዊና የአካባቢያዊ አያያዝ ዕቅድን መርምሮ የማሕበራዊና የአካባቢ የሃላፊነት ደረጃዉን የማረጋገጥ፤
   ሐ) አመልካቹ በማሕበራዊ እና የአካባቢያዊ አያያዝ ዕቅዱ ላይ የተዘረዘሩ ተግባራትን ለመፈጸም ያለዉን አቅም የማረጋገጥ፤
   መ) የአመልካቹን የማሕበራዊ እና የአካባቢያዊ ሓላፊነት ደረጃ የሚመለከት የዉሳኔ ሃሳብ ለባለስልጣኑ የማቅረብ፤
   ሠ) ለባለሥልጣኑ ዓመታዊ የሥራ አፈጻፀም ዘገባ የማቅረብ፤
   ተግባራትን ለማከናወን ይችላል፡፡
2. አረጋጋጩ የዚህን ደንብ አፈጻፀም የሚመለከቱትን መዛግብትንና ሌሎች ሠነዶቹን ቢያንስ ለሁለት ዓመት ማስቀመጥ አለበት፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>የምስክር ወረቀት ስለመስጠት</u>

10. <u>የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ</u>

1. የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች የሚያሟላ ማንኛዉም እርሻ የምስክር ወረቀት ማግኘት ይችላል፡፡
2. በዚህ ደንብ መሠረት የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚፈልግ ማንኛዉም እርሻ በባለሥልጣኑ የተዘጋጀዉን የማመልከቻ ቅጽ ሞልቶና ከቅፁ ጋር ብቃት ባላቸዉ ባለሙያዎች ያዘጋጀዉን የማሕበራዊ እና የአካባቢ አያያዝ ዕቅድ እንዲሁም በታወቀ ገለልተኛ ኦዲተር የተመሰከረለት የፋይናንስ ኦዲት ዘገባዉን ለባለስልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡
3. ማንኛዉም እርሻ የሥራ ቦታዉን ወይም አሠራሩን ሲለዉጥ ወይም ቀድሞ የተሰጠዉን ደረጃ ለማሻሻል ሲፈልግ አዲስ ማመልከቻ ለባለሥልጣኑ በማቅረብ የማሕበራዊና የአካባቢ የኃላፊነት ደረጃዉን ማስመደብ አለበት፡፡

4. በዚህ ደንብ መሠረት የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚወጣ ወጪን አመልካቹ መሸፈን አለበት፡፡

## 11.የምስክር ወረቀት የመስጠት ዉሳኔ

1. ባስልጣኑ በዚህ ደንብ አንቀጽ 10 መሠረት የምስክር ወረቀት እንዲሰጥ ማመልከቻ ሲቀርብለት አረጋጋጭን በመመደብ የሰነድ ምርመራ የመስክ ጉብኝትና እንደአስፈላጊነቱም የናሙና ፍተሻ እንዲካሄድ ማድረግ አለበት፡፡
2. በዚህ ደንብ የተመለከቱትን ተፈላጊ ሁኔታዎች ለሚያሟላ እርሻ ባለሥልጣኑ የምሥክር ወረቀት መስጠት አለበት፡፡
3. ባለሥልጣኑ ለእርሻው የምስክር ወረቀት ሲሰጥ እርሻው የደረሰበትን የማሕበራዊ እና የአካባቢ የኃላፊነት ደረጃ የሚገልፅ ደብዳቤ መፃፍ አለበት፡፡
4. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (3) የተመለከተው የማረጋገጫ ደብዳቤ የእርሻውን ስም፣አድራሻ፣ የእርሻውን ተወካይ ስም እና አድራሻ እና የምስክር ወረቀቱ ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ መግለፅ አለበት፡፡
5. እርሻዉ የሚጠበቅበትን መሥፈርት ሳያሟላ የቀረ እንደሆነ ባለሥልጣኑ የቀረበለትን ማመልከቻ ውድቅ ማድረግ አለበት፡፡
6. ማመልከቻው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) መሠረት ተቀባይነት ያላገኘለት እርሻ ይህንኑ ውሳኔ ካገኘበት ቀን አንስቶ በስድስት ወራት ውስጥ የምስክር ወረቀት እንዲስጠው ሌላ ማመልከቻ እንዲያቀርብ አይፈቀድለትም፡፡

## 12.የምስክር ወረቀትን ስለማሻሻል

1. ማንኛውም እርሻ ሥሙን ወይም የዋና ኃሳፊውን ስም ሲለውጥ ወይም ማረጋገጫ የተሰጠውን የእርሻ ስፍራ ስፋትንም ሆነ የምርት ዓይነትን ሲጨምር፣ ሲቀንስ ወይም ሲያሻሽል፣ ወይም ደግሞ ተቀባይነት አግኝቶ የነበረውንየማኅበራዊና የአካባቢ አያያዝ ዕቅዱን ሲቀይር ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ አለበት፡፡
2. ባለሥልጣኑ አስቀድሞ ከሰጠው የምስክር ወረቀት ፀንቶ የመቆያ ጊዜ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ሌላ የምስክር ወረቀት ሊሰጥ የሚችለው የታሰበው ለውጥ አስቀድሞ በሰጠው የምስክር ወረቀት በተዘረዘሩ ግዴታዎች የሚጠበቅ አፈፃፀምን የማይቀንስ ከሆነ ነው፡፡

13.<u>የምስክር ወረቀት ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ</u>

1. የእርሻውን የማሕበራዊ እና የአካባቢ ኃላፊነት ደረጃ የሚያረጋግጠው የምስክር ወረቀት ፀንቶ የሚቆየዉ ለሁለት ዓመት ነው፡፡
2. የምስክር ወረቀት የተሰጠው እርሻ የተሰጠው የምስክር ወረቀት ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ከማብቃቱ ከሦስት ወር በፊት የምስክር ወረቀት እንዲታደስለት ለባለስልጣኑ ማመልከቻ ማቅረብ አለበት፡፡
3. በዚህ ደንብ መሠረት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ማንኛውም እርሻ ማሕበራዊ እና አካባቢያዊ የኃላፊነት ደረጃውን ስለመጠበቁ በየሁለት ዓመቱ በአረጋጋጭ መመዘን እና በባለሥልጣኑ እንደገና መረጋገጥ አለበት፡፡
4. የምስክር ወረቀት የሚታደሰው በዚህ አንቀጽ በንዑስ (2) መሠረት የተጠየቀው ማመልከቻ እንደገና ከተገመገመ እና ከተረጋገጠ በኋላ ነው፡፡

14.<u>የምስክር ወረቀት ያገኙ እርሻዎች ግዴታ</u>

1. የምስክር ወረቀት የተሰጣቸው እርሻዎች በዚህ ደንብ እና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች በተደነገጉ አካባቢያዊ እና ማህበራዊ ግዴታዎች መሰረት የራሳቸውን የውስጥ ኦዲት ማካሔድ አለባቸው።
2. እያንዳንዱ እርሻ በማረጋገጫው ሂደት መጀመሪያ እና ከዚያም በኋላ በየሁለት ዓመቱ የተሟላ የውስጥ ኦዲት ማካሔድ አለበት፡፡

15.<u>የባለሥልጣኑ ተግባራት</u>

1. ባለሥልጣኑ በአረጋጋጩ በሚቀርብለት ዘገባ መሠረት አግባብነት ያለዉን የማሕበራዊ እና የአካባቢ ኃላፊነት ደረጃ በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ በመወሰን ለእርሻዎች የምስክር ወረቀት መስጠት አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ(1 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሥልጣኑ የማሕበራዊ እና የአካባቢ የሃላፊነት ደረጃ የሚወስን የምስክር ወረቀት ለእርሻው ከመስጠቱ በፊት የመስክ ጉብኝት ሊያካሂድ ይችላል፡፡
3. ባለሥልጣኑ ከነሐስ ደረጃ በታች ዝቅ ባሉ እርሻዎች ላይ አግባብነት ያለውን እርምጃ እንዲወስድ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 152/2000 ለተቋቋመው ለኢትዮጵያ የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ማሳወቅ አለበት፡፡
4. ባለሥልጣኑ በዚህ ደንብ መሠረት በማረጋገጥ ተግባር ላይ ለመሰማራት ለሚፈልጉ ብቁ ድርጅቶች የሚያቀርቡለትን ማመልከቻ በመመርመር የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፡፡

5. ባለሥልጣኑ በተጠየቀ ጊዜ መሟላት የሚገባቸውን የአካባቢ፣ የማሕበራዊ እና የጤና መሥፈርቶችን ለእርሻዎች ማሳወቅ አለበት፡፡
6. ባለሥልጣኑ በዚህ ደንብ መሠረት የተገለጹትን አገልግሎቶች ለመስጠት ብቁ የሆኑ አረጋጋጮች ዝርዝር መያዝ አለበት፡፡
7. ባለሥልጣኑ ከሠራተኛና ማሕበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ከኢትዮጵያ የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ እንዲሁም ከሚመለከታቸው ሌሎች የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ጋር በመመካከር የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ተከባሪነትና ውጤታማነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ እርምጃዎችን መውሰድ አለበት፡፡

16.<u>ተቆጣጣሪዎች</u>

1. የዚህን ደንብ መከበር የሚያረጋግጡ ተቆጣጣሪዎችን ባለስልጣኑ ሊመድብ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀፅ (1) መሠረት ለተመደበ ተቆጣጣሪ ማንነቱን የሚገልጽ የመታወቂያ ወረቀት በባለሥልጣኑ ኃላፊ ተፈርሞ ይሰጠዋል።
3. ተቆጣጣሪው ሥልጣንና ተግባሩን በትጋትና ያለአድልዎ መፈጸም አለበት፡፡
4. የፍርድ ቤት ትዕዛዝ መያዝ ሳይጠበቅበትተቆጣጣሪው፡-
   ሀ) የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች እየተጣሱ ነው የሚያሰኘውን ምክንያት ሲያገኝ ወደ ማንኛውም የሥራ ቦታ ለመግባት፤
   ለ) ምርመራ ለማካሔድና የእርምት እርምጃዎች እንዲወሰዱ ለማዘዝ፤
   ሐ) እርሻውን በማስተዳደር ላይ ካለ ከማንኛውም ሰው መረጃን ጠይቆ ለማግኘት፤
   መ) የዚህን ደንብ ማናቸውም ድንጋጌዎች በመተላለፍ ጥፋት ተፈፅሞበታል ያለውን መሣሪያ፣ ማሕደር፣ ፅሑፍ ወይም ማንኛውንም ሌላ ሠነድ በማስረጃነት መያዝ፤
   ሠ) የማንኛውንም ቁስ ናሙናዎች እንደአስፈሳጊነቱ ያለክፍያ መውሰድ እና መመርመር ወይም እንዲመረመሩ ማድረግ፤

   ይችላል፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 17. መረጃን ስለማጠናቀር

1. እርሻዎች የአካባቢ፣ የማሕበራዊና የጤና ግዴታዎችን ስለማክበራቸው ዓመታዊ ዘገባ ባለሥልጣኑ በሚያዘጋጀዉ ቅፅ ማጠናቀርና ማቅረብ አለባቸው።
2. እርሻዎች በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰዉን ዘገባ የሚመለከቱትን ሠነዶቻቸዉን በሥራ ቦታቸዉ ቢያንስ ለአምስት ዓመታት ያህል ማቆየት እና ለተቆጣጣሪዎችም ክፍት መድረግ አለባቸዉ፡፡
3. በዚህ ደንብ መሠረት አስፈላጊ ሠነዶችን አለመስጠት ወይም በዚህ ደንብ ላይ የተጠቀሱ ተቆጣጣሪዎች ሥራን ማደናቀፍ አግባብነት ባለቸዉ የፍትሐብሔርና የወንጀል ሕጎች ያስጠይቃል፡፡

### 18. መመሪያዎችን የማዉጣት ሥልጣን

በአዋጅ ቁጥር 295/1995 መሠረት የተቋቋመዉ የአካባቢ ምክር ቤት[48] ይህንን ደንብ ተግባራዊ ለማድረግ አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

### 19. ደንብ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት 30 ቀን 2003 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

---

[48] 25/08 (2011) አ. 1097)11 አንቀጽ 36(17) የአካባቢ ደንና አየር ንበረት ለውጥ ኮሚሽን ሆኗል፡፡

## የፍትህ ሚኒስቴር

**<u>አዋጅ ቁጥር 482/1998</u>**

## <u>የጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰብ ዕውቀት አርክቦት እና የማህበረሰብ መብቶች አዋጅ</u>

ኢትዮጵያ ያላት ከፍተኛ ብዝሀ ህይወት ፀጋ ለሕዝቦቿ ጥቅምና ብልጽግና እንዲውል በአግባቡ መጠበቅና በዘላቂነት ጥቅም ላይ መዋል ያለበት በመሆኑ፣

ብዝሀ ህይወትን በመንከባከብ፣ በማበልፀግና በዘለቂነት በመጠበቅ ረገድ የኢትየጵያ ማህበረሰቦች ላደረጉት ታሪካዊ አስተዋጽኦ እዉቅና መስጠትና ይህንን አስተዋጽኦቸዉን እንዲቀጥሉበት ማበረታታት አስፈላጊ በመሆኑ፣

ኢትዮጵያ የብዘሀ ህይወት ኮንቬንሽንን የተቀበለች እና የኮንቬንሽኑም አርክቦት ህግ እንዲወጣ የሚጠይቅ በመሆኑ፣

የማህበረሰቦች፣ የአርሶ አደሮችንና የዕፅዋት አዲቃዮችን መብት እንዲሁም የሕይታዊ ሀብት አርክቦትን በሚመለከት የወጣዉን የአፍሪካ ሞዴል ሕግን ኢትዮጵያ የተቀበለች በመሆኑ፣

የጀነቲክ ሀብት እንዲጠበቅና በዘላቂነት ጥቅም ላይ እንዲውል ለማድረግ የሚያስችልና የኢትዮጵያ ማህበረሰቦች ያዳበሩት ልማዳዊ የጀነቲክ ሀብት ክብካቤና አጠቃቀም ሥርዓት ሊጠበቅና ሊበረታታ የሚገባው በመሆኑ፣

የጀነቲክ ሀብት ክብካቤና አጠቃቀምን በሚመለከት የኢትዮጵያ ማህበረሰቦች ያካበቱትና ያዳበሩት ዕውቀት እውቅና ሊያገኝና ጥበቃ ሊደረግለት እንዲሁም በእነዚህ ማህበረሰቦች ፈቃድና የጥቅም ተከፋይነት በሰፊው ጥቅም ላይ እንዲውል ሊበረታታ የሚገባው በመሆኑ፣

የጀነቲክ ሀብት ጥቅም ላይ እንዲውል በመፍቀዱና ጥቅም ላይ መዋሉ ከሚገኘው ገቢ በመጋራት ረገድ በሚሰጥ ውሳኔ ላይ የአካባቢ ማህበረሰቦች እንዲሳተፉ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

እነዚህን ዓላማዎች በተግባር ለማዋል የጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰብ ዕውቀት አርክቦትና ማህበረሰቦች በጀነቲክ ሀብታቸውና የማህበረሰብ ዕውቀታቸው ላይ ያላቸውን መብት በሕግ መወሰን አስፈላጊ በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55)1) መሠረት የሚከተለዉ ታዉጇል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ ‹‹የጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰብ ዕውቀት አርክቦት እና የማህበረሰብ መብቶች አዋጅ ቁጥር 482/1998›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ወስጥ፡-

1. ‹‹አርክቦት›› ማለት የጀነቲክ ሀብትን ወይም የማህበረሰብ ዕውቀትን መሰብሰብ፣ መውሰድ፣ ማስተላለፍ፣ ወይም መጠቀም ነው፣
2. ‹‹ሕይወታዊ ሀብት›› ማለት ለሰው ልጅ ጠቀሜታ ያለው ወይም ወደፊት ሊኖረው የሚችል የጀነቲክ ሀብት፣ የእዚሁ ሕዋሳት ወይም አካላት ወይም የእርሱ ስብስብ ወይም ማናቸውም የሥርዓት ምህዳር ሕይወት ያለው አካል ነው፣
3. ‹‹ተዋጽኦ›› ማለት ከሕይወታዊ ሀብት ተለይቶ የወጣ ወይም የተዘጋጀ ውጤት ሲሆን የዕፅዋት ዝርያዎችን፣ ዘይቶችን፣ ዕጣኖችን ሙጫዎችን፣ ፕሮቲንና የመሳሰሉትን ይጨምራል፣
4. ‹‹ኢዘቦታ›› ማለት የጀነቲክ ሀብት በተፈጥሮ ከሚገኝበት ቦታው ውጪ የሚገኝበት ሁኔታ ነው፣
5. ‹‹አሰሳ››ማለት አንድ የጀነቲክ ሀብት መኖሩን ወይም ያለበትን ሁኔታ ለማወቅ በሀገሪቱ ውስጥ የሚደረግ ፍለጋ ነው፣
6. ‹‹የጀነቲክ ሀብት›› ማለት ለሰው ልጅ ጠቀሜታ ያለው ወይም ወደፊት ጠቀሜታ ሊኖረው የሚችል የሕይወታዊ ሀብትን የዘር ባሕሪ የያዘ የጀነቲክ ቁስ ሲሆን ተዋጽኦን ይጨምራል፣
7. ‹‹ዘቦታ››ማለት የጀነቲክ ሀብት በተፈጥሮ በሚገኝበት አካባቢ ወይም ሥርዓት ምህዳሩ ውስጥ የሚገኝበት ሁኔታ ነው፣
8. ‹‹ኢንስቲትዩት›› ማለት በአዋጅ ቁጥር 120/1999[49] (እንደተሻሻለ) የተቋቋመው የብዝሀ ሕይወት ጥበቃ ኢንስቲትዩት ነዉ፡፡

[49]በ19/57 (2005) ደ. 291 እንደገና የተቋቋመው የኢትዮጲያ ብዝሀ ህይወት ኢንስቲትዩት ነው፡፡

9. ‹‹የአካባቢ ማህበረሰብ›› ማለት አንድ የጀነቲክ ሀብትን ተንከባክቦ ይዞ የሚገኝ ወይም የአንድ የማህበረሰብ ዕውቀት ፈጣሪ የሆነና በኢትዮጵያ በአንድ በተወሰነ የመልክዓ ምድራዊ አካባቢ የሚገኝ የሰዎች ስብስብ ነው፣
10. ‹‹ሰው›› ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፣
11. ‹‹አስቀድሞ ተገንዝቦ የሚሰጥ እሽታ›› ማለት የተወሰነ የጀነቲክ ሀብትን ወይም የማህበረሰብ ዕውቀትን ማርከብ የሚፈልግ ሰው አርክቦት ከመፈጸሙ በፊት በሚያቀርበው ትክክለኛና የተሟላ መረጃን የያዘ የአርክቦት ጥያቄ ላይ በመመሥረት ግለሰቡ የጀነቲክ ሀብቱን ወይም የማህበረሰብ ዕውቀትን እንዲያስረክብ ኢንስቲትዩቱ እና የሚመለከተው የአካባቢ ማህበረሰብ የሚሰጡት ፈቃድ ነው፣
12. ‹‹አግባብ ያለው ተቋም›› ማለት አንድን የጀነቲክ ሀብት ዘርፍ የማስተዳደር ኃላፊነት የተሰጠው ወይም በአንድ የጀነቲክ ሀብት ወይም የማህበረሰብ ዕውቀት ዘርፍ ልዩ ዕውቀት ያለው የመንግሥት አካል ነዉ፡፡
13. ‹‹መንግሥት›› ማለት አንደ አግባቡ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ወይም የክልል መንግሥት ማለት ነው፣
14. ‹‹የማህበረሰብ ዕውቀት›› ማለት የጀነቲክ ሀብት ማንበርን ወይም መጠቀምን በሚመለከት የአካባቢ ማህበረሰቦች የፈጠሩት ወይም ለዘመናት ያዳበሩት ዕውቀት፣ አሠራር፣ ፈጠራ ወይም ጥበብ ነው።
15. ‹‹ብዘኃ ሕይወት›› ማለት በየትኛውም ሥርዓተ ምህዳር በሚገኙ ህይወት ባላቸው ነገሮች መካከል የሚገኙ ተለያይነት ሲሆን፣ ይህም በዝርያዎች ውስጥ፣ ዝርያዎች እና በሥርአተ-ምህዳሮች መካከል ያለውን ተለያይነት ይጨምራል።

3. <u>ዓላማ</u>

የዚህ አዋጅ ዓላማ የሀገሪቱ የጀነቲክ ሀብት እና የማህበረሰብ እውቀት ጥቅም ላይ በመዋሉ ከሚገኘው ጥቅም ሀገሪቱና ማህበረሰቦቿ ፍትሐዊና ሚዛናዊ የሆነ ድርሻ እንዲያገኙ በማድረግ፣ የብዝሀ ህይወት ሀብት እንዲጠበቅና በዘላቂነት ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ ነው።

4. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

1. ይህ አዋጅ በዘቦታ ወይም በኢዘቦታ በሚገኙ የጀነቲክ ሀብቶች እና በማህበረሰብ ዕውቅት አርክቦት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም፣ ይህ አዋጅ ቀጥሎ በተጠቀሱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት የለውም፣
   ሀ) የኢትዮጵያ አካባቢ ማህበረሰቦች ራሳቸዉ ወይም በመካከላቸዉ በሚያደርጉት ልማዳዊ የጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰብ ዕውቀት ልዉዉጥና መጠቀም፣ እና
   ለ) የጀነቲክ ሀብቱን መጠቀምን ለማያስከትል ለምግብ ወይም ለመኖ መጠቀምን ለመሰለ የተለየ ጠቀሜታ በቀጥታ ለማዋል ሲባል በሚደረግ የህይወታዊ ሀብት ምርት ግብይት፣

5. **ባለቤትነት**

1. የጀነቲክ ሀብት ባለቤትነት የመንግሥትና የሕዝብ ይሆናል፡፡
2. የማህበረሰብ ዕውቀት ባለቤትነት የሚመለከተው የአካባቢ ማህበረሰብ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት
## የማህበረሰብ መብቶች መከበር

6. ***መሠረቱ***

የአካባቢ ማህበረሰቦች በጀነቲክ ሀብታቸዉና በማህበረሰብ ዕውቀታቸው ላይ የሚከተሉት መብቶች አሏቸዉ፡-

1. በማህበረሰብ ዕውቀታቸው ላይ የሚፈፀም አርክቦትን የመቆጣጠር መብት፣
2. የጀነቲክ ሀብታቸዉንና የማህበረሰብ ዕውቀታቸዉን የመጠቀም ሊገሰስ የማይችል መብት፣
3. የጀነቲክ መብታቸውንና የማህበረሰብ ዕውቀታቸዉን ጥቅም ላይ በመዋሉ ከሚገኘዉ ጥቅም የመጋራት መብት፡፡

7. **አርክቦትን የመቆጣጠር መብት**

1. የአካባቢ ማህበረሰቦች አርክቦትን ለመቆጣጠር ያለቸዉ መብት የሚከተሉትን ይጨምራል፡፡
   ሀ) ለማህበረሰብ ዕውቀት አርክቦት አስቀድሞ ተገንዝቦ የሚሰጥ እሽታ የመስጠት መብት፣
   ለ) አስቀድሞ ተገንዝቦ የሚሰጥ እሽታ እንዲሰጡ በሚጠየቁ ጊዜ የታሰበው የአርክቦት ተግባር የባህላዊና የተፈጥሮ ቅርሶቻቸው ላይ አደጋ የሚፈጥር መስሎ ከታያቸው ፈቃድ የመከልከል መብት፣

ሐ) ቀደም ሲል ሰጥተውት የነበረው አስቀድሞ ተገንዝቦ የሚሰጥ ፈቃድ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሕይታቸው ወይም በባህላዊና የተፈጥሮ ቅርሶቻቸው ላይ አደጋ ሊያስከትል የሚችል ሆኖ ካገኙት ፈቃዱን የማንሳት ወይም የመገደብ መብት፣

መ) ኢንስቲትዩቱ የሰጠው የጀነቲክ ሀብት አርክቦት ፈቃድ በባህላዊና የተፈጥሮ ቅርሶቻቸው ላይ አደጋ ሊያስከትል የሚችል ሆኖ ካገኙት ኢንስቲትዩቱ የሰጠው የአርክቦት ፈቃድ ገደብ እንዲደረግበት ወይም እንዲነሳ የመጠየቅ መብት።

2. የአካባቢ ማህበረሰቦች አስቀድሞ ተገንዝቦ የሚሰጥ እሽታ የሚሰጡበት ሁኔታና ሥርዓት በደንብ ይወሰናል፡፡

8. <u>**የመጠቀም መብት**</u>

1. የአካባቢ ማህበረሰቦች ለመኖር በሚያደርጉ እንቅስቃሴ የጀነቲክ ሀብታቸውን ወይም የማህበረሰብ ዕውቀታቸውን በልማዳዊ አሠራራቸውና ደንባቸው መሠረት የመጠቀም ወይም በመካከላቸው የመለዋወጥ ሊገሰስ የማይችል መብት አላቸው፡
2. በአካባቢ ማህበረሰቦች የጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰብ ዕውቀትን የመጠቀምና የመለዋወጥ ባህላዊ ሥርዓት ላይ የሕግ ገደብ አይደረግበትም፡፡

9. <u>**ጥቅም የመጋራት መብት**</u>

1. የአካባቢ ማህበረሰቦች የማህበረሰብ ዕውቀት ጥቅም ላይ በመዋሉ ከሚገኘው ገቢ ላይ የመጋራት መብት አላቸው፣
2. የአካባቢ ማህበረሰቦች የጀነቲክ ሀብታቸው ጥቅም ላይ በመዋሉ ምክንያት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 18)1)መሠረት መንግሥት በገንዘብ መልክ ከሚያገኘው ጥቅም ላይ 50 በመቶ የሚሆነውን የመጋራት መብት ይኖራቸዋል፣
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሠረት የሚገኘው ገንዘብ ለሚመለከታቸው የአካባቢው ማህበረሰቦች የጋራ ጥቅም ይውላል፣
4. ከአርክቦት ጥቅም መጋራት የሚገኘው ገንዘብ ለአካባቢ ማህበረሰቦች የጋራ ጥቅም የሚውልበት ሥርዓት በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

10. <u>**የማህበረሰብ መብቶች አከባበር**</u>

1. የአካባቢ ማህበረሰቦች በጀነቲክ ሀብታቸውና በማህበረሰብ ዕውቀታቸው ላይ ያላቸው መብት በራሳቸው ልማዳዊ አሠራርና ደንቦች መሠረት ጥበቃ ይደረግለታል፡፡

2. የማህበረሰብ ዕውቀት የሚለየው፣ የሚተረጐመውና የሚረጋገጠው በሚመለከተው የአካባቢ ማህበረሰብ ልማዳዊ አሠራሮችና ደንቦች መሠረት ነው፣
3. የማህበረሰብ ዕውቀት ተመዝግቦ አለመገኘቱ በማህበረሰብ መብትነት የሚከበር መሆኑን አያስቀርም፣
4. የጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰብ ዕውቀት በጽሑፍ ታትሞ መውጣቱ ወይም በቃል መገለጹ ወይም የጀነቲክ ሀብቱ በጅን ባንክ ወይም በሌላ ማናቸውም የማንበሪያ ቦታ ወይም ጥቅም ላይ ውሎ መገኘቱ በማህበረሰብ መብትነት የሚከበር መሆኑን አያስቀርም፡፡

## ክፍል ሦስት

## አርክቦት ስለሚፈጸምበት ሁኔታ

### 11. የፈቃድ አስፈላጊነት

1. የዚህ አዋጅ አንቀጽ(4) ንዑስ አንቀጽ 2(ሀ) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ከኢንስቲትዩቱ የአርከቦት ፈቃድ የተሰጠው ካልሆነ በስተቀር ለማናቸውም ሰው የጀነቲክ ሀብት ወይም የማህበረሰብ ዕውቀት ማርከብ የተከለከለ ነው፣
2. በግልጽ ተለይቶ ካልተፈቀደ በስተቀር የጀነቲክ ሀብትን ለማርከብ የተሰጠ ፈቃድ ከጀነቲክ ሀብቱ ጋር ተያይዞ የሚገኘውንም የማህበረሰብ ዕውቀት ለማርከብ ፈቃድ እንደተሰጠ አያስቆጥርም፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታም የማህበረሰብ ዕውቀት ለማርከብ የተሰጠ ፈቃድ ከዕውቀቱ ጋር ተያይዞ የሚገኘውን የጀነቲክ ሀብት ለማርከብ ፈቃድ እንደተሰጠ አያስቆጥርም፣
3. የዚህ አዋጅ አንቀጽ (4) ንዑስ አንቀጽ 2(ለ) እንደተጠበቀ ሆኖ ከኢንስቲትዩቱ ፈቃድ የተሰጠው ካልሆነ በስተቀር ለማናቸውም ሰው የጀነቲክ ሀብት ከሀገር ማስወጣት የተከለከለ ነው፣
4. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም የጀነቲክ ሀብትን ለመጠበቅ በሕግ ኃላፊነት የተሰጣቸው የመንግሥት አካላት ኃላፊነታቸውን ለመወጣት ጀነቲክ ሀብት ወይም የማህበረሰብ ዕውቀት ለመሰብሰብ ከኢንስቲትዩቱ የአርክቦት ፈቃድ ማግኘት አያስፈልጋቸውም፣ ሆኖም ከኢንስቲትዩቱ ፈቃድ ካላገኙ በስተቀር የጀነቲክ ሀብቱን ለሌላ ሰው ማስተላለፍ ወይም ከሀገር ማስወጣት አይችሉም። የእነዚህ መንግሥታዊ አካለት ሠራተኞች የጀነቲክ ሀብት አርክቦት በሚፈጽሙበት ጊዜ አርከቦት የሚፈጽሙ መሆናቸውን የሚገልጽ ደብዳቤ መያዝ ይገባቸዋል።

## 12. የአርክቦት መሠረታዊ ቅድመ ሁኔታዎች

1. የጀነቲክ ሀብትን ለማርከብ በቅድሚያ የኢንስቲትዩቱን አስቀድሞ ተገንዝቦ የሚሰጥ እሽታ ማግኘት ያስፈልጋል፣
2. የማህበረሰብ ዕውቀትን ለማርከብ በቅድሚያ የሚመለከተውን የአካባቢ ማህበረሰብ አስቀድሞ ተገንዝቦ የሚሰጥ እሽታ ማግኘት ያስፈልጋል፣
3. የጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰብ ዕውቀትን በመጠቀም ከሚገኘው ገቢ መንግሥትና የሚመለከተው የአካባቢ ማህበረሰብ ፍትሐዊና ሚዛናዊ የሆነ ጥቅም ማግኘት አለባቸው፣
4. የውጭ ሀገር ዜጋ የሆነ አርክቦት ጠያቂ የሀገሩ ወይም የሚኖርበት ሀገር አግባብ ያለው ባለሥልጣን አመልካቹ የሚኖሩበትን የአርክቦት ግዴታዎች በዚያ ሀገር የሚያስከብርና የሚያስፈጽም መሆኑን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ ማቅረብ ይኖርበታል፣
5. አርክቦት የሚፈጸመው በውጭ ሀገር ዜጋ በሆነ ጊዜ የጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰብ ዕውቀትን መሰብሰቡ የሚከናወነው የኢንስቲትዩቱ ወይም ኢንስቲትዩቱ የሚወክለው አግባብ ያለው ተቋም ባለሙያዎች በተሳታፊነት በተገኙበት መሆን አለበት፣
6. የማይቻል እስካልሆነ ድረስ በአርክቦት በተገኘ የጀነቲክ ሀገር ላይ የሚካሄድ ምርምር በኢትዮጵያ ውስጥና ኢንስቲትዩቱ የሚመድባቸው ኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች በሚሳተፉበት ሁኔታ መካሄድ አለበት፣
7. በአርክቦት በተገኘው የጀነቲክ ሀብት ላይ የሚካሄደው ምርምር ከኢትዮጵያ ውጪ እንዲካሄድ በሚፈቀድበት ጊዜ ምርምሩን የደገፈው ወይም ምርምሩ የሚካሄድበት ተቋም አርካቢውና ተቋሙ የአርክቦት ግዴታዎችን የሚያከብሩ ለመሆናቸው ማረጋገጫ መስጠት አለበት፡፡

## 13. አርክቦት የሚከለከልባቸው ሁኔታዎች

የሚከተሉት ሁኔታዎች በሚያጋጥሙበት ጊዜ ኢንስቲትዩቱ የአርክቦት ፈቃድ ለመከልከል ይችላል፡-

1. የቀረበው የአርክቦት ጥያቄ ዝርያው የተመናመነን የጀነቲክ ሀብት የሚመለከት ከሆነ፣
2. አርከቦቱ በሰው ጤና ወይም በአካባቢው ማህበረሰብ ባሕላዊ እሴት ላይ ጉጂ ተጽዕኖ የሚያስከትል ከሆነ፣

3. አርከቦቱ በአካባቢ ላይ ያልተፈለገ ጎጂ ተጽዕኖ የሚያስከትል ከሆነ፣
4. አርክቦቱ የሥርዓተ ምህዳር መጥፋት አደጋን የሚያስከትል ከሆነ፣
5. አርከቦቱ የጀነቲክ ሀብትን የኢትዮጵያን ብሔራዊ ሕግ ወይም ኢትዮጵያ ያፀደቀችዉን ዓለም አቀፍ ስምምነት ተጻራሪ ለሆነ ዓላማ ጥቅም ላይ ለማዋል ከሆነ፣
6. አርከቦት ጠያቂው ቀደም ሲል የአርከቦት ቅድመ ሁኔታዎችን ወይም የአርከቦት ውሎችን የጣሰ እንደሆነ።

14. **<u>የአርከቦት ፍቃድ ስለመስጠት</u>**

1. የጀነቲክ ሀብት ወይም የማህበረሰብ ዕውቀት አርከቦት ፈቃድ ማግኘት የሚፈልግ ሰው የአርከቦት ማመልከቻ በጽሑፍ ለኢንስቲትዩቱ ማቅረብ አለበት፡፡ የአርከቦትማመልከቻው የሚቀርብበትና ውሳኔ የሚሰጥበት ሁኔታና ሥርዓት በደንብ ይወሰናል፣
2. ኢንስቲትዩቱ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ላይ በመመሥረት የጀነቲክ አርከቦት ውል ተደራድሮ ይፈራረማል። የአርከቦት ውል ሲፈራረምም ኢንስቲትዩቱ የአርከቦት ፈቃድ ለጠያቂው ይሰጣል፡፡ ፈቃዱ የአርከቦቱን ዓላማ የሚገልጽና በአርከቦቱ የሚገኘውን የጀነቲክ ሀብት ከሀገር ለማስወጣት የተፈቀደ መሆን አለመሆኑን የሚያሳይ መሆን አለበት፣
3. የአርከቦት ጥያቄው የማህበረሰብ ዕውቀት አርክቦትን የሚጨምር በሆነ ጊዜ ኢንስቲትዩቱ የሚመለከተው የአካባቢ ማህበረሰብ የሰጠው አስቀድሞ ተገንዝቦ የሚሰጥ አሽታ ላይ በመመስረት የአርከቦት ውል ተደራድሮ ይፈርማል፣
4. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12(6) የተደነገገው ቅድመ ሁኔታ የተሟላ ካልሆነ በስተቀር የጀነቲክ ሀብት ከሀገር እንዲወጣ ፈቃድ አይሰጥም።

15. **<u>የተለየ የአርክቦት ፈቃድ</u>**

1. ኢንስቲትዩቱ በዚህ አዋጅ ውስጥ የተደነገገውን ሥርዓት በጥብቅ መከተል ሳያስፈልገው የመንግሥት የምርምር ተቋማት፣ ሀገራዊ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና በኢትዮጵያ የሚገኙ የበይነ መንግሥታት የምርምር ተቋማት በሀገር ውስጥ ለሚያካሂዱት የልማትና የአካዳሚ ምርምር ሥራ የጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰብ ዕውቀት በቀላሉ ማግኘት እንዲችሉ የተለየ የአርክቦት ፈቃድ ሊሰጣቸው ይችላል፡፡ ሆኖም የተለየ የአርክቦት ፈቃድ የሚሰጣቸው ተቋማት

አርክቦቱን በሚፈጽሙበት ጊዜ የሚኖርባቸውን ግዴታዎች ኢንስቲትዩቱ እንደአግባብነቱ ይወሰናል፣

2. ኢትዮጵያ አባል በመሆን ባፀደቀችው የባለ ብዙ ወገን የአርክቦት ሥርዓት መሠረት የሚደረግ የጀነቲክ ሀብት አርክቦት በባለብዙ ወገን የአርክቦት ሥርዓቱ በተገለፀው ሁኔታና ሥርዓት መሠረት ይፈፅማል፡፡ የባለብዙ ወገን የአርክቦት ሥርዓት አፈጻጸም የሚመራበት ሁኔታ በደንብ ይወሰናል፡፡

16.<u>የአርክቦት ውል ይዘት</u>

የአርክቦት ውል የሚከተሉትን ጉዳዮች መያዝ አለበት፡-

1. የአርክቦት ውሉ ተዋዋይ ወገኖችን ማንነት፣
2. ለማርከብ የተፈቀደውን የጀነቲክ ሀብት ዓይትና መጠን፣
3. ለማርከብ የተፈቀደውን ወይም ለማርከብ ከተፈቀደው የጀነቲክ ሀብት ጋር ተያይዞ የሚገኘውን የማህበረሰብ ዕውቀት መግለጫ፣
4. የጀነቲክ ሀብት ወይም የማህበረሰብ ዕውቀቱ የሚሰበሰብበት አካባቢ ወይም ይህንኑ የሚያቀርበው ሰው፣
5. ለማርከብ የተፈቀደው የጀነቲክ ሀብት ናሙና እና የማህበረሰብ ዕውቀት መግለጫ የሚቀመጥበትን ተቋም፣
6. ለማርከብ የተፈቀደው የጀነቲክ ሀብት ወይም የማህበረሰብ ዕውቀት ሊውል የታሰበበት አገልግሎት፣
7. የአርክቦት ውሉ በተጠቀሰው የጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰብ ዕውቀት ላይ በወቅቱ ካሉ ወይም ወደፊት ከሚፈጸሙ የአርክቦት ውሎች ጋር የሚኖረው ግንኙነት ምን እንደሚሆን፣
8. የጀነቲክ ሀብቱን በመሰብሰብ ወይም በጀነቲክ ሀብቱ ላይ በሚደረገው ምርምር ላይ እንዲሳተፍና የአርክቦት ውሉን አፈጻጸም እንዲቆጣጠር ኢንስቲትዩቱ የወከለው አግባብነት ያለው ተቋም የቱ እንደሆነ፣
9. መንግሥት ከጀነቲክ ሀብት አርክቦቱ የሚያገኘውን ጥቅም፣
10. የአርክቦት ዉሉ የማህበረሰብ ዕውቀት አርክቦትን የሚጨምር በሆነ ጊዜ የአካባቢ ማህበረሰቡ ከዚሁ የሚያገኘውን ጥቅም፣
11. የአርክቦት ውሉ የሚቆይበት ዘመን፣
12. አለመግባባቶች የሚፈቱበት መንገድ፣ እና
13. የአርክቦት ባለፈቃዱ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚኖሩት ግዴታዎች፡፡

17.<u>የአርክቦት ባለፈቃድ ግዴታዎች</u>

የአርክቦት ፈቃድ የተሰጠው ሰው የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፡-

1. የአርክቦት ፈቃዱን ቅጂ የጀነቲክ ሀብቱ በሚሰበስብበት አካባቢ ላለው ወረዳ አግባብነት ያለው አካል የመስጠትና በተጠየቀ ጊዜም የአርክቦት ፈቃዱን የማሳየት፣
2. የጀነቲክ ሀብት በሚሰበሰብበት ጊዜ የገበሬዎችን ዘር ወይም የዱር በቀል ዝርያዎችን ክምችት እንዲመናመን ያለማድረግ ወይም ከጀነቲክ ክምችት ውስጥ ከፍተኛ መጠን ያለውን የጀነቲክ ሀብት ተለያይነት ያለመውሰድ፣
3. ከጥብቅ ቦታዎች የጀነቲክ ሀብት በሚሰበሰብበት ወቅት የጥብቅ ቦታዎችን አስተዳደር ደንቦች የማክበር፣
4. የተሰበሰበውን የጀነቲክ ሀብት ናሙና፣ አሰባሰብ መረጃና የማህበረሰብ ዕውቀት መግለጫን በኢንስቲትዩቱ ወይም ኢንስቲትዩቱ በሚሰይመው አግባብነት ያለው ተቋም ዘንድ እንዲቀመጥ የማድረግ፣
5. ለማርከብ ከተፈቀደለት የጀነቲክ ሀብት ዓይትና መጠን ያለማለፍ፣
6. ኢንስቲትዩቱ ሲጠይቀው በአርክቦት ከወሰደው የጀነቲክ ሀብት ላይ ናሙና እና የማህበረሰብ ዕውቀት ቅጅ የመስጠት፣
7. ምርምሩ ስለሚገኝበት ደረጃ በመደበኛ ሁኔታ ለኢንስቲትዩቱ ሪፖርት የማቅረብና የጀነቲክ ሀብት በተደጋጋሚ የሚሰበሰብ ከሆነ ስለሚደርሰው የአካባቢ፣ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተጽዕኖ በመከታተል ለኢንስቲትዩቱ ሪፖርት የማቅረብ፣
8. ከምርምሩ የተገኙ ውጤቶችንና የተወሰደው የጀነቲክ ሀብት ከምን እንደደረሰ ለኢንስቲትዩቱ በጽሑፍ ማሳወቅ፣
9. ለኢንስቲትዩቱ አሳውቆ በጽሁፍ ፈቃድ ሳያገኝ በአርክቦት የተገኘን የጀነቲክ ሀብት ወይም ማህበረሰብ ዕውቀት ለሌላ ሦስተኛ ወገን አሳልፎ ያለመስጠት ወይም እንዲውል ከተፈቀደው የአገልግሎት ዓላማ ውጪ ለሆነ ጉዳይ ያለመጠቀም፣
10. የታቀደው ምርምር ወይም የአርክቦት ስምምነቱ ሲቋረጥ በጥቅም ላይ ያልዋለውን የጀነቲክ ሀብት ለኢንስቲትዩቱ የመመለስ፣
11. ለኢንስቲትዩቱ አሳውቆ ፈቃድ ሳያገኝ የአርክቦት ፈቃዱን ወይም ከፈቃዱ የሚመነጨውን መብትና ግዴታ ለሦስተኛ ወገን ያለማስተሳለፍ፣

12.በአርክቦት በተገኘው የጀነቲክ ሀብት ወይም የጀነቲክ ሀብቱ አካል በሆነ ነገር ላይ ማናቸውም የአእምሮአዊ ንብረት መብት ለማግኘት ሲፈለግ አግባብ ያለው የኢትዮጵያ ሕግ በሚፈቅደው መሠረት ከኢንስቲትዩቱ ጋር አዲስ ውል የመዋዋል፣

13.ከኢንስቲትዩቱ ግልጽ ፈቃድ ሳይሰጥ በአርክቦት በተገኘ የማህበረሰብ ዕውቀት ላይ ፓተንት ወይም ሌላ ማናቸውም ዓይነት የአእምሮአዊ ንብረት ጥበቃ ለማግኘት ያለመጠየቅ፣

14.በአርክቦት የተገኘውን ጀነቲክ ሀብት ወይም የማህበረሰብ ዕውቀት በመጠቀም ለተገኘ የምርት ውጤት የአእምሮአዊ ንብረት ጥበቃ ለማግኘት በሚቀርብ ማመልከቻ ውስጥ የጀነቲክ ሀብቱ ወይም የማህበረሰብ ዕውቀቱ የተገኘበትን አካባቢ በምንጭነት የመጥቀስ፣

15.በአርክቦት የተገኘ የጀነቲክ ሀብትን ወይም የማህበረሰብ ዕውቀትን በመጠቀም ከሚገኘው ገቢ ላይ ለመንግሥትና ለሚመለከተው የአካባቢ ማህበረሰብ የማጋራት፣

16.የሀገሪቱን ሕጐች በተለይም የጤና፣ የደህንነተ ሕይወትና የአካባቢ ጥበቃን በሚመለከት የወጡ ሕጐችን የማክበር፣

17.የአካባቢ ማህበረሰቦችን ባሕላዊ ልምዶች፣ ባሕላዊ እሴቶችና ደንባቸዉን የማክበር፣

18.የአርክቦት ውሉን ግዴታዎች የማክበር።

18.<u>**ጥቅም መጋራት**</u>

1. በአርክቦት የተገኘ የጀነቲክ ሀብትን ወይም የማህበረሰብ ዕውቀትን በመጠቀም ከሚገኘው ገቢ ላይ መንግሥትና የአካባቢ ማህበረሰቦች የሚጋሩት የጥቅም ዓይነትና መጠን በሚፈረመው በእያንዳንዱ የአርክቦት ስምምነት የሚወሰን ይሆናል፣
2. በገንዘብ መልክ ከሚገኘው ጥቅም ላይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9)1) የተመለከተው የአካባቢው ማህበረሰብ ድርሻ ከተቀነሰ በኋላ የሚቀረዉ ገንዘብ የጀነቲክ ሀብትን ለመንከባከብና ለማበልጸግ እና የማህበረሰብ ዕዉቀትን ለማስፋፋት ተግባር ይዉላል፡፡ ገንዘቡ ለዚህ ተግባር የሚዉልበት ሁኔታ ኢንስቱትዩቱ በሚያወጣዉ መመሪያ ይወሰናል፣

3. በመንግስትና በሚመለከተዉ የአካባቢ ማህበረሰብ መካከል የሚኖረው በገንዘብ ያልሆነ የጥቅም መጋራት ከአርክቦት ባለፈቃዱ ጋር በሚደረገው የጥቅም ክፍፍል ላይ ተመስርቶ በሚፈረመው የአርክቦት ስምምነት ዉስጥ የሚገለጽ ይሆናል፡፡

19. **የጥቅም አይነቶች**

የጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰብ ዕውቀትን ከማርከብ በመጋራት ሊገኝ የሚችለው ጥቅም የሚከተሉትን ሊጨምር ይችላል፡-

1. የፍቃድ ክፍያ፣
2. የቅድሚያ ክፍያ፣
3. በየደረጃው የሚፈፀም ክፍያ፣
4. ሮያሊቲ፣
5. ለምርምር የሚውል የገንዘብ ክፍያ፣
6. የአእምሮ ንብረት የጋራ ባለቤት መሆን፣
7. የሥራ ዕድል፣
8. በአርክቦት በተገኘው የጀነቲክ ሀብት ወይም የማህበረሰብ ዕውቀት ላይ በሚደረገው ምርምር በኢንስቲትዩቱ ወይም አግባብነትባለው ተቋም ውስጥ የሚሰሩ ኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች መሳተፍ፣
9. የጀነቲክ ሀብቱን በመጠቀም ምርት ለማምረት የሚያስፈልገውን የጀነቲክ ሀብት ጥሬ ዕቃ ለማቅረብ ቅድሚያ የማግኘት፣
10. የጀነቲክ ሀብትን ወይም የማህበረሰብ ዕውቀትን በመጠቀም የሚገኙ ምርቶችንና ቴክኖሎጂዎችን የማግኘት፣
11. የጀነቲክ ሀብትን የመጠበቅ፣ የመገምገም፣የማበልፀግ፣ የማራባትና የመጠቀም ችሎታን ለማዳበር በተቋምና በአካባቢ ማህበረሰብ ደረጃ ሥልጠናን የማግኘት፣
12. የመሣሪያ፣ መሠረተ ልማትና የቴክኖሎጂ ድጋፍ የማግኘት፣ እና
13. እንደ አግባብነቱ የሚገኝ ማናቸውም ሌላ ጥቅም፡፡

## ክፍል አራት

## ክትትል እና የማረሚያ እርምጃ

20. **ክትትል**

1. ኢንስቲትዩቱ የአርክቦት ውል አፈጻጸምን በሚከተሉት መንገዶች ይከታተላል፡-

    ሀ) በፍተሻ፣

ለ) የአርክቦት ባለፈቃዶችና በጀነቲክ ሀብት አሰባሰብና ምርምር ላይ እንዲሳተፉና አርክቦትን እንዲቆጣጠሩ የተመደቡ ተቋሞች በየጊዜው በሚያቀርቡት የክንውንና የውጤት ሪፖርት፣

ሐ) ማናቸውም ሰው ወይም ግለሰብ በሚያቀርበው ሪፖርት፣ እና

መ) አግባብ ሆኖ በሚገኝ ማናቸውም ሌላ የመከታተያ መንገድ፣

2. በጀነቲክ ሀብት አሰባሰብና በምርምር ላይ እንዲሳተፉና የአርክቦት ውል አፈጻጸምን እንዲቆጣጠሩ የተሰየሙ አግባብነት ያላቸው ተቋማት በተከናወነው የአሰባሰብና የምርምር እንቅስቃሴ በተገኘው ግኝትና በአርክቦት ውል አፈጻጸም ላይ በየወቅቱ ሪፖርት ለኢንስቲትዩት ማቅረብ አለባቸው፣

3. ኢንስቲትዩቱ አርከቦት በተፈፀመበት የማህበረሰብ ዕውቀት ላይ የተካሄደው ምርምር የደረሰበትን ደረጃና የተገኘውን ውጤት የማህበረሰብ ዕውቀቱን አጠቃቀምና የተገኘውን የጥቅም መጋራት በተመለከተ ለሚመለከተው የአካባቢ ማህበረሰብ መረጃ መስጠት አለበት፡፡

21.<u>የማረሚያ ዕርምጃ</u>

1. የጀነቲክ ሀብት አርከቦቱ በቀላሉ ሊመለስ የማይችል የጀነቲክ ሀብት መመናመን፣ የአካባቢ መራቆት ወይም የማህበረሰቦች ባሕላዊ እሴቶች መመናመን አደጋ የሚያስከትል ሆኖ ከተገኘ ኢንስቲትዩቱ የአርከቦት ውሉን መለወጥና የሚሰበሰበውን የጀነቲክ ሀብት መጠን መወሰን ወይም እንደ አግባብነቱ ማናቸውንም ሌላ ገደብ ማድረግ ይችላል፣

2. የአርከቦትባለፈቃዱ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችን ወይም የአርከቦት ውሉን ግዴታዎች የጣሰ ወይም ሳያከብር የቀረ እንደሆነ ወይም አርከቦቱ በብዝሀ ሕይወት ሀብት ወይም በአካባቢ ላይ የውድመት አደጋ ካስከተለ ወይም ቅድሚያ በሚሰጣቸው የሕዝብ ጥቅሞች ላይ ጉዳት ካስከተለ ኢንስቲትዩቱ የአርከቦት ውሉን አግዶ ወይም አቋርጦ የጀነቲክ ሀብት ወይም የማህበረሰብ ዕውቀት አርከቦቱ እንዳይቀጥል መከልከል አለበት፣

3. ኢንስቲትዩቱ የአርከቦት ውልን የመለወጥ፣ የማገድ ወይም የማቋረጥ እርምጃ ሲወሰድ ውሳኔውን ለሚመለከተው የአካባቢ ማህበረሰብና ለአርከቦት ባለፈቃዱ መግለጽ አለበት።

## ክፍል አምስት

## የጀኒቲክ ሀብት አሰሳ

### 22.ክልከላ

1. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 4)2) ድንጋጌ እንደ ተጠበቀ ሆኖ ከኢንስቲትዩቱ የጀነቲክ ሀብት አሰሳ ፈቃድ የተሰጠው ካልሆነ በስተቀር ማናቸውም ሰው የጀነቲክ ሀብት አሰሳ ለማካሄድ አይችልም፣
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ )1) ድንጋጌ ቢኖርም የጀነቲክ ሀብትን ለመጠበቅ በሕግ ኃላፊነት የተሰጣቸው የመንግሥት አካላት ኃላፊነታቸውን ለመወጣት ለሚያደርጉት የጀነቲከ ሀብት አሰሳ ከኢንስቲትዩቱ ፈቃድ ማግኘት አያሰፈልጋቸውም፡፡

### 23.ማመልከቻ ስለማቅረብ

1. የጀነቲክ ሀብት አሰሳ ፈቃድ ለማግኘት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ለኢንሰቲትዩቱ የጽሑፍ ማመልከቻ ማቅረብ ይኖርበታል፣
2. ማመልከቻው የአሰሳውን ዓላማ፣ የሚታሰሰውን የጀነቲክ ሀብት ዓይነት አሰሳው የሚካሄድበትን አካባቢና አሰሳውን ለማካሄድ የታቀደበትን ጊዜ ማመልከትአለበት፡፡

### 24.የአሰሳ ፍቃድ ስለመስጠት

1. ኢንስቲትዩቱ የተሟላ የጀነቲክ ሀብት አሰሳ ማመልከቻ ሲቀርብለት፣ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ አግባብነት ካለው ተቋም ጋር በመመካከር፣ አመልካቹ የአሰሳ ፈቃድ ይሰጣል፣
2. የአሰሳ ፈቃዱ የሚታሰሰውን የጀነቲክ ሀብት ዓይነት አሰሳው የሚካሄድበትን አካባቢ፣ አሰሳው ሊካሄድ የታቀደበት የጊዜ ሰሌዳና ኢንስቲትዩቱ አስፈላጊ ናቸው የሚላቸው ሌሎች ሁኔታዎችን ማመልከት አለበት፣
3. ኢንስቲትዩቱ የአሰሳ ፈቃድ ለውጭ ሀገር ዜጋ በሚሰጥበት ጊዜ በአሰሳው ላይ አብረው እንዲገኙ ባለሙያዎቹን መመደብ ወይም አግባብነት ያለውን ተቋም መወከል አለበት፡፡

### 25.የአሳሾች ግዴታዎች

የአሰሳ ባለፈቃድ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፡-

1. የአሰሳ ፈቃዱን ቅጅ አሰሳው በሚካሄድበት አካባቢ ላለው ወረዳ አግባብነት ላለው አካል የመስጠት፣

2. በአሰሳ ፈቃዱ ውስጥ የተጠቀሱ ግዴታዎችን በሚገባ የማክበር፣
3. አሰሳው ሲጠናቀቅ ሰለ አሰሳው ክንዋኔ ዝርዝርና የተሟላ ሪፖርት ለኢንሰቲትዩቱ የማቅረብ፣
4. ጥያቄ በቀረበለት ጊዜ የአሰሳ ፈቃዱን የማሳየት፣
5. አሰሳው በሚካሄድበት አካባቢ ያለውን ባሕል፣ ልማድ፣ አሴት፣ የንብረት መብቶችና የሀገሪቱን ህጎች የማክበር፡፡

## ክፍል ስድስት

## የአርክቦት አስተዳደር

### 26.የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር[50] ሥልጣን

በዚህ አዋጅ ውስጥ የዱር እንስሳት ጀነቲክ ሀብትን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች የማስፈፀም ሥልጣን የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ይሆናል።

### 27.የኢንስቲትዩቱ ሥልጣንና ተግባር

በዚህ አዋጅ በሌሎች አንቀጾች የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰብ ዕውቀት አርክቦት በዚህ አዋጅና ይህንን አዋጅ መሠረት በማድረግ በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት መከናወኑን የማረጋገጥ፣
2. ከአርክቦት የሚገኙ ጥቅሞችን መቀበልና ለባለጥቅሙ እንዲደርስ የማድረግ፣
3. የአርክቦት ውል ሞዴሎችን የማዘጋጀት፣
4. የዚህን አዋጅ ይዘት ለሕዝብ የማስተዋወቅ፣
5. የጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰብ ዕውቀት አርክቦት መረጃዎችን የመሰብሰብ፣ የማጠናቀር፣ የመተንተንና እንደአሰፈሳጊነቱ ለተጠቃሚዎች የማሠራጨት፣
6. ይህንን አዋጅ በመተላለፍ በሚፈፀሙ የወንጀል ተግባሮች ላይ ሕጋዊ እርምጃ እንዲወስድ የማድረግ፣
7. ይህንን አዋጅ በተግባር ለማዋል አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን የማውጣትና ሌሎች አስፈላጊ ተግባራትን ማከናወን፣
8. ተግባሩን በተሻለ መንገድ ለማካሄድ አስፈላጊና አመቺ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ሥልጣንና ተግባሩን በሕግ ለተቋቋመ አካል በውክልና የመስጠት፡፡

[50]በ14/31 (2000) አ.575 አንቀጽ 12 መሰረት የዱር እንስሳትን በተመለከተ የሚኒስቴሩን ስልጣን ለዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን ስለተላለፈ በዚሁ መሰረት ባለስልጣኑ በሚል ይነበብ፡፡

28.<u>**የአካባቢ ማህበረሰቦች ኃላፊነት**</u>

የአካባቢ ማህበረሰቦች፡-

1. የማህበረሰቡ አባል ያልሆነ ማናቸውም ሰው ፈቃድ ሳይኖረው የጀነቲክ ሀብት ከአካባቢው እንዳይሰበሰብና እንዳይወሰድ የመከልከል፣ እና
2. የማህበረሰቡ አባል ያልሆነ ማናቸውም ሰው የጀነቲክ ሀብት ከአካባቢው ሲሰበሰብ ወይም ሰብስቦ ይዞ ሲሄድ ፈቃድ ያለው መሆኑን የመጠየቅና ፈቃድ የሌለው ከሆነ ወዲያውኑ በአቅራቢያው ለሚገኝ የቀበሌ ወይም የወረዳ መስተዳድር የማሳወቅ ወይም ወደነዚሁ እንዲቀርብ የማድረግ፣

ኃላፊነት አለባቸው።

29.<u>**የክልል መስተዳድር አካላት ኃላፊ**</u>

የቀበሌ መስተዳድሮችና በየደረጃው የሚገኙ የጀነቲክ ሀብት ጥበቃ የሚመለከታቸው የክልል መስተዳድር አካላት፡-

1. የአካባቢው ማህበረሰብ አባል ያልሆነ ማናቸውምሰው ፈቃድ ሳይኖረው የጀነቲክ ሀብት ከክልላቸዉ እንዳይሰበሰብና እንዳይወሰድ የመቆጣጠር፣ እና
2. የአካባቢዉ ማህበረሰብ አባል ያልሆነ ማናቸዉም ሰዉ የጀነቲክ ሀብት ሲሰበሰብ ወይም ሰብስቦ ይዞ ሲሄድ ይህንን ለማድረግ ፈቃድ የያዘ መሆኑን መጠየቅና ፈቃድ የሌለው ከሆነ የሰበሰበዉ ጀነቲክ ሀብት በመያዝ ለህግ እንዲቀርብ የማድረግና የተያዘውን የጀነቲክ ሀብት ዓይነትና ይዞ የተገኘውን ሰዉ ማንነት ለኢንስቲትዩቱ በዝርዝር የማሳወቅ፣

   ኃላፊነት አለባቸዉ፡፡

30.<u>**የጉምሩክ ባለሥልጣኖች ኃላፊነት**</u>

የጉምሩክ ባለሥልጣኖች ከኢንስቲትዩቱ በሚሰጣቸው መመሪያ መሠረት የሚከተሉትን የመፈጸም ኃላፊነት ይኖርባቸዋል፡-

1. ከሀገሪቱ የሚወጣ የጀነቲክ ሀብት የመውጫ ፈቃድ ከኢንስቲትዩቱ የተሰጠበት መሆኑን የመቆጣጠር፣
2. የጀነቲክ ሀብት የሚያጓጉዝ ወይም የያዘ ከሀገር የሚወጣ ማናቸውም ሰው ከኢንስቲትዩቱ የተሰጠውን የጀነቲክ ሀብት ከሀገር የማስወጫ ፈቃድ እንዲያሳይ የመጠየቅ፣

3. አስፈላጊው ፈቃድ ሳይኖር ከሀገር በመውጣት ላይ የሚገኝ የጀነቲክ ሀብትንና የጀነቲክ ሀብቱን ከሀገር በማስወጣት ላይ የሚገኝን ሰው መያዝና ወዲያውኑ በአካባቢው ለሚገኝ አግባብነት ላለው አካልና ለኢንስቲትዩቱ የማሳወቅ፣
4. ወደ ውጭ ሀገር በሚላክ የጀነቲክ ሀብት ምርት መያዣ ላይ በምርቱ ውስጥ የሚገኘውን የጀነቲክ ሀብት መጠቀም የተከለከለ መሆኑንና ተጠቅሞ መገኘትም በሕግ የሚያስቀጣ ድርጊት መሆኑን የሚገልጽ ቃል የተፃፈበት መሆኑን የማረጋገጥ፡፡

31.<u>የመልዕክት አስተላላፊ ድርጅቶች ኃላፊነት</u>

የፖስታና ሌሎች የፈጣን መልዕክት አስተላላፊ ድርጅቶች የጀነቲክ ሀብትን በመልዕክትነት ከኢትዮጵያ ውጪ ለመላክ ከመቀበላቸውና ከመላካቸው በፊት ደንበኞቻቸው የጀነቲክ ሀብትን ከሀገር ለማስወጣት ከኢንስቲትዩቱ የተሰጣቸውን ፊቃድ እንዲያቀርቡ መጠየቅ አለባቸው።

32.<u>የኳራንቲን ተቆጣጣሪ መሥሪያ ቤቶች ኃላፊነት</u>

የኳራንቲን ተቆጣጣሪ መሥሪያ ቤቶች ለሕይወታዊ ሀብት ምርት የሚሰጡት የኳራንቲን ሰርተፊኬት በሕይወታዊ ሀብቱ ውስጥ የሚገኝን የጀነቲክ ሀብት ለመጠቀም የሚያስችል ፊቃድ አለመሆኑንና በኳራንቲን ሰርተፊኬቱ ብቻ በሕይወታዊ ሀብቱ ውስጥ የሚገኝን የጀነቲክ ሀብት መጠቀም የተከለከለና ወንጀል መሆኑን የሚገልጽ ቃል እንዲይዝ ማድረግ አለባቸው።

<u>ክፍል ሰባት</u>

<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

33.<u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች</u>

1. ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት የተደረጉ የአርክቦት ውሎች መከለስና ከዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ጋር እንዲጣጣሙ መደረግ አለባቸው።
2. ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት የተደረጉ የአርክቦትውሎች እስከሚከለሱና ከዚህ አዋጅ ጋር እንዲጣጣሙ እስከሚደረጉ ድረስ ከመፈፀም ታግደው ይቆያሉ።

34.<u>የመተባበር ግዴታ</u>

ለዚህ አዋጅና በአዋጁ መሠረት ለሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች አፈጻጸም ማናቸውም ሰው ከኢንስቲትዩቱ፣ አግባብነት ካላቸው ተቋማትና ከሚመለከታቸው የአካባቢ ማህበረሰቦች ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት፡

35. **ቅጣት**

1. ማናቸውምሰዉ፡-

   ሀ) ከኢንስቲትዩቱ የአርክቦት ፈቃድ በቅድሚያ ሳያገኝ የጀነቲክ ሀብት ወይም የማህበረሰብ ዕውቀትን ያረከበ፣

   ለ) በአርክቦት ማመልከቻ ውስጥ ወይም የአርክቦት ውል አፈጻጸም ክትትል ወቅት የሀሰት መረጃ የሰጠ፣

   ሐ) ከኢንስቲትዩቱ ፈቃድ ሳያገኝ በአርክቦት ውሉ ውስጥ የተጠቀሰውን የአርክቦት ዓላማ የለወጠ፣

   መ) የአሰሳ ፈቃድ በቅድሚያ ከኢንስቲትዩቱ ሳያገኝ የጀነቲክ ሀብት አሰሳያካሄደ ወይም የአሰሳ ፈቃድ ማመልከቻ ውስጥ የሀሰት መረጃ የሰጠ ከሆነ፣

   ያረከበው የጀነቲክ ሀብት መወረሱና የተሰጠው ፈቃድ መሠረዙ እንደዚሁም በፍትሐብሔር ረገድ የሚኖርበት ኃላፊነት ሳይቀር እንደነገሩ ሁኔታ ከሦስት ዓመት በማያንስ ጽኑ አሥራትና ከብር አስር ሺህ እስከ ሰላሳ ሺህ ሊደርስ በሚችል መቀጮ ይቀጣል፡፡

2. ድርጊቱ የተፈፀመው ብርቅዬ የጀነቲክ ሀብትን በሚመለከት የሆነ እንደሆነ እንደነገሩ ሁኔታ ከአምስት ዓመት በማያንስ ጽኑ አሥራትና ከሃምሳ ሺህ ብር እስከ አንድ መቶ ሺህ ብር ሊደርስ በሚችል መቀጮ ይቀጣል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ የተመለከቱት ድርጊቶች የተፈፀሙት በቸልኝነት የሆነ እንደሆነ ቅጣቱ ከአምስት ሺህ ብር የማያንስ መቀጮ ወይም እንደነገሩ ሁኔታና እንደወንጀሉ ከባድነት ከሦስት ወር የማያንስ ቀላል እሥራት ይሆናል፡፡

36. **ተፈጻሚ የማይሆኑ ሕጎች**

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።

37. **ደንብ የማዉጣት ስልጣን**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ በሚገባ ለማስፈጸም አስፈላጊ የሆኑ ደንቦችን ማውጣት ይችላል።

**38.** **<u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ የካቲት 20 ቀን 1998 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## ደንብ ቁጥር 169/2001

## የጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰብ ዕውቀት አርክቦትና የማህበረሰብ መብቶች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 471/1998 አንቀጽ 5 እና የጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰብ ዕውቀት አርክቦትና የማህበረሰብ መብቶችን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 482/1998 አንቀጽ 37 መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ ‹‹የጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰብ ዕውቀት አርክቦት እና የማህበረሰብ መብቶች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር169/2001›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

   1. ‹‹የአርክቦት ውል›› ማለት የጀነቲክ ሀብት እና/ወይም የማህበረሰብ ዕውቀት ለማርከብና ከዚያም የሚገኘውን ጥቅም ለመጋራት በአዋጁ አንቀጽ 14(2) መሠረት የሚፈረም ስምምነት ነዉ፤
   2. ‹‹የአርክቦት አመልካች›› ማለት በአዋጁ አንቀጽ14(1) መሠረት የአርክቦት ማመልከቻ ለኢንስቲትዩቱ ያቀረበ ሰዉ ነዉ፤
   3. ‹‹የአርክቦት ማመልከቻ›› ማለት የጀነቲክ ሀብት እና)ወይም የማህበረሰብ ዕውቀት ለማርከብ በአዋጁ አንቀጽ 14(1) መሠረት ለኢንስቲትዩቱ በጽሑፍ የቀረበ ጥያቄ ነው፤
   4. ‹‹የአርክቦት ገንዘብ›› ማለት በአርክቦት ውል መሠረት የጀነቲክ ሀብት እና)ወይም የማህበረሰብ ዕውቀት ጥቅም ላይ በመዋሉ ከተገኘው ገቢ በጥቅም ተጋሪነት የሚገኝ ገንዘብ ነው፤
   5. ‹‹ሥልጣን ያለው አካል›› ማለት በአርክቦት አመልካቹ ሀገር ውስጥ የአርክቦት ውልን ለማስፈጸም ሥልጣን የተሰጠው የመንግሥት አካል ነው፤

6. ‹‹የማህበረሰብ እሺታ›› ማለት የማህበረሰብ ዕውቀት አርክቦትን ለመፍቀድ የአካባቢ ማህበረሰቦች በአዋጁ አንቀጽ 7(1)(ሀ) መሠረት የሚሰጡት አስቀድሞ ተገንዝቦ የሚሰጥ ፈቃድ ነው፤
7. ‹‹ኢንስቲትዩት›› ማለት በአዋጅ ቁጥር 120/1990[51] (እንደተሻሻለ የተቋቋመው የብዝሀ ህይወት ጥበቃ ኢንስቲትዩት ነው፤
8. ‹‹ዓለም አቀፍ ስምምነት›› ማለት በተባበሩት መንግሥታት የምግብና እርሻ ድርጅት ሰላሳ አንደኛ ጉባኤ እ.ኤ.አ. በኖቬምበር 3 ቀን 2001 የፀደቀው እና በአዋጅ ቁጥር 330/1995 ኢትዮጵያ ያፀደቀችው የምግብና ግብርና ዕፀዋት ጀኒቲክ ሀብት ዓለም አቀፍ ስምምነት ነው፤
9. ‹‹የባለብዙ ወገን አርክቦት ሥርዓት›› ማለት በዓለም አቀፍ ስምምነቱ አንቀጽ 10 መሠረት የምግብና ግብርና ዕፀዋት ጀነቲክ ሀብቶችን አርክቦት እና ከዚያም የሚገኘውን ጥቅም ፍትሐዊና ሚዛናዊ በሆነ ሁኔታ መጋራትን ለማቀላጠፍ የተመሠረተው ሥርዓት ነው፤
10. ‹‹አዋጅ›› ማለት የጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰብ ዕውቀት አርክቦት እና የማህበረሰብ መብቶች አዋጅ ቁጥር 482/1998 ነው፤
11. ‹‹አግባብነት ያለው የክልል አካል›› ማለት የጀነቲክ ሀብት እና)ወይም የማህበረሰብ ዕውቀትን እንዲያስተዳድር ሥልጣንና ኃላፊነት የተሰጠው የክልል መንግሥት መሥሪያ ቤት ነው፤
12. ‹‹የጀነቲክ ቁስ ማስተላለፊያ መደበኛ ውል›› ማለት በዓለም አቀፍ ስምምነቱ አንቀጽ 12 መሠረት የፀደቀው የምግብና ግብርና ዕፅዋት ጀነቲክ ሀብት ቁስ ማስተላለፊያ ስምምነት ነው፤
13. ‹‹አርክቦት››፣ ‹‹የጀነቲክ ሀብት››፣ ‹‹የማህበረሰብ ዕውቀት››፣ ‹‹የአካባቢ ማህበረሰብ››፣ «ሰዉ››፣ «በአግባበነት ያለው ተቋም›› እና ‹‹መንግሥት›› የሚሉት ቃላት በአዋጁ የተሰጣቸው ትርጉም ይኖራቸዋል፤
14. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል።

[51]በ19/57 (2005) ደ.291 እንደገና የተቋቋመው የኢትዮጲያ ብዝሀ ህይወት ኢንስቲትዩት ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

## የአርክቦት ሥነ-ሥርዓት

## ንዑስ ክፍል አንድ

## ለንግድ ዓላማ የሆነ አርክቦት ስነ-ሥርዓት

3. **የአርክቦት ማመልከቻ አቀራረብ**

የጀነቲክ ሀብት እና/ወይም የማህበረሰብ ዕውቀትን ለማርከብ በአዋጁ አንቀጽ 14 (1) መሠረት የሚቀርበውን የአርክቦት ማመልከቻ በዚህ ደንብ አባሪ 1 ላይ በተገለጸው መሠረት መቅረብ ይኖርበታል።

4. **የአርክቦት ማመልከቻን ስለመቀበል**

ኢንስቲትዩቱ የአርክቦት ማመልከቻ ሲቀርብለት፡-

1. የአርክቦት ማመልከቻው በዚህ ደንብ አባሪ 1 ውስጥ የተገለፁትን መረጃዎች አሟልቶ የቀረበ መሆኑን ካረጋገጠ ማመልከቻውን በመቀበል በአርክቦት መዝገብ ላይ ይመዘግባል፣ ወይም
2. የአርክቦት ማመልከቻው በዚህ ደንብ አባሪ 1 ላይ የተገጹትን መረጃዎች አሟልቶ የቀረበ አለመሆኑን ካረጋገጠ የሚጎድለውን መረጃ በመግለጽ ተሟልቶ እንዲቀርብ ለአማልካቹ ይመልስለታል፡፡

5. **የአርክቦት ማመልከቻን ስለመመርመር**

1. ኢንስቲትዩቱ በዚህ ደንብ አንቀጽ 4 መሠረት ተቀብሎ የመዘገበውን የአርክቦት ማመልከቻ፣ ከአዋጁ ድንጋጌ እና ቀደም ሲል ከተፈረሙየአርክቦት ውሎች አንጻር በመመርመር የተጠየቀው አርክቦት ሊፈቀድ የሚችል ወይም መከልከል ያለበት መሆኑን ይወስናል።
2. ኢንስቲትዩቱ የአርክቦት ማመልከቻውን ከመረመረ በኋላ፡-
   ሀ) የተጠየቀዉን አርክቦት ለመፍቀድ የሚከለክል በቂ ምክንያት መኖሩን ካረጋገጠ፣ አርክቦቱን በመከልከል የከለከለበትን ምክንያት በመግለጽ ለአመልካቹ በጽሑፍ ያሳዉቃል፣ ወይም
   ለ) የተጠየቀውን አርክቦት መፍቀድ የሚከለክል ምክንያት አለመኖሩን ካረጋገጠ ማመልከቻው ለሕዝብ እንዲገለጽ ያደርጋል፡፡

6. **የአርክቦት ማመልከቻን ለሕዝብ ስለመግለጽ**

1. ኢንስቲትዩቱ የአርክቦት ማመልከቻዉን በአመልካቹ ወጪ ሰፊ ስርጭት ባለው ብሔራዊ ጋዜጣ እና እንደ ሁኔታዉ አርክቦቱ ሊፈፀም በታቀደበት አከባቢ በሚታተም የአካባቢ ጋዜጣ ላይ ታትሞ ለሕዝብ እንዲገለጽ ያደርጋል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1 የተጠቀሰው የህዝብ ማስታወቂያ፡-

   ሀ) የአመልካቹን ማንነትና ሌሎች አስፈላጊ ዝርዝሮችን፣

   ለ) ማርከብ የተፈለገዉን የጀነቲክ ሀብት እና/ወይም የማህበረሰብ ዕውቀት መግለጫ፣እና

   ሐ) የጀነቲክ ሀብቱ እና)ወይም የማህበረሰብ ዕውቀቱ ሊውል የታሰበበትን አገልግሎት የሚገልጹ ዝርዝሮችን፣

   መያዝ አለበት፡፡
3. ማናቸውም ሰው የሕዝብ ማስታወቂያው ለህዝብ ከተገለፀበት ዕለት አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ በአርክቦት ማመልከቻው ላይ ተቃዉሞ ለማቅረብ ወይም አስተያየት ለመስጠት ይችላል፡፡
4. ኢንስቲትዩቱ እንደ አስፈላጊነቱ አግባብነት ያላቸው ተቋማት በአርክቦት ማመልከቻው ላይ አስተያየት እንዲሰጡ ለማድረግ ይችላል፡፡

7. **የአርክቦት መረጃ ለሕዝብ ግልጽ ስለማድረግ**

የአርክቦት ማመልከቻ በማቅረብ ወይም አርክቦትን በመቆጣጠር ሂደት ለኢንስቲትዩቱ የሚቀርብ የአርክቦት መረጃ ለሕዝብ ግልጽ ይደረጋል፤ መረጃውን መመልከት የፈለገም ማንኛውም ሰው ሊመለከተው ይችላል፡፡

8. **በሚስጥር የሚያዝ መረጃ**

1. የዚህ ደንብ አንቀጽ 7 ድንጋጌ ቢኖርም፣ አሳማኝ ምክንያት በቀረበ ጊዜ ኢንስቲትዩቱ የአርክቦት ማመልከቻ በሚቀርብበት ወይም የአርክቦት ቁጥጥር በሚደረግበት ሂደት ለኢንስቲትዩቱ የሚቀርብ፣ በይፋ ያልተገጸና በሦስተኛ ወገኖች ቅን ላልሆነ የንግድ ዓላማ ሊዉል የሚችል የአርክቦት መረጃ ከ10 ዓመት ላልበለጠ ጊዜ በሚስጥር እንዲያዝ ለመፍቀድ ይችላል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም የአርክቦት አመልካቹን ማንነት፣ ለማርከብ የተፈለገውን የጀነቲክ ሀብት ዓይነት፣ የጀነቲክ ሀብቱ የሚገኝበትን አካባቢ፣ የጀነቲክ ሀብቱን የሚያቀርበው ሰው ማንነት ወይም የጀነቲክ ሀብቱ በሚሰበሰብበት ወቅት አብሮ የሚገኘዉንና አርክቦቱን

የሚቆጣጠረውን ተቋም ማንነት የሚመለከት መረጃ በሚስጥር እንዲያዝ አይፈቀድም፡፡

3. የአርክቦት መረጃ በሚስጥር እንዲያዝለት የሚፈልግ የአርክቦት አመልካች፣ መረጃው በሚስጥር እንዲያዝ የሚያስፈልግበትን ምክንያትና በሚስጥር እንዲያዝ የተፈለገውን መረጃ በመግለጽ ጥያቄውን በጽሑፍ ለኢንስቲትዩቱ ማቅረብ አለበት፡፡
4. ኢንስቲትዩቱ የአርክቦት መረጃ በሚስጥር እንዲያዝ ሲፈቅድ፣ በሚስጥር የሚያዘውን መረጃና በሚስጥር የሚቆይበትን ጊዜ ማመልከት ይኖርበታል።
5. ኢንስቲትዩቱ በሚስጥር እንዲያዝ የፈቀደውን መረጃ በተለየ ፋይል በማድረግ በሚስጥር ይይዛል።

9. **<u>በሚስጥር የተያዘ መረጃን ስለመግለጽ</u>**

1. በሚስጥር እንዲያዝ የተፈቀደ መረጃ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ፣ በሚስጥር እንዲያዝ የተፈቀደበት ጊዜ ሲያበቃ ወይም በተዋዋይ ወገኖች የጋራ ስምምነት መሠረት ካልሆነ በስተቀር ለሦስተኛ ወገን አይገለጽም፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1 ድንጋጌ ቢኖርም፣ ኢንስቲትዩቱ በሚስጥር እንዲያዝ የተፈቀደ መረጃን ሠራተኞቹ ወይም አማካሪዎቹ እንዲገመግሙት ሊገልጽላቸው ይችላል፡፡ ሆኖም ይህ በሚፈፀምበት ወቅት ኢንስቲትዩቱ መረጃው በሚስጥር የተያዘ መሆኑን ሠራተኞቹንና አማካሪዎቹን ማስገንዘብ አለበት፡፡

10. **<u>የአርክቦት ውሳኔ አሰጣጥ</u>**

1. በአርክቦት ማመልከቻው ላይ ተቃውሞ ለማቅረብ ወይም አስተያየት ለመስጠት የተቀመጠው የጊዜ ገደብ እንዳበቃ፣ ኢንስቲትዩቱ የቀረቡለትን ተቃውሞዎችና አስተያየቶች በመመርመር፡-
   ሀ) የአርክቦት ማመልከቻው ሲከለከል የሚችልበት ምክንያት መኖሩን ካረጋገጠ፣ የአርክቦት ማመልከቻውን ውድቅ በማድረግ ይህንኑ ለአመልካች ያሳዉቃል፣ ወይም
   ለ) የአርክቦት ማመልከቻውን የሚያስከለክል ምክንያት አለመኖሩን ካረጋገጠ፣ አርክቦቱ ሊፈቀድ እንደሚችል በመወሰን የአርክቦትና ጥቅም ተጋሪነት ድርድር እንዲደረግ ለአርክቦት አመልካቹ ያሳዉቃል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ለ) መሠረት ሊፈቀድ እንደሚችል የተወሰነ የአርክቦት ማመልከቻ የማህበረሰብ ዕውቀት ማርከብን የሚጨምር በሆነ ጊዜ፣ እንስቲትዩቱ በዚህ ደንብ ክፍል ሦስት በተገለጸው መሠረት የማህበረሰብ እሺ.ታ እንዲስጥበት ያደርጋል፡፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## ለንግድ ዓላማ ያልሆነ አርክቦት ሥነ-ሥርዓት

### 11.የማመልከቻ አቀራረብ

በአዋጁ አንቀጽ 15 መሠረት ለሚያከናውኑት የትምህርት ወይም የምርምር ተግባራት ለማዋል የጀነቲክ ሀብት እና)ወይም የማህበረሰብ ዕውቀት ማርከብ የሚፈልጉ የኢትዮጵያ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትና የምርምር ተቋማት እንዲሁም ተቀማጭነታቸው በኢትዮጵያ የሆነ የበይነ-መንግሥታት ተቋማትለኢንስቲትዩቱ የሚያቀርቡት የአርክቦት ማመልከቻ በዚህ ደንብ አባሪ 2 መሠረት መቅረብ ይኖርበታል።

### 12.ፍቃድ አሰጣጥ

ኢንስቲትዩቱ በዚህ ደንብ አንቀጽ 11 መሠረት በኢትዮጵያ የትምህርት ወይም የምርምር ተቋም ወይም ተቀማጭነቱ በኢትዮጵያ በሆነ የበይነ መንግሥታት ተቋም የአርክቦት ማመልከቻ ሲቀርብለት አመልካቹ አርክቦቱን ሲያካሄድ የሚኖሩበትን ግዴታዎች በመወሰንና ለዚህም የአርክቦት ውል በማስፈረም የአርክቦት ፈቃድ ይሰጣል፡፡

### 13.የጀነቲክ ሀብትን ከሀገር ስለማስወጣት

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 12 መሠረት የአርክቦት ፈቃድ የሚሰጣቸው የኢትዮጵያ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትና የምርምር ተቋማት እንዲሁም ተቀማጭነታቸው በኢትዮጵያ ውስጥ የሆነ የበይነ-መንግሥታት ተቋማትየጀነቲክ ሀብትን ወደ ውጭ እንዲልኩ ፈቃድ ካልተሰጣቸው በስተቀር የአርከቡትን የጀነቲክ ሀብት ከኢትዮጵያ ማስወጣት አይችሉም።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1 ድንጋጌ ቢኖርም፣ የኢትዮጵያ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ወይም የምርምር ተቋም ወይም ተቀማጭነቱ በኢትዮጵያ የሆነ የበይነ-መንግሥታት ተቋም ምርምሩን ኢትዮጵያ ውስጥ ለማካሄድ የማይችል መሆኑን ኢንስቲትዩቱ ካረጋገጠ፣ የጀነቲክ ሀብትን ወደውጪ መላክ የሚችል መሆኑን በሚሰጠው የአርክቦት ፈቃድ ውስጥ ማመልከት ይችላል፡፡

3. ኢንስቲትዩቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2 መሠረት የጀነቲክ ሀብትን ከኢትዮጵያ ለማስወጣት ፈቃድ ሲሰጥ፣ ሀገሪቱ በጀነቲክ ሀብቱ ላይ ያላትን መብት ሊያስጠብቅ የሚችልና የጀነቲክ ሀብቱ የሚወሰድበትን የውጭ ሀገር ተቋም ያካተተ የአርክቦት ውል ማስፈረምና የስምምነቱን አፈጻጸም መከታተል ይኖርበታል።

## ንዑስ ክፍል ሦስት

## የባለብዙ ወገን አርክቦት ሥነ ሥርዓት

### 14.የባለብዙ ወገን አርክቦት ቅድመ ሁኔታዎች

በባለብዙ ወገን አርክቦት ሥርዓት መሠረት የጀነቲክ ሀብት አርክቦት የሚፈቀደው፡-

1. የተጠየቀውን የጀነቲክ ሀብት ዓይነት በዓለም አቀፍ ስምምነቱ አባሪ 1ውስጥ ተጠቅሶ የሚገኝ ከሆነ እና የጀነቲክ ሀብቱ ለምግብና ግብርና ምርምር፣ ማዳቀልና ሥልጠና አገልግሎት ለመጠቀምና ለማንበር ብቻ የሚውል እና ይህም አገልግሎት ለኬሚካል፣ለመድሀኒት እና)ወይም ለሌላ ለምግብ ወይም ለመኖ ያልሆነ ኢንዱስትሪያዊ አገልግሎት ማዋልን የማይጨምር ከሆነ፣
2. የአርክቦት አመልካቹ የዓለም አቀፍ ስምምነቱ ፈራሚ የሆነ ሀገር ዜጋ ወይም ነዋሪ ከሆነ፣ እና
3. የጀነቲክ ሀብቱ ለሕዝብ ጥቅም አገልግሎት እንዲውል በኢትዮጵያ መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የዘቦታ ወይም የኢዘቦታ ጥበቃና አስተዳደር ስር የሚገኝ ከሆነ ወይም የጀነቲክ ሀብቱ ባለይዞታ የሆነ በኢትዮጵያ ውስጥየሚገኝ ሰው የጀነቲክ ሀብቱ በባለብዙ ወገን አርክቦት ሥርዓቱ ውስጥ እንዲካተት የፈቀደ በሆነ ጊዜ ብቻ፣

ነው፡፡

### 15.የአርክቦት ማመልከቻ

በባለብዙ ወገን አርክቦት ሥርዓት መሠረት የጀነቲክ ሀብት ለማርከብ የሚፈልግ ሰው በዚህ ደንብ አባሪ 3 በተገለጸው መሠረት የተዘጋጀ የአርክቦት ማመልከቻ ለኢንስቲትዩቱ ማቅረብ አለበት፡፡

16.**የባለብዙ ወገን አርክቦት ውሳኔ አሰጣጥ**

ኢንስቲትዩቱ የቀረበለትን የባለብዙ ወገን አርክቦት ማመልከቻ ከመረመረ በኋላ፡-

1. የአርክቦት ማመልከቻው በዚህ ደንብ አንቀጽ 14 የተጠቀሱትን የባለብዙ ወገን አርክቦት ቅድመ ሁኔታዎች ያሟላ መሆኑን ካረጋገጠ፣ የባለብዙ ወገን አርክቦት ፈቃድ ለአመልካቹ ይሰጣል፤ ወይም
2. የአርክቦት ማመልከቻው በዚህ ደንብ አንቀጽ 14 የተጠቀሱትን የባለብዙ ወገን አርክቦት ሥርዓት ቅድመ ሁኔታዎች የማያሟላ መሆኑን ካረጋገጠ፣ አርክቦቱን በመከልከል ይህንኑ ለአመልካቹ ያሳውቃል።

17.**የአርክቦት ክፍያ**

1. የባለብዙ ወገን አርክቦት የተፈቀደለት አመልካች የጀነቲክ ሀብቱን ለማቆየትና ለእርሱ ለማቅረብ የሚያስፈልገውን ወጪ መሸፈን ይገባዋል።ይህም የጀነቲክ ሀብቱን ለመጠበቅ የወጣውን ወጪ፣ ናሙናውሊሰጠው የሚችለው ተባዝቶ ወይም ተሰብስቦ ከሆነ ለማባዛት ወይም ለመሰብሰብ የሚያስፈልገውን ወጪ፣ እንዲሁም ናሙናው ከበሽታ ነጻ መሆኑን ለማረጋገጥ፣ ለማሸግና በፖስታ ለመላክ የሚያስፈልጉ እና የመሳሰሉ ወጪዎችን ይጨምራል።
2. ኢንስቲትዩቱ የባለብዙ ወገን ጀነቲክ ሀብት አርክቦት ፈቃድ ሲሰጥ አመልካቹ መክፈል የሚገባውን የአርክቦት ክፍያ ይወሰናል፡፡

18.**የተቀላጠፌ አርክቦት ስለመስጠት**

ኢንስቲትዩቱ የባለብዙ ወገን የአርክቦት ፈቃድ ሲሰጥ፣ ሌላ ተጨማሪ ቅድመ ሁኔታ ሳይጠይቅ የጀነቲክ ሀብት ቁስ ማስተላለፊያ መደበኛ ውል በማስፈረምና የአርክቦት ክፍያ በማስከፈል የጀነቲክ ሀብቱን ካለው የፓስፖርት መረጃና ሚስጥር ያልሆነ ተያያዥ ገላጭ መረጃዎች ጭምር ለአመልካቹ ይሰጣል፡፡

19.**ክትትልና ቁጥጥር**

ኢንስቲትዩቱ በባለብዙ ወገን አርክቦት ሥርዓት መሠረት የሰጠው የጀነቲክ ሀብት በተፈረመው የጀነቲክ ቁስ ማስተላለፊያ መደበኛ ውል መሠረት ጥቅም ላይ መዋሉን በመከታተልና በመቆጣጠር አግባብነት ባለው ህግ መሠረት አስፈላጊዉን እርምጃ መውሰድ አለበት፡፡

20.**ክስ ስለማቅረብ**

የጀነቲክ ቁስ ማስተላለፊያ መደበኛ ዉል አፈጻጸምን አስመልክቶ የሚነሳ ክርክር ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊቀርብ ይችላል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የማህበረሰብ እሺታ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት

### 21. እሺታ የሚሰጠውን ማህበረሰብ ስለመለየት

1. የማህበረሰብ ዕውቀትን ለማርከብ ለሚቀርብ የአርክቦት ማመልከቻ እሺታ የሚሰጠው የዕውቀቱ ባለቤት የሆነው ማህበረሰብ ነው፡፡
2. የማህበረሰብ ዕውቀትን ለማርከብ ማመልከቻ ሲቀርብለት፣ ኢንስቲትዩቱ ቀደም ሲል ባካሄደው የጀነቲክ ሀብት እና)ወይም የማህበረሰብ ዕውቀት ስርጭት አሰሳ ላይ በመመስረትና አግባብነት ካላቸው የክልል አካላት ጋር በመመካከር የማህበረሰብ ዕውቀቱ ባለቤት የሆነው ማህበረሰብ እንዲለይና የማህበረሰብ እሺታ እንዲሰጥበት ያደርጋል፡፡

### 22. የማህበረሰብ እሺታ አሰጣጥ

የማህበረሰብ እሺታ የሚሰጠው የማህበረሰብ ዕውቀቱ ባለቤት የሆነው ማህበረሰብ የሚገኘው፡-

1. በአንድ ወረዳ ውስጥ ብቻ ከሆነ፣ በወረዳው ምክር ቤት፣
2. በአንድ ክልል ውስጥ በሚገኙ የተለያዩ ወረዳዎች ወይም ዞኖች ውስጥ ከሆነ፣ ከእነዚህ ወረዳዎች ወይም ዞኖች የተወከሉ የክልል ምክር ቤት አባላትን በማካተት በሚቋቋም የክልል ምክር ቤት ጊዜያዊ ኮሜቴ፣ ወይም
3. በተለያዩ ክልሎች ውስጥ ከሆነ፣ ማህበረሰቡ ከሚገኝባቸው አካባበዎች የተወከሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላትን በማካተት በሚቋቋም የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጊዜያዊ ኮሚቴ፣

አማካይነት ይሆናል፡፡

### 23. የአርክቦት ማመልከቻን ለእሺታ ስለማቅረብ

ለማህበረሰብ ዕውቀት አርክቦት ማመልከቻው እሺታ የሚሰጠው ማህበረሰብ በዚህ ደንብ አንቀጽ 21(2) መሠረት ተለይቶ እንደታወቀ ኢንስቲትዩቱ፡-

1. የማህበረሰብ እሺታ የሚሰጠው በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚቋቋም ጊዜያዊ ኮሜቴ ከሆነ፣ የአርክቦት ማመልከቻውን ከውሳኔ ሀሳብ ጋር ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያቀርባል፣

2. የማህበረሰብ እሺታ የሚሰጠው በወረዳ ምክር ቤት ወይም በክልል ምክር ቤት በሚቋቋም ጊዚያዊ ኮሚቴ ከሆነ፣ የአርክቦት ማመልከቻውን ከውሳኔ ሀሳብ ጋር እሺታውን ለሚሰጠዉ የወረዳ ምክር ቤት ወይም የክልል ምክር ቤት እንዲያቀርብ አግባብነት ላለው የክልል አካል ያስተላልፋል፡፡

24.<u>የእሺታ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት</u>

1. የወረዳ ምክር ቤቶች፣ የክልል ምክር ቤት ጊዜያዊ ኮሚቴዎች እና የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጊዜያዊ ኮሜቴዎች የማህበረሰብ እሽታ የሚሰጡት የምክር ቤቶቻቸውን የስብሰባና የውሳኔ አሰጣጥ ሥነሥርዓት በመከተል ይሆናል፡፡
2. የወረዳ ምክር ቤቶች፣ የክልል ምክር ቤት ጊዜያዊ ኮሜቴዎች እና የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጊዜያዊ ኮሜቴዎች የሚሰጡት ውሳኔ ቅጂ ለኢንስቲትዩቱ ቀርቦ ከአርክቦት መዝገቡ ጋር ይያያዛል።

25.<u>ወጪን ስለመሸፈን</u>

የማህበረሰብ እሺታ ለማሰጠት የሚያስፈልገውን ወጪ የአርክቦት አመልካቹ ይሸፍናል፡፡

<u>**ክፍል አራት**</u>

<u>**የአርክቦት ገንዘብ አስተዳደርና አጠቃቀም**</u>

26.<u>የአርክቦት ገንዘብ አስተዳደር</u>

1. ከጀነቲክ ሀብት እና)ወይም የማህበረሰብ ዕዉቀት አርክቦት የሚገኘዉ ገንዘብ ሁሉ ጥቅም ላይ እስከሚዉል ድረስ ‹‹የአርክቦት ፈንድ›› በሚሰኝ ልዩ ሂሳብ እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡
2. ከእያንዳንዱ የአርክቦት ዉል የሚገኝ ገንዘብ በተለየ የባንክ ሂሳብ ሆኖ በአርክቦት ፈንዱ ዉስጥ ተለይቶ ይቀመጣል፡፡
3. ኢንስቲትዩቱ የእያንዳንዱ የአርክቦት ዉል ዘመን ሲያበቃ ወይም እንደ አስፈላጊነቱ ከዚያም በፊት በማናቸውም ጊዜ የአርክቦት ገንዘቡ በዚህ ደንብ አንቀጽ 27 እና ለ28 በተደነገገዉ መሠረት ጥቅም ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡

27.<u>የአርክቦት ገንዘብን ለብዝሀ ህይወት ጥበቃ ስለማዋል</u>

1. በአዋጁ አንቀጽ 18(1) መሰረት ለብዝሀ ህይወትና ለማህበረሰብ ዕውቅት ጥበቃ እንዲውል የተመደበው የአርክቦት ገንዘብ፣ ገንዘቡን ያስገኘውን የጀነቲክ ሀብት ለመጠበቅ፣ ወይም ገንዘቡን ያስገኘው የጀነቲክ ሀብት የመመናመን አደጋ ከሌለበት ሌሎች የጀነቲክ ሀብቶችን ለመጠበቅና በዘላቂነት ለመጠቀም

እንዲሁም ተያያዥ የማህበረሰብ ዕውቀቶችን ለመጠበቅለሚነደፉ ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ ይውላል፡፡

2. የአርክቦት ገንዘቡ ጥቅም ላይ የሚውልባቸው የብዝሃ ሕይወት ጥበቃ ፕሮጀክቶች የሚመረጡት ኢንስቲትዩቱ አግባብነት ላላቸው የክልልና የፌዴራል አካላት በሚያደርገው ግብዣ መሠረት ከሚቀርቡለት የፕሮጀክት ሀሳቦች መሀከል ይሆናል፡፡
3. ኢንስቲትዩቱ የእያንዳንዱ የአርክቦት ውል ዘመን ሲያበቃ ወይም እንደ አስፈላጊነቱ ከዚያም በፊት በማናቸውም ጊዜ ኢንስቲትየቱ የፕሮጀክት ሀሳቦች የሚቀርበብትንና የሚመረጡበትን መመዘኛዎች በሚወሰን የፕሮጀክት ሀሳቦች እንዲቀርቡ አግባብነት ላላቸውየክልልና የፌዴራል አካላት ጥሪ ያደርጋል፡፡
4. አሸናፊው ፕሮጀክት እንደተመረጠ፣ ፕሮጀክቱ ማስፈጸሚያ የሚሆን ገንዘብ ከአርክቦት ገንዘብ ሂሳቡ ወጪ ሆኖ ፕሮጀክቱን ለሚያሰፈጽመው አካል ይከፈላል፡፡

28.<u>**የአርክቦት ገንዘብን ለማህበረሰቦች ጥቅም ስለማዋል**</u>

በአዋጁ አንቀጽ 9(1 እና (2 መሠረት ለማህበረሰቦች ጥቅም እንዲውል የተወሰነው የአርክቦት ገንዘብ የዚያ የጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰብ ዕውቀት ባለቤት ለሆነው ማህበረሰብ ጠቀሜታ ለሚነደፉ የልማት ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ ይውላል፡፡

29.<u>**ተጠቃሚውን ማህበረሰብ ስለመለየት**</u>

1. ኢንስቲትዩቱ ባካሄደው የጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰብ ዕዉቀት ስርጭት ቅኝት ላይ በመመስረት አግባብነት ካላቸው የክልል አካላት ጋር በመመካከር ከእያንዳንዱ የአርክቦት ዉል የሚገኘው ገንዘብ ተጠቃሚ መሆን የሚገባዉን ማህበረሰብ እንዲለይ ያደርጋል፡፡
2. የአርክቦት ገንዘቡ ተጠቃሚ የሆነዉ ማህበረሰብ የሚገኘው በተለያዩ ወረዳዎች፣ ዞኖች ወይም ክልሎች ውስጥ በሆነ ጊዜ፣ በነዚህ ወረዳዎች፣ ዞኖች እና ክልሎች ውስጥ የሚገኙት ማህበረሰቦች የተጠቃሚነት ድርሻ መጠን የጀነቲክ ሀብቱን እና)ወይም የማህበረሰብ ዕውቀቱን ለመጠበቅ ካደረጉት አስተዋጽኦ አንጻር እየታየ የሚወሰን ይሆናል፡፡

30.<u>**የአርክቦት ገንዘብ አጠቃቀምን ስለመወሰን**</u>

ለማህበረሰቦች ጥቅም የሚነደፉት የልማት ፕሮጀክቶች የሚወሰኑት ተጠቃሚው ማህበረሰብ የሚገኘው፡-

1. በአንድ ወረዳ ውስጥ ብቻ ከሆነ፣ በወረዳው ምክር ቤት፣
2. በአንድ ክልል በተለያዩ ወረዳዎች ወይም ዞኖች ውስጥ ከሆነ፣ ከእነዚህ ወረዳዎች ወይም ዞኖች የተወከሉ የክልል ምክር ቤት አባላትን በማካተት በሚቋቋም የክልል ምክር ቤት ጊዜያዊ ኮሜቴ፤ ወይም
3. በተለያዩ ክልሎች ውስጥ ከሆነ፣ ማህበረሰቡ ከሚገኝባቸዉ አካባቢዎች የተወከሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላትን በማካተት በሚቋቋም የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጊዜያዊ ኮሚቴ፣

አማካይነት ይሆናል፡፡

31.<u>የፕሮጀክት ሀሳቦችን ስለማቅረብ</u>

የእያንዳንዱ የአርክቦት ውል ዘመን ሲያበቃ ወይም እንደ አስፈላጊነቱ ከዚያም በፊት በማናቸውም ጊዜ ኢንስቲትዩቱ ፡-

1. ተጠቃሚው ማህበረሰብ የሚገኘው በተለያዩ ክልሎች ውስጥ ከሆነ፣ ለማህበረሰቡ ጥቅም የሚዉሉ የልማት ፕሮጅክት ሀሳቦችን በማዘጋጀት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለውሳኔ ያቀርባል፤
2. ተጠቃሚዉ ማህበረሰብ የሚገኘዉ በአንድ ክልል ዉስጥ ከሆነ፣ ለማህበረሰቡ ጥቅም የሚዉሉ የልማት ፕሮጀክት ሀሳቦች በማዘጋጀት የገንዘቡን አጠቃቀም ለሚወስነው የወረዳ ምክር ቤት ወይም የክልል ምክር ቤት እንዲያቀርብ የአርክቦት ገንዘቡን መጠን አግባብነት ላለው የክልል አካል ያሳውቃል፡፡

32.<u>የውሳኔ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት</u>

የወረዳ ምክር ቤቶች፣ የክልል ምክር ቤት ጊዜያዊ ኮሚቴዎች እና የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጊዜያዊ ኮሚቴዎች የአርክቦት ገንዘብ ጥቅም ላይየሚዉልበትን የልማት ፕሮጀክት የሚወስኑት የምክር ቤቶቻቸውን የስብሰባና የውሳኔ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት በመከተል ይሆናል፡፡

33.<u>ወጪን ስለመሸፈን</u>

ለማህበረሰብ ጥቅም የሚነደፉ የልማት ፕሮጀክቶችን ለማስወሰን ወጪ የሚጠይቅ ከሆነ ወጪው ከማህበረስቡ የአርክቦት ገንዘብ ድርሻ ላይ የሚሸፈን ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

34.<u>የአርክቦት መዝገብ</u>

1. ኢንስቲትዩቱ ለሕዝብ ክፍት የሆነ የአርክቦት መዝገብ ይይዛል፡፡

2. የአርክቦት መዝገቡ የሚከተሉትን ሰነዶች ያካትታል፡-
   ሀ) የአርክቦት ማመልከቻዎችን፤
   ለ) የአርክቦት ማመልከቻዎች ውድቅ የተደረገባቸውን ውሳኔዎች፤
   ሐ) የአርክቦት ማመልከቻዎች ለሕዝብ የተገለጸባቸዉን ማስታወቂያዎች፤
   መ) በአርክቦት ማመልከቻዎች ላይ የቀረቡ መቃወሚያዎችንና አስተያየቶችን፤
   ሠ) የአርክቦትና ጥቅም ተጋሪነት ውሎችን፤
   ረ) የተፈረሙ የጀነቲክ ቁስ ማስተላለፊያ መደበኛ ስምምነቶችን፤
   ሰ) የአርክቦት ፈቃዶችን፤
   ሸ) የአርክቦት ውል ክትትልና ቁጥጥር ሪፖርቶችን፤
   ቀ) የአርክቦት ውል ማሻሻያዎችን፣ ዕገዳዎችን ወይም መቋረጦችን፤
   በ) የአርክቦት ውሎችን እና የጀነቲክ ቁስ ማስተላለፊያ መደበኛስምምነቶችን በሚመለከት የተሰጡ የፍርድ ቤት ዉሳኔዎች፡፡

35.<u>የኢንሲቲትዩቱ ሥልጣንና ሃላፊነት</u>

ኢንሲቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ሀላፊነት ይኖሩታል፡፡

1. ይህንን ደንብ ለማስፈፀም የሚያስፈልግ መመሪያ የማውጣት፤
2. አግባብነት ያላቸውን አካላት በማስተባበር ለክልሎች የቴክኒክ ድጋፍ የመስጠት፣
3. በባለብዙ ወገን የአርክቦት ሥርዓቱ የሚሸፈን የጀነቲክ ሀብት በእጃቸው የሚገኝ በኢትዮጵያ ውስጥ የማይገኙ ሰዎች የጀነቲክ ሀብቱን በባለብዙ ወገን ሥርዓቱ ውስጥ እንዲያካትቱ የማበረታታት።

36.<u>የክልሎች ሥልጣንና ሃላፊነት</u>

ክልሎች የሚከተሉት ሥልጣንና ሀላፊነቶች ይኖራቸዋል፡-

1. ይህንን ደንብ በክልላቸው ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ማውጣት፤ እና
2. ይህንን ደንብ በክልላቸው የሚያስፈፅም አካል የመሰየምና የማጠናከር፡፡

37.<u>ተፈጻሚነት የሌላቸዉ ሕጎች</u>

ማናቸውም ደንቦች፣ መመሪያዎች ወይም አሠራሮች ይህንን ደንብ እስከተቃረኑ ድረስ በዚህ ደንብ ውስጥ በተደነገጉ ጉዳዮች ላይ ተፈጻማሪነት አይኖራቸውም፡፡

38.<u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥቅምት 30 ቀን 2002 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስቴር**

# አባሪ 1

## ለንግድ ዓላማ የሆነ አርክቦት ማመልከቻ ፎርም

1. ጠቅላላ መረጃ
   1.1. የተፈጥሮ ሰዉ የሆነ የአርክቦት አመልካች የሚያቀርበው መረጃ፡-
      ሀ) የአመልካቹ ሥም፤
      ለ) አድራሻው፤
      ሐ) ያለው ሙያ (ካሪኩለም ቪቴ ይያያዛል፡፡
   1.2. በሕግ የሰውነት መብት ያለው የአርክቦት አመልካች የሚያቀርበው መረጃ፡-
      ሀ) የድርጅቱ ስም፤
      ለ) የተመዘገበ አድራሻው፤
      ሐ) የተቋቋመበት ሰነድ (የሰነዱ ኮፒ ይያዛል፤
      መ) በታቀደው ፕሮጀክት ውስጥ የሚሳተፉት ሰዎች የስም ዝርዝርና ሙያ (ካሪኩለም ቪቴ ይያያዛል፤
      ሠ) የድርጅቱ ዝርዝር ሁኔታ፡-
         i) እናት ወይም ቅርንጫፍ ኩባንያዎች፤
         ii) ከአርክቦት ፕሮጀክቱ ጋር ግንኙነት ያላቸው ግለሰቦች ዝርዝር፤
         iii) የአርክቦት ማመልከቻውን በሚመለከት ማናገር የሚቻለው ሰው ስም፣ አድራሻ እና በድርጅቱ ውስጥ ያለው ሀላፊነት፡፡
2. ዝርዝር የአርክቦት መረጃ
   2.1. ገንዘብ ነክ መረጃ
      ሀ) የአርክቦት ፕሮጀክቱ በጀት፤
      ለ) የአርክቦት ፕሮጀክቱን በገንዘብ የደገፉ ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች ካሉ ዝርዝራቸው፡፡
   2.2. የቴክኒክ መረጃ
      ሀ) ለማርከብ የተፈለገው የጀነቲክ ሀብት ዓይነት ዝርዝር፡-
         i) ስለጀነቲክ ሀብቱ ሳይንሳዊ መረጃ፤
         ii) ጀነቲክ ሀብቱ ወይም የርሱ ውጤት የሚሰጠው ወይም ወደፊት ሊሰጥ የሚችለው ጠቀሜታ፤

iii) የጀነቲክ ሀብቱ ሊሰበሰብ የታሰበበት አካባቢ (የሚታወቅ ከሆነ፤

iv) የጀነቲክ ሀብቱ ሊገኝ የሚችልባቸው ሌሎች አካባቢዎች ዝርዝር (የሚታወቅ ከሆነ፤

v) ለማርከብ የተፈለገው ጀነቲክ ሀብት አካል መግለጫ (ሕብረ ሕዋስ፣ ዘር፣ ቅጠል…ወዘተ

vi) የሚሰበሰበው ጀነቲክ ሀብት መጠን፤

vii) ከጀነቲክ ሀብቱ ጋር ተያይዞ የሚገኝ የማሕበረሰብ ዕዉቀት፤

viii) አርክቦት የሚፈፀምበት የጀነቲክ ሀብት የሚገኘዉ በኢዘቦታ ከሆነ የጀነቲክ ሀብቱን ይዞ የሚገኘዉ ማንነት፡፡

ለ) የአሰባሰብ ተልዕኮዉ ዕቅድ ዝርዝር፣

i) ለማርከብ የፈለገዉን የጀነቲክ ሀብት የሚያቀርበው ሰው ማንነት፤

ii) የጀነቲክ ሀብቱ የሚገኘው በመሰብሰብ ከሆነ የሚሰበሰብበት ስልት፤

iii) በጀነቲክ ሀብት አሰባሰብ ላይ ኢትዮጵያዉያን ባለሙያዎችና ተቋሞች የሚሳተፉ ከሆነ እነማን እንደሆኑ፤

iv) የጀነቲክ ሀብት አሰባሰቡ የሚጀመርበትና የሚጠናቀቅበት ጊዜ ሰሌዳ፤

v) አመላካቹ የጀነቲክ ሀብቱን ለመለየትና ለመሰብሰብ ድጋፍ የሚፈልግ ከሆነ የሚፈልገዉ የድጋፍ ዓይነት፣

ሐ) ጀነቲክ ሀብቱ የሚዉልበት አገልግሎት ዝርዝር፡-

i) ጀነቲክ ሀብቱ ሊዉል የታሰበበት ጠቀሜታ፤

ii) የምርምሩ ዓይነትና ጥልቀት እንዲሁም ጥቅም ላይ የሚዉለዉ የባሙያና የመሣሪያ ዓይነት፤

iii) ከምርምሩ የሚጠበቀዉ ዉጤትና ምርምሩ የሚፈጀዉ ጊዜ ግምት፤

iv) ምርምሩና የማልማት ሥራዉ የተለያዩ ክፍሎች የሚካሄድባቸዉ ቦታዎች፤

v) ኢትዮጵያዉያን ባለሙያዎች በምርምሩ ዉስጥ የሚሳተፉ ከሆነ የሚሳተፉበት ሁኔታና የተሳትፏቸዉ ጥልቀት፤

vi) በምርምሩ ውስጥ ሊሳተፉ እና ሂደቱን ሊቆጣጠሩ የሚችሉ ኢትዮጵያዊያን ተቋማት እነማን እንደሆኑ (ሊታወቅ የሚችልከሆነ

vii) የጀነቲክ ሀብቱ መጀመሪያ እና በቀጣይነት ሊወሰድ የሚችልባቸዉ ቦታዎች፤

viii) የአርክቦት አመልካቹ የውጭ ሀገር ዜጋ ከሆነ፣ ከሀገሩ መንግሥት ሥልጣን ያለው አካል አመልካቹ የአርክቦት ፈቃድ ቢሰጠው የሚኖርበትን የአርክቦት ግዴታዎች በዚያ ሀገር የሚያስከብርና የሚያስፈጽም መሆኑን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ ማቅረብ የሚችል መሆኑን ማረጋገጥ፡

መ) የጥቅም ተጋሪነት መረጃ

i) የታቀደዉ የጥቅም መጋራት ስልትና የአተገባበር ሁኔታ ዝርዝር፤

ii) ለሀገሪቷ ወይም ለሚመለከተው የአካባቢ ማህበረሰብ ይገኛል ተብሎ የታሰበው ወይም ሊገኝ የሚችለው ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ቴክኖሎጂያዊ፣ሳይንሳዊ አካባቢያዊ ወይም ሌሎች ማናቸውም ጥቅሞች ዝርዝር፤

iii) አርክቦት ማመልከቻው ላይ በበቂ ግንዛቤ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ ለመስጠት ሊረዳ ይችላል በማለት የአርክቦት አመልካቹ የሚገምተው ሌላ ማናቸውም መረጃ፡፡

3. <u>**የቃለ መሓላ ማረጋገጫ**</u>

እኔ ከዚህ በታች የፈረምኩት የአርክቦት አመልካች በዚህ ማመልከቻ ውስጥ የጠቀሰው መረጃ ትክክለኛና እውነት መሆኑን በመሓላ ቃል አረጋግጣለሁ፡፡

4. <u>**ፊርማ**</u>

የፈራሚው ስም.............................................................

ኃላፊነት (በህግ የሰዉነት መብት የተሰጠዉን አካል በመወከል ሲሆን........................................................................

ፊርማ.........................................

ቀን.........................................................

## አባሪ 2

## ለንግድ ላልሆነ ዓላማ አርክቦት ማመልከቻ ፎርም

1. **ጠቅላላ መረጃ**
   1.1. የአመልካቹ ተቋም ስም፤
   1.2. የአመልካቹ ተቋም አድራሻ፤
   1.3. የአመልካቹ ተቋም የተቋቋመበት ሰነድ(ተቋሙ የተቋቋመበት ህግ ወይም የምዝገባ ሰርተፍኬት እንዲሁም ተቋሙ በኢትዮጵያ የሚገኝ በይነ-መንግሥታዊ ተቋም ከሆነ በኢትዮጵያ ዉስጥ እንዲሠራ ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር ያደረገዉ ስምምነት ኮፒ ይያዛል፡፡
2. **ዝርዝር የቴክኒክ መረጃ**
   2.1. ስለጀነቲክ ሀብቱ ሳይንሳዊ መረጃ፤
   2.2. ጀነቲክ ሀብቱ የሚገኝበት ቦታ፤
   2.3. የጀነቲክ ሀብቱ ሊውል የታስበበት ጠቀሜታ ዝርዝር፣
   2.4. የታሰበው ምርምር ዓይነትና ጥልቀት እንዲሁም ጥቅም ላይ የሚውለው የባለሙያና የመሣሪያ ዓይነት፤
   2.5. ምርምሩ የሚፈጀዉ ጊዜና ከምርምሩ የሚጠበቀው ውጤት
   2.6. የምርምሩ የተለያዩ ክፍሎች የሚካሄዱባቸው ቦታዎች
   2.7. የጀነቲክ ሀብቱ መጀመሪያ እና በቀጣይነት ሊወሰድ የሚችልባቸው ቦታዎች፤
   2.8. ምርምሩ በጠቅላላ ወይም የምርምሩ ክፍል የሚካሄድበት ቦታ ከኢትዮጵያ ውጪ በሆነ ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ መካሄድ የማይችልበት ምክንያት ዝርዝር።
3. **የመሀላ ቃል**

   እኔ ከዚህ በታች የፈረምኩት የአርክቦት አመልካች በዚህ ማመልከቻ ውስጥየጠቀሰው መረጃ ትክክለኛና እውነት መሆኑን በመሐላ ቃል አረጋግጣለሁ፡፡
4. **የአመልካቹፊሪማ**

   የፈራሚዉ ስም....................................
   ኃለፊነት......................................................
   ፊርማ....................................
   ቀን..........................................

# አባሪ -3

## የባለብዙ ወገን አርክቦት ማመልከቻ ፎርም

1. **ጠቅላላ መረጃ**
   1.1. የተፈጥሮ ሰው ከሆነ የአርክቦት አመልካች የሚያቀርበው መረጃ፣
      ሀ) የአመልካቹ ስም
      ለ) የአመልካቹ አድራሻ ፡፡
   1.2. በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው የአርክቦት አመልካች የሚያቀርበው መረጃ፤
      ሀ) የድርጅቱ ስም፤
      ለ) የድርጅቱ አድራሻ፤
      ሐ) ድርጅቱ የተቋቋመበት ወይም የተመዘገበበት ሰነድ (የሰነዱ ኮፒ ይያያዛል፡፡
2. **ለማርከብ የተፈለገው የጀነቲክ ሀብት ዝርዝር መግለጫ**
   2.1. ስለጀነቲክ ሀብቱ ሳይንሳዊ መረጃ፤
   2.2. ሊውል የታሰበበት አገልግሎት፤
   2.3. ጀነቲክ ሀብቱን ይዞ የሚገኘዉ ወይም የሚያቀርበዉ ተቋም፡፡
3. **የመሐላ ቃል**

   እኔ ከዚህ በታች የፈረምኩት የአርክቦት አመልካች በዚህ ማመልከቻ ውስጥ የተጠቀሰው መረጃ ትክክለኛና እውነት መሆኑን እና በጀነቲክ ቁስ ማስተላለፊያ ስምምነቱ ውስጥ የተቀመጡ ቅድመ ሁኔታዎችንና ግዴታዎችን የማከብር መሆኔን በመሓላ ቃል አረጋግጣለሁ፡፡
4. **ፊርማ**

   የፈራሚውስም........................................

   ኃላፊነት (በህግ የሰውነት መብት የተሰጠውን አካል በመወከል ሲሆን........................................................

   ፊርማ........................................................

   ቀን..............................................................

## አዋጅ ቁጥር 513/1999

## የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ አዋጅ

ከደረቅ ቆሻሻ የሚከተል አሉታዊ ተፅዕኖን ለመከላከልና ጠቃሚነቱን ለማጎልበት የማኅበረሰቡ ተሳትፎ አስፈላጊ በመሆኑ፣

በዝቅተኛው የከተማ የአስተዳደር እርከን ታቅዶ የሚተገበር የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ የድርጊት መርሐ ግብር ማኅበረሰቡን ለማሳተፍ የሚያስችል በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55)1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ ‹‹የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ አዋጅ ቁጥር 513)1999›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

   1. ‹‹የአካባቢ ጥበቃ መሥሪያ ቤት›› ማለት ባለሥልጣኑ ወይም የክልል የአካባቢ ጥበቃ አካል ነው፤
   2. ‹‹ባለሥልጣን›› ማለት በአዋጅ ቁጥር 295)1995 የተቋቋመው የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ነው፤[52]
   3. ‹‹ጉድፍ›› ማለት የጠርሙስ ስባሪን፣ የብረት፣ የሲጋራ፣ ወይም የወረቀት ቁርጥራጭን፣ የጨርቅ እራፊን፣ የምግብ ትራፊን እና የዕፅዋት ቅሪትን ጨምሮ የተጣለበትን ቦታ ውበት ወይም ንፅሕና የሚያሳጣ የሚጠቅምም ይሁን የማይጠቅም ማንኛውም ነገር ነው፤
   4. ‹‹ሰው›› ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

[52] በ25/08 (2011) አ. 1097 አንቀጽ 36/17 መሰረት የአካባቢ፣ የደን እና አየር ለውጥ ኮሚሽን ስለሆነ በአዋጁ ውሰጥ ባለስልጣኑ የሚለው ኮሚሽኑ በሚል ተተክቶ ይነበብ፡፡

5. ‹‹ክልል›› ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግሥት በአንቀ 47)1) የተመለከቱት ክልሎች ማለት ሲሆን ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤
6. ‹‹ደረቅ ቆሻሻ›› ማለት የማይፈለግ ተብሎ የተጣለ ማንኛውም ፈሳሽ ወይም ፈሳሽ ያልሆነ ነገር ነው፤
7. ‹‹የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ›› ማለት ደረቅ ቆሻሻን መሰብሰብ፣ማጓጓዝ፣ማከማቸት፣ መልሶ መጠቀም፣ማስወገድ ወይም አገልግሎት ሰጥቶ ያበቃለትን የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ለሌላ ተግባር እንዲውል ማድረግ ነው፡፡

3. **<u>የአዋጁ ዓላማ</u>**

የአዋጁ ዓላማ ከአያያዙ ሊከተል የሚችል አሉታዊ ተፅዕኖን እየተከላከሉ ኢኮኖሚያዊና ማህበረሰባዊ ፋይዳ ከደረቅ ቆሻሻ እንዲገኝ የሚያስችል አቅምን በሁሉም ደረጃ ማጐልበት ነው፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ</u>

4. **<u>የከተማ አስተዳደሮች አጠቃላይ ግዴታ</u>**

1. የከተማ አስተዳደሮች በደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት መስክ ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ የሚያግዝ ምቹ ሁኔታ መፍጠር አለባቸው፡፡
2. ደረቅ ቆሻሻን በመሰብሰብ፣ በማጓጓዝ፣ በጥቅም ላይ በማዋል ወይም በማስወገድ ተግባር ላይ የሚሰማራ ማንኛውም ሰው ከሚመለከተው የከተማው አስተዳደር አካል በቅድሚያ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡

5. **<u>የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ዕቅድ ዝግጅት</u>**

1. የከተማ አስተዳደሮች ዝቅተኛዉን የአስተዳደር እርከናቸውንና የአካባቢያቸውን ማኀበረሰብ መነሻ ባደረገ አሳታፊ የአሰራር ዘዴ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ዕቅድ ተዘጋጅቶ እንዲተገበር ማድረግ አለባቸው፡፡
2. እያንዳንዱ ክልል ወይም የከተማ አስተዳደር ራሱ በሚወስነው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ዕቅድና የዕቅድ አፈፃፀም ዘገባ ማዘጋጀት አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተዉ ዕቅድና ዘገባ በዝቅተኛዉ የአስተዳደር እርከን በሚዘጋጅ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ዕቅድና በእቅድ አፈጻጸም ዘገባ ላይ ተመስርቶ መጠናቀር አለበት፡፡

4. የከተማ አስተዳደሮች፣
   ሀ) የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ዕቅድ የማዘጋጀትና የመተግበር፣
   ለ) ምልክት የተደረገባቸው የጉድፍ ማጠራቀሚያዎች በየጎዳናዉ ዳርና በሌሎች የህዝብ ማዘውተሪያ ሥፍራዎች መቀመጣቸውን የማረጋገጥ፣
   ሐ) የጉድፍ ማጠራቀሚያ ሳይዝረከረክ ቆሻሻው በየወቅቱ መነሳቱን የማረጋገጥ፣
   መ) አካባቢ ግንዛቤ ማስፋፊያ ተግባራትን የማቀድና የማከናወን፣
   ሠ) ከደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ጉድለት ሊደርስ የሚችል ብክለትን የመከላከያ እርምጃ መወሰዱን ማረጋገጥ፣

   ኃላፊነቶችን ለዝቅተኛው የአስተዳደር እርከናቸው ሊያስተሳልፉ ይችላሉ፡፡

6. <u>በክልሎች መካከል የሚደረግ የደረቅ ቆሻሻ ዝውውር</u>
   1. እያንዳንዱ ክልል ወደ ሌላ ክልል በመላክ የሚያስወግደውን ደረቅ ቆሻሻ በተቻለ መጠን ማሳነስ አለበት፡፡
   2. ክልሎች በክልላቸው አልፎ የሚጓጓዝ ደረቅ ቆሻሻ በሚመለከተው የአካባቢ ጥበቃ መሥሪያ ቤት በወጣ መመሪያና ደረጃ መሠረት ታሽጎ እንዲጓጓዝ ሊያስገድዱ ይችላሉ፡፡
   3. ደረቅ ቆሻሻን ከአንድ ክልል ወይም የከተማ አስተዳደር ወደ ሌላ ክልል ወይም የከተማ አስተዳደር ልኮ ማስወገድ የሚቻለው ተረካቢው ክልል ወይም የከተማ አስተዳደር በቆሻሻው መልሶ ለመጠቀም ወይም አካባቢያዊ ተቀባይነት ባለው መንገድ ለማስወገድ አቅም እንዳለው ለላኪው በፅሁፍ ሲያሳውቅ ብቻ ነው፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>

7. <u>ጠርሙስና ጣሳ</u>
   1. የጠርሙስ ወይም የቆርቆሮ ጣሳ አምራች ወይም አስመጪ፣ ጠርሙሱ ወይም የቆርቆሮ ጣሳው የአገልግሎት ዘመኑ እንዳበቃ መልሶ የሚወስድበትን ወይም እንዲወስድ የሚያስደርግበትንና መልሶ በጥቅም ላይ የሚውልበትን ዘዴ መዘርጋትና መተግበር አለበት፡፡
   2. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አተገባበር፣ የከተማ አስተዳደሮች ተመላሽ ጠርሙስ ወይም የቆርቆሮ ጣሳ በጊዜያዊነት የሚከማችበት ቦታ መመደቡንና ክምችቱም በየወቅቱ መነሳቱን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

8. **ስለፕላስቲክ ከረጢቶች**

1. በባለሥልጣኑ በሚወጣ መመሪያ ከሚወሰነው ቀን ጀምሮ በቀላሉ በስብሶ ወደ አፈር የሚደባለቅ መሆን አለመሆኑን የሚያሳይ ምልክት ያልተደረገበትን የፕላስቲክ ከረጢት ለገበያ ማቅረብ የተከለከለ ነው፡፡
2. ውፍረቱ 0.03 ሚሊ ሜትር እና ከ0.03 ሚሊ ሜትር በታችም ሆኖ በስብሶ ከአፈር ጋር የማይዋሃድ የፕላስቲክ ከረጢት የማምረት ወይም ወደ ሃገር ውስጥ የማስገባት ፈቃድ መስጠት የተከለከለ ነው፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሥልጣኑ ውፍረቱ 0.03 ሜሊ ሜትር እና ከ0.03 ሚሊ ሜትር የሚያንስ ሆኖ በስብሶ ከአፈር ጋር የማይዋሃድ የፕላስቲክ ከረጢትን ተለይቶ ለተገለፀ አገልግሎት ብቻ ወደ አገር ውስጥ እንዲገባ ወይም በአገር ውስጥ እንዲመረት የሚወስን መመሪያ ያወጣል፡፡

9. **የአገለገለ የተሽከርካሪ ጎማ**

1. የአገለገለ የተሽከርካሪ ጎማን ለማስወገድ ወደ ኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ማስገባት የተከለከለ ነው፡፡
2. የአገለገለ የተሽከርካሪ ጎማ አካባቢያዊ ተቀባይነት ላለው አገልግሎት ወደ አገር ውስጥ ሊገባ የሚችልበት ሁኔታ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

10. **ከምግብ ጋር የተያያዙ ደረቅ ቆሻሻዎች**

1. የምግብ ኢንዳስትሪዎችና የምግብ ቤቶች የሚያመነጩትን ከምግብ ጋር የተያያዘ ደረቅ ቆሻሻ አካባቢያዊ ተቀባይነት ባለዉ ሁኔታ መሰብሰብና ማስወገድ አለባቸዉ፡፡
2. ምግብ ቤቶች የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ሥርዓታቸውን የሚመለከተው የአካባቢ ጥበቃ መሥሪያ ቤት በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ማዘጋጀትና መተግበር አለባቸው፡
3. ነባር ምግብ ቤቶች የሚያመነጩትን ደረቅ ቆሻሻ የሚመለከት የአካባቢ ኦዲት ማካሄድና የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ዕቅድ ማዘጋጀትና መተግበር አለባቸው።

11. **የመኖሪያ ቤት ደረቅ ቆሻሻ አያያዝ**

1. የእያንዳንዱ መኖሪያ ቤት ኃላፊ ለዳግም አገልግሎት የሚውለውን ከናካቴው ከሚጣል ደረቅ ቆሻሻ ለይቶ ለቆሻሻ ማስወገጃ ወደ ተወሰነው ቦታ እንዲደርስ ማድረግ አለበት፡፡

2. የከተማ አስተዳደሮች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ )4) መሠረት በተወሰኑ የመኖሪያ አካባቢዎች የመኖሪያ ቤት ደረቅ ቆሻሻ ለመሰብሰብ የሚያስችሉ በቂ የአገልግሎት መስጪያ መሣሪያዎች መሟላታቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡
3. ለዚሁ ተግባር ተብሎ የተዘጋጀ ማጠራቀሚያ በአቅራቢያው እያለ ጉድፍን በመንገድ፣ በጎርፍ መሄጃ ቦይ፣ በፓርክ፣ በአውቶቡስ ወይም በባቡር ጣቢያ፤ በስፖርት ሜዳ፣ በከተማ ውስጥ በሚገኝ የውሃ አካል ወይም በሌላ የሕዝብ መጠቀሚያ ቦታ መጣል የተከለከለ ነው፡፡
4. እያንዳንዱ የከተማ አስተዳደር የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች በግዴታ ተፈጻሚ የሚሆኑባቸውን የመኖሪያ አካባቢዎች መከለል አለበት፡፡

12.<u>የግንባታና የፍርስራሽ ደረቅ ቆሻሻ</u>

1. የከተማ አስተዳደሮች በራሳቸው ወይም ከግንባታ ድርጅቶች ጋር በመዋዋል የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎችን ወይም የካባ ጉድጓዶችን ከሕንፃ ፍርስራሽ በሚገኝ ጠጣር ወይም አሸዋ ወይም ተቆፍሮ በወጣ አፈር እንዲሞሉ ማድረግ ይችላሉ፡፡
2. የግንባታ ፈቃድ የሚሰጠው የግንባታ ፍርስራሽ ወይም ተቆፍሮ የወጣ አፈር በተገቢው መንገድ እንደሚያስወግድ የሥራ ተቋራጩ የሥራ አፈፃፀም ወይም ሌላ ተመሳሳይ ሕጋዊ ዋስትና ሲያቀርብ ብቻ ነዉ፡፡
3. ማንኛውም የከተማ መኖርያ ቤት ግንባታ ከመጀመሩ በፊት የከተማ አስተዳደሮች አካባቢያዊ ተቀባይነት ላለው የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ በቂ ዝግጅት መኖሩን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

13.<u>የደረቅ ቆሻሻ ማጓጓዣ ተሽከርካሪዎችና መሣሪያዎች</u>

1. ባለሞተር ተሽከርካሪን ለመመዝገብ ዓመታዊ ምዝገባና የቴክኒክ ምርመራ ለማካሄድ እንዲሁም የመንጃ ፈቃድ ለመስጠት የሕግ ሥልጣን ያለው አካል ተግባርና ሃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የደረቅ ቆሻሻ ማጓጓዣ ተሽከርካሪ ወይም መሣሪያ በሥራ ላይ ከመዋሉ አስቀድሞ አገልግሎት የመስጠት ብቃቱ የሚመለከተው የአካባቢ ጥበቃ መሥሪያ ቤት ካወጣው መስፈርት ጋር የሚስማማ ስለመሆኑ በከተማ አስተዳደሩ መረጋገጥ አለበት፡፡

2. አግባብ ባለው ሕግ የተወሰነው የተሽከርካሪ ክብደትና መጠን እንደተጠበቀ ሆኖ፣ እያንዳንዱ የከተማ አስተዳደር የደርቅ ቆሻሻ ማጓጓዣ ተሽከርካሪ ሾፌሮችንና የመሣሪያ አንቀሳቃሾችን ክህሎት ለመወሰን እንዲሁም ከልክ ያለፈ የደረቅ ቆሻሻ ጭነትን ለመከላከል የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን ማውጣት አለበት፡

14.<u>የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎች ግንባታ</u>

1. እያንዳንዱ የከተማ አስተዳደር አግባብነት ያለውን የፌዴራል የአካባቢ ደረጃ በመከተል የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ እንዲገነባና አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግ አለበት፡፡
2. የከተማ አስተዳደሮች ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት ግንባታው በተጀመረ ወይም በተከናወነ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ላይ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የአካባቢ ኦዲት መካሄዱን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡
3. የከተማ አስተዳደሮች አዲስ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ሲገነባ ወይም ነባር የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ሲሻሻል አግባብነት ባለዉ ሕግ መሠረት የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ የተካሄደበት መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

15.<u>በነባር የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎች ላይየአካባቢ ኦዲት ስለሚካሄድ</u>

1. በነባር የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎች ላይ የአካባቢ ኦዲት መካሄዱን የማረጋገጥ ኃላፊነት የየከተማው አስተዳደር ይሆናል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ )1) መሠረት በተካሄደው የአካባቢ ኦዲት መሠረት የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃው ቦታ አገልግሎት መስጠት መቀጠል በሕዝብ ጤና ወይም በአካባቢው ላይ ጉዳት ሊያስከትል እንደሚችል ከተጠረጠረ ባለቤቱ አስፈላጊውን ማሻሻያ ማድረግ አለበት፡፡
3. ሥራ ያቆመ ወይም የተተወ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ለሌላ አገልግሎት እንዲውል የሚወሰንበትን የአካባቢ መስፈርት ባለሥልጣኑ በመመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡

## <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

16.<u>የፍትሐ ብሔር ኃላፊነት</u>

1. የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ በሥራ ላይ እያለ ወይም ከተዘጋ በኋላ በአካባቢ፣ በሰው ጤና ወይም በንብረት ላይ ጉዳት ካደረሰ ጥፋተኝነት ማረጋገጥ ሳያስፈልግ ባለቤቱ ኃላፊ ይሆናል፡፡

2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆነ፣ ከኃላፊነት ነፃ መሆን የሚቻለው ጉዳቱ በተጎጂው በራሱ ወይም ደግሞ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጂያው ባለቤት ኃላፊነት በሌለበት በሦስተኛ ወገን መድረሱ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ማንኛውም የካሳ ጥያቄ መቅረብ የሚችለው ጉዳት መድረሱ ከታወቀበት ቀን ጀምሮ በሁለት አመት ውስጥ ይሆናል፡፡

17.**<u>ቅጣት</u>**

1. በሚመለከተው የአካባቢ ጥበቃ መሥሪያ ቤት በወጣ መመሪያ መሠረት ልዩ ፈቃድ ከተገኘ በኋላ እንዲተገበር የተወሰነበትን የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ፕሮጀክት ያለፈቃድ የተገበረ ሰው ጥፋት ፈፅሚልና አግባብ ያለው የወንጀል ሕግ ተፈፃሚ ይሆንበታል፡፡
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሠረት ፈቃድ መሰጠቱ፣ የፕሮጀክቱን ባለቤት አግባብ ባለው የአካባቢ ደረጃ የተዘረዘረ ተፈላጊ ሁኔታን በመተላለፍ ከሚከተል ሃላፊነት ነፃ አያደርገውም፡፡
3. የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች የሚተላለፍ ማንኛውም አምራች፣ አስመጪ፣ወይም ሻጭ ጥፋት ፈፅሞአልና አግባብ ያላቸው የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆኑበታል፡፡
4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ እያንዳንዱ የከተማ አስተዳደር ስለደረቅ ቆሻሻ አያያዝ በዚህ አዋጅ የተደነገጉ ግዴታዎችን ባለመወጣት ጥፋት በሚፈፅም ሰው ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑ የገንዘብ ቅጣቶችን መወሰንና ማስፈጸም ይችላል፡፡

18.**<u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>**

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህንን አዋጅ በሚገባ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ባለሥልጣኑ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የሚወጡ ደንቦችን በሚገባ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

19.<u>አዋጁ የሚፀናበት</u>

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ የካቲት 5 ቀን 1999 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## አዋጅ ቁጥር 571)2000[53]

## የጨረራ መከላከያ አዋጅ

በሀገሪቱ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት ውስጥ ጨረራንና ሬዲዮ አይሶቶፖችን ጥቅም ላይ የማዋል ፍላጎት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመምጣቱና ይህም አጠቃቀም አግባብ ያለውና ውጤታማ የመከላከል ዘዴ በሥራ ላይ እስካልዋለ ድረስ በጤና በንብረትና በአካባቢ ላይ ተጓዳኝ ጠንቅ ሊያስከትል የሚችል በመሆኑ፣

የጨረራ አመንጪዎችና ተያያዥነት ላላቸው ተግባራት ለሕብረተሰቡ ጥቅም አገልግሎት ላይ ሲውሉ በግለሰቦች፣ በሕብረተሰቡ፣ በንብረትና በአካባቢ በአሁኑና በወደፊቱ ትውልድ ጭምር ሊያደርሱ የሚችሉትን ተጓዳኝ የጨረራ ጠንቅ መከላከል እንዲቻል የሬጉላቶሪ ቁጥጥር የሚያደርግ ባለሥልጣን ማቋቋም በማስፈለጉ፤

የጨረራ ደህንነትና የጨረራ አመንጪ ቁሶች ጥበቃ የሚመለከታቸው ሰዎችን ሕጋዊ ኃላፊነት በመወሰንና ተቀባይነት ካለው የመጋለጥ መጠን በላይ የጨረራ መጋለጥ በሚያደርሱ ሰዎች ላይ መወሰድ የሚገባቸውን ተገቢ እርምጃዎች በመደንገግ የጨረራ መከላከሉን ሥራ ማጠናከር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 55/1 መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የኢትዮጵያ ጨረራ መከላከያ ባለሥልጣን

### 4. መቋቋም

1. የኢትዮጵያ ጨረራ መከላከያ ባለሥልጣን ) ከዚህ በኋላ ባለሥልጣን እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ እንደገና ተቋቁሟል፡፡

### 5. ዋና መሥሪያ ቤት

የባለሥልጣኑ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ውስጥ ሆኖ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶችን እንደ አስፈላጊነቱ በሌሎች የሀገሪቱ ክልሎች ማቋቋም ይችላል፡፡

---

[53] ይህ በ23/67 (2009) አ.1025አንቀጽ 27/1 የተሻረ ቢሆንም በአንቀፅ 28(1) "የኢትዮጵያ ጨረራ መከላከያ ባለሥልጣን በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ እስኪቋቋም ድረስ የጨረራ መከላከያ አዋጅ ቁጥር 571/2000 ከአንቀጽ 4 እስከ አንቀጽ 15 ድረስ ያሉ ድንጋጌዎች ከአንቀጽ 4(2) እና አንቀፅ 13 በስተቀር ፀንተው ይቆያሉ፡፡" ተብሎ በተደነገገው መሰረት ፀንተው የቆዩት አንቀፆች ተካተዋል፡፡

6. **<u>የባለሥልጣኑ ዓላማዎች</u>**

የባለሥልጣኑ ዓላማ፤

1. የኤክስሬይ መሳሪያዎችን ጨምሮ ከቁጥጥር ነጻ ያልሆኑ የጨረራ አመንጪዎችና ተዛማጅ ተግባራት በግለሰቦች፣ በሕብረተሰቡ፣ በንብረትና በአካባቢ ላይ የወደፊቱን ትውልድ ጨምሮ ሊያደርሱ የሚችሉትን የጨረራ ጠንቅ የመከላከል፣ እና
2. የጨረራ መከላከል እንቅስቃሴውን በሚያግዙ ጉዳዮች ላይ ጥናትና ምርምር የማድረግ ወይም የሚደረጉ ጥናትና ምርምሮችን የማበረታታት፣

ይሆናል፡፡

7. **<u>የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር</u>**

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 16/1/እና16/2/ የተዘረዘሩትን እንቅስቃሴዎች ለማከናወን የሚያስችል ፈቃድ የመስጠት፣ የማደስ፣ የማገድና የመሰረዝ እንዲሁም በተሰጠው ፈቃድ ላይ አስፈላጊ የሆኑ ግዴታዎችን የማስቀመጥ፣
2. የጨረራ መከላከልን የሚመለከቱ ፖሊሲዎችን እንዳስፈላጊነቱ የመንደፍ፣ ረቂቅ ሕጎችን የማዘጋጀትና ለመንግሥት አቅርቦ የማስጸደቅ፣
3. የጨረራ መከላከል ፖሊሲዎችንና ሕጎችን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ዝርዝር መመሪያዎችን የማውጣትና ተፈፃሚነታቸውን የመከታተል፣
4. የጨረራ ደህንነትንና የጨረራ አመንጪዎችን ጥበቃ በሚገባ ለማረጋገጥ የመንግሥትንና የግል እንቅስቃሴዎችን ለማስተባበር የሚረዳ ሥርዓትየመዘርጋት፣
5. የጨረራ መከላከል አገልግሎት የመስጠት፣
6. የጨረራ መከላከያ ሕጎችና መመሪያዎች ሥራ ላይ መዋላቸውን ለማረጋገጥ ቁጥጥር ማካሄድና አግባብ ያላቸው እርምጃዎችን የመውሰድ፣
7. የጨረራ መከላከል እንቅስቃሴን በሚያግዙ ጉዳዮች ላይ ጥናትና ምርምር የማድረግ ወይም የሚደረጉ ጥናትና ምርምሮችን የማበረታታትና በሚደረጉ ጥናትና ምርምሮች የሚገኙ ውጤቶችን መሠረት በማድረግ እርምጃዎች የመውሰድ ወይም እንዲወሰዱ የማማከር፣
8. ከአቶሚክ ኢነርጂና ጨረራ ጋር በተዛመዱ ጉዳዮች መንግሥትን የማማከር፣
9. የጨረራ መከላከልና ተዛማጅነት ያላቸውን ጉዳዮች የሚመለከቱ መረጃዎችን የማደራጀትና በሥልጠና ኮርሶች፣ በሴሚናሮች፣ በሚበተኑ ጽሁፎችና በመሳሰሉት የማሰራጨት፣

10. ጨረራ የሚያደርሰውን አደጋ ለመከላከል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የድንገተኛ አደጋ ዝግጁነትና ምላሽ ብሔራዊ ቡድን ማቋቋምና እቅድ የማውጣት፣ እንደአስፈላጊነቱ እርምጃ የመውሰድና የማማከር፣
11. ሀገሪቱ በመስኩ ተዋዋይ ወገን የሆነችባቸውን ዓለም ዐቀፍ ስምምነቶች የማስፈጸምና ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው የአገር ውስጥ፣ የውጭና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር የመተባበር፣
12. የዉስድ መጠኖችን፣ ከቁጥጥር ነጻ፣ የመልቀቂያ ወሰኖችንና ከግዴታ ውጭ እርከኖች እንዲሁም ቁጥጥር ሊደረግባቸው የሚገቡ ተዛማጅ የመለዋወጫ መሳሪያዎችን በሚያወጣቸው መመሪያዎች የመወሰን፣
13. ለጨረራ አመንጪዎችና ተዛማጅ ተግባራት ብሔራዊ የምዝገባ ስርዓት መዘርጋት፣
14. ከጨረራ መከላከል ጋር የተያያዙ አገልግሎቶችን መስጠት ለሚያቅዱ ሰዎች የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የመስጠት፣የመቆጣጠርና አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘዉም የምስክር ወረቀቱን የማገድና የመሰረዝ፣ የምስክር ወረቀቱ መታገዱን ወይም መሰረዙን ለሚመለከታቸዉ አካላት በወቅቱ የማሳወቅ፣
15. የንብረት ባለቤት የመሆን፣ ዉል የመዋዋልና በስሙ የመክሰስና የመከሰስ፣
16. ዓላማዎቹን ለማስፈጸም አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተግባራትን የማከናወን

8. <u>የባለሥልጣኑ አቋም</u>

ባለሥልጣኑ፣

1. የኢትዮጵያ የጨረራ መከላከያ ቦርድ )ከዚህ ቦኋላ ቦርድ እየተባለ የሚጠራ)፣
2. በመንግሥት የሚሾም ዋና ዳይሬክተር፣ እና
3. አስፈላጊው ሠራተኞች፣

ይኖሩታል።

9. <u>የቦርድ አደረጃጀት</u>

የቦርዱ አደሪጃጀት በመንግሥት የሚወሰን ሆኖ እንዳስፈላጊነቱ መንግሥት አንድ ከፍተኛ ሳይንቲስት በቦርድ አባልነት ሊመድብ ይችላል።

10. <u>የቦርዱ ሥልጣንና ተግባራት</u>

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

1. በባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር የሚቀርቡ መመሪያዎችን፣ እንዲሁም ለጨረራ መከላከል የሚቀመጡ ግዴታዎችንና የነዚህኑ ማሻሻያዎች የማጽደቅ፣

2. የባለሥልጣኑን ዘገባዎች መመርመርና እቅዱን፣ የሥራ ፕሮግራሙን፣ በጀቱንና የውስጥ ደንቡን ማጽደቅ፣
3. በባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ውሳኔዎች ላይ ከባለጉዳዮች የሚቀርቡ ይግባኞችን ተቀብሎ የመወስን፣
4. በሚቀርቡለት ይግባኞች ላይ ቴክኒካዊ ምክሮችን የሚሰጡ ባለሙያዎች መርጦ የመሰየምና ተገቢውን ሙያዊ ድጋፍ የማግኘት፣
5. መንግሥት በቦርድ አባልነት የሚመድበውን አንድ ከፍተኛ ሳይንቲስት መርጦ እንዲልክለት ከጠየቀ ማቅረብ፣
6. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7)2) መሠረት ለመንግሥት በሚቀርቡ ረቂቅ ሕጎች ላይ እንደአስፈላጊነቱ ሃሳብ የማቅረብ።

11.<u>የቦርዱ ስብሰባዎች</u>

1. ቦርዱ ቢያንስ በስድስት ወር አንድ ጊዜ ይስበስባል፣ ሆኖም በሰብሳቢው ጥሪ በማናቸውም ጊዜ ሊስበስብ ይችላል፡፡
2. ከቦርዱ አባላት ከግማሽ በላይ ሲገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡
3. የቦርዱ ውሳኔዎች በድምፅ ብልጫ ይተላለፋሉ፣ ሆኖም የድምፅ አሰጣጡ እኩል በኩል የተከፈለ ሲሆን ሰብሳቢው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል።
4. ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

12.<u>የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር</u>

1. ዋና ዳይሬክተሩ የባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሆኖ ቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የባለሥልጣኑን ሥራዎች ይመራል፣ያስተዳድራል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ )1) የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ዋና ዳይሬክተሩ፣
   ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 የተመለከቱትን የባለስሥልጣኑን ሥልጣንና ተግባሮች ሥራ ላይ ያውላል፣
   ለ) የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ ዓላማዎች ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት የባስሥልጣኑን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፣
   ሐ) የባስሥልጣኑን ሪፖርት፣ እቅድ፣ የሥራ ፕሮግራም፣ በጀት፣ ድርጅታዊ መዋቅርና የውስጥ ደንብ ለቦርዱ ያቀርባል፣

መ) ለባለሥልጣኑ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፣

ሠ) ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ባለስሥልጣኑን ይወክላል፣

ረ) ከባለስሥልጣኑ አቅም በላይ የሆኑ የጨረራ አደጋዎችና ድንገተኛ አጋጣሚዎች ሲከሰቱ ለሚመለከተው አካል ወዲያውኑ ያሳውቃል።

3. ዋናው ዳይሬክተር ለባለሥልጣኑ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለባለሥልጣኑ ኃላፊዎችና ሌሎች ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፣ ሆኖም እርሱን ተክቶ የሚሰራው ኃላፊ ከ 30 ቀናት ለሚበልጥ ጊዜ የሚሰራ ከሆነ ውክልናው አስቀድሞ ለኢትዮጵያ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር ቀርቦ መፈቀድ አለበት።

13.

14.<u>የባለሥልጣኑ በጀት</u>

ባለሥልጣኑ መንግሥት በሚመድበው በጀት ይተዳደራል።

15.<u>የሂሳብ መዛግብት</u>

1. ባለሥልጣኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፡፡
2. የባለሥልጣኑ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡

**አዲስ አበባ ሚያዚያ 14 ቀን 2000 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ**

**ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## አዋጅ ቁጥር 655/2001

## ስለደህንነት ሕይወት የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 44 እና አንቀጽ 92 የተደነገገው የአካባቢ ደህንነት መብት የሰውና የእንስሳት ጤናን፣ የአካባቢ ደህንነትን፣ ባጠቃላዩም የአገሪቷን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን ከልውጥ ሕያዋን ሊከተል ከሚችል ጠንቅ መጠበቅን አስፈላጊ ስለሚያደርገው፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55/1/መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ ‹‹የደህንነት ሕይወት አዋጅ ቁጥር 655/2001›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም ካላሰጠዉ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

   1. ‹‹ልውጥ ሕያው›› ማለት ሰው ሰራሽ የሆነ ወይም ከሌላ ሕያው የተወሰደ ይሁን ከቅሪት የተወሰደ ወይም እንደ አዲስ የተቀመመ ባይተዋር ዘረመል ወይም ሌላ ንጥረ ነገር ለተከተተበት የዘረመሎች ይዘቱ ወይም የባሕርዩ ክስተት የተለወጠበት ሕያው ነው፤
   2. ‹‹እንቅስቃሴ›› ማለት ልውጥ ሕያውን መሥራት ወይም ለትምህርት፣ ለምርምር፣ ለምርት፣ ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት፣ ወደ ዉጪ ለመላክ፣ በትራንዚት ለማስተላለፍ፣ ለተጨነ ልቀት፣ በዝግ ለማምረት፣ ለማጓጓዝ፣ ለገበያ ለማቅረብ፣ ለሰው ወይም ለእንስሳ በመድኃኒትነት ለመጠቀም፣ ለምግብነት፣ ለመኖነት ወይም ለፋብሪካ ጥሬ ዕቃነት ማዋል ነው፤
   3. ‹‹መሥራት›› ማለት በዘመናዊ ጥበበ ሕይወት ልውጥ ሕያው እንዲገኝ ማድረግ ነው፤
   4. ‹‹ዝግ አጠቃቀም›› ማለት በሰው ወይም በእንስሳት ጤና ወይም በአካባቢ ላይ የሚከተል ያልታቀደ ተፅዕኖን ለመከላከል በቁሳዊና በንጥረ ነገራዊ ከለላ ታጥረውና በባለሥልጣኑ በወጣው በተገቢው መመሪያ ከተፈቀደው ስፋት ባልበለጠ ቦታ ተወስነው ልውጥ ሕያዋን እንዲሰሩ፣ እንዲያድጉ፣ እንዲከማቹ፣

እንዲወገዱ ወይም ትምህርትንና ምርምርን ጨምሮ በሆነ ሌላ መንገድበጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ ነው፤

5. ‹‹የተጨነ ልቀት›› ማለት ከግንዛቤ በመነጨ ስምምነት መሠረት ልውጥ ሕያውን ለንግድ፣ ለምግብ፣ ለእርዳታ ምግብ፣ አካባቢን ለማፅዳት፣ ለማስተማሪያነት፣ ለምርምር፣ ለመስተዋት ቤት፣ ለውሃ ውስጥ አርባታ፣ ለእንስሳት መኖ፣ ለሰው ወይም ለእንስሳት ህክምና ወይም ለሌላ ጥቅም በመዋል ወደ አካባቢ እንዲዳረስ ማድረግ ነው፤
6. ‹‹ከግንዛቤ የመነጨ ስምምነት›› ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት አንድ እንቅስቃሴ እንዲተገበር ከባለሥልጣኑ የሚሰጥ የአዎንታ ጽሑፍ ነው፤
7. ‹‹ለገበያ ማቅረብ›› ማለት ልውጥ ሕያውን ለተጨነ ልቀት ለማዋል ከግንዛቤ የመነጨ ስምምነትን ከተቀበሉ በኋላ በእርዳታ ምግብነት መስጠትን ጨምሮ ለሶስተኛ ወገን በሽያጭ፤ በስጦታ ወይም በሌላ መንገድ ማስተላለፍ ነው፤
8. ‹‹ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖ›› ማለት ከማንኛውም እንቅስቃሴ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የአገር ኢኮኖሚን ጨምሮ በማሕበረሰቦች ማህበራዊ ወይም ባሕላዊ ሁኔታዎች፣ የኑሮ መሠረት፣ ነባር ዕውቀት ወይም ጥበብ ላይ የሚደርስ አሉታዊ ውጤት ነው፤
9. ‹‹ጠንቅ›› ማለት ከየትኛውም እንቅስቃሴ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ፣ በአጭር፣ በመካከለኛ ወይም በረጅም ጊዜ በሰው ወይም በእንስሳ ጤና፣ በብዝሐ ሕይወት፣ በአካባቢ፣ በማህበረሰቦች ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ወይም ባህላዊ ሁኔታ፣ ወይም በአገሪቷ ኢኮኖሚ፣ ላይ ሊከተል የሚችል አደጋ ነው፤
10. ‹‹ፕሮቶኮል›› ማለት በአዋጅ ቁጥር 362)1995 የፀደቀው የብዝሐ ሕይወት ኮንቬንሽን የካርታኼና የደሕንነተ ሕይወት ፕሮቶኮል ነው፤
11. ‹‹ሥልጣን ያለው ብሔራዊ መሥሪያ ቤት›› ማለት በፕሮቶኮሉ ከአንቀጽ 7 እስከ 12 የተዘረዘሩትን ተግባራት እንዲያስፈፅም ልውጥ ሕያው ወደ ኢትዮጵያ ከሚላክበት አገር መንግሥት ሥልጣን የተሰጠው ተቋም ነው፤
12. ‹‹ባለሥልጣን›› ማለት በአዋጅ ቁጥር 295)1995 የተቋቋመው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ነው፤[54]

[54] በ25/08 (2011) አ. 1097 አንቀጽ 36(17) መሰረት የአካባቢ፣ የደን እና አየር ለውጥ ኮሚሽን ስለሆነ በአዋጁ ውሰጥ ባለስልጣኑ የሚለው ኮሚሽኑ በሚል ተተክቶ ይነበብ፡፡

13.‹‹ሥልጣን የተሰጠው ፈቃድ ሰጪ መሥሪያ ቤት›› ማለት የንግድ ወይም የሥራ ፈቃድ እንዲሰጥ በህግ ሥልጣን የተሰጠው ማንኛውም የመንግሥት አካል ነው፤

14.‹‹ተቆጣጣሪ›› ማለት ይህ አዋጅና በአዋጁ መሠረት የወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ የፍተሻና ሌላ የቁጥጥር እርምጃ እንዲወስድ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የተሾመ ሰው ነው፤

15.‹‹ብሔራዊ የደህንነተ ሕይወት የመረጃ ሥርዓት›› ማለት በፕሮቶኮሉ አንቀፅ 20 መሠረት ስለልውጥ ህያዋን የሚዘግቡ ሳይንሳዊ፣ ጥበባዊ፣ አካባቢያዊና ሕግ ነክ መረጃዎችንና የልውጥ ህያዋን አያያዝን በሚመለከት የልምድ ልውውጥ ለማስገኘት በባለሥልጣኑ የተዘረጋ ሥርዓት ነው፤

16.‹‹ክልል›› ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47 የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ የከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

17.‹‹አመልካች››ማለት የሚጠይቀዉን እንቅስቃሴ ለማካሄድ ከግንዘቤ የመነጨ ስምምነት እንዲሰጠዉ ለባለሥልጣኑ ያመለከተ ሰዉ ነዉ፤

18.‹‹ፈቃድ የተሰጠዉ ሰው›› ማለት ከግንዛቤ የመነጨ ስምምነት ከባለሥልጣኑ የተሰጠው ሰው ነው፤

19.‹‹ሰዉ›› “ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተስጠው አካል ነው፤

20.ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል።

3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ይህ አዋጅ በማንኛውም እንቅስቃሴ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
2. ኢትዮጵያ ያፀደቀችው እስከሆነ ድረስ ለሰው ሕክምና የሚሆንን፣ በኢትዮጵያ ግዛት በትራንዚት የሚያልፍን ወይም ጎጂ ተፅዕኖ የማምጣት እድል የለውም የተባለን ልውጥ ሕያው የሚመለከት ዓለም ዓቀፍ ስምምነት በኢትዮጵያ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
3. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተጠቀሱት እንቅስቃሴዎችን የሚመለከት መረጃ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 13 መሠረት በተቋቋመው ብሔራዊ የደሕንነተ ሕይወት የመረጃ ሥርዓት ማስገባት አለበት፡፡

4. **የአዋጁ ዓላማ**

የአዋጁ ዓላማ በሰውና በእንስሳት ጤና፣ በብዝሐ ሕይወት፣ በአካባቢ፣ በማኅበረሰቦችና በአጠቃላዩም በሀገር ላይ ከልውጥ ሕያዋን ሊደረስየሚችለውን አሉታዊ ተፅዕኖ ማስቀረት ወይም ቢያንስ እስከ ኢምንታዊነት ደረጃ ድረስ ማሳነስ ነው፡፡

5. **ከግንዛቤ የመነጨ ስምምነት**

1. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ከግንዛቤ የመነጨ ስምምነትን ያላገኘ ሰው በማንኛውም እንቅስቃሴ ለመሰማራት አይፈቀድለትም።
2. በማንኛውም እንቅስቃሴ ለመሰማራት የሚፈልግ ሰው በዚህ አዋጅና በአዋጁ መሠረት በሚወጡት ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት የተዘጋጀ ማመልከቻ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት።
3. ባለሥልጣኑ ከግንዛቤ የመነጨ ስምምነት ለመስጠት እንዲቻለው አመልካቹ በዚህ አዋጅ የተመለከቱ ግዴታዎችን ለማሟላት በቂ ዋስትና እንዲያቀርብ መጠየቅ ይችላል፡፡

6. **የአመልካች ግዴታ**

1. አመልካቹ የጠንቅ ግምገማውን በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት ብቃት ባለው ባለሙያ ማካሄድና ዘገባ ማዘጋጀት፣ ዘገባውንም ባለሥልጣኑ ያስፈልጋሉ ካላቸው ከሌሎች ሰነዶች ጋር ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡
2. የጠንቅ ግምገማ ዘገባው ከዝርዝር ሙያዊ ትንታኔው በተጨማሪ ማንም ሊረዳው በሚችል ቋንቋ የትንታኔውን ይዘት ባጭሩ ከያዘ መግለጫ ጋር መቅረብ አለበት፡፡
3. የጠንቅ ግምገማ የማካሄጃና ዘገባ የማዘጋጃ ወጪ በአመልካቹ መሸፈን አለበት፡፡

7. **ምንነትን መለየትና ጽፎ መለጠፍ**

1. በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጡ አግባብነት ባላቸው ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት የልውጥ ሕያዉን ምንነት በአማርኛና በእንግሊዘኛ ቋንቋዎች የሚገልፅ ፅሁፍ በልውጥ ሕያው ጥቅል ላይ ባልተለጠፈበት ልውጥ ህያው ከቤተ ሙከራ ዝግ ሁኔታ ውጪ ማንኛውም እንቅስቃሴ መካሄድ የለበትም፡፡
2. ‹‹በዘረመላዊ ምሕንድስና የተለወጠ ሕያው ይገኝበት ይሆናል›› የሚል ወይም ተመሳሳይ ግልጽ ያልሆነ ጽሁፍ በጥቅሉ ላይ መለጠፍ የተከለከለ ነው፡፡

3. በልውጥ ሕያዋን ጥቅል ውስጥ የሚገኘውን ማንኛውንም ልውጥ ሕያዉ ምንነት በተለጠፈበት ጽሁፍ ላይ ሳይገልጹ መተው የተከለከለ ነው፡፡
4. ማንኛውም ሰው በጥቅሉ ውስጥ ምንም ዓይነት ልውጥ ሕያው የማይገኝበት መሆኑን ካረጋገጠ ‹‹ልውጥ ሕያው የለበትም›› የሚል ጽሁፍ ሊለጥፍበት ይችላል።

## 8. ልውጥ ሕያው ወደ አገር ውስጥ ማስገባት

1. ከግንዛቤ የመነጨ ስምምነት ሳይዙ ልውጥ ሕያውን ወደ አገር ውስጥ ማስገባት የተከለከለ ነው፡፡
2. ልውጥ ሕያውን ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት ከግንዛቤ የመነጨ ስምምነት እንዲሰጥ ከሚቀርበው ማመልከቻ ጋራ የሚያያዘው መረጃ ትክክለኛና የተሟላ ስለመሆኑ የላኪው አገር ሥልጣን ያለው ብሔራዊ መሥሪያ ቤት ሙሉ ኃላፊነት መውሰዱን የመሥሪያ ቤቱ ኃላፊ በፊርማው ያረጋገጠበት መሆን አለበት፡፡

## 9. መሥራትና ሌሎች ዝግ አጠቃቀሞች

1. ልውጥ ሕያውን የሚሰራ ሰው የሚጠቀምባቸው ወላጅ ሕያዋንን ባሕርያት፣ ምርምሩ የሚካሄድበትን ቦታና የአካባቢውን ሁኔታ በመገምገም በቅድመ ጥንቃቄ መርሕ ተመስርቶ በሳይንሳዊነቱ ተቀባይነት ያለውንና በአካባቢ ላይ ጠንቅ የማያስከትልን አሠራር በመከተል ሊከሰት የሚችል ጠንቅን ወደ ኢምንታዊነት ደረጃ መቀነስ አለበት፡፡
2. በዝግ የአጠቃቀም ሁኔታ በልውጥ ሕያው ተጠቃሚ የሆነ ሰው ባልተጠኑ ልቀት ምክንያት የሚከተለውን ጨምሮ ማንኛውንም ምንም አደጋ ለማስቀረት አስፈላጊ የሆኑ የደህንነት ጥንቃቄዎች መወሰዳቸውን ማረጋገጥ እና የተሰራውን ልውጥ ሕያው ወይም የዋለበትን አገልግሎት እንዲሁም ማንኛውንም ያልታሰበ ክስተት በመዝገብ መያዝ አለበት፡፡
3. ዝግ አጠቃቀም በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት ለዚሁ ተግባር ማካሄጃ በባለሥልጣኑ ተመዝግቦ ፈቃድ በተሰጠው ቦታ ብቻ መካሄድ አለበት፡፡

## 10. በትራንዚት ማሳለፍ

1. ልውጥ ሕያውን በኢትዮጵያ ግዛት በኩል በትራንዚት ለማሳለፍ የሚፈልግ ሰው ይህንኑ ለባለሥልጣኑ በቅድሚያ ማሳወቅ አለበት፡፡

2. ባለሥልጣኑ በኢትዮጵያ ግዛት በኩል በትራንዚት ቢያልፍ አደገኛ ሆኖ የሚያገኘውን ልውጥ ሕያው በፕሮቶኮሉ የመረጃ ሥርዓት እንዲገለፅ ማድረግ አለበት፡፡

11.<u>የሕዝብ ተሳትፎ</u>

1. ባለሥልጣኑ የጠንቅ ግምገማ ዘገባ እንደደረሰው ዘገባውን በሕዝብ ማስታወቂያ አውታሮች በኩል ለባለድርሻዎች በማሰረጨት ከአንድ ወር ላልበለጠ ጊዜ አስተያየቶችን መሰብሰብ አለበት።
2. ከግንዛቤ የመነጨ ስምምነት ስለመስጠት ወይም ስላለመስጠት የሚቀርቡ አስተያየቶች ባለሥልጣኑ በወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ በጽሑፍ መቅረብ አለባቸው፡፡

12.<u>ብሔራዊ የደህንነተ ሕይወት መረጃ ስርዓት</u>

1. ባለሥልጣኑ ብሔራዊ የደህንነተ ሕይወት መረጃ ሥርዓት ማቋቋም አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ )1) መሠረት የሚቋቋመው የደህንነተ ሕይወት መረጃ ሥርዓት የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፡-
   ሀ) በልውጥ ህያዋን እውቀት ያላቸው በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ባለሙያዎች ስም፣ አድራሻና ሌሎች ተዛማጅ መረጃዎች፤
   ለ) ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡና ወደ ውጭ እንዲላኩ ፈቃድ የተሰጣቸውና የተከለከሉ የልውጥ ህያዋንን ዝርዝር፤
   ሐ) ይህ አዋጅ በሚፈቅደው መሠረት የቀረቡ ማመልከቻዎችን፤
   መ) አግባብነት ያላቸውን አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና የአሠራር ደንቦችን፤
   ሠ) ያልተጤነ ልቀትን ለመቋቋም የተዘረጋ ማንኛውንም ብሔራዊ የአደጋ ጊዜ ዝግጅትን፤
   ረ) ከግንዛቤ የመነጨ ስምምነት ለመስጠት ባለሥልጣኑ የሚፈልጋቸው መረጃዎችን፤
   ሰ) ማንኛውም አግባብነት ያለው የሁለትዮሽ አህጉራዊና የብዙ አገሮች ስምምነቶችና የአሠራር ሂደቶችን፤
   ሸ) ልውጥ ህያዋን ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ እና የተጤነ ልቀትእንዲካሄድባቸው ባለስልጣኑ የፈቀደበትን የመጨረሻ ውሳኔ፤
   ቀ) ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ሌሎች መረጃዎችን፡፡

3. ወደ ብሔራዊ ደህንነተ ሕይወት የመረጃ ስርዓት ውስጥ የገቡት ማናቸውም ዘገባዎችና ሰነዶች ለሕዝብ ክፍት መሆን አለባቸው።
4. በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 13 መሠረት በምስጢር እንዲያዝ የተወሰነበት መረጃ ወደ ብሔራዊ የደህንነተ ሕይወት መረጃ ሥርዓቱ እንዳይገባ የተከለከለ ነው።

13.<u>በሚስጥር የሚያዝ መረጃ</u>

1. እያንዳንዱ አመልካች በምስጢር እንዲያዙለት የሚፈልጋቸውን መረጃዎች ለባለሥልጣኑ የማሳወቅ መብት አለው፡፡
2. ለደህንነተ ሕይወትና ለሌላ ምክንያት አስፈላጊ በመሆኑ በምስጢር መጠበቅ የለበትም ብሎ ባለሥልጣኑ ያመነበትን መረጃ ለይቶ ለአመልካቹ ይገልጽለታል። አመልካቹም በዚሁ ይስማማል ወይም ማመልከቻውን ይስርዛል።
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ድንጋጌዎች ቢኖሩም በአመልካቹ የሚቀርቡት የሚከተሉት መረጃዎች ምንጊዜም በምስጢር እንዲያዙ አይፈቀደም፡-
   ሀ) የልውጥ ህያው ምንነት መግለጫ፣ የአመልካቹ ስምና አድራሻ፣ የእንቅስቃሴው ዓላማና ቦታ፤
   ለ) ልውጥ ሕያውን ለመከታተል የሚያስችል ዘዴና እቅድ እንዲሁም የአደጋ መቋቋሚያ ዝግጅት፤
   ሐ) ሊደርስ የሚችል አደጋ ግምገማ፣ በተለይም በሽታ የማስያዝ ወይም አካባቢን የማወክ ተጽዕኖ።
4. አመልካቹ አቅርቦት የነበረውን ማመልከቻ ከሰረዘ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (3) ከተዘረዘሩት በስተቀር የመረጃውን ምስጢራዊነት ባለሥልጣኑ መጠበቅ አለበት።

14.<u>ውሳኔ አሰጣጥ</u>

1. ባለሥልጣኑ በአመልካቹ የቀረበውን እንዲሁም በፕሮቶኮሉና በብሔራዊ የደህንነተ ሕይወት የመረጃ ሥርዓት ውስጥ የሚገኘውን መረጃ፣ የባለሙያዎች አስተሳሰብንና የየባለድርሻዎች አስተያየትን በማጤንናከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመመካከር በቀረበው ማመልከቻ ላይ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

2. ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ባለሥልጣኑ አስፈላጊ መስሎ የታየውን ተጨማሪ መረጃ አመልካቹ እንዲያቀርብ ሊጠይቅ ይችላል፡፡ የተጠየቀውን መረጃ ያላቀረበ ማንኛውም አመልካች ማመልከቻውን እንደሰረዘ ይቆጠራል።
3. ባለሥልጣኑ የባለሙያዎች አስተሳሰብና የባለድርሻዎች አስተያየቶች በደረሱት በ15 ቀናት ውስጥ የጠንቅ ግምገማ ዘገባውን በመገምገም፦
   ሀ) እንቅስቃሴውን ከኢምንት ያለፈ ጠንቅ የማያስከትል መሆኑን ካመነ ዘገባውን ያለ ቅድመ ሁኔታ በማጽደቅ ከግንዛቤ የመነጨ ስምምነቱን ይሰጣል፤
   ለ) ሊከተሉ የሚችሉ ጠንቆች በአስተማማኝነት ሊወገዱ ወይም ወደ ኢምንትነት ደረጃ ሊቀነሱ እንደሚችሉ ካመነ ዘገባውን ያጸድቅና ጠንቆቹን ለመግታት የሚያስፈልጉ ግዴታዎች እንዲሟሉ ከግንዛቤ የመነጨ ስምምነቱን ይሰጣል፤
   ሐ) በተሻለ መረጃ የተደገፈ ውሳኔ ለመስጠት እንዲቻለው አመልካቹን ተጨማሪ መረጃ እንዲያቀርብ ይጠይቃል፤ ወይም
   መ) ዘገባውን ውድቅ በማድረግ ከግንዛቤ የመነጨ ስምምነቱን ይከለክላል።
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ውሳኔው ከተሰጠ በኋላ በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ ባለሥልጣኑ የውሳኔውን ቅጂ ወደ ብሔራዊ የደህንነት ሕይወት የመረጃ ሥርዓት ማስገባት አለበት፡፡

15.<u>ውሳኔ ስለመከለስ</u>

1. ባለሥልጣኑ ስለልውጥ ሕያው ያገኘው አዲስ መረጃ ወይም የነበረው መረጃ ሲገመገም ከባድ ጠንቅ ሊከተል እንደሚችል ካመለከተ ተሰጥቶ የነበረ ከግንዛቤ የመነጨ ስምምነት ሊሰረዝ፣ ወይም ተጨማሪ ግዴታዎች ሊካተቱበት ይችላል።
2. አመልካቹ ከግንዛቤ የመነጨ ስምምነቱን ካገኘ በኋላ ሊደርስ ስለሚችል ከባድ ጠንቅ መረጃ ካገኘ ለባለሥልጣኑ ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፡፡
3. በተሰጠው ከግንዛቤ የመነጨ ስምምነት የተካተተ ማንኛውም ግዴታ ሳይሟላ ከቀረ ባለሥልጣኑ እንቅስቃሴውን ሊያሰቆምና ልውጥ ሕያው እንዲወገድ እስከማድረግ ድረስ ተገቢ ሆኖ ያገኘውን እርምጃ ሊወስድ ይችላል፡፡
4. ለማንኛውም እንቅስቃሴ ከግንዛቤ የመነጨ ስምምነት በመከልከሉ ምክንያት እንደገና እንዲታይ የሚቀርብ ማመልከቻ በአዲስ ሳይንሳዊ መረጃ ከተደገፈ እንደ አዲስ ማመልከቻ በድጋሚ ሊታይ ይችላል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ክልከላው የፀና ይሆናል።

16.<u>ከግንዛቤ የመነጨ ስምምነት ፀንቶ ሊቆይ የሚችልበት ጊዜ</u>

1. በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ እንቅስቃሴው ካልተከናወነ ተሰጥቶ የነበረ ከግንዛቤ የመነጨ ስምምነት ተፈፃሚነት ይቋረጣል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ተሰጥቶ የነበረ ከግንዛቤ የመነጨ ስምምነት ተፈፃሚነት መቋረጥን ተገቢነት የሚቃወም አመልካች ተቃውሞውን በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ በጽሑፍ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ ይችላል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ማመልከቻ ሲቀርብለት ባለሥልጣኑ ከግንዛቤ የመነጨው ስምምነት ተፈፃሚነት እንዲራዘም ወይም የጠንቅ ግምገማው እንዲከለስ ወይም በድጋሚ እንዲሰራ በ 30 የሥራ ቀናት ውስጥ መወሰን አለበት፡፡

17.<u>ፈቃድ የተሰጣቸው ሰዎች ግዴታዎች</u>

1. ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው በጸደቀው የጠንቅ ግምገማ ዘገባ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ስለሚያካሂደው እንቅስቃሴ የፅሁፍ ዘገባ ለባስሥልጣኑ ማቅረብ አለበት።
2. ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው በይዞታው ያለውን ማንኛውንም ለገቢያ ያልቀረበ ልውጥ ሕያው ከባለሥልጣኑ አዲስ ከግንዛቤ የመነጨ ስምምነት ሳያገኝ ለሌላ ሰው አሳልፎ እንዲሰጥ አይፈቀድለትም፡፡
3. ማንኛውም ፈቃድ የተሰጠው ሰው የሰውንና የእንስሳትን ጤንነት እንዲሁም አካባቢን ከማንኛውም ጠንቅ የሚጠብቅበትን የአደጋ መቋቋሚያ ስልት በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት አዘጋጅቶ መተግበር አለበት፡፡
4. ማንኛውም ፈቃድ የተሰጠው ሰው በይዞታው የነበረ ማንኛውም ልውጥ ሕያው ቢጠፋበት ወይም ቢሰረቅበት ወዲያውኑ ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

18.<u>ሥልጣን የተሰጣቸው የፈቃድ ሰጪ መሥሪያቤቶች ተግባራት</u>

1. ሥልጣን የተሰጠው ፈቃድ ሰጪ መሥሪያ ቤት ከግንዛቤ የመነጨ ስምምነት ላላቀረበ አመልካች እንቅስቃሴውን እንዲያካሄድ ከመፍቀድ የተከለከለ ነው፡፡
2. ባለሥልጣኑ የሰጠውን ከግንዘቤ የመነጨ ስምምነት ሲያግድ ወይም ሲሰርዝ ሥልጣን የተሰጠው ፈቃድ ሰጪ መሥሪያ ቤት ለዚያው እንቅስቃሴ ሰጥቶት የነበረውን ፈቃድ ማገድ ወይም መሰረዝ አለበት፡፡

## 19. የተቆጣጣሪዎች ሥልጣንና ተግባር

1. ማንኛውም ተቆጣጣሪ የዚህ አዋጅና በአዋጁ መሠረት የሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ፡-
   ሀ) ማንኛውም እንቅስቃሴ ወደሚካሄድበት ቦታ ወይም ተቋም ውስጥ መግባት፣
   ለ) የሚካሄደውን እንቅስቃሴ መፈተሽና ማስተካከያ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ትዕዛዝ መስጠት፣
   ሐ) እንቅስቃሴ ከሚያካሄደው ሰው ወይም ከኃላፊው መረጃ መጠየቅና ማግኘት፣
   መ) ከእንቅስቃሴ ጋር ግንኙነት ያለውን ማንኛውንም መዝገብ ወይም ሰነድ መመርመርና ቅጅው እንዲሰጠው መጠየቅ፣ እና
   ሠ) የማንኛውንም ቁስ ናሙና ያለ ክፍያ መውሰድና አስፈላጊ የሆነ ፍተሻ ማካሄድ ወይም እንዲካሄድ ማድረግ፣

   ይችላል።
2. ማንኛውም ተቆጣጣሪ በዚህ አዋጅ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር በትጋትና ባለማዳላት ማከናወን እንዲሁም በተጠየቀ ጊዜ መታወቂያውን ማሳየት አለበት።

## 20. በመግቢያና በመውጫ ቦታዎች የሚደረግ ቁጥጥር

1. ማንኛውንም ልውጥ ህያው ይዞ ወደ አገር ውስጥ የሚገባ ወይም ከአገር የሚወጣ ግለሰብ በመግቢያ ወይም በመውጫ በሩ በስራ ላይ ሳለ የጉምሩክ ሠራተኛ ማሳወቅ አለበት፡፡
2. ማንኛውም የጉምሩክ ሠራተኛ ከግንዛቤ የመነጨ ስምምነት ሳይኖር ማንኛውም ግለሰብ ልውጥ ህያው መያዙን ከጠረጠረ ወይም ልውጥ ህያው ይዟል ብሎ የጠረጠረውን ጭነት ካገኘ ያግተውና ለባለሥልጣኑ ያሳውቃል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የታገተውን ነገር የጉምሩክ ሠራተኛው በብዝሀ ሕይወት፣ በአካባቢ ወይም በሰው ወይም በእንስሳት ጤንነት ሊደርሱ የሚችሉ ጠንቆችን በሚያሳንስ ዘዴ ያስቀምጠዋል።
4. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ከታገተው ነገር ላይ ናሙና ወስዶ በመመርመር ልውጥ ሕያው ያለበት መሆን አለመሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

5. የጉምሩክ ሠራተኛ የተረከበው ሕያው ልውጥ አለመሆኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት በተካሄደ ፍተሻ ከተረጋገጠ ለምርመራ በጥቅም ላይ የዋለው መጠን ብቻ ተቀንሶበት ለተያዘበት ሰው መመለስ አለበት፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ታግቶ የተቀመጠው ነገር ልውጥ ሕያው መሆኑ ከተረጋገጠና በ30 ቀናት ውስጥ ከኢትዮጵያ እንዲወጣ ካልተደረገ ባለሥልጣኑ በማቃጠል ወይም ተገቢ በሆነ ሌላ መንገድ እንዲወገድ ያደርጋል፡፡
7. ወደ አገር ውስጥ የገባ ልውጥ ሕያው ተቀባይ አጥቶ በደረሰበት ቦታ ከሁለት ሳምንታት በላይ ከቆየ ባለሥልጣኑ ከጉምሩክ ሠራተኛ ወይም ከሌላ ተገቢ የመንግሥት ባለሥልጣን ጋር በመሆን ልውጥ ህያው ወደ መጣበት አገር እንዲመለስ ወይም አካባቢያዊ ተቀባይነት ባለው ዘዴ እንዲወገድ እርምጃ ሊወሰድ ይችላል፡፡
8. ተገቢው እርምጃ ላለመወሰዱ ግለጽ ጥፋት መኖሩ ካልተረጋገጠ በስተቀር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት ታግቶ የተቀመጠው ነገር ይዘቱ ቢበላሽ ባለሥልጣኑም ሆነ የጉምሩክ ሠራተኛው ተጠያቂ አይሆኑም።
9. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ታግቶ የቆየውን ልውጥ ህያው ለማስወገድ ለማስቀመጥ ወይም መልሶ ወደ ለመላክ የወጣው ማንኛውም ወጪ በታገተበት ሰው መሸፈን አለበት፡፡

21.<u>ቅጣት</u>

1. በወንጀል ሕግ ድንጋጌዎች የበለጠ የሚያስቀጣ ካለሆነ በስተቀር፡-
   ሀ) ማንኛውም ሰው ሆን ብሎ በሰው ጤንነት፣ በብዝሐ ሕይወት፣ በአካባቢ ወይም በንብረት ላይ ጉዳት ለማድረስ ወይም በሌላ መንገድ ለማወክ እንቅስቃሴ ካካሄደ ከ10 እስከ 15 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፤
   ለ) የዚህን አዋጅ ድንጋጌ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት በወጣ ደንብ ወይም መመሪያ የተደነገገውን የተላለፈ ማንኛውም ሰው ከ4ሺ እስከ 7ሺ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ወይም ከአንድ እስከ ሦስት ዓመት በሚደርስ እስራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል።
2. የወንጀሉ ድርጊት የተፈጸመው በሕግ የሰውነት መብት በተሰጠው አካል ሲሆን የቅጣቱ አወሳሰን በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ወንጀል ሕግ አንቀጽ 90 ድንጋጌዎች መሠረት ይፈጸማል፡፡

3. በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ጥፋት ሲፈፅም ከሚወሰንበት መቀጮ በተጨማሪ የሕጉን መከበር ለማረጋገጥ መፈፀም የሚገባውን ተግባር በትጋት ያልተወጣው የሥራ መሪ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) (ለ)መሠረት ይቀጣል።

22.<u>**ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**</u>

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ባለሥልጣኑ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

23.<u>**አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ጳጉሜ 4 ቀን 2001 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ**

**ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## አዋጅ ቁጥር 716/2003

## የኦዞን ንጣፍን የሚያሳሱ ኬሚካሎችን ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ

ኢትዮጵያ የኦዞንን ንጣፍ የሚያሳሱ ኬሚካሎችን የሚመለከተውን የሞንትሪያል ፕሮቶኮልና ማሻሻያዎቹን ተቀብላ ያፀደቀች በመሆኑ፤

የሞንትሪያል ፕሮቶኮል እያንዳንዱ ፈራሚ አባል ሀገር በፕሮቶኮሉ አባሪዎች የተዘረዘሩትን ቁጥጥር የሚደረግባቸውን ንጥረ ነገሮች ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባትና ከሀገር ለማስወጣት የሚያስችል የፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓት እንዲኖረው የሚጠይቅ በመሆኑ፤

ይህንኑ የፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓት ለመዘርጋት የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ እንዲኖር የማድረግ አስፈላጊነቱ የታመነበት በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

1. **<u>አጭር ርዕስ</u>**

   ይህ አዋጅ "የኦዞን ንጣፍን የሚያሳሱ ኬሚካሎችን ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁጥር 716/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **<u>ትርጓሜ</u>**

   የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

   1. "ባለሥልጣን"ማለት የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ነው፤[55]
   2. "መሣሪያ" ማለት የኦዞን ንጣፍን የሚያሳሳ ኬሚካል የሚጠቀም ወይም የሚያመነጭ ቴክኖሎጂ ወይም መሣሪያ ነው፤
   3. "ነጋዴ" ማለት ማንኛውም የኦዞን ንጣፍን የሚያሳሱ ኬሚካሎችን ወይም መሣሪያዎችን በማስመጣት ወይም በመሸጥ ወይም መሳሪያዎችን በማደስ ወይም በመጠገን የንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ሰው ነው፤
   4. "ፈቃድ ሰጪ አካል" ማለት የንግድ ፈቃድ ለመስጠት ወይም ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎችን ሕጋዊነት ለመቆጣጠር በሕገ ሥልጣን የተሰጠው ማንኛውም የፌዴራል ወይም የክልል መንግሥት አካል ነው፤
   5. "የኦዞን ንጣፍ" ማለት ስትራቶስፌር በመባል በሚታወቀው ከባቢ አየር ውስጥ የሚገኝ የኦዞን ክምችት ነው፤

[55] በ25/12 (2011) ኢ. 1097 አንቀጽ 36(17) መሰረት የአካባቢ፣ የደን እና አየር ለውጥ ኮሚሽን ስለሆነ በአዋጁ ውስጥ ባለስልጣኑ የሚለው ኮሚሽኑ በሚል ተተክቶ ይነበብ፡፡

6. “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ 47 (1 የተጠቀሰው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችንም ይጨምራል፤
7. “የአዞን ንጣፍን የሚያሳሱ ኬሚካሎች” ማለት ሳይደባለቁም ሆነ ተደባልቀው ጥቅም ላይ ሲውሉ የኦዞን ንጣፍን የሚያሳሱ ከዚህ አዋጅ ጋር ተያይዞ በሚገኘው ሠንጠረዥ የተዘረዘሩ ኬሚካሎች ናቸው፤
8. “ሰዉ” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
9. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል።

3. <u>የኦዞን ንጣፍን የሚያሳሱ ኬሚካሎችን ወደሀገር ዉስጥ ስለማስገባት</u>

1. ማንኛውንም የኦዞን ንጣፍን የሚያሳሳ ኬሚካል ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተመለከተው የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ ሀገር ውስጥ ማስገባት የተከለከለ ነው።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም የኬሚካል ግዥው የተፈፀመው ይህ አዋጅ ከመዉጣቱ በፊት ስለመሆኑ ወይም ኬሚካሉ የተፈለገው የአገልግሎት ጊዜው ያላለፈ መሳሪያን ለማንቀሳቀሻ፣ ለማደሻ ወይም ለመጠገኛ ስለመሆኑ አሳማኝ ማስረጃ ከቀረበ ባለሥልጣኑ ክልከላን ሊያነሳ ይችላል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ክልከላው እንዲነሳለት የሚፈልግ ነጋዴ ተገቢውን ፎርም በመሙላት ለባለሥልጣኑ ማመልከት አለበት።
4. ባለስልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት የቀረበለትን ጥያቄ ያልተቀበለበትን ሆነ የተቀበለበትን ምክንያት ለአመልካቹ በጽሑፍ ያሳውቃል።

4. <u>መሳሪያዎችን ወደ ሀገር ዉስጥ ስለማስገባት</u>

1. የኦዞን ንጣፍን የሚያሳሳ ኬሚካል የሚጠቀም ወይም የሚያመነጭ መሣሪያ ወይም ቴክኖሎጂ ወደ ሀገር ዉስጥ ማስገባት የተከለከለ ነው።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም ግዢዉ የተፈፀመው ይህ አዋጅ ከመዉጣቱ በፊት ስለመሆኑ ወይም አማራጭ መሣሪያ ወይም ቴክኖሎጂ የሌለ ስለመሆኑ አሳማኝ ማስረጃ ካቀረበ ባለሥልጣኑ ክልከላዉን ሊያነሳ ይችላል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ክልከላዉ እንዲነሳለት የፈለገ ነጋዴ ተገቢውን ፎርም በመውላት ለባለሥልጣኑ ማመልከት አለበት።
4. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት የቀረበለትን ጥያቄ ያልተቀበለበትን ሆነ የተቀበለበትን ምክንያት ለአመልካቹ በጽሑፍ ያሳውቃል።

5. <u>***መሳሪያዎችን ስለመጠገን እና ስለማደስ***</u>

*መሣሪያዎች ሲጠገኑና ሲታደሱ የኦዞንን ንጣፍ የሚያሳሱ ኬሚካሎች በማያመነጩበት መንገድ መሆን ይኖርበታል።*

6. <u>***ድርጅቶችን ስለማቋቋምማካሄድና ማስፋፋት***</u>

   1. *ማንኛውም ሰው ከባለሥልጣኑ የተሰጠ ፈቃድሳይኖረው የኦዞንን ንጣፍ የሚያሳሱ ኬሚካሎችን አጠቃቀም ሊያሳድግ የሚችል አሠራር የሚኖረው ድርጅት ማቋቋም፣ ማካሄድ ወይም ማስፋፋት አይችልም፡፡*
   2. *የኦዞን ንጣፍን የሚያሳሱ ኬሚካሎችን አጠቃቀም ሊያሳድግ የሚችል አሠራር የሚኖረው ድርጅትን ለማቋቋም፣ ለማካሄድ ወይም ለማስፋፋት የሚፈልግ ማንኛውም ሰውበተገቢው ፎርም ለባለሥልጣኑ ማመልከት አለበት፡፡*
   3. *ባለሥልጣኑ የፈቃድ መጠየቂያ ማመልከቻውን እንደተቀበለ ማመልከቻውን መርምሮ ፈቃዱን በመከልከል ወይም ቅድመ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ወይም ያልተመሰረተ ፈቃድ በመስጠት መወሰን አለበት።*
   4. *ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ* (3) *መሠረት የቀረበለትን ጥያቄ ያልተቀበለው እንደሆነ ያልተቀበለበትን ምክንያት ለአመልካቹበ ጽሑፍ ያሳውቃል።*

7. <u>***ስለፈቃድ ዕድሳት***</u>

*በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠ ፈቃድ ካልታደሰ በቀር የሚያገለግለው ለአንድ ዓመት ብቻ ይሆናል፡፡*

8. <u>***ፈቃድን ስለማገድና መሰረዝ***</u>

   1. *ማንኛውም ሰው በተሰጠው ፈቃድ የተቀመጡ ገደቦችንና ሁኔታዎችን ለመተላለፉ አሳማኝ ምክንያት ሲገኝ ወይም ለሕብረተሰቡ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠን ፈቃድ ሊያግድ ወይም ሊሰርዝ ይችላል፡፡*
   2. *በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ* (1) *መሠረት ፈቃዱ የታገደበት ወይም የተሰረዘበት ማንኛውም ሰው ስለፈቃዱ መታገድ ወይም መሰረዝ ማስታወቂያ በደረሰው በ*15 *የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን በጽሑፍ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ ይችላል፡፡ ባለሥልጣኑም የቀረበለትን ቅሬታ መርምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የመጨረሻ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡*

3. ባለሥልጣኑ ቅሬታውን መርምሮ የመጨረሻ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የተሰጠ የፈቃድ መሠረዝ አይነሳም፡፡

9. <u>የነጋዴዎች ግዴታ</u>

1. ማንኛውም ነጋዴ ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባቸውን፣ የሸጣቸውን፣ የጠገናቸውን፣ ያደሳቸውን ወይም ያመረታቸውን መጠን፣ ዓይነት እንዲሁም የተሰሩበትን ሀገር የሚመዘግብበት መዝገብ መያዝ እና በየጊዜው ለባለሥልጣኑ ሪፖርት የማድረግ ግዴታ አለበት።
2. ማንኛውም ነጋዴ አግባብነት ያለውን የምርቱን አጠቃቀም መመሪያ በመጠቀም በሚሸጣቸው የኦዞን ንጣፍን የሚያሳሱ ኬሚካሎች ወይም መሣሪያዎች ላይ ተገቢውን መለያ በማድረግ ማስተዋወቅ አለበት፡፡
3. ማንኛውም ነጋዴ በፈቃዱ የተመለከቱ አስገዳጅ ሁኔታዎችን የማክበርና የመተግበር ግዴታ አለበት፡፡

10. <u>የፈቃድ ሰጪ አካል ግዴታ</u>

ፈቃድ ሰጪ አካላት በባለሥልጣኑ የተሰጠ ፈቃድ የመከልከል፣ የመስጠት፣ የማገድ ወይም የመሰረዝ ውሳኔን በመከተል በተመሳሳይ የንግድ ፈቃድ የመከልከል፣ የመስጠት፣ የማገድ ወይም የመሰረዝ ኃላፊነታቸውን መወጣት አለባቸው።

11. <u>የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር</u>

በሞንትሪያል ፕሮቶኮል ላይ የተደረጉ ማሻሻያዎች ማጽቂያ አዋጅ ቁጥር 656)2001 አንቀጽ 3 ድንጋጌ ቢኖርም ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ኬሚካሎችና መሣሪያዎች ጊዜያቸውን ጠብቀው ቀስበቀስ ከገበያ የሚወጡበትን የጊዜ ሰሌዳ የማቀድና ዝርዝራቸውንም የማተም፤
2. ፈቃድ የመስጠት፣ የማደስ፣ የማገድ ወይም የመሰረዝ እንዲሁም የጥገና አገልግሎት ሰጪዎችን፣ የአምራቾችን፣ የአቅራቢዎችን፣ የአስመጪዎችንና ላኪዎችን ስምና አድራሻ መዝግቦ የመያዝ፤
3. በዘርፉ መደበኛ ባልሆነ መልኩ ከጥገናና ከዕድሳት ጋር በተያያዘ ለተሰማሩ ክፍሎችሕጉን ለመከተል የሚያስችላቸውን መንገድ የመቀየስ፣ የማስተዋወቅና የመተግበር፤
4. የኦዞን ንጣፍን የማያሳሱ አማራጭ ኬሚካሎች፣ ልምዶችና ቴክኒኮች እንዲስፋፉ በህዝብ ዘንድ የግንዛቤ ማስጨበጫና የሥልጠና ፕሮግራሞች ለመስጠት እንዲሁም የቴክኒክና ገንዘብ ድጋፍለማድረግ የሚያስችል ሀብት የማፈላለግ፤

5. ይህን አዋጅ የሚፃረር ተግባር ተፈጽሟል ወይም እየተፈፀመ ነው ብሎ ሲያምን ወደ ማንኛውም ቅጥር ግቢ በመግባት ማንኛውንም መሣሪያ ወይም ንጥረ ነገር የመመርመር እንዲሁም ለምርመራ የንጥረ ነገርናሙና የመዉሰድ፤
6. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለሌሎች የፌዴራል ወይም የክልል መንግሥት አካላት የሥልጣን ውክልና የመስጠት፤
7. ስለዚህ አዋጅ አፈጻጸም አግባብነት ላላቸው አካላት ሪፖርት የማቅረብ፤
8. ይህን አዋጅ ለማስፈፀም አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተግባራትን የማከናወን፡፡

12.<u>ቅጣት</u>

1. የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ይህን አዋጅ ወይም ሌላ አግባብ ያለውን ህግ የሚተላለፍ ማንኛውም ሰው ጥፋት ፈጽሟልና ቅጣት ይጣልበታል፡፡
2. ማንኛውንም የኦዞን ንጣፍን የሚያሳሳ ኬሚካል ወደ ሀገር ውስጥ ከመግባቱ በፊት በባለሥልጣኑ ወይም ከሚመለከተው የክልል የአካባቢ ጥበቃ መሥሪያ ቤት ይሁንታ ሳያገኝ ተግባራዊ ያደረገ እንደሆነ ጥፋት ፈፅሟልና ከ10ሺ ብር (ከአስር ሺ ብር) በማያንስ የገንዘብ መቀጮ ወይም እስከ ሁለት ዓመት በሚደርስ እሥራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡
3. ማንኛውንም የኦዞን ንጣፍን የሚያሳሳ ኬሚካል የሚጠቀሙ መሣሪያዎች ሲጠገኑና ሲታደሱ ኬሚካሎች በማያመነጩበት መንገድ መሆን ይኖርበታል። ይህን ግዴታ ያልተወጣ ጥፋት ፈፅሟልና ከ10ሺ ብር (ከአስር ሺ ብር) በማያንስ የገንዘብ መቀጮ ወይም እስከ አንድ ዓመት በሚደርስ እሥራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡
4. ማንኛውም የኦዞን ንጣፍን በሚያሳሳ የኬሚካል መሣሪያዎች ንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ነጋዴ ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባቸውን፣ የሸጣቸውን፣ የጠገናቸውን፣ ያደሳቸውን ወይም ያመረታቸውን መሳሪያዎች መጠን፣ አይነት እንዲሁም የተሰሩበትን ሀገር የሚመዘገብበት መዝገብ መያዝ እና በየጊዜው ለባለሥልጣኑ ሪፖርት የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡ይህን ግዴታ ካልተወጣ ጥፋት ፈፅሟልና ከ10ሺ (ከአስር ሺ ብር) በማያንስና ከ20ሺ ብር (ከሃያ ሺ ብር) በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

5. ይህን አዋጅ ወይም በአዋጁ መሠረት የሚወጣውን ማንኛውንም ደንብ ወይም መመሪያ በመጣስ ጥፋተኝነቱ የተረጋገጠ ሰው ከሚወሰንበት ከማንኛውም ቅጣት በተጨማሪ የደረሰዉን ጉዳት በሙሉ በራሱ ወጪ እንዲያስተካክል ወይም እንዲተካ ፍርድ ቤቱ ማዘዝ ይችላል።

13.<u>ደንብና መመሪያ የማዉጣት ሥልጣን</u>

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤትይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል።
2. ባለሥልጣኑ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስአንቀጽ (1) መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

14.<u>ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸዉ ሕጎች</u>

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ህግ በዚህ አዋጅ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

15.<u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥቅምት 24 ቀን 2004 ዓ.ም**

**ግርማወልደ ጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ**

**ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

ሰንጠረዥ

| ተ.ቁ | ቁጥጥር የሚደረግባቸው ኬሚካሎች ዝርዝር ምልክት | የጊዜ ገደብ) እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር) |
|---|---|---|
| 1 | $CHFBr_2$ | 1996 |
| 2 | $CHF_2Br$ | 1996 |
| 3 | $CH_2FBr$ | 1996 |
| 4 | $C_2HFBr_4$ | 1996 |
| 5 | $C_2HF_2Br_3$ | 1996 |
| 6 | $C_2HF_3Br_2$ | 1996 |
| 7 | $C_2HF_4Br$ | 1996 |
| 8 | $C_2H_2F_2Br_2$ | 1996 |
| 9 | $C_2H_2F_3Br$ | 1996 |
| 10 | $C_2H_3FBr_2$ | 1996 |
| 11 | $C_2H_3F_2Br$ | 1996 |
| 12 | $C_2H_4FBr$ | 1996 |
| 13 | $C_3HFBr_6$ | 1996 |
| 14 | $C_3HF_2Br_5$ | 1996 |
| 15 | $C_3HF_3Br_4$ | 1996 |
| 16 | $C_3HF_4Br_3$ | 1996 |
| 17 | $C_3HF_5Br_2$ | 1996 |
| 18 | $C_3HF_6Br$ | 1996 |

| | | |
|---|---|---|
| 19 | $C_3H_2FBr_5$ | 1996 |
| 20 | $C_3H_2F_2Br_4$ | 1996 |
| 21 | $C_3H_2F_3Br_3$ | 1996 |
| 22 | $C_3H_2F_4Br_2$ | 1996 |
| 23 | $C_3H_2F_5Br$ | 1996 |
| 24 | $C_3H_3FBr_4$ | 1996 |
| 25 | $C_3H_3F_2Br_3$ | 1996 |
| 26 | $C_3H_3F_3Br_2$ | 1996 |
| 27 | $C_3H_3F_4Br$ | 1996 |
| 28 | $C_3H_4FBr_3$ | 1996 |
| 29 | $C_3H_4F_2Br_2$ | 1996 |
| 30 | $C_3H_4F_3Br$ | 1996 |
| 31 | $C_3H_5FBr_2$ | 1996 |
| 32 | $C_3H_5F_2Br$ | 1996 |
| 33 | $C_3H_6FBr$ | 2002 |
| 34 | $CH_2BrCl$ | 2010 |
| 35 | $CFCl_3$ | 2010 |
| 36 | $CF_2Cl_2$ | 2010 |
| 37 | $C_2F_3Cl_3$ | 2010 |
| 38 | $C_2F_4Cl_2$ | 2010 |

| | | |
|---|---|---|
| 39 | $C_2F_5Cl$ | 2010 |
| 40 | $CF_2BrCl$ | 2010 |
| 41 | $CF_3Br$ | 2010 |
| 42 | $C_2F_4Br_2$ | 2010 |
| 43 | $CF_3Cl$ | 2010 |
| 44 | $C_2F_2Cl_4$ | 2010 |
| 45 | $C_3FCl_7$ | 2010 |
| 46 | $C_3F_2Cl_6$ | 2010 |
| 47 | $C_3F_3Cl_5$ | 2010 |
| 48 | $C_3F_4Cl_4$ | 2010 |
| 49 | $C_3F_5Cl_3$ | 2010 |
| 50 | $C_3F_6Cl_2$ | 2010 |
| 51 | $C_3F_7C_1$ | 2010 |
| 52 | $CCl_4$ | 2010 |
| 53 | $C_2H_3Cl_3$ | 2015 |
| 54 | $CH_3B_r$ | 2015 |
| 55 | $CHFCl_2$ | 2030 |
| 56 | $CHF_2Cl$ | 2030 |
| 57 | $CH_2FCl$ | 2030 |
| 58 | $C_2HFCl_4$ | 2030 |

| | | |
|---|---|---|
| 59 | $C_2HF_2Cl_3$ | 2030 |
| 60 | $CHCl_2CF_3$ | 2030 |
| 61 | $C_2HF_4Cl$ | 2030 |
| 62 | $CHFClCF_3$ | 2030 |
| 63 | $C_2H_2FCl_3$ | 2030 |
| 64 | $C_2H_2F_2Cl_2$ | 2030 |
| 65 | $C_2H_2F_3Cl$ | 2030 |
| 66 | $C_2H_3FCl_2$ | 2030 |
| 67 | $CH_4CFCl_2$ | 2030 |
| 68 | $C_2H_3F_2Cl$ | 2030 |
| 69 | $CH_3CF_2Cl$ | 2030 |
| 70 | $C_2H_4FCl$ | 2030 |
| 71 | $C_3HF\ Cl_6$ | 2030 |
| 72 | $C_3HF_2\ Cl_5$ | 2030 |
| 73 | $C_3HF_3\ Cl_4$ | 2030 |
| 74 | $C_3HF_4\ Cl_3$ | 2030 |
| 75 | $C_3HF_5\ Cl_2$ | 2030 |
| 76 | $C\ F\ _3CF_2CHCl_2$ | 2030 |
| 77 | $C\ F\ _3ClCF_2CHClF$ | 2030 |
| 78 | $C_3H\ F_6Cl$ | 2030 |

| | | |
|---|---|---|
| 79 | $C_3H_2FCl_5$ | 2030 |
| 80 | $C_3H_2F_2Cl_4$ | 2030 |
| 81 | $C_3H_2F_3Cl_3$ | 2030 |
| 82 | $C_3H_2F_4Cl_2$ | 2030 |
| 83 | $C_3H_2F_5Cl$ | 2030 |
| 84 | $C_3H_3F_2Cl_3$ | 2030 |
| 85 | $C_3H_3F_2Cl_3$ | 2030 |
| 86 | $C_3H_3F_3Cl_2$ | 2030 |
| 87 | $C_3H_3F_4Cl$ | 2030 |
| 88 | $C_3H_4FCl_3$ | 2030 |
| 89 | $C_3H_4F_2Cl_2$ | 2030 |
| 90 | $C_3H_4F_2Cl$ | 2030 |
| 91 | $C_3H_5FCl_2$ | 2030 |
| 92 | $C_3H_5F_2Cl$ | 2030 |
| 93 | $C_3H_6FCl$ | 2030 |

## አዋጅ ቁጥር 1223/2012

## የማህበረሰብ ተፋሰሶች ልማት፣ አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ

የአካባቢ መራቆትንና የተፈጥሮ ሀብት መመናመንን በመከላከል፣ የብዝሀ ሕይወት ሀብትን በመጠበቅ፣ የውኃ ሀብትን በማጎልበትና የሙቀት አማቂ ጋዞችን ልቀት በመቀነስ የመሬት የማምረት አቅም ተጠብቆ ለመጪው ትውልድ እንዲተላለፍ እና በዚህም ለሰብልና ለእንስሳት ሃብት ልማት ሥራ ምቹ ሁኔታ መፍጠር በማስፈለጉ፤

የአርሶ አደሩ፣ አርብቶ አደሩ እና ከፊል አርብቶ አደሩ ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር በማድረግ ለምግብ ዋስትና መረጋገጥና ለሥራ ዕድል ፈጠራ ምቹ መደላድል ለመፍጠር ይቻል ዘንድ ቀደም ሲል የተጀመሩትን የተፋሰስ ልማት ሥራዎች ማስቀጠል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ባለፉት ዓመታት የተከናወኑት የተፋሰስ ልማት ሥራዎች ከፍተኛ የሰው ጉልበትና የገንዘብ ወጪ ተደርጐባቸው እንዲለሙ የተደረገ ቢሆንም ዘላቂነታቸውን ለማረጋገጥ የተፋሰሱ ተጠቃሚዎች በባለቤትነት ስሜት ተረክበው የተፈጥሮ ሀብቶችን የሚያስተዳድሩበት የርክክብ፣ የአጠቃቀም፣ የአጠባበቅና የተጠያቂነት አሠራር ማስፈን ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤ የማህበረሰብ ተፋሰስ ተጠቃሚዎች ያለሙትን ሀብት ለማስተዳደር፣ ለመጠቀምና ለመጠበቅ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ የሚችሉበትን ሁለንተናዊ አቅም ማሳደግ በማስፈለጉ።

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 55(1) እና (2) (ሀ) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ የማህበረሰብ ተፋሰሶች፣ ልማት፣ አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 1223/2012 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

1. “የማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት ሕብረት ሥራ ማኀበር” ማለት ሰዎች የማህበረሰብ ተፋሰስን ለማልማት ፣ ለመጠበቅና ለመጠቀም በፈቃደኝነት የሚያቋቋሙት በጋራ ባለቤትነት የሚያስተዳድሩት፣ በህብረት ሥራ መርህ መሠረት የሚመሩትና ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የሚመራ ራሱን የቻለ ሕጋዊ ሰውነት ያለው ማህበር ነው፤
2. “ማህበረሰብ ተፋሰስ” ማለት ወደ አንድ መልክዓ-ምድራዊ አቅጣጫ የሚፈስሱ የገፀምድርና የከርሰ ምድር ውኃዎች የሚያካልሉትን አካባቢ የሚያካትት፣ አነስተኛ ተፋሰስ ሆኖ አማካይ ስፋቱ ከ500 ሄክታር የማይበልጥ የመሬት ክፍል ነው፤
3. “የማህበረስብ ተፋሰስ ልማት” ማለት በማህበረሰብ ተፋሰሱ ክልል ውስጥ የሚገኘውን የአፈር፣ የውሃ እና የዕጽዋት ሀብት ለመጠበቅና ምርታማነቱን ለማሳደግ የሚረዱ ተግባራትን አቀናጅቶና አጣጥሞ ማከናወን ማለት ነው፤
4. “የማህበረሰብ ተፋሰስ ተጠቃሚዎች” ማለት በማህበር ተደራጅተውም ይሁን ሳይደራጁ ተፋሰሱ በመልማቱ ምክንያት የሚፈጠረውን ሀብት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ የሚጠቀሙ የህብረተሰብ ክፍሎች ማለት ነው፤
5. “የወል ይዞታ" ማለት በተጠቃሚዎች ስምምነት በሚተዳደር ተፋሰስ ውስጥ በግል፣ በመንግሥታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶችና ተቋማት ያልተያዙ ይዞታዎች እና የአካባቢው ነዋሪዎች በጋራ ይዞታነት የተፈጥር ሀብት ሥራዎች በመሥራት አልምተው እንዲጠቀሙበት በመንግሥት የተሰጣቸው የገጠር መሬት ነው፤
6. “ግል ይዞታ" ማለት በአርሶ አደሮች ከፊል አርብቶ አደሮች እና አርብቶ አደሮች ወይም በሌሎች በሕግ መብት በተሰጣቸው ሰዎች የተያዘ መሬት ነው፤
7. “መንግስት ይዞታ" ማለት በፌደራል ወይም በክልል መንግስት ተከልሎ የተያዘና ወደፊት የሚከለለውን መሬት የሚገልፅ ሲሆን የደን መሬቶችን፣ የዱር እንስሳት ጥብቅ ቦታዎችን ፣የመንግስት እርሻዎችን፣ የማዕድን መሬቶችን ሃይቆችን፣ ወንዞችንና በተመሳሳይ መልኩ የተያዙትን ያጠቃልላል፤

8. “ልዩ ትኩረት የሚሹ የኅብረተሰብ ክፍሎች” ማለት በማህበራዊ፣ በጤና ወይም በኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ምክንያት መብታቸውን ለመጠየቅና ለማግኘት ችግር የሚገጥማቸው እንደ ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ ሕጻናት እና አረጋውያን የመሳሰሉት የኅብረተሰብ ክፍሎች ናቸው፤
9. “ተሳትፎ” ማለት በውሳኔ ሊነኩ በሚችሉ ሀብቶች ላይ መብት ያላቸው ሰዎች በውሳኔ ሰጪነት ሂደት ውስጥ የመሳተፍ መብት ማለት ነው፤
10. “ልዩ መለያ” ማለት አንድን አነስተኛ የማህበረሰብ ተፋሰስ ከሌላው ለይቶ ለማወቅና ከክልል፣ ከዞንና ከወረዳ የአስተዳደር ወሰኖች እንዲሁም ከዋና ተፋሰስ ጋር እንዴት እንደሚተሳሰር ለማመላከት የመልክዓ-ምድር መረጃ ሥርዓት (ጂ.አይ.ኤስ እና የቦታዎች መገኛ ውቅሮችን (የጂኦግራፊያዊ ኮርዲኔቶችን በማቀነባበር የሚሰጥ መለያ ነው፤
11. “የህብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ” ማለት የህብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985)2009 ነው፤
12. “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግስት አንቀጽ 47(1 የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤
13. "ሚኒስቴር )ሚኒስትር” ማለት የግብርና ሚኒስቴር) ሚኒስትር ማለት ነው፤
14. “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ማለት ነው፤
15. በዚህ አዋጅ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው ለሴት ፆታም ያገለግላል።

3. <u>**የተፈፃሚነት ወሰን**</u>

ይህ አዋጅ በሀገሪቱ ውስጥ በሚገኙ የማኅበረሰብ ተፋሰሶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

4. <u>**የአዋጁ ዓላማዎች**</u>

ይህ አዋጅ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፦

1. የአካባቢ መራቆትንና የተፈጥሮ ሀብት መመናመንን በመከላከል፣ የብዝሃሕይወት ሀብትን በመጠበቅ የውሃ ሀብትን በማጎልበትና የሙቀት አማቂ ጋዞችን ልቀት በመቀነስ የማህበረሰቡን ለድርቅ ተጋላጭነት መቀነስና የመቋቋም አቅምን ማሳደግ፤

2. ዘላቂነት ያለው የማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀምን በማረጋገጥ የመሬትን የማምረት አቅም ማሳደግ የአርሶ/አርብቶ አደሩን ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር ማድረግ፣ እንዲሁም ለምግብ ዋስትና መረጋገጥና ለሥራ ዕድል ፈጠራ ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣
3. የማህበረሰብ ተፋሰስ ተጠቃሚዎች በባለቤትነት ስሜት የተፈጥሮ ሀብቶችን ለማልማት፣ ለመጠበቅ፣ ለማስተዳደርና ለመጠቀም የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት ማስፈን ለዚህም የማህበረሰብ ተፋሰስ ተጠቃሚዎችን ሁለንተናዊ አቅም ማሳደግ፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>ስለ ተፋሰስ ዕቅድና ልማት</u>

### 5. <u>የተፋሰስ ዓይነቶች</u>

1. በዚህ አዋጅ መሠረት እውቅና የተሰጣቸው ተፋሰሶች የማህበረሰብ ተፋሰስና በወረዳ ደረጃ የሚለይ ዋና ተፋሰስ ናቸው።
2. የማንኛውም የማህበረሰብ ወይም ዋና ተፋሰስ ስፋት ወይም መልክዓ-ምድራዊ ወሰን በአንድ ውስን አካባቢ የሚገኘውን የተፈጥሮ ሀብት በአንድነት ለማልማትና ብቃት ባለው መንገድ ለመንከባከብ አመች ወይም ተመጣጣኝ ሆኖ የተከለለ መሆን አለበት።

### 6. <u>የማህበረሰብ ተፋሰስ</u>

1. የማህበረሰብ ተፋሰስ አማካይ ስፋት 500 ሄክታር ሆኖ እንደ አካባቢው መልክዓ-ምድራዊ አቀማመጥ ወይም የተፋሰስ ልማቱን ዓላማ ግምት ውስጥ በማስገባት መጠኑ ከፍ ወይም ዝቅ ሊል ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም የማህበረሰብ ተፋሰሱ ከ500 ሄክታር በላይ በሚሆንበት ጊዜ ይህንኑ እንደ አመችነቱ ከፋፍሎ ማልማትና መንከባከብ ይቻላል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ቢኖርም በመከፋፈሉ ምክንያት የሚፈጠረው ተፋሰስ ስፋት ከ200 ሄክታር በታች ሊሆን አይችልም።

### 7. <u>ዋና ተፋሰስ</u>

1. ዋና ተፋሰስ የማህበረሰብ ተፋሰሶች ስብስብ ሲሆን ስፋቱ እስከ 20 ሺ ሄክታር ሊደርስ ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም እንደ አካባቢው መልክዓ-ምድራዊ አቀማመጥ ወይም ለአስተዳደር አመችነት ሲባል መጠኑ ከፍ ወይም ዝቅ ሊል ይችላል።
3. ዋና ተፋሰሶች በወረዳው ውስጥ የሚገኙ ዋና ዋና ወንዞችን መነሻ በማድረግ ይለያሉ።
4. ከዋና ተፋሰሱ ተለይተው የወጡትን የማህበረሰብ ተፋሰሶች ለማልማት ከላይኛው የተፋሰሱ ክፍል በመጀመር ወደታችኛው በቅደም ተከተል መውረድ ያስፈልጋል።
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከራስጌ በታች ጎንና ጎን ከሚገኙ የማህበረሰብ ተፋሰሶች በቅድሚያ የሚለማውን የመራቆት ደረጃ፣ የሰው ሀይልና የሀብት አቅርቦት ግምት ውስጥ በማስገባት ሊለሙ የሚገባቸውን ተፋሰሶችን የመለየት ቅድሚያ ይሰጣል፡፡

8. <u>የማህበረሰብ ተፋሰስ ዕቅድ ዝግጅት</u>

1. የማህበረሰብ ተፋሰስ ዕቅድ ዝግጅት የአሳታፊነት መርሕን የተከተለ መሆን አለበት።
2. በሚመለከተው አካል የፀደቀ የመሬት አጠቃቀም ሥርዓት ተግባራዊ በሚሆንባቸው አካባቢዎች የመሬት አጠቃቀም እቅዶች በሚኖሩበት ጊዜ የማህበረሰብ ተፋሰስ እቅዶች እነዚህኑ መነሻ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡
3. የማህበረሰብ ተፋሰስ የሚያለሙ አካላት በቅድሚያ የማህበረሰብ ተፋሰስ ዕቅድ ማዘጋጀት አለባቸው፡፡
4. የማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት መነሻ ዕቅድ የሚዘጋጀው የህብረት ሥራ ማኅበር ከመቋቋሙ በፊት ሲሆን የህብረት ሥራ ማኅበሩ መሥራች ኮሚቴ የተፋሰስ ተጠቃሚዎች ማኅበሩን ከማደራጀት ጎን ለጎን በሚመለከተው የግብርና ጽ)ቤት በመታገዝ ዕቅዱን ማዘጋጀት አለበት።
5. በሚዘጋጀው ዕቅድ ውስጥ የሚካተቱ ተግባራት የአካባቢ መራቆትንና የተፈጥሮ ሀብት መመናመንን ለመከላከል፣ የውኃ ሀብትን ለማጎልበትና የሙቀት አማቂ ጋዞችን ልቀት በመቀነስ የመሬትን የማምረት አቅም ለማሳደግ የሚያስችሉ መሆን አለባቸው።

6. የማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት በሚታቀድበት ጊዜ መላ ተፋሰሱን ለማልማት የሚያስችል ዝግጅት በማድረግ ከፊሉ ለምቶ ከፊሉ ሣይለማ እንዳይቀር ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ አለበት።
7. ዋና ተፋሰስ የማህበረሰብ ተፋሰሶች ስብስብ በመሆኑ ለልማት ዕቅዱ ተፈፃሚነት ያመች ዘንድ እንደ አስፈላጊነቱ በማህበረሰብ ተፋሰስ ስፋት መጠን ተከፋፍሎ መዘጋጀት ይኖርበታል።
8. በተፈጥሮ የተፋሰስና የአስተዳደር ወሰን ልዩነት በሚያሳይ የማህበረሰብ ተፋሰስ ላይ የሚዘጋጀው ዕቅድ የተፋሰስ ወሰንን ተከትሎ ሲሆን ሁሉንም የተፋሰስ ተጠቃሚ ማህበረሰብ ያሳተፈ መሆን አለበት።
9. የማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት ዕቅድ አዘገጃጀት የአካባቢና ማኅበራዊ ዘላቂነት መርሕን የተከተለ መሆን አለበት።
10. አንድ የማህበረሰብ ተፋሰስ በካርታ የተደገፈ የተሟላ ከ5 እስከ 10 ዓመት የረዥም ጊዜ ዕቅድ ሊኖረው ይገባል።
11. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (9) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የማህበረሰብ ተፋሰሶች የረጅም ጊዜ ዕቅዳቸውን መሠረት ያደረገ ዓመታዊ ዕቅድ ሊዘጋጅላቸው ይገባል።
12. የማህበረሰብ ተፋሰስ ዕቅድ አገራዊ ዋና የተፋሰስ ስትራቴጂክ ዕቅድ ለማዘጋጀት በህግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የወጣ ዕቅድን መሠረት ማድረግ ይኖርበታል፡፡
13. በማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት ህብረት ሥራ ማኅበሩ የተዘጋጀው ዕቅድ ከአንድ ወረዳ በላይ ወሰን ተሻጋሪ ከሆነ ዕቅዱ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ወረዳዎች ሁሉ በወረዳዎቹ ግብርና ጽ)ቤቶች ስምምነት መጽደቅ አለበት፡፡
14. በየአካባቢው የሚለዩ የማህበረሰብ ተፋሰሶች እና ዋና ተፋሰሶች አገራዊውን የልዩ መለያ አሰጣጥ ሂደት ተከትለው ልዩ መለያ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

9. <u>**የማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት**</u>

1. የማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት ሥራዎች ከላይኛው የተፋሰሱ አካል ተጀምረው ወደታችኛው የተፋሰሱ ክፍል መውረድ አለባቸው።
2. ለሚለማው ተፋሰስ ተስማሚ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን በመምረጥ በአግባቡ መተግበር ያስፈልጋል።

3. የማህበረሰብ ተፋሰሶች በተፋሰሱ ተጠቃሚዎች፣ በመንግሥት ወይም መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች በሚቋቋሙ ፕሮጀክቶች ወይም በግለሰቦች ሊለሙ ይችላሉ።
4. የማህበረሰብ ተፋሰስ ዕቅድ በተፈጥሮ ተፋሰስና በአስተዳደር ወሰን መካከል ልዩነት ባለው ቦታ ላይ የሚያርፍ በሆነ ጊዜ ዕቅዱ የሚተገበረው የአስተዳደር ወሰንን በመከተል ይሆናል፡፡
5. በተፋሰስ ልማት ሥራዎች ላይ ተባይና የተቀናጁ የመከላከያ በተፋሰስ ልማት በሽታን ለመቆጣጠር ዘዴዎች ይተገበራሉ።
6. የማህበረሰብ ተፋሰስ አልሚዎች የሚገለገሉበትን ማናቸውም ሰው ሠራሽ ማዳበሪያ ወይም መሠል ኬሚካላዊ ግብዓት የሚያገኙት ከመንግሥት ወይም ሕጋዊ ፈቃድ ከተሰጣቸው ድርጅቶች ብቻ ይሆናል።
7. ማንኛውም ፀረ-ተባይ ኬሚካል ጥቅም ላይ በሚውልበት ጊዜ ሁሉ በንብ እርባታ፣ በሰብልና በአካባቢው ላይ ጉዳት እንዳያስከትል ኬሚካሉን የሚያሰራጨው ሕጋዊ አካል ለኬሚካሉ ተጠቃሚዎች በቂ ዕውቀት ማስጨበጥና ተገቢውን ወቅትና የአጠቃቀም ጊዜ መርጠው ርጭቱን እንዲያካሂዱ ማድረግ ይኖርበታል። ለንብ አርቢዎችም ርጭቱ ከመደረጉ በፊት የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ተግባራት መፈፀም አለባቸው፡፡
8. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (7) ስር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አንዳንድ ኬሚካሎች ካላቸው ጠንካራ መርዛማነት የተነሳ በዕፅዋትና በአካባቢው ላይ የሚያደርሱት ጉዳት ከፍተኛ በመሆኑ በባለሙያ ድጋፍ እንዲረጩ ወይም በእርሱ የቅርብ ክትትል ጥቅም ላይ እንዲውሉ መደረግና የቅሪቶች አወጋገድ የአካባቢ ጥበቃ ሕግ በሚፈቅደው መሠረት ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል።
9. በማህበረሰብ ተፋሰሱ ክልል ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ ግብዓቶች ደረጃቸውን የጠበቁና የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያላለፈ መሆን አለበት።
10. የማህበረሰብ ተፋሰስ አልሚዎች ተፈጥሯዊ የግብርና ግብዓቶችን እንዲጠቀሙ ይበረታታሉ።

## ክፍል ሦስት

## ስለ ማህበረሰብ ተፋሰስ ተጠቃሚዎች ህብረት ሥራ ማኅበር አመሠራረት

### 10.ስለ ህብረት ሥራ ማኅበር አመሠራረት

1. የኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በክፍል ሦስት የተደነገጉት ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ።
2. መሠረታዊ ማኅበሩ በማህበረሰብ ተፋሰሱ ስፋት ወይም ወሰን መሠረት መቋቋም አለበት። ሆኖም ግን የማህበረሰብ ተፋሰሱና የአስተዳደር ወሰኖች የሚለያዩ ከሆነ ማኅበሩ የወረዳውን ወሰን ተከትሎ መቋቋም አለበት፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡
3. የማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት ህብረት ሥራ ዩኒየኖች የዞን አስተዳደር ወሰንን ተከትለው የሚደራጁ ሲሆን በዞን ውስጥ በተመሳሳይ ተግባር ከአንድ በላይ የማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት ህብረት ሥራ ዩኒየን ሊኖር አይችልም፡፡
4. የማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት ህብረት ሥራ ፌደሬሽኖች የክልል ወሰንን ተከትለው የሚደራጁ ሲሆን በክልል ውስጥ በተመሳሳይ ተግባር ከአንድ በላይ ሊኖር አይችልም፡፡
5. እንደአስፈላጊነቱ በአገር ደረጃ አንድ የማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት ህብረት ሥራ ፌደሬሽን ሊደራጅ ይችላል፡፡
6. የማኅበሩ መመስረቻና መተዳደሪያ ደንብ ተፋሰሱን በባለቤትነት ይዘው እንዴት እንደሚያለሙት ፣ እንደሚያስተዳድሩት፣ እንደሚጠብቁትና እንደሚጠቀሙበት በዝርዝር የሚደነግግ ሆኖ ተጠቃሚ ማህበረሰቡ የመከረበትና ስምምነት ላይ የደረሰበት መሆን አለበት።
7. የማህበረሰብ ተፋሰስ ተጠቃሚዎች ህብረት ሥራ ማኅበር አስፈላጊ መመዘኛ መስፈርቶችን አሟልቶ በመቅረብ በህብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ መሥረት አግባብ ካለው ባለሥልጣን ሕጋዊ ሰውነት ያገኛል።
8. ከተፋሰሱ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብት ውጤቶች እንደ ሣር፣ ደን እና የደን ውጤቶች ወይም መሰል የተፈጥሮ ሀብት ውጤቶች በዓይነትም ሆነ በገንዘብ ተሸጠው ከተገኘው ገንዘብ ላይ የሚከፋፈልና ለተፋሰሱ ልማት ዓላማ በማኅበሩ ስም በሚከፈት የባንክ ሂሳብ ተቀማጭ የሚሆነው የገንዘብ መጠን በማኅበሩ የውስጥ ደንብ ይወሰናል።

11. <u>**ስለተፋሰስ ተጠቃሚዎች ማህበር አባላት**</u>

ከሚከተሉት መስፈርቶች አንዱን የሚያሟሉ ኢትዮጵያውያን በዚህ አዋጅ መሠረት የተፋሰስ ተጠቃሚዎች ህብረት ሥራ ማህበር አባል ለመሆን መብት አላቸው፦

1. በተፋሰሱ ክልል ውስጥ የመሬት ይዞታ ያላቸውና ከዚሁ በሚገኝ ገቢ የሚተዳደሩ፣
2. በተፋሰሱ ክልል ውስጥ የመሬት ይዞታ ባይኖራቸውም በዙሪያው ነዋሪዎች ከመሆናቸው የተነሣ ከተፈጥሮ ሀብቱ ተጠቃሚዎች የሆኑ ወገኖች፣
3. ኗሪነታቸው በተፋሰሱ ክልል ውስጥ ባይሆንም መሬት ተከራይተውም ሆነ በሌላ ህጋዊ መንገድ ከተፋሰሱ ጋር ግንኙነት ያላቸው ሰዎች።
4. በህብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ የተደነገገው ቢኖርም በማህበረሰብ ተፋሰስ በተፋሰስ ክልሉ ውስጥ የመሬት ይዞታ ያላቸውና ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ሰዎች  በሞግዚቶቻቸው አማካኝነት በአባልነት ሊመዘገቡ ይችላሉ።
5. በዚህ አንቀጽ የተደነገጉትን መስፈርቶች አሟልተው የተገኙ ልዩ ትኩረት የሚያሻቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች የህብረት ሥራ ማህበሩ አባል የመሆንና ማኅበሩ የሚያስገኛቸውን ጥቅሞች ተካፋይ የመሆን ሙሉ መብት አላቸው።

12.<u>**ስለማህበረሰብ ተፋሰስ ተጠቃሚዎች ማኅበር የክብር አባላት**</u>

1. የተፋሰስ ተጠቃሚዎች ማኅበር ለዓላማው ተፈፃሚነት የሚያግዙ ሆነው በተፋሰሱ አካባቢ የሚንቀሳቀሱ ነገር ግን የተፋሰሱ ቀጥተኛ ተጠቃሚ ያልሆኑትን ግለሰቦች፣ ድርጅቶች ወይም ተቋማት በክብር አባልነት ሊቀበል ይችላል።
2. የክብር አባላት በተፋሰሱ ተጠቃሚዎች ማኅበር ውስጥ የመምረጥም ሆነ የመመረጥ ወይም በማናቸውም ጉዳይ ድምፅ የመስጠት መብት አይኖራቸውም።

13.<u>**የክብር አባላት ሚና እና ኃላፊነት**</u>

1. የክብር አባላቱ በራሳቸው ተነሳሽነት ወይም በማኅበሩ ሥራ አስፈጻሚ ጥያቄ ስለተፈጥሮ ሀብቱ ልማትና ጥበቃ ትምህርትና ምክር ይለግሳሉ፣ እንደዚሁም የቴክኒክ፣ የዓይነትና የገንዘብ ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡
2. የክብር አባላቱ በተፋሰሱ ሥራ አመራር ኮሚቴ በሚቀርብላቸው ጥሪ መሠረት በጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባዎች እንዲሳተፉ በማድረግ ሀሳብ ይሰጣሉ፡፡

## 14.የማህበረሰብ ተፋሰስ ተጠቃሚዎች ህብረት ሥራ ማኅበር አባላት መብት

በህብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የተፋሰስ ተጠቃሚዎች ህብረት ሥራ ማህበር አባል የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል ፡-

1. የዚህ አዋጅ አንቀፅ 23 እና 24 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በማህበረሰብ ተፋሰስ ውሰጥ የሚገኙትን የተፈጥሮ ሀብቶች በጋራ ወይም በግል የመጠቀም፤
2. በማህበሩ ሥር አባላት እንደሙያቸውም ሆነ ፍላጎታቸው የተጠቃሚዎች ቡድን በመፍጠር ተፋሰሱን በማይጎዳ ሁኔታ ገቢ በሚያስገኙ ሥራዎች ላይ የመሰማራት፤
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) መሠረት ገቢ የሚያስገኙ ሥራዎች እንደ ንብ ማነብ፣ ወተትና የወተት ተዋፅኦ ማቀነባበር እና ማቅረብ፣ እንስሳት ማድለብ፣ እንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶች ማምረት እና ማቅረብ፣ አትክልት እና ፍራፍሬ ማምረትና ማቅረብ እንዲሁም አንደ መኖ ልማት ያሉ የተፋሰስ ልማቱን የማይጎዱ ሥራዎችን ያጠቃልላል፤
4. የማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት፣ጥበቃና አጠቃቀም ላይ የግንዛቤ ዕውቀት በሚያስጨብጡ መድረኮች የመሳተፍ፡፡

## 15.የማህበሩ አባል ያልሆኑ የማህበረሰብ ተፋሰሱ ተጠቃሚዎች መብቶች

1. በማህበረሰብ ተፋሰሱ ውስጥ በግል ወይም በማህበረሰቡ ወይም በህጋዊ አካል በተረጋገጠ የወል ይዞታ ላይ የሚገኙትን የተፈጥሮ ሀብቶች የመጠቀም፤
2. አባል ለመሆን የሚያሰፈልጉ መስፈርቶችን ካሟሉ በማንኛውም ጊዜ የማህበረሰብ ተፋሰስ ተጠቃሚዎች ህብረት ሥራ ማህበር አባል የመሆን፤
3. የማህበረሰብ ተፋሰስን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም በሚመለከት ግንዛቤና ዕውቀት በሚያስጨብጡ መድረኮች ላይ የመሳተፍ፤
4. ማህበሩ ከተፋሰሱ ልማት ጋር በተያያዘ በሚያከናውኗቸው ተግባራት ምክንያት በግል ይዞታ ላይ ከሚከሰት ጉዳት የመጠበቅ፡፡

## 16.የማህበረሰብ ተጠቃሚዎች ህብረት ሥራ ማኅበር አባላት ግዴታዎች

የማህበረሰብ ተፋሰስ ተጠቃሚዎች ህብረት ሥራ ማኅበር አባል የሆነ ማንኛውም ሰው በህብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ የተደነገጉ ግዴታዎች እንደአግባብነታቸው መፈፀማቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፡-

1. በተፋሰሱ ውስጥ በሚካሄድ የተፈጥሮ ሀብት ልማት ላይ የመሳተፍ፣

2. በተፋሰሱ ክልል ያሉትን ተፈጥሯዊና በልማት የተገኙ ሀብቶች ከውድመት የመጠበቅና የመከላከል፣
3. በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት የሚወሰን የአባልነት ክፍያ የመክፈል፣
4. በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት በግል፣ በቡድንና በአጠቃላይ በሚከናወኑ የውይይት፣ የዕቅድ ዝግጅት፣ የጥበቃና የልማት ተግባራት ላይ የኑሮ ሁኔታቸውን በማይጎዳ መልኩ የጉልበት አስተዋጽኦ ማድረግን ጨምሮ በንቃት የመሳተፍ፣
5. ጥገና የሚያስፈልጋቸውን ልዩ ልዩ የተፈጥሮ ሀብት ልማት መሠረተ ልማቶች፣ ተጠግነው የዘወትር ጥቅም መስጠታቸውን እንዲቀጥሉ ማኅበሩ በሚያወጣው ፕሮግራም መሠረት በጥገና ሥራ ላይ የመሰማራት።
6. አባል ባልሆኑ የግል ባለይዞታዎች መሬት ላይ ጉዳት ሊያስከትሉ የሚችሉ ተግባራት አለማከናወን፡፡

17.<u>የማህበሩ አባል ያልሆኑ የማህበረሰብ ተፋሰሱ ተጠቃሚዎች ግዴታዎች</u>

1. በወል ይዞታ ላይ ተጠቃሚ ለመሆን የልማትና የጥበቃ ተግባር ላይ ከማህበር አባላት እኩል ተሳትፎ የማድረግ፤
2. የማህበረሰብ ተፋሰስን ሊጎዱ የሚችሉ ተግባራትን ከመፈፀም መቆጠብ፤
3. በግል ይዞታቸው ላይ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶች አጠቃቀም የተፋሰሱን ደህንነት የሚጎዱና የተፈጥሮ ሀብት መራቆትን የሚያስከትሉ እንዳይሆኑ ጥንቃቄ ማድረግ፤ በተፋሰሱና በአካባቢው በሚገኝ የደን ሀብት ላይ እሳትና መሰል አደጋ በሚከሰት ጊዜ ማህበሩ ለሚያደርገው የልማትና የጥበቃ እንቅስቃሴ የመተባበር ግዴታ ይኖርባቸዋል፡፡

18.<u>ከአባልነት ስለመሰናበት</u>

የማህበረሰብ ተፋሰስ አባል የሆነ ሰው በህብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ አዋጅ አንቀፅ 11 የተዘረዘሩትን መስፈርቶች በጊዜ ሂደት ሳያሟላ ቀርቶ ሲገኝ ከአባልነት ይሰናበታል፡፡

19.<u>የማኅበሩ አደረጃጀት</u>

ማኅበሩ ከዚህ በታች የተገለፀው አደረጃጀት ይኖረዋል፦

1. የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባዔ፣
2. የሥራ አመራር፣
3. እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች ንዑሳን ኮሚቴዎች።

20.<u>ማኅበሩ ከሌሎች አካላት ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት</u>

1. ከቀበሌ አስተዳደሩ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት በመፍጠር አስፈላጊውን ድጋፍ ማግኘት ይችላል።
2. በአካባቢው ከሚንቀሳቀሱም ሆነ ከሌሎች መንግሥታዊ ወይም መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ወይም ማኅበራት ጋር የማኅበሩን ዓላማ እውን ለማድረግ የሚያግዙ ስምምነቶችን ሊያደርግ ይችላል።
3. አንድን ውስን ሥራ በክፍያ ወይም ያለክፍያ ለማከናወን ከተለያዩ አካላት ጋር ሊዋዋል ይችላል፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>የማህበረሰብ ተፋሰስ ጥበቃ፣አስተዳደርና አጠቃቀም</u>

21.<u>የተፋሰስ ልማት ሥራዎች አጠባበቅ፣ አስተዳደርና አጠቃቀም</u>

1. የገጠር መሬት ባለይዞታ መብቶችና ግዴታዎችን አስመልክቶ የሌሎች ሕጎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም በተፋሰስ ውስጥ የሚገኝ የግል ወይም የወል ባለይዞታ እንደ መሬቱ ተፈጥሯዊ አቀማመጥ የአፈርና ውኃ መጠበቂያ ሥራዎችን በመሥራትና በመንከባከብ እንዲሁም በመጠገን የአፈር ክለትን በመከላከል የአፈርን ለምነት የመጠበቅ ግዴታ አለበት።
2. ማንኛውም የግል ወይም የወል ባለይዞታ፡-

ሀ) በተፋሰሱ ውስጥ በተሠሩ የልማት ሥራዎች ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ልቅ የእንስሳት ስምሪትን የመቆጣጠርና የመጠበቅ ኃላፊነት አለበት፤

ለ) በተፋሰሱ ውስጥ በሚገኙት የመሬት ይዞታዎቹ ዳር ድንበር፣ በማሳው ውስጥና በመንገዶች ዳር የደን፣ የመኖ ዛፎችንና አልሚ የእፅዋት ዝርያዎችን በመትከል፣ በመንከባከብና በመጠበቅ የአካባቢውን ለምነትና ጤንነት የመጠበቅ ግዴታ አለበት፤

ሐ) በተፋሰሱ ውስጥ በሚገኙ የይዞታ መሬቶቹ አካባቢ ወንዞች፣ ሐይቆች ምንጮች፣ ቦረቦር ስፍራዎችና ውኃ አዘል መሬቶች ያሉ እንደሆነ እነዚሁ በአጠቃቀምና በአያያዝ ጉድለት ጉዳት እንዳይደርስባቸው እንደ አካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል በሚያወጣው ሕግ መሠረት በቂ የመከላከያ ርቀት የመተው ግዴታ አለበት፤

መ) በተፋሰሱ ውስጥ በሚገኘው ይዞታው ላይ የሚፈጠር ትርፍ የጎርፍ ውኃ ቢያጋጥም ይኸው በሌሎች አጎራባች ማሳዎች ላይ ጉዳት እንዳያስከትል፣ ከሌሎች የሚመጣውንም በማቀባበል ወደ ሰው ሠራሽ ወይም የተፈጥሮ መፋሰሻ ቦዮች እንዲፋሰስ የማድረግ ግዴታ አለበት፤

ሠ) በተፋሰሱ ክልል ውስጥ የሚገኝ ባለይዞታ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) (መ) የተጣለውን ግዴታ ለመወጣት ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ያጋጠመው እንደሆነ ይህንኑ ለሚመለከተው የተፈጥሮ ሃብት ተቋምና ለማህበሩ ማሳወቅ አለበት፤

ረ) በተፋሰሱ ውስጥ በሚገኘው የይዞታ መሬቱ ውስጥ ወይም ዳር ድንበሮች ላይ ያለማቸው ወይም የሚያለማቸው የደንና የእፀዋት ዝርያዎች በጥላቸውና በጠፈጠፋቸው ምክንያት የተጎራባቹን ባለይዞታ የሰብል ምርትና ሌሎች መብቶች የሚጎዳ መሆን የለበትም፣

ሰ) በተፋሰሱ ውስጥ በሚመለከተው አካል የፀደቀ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ በሚኖርበት ጊዜ መሬቱን በዕቅዱ መሠረት የማልማትና የመንከባከብ ግዴታ አለበት፤

ሸ) በተፋሰሱ ውስጥ የእሳት ቃጠሎ እንዳይነሳ አስፈላጊውን የጥንቃቄ እርምጃ የመውሰድ ግዴታ አለበት፤

ቀ) ሰብሉን ለመጠበቅ ከሚያከናውኗቸው ተግባራት በስተቀር በማህበረሰብ ተፋሰሱ ውስጥ በሚገኙ ማሳዎቹና በአካባቢው የሚገኙ የዱር እንስሳትና አዕዋፋት አካባቢውን ለቅቀው እንዳይሰደዱ ጥንቃቄ የማድረግ ግዴታ አለበት፣

በ) በተፋሰሱ ውስጥ በሚገኙ የይዞታ መሬቶቹ ውስጥ ተክሎና ተንከባክቦ ያሳደጋቸውን የደን ዛፎች፣ የመኖና አልሚ የእፅዋት ዝርያዎች አጠቃቀምን በተመለከተ በደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ህግና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ህጎች መሰረት ተግባራዊ መደረግ አለበት።

22. **ስለ እንጨት፣ እንጨት ያልሆኑ የደን ውጤቶች እና ሣር አጠቃቀም**

1. በተፋሰሱ ክልል ውስጥ በግል ወይም በወል ይዞታዎች ላይ የመጠቀም መብት ያላቸው ሰዎች በእነዚህ ይዞታዎች ላይ ያለሙትን ወይም የተተከሉትን ደረቅ እንጨት፣ ዛፍ፣ቁጥቋጦ፣ ሣር እና እንጨት ያልሆኑ የደን ውጤቶች የመጠቀም መብት አላቸው፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተጠቀሱት ባለይዞታዎች ውጭ በተፋሰስ ክልል ውስጥ የሚገኝ ማናቸውም ደረቅ እንጨት፣ ዛፍ፣ ቁጥቋጦ፣ እንጨት ያልሆነ የደን ውጤት ወይም ሣር የማኅበሩ አባላት የጋራ ንብረት ስለሆነ፣ በማኅበሩ ውስጠ ደንብ መሥረት ማኅበሩ ቆርጦ፣ አጭዶና ሰብስቦ መጠቀም ይችላል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተጠቀሱት ሀብቶች አጠቃቀም አቅርቦቱን ዘላቂነት ባለው መንገድ ለመጠበቅ በሚያስችል አግባብ መፈፀም ይኖርበታል።

23.<u>በተፋሰሱ ክልል ውስጥ ስለሚገኝ ድንጋይና አሸዋ አጠቃቀም</u>

በማዕድን ሥራዎች አዋጅ መሠረት ቀድሞ ማዕድን በማምረት ሥራ ላይ የተሰማሩ አካላት መብትና ግዴታ እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 25(1) በተጠቀሱት ይዞታዎች ላይ የሚገኙት አሸዋ እና ድንጋይ የመጠበቅ እና የመጠቀም ኃላፊነት እና መብት አግባብነት ባለው የማዕድን ሥራዎች ህግ መሰረት የባለይዞታዎች ይሆናል፤
2. በተፋሰሱ ክልል ውስጥ በታቀፈና የወል ወይም የመንግሥት ይዞታ በሆነ ሥፍራ ላይ የሚገኝ ድንጋይና አሸዋ አግባብነት ባለው የማዕድን ሥራዎች ህግ መሠረት ድንጋይና አሸዋውን ለተፋሰሱ ልማት ሊጠቀሙበት ይችላሉ፤
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ድንጋጌዎች ቢኖሩም የድንጋይና አሸዋ አቅርቦቱን ዘለቄታዊ በሆነ መንገድ ለመጠቀምና ለመጠበቅ እንዲቻል የአፈር ክለትና የአካባቢ መጎዳት እንዳያስከትል ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል።

24.<u>በማህበረሰብ ተፋሰሱ ክልል ውስጥ ስለሚገኝ የውሃ ሀብት አጠቃቀም</u>

በማህበረሰብ ተፋሰስ ክልል ውስጥ የሚገኘውን የውሃ ሃብት አጠቃቀም አግባብነት ያለው የውሃ ሃብት አስተዳደር ህግ በሚፈቅደው መሠረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡

25.<u>ስለ ሥርዓተ ምሕዳር አገልግሎት ክፍያ</u>

1. የማህበረሰብ ተፋሰሱ ምክንያት ተጠቃሚ የሆኑ አካላት ለማህበረሰቡ የተፋሰስ ልማት የሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎት ክፍያ የመክፈል ግዴታ አለባቸው።
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ድንጋጌ መሠረት የሚከፈል ከውሃ ጋር የተያያዘ የሥርዓት ምህዳር አገልግሎት ክፍያ በውሃ ሀብት አስተዳደር ሕግ መሠረት የሚፈፀም ይሆናል፡፡

26. <u>የሥርዓት ምሕዳር ጉዳት ካሣ</u>

በመሠረተ ልማት ግንባታ ወይም በሌላ ምክንያት በማንኛውም ሁኔታ በተፋሰሱ ወይም በተፋሰስ ተጠቃሚዎች ላይ ጉዳት ያደረሱ አካላት ላደረሱት ጉዳት አግባብነት ባለው ህግ መሰረት ተመጣጣኝ ካሣ መክፈልና አካባቢውን ተመጣጣኝ ወደሆነ ሥነ-ምህዳር የመመለስ ግዴታ አለባቸው።

## ክፍል አምስት

## የተፋሰስ ማኅበረሰቡን የሚመለከቱ ሌሎች ጉዳዮች

27.<u>የተጠናቀቁ የተፋሰስ ሥራዎች ርክክብ</u>

1. ማንኛውም የግል ወይም የወል ባለይዞታ በራሱ፣ በኅብረተሰቡ፣ በማኅበሩ ወይም ሥራውን አጠናቅቀው በሚያስረክቡ መንግሥታዊ ወይም መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የተከናወኑትን የተፋሰስ ልማት ሥራዎች ቆጥሮ መረከብ አለበት።
2. ርክክብ ሲካሄድ የተሠሩ የልማት ሥራዎች ጥራታቸው የተጠበቀ ስለመሆኑ የሚመለከተው የወረዳ ተቋም ማረጋገጥ አለበት።

28. <u>ስለማበረታቻ</u>

1. በተፋሰሱ ክልል ውስጥ በግልም ሆነ በወል የተሠሩ የአፈርና ውኃ ልማትና ጥበቃ ሥራዎችን እየጠገነ በአግባቡ በመንከባከብ በተፋሰስ ውስጥ የላቀ ውጤት ላስመዘገበ ባለይዞታ የዕውቅና እና ማበረታቻ ሽልማት የሚሰጥበትን ሥርዓት ወረዳው ይዘረጋል።
2. በወረዳው ውስጥ ካሉት ማኅበራት የተሻለ የተፋሰስ ልማት ሥራ ላከናወነ ማኅበር ወረዳው የዕውቅናና ማበረታቻ ሽልማት የሚሰጥበትን ሥርዓት ይዘረጋል።

29.<u>ስለ ሥርዓተ-ፆታ እና ልዩ ትኩረት የሚሹ የኅብረተሰብ ክፍሎች</u>

1. በማናቸውም የተፋሰስ አስተዳደርና አጠቃቀም ሂደት ሚዛናዊ የፆታ ስብጥር መኖር አለበት።
2. ሴቶችና ልዩ ትኩረት የሚሹ የኅብረተሰ ክፍሎች ጥቅም በሚያስገኙ በማናቸውም የተፋሰሱ ልማት ተግባራት ሁሉ አቅማቸውና ሙያቸው በሚፈቅደው መጠን እኩል የመሣተፍ እና ተጠቃሚ የመሆን መብት ይሰጣቸዋል።

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 30.የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ኃላፊነት

1. አግባብነት ያላቸውን ተቋማት በማስተባበርና አስፈላጊውን የሙያ ድጋፍ በመስጠት ይህንን አዋጅ የማስፈጸም ኃላፊነት አለበት።
2. በክልሎችና በፌደራል መካከል የተፋሰስ ልማት አስተዳደርና አጠቃቀም የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል።

### 31.የክልሎች ኃላፊነት

1. ክልሎች ይህንን አዋጅና ሌሎች ከተፋሰስ አስተዳደርና አጠቃቀም እንዲሁም ከማኅበራት አመሠራረትና አደረጃጀት ጋር ግንኙነት ባላቸው ሕጎች ላይ. ግንዛቤ የመፍጠርና ማኅበራት እንዲመሠረቱ የመቀስቀስና ሕጎቹን የማስፈፀም ኃላፊነት አለባቸው።
2. ይህንን አዋጅና አዋጁን ለማስፈፀም የሚወጣውን ደንብ ተከትለው ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ ያወጣሉ።

### 32.የግብርና ጽ)ቤት ተግባርና ኃላፊነት

የግብርና ጽ)ቤት ከማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት ጥበቃና አስተዳደር አኳያ ከዚህ በታች የተጠቀሱት ተግባርና ኃላፊነቶች አሉት፡-

1. የማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት ዕቅድ ዝግጅትን ይደግፋል ፤ የተዘጋጁትንም መርምሮ ያጸድቃል፡፡
2. የተፋሰስ ልማት፣ አስተዳደርና አጠቃቀምን ያስተባብራል፣ ይመራል፣ ይከታተላል፤
3. የማህበረሰብ ተፋሰስ ማህበር አባላት የተጠቃሚዎች ቡድን በመመስረት ገቢ በሚያስገኙ ስራዎች ላይ እንዲሰማሩ ይደግፋል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡
4. የዋና ተፋሰስ እና የማህበረሰብ ተፋሰስን ስፋት እንደ አካባቢው መልክዓ-ምድራዊ አቀማመጥ መሰረት በማድረግ ይወስናል፡፡
5. ከሚመለከተው የህብረት ሥራ ማህበር አደራጅ መስሪያ ቤት ጋር በመተባበር የማህበረሰብ ተፋሰስ ተጠቃሚዎች ህብረት ሥራ ማህበራት መሥራች ኮሚቴ እንዲደራጅ ያደርጋል፡፡

**33.የህብረት ሥራ ኤጀንሲ ተግባርና ኃላፊነት**

ህብረት ሥራ ማህበራትን ለማደራጀት ስልጣን የተሰጠው አካል ተግባርና ኃላፊነት በህብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ በተቀመጠው መሠረት ይሆናል፡፡

**34.ስለጥፋቶችና ቅጣት**

1. ከዚህ አዋጅ አተገባበር ጋር በተያያዘ ለሚፈፀሙ ወንጀሎች በወንጀል ሕጉና በሌሎች ሕጎች የተደነገጉ ቅጣቶች ተፈጻሚ ይሆናሉ።
2. በዚህ አዋጅ ውስጥ የተደነገጉ ግዴታዎችን አለመወጣት የሚያስከትሉትን አስተዳደራዊ ቅጣት ዝርዝር አዋጁን ለማስፈጸም በሚወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

**35.የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

1. ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት የተቋቋሙ የማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት ህብረት ሥራ ማህበራት ይህ አዋጅ በፀደቀ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በዚህ አዋጅ መሠረት አስፈላጊውን ማስተካከያ በማድረግ የማህበረሰብ ተፋሰስ ህብረት ሥራ ማህበር ሆነው መመዝገብ አለባቸው፡፡
2. ቀደም ሲል በነበረው አሠራር የተቋቋመ የተፋሰስ ኮሚቴ የዚህን አዋጅ መውጣት ተከትሎ በሚቋቋመው ህብረት ሥራ ማኅበር ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እስከሚተካ ድረስ ተቀባይነት ይኖረዋል።

**36.ደንብ የማውጣት ሥልጣን**

ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ያወጣል፡፡

**37. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች**

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም አዋጅ፣ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ አዋጅ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

**38.አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ነሐሴ 19 ቀን 2012 ዓ.ም**

**ሳሕለወርቅ ዘውዴ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ**

**ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## አዋጅ ቁጥር 1025/2009

## ስለጨረራና ኒውክለር መከላከያ የወጣ አዋጅ

በሀገራችን የጨረራና የኒውክለር ቴክኖሎጂን የመጠቀም ባህል ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመምጣቱና አግባብ ያለውና ውጤታማ የመከላከል ዘዴ በሥራ ላይ እስካልዋለ ድረስ ጨረራ በጤና፣ በንብረትና በአካባቢ ላይ ሊያስከትል የሚችለው ተጓዳኝ ጠንቅ እየጨመረ የሚሄድ በመሆኑ፤

ቁጥጥርሊደረግባቸው የሚገቡ የጨረራ አመንጪዎችና ኒውክለር እና ተያያዥነት ያላቸው ተግባራት ለሕብረተሰቡ ጥቅም አገልግሎት ላይ ሲውሉ በግለሰቦች፣ በሕብረተሰቡ፣ በንብረትና በአካባቢ በአሁኑና በወደፊቱ ትውልድ ጭምር ሊያደርሱ የሚችሉትን ተጓዳኝ የጨረራ ጠንቅ መከላከል በማስፈለጉ፤

ከጨረራ አመንጪና ኒውክለር ቁሶች አጠቃቀም ጋር በተያያዘ የሚመለከታቸው አካላት ግዴታቸውን በግልጽዕ እንዲያውቁ ለማድረግና ሕግን በመተላለፍ ለሚደርስ የጨረራ ጉዳት ተመጣጣኝ የሆነ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችሉ ሕጎችን በመደንገግ ከዓለም አቀፍ ስርዓቱ ጋር የተጣጣመ የጨረራ መከላከሉን ስራ ማጠናከር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግስት አንቀጽ 55 (1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የጨረራና ኒውክለር መከላከያ አዋጅ ቁጥር 1025/2009" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

   1. "አደጋ" ማለት ከጨረራ አመንጪዎች ወይም ከኒዩክለር ቁሶች ጋር የተያያዘ ከደህንነት አንጻር የቅርብ ወይም የሩቅ ጊዜ ዉጤቱ ቀላል ሊባል የማይችል የአሠራር ስህተት፣ የመሣሪያዎች ብልሽት ወይም በማጓጓዝ ላይ በሚደርስ ችግር

ወይም ሌሎች ችግሮችን የሚያካትት ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ያልታሰበ ክስተት ነው፤

2. “ተግባራት” ማለት የጨረራ አመንጪዎችን ለኢንዱስትሪ፣ ለምርምር እና ለህክምና አገልግሎቶች ማምረትን፣ መጠቀምን፣ ወደሀገር ውስጥ ማስገባትን፣ ከሀገር ውጪ መላክን፤ የራድዮአክቲቭ ቁሶችን ማጓጓዝን፤ የኒውክለር ፋሲሊቲ ቦታ ግንባታዎችን፣ አገልግሎት ማስጀመር፣አገልግሎት መስጠትን፣ አገልግሎት ማቋረጥ፤ የራድዮአክቲቭ ዝቃጭ አስተዳደር፣ የቦታዎች ማገገም ተግባራት፣ ለሰላማዊ አገልግሎቶች ብቻ ማዋልን የሚያመለክት ሲሆን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5(2 የተጠቀሱትን ተግባራቶች ይጨምራል፤
3. “አቶሚክ ኢነርጂ” ማለት ከራድዮ አይሶቶፖች፣ ከኒውክለር ሪአክሽን፣ ከኒውክለር ማብላያ፣ ከኤክስሬይ መሳሪያዎችና ከሌሎችም አዮን ፈጣሪ ጨረራ አመንጪዎች የሚገኝ ኢነርጂ ነው፤
4. “ባለስልጣን” ማለት የኢትዮጵያ ጨረራ መከላከያ ባለሥልጣን ነው፤ ተጠሪነቱም ለሳይንስና ቴክኒዮሎጂ ሚኒስቴር ይሆናል
5. “የሥራ ፈቃድ” ማለት ኦፕሬተሩ ለሚያከናውናቸው ውስን ተግባራት ባለስልጣኑ በጽሁፍ የሚሰጠው ፈቃድ ሲሆን የምስክር ወረቀት ወይም ምዝገባንም ሊጨምር ይችላል፤
6. “አገልግሎት ማቋረጥ” ማለት በባለስልጣኑ ቁጥጥር መስፈርት መሰረት ማስወገድን ሳይጨምር አንድ ማዕከል የሚሰጠውን አገልግሎት ማቋረጥ ሲሆን የአገልግሎት ማቋረጥን ሂደት እና መነቃቀልን ይጨምራል፤
7. “መልቀቅ” ማለት በባለስልጣኑ በተወሰነ ፈቃድ መሰረት የራድዮአክቲቭ ቁሶችን መደበኛ የሆነ ስራቸውን በሚከውኑበት ጊዜ ዕቅድና ቁጥጥር በማድረግ፣ በሕጋዊ አሰራር ጠጣር፣ ፈሳሽ፣ ወይም ጋዝ የሆኑ የራድዮአክቲቭ ቁሶችን ወደ አካባቢ መልቀቅ ነው፤
8. “ማስወገድ” ማለት በድጋሚ አገልግሎት ላይ ሊውሉ እንደማይችሉ ታሳቢ ተደርጎ አገልግሎታቸውን የጨረሱ የኒውክለር ነዳጆች ወይም የራድዮአክቲቭ ዝቃጮችን በተገቢው ማዕከል ውስጥ ማስወገድ ነው፤
9. “የውሰድ መጠን” ማለት ቁጥጥር በሚደረግበት ድርጊት ለእያንዳንዱ ሰው ከሚፈለገው ወጤታማ የጨረር መጠን መብለጥ የለበትም፤

10."የኒውክለር ወይም የጨረራ ድንገተኛ አደጋ" ማለት በኒውክለር ተከታታይ መፈነጣጠር ወይም በሂደቱ በሚፈጠር ኢነርጂ ሳቢያ ወይም በጨረራ መጋለጥ የተከሰተ ወይም ሊከሰት የሚችል ድንገተኛ አደጋ ነው፤

11."ከግዴታ ውጭ" ማለት ቁጥጥር ለማድረግ የማይቻል በመሆኑ በዚህ አዋጅ የተፈፃሚነት ወሰን መሰረት ከግዴታ ውጪ እንዲሆኑ በጥንቃቄ ተለይተው የተመደቡ የመጋለጥ ዓይነት ላይ የተመለከቱ ተግባራት ናቸው፤

12."ከቁጥጥር ነፃ" ማለት ከጨረራ አመንጪው ወይም ከተግባሩ የሚጠበቀው መጋለጥ በጣም አነስተኛ በመሆኑ ምክንያት በተወሰነ ደረጃ ወይም ሙሉ በሙሉ የገደብና የማስተካከያ ቁጥጥር የማይደረግበት ተብሎ በባለስልጣኑ የተመደበ ተግባር ወይም የጨረራ አመንጪ ነው፤

13."ማዕከላት" ማለት የኤክስሬይ መሣሪያዎች፣ ማጭረሪያዎች፣ የሚተከሉባቸው፣ ዩራኒየምና ሌሎች ጨረራ አመንጪ የሆኑ ማዕድናት የሚወጣባቸውና የሚቀነባበርባቸው፣ ራዲዮ አክቲቭ ዝቃጭ አስተዳደር የሚከናወንባቸው ማዕከላት፣ ወይም ሌሎች ማናቸውም ጥበቃ፣ ጥንቃቄና ደህንነት ቁጥጥር የሚሹ በባለስልጣኑ የሚወሰኑ የራዲዮአክቲቭ ቁሶች የሚመረትባቸው፣ የሚቀነባበርባቸው፣ ጥቅም ላይ የሚውልባቸው፣ የሚያዝባቸው፣ የሚከማችባቸው ወይም የሚወገድባቸው ቦታዎች ናቸው፤

14."ኢንስፔክተር" ማለት ባለፈቃዶች ይህን አዋጅ እና በአዋጁ መሰረት የወጡ ደንቦች እና መመሪያዎችን አክብረው መስራታቸውን የሚቆጣጠር እና የሚያስፈጽም በባለስልጣኑ የሚመደብ ሠራተኛ ነው፤

15."ጣልቃገብነት" ማለት የቁጥጥር ተግባራት አካል ያልሆኑ ወይም ከቁጥጥር ተግባራት ሽፋን ወሰን ውጪ የሆኑ መጋለጦችን ለመቀነስ ወይም ከአቅም በላይ በሆኑ ቁጥጥር በሚደረግባቸው መሰል ጨረራ አመንጪዎች ተግባራት የአደጋ መዘዞችን ወይም ለአደጋ መዘዝ ተጋላጭነትን ለመቀልበስ ሲባል ታስቦበት የሚወሰድ እርምጃ ነው፤

16."ባለፍቃድ" ማለት አንድን ተግባር ወይም ድርጊትን ለማከናወን በባለስልጣኑ የተሰጠ የፀና ምስክር ወረቀት የያዘ ሰው ነው፤

17."ማሳወቂያ"ማለት ተግባራትን ለማከናወን ወይም ማንኛውንም የጨረራ አመንጪዎች ለመጠቀም ያቀደሰውለባለስልጣኑ ለማሳወቅ የሚያቀርበው ሰነድ ነው፤

18."የኒውክለር ቁስ" ማለትየኘሉቶኒየም 239 አይሶቶፕን መጠኑ ከ80 በመቶ በላይ ካልያዘ በስተቀር፣ የዩራኒየም 233፣ 235 ወይም 233 አይሰቶፖች የበለጸገ ዩራኒየም፣የዩራኒየም ማዕድንን ወይም የዚህኑ ዝቃጭ ሳይጨምር ተፈጥሯዊ የሆኑ የዩራኒየም አይሶቶፖች ድብልቅ ወይም በዚህ ከተጠቀሱት አንዱን ወይም ከዚህ በላይ የያዘ ቁስ ነው፤

19."ኒውክለር ሴፍጋርድ" ማለት የኒውክለር ቁስ የሆነ ፑሉቶኒየም፣ ዩራኒየም፣ እና ቶሪዬም፤ የኒውክለር ቁስ ያልሆኑ ደረጃ ግራፋይት፣ በሃድሮጅን የበለፀገ ውሃ እና በኒውክለር ነዳጅ ሳይክል ተግባር እና ለሌላ ቴክኖሎጂ የሚጠቅሙ አገልግሎት ላይ የሚውሉ መሣሪያዎች ወደ ኢትዮጵያ ግዛት ማስገባት ወይም ማስወጣት እና ጥቅም ላይ ማዋል ቁጥጥር የሚደረግበት ነው፤

20."የኒውክለር ወይም የራዲዮሎጂካል ድንገተኛ አደጋ ዕቅድ" ማለት የአደጋ ምላሽ ቡድኑን ዓላማ፣ ፖሊሲ፣ የአተገባበር ፅንሰ ሀሳብና የተደራጀ የሥራ መርሀ ግብር የያዘ በድንገተኛ አደጋ ወቅት የሚተገበር፤ አደረጃጀትን፣ ሥልጣንና ኃላፊነትን የሚያመላክት ሥርዓት ባለው ሁኔታ ለማስተባበርና ቀልጣፋ ምላሽ ለመስጠት ብቃት ያለውና የሌሎችን ዕቅድና የአሰራር ሥነ-ሥርዓትን መሠረት ያደረገ ዝርዝር ዕቅድ ነው፤

21.“ኦፕሬተር” ማለት ከኒውክለር ማዕከል ወይም ከጨራራ አመንጪዎች ጋር በተያያዘ ስለኒውክሌር፣ ጨረራ፣ ራዲዮአክቲቭ ዝቃጭን የማስወገድ ወይም በጥንቃቄ የማጓጓዝ ተግባራትን አስመልክቶ ፈቃድ የጠየቀ፣ ወይም ፈቃድ ተሰጥቶት እያከናወነ የሚገኝ ኃላፊነት ያለበት ማንኛውም ሰው ነው፤

22."ባለቤት አልባ ቁስ" ማለት በባለሥልጣኑ ቁጥጥር ሥር ሆኖ የማይታወቅ ወይም የተጣለ፣ የጠፋ፣ የተሰረቀ ወይም ያለፈቃድ ተላልፎ የተሰጠ በመሆኑ ባለሥልጣኑ የሚቆጣጠረው የራዲዮአክቲቭ ቁስ ነው፤

23."አካላዊ መከላከል" ማለት ኒውክለር የተተከለበት፣ የራድዮአክቲቭ ቁስ ወይም የተመረጡ ዕቃዎች ያሉበት ቦታን ካልተፈቀዱ ተግባራት ለመከላከል ሲባል የሚወሰድ የቴክኒክና መዋቅራዊ እርምጃ ነው፤

24."ጨረራ" ማለት ኃይል በቁስ ውስጥ በሚያልፍበት ጊዜ አዮን የመፍጠር ወይም ያለመፍጠር አቅም ነው፤

25."የጨረራ አመንጪ" ማለት ከኒውክሌር ነዳጅ ኡደት እና ከምርምርና የኃይል ማብላያ ውጪ ያሉ ጨረራ አፈንጣቂ ወይም የራዲዮአክቲቭ ምንጭ ወይም ሌላ የራዲዮአክቲቭ ቁስ ነው፤

26."የራዲዮአክቲቭ ቁስ" ማለት በባለስልጣኑ ቁጥጥር የሚደረግበት ማንኛውም ጨረራ አመንጪ ቁስ ነው፤

27."የጨረራ ሰራተኛ" ማለት የጨረራ መከላከል፣ ደህንነት ወይም ጥበቃ እውቀትና ችሎታ ያለው በባለ ሥራ ፈቃዱ የተመደበ ባለሞያ ነው፤

28."ደህንነት" ማለት ሰዎችንና አካባቢን ከጨረራ ጠንቅ ለመከላከል የማዕከላቱን እና የተግባራቱን የጨረራ ስጋትን መቀነስ ነው፤

29."አገልግሎቱን የጨረሰ የኒውክለር ማብላያ ነዳጅ" ማለት በኒውክለር ማብላያ ውስጥ በማጭረር ሂደት ከቆየ በኋላ ከማብላያው እምብርት ውስጥ ጨርሶ የተወገደ የኒውክለር ማብላያ ነዳጅ ነው፤

30."ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም የሕግ ሰውነት ያለው አካል ነው፤

31.በወንድ ጾታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ያካትታል፡፡

3. <u>ዓላማ</u>

ይህ አዋጅ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፦

1. የጨረራና የኒውክለር ቴክኖሎጂን ደህንነት በማረጋገጥ፤ ጥበቃ በማድረግና ለሠላማዊ አገልግሎት እንዲውልና የሀገር ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ቴክኖሎጂ ዕድገትን የሚደግፍበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤
2. ግለሰብን፣ ማህበረሰብንና አካባቢን እንዲሁም የአሁኑን እና የወደፊቱን ትውልድ ጨረራ ከሚያስከትለው ጠንቅ መጠበቅ፤
3. በራዲዮ አክቲቭ ቁሶችና ተዛማጅ ተግባራት ላይ የቁጥጥር ሥራን የሚደግፉ የምርምርና ልማት ሥራዎች እንዲካሄዱና እንዲበረታቱ ማድረግ፡፡

4. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

1. ይህ አዋጅ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ግዛት ውስጥ በተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ የሆኑ የኒውክለርና ሬድዮአክቲቭ ቁሶች ወይም ተዛማጅነት ባላቸው ማናቸውም ተግባራት ወይም ጨረራ በሚያስከትላቸው ስጋቶች ወይም ጉዳቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አዋጅ ከግዴታ እና ከቁጥጥር ነፃ የሆኑ የጨረራ አመንጪዎችና ተግባራት ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለማሳወቅና የፈቃድ አሰጣጥ

5. **ጠቅላላ**

1. ከማንኛውም የጨረራ አመንጪ ተግባር የሚጠበቀው መጋለጥ ከግዴታዎች ውጭ ካልሆነ ወይም ተግባሩ ከቁጥጥር ነፃ ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም ተግባርማሳወቅንና ፈቃድ ማግኘትን ጨምሮ ባለሥልጣኑ ያወጣውን መስፈርት ሳያሟላ አይጀመርም፤ አይተዋወቅም፤ አይከናወንም፤ አይቋረጥም ወይም አይቆምም፡፡
2. ማንኛውም የጨረራ አመንጪ የሚጠበቀው መጋለጥ ከግዴታዎች ውጪ ካልሆነ ወይም ከቁጥጥር ነፃ ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም ሬዲዮአክቲቭ ቁስ ማሳወቅንና ፈቃድ ማግኘትን ጨምሮ ባለሥልጣኑ ያወጣውን መስፈርት ሳያሟላ በማዕድን መልክ አይወጣም ወይም አይፈጭም፣ አይመረትም፣ አይሰራም ወይም አይገጣጠምም፣ አይቀነባበርም፣ በባለቤትነት አይያዝም፣ አይተላለፍም፣ ወደ አገር አይገባም፣ ወደውጭ አይላክም፣ አይከፋፈልም፣ አይሸጥም፣ አይዋስም፣ አይከራይም፣ አይከማችም፣ ጥቅም ላይ አይውልም፣ ሥራ አይቆምም፣ አይጠገንም ወይም አይፈታታም፣ አይጓጓዝም፣ አይወገድም፡፡

6. **ስለማሳወቅ**

1. በዚህ አዋጅ ከተገለፁት በአንዱ ተግባር ለመሰማራት ያቀደ ማንኛውም ሰው ሊያከናውን ስላቀደው ተግባር ወይም ድርጊት ለዚህ ዓላማ የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት በጽሁፍ ለባለሥልጣኑ መግለፅ እና ዝርዝር ዕቅዱን በደንቡ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ለባለስልጣኑ ማሳወቅ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማሳወቅን ብቻ የሚጠይቁ የጨረራ አመንጪዎች ወይም ተግባራት በባለሥልጣኑ ይወሰናሉ።

7. **ፈቃድ ስለማግኘት**

ማንኛውም ሰው ተግባሩ ከቁጥጥር ነፃ ወይም ማሳወቅን ብቻ የሚጠይቅ ካልሆነ በስተቀር ባለሥልጣኑ ያወጣውን መስፈርት አሟልቶ ፈቃድ ካላገኘ በስተቀር በዚህ አዋጅ የተመለከተውን ተግባር ወይም ድርጊት ማከናወን አይችልም፡፡

8. <u>የኒውክለር ማዕከል ስራ ፈቃድ</u>

በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 7 መሰረት ለኒውክለር ማዕከል ሥራ ፈቃድ የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተሉት የደህንነት ጥናት ያካተተ መሆን ይኖርበታል፦

1. የደህንነት ምዘና እና የደህንነት ማረጋገጫ፤
2. የገንዘብ አቅም፤
3. የሥራ አመራር ሥርዓት፤
4. የሰው ሀብት ሁኔታ፤
5. ጨረራ መከላከል፤
6. የድንገተኛ አደጋ ዝግጁነት፤
7. የቦታ መረጣ ሁኔታ፤
8. ዲዛይን፣ ግንባታ እና የሥራ መጀመር፤
9. የሥራ፣ የጥገና፣ የማሻሻያና አጠቃቀም፤
10. የአገልግሎት ጊዜን ስለማራዘም፤
11. አገልግሎት መቋረጥና ይህን ተከትሎ ስላለው ወጪ የገንዘብ ምንጭ፡፡

9. <u>የራዲዮአክቲቭ ቁሶችን በማዕድን መልክ ማውጣትና ማቀነባበር</u>

በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 7 መሠረት ራዲዮአክቲቭን በማዕድን መልክ ለማውጣትና ለማቀነባበር የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተሉትን መያዝ ይኖርበታል፦

1. የከርሰ ምድርና ማዕድን ጥናት ጨምሮ የቦታ መረጣ ባህሪ፤
2. የቦታ መረጣ ወይም የግንባታ ዕቅዶች፤
3. የማዕድን ማውጣትና የማቀነባበሪያ ማዕከላት የዲዛይን ንድፈ ሃሳብ፤
4. የሚከናወኑ ተግባራት፣ የማውጣት ቴክኒክና በሥራ ላይ የሚውሉትን መሣሪያዎች ዓይነት፤
5. ያልተጣራ የራዲዮአክቲቭ ማዕድን የሚጓጓዝበት ሁኔታ፤
6. የሰራተኛው የጨረራ መጋለጥ እና የጨረራ ውስድ መጠን፤
7. ጨረራን ለመከላከል ሊወሰድ የሚችል እርምጃ፤
8. ጨረራ የሚያስከትለውን አደጋ ለመከላከል የተዘጋጀ የሥራ ቅደም ተከተል፤
9. ወደ አካባቢ ሊለቀቅ የሚችለውን የራዲዮአክቲቭ ዝቃጭ ለማስተዳደር የሚያስችል የሥራ ቅደም ተከተልና ዕቅድ፤

10.በድንገት ወደ አካባቢ ሊለቀቅ የሚችል የራዲዮአክቲቭ እና ራዲዮአክቲቭ ያልሆነ ብክለትን ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት ለመግታት የሚያስፈልግ የሥራ ቅደም ተከተል፤

11.በህብረተሰቡና በአካባቢ ላይ ሊያስከትል የሚችለውን የጤናና የደህንነት ተፅዕኖ፤

12.በማዕድን ማውጫ አካባቢ እና በመጋዝን ማዕከላት የሚከማቸውን ጥሬ ምርት እና የዓለት ዝቃጭ ክምችት መጠን፤

13.አገልግሎት የሚቋረጥበትን ዕቅድና ይህን ተከትሎ ስላለው ወጪ የተመደበ ገንዘብና ምንጩ፤

14.የጥበቃ ሁኔታ፡፡

10.<u>ምግብ እና ምግብ ነክ ባልሆኑ ምርቶች ላይ የሚካሄድ የራዲዮአክቲቭ ቁጥጥር</u>

ባለስልጣኑ ምግብ እና ምግብ ነክ ባልሆኑ ምርቶች ላይ የሚካሄደውን የራዲዮአክቲቭ ቁጥጥርን በተመለከተ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመማከር ሥርዓት ይቀይሳል፤ይቆጣጠራል፡፡

11.<u>ወደ አገር ውስጥ በሚገቡ ወይም ወደ ውጭ አገር በሚላኩ የኒውክለር ወይም የጨረራ አመንጭ ቁሶችን የያዙ ምርቶች ላይ የሚደረግ ቁጥጥር</u>

የኒውክለር ወይም የጨረራ አመንጭ ቁሶችን የያዙ ምርቶች ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት ወይም ወደ ውጭ አገር ለማስወጣት ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሁኔታዎች ስለመሟላታቸው ቁጥጥር በማድረግ ፈቃድ ይሰጣል፦

1. በሬጉላቶሪ ቁጥጥር ሥር የሚያልፉትን የኒውክለር ቁሶች ወደ ውጭ ለመላክ አመልካቹ ተጠቃሚውን የሚመለከቱ አስፈላጊ ማስረጃዎች መቅረባቸውን፤
2. ማናቸውንም የኒውክለርና የራዲዮአክቲቭ ቁስ ወደ አገር ውስጥ የሚያስገባ ሰው የቴክኒካል እና ቁሱን የማስተዳደር ችሎታውን እንዲሁም የሚገባውን ቁስ ለመጠቀም የሚያስችል የመሣሪያ ወይም የቴክኒዮሎጂ አቅም መኖሩን፤
3. በደንብና መመሪያ ውስጥ የተዘረዘሩ ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ መስፈርቶች መሟላታቸውን፡፡

12.<u>የፈቃድ አሰጣጥና ይዘት</u>

1. ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅና አዋጁን ተከትለው በሚወጡት ደንቦች እና መመሪያዎች እንደየተግባራቱ የተቀመጡትን መስፈርቶች እና የሙያ ሥነ-ምግባር ለሚያሟላ ሰው የፈቃድ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

2. ማንኛውም የፈቃድ የምስክር ወረቀት ከጨረራና ኒውክለር ቁጥጥር ጋር የተያያዘ አስፈላጊ ሁኔታዎችን ሊይዝ ይችላል፡፡
3. የፈቃድ የምስክር ወረቀቱ ለዚሁ አገልግሎት በተዘጋጀው ፎርም መሠረት ይሰጣል፡፡

13. <u>የፈቃድ ምስክር ወረቀት ዕድሳት</u>

1. የፈቃድ ምስክር ወረቀት ዕድሳት ማመልከቻ ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣው ደንብ በተቀመጠ የጊዜ ገደብ ውስጥ ተገቢ መስፈርቶችን በማሟላት ለባለስልጣኑ መቅረብ ይኖርበታል፤
2. አንድ የፈቃድ የምስክር ወረቀት ይዘቱን እንደተጠበቀ ወይም ይዘቱ ተሻሽሎ ሊታደስ ይችላል፤
3. የዕድሳት ጊዜን ሳይጠብቅ በድጋሚ የፈቃድ ማመልከቻ መቅረብ የሚያስፈልገው የተለዩ የሬዲዮአክቲቭ ቁሶችን አገልግሎት ላይ ለማዋል ወይም ተግባራቱ ወይም በጨረራ መጋለጥ መጠኑ ላይ ለውጥ የሚያመጣ ወይም የተሻሻለ መሣሪያ ለመጠቀም ወይም የሥራ ቦታ ለውጥ ለማድረግ ሲፈለግ ይሆናል።
4. ባለሥልጣኑ የቀረበው የዕድሳት ማመልከቻ ተገቢውን መሥፈርት ያሟላ መሆኑን ሲያረጋግጥ የታደሰ የፈቃድ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

14.<u>የባለፈቃዱና ሌሎች የሚመለከታቸው ሰዎች ተግባርና ኃላፊነት</u>

1. ማንኛውም ባለሥራ ፈቃድ ተግባራቱን ወይም ድርጊቱን ለማከናወን አዋጁን እና አዋጁን ለማስፈፀም የሚወጡ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ መስፈርቶች እና አስፈላጊ ሁኔታዎችን አሟልቶ መስራቱን ማረጋገጥ፣ ለተግባራቱና ድርጊቱ ደህንነትና ጥበቃ ተቀዳሚ ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡
2. ማንኛውም ባለሥራ ፈቃድ ባለሥልጣኑ የቁጥጥር ሥራውን ለማከናወን ለሚያቀርብለት ማናቸውም የትብብር ጥያቄ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡
3. ማንኛውም ባለሥራ ፈቃድ የሥራ ፈቃድ ያገኘበትን ተግባር ወይም ድርጊት ለማቆም ሲፈልግ ለባለስልጣኑ አስቀድሞ ተግባሩን ወይም ድርጊቱን ማሳወቅ አለበት፡፡
4. ማንኛውም ባለሥራ ፈቃድ የሥራ ፈቃድ ከወሰደበት ተግባር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የሚመነጨው የጨረራ መጋለጥ በተቻለ ሁኔታ ከተወሰነው አነስተኛ ገደብ በታች መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡ ዝርዝሩ በደንብ የሚወሰን ይሆናል፡፡

5. ማንኛውም ባለሥራ ፈቃድ በጨረራ ጤንነትና ደህንነትበቂ የትምህርት ዝግጅት እና የሥራልምድ ያለው የጨረራ ሠራተኛ መመደብ አለበት፡፡
6. ማንኛውም ባለሥራ ፈቃድ በጨረራ ሥራ ላይ ያሰማራው ሰው የጤንነት ምርመራ ማድረጉን የማረጋገጥ እና በየስድስት ወሩ የጤንነት ምርመራ ክትትል ማድረጉን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡
7. ማንኛውም ባለሥራ ፈቃድ ፈቃድ ካገኘበት የጨረራ አመንጪ ወይም ተግባር ከሚጠበቅ ጉዳት ጋር በተመጣጠነ መልኩ የጨረራ ሠራተኛው የጨረራ ውስድ መጠን መከታተያ መሣሪያና የጨረራ ሥራን በመስራት ሊደርስባቸው ይችላል ተብሎ የሚገመተውን ጉዳት ተቀባይነት ባለው መጠን ዝቅ ለማድረግ አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተጨማሪ መሣሪያዎች እና ሙያው ለሚያስከትለው ስጋት ተመጣጣኝ ክፍያ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡
8. ማንኛውም ባለሥራ ፈቃድ የኒውክለርና የጨረራ አመንጪዎች ደህንነት አስተዳደርና ቁጥጥር እየተተገበረ መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡
9. ማንኛውም ባለሥራ ፈቃድ ፈቃድ ካገኘበት ተግባር ጋር በተያያዘ የጨረራ ደህንነትና መከላከል ጋር የግልፅነትና የተጠያቂነት ሥርዓት መዘርጋት ይኖርበታል፡፡
10. ማንኛውም ባለሥራ ፈቃድ በመስኩ ተገቢውን ሥልጠና ያላገኘ ወይም ከ18 ዓመት በታች ዕድሜ ያለው ወይም በሥራው ምክንያት ሊፈጠር ለሚችል የጤና ጠንቅ በቀላሉ እንዲጋለጥ ሊያደርገው ከሚችል በሽታ ወይም ድክመት ነፃ መሆኑ ያልተረጋገጠለት ማንኛውንም ሰው በጨረራ ሥራ ላይ ማሰማራት የለበትም፡፡
11. ከላይ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 10 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሥራ ፈቃዱ ነፍሰጡር ሴቶች እርግዝና መከሰቱን ካሳወቁበት ጀምሮ የፅንሱን ደህንነት ከጨረራ ጠንቅ ለመከላከል በሥራ ክፍሉ በጨረራ አመንጭዎች በሚያጋልጡ ሥራዎች ላይ በጊዜያዊነት የሚሰሩበት ሁኔታ ማመቻቸት አለበት፤ ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች በደንቡ ይገለፃሉ፡፡

12. ማንኛውም ባለሥራ ፈቃድ በጨረራ ሥራ ላይ የተሰማራ ወይም በሥራው ምክንያት ለጨረራ የተጋለጠ ማንኛውም ሰው በጨረራ ምክንያት ሊገመት የሚችል የጉዳት ምልክት ሲያሳይ በፍትሃብሄር ሕጉ መሠረት ካሣ የማግኘት መብቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ወዲያውኑ የሕክምና ምርመራ እንዲደረግለት የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡
13. ማንኛውም ሰው በአገሪቱ ውስጥ አገልግሎት የሰጠ የራዲዮአክቲቭ ዝቃጭና የአገልግሎት ዘመኑን የጨረሰ የኒውክለር ማብላያ ነዳጅ ከአገር ለማስወጣት ሲፈልግ ከባለሥልጣኑ ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል፡፡
14. ማንኛውም በጨረራ ሥራ ላይ የተሰማራ ሰው በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (6 ከተደነገገው መደበኛ የጤና ምርመራ በተጨማሪ ባለሥልጣኑ በሚወስነው መሠረት የሕክምና ምርመራ ማድረግ አለበት፡፡
15. ባለሥራ ፈቃዱ፣ የጨረራ ሠራተኛው ወይም ማንኛውም ሰው የጨረራ አመንጪው ሲጠፋ፣ ሲሰረቅ፣ ላልተፈቀደ ተግባር ሲውል ወዲያውኑ ለባለሥልጣኑ የማሳወቅ፤ ወይም ተቀባይነት ካለው መጠን በላይ የጨረራ መጋለጥ ሁኔታ ሲከሰት ወይም ማንኛውም ዓይነት አደጋ ሲያጋጥም ስለሁኔታው መጀመሪያ ካወቀበት ጊዜ አንስቶ ከ24 ሰዓት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለባለሥልጣኑ የማሳወቅ ግዴታ ያለበት ሲሆን፣ ባለሥልጣኑ በአስቸኳይ ጊዜ እንዲወሰዱ ያስቀመጣቸውን እርምጃዎች ማክበር አለበት፡፡
16. ባለፈቃድ የሆነው ግለሰብ የሞተ እንደሆነ ንብረቱን በኃላፊነት የሚያስተዳድር ማንኛውም ሰው ባለፈቃዱ ስለመሞቱ ለባለሥልጣኑ ወዲያውኑ ማሳወቅና ተገቢው የጨረራ መከላከልና ደህንነት መስፈርት መሟላቱን እንዲሁም የጨረራ አመንጪው በአግባቡ መጠበቁን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡
17. ባለሥራ ፈቃድ የሆነው ሰው በሞት ሲለይ የጨረራ አመንጪው ፈቃድ የይዞታ መብትን በሚመለከት ብቻ የሚች ንብረት ሆኖ ለሶስት ወር ይቆያል፡፡
18. የራዲዮአክቲቭ ዝቃጭ ማስወገጃ ማዕከል ኦፕሬተር ስለማዕከሉ አዘጋግና የዝቃጩ ባለቤት ስለሆነው ተቋም ቀልጣፋ ቁጥጥር መርሐግብር ያወጣል፤ ባለሥልጣኑ ፈቃድ ከመስጠቱ በፊት መርሐ-ግብሩን መርምሮ ማፅደቅ ይኖርበታል፡፡

## ክፍል ሶስት

## ኢንስፔክሽን እና ሕግማስፈፀም

### 15. ኢንስፔክተር ስለመሰየም

ባለስልጣኑ ተገቢው የትምህርት ዝግጅት፣ ሥልጠና እና ልምድ ያላቸውን ኢንስፔክተሮች ይሰይማል፤ ኃላፊነታቸውን የሚያሳይ መታወቂያ ይሰጣቸዋል፡፡

### 16. ስለ ኢንስፔክተሮች ስልጣንና ኃላፊነት

ኢንስፔክተሮች የሚከተሉት ሥልጣንና ኃላፊነት ይኖራቸዋል፦

1. የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎችና አዋጁን ተከትለው የሚወጡ ደንቦችን፣ መመሪያዎችን፣ መስፈርቶችንና ቅድመ ሁኔታዎች ባለሥራ ፈቃዱ ማክበሩን ማረጋገጥ እና ከኢንስፔክሽን ተግባሩ ጋር የተያያዙ ሌሎች ምርመራዎችን የማድረግ፤
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1 አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በማንኛውም ጊዜ ተግባራት ወይም ድርጊቶች በሚከናወኑበት ማዕከላት ወይም እየተከናወኑ ሊሆኑ ይችላሉ ብሎ በበቂ ሁኔታ ሲያምን በማንኛውም የሥራቦታ ወይም ከዚሁ ጋር በተያያዘ በተሽከርካሪ፣ በጀልባ፣ በአይሮኘላን ውስጥ ገብቶ በመመልከት፣
   ሀ) የጨረራ ደህንነትና ጥበቃ ያለበትን ደረጃ መረጃ የማግኘት፤
   ለ) ከኢንስፔክሽን ተግባሩ ጋር የተያያዙ የፈቃድ የምስክር ወረቀትን፣ መረጃን ወይም ሰነዶችን ለመመርመር ወይም የእነዚህኑ ኮፒዎች እና ለምርመራ ናሙናዎችን የመውሰድ፤
   ሐ) ከኒውክለር ቁስ ወይም ከጨረራ አመንጪዎች ጋር የተያያዘ ማናቸውንም ክስተት ወይም አደጋን የመመርመር፤
   መ) በባለሥራ ፈቃዱ ተወክሎ የሥራ ግዴታ የገባ ማንኛውንም ሰው ለኢንስፔክሽን አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የመጥራትና የመጠየቅ፤
3. ለኢንስፔክሽኑ ሥራ ሂደት የሚያገለግሉ ሰነዶችን ማዘጋጀት እና መመዝገብ፤
4. ከኢንስፔክሽን ሥራ በኋላ ለሚመለከታቸው ኃላፊዎች እና ለባለሥራ ፈቃዱ ሪፖርት ማቅረብ፤
5. የባለሥራ ፈቃዱ ተጠያቂነትና የሥራ ሪከርድ ማህደር በቦታው መገኘቱንና በትክክል መጠበቁን የማረጋገጥ፤

6. ማናቸውም የኒውክለር ቁሶች፣ የጨረራ አመንጪዎች ወይም ማዕከላት በአግባቡ የተመዘገቡ፣ በማንኛውም ወቅት የሚገኙበት ቦታና አድራሻ የሚታወቅ፣ ያለአግባብ ጥቅም ላይ እንዳይውሉ፣ እንዳይሰረቁ እና መሰል ተግባራት ቢፈፀም መቆጣጠር የሚቻል ስለመሆኑ የማረጋገጥ፡፡

17. ሕግ ስለማስፈፀም

1. ኢንስፔክተሩ የዚህ አዋጅ እና ይህን አዋጅ ተከትሎ የወጡ ደንቦች፣ መመሪያዎች ፣የሥራ ፈቃዱ አስፈላጊ መስፈርቶች እና ሁኔታዎች ባለስራ ፈቃዱ ተግባሩን ወይም ድርጊቱን በሚያከናውንበት ጊዜ ተጥሶ እና በሰዎች ላይ አጣዳፊ ስጋቶች ወይም ከባድ የንብረት ወይም የአካባቢ ጉዳት ተጋርጧል ብሎ ሲወስን እንደሁኔታው፡-
   ሀ) ተግባሩን ወይም ድርጊቱን በጊዜያዊነት በማገድ ወይም፣ የጨረራ ምንጩን የሥራ ክፍል በማሸግ፣
   ለ) ባለስራ ፈቃዱ የጨረራ ሠራተኛው ተግባሩን ወይም ድርጊቱን በሚያከናውንበት ጊዜ መስፈርቶቹን የማይጠብቅ ሆኖ ሲገኝ ሠራተኛውን እንዲያግደው በማዘዝ፣
   ሐ) ከታገዱት የኒውክለር ወይም የራዲዮ አክቲቭ ቁሶች ተግባራት ወይም ድርጊት የሚመነጩ ጨረራዎች በጥንቃቄ እንዲቀመጡ ወይም እንዲያዙ በማዘዝ፣
   መ) የጨረራና የኒውክለር ቁጥጥር ተግባራትን በሚመለከቱ ጉዳዮች ማንኛውንም ሰው በመጥራት ለብቻው ወይም ራሱ ተገቢ ነው ብሎ የሚመርጠው ሌላ ሰው በተገኘበት ቃል የመቀበል ወይም ማንኛውንም ማስረጃ እንዲሰጥ በማድረግ፣ ወይም
   ሠ) ከተጣለበት ኃላፊነት አኳያ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የህክምና ምርመራ እንዲከናወን በማዘዝ፤

   ሕግ ያስፈፅማል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በኢንስፔክተሩ የተሰጠ ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ ባለሥራ ፈቃዱ በትዕዛዙ መሠረት እስኪያስተካክል ድረስ የሚተገበርና ፀንቶ የሚቆይ ይሆናል፡፡

3. የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ ቢኖርም የኢንስፔክተሩ ውሳኔ ተፈፃሚ የማይሆነው፡-

ሀ) የኢንስፔክተሩን ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ የሚያስለውጥ ወይም የሚያሻሽል እርምጃ በባለስልጣኑ የበላይ ኃላፊ ሲወሰድ፤ ወይም

ለ) በቅሬታሰሚ አካል የኢንስፔክተሩ ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ ሲለወጥ፡፡

4. ኢንስፔክተሩ ሕግ ያስፈፀመበት ሪፖርት ዋና ግኝቱን እና ለግኝቱ መነሻ ማስረጃ የሆኑትን፣ እርምጃዎቹን፣ የምርመራ ውጤቱን፣ ትንተናዎች ወይም ሌሎች መረጃዎችን ማካተት ይኖርበታል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት የተዘጋጀው ሪፖርት ለባለ ሥራ ፈቃዱ መድረስ ያለበት ሲሆን፣ ባለ ሥራ ፈቃዱም ስለጉዳዩ ማብራሪያ እንዲሰጠው የመጠየቅ ወይም ሪፖርቱ በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ለቅሬታ ሰሚው አካል ተቃውሞውን የማቅረብ መብት አለው፡፡

18.<u>ስለ ፈቃድ ማሻሻል፣ማገድ እና መሰረዝ</u>

1. ኢንስፔክተሩ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 17 መሠረት ሕግን የማስፈፀም ሥልጣንና ተግባሩን ሥራ ላይ ሲያውል ፈቃዱ እንዲሻሽል፣ እንዲታገድ ወይም እንዲሰረዝ የውሳኔ ሀሳብ ለባለሥልጣኑ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

2. ኢንስፔክተሩ ፈቃዱ እንዲሻሽል፣ እንዲታገድ ወይም እንዲሰረዝ የውሳኔ ሀሳብ ለባለሥልጣኑ ሊያቀርብ የሚችለው፦

ሀ) በባለ ሥራ ፈቃዱ የዚህ አዋጅ ወይም አዋጁን ለማስፈፀም የወጣ ደንብ ወይም መመሪያ ድንጋጌ ተጥሶ ሲገኝ፣

ለ) ባለሥራ ፈቃዱ የፈቃዱን መስፈርቶች እና ሁኔታዎች መተላለፉ ሲረጋገጥ፤

ሐ) ባለሥራ ፈቃዱ የተሳሳተ መረጃ ለባለስልጣኑ በመስጠት ፈቃዱን ያገኘ መሆኑ ሲረጋገጥ፣ ወይም

መ) የሕዝብን ጥቅም ማስከበር አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያምን ይሆናል፡፡

3. ኢንስፔክተሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሠረት ፈቃዱን የማሻሻል፣ የማገድ ወይም የመሰረዝ ውሳኔ ሀሳብ ለባለሥልጣኑ ሲያቀርብ የውሳኔ ሀሳቡን ቅጂ ከነምክንያቱ በጽሁፍ ለባለሥራ ፈቃዱ መስጠት ይኖርበታል፡፡

4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ድንጋጌ ቢኖርም ኢንስፔክተሩ ሁኔታው አስቸኳይ ውሳኔ ያስፈልገዋል ብሎ ሲያምን የውሳኔ ሀሳብ ለባለሥልጣኑ እና ለባለፈቃዱ ከማቅረቡ በፊት ፈቃዱን ሊያግደውይችላል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት የቀረበለትን የውሳኔ ሀሳብ መሠረት አድርጎ የባለሥልጣኑ የፈቃድ አሰጣጥ የሥራ ክፍል ኃላፊ የባለሥራ ፈቃዱን ፈቃድ የማሻሻል፣ የመሰረዝ ወይም የማገድ ወይም የኢንስፔክተሩን እገዳ የማፅናት ውሳኔ ይሰጣል፡፡
6. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት የተሰጠ የፈቃድ ማገድ ውሳኔ በባለሥልጣኑ የፈቃድ አሰጣጥ የሥራ ክፍል ኃላፊ ሳይፀድቅ ከ30 ቀናት በላይ ያለፈው እንደሆነ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡
7. የሥራ ፈቃዱ ከታገደ ወይም ከተሰረዘ፦
   ሀ) ኢንስፔክተሩ የባለሥራ ፈቃዱን ማዕከል ወይም የኒውክለርና የራዲዮአክቲቭ ቁሱን ወይም ፈቃድ የተሰጠበትን የጨረራ አመንጪ መሣሪያ የሚገኝበት ክፍል እሽጉ ካልተፋቀ ወይም ካልተሰበረ በስተቀር አገልግሎት እንዳይሰጥ በማድረግ ያሽጋል፣
   ለ) ባለስራ ፈቃዱ ከኢንስፔክተሩ በተሰጠው አቅጣጫ መሰረት የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ለባለሥልጣኑ ሪፖርት የማድረግ ግዴታ አለበት፣
   ሐ) ባለስራ ፈቃዱ ለስረዛው ወይም ለዕገዳው ምክንያት የሆኑ ጉድለቶችን በተወሰነየጊዜ ገደብ ውስጥ ለማስተካከል ፈቃደኛ መሆኑን በጽሁፍ ያረጋገጠ እንደሆነ ኢንስፔክተሩ ከባለሥልጣኑ የፈቃድ አሰጣጥ የሥራ ክፍል ኃላፊ ጋር በመመካከር እሽጉን ሊያነሳ ይችላል፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

19.<u>አቤቱታ የማቅረብ መብት</u>

1. በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 18 መሠረት የተላለፈ ውሳኔን የሚቃወም ማንኛውም ባለሥራ ፈቃድ ፈቃዱ ሊሻሻል፣ ሊታገድ ወይም ሊሰረዝ አይገባም የሚልበትን ምክንያት በመዘርዘር የውሳኔው ግልባጭ በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ለባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር አቤቱታውን ሊያቀርብ ይችላል፡፡
2. የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር በሚቀርቡለት አቤቱታዎች ላይ የውሳኔ ሀሳብ የሚያቀርብ ኮሚቴ ያቋቁማል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የሚቋቋመው ኮሚቴ አንድ የሕግ ባለሙያና ሁለት በጨረራና ኒውክለር መከላከል ልምድ ያላቸው ባለሙያዎችን የሚያካትት ይሆናል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት የተቋቋመው ኮሚቴ ከባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር የሚመራለትን አቤቱታ፣ ውሳኔና አስፈላጊ ማስረጃዎችን በመመርመር በ30 ቀናት ውስጥ የውሳኔ ሀሳቡን ለባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ማቅረብ አለበት፡፡
5. የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር የኮሚቴውን ውሳኔ ሀሳብ መሠረት አድርጎ ውሳኔ ይሰጣል፤ በባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው በ30 ቀናት ውስጥ አቤቱታውን ለመደበኛ ፍርድ ቤት ሊያቀርብ ይችላል፡፡
6. አቤቱታ የቀረበለት ፍርድ ቤት አስተዳደራዊ ውሳኔውን ሊያፀናው፣ ሊሽረው ወይም ሊያሻሽለው ወይም እንደገና እንዲታይ ሊመልሰው ይችላል፡፡
7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) መሰረት ቅሬታ የቀረበበት ቢሆንም በፍርድ ቤት እስካልታገደ ድረስ የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ውሳኔ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 20.<u>የኒውክለር ቁሶችን ለሠላማዊ አግልግሎት ለማዋል ስለሚወሰዱ እርምጃዎች</u>

1. የሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ እና ባለሥራ ፈቃዱ ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸውን አህጉራዊና ዓለም አቀፍ የጨረራና ኒውክለር ስምምነቶችን ተግባራዊ ለማድረግ ከባለሥልጣኑ ጋር ሙሉ በሙሉ የመተባበር ግዴታ ይኖርባቸዋል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የኒውክለር ጦር መሣሪያዎችንና ሌሎች የሚፈነዱ መሣሪያዎችን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ማምረት ወይም መያዝ፣ ወይም ለማምረት ወይም ለመያዝ ሙከራ ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡
3. የራዲዮአክቲቭ ዝቃጭና አገልግሎቱን የጨረሰ የኒውክለር ማብላያ ነዳጅ ለማናቸውም ዓላማ ወደ ኢትዮጵያ የግዛት ክልል ማስገባት በጥብቅ የተከለከለ ነው፡፡

## 21.<u>የጨረራ መከላከል አገልግሎት ሰጪዎች ምዝገባ</u>

የጨረራ መከላከልና ተያያዥ አገልግሎት በመስጠት ሥራ የሚሰማራ ማንኛውም ሰው በባለሥልጣኑ ዘንድ ቀርቦ መመዝገብ እና ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል፡፡

የጨረራ መከላከልና ተያያዥ አገልግሎት የሚሰጥ ሰው አመዘጋገብ እና ፈቃድ አሠጣጥ ሁኔታ ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

22.የጨረራና የኒዩክለር ምርምርና ልማት

ከጨረራና ኒዩክለር ቴክኒዮሎጂ ጋር የተያያዘ የቁጥጥር ስራን ሊደግፉ የሚችሉ ጥናትና ምርምር ስራዎች የሚካሄዱበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡

23.ሚስጥር ስለመጠበቅ

የዚህን አዋጅ ዓላማ ለማሳካት በአዋጁ ሚስጥር ናቸው ተብለው የሚደነገጉ በሚመለከተው አካል ስለሚስጥራዊ መረጃነታቸው የተረጋገጡ ጉዳዮችን ያለበቂ ምክንያት አሳልፎ መስጠት የተከለከለ ነው፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

24.የወንጀል ድንጋጌዎች

1. ማንኛውም ሰው ለባለስልጣኑ በአግባቡ ሳያሳውቅ እና የሥራ ፈቃድ ሳይሰጠው በራዲዮአክቲቭ ቁስ ወይም ተግባራት ዙሪያ ከተሰማራ ከሦስት ዓመት በማያንስና ከሰባትዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከ30 ሺ.ብር በማያንስና ከ70 ሺ.ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡
2. ማንኛውም ሰው ለባለስልጣኑ በአግባቡ አሳውቆ ነገር ግን የሥራ ፈቃድ ሳይሰጠው በራዲዮአክቲቭ ቁስ ወይም ተግባራት ዙሪያ ከተሰማራ ከአንድ ዓመት በማያንስና ከሁለት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከ10 ሺ.ብር በማያንስና ከ20 ሺ.ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡
3. ማንኛውም ሰው ከባለስልጣኑ እውቅና ውጪ ፈቃዱን ወይም ተግባራቱን ወይም መገልገያውን ወይም ሙያውን ወይም ድርጅቱን ያስተላለፈ ወይም ያከራዬ፣ ወይም በማንኛውም ሁኔታ መብቱን እና ለሥራ የተሠጠውን ኃላፊነቱን ያለአግባብ የተጠቀመ እንደሆነ ከሁለት ዓመት በማያንስና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከ20 ሺ.ብር በማያንስና ከ50 ሺ.ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

4. ማንኛውም ሰው ከተሰጠው ፈቃድ ጋር የተገናኙ ቴክኒካል ሰነዶችን ወይም አስፈላጊ መረጃዎችን ያጠፋ፣ ወይም ሀሰተኛ ሪፖርት ያቀረበ፣ ወይም ስለ ተግባሮቹ መረጃ እንዲያቀርብ ተጠይቆ ያላቀረበ እንደሆነ ከአንድ ዓመት በማያንስና ከሦስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከ10 ሺ.ብር ያላነሰና ከ30 ሺ.ብር ባልበለጠ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል::
5. ማንኛውም ሰው በፈቃዱ ተዘርዝሮ ከተሠጠው ፈቃድ ወሰን በላይ ሙያዊ ግዴታውን፣ በሙያ ሥነ-ምግባሩ፣ ወይም በማንኛውም ተመሳሳይ አኳኋን ይህን አዋጅ እና የደህንነትና ጥበቃ እርምጃዎችን የተላለፈ እንደሆነ ከሁለት ዓመት በማያንስና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከ20 ሺ.ብር በማያንስና ከ50 ሺ.ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል:
6. ማንኛውም ሰው በማንኛውም አኳኋን የኢንስፔክሽን ሥራውን ያሰናከለ ወይም ኢንስፔክተሩን ያንገላታ ወይም ከኢንስፔክተሩ ጋር ለመተባበር ፈቃደኛ ያልሆነ እንደሆነ ከአንድ ዓመት በማያንስ እና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከ10 ሺ.ብር በማያንስና ከ50 ሺ.ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡
7. ማንኛውም ሰው የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች በመተላለፍ በኒዩክለር ወይም የራድዮአክቲቭ ቁስ ሕገወጥ ዝውውር ላይ የተሳተፈ እንደሆነ ከሦስት ዓመት በማያንስና ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከ30 ሺ.ብር በማያንስና ከ100 ሺ.ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡
8. ማንኛውም ሰው የሙያ ሥህተት መፈጠሩን ወይም ይህን አዋጅ የሚፃረር ማንኛውም ተመሳሳይ ተግባር መኖሩን እያወቀ ወይም የኒዩክለር ወይም ራዲዮሎጅካል አደጋ እንደሚፈጠር እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው ሪፖርት ያላደረገ እንደሆነ ከአንድ ዓመት በማያንስና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከ10 ሺ. ብር በማያንስና ከ50 ሺ. ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡
9. የኒውክለር ወይም የራድዮአክቲቭ ቁስ ሚስጥር ያባከነ ማንኛውም ሰው ከአንድ ዓመት በማያንስና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ወይም ከ10 ሺ.ብር በማያንስና ከ50 ሺ.ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

10. የኒዩክለር ወይም የራዲዮአክቲቭ ቁስን ለሽብርተኝነት ዓላማ ያለማ ወይም ለሰላም ተቃራኒ ለሆኑ ተግባራት የተጠቀመ ማንኛውም ሰው ከ20 ዓመት ባላነሰ ፅኑ እስራት እና ከ200 ሺ ብር ያላነሰና ከ1 ሚሊዮን ብር ያልበለጠ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡
11. በባለስልጣኑ ፈቃድ ሳያገኝ በሰው ላይ የሞት ወይም ከፍተኛ የአካል ጉዳት ወይም በንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያስከትል የሚችል የኒዩክለር ወይም የራዲአክቲቭ ቁስ የመቀበል፣የማስተላለፍ፣የመለወጥ፣የማሰወገድ፣ የማሰራጨት ወይም የማጓጓዝ ድርጊት የፈፀመ ማንኛውም ሰው ከሦስት ዓመት ባላነሰና ከአስራ አምስት ዓመት ባልበለጠ ፅኑ እስራት እና ከብር 50 ሺ ባላነሰ እና ከብር 500 ሺ ባልበለጠ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡
12. ያለባለሥልጣኑ ፈቃድ የኒዩክለር ወይም የራዲዮአክቲቭ ቁስን በመጠቀም ጉዳት ያደረሰ ከአሥር ዓመት በማያንስና ከሃያ ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከብር 100 ሺ ባላነሰና ከብር 500 ሺ ባልበለጠ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

25. <u>ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት</u>

በዚህ አዋጅና በደንቡ የተመለከቱ ጉዳዮችን በሚመለከት የሚነሱ ክርክሮችንና ተዛማጅ ጉዳዮችን የማየት ሥልጣን ያለው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይሆናል፡

26. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ የተሰጠውን ኃላፊነት በብቃት መወጣት እንዲችል ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግስት አካላት እና ማንኛውም ሰው የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

27. <u>ስለተሻረና ተፈፃሚነት ስለማይኖረው ሕግ</u>

1. የጨረራ መከላከያ አዋጅ ቁጥር 571/2000 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡
2. ይህን አዋጅ የሚቃረን ሌላ ማንኛውም ሕግ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ ውስጥ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

28. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

1. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም የኢትዮጵያ ጨረራ መከላከያ ባለሥልጣን በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ እስኪቋቋም ድረስ የጨረራ መከላከያ አዋጅ ቁጥር 571/2000 ከአንቀጽ 4 እስከ አንቀጽ 15 ድረስ ያሉ ድንጋጌዎች ከአንቀጽ 4(2) እና አንቀፅ 13 በስተቀር ፀንተው ይቆያሉ፡፡

2. በሂደት ላይ የሚገኙ የፈቃድና የምዝገባ ማመልከቻዎች በዚህ አዋጅ መሰረት ይፈፀማሉ፡፡
3. በጨረራ መከላከያ አዋጅ ቁጥር 571/2000 መሰረት የተሰጡ ወይም የታደሱ ፈቃዶች እንዲሁም የተደረጉ ምዝገባዎች ፀንተው የሚቆዩበት ጊዜ እስኪጠናቀቅ ድረስ ሕጋዊነታቸው ይቀጥላል፡፡

29.<u>ደንብ እና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

1. የሚኒስትሮችምክርቤት፡-
   - ሀ አዮን ፈጣሪ የሆኑ እና አዮን ፈጣሪ ካልሆኑ የጨረራ አመንጪዎች ጋር የተያያዙ የማሳወቅና ፈቃድ የማግኘት ግዴታዎች፤ የቁጥጥርና የክትትል ጉዳዮችን በሚመለከት፣
   - ለ የፈቃድ ማመልከቻ እና ተያያዥ ጉዳዮችን በሚመለከት፣
   - ሐ የፈቃድ የምስክር ወረቀት አሠጣጥ፣ የፈቃድ ይዘት እና ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜና የአገልግሎት ክፍያ ተመን በሚመለከቱ፤
   - መ ይህን አዋጅ በሚገባ ሥራ ላይ ለማዋል በሚያስፈልጉ ሌሎች ጉዳዮች ላይ፤ ደንቦችንሊያወጣይችላል፡፡
2. ባለስልጣኑ፡-
   - ሀ በምግብ እና ምግብ ነክ ባልሆኑ ምርቶች ላይ የሚካሄድ የራዲዮአክቲቭ ቁጥጥርን በሚመለከት፣
   - ለ የራድዮአክቲቭ ቁሶች በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ስለሚጓጓዙበት እና ባለቤት አልባ የራድዮአክቲቭ ቁሶች ላይ ቁጥጥር ስለሚደረግበት ሁኔታ፣
   - ሐ የራድዮአክቲቭ ቁሶችና ተዛማጅ ተግባራት ለንግድ ዓላማ በመገናኛ ብዙሃን ወይም በሌላ ዘዴዎች ስለሚተዋወቁበት ሁኔታ፤ እና
   - መ ይህንን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የወጣውን ደንብ በሚገባ ማስፈፀም በሚያስፈልጉ ሌሎች ጉዳዮች ላይ፤

   መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

30.<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል

**አዲስ አባባ ሐምሌ 12 ቀን 2009 ዓ.ም**

**ዶ)ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

# አዋጅ ቁጥር 1075/2010

## ስለኢንዱስትሪ ኬሚካሎች ምዝገባና አስተዳደር የወጣ አዋጅ

ሀገራችን ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ በሽግግር ሂደት ላይ በመሆኗ ከውጪ ሀገር የሚገቡ ወይም በሀገር ውስጥ የሚመረቱ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች መጠን እያደገ በመምጣቱ፤

የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት፣በማጓጓዝ፣ በማከማቸት፣ በማምረትና በመጠቀም ሂደት ከአያያዝጉድለት በሰው፣ በእንስሳት ጤና እና በአካባቢ ደህንነት ላይ ሊከሰቱ የሚችሉ ጉዳቶችን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የሚያስችልሥርዓትመዘርጋት በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥትአንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለውታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች ምዝገባና አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1075/2010" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

   1. "የኢንዱስትሪ ኬሚካል" ማለት ለኢንዱስትሪ፣ ለትምህርት፣ ለሥልጠና ለምርምርና ስርፀት አገልግሎት ጥቅም ላይ የሚውል ማንኛውንም ኬሚካል የሚጨምር ሲሆን የመድሃኒት እና የህክምና፣ የምግብና የምግብ ነክ፣ የግብርና፣የኬሚካል ጦር መሳሪያዎች እና የጨረር አመንጪ ኬሚካሎችን አይጨምርም፤
   2. "አካባቢ" ማለት በመሬት፣ በከባቢ አየር፣ በአየር ሁኔታ እና በአየር ንብረት፣ በውሃ፣ በህያዋን፣ በድምጽ፣ በሽታ፣ በጣዕም፣ በማህበራዊ ጉዳዮች እና በሥነ ውበት ሳይወሰን፣ በተፈጥሮአዊ ሁኔታዎች ወይም በሰው አማካኝነት ተለውጠው የሚገኙ ነገሮች በሙሉ ያሉበት ቦታ፣ እንዲሁም መጠናቸው ወይም ሁኔታቸው ወይም ደግሞ የሰው ወይም የሌሎች ህያዋን በጎ ሁኔታን የሚነኩ መስተጋብሮቶቻቸው ድምር ነው፤

3. “አግባብነት ያለው አካል" ማለት የኢንዱስትሪ ሚኒስቴርና የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስትቲዩት፣ የእርሻና ተፈጥሮ ሃብት ሚኒስቴር፣ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴርና የምግብ፣ መድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አስፈፃሚ አካል፣ የንግድ ሚሂኒስቴር፣ የሰራተኛና ማህበራዊጉዳይ ሚኒስቴር፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፣ የትምህርት ሚኒስቴር፣ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እና የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን ለመመዝገብ ወይም ለማስተዳደር በዚህ አዋጅ እና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች ሥልጣን የተሰጣቸውን አካላት እንዲሁም በክልል ደረጃ የእነዚህን ተቋማት ተግባር የመምራት ሃላፊነት የተሰጣቸውን አካላት ያጠቃልላል፤
4. "የምዝገባ ቁጥር" የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን በዓይነታቸው ለመለየትና ጥቅም ላይ ለማዋል የሚሰጥ ቁጥር ነው፤
5. “ዳግም ማሸግ" ማለት የኢንዱስትሪ ኬሚካልን ለቀጣይ ሽያጭ እንዲመች ለማድረግ ከአንድ የንግድ እሽግ ወደ ሌላ አብዛኛውን ጊዜ አነስወዳለ እሽግ የሚገለበጥበትና እንደገና የሚታሸግበት አሰራር ነው፤
6. "ጥቅም ላይ ሊውል የማይችል ኬሚካል" ማለት የኢንዱስትሪ ኬሚካል ሆኖ፤
   ሀ) በስቶክሆልም ወይም በሮተርዳም ስምምነት መሠረት ከአካባቢና ከጤና አንፃር ጥቅም ላይ እንዳይውል የታገደ፣ ወይም
   ለ) የአገልግሎት ጊዜው ያበቃ፤ ወይም
   ሐ) በአያያዝ ጉድለት የተነሳ የተበላሸ በመሆኑ ምክንያት ጥቅም ላይ ሊውል የማይችልነው፤
7. "በግንዛቤ ላይ የተመሠረተ ቅድመ ይሁንታ አሰራር" ማለት በሮተርዳምስምምነት ውስጥ በዓለም አቀፍ የንግድ ልውውጥ የተወሰኑ አደገኛየኢንዱስትሪ ኬሚካሎችንና ፀረ-ተባዮችን በተመለከተ ባስቀመጠው መሠረት የታገዱ ወይም በጥብቅ ገደብየተጣለባቸው ኬሚካሎችና በጣም አደገኛ የሆኑ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች ልውውጥና አያያዝ የማሳወቅ አሰራር ነው፤
8. "ገደብ የተጣለበት ኬሚካል"ማለት በስቶክሆልም ወይም በሮተርዳም ስምምነት መሠረት ከአካባቢና ከጤና አንፃር ጥብቅ የአጠቃቀም ገደብ የተጣለባቸው እና በግንዛቤ ላይ የተመሠረተ ቅድመ ይሁንታ አሰራር የሚጠይቁ ኬሚካሎች ናቸው፤
9. "የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት" ማለት በሮተርዳም ስምምነት እና ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በሚያወጣው መመሪያ ጥብቅ የአጠቃቀም ገደብ የተጣለባቸውን

የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን ለማምረት፣ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባትና ለመጠቀም የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን ያሟላመሆኑን በማረጋገጥ ከሚኒስቴሩ ወይምአግባብነት ካለው አካል የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው፤

10. የሮተርዳም ስምምነት" ማለት በተወሰኑ አደገኛ ኬሚካሎችና ፀረ-ተባዮች የዓለም አቀፍ ንግድን አስመልክቶ በግንዛቤ ላይ የተመሠረተ ቅድመይሁንታ አሰራር ሥርዓት እንዲተገበር በአዋጅ ቁጥር 278/1994 የፀደቀ ዓለም ዓቀፍ ስምምነት ነው፤

11. "ስቶክሆልም ስምምነት" ማለት ለረዥም ጊዜሳይመክኑ የሚቆዩ ከካርበን የተሰሩ በካዮችን በሚመለከት በአዋጅ ቁጥር 279/1994 የፀደቀ ዓለም ዓቀፍ ስምምነት ነው፤

12. “መለያ" ማለት የተፃፈ፣ የታተመ ወይም በምስልየተቀረፀና በኢንዱስትሪ ኬሚካል ቀጥተኛ መያዣና በቀጥተኛ መያዣያዎች ውጫዊመያዣ ወይም መጠቅለያ ላይ የተደረገ ወይም ከዚህ ጋር የተያያዘ መግለጫ ነው፤

13. “ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት ንደየቅደም ተከተሉ የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

14. "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት በአንቀጽ 47(1 የተመለከቱት ክልሎች እና የአዲስ አበባና የድሬደዋ የከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

15. "የኢንዱስትሪ ኬሚካል እንቅስቃሴ" ማለት የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን ማምረት፣ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት፣ ወደ ውጭ ሀገር መላክ፣ ማሸግ፣ ማጓጓዝ፣ ማከፋፈል፣ ማከማቸት፣ መጠቀም እና ወደ ሶስተኛ ወገን ማስተላለፍ ነው፤

16. "አደጋ" ማለት በሰው ወይም በእንስሳት ጤና፣ በአካባቢ ወይም በንብረት ላይጉዳት ሊያደርስ የሚችል የኢንዱስትሪ ኬሚካል ተፈጥሯዊ ባህሪይ ነው፤

17. "መያዣ" ማለት ማንኛውም የኢንዱስትሪ ኬሚካል የተያዘበት፣ የተቀመጠበት፣ የታሸገበት ወይም የተሸፈነበት ሲሆን ከኢንዱስትሪ ኬሚካሉ ጋርንክኪ ያለውን ማንኛውንም ነገር ይጨምራል፤

18. ”ማምረት" ማለት የኢንዱስትሪ ኬሚካልንማሰናዳት፣ ማዋሀድ፣ ማዘጋጀት መቀላቀል ወይም ለማሰራጨት ወይም በጥቅም ላይ ለማዋል እንዲችል ማድረግ ነው፤

19."ተጠቃሚ" ማለት የተለያዩ ምርቶችን ለማምረት ወይም ለሌላ አገልግሎት የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን በግብዓትነት የሚጠቀም ማንኛውም ድርጅት ወይም ተቋም ነው፤

20."ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

21.ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው ሴትንም ያካትታል፡፡

3. **የአዋጁ ተፈጻሚነት**

ይህ አዋጅ በኢንዱስትሪ ኬሚካሎች እንቅስቃሴ ላይ በሚሰማራ ማንኛውም ሰው ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

4. **አዋጁ ዓላማ**

ይህ አዋጅ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፦

1. የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን ለመመዝገብ እና ለማስተዳደር የሚያስችል ሀገራዊ ሥርዓት መዘረጋት፤ እና
2. ከኢንዱስትሪ ኬሚካሎች እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ በሰው እና በእንስሳት ጤና እንዲሁም በአካባቢ ደህንነት ላይ ሊከሰቱ የሚችሉ ጉዳቶችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር።፡

## ክፍል ሁለት

## ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እና ምዝገባ

5. **የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት**

በሮተርዳም ስምምነት እና ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በሚያወጣው መመሪያ ጥብቅ የአጠቃቀም ገደብ የተጣለባቸውን የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት፣ ወደ ውጪ በመላክ እንዲሁም በማከፋፈል ሥራ ለመሰማራት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ከሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ካለው አካል በቅድሚያ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት።

6. **የኢንዱስትሪ ኬሚካል ምዝገባ እና መዝገብ ስለማደራጀት**

1. ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በሀገር ውስጥ የሚመረቱናከውጭ ሀገርወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ኬሚካሎችን ዝርዝር እና መረጃ የያዘ መዝገብ ያደረጃል፤ መዝገቡ መያዝ የሚገባቸውን ዝርዝር መረጃዎች በደንብ ይወስናል።
2. ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው አካል ያልተመዘገበ የኢንዱስትሪ ኬሚካልን ማምረት፣ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት፣ ማሸግ፣ መሸጥ፣ ማከፋፈል፣ ማከማቸት ወይም መጠቀም አይችልም፡፡

3. አግባብነት ያላቸው አካላት የሚያስተዳድሯቸውን ኬሚካሎች መረጃ በየዓመቱ ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር መላክ አለባቸው፡፡
4. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የኬሚካሎችን መረጃ ለሚኒስቴሩ በየዓመቱ ይልካል።

## ክፍል ሦስት

## መረጃ አያያዝ እና የሪፖርት አቀራረብ

7. መረጃ አያያዝ

1. ማንኛውም የኢንዱስትሪ ኬሚካል የሚያመርት፣ የሚልክ፣ የሚያስመጣ፣ የሚያከፋፍል፣ ወይም የሚጠቀም ሰው የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝአለበት፦

ሀ ያመረተውን፣ ወደ ውጭ ሀገር የላከውን፣ ያከፋፈለውን፣ ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባውን ወይም የተጠቀመውን የኢንዱስትሪ ኬሚካል ዓይነትና መጠን፤

ለ በሀገር ውስጥ ገበያ የተሸጠውን እና የተከፋፈለውን የኢንዱስትሪ ኬሚካል ዓይነትና መጠን፤

ሐ በአያያዝ ጉድለት የተበላሹ ወይም የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸውንየኢንዱስትሪ ኬሚካሎች ዓይነትና መጠን፤ እና

መ የኢንዱስትሪ ኩሚካሎቹ የተመረቱበት ሀገር፣ ያመረተው ድርጅት ስምና አድራሻ፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ላይ የተመለከቱት መረጃዎች ቢያንስ ለአምስት ዓመታት ተይዘው መቆየት አለባቸው፡፡

8. ሪፖርት አቀራረብ

1. ማንኛውም የኢንዱስትሪ ኬሚካል አምራች፣አስመጪ፣ላኪ፣ አከፋፋይ ወይም ተጠቃሚ ያስመጣውን፣ የላከውን፣ ያመረተውን፣ ያከፋፈለውን፣ የተጠቀመውን ወይም ወደ ሦስተኛ ወገን ያስተላለፈውን የኬሚካል ዓይነትና መጠን በየዓመቱ ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሪፖርት ማድረግ አለበት።
2. ማንኛውም ሰው ያመርተውን ወይም ያስመጣውን የኢንዱስትሪ ኬሚካል ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሪፖርት ሳያደርግ የኢንዱስትሪ ኬሚካል ንግድ ማከናወን አይችልም፡፡
3. ማንኛውም የኢንዱስትሪ ኬሚካል አምራች፣ አስመጪ፣ ላኪ፣ አከፋፋይ ወይምተጠቃሚ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች የመጠቀሚያ ጊዜ ከማለፉ ከአንድ ዓመት በፊት ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ማሳወቅ አለበት።

4. ማንኛውም የኢንዱስትሪ ኬሚካል አምራች፣ አስመጪ፣ ላኪ፣ አከፋፋይ ወይም ተጠቃሚ በይዞታው የሚገኙ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች በስርቆት ወይም በኃይል ወይም በሌላ መሰል ሁኔታዎች ወደ ሶስተኛ ወገን የተላለፉ ከሆነ 48 ሰዓት ውስጥ ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ላለው አካል ማሳወቅ አለበት።

## ክፍል አራት

## የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን ወደ አገር ዉስጥ ማስገባት፣ ማሸግ መለያ መስጠት፣ ማጓጓዝና ማከመቸት

### 9. ወደ አገር ዉስጥ ማስገባት

1. የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ከ18 ወር በታች የሆኑ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት የተከለከለ ነው፡፡
2. ማንኛውም ሰው በአካባቢና በሰው ጤና ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ለመገምገም የሚያስችል የኬሚካል ባህሪይ እና የንጥረ ነገር ይዘት መረጃ በተጠየቀ ጊዜ ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ላለው አካል ማቅረብ ይኖርበታል።
3. ሚኒስቴሩ ልዩ ፈቃድ በመስጠት የመጠቀሚያ ጊዜያቸው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተጠቀሰው ጊዜ በታች የሆኑ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች እንዲገቡ ሊፈቅድ ይችላል።
4. "ልዩ ፈቃድ" ማለት ለአስቸኳይ የአደጋ ጊዜ ወይም ወረርሽኝን ለመከላከል ወይም ለመሰል ዓላማዎች ሲባል ለአስገቢው የሚሰጥ የጽሑፍ ማረጋገጫ ነው፤ ዝርዝሩ በሚወጣው ደንብ ይወሰናል።

### 10. ማሸግና መለያ መስጠት

1. የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገባ፣ የሚያመርት፣የሚያከማች ወይም የሚያጓጉዝ ማንኛውም ሰው በመያዣያው ወይምበማሸጊያው ላይ፦

   ሀ የኬሚካሉ ምዝገባ ቁጥር፣ መጠሪያ ስም፣ መጠን እና የአገልግሎት ዓይነት፤

   ለ ኬሚካሉ የተመረተበት እና የአገልግሎት ማብቂያ ጊዜ፤

   ሐ የኬሚካሉ ባህሪይ እና የንጥረ ነገር ይዘት የሚያሳይ መረጃ፤ እና

   መ ኬሚካሉ የተመረተበት ሀገር፣ የአምራቹ ድርጅት ስም እና አድራሻ መረጃዎች የተለጠፉ መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት

   አለበት።

2. ማንኛውም ሰው የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን ማሸግ ወይም ዳግም ማሸግ የሚችለው መያዣያዉ፦

ሀ) አደጋ በማያደርስ ሁኔታ ኬሚካሉን ለማከማቸት፣ ለአያያዝ እና ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችል፤እና

ለ) በግልፅ ጎልቶ የሚታይ በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ የተዘጋጀ እና በቀላሉ የማይለቅ የመለያምልክት ያለው ከሆነ፣

ብቻ ነው፡፡

11.<u>የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን ማጓጓዝ</u>

የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን በማጓጓዝ ላይ የተሠማራ ማንኛውም ሰው ፦

1. ኬሚካሎች በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 10(1 የተገለፁ መረጃዎች በመያዣቸው ወይም በማሸጊያቸው ላይ የተለጠፈባቸው መሆኑን፤
2. ለኢንዱስትሪ አገልግሎት የሚውሉ ኬሚካሎችን ከመንገደኞች፣ ከእንስሳት ወይም ከምግብና መድሀኒት ጋር በአንድ ላይ አለመጓጓዙን፤
3. የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን ለማጓጓዝ የሚጠቀምበት ተሽከርካሪ የድንገተኛ አደጋ መከላከያ መሳሪያዎችን ያሟላ መሆኑን፤ እና
4. የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች በሚጫኑበት እና በሚራገፉበት ጊዜ የአደጋ ሥጋት የማያስከትሉ መሆኑን፤ ማረጋጥ አለበት፡፡

12.<u>የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን ማከማቸት</u>

1. ማንኛውም የኢንዱስትሪ ኬሚካል ማከማቻ፦

ሀ) የሕንፃ ዲዛይኑ፣ ግንባታና አደረጃጀት በሰው፣ በእንስሳት እና በአካባቢ ላይ አደጋ እንዳያስከትል ለዚሁ ተግባር ተብሎ የተጠቀሰውን ደረጃ በሚያሟላ መልኩ የተገነባ መሆን አለበት፤

ለ) የተበላሹ ወይም የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች ተለይተው የሚከማቹበት የተለየ ክፍል የተዘጋጀለት መሆን ይኖርበታል፤

ሐ) የኬሚካሎችን እና የመያዣቸውን ሁኔታ መደበኛ የሆነ የምልከታ ቁጥጥር ለማድረግ ተደራሽ የሆነ እና በመያዣቸው ላይ የደረሰን ጉዳትና ትክክለኛ ያልሆነ መለያን ለማስተካከል የሚያስችል ሥርዓት የተዘረጋለት መሆን ይኖርበታል።

2. የደረቅ ወደቦች እና ኤርፖርቶች ጊዜያዊ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች ማቆያ ወይምማከማቻ የሚሆን የተለየ ስፍራ ማዘጋጀት አለባቸው፡፡

13.**የመተባበር ግዴታ**

1. አግባብነት ያላቸው አካላት ኬሚካሎች በሰው እና በእንስሳት ጤና እንዲሁም በአካባቢ ደህንነት ላይ ጉዳት በማያሥከትል ሁኔታ እንዲያዙ፣ ጥቅም ላይ እንዲውሉ እና እንዲወገዱ በቅንጅት መስራት አለባቸው።
2. አግባብ ያላቸው አካላት የሚያሥተዳድሯቸው ኬሚካሎች የተመዘገቡ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡
3. አግባብነት ያላቸው አካላት ሃላፊነት እና ሚና ዝርዝር የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል።

14.**የክትትል እና የቁጥጥር ሃላፊነት**

ሚኒስቴሩ በዚህ አዋጅ እና ይህን አዋጅ ተከትለው በሚወጡ ሕጎች መሠረት ኬሚካሎችን የተመለከቱ ተግባራትን በበላይነት የመከታተል፣ተፈፃሚነቱን የመቆጣጠር ኃላፊነት ተሰጥቶታል።

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

15.**ቅጣት**

ማንኛውም ሰው፡-

1. የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችን በሚቃረን ሁኔታየኢንዱስትሪ ኬሚካሎች እንቅስቃሴ ላይ የተሳተፈ እንደሆነ፣ ወይም
2. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከሚኒስቴሩ ሳያገኝ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን ያመረተ፣ ከውጭ ሀገር ያስገባ፣ የተጠቀመ ወይም ያከፋፈለ እንደሆነ፤ ወይም
3. አግባብ ባለው የደረጃ አውጪ አካል የወጣውን የደረጃ መስፈርት የማያሟላ የኢንዱስትሪ ኬሚካል ያመረተ፣ ከውጭ ሀገር ያስገባ፣ የተጠቀመ ወይም ያከፋፈለ እንደሆነ፤ ወይም
4. በዚህ አዋጅ የተጠቀሱትን መረጃዎች ወይም ሰነዶችን በሚመለከት ሆን ብሎ የሀሰት ማስረጃ ያቀረበ እንደሆነ፤ ወይም
5. ያልተመዘገቡ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን ያመረተ፣ ከውጭ ሀገር ያስገባ፣ የተጠቀመ፣ ወይም ያከፋፈለ እንደሆነ፤ ወይም
6. የአገልግሎት ጊዜ በማብቃቱ ወይም በመበላሸቱ ምክንያት ጥቅም ላይ የማይውል የኢንዱስትሪ ኬሚካል ለሚኒስቴሩ ሪፖርት ያላቀረበ እንደሆነ፤

ከሁለት ዓመት በማያንስ እና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራትና ከ100,000 ብር በማያንስእና 500,00 ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮይቀጣል፡፡

16.<u>**ደንብ እና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**</u>

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም አስፈላጊ የሆኑ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅን እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1 መሰረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣዉ ይችላል።

17.<u>**ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጎች**</u>

ይህንአዋጅ የሚቃረን ማናቸውም ሕግ ወይም የአሰራር ልማድ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

18. <u>**አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**</u>

ይህአዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮየጸና ይሆናል።

**አዲስ አበባ መጋቢት 27 ቀን 2010 ዓ.ም**

**ሙላቱ ተሾመ (ዶ)ር**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## አዋጅ ቁጥር 109/) 2010

## የአደገኛ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ቁጥጥር አዋጅ

የአደገኛ ቆሻሻዎች በሀገራችን ከሚታዩ አካባቢያዊ ችግሮች መካከል ዋነኛ በመሆኑ፤

ከአደገኛ ቆሻሻዎች አያያዝ እና አወጋገድ ጉድለት ሣቢያ ተያይዞ በአካባቢ ላይ እየደረሰ ያለውን የብክለት ችግር መከላከልና መቆጣጠር በማስፈለጉ፤

አደገኛ ቆሻሻዎች በአግባቡ ባለመያዛቸው በሰው እና በእንስሳት ጤና እንዲሁም በአካባቢ ላይሊያደርሱ የሚችሉትን ጉዳት ለመከላከልና የአደገኛ ቆሻሻዎች እንቅስቃሴ፣ መመንጨት፣ መጓጓዝ፣ መከማቸት፣ መታከም፣ ለዳግም እና መልሶ ጥቅም መዋል እና ማስወገድ ለመቆጣጠር የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት በማስፈላጉ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 55 (1) መሠረት የሚከተለውታውጀል፡፡

## ምዕራፍ አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የአደገኛ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1090/2010 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

   1. "የባማኮ ስምምነት" ማለት አደገኛ ቆሻሻዎች ወደ አፍሪካ እንዳይገቡ ለማገድ እና በአፍሪካ አገሮች መካከል የአደገኛ ቆሻሻዎችን ድንበርዘለል ዝውውር እንዲሁም አወጋገድ ለመቆጣጠር የተደረገውን የባማኮ ስምምነት ነው፤
   2. "የባዛል ስምምነት" ማለት የአደገኛ ቆሻሻ ድንበር ዘለል እንቅስቃሴ፣ ዝውውርና ማስወገድን ለመቆጣጠር የተደረገው የባዝል ስምምነት ነው፣፤
   3. "ማስወገድ" ማለት በዚህ አዋጅ አባሪ ሦስት ላይ የተጠቀሰውን ማንኛውም የአደገኛ ቆሻሻ አወጋገድ የሚያካትት ድርጊት ነው፤
   4. "አስወጋጅ" ማለት አደገኛ ቆሻሻን በማስወገድሥራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው ነው፤
   5. "አካባቢ'"ማለት በመሬት፣ በከባቢ አየር፣ በአየርሁኔታ እና በአየር ንብረት፣ በውሃ፣ በህያዋን፣ በድምፅ፣ በሽታ፣ በጣዕም፣ በማህበራዊ ጉዳዮች እና በሥነ-ውበት ሳይወሰን፣ በተፈጥሯዊ ሁኔታዎች በሰው አማካኝነት ተሻሽለው ወይም

ተለውጠው የሚገኙ ነገሮች በሙሉና ያሉበት ቦታ እንዲሁም መጠናቸው ወይም ሁኔታቸውን ወይም ደግሞ የሰው ወይም የሌሎች ህያዋንበነ ሁኔታን የሚነኩ ተስተጋብሮቶቻቸው ድምር ነው፤

6. "ለአካባቢ ተስማሚ የቆሻሻ አያያዝ" ማለት በአደገኛ ቆሻሻዎች አማካኝነት ሊከሰቱ የሚችሉ አሉታዊ ተፅዕኖዎችን የሰው ጤና፣አካባቢን እና ሀብት ደህንነት በሚጠብቅ መልኩ መያዛቸውን ለማረጋገጥ ሊተገበሩ የሚችሉ ሁሉንም እርምጃዎችን መውሰድነው፤
7. "ላኪ" ማለት አደገኛ ቆሻሻን ከኢትዮጵያ ወደውጭ ሀገር የሚልክ ሰው ነው፣
8. "አመንጪ" ማለት ማንኛውንም አደገኛ ቆሻሻን የሚያመነጭ ሰው ሲሆን፣ አመንጪው ባልታወቀበት ሁኔታ አደገኛ ቆሻሻውን በማወቅ ወይም ባለማወቅ በይዞታው ሥር አድርጎ የሚገኘው ሰው ነው፤
9. "አደጋ" ማለት በሰው ወይም በእንስሳት ጤና፣ በአካባቢ፣ በብዝሃ ህይወት እና በንብረት ላይአሉታዊ ተጽእኖ ወይም ጉዳት ሊያስከትል የሚችል የአንድ ነገር አካል ወይም ሁኔታ ተፈጥሯዊ ባህሪ ነው፤
10. "አደገኛ ቆሻሻ" ማለት በዚህ አዋጅ በአባሪ አንድ የተዘረዘሩ ቆሻሻዎች ምድብ ውስጥ የሚካተት እና በአባሪ ሁለት የተዘረዘሩ ባህሪያት ያላቸውን ቆሻሻዎች የሚያጠቃልል እና ሚኒስቴሩ በመመሪያ አደገኛ ቆሻሻ በማለት የሚወስናቸውን ማንኛውንም ቆሻሻ ይጨምራል፤
11. "አስመጪ" ማለት አደገኛ ቆሻሻን ከውጭ ሀገርወደ ኢትዮጵያ የሚያስገባ ሰው ነው፤
12. "መለያ" ማለት የተፃፈ፣ የታተመ ወይም በምስል የተቀረፀና በአደገኛ ቆሻሻ ቀጥተኛ መያዣና በቀጥተኛ መያዣዎቹ ውጫዊ መያዣ ወይም መጠቅለያ ላይ በሚታይ መልኩ የተለጠፈ ወይም ከእነዚሁ ጋር የተያያዘ መግለጫ ነው፤
13. "ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለዉጥ ሚኒስቴር[56] ወይም ሚኒስትር ነው፤
14. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

---

[56] 25/08 (2011) አ. 1097 አንቀጽ 36(17) የአካባቢ ደንና አየር ለውጥ ኮሚሽን ሆኗል በአዋጁ ውስጥ ሚንስቴር ሚለው ኮሚሽን በማለት ተተክቶ ይነበብ፡፡

15. “ብክለት” ማለት በዚህ አዋጅ ወይም አግባብነት ባለው ሌላ ሕግ የተደነገገን ማንኛውም ግዴታ፣ ማዕቀብ ወይም ገደብ ጥሶ የማንኛውም አካባቢ ክፍል ቁሳዊ ጨረራዊ፣ ሙቀታዊ፣ ንጥረነገራዊ፣ ሥነ-ሕይወታዊወይም ሌላ ባህርይን በመለወጥ የተፈጠረ፣ በሰው ጤና ወይም በጎነት ወይም ደግሞ በሌሎች ሕያዋን ላይ አደገኛ የሆነ ወይም አደገኛ ሊሆን የሚችል ሁኔታ ነው፤
16. “መልሶ መጠቀም” ማለት አንድን አደገኛ ቆሻሻ አዲስ ሥራ ወይም አገልግሎት መጠቀም ነው፤
17. “መልቀቅ” ማለት በማወቅም ይሁን በቸልተኝነት አንድ አደገኛ ቆሻሻን ወደ አካባቢ ማስወጣት ነው፤
18. “አግባብነት ያለው ባለስልጣን" ማለት የአካባቢ የደንና አየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር እና የሚመለከተው የክልል መንግስት ወይም የከተማ አስተዳደር ባለስልጣን ነው፤
19. “በድጋሚ መጠቀም” ማለት አደገኛ ቆሻሻን ቀድሞ ለተሰራበት ዓላማ በድጋሜ ጥቅም ላይ የሚውልበት አሰራር ነው፤
20. “ማከማቻ ማዕከል” ማለት አደገኛ ቆሻሻ ለማከማቸት የተለየ ስፍራ ነው፤
21. “አጓጓዥ” ማለት አደገኛ ቆሻሻዎችን በማጓጓዝ ሥራ ላይ የተሰማራ ሰው ነው፤
22. “ማከም” ማለት የአደገኛ ቆሻሻዎች ጎጂነትን ለመቀነስ ወይም ለማስቀረት የሚከናወን ተግባር ነው፤
23. “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 47(1) የተመለከተ ማንኛውም ክልል ሲሆን አዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮች ይጨምራል፤
24. በወንድ ፆታ የተገለፀው ማንኛውም አገላለጽ ሴትንም ይጨምራል፡፡

3. <u>ዓላማ</u>

ይህ አዋጅ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፦

1. አካባቢያዊ ተቀባይነት ያለው የአደገኛ ቆሻሻዎች አያያዝና አወጋገድ ሥርዓት መዘርጋት፤
2. በአደገኛ ቆሻሻ አያያዝ ጉድለት በሰው ወይም በእንስሳት ጤና፣ በአካባቢ፣ በብዝሃ ህይወት እና በንብረት ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ማስቀረት፡፡

4. **የተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ አዋጅ፦

1. በዚህ አዋጅ በአባሪ አንድ የተዘረዘሩ ቆሻሻዎች ምድብ ውስጥ በሚካተቱ ቆሻሻዎች ላይ እና በአባሪ ሁለት የተዘረዘሩ ባህሪያት ያላቸው ቆሻሻዎች ላይ እንዲሁም ሚኒስቴሩ በመመሪያ አደገኛ ቆሻሻ በማለት የሚወስናቸውን ማንኛውንም ቆሻሻዎች ላይ፤
2. በመላ ሃገሪቱ የአደገኛ ቆሻሻ በሚያመነጭ፣ በድጋሚ በሚጠቀም፣ መልሶ በጥቅም ላይ በሚያውል፣ በሚያከማች በሚያጓጉዝ ወይም በሚያስወግድ ማንኛውም ሰው ላይ፤ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## የአደገኛ ቆሻሻ አያያዝ

5. **የንጹህ ምርት መርሆዎች**

ማንኛውም የምርት አምራች አደገኛ ቆሻሻን ለመቀነስ የሚከተሉትን የንጹህ ምርት መርሆዎች መከተል አለበት፥፦

1. በአመራረት ሂደት ውስጥ በጥሬ ዕቃዎች ላይ ሊገኝ የሚችለውን አደገኛ ንጥረ ነገር በመቀነስ ወይም በማስወገድ የአደገኛ ቆሻሻ ልቀትን መቀነስ፤
2. የምርት ሂደትን በመቆጣጠር፦

   ሀ የግብዓቱን ወይም የምርቱን ብክነት መቀነስ፣

   ለ የምርቱ የአገልገሎት ዘመን ሲያበቃ እንዲሰበሰብና ለዳግም ጥቅም ወይም መልሶ ጥቅም ላይ የሚውልበትን ሁኔታ መፍጠር፡፡

6. **የአደገኛ ቆሻሻ አመንጪ ኃላፊነት**

የአደገኛ ቆሻሻ አመንጪ የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩበታል፦

1. አደገኛ ቆሻሻን የመሰብሰብ፣ የመለየት፣ የማስወገድ ወይም ፈቃድ ባለው አካል እንዲሰበሰብና መልሶ ጥቅም ላይ እንዲውል ወይም እንዲወገድ ማድረግ፤
2. አደገኛ ቆሻሻው የተከማቸበት ኮንቴነር በአግባቡ መታሸጉን እንዲሁም በግልፅ ሊታይ በሚችል መልኩ በአማርኛ እና በእንግሊዝኛ ቋንቋ መለያው መጻፉን ማረጋገጥ፣፤
3. በአደገኛ ቆሻሻ ጊዜያዊ ማከማቻ ማዕከሉ የሚገኙትን የአደገኛ ቆሻሻ ዓይነትና መጠን የተመለከተ መዝገብ መያዝ፤ እና መዝገቡን በተቆጣጣሪ አካል በተጠየቀ ጊዜ የማሳየት፣

4. በጊዜያዊ የማከማቻ ሥፍራ አደገኛ ቆሻሻን ከአንድ ወር በላይ ያለማከማቸት፡፡

7. **አደገኛ ቆሻሻ ላይ መለያ ስለማድረግ**

1. ማንኛውም አደገኛ ቆሻሻ አመንጭ፣ አከማች፣ አጓጓዥ ወይም አስመጭ ለአደገኛ ቆሻሻው ግልጽ የሚታይ መለያ ማድረግ አለበት፡፡
2. የአደገኛ ቆሻሻ መለያው የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፦

   ሀ የአመንጪው ሙሉ አድራሻ፤

   ለ የአደገኛ ቆሻሻውን ዓይነት፣ መጠን እና ባህሪ፤

   ሐ መደበኛ አያያዝ እና የአያያዝ ዘዴ፣
3. ማንኛውም አደገኛ ቆሻሻ አመንጭ፣ አከማች፣ አጓጓዥ ወይም አስመጭ በቆሻሻው ላይ ወይም መያዣው ላይ በአማርኛ እና በእንግሊዝኛ ቋንቋ ወይም እንደ አስፈላጊነቱ በሌሎች የአገሪቱ ቋንቋዎች በግልጽ የሚታይየማስጠንቀቂያ ወይም የማሳሰቢያ ጽሑፍ ወይም ምልክት ማድረግ አለበት፡፡

8. **አደገኛ ቆሻሻን ስለማጓጓዝ**

1. አደገኛ ቆሻሻ በማጓጓዝ ሥራ ላይ ለመሰማራት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ከሚኒስቴሩ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡
2. ሚኒስቴሩ ፈቃድ ጠያቂው ለዚሁ ዓላማ በሚወጣ መመሪያ የተመለከተውን መስፈርት ማሟላቱን ሲያረጋገጥ በ30 የሥራ ቀናት ውስጥ ፈቃድ ይሰጣል፣ አመልካቹ መስፈርቶቹን ያላሟላ እንደሆነ በአስራ አምስት የስራ ቀናት ውስጥ ተጨማሪ መረጃ ማቅረብ እንደሚችል ወይም ፈቃዱ የማይሰጥ ስለመሆኑ በጽሑፍ ያሳውቃል፡፡
3. አመልካቹ በውሳኔው ላይ ቅሬታ ካለው በ15 የሥራ ቀናት ውስጥ ለሚኒስትሩ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፡፡
4. ማንኛውም አደገኛ ቆሻሻ አጓጓዥ ቆሻሻው በሰው ወይም በእንስሳት ጤንነት ወይም በአካባቢ ላይ ጉዳት በማያደርስ መልኩ እንዲሁም ቆሻሻ በድጋሚ በጥቅም ላይ ሊውል የመቻል ሁኔታን እና ቀጣይ ማከምን በማያናጋ መንገድ ማጓጓዝ አለበት።
5. አደገኛ ቆሻሻ በማጓጓዝ ሥራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው ለአሽከርካሪዎቹ ስለአደገኛቆሻሻ አያያዝ እና ማጓጓዝ ላይ ስልጠናእንዲወስዱ ማድረግ አለበት፡፡

6. አደገኛ ቆሻሻ በማጓጓዝ ሥራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ተቋም በድንገተኛ ሁኔታ በሚያጋጥም ልቀት በሰው ወይም በእንስሳት ጤንነት ወይም በአካባቢ ላይ ሊደርሱ ከሚችሉ ጉዳቶች የሚመነጭ የኃላፊነት ካሣን ለመክፈል እንዲቻል ለሚጓጓዘው አደገኛ ቆሻሻ በቂ የመድህን ሽፋን የተደረገለት መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡
7. አደገኛ ቆሻሻ በማጓጓዝ፣ በማመንጨት፣ በማከማቸትና በድጋሚ መጠቀም፣ መልሶ በመጠቀምና ማከምን እንዲሁም በማስወገድ ሂደት አካባቢውን፣ ሰውን እና እንስሳትን የበከለና ለጉዳት የዳረገ ማንኛውም አካል የካሳ ክፍያ ይከፍላል፤ የካሳ ክፍያ አፈፃፀሙም ከዚህ በፊት በወጣው የብክለት አዋጅ ድንጋጌ መሠረት የሚፈፀም ይሆናል፡፡
8. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው ለዚሁ ዓላማ በወጣው መመሪያ የተመለከተውን መስፈርት በማሟላት ፍቃዱን በየዓመቱ ማሳደስ አለበት፡፡

9. <u>ከአደገኛ ቆሻሻ ጭነት ጋር የሚያያዙ ሰነዶች</u>

1. አደገኛ ቆሻሻ በሚጓጓዝበት ወቅት ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተሰጡ የፍቃድ ሰነዶች በማንኛውም ጊዜ አጓጓዡ ዘንድ መቀመጥ አለባቸው፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ተጨማሪ መረጃዎችን የሚያሳይ ሰነድ አጓጓዡ መያዝ አለበት፡-

   ሀ) የሚጓጓዘው ጥቅል የተነሳበት ቀን እና የሚደርስበት ቦታ ስምና ሙሉ አድራሻ፣

   ለ) የአደገኛ ቆሻሻ ሳይንሳዊና የተለምዶ ስሞች፣

   ሐ) የጥቅሎቹ ቁጥርና ዓይነት እንዲሁም ጠቅላላ መጠን፤

   መ) የአደገኛ ቆሻሻ ላኪና ተቀባይ ሙሉ አድራሻ፣

   ሠ) በአደጋ ጊዜ ሊወሰዱ የሚገባቸውን የጥንቃቄ እርምጃዎችን ያካተተ መረጃ፡፡
3. አጓጓዡ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (2) የተጠቀሱትን ሰነዶች አግባብ ባለው ባለሥልጣን የተሰየመ ተቆጣጣሪ ሲጠይቅ በማንኛውም ጊዜ የማሳየት ግዴታ አለበት፡፡

10.**<u>በማጓጓዝ ወቅት ሊወሰዱ የሚገባቸው ጥንቃቄዎች</u>**

1. አደገኛ ቆሻሻን የሚያጓጉዝ ማንኛውም አሽከርካሪ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 9 የተጠቀሱትን ሰነዶች ከተቀበለ በኋላ የጭነቱን ሰነዶች ከይዘቱ ጋር መጣጣማቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡
2. በመጓጓዝ ላይ ያለ አደገኛ ቆሻሻ በጉዞ ወቅት አቀማመጡ እንዳይቀያየር እና እንዳይወድቅ በጥብቅ መታሰር አለበት፡፡
3. ቆሻሻው በሚጓጓዝበት ወቅት አደጋ ሲያጋጥም አሽከርካሪው ቀጥሎ የተዘረዘሩትን እርምጃዎችን መውሰድ አለበት፦
   ሀ) ተሽከርካሪው የቆመበትና ጭነቱ የፈሰሰበትን አካባቢ መከለል፣
   ለ) የአደጋ ጊዜ የእርዳታ ጥሪ ማድረግ፣
   ሐ) ስለተፈጠረው አደጋ ወይም ስለ አፈሳሰሱ ለአስጫኙ፣ ለጥቅሉ ተቀባይና አግባብላለው ባለሥልጣን ወዲያውኑ ማሳወቅ፡፡

11.**<u>አደገኛ ቆሻሻ ስለማከማቸ</u>**

1. አደገኛ ቆሻሻ በማከማቸት ሥራ ለመሰማራት የሚፈልግ ማንኛውም ከሚኒስቴሩ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡
2. አደገኛ ቆሻሻ ለማከማቸት የሚቀርበው ማመልከቻ ለውሣኔ ከመቅረቡ በፊት ሚኒስቴሩ የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላታቸውን ማረጋገጥ አለበት፦
   ሀ አደገኛ ቆሻሻውን በጥንቃቄ ለመያዝ የሚያስችል በቂ መሣሪያዎች እና ሌሎች አስፈላጊ ቁሳቁሶች በማከማቻ ስፍራ ስለመኖራቸው፤
   ለ በማከማቻ ስፍራ በቂ የሆነ የጥበቃ እና የጤናና የቅድመ ጥንቃቄ ቁሳቁሶች መኖራቸውን፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ እንደ አስፈላጊነቱ፦
   ሀ ፈቃድ ለመስጠት ሌሎች መሟላት ያለባቸውን ሥርዓቶችና ተጨማሪ ቅድመ ሁኔታዎች ያዘጋጃል፤
   ለ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የአደገኛ ቆሻሻ ማከማቻ ስፍራ ዝርዝር መስፈርት ያዘጋጃል፡፡
4. አደገኛ ቆሻሻ ለማከማቸት ፈቃድ የጠየቀው ሰው ፈቃዱ ከተሰጠው በኋላ ሥራ ከመጀመሩ በፊት በሰው፣ በእንስሳት ወይም በአካባቢ ላይ የሚደርስ ጉዳት ኃላፊነትን ለመሸፈን ኢንሹራንስ መግባት አለበት፡፡

5. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ፈቃድ ጠያቂው ሰው መስፈርቱን ማሟላቱን ሲያረጋገጥ በ30 የሥራ ቀናት ውስጥ ፈቃድ ይሰጣል፤ አመልካቹ መስፈርቶቹን ያላሟላ እንደሆነ በአስራ አምስት የስራ ቀናት ውስጥ ተጨማሪ መረጃ ማቅረብ እንደሚችል ወይም ፈቃዱ የማይሰጥ ስለመሆኑ በጽሑፍ ያሳውቃል፡፡
6. አመልካቹ በውሳኔው ላይ ቅሬታ ካለው በ15 የሥራ ቀናት ውስጥ ለሚኒስትሩ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፡፡
7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው መስፈቶችን በማሟላት ፍቃዱን በየሁለት ዓመቱ ማሳደስ አለበት፡፡

12.**<u>በማከማቸት ወቅት ሊወሰዱ የሚገቡ የጥንቃቄ እርምጃዎች</u>**

ማንኛውም የአደገኛ ቆሻሻ ማከማቻ ማዕከል ባለቤት ወይም አስተዳዳሪ፦

1. ከተፈቀደለት ሰው ውጪ ወደ አደገኛ ቆሻሻ ማከማቻ ማዕከሉ ውስጥ እንዳይገባ መከልከል አለበት፤
2. በማከማቻ ማዕከሉ ውስጥ የሚገኙ አደገኛ ቆሻሻዎች መታሸጋቸውን፣ መለያ የተጻፈባቸው እንዲሁም ተለይተው መቀመጣቸውን ማረጋገጥ አለበት፤
3. በማከማቻው ስፍራ የሚገኙ አደገኛ ቆሻሻዎች ዓይነት፣ ባህሪና መጠን የተመለከተ መረጃ መያዝና በማንኛውም ጊዜ ሲጠየቅ ለተቆጣጣሪው ማሳየት አለበት፣
4. ያልታሰበ አደጋን ለመከላከል የሚያስችሉና ለቅድመ ጥንቃቄ የሚረዱ መሣሪያዎች በተገቢው ስፍራ መኖራቸውን ማረጋገጥ አለበት፤
5. የአደገኛ ቆሻሻን ያልታሰበ ልቀት ለመቆጣጠር የዕለት ተዕለት ቁጥጥር በባለሙያ እንዲካሄድ ማድረግ አለበት፣
6. የአደገኛ ቆሻሻ ማከማቻ ሥፍራውን ወሰን የሚያሳይ ምልክት ማድረግ አለበት
7. በአደገኛ ቆሻሻ አያያዝ ላይ የተሰማሩት ሠራተኞቹ በመስኩ ተገቢውን ሥልጠና ያገኙ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

13.**<u>አደገኛ ቆሻሻዎችን በድጋሚ ጥቅም ላይ ስለማዋል</u>**

አደገኛ ቆሻሻዎች በሰው እና በእንስሳት ጤናና በአካባቢ ላይ ጉዳት የማያደርሱ መሆናቸው ተፈትሾ ሲረጋገጥ በድጋሚ ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ፡፡

14.**አደገኛ ቆሻሻዎችን ማከምና መልሶ ጥቅም ላይ ስለማዋል**

1. አደገኛ ቆሻሻን ለማከምና መልሶ ጥቅም ላይ በማዋል ሥራ ላይ ለመሰማራት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ለሚኒስቴሩ ማመልከቻ በማቅረብ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለሚኒስቴሩ ማመልከቻ ያቀረበ ማንኛውም ሰው የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላቱ ሲረጋገጥ ፈቃድ ይሰጠዋል፦

   ሀ) ሚኒስቴሩ በመመሪያ የወሰናቸውን የምዝገባ መስፈርቶችን ማሟላቱ፤

   ለ) ለማከም ወይም መልሶ ጥቅም ላይ ለማዋል ማዕከሉና መልሶ ጥቅም ላይ የማዋል አሰራሩ ሚኒስቴሩ ያዘጋጃቸውን መስፈርቶች ያሟሉ መሆናቸው፤ እና

   ሐ) በማከም ወይም መልሶ ጥቅም ላይ በማዋል ሂደት የሚመነጩ አደገኛ ቆሻሻዎች ለአካባቢ ተስማሚ በሆነ መንገድ ማስወገድ የሚችል ሥርዓት ያዘጋጀ መሆኑ፡፡
3. ሚኒስቴሩ ፈቃድ ጠያቂው ሰው መስፈርቱን ማሟላቱን ሲያረጋገጥ በ30 የሥራ ቀናት ውስጥ ፈቃድ ይሰጣል፤ አመልካቹ መስፈርቶቹን ያላሟላ እንደሆነ በአስራ አምስት የስራ ቀናት ውስጥ ተጨማሪ መረጃ ማቅረብ እንደሚችል ወይም ፈቃዱ የማይሰጥ ስለመሆኑ በጽሑፍ ያሳውቃል፡፡
4. አመልካቹ በውሳኔው ላይ ቅሬታ ካለው በ15 የሥራ ቀናት ውስጥ ለሚኒስትሩ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው መስፈርቶችን በማሟላት ፍቃዱን በየሁለት ዓመቱ ማሳደስ አለበት፡፡

15.**አደገኛ ቆሻሻዎችን መልሶ በጥቅም ላይ ከማዋልእና ከማስወገድ በፊት የሚከናወን ህክምና እና አያያዝ**

1. አደገኛ ቆሻሻ በሚከማችበት ወቅት በአያያዝ ጉድለት ሳቢያ ሊደርስ የሚችል የዕቃ መሰበርንእና ለአደጋ ሊያጋልጡ የሚችሉ ቁሶች መለቀቅ ጠንቅን ለማስቀረት ተገቢ የሆኑ የጥንቃቄ እርምጃዎች መውሰድ አለባቸው፡፡
2. በመልሶ ጥቅም ላይ ማዋያ ማዕከላት ሊያጋጥሙ የሚችሉ አደጋዎችን ለመቀነስ እና ለማስቀረት አደገኛ ቆሻሻን መልሶ ጥቅም ላይ በማዋል ሥራ ላይ የተሰማሩት ሠራተኞቹ በመስኩ ተገቢውን ሥልጠና ያገኙ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

3. በመልሶ ጥቅም ላይ ማዋያ እና ማስወገጃ ማዕከላት ማናቸውም እንቅስቃሴዎች ላይ የተሰማሩ ሠራተኞች የሥራ ላይ ደህንነት ለማረጋገጥ ተገቢው ቁሳቁሶች መሟላት አለባቸው፡፡
4. አደገኛ ቆሻሻን በማከም ሥራ ላይ የተሰማራሰው የሚያክመውን የቆሻሻ ዓይነት፣ መጠንና የህክምና ዘዴውን ለሚኒስትሩ ማሳወቅ አለበት፡፡

16.<u>የአደገኛ ቆሻሻ አወጋገድ</u>

1. አደገኛ ቆሻሻ ህክምና ከተደረገለት በኋላ መልሶ ጥቅም ላይ ለማዋል የማይቻል መሆኑ ከተረጋገጠ መወገድ አለበት፡፡
2. አደገኛ ቆሻሻ የማስወገድ ተግባር በዚህ አዋጅ አባሪ 3 በተዘረዘሩት አማራጮች መሠረት መከናወን አለበት፡፡

## <u>ምዕራፍ ሦስት</u>

## <u>ድንበር ዘለል የአደገኛ ቆሻሻ እንቅስቃሴ</u>

17.<u>ድንበር ዘለል የአደገኛ ቆሻሻ እንቅስቃሴ</u>

1. ድንበር ዘለል የአደገኛ ቆሻሻ እንቅስቃሴ ላይ ለመሰማራት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ለሚኒስቴሩ ማመልከቻ በማቅረብ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡
2. ሚኒስቴሩ ፈቃድ ጠያቂው ሰው ለዚሁ ዓላማ በወጣው መመሪያ የተመለከተውን መስፈርት ማሟላቱን ሲያረጋገጥ በ30 የሥራ ቀናት ውስጥ ፈቃድ ይሰጣል፤ አመልካቹ መስፈርቶቹን ያላሟላ እንደሆነ በአስራ አምስት የስራ ቀናት ውስጥ ተጨማሪ መረጃ ማቅረብ እንደሚችል ወይም ፈቃዱ የማይሰጥ ስለመሆኑ በጽሑፍ ያሳውቃል፡፡
3. አመልካቹ በውሳኔው ላይ ቅሬታ ካለው በ15 የሥራ ቀናት ውስጥ ለሚኒስትሩ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፡፡
4. ማንኛውንም አደገኛ ቆሻሻ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት የተከለከለ ነው።
5. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ አደገኛ ቆሻሻ ተለይቶ ለታወቀ ዓላማ ሃገር ውስጥ እንዲገባ የሚፈቅድ መመሪያ ሚኒስቴሩ ያወጣል።
6. ከሀገር የሚወጡ አደገኛ ቆሻሻዎች በባዝል ወይም በባማኮ ስምምነት መሰረት በቅድሚያ የሚጓጓዙበት ሀገር ይሁንታ መገኘቱን ሚኒስቴሩ ማረጋገጥ አለበት፡፡
7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው መስፈቶችን በማሟላት ፍቃዱን በየዓመቱ ማሳደስ አለበት፡፡

18.<u>ሕገወጥ የአደገኛ ቆሻሻ እንቅስቃሴ</u>

1. በዚህ አዋጅ መሰረት የአደገኛ ቆሻሻ እንቅስቃሴ ሕገወጥ ነው የሚባለው፦

ሀ ከሚኒስቴሩ የተሰጠ ፈቃድ የሌለው እንደሆነ፣፤

ለ ከሚኒስቴሩ የተገኘው ፈቃድ በማጭበርበር፣ የሀሰት መረጃ በማቅረብ ከሆነ፣ እንዲሁም አደገኛ ቆሻሻውን በተገቢው መንገድ የማይገልፅ እንደሆነ፤

ሐ በማጓጓዣ ሰነዱ ላይ ከተሰጠው መዘርዝር ጋር የማይዛመድ መሆኑ ሲረጋገጥ፤

መ የባዝል ስምምነትን፣ ኢትዮጵያ ያጸደቀቻቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ወይም ማናቸውንም የሀገራችን የአደገኛ ቆሻሻዎች አያያዝ የሚመለከቱ የሕግ ድንጋጌዎች የጣሰ እንደሆነ፤

2. አደገኛ ቆሻሻ በሕገ ወጥ መንገድ ወደ ሀገር ውስጥ የገባ እንደሆነ፣ ቆሻሻውን ወደ ሀገር ውስጥያስገባው ሰው በራሱ ወጪ ቆሻሻው ወደ ሀገር ውስጥ በገባ በ90 ቀናት ውስጥ ወደ መጣበት እንዲመለስ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

3. ሚኒስቴሩ አግባብ ካላቸው መንግሥታዊ አካላት ጋር በመተባበር በዚሁ አንቀጽ ንዑስአንቀጽ (2) የተደነገገውን ተከታትሎያስፈጽማል።

## <u>ምዕራፍ አራት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

19.<u>በክልሎች መካከል የሚደረግ የአደገኛ ቆሻሻ ዝውውር</u>

1. እያንዳንዱ ክልል ወደ ሌላ ክልል በመላክ የሚያስወግደውን አደገኛ ቆሻሻ መጠን መቀነስ አለበት፡፡

2. በሀገር ውስጥ የሚደረግ ማንኛውም ክልል ተሻጋሪ አደገኛ ቆሻሻ ለማጓጓዝ ከሚኒስቴሩ ፈቃድ ሊያገኝ የሚችለው ከቆሻሻው መድረሻ ክልል የአካባቢ ጥበቃ አግባብነት ካለው ተቋም በዝውውሩ መስማማቱን በጽሑፍ ሲያረጋግጥ ብቻ ይሆናል፡፡

3. አደገኛ ቆሻሻን ከአንድ ክልል ወደ ሌላ ክልል ወይም የከተማ አስተዳደር በመውሰድ ማስወገድ የሚቻለው ተረካቢው ክልል ቆሻሻውን መልሶ ለመጠቀም ወይም አካባቢያዊ ተቀባይነት ባለው መንገድ ለማስወገድ አቅም እንዳለው እና ፈቃደኝነቱን ለላኪው በጽሁፍ ሲያሳውቅ ብቻ ነው፡፡

20.<u>ፍቃድን የማገድና የመሰረዝ ስልጣን</u>

1. ሚኒስቴሩ በማንኛውም ጊዜ አደገኛ ቆሻሻ ለማጓጓዝ፣ ለማከማቸት፣ መልሶ ጥቅም ላይ ለማዋል ወይም አደገኛ ቆሻሻ ድንበር ዘለል እንቅስቃሴ ላይ ለመሰማራት ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው ቅድመ ሁኔታዎች ወይም መስፈርቶችን አጓድሎ ሲገኝ ወይም የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ተላልፎ ሲገኝ በ15 የሥራ ቀናት ውስጥ ቅድመ ሁኔታዎችን ወይም መስፈርቶችን እስኪያሟላ ድረስ ፈቃዱን ሊያግድ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ፈቃዱ የታገደበት ሰው በጊዜ ገደቡ ውስጥ በጉድለት የታየውን ቅድመ ሁኔታ ወይም መስፈርት ሳያሟላ የሚቀር ከሆነ ሚኒስቴሩ ፈቃዱን ሊሰርዝ ወይም እንቅስቃሴውን ወዲያውኑ እንዲያቆም ሊወስን ይችላል፡፡
3. ማንኛውም ፈቃዱ የታገደበት ወይም የተሰረዘበት ሰው በእገዳውና በስረዛው ወቅት አደገኛ ቆሻሻውን በአግባቡ መያዝ አለበት።

21.<u>ቅጣት</u>

በወንጀል ህጉ የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም ሰው፦፡

1. ያለ ሚኒስቴሩ ፈቃድ አደገኛ ቆሻሻን ወደሀገር ውስጥ ያስገባ እንደሆነ ከ 5 ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከ500ሺ ብር በማያንስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፣
2. ያለ ሚኒስቴሩ ፈቃድ ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባውን አደገኛ ቆሻሻ በ90 ቀናት ውስጥ ወደመጣበት ሀገር ያልመለሰ ወይም ያላስወገደ እንደሆነ ከ 5 ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከ500ሺ ብር በማያንስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤
3. በሕገ-ወጥ መንገድ ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባው አደገኛ ቆሻሻ አካባቢን የበከለ እንደሆነ ከ10ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከአምስት ሚሊዮን ብር በማያንስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤
4. በሕገ-ወጥ መንገድ ሀገር ውስጥ ያስገባው አደገኛ ቆሻሻ አካባቢን የበከለ ሆኖ የተበለከለውን አካባቢ ያላከመ እንደሆነ ከ20 ዓመት በማይበልጥ ፅኑእስራት እና 10 ሚሊዮን ብር በማያንስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤
5. ያለሚኒስቴሩ ፈቃድ፣ ባልታደሰ ፈቃድ አደገኛ ቆሻሻ ያጓጓዘ፣ ያከማቸ ወይም መልሶ ጥቅም ላይ ያዋለ እንደሆነ ከ 5 ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከ500ሺ ብር በማያንስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤

6. ያልታከመ አደገኛ ቆሻሻ ወደ አካባቢው የለቀቀ እንደሆነ የተበከለውን አካባቢ የማከም ግዴታው እንደተጠበቀ ሆኖ ከ5 ዓመት በማያንስ ፅኑ እስራት እና ከ500ሺ ብር በማያንስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤፤
7. የሀሰት መረጃ በማቅረብም ሆነ በሌላ ማንኛውም መልኩ የተቆጣጣሪውን ሥራ ያደናቀፈ እንደሆነ ከ 5 ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና 500ሺ ብር በማያንስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

22.<u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

ይህ አዋጅ ከመዉጣቱ በፊት አደገኛ ቆሻሻ እንቅስቃሴ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ከዋለበት ቀን አንስቶ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ይህ አዋጅ በሚያዝዘው መሠረት ቅድመ ሁኔታዎችንና መስፈርቶችን ማሟላት አለበት፡፡

23.<u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልግ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1 መሠረት የወጣውን ደንብ በአግባቡ ለማስፈጸም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

24.<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጳጉሜ 2 ቀን 2010 ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**አባሪ 1**

**ቁጥጥር የሚደረግባቸዉ የቆሻሻ ምድቦች**

**የቆሻሻ ዓይነቶች**

- ከሆስፒታሎች ከጤና ጣቢያዎችና ከክሊኒኮች እና ከሌሎች ተቋሞች የሚወገዱ ቆሻሻዎች
- ከመድሀኒቶች አመራረትና አዘገጃጀት የሚወገዱ ቆሻሻዎች
- ተወጋጅ መድሀኒቶች
- ከባዮሳይድስና(ተባይ ማጥፊያ፡ ፀረ ተባይ ከፋይቶ )ከዕፅዋት ፋርማሶቲካልስ ከሚመረቱ ከሚቀመሙና አገልግሎት ላይ ከሚዉሉ ተወጋጅ ቆሻሻዎች
- ለእንጨት ማቆያነት ከሚመረቱ ከሚቀመሙና አገልግሎት ላይ ከሚዉሉ ተወጋጅ ቆሻሻዎች
- ከሚመረቱ ከሚቀመሙና አገልግሎት ላይ ከሚዉሉ ኦርጋኒክ አሟሟዎች
- የሣያናይድ ከሚካሎችን የያዙና ለሙቀት እንዲሁም ለቴምፐሪነግ (የሙቀትናየማቀዝቀዝክንዋኔዎች የሚዉሉ ተወጋጅ ቆሻሻዎች
- ጥቅም ላይ ሊዉሉ የማይችሉ ተወጋጅ የተፈጥሮ ነዳጅ ዘይቶች
- ተወጋጅ ዘይቶች (ዉሃ የሃይድርካረቦን) ዉሃ ድብልቆች፡ emulsions (ጉሽት
- ፖሊክሎሪነትድባዬፊናየልስ (ፒሲቢእና) ወይም ፖሊክሉሪነትድትቴረፊናየልስ (ፒሲቲ ይያዙ ወይም የተበከሉ ተወጋጅ ቆሻሻዎች
- ከነዳጅ ማጣሪያና እነዲሁም ከማናቸዉም በከፍተኛ ሙቀት ጋር የተያያዙ ክንዋኔዎች የሚቀር ተወጋጅ ካትራሜ
- ከሚመረቱ ከሚቀመሙና አገልግሎት ላይ ከሚዉሉ ቀለሞች ማቅለሚያዎች ፒግመንቶች ላከሮአናቫረኒሽ የሚገኙ ተወጋጅ ቆሻሻዎች
- ከሚመረቱ ከሚቀመሙና አገልግሎት ላይ ከሚዉሉ ሬዚኖች ፕላሰቲሳይዝሮች፣ ማጣበቂያዎችየሚገኙ ተወጋጅ ቆሻሻዎች
- ከምርምር እና ከማስተማር ተግባራት ጋር የተያያዙና ምንነታቸዉ ያልታወቀ እና)ወይም አዳዲስኬሚካሎች ሆነዉ በሰዉና)ወይም በአካባቢ ላይ ያላቸዉ ተጽዕኖ ያልታወቀ
- የፈነጂነት ጠባይ ያላቸዉና በሌላ የህግ ማዕቀፍ ያልተካተቱ ተወጋጅ ቆሻሻዎች

- ከሚመረቱ ከሚቀመሙና አገልግሎት ላይ ከሚዉሉ የፎቶግራፍ ኬሚካሎችና የማቀናበሪያ ቁሳቁሶችየሚገኙ ተወጋጅ ቆሻሻዎች
- ከብረታብረቶችና ከፕላስቲኮች የገጽታ ስራዎች(surface treatment ጋር የተያያዙ የኢንዱስትሪቆሻሻዎች አወጋገድ
- የኢንዱስትሪ ቆሻሻዎች የአወጋገድ ስራዎች ጋር የተያያዙ የሚከተሉትን ንጥረ ነገሮች የያዙ ቆሻሻዎች
- ሜታል ካርቦናይሎች
- ቤሪሊየም፣ የቤሪሊየም ዉህዶች
- የክሮሚየም (VI ዉህዶች
- የመዳብ ዉህዶች
- የዚንክ ዉህዶች
- አርዜኒክ፣ የአርዜኒክ ዉህዶች
- ሴሌንየም፣ የሴሌንየም ዉህዶች
- ካድሚየም፣ የካድሚየም ዉህዶች
- አንቲሞኒ፣ የአንቲሞኒ ዉህዶች
- ቴሉሪየም፣ የቴሉሪየም ዉህዶች
- ሜርኩሪ፣ የሜርኩሪ ዉህዶች
- ታሊየም፣ የታሊየም ዉህዶች
- አርሳስ፣ የእርሳስ ዉህዶች
- የኢነኦርጋኒክ ፍሉዎሪን ዉህዶች (ከካለሺየም ፍናሉዎራይድ በስተቀር ኢንኦርጋኒክ ሣያናይዶ
- አሲዳዊ ሙመት ወይንም ጥጥር አሲድ
- ቤዛማ (ቤዚክ ከሙመት ወይንም ጥጥር ቤዝ
- አስቤስቶስ (አቧራና አሰር (ፋይበር
- ኦርጋኒክ የድኝ ዉህዶች
- ኦርጋኒክ ሣያናይዶች
- ፊኖሎች የፊኖል ዉህዶች ከክሎሮ ፊኖል ጭምር
- ኦርጋኒክ አሚሚዎች ከሃሉጅኔትድ አሚሚዎች በስተቀር
- ማናቸዉም የፖሊክሎሪኔትድዳይቤንዞ-ፉራን ተዛማች ኬሚካሎች
- ማናቸዉም የፖሊክሎሪኔትድዳይቤንዞ-ፓራ ዳይኦክሲን ኬሚካሎች

- በዚህ አባሪ ያልተጠቀሱ የኦረጋኖሃሎጅን ዉህዶች

## አባሪ 2

## የአደገኛ ቆሻሻዎች ባሕሪይ

- ፈንጂዎች

  ፈነጂ ወይንም የሚወገድ ቆሻሻ ጠጣር ወይንም ፈሳሽ የሆነ ቆሻሻ (ወይንም የቆሻሻ ውሁድ ፤

  በራሱ ሀይል ኬሚካዊ ሪአክሽን በማካሄድ በከፍተኛ ሙቀት ግፊትና ፍጥነት ጋዝ በመፍጠር አካባቢን ለጉዳት የሚዳርግ ማለት ነዉ፡፡
- ተቀጣጣይ ፈሳሾች “Flammable” የሚለዉ ቃል “inflammable” ከሚለዉ ቃል ጋር ትርጉሙ አንድ ነዉ፡፡ ተቀጣጣይ ፈሳሾች ፈሳሽ ወይንም ፈሳሽ ዉህዶች ወይንም ጥጥር ነገሮችን በሙሙት (በሶሉሽን ወይንም ሰስፔንሽን የያዙ (ለምሳሌ ቀለሞች፣ ቫርኒሾች ላከሮች ወዘተ. ነገር ግን በአደገኛነት ባህሪያቸዉ ምክንያት በሌላ ምድብ የተፈረጁትን የማያጠቃልሉ የሙቀቱ መጠን ከ 60.5 "ር ያልበለጠ (open cup test ወይንም ከ65.6 “ር ያልበለጠ (closed-cup tests ሲሆን ተቀጣጣይ ላቦት(vapour የሚያመነጩ ናቸዉ፡፡ (የ open-cup tests ሆነ የ closed-cup tests ዉጤቶች በቀጥታ ማነፃፀርም ሆነ በአንድ አይነት መንገድ ተሠርተዉ የሚገኙትም ዉጤቶች አብዛኛዉን ጊዜ ስለሚለያዩ ከላይ የተጠቀሱትን መስፈርት የማያሟሉትንም በዚህ ትርጓሜ ማካተት የግድ ይላል፡፡
- ተቃጣይ ጥጥር ጥጥር ነገሮች ወይንም ጥጥር ቆሻሻዎች በፈነጂነት ከተመደቡት ዉጭ ሆነዉ በመጓጓዝ ላይ በሚያጋጥሙ ሁኔታዎች በቀላሉ ተቃጣይ ወይንም በፍትጊያ እሳት ለማስነሳት የሚችሉ ወይንም አስተዋፅዎ የሚያደርጉ
- በግብታዊነት ተቃጣይ ሊሆኑ የሚችሉ ቁሳቁሶች ወይንም ቆሻሻዎች በመጓጓዝ ላይ በሚያጋጥሙ ምድብ ሁኔታዎች ወይንም ከከባቢ አየር ጋር ግንኙነት ሲፈጠር በግብታዊነት ሙቀት የሚፈጥሩና እሳት ሊያስነሱ የሚችሉ ቁሳቁሶች ወይንም ቆሻሻዎች
- ከዉሃ ጋር ግንኙነት ሲፈጠር ተቃጣይ ጋዞችን ሊፈጥሩ የሚችሉ ቁሳቁሶች ወይንም ቆሻሻዎች
- ከዉሃ ጋር ግንኙነት ሲፈጠር በግብታዊነት ተቃጣይ ሊሆኑ የሚችሉ ወይንም በአደገኛ መጠንተቃጣይ ጋዞችን ሊፈጥሩ የሚችሉ ቁሳቁሶች ወይንም ቆሻሻዎች

- ወከሳጅ (ኦክሲዳይዚንግ
  ምንም እንኳን በራሳቸዉ ተቃጣይ ባይሆኑም ኦክሲጂን በመልቀቅ በሌሎች ቁሳቁሶች ላይ እሳት ለማስነሳት የሚችሉ ወይንም አስተዋፅዎ የሚያደርጉ
- ኦርጋኒክ ፐርኦክሳይድስ
- የኦክሲጂን-የኦክሲጂን (0-0 እስስር ያላቸዉ ኦረጋኒክ ቁሳቁሶች ወይንም ቆሻሻዎች ሙቀት መቋቋም ስልማይችሉ በራሳቸዉ ሀይል ሙቀት ተፊ (ኤክሶተርሚክ ፍርስት (ዲኮምፖዚሺን ሊፍጥሩ ይችላሉ
- መርዛማ (አጣዳፊ
- በሚዋጡበት ወይንም በምጋት (ኢንሄልድ ወይንም በቆዳ ንክኪበሰዉ ልጅ ላይ ሞትን ወይንም ከፌተኛ ጉዳትን የሚያስከትሉ ቁሳቁሶች ወይንም ቆሻሻዎች
- ተላላፊ በሽታዎችን የሚያሰከትሉ ቁሳቁሶች
- ጥቅን ሕዋሳት (ማይክሮኦርጋኒዝም ወይንም የእነሱን መርዝ የያዙና በአንስሳትና በሰዉ ላይ በሽታን ያስከትላሉ ተብለዉ የሚጠረጠሩ ቁሳቁሶች ወይንም ቆሻሻዎች
- ብሎት (ዝገት በኬሚካዊ አፀግብሮት (chemical action አማካይነት በህብረህዋሳት ጋር በሚፌጠር ግንኙነት ከፍትኛ ጉዳትን ወይንም አዝት(leakage በሚከሰትበት ጊዜ በሌሎች ቁሳቁሶች ወይንም በማጓጓዣላይ ጉዳት የሚያደርሱ ወይንም የሚያበላሹ ቁሳቁሶች ወይንም ቆሻሻዎች
- ከአየር ወይንም ከዉሃ ጋር ግንኙነት በሚፌጠርበት ጊዜ የመርዛማ ጋዞች ልቀት
- ከአየር ወይንም ከዉሃ ጋር ግንኙነት በሚፌጠርበት ጊዜ መርዛማ ጋዞችን በአደገኛ መጠን ሊፌጥሩ የሚችሉ ቁሳቁሶች ወይንም ቆሻሻዎች
- መርዛማ (አርፍዳዊ ወይንም ስር ሰደድ
  በምጋት፤ወይንም በመብላት )መጠጣት ወይንም ቆዳ ዉሰጥ በመዝለቅ አርፍዳዊ ወይንም ስር ሰደድጉዳቶችን ነቀርሳን ጭምር ይሚያስከትሉ ቁሳቁሶች ወይንም ቆሻሻዎች
- መርዛማ (በአካባቢ ላይ
- በአካባቢ ላይ ከተለቀቁ በክምችትና)ወይንም በመርዛማነት በአፋጣኝ ወይንም አርፍዳዊ ጉዳቶችን የሚያስከትሉ ወይንም ሊያስከትሉ የሚችሉ ቁሳቁሶች ወይንም ቆሻሻዎች

- ከተወገደ በኋላ በማናችዉም መንገድ ሌላ ቁሳቁስ ለምሳሌ በኬሚካዊ እጥበት (leaching ከላይ የተጠቀሱትን በሀርይ መፍጠር የሚችል

## አባሪ 3

## የአወጋገድ ክንዋኔዎች

ሀ. የሀብት ሪከቨሪ ፡ምልልስነት ፤ተወጋጅን መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል (reclamation በቀጥታ መልሶ የመጠቀምን ወይንም ሌላ አማራጭ ጥቅም ላይ ማዋልን የማያስከትሉ ክንዋኔዎች

ክፍል 1 ሁሉንም የሚተገበሩ የአወጋገድ ክንዋኔዎች ያጠቃልላል

- በመሬት ላይ ማከማቸት (ለምሳሌ ለባሳአፈር (landfill
- የመሬት አንክብካቤ (ለምሳሌ የፈሳሽ ቆሻሻዎች ባዮ ኩስት (biodegradation)
- በጥልቀት ማስገባት (ለምሳሌ በአየር መነፋት የሚቻሉትን ቆሻሻዎች ወደ ጥልቅ ጉድጓዶች፣ በተፈጥሮ የሚገኙ የጨዉ እንቁላሉች (salt domes ወዘተ. ማስገባት

  በመሬት ላይ (ለምሳሌ ፈሳሽ ቆሻሻዎችን በጉድጓዶች፣ ኩሬዎች ወይንም ቆራጭ (lagoonsወዘተ ማጠራቀም
- በተለይ የተሰራ ለባሳአፈር (landfill) (ለምሳሌ የሚከደኑና እያንዳንዳቸዉ ከሌላዉና ከአካባቢዉ ጋር የማይገናኙ "ወዘተ.
- ከባህሮች)ዉቂያኖሶች በስተቀር ወደ ተጠራቀመ ዉሃ(water bodyመልቀቅ
- ወደ ባህሮች)ዉቂያኖሶች የባህር ወለል ጭምር ማስገባት
- በዚህ አባሪ ያልተካተተ ህይወታዊ (ባዮሎጂካል ክንዉን ሆኖ በመጨረሻ የሚገኘዉ ዉህድ ወይንም ድብልቅ በክፍል 1 በተጠቀሱት ማናቸዉም የአወጋገድ ክንዋኔዎች የሚፈጸም
- በዚህ አባሪ ያልተካተተ ፊዚኮ-ኬሚካዊ ክንዉን ሆኖ በመጨረሻ የሚገኘዉ ዉህድ ወይንም ድብልቅ በክፍል 1 በተጠቀሱት ማናቸዉም የአወጋገድ ክንዋኔዎች የሚፈጸም (ለምሳሌ ትነት፣ ማድረቅ፣ ግይት(calcinations፤ ኒዉትራላይዜሽን፣አትለት (ፕርሲፒትሽን፤ ወዘተ.
- በመሬት ላይ ማቃጠል

ለ. የሀብት ሪከቨሪ፣ ምልልስነት፤ተወጋጅን መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል (reclamation በቀጥታ መልሶ የመጠቀምን ወይንም ሌላ አማራጭ ጥቅም ላይ ማዋልን የሚያስከትሉ ክንዋኔዎች

**ክፍል 2 ሁሉንም በህግ የተደነገጉትን ወይንም አደገኛ ቆሻሻዎች ተብለዉ የሚገመቱትንና በክፍል 1 ያልተፈረጁትን ክንዋኔዎች ያጠቃልላል**

- ለነዳጅነት የሚያገለግል (በቀጥታ ማቃጠልን ሳይጨምር ወይንም ሌላ ሀይል የማመንጫ መንገድ
- አሟሚን መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል)እቀጣይነት (regeneration
- ለአሟሚነት ጥቅም ላይ የማይዉሉ ኦርጋኒክከ ቁሳቁሶች
- ብረታብረቶችን መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል)እቀጣይነት(regeneration
- ሌሎች ኢንኦረጋኒክ የሆኑ ቁሳቁሶችን ጥቅም ላይማዋል) እቀጣይነት (regeneration
- አሲዶችንና ቤዞችን መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል
- የአካባቢ ብክለትን መቀነሻ ምንዝሮች (components) ሪከቨሪ
- የአብያይ ምንዝሮች ሪከበቨሪ (catalyst components)

**ደንብ ቁጥር425/2011**

# የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ አያያዝ እና አወጋገድ ለመደንገግ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን ባወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀጽ 5 እና በአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 300/2000 አንቀጽ 20 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ አያያዝ እና አወጋገድ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 425/ 2011" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጓሜ

በዚህ ደንብ ውስጥ፤

1. "የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሣሪያ" ማለት የኤሌክትሪክ ኃይልን ለማመንጨት፣ ለማስተላለፍ እና ለመለካት የሚያገለግሉ መሣሪያዎችን ጨምሮ በኤሌክትሪክ ወይም በኤሌክትሮ ማግኔቲክ ኃይል የሚሰራ እና ለተለዋዋጭ ከረንት እንዲሁም ለቀጥተኛ ከረንት የተሰራ መሳሪያ ነው፤
2. "የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ" ማለት ከጨረራ አመንጪ መሳርያዎች ዉጪ ሁሉም ዓይነት የተጣለ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሣሪያ እና የመሳርያ ክፍል ነው፤
3. "የተራዘመ የአምራቾች ሀላፊነት" ማለት ማንኛውም የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሣሪያዎች አምራች ምርቱን አካባቢያዊ ተቀባይነት ባለው መንገድ የመያዝ ሀላፊነት ነው፤
4. "አምራች" ማለት ማንኛውም፣
   ሀ) የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎችን በራሱ የንግድ ምልክት በፋብሪካ አምርቶ ለሽያጭ የሚያቀርብ፣ ወይም
   ለ) የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎችን በመገጣጠም ለሽያጭ የሚያቀርብ፤ ሰው ነው፤
5. "አስመጪ" ማለት የኤለክትሪክና የኤለክትሮኒክስ ዕቃዎችን ከውጭ ሀገር ወደ ኢትዮጵያ የሚያስመጣ ሰው ነው፤

6. “ተጠቃሚ” ማለት የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሣሪያዎችን የሚጠቀም ማንኛውም ሰው ነው፤
7. “የጅምላ ሻጭ” ማለት የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሣሪያን ከፋብሪካ ወይም ከአስመጪ ገዝቶ ለቸርቻሪ የሚሸጥ ማንኛውም ሰው ነው፤
8. “የችርቻሮ ሻጭ” ማለት የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሣሪያዎችን ከጅምላ ሻጭ ወይም ከአምራች ወይም ከአስመጪ ገዝቶ ለሸማች ወይም ለተጠቃሚ የሚሸጥ ማንኛውም ሰው ነው፤
9. “በድጋሚ መጠቀም” ማለት ቆሻሻ ያልሆኑ ምርቶች ወይም ክፍሎች ለተሰሩበት አላማ በድጋሚ ጥቅም ላይ የሚውሉበት ማንኛውም አሰራር ነው፤
10. “መሰብሰብ” ማለት የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ ወደ ቆሻሻ ህክምና ማዕከል ለማጓጓዝ ቆሻሻዎቹን በቅድሚያ በመለየት እና በማከማቸት ማሰባሰብ ነው፤
11. “የማሰባሰቢያ ማዕከል” ማለት የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ ለማሰባሰብ የተቋቋመ ማዕከል ነው፤
12. “መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል” ማለት የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ ቁሶችን ከተሰሩበት ዓላማ ዉጪ ለሌላ አገልግሎት እንደገና የመጠቀም ሂደት ነው፤
13. “መልሶ ጥቅም ላይ የሚያውል” ማለት የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ መልሶ ጥቅም ላይ በማዋል ሥራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው ነው፤
14. “ማደስ” ማለት ያገለገለ ወይም የተጣለ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሣሪያዎችን ወይም ክፍሎችን መልሶ ለመሸጥ ወይም በድጋሚ ለመጠቀም የሙከራ ፍተሻ፣ የመጠገን፣ የማሻሻል ወይም የማሳደግ አገልግሎት ነው፤
15. “አዳሽ” ማለት ያገለገለ ወይም የተጣለ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሣሪያን ወይም ክፍሎች በማደስ ሥራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው ነው፤
16. “መለያየት” ማለት የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሣሪያን በመገነጣጠል የተለየው ክፍሉ ባለበት ሁኔታ ጥቅም ወደሚሰጥበት፣ ወይም በለውጥ ሂደት አልፎ ምርትን ለማምረት የጥሬ ዕቃ ወደሚሆንበት፣ ወይም መወገድ ያለበትአደገኛ ቁስነት የመለየት ተግባር ነው፤
17. “አወላላቂ” ማለት የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎችን በማወላለቅ ስራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው ነው፤

18.“ማከም” ማለት ከኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ ውስጥ ጠቃሚ ቁሶችን በማውጣት በድጋሚ መጠቀም ወይም መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል ወይም ጥቅም እንደማይሰጡ ሲረጋገጥ ማስወገድ ነው፤

19.“መልሶ ማግኘት” ማለት ከኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ ወይም ክፍሎች ወይም ክፍልፋዮች ቁስ ነገሮችን መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል ወይም ሀይልን መልሶ ለማግኘት ማቃጠል ነው፤

20.“አጓጓዥ” ማለት የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ በየብስ ወይም በባህር ወይም በአየር በማጓጓዝ ስራ ላይ የተሰማራ ሰው ነው፤

21.“ማስወገድ” ማለት ማንኛውም መልሶ መጠቀም ወይም እንደገና ማግኘትን የማይጨምር ስራ ሲሆን የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ ማቃጠል ፣ መቅበር ወይም ጥብቅ በሆነ የቆሻሻ መጣያ ማከማቸት ነው፤

22.“ለአካባቢ ተስማሚ የቆሻሻ አያያዝ” ማለት በአደገኛ ቆሻሻ አማካኝነት ሊከሰቱ የሚችሉ አሉታዊ ተፅዕኖዎችን የሰው ጤና፣ አካባቢን እና ሀብትን በሚጠብቅ መልኩ መያዛቸውን ለማረጋገጥ ሊተገበሩ የሚችሉ ሁሉንም እርምጃዎችን መውሰድ ነው፤

23.“ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት 47(1) የተመለከተው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴምክራሲያዊ ሪፑብሊክ ማንኛውም ክልል ማለት ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችንም ይጨምራል፤

24.“ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

25.“ሚኒስቴር እና ሚኒስትር” ማለት እንደቅደም ተከተሉ የአካባቢ፣ ደን እና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር[57] እና ሚኒስትር ነው፤

26.በወንድ ጾታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ያካትታል፡፡

3. <u>**የተፈፃሚነት ወሰን**</u>

ይህ ደንብ ከዚህ ደንብ ጋር አባሪ አንድ ተደርገው የተዘረዘሩት የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሣሪያዎች እና ሚኒስቴሩ በዚህ ደንብ መሠረት በሚያወጣው መመሪያ ውስጥ የሚያካትታቸው ሌሎች መሣሪያዎችን በሚያመርቱ፣ በሚያከፋፍሉ፣ በሚቸረችሩ፣ ወደ ሀገር ውስጥ በሚያስገቡ፣ በሚያጓጉዙ፣ በማሰባሰቢያ

[57] 57 25/08 (2011) አ. 1097 አንቀጽ 36(17) የአካባቢ ደንና አየር ለውጥ ኮሚሽን ሆኗል በአዋጁ ውስጥ ሚንስቴር ሚለው ኮሚሽን በማለት ተተክቶ ይነበብ፡፡

ማዕከሎች፣ በአዳሾች፣ በአወላላቂዎች ወይም መልሶ ጥቅም ላይ በሚያውሉ እና በተጠቃሚዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ አያያዝ

### 4. የቆሻሻ አያያዝ ቅደምተከተል

የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ በአካባቢ ላይ የሚያሳድሩትን ተፅዕኖ ለመቀነስ የሚከተሉት የቆሻሻ አያያዝ ደረጃዎች ተፈፃሚ መሆን አለባቸው፤

1. የቆሻሻ ምንጮችን መቀነስ፤
2. ቆሻሻን ማደስ እና በድጋሚ መጠቀም፤
3. ቆሻሻን መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል፤
4. ቆሻሻን ማስወገድ፡፡

### 5. የተራዘመ የአምራቾች ሀላፊነት

1. የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ ምንጮችን ለመቀነስ እና የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሣሪያ በድጋሚ መጠቀምን፣ ማደስን እና መልሶ ጥቅም ላይ ማዋልን ለማጠናከር ማንኛውም የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሣሪያ አምራች፣ ጅምላ ሻጭ፣ ቸርቻሪ ወይም ወደ አገር ውስጥ የሚያስገባ ሰው የተራዘመ የአምራቾች ሀላፊነት ይኖርበታል፡፡
2. የተራዘመ የአምራቾች ኃላፊነት የሚከተሉትን ኃላፊነቶች ያስከትላል፡-

   ሀ) የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሣሪያዎች በሚመረቱበት ወቅት የሚመነጩ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻን ማሰባሰብ እና ቆሻሻዎቹን ለማደሻ፣መልሶ ጥቅም ላይ ማዋያ ወይም ለማስወገጃ ማዕከሎች ማስተላለፍ፤

   ለ) የአገልግሎት ዘመናቸውን ያጠናቀቁ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሣሪያዎች ማሰባሰብ ወይም ከሸማቾች መልሶ መቀበል እና ፍቃድ ለተሰጣቸው የማደሻ፣ የማወላለቂያ እና መልሶ ጥቅም ላይ ማዋያ ማዕከሎች መተላለፋቸውን ማረጋገጥ፤

   ሐ) የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻን አካባቢያዊ ተቀባይነት ባለው መንገድ ለመያዝ እና ለማስወገድ የሚያስፈልግ ወጪን ለመሸፈን የሚያስችል አደረጃጀት መዘርጋት እና በገንዘብ መደገፍ፡፡

3. ሚኒስቴሩ የአምራቾች መዝገብ እና የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ ዝርዝር ቆጠራ መዝገብ ሊኖረው ይገባል፡፡
4. ማንኛውም አምራች ፣ጅምላ ሻጭ እና ቸርቻሪ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ ዝርዝር መዝገብ መያዝ ያለበት ሲሆን መዝገቡም ሚኒስቴሩ ለሚያደርገው ምርመራ ተደራሽ መሆን ይኖርበታል፡፡

6. <u>**የተጠቃሚ ኃላፊነት**</u>

ተጠቃሚዎች የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ ማሰብሰቢያ ማዕከሎች ወይም ቆሻሻዎቹን የሚሰበስቡ ሰዎች መረከባቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት ይኖርባቸዋል፡፡

7. <u>**ቆሻሻን ስለመሰብሰብ**</u>

1. የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ ማሰባሰቢያ ማዕከልን ለመክፈት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ለሚኒስቴሩ ማመልከቻ በማቅረብ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ማግኘት እና መመዝገብ አለበት፡፡
2. የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ ማሰባሰቢያ ማዕከልን ለመክፈት ከሚኒስቴሩ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ያገኘ ማንኛውም ሰው ከዚህ በታች የተመለከቱት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፤

ሀ) የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ አሰባሰብ ከሌሎች ዓይነት ቆሻሻ ተለይቶ መካሄዱን የማረጋገጥ፤

ለ) የቆሻሻው ዝቃጭ እንቅስቃሴ ተለይቶ የሚታወቅ መሆኑን የማረጋገጥ፤

ሐ) የተሰበሰበው የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ ፍቃድ ወደተሰጠው ማወላለቂያ፣ ማደሻ ወይም መልሶ ጥቅም ላይ ማዋያ ተቋም እስከሚወሰድ ድረስ ማንም ሰው በማይደርስበት እና ምንም ሊበክል በማይችልበት ሁኔታ መከማቸቱን የማረጋገጥ፤

መ) የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻው በሚሰበሰብበት፣ በሚከማችበትም ሆነ በሚጓጓዝበት ወቅት በሰው ጤና ወይም በአካባቢ ደህንነት ላይ ምንም አይነት ጉዳት የማያመጣ መሆኑን እና

ሠ) የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ ማሰባሰቢያ ቦታ ለተጠቃሚዎች በቅርበት የሚገኝ መሆኑ እና የሚሰጠው አገልግሎት በበቂ ሁኔታ ማስተዋወቁ የማረጋገጥ፡፡

8. **ቆሻሻ ስለማወላለቅ**

1. የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ የማወላለቂያ ማዕከልን ለማቋቋም የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ለሚኒስቴሩ ማመልከቻ በማቅረብ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ማግኘት እና መመዝገብ አለበት፡፡
2. የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሣሪያዎችን በማወላለቅ ስራ ላይ ለመሰማራት 8. ከሚኒስቴሩ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ያገኘ ማንኛውም ሰው ከዚህ በታች የተመለከቱት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፤

   ሀ) የማወላለቅ ሂደቱ በሰው ጤና ወይም በአካባቢ ደህንነት ላይ ምንም ዓይነት ጉዳት የማያደርስ መሆኑን፤

   ለ) የማወላለቁ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ ተለያይተው ሊቀመጡ የሚችሉበት ቦታ ወይም ክፍል የተዘጋጀ መሆኑን፤

3. ማንኛውም የማወላለቂያ ማዕከል የሚከተሉትን መረጃዎች መዝግቦ መያዝና መዝገቡም ለሚኒስቴሩ ለምርመራ ተደራሽ ማድረግ አለበት፤

   ሀ) ወደ ማዕከሉ የመጡ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ ዓይነት እና ክብደት፤

   ለ) ከማዕከሉ የወጡ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ ክፍልፋዮች ዓይነት እና ክብደት፤

   ሐ) ከማዕከሉ የወጡ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ ክፍልፋዮች መዳረሻዎችን የሚያሳይ ማስረጃ፡፡

9. **ቆሻሻን በድጋሚ ጥቅም ላይ ስለማዋል**

በድጋሚ ጥቅም ላይ ሊውሉ የታቀዱ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ መስራት እንደሚችሉ በአዳሽ ተቋማት አማካይነት በተገቢው ሊፈተሹ እና ውጤቱም ሊመዘገብ ይገባል፡፡

10. **ቆሻሻን መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል**

1. የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻን መልሶ ጥቅም ላይ በማዋል ሥራ ላይ ለመሰማራት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ለሚኒስቴሩ ማመልከቻ በማቅረብ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ማግኘት እና መመዝገብ አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ከሚኒስቴሩ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ያገኘ ማንኛውም ሰው ከዚህ በታች የተመለከቱት ኀላፊነቶች ይኖሩታል፤

   ሀ) የምዝገባ ግዴታዎችን የማሟላት፤

   ለ) መልሶ ጥቅም ላይ በማዋል ሂደት የተገኙ የተለያዩ ቁሶችን ብዛት የሚያሳይ ሰነድ የመያዝ፤

   ሐ) መዛግብቱን ሁሉ ለሚኒስቴሩ ግልጽና ተደራሽ የማድረግ፤

   መ) መልሶ ጥቅም ላይ በማዋል ሂደት የሚመነጩ አደገኛ ዝቃጮች ለአካባቢ ተስማሚ በሆነ የቆሻሻ አያያዝ ዘዴ እንዲወገዱ የማድረግ፡፡

## 11.<u>ቆሻሻን ስለማደስ</u>

1. የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻን በማደስ ሥራ ላይ ለመሰማራት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ለሚኒስቴሩ ማመልከቻ በማቅረብ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ማግኘት እና መመዝገብ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1 መሠረት ከሚኒስቴሩ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ያገኘ ማንኛውም ሰው ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፤

   ሀ) የምዝገባ ግዴታዎችን የማሟላት፤

   ለ) መዛግብቱን ሁሉ ለሚኒስቴሩ ግልጽና ተደራሽ የማድረግ፤

   ሐ) በማደስ ሂደት የሚመነጩ አደገኛ ዝቃጮች ለአካባቢ ተስማሚ ቆሻሻ አያያዝ ዘዴ እንዲወገዱ የማድረግ፡፡

## 12.<u>ቆሻሻ ላይ መለያ ስለማድረግ</u>

በድጋሚ በጥቅም ላይ የዋሉ፣የታደሱ እና መልሶ ጥቅም ላይ የዋሉ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ በሙሉ በድጋሚ ጥቅም ላይ እንደዋሉ፣ እንደታደሱ ወይም መልሰው ጥቅም ላይ የዋሉ ምርቶች መሆናቸውን እና ያደሳቸው ወይም መልሶ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደረጋቸውን ተቋም ማንነት የሚገልጽ የፅሁፍ ማስታወቂያ በአማርኛ እና በእንግሊዘኛ ቋንቋዎች በግልጽ እና በቋሚነት መለጠፍ አለባቸው፡፡

13.**ቆሻሻን መልሶ በጥቅም ላይ ከማዋል በፊት ስለማከምና አያያዝ**

1. የማከም ስራ ከተደረገለት በኋላ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሣሪያን በድጋሚ መጠቀም እንደማይቻል ከታመነ ሚኒስቴሩ ባወጣው መመሪያ መሠረት አግባብነት ባለው የቆሻሻ ማከማቻ ውስጥ መቀመጥ አለበት፡፡
2. በአያያዝ ጉድለት ሳቢያ ሊደርስ የሚችል የዕቃ መሰበርን እና ለአደጋ ሊያጋልጡ የሚችሉ ቁሶች መለቀቅ ጠንቅን በተቻለ መጠን ለመቀነስ በቂ ጥንቃቄ መደረግ አለበት፡፡
3. በመልሶ ጥቅም ላይ ማዋያ ማዕከልነት የተመዘገበው ድርጅት ባለቤት ወይም አስተዳዳሪ ሊያጋጥሙ የሚችሉ አደጋዎችን ለማስወገድ እንዲሁም አደጋ ለመከላከል የሚያስችል ዘዴን በሚመለከት ለሠራተኞቹ በቂ ስልጠና መሰጠቱን ማረጋገጥ አለበት፡፡

14. **ቆሻሻን መለየት እና በጊዜያዊነት ማከማቸት**

1. የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ ለተጨማሪ ምርመራ ተለይተው መከማቸት አለባቸው፡፡
2. የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ ማከማቻ ማዕከል ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች በሚያሟሉ ስፍራዎች ሊገኙ ይገባል:

   ሀ) የማከማቻ ማዕከሉ ለእሳት ማጥፋትና ለሌሎች አስቸኳይ የአደጋ ጊዜ ሁኔታዎች አመቺ መሆኑ፤

   ለ) የማከማቻ ማዕከሉ ለጎርፍ ያልተጋለጠ መሆኑ፤

   ሐ) የማከማቻ ማዕከሉ በመሬት ላይ እና በመሬት ውስጥ የሚገኝ የውሀ ክምችት ላይ ጉዳት የማያደርስ መሆኑ፡፡

3. ማንኛውም ያልተፈቀደለት ሠራተኛ ወይም ግለሰብ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተጠቀሰው የማከማቻ ሥፍራ መግባት አይፈቀድም።
4. የማከማቻ ተቋሙ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ መከማቸታቸውን የሚገልፁ ምልክቶችን መያዝ ይኖርበታል፡፡
5. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (4) ላይ የተገለፁት ምልክቶች በቅርብ ርቀት ሊታዩ የሚችሉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡
6. የማከማቻ ቦታዎች ለኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሣሪያ መለዋወጫዎች፣ መልሶ ጥቅም ላይ ለሚውሉ ክፍልፋዮች እና ክፍሎች፣ ለሚወገዱ

ክፍልፋዮች እና ክፍሎች እና ለማደስ የሚውሉ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሣሪያዎች ተብለው መመደብ አለባቸው።

7. የማከማቻ ማዕከሉ ባለቤት ወይም አስተዳዳሪ በማከማቻ ማዕከሉ ለመከማቸት የገቡ ወይም የወጡ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ አይነት፣ የተከማቹበት ስፍራ፣መጠን እና ቀን የሚገልፅ ሰነድ መያዝ ይኖርበታል፡፡

15. **ቆሻሻን ማጓጓዝ**

1. በኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ በማጓጓዝ ሥራ ላይ ለመሰማራት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ለሚኒስቴሩ ማመልከቻ በማቅረብ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ማግኘት እና መመዝገብ አለበት፡፡
2. የማንኛውም የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ አጓጓዥ ቆሻሻው በድጋሚ በጥቅም ላይ ሊውል የመቻል ሁኔታን እና ቀጣይ ህክምናን በማያናጋ መንገድ ማጓጓዝ አለበት።
3. በኢትዮጵያ ውስጥ የሚደረግ ማንኛውም ክልል ተሻጋሪ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ ማጓጓዝ ከሚኒስቴሩ ፈቃድ ሊያገኝ የሚችለው ከቆሻሻው መዳረሻ ክልል የአካባቢ ጥበቃ ተቋም በዝውውሩ መስማማቱን በጽሑፍ ሲገልጽ ብቻ ይሆናል፡፡

16. **የቆሻሻ አወጋገድ**

1. የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ እንዲወገዱ የሚደረጉት በድጋሚ የመጠቀም፣የማደስ እና መልሶ ጥቅም ላይ የማዋል አማራጮች ሁሉም ተሞክረው ከተሟጠጠ በኋላ ብቻ ነው፡፡
2. የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ በጥብቅ የቆሻሻ መጣያ ቦታ ወይም በማቃጠል እናሚኒስቴሩ በዚህ ደንብ መሠረት በሚያወጣው መመሪያ መሰረት በሚወሰኑ ቴክኖሎጂዎች መወገድ አለባቸው፡፡

## ክፍል ሦስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

17. **የሙያ ደኅንነት፣ጤንነትና የሥራ አካባቢ**

1. ማንኛውም በኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ አያያዝ ሥራ ላይ የተሰማራ ተቋም የሠራተኞችን ደኅንነትና ጤንነት በሚገባ ለመጠበቅ የሚያስፈልጉ እርምጃዎችን መውሰድ ይኖርበታል፡፡

2. በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ላይ የተደነገገው የሙያ ደኅንነት፣ጤንነትና የሥራ አካባቢ መስፈርቶች በኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ አያያዝ እና አወጋገድ ሥራ ላይ ለተሰማሩ ሰዎችም ተግባራዊ ይሆናል፡፡

18. <u>የወንጀልና የፍትሐ ብሔር ኃላፊነት</u>

የዚህን ደንብ ድንጋጌ መጣስ አግባብ ባላቸው የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ ድንጋጌዎች እና በሌሎች ሕጎች መሠረት የወንጀልእና የፍትሐ ብሔር ኃላፊነት ያስከትላል፡፡

19. <u>ውክልና የመስጠት ሥልጣን</u>

ሚኒስቴሩ ተገቢ ሆኖ ሲታየው ከኃላፊነቶቹና ከተግባሮቹ በከፊል ለሌሎች መሥሪያ ቤቶች በውክልና ይሠጣል፡፡

20. <u>መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

ይህንን ደንብ ለማስፈጸም አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን ሚኒስቴሩ ሊያወጣ ይችላል፡፡

21. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የጸናይሆናል።

**አዲስ አበባ ………… 2011 ዓ.ም**

**አብይ አሕመድ (ዶ)ርየኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ**

**ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**አባሪ አንድ**

**የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎች የሚከተሉት የሚጨምር ሆኖ በእነዚህ ብቻ ግን የተወሰነ አይደለም**

| | |
|---|---|
| **ትላልቅ የቤት ውስጥ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎች** | |
| 1 | ማቀዝቀዣዎች |
| 2 | የአየር ሙቀት ማመጣጠኛ መሳሪያዎች |
| 3 | የልብስ ማድረቂያዎች |
| 4 | የልብስ ማጠቢያ ማሽኖች |
| 5 | የኤሌክትሪክ ምድጃዎች |
| 6 | የሰሀን ማጠቢያ ማሽኖች |
| 7 | የኤሌክትሪክ ማሞቂያ መሳሪያዎች |
| 8 | የማይክሮዌቭ ምድጃ እና ሌሎች |
| **ትናንሽ የቤት ውስጥ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎች** | |
| 1 | ቫኪዩም ክሊነሮች |
| 2 | የምንጣፍ ማፅጃ |
| 3 | የልብስ ስፌት እና የሽመና መሳሪያዎች |
| 4 | የልብስ መተኮሻ ማሽኖች |
| 5 | መጥበሻዎች |
| 6 | የቡና ማሽኖች |
| 7 | የቡና መፍጫዎች |
| 8 | የኤሌክትሪክ ቢላዎች |

| | |
|---|---|
| 9 | የፀጉር መቁረጫ፣ የፀጉር ማድረቂያ፣ የጺም መላጫ፣ የማሳጅ እና ሌሎች የሰውነት መጠበቂያ መሣሪያዎች እና ሌሎች |

**የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና የቴሌኮሚዩኒኬሽን**

**የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎች**

| | |
|---|---|
| 1 | ሚኒኮምፒዩተር |
| 2 | ሜይንፍሬም ኮምፒዩተር |
| 3 | የግል ኮምፒዩተሮች (ሴንትራል ፕሮሰሲንግ፣ማውስ፣ስክሪን እና ኪቦርድ ጨምሮ |
| 4 | ላፕቶፕ ኮምፒዩተሮች (ሴንትራል ፕሮሰሲንግ፣ማውስ፣ስክሪን እና ኪቦርድ ጨምሮ |
| 5 | ፕሪንተሮች |
| 6 | ኖትፓድ ኮምፒዩተሮች |
| 7 | የኮፒ ማሽኖች |
| 8 | የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ታይፕ ራይተር |
| 9 | የኪስ እና የጠረጴዛ የሂሳብ መሳሪያዎች |
| 10 | የመረጃ ማሰባሰቢያ እና ማከማቻ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎች |
| 11 | ቴሌክስ |
| 12 | ስልኮች |
| 13 | ተንቀሳቃሽ ስልኮች |
| 14 | ገመድ አልባ ስልኮች እና ሌሎች |

| የፍትህ ሚኒስቴር | |
|---|---|
| **የተጠቃሚ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎች** | |
| 1 | ሬድዮ |
| 2 | ቴሌቪዥኖች |
| 3 | የቪዲዮ ካሜራዎች |
| 4 | የቪዲዮ መቅጃዎች |
| 5 | ሀይ ፋይ መቅጃዎች |
| 6 | የኦድዮ አምፕሊፋየሮች |
| 7 | የሙዚቃ መሳሪያዎች እና ሌሎች |
| **የመዝናኛ የስፖርት የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎች** | |
| 1 | ቪዲዮ ጌም እና አክሰሰሪዎቹ |
| 2 | የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ አሻንጉሊቶች |
| 3 | የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ የስፖርት መሳሪያዎች እና ሌሎች |
| **የህክምና የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎች** | |
| 1 | የራዲዮ ቴራፒ መሳሪያዎች |
| 2 | የካርዲዮሎጂ መሳሪያዎች |
| 3 | የዳያሊሲስ መሳሪያዎች |
| 4 | የላቦራቶሪ መሳሪያዎች |
| 5 | ህመምን ወይም የአካል ጉዳትን ለማወቅ፣ለመከላከል፣ለመቆጣጠር፣ለማከም እና ለመቀነስ የሚያገለግሉ መሳሪያዎች እና ሌሎች |
| **የልኬት ፣የክትትል እና የቁጥጥር የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎች** | |

| የፍትህ ሚኒስቴር | |
|---|---|
| 1 | የጭስ ዲቴክተር |
| 2 | የእሳት ዲቴክተር እና የአደጋ ምልክት |
| 3 | የሙቀት መቆጣጠሪያዎች |
| 4 | ቴርሞስታትስ |
| 5 | በኢንዱስትሪዎች ውስጥ ለክትትል እና ለቁጥጥር አገልግሎት የሚውሉ መሳሪያዎች እና ሌሎች |
| **ብርሀን አመንጪ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎች** | |
| 1 | ፍሎረሰንት አምፖሎች |
| 2 | ኮምፓክት ፍሎረሰንት አምፖሎች |
| 3 | ከፍተኛ እና ዝቅተኛ ፕሬሽር ሶድየም አምፖሎች |
| 4 | ኤል.ኢ.ዲ አምፖሎች እና ሌሎች |
| **አውቶማቲክ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ዲስፔንሰር** | |
| 1 | የትኩስ መጠጦች አውቶማቲክ ዲስፔንሰር |
| 2 | የቀዝቃዛ የጠርሙስ ወይም የጣሳ አውቶማቲክ ዲስፔንሰር |
| 3 | ለገንዘብ ማውጫ የሚሆን አውቶማቲክ ዲስፔንሰር |
| 4 | ማንኛውንም ዓይነት ምርት ሊሰጡ የሚችሉ አውቶማቲክ መሣሪያዎች እና ሌሎች |

## ደንብ ቁጥር 429/2010

## የሊድ ቀለምን ለመቆጣጠር የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ 916/2008 አንቀጽ 5 እና በአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 300/1994 አንቀጽ 20 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የሊድ ቀለምን መቆጣጠሪያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 429/2010" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጥ ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

   1. በአዋጁ አንቀፅ 2 የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ ደንብም ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡
   2. "ቀለም" ማለት ቫርኒሽን፣ ላኳየርስ፣ ስቴይንስ፣ ኤናሜልስ፣ ግላዝስ፣ፕሪመርስ ወይም ማንኛውም ለቅብ አገልግሎት የሚውል ሲሆን እና በዋናነት የሬዚንስ፣ ፒግመንት፣ ፊለርስ፣ ሶልቨንትስ እና ሌሎች አድቲቨስ ድብልቅ) ቅይጥ ነው፣
   3. "የሊድ ቀለም" ማለት አንድና ከአንድ በላይ የሊድ ውህድ የተጨመረበት ቀለም ሲሆን በሊድ ካርቦኔት፣ ሊድ ክሮሜት፣ ሊድ ክሮሜት ኦክሳይድ፣ ሊድ ክሮሜት ሞሊብዴት ቀይ ሰልፌት፣ ቢጫ ሊድ ሰለፈሮክሮሜት፣ ሊድ 2 ኤታይልሄክሶኔት፣ ሊድ ሞሊብዴት፣ ሊድ ናፍቴኔት፣ ሊድ ናይትሬት፣ ሊድ ሞኖኦክሳይድ፣ ሊድ ኦክሳይድ፣ ሊድ ኦክታኔት፣ ሊድ ፐርኦክሳይድ፣ ሊድ ሰልፌት እና ትራይ ሊድ ባይካርቦኔት ዳይሀይድሮኦክሳይድ ይጨምራል፤
   4. "ሊድ ያለው ቀለምን በግብዓትነት የሚጠቀሙ ምርቶች" ማለት የሕፃናት አሻንጉሊቶች፣ የቤት ውስጥና የውጪ የሕፃናት የመጫወቻ ዕቃዎች፣ የሕፃናት መጽሐፍት፣ የስዕል መሣሪያዎች፣ የቤት ቁሳቁሶችና ሌሎች ሊድ ያለው ቀለምን የሚጠቀሙ ምርቶችን ይጨምራል፤
   5. "የተስማሚነት ምዘና የምስክር ወረቀት" ማለት ሊድ ያለው ቀለም ምርት በዚህ ደንብ የተቀመጠውን ዝቅተኛ የሊድ መጠን መያዙን በማረጋገጥ የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው፤

6. "መለያ" ማለት በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተፃፈ፣ የታተመ ወይም በምስል የተቀረፀና በቀለም ቀጥተኛ መያዣና በቀጥተኛ መያዣዎቹ ውጫዊ መያዣ ወይም መጠቅለያ ላይ የተደረገ ወይም ከነዚሁ ጋር የተያያዘ አጠቃላይ የሊድ መጠንን የሚገልፅ መግለጫ ነው፤
7. "አጠቃላይ የሊድ መጠን" ማለት የምርቱ ወይም የደረቀው ቀለም አጠቃላይ ሊተን የማይችል ክብደት በመቶኛ መጠን ነው፤
8. "አግባብነት ያለው አካል" ማለት በዚህ ደንብ እና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች መሠረት በቀለም ውስጥ የሊድ መጠንን ለመቆጣጠር ሥልጣን የተሰጠው መንግሥታዊ አካል ነው፤
9. "ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት እንደየቅደም ተከተላቸው የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር[58] ወይም ሚኒስትር ነው፤
10. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
11. በወንድ ጾታ የተገለፀው ድንጋጌ ሴትንም ያካትታል፡፡

3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ ደንብ ማንኛውንም የሊድ ቀለም እና ሊድ ያለው ቀለምን በግብዓትነት የሚጠቀሙ ምርቶችን በሚያመርት፣ ወደ ሀገር ውስጥ በሚያስገባ፣ ወደ ውጭ ሀገር በሚልክ፣ በጅምላ በሚሸጥ፣ በሚያከፋፍል እና በሚቸረችር ማንኛውም ሰው ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>በቀለም የሊድ መጠን</u>

4. <u>በቀለም ውስጥ ሊኖር የሚገባው የሊድ መጠን</u>

1. በሊድ ቀለም ወይም ሊድ ያለው ቀለምን በግብዓትነት በሚጠቀሙ ምርቶች ውስጥ የሊድ መጠኑ ከ90 ፓርትስ ፐር ሚሊየን መብለጥ የለበትም፡፡
2. ማንኛውም ሰው አጠቃላይ የሊድ መጠኑ ከፓርትስ ፐር ሚሊየን በላይ የሆነ ሊድ ቀለምን ወይም ሊድ ያለው ቀለምን በግብዓትነት በሚጠቀሙ ምርቶች

---

[58] 58 25/08 (2011) አ. 1097 አንቀጽ 36(17) የአካባቢ ደንና አየር ለውጥ ኮሚሽን ሆኗል በአዋጁ ውስጥ ሚንስቴር የሚለው ኮሚሽን በማለት ተተክቶ ይነበብ፡፡

ማምረት፣ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት፣ ወደ ውጭ ሀገር መላክ፣ በጅምላ መሸጥ፣ ማከፋፈል ወይም መሸጥ አይችልም፡፡

3. ሚኒስቴሩ አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመመካከር በሊድ ቀለም ውስጥ ወይም ሊድ ያለው ቀለምን በግብዓትነት በሚጠቀሙ ምርቶች ላይ ሊኖር የሚገባው አጠቃላይ የሊድ መጠንን መከለስና በኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ ማስወሰን ይችላል፡፡

5. <u>ስለ መለያ ምልክት</u>

1. ማንኛውም ሰው ሊድ ቀለም ወይም ሊድ ያለው ቀለምን በግብዓትነት የሚጠቀሙ ምርቶች የሚያመርት፤ ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገባ፣ ወደ ውጭ ሀገር የሚልክ፣ በጅምላ የሚሸጥ፣ የሚቸረችር ወይም የሚያከፋፍል መያዣያው ላይ አጠቃላይ የሊድ መጠን በግልጽ በሚታይ መልኩ በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ ቋንቋ የመለያ ምልክት መለጠፍ ወይም መለያ ምልክት መኖሩን ማረጋገጥ አለበት፡፡
2. የመለያ ምልክት ያልተደረገበት ሊድ ቀለም ወይም ሊድ ያለውን ቀለም በግብዓትነት የሚጠቀሙ ምርቶችን ማምረት፣ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት፣ በጅምላ መሸጥ፣ ማከፋፈል፣ መቸርቸር ወይም ወደ ውጭ ሀገር መላክ የተከለከለ ነው፡፡

6. <u>የተስማሚነት ምዘና የምስክር ወረቀት</u>

1. ሊድ ቀለምን ወይም ሊድ ያለው ቀለምን በግብአትነት የሚጠቀም ምርት በማምረት ሥራ ለመሰማራት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው አግባብነት ካለው መስሪያ ቤት የተስማሚነት ምዘና የምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት፡፡
2. ሊድ ቀለምን ወይም ሊድ ያለው ቀለምን በግብዓትነት የሚጠቀሙ ምርቶች ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት ወይም ወደ ውጭ ሀገር ለመላክ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው አግባብነት ካለው መስሪያ ቤት ዘንድ ናሙና አቅርቦ በማስመርመር የተስማሚነት ምዘና የምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት፡፡

## <u>ክፍል ሶስት</u>

## <u>የሊድ ቀለም አወጋገድና የጥንቃቄ እርምጃዎች</u>

7. <u>የሊድ ቀለም አወጋገድ</u>

1. የአገልግሎት ጊዜ ያለፈባቸው ሊድ ቀለሞች ወይም ሊድ ያለበትን ቀለምን በግብዓትነት የሚጠቀሙ ምርቶች፤ ወይም ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ ሊድ ቀለሞች

ወይም ሊድ ያለበትን ቀለምን በግብዓትነት የሚጠቀሙ ምርቶች ይህ ደንብ በሥራ ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ አካባቢያዊ ተቀባይነት ባለው ዘዴ መወገድ አለባቸው፡፡

2. አካባቢያዊ ተቀባይነት ያለው የአደገኛ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ መርሆችና ዘዴዎች እንደአግባብነቱ በሊድ ቀለም ወይም ሊድ ያለበትን ቀለምን በግብዓትነት የሚጠቀሙ ምርቶች አወጋገድ ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

8. <u>የጥንቃቄ እርምጃዎች</u>

1. ሊድ ቀለምን ወይም ሊድ ያለው ቀለምን በግብዓትነት የሚጠቀሙ ምርቶች አያያዝ ወይም አመራረት ሥራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው የሠራተኞችን ደኅንነትና ጤንነት ለመጠበቅ አስፈላጊና በቂ እርምጃዎችን መውሰድ ይኖርበታል፡፡
2. በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ላይ የተደነገገው የሙያ ደኅንነት፣ ጤንነትና የሥራ አካባቢ መስፈርቶች ሊድ ቀለም ወይም ሊድ ያለው ቀለምን በግብዓትነት የሚጠቀሙ ምርቶች አያያዝ ወይም አመራረት ሥራ ላይ በተሰማራ ሰው ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
3. ማንኛውም ሰው ወይም የሕንጻ ባለቤት የሕንጻ ግንባታዎችን ከማፍረሱ በፊት ሕንጻው የተቀባበት አጠቃላይ የሊድ ቀለም መጠኑ በዚህ ደንብ ከተቀመጠው የሊድ መጠን በላይ መሆን አለመሆኑን ማስመርመር እና የሊድ ቀለም መጠኑ በዚህ ደንብ ከተመለከተው መጠን በላይ መሆኑ ሲረጋገጥ ግንባታው በሚፈርስበት ወቅት ተገቢ የጥንቃቄ እርምጃዎችን መውሰድ ወይም የጥንቃቄ እርምጃዎች መወሰዳቸውን መረጋገጥ አለበት፡፡
4. የሊድ ቀለም ወይም ሊድ ያለው ቀለምን በግብዓትነት በሚጠቀሙ ምርቶች አያያዝ ላይ ወይም አመራረት ሥራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው ሚኒስቴሩ የሚያወጣውን መመሪያ የመከተል እና፡-

   ሀ ስለጥንቃቄ እርምጃዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት የመስጠት እና

   ለ በሕፃናት ላይ የሚያደርሱትን ጉዳት ለመከላከል እና ተጋላጭነትን ለመቀነስ የሚያስችሉ እርምጃዎችን የመውሰድ ኃላፊነት አለበት፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 9. አስተዳደራዊ እርምጃዎች

1. ማንኛውም ሰው በዚህ ደንብ ከተመለከተው መጠን በላይ የሆነን ሊድ ቀለም ወይም ሊድ ያለው ቀለምን በግብዓትነት የሚጠቀሙ ምርቶችን ያመረተ፣ ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባ ወይም ወደገበያ ያሠራጨ እንደሆነ አግባብነት ያለው አካል፡ ሀ ምርቱ በአገር ውስጥ በአገልግሎት ላይ እንዳይውል የማገድ፤

   ለ የባለፈቃዱ የንግድ ሥራ ፈቃድ እንዲታገድ ወይም እንዲሰረዝ አስተዳደራዊ እርምጃ ሊወስድ ይችላል፡፡

2. አግባብነት ያለው አካል በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፩ መሠረት የወሰደውን አስተዳዳራዊ እርምጃ ለሚመለከተው ፈቃድ ሰጪ አካል በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

### 10.የመተባበር ግዴታ

የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች በአግባቡ ሥራ ላይ ለማዋል የፌደራልና የክልል መንግሥት አካላት እንዲሁም ማንኛውም ሰው ከሚኒስቴሩ ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

### 11.የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

1. ይህ ደንብ ከመጽደቁ በፊት የሊድ ቀለም በማምረት፣ ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት፣ ወደ ውጭ ሀገር በመላክ፣ በጅምላ በመሸጥ፣ በማከፋፈልና በመቸርቸር ሥራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው ይህ ደንብ በሥራ ላይ በዋለ በአንድ ዓመት ውስጥ የቀለም ሊድ መጠኑን 90 ፓርትስ ፐር ሚሊየን ወይም ከዚያ በታች ማውረድ አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1 የተመለከተው የመሸጋገሪያ ጊዜ የሊድ ቀለምን በግብዓትነት በሚጠቀሙ ምርቶች ንግድ ሥራ ላይ በተሰማራ ማንኛውም ሰው ላይ ተፈፃሚ ይሆንበታል፡፡

### 12.መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

ይህንን ደንብ ለማስፈጸም አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን ሚኒስቴሩ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**13.**<u>**ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ኅዳር 4 ቀን 2011**

**አብይ አህመድ (ዶ)ር**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ክፍል ሃያ ሰባት

## የመንግስት የልማት ድርጅቶች

## ሀ) የመንግስት ልማት ድርጅቶች አስተዳደር እና ፕራይቬታይዜሽን

## አዋጅ ቁጥር 25/1984

## የመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ

የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት የሽግግር ወቅት የኢኮኖሚ ፖሊሲ ስላወጣና ይህንኑ ተግባራዊ ለማድረግ ተከታታይ እርምጃዎች መውሰድ ስለአስፈለገ፣

የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በመንግሥት ይዞታ እስካሉ ድረስ ውጤታማ፣ ምርታማና አትራፊ እንዲሆኑ የአሠራር ነፃነት የሚያገኙበት መዋቅርና ሥርዓት መዘርጋት እንደዚሁም ከግል ኩባንያዎች ጋር እየተወዳደሩ ለመሥራት የሚያስችላቸውን የብቃት አቅጣጫ መቀየስ አስፈላጊ ስለሆነ፣

በሽግግር ወቅት ኢኮኖሚ ፖሊሲ መሠረት በመንግሥት ከሚያዙ የልማት ድርጅቶች በስተቀር ቀሪዎቹ በግል ባለሀብቶች ተሳትፎም ሆነ በሙሉ ባለቤትነት የሚመሩበትን ሥርዓት ማመቻቸት ተገቢ ስለሆነ፣

እነዚህን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ ስለመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዲስ ሕግ ማውጣት አስፈላጊ ስለሆነ፣

በሽግግሩ ወቅት ቻርተር አንቀጽ 9 መመሠረት የሚከተለው ታውጆአል፡፡

## ምዕራፍ 1

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ፣**

   ይህ አዋጅ "የመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ፣**

   የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

   1. "ድርጅት" ማለት በመንግሥት ሙሉ ባለቤትነት የማምረት፣ የማከፋፈል፣ አገልግሎት የመስጠት ወይም ሌሎች የኢኮኖሚ ተግባሮችንና ከእነዚሁ ጋር የተያያዙ ሥራዎችን በንግድ መልክ ለማካሄድ በዚህ አዋጅ መሠረት የተቋቋመ የመንግሥት ድርጅት ነው፤

2. “ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን” ማለት የመንግሥት የባቤትነት መብትን ለማስከበር ሲባል የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚሰይመው አካል ነው፤
3. “ጠቅላላ ንብረት” ማለት የድርጅት የማይንቀሳቀስና ተንቀሳቃሽ ንብረቶች ድርጅቱ ገና ያልተቀበላቸው ገቢዎች፣ ጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ ሲሆን ግዙፍ ያልሆኑ ንብረቶች በቅድሚያ የተከፈሉ ወጪዎችንና ሌሎች ገቢ መሆን ያለባቸው ሂሳቦችን ይጨምራል፤
4. “የተጣራ ጠቅላላ ንብረት” ማለት ከጠቅላላ ንብረት ላይ በተያዘው የሂሳብ ዓመት ውስጥ የሚከፈሉ ዕዳዎች በረጅም ጊዜ የሚከፈሉ ዕዳወች በቅድሚያ የተከፈለ ገቢና ሌሎች ዕዳዎች ተቀንሰው የሚቀረው ንብረት ነው፤
5. “ካፒታል” ማለት አንድ ድርጅት በተቋቋመ ጊዜና ከዚያም በኋላ መንግሥት የሚመደብለት የተጣራ ጠቅላላ ንብረት በተመደበበት ጊዜ ያለው ዋጋ ነው፤
6. “ኦዲተር” ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 32 በተመለከተው መሠረት የማናቸውንም ድርጅት ሂሳብ የሚመረምር የተፈጥሮ ሰው ወይም የሕግ ሰውነት የተሰጠው አካል ነው፤
7. “የተጣራ ትርፍ” ማለት ከገቢዎችና ከሌሎች ክፍያዎች ከተገኘው ገንዘብ ላይ ወጪዎችና በሂሳብ ዓመቱ ውስጥ ለሥራ ማስኬጃና ደመወዝ ባግባቡ ወጪ የተደረጉ ሂሳቦች፣ የእርጅና ቅናሽ)ዲፕሪሼሽን)፣ ወለድና ልዩ ልዩ ታክሶች ተቀንሰው የሚቀረው ሂሳብ ነው፤
8. “መንግሥት” ማለት ማዕከላዊ መንግሥት ነው፣[59]
9. “የመንግሥት የትርፍ ድርሻ” ማለት ከተጣራው ትርፍ ላይ ወደ ሕጋዊ መጠባበቂያ ሂሳብና ሌሎች መጠባበቂያ ሂሳቦች ገቢ የሚሆነው ገንዘብ ተቀንሶ የሚቀረው ሂሳብ ነው፣
10. “ቦርድ” ማለት በዚህ ዓዋጅ አንቀጽ 10 (2) እና አንቀጽ 12 መሠረት የሚቋቋም የድርጅት የሥራ አመራር ቦርድ ነው፡፡

3. <u>የተሻሩና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች፣</u>
   1. የሚከተሉት በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፣
      ሀ) የመንግሥት የልማት ሥራ ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 20/1967፣

[59]በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀፅ 50 (1) መሠረት የፌደራል መንግስት ሆኖል፡፡

ለ) አንዳንድ የመንግሥት የልማት ሥራ ድርጅቶችን በአንዳንድ ሚኒስቴሮች ቁጥጥር ሥር ለማዋል የወጣው አዋጅ ቁጥር 131/1970፣

ሐ) የመንግሥት የልማት ሥራ ድርጅቶች ደንብ ቁጥር 5/1967፣

መ) የእርሻ ልማት ድርጅቶች ደንብ ቁጥር 60/1970፣

2. የሚከተሉት በድርጅቶች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፣

ሀ) የመንግሥት ገንዘብ እንቅስቃሴ መቆጣጠሪያና ማስተባበሪያ አዋጅ ቁጥር 163/1971፣

ለ) ይህን አዋጅ የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ ደንብ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ፡፡

4. <u>የሌሎች ሕጎች ተፈጻሚነት፣</u>

በዚህ አዋጅ በሌላ ሁኔታ ካልተወሰነ በስተቀር አግባብነት ያላቸው የፍትሐብሔር ሕግና የንግድ ሕግ ድንጋጌዎች በድርጅቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## <u>ምዕራፍ 2</u>

## <u>የድርጅት አመራረት፣ የሕግ ሰውነትና ችሎታ</u>

5. <u>ድርጅት ከመቋቋሙ በፊት ሊሟሉ ስለሚገባቸው ሁኔታዎች</u>

1. አንድ ድርጅት ከመቋቋሙ በፊት ተቆጣጣሪው ባለሥልጣን፣

ሀ) በዓይነት የተደረገ ክፍያ ካለ፣ ንብረቱ በባለሙያዎች በትክክል የተገመተ መሆኑን፤

ለ) በካፒታልነት የተከፈለ ጥሬ ገንዘብ ካለ በሚቋቋመው ድርጅት ስም በተከፈተ የባንክ ሂሳብ ተቀማጭ መሆኑን፤ያረጋግጣል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) የተደነገገው ቢኖርም በዓይነት የተደረገው ክፍያ በኦዲተር የተረጋገጠ ሂሳብ ያለው ከሆነ ግምቱ በሂሳብ መዝገቡ መሠረት ሊሆን ይችላል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) የተመለከቱት ባለሙያዎች የንብረቱን ዝርዝር መግለጫ፣ ለእያንዳንዱ ንብረት የተሰጠውን ዋጋ እና የአገማመቱን ዘዴ የያዘ ሪፖርት ያዘጋጃሉ፡፡ ተቆጣጣሪው ባለሥልጣን፣ ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በሌላ ሕግ የተቋቋመ የመንግሥት የልማት ሥራ ድርጅትን ሲያስተዳድር የነበረ አግባብ ያለው የመንግሥት መሥሪያ ቤትና ድርጅቱ እያንዳንዳቸው የሪፖርቱን አንድ ኮፒ ያገኛሉ፡፡

4. ድርጅቱ ከመቋቋሙ በፊት ተቆጣጣሪው ባለሥልጣን ለድርጅቱ ምሥረታ ያደረገው ወጪ ካለና ይኸው በኦዲተር የተረጋገጠ ከሆነ ለድርጅቱ በካፒታልነት ይታሰባል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) የተመለከተው ገንዘብ የድርጅቱ ማቋቋሚያ ደንብ እስኪወጣ ድረስ ከባንክ ወጭ አይሆንም፡፡

6. **መመሥረቻ ሕግ፣**

ማናቸውም ድርጅት የሚቋቋመው በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ ይሆናል፡፡ በማቋቋሚያ ደንቡ የሚከተሉት ዝርዝር ጉዳዮች ይገለጻሉ፣

1. የድርጅቱ ስም፣
2. ድርጅቱ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚተዳደር መሆኑ፣
3. ድርጅቱ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች፣
4. የተፈቀደው ካፒታል፣
5. በጥሬ ገንዘብና በዓይነት የተከፈለው መነሻ ካፒታል መጠን፣
6. ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ የማይጠየቅ መሆኑ፣
7. የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት፣
8. ድርጅቱ ቅርንጫፎች ሊኖሩት የሚችል መሆኑ፣
9. የተቆጣጣሪው ባለሥልጣን ስም፣
10. ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ፡፡

7. **የሕግ ሰውነትና ኃላፊነት፣**

1. አንድ ድርጅት የሕግ ሰውነት ይኖረዋል፣ ስለዚህም መብቶችና ግዴታዎች ይኖሩታል፡፡
2. የአንድ ድርጅት ዕዳዎች ሊሸፈኑ የሚችሉት ድርጅቱ ባለው ጠቅላላ ንብረት ብቻ ይሆናል፡፡

8. **አድራሻ፣**

የአንድ ድርጅት አድራሻ ዋና መሥሪያ ቤት ያለበት ሥፍራ ይሆናል፡፡

9. **ችሎታ፣**

1. አንድ ድርጅት ዓላማውን ከግቡ ለማድረስና ከዓላማው ጋር የተዛመዱ ተግባራትን ለማከናወን የሚያስፈልገው ችሎታ ይኖረዋል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ ድርጅት፣

ሀ) በራሱ ስም ለመከሰስና ለመክሰስ፣

ለ) የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት ለማግኘት፣ ባለይዞታና ባለቤት ለመሆን፣ ለማስተላለፍና በመያዣነት ለመስጠት፣

ሐ) ውል ለመዋዋል፣ ብድር ለመበደር፣

ሐ) የንግድና ሌሎች ተመሳሳይ ሰነዶችን ለማውጣትና ለመቀበል፣

ሠ) የባንክ ሂሳብ ለመክፈትና ለማንቀሳቀስ፤

ረ) ኢንቨስት ለማድረግ፤

ይችላል፡፡

## ምዕራፍ 3

## የድርጅቱ አቋምና አመራር

### 10. አቋም፣

እያንዳንዱ ድርጅት፣

1. ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን፣
2. የሥራ አመራር ቦርድ፣
3. ዋና ሥራ አስኪያጅ፣ እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ እና
4. ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች፤

ይኖሩታል፣

### 11. የተቆጣጣሪው ባለሥልጣን ሥልጣንና ተግባር፣

ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን፣

1. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 12(2) እንደተጠበቀ ሆኖ የቦርድ አባላትን ይመድባል፣ ያነሳል፣
2. ከሚመድባቸው አባላት መካከል የቦርዱን ሊቀመንበር ይሾማል፣
3. ለቦርዱ አባላት ሊከፈል የሚገባውን አበል ይወስናል፣
4. የውጭ ኦዲተሮችን ይሰይማል፣
5. የድርጅቱን መነሻ ካፒታል ከመንግሥት ያስመድባል፣
6. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 21 እና 22 መሠረት የድርጅቱ ካፒታል እንዲጨምር ወይም እንዲቀንስ ይወስናል፣
7. የድርጅቱ የተፈቀደ ካፒታል በአንቀጽ 20(2) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ተከፍሎ እንዲያልቅ የመጠባበቂያ ሂሳቦች እንዲያዙ ወይም ከመንግሥት ገንዘብ እንዲመደብ ያደርጋል፣

8. ከቦርዱ በሚቀርብለት ሃሳብ መሠረት ከተጣራው ትርፍ ውስጥ በየዓመቱ ለመንግሥት ፈሰስ ሊደረግ የሚገባውን መጠን ይወስናል፣
9. የድርጅቱን የሂሳብ ሪፖርትና የውጭ ኦዲት ሪፖርት ያጸድቃል፣
10. በቦርዱ የሚቀርብለትን የድርጅቱን የኢንቨስትመንት ዕቅድ ያጸድቃል፣
11. አስፈላጊ ሲሆን በቁጥጥሩ ሥር የሚገኝ ድርጅት እንዲፈርስ ከሌላ ድርጅት ጋር እንዲዋሐድ ወይም እንዲከፋፈል ወይም እንዲሸጥ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ሃሳብ እያቀረበ ያስወስናል፣
12. ከቦርዱ ጋር በመመካከር የድርጅቱን ዓመታዊና አጠቃላይ ግቦችን ያጸድቃል፣ አፈጻጸማቸውንም ይከታተላል፣
13. ለቦርዱ የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደጠበቀ ሆኖ፣ የመንግሥትየባለቤትነት መብትን ለማስከበር የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባሮችን ያከናውናል፡፡

12.<u>የቦርድ አመሠራረት፣</u>

1. የቦርድ አባላት ቁጥር ቢያንስ ሶስት ቢበዛ አሥራ ሁለት ይሆናል፡፡
2. ከቦርድ አባላት መካከል ቁጥራቸው ከአንድ ሶስተኛ የማይበልጥ የሚሆነው አባላት የሚመረጡት በሠራተኞች ጠቅላላ ጉባዔ ይሆናል፡፡ ሌሎች አባላት በተቆጣጣሪው ባለሥልጣን የሚመደቡ ይሆናል፡፡
3. የቦርዱ ሊቀመንበር በዚህ አዋጅ አንቀጽ 11(2) መሠረት ይመደባል፣
4. የቦርዱ አባላት ምደባና ምርጫ በሙያ፣ በሥራ ልምድና በችሎታ ብቃት ላይ የተመሠረተ ይሆናል፣
5. ማንኛውም የቦርድ አባል ተወዳዳሪ ያልሆነ የሌላ ድርጅት ቦርድ አባል ሆኖ እንዲሠራም ሊመደብ ይችላል፡፡
6. የቦርድ አባላት የሥራ ጊዜ ከሶስት (3) ዓመት ለማያንስ ከአምስት )5) ዓመት ለማይበልጥ ጊዜ ይሆናል፡፡ አስፈላጊ ሲሆን አንድ የቦርድ አባል የሥራ ጊዜው ሲያልቅ እንደገና ሊመደብ ወይም ሊመረጥ ይችላል፡፡
7. የቦርዱ የሥራ እንቅስቃሴ ቀጣይነት ይኖረው ዘንድ የአባላቱ የሥራ ዘመን ማብቂያ በአንድ ወቅት አይሆንም፡፡
8. ማንኛውም የቦርድ አባል የቦርድ አባልነቱን የተወ እንደሆነ ቦርዱ አባልነቱን የተወው አባል በተመደበበት አኳኋን ተተኪ አባል እንዲመደብ ለተቆጣጣሪው ባለሥልጣን ማሳሰቢያ ያቀርባሉ፡፡

9. ለሥራው ተገቢ ላለመሆኑ በቂ ምክንያት ሲኖር አንድን የቦርድ አባል ተቆጣጣሪው ባለሥልጣን በማናቸውም ጊዜ ሊያነሳው ይችላል፡፡ ይህ ንዑስ አንቀጽ በሠራተኛው በሚመረጥ የቦርድ አባል ላይም ተፈጻሚ በሚሆንበት ወቅት የሠራተኛው ጠቅላላ ጉባዔ መረጃው እንዲደርሰው ተደርጐ ተተኪ አባል ሊመርጥ ይችላል፡፡

13.<u>የቦርዱ ስብሰባ ሥነ ሥርዓት፣</u>

1. ቦርዱ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፡፡
2. አስቸኳይ ሁኔታ ሲያጋጥም ወይም ከቦርዱ አባላት መካከል ቢያንስ ሁለት አባለት ሲጠይቁ በማናቸውም ጊዜ ቦርዱን ሊቀመንበሩ ይሰበስባል፡፡
3. የቦርዱ ስብሰባ አጀንዳ በቅድሚያ ለቦርዱ አባላት እንዲደርስ ይደረጋል፡፡
4. ከቦርዱ አባላት መካከል አብዛኛው ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡፡
5. ቦርዱ በድምጽ ብልጫ ይወስናል፡፡ ድምጹ እኩል ለእኩል በሚሆንበት ጊዜ ሊቀመንበሩ ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡
6. ቦርዱ ከድርጅቱ ሠራተኞች መካከል መርጦ ፀሐፊ ይመድባል፡፡
7. የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ድምጽ የመስጠት መብት ሳይኖረው በቦርዱ ስብሰባ ላይ ሊገኝ ይችላል፡፡
8. ቦርዱ በየስብሰባው በተገኙት አባላት የሚፈረም ቃለ-ጉባኤ ይይዛል፡፡
9. ቦርዱ የራሱን የአሠራር ደንብ ያወጣል፡፡

14.<u>የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር፣</u>

ቦርዱ፡-

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 መሠረት ለተቆጣጣሪው ባለሥልጣን መቅረብ ከሚገባቸው በስተቀር ሌሎች የፖሊሲ ጉዳዮችን ይወስናል፡፡
2. የድርጅቱን ዋና ሥራ አስኪያጅ ይቀጥራል፣ ደመወዝና አበሉን ይወስናል፣ ያሰናብታል፣
3. ለድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ተጠሪ የሆኑ የሥራ ኃላፊዎችን ቅጥር ምደባና ስንብት ደመወዝና አበል ያጸድቃል፣
4. የድርጅቱን የሥራ ፕሮግራም፣ በጀትና የውስጥ ደንብ ያጸድቃል፣ አፈጻጸማቸውንም ይከታተላል፣
5. የድርጅቱን የረጅም ጊዜ ብድሮችና ክሬዲቶች ያጸድቃል፣
6. በድርጅቱ ሕልውና ላይ ወሳኝነት የሌላቸውን ቋሚ ንብረቶች ሽያጭ ያጸድቃል፣

7. የድርጅቱ ሂሣቦችና ንብረቶች ባግባቡ መያዛቸውን ያረጋግጣል፣
8. ለድርጅቱ ኦዲተሮች የድርጅቱን የሂሳብ መዝገቦች ለተቆጣጣሪው ባለሥልጣን ደግሞ ስለድርጅቱ የሥራ አፈጻጸም ወቅታዊ ሪፖርትና የሂሳብ መግለጫዎች ያቀርባል፣
9. የድርጅቱ ካፒታል እንዲጨምር ወይም እንዲቀንስ ለተቆጣጣሪው ባለሥልጣን ሐሳብ ያቀርባል፣

15.**<u>የቦርድ አባላት ተጠያቂነት፣</u>**

1. የቦርድ አባላት በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጣቸውን ተግባር በጥንቃቄ መፈጸም አለባቸው፡፡
2. አባላቱ ተግባራቸውን በአግባብ ባለመፈጸማቸው ምክንያት በድርጅቱ ላይ ለሚደርሰው ጉዳት በአንድነትና በነጠላ ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተገለጸው ቢኖርም የቦርዱ ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ ውሳኔው ትክክል አይደለም ብሎ በድምጽ የተለየ የቦርድ አባል ውሳኔው ለሚያስከትለው ጉዳት ተጠያቂ አይሆንም፡፡

16.**<u>የድርጅት ዋና ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር፣</u>**

1. ዋናው ሥራ አስኪያጅ፣
   ሀ) የድርጅቱን ሥራ ያደራጃል፣ ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፣
   ለ) ድርጅቱ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርገው ግንኙነት፣ ድርጅቱ በሚያቀርባቸው ክሶችና በድርጅቱ ላይ በሚቀርቡ ክሶች ድርጅቱን ወክሎ ይሠራል፣
   ሐ) ቦርዱን እያስፈቀደ ለእሱ ተጠሪ የሆነ የሥራ ኃላፊዎችን ይቀጥራል፣ ይመድባል፣ ተግባራቸውን ይወስናል፣
   መ) በድርጅቱ የውስጥ ደንብና አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ሌሎች ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ ይመድባል፣ ያሰናብታል፣ ደመወዛቸውንና አባላቸውን ይወስናል፣
   ሠ) የድርጅቱን ሂሳቦች ባግባቡ ይይዛል፣ ለድርጅቱ የባንክ ሂሳብ ይከፍታል፣ ያንቀሳቅሳል፣
   ረ) ለድርጅቱ ሥራ ማስኬጃ የሚውል የአጭር ጊዜ ብድር ውል ይዋዋላል፣ ቦርዱን በማስፈቀድ የረጅም ጊዜ ብድር ይበደራል፣ ለእነዚሁ ዓላማዎች ቦርዱን እያስፈቀደ የድርጅቱን የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት በመያዣነት ይሰጣል፣

ሰ) የድርጅቱን የሥራ ፕሮግራምና በጀት እንዲሁም የውስጥ ደንብ አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላል፣

ሸ) ቦርዱን በማስፈቀድ በድርጅቱ ሕልውና ላይ ወሳኝነት የሌላቸውን የድርጅቱን ቋሚ ንብረቶች ይሸጣል፣

ቀ) የቦርዱን ውሳኔዎች ይፈጽማል፣ ያስፈጽማል፣

በ) ቦርዱ በሚወስነው ሁኔታ ለቦርዱ ሪፖርት ያቀርባል፣

ተ) አስፈላጊ ሆኖ በተገኘው መጠን ሥልጣኑን ለድርጅቱ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ይሰጣል፣

ቸ) በሥራው ሂደት ላይ የሚመክርና በሥራ ግምገማዎች፣ በዕቅዶችና ውሳኔዎች ላይ የሚወያይ የማኔጅመንት ኮሚቴ ያቋቁማል፣ ስብሰባውንም ይመራል፣

ኀ) ቦርዱ የሚሰጠውን ሌላ ተግባር ይፈጽማል፣

2. ዋናው ሥራ አስኪያጅ ለቦርዱ ተጠሪ ይሆናል፡፡

17. <u>የዋናው ሥራ አስኪያጅ ኃላፊነትና ተጠያቂነት፣</u>

ዋናው ሥራ አስኪያጅ ተግባሩን በሚፈጽምበት ጊዜ በቸልተኝነት ወይንም ሆን ብሎ በድርጅቱ ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት በሕግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

18. <u>ውክልና፣</u>

ማናቸውም ድርጅት በዋናው ሥራ አስኪያጅና በዚህ አዋጅ መሠረት ሥልጣን በተሰጣቸው ሌሎች ወኪሎች አማካይነት ሥራውን ይፈጽማል፣ መብት ያገኛል ግዴታ ይገባል፡፡

## <u>ምዕራፍ 4</u>

## <u>የድርጅቱ ካፒታል</u>

19. <u>ድርጅት ለማቋቋም ስለሚያስፈልገው ካፒታል፣</u>

1. ማናቸውም ድርጅት ካፒታል ይኖረዋል፣
2. አንድ ድርጅት ለማቋቋም የሚያስፈልገውን መነሻ ካፒታል ተቆጣጣሪው ባለሥልጣን በመንግሥት እንዲመደብለት ያደርጋል፡፡ ካፒታሉ በዓይነት ወይም በጥሬ ገንዘብ ሊሆን ይችላል፣ በዓይነት ከሆነ ተቆጣጣሪው ባለሥልጣን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 መሠረት የተገመተ ወይም በመዝገቡ መሠረት ትክክል መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

20.**<u>ስለተከፈለና ስለተፈቀደ ካፒታል፣</u>**

1. ማናቸውም ድርጅት ሲቋቋም ድርጅቱ የሚኖረው የተከፈለ ካፒታል መጠን ከተፈቀደው ካፒታል 25 በመቶ ሊያንስ አይችልም፡፡
2. የአንድ ድርጅት የተፈቀደ ካፒታል ድርጅቱ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ በአምስት ዓመት ውስጥ በሙሉ ተከፍሎ ያልቃል፡፡
3. የተፈቀደው ካፒታል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 በተወሰነው ጊዜ በሙሉ ተከፍሎ ካላለቀ ተቆጣጣሪው ባለሥልጣን የሦስተኛ ወገኖች መብት ሳይነካ የድርጅቱን ካፒታል ወደ ተከፈለው የካፒታል መጠን ዝቅ ያደርገዋል፡፡

21.**<u>የተፈቀደ ካፒታል ስለመጨመር፣</u>**

ተቆጣጣሪው ባለሥልጣን ከመንግሥት ገንዘብ በማስመደብ ወይም ከድርጅቱ ገቢ የድርጅቱ ካፒታል እንዲጨምር ሊያደርግ ይችላል፡፡

22.**<u>ካፒታል ስለመቀነስ፣</u>**

የሦስተኛ ወገኖች መብት ሳይነካ የአንድ ድርጅት ካፒታል የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ሊቀንስ ይችላል፣

1. የድርጅቱ ካፒታል እንዲቀነስ ኦዲተሮች ሐሳብ ሲያቀርቡ፣
2. በድርጅቱ ቦርድ በሚቀርበው ሐሳብ መሠረት ካፒታሉ እንዲቀነስ ሲወሰን፣
3. የድርጅቱ የተፈቀደ ካፒታል በዚህ አዋጅ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት በሙሉ ተከፍሎ ያላለቀ ሲሆን፡፡

## <u>ምዕራፍ 5</u>

## <u>የድርጅት ስምና የንግድ ምልክት</u>

23.**<u>የድርጅት ስም፣</u>**

1. የአንድ ድርጅት ስም ሥራውን የሚያከናውንበት ስም ሲሆን የድርጅቱን ሥራ በግልጽ የሚያመለክት ይሆናል፡፡
2. የአንድ ድርጅት ስም የመንግሥት ፖሊሲን እንዲሁም መልካም ሥነ ምግባርን የሚቃረንና የሶስተኛ ወገኖችን መብት የሚነካ አይሆንም፣
3. የማናቸውም ድርጅት ስም በሥራ ቦታው በግልጽ እንዲታይ ይደረጋል፡፡

24.**<u>የስም አጠቃቀም ሁኔታዎች፣</u>**

1. የአንድ ድርጅት ስም አመራረጥ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 23(2) በተመለከተው መሠረት መሆኑን ተቆጣጣሪው ባለሥልጣን ያረጋግጣል፡፡

2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 23(2) የተመለከተውን የተላለፈ ድርጅት ለደረሰው ጉዳት ካሣ እንዲከፍል እና ወይም ክርክር ባስነሳው ስም እንዳይጠቀም በፍርድ ቤት ሊወሰን ይችላል፡፡

25.**የንግድ ምልክት፣**

የንግድ ምልክት አንድ ድርጅት ለሚያመርተው ዕቃ ወይም ለሚሰጠው አገልግሎት መለያ በማድረግ የሚጠቀምበት ስም፣ ስያሜ፣ ዓርማ፣ ወይም ሌላ ማናቸውም መለያ ምልክት ነው፡፡

26.**የንግድ ምልክት አጠቃቀም ሁኔታዎች፣**

1. አንድ ድርጅት ማንኛውንም የንግድ ምልክት ሊመርጥ ይችላል፡፡
2. ማናቸውም የንግድ ምልክት የመንግሥት ፖሊሲ እንዲሁም መልካም ሥነ ምግባርን የሚቃረንና የሶስተኛ ወገኖችን መብት የሚነካ አይሆንም፡፡
3. የማናቸውም ድርጅት የንግድ ምልክት በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት አግባብ ባለው መሥሪያ ቤት ይመዘገባል፣ በሰፊው በሚሰራጭ ጋዜጣም ታትሞ ይወጣል፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከተውን የተላለፈ ድርጅት ላደረሰው ጉዳት ካሣ እንዲከፍል እና ወይም ክርክር ባስነሳው የንግድ ምልክት እንዳይጠቀም በፍርድ ቤት ሊወሰን ይችላል፡፡

**ምዕራፍ 6**

**ስለድርጅት ሂሳብና የሂሳብ ምርመራ**

**ዘርፍ አንድ**

**የድርጅት ሂሳብ**

27.**የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት፣**[60]

ማናቸውም ድርጅት በንግድ አሠራር ተቀባይነት ያለው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት ይኖረዋል፡፡ ይህንኑ ተግባራዊ ለማድረግ ተቆጣጣሪው ባለሥልጣን አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

28.**የሂሳብ ዓመት፣ ሂሣብ መዝጋትና ዓመታዊ ሪፖርት፣**

1. የአንድ ድርጅት የሂሳብ ዓመት በተቆጣጣሪው ባለሥልጣን ይወሰናል፣
2. ማናቸውም ድርጅት ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ሂሣቡን ይዘጋል፡፡ ዓመታዊው ሂሳብ የበጀት ዓመቱ ባለቀ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ መዝጋት አለበት፡፡

[60] ለ20/81 (2006) አ. 847 ዓላማ ይህ አንቀፅ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

3. ድርጅቱ ስላለፈው ዓመት የድርጅቱ ሥራዎችና አቋሞች ሁኔታ፣ ስለተከናወኑ ተግባሮችና በቅርብ ሥራ ላይ ሊውሉ ስለታሰቡ ዋና ዋና ዕቅዶችና ፕሮግራሞች ጭምር ሪፖርት ያዘጋጃል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የድርጅቱን ሂሳብ በወቅቱ አለመዘጋት በኃላፊነት የሚያስጠይቅ ይሆናል፡፡

29.<u>ስለመጠባበቂያ ሂሣቦችና አጠቃቀም፣</u>

1. ማናቸውም ድርጅት ሕጋዊ መጠባበቂያ ሂሳብ ይይዛል፡፡
2. በሌላ ሕግ በተለየ ሁኔታ የተወሰነው እንደተጠበቀ ሆኖ ማናቸውም ድርጅት ከተጣራ ትርፉ ላይ 5 በመቶ በየዓመቱ እያነሳ ሕጋዊ መጠባበቂያው ሂሳብ የድርጅቱን ካፒታል 20 ከመቶ እስኪያህል ድረስ ወደ መጠባበቂያ ሂሣቡ ያስገባል፡፡
3. ሕጋዊ መጠባበቂያ ሂሣቡ፣

   ሀ) ኪሣራን ለመሸፈን፣

   ለ) ያልታሰቡ ወጪዎችንና ዕዳዎችን ለመሸፈን፤ ሊውል ይችላል፣
4. የማናቸውም ድርጅት ቦርድ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑን እያስፈቀደ ሌሎች መጠባበቂያ ሂሣቦችን እንዲያዙ ለማድረግና አጠቃቀማቸውንም ለመወሰን ይችላል፡፡

30.<u>ስለግብር እና ቀረጥ ክፍያ፣</u>

1. የግብር እና ቀረጥ ክፍያን በሚመለከት አግባብ ያላቸው ሕጐች በድርጅቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡
2. ድርጅቶች በሌላ ሕግ መሠረት ከግብር እና ቀረጥ ነፃ ለመሆን ያላቸውን መብትና ሌላም መብት ይህ አዋጅ አያስቀርባቸውም፡፡

31.<u>የመንግሥት የትርፍ ድርሻ ክፍያ፣</u>

የዚህ አዋጅ አንቀጽ 11(8) እንደተጠበቀ ሆኖ ማናቸውም ድርጅት የሂሣብ ዓመቱ ከተፈጸመበት ጊዜ አንስቶ ባሉት ሰባት(7) ወራት ውስጥ የመንግሥቱን የትርፍ ድርሻ ለመንግሥት ፈሰስ ያደርጋል፡፡

## ዘርፍ ሁለት

## ስለ ሂሣብ ምርመራ

### 32. የኦዲተሮች አመዳደብ፣

1. በሌላ ሕግ ለዋናው ኦዲተር የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የማናቸውም ድርጅት ሂሣብ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን በሚሰይማቸው የውጭ ኦዲተሮች ይመረመራል፡፡
2. ተቆጣጣሪው ባለሥልጣን የሚሰይማቸውን የውጭ ኦዲተሮች በዋናው ኦዲተር የወጡ መመዘኛዎችን የሚያሟሉና ከማናቸውም ዓይነት ተጽእኖ ነፃ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡[61]
3. ተቆጣጣሪው ባለሥልጣን የውጭ ኦዲተሮችን የሥራ ጊዜ ይወስናል፡፡

### 33. ሂሣብ የማስመርመር ግዴታ፣

የተመርማሪውን ድርጅት ገንዘብ ወይም ንብረት የተረከበ ወጪ ያደረገ የከፈለ ወይም ለሂሳቡ ኃላፊ የሆነ ማንኛውም ሰው ሲጠየቅ ሂሣቡን የማስመርመርና አስፈላጊውን መረጃ የማቅረብ ግዴት አበለት፡፡

### 34. የኦዲተሮች ሥልጣን፣ ተግባርና ተጠያቂነት፣[62]

የንግድ ሕግ ቁጥር 373፣ 374፣ 375፣ 376፣ 378 እና 380 አስፈላጊው ለውጥ ተደርጎባቸው የኦዲተሮችን ሥልጣን ተግባርና ኃላፊነት በሚመለከት ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## ምዕራፍ 7

## ስለመዋሐድና ስለመከፋፈል

### 35. መሠረቱ፣

1. ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆነ ድርጅቶች አንዱ ሌላውን በመጠቅለልም ሆነ አንድ ሌላ አዲስ ድርጅት በመፍጠር በሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ ሊዋሐዱ ይችላሉ፡፡
2. አንድ ድርጅት ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ አዲስ ድርጅቶች እንዲሆን በሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ ሊከፋፈል ይችላል፡፡
3. የማዋሐዱም ሆነ የመከፋፈሉ ውሳኔ ተግባራዊ የሚሆነው በዚህ አዋጅ መሠረት በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ነው፡፡

---

[61] ለ20/81 (2006) አ. 847 ዓላማ ይህ ንዑስ አንቀፅ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

[62] ለ20/81 (2006) አ. 847 ዓላማ ይህ አንቀፅ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

36.የወል ድንጋጌዎች፣

1. ከአበዳሪ ድርጅት ጋር የብድር ስምምነት አድርጎ ዕዳውን ገና ያልከፈለ ድርጅት ከመዋሐዱ ወይም ከመከፋፈሉ በፊት የአበዳሪውንና የዋስትና ሰጪውን ስምምነት ይጠይቃል፡፡
2. አንድ ለማዋሐድ ወይም ለመከፋፈል የታሰበ ድርጅት ዕዳ ያለበት ሲሆን በመዋሐድ ወይም በመከፋፈል የሚፈጠረው ድርጅት በገንዘብ ጠያቂዎች በኩል የሚፈለግበትን ግዴታ ለመፈጸም የማይችል ከሆነ የማዋሐዱም ሆነ የመከፋፈሉ ውሳኔ አይሰጥም፡፡
3. የሚዋሐደው ወይም የሚከፋፈለው ድርጅት ካለፈው የሂሣብ ዓመት መጀመሪያ አንስቶ መዋሐዱ ወይም መከፋፈሉ እስከተፈጸመበት ጊዜ ድረስ ያለውን ሂሣብ ይዘጋል፣ በኦዲተርም ይመረመራል፡፡

37.የመብትና ግዴታ መተላለፍ፣

1. በመዋሐዱ ምክንያት ሕልውናውን የሚያጣው ድርጅት መብትና ግዴታ ወደሚጠቀልለው ወይም በመዋሐድ ወደሚፈጠረው አዲስ ድርጅት ይዛወራል፡፡
2. የሚከፋፈል ድርጅት መብትና ግዴታ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 38 በተመለከተው የመብትና ግዴታ ምደባ መሠረት በመከፋፈሉ ወደሚፈጠሩት አዲስ ድርጅቶች ይዛወራል፡፡

38.የሚከፋፈል ድርጅት መብትና ግዴታ አመዳደብ፣

1. ሀ) በመከፋፈል ላይ ያለ ድርጅት መብትና ግዴታ በመከፋፈል ወደሚፈጠሩት ድርጅቶች የሚመደበው ጉዳዩ የሚመለከተው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣንበሚወስነውመሠረት ይሆናል፡፡
   ለ) ተቆጣጣሪው ባለሥልጣን የድርጅቱን መከፋፈል ውሳኔ የያዘና መብትና ግዴታው በመከፋፈሉ በተፈጠሩት ድርጅቶት መካከል እንዴት እንደተመደበ የሚያሳይ የተሟላ ሪፖርት ያዘጋጃል፡፡
   ሐ) የሪፖርቱ አንድ ቅጅ በመከፋፈሉ የተፈጠረው እያንዳንዱ ድርጅት በሚቋቋምበት ጊዜ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ይቀርባል፣ በመከፋፈሉ የተፈጠረው እያንዳንዱ ድርጅትም አንድ ቅጅ ይሰጠዋል፡፡
   መ) ተቆጣጣሪው ባለሥልጣን የሪፖርቱን ዋና ዋና ነጥቦች የያዘ ማስታወቂያ በሰፊው በሚሰራጩ ጋዜጦች በአማርኛና በእንግሊዝኛ ታትሞ እንዲወጣ ያደርጋል፡፡

ሠ) በሌላ ሕግ የተቋቋመ የመንግሥት የልማት ሥራ ድርጅት መከፋፈልን በሚመለከት በዚህ ንዑስ አንቀጽ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ማለት በዚያው ሕግ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን የነበረው አካል ነው፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ቢኖርም፣ በመከፋፈሉ የተፈጠሩት ድርጅቶች ሁሉ የተከፋፈለው ድርጅት ለሶስተኛ ወገኖች የገባውን ግዴታ በሚመለከት በአንድነትና በነጠላ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

## ምዕራፍ 8

## ስለድርጅቶች መፍረስና ሂሣብ ስለማጣራት

**39.ድርጅት የሚፈርስባቸው ምክንያቶች፣**

ማናቸውም ድርጅት ከሚከተሉት ምክንያቶች ባንዱ ሊፈርስ ይችላል፡፡

1. በማቋቋሚያው ደንብ የተመለከተው የድርጅቱ የመቆያ ጊዜ ሲያልቅ፣
2. ድርጅቱ የተቋቋመበት ሥራ ሲያልቅ፣
3. ድርጅቱ የተቋቋመበት ዓላማ ሲከሽፍ ወይም ሊፈጸም የማይችል ሲሆን፣
4. ከመቶ ሰባ አምስት (75 በመቶ የሚሆነው የተከፈለው የድርጅቱ ካፒታል ሲጠፋ፣
5. የሚኒስትሮች ምክር ቤት የድርጅቱን ሕልውና የሚነካ ውሳኔ ሲሰጥ፣
6. የድርጅቱ መክሰር በፍርድ ቤት ሲወሰን፡፡

**40.በኪሣራ ጊዜ ስለሚደረግ የሂሣብ ማጣራት፣**

1. የመክሰር ሥርዓትን በሚመለከት የንግድ ሕግ 5ኛ መጽሐፍ ድንጋጌዎች አስፈላጊው ለውጥ ተደርጐባቸው በድርጅቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡
2. በንግድ ሕግ ቁጥር 1166 (1-2) የተደነገገው ቢኖርም ፍርድ ቤቱ የድርጅት መክሰር በንግድ ሕግ መሠረት በአጭር ሥነ ሥርዓት እንዲመራ ሊወስን ይችላል፡፡

**41.ስለሂሣብ አጣሪዎች ሹመት ተግባርና ሥልጣን፣**

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 39 (1-5) የተመለከቱት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ተቆጣጣሪው ባለሥልጣን በዋናው ኦዲተር የወጣውን መመዘኛ የሚያሟላ የድርጅቱ ሠራተኛ ያልሆነ አንድ ወይም ከአንድ በላይ ሂሣብ አጣሪዎች ይሾማል፡፡ በቂ ምክንያት ሲያጋጥም ተቆጣጣሪው ባለሥልጣን ሂሣብ አጣሪዎቹን ይሽርና በምትካቸው ሌሎች ሊሾም ይችላል፡፡

2. የሂሣብ አጣሪዎች በመፍረስ ላይ ያለውን ድርጅት መዝገቦችና ሂሣቦች ይረከባሉ፡፡
3. ተቆጣጣሪው ባለሥልጣን በተለየ ሁኔታ ካልወሰነ በስተቀር፣ ሂሣብ አጣሪዎች የድርጅቱን ንብረት በኃላፊነት ይይዛሉ፣ በዚህ አዋጅ ለቦርዱና ለዋናው ሥራ አስኪያጅ የተሰጠውም ሥልጣንና ኃላፊነት ይኖራቸዋል፣ ሆኖም ግዴታቸው ያላለቀ ውሎችን ለመፈጸም ወይም የሂሣብ ማጣራቱን ተግባር ለማሳካት አስፈላጊ ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር አዲስ ሥራ መጀመር አይችሉም፡፡
4. ቦርዱ ካለፈው የሂሣብ ዓመት መጨረሻ ጀምሮ የሂሣብ ማጣራት ተግባር እስከተጀመረበት ቀን ያለውን ጊዜ የሚሸፍን ስለድርጅቱ አቋም ሪፖርት አዘጋጅቶ ለሂሣብ አጣሪዎች ይሰጣል፡፡
5. ሂሣብ አጣሪዎችና ቦርዱ የድርጅቱን መብቶችና ግዴታዎች ባጭሩ የያዘ መግለጫ በጋራ አዘጋጅተው ይፈርሙበታል፡፡
6. ተቆጣጣሪው ባለሥልጣን በተለየ ሁኔታ ካልወሰነ በስተቀር ቦርዱና ዋናው ሥራ አስኪያጅ ሂሣብ አጣሪዎቹን በሥራቸው ይረዷቸዋል፡፡

42.<u>ባለገንዘቦችን ስለመጥራት፣</u>

1. ሂሣብ አጣሪዎች ድርጅቱ የሚፈርስ መሆኑንና ያላቸውን የገንዘብ ጥያቄም በማስረጃ በማስደገፍ እንዲያቀርብ ለባለገንዘቦች ያስታውቃሉ፡፡
2. ስማቸው በድርጅቱ መዝገብ ተይዞ ለሚገኘው፣ እንዲሁም በሌላ ሁኔታ ለታወቁ ባለገንዘቦች ማስታወቂያ በሪኮማንዴ ይላክላቸዋል፡፡ ሌሎች ባለገንዘቦች በሰፊው በሚሰራጭ ጋዜጣ በየሳምንቱ በሚወጡ ሶስት ተከታታይ ማስታወቂያዎች እንዲያውቁ ይደረጋል፡፡ ባለገንዘቦች ያላቸውን የገንዘብ ጥያቄ እንደነገሩ ሁኔታ ደብዳቤ ከደረሳቸው ወይም የመጨረሻው የጋዜጣ ማስታወቂየ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በዘጠና )90) ቀን ውስጥ የገንዘብ ጥያቄዎቻቸውን እንዲያቀርቡ ይደረጋል፡
3. ሂሣብ አጣሪዎች ስለድርጅቱ የሂሣብ አቋም መግለጫ አዘጋጅተው ስለዕዳው አከፋፈል ያላቸውን ሐሳብ የባለገንዘቦችን ዝርዝርና የአከፋፈሉን ቅደም ተከተል )የሚኖር ከሆነ) በመጨረሻ ለተቆጣጣሪው ባለሥልጣን ያቀርባሉ፡፡
4. ተቆጣጣሪው ባለሥልጣን ሂሣብ አጣሪዎች ያዘጋጁትን የሂሣብ አቋም መግለጫ መሠረት በማድረግና ስለዕዳው አከፋፈል ያቀረቡትን ሃሳብ በማመዛዘን፣

ሀ) የገንዘብ ጥያቄያቸውን በማስረጃ በማስደገፍ ላቀረቡ ባለገንዘቦች ክፍያው እንዲፈጸም ይፈቅዳል፣

ለ) የድርጅቱ ጥሬ ገንዘብ ለባለገንዘቦች መከፈል ያለበት ዕዳ የማይሸፍን ሆኖ ሲገኝ የሶስተኛ ወገኖች መብት ሳይነካ በሚያጸድቀው የሽያጭ ዘዴ አማካይነት የድርጅቱን ንብረቶች ሂሣብ አጣሪዎች እንዲሸጡ ይፈቅዳል፡፡

5. የድርጅቱ ጠቅላላ ንብረት ዕዳውን ለመክፈል በቂ በማይሆንበት ጊዜና የተፈቀደው ካፒታል በሙሉ ሳይከፈል ከቀረ ሂሣብ አጣሪዎች ቀሪው ሂሳብ እንዲከፈል ተቆጣጣሪውን ባለሥልጣን ይጠይቃሉ፡፡

43. <u>የባለገንዘቦችን መብት ስለመጠበቅ፣</u>

1. የታወቁ ባለገንዘቦች በዚህ አዋጅ አንቀጽ 42(2) በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጥያቄያቸውን ሳያቀርቡ የቀሩ እንደሆነ ሊከፈላቸው የሚገባ ገንዘብ በባለገንዘቦቹ ስም በባንክ ተቀማጭ ይሆናል፡፡

2. ባልተጠናቀቁ የድርጅቱ ሥራዎች መነሻነት የሚቀርቡ የገንዘብ ጥያቄዎችን ለመሸፈን የሚያስፈልገው ገንዘብ እንዲሁም ባለገንዘቦቹ ዋስትና ያልተሰጣቸው ከሆነ ክርክር ያስነሱ ዕቃዎችን ለመሸፈን የሚያስፈልገው ገንዘብ ክርክሩ እስከሚወሰን ድረስ ለብቻ ተቀማጭ ሆኖ ይያዛል፡፡

3. በአንቀጽ 44)2) መሠረት የድርጅቱ ሕልውና ካበቃ በኋላ የሚቀርብ በድርጅቱ መዝገብ ያልታወቀ ገንዘብ ጠያቂዎች የገንዘብ ጥያቄያቸውን በአንቀጽ 42(2) በተወሰነው ጊዜ ያላቀረቡት ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ከሆነ፣ በትርፍነት ለመንግሥት ከገባው ሀብት ላይ እንዲከፈላቸው ሊጠይቁ ይችላሉ፡፡ እንዲሁም በሂሣብ አጣሪዎች ቸልተኝነት ምክንያት ያልተከፈላቸው ባለገንዘቦች ሂሣብ አጣሪዎችን በኃላፊነት ሊጠይቁ ይችላሉ፡፡

44. <u>የመጨረሻ የሀብትና ዕዳ መግለጫ እና የመፍረስ ማስታወቂያ ስለማውጣት</u>

1. ባለገንዘቦች ከተከፈላቸውና ሊቀርቡ የሚችሉ የገንዘብ ጥያቄዎችን ለመሸፈን የሚያስፈልገው ገንዘብ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 43(1-2) መሠረት ተቀማጭ ከሆነ በኋላ ሂሣብ አጣሪዎች ድርጅቱ ትርፍ ሀብት ካለው ይህንኑ የሚያሳይ የመጨረሻ የሀብትና የዕዳ መግለጫ አዘጋጅተው ለተቆጣጣሪው ባለሥልጣን ያቀርባሉ፣ ለገንዘብ ሚኒስቴርና ለዋናው ኦዲተርም ግልባጭ ያደርጋሉ፡፡ ዋናው ኦዲተር የሚሰጠው አስተያየት ካለው ወዲያውኑ ለገንዘብ ሚኒስቴርና ለተቆጣጣሪው ባለሥልጣን ይሰጣል፡፡ ተቆጣጣሪው ባለሥልጣን የገንዘብ

ሚንስቴርን ስምምነት በማግኘት የመጨረሻውን የሀብትና የዕዳ መግለጫ ሲያጸድቀው ወዲያውኑ ድርጅቱ እንዲፈርስ መወሰኑን ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ያስታውቃል፡፡

2. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ድርጅቱ የተቋቋመበትን ደንብ ይሠርዛል፡፡ ከዚህም ጊዜ ጀምሮ የድርጅቱ ሕልውና ያበቃል፡፡
3. የፈረሰ ድርጅት መዝገቦች በተቆጣጣሪው ባለሥልጣን ዘንድ ተቀምጠው ለ10 ዓመት ይቆያሉ፡፡ እነዚህን መዝገቦች ለማየት የሚፈልጉ ሰዎችም ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ በመክፈል መመርመር ይችላሉ፡፡

45.<u>ለመንግሥት ገቢ ስለሚሆን ሀብት</u>

ፈርሶ ሂሣቡ የተጣራ ድርጅት ትርፍ ሀብት ለመንግስት ገቢ ይሆናል፡፡

## <u>ምዕራፍ 9</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

46.<u>በሌሎች ሕጐች ስለተቋቋሙ ድርጅቶች፣</u>

1. ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በሌላ ሕግ የተቋቋመ ማንኛውም ድርጅት፣
   ሀ) በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ እንደገና እንዲቋቋም፣ ተከፋፍሎ አዲስ በሚቋቋሙ ድርጅቶች እንዲተካ ወይም ከሌላ ድርጅት ጋር እንዲዋሃድ ሊደረግ ወይም፣
   ለ) በዚህ አዋጅ መሠረት እንደተቋቋመ ተቆጥሮ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ሊሰይምለትና በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት እንዲተዳደር ሊደረግ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1)ሀ) መሠረት የሚቋቋሙ ድርጅቶች አንድን ድርጅት በመከፋፈል ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ድርጅቶችን በማዋሐድ የሚፈጠሩ ሲሆን የተከፈለውን ድርጅት ወይም የተዋሐዱትን ድርጅቶች ሂሳብ መዝጋትና መመርመር እንዲሁም መብትና ግዴታ ማስተላለፍን በሚመለከት የዚህ አዋጅ አንቀጽ 36(3)፣ 37 እና 38 ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

47.<u>የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር፣</u>

የሚኒስትሮች ምክር ቤት፣

1. በዚህ አዋጅ መሠረት፣
   ሀ) ድርጅት የማቋቋም፣

ለ) ለሚያቋቁመው ድርጅት ካፒታል የመመደብና ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን የመሰየም፣

ሐ) ድርጅት የማፍረስ፣

መ) አንድ ድርጅት ከሌላ ድርጅት ጋር እንዲዋሐድ ወይም እንዲከፋፈል የመወሰን፣

2. የሶስተኛ ወገኖች መብት ሳይነካ፣

ሀ) ማናቸውም ድርጅት በንግድ ሕግ መሠረት የንግድ ማኅበር ሆኖ እንዲቋቋም፣

ለ) ማናቸውም ድርጅት እንዲሸጥ ወይም በሌላ አኳኋን ድርጅቱ ወይም ማኔጅመንቱ እንዲተላለፍ የመወሰን፣

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2)ሀ) መሠረት በሚቋቋም የንግድ ማኅበር በመንግሥት የተያዘ አክስዮን እንዲሸጥ የመወሰን፣

4. ይህን አዋጅ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ደንቦችን የማውጣት፣ ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡፡

48.<u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ፣</u>

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ 21 ቀን 1984 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት ፕሬዚዳንት**

## አዋጅ ቁጥር 1206/2012

## የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ወደግል ስለማዛወር የወጣ አዋጅ

የሀገሪቱን የኢኮኖሚ እድገትና ትራንስፎርሜሽን ዘላቂነት እንዲኖረው ለማድረግ እና ለግል ኢንቨስትመንት አመቺ የሆነ የፖሊሲ ከባቢዎችን ለመፍጠር የሕግ ማሻሻያዎች ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ለሀገሪቱ የኢኮኖሚ ልማት ስትራቴጂ አፈጻጸም አስተዋጽዎ እንዲኖረው ለማድረግ ለልማት የሚውልን የፋይናስ አቅርቦት ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የግል ዘርፉ በኢኮኖሚ ውስጥ የሚኖረውን ሚናና ተሳትፎ ማስፋፋትና ማዳበር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ቅልጥፍና ማሻሻል፣ ተወዳዳሪነታቸውን ማጎልበት፣ ለካፒታል ያላቸውን ተደራሽነት እና የአገልግሎታቸውን ጥራትና ተደራሽነት ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ይህንኑ ዓላማ ከግብ ለማድረስ በሰፊ መሠረት ላይ የተጣለ ይፋና ግልጽ የሆነ የፕራይቬታይዜሽን ፕሮግራም ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የመንግሥት የልማት ድርጀቶችን ወደ ግል ስለማዛወር የወጣ አዋጅ ቁጥር 1206/2012" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፣ በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. "ፕራይቬታይዜሽን" ማለት የልማት ድርጅትን ንብረት ወይም አክሲዮኖችን በሙሉ ወይም በከፊል ለግል ዘርፉ በሽያጭ የማስተላፍ ውጤት የሚያስከትል ግብይት ነው፤

2. “የመንግሥት የልማት ድርጅት” ማለት በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 የሚተዳደር የመንግሥት የልማት ድርጅት ነው፤
3. “ቅድመ ፕራታይዝሽን ሥራዎች” ማለት በሚኒስቴሩ የሚከናወን የልማት ድርጅትን ንብረት ወይም አክሲዮኖችን በሙሉ ወይም በከፊል ወደ ግል ለማዛወር የታቀደ ማናቸውም ዝግጅት ወይም ሂደት ነው፤
4. “ወርቃማ አክሲዮን“ ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የመንግሥት የልማት ድርጅትን በመለወጥ የካፒታሉ አካል የሆነና በማናቸውም የቦርድ ውሳኔ ላይ ድምፅ የመስጠትና ድምፅን በድምፅ የመሻር መብቶችን ለመንግሥት የሚያጎናጽፍ በአክሲዮን መመስረቻ ፁሁፍ ውስጥ የተደነገጉ ልዩ መብቶችን የያዘ አክሲዮን ነው፤
5. “ኤጀንሲ” ማለት የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ ነው፤
6. “ሚኒስቴር” እና “ሚኒስትር” ማለት እንደቅደምተከተሉ የገንዘብ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤
7. “ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን” ማለት ኤጀንሲውን ጨምሮ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 መሠረት የመንግሥት የባለቤትነት መብቶችን ለመከታተል፣ ለመጠበቅ፣ ለመተግበር በሚኒስትሮች ምክር ቤት የተሰየመ ባለሥልጣን ነው፤
8. “ባለአደራ” ማለት በሚኒስቴሩ ሥር የተደራጀ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ዳይሬክቶሬት ጄነራል ነው፡፡
9. “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
10. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ፆታ ይጨምራል፡፡

3. **<u>የፕራይቬታይዜሽን ዓላማዎች</u>**

ፕራይቬታይዜሽን ፕሮግራም የሀገሪቱን የኢኮኖሚ ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን የሚደግፍ በግልፅነት፣ በአሳታፊነትና በተአማኒነት መርሆዎች ላይ ተመሥርቶ የሚከናወን ሲሆን የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፦

1. የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ውጤታማነትን ማሻሻል፣ ተወዳዳሪነታቸውን ማጎልበት፣ የቴክኒክ ሙያንና ክህሎትን መጋበዝ እና የካፒታል አቅርቦትን ማሻሻል፤
2. መንግሥት የሚያካሂዳቸውን የፋይናንስ እንቅስቃሴዎች ለማጎልበት ገቢዎችን ማሰባሰብና የልማት ፋይናንስ አቅርቦትን ማጎልበት፤

3. ለግል ኢንቨስትመንት የፖሊሲ ከባቢዎችን በማጎልበትና የግል ዘርፉን መስፋፋት በማበረታት የሀገሪቱን የኢኮኖሚ ልማት ማሳደግ፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለቅድመ ፕራይቬታይዚሽን ሥራዎች

4. ለቅድመ ፕራይቬታይዜሽን ሥራዎች የተለያዩ አካላት ኃላፊነት

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚኒስቴሩን እና የተቆጣጣሪውን ባለሥልጣን የውሳኔ ሃሣብ ከግምት ውስጥ በማስገባት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ወደ ግል መዞር ያለበትን የልማት ድርጅት ይወሰናል፡፡
2. ሚኒስቴሩ፡-

ሀ) ማናቸውንም የቅድመ ፕራይቬታይዜሽን ሥራዎች የሚያከናውን ሲሆን የሚመለከተውን የመንግሥት የልማት ድርጅት ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን በማማከር የቅድመ ፕራይቬታይዜሽን ሂደት መቼ መጀመር እንዳለበትና የትኞቹ ሥራዎችም መካተት እንዳለባቸው፣

ለ) ከመንግሥት የልማት ድርጅት ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ጋር በመመካከር የእያንዳንዱን ሽያጭ አመላካች የሽያጭ ዋጋ (ወይም መነሻና መድረሻ ዋጋ እና ወደ ግል የሚዛወረውን የአክሲዮን መጠንን (የድርጅቱን መጠን፣

ሐ) የመንግሥት የልማት ድርጅት ዋጋ ግምትን፣ እንደገና የማዋቀር ጥረቶች ውጤቶችን፣ ወቅታዊው የገበያ ሁኔታዎችን እና ድርጅቱ ኢንቬስተሮችን መሳብ የመቻሉን ዕድል ከግምት ውስጥ በማስገባት እያንዳንዱ የመንግሥት የልማት ድርጅት ወደ ግል ለመዛወር ያለውን ዝግጁነት፣ ይወስናል፡፡

3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግሥት የልማት ድርጅቱ ለፕራይቬታይዜሽን ዝግጁ መሆኑ ታምኖ የፕራይቬታይዜሽን ስልቱ ሲወሰን ኤጀንሲው ፕራይቬታይዜሽኑን የመተግበር እንቅስቃሴ ይጀምራል፡፡
4. ወደ ግል የሚዛወር የልማት ድርጅት የሥራ አመራር ቦርድ፡-

ሀ) ከሚኒስቴሩ እና ከተቆጣጣሪው ባለሥልጣን በሚቀርብለት ጥያቄ መሠረት የመንግሥት የልማት ድርጅቱን በሚመለከት የተሟላ መረጃ ይሰጣል፤

ለ) ከተቆጣጣሪው ባለሥልጣን ጋር በመመካከር በሚኒስቴሩ በተሰጡ መመሪያዎች መሠረት የመንግሥት የልማት ድርጅቱን ለቅድመ ፕራይቬታይዜሽንና ለፕራይቬታይዜሽን ያዘጋጃል፤

ሐ) በቅድመ ፕራይቬታይዜሽን ሂደትና በፕራይቬታይዜሽን ወቅት የልማት ለብክነት አለመዳረጉን ያረጋግጣል፤

መ) በመደበኛው የንግድ እንቅስቃሴ ምክንያት ወይም በሚኒስቴሩ ስምምነት ካልሆነ በቀር፣ በቅድመ ፕራይቬታይዜሽን ወቅትና በፕራይቬታይዜሽን ደረጃ ማናቸውም አዲስ ኢንቬስትመንት ከማድረግ መቆጠብ ይኖርበታል፡፡

5. <u>በቅድመ ፕራይቬታይዜሽን የመንግሥት የልማት ድርጅትን እንደገና ስለማዋቀርና ሌሎች ተግባሮች</u>

1. ሚኒስቴሩ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) መሠረት ከተቆጣጣሪው ባለሥልጣን ጋር በመቀናጀት የልማት ድርጅቱ ወደ ግል ከመዛወሩ በፊት ተገቢው የካፒታል አደረጃጀቶች፣ የንግድ ስትራቴጂ፣ የኮርፖሬት አስተዳዳር መዋቅሮች እና የሪፖርት አቀራረብና የመረጃ አገላለጽ ልምዶች ያለው መሆኑን ይገመግማል፤ ጉድለት በሚኖርበትም ጊዜ አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል፡፡
2. ተቆጣጣሪው ባለሥልጣን የሚኒስቴሩን የቅድመ ፕራይቬታይዜሽን እንቅስቃሴን ለመደገፍ በመንግሥት የልማት ድርጅቱ ላይ ክትትል ባደረገበት ወቅት ያደረጋቸውን ማናቸውንም የኦፕሬሽን ግምገማዎችንና ተዛማጅ መረጃዎችን ለሚኒስቴሩ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
3. ሚኒስቴሩ አስፈላጊ የሆኑ ማናቸውም የኦፕሬሽንና የፋይናንስ ሥርዓትን እንደገና የማዋቀር ኃላፊነት አለበት፤ ወደ ግል ከመዛወሩ በፊትም እንደገና መዋቀሩ የመንግሥት የልማት ድርጅቱን ዋጋና ተፈላጊነቱን የሚያሳድግ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡
4. ሚኒስቴሩ ከፕራይቬታይዜሽን በኋላ ተገቢ ያልሆነ የውድድር ባህርያት፣ የገበያ ልምዶች እና መጠኑ ያለፈ የገበያ የበላይነት እንዳይከሰት በፕራይቬታይዜሽን ደረጃ ወይም ወቅት በሥራ ላይ ባለው ሕግ መሠረት አስፈላጊውን እርምጃ ሁሉ ይወስዳል፡፡

6. <u>የመንግሥት የልማት ድርጅትን ወደ አክሲዮን ማኅበርነት ስለመለወጥ</u>

1. የንግድ ሕግ አንቀጽ 307/1 ቢኖርም፣ አንድን የመንግሥት የልማት ድርጅትን ለፕራይቬታይዜሽን ዝግጁ ለማድረግ በአንድ ባለአክሲዮን ባለቤትነት ወደሚያዝ የአክሲዮን ማኅበርነት ሊለወጥ ይችላል፡፡

2. የልማት ድርጅቱ ወደ አክሲዮን ማኅበርነት በሚለወጥበት ወቅት አክሲዮኖቹ ወደ ግል ባለቤትነት እስከሚዛወሩ ድረስ የድርጅቱ ካፒታል በአክሲዮኖች ተከፋፍሎ አክሲዮኖቹ በመንግሥት ይያዛሉ፡፡
3. በንግድ ሕጉ ለባለአክሲዮኖች ጉባዔ የተሰጡ ሥልጣኖች በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ መሠረት አግባብነት ላለው የመንግሥት የልማት ድርጅት ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን እንደተሰጡ ይቆጠራሉ፡፡
4. ከንግድ ሕጉ አንቀጽ 307/1፣ አንቀጽ 311፣ አንቀጽ 347 /1 እና አንቀጽ 349 በስተቀር ሌሎቹ የንግድ ሕግ ድጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡
5. በንግድ ሕጉ አንቀጽ 546 ከንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (4) እና በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 69/1 እና 2 የተደነገጉት ቢኖሩም፣ ሚኒስቴሩ የመንግሥት የልማት ድርጅትን ወደ አክስዮን ማኅበርነት በሚለውጥበት ጊዜ ለአክሲዮን ማኅበሩ የሚተላለፉትን የመንግሥት የልማት ድርጅቱን ሀብትና ዕዳዎች እንዲሁም ንብረቶቹ እንደገና ከተገመቱ በኋላ ካፒታሉን የመወሰንና የማሳደግ ሥልጣን ይኖረዋል፡፡
6. ወደ አክሲዮን ማኅበርነት የተለወጠ የመንግሥት የልማት ድርጅት እንደተመዘገበ ህልውናው ያከትማል፡፡

7. <u>***የመንግሥት የልማት ድርጅቱን ዋጋ ስለመተመን***</u>

1. ሚኒስቴሩ የልማት ድርጅትን፣ የልማት ድርጅትን የተወሰነ ክፍል ወይም ንብረት ወይም የመንግሥት አክሲዮንን ወደ ግል ለማዛወር በቅድሚያ ዋጋው ገለልተኛ በሆነ ብቃት ባለው ባለሙያ እንዲተመን ማስደረግ አለበት፡፡
2. የዋጋ ትመናው የሚከናወነው በሚኒስቴሩ ቁጥጥር ሥር የሚደረገው የልማት ድርጅቱን የፋይናንስ እና)ወይም የኦፕሬሽን እንደገና የማደራጀት ሥራ መጠናቀቅ ተከትሎ ሚኒስቴሩ ባወጣው የዋጋ ትመና መመሪያ መሰረት ይሆናል፡፡
3. በዋጋ ትመናው መሰረት የሚወሰነው የመሸጫ መነሻ ወይም አመልካች ዋጋ በፕራይቬታይዚሽኑ ሂደት በኤጀንሲው ጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት በሚኒስቴሩ መጽደቅ አለበት፡፡

## ክፍል ሦስት

## የፕራይቬታይዚሽን አፈጻጸም ማዕቀፍ

### 8. የፕራይቬታይዜሽን አፈጻጸም

1. ሚኒስትሮች ምክር ቤት የፕራይቬታይዜሽን አፈጻጸምን በተመለከተ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

ሀ) ከኤጀንሲው ውጭ ላለ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ተጠሪ የሆነን የመንግሥት የልማት ድርጅት ወይም በተቆጣጣሪ ባለሥልጣን የተያዙ አክሲዮኖች ወደ ግል ማዛወሩ ከመከናወኑ በፊት ለኤጀንሲው መተላለፋቸውን ያፀድቃል፤

ለ) የሚኒስቴሩንና የኤጀንሲውን የውሳኔ ሀሳብ ከግምት ውስጥ በማስገባት የማናቸውም ወርቃማ አክሲዮን አጠቃቀም፣መዋቅር እና አተገባበሩን ያፀድቃል፤

2. ኤጀንሲው የፕራይቬታይዜሽንን አፈጻጸም በተመለከተ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፦

ሀ) የሽያጭ ማከናወኛ ሥነ ሥርዓቶችን ያዘጋጃል፤

ለ) ለእያንዳንዱ ሽያጭ የሚያገለግል የጨረታ መመዘኛ መስፈርቶችን ይወስናል፤

ሐ) የመሸጪያ ጊዜን ይወስናል፣እያንዳንዱን ሽያጭ ያመቻቻል፣ ሽያጩን በበላይነት ይከታተላል፤

መ) ሽያጭ ሲከናወን የሚያግዙ ባለሙያዎችን ይቀጥራል፤

ሠ) ፍላጎት ያላቸው ኢንቬስተሮች በግዢው እንዲሳተፉ ከበቂ ጊዜ ጋር ሽያጩን በሕዝብ መገናኛ ያሳውቃል፤

ረ) አስፈላጊውን ሰነዶችና ናሙና ውሎችን ያዘጋጃል፤

ሰ) በማናቸውም ድህረ ፕራይቬታይዜሽን ኢንቬስትመንት መስፈርቶች ላይ ውሳኔ ይሰጣል፤

ሸ) ማንኛውም ባለሀብት በረዥም ጊዜ በሚፈጸም ክፍያ የሽያጩን ዋጋ የመክፈል መብት የሚሰጠው መሆን አለመሆኑን እና ክፍያ የሚፈጸምበትን ሕጋዊ ገንዘብ ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ጋር በመመካከር ይወስናል፤

ቀ) የፕራይቬታይዜሽን ሂደት አተገባበሩ ሥርዓት ያለው፣ ሕጋዊ፣ግልጽና ቀልጣፋ መሆኑን ያረጋግጣል፤

በ) ከፕሮግራሙ አፈጻጸም ጋር በተያያዙ የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ እንደአግባቡ ለመንግሥት የውሳኔ ሃሣብ ያቀርባል፤

ተ) ከሕዝብ ጋር ግንኙነት ይፈጥራል፣ የፕራይቬታይዜሽን ፕሮግራም እንቅስቃሴዎችን ወይም ክንዋኔዎችን ያስተዋውቃል፡፡

3. የመንግሥት የልማት ድርጅት ለፕራይቬታይዜሽን ዝግጁ መሆኑ ከተረጋገጠ እና የፕራይቬታይዜሽን ስልቱ በሚኒስቴሩ ሲወሰን ኤጀንሲው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 ከንዑስ አንቀጽ (2) እስከ (4) በተደነገገው መሠረት ለዚሁ ባቋቋመው ክፍል አማካይነት ወደ ግል የማዛወሩን ተግባር ማከናወን ይጀምራል፡፡
4. ኤጀንሲው ከሚኒስቴሩ ጋር በመቀናጀት የመሸጪያ መነሻ ዋጋ ወይም በግብይት ወይም በንግድ ላይ የተመሠረተ ተመሳሳይ ዋጋ ወይም በውድድር ላይ የተመሠረተ ጨረታ ወይም በጨረታ ላይ የተመሠረተ ተመሳሳይ ሽያጭ ከመጀመሩ ቀድም ብሎ የሚቀርበውን የመጨረሻውን የሽያጭ መጠንን እና የአክሲዮን ዋጋን ይወስናል፡፡
5. ኤጀንሲው ፕራይቬታይዜሽንን፣ ለሽያጭ የሚቀርበውን የአክሲዮን ዋጋን ወይም መጠንን ወይም የልማት ድርጅቱን ድርሻ በተመለከተ የቀረበውን ሀሳብ በገበያው፣ በዘርፉ ሁኔታዎች ወይም በሌሎች ምክንያቶች መቀያየር ማሻሻል የሚያስፈልግ ሆኖ ከተገኘ ለሚኒስቴሩ መልሶ ያሳውቃል ፡፡
6. የመንግሥት የልማት ድርጅትን ወደ ግል ማዛወር ያልተቻለ እንደሆነ ተቆጣጣሪው ባለሥልጣን አግባብ ባላቸው የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ሕግ መሠረት ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ጥያቄ አቅርቦ ሲፀድቅለት የመንግሥት የልማት ድርጅቱ ሊፈርስ ይችላል፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>የፕራይቬታይዜሽን ስልቶች</u>

### 9. <u>የፕራይቬታይዜሽን ስልቶች</u>

1. በሥራ ላይ የሚውል ማናቸውም የፕራይቬታይዜሽን ስልት አተገባበር በግልጽነት መርሆዎች ላይ የተመሠረተ እና ግቡም ለመንግሥት ተስማሚ የሆኑ ስምምነቶች ላይ መድረስ ነው፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ከዚህ በታች ከተመለከቱት የፕራይቬታይዜሽን ስልቶች አንዱ እንደአግባቡ ተፈጻሚ ሊሆን ይችላል፤

ሀ) በውድድር ላይ በተመሠረተ ጨረታ፤

ለ) ለሕዝብ ክፍት በሆነ ጨረታ፤

ሐ) የአክሲዮን ገበያ ወይም ሌሎች ተስማሚ የግብይት መድረኮች ያሉ እንደሆነ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ለሕዝብ ለሽያጭ በሚቀርብ አክሲዮን፤

መ) በረዥም ጊዜ ተከፋፍሎ በሚሸጥ የተሰበጣጠረ ግገር፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ኤጀንሲው በሚኒስቴሩ ፈቃድ ተስማሚና ለኢንዱስትሪው ደረጃ የሚመጥን የንግድ ወይም የስትራቴጂክ ሽያጭን በቅድሚያ በተመረጡ አነስተኛ ቁጥር ባላቸው የኮርፖሬት ኢንቬስተሮች ላይ ያነጣጠረ ሽያጮችን የመሳሰሉ ሌሎች የፕራይቬታይዜሽን ስልቶችን መምረጥ ይችላል፡፡ጠቀሜታቸው በበቂ ምክንያት የተደገፈ ከሆነ ሂደቱም በተቻለ መጠን በግልጽነት መሆን ይኖርበታል፡፡

4. የፕራይቬታይዜሽን ስልቶች በተመለከተ የተደነገገው ቢኖርም፣ ሚኒስቴሩ ከኤጀንሲው ጋር በመመካከር ከሚሸጡት አክሲዮኖች ውስጥ የተወሰኑት በመንግሥት የልማት ድርጅቱ ሠራተኞች ተለይተው የሚያዙበትን ሁኔታ እና የአክሲዮኖቹን ዋጋና መጠን ይወስናል፡፡

5. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የፕራይቬታይዜሽን ሽያጭ የመንግሥትን አክሲዮኖች መቶ በመቶ ወይም ከፊሉን ሊያካትት ይችላል፡፡

6. አብላጫውን ወይም ወሳኝ የሆኑ አክሲዮኖችን ሽያጭ በሚመለከት መንግሥት ወርቃማውን አክሲዮን ማስቀረትን መምረጥ ይችላል፡፡ ወርቃማ አክሲዮን መንግሥት የሕዝብ ጥቅምን አያስጠብቅም ብሎ ባመነበትን በማናቸውንም የቦርድ ውሳኔ ላይ ድምፅ የመስጠትና ድምፅን በድምጽ የመሻር መብት ያጎናጽፈዋል፡፡

7. የፍታብሔር ሕግ አንቀጽ 1750 ድንጋጌ ቢኖርም፣ የመንግሥት የልማት ድርጅቱ የሽያጭ ዋጋ የሚከፈለው በውሉ በተመለከተው ሕጋዊ ገንዘብ ይሆናል፡፡

## ክፍል አምስት

## ድህረ ፕራይቬታይዜሽን ታሳቢዎችና ግምገማዎች

### 10.ድህረ ፕራይቬታይዜሽን የኢንቬስትመንት ታሳቢዎች እና ግምገማዎች

1. የድህረ ፕራይቬታይዜሽን የኢንቬስትመንት ግዴታዎች የፕራይቬታይዜሽን ውሉ አካል ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

2. የልማት ድርጅት ገዢ በውሉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ እና በሽያጭ ውሉ በተደረሰው ስምምነት መሠረት ማናቸውንም ድህረ ፕራይቬታይዜሽን ኢንቬስትመንት የመፈጸም ግዴታ አለበት፡፡

3. ኤጀንሲው የድህረ ፕራይቬታይዜሽን ግዴታዎች አፈጻጸምን ይከታተላል፡፡
4. ባለሀብቱ የውል ግዴታዎችን ለመከታተል የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ለኤጀንሲው በየጊዜው የማቅረብ እና የኤጀንሲው ተወካዮች ቅድመ ዝግጅት በማድረግ በማናቸውም ጊዜ ወደ ተሸጠው የልማት ድርጅት እንዲገቡና ግምገማ እንዲያካሂዱ የመፍቀድ ግዴታ አለበት፡፡

11.<u>ድህረ ፕራይቬታይዜሽን ግምገማ</u>

1. ኤጀንሲው በፕራይቬታይዜሽን ክንውኑ ላይ ግምገማ የሚያካሂድ ገለልተኛ ባለሙያ በመሾም በግኝቶቹ ላይ ዓመታዊ ሪፖርት ማውጣት ይኖርበታል፡፡
2. የግምገማው ሪፖርት የተላለፉና ቀሪ የሆኑ ወይም የተከፈሉ የመንግሥት ዕዳዎችን፣ የመንግሥት ዋስትናዎች ያሉበትን ደረጃና ሌሎች ተያያዥ ዕዳዎችን፣ ወደ ግል በተዛወረው የመንግሥት የልማት ድርጅት የመንግሥት ገንዘብ ያለመኖር ያስከተለውን ተፅዕኖ ወይም ውጤቶች፣ በግል ዘርፉ ውጤታማነት መገምገም ይኖርበታል፡፡እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች የግምገማ መለኪያዎችን ማካተት ይኖርበታል፡፡

12.<u>ስለ ልማት ድርጅቶች መብትና ግዴታ መተላለፍ</u>

1. ወደ ግል የተዛወረ የመንግሥት የልማት ድርጅት በአክሲዮን ማኅበርነት እንደተመዘገበ ህልውናውን ያጣል፡፡ የመንግሥት የልማት ድርጅቱ መብቶችና ግዴታዎች በሽያጭ ውሉ መሠረት ለገዢው መተላለፍ ይኖርባቸዋል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም፣ ተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሣቦች ወደ ገዢው እንደማይተላለፉ በሽያጭ ውሉ ውስጥ ስምምነት ከተደረገ ከዚሁ ጋር የተያያዙ መብትና ግዴታዎች ወደ ባለአደራ ይተላለፋሉ፡፡
3. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (5) መሠረት ከሚኒስቴሩ ውሳኔ በኋላ ወደ አክሲዮን ማኅበርነት ወደ ተለወጠው የመንግሥት የልማት ድርጅት ከተላለፉት ሀብትና ዕዳዎች ላይ ዕዳቸው ተከፍሎ የቀሩ ንብረትና ዕዳዎች ወደ ባለአደራ መተላፍ ይኖርባቸዋል፡፡
4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ድንጋጌዎች በአዋጅ ቁጥር 110/1987 መሠረት በኤጀንሲው በተሰጠ ውሳኔ ለቀድሞው ባለንብረቶች ለተመለሱ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የሚተላለፉ መብትና ግዴታዎችን በተመለከተ በተመሳሳይ ሁኔታ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

5. የመንግሥት የልማት ድርጅት ወደ ግል ከመዛወሩ በፊት የነበረ የጡረታ ሽፋን ሳይቋረጥ ይቀጥላል፡፡ የአዲሱ ድርጅት ባለቤት የሠራኞችን ጡረታ በተመለከተ አግባብ ባላቸው ሕጎች በአሠሪዎች ላይ የተጣሉትን ግዴታዎች ማክበር ይኖርበታል፡፡

13.<u>አለመግባባትን ስለመፍታት</u>

1. በውላቸው ውስጥ በግልጽ በተመለከተ የግልግል ዳኝነት ሂደት ወይም አካል እንዲታይ የተስማሙ ካልሆነ በስተቀር፣ በኤጀንሲውና በመንግሥት የልማት ድርጅት ገዢ መካከል የሚነሳ ክርክር የሚቀርበው ሥልጣን ላለው የፌደራል ፍርድ ቤት ይሆናል፡፡
2. ተዋዋይ ወገኖች ክርክራቸው በግልግል ዳኝነት አካል እንዲታይ የተስማሙ ከሆነ፣ የግልግል ሂደቱ በውሉና አግባብ ባላቸው የፍትሐብሔር ሕግና የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ይመራል።

14.<u>ስለታክስ</u>

1. ታክስ የሚያርፍባቸውን ገቢዎች መወሰንን በተመለከተ የንብረት የእርጅና ቅናሽ ስሌት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 መሠረት በተደረገው የልማት ድርጅቶች ዋጋ ግምት ላይ የተመሠረተ ይሆናል፡፡ ሆኖም የጨረታው ዋጋ አነስተኛ ከሆነ ገዢው በከፈለው ትክክለኛ ገንዘብ ላይ የተመሠረተ ይሆናል፡፡
2. ኤጀንሲው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተወሰነውን የንብረቶቹን ዋጋ ዝርዝር ለሚመለከተው የታክስ ባለሥልጣን ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
3. ኤጀንሲው ከንብረት ባለቤትነት ሰነድ ጋር በተያያዘ የቀረጥ ቴምብር የተከፈለባቸውን ለገዢው የተላለፉ ንብረቶች ዋጋ ዝርዝርንም ሚመለከተው የታክስ ባለሥልጣን ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

<u>**ክፍል ስድስት**</u>

<u>**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**</u>

15.<u>ከፕራይቬታይዜሽን የተገኘ ገንዘብን ስለመጠቀም</u>

ከፕራይቬታይዜሽን ከተገኘ ገንዘብ ላይ ለክንውኑ የተደረገው ወጪ ተቀንሶ ቀሪው ገንዘብ ሚኒስቴሩ በሚያስተዳድረው የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ የባንክ ሂሣብ ተቀማጭ ይደረጋል፡፡

16.<u>የመተባበር ግዴታ እና የኤጀንሲው ኃላፊነት</u>

1. ማንኛውም የፌደራል ወይም የክልል መንግሥት አካል ወይም የመንግሥት ባለሥልጣን የፕራይቬታይዜሽን ፕሮግራሙን በማስፈጸም ሂደት የሚጠየቀውን መረጃ ወይም ድጋፍ በመስጠት የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ለኤጀንሲው የሚተላለፉ መረጃዎችና ለገዢዎች የሚሰጡ አገልግሎቶች የሚቀርቡበት የጊዜ ገደብ በኤጀንሲው ይወሰናል፡፡
3. ከባለቤትነት ማስረጃዎች፣ ከአገልግሎት ውሎች እና ከንግድ ፈቃዶች ዝውውር ጋር በተያያዘ ገዥው ፎርማሊቲዎችን ለማሟላት የሚያጠፋው ጊዜ የጊዜ ገደቡን ለማስላት ታሳቢ አይሆንም፡፡

17.<u>ሕገወጥ ባለይዞታዎችን ስለማስለቀቅ</u>

1. ወደ ግል እንዲዛወር የተደረገ የልማት ድርጅት ሕንፃን ወይም ቅጥር ግቢን በሕገወጥ መንገድ በመያዝ ርክክብ እንዳይፈጸም ያወከ ሰውን ለማስለቀቅ የክስ አቤቱታ የቀረበለት ፍርድ ቤት የይዞታውን ሕጋዊነት የሚያሳይ መከላከያ ካልቀረበለት በስተቀር በ30 (ሰላሣ) ቀናት ውስጥ የማስለቀቂያ ትእዛዝ በመስጠት ውሳኔውን ያስፈጽማል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ከአዋጅ ውጭ ስለተወሰዱ ንብረቶች በወጣው አዋጅ ቁጥር 110/1987 መሠረት በኤጀንሲው ውሳኔ ለቀድሞ ባለቤቶቻቸው በሚመለሱ ንብረቶችም ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ ሆኖም የይዞታውን ሕጋዊነት የሚመለከት መከላከያ ተቀባይነት አይኖረውም።

18.<u>የተሻሩ እና ተፈጻሚ የማይሆኑ ህጎች</u>

1. የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ወደ ግል ለማዛወር በወጣው አዋጅ ቁጥር 146/1991 (እንደተሻሻለ በዚህ አዋጅ ተሽሯል።
2. ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ ደንብ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

19. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

ከዚህ አዋጅ መውጣት በፊት የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ወደ ግል ለማዛወር በወጣው አዋጅ ቁጥር 146/1991 (እንደተሻሻለው መሰረት ከፕራይቬታይዜሽን ጋር ተያይዞ ለተደረጉ ውሎችና ፍጻሜ ላላገኙ ጉዳዮች የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

20.<u>ተፈጻሚነት ያለው ሕግ</u>

1. ነባር ድርጅትን ለማስፋፋትና ለማሻሻል ስለሚሰጡ ማበረታቻዎች እንዲሁም የውጭ ዜጎችና ባለሀብቶች በኢንቨስትመንት መስክ ስለሚሳተፉበት ሁኔታ ስለሚጠበቁላቸው መብቶች አግባብነት ባላቸው ኢንቨስትመንት ሕጎች የተደነገጉት የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ወደ ግል በተዛወረላቸው ላይም ተፈጻሚ ይሆናል፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ቢኖርም፣ በኢንቨስትመንት ሕጉ ለሀገር ውስጥ ባለሀብት የተሰጠው ትርጉም ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም መንግሥትንና የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን አይጨምርም፡፡

21.<u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ 3 ቀን 2012 ዓ.ም.**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚደንት**

## አዋጅ ቁጥር 412/1996[63]

## የፕራይቪታይዜሽንና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣንን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

መንግሥት በኢኮኖሚ ዘርፍ ያለውን ተሳትፎ በመለወጥና የግሉን ክፍለ ኢኮኖሚ ድርሻ በማስፋፋት የአገሪቱን የኢኮኖሚ ልማት ማፋጠን አስፈላጊ በመሆኑ፤

የልማት ድርጅቶች በመንግሥት ይዞታ ሥር እስካሉ ድረስ ተወዳዳሪና አትራፊ ሆነው በመቀጠል የሀገሪቱን የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ በማስፈጸምና ኢኮኖሚያዊ እድገት በማምጣት ረገድ ተገቢውን ሚና እንዲጫወቱ ለማድረግ የሚያስችል አመራርና ድጋፍ መስጠት በማስፈለጉ፤

እነዚህን ዓላማዎች ለማስፈጸም የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲንና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣንን በማዋሃድ የፕራይቬታይዜሽን ፕሮግራሙን አፈጻጸምና የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን የመቆጣጠር ተግባር ማቀናጀት በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 55(1 መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

13. <u>የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ</u>[64]

1. በአዋጅ ቁጥር 277/1994 አንቀጽ 11 ተቋቁሞ የነበረው የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ በዚህ አዋጅ እንደተቋቋመ ይቆጠራል።
2. የፈንዱ የገንዘብ ምንጭ በመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 አንቀፅ 2(1) ከተመለከቱት የመንግስት የልማት ድርጅቶችና አክሲዮኖቻቸው ሙሉ በሙሉ በመንግስት ከተያዙ አክሲዮን ማኀበራት የተጣራ ትርፍ እንዲሁም ሽያጭ የሚገኝ ገቢ ይሆናል፡፡
3. ፈንዱ ለሚከተሉት ዓላማዎች ይውላል፤
   ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5(3) መሠረት ለሚቋቋሙ የልማት ድርጅቶች ፕሮጀክቶች ጥናት ማስፈጸሚያና ለማቋቋሚያ መነሻ ካፒታል፣
   ለ) በአገሪቱ የኢኮኖሚ ልማት ቁልፍ ሚና ሊጫወት የሚችል በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 አንቀፅ 2(1) የተመለከተውን ትርጓሜ የሚያሟላ የመንግስት የልማት ድርጅትን የተፈቀደ ካፒታል ለመክፈል ወይም የመንግስት የልማት ድርጅትን ወይም አክሲዮኖቹ ሙሉ በሙሉ በመንግስት

[63] ይህ አዋጅ ከአንቀፅ 13 በቀር በ22)12 (2008 አ. 916 ተሻረ፡፡
[64] የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2 )፣ (3 )(ለ) እና (4) በ18/18 (2004) አ. 730 አንቀፅ 2 ተሻሻሉ፡፡

የተያዙ አክሲዮን ማኅበርን ለማሻሻል ወይም ለማስፋፋት የሚያስፈልገውን የካፒታል ወጭ ለመሸፈን፤

ሐ) ኪሣራ የደረሰበት የመንግሥት የልማት ድርጅት ከመፍረስ እንዲድን ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በኪሣራ የገደለውን ካፒታል ለመተኪያ፡፡

4. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር[65]በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ )2) ከተመለከተው የገንዘብ ምንጭ ወደ ፈንዱ ገቢ የሚደረገውን መቶኛ፣ በፈንዱ በተቀመጠው ገንዘብ ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚገባ የመንግስት የልማት ድርጅቶችናን አክሲዮኖቻቸው ሙሉ በሙሉ በመንግስት የተያዙ አክሲዮን ማኅበራትን እና ከፈንዱ ላይ የሚደረገውን የክፍያ መጠን ለመወሰን ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡

5. ባለሥልጣኑ የፈንዱን ሂሳብ በሚመለከት የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት በተለይ ይይዛል፡፡

6. የፈንዱ ሃሳብ በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ 26 ቀን 1996 ዓ.ም**

**ግርማ ወ)ጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ፕሬዝዳንት**

[65]በ25/08 (2011) አ. 1097 አንቀፅ 9/4 የገንዘብ ሚንስቴር ሆኗል፡፡

## ደንብ ቁጥር 107/1996

## የመንግሥት ልማት ድርጅቶች የትርፍ ድልድል የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 4/1987 አንቀጽ 5 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የመንግሥት ልማት ድርጅቶች የትርፍ ድልድል የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 107/1996" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ ደንብ ውስጥ፣

   1. "የመንግሥት የልማት ድርጅቶች" ማለት በአዋጅ ቁጥር 412/1996[66] አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 2 የተሰጠው ትርጓሜ ይኖረዋል፣
   2. "የተጣራ ትርፍ" ማለት በአዋጅ ቁጥር 25/1984 አንቀጽ 2/7 የተሰጠው ትርጓሜ ይኖረዋል፣
   3. "ባለሥልጣን" ማለት በአዋጅ ቁጥር 412/1996 የተቋቋመው የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ነው።[67]
   4. "ሚኒስቴር" ማለት የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ነው።

3. **የትርፍ ድልድል**

   1. ከመንግሥት የልማት ድርጅት የተጣራ ትርፍ ላይ በአዋጅ ቁጥር 25/1984 አንቀጽ 29/2 መሠረት የሕጋዊ መጠባበቂያ ሂሣብ ከተቀነሰ በኋላ የሚቀረው ትርፍ እንደሚከተለው ይደለደላል፡፡

      ሀ) ለመንግሥት የትርፍ ድርሻ ...................... 60 %

      ለ) ለኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ................ 40% ይሆናል፡፡

---

[66] ይህ አዋጅ ከአንቀፅ 13 በቀር በ22)12 (2008 አ. 916 ተሻረ፡፡ በተሻረዉ አዋጅ የተሰጠዉ ትርጉም"የመንግሥት የልማት ድርጅት" ማለት በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25)1984 አንቀጽ 2(1 የተመለከተውን ትርጓሜ የሚያሟላ ድርጅት ወይም አክስዮኖቹ ሙሉ በሙሉ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዙ አክሲዮን ማኀበር ሲሆን በሌሎች ሕጎች ወይም በመንግሥት ውሳኔ የተለየ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን የተሰየመላቸውን ድርጅቶች አይጨምርም፤" የሚል ነዉ፡፡

[67] ባለስልጣኑ" የሚለዉ በ25)08 (2011 አ.1097 አንቀጽ 36(23 እና በደንብ ቁጥር 445)11 አንቀጽ 5(16 መሰረት የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለስልጣን በአዋጅ ቁጥር 1097)11 አንቀጽ 32(15 ለተቋቋመው የመነግስት ልማት ድርጅቶ ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ ተሰጥቷል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው የትርፍ ክፍፍል ድልድል ቢኖርም ከሚኒስቴሩ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚቀርበው የውሣኔ ሃሣብ መሠረት ድልድሉ ሊሻሻል ይችላል፡፡
3. የመንግሥት የትርፍ ድርሻ በአዋጅ ቁጥር 25/1984 አንቀጽ 31 በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ በቅድሚያ ለመንግሥት ፈሰስ ከተደረገ በኋላ ለኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ የተመደበው ገንዘብ ይከፈላል፡፡

4. **የትርፍ መግለጫ ስለማቅረብ**

ማንኛውም የመንግሥት የልማት ድርጅት ዓመታዊ የተጣራ ትርፍ ግምት መግለጫ የዘጠኝ ወራት ክንውንና የቀሪዎቹ ሦስት ወራት ግምት መሠረት በማድረግ በበጀት ዓመቱ እስከ ሚያዚያ ወር መጨረሻ ድረስ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

5. **የባለሥልጣኑ ተግባር**

1. ባለሥልጣኑ በዚህ ደንብ አንቀጽ 4 መሠረት የቀረበለትን መረጃ መሠረት በማድረግ የእያንዳንዱን የመንግሥት የልማት ድርጅት ዓመታዊ ትርፍና በዚህ ደንብ መሠረት ስለሚደረገው ክፍፍል የተዘጋጀ መግለጫ በበጀት ዓመቱ እስከ ግንቦት ወር መጨረሻ ባለው ጊዜ ውስጥ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።
2. ባለሥልጣኑ በጊዜያዊ የሂሣብ መግለጫ ላይ ተመስርቶ በበጀት ዓመቱ የተገኘውን የተጣራ ትርፍ በጀት ዓመቱ ካለቀ እስከ ህዳር 15 ቀን ድረስ ለሚኒስቴሩ ያሳውቃል።ሆኖም በጊዜያዊ ሂሣብ መግለጫና ትርፍና በኦዲተር በተረጋገጠ ሂሣብ መግለጫ ትርፍ መካከል ልዩነት ሲኖር በውጤቱ ላይ ተመስርቶ ማስተካከያ ይደረጋል፡፡

6. **የፈንዱ ዓላማ**

ፈንዱ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ለማሻሻል፣ ለማስፋፋት፣ ወይም አዲስ ለሚቋቋሙ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ፕሮጀክቶች ጥናት ማስፈጸሚያ እና ማቋቋሚያ መነሻ ካፒታል ይውላል፡፡

7. **የፈንዱ አጠቃቀም**

ፈንዱ መንግሥት በሚያወጣው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት በሚኒስቴሩ እየተፈቀደ ጥቅም ላይ ይውላል፡፡

8. **መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

ሚኒስቴሩ ለዚህ ደንብ አፈጻጸም የሚረዱ መመሪያዎችን ለማውጣት ይችላል፡፡

9. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ 20 ቀን 1996 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስቴር**

## ለ) የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ማቋቋሚያ ህጎች

### 1) ለመንግስት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ የመንግስት ልማት ድርጅቶች ማቋቋሚያ ህጎች

**ደንብ ቁጥር 22/1985**

**ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ለማቋቋም የወጣ**

**የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የጠቅላይ ሚኒስትርንና የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 2)1983 አንቀጽ 4)2) እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25)1984 በአንቀጽ 47)1)ሀ) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 22/1985" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**

   1. ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት )ከዚህ በኋላ "ድርጅት" እየተባለ የሚጠራ) የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. ድርጅቱ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን**

   በመንግሥት የሚሰየም አካል የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል፡

4. **ዓላማ**

   ድርጅቱ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፤

   1. የማተም፣ ፊደሎችን የመቅረጽ፣ ጽሑፎችን አትሞ የማውጣትና የታተመውን እንደገና የማተም ሥራ መሥራት፣ እንዲሁም በጠቅላላው ድርሰት ነክ ሥራዎችን፣ የሚከተሉትንም ጭምር ማለትም፤

      ሀ) ማናቸውም ዓይነት መጽሐፍ፣ መጽሐፍ መሰል ጽሑፎች፣ ጋዜጦች፣ በየጊዜው የሚወጡ ጽሑፎች፣ ትችቶችና መጽሔቶች፣

      ለ) ለማስታወቂያ የሚያገለግሉ ጽሑፎችን ሰሌዳዎችንና ማስታወሻዎችን፣

ሐ) የማዘዣ ወረቀት፣ ፋክቱር ወይም ደረሰኝ ማስታወሻ ወረቀት፣ የጥሪ ካርድ የግብዣና ሌላም ተመሳሳይ ፎርም፣ ካታሎግ የሂሣብ፣ የንብረትና የዕቃ ዝርዝር ፎርም፣ ቀን መቁጠሪያዎች፣ አጀንዳ፣ ማስታወሻ ደብተሮች፣ ኤንቬሎፖችና እንዲሁም እነዚህን የመሳሰሉ ለግልም ሆነ ለቢሮ ሥራ የሚያገለግሉ የጽሕፈት መሣሪያዎችን፣ የማተም፣ አትሞ የማውጣትና እንደገና የማተም ጥበብን የሚመለከቱ ሥራዎችን ሁሉ መሥራት፣

2. የጥርዛት ሥራዎችን መሥራት፣
3. የድርጅቱን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ የሚጠቅሙ የሳይንስ፣ የኢንዱስትሪና የቴክኒክ ጥናቶችንና ምርምሮችን ማድረግ፣
4. ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ የሚረዳ ሌላ ማናቸውንም የንግድ ሥራ መሥራት፣

5. **ካፒታል**

ለድርጅቱ የተፈቀደው ካፒታል ብር 1 ቢሊዮን 528 ሚሊዮን 7 መቶ ሺህ (አንድ ቢሊዮን አምስት መቶ ሀያ ስምንት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሺህ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 3 መቶ 82 ሚሊየን 1 መቶ 76 ሺህ (ሶስት መቶ ሰማንያ ሁለት ሚሊየን አንድ መቶ ሰባ ስድስት ሺህ በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል፡፡[68]

6. **ዋና መሥሪያ ቤት**

የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ይሆናል፤ እንደአስፈላጊነቱም በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

7. **ኃላፊነት**

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

8. **ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ**

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

9. **ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ኅዳር 1 ቀን 1985 ዓ.ም**

**ታምራት ላይኔ**

**የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት ጠቅላይ ሚኒስትር**

---

[68]በ23)84(2009 ደ.412 አንቀፅ 2 ተሻሻለ፡፡

**ደንብ ቁጥር 23)1985**

## አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የጠቅላይ ሚኒስትርንና የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 2/1983 አንቀጽ 4(2) እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 አንቀጽ 47/1/ሀ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 23/1985" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**

   1. አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት (ከዚህ በኋላ "ድርጅት" እየተባለ የሚጠራ የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. ድርጅቱ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን**

   በመንግሥት የሚሰየም አካል የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል፡፡

4. **ዓላማ**

   ድርጅቱ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፤

   1. የማተም፣ ፊደሎችን የመቅረጽ፣ ጽሑፎችን አትሞ የማውጣትና የታተመውን እንደገና የማተም ሥራ መሥራት፣ እንዲሁም በጠቅላላው ድርሰት ነክ ሥራዎችን የሚከተሉትንም ጭምር ማለትም፤
      ሀ) ማናቸውንም ዓይነት መጽሐፍ፣ መጽሐፍ መሰል ጽሑፎች፣ ጋዜጦች፣ በየጊዜው የሚወጡ ጽሑፎች፣ ትችቶችና መጽሔቶች፣
      ለ) ለማስታወቂያ የሚያገለግሉ ጽሑፎችን፣ ሰሌዳዎችንና ማስታወሻዎችን፣
      ሐ) የማዘዣ ወረቀት፣ ፋክቱር ወይም ደረሰኝ፣ ማስታወሻ ወረቀት፣ የጥሪ ካርድ የግብዣና ሌላም ተመሳሳይ ፎርም፣ ካታሎግ፣ የሂሳብ፣ የንብረት ዕቃ ዝርዝር ፎርም፣ ቀን መቁጠሪያዎች አጀንዳ፣ ማስታወሻ ደብተሮችኤንቬሎፖችና እንዲሁም እነዚህን የመሳሰሉ ለግልም ሆነ ለቢሮ ሥራ የሚያገለግሉ የጽሕፈት መሣሪያዎችን፣ የማተም፣ አትሞ የማውጣትና እንደገና የማተም ጥበብን የሚመለከቱ ሥራዎችን ሁሉ መሥራት፣

2. የጥርዛት ሥራዎችን መሥራት፣
3. የድርጅቱን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ የሚጠቅሙ የሳይንስ፣ የኢንዱስትሪና የቴክኒክ ጥናቶችንና ምርምሮችን ማድረግ፣
4. የድርጅቱ ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ የሚረዳ ሌላ ማናቸውንም የንግድ ሥራ መሥራት፡፡

5. <u>ካፒታል</u>

የድርጅቱ ካፒታል ብር 2 ሚሊዮን 703 ሺህ (ሁለት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሶስት ሺህ ብር ሲሆን ይኸውም በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል፡፡

6. <u>ዋና መሥሪያ ቤት</u>

የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ይሆናል፡፡ እንደ አስፈላጊነቱም በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

7. <u>ኃላፊነት</u>

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት ላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

8. <u>ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ</u>

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

9. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ኅዳር 1 ቀን 1985 ዓ.ም**

**ታምራት ላይኔ**

**የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት**

**ጠቅላይ ሚኒስትር**

**ደንብ ቁጥር 74/1985**

**ብሔራዊ አልኮልና አረቄ ፋብሪካ ለማቋቋም**

**የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የጠቅላይ ሚኒስትርንና የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 2/1983 አንቀጽ 4/2 እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 በአንቀጽ 47/1/ሀ/ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የብሔራዊ አልኮልና አረቄ ፋብሪካ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 74/1985" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**

   1. ብሔራዊ አልኮልና አረቄ ፋብሪካ (ከዚህ በኋላ "ድርጅት" እየተባለ የሚጠራ የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. ድርጅቱ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን**

   በመንግሥት የሚሰየም አካል የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል፡፡

4. **ዓለማ**

   ድርጅቱ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፣

   1. ማናቸውንም ዓይነት አልኮል፣ አረቄና አልኮል ነክ መጠጦችን በፋብሪካ መሥራትና አሽጐ ማውጣት፣
   2. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሱትን መጠጦች ለመሥራት የሚጠቅሙ ሌሎች ነገሮችን የማዘጋጀትና በፋብሪካ ሠርቶ ማውጣት፣
   3. ምርቶቹን በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ገበያ መሸጥ፣
   4. ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ የሚረዳ ሌላ ማናቸውንም የንግድ ሥራ መሥራት፡

5. **ካፒታል**

   ለፋብሪካው የተፈቀደው ካፒታል ብር 220 ሚሊዮን 985 ሺ 434 ብር 93 ሳንቲም (ሁለት መቶ ሀያ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሰማኒያ አምስት ሺ አራት መቶ ሰላሳ አራት ብር ከዘጠና ሶስት ሳንቲም ሲሆን ይኸውም በጥሬ ገንዘብና በአይነት ተከፍሏል፡፡[69]

---

[69]በ23)88(2009 ደ.415 አንቀፅ 2 ተሻሻለ፡፡

6. <u>**ዋና መሥሪያ ቤት**</u>

የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ይሆናል፡፡ እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

7. <u>**ኃላፊነት**</u>

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

8. <u>**ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ**</u>

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

9. <u>**ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**</u>

ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ኅዳር 1 ቀን 1985 ዓ.ም**

**ታምራት ላይኔ**

**የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት ጠቅላይ ሚኒስትር**

**ደንብ ቁጥር 76/1985**

**አሰላ ብቅል ፋብሪካ ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የጠቅላይ ሚኒስትርንና የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 2/1983 አንቀጽ 4/2 እና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 በአንቀጽ 47 1/ሀ/ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የአሰላ ብቅል ፋብሪካ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 76/1985" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**

   1. አሰላ ብቅል ፋብሪካ /ከዚህ በኋላ "ድርጅት" እየተባለ የሚጠራ/ የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. ድርጅቱ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን**

   በመንግሥት የሚሰየም አካል የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል፡፡

4. **ዓላማ**

   ድርጅቱ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፣

   1. ማናቸውንም ዓይነት ብቅል፣ ጌሾ፣ እርሾና ሌሎች ለመጠጥ ምርት የሚውሉ ጥሬ ዕቃዎችን በፋብሪካ መሥራት፡፡
   2. በዚሁ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ /1/ የተጠቀሱትን ምርቶች ለመሥራት የሚጠቅሙ ሌሎች ነገሮችን ማዘጋጀትና በፋብሪካ ሠርቶ ማውጣት፣
   3. ምርቶችን በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ገበያ መሸጥ፣
   4. ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ የሚረዳ ሌላ ማናቸውንም የንግድ ሥራ መሥራት፡

5. **ካፒታል**

   ካፒታል ለፋብሪካው የተፈቀደው ካፒታል ብር 232 ሚሊዮን 255 ሺ 996 (ሁለት መቶ ሰላሳ ሁለት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሃምሳ አምስት ሺ ዘጠኝ መቶ ዘጠና ስድስት ብር ሲሆን ይኸውም በጥሬ ገንዘብና በአይነት ተከፍሏል፡፡[70]

6. **ዋና መሥሪያ ቤት**

[70]በ23)87(2009 ደ.414 አንቀፅ 2 ተሻሽለ፡፡

የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአሰላ ይሆናል፡፡ እንደአስፈላጊነቱም በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

7. <u>ኃላፊነት</u>

ድርጅቱ ካለሙ ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

8. <u>ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ</u>

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

9. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ኅዳር 1 ቀን 1985**

**ታምራት ላይኔ**

**የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 106/1985

## የኢትዮጵያ ቱሪስት ንግድ ሥራ ድርጅትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የጠቅላይ ሚኒስትርንና የሚኒስትሮች ምክር ቤትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 2/1983 አንቀጽ 4/2/ እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 አንቀጽ 47/1/ሀ መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ቱሪስት ንግድ ሥራ ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጠር 106/1985" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ ደንብ ውስጥ፣

   1. "የቀረጥ ነጻ ዕቃዎች ሱቅ" ማለት ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ ወይም ከኢትዮጵያ የሚወጡ መንገደኞች ወይም ተቀማጭነታቸው ኢትዮጵያ ውስጥ የሆኑ የቀረጥ ነጻ ተጠቃሚዎች ቀረጥ ሳይከፈልባቸው ዕቃዎች የሚገዙበት መደብር ነው፤
   2. "የመታሰቢያ ዕቃዎች መሸጫ ሱቅ" ማለት ከጥንታዊ ቅርሶች በስተቀር በተለይ የዕደ ጥበባት ዕቃዎች፣ የመታሰቢያ ዕቃዎች፣ እና የመሳሰሉት የሚሸጡበት መደብር ነው፤
   3. "ቀረጥ የተከፈለባቸው ዕቃዎች ሱቆች" ማለት ቀረጥ የተከፈለባቸው ዕቃዎች በውጭ ምንዛሪ የሚሸጡበት መደብር ነው፡፡

3. **መቋቋም**

   1. የኢትዮጵያ ቱሪስት ንግድ ሥራ ድርጅት /ከዚህ በኋላ "ድርጅት"/ እየተባለ የሚጠራ የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. ድርጅቱ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 መሠረት ይተዳደራል፡፡

4. **ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን**

   በመንግሥት የሚሰየም አካል የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል፡፡

5. **ዋና መሥሪያ ቤት**

   የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ይሆናል፡፡ እንዳስፈላጊነቱም በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

6. **የድርጅቱ ዓላማ**

ድርጅቱ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. ከውጭ አገር ዕቃዎች በማስመጣት ወይም ከአገር ውስጥ ገበያ በማቅረብ ዕቃዎቹ ለቀረጥ ነጻ ተጠቃሚዎች የሚሸጡባቸውን ሱቆች ማቋቋም፣ ማደራጀት፣ ማካሄድና ማስፋፋት፤
2. ቅርሶችን የሚመለከቱ ሕጐች እንደተጠበቁ ሆኖ፤ የዕደ ጥበብ ውጤቶች እና የመታሰቢያ ዕቃዎች ማምረት፣ ዕቃዎቹ የሚሸጡባቸውን ሱቆች ማቋቋም፣ ማደራጀት፣ ማካሄድና ማስፋፋት፣
3. ቀረጥ የተከፈለባቸው ዕቃዎች በውጭ ምንዛሪ የሚሸጡባቸውን ሱቆች ማቋቋም፣ ማደራጀት፣ ማካሄድና ማስፋፋት፣
4. ዓላማውን ከግቡ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ የሆኑ ሥራዎችን ማካሄድ፣

7. **<u>የድርጅቱ ካፒታል</u>**

ለድርጅቱ የተፈቀደው ካፒታል 10,233,918 ብር ከ84 ሳንቲም (አስር ሚሊዮን ሁለት መቶ ሰላሳ ሶስት ሺ ዘጠኝ መቶ አስራ ስምንት ብር ከሰማንያ አራት ሳንቲም ሲሆን ይህም በዓይነትና በጥሬ ገንዘብ በሙሉ ተከፍሏል፡፡

8. **<u>ኃላፊነት</u>**

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

9. **<u>ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ</u>**

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

10. **<u>የተሻረ ደንብ</u>**

የኢትዮጵያ ቱሪስት ንግድ ሥራ ድርጅት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 90/1977 በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

11. **<u>መብት እና ግዴታ ስለማስተላለፍ</u>**

በደንብ ቁጠር 90/1977 ተቋቁሞ የነበረው የኢትዮጵያ ቱሪስት ንግድ ሥራ ድርጅት መብት እና ግዴታ በዚህ ደንብ ለድርጅቱ ተላልፎአል፡፡

12. **<u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ታኅሣሥ 23 ቀን 1985 ዓ.ም**

**ታምራት ላይኔ**

**የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት ጠቅላይ ሚኒስትር**

**ደንብ ቁጥር 107/1985 ዓ.ም**

**የግዮን ሆቴሎች ድርጅትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የጠቅላይ ሚኒስትርንና የሚኒስትሮች ምክር ቤትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 2/1983 አንቀጽ 4/2/ እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 አንቀጽ 47/1/ሀ/ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የግዮን ሆቴሎች ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 107/1985" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ ደንብ ውስጥ "የሆቴል አገልግሎት" ማለት በሆቴል፣ በሬስቶራንት፣ በፔንሲዮን፣ በሎጅና በሞቴል የሚሰጥ አገልግሎት ሲሆን፤ ከሆቴል ጋር በተያያዙ ፍልውሃዎች፣ መዝናኛ ሥፍራዎችና አፓርትመንቶች የሚሰጠውን አገልግሎት ይጨምራል፡፡

3. **መቋቋም**

   1. የግዮን ሆቴሎች ድርጅት (ከዚህ በኋላ "ድርጅት" እየተባለ የሚጠራ የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. ድርጅቱ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 መሠረት ይተዳደራል፡፡

4. **ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን**

   በመንግሥት የሚሰየም አካል የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል፡፡

5. **ዋና መሥሪያ ቤት**

   የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ይሆናል፡፡ እንደአስፈላጊነቱም በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

6. **ዓላማ**

   የድርጅቱ ዓላማ የሆቴል አገልግሎት ሥራዎችን መሥራት ይሆናል፡፡

7. **ካፒታል**

   ለድርጅቱ የተፈቀደው ካፒታል ብር 19,280,040 (አስራ ዘጠኝ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሰማንያ ሺ አርባ ብር በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል፡፡

8. **ኃላፊነት**

   ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

9. **ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ**

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

10. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ታኅሳስ 23 ቀን 1985 ዓ.ም**

**ታምራት ላይኔ**

**የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት ጠቅላይ ሚኒስትር**

**ደንብ ቁጥር 111/1985**

## የፍልውሃ አገልግሎት ድርጅትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የጠቅላይ ሚኒስትርንና የሚኒስትሮች ምክር ቤትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 2/1983 አንቀጽ 4/2/ እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 አንቀጽ 47/1/ሀ/ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የፍልውሃ አገልግሎት ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 111/1985" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ ደንብ ውስጥ፣

   1. "ፍልውሃ (ማየ-ሕይወት" ማለት ለመታጠቢያ፣ ለመዝናኛና ለፈውስ አገልግሎት ሊውል የሚችል ወይም የዋለ የተፈጥሮ ፍልውሃ ነው፣
   2. "የሆቴል አገልግሎት" ማለት በሆቴል፣ በሬስቶራንት፣ በፔንስዮን፣ በሎጅና በሞቴል የሚሰጥ አገልግሎት ሲሆን፤ ከሆቴል ጋር በተያያዙ መዝናኛ ሥፍራዎችና አፓርትመንቶች የሚሰጠውን አገልግሎት ይጨምራል፡፡

3. **መቋቋም**

   1. የፍልውሃ አገልግሎት ድርጅት (ከዚህ በኋላ "ድርጅት" እየተባለ የሚጠራ የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. ድርጅቱ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 መሠረት ይተዳደራል፡፡

4. **ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን፣**

   በመንግሥት የሚሰየም አካል የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል፡፡

5. **ዋና መሥሪያ ቤት**

   የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ይሆናል፡፡ እንደአስፈላጊነቱም በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

6. **ዓላማ**

   ድርጅቱ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፣

   1. የፍልውሃ (የማየ-ሕይወት አገልግሎት ማቋቋም፣ ማደራጀትና ማካሄድ፤
   2. ከፍልውሃ (ከማየ-ሕይወት አገለግሎት ጋር የተያያዘ የሆቴል አገልግሎት መስጫ ተቋም ማቋቋም፣ ማደራጀትና ማካሄድ፡፡

7. **<u>ካፒታል</u>**

ለድርጅቱ የተፈቀደው ካፒታል ብር 4,382,705 (አራት ሚሊዮን ሶስት መቶ ሰማንያ ሁለት ሺ ሰባት መቶ አምስት ብር ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 3,632,705 (ሶስት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሰላሳ ሁለት ሺ ሰባት መቶ አምስት ብር በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል፡፡

8. **<u>ኃላፊነት</u>**

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

9. **<u>ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ</u>**

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

10. **<u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ታኅሣሥ 23 ቀን 1985 ዓ.ም**

**ታምራት ላይኔ**

**የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት ጠቅላይ ሚኒስትር**

**ደንብ ቁጥር 141/2000**

## ኢትዮጵያ የምድር ባቡር ኮርፖሬሽንን ለማቋቋም የወጣ ሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣ አዋጅ ቁጥር 471/1998 አንቀጽ 5 እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 አንቀጽ 47(1(ሀ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ የምድር ባቡር ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 141/2000" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡

2. **መቋቋም**

   1. የኢትዮጵያ የምድር ባቡር ኮርፖሬሽን (ከዚህ በኋላ "ኮርፖሬሽን" እየተባለ የሚጠራው) የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡
   2. ኮርፖሬሽኑ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን**

   የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር የኮርፖሬሽን ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል፡
   7172

4. **ዋና መሥሪያ ቤት**

   የኮርፖሬሽኑ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ይሆናል፡፡ እንደአስፈላጊነቱም በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

5. **ዓላማ**[73]

   ኮርፖሬሽኑ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው።

   1. የባቡር ትራንስፖርት መሠረተ ልማቶችን መገንባት፤
   2. የጭነት የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ማካሄድ፤
   3. የመንገደኞች የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ማካሄድ፤

---

[71] በ22)12 (2008 አ. 916 አንቀጽ 38(18(ሐ መሰረት ተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ የመንግስት ልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር ሆኗል፡፡

[73]በ15)38 (2004 ደ. 266አንቀፅ 2(1 መሰረት አዲስ ንዑስ አንቀፅ (4 የገባ ሲሆን ነባሩ ንዑስ አንቀፅ (4 ንዑስ አንቀፅ (5 ሆኗል፡፡

4. የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የሚያወጣውን መመሪያና የፖሊሲ አቅጣጫ መሠረት በማድረግ ቦንድ መሸጥና በዋስትና ማስያዝ እና ከአገር ውስጥና ከውጭ የገንዘብ ምንጮች ጋር የብድር ውል መደራደርና መፈራረም፤
5. ዓላማውን ከግቡ ለማድረስ ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎችን ማካሄድ፡፡

6. **ካፒታል**[74]

የኮርፖሬሽኑ የተፈቀደ ካፒታል ብር 39,780,000,000 (ሰላሳ ዘጠኝ ቢሊዮን ሰባት መቶ ሰማንያ ሚሊዮን ብር ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 9,945,000,000 (ዘጠኝ ቢሊዮን ዘጠኝ መቶ አርባ አምስት ሚሊዮን ብር በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል፡፡

7. **ኃላፊነት**

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ሊጠየቅ አይችልም።

8. **ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ**

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

9. **ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ህዳር 19 ቀን 2000 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስቴር**

---

[74] በ15)38 (2004 ደ. 266አንቀፅ 2(2 መሠረት ተሻረ፡፡

**ደንብ ቁጥር 192/2003**

## የስኳር ኮርፓሬሽንን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 አንቀጽ 47 /1 /ሀ መሠረት ይህን ደንብ አዉጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የስኳር ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 192/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**

   1. የስኳር ኮርፖሬሽን (ከዚህ በኃላ "ኮርፖሬሽን" እየተባለ የሚጠራ የመንግስት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. ኮርፖሬሽኑ በመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን**

   በመንግሥት የሚሰየም አካል የኮርፖሬሽኑ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል፡፡

4. **ዋና መሥሪያ ቤት**

   የኮርፓሬሽኑ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸዉም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረዉ ይችላል፡፡

5. **ዓላማ**

   ድርጅቱ የተቋቋመባቸዉ ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸዉ፡-

   1. የሸንኮራ አገዳና ስኳር የሚያስገኙ ሌሎች ሰብሎችን ማልማት፤
   2. ስኳር፣ የስኳር ዉጤቶችን፣ የስኳር ተረፈ ምርቶችን እና የስኳር ተረፈ ምርቶች ዉጤቶችን በፋብሪካ ማዘጋጀትና ማምረት፤
   3. ምርቶቹንና ተረፈ ምርቶቹን ለአገር ዉስጥና ለዉጭ ገበያ ማቅረብ፤
   4. አዳዲስና የማስፋፊያ የስኳር ልማት ፕሮጀክቶች የአዋጭነት ጥናት፣የዲዛይን ዝግጅት፣ የቴክኖሎጂ መረጣና ድርድር፣ የተከላና ኮሚሽኒንግ ሥራዎች እንዲካሄዱ ማድረግ፤
   5. ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በመተባበር በሸንኮራ አገዳና በስኳር አመራረት ቴክኖሎጂ ጥናትና ምርምር ማካሄድና ጠቃሚ ዉጤቶችን በሥራ ላይ ማዋል፤

6. አቅሙ ካላቸዉ የሀገር ዉስጥ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ለመንግሥት የስኳር ፋብሪካዎች የሚያስፈልጉ የማምረቻ መሣሪዎችና መለዋወጫዎች ዲዛይንና ፋብሪኬሽን ሥራዎች በሀገር ዉስጥ እንዲከናወኑ ማድረግ፤
7. በሕግ መሠረት ለሥራዉ የሚያስፈልገዉ መሬት ባለይዞታ መሆንና ማልማት፤
8. የአገዳ ምርታቸዉን ለመንግሥት የስኳር ፋብሪካዎች የሚያቀርቡ አገዳ አብቃዮችን ማበረታታትና መደገፍ፤
9. ለስኳር እንዱስትሪ የሚፈለገዉን የሰለጠነ የሰዉ ኃይል በሚፈለገዉ ዓይነት፣ መጠንና ጥራት ለማፍራት እንዲቻል ከሚመለከታቸዉ የትምህርት ተቋማት ጋር መተባበር፤
10. የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር[75] የሚያወጣዉን መመሪያና የፓሊሲ አቅጣጫ መሠረት በማድረግ ቦንድ መሸጥና በዋስትና ማስያዝ እና ከአገር ዉስጥና ከዉጭ የገንዘብ ምንጮች ጋር የብድር ዉል መደራደርና መፈራረም፤
11. ዓላማዉን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎችን መሥራት፡፡

6. <u>ካፒታል</u>

ለኮርፓሬሽኑ የተፈቀደዉ ካፒታል ብር 41,999,731,264(አርባ አንድ ቢሊዮን ዘጠኝ መቶ ዘጠና ዘጠኝ ሚሊዮን ሰባት መቶ ሠላሳ አንድ ሺ ሁለት መቶ ስድሳ አራት ብር ሲሆን ከዚህ ዉስጥ ብር 6,042,512,614 (ስድስት ቢለዮን አርባ ሁለት ሚሊዮን አምስት መቶ አሥራ ሁለት ሺ ስድስት መቶ አስራ አራት ብር በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል፡፡

7. <u>ኃላፊነት</u>

ኮርፓሬሽኑ ካለዉ ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

8. <u>ኮርፖሬሽኑ የሚቆይበት ጊዜ</u>

ኮርፓሬሽኑ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

9. <u>የተሻሩ ደንቦች</u>

የሚከተሉት በዚህ ደንብ ተሸረዋል፡-

1. የመተሃራ ስኳር ፋብሪካ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 88/1985፤
2. የወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር89/1985፤

---

[75]በ25)08 (2011 አ. 1097 አንቀጽ 9(4 መሰረት የገንዘብ ሚኒስቴር ሆኗል፡፡

3. የፊንጫ ስኳር ፋብሪካ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 199/1986፣
4. የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 122/1998(እንደተሻሻለዉ፡፡

10. <u>ስለኢትዮጵያ ስኳር ልማት ኤጀንሲ መፍረስ</u>

በአዋጅ ቁጥር 504/1998 ተቋቋሞ የነበረዉ የኢትዮጵያ ስኳር ልማት ኤጀንሲ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 34 መሠረት በዚህ ደንብ ፈርሷል፡፡

11. <u>የመብትና ግዴታዎች መተላለፍ</u>

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 88/1985 ተቋቋሞ የነበረዉ የመተሃራ ስኳር ፋብሪካ፣በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 89/1985 ተቋቁሞ የነበረዉ የወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ፣ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 199/1986 ተቋቁሞ የነበረዉ የፊንጫ ስኳር ፋብሪካ፣በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 122/1998 (እንደተሻሻለ ተቋቁሞ የነበረዉ የኢትዮጵያ ስኳር ልማት ኤጀንሲ መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለኮርፖሬሽኑ ተላልፈዋል፡፡

12. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ ከጥቅምት 19 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ህዳር 23 ቀን 2003 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ**

**ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 255/2004

## የኢትዮጵያ የባሕር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 አንቀጽ 47 (1 (ሀ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ የባሕር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 255/2004" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**

   1. የኢትዮጵያ የባሕር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልገሎት ድርጅት (ከዚህ በኋላ "ድርጅት" እየተባለ የሚጠራ የመንግስት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. ድርጅቱ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን**

   በመንግስት የሚሰየም አካል የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል፡፡

4. **ዋና መስሪያ ቤት**

   የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ስፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

5. **ዓላማ**

   ድርጅቱ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

   1. በጠረፍ አካባቢ፣ በአለም ዓቀፍ ባሕሮች እና የሀገር ዉስጥ ውሃ ትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት፤
   2. የዕቃ አስተላላፊነት ውክልና፣ የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት፣ የመርከብ ውክልና እና የአየር ውክልና አገልግሎት መስጠት፤
   3. ለወጪና ገቢ ዕቃዎች የስቴቨዶሪንግ፣ ሾር ሃንሊግ፣ የደረቅ ወደብ፣ የመጋዘን እና ሌሎች የሎጅስቲክስ አገልግሎቶች መስጠት፤

4. የኮንቴይነር ማስተናገጃና ማከማቻ አገልግሎት መስጠት፤
5. የወደብ ይዞታዎችን ማልማት፣ ማስተዳደርና አገልግሎት መስጠት፤
6. የማሪታይም ዘርፍ የሙያ ክህሎት ማሳደጊያ የሰው ኃይል ልማትና ስልጠና ማዕከል ማቋቋምና ማስተዳደር፤
7. የሃገሪቱን የገቢና የወጪ ንግድ ፍላጎት በማጥናት የማሪታይምና ትራንዚት ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥን ብቃት ለማጎልበት የሚያስችል የቴክኖሎጂ አቅም ማሳደግ፤
8. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ የሆኑ ሥራዎችን ማካሄድ፡፡

6. <u>ካፒታል</u>[76]

ለድርጅቱ የተፈቀደው ካፒታል ብር 20,000,000,000 (ሃያ ቢሊዮን ብር ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 6,541,793.00 (ስድስት ቢሊዮን አምስት መቶ አርባ አንድ ሚሊዮን ስምንት መቶ ሰባ ሶስት ሺ ሰባት መቶ ዘጠና ሶሰት ብር በጥሬ ገንዘብና በአይነት ተከፍሏል፡፡

7. <u>ኃላፊነት</u>

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም።

8. <u>ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ</u>

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

9. <u>የተሻሩ ደንቦች</u>

የባሕርና ትራንዚት አገልግሎት ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/1986 እና የደረቅ ወደብ አገልግሎት ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 136/1999 በዚህ ደንብ ተሽረዋል፡፡

10. <u>የመብትና ግዴታ መተላለፍ</u>

የኢትዮጵያ ንግድ መርከብ ድርጅት አክስዮን ማህበር በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/1986 ተቋቁሞ የነበረው የባሕርና ትራንዚት አገልግሎት ድርጅት እና በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 136/ 1999 ተቋቁሞ የነበረው የደረቅ ወደብ አገልግሎት ድርጅት መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለድርጅቱ ተላልፈዋል፡፡

11. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

---

[76]በ22)68(2008 ደ. 386አንቀፅ 2 ተሻሻለ፡፡

## አዲስ አበባ ህዳር 11 ቀን 2004 ዓ.ም

## መለስ ዜናዊ

## የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

## ደንብ ቁጥር 280/2005

## የኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 አንቀጽ 47(1(ሀ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 280/2005 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**

   1. የኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን (ከዚህ በኋላ "ኮርፖሬሽን" እየተባለ የሚጠራ የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. ኮርፖሬሽኑ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን**

የመንግስት ልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር የኮርፖሬሽኑ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል፡፡[77]

4. **ዋና መስሪያ ቤት**

የኮርፖሬሽኑ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

5. **ዓላማ**

ኮርፖሬሽኑ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

   1. ማዳበሪያ፣ የጐማ ዛፍ ውጤቶች፣ ሲሚንቶ እና ሌሎች የኬሚካል ምርቶችን በፋብሪካ ማዘጋጀትና ማምረት፤
   2. ምርቶቹንና ተረፈ ምርቶችን ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያ ማቅረብ፤
   3. የአዳዲስና ማስፋፊያ ፕሮጀክቶችን አዋጪነት ጥናት፣ የዲዛይን ዝግጅት፣ የቴክኖሎጂ መረጣና ድርድር፣ የተከላና ኮሚሽኒንግ እንደዚሁም የምርምር ሥራዎች እንዲካሄዱ ማድረግ፤

[77]በ25)08 (2011 አ.1097 አንቀጽ 36(23 የመንግስት ልማት ድርጅቶ ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ ሆኗል፡፡

4. አቅሙ ካላቸው የአገር ውስጥ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ለመንግሥት የኬሚካል ፋብሪካዎች የሚያስፈልጉ የማምረቻ መሣሪያዎችና መለዋወጫዎች ዲዛይንና ፍብረካ ሥራዎች በአገር ውስጥ እንዲከናወኑ ማድረግ፤
5. ለኬሚካል ኢንዱስትሪ የሚፈለገውን የሰለጠነ የሰው ኃይል በሚፈለገው ዓይነት፣ መጠንና ጥራት ለማፍራት እንዲቻል ከሚመለከታቸው የትምህርት ተቋማት ጋር መተባበር፤
6. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር[78]የሚያወጣውን መመሪያና የፖሊሲ አቅጣጫ መሠረት በማድረግ ቦንድ መሸጥና በዋስትና ማስያዝ እና ከአገር ውስጥና ከውጭ የገንዘብ ምንጮች ጋር የብድር ውል መደራደርና መፈራረም፤
7. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎችን መሥራት፡፡

6. **ካፒታል**

ለኮርፖሬሽኑ የተፈቀደው ካፒታል ብር 21,719,751,376 (ሃያ አንድ ቢሊዮን ሰባት መቶ አሥራ ዘጠኝ ሚሊዮን ሰባት መቶ ሃምሳ አንድ ሺ ሦስት መቶ ሰባ ስድስት ብር ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 5,429,937,844 (አምስት ቢሊዮን አራት መቶ ሃያ ዘጠኝ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሠላሳ ሰባት ሺ ስምንት መቶ አርባ አራት ብር በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል፡፡

7. **ኃላፊነት**

ኮርፖሬሽኑ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም።

8. **ኮርፖሬሽኑ የሚቆይበት ጊዜ**

ኮርፖሬሽኑ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

9. **የተሻረ ደንብ**

የሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ እንደገና ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 53/1991 በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

10. **የመብትና ግዴታዎች መተላለፍ**

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 53/1991 እንደገና ተቋቁሞ የነበረው የሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለኮርፖሬሽኑ ተላልፈዋል፡፡

11. **ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

---

[78] በ25)08 (2011 አ.1097 አንቀጽ 9(4 የገንዘብ ሚኒስቴር ሆኗል፡፡

**አዲስ አበባ ታህሳስ 30 ቀን 2005 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 365/2008

## የኢትዮጵያ የኮንስትራክሽን ዲዛይንና ሱፐርቪዥን ሥራዎች ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራሊዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀጽ 5 እና የመንግስት ልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 አንቀጽ 47(1 (ሀ መሠረት ይህን ደንብ አዉጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕሰ**

   ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ የኮንስትራክሽን ዲዛይንና ሱፐርቪዥን ሥራዎች ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ደንብ ቁጥር 365/2008" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**

   1. የኢትዮጵያ የኮንስትራክሽን ዲዛይንና ሱፐርቪዥን ሥራዎች ኮርፖሬሽን (ከዚህ በኃላ "ኮርፖሬሽን" እየተባለ የሚጠራ የፌደራል መንግስት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. ኮርፖሬሽኑ በመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ተቆጣጣሪ ባለስልጣን**

   የመንግስት ልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር የኮርፖሬሽኑ ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ይሆናል፡

4. **ዋና መስሪያ ቤት**

   የኮርፖሬሽኑ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በሌሎች የአገሪቱ ክፍልች ቅርንጫፍ ሊከፍት ይችላል፡፡

5. **ዓላማ**

   ኮርፖሬሽኑ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች ከዚህ የሚከተሉት ይሆናል:-

   1. የመንገድ፣ የድልድይ፣ የዋሻ፣ የኤርፊልድ፣ የባቡር መንገድ፣ የሕንፃ፣ የአርክቴክቸራል ምህንድስና፣ የግድብ፣ የመስኖ፣ የድሬይኔጅ፣ የመጠጥ ውሀ፣ የውሃ ጥራት፣ የፍሳሽ ማስወገጃ፣ የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ፣ የኃይድሮ ፓወር፣ የንፋስና የእንፋሎት ኢነርጂ ልማት፣ የተቀናጀ የውሀ ሀብት አጠቃቀም፣ የተቀናጀ የተፋሰስ ልማት፣ የጎርፍ ትንበያ እና ማስቀየስ፣ የውኃ መሰረተ ልማት፣ የከተማ እና የክፍለ ከተማ ፕላንና አርክቴክቸራል ምህንድስና፣ የገጠር ልማት ፕላንና አሰፋፈር፣ የመሬት አጠቃቀም ፕላን፣ የጂኦ-ቴክኒክ እና

የፋውንዴሽን ኢንጂነሪንግ እና ሌሎች የመሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች ጥናት፣ ቅየሳ፣ ዲዛይን፣ የግንባታ ቁጥጥር፣ የውል አስተዳደር፣ የማማከር፣ የስልጠና፣ የማቴሪያል ምርመራና የላብራቶሪ አገልግሎት በመስጠት በዘርፉ የሚታየውን የገበያ ክፍተት መሙላት፤

2. የመሠረተ ልማት ግንባታዎች ደህንነት ክትትል ማዕከልና የፊዚካል ሞዴሊንግ አገልግሎት በመስጠት የሚገነቡ መሰረተ ልማት ግንባታዎች ደህንነት ማረጋገጥ፤
3. ለኮርፖሬሽኑ ልማት የሚያስፈልገውን የሰለጠነ የሰው ኃይል በሚፈለገዉ አይነት፣ መጠንና ጥራት ለማፍራት እንዲቻል ከሚመለከታቸው የምርምር፣ የትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ጋር መተባበር፤
4. በመንግስት ልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር በሚሰጠው አቅጣጫ ላይ በመመስረት በአገር ውስጥና በውጭ አገራት ተወዳዳሪና አትራፊ ሆኖ እንዲንቀሳቀስ እገዛ የሚያደርጉለትን የፋይናንስ፣ የቴክኖሎጂና የዘመናዊ አስተዳደር ግብአቶችን ለማግኘት የሚያስችለውን (ኢንቨስትመንት መሳብና በኢንቨስትመንት መሳተፍን ጨምሮ ጥናት ማካሄድ፣ የውሣኔ ሀሣብ ማቅረብና ሲፈቀድ ተግባራዊ ማድረግ፤
5. ለኮርፖሬሽኑ መሰረተ ልማት ግንባታ ዘርፍ ለጥናት፣ ዲዛይን እና ግንባታ ቁጥጥር የሚያስፈልጉ ደረጃዎች ዝግጅት አገልግሎት መስጠት፣ ለቴክኖሎጂ ሽግግር የሚያግዙ የዲዛይን፣ ሱፐርቪዥን እና መሰል አገልግሎቶች ላይ የስልጠና፣ ምርምርና ስርፀት አገልግሎት መስጠት፤
6. የመሰረተ ልማት ግንባታዎች ስትራቴጂዎች ማዘጋጀት፣ ቴክኒካዊና ሕጋዊ ሁኔታዎችን እንድምታ ትንተና አገልግሎት እንዲሁም ለፖሊሲው ውሳኔ የሚረዱ መረጃዎችን መተንተንና የአጠቃቀም አቅጣጫ ሃሳብ የማመንጨት አገልግሎት መስጠት፤
7. በትራንስፖርት፣ በውሀ፣ በመንገድ፣ ህንፃና  መሰል የሲቪል ምህንድስና ሥራዎችን በሚመለከት የጨረታ ሰነድና ውል የማዘጋጀት እና ተቋራጮችን የመምረጥ አገልግሎት መስጠት፤
8. የገንዘብና የኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት ቦንድ የመሸጥና በዋስትና የማስያዝ እና ከሀገር ውስጥና ከውጭ የገንዘብ ምንጮች የብድር ዉል መደራደርና ሲፈቀድም መፈራረም፤

9. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉ ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎችን ማካሄድ፣

6. <u>ካፒታል</u>

የኮርፖሬሽኑ የተፈቀደ ካፒታል 1,301,515,785 (አንድ ቢሊዮን ሦስት መቶ አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ አስራ አምስት ሺ ሰባት መቶ ሰማንያ አምስት ብር ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 393,771,990 (ሦስት መቶ ዘጠና ሦስት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሰባ አንድ ሺ ዘጠኝ መቶ ዘጠና ብር በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል፡፡

7. <u>ኃላፊነት</u>

ኮርፖሬሽኑ ካለዉ ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

8. <u>ኮርፖሬሽኑ የሚቆይበት ጊዜ</u>

ኮርፖሬሽኑ የተቋቋመዉ ላልተወሰነ ጊዜ ነዉ፤፤

9. <u>የተሻሩ ደንቦች</u>

የሚከተለት ደንቦች በዚህ ደንብ ተሽረዋል:-

1. የውሃ ሥራዎች ዲዛይንና ቁጥጥር ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 42/1991 ( እንደተሻሻለ፤
2. የኮንስትራክሽን ዲዛይን አክስዮን ማህበር ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 180/1986፤
3. የትራንስፖርት ኮንስትራክሽን ዲዛይን አክስዮን ማህበር ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 161/1986፡፡

10. <u>የመብትና ግዴታዎች መተላለፍ</u>

የሚከተሉት የመንግስት ልማት ድርጅቶች መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለኮርፖሬሽኑ ተላልፈዋል፤

1. በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 42/1991 (እንደተሻሻለ ተቋቁሞ የነበረው የውሃ ሥራዎች ዲዛይንና ቁጥጥር ድርጅት፤
2. በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 180/1986 ተቋቁሞ የነበረው የኮንስትራክሽን ዲዛይን አክስዮን ማህበር፤
3. በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 161/1986 ተቋቁሞ የነበረዉ የትራስፖርት ኮንስትራክሽን ዲዛይን አክሲዮን ማህበር፡፡

11. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ታህሳስ 7 ቀን 2008 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 366/2008

## የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽንን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀጽ 5 እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 አንቀጽ 47(1 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭርርዕስ**

   ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክርቤት ደንብ ቁጥር 366/2008" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**

   1. የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን (ከዚህ በኃላ "ኮርፖሬሽን" እየተባለ የሚጠራ የፌደራል መንግስት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. ኮርፖሬሽኑ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ተቆጣጣሪ ባለስልጣን**

   የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር የኮርፖሬሽኑ ተቆጣጣሪ ባለስልጣን[79] ይሆናል፡፡

4. **ዋናዉመሥሪያቤት**

   የኮርፖሬሽኑ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈሊጊነቱ በሌሎች የአገሪቱ ክፍልች ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

5. **ዓላማ**[80]

   ኮርፖሬሽኑ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተለት ናቸው፡-

   1. የሥራት ቋራጭ ሆኖ በአገር ውስጥና በውጭ አገር መንገዶችን፣ ድልድዮችን፣ የግድብ ሥራዎችን፣ የመስኖ ሥራዎችን፣ የውኃ ኃይል ማመንጫ ግንባታዎችን፣ የውኃ ማከፋፊያ መስመሮችን፣ የቆሻሻ ማስወገጃ መስመሮች ስራዎችን፣

---

[79] በ25)08 (2011 አ.1097 አንቀጽ 36(23 የመንግስት ልማት ድርጅቶ ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ ሆኗል፡፡
[80] የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (8 እና (9 በ22)110(2008 ደ.390 አንቀፅ 2(1 አዲስ የገቡ ሲሆኑ፣ ነባሩ ንዑስ አንቀፅ (8 ንኡስ አንቀፅ (10 ሆኖ ተሸጋሽጓል፡፡

የድሬኔጅ፣ የጥልቅ ውኃ ጉድጓድ ሥራዎችን፣ የሪክላሜሽን ግንባታዎችን፣የወንዝ መቀልበስ ግንባታዎችን፣ የሕንፃ ግንባታዎችን፣ የአየር ማረፊያዎችን፣የባቡር መንገድችን፣ ወደብ ግንባታዎችን እና ሌሎች የሲቪል ግንባታሥራዎችን መሥራት፣ ማሻሻል እና መጠገን፤

2. የኮንስትራክሽን መሣሪያዎችና ተሽከርካሪዎችን የመገጣጠም፣መለዋወጫዎችን ማምረት፣የጥገና አገልግሎት መስጠት እንዲሁም ለሥራው የሚያስፈልጉትን የግንባታ ቁሳቁሶችንና የተለያዩ ቧንቧዎችን ማምረትና እንደ አግባብነቱም መሸጥ፤
3. በፌደራል መንግሥት በጀት የተገነቡና የሚገነቡ የመስኖ ግድቦችን፣ጥልቅ የውኃ ጉድጓዶችን እንደ አስፈላጊነቱ የውኃ ማስተላለፊያ ቦዮችን በመረከብ በባለቤትነት ማስተደዳር፣ ከተጠቃሚዎች ገቢ መሰብሰብ፤
4. የኮንስትራክሽን መሣሪያዎችን፣ ማሽነሪዎችን፣መጋዘኖችንና ሕንፃዎችን ማከራየት፤
5. ለኮርፖሬሽኑ የሚፈለገውን የሰለጠነ የሰው ኃይል በሚፈለገው ዓይነት፣ መጠን፣ ጥራት ለማፍራት እንዲቻል በራሱ የሥልጠና ማዕከላት ወይም ከሚመለከታቸው የአገር ውስጥና የውጭ ሀገር የምርምር፣ የትምህርት እና የሥልጠና ተቋማት ጋር በቅንጅት መስራት፤
6. በመንግስት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር በሚሰጠው አቅጣጫ ላይ በመመሥረት በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ተወዳዳሪና አትራፊ ሆኖ እንዲንቀሳቀስ እገዛ የሚያደርጉለትን የፋይናንስ፣ የቴክኖልጂና የዘመናዊ አስተዳደር ግብዓቶችን ለማግኘት የሚያስችለዉን (ኢንቨስትመንትን መሳብንም ሆነ በኢንቨስትመንት ላይ መሳተፍን ጨምሮ ጥናት በማካሄድ የውሳኔ ሃሳብ ማቅረብ፣ ሲፈቀድ ተግባራዊ ማድረግ፤
7. የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የሚያወጣውን መመሪያ እና የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር የሚሰጠውን አቅጣጫ መሠረት በማድረግ ቦንድ መሸጥና ዋስትና ማስያዝ እና ከአገር ውስጥና ከውጭ የገንዘብ ምንጮች ጋር የብድር ዉል መደራደርና ሲፈቀድ መፈራረም፤
8. የዲዛይንና ግንባታ፣ የኢንጅነሪንግ ግዢና ኮንትራት፣ የዲዛይን ግንባታ ኦፕሬሽን እና አስተዳደር ወይም ማስተላለፍ እና መሰል አጠቃላይ የኮንስታራክሽን ፕሮጀክት ማኔጅመንት አገልግሎት መስጠት፣

9. የኤሌክትሮ መካኒካል ረቂቅ የመሰረተ ቁፋሮ እና ሙሌት፣ የዋሻ ቁፋሮ፣ ተደባልቆ የተዘጋጀ አርማታ ሙሌት፣ ኮንክሪት እና ብረት ውቅር ተገጣጣሚ ሕንፃ ዲዛይን፣ ግንባታ፣ ተከላ፣ ማወላለቅ፣ ማፍረስ እና መሰል የሕንፃ ቴክኖሎጂ እና የሕንፃ ኮንስትራክሽን አገልግሎት መስጠት፤
10. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዳ ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎችን መስራት፡፡

6. **ካፒታል**[81]

የኮርፖሬሽኑ የተፈቀደ ካፒታል 20,324,608,143.90 (ሃያ ቢሊየን ሶስት መቶ ሀያ አራት ሚሊየን ስድስት መቶ ስምንት ሺህ አንድ መቶ አርባ ሶስት ብር ከዘጠና ሳንቲም ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ብር 7,754,333,613.80 (ሰባት ቢሊየን ሰባት መቶ ሃምሳ አራት ሚሊየን ሶስት መቶ ሰላሳ ሶስት ሺህ ስድስት መቶ አስራ ሶስት ብር ከሰማን ያሳንቲም በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል፡፡

7. **ኃላፊነት**

ኮርፖሬሽኑ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

8. **ኮርፖሬሽኑ የሚቆይበት ጊዜ**

ኮርፖሬሽኑ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

9. **የተሻሩ ህጎች**

የሚከተሉት ደንቦች በዚህ ደንብ ተሽረዋል፦

1. የኢትዮጵያ መንገድ ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክርቤት ደንብ ቁጥር 248/2003፤
2. የኢትዮጵያ ውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክርቤት ደንብ ቁጥር 316/2006::
3. የተገጣጣሚ ሕንፃ አካላት ማምረቻ ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 118/1985፡፡[82]

10. **የመብትና ግዴታዎች መተላለፍ**

የሚከተሉት የመንግስት የልማት ድርጅቶች መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለኮርፖሬሽኑ ተላልፈዋል፦

1. በሚኒስትሮች ምክርቤት ቁጥር 248/2003 ተቋቁሞ የነበረው የኢትዮጵያ መንገዶች ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን፤

---

[81] በ22)110(2008 ደ.390 አንቀፅ 2(2 ተሻሻለ፡፡
[82] በ22)110(2008 ደ.390 አንቀፅ 2(3 መሰረት አዲስ የገባ ነዉ፡፡

2. በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 316/2006 ተቋቁሞ የነበረው የኢትዮጵያ የውኃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት፡፡
3. በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 118/1985 ተቋቁሞ የነበረው የተገጣጣሚ ሕንፃ አካላት ማምረቻ ድርጅት፡፡[83]

11. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ታህሣሥ 8 ቀን 2008 ዓ.ም**

**ኃይለ ማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስትር**

[83] በ22)110(2008 ደ.390 አንቀፅ 2(4 መሰረት አዲሰ የገባ ነዉ፡፡

## ደንብ ቁጥር 367/2008

## የኢትዮጵያ ማዕድን፣ ነዳጅና ባዮፌዩል ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀጽ 5 እና የመንግስት ልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 አንቀጽ 47(1 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ የማዕድን፣ ነዳጅና ባዮፌዩል ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 367/2008" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   1. "ነዳጅ "ማለት ከኦይል ሼል ወይም ከታር ሳንድ የተገኘውን ሀይድሮ ካርቦን ጨምሮ የነዳጅ ድፍድፍ ዘይት እና የተፈጥሮ ጋዝ ሲሆን ከሼል ጋዝ፣ ከድንጋይ ከሰል እና ከባዮፌዩል ሥራዎች የሚመረቱ ተመሳሳይ ምርቶችን ያካትታል፤
   2. "የነዳጅ ሥራዎች" ማለት ድፍድፍ ዘይትና የተፈጥሮ ጋዝ መፈለግ፣ማልማት፣ ማውጣት፣ ማምረት፣ በመስክ መለያየት፣ ማዘጋጀት፣ ማከማቸት፣ ወደ ውጭ ሀገር እስከሚላክበት ወይም ለአገር ውስጥ ፍጆታ ወደሚሰራጭበት ሥፍራ ማጓጓዝ እና ለገበያ ማቅረብ ሲሆን ከተፈጥሮ ጋዝ የተለያዩ ምርቶችን ማውጣትና የነዳጅ ድፍድፍ ዘይት ማጣራትን ይጨምራል፤
   3. "ማዕድን" ማለት ማናቸውም ዋጋ ያለው በጠጣር፣ በፈሳሽ ወይም በጋዝ መልክ በተፈጥሮ በመሬት ላይ ወይም ውስጥ፣ በውሃ ውስጥ ወይም ስር የሚገኝ የጂኦሎጂ ሂደት ወይም ሁኔታዎች የተፈጠረ ሲሆን ቀደም ሲል ተቆፍሮ በወጣና ተርፎ የተቆለለ ማዕድን አዘል አፈር ወይም በቀሪ የማዕድን ክምችቶች ውስጥ የሚገኝ ማዕድንን ይጨምራል፤ ሆኖም የሚከተሉትን አይጨምርም፡-

      ሀ) ለመታጠቢያ፣ ለመዝናኛ፣ ለሕክምና ከሚውል የጂኦተርማል ውሃና ከውስጡ ማዕድን ለማውጣት ከሚውል እንደብራይን ውሃ በስተቀር ሌላውን ውሃ፤

      ለ) አግባብ ባለው የነዳጅ ሕግ ትርጓሜ የሚካተቱ የተፈጥሮ ዘይትና ጋዝ፤

      ሐ) ለም አፈርን እና ነዳጅ አዘል አካላትን፡፡

4. “የማዕድን ሥራዎች” ማለት የማዕድናት ቅኝት፣ ምርመራ፣ ይዞ መቆየት፣ ወይም ማምረት ጋር የተያያዙ ተግባራት ሲሆን በከበሩ ማዕድናት ግብይት አዋጅ ቁጥር 651/2001 መሠረት የማዕድናት ግብይት ሥራዎች መሥራትን ያካትታል፤
5. “የባዮ-ፊዩል ሥራዎች” ማለት ከሞላሰስ፣ ከተክሎች፣ ከእንስሳት ስብና ከሌሎች የተለያዩ ግብዓቶች ነዳጅ የማምረት ተግባር ነው፡፡

## 3. መቋቋም

1. የኢትዮጵያ የማዕድን፣ ነዳጅና ባዮ-ፊዩል ኮርፖሬሽን (ከዚህ በኋላ “ኮርፖሬሽን” እየተባለ የሚጠራ የፌደራል መንግስት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
2. ኮርፖሬሽኑ በመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 መሠረት ይተዳደራል፡፡

## 4. ተቆጣጣሪ ባለስልጣን

የመንግስት ልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር የኮርፖሬሽኑ ተቆጣጣሪ ባለስልጣን[84] ይሆናል፡

## 5. ዋና መስሪያ ቤት

የኮርፖሬሽኑ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በሌሎች የአገሪቱ ክፍሎች ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

## 6. ዓላማ

ኮርፖሬሽኑ የተቋቋመበት ዓላማ የሚከተሉት ናቸው፡-

1. በነዳጅ፣ በማዕድንና በባዮ-ፊውል ሥራዎች ውስጥ በቀጥታ በመሳተፍ የአገሪቱን የተፈጥሮ ሀብት በተገቢ ሁኔታ በማልማት የበለጠ ተጠቃሚ እንድትሆን ማስቻል፤
2. በዘርፉ አገር በቀል አቅምን በመገንባት በዘርፉ ለሚሰማሩ ሌሎች እገዛ ማድረግና ከዘርፉ የአገሪቱን ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፤
3. ከስትራቴጂካዊ አስፈላጊነታቸው አንፃር ከፍተኛ ግምት በሚሰጣቸውና በግሉ ዘርፍ ሊሟሉ በማይችሉ ዘርፎች ላይ በመሳተፍ ክፍተቱን መሙላት፤
4. ተወዳዳሪ የመንግስት ልማት ድርጅት በመሆን በአገሪቱ ኢኮኖሚ ግንባታ እገዛ ማድረግ፤

---

[84] በ25)08 (2011 አ.1097 አንቀጽ 36(23 የመንግስት ልማት ድርጅቶ ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ ሆኗል፡፡

5. ራሱ ወይም እንደሁኔታው ከሌሎች ጋር በመሆን በማዕድን፣ ነዳጅና ባዮፊዩል ሥራዎች ኢንቨስትመንት ላይ መሳተፍ፣ ማልማትና ማምረት፤
6. በሌሎች ባለሀብቶች በሚካሄዱ የነዳጅ፣ የማዕድንና የባዮፊዩል ሥራዎች ውስጥ ኢንቨስት ማድረግ፤
7. የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር በሚሰጠው የፖሊሲ አቅጣጫ መሰረት አክስዮን መሸጥ ወይም መግዛት፤
8. የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያና የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር በሚሰጠው አቅጣጫ መሠረት ቦንድ መሸጥና ዋስትና የማስያዝ፣ ከአገር ውስጥና ከውጭ የገንዘብ ምንጮች ጋር የብድር ውል መደራደርና መፈራረም፤
9. ከማዕድን፣ ከነዳጅና ከባዮፊዩል ጋር የተያያዙ የማማከር፣ የድሪሊንግ፣ የላብራቶሪ፣ መረጃ የመሰብሰብ፣ የመተንተንና የመተርጎም፣ የአዋጭነት ጥናት ሥራዎችን መሥራት፣ ስልጠናና የመሳሰሉ አገልግሎቶችን መስጠት፤
10.በአገር ውስጥና በውጭ አገራት ተወዳዳሪና አትራፊ ሆኖ እንዲንቀሳቀስ እገዛ የሚያደርጉለትን የፋይናንስ፣ የቴክኖሎጂና የዘመናዊ አሰተዳደር ግብዓቶችን ለማግኘት የሚያስችለውን (ኢንቨስትመንት መሳብንም ሆነ በኢንቨስትመንት ላይ መሳተፍን ጨምሮ ጥናት በማካሄድ የውሳኔ ሀሳብ ማቅረብ፤ ሲፈቀድ ተግባራዊ ማድረግ፤
11.በመንግስት ልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎችን መሥራት፡፡
12.በግል ኩባንያዎች አማካይነት በሚካሄዱ የነዳጅና ተፈጥሮ ጋዝ እንዲሁም በማዕድን ልማት ሥራዎች ውስጥ የመንግሥትን ድርሻ በመወከል መሳተፍና ማስተዳደር፡፡[85]

## 7. ካፒታል

ለኮርፖሬሽኑ የተፈቀደው ካፒታል ብር 1 ቢሊዮን 678 ሚሊዮን 640 ሺ (አንድ ቢሊዮን ስድስት መቶ ሰባ ስምንት ሚሊዮን ስድስት መቶ አርባ ሺ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 419 ሚሊዮን 660 ሺ (አራት መቶ አስራ ዘጠኝ ሚሊዮን ስድስት መቶ ስልሳ ሺ በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል፡፡[86]

[85] በ23)85(2009 ደ.413 አንቀፅ 2(1 መሰረት አዲስ ገባ ነው፡፡
[86] በ23)85(2009 ደ.413 አንቀፅ 2(2 ተሻሻለ፡፡

8. <u>ኃላፊነት</u>

ኮርፖሬሽኑ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

9. <u>ኮርፖሬሽኑ የሚቆይበት ጊዜ</u>

ኮርፖሬሽኑ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

10. <u>የተሻረ ደንብ</u>

የኢትዮጵያ የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ልማት ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 260/2004 በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

11. <u>የመብቶችና ግዴታዎች መተላለፍ</u>

የሚከተሉት የመንግስት ልማት ድርጅቶች መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለኮርፖሬሽኑ ተላልፈዋል፡-

1. በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 264/2004 የኢትዮጵያ የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ልማት ድርጅት፤
2. የኢትዮጵያ የማዕድን ልማት አክስዮን ማህበር፡፡

12. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ ከታህሳስ 8 ቀን 2008 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ታህሳስ 8ቀን 2008 ዓ.ም**

**ኃይለማሪያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

# ደንብ ቁጥር 368/2008

# የኢትዮጵያ የግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀጽ 5 እና በመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25 /1984 አንቀጽ 47(1መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ የግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 368/2008"ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**
   1. የግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን (ከዚህ በኋላ "ኮርፖሬሽን" እየተባለ የሚጠራ የፌደራል መንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. ኮርፖሬሽኑ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ተቆጣጣሪ ባለስልጣን**

   የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር የኮርፖሬሽኑ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን[87] ይሆናል፡፡

4. **ዋና መስሪያ ቤት**

   የኮርፖሬሽኑ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በሌሎች የአገሪቱ ክፍሎች ቅርንጫፍ ሊኖረዉ ይችላል፡፡

5. **ዓላማ**

   ኮርፖሬሽኑ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፦
   1. የግብርና ምርት ማሳደጊያዎችን ከሀገር ውስጥና ከውጭ አገር ገዝቶ ለገበያ ማቅረብ፣ ማዘጋጀት፣ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎችን የገበያ ዋጋ የማረጋጋት ተግባራትን ማከናወን፣

[87] በ25)08 (2011 አ.1097 አንቀጽ 36(23 የመንግስት ልማት ድርጅቶ ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ ሆኗል፡፡

2. የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት፣ የእርሻና የኮንስትራክሽን መሣሪያዎችን የጥገና አገልግሎት፣ የእርሻ መሣሪያዎችንና የትራንስፖርት ተሽከርካሪዎችን የኪራይ አገልግሎት በክፍያ መስጠት፤
3. የእርሻ መሣሪያዎችንና መለዋወጫዎችን፣ የኮንስትራክሽን መሣሪያዎችን እና አግሮ ኬሚካልችን ከሀገር ውስጥና ከውጭ አገር ገዝቶ ለሽያጭ ማቅረብ፤
4. ዘመናዊ የእርሻ መሣሪያዎች አጠቃቀም እንዲለመድ አስፈሊጊውን ትምህርት መስጠት፤ስለእርሻ መሣሪያዎች አያያዝና አጠቃቀም የምክር አገልግሎት መስጠት፤ የቴክኒክ ሙያ ማሻሻያ ሥራ ሥልጠና መስጠት፤
5. የተፈጥሮ ሙጫ ምርት መሰብሰብ፣ መግዛት፣እሴት መጨመር፣ ማዘጋጀት፤ሌሎች ከደን ውጤቶች የሚመረቱ ምርቶችን ማምረት፣ ለሀገር ዉስጥና ለዉጭ ገበያዎች ማቅረብ፤
6. የእርሻ መሬት ልማት ጥናትና ዲዛይን፣ የእርሻ መሬት ቅየሳ፣ ምንጣሮና ማስተካከል፣ የውኃ ተፋሰስና የመስኖ ሥራ እንዲሁም ከእርሻ መሬት ልማት ጋር የተዛመዱ ሥራዎችን ማከናወን፤
7. የአዳዲስና ማስፋፊያ ፕሮጀክቶችን አዋጪነት ጥናት፣ የዲዛይን ዝግጅት፣የቴክኖሎጂ መረጣና ድርድር፣የተከላና የኮሚሽኒንግ እንዲሁም የምርምር ሥራዎች እንዲካሄዱ ማድረግ፤
8. አቅሙ ካላቸው የአገር ውስጥ እና የውጪ ኩባንያዎች ጋር በመተባበር የግብርና የማምረቻ መሣሪያዎችና መለዋወጫዎች ዲዛይንና የማምረት ሥራዎች በአገር ውስጥ እንዲከናወኑ ማድረግ፤
9. ለመስኩ የሚፈለገውን የሰለጠነ የሰው ኃይል በሚፈለገው ዓይነት፣ መጠንና ጥራት ለማፍራት እንዲቻል ከሚመለከታቸው የትምህርት የምርምርና የሥልጠና ተቋማት ጋር በመተባበር መሥራት፤
10. በመንግስት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር በሚሰጠው አቅጣጫ ላይ በመመሥረት በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ተወዳዳሪና አትራፊ ሆኖ እንዲንቀሳቀስ እገዛ የሚያደርጉለትን የፋይናንስ፣ የቴክኖሎጂና የዘመናዊ አስተዳደር ግብዓቶችን ለማግኘት የሚያስችለውን (ኢንቨስትመንት መሳብንም ሆነ በኢንቨስትመንት መሳተፍን ጨምሮ ጥናት በማካሄድ ሲፈቀድ ተግባራዊ ማድረግ፤
11. የተለያዩ የአዝዕርት፣ የአትክልት፣ የፍራፍሬና የመሳሰሉት ቅድመ መሥራች፣ መሥራችና የተመሠከረለት ዘር ማባዛት፣ ማበጠርና ማዘጋጀት፣እንደ አስፈላጊነቱም

ቅድመ መሥራች ዘሮችን ከውጭ አገር በማስመጣት ማስመረት ወይም መሸጥ፣ተረፈ ምርቶችን ለገበያ ማቅረብ፤

12. በግብርና ግብዓት አቅርቦት፣ በእርሻ መሣሪያዎች አቅርቦት፣ በእርሻ መሣሪያዎች ጥገና፣ በተፈጥሮ ሙጫ ምርትና ገበያ በሜካናይዜሽን አገልግሎትና በተዛማጅ ሥራዎች ዙሪያ ምርምር በማካሄድ የተሻሻሉትን ተግባራዊ ማድረግ፣ በውጤቱም ተወዳዳሪነት ማረጋገጥ፤

13. የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያና የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር በሚሠጠው አቅጣጫ መሠረት ቦንድ መሸጥ፣ ዋስትና ማስያዝ፣ ከሀገር ውስጥና ከውጪ የገንዘብ ምንጮች የብድር ዉል መደራደርና ሲፈቀድ መፈራረም፤

14. ዓላማዉን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛምጅ ሥራዎችን መሥራት፤፤

6. <u>**ካፒታል**</u>

የኮርፖሬሽኑ የተፈቀደ ካፒታል ብር 2,440,000,000.00 (ሁለት ቢሊዮን አራት መቶ አርባ ሚሊዮን ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 610,000,000.00(ስድስት መቶ አስር ሚሊዮን በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል፡፡

7. <u>**ኃላፊነት**</u>

ኮርፖሬሽኑ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

8. <u>**ኮርፖሬሽኑ የሚቆይበት ጊዜ**</u>

ኮርፖሬሽኑ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

9. <u>**የተሻሩ ደንቦች**</u>

የሚከተሉት ደንቦች በዚህ ደንብ ተሽሯል፡-

1. የኢትዮጵያምርጥዘርድርጅትማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 154/1986፤
2. የተፈጥሮ ሙጫ ምርትና ገበያ ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 179/1986፤
3. የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 177/1986፤
4. የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ድርጅት ማቋቋሚያ ሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 97/1986፡፡

10. <u>**የመብትና ግዴታዎች መተላለፍ**</u>

የሚከተሉት የመንግስት የልማት ድርጅቶች መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን ተላልፈዋል፦

1. በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 154/1986 ተቋቁሞ የነበረው የኢትዮጵያ ምርጥ ዘር ድርጅት፤
2. በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 179/1986 ተቋቁሞ የነበረው የተፈጥሮ ሙጫ ምርት ገበያ ድርጅት፤
3. በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 177/1986 ተቋቁሞ የነበረው የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት፤
4. በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ተቋቁሞ በመቀጠልም በአዋጅ ቁጥር146/1991 አንቀጽ 5 መሠረት ጥር1/1994 እንደ አዲስ ወደ አክሲዮን ማህበርነት ተለዉጦ የነበረው የእርሻ መሣሪያዎችና የቴክኒክ አገልግሎት አክሲዮን ማህበር፤
5. በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 97/1986 ተቋቁሞ የነበረው የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎትድርጅት፡፡

11.<u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ታህሣሥ 12 ቀን 2008ዓ.ም**

**ኃይማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራልዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብልክ**

**ጠቅላይ ሚኒስቴር**

**ደንብ ቁጥር 398/2009**

**የፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽንን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀጽ 5 እና በመንግስት የልማት ድርጅቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 25/1994 አንቀጽ 47(1 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የፌደራል ቤቶች ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 398/2008" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**
   1. የፌደራል ቤቶች ኮርፖሬሽን (ከዚህ በኋላ "ኮርፖሬሽን" እየተባለ የሚጠራ ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. ኮርፖሬሽኑ በመንግስት የልማት ድርጅቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 25/1984 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን**

   በመንግሥት የሚሰየም አካል የኮርፖሬሽኑ ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ይሆናል፡፡

4. **ዋና መሥሪያ ቤት**

   የኮርፖሬሽኑ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ከተማ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ስፍራ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ሊኖረው ይችላል፡፡

5. **ዓላማዎች**

   ኮርፖሬሽኑ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ይሆናሉ፡-
   1. ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውሉ ቤቶችን መገንባት፣ ማስገንባት፣ ማከራየት፣ መሸጥ እንዲሁም በተለየ ሁኔታ ሲወሰን መግዛት፤
   2. የፌደራል መንግሥት በባለቤትነት የያዛቸውን ቤቶችና ይዞታዎች ማስተዳደር፣ ማከራየት፤

3. ለፌደራል መንግሥት ቤቶችና ሕንፃዎች አስፈላጊውን ጥገናና ዕድሳት በማድረግ የመጠበቅና የመንከባከብ፤
4. የፌደራል መንግሥት ንብረት የሆኑትን ቤቶችና ይዞታዎች በሕግ አግባብ መመዝገባቸውንና መጠበቃቸውን ማረጋገጥ፤
5. የፌደራል መንግሥት ቤቶችን በአግባቡ ለማስተዳደር የሚያስችል ዘመናዊ የቤት አስተዳደር ሥርዓትን በመዘርጋት ሥራ ላይ ማዋል፤
6. በመንግሥት ቤቶችና ይዞታዎች ላይ የሚፈፀሙ ሕገ-ወጥ ድርጊቶችን መከላከል፣ የመንግሥትን ጥቅም ማስከበር እና አስፈላጊ ሕጋዊ እርምጃዎችን መውሰድ፤
7. መንግሥት በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት በመንግሥት ወጪ ተሸፍነው ለመንግሥት ኃላፊዎች እና ሰራተኞች የመኖሪያ ቤት መገንባት፣ ማከራየት እና ማስተዳደር፤
8. ለሚያስተዳድራቸው ቤቶችና ይዞታዎች የኪራይ ተመን ጥናት ማካሄድና ተግባራዊ ማድረግ፤
9. በሽያጭ እንዲተላለፉ በመንግሥት ውሳኔ የተሰጠባቸውን ቤቶች ዋጋ አተማመን ጥናት ማካሄድ፣ ሲወሰን በውሳኔው መሠረት መፈፀምና የሽያጭ ገቢ መሰብሰብ፤
10. ለአስተዳደር አመቺ ያልሆኑ፤ መልሶ ለማልማት የማያስችሉና ኪራያቸው አነስተኛ የሆኑት ቤቶችንና ይዞታዎችን በመንግሥት ውሳኔ ማስተላለፍ፤
11. ለተወረሱ ቤቶች የቀድሞ ባለንብረቶች በሕጉ መሠረት አበል መክፈል፤
12. ከቤት አስተዳደርና ልማት ጋር የተያያዙ ጥናቶችን በማካሄድ በመንግሥት ሲፈቀድ ተግባራዊ ማድረግ፤
13. ከተቆጣጣሪው ባለስልጣን በሚሰጠው አቅጣጫ ላይ በመመስረት በሀገር ውስጥ ተወዳዳሪና አትራፊ ሆኖ እንዲንቀሳቀስ እገዛ የሚያደርጉለትን የሰው ሀይል፣ የፋይናንስና የዘመናዊ አስተዳደር ግብአቶችን ለማግኘት የሚያስችለውን ጥናት በማካሄድ ተግባራዊ ማድረግ፤
14. የሕንፃ ዕቃዎችን አምርቶ ወይም ገዝቶ ለቤት ግንባታ፣ ለጥገና፣ለዕድሳት እና ለሌሎች ኮንስትራክሽን ሥራዎች አገልግሎት እንዲውሉ ማቅረብ፤[88]
15. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎችን ማካሄድ፡፡

---

[88]በ24)48 (2010 ደ.427 አንቀፅ 2(1 መሰረት አዲስ ገባ ሲሆን ነባሩ ንዑስ አንቀፅ (14 ንዑስ አንቀፅ (15 ሆኖ ተሸጋሽጓል፡፡

6. **<u>ካፒታል</u>**[89]

ለኮርፖሬሽኑ የተፈቀደለት ካፒታል ብር 33,165,674,166(ሰላሳ ሶስት ቢሊዮን አንድ መቶ ስልሳ አምስት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሰባ አራት ሺ አንድ መቶ ሰላሳ ስድስት ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 11,069, 159,378 (አስራ አንድ ቢሊዮን ስልሳ ዘጠኝ ሚሊዮን አንድ መቶ ሃምሳ ዘጠኝ ሺ ሶስት መቶ ሰባ ስምንት ብር በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል።

7. **<u>ኃላፊነት</u>**

ኮርፖሬሽኑ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

8. **<u>ኮርፖሬሽኑ የሚቆይበት ጊዜ</u>**

ኮርፖሬሽኑ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

9. **<u>የተሻረ ሕግ</u>**[90]

የሕንፃ ዕቃዎች አቅራቢ ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 164/1986 በዚህ ደንብ ተሽሯል።

10. **<u>የመብቶችና ግዴታዎች መተላለፍ</u>**[91]

1. በአዋጅ ቁጥር 555/2000 ተቋቁሞ የነበረው የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለኮርፖሬሽኑ ተላልፈዋል፡፡
2. በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 164/1986 ተቋቁሞ የነበረው የሕንፃ ዕቃዎች አቅራቢ ድርጅት መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን ተላልፈዋል፡፡

11. **<u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ የካቲት 24 ቀን 2009 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሣለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

---

[89] በ24)48 (2010 ደ.427 አንቀፅ 2(2 ተሻሻለ፡፡
[90] በ24)48 (2010 ደ.427 አንቀፅ 2(3 መሰረት አዲስ ገባ ሲሆን ነባሩ አንቀፅ (9 እና (10 አንቀፅ (10 እና (11 ሆነው ተሸጋሽጓል፡፡
[91] በ24)48 (2010 ደ.427 አንቀፅ 2(4 መሰረት ተሻሻለ፡፡

## 2 /ለትራንስፖርት ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ የመንግስት ልማት ድርጅቶች ማቋቋሚያ ህጎች

## ደንብ ቁጥር 298/2006

## የፐብሊክ ሰርቪስ ሠራተኞች የትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 አንቀጽ 47(1(ሀ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የፐብሊክ ሰርቪስ ሠራተኞች የትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 298/2006" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ ደንብ ውስጥ "የፐብሊክ ሰርቪስ ሠራተኞች" ማለት በአዲስ አበባ የሚገኙ የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶችን እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሥሪያ ቤቶችን ሠራተኞች ያጠቃልላል፡፡

3. **መቋቋም**

   1. የፐብሊክ ሰርቪስ ሠራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት (ከዚህ ቦኋላ "ድርጅት" እየተባለ የሚጠራ የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. ድርጅቱ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 መሠረት ይተዳደራል፡፡

4. **ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን**

   የትራንስፖርት ሚኒስቴር የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል፡፡

5. **ዋና መሥሪያ ቤት**

   የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ይሆናል፡፡

6. **ዓላማ**

   ድርጅቱ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸዉ

   1. ለፐብሊክ ሰርቪስ ሠራተኞች በሥራ መግቢያና መውጫ ሰዓት የትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት ፤

2. ከፐብሊክ ሰርቪስ ሠራተኞች የሥራ መግቢያና መውጫ ሰዓት ውጪ ለሌሎች ተገልጋዮች የትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት፤
3. ከዓላማው ጋር ተዛማጅ የሆኑ ሌሎች ሥራዎችን ማከናወን፡፡

7. **ካፒታል**

ለድርጅቱ የተፈቀደው ካፒታል ብር 1,572,618,280 (አንድ ቢሊዮን አምስት መቶ ሰባ ሁለት ሚሊዮን ስድስት መቶ አስራ ስምንት ሺህ ሁለት መቶ ሰማኒያ ብር ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 1,072,618,280 (አንድ ቢሊዮን ሰባ ሁለት ሚሊዮን ስድስት መቶ አስራ ስምንት ሺህ ሁለት መቶ ሰማኒያ ብር በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል፡፡[92]

8. **ኃላፊነት**

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም።

9. **ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ**

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

10. **ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥቅምት 28 ቀን 2008 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስትር**

[92]በ22)14(2008 አ. 362አንቀፅ 2 ተሻሻለ፡፡

## ደንብ ቁጥር 310/2006

## የኢትዮጵያ የክፍያ መንገዶች ኢንተርፕራይዝ ማቋቋሚያ

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 አንቀጽ 47(1 (ሀ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ የክፍያ መንገዶች ኢንተርፕራይዝ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 310/2006" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**

   1. የኢትዮጵያ የክፍያ መንገዶች ኢንተርፕራይዝ (ከዚህ በኋላ "ኢንተርፕራይዝ" እየተባለ የሚጠራ የመንግስት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. ኢንተርፕራይዙ በመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን**

   የትራንስፖርት ሚኒስቴር የኢንተርፕራይዙ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል፡፡

4. **ዋና መስሪያ ቤት**

   የኢንተርፕራይዙ ዋና መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

5. **ዓላማ**

   ኢንተርፕይዙ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

   1. ለመንገድ ተጠቃሚዎች የክፍያ መንገዶች አገልግሎት የመስጠት፤
   2. የክፍያ መንገዶችን የማስተዳደርና የማስጠገን፤
   3. በክፍያ መንገዶች ክልል ውስጥ የተሰሩ የአገልግሎት መስጫ ጣቢያዎችን የማስተዳደር፤
   4. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ የሆኑ ሥራዎች ማካሄድ፡፡

6. **ካፒታል**

   ለኢንተርፕራይዙ የተፈቀደለት ካፒታል ብር 202,401,843.00 (ሁለት መቶ ሁለት

ሚሊዮን አራት መቶ አንድ ሺህ ስምንት መቶ አርባ ሶስት ብር ሲሆን በጥሬ ገንዘብና በአይነት በሙሉ ተከፍሏል፡፡

7. <u>**የኃላፊነት ወሰን**</u>

ኢንተርፕራይዙ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

8. <u>**ኢንተርፕራይዙ የሚቆይበት ጊዜ**</u>

ኢንተርፕራይዙ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

9. <u>**የተሻሩ ሕጎች**</u>

በኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን እንደገና ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 247/2003 አንቀጽ 6(23 ላይ "ከተጠቃሚዎች የሚሰበሰብ የአገልግሎት ክፍያን ይሰበሰባል፤ ለመንገድ ፈንድ ገቢ ያደርጋል" የሚለው ሐረግ በዚህ ደንብ ተሠርዟል፡፡

10. <u>**ደምቡ የሚጸናበት ጊዜ**</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ 16 ቀን 2007 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስትር**

**ደንብ ቁጥር 406/2009**

**የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀጽ 5 እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 አንቀጽ 47(1(ሀ መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 406/2009" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

1. "የአየር ማመላለሻ አገልግሎት" ማለት መደበኛ የሆነ በአየር መንገደኞችን፣ ጭነትን እና ፖስታን የማመላለስ ተግባር ነው፤
2. "ጠቅላላ የአውሮፕላን አገልግሎት" ማለት መደበኛ ያልሆነ የአየር ማመላለሻ አገልግሎት እና የዚሁ አስፈላጊ ተጓዳኝ ወይም ተያያዥየሆነ በአየር ሊሰጥ የሚችል ሌላ አገልግሎት ነው፤
3. "ኤርፖርት" ማለት የአየር ማመላለሻ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ዝርዝሩ በዚህ ሳይወሰን የአውሮፕላን ማረፊያ፣ የመንገደኞች ማስተናገጃ ተርሚናል፣ ለአውሮፕላን አገልግሎት የሚውሉ ሕንፃዎች፣ ተቋሞችና መሣሪያዎች እንዲሁም ሌሎች ለዚሁ ተግባር አስፈላጊ የሆኑ አቅርቦቶች ያሉበት ደህንነቱ የተጠበቀ ቦታ ነው፤
4. "የኤርፖርት አገልግሎት" ማለት በኤርፖርት ውስጥ ለኤር ኦፕሬተሮች እና ለመንገደኞች የሚሰጥ አገልግሎት ሆኖ ዝርዝሩ በዚህ ሳይወሰን የተርሚናል አገልግሎት፣ የተርሚናል ድልድይ አገልግሎት፣ የመንገደኛ ሻንጣ አገልግሎት፣ የአውሮፕላን መነሻ፣ ማረፊያ፣ መንደርደሪያ እና ማቆሚያ አገልግሎት፣ የመንገደኞች መለያ ካውንተር አገልግሎት፣ የአውሮፕላን ማረፊያ ሜዳ መብራት አገልግሎት እና ሌሎች ተያያዥ አገልግሎቶችን ይጨምራል፡፡

3. **ስያሜና መጠቀለል**[93]

[93] በ25)70(2011 ደ.452 አንቀፅ 2(1 መሰረት ተሻሻለ፡፡

1. የኢትዮጵያ አየር መንገድ ድርጅት ስያሜ ወደ ኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ ተቀይሯል፡፡[94]
2. የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ የኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅትን ጠቅልሎታል
3. የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 መሠረት ይተዳደራል፡፡

4. <u>ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን</u>

የትራንስፖርት ሚኒስቴር የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል፡፡

5. <u>ዋና መስሪያ ቤት</u>

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ ዋና መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ስፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

6. <u>ዓላማ</u>

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

1. የሀገር ውስጥና ዓለም አቀፍ የአየር ማመላለሻ አገልግሎት እና ጠቅላላ የአውሮፕላን አገልግሎት መስጠት፤
2. አውሮፕላንና የአውሮፕላን አካላትን መፈብረክና መጠገን፤
3. ኤርፖርቶችን መገንባት፣ ማስፋፋት፣ መጠገን እና ማስተዳደር፤
4. የኤርፖርት አገልግሎቶችን፣ ሌሎች ኤሮኖቲካል አገልግሎቶችን እና ኤሮኖቲካል ያልሆኑ አገልግሎቶችን መስጠት፤ ለኤር ኦፕሬተሮች የሚሰጡ አገልግሎቶችን ያለአድልዎ መስጠት፤
5. እንደአስፈላጊነቱ የተወሰኑ አገልግሎቶቹን በውል ላይ ተመሥርቶ በሌሎች ወገኖች እንዲሰጡ ማድረግ፤ በውሎቹ ውስጥ በተዘረጋው ሥርዓት መሠረት የአገልግሎቶቹ አሰጣጥ የጥራት ደረጃውን የጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ፤
6. አግባብ ላላቸው አካላት የተሰጡ ሥልጣንና ተግባሮች እንደተጠበቁ ሆነው በኤርፖርቶች ውስጥ አስተማማኝ እና ደህንነቱ የተረጋገጠ አገልግሎት ለመስጠት የኤርፖርት አገልግሎት ደህንነት ማደራጀት፤
7. የአቪየሽን ሥራ ባለሙያዎችን የማሰልጠን አገልግሎት መስጠት፤

[94] በ25)70(2011 ደ.452 አንቀፅ 2(2 መሰረት የደንቡ አንቀጽ 3 (1 ተሰርዞ አዲስ ንዑስ አንቀጾች (1 እና (2 የተጨመሩ ሲሆን ንዑስ አንቀጽ (2 ንዑስ አንቀጽ (3 ሆኖ ተሸጋሽጓል፡፡

8. በሌሎች አየር መንገዶች፣ አውሮፕላን አምራቾችና የአቪየሽን አገልግሎቶች፣ የኢንቨስትመንት አክሲዮን ድርሻ በመያዝ መሳተፍ፤
9. ከአቪየሽን ኢንዱስትሪው ጋር በተያያዘ የሆቴል፣ የመዝናኛና ሌሎች የቱሪዝም አገልግሎቶች መስጠት ወይም በእነዚሁ አገልግሎቶች የኢንቨስትመንት አክሲዮን በመያዝ መሳተፍ፤
10. ቦንድ መሸጥ፣ ዋስትና ማስያዝ፣ ከሀገር ውስጥና ከውጪ የገንዘብ ምንጮች የብድር ውል መደራደርና መፈራረም፤
11. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ የሆኑ ሥራዎችን ማካሄድ፡፡

7. <u>**ካፒታል**</u>

ለኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ የተፈቀደው ካፒታል ብር 100 ቢሊዮን (አንድ መቶ ቢሊዮን ብር ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 31 ቢሊዮን 216 ሚሊዮን 632 ሺ 692 (ሠላሳ አንድ ቢሊዮን ሁለት መቶ አሥራ ስድስት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሠላሳ ሁለት ሺህ ስድስት መቶ ዘጠና ሁለት ብር በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል፡፡

8. <u>**ኃላፊነት**</u>

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

9. <u>**የሚቆይበት ጊዜ**</u>

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

10. <u>**የተሻሩ ደንቦች**</u>

የሚከተሉት ደንቦች በዚህ ደንብ ተሽረዋል፤

1. የኢትየጵያ አየር መንገድ ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቀጥር 216/1987 (እንደተሻሻለ፤
2. የኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 82/1995፡፡

11. <u>**የመብቶችና ግዴታዎች መተላለፍ**</u>

የሚከተሉት ድርጅቶች መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ ተላልፈዋል፤

1. በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 82/1995 ተቋቁሞ የነበረው የኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት፡፡[95]

---

[95] በ25)70(2011 ደ.452 አንቀፅ 2(3 መሰረት አንቀጽ 11 (1 ተሰርዞ ንዑስ አንቀጽ(2 ተሸጋሽጓል፡፡

12.<u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ ከሐምሌ 1 ቀን 2008 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ 1 ቀን 2009ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክጠቅላይ ሚኒስትር**

**ደንብ ቁጥር 165/2001**

**የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት ማቋቋሚያ**

**የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 471/1998 አንቀጽ 5 እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 አንቀጽ47 (1 ሀ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 165/2001" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ፡፡

2. **መቋቋም**

   1. የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት (ከዚህ በኋላ "ድርጅት" እየተባለ የሚጠራ የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. ድርጅቱ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን**

   የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል፡፡

4. **ዋና መሥሪያ ቤት**

   የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች እና ወኪሎች በአዲስ አበባና እንደአስፈላጊነቱ በሌሎች ሥፍራዎች ሊኖሩት ይችላል፡

5. **ዓላማ**

   ድርጅቱ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉትናቸው፡፡

   1. የመንግሥት የልማት ፖሊሲን መሠረት በማድረግ የፖስታ አገልግሎቶችን ማቋቋምና ማስፋፋት፤
   2. የሀገር ውስጥና ዓለም አቀፍ የደብዳቤ፣ የጥቅል ፖስታ ፣ የፈጣን ፖስታ፣ የሀዋላ፣ የቀጥታ ደብዳቤ፣ የፖስታ ባንክና ሌሎች የፋይናንስ አገልግሎቶች፣ ኤሌክትሮኒክ ሜይል አገልግሎትና የውክልና አገልግሎት መስጠት፤
   3. የፖስታ ሣጥኖችን ማከራየትና የፖስታ ማጠራቀሚያ ሣጥኖችን አስፈላጊ በሆኑ ቦታዎች ሁሉ መትከል፤

4. የፊላቴሊ ቴምብሮችን፣ የመጀመሪያ ቀን ኢንቨሎፖችና የፊላቴሊ ውጤቶችን ማዘጋጀትና መሸጥ፤
5. ለፖስታ ባለሙያዎች የሥልጠና አገልግሎት መስጠት፤
6. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተዛማጅ የሆኑ ሥራዎችን ማካሄድ፡፡

6. <u>ካፒታል</u>

ለድርጅቱ የተፈቀደለት ካፒታል ብር 380,000,000 (ሦስት መቶ ሰማኒያ ሚሊዮን ብር ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 109,097,601.14(አንድ መቶ ዘጠኝ ሚሊዮን ዘጠና ሰባት ሺ ስድስት መቶ አንድ ብር ከአስራ አራት ሳንቲም በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል፡፡

7. <u>ኃላፊነት</u>

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም።

8. <u>ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ</u>

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

9. <u>የመብትና ግዴታዎች መተላለፍ</u>

በአዋጅ ቁጥር 240/1958 መሠረት ይተዳደር የነበረው የቀድሞው የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለድርጅቱ ተላልፈዋል፡፡

10. <u>ደንቡ የማፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መጋቢት 15 ቀን 2001 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**ደንብ ቁጥር 462/2012**

## የኢትዮጵያ የማዕድን፣ ነዳጅና ባዮፌዩል ኮርፖሬሽንን እንደገና ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2012 አንቀጽ 34 እና በመንግሥት ልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 አንቀጽ 47(1 (ሀ እና (መ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ የማዕድን ነዳጅና ባዮፌዩል ኮርፖሬሽን እንደገና ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 462/2012" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ:-

   1. "ማዕድን" ማለት ማናቸውም ዋጋ ያለው በጠጣር፣ በፈሳሽ ወይም በጋዝ መልክ በተፈጥሮ በመሬት ላይ ወይም ውስጥ፣ በውኃ ውስጥ ወይም ሥር የሚገኝ በሥነ-ምድር ሂደት ወይም ሁኔታዎች የተፈጠረ ሲሆን ቀደም ሲል ተቆፍሮ የወጣና ተርፎ በተቀለለ ማዕድን አዘል አፈር ወይም በቀሪ የማዕድን ክምችቶች ውስጥ የሚገኝ ማዕድንን ይጨምራል፤ ሆኖም የሚከተሉትን አይጨምርም:-

      ሀ ለመታጠቢያ፣ ለመዝናኛ፣ ለሕክምና ከሚውሉ የጂኦተርማል ውኃና ከውስጡ ማዕድን ለማውጣት ከሚውል እንደ ብራይን ከመሳሰለ ውኃ በስተቀር ሌላውን ውኃ፤

      ለ አግባብ ባለው የነዳጅ ሕግ ትርጓሜ የሚካተቱ የተፈጥሮ ዘይትና ጋዝ፤

      ሐ ለም አፈርን እና ነዳጅ አዘል አለትን፤

   2. የማዕድን ሥራዎች" ማለት የማዕድናት ቅኝት፣ ምርመራ፣ ይዞ መቆየት፣ ወይም ማምረት ጋር የተያያዙ ተግባራት ሲሆኑ፣ የማናቸውም ማዕድናት ግብይት ሥራዎች መሥራትን ያካትታል፤
   3. "ነዳጅ" ማለት ከኦይል ሼል ወይም ከታር ሳንድ የተገኘውን ኃይድሮካርቦን ጨምሮ. የነዳጅ ድፍድፍ ዘይት እና የተፈጥሮ ጋዝ ሲሆን ከሼል ጋዝ፣

ከድንጋይ ከሰል እና ከባዮፊዩል ሥራዎች የሚመረቱ ተመሳሳይ ምርቶችን ያካትታል፤

4. የነዳጅ ሥራዎች" ማለት ድፍድፍ ዘይትና የተፈጥሮ ጋዝ መፈለግ፣ ማልማት፣ ማውጣት፣ ማምረት፣ በመስክ መለያየት፣ ማዘጋጀት፣ ማከማቸት፣ ወደ ውጭ ሀገር እስከሚላክበት ወይም ለሀገር ውስጥ ፍጆታ ወደ ሚሰራጭበት ሥፍራ ማጓጓዝ እና የተጣሩ የነዳጅ ምርቶችን ለተጠቃሚ ማቅረብ ሲሆን፣ ከተፈጥሮ ጋዝ የተለያዩ ምርቶችን ማውጣትና የነዳጅ ድፍድፍ ዘይት ማጣራትን ይጨምራል፤
5. "ባዮፊዩል" ማለት በካርቦሃይድሬት እና በዘይት ከበለጸጉ የተክሎች ግንድ፣ ፍሬ፣ ሥር ወይም ቅጠል፤ የከተማ ውጋጅ፣ የግብርና እና የደን ተረፈ ምርት፣ አልጌ፣ ወይም የእንስሳት ስብ እና ጥቅም ላይ ከዋለ ዘይት በማቀነባበር የሚገኝ ታዳሽ የሆነ ፈሳሽ ነዳጅ ማለት ነው፤
6. "የባዮፊዩል ሥራዎች" ማለት ከሞላሰስ፣ ከተክሎች ከእንስሳት ስብና ከሌሎች የተለያዩ ግብዓቶች ባዩፊዩል የማምረት ተግባር ነው፤
7. "ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት እንደ ቅደም ተከተላቸው የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፡፡

3. <u>መቋቋም</u>

1. የኢትዮጵያ የማዕድን፣ ነዳጅና ባዮፊዩል ኮርፖሬሽን (ከዚህ በኋላ "ኮርፖሬሽን" እየተባለ የሚጠራው የራሱ ህጋዊ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ እንደገና ተቋቁሟል፡፡
2. ኮርፖሬሽኑ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/፲1984 መሠረት ይተዳደራል፡፡

4. <u>ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን</u>

ሚኒስትሩ የኮርፖሬሽኑ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል፡፡

5. <u>ዋና መሥሪያ ቤት</u>

የኮርፖሬሽኑ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በሌሎች ስፍራዎች ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

6. <u>ዓላማ</u>

ኮርፖሬሽኑ የተቋቋመበት ዓላማ የሚከተሉት ናቸው:-

1. በማዕድን፣ በነዳጅና በባዮፊዩል ሥራዎች ውስጥ በቀጥታ በመሳተፍ የሀገራችን የተፈጥሮ ሃብት በተገቢ ሁኔታ በማልማት የበለጠ ተጠቃሚ እንድትሆን ማስቻል፣
2. ሀገር በቀል አቅምን በመገንባትና በዘርፉ ለተሰማሩ ባለሃብቶች እገዛ በማድረግ የሀገራችንን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፤
3. ከስትራቴጂካዊ አስፈላጊነታቸው አንፃር ከፍተኛ ግምት በሚሰጣቸውና በግሉ ዘርፍ ሊሟሉ በማይችሉ ዘርፎች ላይ በመሳተፍ ክፍተቱን መሙላት፤
4. በዘርፉ ተወዳዳሪ የመንግሥት ልማት ድርጅት በመሆን ለሀገራችን ኢኮኖሚ ግንባታ እገዛ ማድረግ እንዲሁም
5. ዓላማውን ለማሳካት ተግባራትን ያከናውናል፡፡

7. <u>ካፒታል</u>

ለኮርፖሬሽኑ የተፈቀደ ካፒታል ብር 16, 700, 000,000(አሥራ ስድስት ቢሊዮን ሰባት መቶ ሚሊዮን ሲሆን ከዚህ ውስጥ የተከፈለው ካፒታል ብር 4,175,000,000 (አራት ቢሊዮን አንድ መቶ ሰባ አምስት ሚሊዮን በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል፡፡

8. <u>ኃላፊነት</u>

ኮርፖሬሽኑ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

9. <u>ኮርፖሬሽኑ የሚቆይበት ጊዜ</u>

ኮርፖሬሽኑ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

10. <u>የተሻሩ ደንቦች</u>

የኢትዮጵያ የማዕድን፣ ነዳጅና ባዮፊዩል ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 367/2008 (እንደተሻሻለ በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

11. <u>መብቶችና ግዴታዎች</u>

መተላለፍ የሚከተሉት የመንግሥት ልማት ድርጅቶች መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለኮርፖሬሽኑ ተላልፈዋል:-

1. በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 367/2008 (እንደተሻሻለ ተቋቁሞ የነበረው የኢትዮጵያ ማዕድን፥፣ ነዳጅና ባዮፊዩልኮርፖሬሽን፤
2. የአዶላ ወርቅ ልማት ድርጅት፤

12. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ የካቲት 3 ቀን 2012 ዓ.ም**

**አብይ አህመድ ዶ/ር**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**3/ ለኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ የመንግስት ልማት ድርጅቶችን ማቋቋሚያ ህጎች**

**ደንብ ቁጥር 177/2002**

**የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ፓርክ ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ**

**የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 471/1998 አንቀጽ 5 እና በመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 አንቀጽ 47(1(ሀ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ፓርክ ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 177/2002" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**

   1. የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ፓርክ ኮርፖሬሽን (ከዚህ በኋላ "ኮርፖሬሽን" እየተባለ የሚጠራ የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡
   2. ኮርፖሬሽኑ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ተቆጣጣሪ ባለስልጣን**

   የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር[96] የኮርፖሬሽኑ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል፡፡

4. **ዋና መሥሪያ ቤት**

   የኮርፖሬሽኑ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

5. **ዓላማ**

   ኮርፖሬሽኑ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡

   1. የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ፓርክ ማልማትና ማካሄድ፤
   2. ከኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ፓርክ ጋር የተያያዙ አገልግሎቶችን መስጠት፡

---

[96] በ25)08 (2011 አ. 1097 አንቀጽ 36(6 የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚንስቴር ሆኗል፡፡

6. <u>ካፒታል</u>

ለኮርፖሬሽኑ የተፈቀደው ካፒታል ብር 5,000,000,000.00 (አምስት ቢሊዮን ብር ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 4,200,000,000.00 (አራት ቢሊዮን ሁለት መቶ ሚሊዮን ብር በጥሬ ገንዘብና በአይነት ተከፍሏል፡፡

7. <u>ኃላፊነት</u>

ኮርፖሬሽኑ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም።

8. <u>ኮርፖሬሽኑ የሚቆይበት ጊዜ</u>

ኮርፖሬሽኑ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

9. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት 13 ቀን 2002 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 197/2003

## የኢትዮ-ቴሌኮም ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 አንቀጽ 47 (1 (ሀ መሠረት ይህን ደንብ አዉጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የኢትዮ-ቴሌኮም ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 197/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**

   1. ኢትዮ-ቴሌኮም (ከዚህ በኃላ "ቴሌኮም" እየተባለ የሚጠራ የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቋሟል፡፡
   2. ቴሌኮሙ በመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 መሠረትይተዳደራል፡፡

3. **ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን**

   በመንግስት የሚሰየም አካል የቴሌኮሙ ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ይሆናል፡፡

4. **ዋና መስሪያ ቤት**

   የቴሌኮሙ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች እንደአስፈላጊነቱ በማናቸዉም ሥፍራ ሊኖረዉ ይችላል፡፡

5. **ዓላማ**

   ቴሌኮሙ የተቋቋመባቸዉ ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸዉ፡-

   1. በቀጣይ ትዉልድ ኔትወርክ ቴክኖሎቺ ላይ ተመስርቶ ዓለም አቀፍ ደረጃዉን የጠበቀ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎትን መስጠትና ማዳረስ፤
   2. የሚቀጥለዉ ትዉልድ ኔትወርክ ቴክኖሎጂ ላይ ተመስርቶ ዓለም አቀፍ ደረጃዉን የጠበቀ የቴሌኮም አገልግሎት መስጠት የሚችል በዕዉቀቱ፣ በችሎታዉ፣ በሥራዉ ዝንባሌውና ባህሉ ብቁና ተስማሚ የሆነ የሰዉ ኃይል መገንባት፤

3. የመንግሥት የልማት ፖሊሲና ቅድሚያ ትኩረት መሰረት በማድረግ የቴሌኮሙኒኬሽን አገለግሎቶችንና ኔትዎርክ ማቋቋም፣ማካሄድ፣ መጠገንና ማስፋፋት፤
4. የሀገር ዉስጥና ዓለም አቀፍ የድምጽ፣ የዳታ፣ የቪዲዮ እና ሌሎች ተዛማጅ ተጨማሪ አገልግሎቶችን መስጠት፤
5. የቴሌቪዥን ፕሮግራሞችን ተቀብሎ ማስተላለፍን ጨምሮ በተቀናጀ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በመደገፍ የሚሰጡ የኮሙኒኬሽን አገልግሎቶችን መስጠት፤
6. የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የሚያወጣዉን መመሪያና የፖሊሲ አቅጣጫ መሠረት በማድረግ ቦንድ መሸጥና በዋስትና ማስያዝ እና ከሀገር ዉስጥና ከዉጭ የገንዘብ ምንጮች ጋር የብድር ዉል መደራደርና መፈራረም፤
7. ዓላማዉን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ የሆኑ ሥራዎችን ማካሄድ፡፡

6. <u>ካፒታል</u>

ለቴሌኮሙ የተፈቀደለት ካፒታል ብር 40,000,000,000 (አርባ ቢሊዮን ብር ሲሆን ከዚህ ዉስጥ ብር 20,200,000,000 (ሃያ ቢሊዮን ሁለት መቶ ሚሊዮን ብር በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል፡፡

7. <u>የኃላፊነት መጠን</u>

ቴሌኮሙ ካለዉ ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

8. <u>ቴሌኮሙ የሚቆይበት ጊዜ</u>

ቴሌኮሙ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

9. <u>የተሻረ ደንብ</u>

የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 10/1989 (በደንብ ቁጥር 93/1996 እንደተሻሻለ በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

10. <u>የመብትና ግዴታ መተላለፍ</u>

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 10/1989 ተቋቁሞ የነበረዉ የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለቴሌኮሙኒኬሽን ተላልፏል፡፡

11. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ ከህዳር 20 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥር 20 ቀን 2003 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስቴር**

4/ ለውሃ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ የመንግስት ልማት ድርጅቶች ማቋቋሚያ ህጎች

## ደንብ ቁጥር 302/2006
## የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ማቋቋሚያ
## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 አንቀጽ 47(1 (ሀ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 302/2006" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**

   1. የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል (ከዚህ በኋላ "ድርጅት" እየተባለ የሚጠራ የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. ድርጅቱ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን**

   የውኃ፣ የመስኖ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል፡፡

4. **ዋና መሥሪያ ቤት**

   የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ሊኖረው ይችላል፡፡

5. **ዓላማ**[97]

   ድርጅቱ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

   1. ከብሔራዊ ግሪድ ጋር የተያያዙ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫዎች፣ ከ66 ኪሎቮልት በላይ የሆኑ ማስተላለፊያ መስመሮችና ማከፋፈያ ጣቢያዎች የግንባታ ሥራዎች የአዋጭነት ጥናት፣ የንድፍ እና የቅየሳ ሥራዎች ማከናወን፣ እንደአስፈላጊነቱ እነዚህኑ ሥራዎች በኮንሰልታንት ማሠራት፤

[97] በ22)52(2008 ደ. 381 አንቀፅ 2(1 ተሻሻለ፡፡

2. ከብሔራዊ ግሪድ ጋር የተያያዙ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫዎች፣ ከ 66 ኪሎ ቮልት በላይ የሆኑ ማስተላለፊያ መስመሮች እና ማከፋፈያ ጣቢያዎች የግንባታና የማሻሻያ ሥራዎችን ማከናወን፤ እንደአስፈላጊነቱ እነዚህኑ ሥራዎች በሥራ ተቋራጭ ማሠራት፤
3. ከብሔራዊ ግሪድ ጋር የተያያዙ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጪያ ጣቢያዎችን፣ ከ 66 ኪሎ ቮልት ኃይል በላይ የመሸከም አቅም ያላቸውን የኤሌክትሪክ ማስተላለፊያ መስመሮችን እና ማከፋፈያ ጣቢያዎችን ማስተዳደር፣ የኦፕሬሽን እና የጥገና ሥራዎችን ማከናወን፤
4. ከ66 ኪሎ ቮልት ደረጃ በላይ በሆኑ መስመሮች የኤሌክትሪክ ኃይልን በጅምላ መሸጥ እና መግዛት፤
5. ከ66 ኪሎ ቮልት በላይ የሆኑ የኃይል ማስተላለፊያ መስመሮችን ሊዝ ማድረግ፤
6. የሚሸጠውን የኤሌክትሪክ ኃይል በተመለከተ የታሪፍ ማሻሻያ ሀሳብ ማቅረብ፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ማድረግ፤
7. የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የሚያወጣውን መመሪያና የፖሊሲ አቅጣጫ መሠረት በማድረግ ቦንድ መሸጥና በዋስትና ማስያዝ እና ከአገር ውስጥ፣ ከውጭ የገንዘብ ምንጮች ጋር የብድር ውል መደራደርና መፈራረም፤
8. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ የሆኑ ሥራዎችን ማካሄድ፡፡

6. <u>**ካፒታል**</u>[98]

ለድርጅቱ የተፈቀደው ካፒታል ብር 120,000,000,000 (አንድ መቶ ሃያ ቢሊዮን ብር ሲሆን ከዚህ ውስጥ 30,000,000,000 (ሰላሳ ቢሊዮን ብር በጥሬ ገንዘብ እና በአይነት ተከፍሏል፡፡

7. <u>**ኃላፊነት**</u>

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም።

8. <u>**ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ**</u>

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

9. <u>**የመብትና ግዴታ መተላለፍ**</u>

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 170/2002 እንደገና ተቋቁሞ የነበረው የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ከኃይል ማመንጫ፣ ማስተላለፊያ እና

[98]በ22)52(2008 ደ. 381 አንቀፅ 2(2 ተሻሻለ፡፡

ማከፋፈያ ጣቢያ ሥራዎቹ ጋር በቀጥታ የተያያዙ መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለድርጅቱ ተላልፈዋል፡፡

10. <u>**ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**</u>

ይህ ደንብ ከህዳር 30 ቀን 2006 ዓ. ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ታህሳስ 18 ቀን 2006 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስትር**

**ደንብ ቁጥር 303/2006**

**የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች**

**ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዉ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 አንቀጽ 47(1(ሀ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 303/2006" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**

   1. የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት (ከዚህ በኋላ "ድርጅት" እየተባለ የሚጠራ የመንግሥት ልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. ድርጅቱ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን**

   የውኃ፣ የመስኖ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል፡፡

4. **ዋና መሥሪያ ቤት**

   የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ሊኖረው ይችላል፡፡

5. **ዓላማ**[99]

   ድርጅቱ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

   1. ከብሔራዊ ግሪድ ጋር ያልተያያዙ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫዎች፣ እስከ 66 ኪሎ ቮልት ደረጃ ያሉ ማስተላለፊያና ማከፋፈያ ጣቢያዎች የግንባታ ሥራዎች የአዋጭነት ጥናት፣ የንድፍ እና የቅየሳ ሥራዎች ማከናወን፣ እንደአስፈላጊነቱ እነዚህኑ ሥራዎች በኮንሰልታንት ማሠራት፤
   2. ከብሔራዊ ግሪድ ጋር ያልተያያዙ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫዎች፣ እስከ 66 ኪሎ ቮልት ደረጃ ያሉ ማስተላለፊያ መስመሮች እና ማከፋፈያ ጣቢያዎች

---
[99] በ22)53(2008 ደ. 382 አንቀፅ 2(1 ተሻሻለ፡፡

የግንባታና የማሻሻያ ሥራዎችን ማከናወን እንደአስፈላጊነቱ እነዚህኑ ሥራዎች በሥራ ተቋራጭ ማሠራት፤

3. ከብሔራዊ ግሪድ ጋር ያልተያያዙ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨ ያ ጣቢያዎችን እስከ 66 ኪሎ ቮልት ኃይል የመሸከም አቅም ያላቸውን የኤሌክትሪክ ማስተላለፊያ እና ማከፋፊያ መስመሮችን እና ማከፋፊያ ጣቢያዎችን ማስተዳደር፣ የኦፕሬሽን እና የጥገና ሥራዎችን ማከናወን፤
4. የኤሌክትሪክ ኃይልን በጅምላ ገዝቶ እስከ 66 ኪሎ ቮልት ደረጃ ባሉ መስመሮች መሸጥ፤
5. እስከ 66 ኪሎ ቮልት ደረጃ ያሉ የኃይል ማስተላለፊያ መስመሮችን ሊዝ ማድረግ፤
6. የአገር አቀፍ ኤሌክትሪክ ማስፋፊያ ሥራዎችን ማከናወን፤
7. የሚሸጠውን የኤሌክትሪክ ኃይል በተመለከተ የታሪፍ ማሻሻያ ሀሳብ ማቅረብ፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ማድረግ፤
8. የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የሚያወጣውን መመሪያና የፖሊሲ አቅጣጫ መሠረት በማድረግ ቦንድ መሸጥና በዋስትናማስያዝ እና ከአገር ውስጥ፣ ከውጭ የገንዘብ ምንጮች ጋር የብድር ውል መደራደርና መፈራረም፤
9. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ የሆኑ ሥራዎችን ማካሄድ፡፡

6. **ካፒታል**[100]

ለድርጅቱ የተፈቀደው ካፒታል ብር 60,000,000,000 (ስልሳ ቢሊዮን ብር ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 15,000,000,000 ( አሥራ አምስት ቢሊዮን ብር በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል፡፡

7. **ኃላፊነት**

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም።

8. **ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ**

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

9. **የተሻረ ደንብ**

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እንደገና ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 170/2002 በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

10. **የመብትና ግዴታ መተላለፍ**

[100]በ22)53(2008 ደ. 382 አንቀፅ 2(2 ተሻሻለ፡፡

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 170/2002 እንደገና ተቋቁሞ የነበረው የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን መብቶችና ግዴታዎች ከኃይል ማመንጫ፣ ማስተላለፊያና ማከፋፈያ ጣቢያ ሥራዎቹ ጋር በቀጥታ የተያያዙትን መብቶችና ግዴታዎች ሳይጨምር በዚህ ደንብ ለድርጅቱ ተላልፈዋል፡፡

11. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ.</u>

ይህ ደንብ ከህዳር 30 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ታህሳስ 18 ቀን 2006 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስቴር**

## 5) ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ የመንግስት ልማት ድርጅቶች ማቋቋሚያ ህጎች

### ደንብ ቁጥር 328/2006
### የኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ግብዓቶች ልማት ድርጅት ማቋቋሚያ
### የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን ባወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 አንቀጽ 47(1 (ሀ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ግብዓቶች ልማት ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 328/2006" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**

   1. የኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ግብዓቶች ልማት ድርጅት (ከዚህ በኋላ "ድርጅት" እየተባለ የሚጠራ የመንግሥት የልማት ድርጅት፡ ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡
   2. ድርጅቱ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን**

   የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል፡፡

4. **ዋና መሥሪያ ቤት**

   የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማንኛውም ሥፍራ በአገር ውስጥ ወይም በውጭ አገር ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

5. **አላማ**

   ድርጅቱ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

   1. የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን አቅርቦት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ድርጅቶችን መገንባት፣ ማስተዳደር እንዲሁም አስፈላጊ ሲሆን ማስተላለፍ፤
   2. በአገር ውስጥ እና በውጭ አገር የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን በማምረት ማቅረብ፤
   3. የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን ከአገር ውስጥና ከውጭ አገር በመግዛት ማቅረብ፤

4. ከአገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች ፍጆታ በላይ የሆኑትን የኢንዱስትሪ ግብዓቶች ወደ ውጭ አገር መላክ፤
5. የኢንዱስትሪ ግብዓቶች ልማት እና ጥሬ ዕቃ በማቅረብ ከተሰማሩ ድርጅቶች ጋር በጋራ መስራት፤
6. ቀልጣፋና ውጤታማ የኢንዱስትሪ ግብዓቶች ልማት ለማረጋገጥ የሚያስችል ጠንካራ የአቅርቦት ሰንሰለት ማኔጅመንት መተግበር፤
7. ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው በአገር ውስጥና በውጭ አገር ከሚገኙ የግልና የመንግስት ተቋማት ጋር ትብብር ማድረግ፤
8. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር[101] የሚያወጣውን እና የፖሊሲ አቅጣጫ መሠረት በማድረግ ቦንድ የመሸጥና በዋስትና የማስያዝ እና ከአገር ውስጥና ከውጭ የገንዘብ ምንጮች ጋር የብድር ውል የመደራደርና የመፈራረም፤
9. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ የሆኑ ሥራዎችን ማከናወን፡

6. <u>ካፒታል</u>

ለድርጅቱ የተፈቀደዉ ካፒታል ብር 3,900,612,520 (ሶስት ቢሊዮን ዘጠኝ መቶ ሚሊዮን ስድስት መቶ አስራ ሁለት ሺ አምስት መቶ ሃያ ብር ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 1,306,042,415 (አንድ ቢሊዮን ሦስት መቶ ስድስት ሚሊዮን አርባ ሁለት ሺ አራት መቶ አሥራ አምስት ብር በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል፡፡

7. <u>ኃላፊነት</u>

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም።

8. <u>ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ</u>

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

9. <u>የተሻረ ደንብ</u>

የሸቀጦች ጅምላ ንግድና አስመጪ ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 103/1985 በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

10. <u>የመብትና ግዴታዎች መተላለፍ</u>

[101] በ22)12 (2008 አ. 916 አንቀጽ 9(6 መሰረት የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሆኗል፡፡

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 103/1985 ተቋቁሞ የነበረው የሸቀጦች ጅምላ ንግድና አስመጪ ድርጅት መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለድርጅቱ ተላልፈዋል፡፡

11.<u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

የዚህ ደንብ አንቀጽ 9 ድንጋጌ ቢኖርም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 285/2005 የተቋቋመው የኢትዮጵያ ንግድ ድርጅት ዓላማውን በአግባቡ ተግባራዊ እስከሚያደርግ ድረስ በሸቀጦች ጅምላ ንግድና አስመጪ ድርጅት ዓላማ የተመለከቱ ተግባራትን ድርጅቱ እያከናወነ ይቆያል፡፡

12.<u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ታህሳስ 22 ቀን 2006 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስትር**

## <u>ደንብ ቁጥር 196/2003</u>

## <u>የኢትዮጵያ የተስማሚነት ምዘና ድርጅትን ማቋቋሚያ</u>

## <u>የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 አንቀጽ 47(1(ሀ መሠረት ይህን ደንብ አዉጥቷል፡፡

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

   ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 196/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. <u>መቋቋም</u>

   1. የኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት(ከዚህ በኃላ “ድርጅት” እየተባለ የሚጠራ የመንግስት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቋሟል፡፡
   2. ድርጅቱ በመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. <u>ተቆጣጣሪ ባለስልጣን</u>

የሳይንስና ቴክኖሎቺ ሚኒስቴር[102] የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ይሆናል፡፡

4. <u>ዋና መሥሪያ ቤት</u>

የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸዉም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊያቋቁም ይችላል፡፡

5. <u>ዓላማ</u>

ድርጅቱ የተቋቋመባቸዉ ዓላማዎች ብቃት ያለዉ የሰርተፊኬሽን፣ የኢንስፔክሽንና የላቦራቶሪ ፍተሻ አገልግሎቶችን በማደራጀት፡-

   1. አምራች ድርጅቶች ወይም አገልግሎት ሰጪዎች አግባብነት ያላቸዉን ብሄራዊ ወይም ዓለም ዓቀፍ ደረጃዎችንና ሕጋዊ መስፈርቶችን ማሟላታቸዉን በመመርመር የተስማሚነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የመስጠት፤
   2. የሀገሪቱ የወጪ ምርቶች የኢትዮጵያ ደረጃዎችን ወይም ዓለም ዓቀፍ ወይም የሌሎች ሀገሮች ደረጃዎችንና ሕጋዊ መሥፈርቶችን ማሟላታቸዉን በመመርመር የተስማሚነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የመስጠት፤
   3. ከዉጭ የሚገቡ ምርቶች አግባብነት ያላቸዉን ብሔራዊ ወይም ዓለም አቀፍ ደረጃዎችንና ሕጋዊ መሥፈርቶችን ያሟሉ መሆኑን በመመርመር የተስማሚነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የመስጠት፤
   4. የሚሰጠዉ የላቦራቶሪ ፍተሻ አገልግሎት ዉጤታማ መሆኑን ለማረጋገጥ ከሌሎች ብሔራዊ ፣አህጉራዊ እና ዓለም ዓቀፍ የላቦራቶሪ ፍተሻ ተቋማት ጋር የፍተሻ ዉጤትን የርስ በርስ ንፅፅር በማድረግ የማረጋገጥ ፕሮግራም ላይ የመሳተፍ፡፡
   5. ዓላማዉን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግብራትን የማከናወን፡፡

6. <u>ካፒታል</u>

ለድርጅቱ የተፈቀደዉ ካፒታል ብር 543,000,000 (አምስት መቶ አርባ ሦስት ሚሊዮን ብር ሲሆን ከዚህም ዉስጥ ብር 135,646,733.53 (አንድ መቶ ሠላሳ

[102] በ25)08 (2011 አ. 1097 አንቀጽ33(10(ጎ ተጠሪነቱ ለ ንግድና ኢንደስትሪ ሚንስቴር ሆኗል፡፡

አምስት ሚሊዮን ስድስት መቶ አርባ ስድስት ሺ ሰባት መቶ ሠላሳ ሦስት ብር ከሃምሳ ሦስት ሣንቲም በጥሬ ገንዘብና በአይነት ተከፍሏል፡፡

7. **<u>ኃላፊነት</u>**

ድርጅቱ ካለዉ ጠቅላላ ንብረት በላይ በእዳ ተጠያቂ አይሆንም

8. **<u>ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ</u>**

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

9. **<u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥር 24 ቀን 2003 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስቴር**

**ደንብ ቁጥር 331/2007 ዓም**

## የኢትዮጵያ የግብርና ምርቶች የመጋዘን አገልግሎት ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 አንቀጽ 47(1 (ሀ መሰረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርእስ**

   ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ የግብርና ምርቶች የመጋዘን አገልግሎት ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 331/2007" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**

   1. የኢትዮጵያ የግብርና ምርቶች የመጋዘን አገልግሎት ድርጅት (ከዚህ በኋላ "ድርጅቱ" እየተባለ የሚጠራው የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. ድርጅቱ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ተቆጣጣሪ ባለስልጣን**[103]

   የንግድ ሚኒስቴር የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል፡፡

4. **ስለኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን ኃላፊነት**

   የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን የግብይት ሥርዓቱን ደህንነት ለማረጋገጥ በማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 551/1999 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የድርጅቱን አሠራር ይቆጣጠራል።

5. **ዋና መስሪያ ቤት**

   የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማንኛውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

6. **ዓላማ**

[103]በ22)76(2008 ደ. 387 አንቀፅ 2(1 ተሻሻለ፡፡

የድርጅቱ ዓላማ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ግብይት ለሚካሄድባቸው የግብርና ምርቶች የመጋዘን አገልግሎት መስጠት ሲሆን በተለይ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1. ስትራቴጂያዊ በሆኑ የአገሪቱ አካባቢዎች ዘመናዊ እና በቴክኖሎጂ የተደገፉ የምርት ማከማቻ መጋዘኖች መገንባትና ማስተዳደር፤
2. ምርቶችን በመቀበል ደረጃ ሰጥቶና መዝኖ በመጋዘን ሥርዓት ማከማቸት የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ መስጠት እና ምርትን ማስረከብ፤ እንዲሁም ዘመናዊ የሆነ የንብረት አስተዳደር ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረግ፤
3. በኢትዮጵያ ምርት ገበያ የወጡትን ደረጃዎች መሠረት በማድረግ የምርቶችን የጥራት ደረጃ የመወሰን ሥራ ማከናወን፤
4. በኤሌክትሮኒክ የተደገፈ ዘመናዊ፣ ቀልጣፋና የተማከለ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ ሥርዓት መዘርጋትና ማስተዳደር ፤
5. በተገቢ የምርት ጥራት ቁጥጥር የሚመራ በምርት ደረጃ ላይ የተመሠረተ የክምችት ሥርዓት ተግባራዊ ማድረግ፤
6. ለመረጃ አመዘጋገብ፣ ለቁጥጥር፣ ለመረጃ መለዋወጫ፣ለሪፖርት ማስተላለፊያ የሚያገለግል እና ከተለያዩ የስራ ማከናወኛ ጣቢያዎች ጋር ያተያያዘ ደህንነቱ የተጠበቀ የኤሌክትሮኒክ የመረጃ መለዋወጫ ሥርዓትን መዘርጋትና መጠቀም፤
7. የተረከባቸውን፣ ያስረከባቸውንና በመጋዘን የቀሩትን ምርቶች በመጠን፣ በዓይነት እና በደረጃ መለየት የየእለቱን ሁኔታ የሚያሳይ መረጃን ጨምሮ በማንኛውም ጊዜ የተሟላ መረጃ መያዝና ደህንነቱ የተጠበቀ ቦታ ማስቀመጥ፤
8. ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች ክፍያ ማስከፈል፤
9. የጥራት ደረጃን አስመልክቶ የሚነሱ ቅሬታዎች የሚስተናገዱበትና ውሳኔ የሚያገኙበት የቅሬታ መፍቻ ሥርዓት እና የአደጋ መከላከያ አስተዳደር ሥርዓትን በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረግ፤
10. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎችን ማከናወን፡፡

7. <u>ካፒታል</u>

ለድርጅቱ የተፈቀደው ካፒታል ብር 1,000,000,000.00 ብር (አንድ ቢሊዮን ብር ሲሆን ከዚህ ውስጥ 250,000,000.00 ብር (ሁለት መቶ አምሳ ሚሊዮን ብር በጥሬ ገንዘብ እና በዓይነት ተከፍሏል።

8. <u>ኃላፊነት</u>

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በእዳ ተጠያቂ አይሆንም።

9. <u>ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ</u>

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል።

10. <u>መብትና ግዴታን ስለማስተላለፍ</u>

በአዋጅ ቁጥር 550/1999 የተቋቋመው የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ከመጋዘን አገልግሎት ጋር የተያያዙ መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለድርጅቱ ተላልፈዋል።

11. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

በዚህ ደንብ መሠረት ድርጅቱ በሙሉ አቅሙ አገልግሎት መስጠት እስኪችል የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ከመጋዘን አገልግሎት ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ዙሪያ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፡፡

12. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>[104]

ይህ ደንብ ከጥቅምት 1 ቀን 2008 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥር 6 ቀን 2007 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስትር**

[104]በ22)76(2008 ደ. 387 አንቀፅ 2(2 ተሻሻለ፡፡

## ደንብ ቁጥር 369/2008

## የኢትዮጵያ የንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽንን ማቋቋሚያ

## የሚኒስትሮች ምክርቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክርቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀጽ 5 እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 አንቀጽ 47(1 መሠረት ይህን ደንብ አዉጥቷል፡ ፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ የንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክርቤት ደንብ ቁጥር 369/2008" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**

   1. የኢትዮጵያ የንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን (ከዚህ በኋላ "ኮርፖሬሽን" እየተባለ የሚጠራ የፌደራል መንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል
   2. ኮርፖሬሽኑ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ተቆጣጣሪ ባለስልጣን**

   የንግድ ሚኒስቴር የኮርፖሬሽኑ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል፡፡

4. **ዋና መሥሪያ ቤት**

   የኮርፖሬሽኑ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በሌሎች የአገሪቱ ክፍልች ቅርንጫፍ ሊኖረዉ ይችላል፡፡

5. **ዓላማ**

   ኮርፖሬሽኑ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው:-

   1. የተመረጡ የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርቶችንና፣ መሠረታዊ ሸቀጦችን ከአገር ውስጥ እና ከውጭ አገር በተወዳዳሪ ዋጋ ገዝቶ በማሠራጨት የአገር ውስጥ ገበያን ማረጋጋት፤
   2. ሰብል፣ አትክልት እና ፍራፍሬ በተመረጠ አኳኋን ማስመረት፣ መግዛትና ማሰራጨት፣ ክምችት መያዝ፣ ለሀገር ውስጥና ለውጪ ገበያ ማቅረብ፤
   3. በወቅታዊ የገበያ መረጃ ላይ ተመሥርቶ የሀገር ውስጥና የውጪ ሀገር ግዥዎችን መፈፀምና መሸጥ፤

4. የአርሶ አደሩ የማምረት ፍላጎት እንዲያድግ ለግብርና ምርቶች አስተማማኝ ገበያ እንዲፈጠር እገዛ ማድረግ፤
5. ዘመናዊ፣ ቀልጣፋ፣ ውጤታማ እና ኃላፊነትና ተጠያቂነት የሠፈነበት የግብይት አሠራር መዘርጋትና መፈፀም፤
6. ሥራው የሚፈልገውን የሰለጠነ የሰው ኃይል በሚፈለገው ዓይነት፣ መጠንና ጥራት ማፍራት እንዲቻል ከሚመለከታቸው የምርምር፣ የትምህርትና የስልጠና ተቋማት ጋር መተባበር፤
7. የሀገር ውስጥና አለም አቀፍ ግዥዎችን በሚመለከት የምክር አገልግሎት መስጠት፣ የውክልና ግዢ መፈፀምና ሥልጠና መስጠት፤
8. የገንዘብና የኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ቦንድ የመሸጥ፣ የመግዛት፣ በዋስትና የማስያዝ፤ ከሀገር ውስጥና ከውጭ የገንዘብ ምንጮች ጋር የብድር ውል መደራደርና ሲፈቀድም ተግባራዊ ማድረግ፤
9. ከተቆጣጣሪው ባለስልጣን በሚሰጠው አቅጣጫ ላይ በመመሥረት በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ተወዳዳሪና አትራፊ ሆኖ እንዲንቀሳቀስ እገዛ የሚያደርጉለትን የሰው ኃብት፣ የፋይናንስ፣ የቴክኖሎጂና የዘመናዊ ስራ አመራር ግብዓቶችን ለማግኘት የሚያስችለው ኢንቨስትመንት መሳብም ሆነ በኢንቨስትመንት ላይ መሳተፍን ጨምሮ ጥናት በማካሄድ ሲፈቀድ ተግባራዊ ማድረግ፤
10. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎችን መሥራት፡፡

6. <u>ካፒታል</u>

የኮርፖሬሽኑ የተፈቀደ ካፒታል ብር 3,836,000,000.00 (ሦስት ቢሊየን ስምንት መቶ ሠላሳ ስድስት ሚሊዮን ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ብር 959,100,000.00 (ዘጠኝ መቶ ሃምሳ ዘጠኝ ሚሊዮን አንድ መቶ ሺ ብር በጥሬ ገንዘብና በአይነት ተከፍሏል

7. <u>ኃላፊነት</u>

ኮርፖሬሽኑ ካለዉ ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

8. <u>ኮርፖሬሽኑ የሚቆይበት ጊዜ</u>

ኮርፖሬሽኑ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

9. <u>የተሻሩ ደንቦች</u>

የሚከተለት ደንቦች በዚህ ደንብ ተሸረዋል:-

1. የኢትዮጵያ ንግድ ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 285/2005 ተቋቁሞ የነበረዉ የኢትዮጵያ ንግድ ድርጅት፣

2. የግዥ አገልግሎት ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 46/1991፣
3. የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 58/1992

10. <u>መብትና ግዴታዎች መተላለፍ</u>

የሚከተሉት የመንግስት የልማት ድርጅቶች መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለኮርፖሬሽኑ ተላልፈዋል:-

1. በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 285/2005 ተቋቁሞ የነበረው የኢትዮጵያ ንግድ ድርጅት፣
2. በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 46/1991 ተቋቁሞ የነበረው የግዥ አገልግሎት ድርጅት፣
3. በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 58/1992 ተቋቁሞ የነበረው የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት፣
4. በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 131/1986 ተቋቁሞ እንደገና ሰኔ 19/1994 እንደ አክስዮን ማህበር ተቋቁሞ የነበረው የኢትዮጵያ አትክልትና ፍራፍሬ ገበያ አክሲዮን ማህበር፡፡

11. <u>ደንቡ የሚጸናት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከተወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ታህሳስ 12 ቀን 2008**

**ኃለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስትር**

## 6) ለአገር መከላከያ ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ የመንግስት ልማት ድርጅቶች ማቋቋሚያ ህጎች ደንብ ቁጥር 171/1986

### የብራና ማተሚያ ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የጠቅላይ ሚኒስትርንና የሚኒስትሮች ምክር ቤትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 2/1983 አንቀፅ 4/2/ እና በመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 አንቀፅ 47/1/ሀ/ መሰረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የብራና ማተሚያ ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 171/1986" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**

   1. ብራና ማተሚያ ድርጅት (ከዚህ በኃላ "ድርጅት" እየተባለ የሚጠራ የመንግስት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. ድርጅቱ በመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 መሰረት ይተዳደራል፡፡

3. **ተቆጣጣሪ ባለስልጣን**

   በመንግስት የሚሰየም አካል የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ይሆናል፡፡

4. **ዋና መስሪያ ቤት**

   የድርጅቱ ዋና መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ ይሆናል፡፡ እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ስፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

5. **ዓላማ**

   ድርጅቱ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች ሚከተሉት ናቸው፡፡

   1. ማናቸውም የህትመት ስራዎችን ማካሄድ፡፡
   2. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ስራዎችን ማካሄድ፡፡

6. **ካፒታል**

   ለድርጅቱ የተፈቀደው ካፒታል ብር 4,980,256.83 (አራት ሚለዮን ዘጠኝ መቶ ሰማንያ ሺ ሁለት መቶ ሃምሳ ስድስት ብር ከ ሰማንያ ሶስት ሳንቲም ሲሆን ይኸውም በጥሬ ገንዘብና በአይነት ተከፍሏል፡፡

7. **ኃላፊነት**

   ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

8. **ድርጅቱ የሚቆይበት ግዜ**

ድርጅቱ ላልተወሰነ ግዜ ይቆያል፡፡

9. <u>**መብትና ግዴታ ስለማስተላለፍ**</u>

ተራመድ ማተሚያ ቤት በመባል ይታወቅ የነበረው ድርጅት መብትና ግዴታ በዚህ ደንብ ለድርጅቱ ተላልፏል፡፡

10. <u>**ደንቡ የሚፀናበት ገዜ**</u>

ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ የካቲት 7 ቀን 1986 ዓ.ም**

**ታምራት ላይኔ**

**የኢትዮጵያ የሽግግት መንግስት**

**ጠቅላይ ሚኒስቴር**

**ደንብ ቁጥር 185/2002**

**የመከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ ማቋቋሚያ**

**የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 471/1998 አንቀፅ 5 እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 አንቀፅ 47(1(ሀ(መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የመከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር185/2002" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**

   1. የመከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ (ከዚህ በኋላ "ኢንተርፕራይዝ" እየተባለ የሚጠራ የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. ኢንተርፕራይዙ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን**

   የኢንተርፕራይዙ ተቆጣጣሪ ባለስልጣን የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ይሆናል፡፡

4. **ዋና መሥሪያ ቤት**

   የኢንተርፕራይዙ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ሊኖረው ይችላል፡፡

5. **ዓላማ**

   ኢንተርፕራይዙ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸዉ፡-

   1. በዋነኛነት የመከላከያን ግንባታ ፍላጎት ለማሟላት ማንኛውንም የመሠረተ ልማት ግንባታ ሥራ መሥራት፤
   2. በተጓዳኝ በሀገሪቱ የሚከናወኑ የመንገድ፣ የግድብ፣ የመስኖ፣ የሕንፃና ሌሎች የመሠረተ ልማት ግንባታ ሥራዎችን መሥራት፤
   3. ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተጓዳኝ ሥራዎችን መሥራት፡፡

6. **ካፒታል**

ለኢንተርፕራይዙ የተፈቀደው ካፒታል ብር 800,000,000.00(ስምንት መቶ ሚሊዮን ብር ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 276,438,724.00 (ሁለት መቶ ሰባ ስድስት ሚሊዮን አራት መቶ ሰላሳ ስምንት ሺ ሰባት መቶ ሃያ አራት ብር በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል፡፡

7. **ኃላፊነት**

ኢንተርፕራይዙ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም።

8. **ኢንተርፕራይዙ የሚቆይበት ጊዜ**

ኢንተርፕራይዙ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

9. **የተሻረ ደንብ**

የመከላከያ ኮንስትራክሽንና ኢንጂነሪንግ ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 148/2000 እና የቃሊቲ ኮንስትራክሽንና የኮንስትራክሽን ዕቃዎች ማምረቻ ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 149/2000 በዚህ ደንብ ተሽረዋል፡፡

10. **የመብትና ግዴታዎች መተላለፍ**

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 148/2000 ተቋቁሞ የነበረዉ የመከላከያ ኮንስትራክሽንና ኢንጂነሪንግ ድርጅት እንዲሁም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 149/2000 ተቋቁሞ የነበረዉ የቃሊቲ ኮንስትራክሽንና የኮንስትራክሽን ዕቃዎች ማምረቻ ድርጅት መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለኢንተርፕራይዙ ተላልፈዋል፡፡

11. **ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ 21 ቀን 2002 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 186/2002

## የመከላከያ ግንባታ ግብዓቶች ማምረቻ ድርጅት ማቋቋሚያ

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 471/1998 አንቀጽ 5 እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 አንቀጽ 47(1 (ሀ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የመከላከያ ግንባታ ግብዓቶች ማምረቻ ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 186/2002" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**

   1. የመከላከያ ግንባታ ግብዓቶች ማምረቻ ድርጅት (ከዚህ በኋላ "ድርጅት" እየተባለ የሚጠራ የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል ፡፡
   2. ድርጅቱ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 መሰረት ይተዳደራል፡፡

3. **ተቆጣጣሪ ባለስልጣን**

   የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ይሆናል፡፡

4. **ዋና መስሪያ ቤት**

   የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ሊኖረው ይችላል፡፡

5. **ዓላማ**

   ድርጅቱ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፦

   1. ለመከላከያ የመሠረተ ልማት ግንባታ የሚያገለግሉ የአርማታ ብረቶች፣ ስትራክቸራል ስቲል፣ የእንጨት ምርት ውጤቶች፣ የጠቅላላ ብረታ ብረት ሥራዎች፣ የኮንክሪት እና ሌሎች የግንባታ ዕቃዎችን ዘመናዊና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች በመጠቀም ማምረትና በተጓዳኝ ለገበያ ማቅረብ፤
   2. ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተጓዳኝ ሥራዎችን መሥራት፡፡

6. **ካፒታል**

   ለድርጅቱ የተፈቀደው ካፒታል ብር 500 ሚሊዮን (አምስት መቶ ሚሊዮን ብር ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 128 ሚሊዮን 341 ሺ 631 (አንድ መቶ ሃያ ስምንት

ሚሊዮን ሶስት መቶ አርባ አንድ ሺ ስድስት መቶ ሰላሳ አንድ ብር በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል፡፡

7. <u>ኃላፊነት</u>

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም።

8. <u>ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ</u>

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

9. <u>የተሻረ ደንብ</u>

የዝቋላ ስቲል ሮሊንግ ሚል ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 26/1990 በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

10. <u>የመብትና ግዴታ መተላለፍ</u>

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 26/1990 ተቋቁሞ የነበረው የዝቋላ ስቲል ሮሊንግ ሚልድርጅት መብትና ግዴታዎች በዚህ ድንብ ለድርጅቱ ተላልፈዋል፡፡

11. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ 7 ቀን 2002 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 187/2002

## የመከላከያ ኮንስትራክሽን ዲዛይን ድርጅት ማቋቋሚያ

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራስያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 471/1998 አንቀጽ 5 እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 አንቀጽ 47(1(ሀ መሠረት ይህን ደንብ አዉጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ “የመከላከያ ኮንስትራክሽን ዲዛይን ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 187/2002” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**

   1. የመከላከያ ኮንስትራክሽን ዲዛይን ድርጅት (ከዚህ በኋላ“ድርጅት” እየተባለ የሚጠራ የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. ድርጅቱ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን**

   የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ይሆናል፡፡

4. **ዋና መሥሪያ ቤት**

   የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች እንደአስፈላጊነቱ በማናቸዉም ስፍራ ሲኖረዉ ይችላል፡፡

5. **ዓላማ**

   ድርጅቱ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸዉ፡-

   1. በዋነኛነት የሀገሪቱን የመከላከያ ግንባታ ፍላጎት ለማሟላት ማንኛውንም የዲዛይን እና ኮንትራት አስተዳደር ሥራዎችን መሥራት፤
   2. በተጓዳኝ የመንገድ፣ የግድብ፣ የመስኖ፣ የሕንጻና ሌሎች የማማከር፣ የዲዛይንና የኮንትራት አስተዳደር ሥራዎች መሥራት፤
   3. ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተጓዳኝ ሥራዎችን መሥራት፡፡

6. <u>ካፒታል</u>

ለድርጅቱ የተፈቀደው ካፒታል 30,000,000( ሠላሳ ሚሊዮን ብር ሲሆን ከዚህ ውስጥ 11,575,000(አሥራ አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሰባ አምስት ሺ ብር በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል፡፡

7. <u>ኃላፊነት</u>

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

8. <u>ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ</u>

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

9. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ 21 ቀን 2002 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስቴር**

## ደንብ ቁጥር 464/2012 ዓ.ም

## የመከላከያ ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2011 አንቀጽ 5 እና 34 እንዲሁም በመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1974አንቀጽ 47 (1 መሰረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የመከላከያ ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 464/2012" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**

   1. የመከላከያ ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን (ከዚህ በኋላ "ኮርፖሬሽን" እየተባለ የሚጠራ ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግስት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. ኮርፖሬሽኑ በመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1974 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ተቆጣጣሪ ባለስልጣን**

የኮርፖሬሽኑ ተቆጣጣሪ ባለስልጣን የመከላከያ ሚኒስቴር ይሆናል፡፡

4. **ዋና መስሪያ ቤት**

የኮርፖሬሽኑ ዋና መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በሌሎች ስፍራዎች ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

5. **ዓላማ**

ኮርፖሬሽኑ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው:-

   1. የሀገሪቱን የመከላከያ አቅም ለማሳደግ የማምረቻ ኢንዱስትሪዎችን ዲዛይን ማድረግ፣ ማምረት፣ መትከልና ኮሚሽን በማድረግ ለምርት ማዘጋጀት፤
   2. ለመከላከያና ለፀጥታ ሀይሎች የሚያገለግሉ የጦር መሳሪያዎችን፣ ቀላልና ከባድ ተሽከርካሪዎችንና ታንኮችን፣ የውጊያ ትራንስፖርት አውሮፕላኖችንና ሄሊኮፕተሮችን ተተኳሾችን፣ መለዋወጫዎቻቸውንና አባሪ እቃዎችን፣ ወቅቱንና የወደፊት ፍላጎትን መሰረት ባደረገ መልኩ ዲዛይን በማድረግ፣ በማምረት፣ በመጠገን፣ በማደስ፣ በማሻሻል እንዲሁም በዘርፉ የማማከርና የማሰልጠን አገልግሎትን መስጠት ሽያጫቸውንም በአገር ውስጥና በውጭ ሀገር ማከናወን፤

3. ለመከላከያና ለጸጥታ ሀይሎች ከሚሰጡ አገልግሎቶችና ምርቶች ጋር ተያያዥነት ያላቸው ለሲቪል አገልግሎት የሚውሉ የካፒታል እቃዎችን፣ ኬሚካሎችን እና ደማሚቶችን፣ ለወታደራዊና ለሲቪል አገልግሎቶች የሚውሉ የአቪዬሺን ምርቶችን፣ የኤሌክትሮኒክስ፣ የኦፕትሮኒክስና የኤሌክትሮ መካኒካል ምርቶችን፣ ኢንዱስትሪያል ማሽኖችን፣ መለዋወጫዎቻቸውንና አባሪ እቃዎችን ማምረት፣ መግጣጠም፣ መጠገን፣ ማደስ፣ ማሻሻል እና ተያያዥ አገልግሎቶቻቸውን መስጠትና፣ ሽያጫቸውንም በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ማከናወን፤
4. ከሀገሪቱ የመከላከያ ሃይል ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ አንጻር በመንግስት ውሳኔና በጀት ሊሰሩ የሚችሉ ወቅታዊና ለሀገር የቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ ስራዎችን ማከናወን፣
5. በኮርፖሬሽኑ የሚመረቱ ምርቶችን ከአገር ውስጥ ፍጆታ አልፎ ኤክስፖርት ማድረግ ፤
6. አቅም ካላቸው የውጭ አገራት ኩባንያዎች ጋር በሽርክና በመስራት ጥራት ያላቸውን ምርቶች ማምረት፤
7. ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ስራዎችን መስራት፡፡

6. <u>የካፒታል</u>

ለኮርፖሬሽኑ የተፈቀደው ካፒታል መጠን ብር 8 ቢሊዮን (ስምንት ቢሊየን ብር ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 2,343,492,900.54(ሁለት ቢሊየን ሶስት መቶ አርባ ሶስት ሚሊየን አራት መቶ ዘጠና ሁለት ሺ ዘጠኝ መቶ ብር ከሃምሳ አራት ሳንቲም በጥሬ ገንዘብ እና በዓይነት ተከፍሏል፡፡

7. <u>ሀላፊነት</u>

ኮርፖሬሽኑ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በእዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

8. <u>የመብትና ግዴታዎች መተላለፍ</u>

በደንብ ቁጥር 186/2002 በብረታ ብረት ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን ስር የነበሩት ጋፋት አርማመንት፤ ሆሚቾ አሙኒሽን ኢንጂነሪንግ፣፤ ደጀን አቪየሽን ኢንጂነሪንግ እና የፌውል/ነዳጅ እና ፕሮፒላንት መብትና ግዴታቸው በዚህ ደንብ ወደ ኮርፖሬሽኑ ተዛውሯል፡፡

9. <u>ኮርፖሬሽኑ የሚቆይበት ጊዜ</u>

ኮርፖሬሽኑ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

10. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ የካቲት 12 ቀን 2012 ዓ.ም**

**አብይ አህመድ ዶ/ር**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 475/2013 ዓ.ም

## የኢትዮ-ኢንጂነሪንግ ግሩፕ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲዊ ሪፐብሊክ የፌደራል አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 1097/2011 አንቀፅ 5 እና

## የፍትህ ሚኒስቴር

በመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984፤ አንቀፅ 47 (1 (ሀ በተሠጠው ሥልጣን መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የኢትዮ-ኢንጂነሪንግ ግሩፕ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 475/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**

   1. የኢትዮ-ኢንጂነሪንግ ግሩፕ የፌደራል መንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. የኢትዮ-ኢንጂነሪንግ ግሩፕ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ተቆጣጣሪ ባለስልጣን**

የመንግስት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ የኢትዮ-ኢንጂነሪንግ ግሩፕ ተቆጣጣሪ ነው፡፡

4. **ዋና መሥሪያ ቤት**

የኢትዮ-ኢንጂነሪንግ ግሩፕ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በሌሎች የኢትዮጵያ ክፍሎች ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች መክፈት ይችላል፡፡

5. **ዓላማ**

የኢትዮ-ኢንጂነሪንግ ግሩፕ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

   1. ለአምራች ኢንዱስትሪዎች ፈጣን ልማት የሚያግዙ ተጨባጭና የወደፊት ፍላጐቶችን በማጥናትና በማልማት ምርትና አገልግሎት አሰጣጥን የሚያሳልጡ የሃይ-ቴክ ውጤቶችን ማምረት፣ የቴክኖሎጂ ሽግግርን ማፋጠንና አቅም ማጎልበት በሚያስችል መልኩ ከትምህርት ተቋማት ጋር ትስስር መፍጠር እና ከአገር ውስጥም ሆነ ከውጭ ተቋማት ጋር በአጋርነት መሥራት፤
   2. በኢትዮጵያ ሥነ-ሐብታዊና ማኀበራዊ ዕድገት ላይ አዎንታዊ አስተዋፅኦ ሊያበረክቱ የሚችሉና የገበያ ክፍተትን ለመሙላት የሚረዱ ልዩ ልዩ የካፒታል እና የፍጆታ ዕቃዎችን እና መለዋወጫዎችን ማምረት፣ መጠገን፣ ማደስና ማሻሻል፣
   3. የማምረቻ ወይም የአገልግሎት መስጫ ማዕከላትን (ፕላንት ዲዛይን ማድረግ፣ መገንባት፣ ቅድመ ምርት ሙከራ እና ፍተሻ (ኮሚሽኒንግ አገልግሎት መስጠት፣ መጠገን፣ ማደስና ማሻሻል፤

4. ምርትና አገልግሎቶቹን በአገር ውስጥና በውጪ አገራት መሸጥ እና የድህረ ሽያጭ አገልግሎቶችን መስጠት፤
5. የተሰማራበትን የማምረቻ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ትኩረት የሚያደርግ የአቅም ግንባታ ስልጠና እና የማማከር አገልግሎት በመስጠት በዘርፉ የሰው ኃይል ግንባታ ላይ አስተዋፅኦ ማድረግ፣
6. የገንዘብ ሚኒስቴር የሚሰጠውን የፖሊሲ አቅጣጫ እና የሚያወጣውን መመሪያ መሠረት በማድረግ ቦንድ መሸጥ፣ በዋስትና ማስያዝ፣ ከአገር ውስጥና ከውጭ አገር የገንዘብ ምንጮች የብድር ውል መደራደርና የመፈረም፤ እና
7. የተቋቋመበትን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉ ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎችን ማከናወን፡፡

6. <u>ካፒታል</u>

ለኢትዮ-ኢንጂነሪንግ ግሩፕ የተፈቀደው ካፒታል ብር 6 ቢሊዮን 765 ሚሊዮን 584 ሺህ 637.80 ሣንቲም (ስድስት ቢሊዮን ሰባት መቶ ስልሳ አምስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሰማንያ አራት ሺህ ስድስት መቶ ሰላሳ ሰባት ብር ከሳንቲም ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ብር 1 ቢሊዮን 691ሚሊዮን 396ሺህ 159.47ሣንቲም (አንድ ቢሊዮን ስድስት መቶ ዘጠና አንድ ሚሊዮን ሦስት መቶ ዘጠና ስድስት ሺህ አንድ መቶ ሀምሳ ዘጠኝ ብር ከ47ሣንቲም በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል፡፡

7. <u>ኃላፊነት</u>

የኢትዮ-ኢንጂነሪንግ ግሩፕ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

8. <u>የቆይታ ጊዜ</u>

የኢትዮ ኢንጂነሪንግ ግሩፕ ላልተወሰነ ጊዜ ተቋቁሟል፡፡

9. <u>በግሩፑ ሥር ስላሉ ድርጅቶች</u>

እንደ አስፈላጊነቱ በኢትዮ-ኢንጂነሪንግ ግሩፕ ሥር ያሉ ድርጅቶች የሕግ ሥርዓቱን ተከትለው በሂደት የራሳቸው የሕግ ሰውነት እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡

10. <u>የመብትና ግዴታዎች መተላለፍ</u>

1. በመከላከያ ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 464/2012 አንቀጽ መሠረት ባለቤትነታቸው ከብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን ወደ መከላከያ ኢንጂነሪን ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን የተዘዋወሩት አራት ኢንዱስትሪዎች እንደተጠበቁ ሆነው፤ በብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር

183/2002 መሠረት የተቋቋመው የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን መብቶችና ግዴታዎች በሙሉ በዚህ ደንብ ወደ ኢትዮ-ኢንጂነሪንግ ግሩፕ ተላልፈዋል፡፡

2. በመከላከያ ግንባታ ግብዓቶች ማምረቻ ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 186/2002 አንቀጽ 10 መሠረት መብትና ግዴታዎቹ ለመከላከያ ግንባታ ግብዓቶች ማምረቻ ድርጅት የተዘዋወረው የዝቋላ ስቲል ሮሊንግ ሚል ድርጅት መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ወደ ኢትዮ-ኢንጂነሪንግ ግሩፕ ተላልፈዋል፡፡

11.<u>የተሻሩ ደንቦች</u>

1. የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 183/2010 በዚህ ደንብ ተሽሯል፣
2. የመከላከያ ግንባታ ግብዓቶች ማምረቻ ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 186/2002 አንቀጽ 10 በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

12.<u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መስከረም 20 ቀን 2013 ዓ.ም**

**አብይ አህመድ ዶ/ር**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## 7) ለግብርና ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ የመንግስት ልማት ድርጅቶች ማቋቋሚያ ህጎች

### ደንብ ቁጥር 52/1991

### ብሔራዊ የእንስሳት ጤና ጥበቃ ኢንስቲትዩትን በልማት ድርጅትነት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 4/1987 አንቀጽ 5 እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/84 አንቀጽ 47(1 (ሀ መሠረት ይህን ደንብ አዉጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "ብሔራዊ የእንስሳት ጤና ጥበቃ ኢንስቲትዩትን በልማት ድርጅትነት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 52/1991" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**
   1. ብሔራዊ የእንስሳት ጤና ጥበቃ ኢንስቲትዩት (ከዚህ በኋላ "ኢንስቲቱዩቱ" እየተባለ የሚጠራ የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. ኢንስቲትዩቱ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/84 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን**

   በመንግሥት የሚሰየም አካል የኢንስቲትዩቱ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል ፡፡

4. **ዋና መሥሪያ ቤት፡**

   የኢንስቲትዩቱ ዋና መሥሪያ ቤት ደብረዘይት ሆኖ ፤ እንደአስፈላጊነቱ በማንኛውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል ፡፡

5. **አላማ**

   ኢንስቲትዩቱ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸዉ፡፡
   1. ለተለያዩ የእንስሳት በሽታዎች ዓለም አቀፍ ደረጃ ያላቸው ክትባቶች ማምረት፡
   2. ልዩ ልዩ የእንስሳት መድኃኒቶችን ማቀነባበርና ማዋሃድ፡
   3. ለምርትና ለእንስሳት በሽታ ምርምር ሥራ የሚያገለግሉ ባዮሎጂካሎችንና ሪኤጀንቶችን ማምረት ፡

4. ምርቶችን ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ አቅርቦት በመሸጥ ትርፍና ትርፋማነትን ማሣደግ፣
5. በተጨማሪም ሌሎች ተዛማጅ ምርቶችን ማምረት፡፡

6. **ካፒታል**

ለኢንስቲትዩቱ የተፈቀደው ካፒታል ብር 45,737,122 (አርባ አምስት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሰላሳ ሰባት ሺ አንድ መቶ ሃያ ሁለት ብር ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 40,189,122 (አርባ ሚሊዮን አንድ መቶ ሰማንያ ዘጠኝ ሺ አንድ መቶ ሃያ ሁለት ብር በዓይነትና በጥሬ ገንዘብ ተከፍሏል ፡፡

7. **የኃላፊነት ወሰን**

ኢንስቲትዩቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም ፡፡

8. **ኢንስቱትዩቱ የሚቆይበት ጊዜ**

ኢንስቲትዩቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል ፡፡

9. **ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ፡**

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሐምሌ 23 ቀን 1991 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስትር**

**8)ለትምህርት ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ የመንግስት የልማት ድርጅት ማቋቋሚያ ህጎች**

**ደንብ ቁጥር 50/1991 ዓ.ም**

**የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት ማቋቋሚያ**

**የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 4/1987 አንቀጽ 5 እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/ 1984 አንቀጽ 47(1 (ሀ መሠረት ይህን ደንብ አዉጥቷል፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 50/1991 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ ደንብ ውስጥ፡ “የትምህርት መሣሪያዎች” ማለት ለትምህርት መስጫ አገልግሎት የሚውሉ መጻሕፍት፡ ሥዕላዊ መግለጫዎች፣ ቻርቶች፡ ካርታዎች፣ የሳይንስ፡ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት መሣሪያዎች፡ የትምህርት ተቋማት ቁሳቁሶች ፈርኒቸር የኦዶቪዥዋል መሣሪያዎች ፡ የሕፃናት መጫወቻዎች ልዩ ልዩ ፎርሞችና ሌሎችም ለትምህርቱ ዘርፍ የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች ናቸዉ፡፡

3. **መቋቋም**

   1. የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት (ከዚህ በኋላ “ድርጅቱ” እየተባለ የሚጠራ የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. ድርጅቱ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 መሠረት ይተዳደራል ፡፡

4. **ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን**

   በመንግሥት የሚሰየም አካል የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል፡፡

5. **ዋና መሥሪያ ቤት**

   የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ይሆናል፡፡ እንደአስፈላጊነቱም በማንኛውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

6. **ዓላማ**

   1. የትምህርት መሣሪያዎችን ማምረት፣ ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገር ገዝቶ ማቅረብ፣
   2. የሥልጠናና የሙያ ምክር አገልግሎት መስጠት ፤

3. ትርፋማነትን ማሳደግና አስተማማኝ ገበያ መፍጠር ፤

4. ዓላማዎችን ከግቡ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎችን ማካሄድ ፡፡

7. **ካፒታል**

ለድርጅቱ የተፈቀደዉ ካፒታል ብር 150,000,000.00 (የአንድ መቶ ሃምሣ ሚሊዮን ብር ሲሆን ከዚህም ውስጥ ብር 110,668,702.74 (የአንድ መቶ አሥር ሚሊዮን ስድስት መቶ ስልሳ ስምንት ሺ ሰባት መቶ ሁለት ብር ከሰባ አራት ሣንቲምን በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል፡፡

8. **ኃላፊነት**

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

9. **ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ**

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

10. **መብትና ግዴታ**

ከአሁን ቀደም የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ይባል የነበረው ድርጅት መብትና ግዴታ በዚህ ደንብ ለድርጅቱ ተላልፉል፡፡

11. **ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሰኔ 15 ቀን 1991 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስትር**

## 9)ለጠቅላይ ሚኒስቴር ጽህፈት ቤት ተጠሪ  የሆኑ የመንግስት የልማት ድርጅት ማቋቋሚያ ህጎች

### ደንብ ቁጥር 265/2004

### የኢትዮጵያ የነዳጅ አቅራቢ ድርጅት ማቋቋሚያ

### የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር691/2003 አንቀጽ 5 እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 አንቀጽ 47(1(ሀ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ የነዳጅ አቅራቢ ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 265/2004" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**

   1. የኢትዮጵያ የነዳጅ አቅራቢ ድርጅት (ከዚህ በኋላ "ድርጅት" እየተባለ የሚጠራ የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. ድርጅቱ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **የተቆጣጣሪ ባለስልጣን**

   በመንግሥት የሚሰየም አካል የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል፡፡

4. **ዋና መሥሪያ ቤት**

   የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

5. **ዓላማ**

   ድርጅቱ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

   1. የሀገሪቱን የነዳጅ ፍላጎት በማጥናት የተጣራ የነዳጅ ምርት ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት እና የነዳጅ ድፍድፍ ወደ ሀገር አስገብቶ በማጣራት ለነዳጅ አከፋፋይ ኩባንያዎች ማቅረብ፤
   2. ሀገሪቱ የማያስፈልጋትን ብሔራዊ የመጠባበቂያ ነዳጅ መጠን ማቀድ፣ ማከማቸት፣ ክምችቱን ማስተዳደር እና ከመንግሥት፣ በሚሰጥ መመሪያ መሠረት ከክምችት ወጥቶ እንዲከፋፈል ማድረግ፤

3. በሀገር ዉስጥና እንደ አስፈላጊነቱ በጎረቤት ሀገሮች የራሱን የነዳጅ ማከማቻ ዴፖዎች መገንባት እና የነዳጅ ማከማቻ ዴፖዎች አገልግሎት በሚሰጡ ኩባንያዎች ዉስጥ ኢንቨስት ማድረግ፤
4. ዓላማዉን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ የሆኑ ሥራዎችን ማከናወን፡

6. **<u>ካፒታል</u>**

ለድርጅቱ የተፈቀደው ካፒታል ብር 2,000,000,000 (ሁለት ቢሊዮን ብር ሲሆን ከዚህ ዉስጥ ብር 500,000,000 ( አምስት መቶ ሚሊዮን ብር በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል፡፡

7. **<u>ኃላፊነት</u>**

ድርጅቱ ካለዉ ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም።

8. **<u>ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ</u>**

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

9. **<u>የተሻረ ደንብ</u>**

የኢትዮጵያ ነዳጅ ድርጅት ማቋቋሚያ የሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 210/1987 በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

10. **<u>ስለብሔራዊ የመጠባበቂያ ነዳጅ ዴፖዎች አስተዳደር መፍረስ</u>**

በአዋጅ ቁጥር 82/1989 ተቋቁሞ የነበረው ብሔራዊ የመጠባበቂያ ነዳጅ ዴፖዎች አስተዳደር የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 34 መሠረት በዚህ ደንብ ፈርሷል።

11. **<u>የመብቶችና ግዴታዎች መተላለፍ</u>**

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 210/1987 ተቋቁሞ የነበረው የኢትዮጵያ ነዳጅ ድርጅት እና በአዋጅ ቁጥር 82/1989 ተቋቋሞ የነበረው ብሔራዊ የመጠባበቂያ ነዳጅ ዴፖዎች አስተዳደር መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለድርጅቱ ተላልፈዋል፡፡

12. **<u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሰኔ 19 ቀን 2004**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስትር**

## 10/ ለገንዘብ ሚንስቴር ተጠሪ የሆኑ የመንግስት ልማት ድርጅቶች ማቋቋሚያ ህጎች

### ደንብ ቁጥር 201/1987

### የኢትዮጵያ መድን ድርጅትን ማቋቋሚያ የሚንስትሮች

### ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የጠቅላይ ሚኒስትርንና የሚኒስትሮች ምክር ቤትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 2/1983 አንቀጽ 4/2/ እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 አንቀጽ 46/1/ ሀ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፣

1. **አጭር ርዕስ፣**

   ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 201/1987" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም፣**

   1. የኢትዮጵያ መድን ድርጅት /ከዚህ በኋላ "ድርጅት" እየተባለ የሚጠራ/ የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. የመድን ሥራን የሚመለከቱ ሕጎች እንደተጠበቁ ሆኖ ድርጅቱ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **የተቆጣጣሪ ባለሥልጣን፣**

   በመንግሥት የሚሰየም አካል የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል፡፡

4. **ዋና መሥሪያ ቤት፣**

   የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ይሆናል፣ እንደአስፈላጊነቱም በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

5. **ዓላማዎች፣**

   ድርጅቱ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፣

   1. ማናቸውንም የመድን አገልግሎት መስጠት ሥራ መሥራት፣
   2. ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎችን ማካሄድ፣

6. **ካፒታል፣**

   ለድርጅቱት የተፈቀደው ካፒታል ብር 61,007,038 / ስልሳ አንድ ሚሊዮን ሰባት ሺህ ሰላሳ ስምንት ብር/ ሙሉ በሙሉ በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል፡፡

7. **ኃላፊነት፣**

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

8. <u>**ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ፣**</u>

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፣

9. <u>**መብትና ግዴታ ስለማስተላለፍ፣**</u>

በአዋጅ ቁጥር 88/1968 ተቋቁሞ የነበረው የኢትዮጵያ መድን ድርጅት መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለድርጅቱ ተላልፈዋል፡፡

10. <u>**ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ፣**</u>

ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መስከረም 9 ቀን 1987 ዓ.ም**

**ታምራት ላይኔ**

**የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት**

**ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 202/1987

## የኢትዮጵያ ንግድ ባንክን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የጠቅላይ ሚንስትርና የሚኒስትሮች ምክር ቤትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 2/1983 አንቀጽ 4/2/ እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 አንቀጽ 47 /1/ /ሀ/ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ፣**

   ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 202/1987" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም፣**

   1. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ (ከዚህ በኋላ "ባንክ" እየተባለ የሚጠራ የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. የገንዘብና የባንክ ሥራን የሚመለከቱ ሕጎች እንደተጠበቁ ሆነው ባንኩ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን፣**

   በመንግሥት የሚሰየም አካለ የባንኩ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል፡፡

4. **ዋና መሥሪያ ቤት፣**

   የባንኩ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ይሆናል፡፡ እንደአስፈላጊነቱም በማንኛውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

5. **ዓላማ፣**

   ባንኩ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

   1. የቁጠባ፣ በተጠየቀ ጊዜ የሚከፈልና የጊዜ ገደብ ያለው ተቀማጭ ገንዘብ መቀበል፣
   2. በኢትዮጵያ ውስጥ ወይም በውጭ ተከፋይ የሚሆኑ የሐዋላ ወረቀቶች፣ የገንዘብ ሰነዶችና የተስፋ ሰነዶች ማውጣት፣ መቀበል፣ በቅናሽ መውሰድ፣ መግዛትና መሸጥ፣
   3. የንግድ መተማመኛ ብድር ደብዳቤዎች መስጠት፣
   4. የአጭርና የመካከለኛ ጊዜ ብድሮችን መስጠት፣ ከተወሰነ ጣሪያ ሳያልፍ የረጅም ጊዜ ብድሮችን መስጠት፣
   5. የውጭ አገር ምንዛሪ መግዛትና መሸጥ፣

6. መንግሥት፣ የግል ድርጅት ወይም ማንኛውም ሰው የሚያወጣቸውን የሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶችና የዋስትና ሰነዶች መግዛትና መሸጥ፣
7. ሰነዶችን፣ ጌጦችንና ሌሎች ዋጋ ያላቸውን ነገሮች በአደራ መቀበልና ማኖር፣
8. ቼኮችና የመንገደኛ ቼኮች ማውጣትና በጠቅላላው በቼኮች መሥራት፣
9. ለሰዎች ወኪል ሆኖ ገንዘቦችና አክስዮኖች መሸጥ፣
10. በማናቸውም ኢንቨስትመንት የአክስዮን ድርሻ በመያዝ መሳተፍ፣
11. ሌሎች የተለመዱ የንግድ ባንክ ሥራዎችን ማከናወን፡፡

6. ካፒታል፣

ለባንኩ የተፈቀደው ካፒታል ብር 40,000,000,000 ቢሊዮን (አርባ ቢሊዮን ብር ሲሆን፣ ይኸዉ በጥሬ ገንዘብና በዓይነት በሙሉ ተከፍሏል፡፡[105]

7. ኃላፊነት፣

ባንኩ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

8. ባንኩ የሚቆይበት ጊዜ፣

ባንኩ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

9. መብትና ግዴታዎች ስለማስተላለፍ፣

በአዋጅ ቁጥር 184/1972 ተቋቁሞ የነበረው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለባንኩ ተላልፈዋል፡፡

10. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ፣

ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምር የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ፣ መስከረም 12 ቀን 1987 ዓ.ም**

**ታምራት ላይኔ**

**የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት ጠቅላይ ሚኒስትር**

[105] በ23) (2009 ደ. 397 አንቀፅ 2 ተሻሻለ፡፡

**ደንብ ቁጥር 83/1995**

**የኢትዮጵያ ልማት ባንክን እንደገና ለማቋቋም የወጣ**

**የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በኢ.ፌዴሪ ሕገ መንግሥት አዋጅ ቁጥር 1/1987 አንቀጽ 77/13/ እና የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 4/1987 አንቀጽ 5 እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 አንቀጽ 47/1/ሀ/ መሠረት ይህን ደንብ አዉጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ልማት ባንክን እንደገና ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 83/1995" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **እንደገና መቋቋም**

   1. የኢትዮጵያ ልማት ባንክ (ከዚህ በኋላ "ባንኩ" እየተባለ የሚጠራ የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ እንደገና ተቋቁሟል፡፡
   2. የገንዘብና የባንክ ሥራን የሚመለከቱ ሕጎች እንደተጠበቁ ሆኖ ባንኩ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን**

   በመንግሥት የሚሰየም አካል የባንኩ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል፡፡

4. **ዋና መሥሪያ ቤት**

   የባንኩ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ይሆናል፡፡ እንደአስፈላጊነቱም በማንኛውም ስፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረውይችላል።

5. **ተልዕኮ**

   ባንኩ የተቋቋመው የሃገሪቱን ልማት ለማፋጠን የሚያስችል የልማት ብድር አገልግሎት ለመስጠት ነው።

6. **የባንኩ ተግባርና ኃላፊነት**

   1. የኢንቨስትመንት ብድር የአጭር ጊዜ ብድርን ጨምሮ በአገሪቱ የኢኮኖሚ ልማት ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላላቸውና ውጤታማ ለሆኑ ፕሮጀክቶች መስጠት፤
   2. ከአገር ውስጥና ከውጭ ምንጭ ለልማት የሚውል ገንዘብ ማሰባሰብ፤
   3. የአደራ ገንዘብ ማስተዳደር፤

4. የአክሲዮን ድርሻ በመያዝ በኢንቨስትመንት መሳተፍ፤
5. ለተበዳሪዎቹ የሃገር ውስጥና የውጭ ሃገር የባንክ አገልግለት መስጠት፤
6. የጊዜ ገደብ ያለው ተቀማጭ ገንዘብ መቀበል፤
7. ለብድሮችና ለሌሎች መሰል የገንዘብ ግዴታዎች ዋስ መሆን፤
8. በኢትዮጵያ ዉስጥ ወይም ከኢትዮጵያ ዉጭ ተከፋይ የሚሆኑ የሐዋላ ወረቀቶች፤ የገንዘብ ሰነዶችና የተስፋ ሰነዶች ማውጣት፤መቀበል፤ በቅናሽ መውሰድ፣ መግዛትና መሸጥ፣
9. ቦንድ ማውጣትና መሸጥ፤
10. እንደ ባለአደራ ወይም እንደ ንብረት ተቀባይና ጠባቂ መስራት፤
11. የቴክኒክና የሥራ አመራር ምክር አገልግሎት መስጠት፤
12. በአገር ውስጥና በውጭ ባንኮች ሂሣብ መክፈትና ማንቀሳቀስ፤
13. ሌሎች የተለመዱ የልማት ባንክ ሥራዎችን ማከናወን።

7. <u>ካፒታል</u>

የባንኩ የተፈቀደ ካፒታል ብር 28 ቢሊዮን 520 ሚሊዮን ("ሀያ ስምንት ቢሊዮን አምስት መቶ ሀያ ሚሊዮን ሲሆን ይህ ካፒታል ሙሉ በሙሉ በጥሬ ገንዘብ እና ዓይነት ተከፍሏል፡፡[106]

8. <u>ኃላፊነት</u>

ባንኩ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

9. <u>ባንኩ የሚቆይበት ጊዚ</u>

ባንኩ ላልተወሰነ ጊዜ እንደገና ተቋቁሟል።

10. <u>መብትና ግዴታዎችን ስለማስተላለፍ</u>

በደንብ ቁጥር 200/1987 ተቋቁሞ የነበረው የኢትዮጵያ ልማት ባንክ መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለባንኩ ተላልፈዋል።

11. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥር 16 ቀን 1995 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

---

[106] በ26)54(2012 ደ.470 አንቀፅ 2 ተሻሻለ፡፡

11) **ለሆቴሎች እና ቱሪዝም ስራ ማሰልጠኛ ማዕከል ተጠሪ የሆኑ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ማቋቋሚያ ህጎች**

**ደንብ ቁጥር 175/2002 ዓ.ም**

**የገነት ሆቴል ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 471/1998 ዓ.ም አንቀጽ 5 እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 አንቀጽ 47(1 (ሀ መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርእስ**

   ይህ ደንብ "የገነት ሆቴል ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 175/2002" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**

   1. የገነት ሆቴል ድርጅት (ከዚህ በኋላ "ድርጅት" እየተባለ የሚጠራ የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. ድርጅቱ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ተቆጣጣሪ ባለስልጣን**

   የሆቴልና ቱሪዝም ስራ ማሰልጠኛ ማዕከል የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ይሆናል፡፡

4. **ዋና መስሪያ ቤት**

   የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

5. **ዓላማ**

   የድርጅቱ ዓላማ የሆቴልና ከሆቴል ጋር የተያያዙ የአገልግሎት ሥራዎችን መሥራትና ለሆቴልና ቱሪዝም ማሰልጠኛ በሞዴል ሆቴልነት ማገልገል ይሆናል፡፡

6. **ካፒታል**

   ለድርጅቱ የተፈቀደው ካፒታል ብር 40,000,000.00 ( አርባ ሚሊዮን ብር ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 9,926,713.00 (ዘጠኝ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሃያ ስድስት ሺ ሰባት መቶ አሥራ ሦስት ብር  በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል፡፡

7. <u>ኃላፊነት</u>

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም።

8. <u>ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ</u>

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል።

9. <u>የመብትና ግዴታዎች መተላለፍ</u>

የገነት ሆቴልን የሚመለከቱ የራስ ሆቴሎች ድርጅት መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለድርጅቱ ተላልፈዋል፡፡

10. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መጋቢት 8 ቀን 2002 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስቴር**

## 12) ለኢንቨስትመንት ኮሚሽን ተጠሪ የሆኑ የመንግስት የልማት ድርጅት ማቋቋሚያ ህጎች ደንብ ቁጥር 326/2007

### የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5፣ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 አንቀጽ 47(1(ሀ እና በኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 769/2004 አንቀጽ 35(1 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡ ፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 326/2007" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**

   1. የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን (ከዚህ በኋላ "ኮርፖሬሽኑ" እየተባለ የሚጠራ የፌደራል መንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. ኮርፖሬሽኑ በመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን**

   በመንግሥት የሚሰየም አካል የኮርፖሬሽኑ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል፡፡

4. **ዋና መሥሪያ ቤት**

   የኮርፖሬሽኑ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ የኢንዱስትሪ ፓርኮች በተቋቋሙባቸው ቦታዎች ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

5. **ዓላማ**

   ኮርፖሬሽኑ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸዉ፡፡

   1. የኢንዱስትሪ ፓርኮችን የማልማት፣የማስተዳደር፣የለማ ቦታ በሊዝ ማከራየት እና ግንባታዎችን የማከራየት ወይም በሽያጭ የማስተ ሳለፍ፤
   2. አገራዊ ስፓሻል ማስተር ፕላንን መሠረት በማድረግ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ዝርዝር ማስተር ፕላን የማዘጋጀት እና ከክልል መንግሥታት ጋር በሚደረግ

ስምምነት መሠረት መሬት በመረከብ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት መሬት ባንክ ሆኖ የማገልገል፤

3. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር አስፈላጊ መሠረተ ልማቶች ለኢንዱስትሪ ፓርኮች አልሚዎች ተደራሽ እንዲሆኑ የማድረግ፤
4. አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የኢንዱስትሪ ፓርኮችን የማስተዳደር ተግባር በሥራ አመራር ውል ለሌሎች አካላት የማስተላለፍ፤
5. የኢንዱስትሪ ፓርኮችን ጠቀሜታ በሠፊው በማስተዋወቅ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የሚሠማሩ ባለሀብቶችን የመሳብ፤
6. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር[107] የሚያወጣውን መመሪያ እና የፖሊሲ አቅጣጫ መሠረት በማድረግ ቦንድ የመሸጥና በዋስትና የማስያዝ እና ከአገር ውስጥና ከውጭ የገንዘብ ምንጮች ጋር የብድር ውል የመደራደርና የመፈራረም፤
7. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ የሆኑ ሥራዎችን የማካሄድ፡

6. **<u>ካፒታል</u>**

የኮርፖሬሽኑ የተፈቀደው ካፒታል ብር 40 ቢሊዮን (አርባ ቢሊዮን ሲሆን ከዚህ ውስጥ 25 ቢሊዮን (ሀያ አምስት ቢሊዮን በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል፡፡ የኮርፖሬሽኑ የተፈቀደው ካፒታል ብር 40 ቢሊዮን (አርባ ቢሊዮን ሲሆን ከዚህ ውስጥ 25 ቢሊዮን (ሀያ አምስት ቢሊዮን በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል፡፡[108]

7. **<u>ኃላፊነት</u>**

ኮርፖሬሽኑ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም።

8. **<u>ኮርፖሬሽኑ የሚቆይበት ጊዜ</u>**

ኮርፖሬሽኑ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

9. **<u>የተሻረ ደንብ</u>**

የኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ልማት ቀጠናዎች ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 297/2005 በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

10. **<u>የመብቶችና ግዴታዎች መተላለፍ</u>**

---

[107] በ22)12 (2008 አ. 916 አንቀጽ 9(6 መሰረት የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሆኗል፡፡
[108] በ23)35(2009 ደ.402 አንቀጽ 2 ተሻሻለ፡፡

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 297/2005 ተቋቁሞ የነበረው የኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ልማት ቀጠናዎች ኮርፖሬሽን መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለኮርፖሬሽኑ ተላልፈዋል፡፡

11. **ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ህዳር 26 ቀን 2007 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 431/2011

## የመሬት ባንክና ልማት ኮርፖሬሽንን ለማቋቋም የወጣ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 (እንደተሻሻለ አንቀፅ 5 እና በመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 አንቀጽ 47(1 (ሀ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭርርዕስ**

   ይህ ደንብ "የመሬት ባንክና ልማት ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 431/2011" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**

   1. የመሬት ባንክና ልማት ኮርፖሬሽን (ከዚህ በኃላ ኮርፖሬሽን እየተባለ የሚጠራ የፌደራል መንግስት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. ኮርፖሬሽኑ በመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 መሰረት ይተዳደራል፡፡

3. **ተቆጣጣሪ ባለስልጣን**

   የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የኮርፖሬሽኑ ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ይሆናል፡፡

4. **ዋና መስሪያ ቤት**

   የኮርፖሬሽኑ ዋና መስሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ እንዳስፈላጊነቱ ቅርንጫፎችን በሌሎች ከተሞችም ሊከፍት ይችላል፡፡

5. **ዓላማ**

   ኮርፖሬሽኑ በፌደራል መንግሰት መስሪያ ቤቶችና የልማት ድርጅቶች ስር የሚገኙ ይዞታዎችን በተመለከተ የሚከተሉት አላማዎች ይኖሩታል፡-

   1. ይዞታዎችን አንድ በአንድ መለየት፤
   2. ይዞታዎችን መቁጠር እና ካርታ እንደኖራቸው ማድረግ፤
   3. ይዞታዎችን በአግባቡ በማልማት እና በማስተዳደር መንግስት ከዘርፉ ማግኘት የሚገባውን ሁሉን አቀፍ ጥቅሞች እንዲያገኝ ማስቻል፤
   4. ይዞታዎች ለሚሰጡት አገልግሎት ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር በሚያስችል መልኩ ማልማት፤

5. ይዞታዎችን አቀናጅቶ በመምራት ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ እንዲሰጡ ማስቻል፤
6. ይዞታዎች ወደ ግል ይዞታነት ሲተላለፉ የመንግሰት ጥቅም እንዲጠበቅ ማድረግ፤
7. በሁሉም የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶችና የልማት ድርጅቶች የተያዙ ይዞታዎች መለየት፣ የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በራሱ ስም ማሰራት፣ ቀደም ብሎ የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያላቸውን ይዞታዎች ወደ ራሱ ሥም ማዞር፣ ለውሳኔ የሚረዳ በማዕከላዊነት የተደራጀ መረጃ መያዝ፤
8. በተለዩት የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶችና የልማት ድርጅቶች ይዞታዎች ባለቤት ሆኖ ከሌሎች ባለ ሐብቶች ጋር በጋራ ወይም በተናጥል ማልማት፤ መቆጣጠር፤ ማስተዳደር፡፡

6. <u>ካፒታል</u>

1. ኮርፖሬሽኑ የተፈቀደ ካፒታል ብር 5 ቢሊዮን (አምስት ቢሊዮን ሲሆን ከዚህ ዉስጥ ብር 1 ቢሊዮን 250 ሚሊዮን (አንድ ቢሊዮን ሁለት መቶ ሃምሳ ሚሊዮን ብር በጥሬ ገንዘብና በአይነት ተከፍሏል፡፡
2. ኮርፖሬሽኑ በጀት በራሱ ያመነጫል፤ ያስተዳድራል፡፡

7. <u>ኃላፊነት</u>

ኮርፖሬሽኑ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

8. <u>ኮርፖሬሽኑ የሚቆይበት ግዜ</u>

ኮርፖሬሽኑ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

9. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥቅምት 26 ቀን 2011 ዓ.ም**

**አብይ አህመድ (ዶ/ር**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ክፍል ሃያ ስምንት

## አዋጅ ቁጥር 985/2009ዓ.ም

## የህብረት ስራ ማህበራት አዋጅ

ተመሳሳይ ፍላጎት ባላቸው ሰዎች መካከል በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ኅብረት በመፍጠር ገንዘብን፣ ዕውቀትን፣ ንብረትንና ጉልበትን በማስተባበር የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊ፣ የባህላዊና ሌሎች የጋራ ፍላጎቶችን በማሟላት እርስ በርስ መደጋገፍንና ቁጠባን የሚፈጥሩ የኅብረት ሥራ ማህበራትን ማቋቋም እና መምራት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የኅብረት ሥራ ማህበራት በገጠር እና በከተማ ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ፣ በአባላት ምርት ላይ ዕሴት በመጨመር፣ የግብይት እና የፋይናንስ ትስስር በመፍጠር፣ አላስፈላጊ የገበያ ሰንሰለትን በማሳጠር፣ በሃገር ውስጥ እና በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ በመሆን ለዜጎች የሥራ ዕድልን በመፍጠር በሀገሪቷ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ዕድገት ውስጥ የራሳቸውን አስተዋጽኦ ለማበርከት በአንድ ወጥ ሃገራዊ የኅብረት ሥራ ማህበር አዋጅ በመመራት በሕገ መንግስታችን  አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ለመፍጠር የተቀመጠውን ዓላማ ለማሳካት ምቹ ሁኔታን መፍጠር በማስፈለጉ፤

የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚከተሏቸውን መሠረታዊ መርሆዎችና ልዩ ባህሪ እንደጠበቁ በነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት ውስጥ ተገቢውን ሚና እንዲጫወቱ ማድረግ በማስፈለጉ፤

የአባላትን ባለቤትነት እና ተጠቃሚነት መብት  የሚያረጋግጡ፣ አባላት የሚመሯቸውና የሚቆጣጠሯቸው ኅብረት ሥራ ማህበራትን ማደራጀት እና ማጠናከር በማስፈለጉ፤

የኅብረት ሥራ ማህበራትን ዓላማ ለማሳካት የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚደራጁበትንና የሚመሩበትን ሕግ በማውጣት በሥራ ላይ ያለውን የኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ መተካት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 55 (6 መሰረት የሚከተለው ታውጇል፦

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. "የኅብረት ሥራ ማህበር" ማለት ሰዎች ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ባህላዊና ሌሎች የጋራ ፍላጎቶቻቸውን ለማሟላት እና በተናጠል ሊፈቱ ያልቻሏቸውን ችግሮች በጋራ ለማቃለል ተመሳሳይ ዓላማ ያላቸው ሰዎች በፈቃደኝነት የሚያቋቁሙት፣ በጋራ ባለቤትነት የሚያስተዳድሩት፣ በኅብረት ሥራ ማህበራት መርህ መሠረትየሚመሩትና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የሚቆጣጠሩት ራሱን የቻለ ሕጋዊ ሰውነት ያለው የኅብረት ሥራ ማህበር ነው፤
2. "መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበር" ማለት የጋራ ፍላጎት እና ዓላማ ባላቸው ግለሰቦች በዚህ አዋጅ በተወሰነው አነስተኛው የአባላት መነሻ ቁጥር መሠረት ለማምረት፣ አገልግሎት ለመስጠት ወይም ሁለቱንም ለማከናወን የሚቋቋም የኅብረት ሥራ ማህበር ነው፤
3. "የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን" ማለት ተመሣሣይ ዓላማ ባላቸው መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት በዚህ አዋጅ በተወሰነው አነስተኛው የአባላት መነሻ ቁጥር መሠረት ከመሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት በላይ የሆነ የማምረት፣ አገልግሎት የመስጠት ወይም ሁለቱንም የማከናወን ተግባር ለመፈፀም የሚቋቋም ሁለተኛ ደረጃ የኅብረት ሥራ ማህበር ነው፤
4. "የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን" ማለት ተመሣሣይ ዓላማ ባላቸው የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖች በዚህ አዋጅ በተወሰነው አነስተኛው የአባላት መነሻ ቁጥር መሠረት ከኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖች በላይ የሆነ የማምረት፣ አገልግሎት የመስጠት ወይም ሁለቱንም የማከናወን ተግባር ለመፈፀም የሚቋቋም ሦስተኛ ደረጃ የኅብረት ሥራ ማህበር ነው፤
5. "የኅብረት ሥራ ማህበራት ሊግ" ማለት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖች እና የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽኖችን የሚወክል ሊግ ነው፤
6. "ሁለገብ የኅብረት ሥራ ማህበር" ማለት ለአባላቱ የማምረት እና አገልግሎት የመስጠት ተግባራትን ለማከናወን የተቋቋመ የኅብረት ሥራ ማህበር ነው፤
7. "የቁጠባና ብድር የኅብረት ሥራ ማህበር" ማለት የቁጠባ፣ የብድር እና የብድር የሕይወት መድን አገልግሎቶችን ለአባላቱ ለመስጠት የተቋቋመ የኅብረት ሥራ ማህበር ነው፤

8. “የብድር የሕይወት መድን” ማለት ከኅብረት ሥራ ማህበር ብድር የወሰደ የኅብረት ሥራ ማህበር አባል ብድሩን ሙሉ በሙሉ ከፍሎ ሳይጨርስ በሞት ቢለይ ቀሪውን ብድር ለመክፈል የሚሰጥ የመድን ዋስትና ነው፤
9. “የኅብረት ሥራ ማኅበር የሥራ ክልል” ማለት በማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር መተዳደሪያ ደንብ የተወሰነና አግባብ ባለው ባለሥልጣን የተመዘገበ የሥራ ክልል ነው፤
10. “አባል” ማለት በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት እንደኅብረት ሥራ ማህበሩ አይነት የተደነገጉትን የአባልነት መመዘኛዎችን በማሟላት ለአባልነት ጥያቄ አቅርቦ ተቀባይነት ያገኘ ግለሰብ ወይም መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር ወይምየኅብረትሥራማህበራት ዩኒዬን ወይም የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን ነው፤
11. “ጠቅላላ ጉባኤ” ማለት የአንድ መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማኅበር ግለሰብ አባላትወይምተወካዮቻቸው ወይም ከመሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበር በላይ ከሆነ የመሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒየኖች ወይም የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽኖች ተወካዮች የሚገኙበት ጉባኤ ነው፤
12. “ተወካይ” ማለት አወካከሉ በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ በሚወሰነው መሠረት ሆኖ በመሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበር በግለሰብ አባላት ተወክሎ በጠቅላላ ጉባኤ ድምጽ የሚሰጥ ወይም በኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን ወይም በኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን በጠቅላላ ጉባኤ ተመርጦ የኅብረት ሥራ ማህበራትን ተክቶ በማንኛ ውም የኅብረት ሥራ ማህበር ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ላይ በመገኘት ድምፅ የሚሰጥ ግለሰብ ነው፤
13. “መተዳደሪያ ደንብ” ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12 የተመለከቱትን ዝርዝሮች አሟልቶ የያዘ፣ አግባብ ባለው አካል የተመዘገበ እና በየጊዜው የሚሻሻለውንም ጨምሮ በኅብረት ሥራ ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ በሁለት ሦስተኛ ድምፅ የፀደቀ የኅብረት ሥራ ማህበሩ የሚተዳደርበት ሕግ ነው፤
14. “ልዩ ውሳኔ” ማለት በአባላቱ ላይ አስገዳጅነት እንዲኖረው በኅብረት ሥራ ማህበሩ አባላት በሁለት ሦስተኛው ድምጽ መጽደቅ ያለበት ውሣኔ ነው፤
15. “የሥራ አመራር ኮሚቴ” ማለት በጠቅላላ ጉባኤ ተመርጦ የአንድን የኅብረት ሥራ ማህበር ሥራዎችን እንዲመራ ኃላፊነት የተሰጠው አካል ነው፤

16.“ሥራ አስኪያጅ” ማለት ለኅብረት ሥራ ማህበር ሥራ አመራር ኮሚቴ ተጠሪ የሆነና በተሰጠው ኃላፊነትና ሥልጣን ገደብ መሰረት የኅብረት ሥራ ማህበሩን የዕለት ተዕለት ሥራዎችን የሚያንቀሳቅስ የሥራ ኃላፊ ነው፤

17.“ሠራተኛ” ማለት ከአሰሪው የኅብረት ሥራ ማህበር ጋር በገባው ውል መሠረት የዕለት ተዕለት ሥራዎችን እንዲያካሄድ በቅጥር ላይ የተመሰረተ የሥራ ግንኙነት ያለው ግለሰብ ነው፤

18.“የመጠባበቂያ ሒሳብ” ማለት የኅብረት ሥራ ማህበሩ ከዓመታዊ ትርፉ በሕጉ መሰረትለመጠባበቂያነትየሚያስቀምጠውና ለአባላት በትርፍ ድርሻነት የማይከፋፈለው ሂሳብ ነው፤

19.“ካፒታል” ማለት የኅብረት ሥራ ማህበር ካለው ጠቅላላ ሀብት ላይ ዕዳው ተቀንሶ የሚቀረው የሀብት መጠን ሲሆን የአባላትን የዕጣ ሽያጭ፣ የመጠባበቂያ ሂሳብ፣ ስጦታ፣ ውርስ እና በመተዳደሪያ ደንቡ የሚወሰኑ ፈንዶች እና ኢንቨስትመንቶችን የያዘ ነው፤

20.“አግባብ ያለዉ ባለስልጣን” ማለት የፌደራል ኅብረት ሥራ ኤጄንሲ ወይም በክልል የኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅን ለማስ ፈጸም፣ ዘርፉን ለመምራት እና ለመቆጣጠር የተቋቋመ አካል ነው፤

21.“ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 47 (1 የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና የድሬዳዋ አስተዳደርን ይጨምራል፤

22.“የኅብረት ስራ ማህበራት ፈንድ” ማለት ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ለተለያዩ የጋራ ጥቅሞች ለትምህርት ወይም ለስልጠና ወይም ለኦዲት አገልግሎት ወይም ለማበ ረታቻ ወይም ለጥናት እና ምርምር ወይም ለህግ አገልግሎት ወይም ለፕሮሞሽንና ኮሙኒኬሽን እና ለማህበራዊ አገልግሎት የሚያውላቸውን ከኅብረት ስራ ማህበራት ዓመታዊ የተጣራ ትርፍ በጠቅላላ ጉባዔ ሲወስን የሚገኝ ገቢ እንዲሁም የኅብረት ስራ ማህበራት ከስጦታ ወይም ከውርስ ወይም የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በመሥራት ከዕርዳታ እና ከተለያዩ ገቢ ማስገኛዎች የተገኙ ገቢዎችን እና የኅብረት ስራ ማህበራት ህልውናቸውን በሚያጡበት ጊዜ የማይከፋፈሉት የጋራ ገንዘብና ንብረት የሚሰባሰብበት ፈንድ ነው፤

23.“የዕጣ ክፍያ” ማለት በኅብረት ስራ ማህበሩ የታወጀ ዋጋ ያለው እና ለአባልነት እንደ መጀመሪያ ቅድመ ሁኔታ በጥሬ ገንዘብ ወይም በዓይነት የተሸጠ ወይምየሚሸጥ ነው፤

24.“ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

25.ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ያካትታል፡፡

3. **የተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ አዋጅ በመላ ሀገሪቱ ውስጥ በሚደራጁ የኅብረት ሥራ ማህበራት ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

4. **የኅብረት ሥራ ማህበር ዓላማዎች**

በዚህ አዋጅ መሠረት የሚቋቋም ኅብረት ሥራ ማህበር የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፦

1. አባላት በተናጠል በመሥራት ሊወጧቸው የማይችሏቸውን የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ችግሮችን በተባበረ ጥረት መወጣት፣ መቋቋም እና መፍታት፤
2. አባላት ያላቸውን ዕውቀት፣ ሀብትና ጉልበት በማቀናጀት የተሻለ ውጤት ማግኘት፤
3. በአባላት ዘንድ በራስ መተማመንን ማጎልበት፤
4. ለማምረት የሚያስፈልገውን ወጪና የአገልግሎት ዋጋን በመቀነስ አባላት የሚፈልጉትን ግብአት ወይም አገልግሎት በአነስተኛ ዋጋ እንዲያገኙ ማድረግ እና ምርታቸው ወይም አገልግሎታቸው የተሻለ የገበያ ዋጋ እንዲያገኝ ማስቻል፤
5. የቴክኒክ ዕውቀትን እና የሥራ ፈጠራን በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች እንዲስፋፉ ማድረግ፤
6. በአባላት መካከል የቁጠባ ባህል እንዲዳብር እና እንዲስፋፋ ማድረግ፤
7. ለአባላት የብድር አገልግሎትን በመስጠት ኢንቨስትመንትን ማስፋፋት፤
8. ለአባላት የብድር የሕይወት መድን ዋስትና መስጠት፤
9. አባላቱ በግላቸው ቢሰሩ ኖሮ ሊደርስባቸው የሚችለውን ጉዳትና ኪሣራ በጋራ በማካፈል የእያንዳንዱን ሰው ጉዳትና ኪሣራ መቀነስ፤
10. አባላትን በማስተማርና በማሰልጠን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ አቅማቸውንና ባህላቸውን ማጎልበት፡፡

5. **የኅብረት ሥራ ማህበራት መሠረታዊ መርሆዎች**

1. የኅብረት ሥራ ማኅበራት አባልነት በማኅበራቱ አገልግሎት ለመጠቀም ለሚፈልጉና የአባልነት ግዴታዎችን ለመቀበል ፈቃደኛ ለሆኑ ሰዎች ሁሉ በጾታ፣ በማኅበራዊ

አቋም፣ በዘር፣ በፖለቲካ አመለካከት፣ በአካል ጉዳተኝነት ወይም በሃይማኖት ልዩነት ሳይደረግ ለሁሉም ክፍት ይሆናል፡፡

2. የኅብረት ሥራ ማኅበራት ፖሊሲ በማውጣትና ውሳኔዎችን በማስተላለፍ የነቃ ተሳትፎ በሚያደርጉ አባላት የሚመሩ ዲሞክራሲያዊ ድርጅቶች፣ እያንዳንዱ አባል እኩል ድምጽ ያለው እንዲሁም አንድ አባል አንድ ድምጽ ብቻ ያለው ይሆናል፡፡
3. ከትርፍ ላይ ለመጠባበቂያ እና ለሌሎች አገልግሎቶች ተቀንሶ ከተቀመጠ በኋላ አባላት ከኅብረት ሥራ ማህበሩ በገዙት ዕጣ መጠን እና ባደረጉት ተሣትፎ መሠረት ቀሪው ትርፍ ይከፋፈላል፡፡
4. የኅብረት ሥራ ማኅበራት ከሌሎች አካላት ጋር መንግሥትንም ጨምሮ ስምምነት የሚያደርጉት ወይም ከኅብረት ሥራ ማኅበራቸው ውጭ ከሚገኝ ምንጭ ገንዘብ በመበደር ካፒታላቸውን ማሳደግ የሚችሉት የአባላትን ዲሞክራሲያዊ ቁጥጥር በሚያረጋግጥ፣ የኅብረት ሥራ ማኅበራቸውን የራስ በራስ ማስተዳደር መብት በሚጠብቅ እንዲሁም የራስ አገዝ ባህሪውን በማይነካ ሁኔታ መሆን ይኖርበታል፡፡
5. የኅብረት ሥራ ማኅበራት አባላት፣ ተመራጮች፣ ሥራ አስኪያጅ እና ሠራተኞች ለኅብረት ሥራ ማኅበራቸው ዕድገት ተገቢውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ትምህርትና ሥልጠና እንዲያገኙ ያደርጋሉ፤ ስለ ኅብረት ሥራ ማኅበራት ምንነትና ጥቅም ለሕዝቡ በተለይም ለወጣቱ ያስተዋውቃሉ፡፡
6. በአካባቢ፣ በሀገር አቀፍ፣ በአህጉር አቀፍ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሚገኙ የኅብረት ሥራ ማህበራት መዋቅሮች ጋር በመተባበር የኅብረት ሥራ ማህበራት እንቅስቃሴን በማጠናከር አባሎቻቸውን በሚገባ ያገለግላሉ፡፡
7. የኅብረት ሥራ ማኅበር አባሎቹ ባፀደቋቸው ፖሊሲዎች አማካኝነት በአካባቢያቸው ላለው ኅብረተሰብ ዘላቂ ልማት ለማምጣት የሚያስችል ተግባር ያከናውናሉ፡፡

## 6. <u>የኅብረት ሥራ ማህበራት እና የአባላት እሴቶች</u>

1. የኅብረት ሥራ ማህበራት እሴቶች የሚከተሉት ይሆናሉ፦

   ሀ) ራስን በራስ መርዳት፤

   ለ) የግል ሃላፊነትን መወጣት፤

   ሐ) የዴሞክራሲባህልን ማስፋፋት፤

   መ) እኩልነት፤

   ሠ) ፍትሃዊነት፤

   ረ) ወንድማማችነት፡፡

2. የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት የሥነ-ምግባር እሴቶች የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

ሀ) ታማኝነት፤

ለ) ግልፀኝነት፤

ሐ) ተጠያቂነት፤

መ) አሳታፊነት፤

ሠ) ማህበራዊ ኃላፊነት፤ እና

ረ) ለሌሎች ማሰብ፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለኅብረት ሥራ ማኅበራት አመሠራረትና ምዝገባ

7. ስለኅብረት ሥራ ማህበራት አመሠራረት

1. የኅብረት ሥራ ማህበራት እንደየባህሪያቸው ከመሠረታዊ እስከ ፌዴሬሽን በየደረጃው ሊመሰረቱ ይችላሉ፡፡

2. የመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበር፡-

ሀ) በተወሰነ  አካባቢ በሚኖሩ ወይም በሚሠሩ ወይም በተወሰነ ሙያ በተሰማሩ ግለሰቦች፤ እና

ለ) ቁጥራቸው ከሃምሣ በማያንሱ አባላት፤

ይደራጃል፡፡

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2 ፊደል ተራ (ለ ቢኖርም የሥራ ባህሪያቸውን እና የኢኮኖሚያዊ አዋጭነታቸውን መሠረት በማድረግ አግባብ ያለው ባለሥልጣን የመነሻ ቁጥርን በመመሪያ ሊወስን ይችላል፤ ሆኖም የመነሻ ቁጥሩ ከ10 ሊያንስ አይችልም፡፡

4. በፌደራል ደረጃ የሚደራጅ መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር አባላት ነዋሪነታቸው ከሁለት እና ከዚያ በላይ ከሆኑ ክልሎች የተውጣጡ ግለሰቦች መሆን አለባቸው፡፡

5. አግባብ ያለው ባለሥልጣን የኅብረት ሥራ ማህበራትን በፌደራል ወይም በክልል ደረጃ በማደራጀት የሚመዘግብ ይሆናል፡፡

8. የኅብረት ሥራ ማኅበራት ዓይነቶች

1. የኅብረት ሥራ ማህበር ምርት የማምረት ወይም አገልግሎት የመስጠት ወይም ምርት የማምረት እና አገልግሎት የመስጠት ሁለገብ ተግባር አጣምሮ የሚያከናውን ሆኖ ሊመሠረት ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1 የተደነገገውእንደተጠበቀሆኖ ለኅብረት ስራ ማህበራት በህግ በተከለከሉ የህዝብን ሞራላዊ እሴቶች በሚነኩ፣ የአካባቢን ደህንነት በሚጎዱ ተግባራት መደራጀት የማይቻል ሲሆን አግባብ ባለው ባለስልጣን የኢኮኖሚ አዋጭነት እንዲሁም በሚደራጁበት አካባቢ ሀብት መኖሩን በጥናት በመለየት የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚደራጁባቸውን የአማራጭ ዓይነቶች በማቅረብ ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

9. <u>የኅብረት ሥራ ማኅበር ስም</u>

1. ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማኅበር መጠሪያ ስም ይኖረዋል፣ የስም አወጣጡም ምክንያታዊ፣ ሕግንና የሕዝብን ሞራል የማይቃረን መሆን አለበት፡፡
2. ከማንኛውም የኅብረት ሥራ ማኅበር ስም መጨረሻ "ኃላፊነቱ የተወሰነ የኅብረት ሥራ ማህበር" የሚል ሐረግ መጻፍ ይኖርበታል፡፡
3. አንድ የኅብረት ሥራ ማህበር በተመዘገበበት ስም፣ መለያ ምልክት እና የሥራ ክልል ውስጥ ሌላ የኅብረት ሥራ ማህበር ተመሳሳይ እና አሳሳች ስም ወይም መለያ ምልክት መጠቀም አይችልም፡፡
4. የማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ስም ጉልህ ሆኖ ተጽፎ የኅብረት ሥራ ማህበሩ ሥራ በሚካሄድበት በማንኛውም ሥፍራ መለጠፍ አለበት፡፡ እንዲሁም በኅብረት ሥራ ማህበሩ ማስታወቂያዎች፣ ደብዳቤዎች፣ ሌሎች መግለጫዎችና በኅብረት ሥራ ማህበሩ ስም በሚፈረሙ ሰነዶች ላይ መጻፍ ወይም ማኅተም መደረግ አለበት፡፡
5. ማንኛውም ሰው አግባብ ካለው ባለሥልጣን ፈቃድ ሳያገኝ "የኅብረት ሥራ ማህበር" የሚለውን ስያሜ መጠቀም አይችልም፡፡

10. <u>ስለ ኅብረት ሥራ ማኅበር ምዝገባ</u>

1. ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማኅበር አግባብ ባለው ባለሥልጣን መመዝገብ አለበት፡፡
2. ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማኅበር፣ የኅብረት ሥራ ማኅበር ሆኖ ለመመዝገብ ማመልከቻውን ከሚከተሉት ጋር አያይዞ አግባብ ላለው ባለሥልጣን ያቀርባል:-

ሀ) የመሥራቾች ስብሰባ ቃለ ጉባኤ፤

ለ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ ሦስት ቅጂዎች፤

ሐ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት ስም፣ አድራሻና ፊርማ፤

መ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን የቁጥጥር ኮሚቴ አባላት ስም፣ አድራሻና ፊርማ፤

ሠ) የኅብረት ሥራ ማህበር አባላት ሆነው የሚመዘገቡት ግለሰቦች በዚህ አዋጅና

በኅብረት ሥራ ማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ በተወሰነው መሠረት አባል ለመሆን ብቁ መሆናቸውን የሚያስረዱ ዝርዝር መግለጫዎች፤

ረ)የኅብረት ሥራ ማህበሩ ከመሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበር በላይ ከሆነ የአባል ኅብረትሥራ ማህበራትን አድራሻ እና የተወካዮች ፊርማ፤

ሰ) ከሶስት እስከ አምስት ዓመት የሚደርስ የኅብረት ሥራ ማህበሩ የስራ እቅድ ሰነድ፤

ሸ) የመነሻ ካፒታሉን መጠንና ተሰብስቦ በባንክ ሂሳብ ገቢ መደረጉን ወይም ባንክ በሌለበት አካባቢ ከሆነ መዝጋቢው በወሰነው የፋይናንስ ተቋም መቀመጡን የሚያረጋግጥ ሰነድ፤

ቀ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ የሚሠራበት ቦታ መግለጫ

በ) ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች የሚወሰኑ ሌሎች መግለጫዎች፡፡

3. አግባብ ያለው ባለሥልጣን የቀረበለትን የምዝገባ ማመልከቻ መርምሮ የተሟላ መሆኑን ሲያረጋግጥ በአምስት ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ የኅብረት ሥራ ማህበሩን መዝግቦ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡ በዚህም የምዝገባ ምስክር ወረቀት ላይ የኅብረት ሥራ ማህበሩ በኅብረት ሥራ ማህበርነት የተመዘገበበት ቀን ይጠቀሳል፡፡
4. አግባብ ያለው ባለሥልጣን አመልካቹን የኅብረት ሥራ ማህበር መመዝገብ አይገባውም ሲል የወሰነ እንደሆነ ምክንያቱን በጽሑፍ በማድረግ ለኅብረት ሥራ ማህበሩ ወኪሎች ካመለከቱበት ቀን ጀምሮ በአምስት ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ መግለፅ አለበት፡፡
5. የአመልካች ወኪሎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት በጽሑፍ በተሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያላቸው ከሆነ፣ በክልል ሲሆን አግባብ ላለው የክልሉ ፍርድ ቤት ወይም በፌደራል ደረጃ ሲሆን ለፌደራል ከፍተኛፍርድ ቤት በ60 ተከታታይ ቀናት ውስጥ አቤቱታ ማቅረብ ይችላሉ፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት የተሰጠ የምዝገባ የምስክር ወረቀት የኅብረት ሥራ ማህበሩ በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት የተመዘገበ ለመሆኑ በቂ ማስረጃ ይሆናል፡፡

7. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት በሕጋዊ መንገድ የተመዘገበ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር በተመዘገበበት ዓላማና በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ ለተፈቀደለት የሥራ መስክ ሌላ ተጨማሪ የንግድ ፈቃድ ሳያስፈልገው ይሠራል፡፡
8. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (2) (ሀ) እስከ (ሸ) የተዘረዘሩት መስፈርቶች የተሟሉ መሆኑን አግባብ ያለው ባለሥልጣን ሲያረግጥ ከአንድ አመት ላልበለጠ ጊዜ የሚያገለግል ጊዜያዊ የምስክር ወረቀት ሰጥቶ የተቀሩት መስፈርቶች በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲሟሉ ማስደረግ ይችላል፡፡
9. ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ከተቋቋመበት ዓላማና መርህ ውጪ ሲንቀሳቀስ ከተገኘ በዚህ ሕግ የተፈቀደለትን ሥራ እንዳይሠራ አግባብ ያለው ባለሥልጣን ሊያግደው ይችላል፡፡
10. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (9) መሠረት የታገደው የኅብረት ሥራ ማህበር ዕግዱ እንዲነሳለት በ30 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ካላመለከተ አግባብ ያለው ባለሥልጣን ሕጋዊ የማፍረስ እርምጃ ይወስዳል፡፡
11. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (9) መሠረት የታገደ የኅብረት ስራ ማህበር ጠቅላላ ጉባኤ ዕግዱ እንዲነሳለት አግባብ ላለው ባለሥልጣን ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል፡፡ ጥያቄውን የተቀበለው አግባብ ያለው ባለሥልጣን የኅብረት ሥራ ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ እግዱ እንዲነሳለት ያቀረበው ምክንያት በቂና አግባብ ሆኖ ሲያገኘው እግዱን ሊያነሳ ይችላል፡፡ አግባብ ያለው ባለሥልጣን እግዱን ያላነሳ እንደሆነ ያላነሳበትን ምክንያት በጽሑፍ ያሳውቃል፡፡ አግባብ ያለው ባለሥልጣን በሰጠው ውሳኔ ያልተስማማ አካል ዕግዱ የተሰጠው በፌደራል ደረጃ ከሆነ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም ዕግዱ በክልል ደረጃ ከሆነ ስልጣን ላለው ለክልሉ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

11. <u>የሕግ ሰውነትና ኃላፊነት</u>

1. ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማኅበር በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 መሠረት ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ በሕግ የሰውነት መብት ይኖረዋል፡፡
2. ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፤ ኃላፊነቱ የተወሰነ ነው፡፡

12. <u>የኅብረት ሥራ ማኅበር መተዳዳሪያ ደንብ</u>

1. ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር መተዳደሪያ ደንብ ይኖረዋል፣ የመተዳደሪያ ደንቡ ይዘት የሚከተሉትን ይጨምራል:-

ሀ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን ስምና አድራሻ፤

ለ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን ዓላማና ተግባር፤

ሐ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን የሥራ ቦታ እና አካባቢ፤

መ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ አባል ለመሆን የሚያበቁ መመዘኛዎችን፤

ሠ) ስለኅብረት ሥራ ማህበሩ አባላት መብትና ግዴታዎች፤

ረ) ስለ ኅብረት ሥራ ማህበሩ አመራር አካላት ሥልጣን፣ ኃላፊነትና ተግባር፤

ሰ) አባላት ከኅብረት ሥራ ማኅበሩ ስለሚወጡበትና ስለሚሰናበቱበት ሁኔታ፤

ሸ) ስለ ኅብረት ሥራ ማህበሩ ሥራ አመራር ኮሚቴ አባላትና ሌሎች የሥራ ኃላፊዎች ምርጫ፣ ሹመትና የሥራ ጊዜ እንዲሁም ከኃላፊነት ስለሚታገዱበት ወይም ስለሚሰናበቱበት ሁኔታ፤

ቀ) ስለ ኅብረት ሥራ ማህበሩ ስብሰባ አጠራር እና ስለድምጽ አሰጣጥ፤

በ) ስለትርፍ አመዳደብና ክፍፍል፤

ተ) ስለሂሣብ ምርመራ፤

ቸ) ስለሠራተኛ አቀጣጠር፤

ኀ) ይህን አዋጅ እና በዚህ አዋጅ መሰረት የሚወጣ ደንብ እና መመሪያን የማይቃረኑ ሌሎች ጉዳዮች፡፡

2. የኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳዳሪያ ደንብ በጠቅላላ ጉባዔው ልዩ ውሣኔ ሊሻሻል ይችላል፤ ሆኖም የማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር መተዳዳሪያ ደንብ ማሻሻያ ሊጸና የሚችለው አግባብ ላለው ባለሥልጣን ቀርቦ ከተመዘገበበት ቀን አንስቶ ይሆናል፡፡

3. የማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር የመተዳደሪያ ደንብ እንዲሻሻል በጠቅላላ ጉባዔው ሲወሰን የተደረገው ማሻሻያ እና በዚህ አዋጅ መሠረት የተላላፈ የኅብረት ሥራ ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ልዩ ውሳኔ በሦስት ቅጅ ተደርጎ ዉሳኔ በተላለፈ በ15 ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ አግባብ ላለው ባለሥልጣን መቅረብ አለበት፡፡ የመተዳደሪያ ደንቡ ማሻሻያ በተጠቀሰው ቀን ውስጥ አግባብ ላለው ባለሥልጣን ካልቀረ በተቀባይነት አይኖረውም፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3 መሠረት የቀረበው የመተዳደሪያ ደንብ ማሻሻያ ይህንን አዋጅና አዋጁን ለማስፈጸም የወጣውን ደንብ እና መመሪያ የማይቃረን መሆኑን አግባብያለውባለሥልጣንሲያረጋግጥ ማሻሻያውን ይመዘግባል፤ የምዝገባ ማስረጃውንም በአምስት ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ይሰጣል፡፡

5. አግባብ ያለው ባለሥልጣን የመተዳደሪያ ደንቡን ማሻሻያ ካልመዘገበ ወይም የማይመዘግብበትን ምክንያት በአምስት ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ለኅብረት ሥራ ማህበሩ ካላሳወቀ የተሻሻለው መተዳደሪያ ደንብ እንደተመዘገበ ተቆጥሮ በሥራ ላይ ይውላል፡
6. ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ የኅብረት ሥራ ማኅበሩን መርሆዎች እና እሴቶች ማካተት አለበት፡፡
7. ማንኛውም የኅብረት ስራ ማህበር በማህበሩ የአመራር አካላት አባልነት ውስጥ የሴቶችን ተሣትፎ ለማሣደግና ለማበረታታት የሚያስችል መስፈርት ማካተት አለበት፡፡
8. ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር የሴቶችን፣ የወጣቶችን እና የአካል ጉዳተኞችን ተሳትፎ የሚያሳድጉ ተግባራትን በስትራቴጂክ እና በዓመታዊ እቅዶቹ ውስጥ ማካተት አለበት።

13.<u>ስለኅብረት ሥራ ማኅበራት ውህደትና መከፋፈል</u>

1. የኅብረት ሥራ ማህበር ጠቅላላ ጉባዔ በልዩ ውሣኔ፦
   ሀ) ራሱን በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ የኅብረት ሥራ ማህበራት ሊከፋፍል፤ ወይም
   ለ) ከአንድ ወይም ከዚያ በላይ ከሆኑ ኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር በመዋሃድ አዲስ የኅብረት ሥራ ማኅበር ሊመሠርት፤

   ይችላል፡፡
2. የኅብረትሥራማኅበርመዋሃድወይምመከፋፈልልዩውሣኔተፈፃሚየሚሆነው፦
   ሀ) የኅብረት ሥራ ማኅበሩ አባላት እና ዕዳ ጠያቂዎች በመዋሃዱ ወይም በመከፋፈሉ የተስማሙበት መሆኑ፤ ወይም
   ለ) ያልተስማሙ አባላትና ዕዳ ጠያቂዎች የተከፈላቸው መሆኑ ወይም የክፍያ ዋስትና የተሰጣቸው መሆኑ ተረጋግጦ ልዩ ውሣኔው አግባብ ባለው ባለሥልጣን የተመዘገበ መሆኑ፤
   ሐ) የቀድሞው የኅብረት ሥራ ማህበራት ወይም ኅብረት ሥራ ማህበር ምዝገባ ከመዝገብ መሰረዙ እና በውህደት ወይም በመከፈሉ የተፈጠረ የኅብረት ሥራ ማህበራት ወይም የኅብረት ሥራ ማኅበር መመዝገቡ፤

   ሲረጋገጥ ይሆናል፡፡

3. በውህደቱ ህልውናቸውንያጡ የኅብረት ሥራ ማህበራት መብት እና ግዴታዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2 መሠረት በተመዘገበው የኅብረት ሥራ ማህበር ልዩ ውሳኔ ላይ በተመለከተው ዝርዝር መሠረት አዲስ ወደ ተቋቋመው የኅብረት ሥራ ማህበር ይተላለፋሉ፡፡
4. በመከፋፈሉ ሕልውናውን ያጣው የኅብረት ሥራ ማህበር መብት እና ግዴታዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2 መሠረት በተመዘገበው የኅብረት ሥራ ማኅበሩ ልዩ ውሣኔ ላይ በተመለከተው ዝርዝር መሠረት አዲስ ወደ ተቋቋሙት የኅብረት ሥራ ማኅበራት ይተላለፋሉ፡፡

## 14.ስለ ኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን አደረጃጀት

1. የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን ተመሳሳይ ዓላማ ባላቸው ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት ይደራጃል፡፡
2. የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬንን በፌደራል ወይም በክልል ደረጃ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አዋጭነቱ እየታየ ማደራጀት የሚቻል ይሆናል፡፡
3. በፌደራል ደረጃ የሚደራጁ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን አባላት ቢያንስ ከሁለት ክልሎች የተውጣጡ መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት መሆን አለባቸው፡

## 15.ስለ ኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን አደረጃጀት

1. ተመሳሳይ ዓላማ ባላቸው ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖች የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን ይደራጃል::
2. ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አዋጭነቱ ታይቶ የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽንን በፌደራል ወይም በክልል ደረጃ ማደራጀት ይቻላል፡፡
3. በፌደራል ደረጃ የሚደራጅ የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን አባላት ቢያንስ ከሁለት ክልሎች የተውጣጡ ሁለት እና ከዚያ በላይ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖች መሆን አለባቸው፡፡

## 16.በሙያ የሚደራጅ የኅብረት ሥራ ማህበር ማሟላት ያለበት መስፈርቶች

1. ማንኛውም መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበር የአባላትን ሙያ መሠረት አድርጎ የሚደራጅ ከሆነ እያንዳንዱ አባል ከሚመለከተው አካል የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ ማቅረብ አለበት::
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የሚቀርብባቸው በህግ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ እንዲያወጡ በሚያስገድዱ የስራ መስኮች ብቻ ላይ ይሆናል፡፡

3. የሙያ የኅብረት ሥራ ማህበራት እሴት ጨምረው ለሚያመርቱት ምርት ወይም ለሚሰጡት አገልግሎት የጥራት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ማቅረብ አለባቸው፡፡

17. <u>ስለ የኅብረት ሥራ ማህበራት ሊግ አደረጃጀት</u>

1. የዚህ አዋጅ እና የሌሎች ሕጎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራትን፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖችን እና ፌዴሬሽኖችን በኢትዮጵያ ውስጥ የሚወክል ሊግ በአገር አቀፍ ደረጃ ሊመሠረቱ ይችላሉ፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚመሰረት ሊግ ቁጥር ከአንድ ሊበልጥ አይችልም፡፡
3. የሊግ አደረጃጀት፣ ተግባራትን እና የፋይናንስ ምንጭ በተመለከተ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይሰወናል፡፡

18. <u>የኅብረት ሥራ ማህበራት ግዴታ</u>

የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖራቸዋል፦

1. የኅብረት ሥራ ማህበራት አባሎቻቸው የሚፈልጉትን አገልግሎት በተያዘው ዕቅድ መሠረት የማቅረብ፤
2. በአገሪቱ የአሠሪና ሠራተኛ ሕግ መሠረት ለቀጠሯቸው ሠራተኞች መብታቸውን የመጠበቅ፤
3. የኅብረት ስራ ማህበራት ከሚያገኙት ገቢ ላይ ከገቢ ግብር በስተቀር ሌሎች ለመንግስት መክፈል የሚገባቸውን ክፍያ በሕጉ መሠረት ወቅቱን ጠብቀው ገቢ የማድረግ፤
4. የመተዳደሪያ ደንቡን አክብሮ የመስራት፤
5. ለሚመለከተው አካል አስፈላጊውን መረጃ በተጠየቁ ጊዜ የመስጠት፤
6. የተቋቋሙበትን መርህ እና ዓላማ አክብረው የመስራት፡፡

19. <u>ሥራ ስለመጀመር</u>

1. ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ከተመዘ ገበበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወር ውስጥ በዕቅዱ መሠረት ሥራ ካልጀመረ በተጨማሪ በሦስት ወር ውስጥ እንዲጀምር ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፡፡
2. የኅብረት ሥራ ማህበሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በተሰጠው የማስጠንቀቂያ ጊዜ ውስጥ ሥራ ካልጀመረ የኅብረት ሥራ ማህበሩ ሂሣብ ከተጣራ

እና መፍረሱ ከተወሰነ በኋላ ምዝገባው ተሰርዞ ሕጋዊ ሰውነቱን እንዲያጣ ይደረጋል፡፡

20.<u>የምዝገባ ምስክር ወረቀትን ስለማሳደስ</u>

1. ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር በዚህ አዋጅ መሠረት ተቋቁሞ ከተመዘገበበት እና ሕጋዊ ሰውነት ካገኘበት ቀን ጀምሮ አግባብ ያለው ባለሥልጣን ባወጣው መመሪያ መሠረት በየሦስት ዓመቱ የምዝገባ ምስክር ወረቀቱን ማሳደስ አለበት፡፡
2. በዚህአንቀጽንዑስአንቀጽ (1) መሠረት የምዝገባ ምስክር ወረቀት ያላሳደሰ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር አግባብ ባለው ባለሥልጣን በሚያወጣው መመሪያ መሠረት እርምጃ ይወሰድበታል፡፡

21.<u>የኅብረት ሥራ ማኅበራት ተግባራትና ኃላፊነቶች፤</u>

1. የኅብረት ሥራ ማኅበራት በየደረጃቸው በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (2 እስከ (9 የተመለከቱት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖራቸዋል፡፡
2. መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበራት በዋናነት ግለሰብ አባላት በተናጠል መወጣት የማይችሉትንና ከአቅማቸዉ በላይ የሆነን የጋራ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ችግር መፍታት የሚችሉ ተግባራት ላይ የሚያከናውኑ ሆኖ በተለይ የሚከተሉትን ያካትታል፡-
   ሀ) ለአካባቢው ህብረተሰብ ስለኅብረት ሥራ ማኅበር ፅንሰ ሃሳብ ግንዛቤ ማስጨበጥ እና ቅስቀሳ የማድረግ
   ለ) በአካባቢ ልማት እና ጥበቃ ሥራ ላይ የመሳተፍ፤
   ሐ) ለአባላት በቅድመ ምርት እና በድህረ ምርት ላይ ስለምርት ጥራት ሥልጠናየመስጠት፤
   መ) ለአባላት የመጋዘን አገልግሎት የመስጠት፤
   ሠ) የአባላትን ችግር የሚፈቱ ፕሮጀክቶችን የመንደፍ፤
   ረ) የአባላትን ምርት በመረከብ ዕሴት በመጨመር አባል ለሆኑባቸው ዩኒዬን ወይም ፌዴሬሽን የማስረከብ ወይም የተሻለ የገበያ መዳረሻ በማፈላለግየመሸጥ፤
   ሰ) ሌሎች በመተዳደሪያ ደንባቸው ላይ የተዘረዘሩትን ተግባራት የማከናወን።
3. የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒየኖች በዋናነት አባል መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበራት በተናጠል መወጣት የማይችሉትን የጋራ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ችግሮች መፍታት የሚችሉ ተግባራት ላይ የሚያከናውኑ ሆኖ በተለይ የሚከተሉትን ያካትታል፡-

ሀ) ለአባል መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት በተሰማሩበት መስክ ሥልጠና መስጠት፤

ለ) ለአባል መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት የማማከር አገልግሎት መስጠት፤

ሐ) ለአባል መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት የገበያ መረጃ አገልግሎት መስጠት፤

መ) ለአባል መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት የገበያ ትስስር ማመቻቸት፤

ሠ) የመጋዘንአገልግሎት መስጠት፤

ረ) የምርት ማሳደጊያዎችን እና የፍጆታ እቃዎችን በጅምላ ማቅረብ፤

ሰ) በአባላት ምርት ላይ እሴት መጨመር እና ሌሎች በመተዳደሪያ ደንባቸው ላይ የተዘረዘሩትን ተግባራት ማከናወን፡፡

4. የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽኖች አባል የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዩኖች በተናጠል መወጣት የማይችሉትን የጋራ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ችግሮች መፍታት የሚችሉ ተግባራት ላይ የሚያከናውኑ ሆኖ በተለይ የሚከተሉትን ያካትታል፡-

ሀ) ለአባል ኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖች የኦዲት አገልግሎት ማመቻቸት እና መስጠት፤

ለ) በኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖች ጉዳይ ላይ አባላትን በመወከል መንግስትን እና ባለድርሻ አካላትን ማግባባት፤

ሐ) የኅብረት ሥራ አስተሳሰብን በማስረጽ እና የኅብረት ሥራ ማኅበራት ገፅታ ግንባታ ሥራ በመሥራት የኅብረት ሥራ ማህበራትን ማስፋፋት፤

መ) የአገር አቀፍ እና የዓለም አቀፍ የኅብረት ሥራ ማህበራት ግኑኙነት መፍጠር እና እንዲጠናከር ማድረግ፤

ሠ) ከመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት እና ከዩኒዬኖች አቅም በላይ የሆኑ አገር አቀፍ እና ዓለም አቀፍ የጅምላ ግብይት ሥራዎች ላይ መሳተፍ፤

ረ) የተለያዩ የእሴት መጨመሪያ ኢንዱስትሪዎችን ማቋቋም ወይም አባላት እንዲያቋቁሙ አቅም መፍጠር፤

ሰ) ስለኅብረት ሥራ ማኅበራት ተግባር ተኮር ጥናት እና ምርምር ማካሄድ፤

ሸ) የማማከር አገልግሎት ለአባል ኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖች መስጠት፤

ቀ) በኅብረት ሥራ ዘርፍ ላይ የሰው ሀብት ልማት ማካሄድ፤

በ) በአገር አቀፍ እና በዓለም አቀፍ የኀብረት ሥራ ማህበራት መካከል የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት መዘርጋት፤

ተ) የኀብረትሥራ ማኀበራት ፈንድ ማቋቋም እና ማስተዳደር፤

ቸ) ለኀብረት ሥራ ማህበራት ተግባራት የሚያግዙ የፋይናንስ እና የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት፤

ኀ) ለኀብረት ሥራ ማህበራት የመሠረተ-ልማት ግንባታዎችን ማስተባበር እና መደገፍ፤

ነ) ሌሎች በመተዳደሪያ ደንባቸው ላይ የተዘረዘሩትን ተግባራት ማከናወን።

5. በዩኒዬን ወይም በፌዴሬሽን ደረጃ የተቋቋመ የኀብረት ሥራ ማህበር በአባላት ምርት ወይም አገልግሎት ላይ እሴት ሳይጨምር አባላቱ የሚያከናውኑትን ተግባራት በተመሳሳይ ሊሠራ አይችልም፡፡

6. ማንኛውም የኀብረት ሥራ ማህበር ከአባላቱ የሰበሰበውን ምርት በወቅቱ ገበያ ዋጋ በምርት ዘመኑ ውስጥ የመሸጥ ኃላፊነት አለበት፡፡

7. የኀብረት ሥራ ማህበራት በሚያደርጉት የሥራ እንቅስቃሴ በአካባቢ እና በሰው ደኅንነት ላይ ጉዳት እንዳይደርስ አካባቢን የመጠበቅ፣ የማልማት እና የመንከባከብ ኃላፊነት አለባቸው፡:

8. ማንኛውም የኀብረት ሥራ ማህበር ለአባሉ አነስተኛ የመድን ዋስትና አገልግሎት ሲሠጥ በሚከተለው መሠረት መሆን አለበት፡-

ሀ) የኀብረት ሥራ ማህበሩ ለራሱ ንብረት ወይም ለአባሉ ንብረት የመድን ዋስትና ሊገባ፤

ለ) ከአባሉ በሚቀርበው ጥያቄና ፍላጎት መሠረት ለሰብል ወይም ለእንሰሳት ወይም በተለያዩ ምርቶች ላይ ለሚደርሰው አደጋ የኢንሹራንስ ሰጪ ድርጅት ወኪል በመሆን የአነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት ሊሰጥ፣ ወይም

ሐ) የኀብረት ሥራ ማህበሩ ለአባሉ ለሚያበድረው ብድር ተበዳሪው የተበደረውን ዕዳ ሣይከፍል ለሚደርሰው የሞት አደጋ አነስተኛ የብድር የሕይወት መድን ዋስትና አገልግሎት ሊሰጥ ወይም ሊገባ፣ ይችላል።

9. የገንዘብ ቁጠባና ብድር የኀብረት ሥራ ማህበር ከአባሉ ቁጠባ ይሰበስባል፣ ብድር ይሰጣል፣ እንዲሁም አባሉ ለተበደረው ወይም ለቆጠበው ወይም ለወደፊት ለሚቆጥበው ገንዘብ ከገንዘብ ቁጠባና ብድር የኀብረት ሥራ ማህበሩ ጋር ውል በመግባት አረቦን ለተከፈለበት የገንዘብ መጠን ልክ ለሚደርሰው የሞት አደጋ

አነስተኛ የብድር የሕይወት መድን ዋስትና አገልግሎት ሊሰጥ ወይም ሊገባ ይችላል፡፡

10. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (8 እና (9 ዝርዝር አፈጻጸም በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

22. <u>መነሻ ካፒታል</u>

1. ማንኛውም መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማኅበር በሚያቀርበው የሥራ ዕቅድ እና የአዋጭነት ጥናት መሠረት ቢያንስ የመጀመሪያ ዓመት የሥራ ማስኬጃ ወጪዎቹን መሸፈን የሚያስችል ካፒታል ይዞ መመሥረት አለበት፡፡
2. የኅብረት ሥራ ማኅበራት ዩኒዬን ሊመሠረት የሚችለው በተደረገው የአዋጭነት ጥናት መሠረት ዕቅዳቸውን ለመፈፀም እንዲያስችል በጠቅላላ ጉባኤ ልዩ ውሳኔ መሰረት አባል የኅብረት ሥራ ማህበራት ቢያንስ የጠቅላላ ካፒታላቸውን 25% ያህል ዕጣ መግዛት ሲችሉ ነው፡፡
3. የኅብረት ሥራ ማኅበራት ፌዴሬሽን ሊመሠረት የሚችለው በተደረገው የአዋጭነት ጥናት መሠረት ዕቅዳቸውን ለመፈፀም እንዲያስችል በጠቅላላ ጉባኤ ልዩ ውሳኔ መሰረት አባል የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒየኖች ቢያንስ የጠቅላላ ካፒታላቸውን 30% ያህል ዕጣ መግዛት ሲችሉ ነው፡፡

23. <u>ከአባላት ዉጭ ለሌሎች አገልግሎት ስለመስጠት</u>

1. የኅብረት ሥራ ማኅበራት ከአባላት ዉጭ የሚሰጡት አገልግሎት በሚመሠረተው ውል መሠረት ሆኖ ለሚከተሉት ዓላማዎች ይሆናል፡-
   ሀ) መንግስት ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ሲል በብድር ከመንግስት ካዝናወጪ ተደርጎ የሚቀርቡ ግብዓቶችን ለማሰራጨት፤
   ለ) ፍላጎትና አቅርቦትን ለማመጣጠን በመንግስት በኩል የሚቀርቡ የፍጆታ ዕቃዎችን ለማሰራጨት፤
   ሐ) ከልዩ ልዩ ድጋፍ ሰጪ አካላት ለህብረተሰቡ የሚቀርቡ ተዘዋዋሪብድሮች እና ማህበራዊ አገልግሎቶችን ለማሰራጨት፤ እና
   መ) በእርሻ ሥራ ላይ ለተሰማሩ አርሶ አደሮች የምርት ማሳደጊያ ግብአቶችንለማቅረብ እና ምርታቸውን ለመረከብ።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ዝርዝር አፈጻጸም በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ይወሰናል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የኅብረት ሥራ ማኅበር አባላት መብትና ግዴታ

### 24.የኅብረት ሥራ ማኅበር አባል ለመሆን መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች

1. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2 እና (3 የተመለከቱትን የሚያሟላ ማንኛውም ሰው የኅብረት ሥራ ማኅበር አባል ለመሆን ይችላል፡፡
2. አባልነቱ ለመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር ከሆነ፡-
   ሀ) ዕድሜው 18 ዓመት የሞላው፤
   ለ) የኅብረት ሥራ ማኅበሩን ዕጣ ለመግዛትና የመመዝገቢያ ክፍያ ለመክፈልየሚችል፤
   ሐ) የኅብረት ሥራ ማኅበሩን ዓላማና መተዳዳሪያ ደንብ የተቀበለና ግዴታዎችን ለመፈጸም ፈቃደኛ የሆነ፤
   መ) ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በወጡት ደንቦችና መመሪያዎች የተወሰኑ ሁኔታዎችን የሚያሟላ፡፡
3. አባልነቱ ከመሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማኅበር በላይ ለሆነ ኅብረት ሥራ ማኅበር ከሆነ አግባብ ባለው ባለሥልጣን ተመዝግቦ ሕጋዊ ሰውነት ያገኘ የኅብረት ሥራ ማኅበር መሆን አለበት፡፡

### 25.የአባላት መብትና ግዴታ

1. ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማኅበር አባል  የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል:-
   ሀ) በተሳትፎው መጠን  አባሉ ወይም ተወካዩ በኅብረት ሥራ ማኅበሩየሚሰጠውን አገልግሎትና ጥቅም የማግኘት፤
   ለ) አባሉ ወይም ተወካዩ በኅብረት ሥራ ማኅበሩ ጉባዔዎች ላይ የመካፈልናድምፅ የመስጠት፤
   ሐ) አባሉ ወይም ተወካዩ በኅብረት ሥራ ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ በመገኘት የመምረጥና የመመረጥ፤
   መ) መብቶቹ እና ጥቅሞቹ ተከብረውለት በጥያቄው መሠረት ከኅብረት ሥራ ማህበሩ የመሰናበት፤
   ሠ) አባሉ ስለ ኅብረት ሥራ ማህበሩ እንቅስቃሴ መረጃ የማግኘት፤

   መብት አለው።
2. ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር አባል የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

ሀ) የኅብረት ሥራ ማኅበሩን መተዳደሪያ ደንብ፣ መመሪያዎችና ውሣኔዎች የማክበር፤

ለ) በኅብረት ሥራ ማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብና መመሪያ መሠረት የሚሠሩ ሥራዎችን የመሥራት፤

ሐ) የኅብረት ሥራ ማኅበሩን የጋራ ንብረት የመንከባከብ፤

መ) አባሉ በገባው ውል ወይም ስምምነት መሠረት ወደ ገበያ ከሚያቀርበውምርት እና ከገበያ ከሚገዛው አገልግሎት ወይም ምርት ውስጥ መጠኑ በመተዳደሪያ ደንብ በሚወሰነው መሠረት ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ጋር የግብይት ግንኙነት የማድረግ፤

ሠ) ይህን አዋጅ፣ ይህን አዋጅ መሠረት አድርገው የሚወጡ ደንቦችን እና መመሪያዎችን የማክበር፡፡

26.<u>ከአባልነት ስለመሰናበት</u>

1. ማንኛውም አባል በራሱ ፈቃድ ከኅብረት ሥራ ማኅበሩ ሊወጣ ይችላል፡፡
2. ማንኛውም አባል በተደጋጋሚ ግዴታዎችን ባለማክበሩ ወይም በኅብረት ሥራ ማህበሩ ላይ ጥፋት በመፈጸሙ ምክንያት ከኅብረት ሥራ ማኅበሩ እንዲወጣ በጠቅላላ ጉባዔ ሊወሰንበት ይችላል፡፡
3. ማንኛውም ከኅብረት ሥራ ማኅበሩ የተሰናበተ አባል የኅብረት ሥራ ማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ በሚፈቅደው መሠረት መብቱ ይጠበቅለታል፡፡
4. በራሱ ፈቃድ ከአባልነት የተሰናበተ አባል ወደ ኅብረት ሥራ ማህበሩ ለመመለስ ጥያቄ ካቀረበ ከአንድ የበጀት ዓመት በኋላ በሥራ አመራሩ ውሳኔ ሊመለስ ይችላል፡
5. ግዴታውን ባለመወጣቱ ከአባልነት የተሰናበተ አባል ጥያቄውን ካቀረበ ከአንድ በጀት ዓመት በኋላ በጠቅላላ ጉባኤ በሚሰጠው ውሳኔ መሠረት ሊመለስ ይችላል፡፡
6. ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ጋር በተያያዘ በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከአባልነት የተሰናበተ አባል ከተሰናበተበት ዓመት ጀምሮ በሚታሰብ ከአምስት በጀት ዓመት በኋላ በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ መሠረት ወደ አባልነት ሊመለስ ይችላል፡፡
7. በማንኛውም ምክንያት የተሰናበተ አባል የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ተመልሶ አባል ለመሆን ይችላል፤ ሆኖም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) እና (6) መሠረት የተሰናበተ አባል ተመልሶ አባል ለመሆን የሚችለው በጠቅላላ ጉባዔው ውሣኔ ሲፈቀድለት ብቻ ነው፡፡

27.**ስለ ዕጣ ክፍያ**

1. ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ሥራውን ለማንቀሳቀስ የሚያስፈልገውን ካፒታል ማግኘት እንዲችል እኩል ዋጋ እና ብዛት ያላቸውን ዕጣዎች በጠቅላላ ጉባኤ አስወስኖ እንዲሸጡ ያደርጋል፡፡
2. ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ሲመሠረት በጠቅላላ ጉባኤ እንዲሸጥ ከተወሰነው የዕጣ መጠን ውስጥ ቢያንስ አንድ አምስተኛው ከአባላት ይሰበሰባል፡፡ እንደዚሁም ቀሪውን ዕጣ ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት አራት ዓመታት ውስጥ ለአባላት መሸጥ ይኖርበታል፡፡
3. በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ መሠረት እንዲሸጥ የተወሰነ የዕጣ መጠን ሲጠናቀቅ ተጨማሪ ካፒታል ካስፈለገ ተጨማሪ ዕጣዎች እንዲሸጡ የኅብረት ሥራ ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት እንደገና ሊወስን ይችላል፡፡
4. የኅብረት ሥራ ማህበሩ የሚሸጠው ዕጣ በጥሬ ገንዘብ ወይም በዓይነት የሚከፈል ሊሆን ይችላል፡፡ በዓይነት የሚከፈል ዕጣ መጠን በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ይወሰናል፡፡
5. ማንኛውም የመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር አባል በጠቅላላ ጉባኤ ተወስኖ ከተሸጠው የዕጣ መጠን 10% በላይ ድርሻ ሊኖረው አይችልም፡፡
6. ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን እና ፌዴሬሽን አባል በጠቅላላ ጉባኤው እንዲሸጥ ከተወሰነው የዕጣ መጠን 50 % በላይ ድርሻ ሊኖረዉ አይችልም፡
7. ቀደም ሲል በአባል ተይዞ የነበረ ዕጣ በአራት ዓመት የጊዜ ገደብ ውስጥ ካልተሸጠ ለጠቅላላ ጉባኤ ልዩ ውሳኔ እንዲቀርብ ይደረጋል፡፡
8. ለጠቅላላ ጉባኤ ልዩ ውሳኔ ቀርበው ዕጣዎቹ እንዲሸጡ ካልተወሰነ አግባብ ያለው ባለሥልጣን የኅብረት ሥራ ማህበሩ የሂሳብ መግለጫዎች እንደገና ተስተካክለው እንዲዘጋጁ ማድረግ አለበት፡፡
9. በአራት ዓመት ውስጥ ያልተሸጡትን ዕጣዎች በስማቸው ይዘው የቆዩት አባላት በገቡት ውል እና በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ በተወሰነው የወለድ መጠን መሰረት ወለድ እንዲከፍሉ ይደረጋል፡፡ በሚቀርበው ማስረጃ መሰረትም ኪሳራ ይከፍላሉ፡፡

28.<u>የአባላት መዝገብ ስለ ማደራጀት</u>

1. ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማኅበር የአባላትን መዝገብ ማደራጀትና መያዝ አለበት፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተደራጀ የአባላት መዝገብ የሚከተሉትን ዝርዝር ይይዛል፦
   ሀ) መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበር ከሆነ የእያንዳንዱን አባል ስም፣ አድራሻ፣ ሥራ፣ ዕድሜ እና ጾታ የያዘ ሲሆን ከመሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበር በላይ ከሆነ ስም፣ አድራሻ፣ የተመሰረተበት ዓመተ ምሕረት እና የተሰማራበት የሥራ መስክ፤
   ለ) አባል የሆነበት ወይም አባልነቱን ያቋረጠበት ቀን፤
   ሐ) እያንዳንዱ አባል የያዘውን የዕጣ መጠን እና የከፈለውን የመመዝገቢያ ክፍያ፤
   መ) በመተዳደሪያ ደንቡ የተወሰኑ ሌሎች ዝርዝሮች።

29.<u>ስለ ድምጽ አሰጣጥ</u>

1. ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ውሳኔ የሚያፀድቀው በአብላጫ ድምፅ (ሃምሳ ሲደመር አንድ ነው፤ ሆኖም ግን ልዩ ውሳኔ የሚፈልጉ ጉዳዮች በሁለት ሶስተኛ ድምፅ መጽደቅ ይኖርባቸዋል፡፡
2. ማንኛውም አባል ያለው የዕጣ መጠን ከግምት ውስጥ ሳይገባ በኅብረት ሥራ ማኅበር ስብሰባ ላይ ተገኝቶ የሚሰጠው ድምጽ አንድ ብቻ ይሆናል፡፡
3. ማንኛውም የመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበር አባል በስብሰባ ላይ ተገኝቶ ራሱ ድምፅ መስጠት ይኖርበታል፤ ሆኖም የመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት ቁጥር ከ500 በላይ ከሆነ ድምጽ በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡
4. በኅብረት ሥራ ማኅበር ውክልና ስለሚሰጥበት ሁኔታ አግባብ ያለው ባለሥልጣን በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡
5. ከመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበር በላይ ባሉት ኅብረት ሥራ ማኅበራት ድምጽ የሚሰጠው በተወካዮች አማካኝነት ይሆናል፡፡
6. በማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዮን ወይም የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን ጠቅላላ ጉባዔ በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ በተወሰነው መሠረት ከእያንዳንዱ አባል ኅብረት ሥራ ማህበር ቢያንስ አንድ ተወካይ መገኘት አለበት፤ አወካከሉም አግባብ ያለው ባለስልጣን በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡
7. የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬንና የፌዴሬሽን የሥራ አመራር ኮሚቴ ምርጫ ድምጽ አሰጣጥ በተመለከተ በመተዳደሪያ ደንቡ በሚወሰነው መሰረት ይሆናል፡

**30.ዕጣን ወይም ጥቅምን ስለማስተላለፍ**

1. ማንኛውም አባል በኅብረት ሥራ ማኅበር ውስጥ የያዘውን ዕጣ ወይም ጥቅምለማስተላለፍ የሚችለው፡-
   ሀ) ዕጣውን ወይም ጥቅሙን ከሦስት ዓመት ላላነሰ ጊዜ ይዞት የቆየ፤ እና
   ለ) የማስተላለፉ ተግባር የሚፈፀመው በሥራ አመራር ኮሚቴ የተፈቀደ፣
   ሲሆን ነው፡፡
2. አንድ የመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበር አባል ሲሞት ዕጣው ወይም ጥቅሙ በሕግ ለመውረስ ለሚችል ወራሹ ይተላለፋል፡፡ ይህም የሚሆነው ወራሹ የኅብረት ሥራ ማኅበሩ አባል ከሆነ ወይም ለመሆን ፈቃደኝነቱን ከገለጸ ነው፡፡
3. ወራሹ የኅብረት ሥራ ማኅበሩ አባል ካልሆነ ወይም አባል ለመሆን የማይፈልግ ወይም የማይፈቀድለት ከሆነ የሟቹ የዕጣው ዋጋ እና ጥቅም ይከፈለዋል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ዕጣ ወይም ጥቅም የሚተላለፍለት አባል ዕጣው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 27 (5) የተወሰነውን ገደብ የሚያልፍ ሆኖ ሲገኝ ልዩነቱ በገንዘብ ይከፈለዋል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የተደረገ ማስተላለፍ ወይም ክፍያ ሦስተኛ ወገኖች በኅብረት ሥራ ማኅበሩ ላይ በሚያቀርቡት ጥያቄ ምክንያት አይሻርም፡፡

## ክፍል አራት

## ስለኅብረት ሥራ ማኅበር አመራር አካላት እናተቀጣሪ ሰራተኞች

**31.ስለኅብረት ሥራ ማኅበር የበላይ አካል**

የማንኛውም ኅብረት ሥራ ማኅበር የበላይ አካል የኅብረት ሥራ ማኅበሩ ጠቅላላ ጉባኤነው፡፡

**32.የጠቅላላ ጉባኤ ሥልጣንና ተግባር**

የኅብረት ሥራ ማኅበር ጠቅላላ ጉባኤ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

1. የኅብረት ሥራ ማኅበሩን አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴዎች እየገመገመ ውሣኔዎችን ያስተላልፋል፤
2. የኅብረት ሥራ ማኅበሩን መተዳደሪያ ደንብና ውስጠ ደንብ ያጸድቃል፣ ያሻሽላል፤
3. የኅብረት ሥራ ማኅበሩን የሥራ አመራር ኮሚቴ፣ የቁጥጥር ኮሚቴ እና የሌሎች ንዑሣን ኮሚቴዎች አባላት ይመርጣል፤ ይሽራል፤
4. የኅብረት ሥራ ማኅበሩን የዕጣ መጠን ይወስናል፤

5. የኅብረት ሥራ ማኅበሩን የተጣራ ትርፍ ድልድል ይወስናል፣
6. በኦዲት ሪፖርት ላይ መክሮ ውሳኔ ይሰጣል፣
7. የሥራ ክንውን ሪፖርቶችን ያዳምጣል፣ ተገቢውን ውሣኔ ይሰጣል፣
8. በዚህ አዋጅ መሠረት የኅብረት ሥራ ማህበሩ ከሌላ የኅብረት ሥራ ማህበር ጋር እንዲዋሀድ ወይም የኅብረት ሥራ ማህበሩ በሁለት ወይም ከዚያ በላይ እንዲከፈል ወይም እንዲፈርስ በአባላት ጠቅላላ ጉባዔ ልዩ ውሳኔ ይወስናል፣
9. የኅብረት ሥራ ማኅበሩን ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና በጀት ያጸድቃል፣
10. በአባልነት መቀበልንና ከአባልነት ስንብትን ከሥራ አመራር ኮሚቴ በሚቀርብለት ሪፖርት መሠረት ያፀድቃል፣
11. በሥራ አመራር ኮሚቴና ሌሎች ኮሚቴዎች የሚቀርቡለትን ማናቸውም ጉዳዮች በመተዳደሪያ ደንብ ውስጥ በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ይወስናል፡፡

33. <u>ጠቅላላ ጉባኤ ስለመጥራት</u>

1. የኅብረት ሥራ ማኅበር ጠቅላላ ጉባኤ ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ ይሰበሰባል::
2. የኅብረት ሥራ ማህበሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ በድምጽ ብልጫ ሲወስን ወይም ከጠቅላላ አባላቱ መካከል አንድ ሦስተኛው ስብሰባ እንዲጠራ ሲጠይቁ የ15 ቀን ቅድሚያ ማስታወቂያ በማውጣት አስቸኳይ የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ከጠቅላላ አባላቱ መካከል አንድ ሦስተኛ የሚሆኑት አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ እንዲጠራ ጠይቀው የሥራ አመራር ኮሚቴ ጥሪ ያላደረገ እንደሆነ አግባብ ያለው ባለሥልጣን ጥሪውን ያደርጋል፣ በዚህ ጊዜ ይህ አስቸኳይ የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ በሥራ አመራር ኮሚቴ እንደተጠራ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ይቆጠራል፡፡
4. የኅብረት ሥራ ማህበራት ምልዓተ ጉባዔ ተሟልቷል የሚባለው፡-
   ሀ) መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ከሆነ ከጠቅላላ የኅብረት ሥራ ማህበራቱ አባላት ወይም ተወካዮች ዉስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ሲገኙ፣ ወይም
   ለ) አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ከሆነ ከጠቅላላ የኅብረት ሥራ ማህበራቱ አባላት ወይም ከተወካዮች ዉስጥ ሁለት ሦስተኛ የሚሆኑት ሲገኙ፣
   
   ይሆናል፡፡

34. <u>የሥራ አመራር ኮሚቴ</u>

1. እያንዳንዱ ኅብረት ሥራ ማኅበር ቁጥራቸውና አመራረጣቸው በመተዳደሪያ ደንቡ የሚወሰን በኅብረት ስራ ማህበሩ አባላት ታማኝና ተቀባይነት ያላቸው እንዲሁም

ኃላፊነትን ሊወጡ የሚችሉ አባላትን የያዘ ለጠቅላላ ጉባኤ ተጠሪ የሆነ የሥራ አመራር ኮሚቴ ይኖረዋል፡፡

2. የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት የሥራ ዘመን ሦስት ዓመት ይሆናል፡፡
3. የማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር የሥራ አመራር ኮሚቴ አባል ከሁለት ተከታታይ የሥራ ዘመን በላይ ሊመረጥ አይችልም፤ ሆኖም የአመራር ኮሚቴ አባል የሥራ ዘመኑን ጨርሶ ከተሰናበተ ከአንድ የበጀት ዓመት በኋላ ዳግም ሊመረጥ ይችላል፡፡
4. የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት በተመረጡበት የሥራ ዘመን ውስጥ በማናቸውም ጊዜ በጠቅላላ ጉባኤ ሊሻሩ ይችላሉ፡፡
5. የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት በማናቸውም ምክንያት ሥራቸውን ሲለቁ በሥራ ዘመናቸው ያከናወኑትን ተግባራት የማስመርመር ግዴታ አለባቸው፡፡
6. የሥራ አመራር ኮሚቴ ምርጫ ከሁለተኛው ምርጫ ዓመት ጀምሮ በየዓመቱ ቢያንስ አንድ ሦስተኛውን የሥራ አመራር የኮሚቴ አባላት በመተካት ይሆናል፤ አተካኩም አግባብ ያለው ባለሥልጣን በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡
7. ቁጥራቸው የሚፈቅድ አባል ሴቶች በሚገኙበት ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ውስጥ ቢያንስ 30% አመራር በሴት አባላት መያዝ አለበት፡፡

35.<u>የሥራ አመራር ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር</u>

የሥራ አመራር ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባሩ በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳዳሪያ ደንብ የሚወሰን ሆኖ በተለይ የሚከተሉትን ያካትታል፡-

1. የስብሰባ ቃለ ጉባኤዎችን በጽሑፍ ይይዛል፤ መዛግብትን ያደራጃል፤
2. የኅብረት ሥራ ማህበሩን መዛግብትና የሂሣብ ሰነድ በሚገባ ይይዛል፤
3. የኅብረት ሥራ ማህበሩን ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፤ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤
4. በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ጠቅላላ ጉባኤውን ይጠራል፤
5. የጠቅላላ ጉባኤ ውሣኔዎችን ያስፈጽማል፤
6. የኅብረት ሥራ ማህበሩን የሥራ እንቅስቃሴ ይመራል፣ ለጠቅላላ ጉባኤ ሪፖርት ያቀርባል፤
7. በጠቅላላ ጉባዔ በፀደቀው የኦዲት ሪፖርት መሰረት በበጀት አመቱ ውስጥ የትርፍ ክፍፍል ያደርጋል፡፡

36.**የቁጥጥር ኮሜቴ**

1. ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማኅበር ቁጥራቸው እና አመራረጣቸው በመተዳዳሪያ ደንቡ የሚወሰን ከሶስት የማያንሱ አባላትን የያዘ ለጠቅላላ ጉባኤ ተጠሪ የሆኑ የቁጥጥር ኮሚቴ ይኖረዋል፡፡
2. የቁጥጥር ኮሚቴ አባላት የሥራ ዘመን ሦስት ዓመትሆኖ ከሁለት ተከታታይ የሥራ ዘመን በላይ ሊመረጡ አይችሉም፤ በተመረጡበት የሥራ ዘመን በማናቸውም ጊዜ በጠቅላላ ጉባኤ ሊሻሩ ይችላሉ፡፡
3. የቁጥጥር ኮሚቴ ምርጫ ከሁለተኛው ዓመት ጀምሮ በየዓመቱ ቢያንስ አንድ ሦስተኛውን የኮሚቴ አባላት በመተካት የሚካሄድ ይሆናል፡፡
4. የማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር የቁጥጥር ኮሚቴ አባል የሥራ ዘመኑን ጨርሶ ከተሰናበተ ከአንድ የበጀት ዓመት በኋላ ዳግም ሊመረጥ ይችላል፡፡

37.**የቁጥጥር ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር**

የቁጥጥር ኮሚቴ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. የሥራ አመራር ኮሚቴ ኃላፊነቱን በትክክል መወጣቱን ይከታተላል፤
2. የኅብረት ሥራ ማህበሩ ገንዘብና ንብረት በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፤
3. የኅብረት ሥራ ማህበሩ ልዩ ልዩ እንቅስቃሴዎች በሕግ፣ በኅብረት ሥራ ማኅበሩ መተዳዳሪያ ደንብ እና ውስጠ ደንብ መሠረት መከናወቸውን ይከታተላል፤
4. የጠቅላላ ጉባኤ ውሣኔዎችን ያስፈጽማል፤
5. በጠቅላላ ጉባኤ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል፡፡

38.**ስለሌሎች ንዑሣን ኮሚቴዎች**

ሌሎች ንዑሣን ኮሚቴዎች በኅብረት ሥራ ማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ሊቋቋሙ ይችላሉ፡፡

39.**ስለኅብረት ሥራ ማህበሩ ሥራ አስኪያጅ እና ተቀጣሪ ሠራተኞች**

1. ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ተጠሪነቱ ለሥራ አመራር ኮሚቴ የሆነ ሥራ አስኪያጅ ሊቀጥር ይችላል፡፡
2. ማንኛውም የህብረት ስራ ማህበር ሥራ አስኪያጅ ወይም ሰራተኛ ሲቀጥር የተቀ ጣሪውን የግል ንብረት እና ሀብት መረጃ በተዘጋጀው የሀብት ማስመዝገቢያ ቅፅ ላይ አስመዝግቦ ማስፈረም አለበት፤ ዝርዝር አፈፃፀሙ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

3. ሥራ አስኪያጁም የኅብረት ሥራ ማህበሩን የዕለት ተዕለት ተግባራት ይመራል፤ በተሰጠው የሥራ ዝርዝር እና ውክልና መሠረት እንዲሁም በሥራ አመራር ኮሚቴ የሚሰጡትን ሥራዎች ያከናውናል፡፡
4. ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ተጠሪነታቸው ለሥራ አስኪያጅ የሆኑ የማህበሩን የዕለት ተዕለት ሥራ የሚያንቀሳቅሱ ተቀጣሪ ባለሙያዎች ይኖሩታል፡፡
5. አግባብ ያለው ባለሥልጣን ስለሠራተኞች አቀጣጠር እና አስተዳደር መመሪያ ያወጣል፡፡

## ክፍል አምስት

## የኅብረት ሥራ ማኅበር ልዩ መብቶች

### 40.ለኅብረት ሥራ ማኅበር ዕዳ ክፍያ ቅድሚያ ስለመስጠት

በማንኛውም ሕግ በሌላ ሁኔታ የተደነገገ ቢኖርም ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማኅበር ከአንድ አባል ወይም ተቀጥረው ከሚሰሩ ሰራተኞች ወይም ከሌሎች አካላት ላይ የሚፈልገው የዕዳ ክፍያ የመንግሥት ዕዳን ሳይጨምር ከሌሎች ዕዳዎች ክፍያ ቅድሚያ ይሰጠዋል፡፡

### 41.የአባላትን ዕጣ ወይም ጥቅም ስለማቻቻል

የማንኛውም አባል ዕጣ ወይም ጥቅም ኅብረት ሥራ ማኅበሩ ለሚፈልግበት የዕዳ ክፍያ ማቻቻያ ሊደረግ ይችላል፡፡

### 42.ዕጣን ወይም ጥቅምን ለማስከበር ወይም ለመሸጥ ስላለመቻል

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 41 ከተደነገገው በስተቀር ማንኛውም አባል በኅብረት ሥራ ማኅበሩ ውስጥ የሚኖረው ዕጣ ወይም ጥቅም አባሉ ላለበት ዕዳ ማስከፈያ ሲባል ሊከበር ወይም ሊሸጥ አይችልም፡፡

### 43.የመንግስት ድጋፍ

1. በኢንቨስትመንት ሕጎችና በሌሎች ሕጎች የተፈቀዱት ማበረታቻዎች ለኅብረት ሥራ ማኅበራት መፈቀዱ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚደራጅ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማኅበር የሚከተሉትን ድጋፍና ማበረታቻ ያገኛል፡-
   ሀ) የሚያገኘው ገቢ ከገቢ ግብር ነፃ ይሆናል፤ ሆኖም ግለሰብ አባላት ከኅብረት ሥራ ማኅበራቸዉ ጋር በሚያደርጉት ተሳትፎና በገዙት ዕጣ መጠን ከሚያገኙት ገቢ ላይ አግባብ ባለዉ ሕግ መሰረት የገቢ ግብር ይከፍላሉ፤
   ለ) የኅብረት ሥራ ማህበራት ለሚያከናውኑት ተግባራት እና ለሚሰጡት አገልግሎት የሚውል መሬት ከክልል በምደባ ያገኛሉ፤

ሐ ከብሔራዊ የኅብረት ሥራ ማህበር ሥልጠና ተቋም የኅብረት ሥራ ማህበር እንቅስቃሴ ማኅልበቻና የሰው ሃይል አቅም ግንባታ ሥልጠና ድጋፍ ያገኛሉ፤

መ ከፌደራሉ ወይም ከክልል መንግሥት አግባብ ያለው ባለሥልጣን በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰኑ ሌሎች ድጋፎችን ያገኛሉ፡፡

2. ማንኛውም መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር ከንብረቱ ጋር በተያያዘ በፍርድ ቤት ላለበት ክርክር ከሚከፈል የዳኝነት ክፍያ ነፃ ናቸው፡፡

## ክፍል ስድስት

## የኅብረት ሥራ ማኅበራት ንብረትና ገንዘብ

### 44.የኅብረት ሥራ ማኅበራት ንብረትና ገንዘብ የማይከፋፈል ስለመሆኑ

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 45 እና 59 መሠረት ለአባላት እንዲከፋፈል ከሚወሰነው በስተቀር የኅብረት ሥራ ማኅበር ንብረትና ገንዘብ ለአባላቱ ወይም ለሌላ ወገን አይከፋፈልም፡፡

### 45.የተጣራ ትርፍ አደላደል

1. ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ከተጣራ ትርፍ ላይ 30 % እየቀነሰ በመጠባበቂያ ሂሳብ ያስቀምጣል፤ ለመጠባበቂያነት የሚቀነሰው ገንዘብ የኅብረት ሥራ ማህበሩን ካፒታል 30% እስኪሞላ ድረስ የሚቀጥል ሆኖ የሚቀመጠውም በኅብረት ሥራ ማኅበሩ ቁጠባ ሂሳብ ውስጥ ይሆናል፡፡
2. ለመጠባበቂያ ከተቀነሰ በኋላ የሚቀረው 70 % የተጣራ ትርፍ ክፍፍል የኅብረት ሥራ ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ በሚወስነው መሠረት ይሆናል፤ ሆኖም ጠቅላላ ጉባኤው በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ከዚሁ የተጣራ ትርፍ ውስጥ ለትምህርት ወይም ለስልጠና ወይም ለማበረታቻ ወይም ለኦዲት ፈንድ ወይም ለማህበራዊ አገልግሎት ደልድሎ ሊመድብ ይችላል፡፡
3. የኅብረት ሥራ ማህበሩ አባላት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2 መሠረት ከሚያገኙት የተጣራ ትርፍ ውስጥ ተጨማሪ ዕጣ ሊገዙበት ይችላሉ፡፡

### 46.ስለኅብረት ሥራ ማህበራት ፈንድ ማቋቋም

1. የኅብረት ሥራ ማህበራት በሂደት ራሳቸውን ችለው በራሳቸው አቅም የኦዲት ወይም የሕግ አገልግሎት ወይም የአቅም ግንባታ ወይም የጥናትና ምርምር ወይም የፕሮሞሽንና ኮሚኒኬሽን ወይም የመሳሰሉትን ወጪዎች ለመሸፈን የሚረዳ የኅብረት ሥራ ፈንድ ማቋቋም ይችላሉ፡፡
2. በዚህአንቀጽንዑስአንቀጽ (1) መሠረትየሚቋቋመውፈንድ አደረጃጀት እና የፋይናንስ ምንጭ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

**47.ስለመበደር ወሰን**

የኅብረት ሥራ ማኅበሩ ከአባላት ወይም ከሌሎች ድርጅቶች የሚበደረው ብድር መጠን እና የብድሩ ሁኔታ በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳዳሪያ ደንብ በሚወሰነው መሠረት ይሆናል፡፡

**48.ስለማበደር ወሰን**

1. የኅብረት ሥራ ማኅበር ለአባላት ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት ለተቋቋመ ሌላ የኅብረት ሥራ ማህበር ካልሆነ በስተቀር ብድር መስጠት አይችልም፡፡
2. ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ለሚያበድረው ገንዘብ በጠቅላላ ጉባኤ ልዩ ውሳኔ መሠረት በመተዳደሪያ ደንብ ውስጥ የወለድ መጠን ይወስናል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1 መሠረት ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር የሚያ በድረው የብድር መጠንና የሚያበድርበት ሁኔታ የኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ በሚወሰነው መሰረት ይሆናል::
4. ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር የሚያበድረው ዓመታዊ የብድር መጠን በየዓመቱ በጠቅላላ ጉባኤ ተወስኖ በዕቅድ መያዝ አለበት::

**49.ስለዋስትና ዓይነት እና አማራጮች**

ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማኅበር ለሚሰጠው የብድር አገልግሎት የሚጠይቀውን የዋስትና ዓይነት እና አማራጮቹን በመተዳደሪያ ደንቡ ወስኖ መጠቀም ይችላል::

**ክፍል ሰባት**

**ስለ ኅብረት ሥራ ማህበራት ኦዲት እና ኢንስፔክሽን**

**50.ስለ ኦዲት**

1. አግባብ ያለው ባለሥልጣን በኅብረት ሥራ ማህበሩ የበጀት ዓመት መሰረት ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ የማንኛውንም ኅብረት ሥራ ማኅበር ሂሣብ ራሱ ወይም እሱ በሚወክለው ሰው ኦዲት ያደርጋል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚደረግ ኦዲት ያልተከፈለ ዕዳ ካለበት ይህንኑ ዕዳውን እና የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ፣ የዋስትና ሰነዶች፣ የሀብቱን ዋጋ፣ ኃላፊነቱንም ኦዲት ማድረግ ይጨምራል፡፡
3. የኦዲት ሪፖርቱ ተጠናቆ ለኅብረት ሥራ ማህበሩ ከደረሰበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ ለጠቅላላ ጉባኤ መቅረብ አለበት፡፡

4. የኦዲት ሪፖርቱ በጠቅላላ ጉባኤ ከፀደቀ በኋላ በኦዲት ሪፖርቱ ላይ ቅሬታ አለኝ የሚል ወገን ሒሳቡ እንደገና ይታይልኝ በማለት የሚያቀርበዉ ጥያቄ ቢኖር በ30 ቀናት ዉስጥ መቅረብ አለበት፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ በኦዲት ሪፖርቱ ላይ ያልቀረበ ቅሬታ እና እንደገና ይመርመርልኝ ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፡፡

51.<u>ስለኦዲተሮች ሥነ-ምግባር</u>

1. ማንኛውምኦዲተርየሚያቀርበውየኦዲትሪፖርት ውጤት የተመርማሪውን ኅብረት ሥራ ማህበር ትክክለኛ አቋም የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡
2. የኦዲት ተደራጊውን የኅብረት ሥራ ማህበር ትክክለኛ የሂሳብ አቋም የማይገልጽ እና ከፍ ወይም ዝቅ አድርጎ የኦዲት ሪፖርት በማቅረብ በኅብረት ሥራ ማህበሩ፣ በተመራጮች፣ በሠራተኞች፣ በሦስተኛ ወገኖች፣ በአበዳሪዎች እና በሌሎች ሰዎች ላይ ሆን ብሎ ጉዳት ያደረሰ ማንኛውም ኦዲተር አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

52.<u>ስለ ኢንስፔክሽን</u>

1. አግባብ ያለው ባለሥልጣን የአንድን ኅብረት ሥራ ማህበር አቋም፣ የሥራ አፈጻጸም፣ መዛግብት እና የገንዘብ ሁኔታ ኢንስፔክት ማድረግ ይችላል፡፡
2. የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት አብዛኛዎቹ ወይም ከጠቅላላው የኅብረት ሥራ ማህበሩ አባላት ወይም ተወካዮች ከአንድ ሦስተኛ ያላነሱ ሲጠይቁ አግባብ ያለው ባለሥልጣን ኢንስፔክት ያደርጋል፡፡
3. ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ከሥራ ባህሪው አንጻር ተቀባይነት ያለው የአፈጻጸም መለኪያ ስታንዳርዶች ጥቅም ላይ በማዋል የአፈጻጸም ደረጃውን ማስለካት አለበት፡፡
4. የኅብረት ሥራ ማህበራትን አቋም ለመለካት የሚያግዙ የአፈፃፀም መለኪያዎቹን በሚመለከት አግባብ ያለው ባለሥልጣን መመሪያ ያወጣል፡፡

53.<u>የኢንስፔክሽን እና የኦዲት ውጤትን ስለማስቀመጥ</u>

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 50 እና 52 መሠረት የተደረገ የኢንስፔክሽንና የኦዲት ውጤት ማንኛውም ሰው በቀላሉ ሊያገኘውና ሊያየው በሚችል አኳኋን አግባብ ባለው ባለሥልጣን እና በኅብረት ሥራ ማህበሩ ጽሕፈት ቤት ውስጥ መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

## 54.በኅብረት ሥራ ማኅበሩ ንብረትና ገንዘብ ላይ ጉድለት ሲደርስ ስለሚወሰድ እርምጃ

1. ኦዲት ወይም ኢንስፔክሽን በሚደረግበት ጊዜ የኅብረት ሥራ ማህበሩን ሥራ እንዲያካሂድ ኃላፊነት የተጣለበት ወይም ተጥሎበት የነበረው ሰው ወይም የኅብረት ሥራ ማህበሩ ሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት ወይም የቦርድ አባላት ወይም የቁጥጥር ኮሚቴ አባላት ወይም የሌሎች ኮሚቴ አባላት ወይም የኅብረት ሥራ ማኅበሩ ሥራ አስኪያጅ ወይም ሠራተኛ፡-
   ሀ) በዚህ አዋጅ፣ በደንቦቹ ወይም በመተዳደሪያ ደንቦቹ ወይም በጠቅላላ ጉባዔ ባልፀደቀ የበጀት እቅድ ያልተፈቀደ ክፍያ ፈጽሞ ከተገኘ፤
   ለ) አግባብ ያለው ባለስልጣን በሚያወጣው መመሪያ የተገለጹ የግዥ ስርዓትን ያልተከተሉ ውሎችን በመዋዋል ግዥዎችን እና ክፍያዎችን ፈፅመውከተገኙ፤
   ሐ) እምነትን በማጉደል ወይም ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት በኅብረት ሥራማኅበሩ ንብረት ላይ ጉዳት አድርሶ ከተገኘ፤ ወይም
   መ) የኅብረት ሥራ ማኅበሩ የሆነውን ገንዘብ አለአግባብ ከወሰደ፤ ተቆጣጣሪው ወይም መርማሪው ስለ ሁኔታው እንደ ጉዳዩ አግባብነት ለሥራ አመራር ኮሚቴ ወይም ለጠቅላላ ጉባኤ ወይም አግባብ ላለው ባሥልጣን ሪፖርት ያደርጋል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(1) መሠረት ሪፖርት የቀረበለት አግባብ ያለው ባለሥልጣን ጉዳዩ የሚመለከተውን ሰው በመጥራት መከላከያ መልስ ካለው በሁለት ተከታታይ የስራ ቀናት እንዲያቀርብ ያደርጋል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ጉድለት አድርሷል የተባለው ሰው ጥፋተኛ ሆኖ ሲገኝ ያጎደለውን ገንዘብ ወይም ንብረት ከነወለዱ እንዲሁም የሚወሰነውን ካሳና ኪሳራ እንዲመልስ ወይም እንዲከፍል አግባብ ያለው ባለስልጣን ይጠይቃል፤ ያጎደለው ሰው ፈቃደኛ ሆኖ ካልተገኘ አግባብ ያለው ባለሥልጣን የኅብረት ሥራ ማህበሩን በመወከል ተገቢው የፍትሐ ብሔር ክስ እንዲቀርብበት ያደርጋል፡፡

## ክፍል ስምንት

## ስለ ኅብረት ሥራ ማኅበራት መፍረስና ሂሣባቸውን ስለማጣራት

## 55.ስለ ኅብረት ሥራ ማኅበር መፍረስ

1. የኅብረት ሥራ ማኅበር ከሚከተሉት በአንዱ ምክንያት ይፈርሳል፡-
   ሀ) እንዲፈርስ በአባላት ጠቅላላ ጉባኤ ልዩ ውሣኔ ሲሰጥ፤

ለ) በመሰረታዊ የኅብረት ሥራ ማኅበር የአባላቱ ቁጥር በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 (2) እና (3) ከተጠቀሰው ቁጥር አንሶ ሲገኝ፤

ሐ) የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን እና ፌዴሬሽን መስራች አባላት ቁጥርበዚህአዋጅ ከተወሰነው ቁጥር ዝቅ ሲል፤

መ) ፍርድ ቤት እንዲፈርስ ሲወስን፤

ሠ) በኅብረት ሥራ ማህበሩ የሂሳብ ምርመራ ውጤት መሠረት የከሰረናየኪሳራውም መጠን የኅብረት ሥራ ማህበሩን ህልውና የሚያሳጣ መሆኑን አግባብ ያለው ባለሥልጣን ሲያረጋግጥና ይኸው በጠቅላላ ጉባኤ ሲጸድቅ፡፡

2. ጠቅላላ ጉባኤ ማንኛውንም የኅብረት ሥራ ማኅበር እንዲፈርስ ሲወስን አግባብላለው ባለሥልጣን የማፍረስ ውሳኔውን በሰባት ቀናት ውስጥ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

## 56.ስለሂሣብ አጣሪ

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 55 መሠረት አንድ የኅብረት ሥራ ማህበር እንዲፈርስ ሲወሰን አግባብ ያለው ባለሥልጣን ሂሣብ አጣሪ ሊመድብ ይችላል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የሂሣብ አጣሪውን የአገልግሎት ዋጋ ከየኅብረት ሥራ ማህበሩ ሂሣብ እንዲከፈል ይወስናል፡፡

2. ሂሣብ አጣሪው እንደተመደበ የኅብረት ሥራ ማህበሩን መዛግብት፣ ሰነዶችና ንብረት ይረከባል፡፡ በኅብረት ሥራ ማኅበሩ ንብረቶችና መብቶች፣ መዛግብትና ሰነዶች ላይ ጉዳት እንዳይደርስም አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል፡፡

## 57.የሂሣብ አጣሪው ሥልጣንና ተግባር

1. ሂሣብ አጣሪው የሂሣብ ማጣራትን ሥርዓት ከፍጻሜ ለማድረስ አስፈላጊው ሥልጣን ሁሉ ይኖረዋል፡፡ ሥራውን በሚገባ ለመፈጸም በተለይ የሚከተሉትን ያከናውናል፦

ሀ) ከኅብረት ሥራ ማኅበሩ የሚጠየቀውን ዕዳ መርምሮ የአከፋፈሉን ቅደም ተከተል ይወስናል፤

ለ) የኅብረት ሥራ ማኅበሩን ሀብትና ንብረት ይሰበስባል፤

ሐ) የኅብረት ሥራ ማኅበሩ ጠቅላላ ስብሰባ ባጸደቀው የሂሣብ ማጣራት እቅድመሠረት ሀብቱንና ንብረቱን ያከፋፍላል፤

መ) የሂሣብ ማጣራቱን ሥራ በሚገባ ለመፈጸም ባስፈለገ መጠን የኅብረት ሥራ ማኅበሩን ሥራ ያካሂዳል፤

ሠ) ኅብረት ሥራ ማህበሩን በሚመለከቱ ክርክሮች ተወካይ ይሆናል፤

ረ) ለሂሣብ ማጣራቱ ሥራ መቃናት አስፈላጊ ሲሆን አባላቱን ለስብሰባ ይጠራል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ (ሐ) መሠረት የንብረት ክፍፍል ከመደረጉ በፊት ኀብረት ሥራ ማህበሩ የሚፈርስ ስለመሆኑ ሰፊ ሥርጭት ባለው ጋዜጣ ማስታወቂያ ያወጣል፡፡ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ ሁለት ወር ድረስ ተቃዋሚ ካልቀረበ የንብረት ክፍፍሉን ያደርጋል፡፡ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ከዚህ ጊዜ ገደብ በኋላ የሚቀርብ የመብት ጥያቄ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡
3. የሂሣብ አጣሪው የሂሣብ ማጣራቱን ሥርዓት እንደፈፀመ ሪፖርቱን አዘጋጅቶ አግባብ ላለው ባለሥልጣን ያቀርባል፤ የኅብረት ሥራ ማህበሩን መዛግብትና ሰነዶችን አግባብ ያለው ባለሥልጣን በሚያዘው ሥፍራ ያስቀምጣል፡፡

58.<u>ገንዘብ ጠያቂዎችን ስለመጥራት</u>

1. የገንዘብ ጠያቂዎች አከፋፈል ሂሣብ አጣሪው ሥራ በሚጀምርበት ጊዜ ባዘጋጀው የሂሣብ ሚዛን መሠረት ይፈጸማል፡፡
2. በሂሳብ አጣሪው አማካኝነት ለገንዘብ ጠያቂዎቹ የኅብረት ሥራ ማኅበሩ መፍረስ ተነግሯቸው አቤቱታቸውን እንዲያስታውቁና የሚጠይቁትንም ገንዘብ በማስረጃ ሰነድ እንዲያስደግፉ ያደርጋቸዋል፡፡
3. በኅብረት ሥራ ማህበሩ መዝገቦች ውስጥ ለተጻፉት ገንዘብ ጠያቂዎች ወይም በሌላ አኳኋን ለታወቁም ገንዘብ ጠያቂዎች በሪኮማንዴ ደብዳቤዎች በቀጥታ ይላክላቸዋል፤ ለሌሎቹ ግን ሰፊ ሥርጭት ባለው ጋዜጣ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ሁለት ተከታታይ ማስታወቂያ በማውጣት ይጠራቸዋል፡፡

59.<u>የገንዘብ ጠያቂዎችን መብት ስለመጠበቅ</u>

1. ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ገንዘብ ጠያቂዎች የሆኑት ካልተከፈላቸው ወይም የእነርሱን ገንዘብ ለመክፈል አስፈላጊ የሆነው ገንዘብ ተቀማጭ ካልተደረገ በቀር አጣሪዎች የኅብረት ሥራ ማህበሩን ንብረት በከፊልም ቢሆን ለኅብረት ሥራ ማህበሩ አባላት ማከፋፈል አይችሉም፡፡
2. የታወቁት ገንዘብ ጠያቂዎች ማስረጃቸውን ሳያቀርቡ የቀሩ እንደሆነ የሚከፈላቸው ገንዘብ ልክ በፍርድ ቤት ውሣኔ ይቀመጣል፡፡
3. ገንዘብ ጠያቂዎቹ ለሚፈልጉት ሂሣብ ተመጣጣኝ የሆኑ ዋስትናዎች ካልተሰጧቸው ወይም የማኅበሩ ንብረት አከፋፈል እነዚሁ ግዴታዎች እስኪከፈሉ ድረስ ሌላ ቀጠሮ ካልተያዘ በቀር ላልተፈጸመው ግዴታ ወይም በክርክር ላይ ላሉት የኅብረት ሥራ ማኅበሩ ግዴታዎች ተመጣጣኝ የሆነ ገንዘብ ተይዞ መቀመጥ አለበት፡፡

4. የኅብረት ሥራ ማኅበሩ ዕዳ ተከፍሎ ካለቀ ወይም ዕዳውን ለመክፈል በቂ የሆነ ገንዘብ መቀመጡ አግባብ ባለው ባለሥልጣን ከተረጋጠ በኋላ አጣሪዎች ቀሪውን የኅብረት ሥራ ማህበሩን ገንዘብ ለኅብረት ሥራ ማህበሩ አባላት በሚገባቸው መጠን ያከፋፍላሉ፡፡

60. <u>ማኅበርን ከመዝገብ ስለመሰረዝ</u>

የሂሣብ ማጣራት ሥራ እንደተፈጸመ የኅብረት ሥራ ማህበሩ የምዝገባ የምስክር ወረቀት አግባብ ላለው ባለሥልጣን ይመለሳል፤ አግባብ ያለው ባለሥልጣንም የኅብረት ሥራ ማህበሩን ከመዝገብ ይሠርዛል፤ የኅብረት ሥራ ማህበሩም ከመዝገብ ከተሠረዘበት ቀን ጀምሮ ሕልውናውን ያጣል፡፡

## <u>ክፍል ዘጠኝ</u>

## <u>ስለክርክር አወሳሰን</u>

61. <u>ጉዳዮችን በዕርቅ ስለመጨረስ</u>

1. በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 64 የተመለከቱት ክርክሮች ለሽምግልና ዳኝነት ከመቅረባቸው በፊት ተከራካሪ ወገኖች በሚመርጡት ሦስተኛ ወገን አስታራቂዎች በእርቅ መታየት ይችላሉ፡፡
2. ጉዳያቸውን በእርቅ ለመጨረስ እያንዳንዱ ወገን አንድ አስታራቂ ይመርጣል፤ የአስታራቂዎች ሰብሳቢ በሁለቱ ወገኖች ስምምነት ይመረጣል፡፡
3. የአስታራቂዎቹን ሰብሳቢ ለመምረጥ ሁለቱ ወገኖች ስምምነት ላይ ያልደረሱ እንደሆነ አግባብ ያለው ባለሥልጣን ሰብሳቢውን ይመረጣል፡፡

62. <u>ስለሽምግልና ዳኝነት</u>

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 64 የተመለከቱት የኅብረት ሥራ ማኅበራት ክርክሮች በእርቅ ያላለቁ እንደሆነ ለሽምግልና ዳኝነት ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡
2. የሽምግልና ዳኞቹ ክርክሮችን የሚሰሙትና ማንኛውም ተግባራትን ሁሉ የሚፈጽሙት በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ መሠረት ነው፡፡

63. <u>የሽምግልና ዳኞች አመራረጥ</u>

1. ለሽምግልና ዳኝነት ተግባር የሚመረጡ ሰዎች ቁጥራቸው ሦስት ሆኖ የማያዳሉና መልካም ስም ያላቸው ይሆናሉ፡፡
2. እያንዳንዱ ወገን አንድ የሽምግልና ዳኛ ይመርጣል፤ ለሽምግልና ዳኝነቱ ሰብሳቢ እንዲሆን የሚመረጠው ሦስተኛ ዳኛ በሁለቱም ወገኖች በጋራ ይመረጣል፡፡

3. ሰብሳቢውን ዳኛ ለመምረጥ ሁለቱ ወገኖች ስምምነት ላይ ያልደረሱ እንደሆነ አግባብ ያለው ባለሥልጣን ይመርጣል፡፡

64. **ለሽምግልና ዳኝነት ስለሚቀርቡ ክርክሮች**

የሽምግልና ዳኞቹ ስለ አንድ ኅብረት ሥራ ማኅበር አቋም፣ ስለሥራው አካሄድ ወይም ስለሥራው አፈጻጸም በተመለከተ በዕርቅ ያላለቁ የሚከተሉትን የሚመለከቱ ክርክሮች አይተው ለመወሰን ሥልጣን ይኖራቸዋል፡-

1. በአባላት ወይም በቀድሞ አባላትና ወይም በቀድሞ አባላት ወኪሎች ወይም በሞት በተለዩ አባላት መብት ስም ክርክር በሚያቀርቡ ሰዎች መካከል የሚነሳ ክርክር፤
2. በአባላት ወይም በቀድሞ አባላት ወይም በአባላት ወይም በቀድሞ አባላት ወኪሎች ወይም በሞት በተለዩ አባላት ወራሾችና በኅብረት ሥራ ማኅበሩ ሥራ አመራር ኮሚቴ አባል፣ በማናቸውም ሥራ አስኪያጅ፣ በወኪሉ ወይም በህብረት ስራ ማህበሩ ቅጥር ሠራተኛ መካከል የሚነሳ ክርክር፤
3. በኅብረት ሥራ ማኅበሩ ወይም በሥራ አመራር ኮሚቴ ወይም በማንኛውም የቀድሞ የሥራ አመራር ኮሚቴ አባል፣ ማንኛውም ሥራ አስኪያጅ፣ ወኪል ወይም ቅጥር ሠራተኛ ወይም የቀድሞ ሥራ አስኪያጅ፣ የቀድሞ ወኪል ወይም የቀድሞ ቅጥር ሠራተኛ ተጠሪው፣ ወራሾቹ ወይም ወኪሎቹ ወይም በሞት በተለዩ የኅብረት ሥራ ማህበሩ ሥራ አስኪያጆች፣ ወኪሎች ወይም ቅጥር ሠራተኞች መካከል የሚነሳ ክርክር፤
4. በአንድ ኅብረት ሥራ ማኅበርና በማንኛውም ሌላ ኅብረት ሥራ ማኅበር መካከል የሚነሳ ክርክር፡፡

65. **የሽምግልና ዳኞች የፍትሐ ብሔር ሥልጣን**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 64 መሠረት የሚታዩ ጉዳዮችን በተመለከተ ምስክሮችን ለመጥራት፣ ማስረጃዎችን ለማስቀረብ፣ ትዕዛዝም ለመስጠትና ሌላ ማንኛውንም ሕጋዊ እርምጃ ለመውሰድ የሽምግልና ዳኞች የፍትሐ ብሔር ችሎት ሥልጣን ይኖራቸዋል፡፡

66. **አፈጻጸም**

በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሰጥ ማንኛውም ውሣኔ፣ ትዕዛዝ ወይም ብይን በመደበኛ ፍትሐ ብሔር ችሎት እንደተሰጠ ተቆጥሮ አስፈላጊ ሲሆን ፍርድ ቤቶች ውሣኔው፣ ትዕዛዙ ወይም ብይኑ እንዲፈጸም የማስገደድ ሥልጣን ይኖራቸዋል፡፡

67.**ስለፍርድ ቤት ሥልጣን**

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 65 መሠረት በሽምግልና ዳኝነት በተሰጡ ውሣኔዎች ላይ ቅሬታ ያለው ሰው በክልል ሲሆን ስልጣን ላለው ለክልሉ ፍርድ ቤት ወይም በፌደራል ደረጃ ሲሆን ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 61 እና 62 የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው በእርቅ እና በሽምግልና ዳኝነት ጉዳያቸውንለ መጨረስ ካልተስማሙ ሥልጣን ላለው መደበኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላሉ፡፡

## ክፍል አሥር

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

68.**የይርጋ ዘመን**

የኅብረት ስራ ማህበር ከንብረት ጋር በተያያዘ ከሚፈፅመው ውል የሚመነጭ መብት ከ10 ዓመት በኋላ ቀሪ ይሆናል፡፡

69.**ስለኅብረት ሥራ ማህበር አድራሻ**

1. ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 10 መሠረት የተመዘገበ አድራሻ ይኖረዋል፤ የሚላኩለት መጥሪያዎች፣ ማስታወቂያዎች እና ሌሎች ግንኙነቶች ሁሉ በዚህ አድራሻ ይላካሉ፡፡
2. የኅብረት ሥራ ማህበሩ አድራሻውን ሲለውጥ በ30 ቀናት ውስጥ አግባብ ላለው ባለሥልጣን ማስታወቅ አለበት፡፡

70.**አግባብ ያለው ባለስልጣን ሥልጣንና ተግባር**

በሌሎች ሕጎች አግባብ ላላው ባለስልጣን የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ በኅብረት ሥራ ማህበራት አሠራር ውስጥ ጣልቃ ሳይገባ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡-

1. የኅብረት ሥራ ማህበራትን ያደራጃል፣ ይመዘግባል፣ ያጠናክራል፣ ይሰርዛል፤
2. የኅብረት ሥራ ማህበራት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት ወጥ ሆኖ እንዲጠናከር ያደርጋል፤
3. ኅብረት ሥራ ማህበራትን በተመለከተ ጥናት እና ምርምር ያካሂዳል፤
4. ኅብረት ሥራ ማህበራትን በተመለከተ የኢንስፔክሽን ሥራ ያከናውናል፣ የኦዲት እና የሕግ ምክር አገልግሎት ይሰጣል፤
5. የኅብረት ሥራ ማህበራትን የብቃት ደረጃ ያረጋግጣል፣ የደረጃ ዕውቅና ይሰጣል፤
6. የኅብረት ሥራ ማህበራትን እና ባለሙያዎችን አቅም ይገነባል፤

7. ለኅብረት ሥራ ማህበራት የምርት ግብይት ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፤
8. ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚመሩበትን የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

71.<u>የኅብረት ሥራ ማኅበር አማካሪ ምክር ቤት ስለማቋቋም</u>

1. ተጠሪነቱ ለእርሻና የተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር የሆነ የኅብረት ሥራ አማካሪ ምክር ቤት (ከዚህ በኋላ ምክር ቤት እየተባለ የሚጠራ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡
2. የምክር ቤቱ አባላት የኅብረት ሥራ ማኅበራትን በአገሪቱ ውስጥ የሚወክሉ ሰዎች ይሆናሉ፡፡
3. የምክር ቤቱ ሰብሳቢ በእርሻና የተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር የሚመደብ ይሆናል፡፡
4. የምክር ቤቱ አባላት አመራረጥ እና ብዛት በፌደራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ ይወሰናል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት የሚመረጡት የምክር ቤቱ አባላት የኅብረት ሥራ ሙያ ያላቸው እና ስለ ኅብረት ሥራ ዕድገት መሪ ሀሳብ የሚያቀርቡ፡-
   ሀ) ከኅብረት ሥራ ማህበራት ንቅናቄ፣ የኅብረት ሥራ ትምህርት ከሚሰጡ ዩኒቨርሲቲዎች እና ማሰልጠኛ ተቋማት፣
   ለ) ከኅብረት ሥራ ማህበራት ባለሙያዎች ማህበር፣
   ሐ) የኅብረት ሥራ ማህበራት ንቅናቄን ከሚደግፉ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች እና ታዋቂ ግለሰቦች፣ ይሆናሉ፡፡
6. የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን በፌደራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ የሚወሰን ሆኖ ከሦስት ዓመት ሊበልጥ አይችልም፤ ሆኖም የሥራ ዘመኑን የጨረሰ የምክር ቤቱ አባል ለሁለተኛ ጊዜ እንደገና ሊመረጥ ይችላል፡፡
7. ማንኛውም የምክር ቤት አባል በጽሑፍ አባልነቱን ሊለቅ ይችላል፡፡
8. የምክር ቤት አባላት ለሚሰጡት አገልግሎት ምንም ክፍያ አይሰጣቸውም፤ ሆኖም ግን ለሥራው ሲባል ያወጡት ወጪ በፌደራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ በሚወሰነው መሰረት ይተካላቸዋል፡፡
9. የምክር ቤት አባል በሚከተሉት ምክንያቶች ያለምንም ማስጠንቀቂያ ከአባልነት ሊሰናበት ይችላል፤
   ሀ) በከፍተኛ የሥነ-ምግባር ጉድለት፤
   ለ) ዘላቂ በሆነ ችሎታ ማነስ፤
   ሐ) የምክር ቤቱን ተአማኒነት የሚያጎድፍ ሥራ ፈፅሞ ሲገኝ፡፡

10. የምክር ቤቱ ስብሰባ ጊዜ፣ ቦታ እና የስብሰባው ሥነ-ሥርዓት ምክር ቤቱ በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ሆኖ በፌዴራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ ሲፀድቅም በሥራ ላይ ይውላል፡፡
11. የምክር ቤቱ አባላት ተግባርና ኃላፊነት የፌዴራል ህብረት ሥራ ኤጀንሲ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

72. **ሕጎችን፣ ደንቦችን፣ መመሪያዎችና መተዳደሪያ ደንብን ተደራሽ ስለማድረግ**

ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማኅበር የኅብረት ሥራ ማህበራትን የሚመለከቱ አዋጆችን፣ ደንቦችን፣ መመሪያዎች እና መተዳደሪያ ደንቦችን በኅብረት ሥራ ማህበሩ አድራሻ እንዲገኙና ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግ አለበት፡፡

73. **የመተባበር ግዴታ**

ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ማንኛውም አካል የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

74. **የተሻሩና ተፈጻሚ የማይሆኑ ሕጎች**

1. የኅብረት ሥራ ማኅበራት አዋጅ ቁጥር 147/1991 (በአዋጅ ቁጥር 402/1996 እንደተሻሻለ በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፡፡
2. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ ደንብ ወይም መመሪያ በዚህ አዋጅ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

75. **የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

1. ከኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 147/1991 (በአዋጅ ቁጥር 402/1996 እንደ ተሻሻለ ወይም በክልል አግባብ ባለው ህግ በተደነገገው አግባብ ሳይመዘገብ እየሠራ ያለ ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ከዋለበት ጊዜ ጀምሮ በሁለት ዓመታት ውስጥ ራሱን በማደራጀት መመዝብ አለበት፤በዚህ ጊዜ ውስጥ ቀርቦ ያልተመዘገበ ኅብረት ሥራ ማህበር መብቱን እና ህልውናውን ያጣል፡፡
2. በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 147/1991 (በአዋጅ ቁጥር 402/1996 እንደ ተሻሻለ ወይም በክልል አግባብ ባለው ህግ ተደራጅተው የተመዘገቡ ኅብረት ሥራ ማህበራት በዚህ አዋጅ እንደ ተመዘገቡ ተቆጥሮ ሥራቸውን ያከናውናሉ፡፡
3. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 74 ድንጋጌ ቢኖርም ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ከዋለበት ቀን በፊት በክርክር ላይ ያሉ ማናቸውም ጉዳዮች በአዋጅ ቁጥር 147/1991 (በአዋጅ ቁጥር 402/1996 እንደተሻሻለ ወይም ጉዳዩ በክልል ከሆነ አግባብነት ባለው የክልሉ ሕግ መሰረት ተፈፃሚነት ያገኛል፡፡

**76.<u>ደንብና መመሪያ ስለማውጣት</u>**

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልግ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ክልሎች ይህን አዋጅ እና ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚወጣ ደንብን በማይቃረን ሁኔታ ሕግ ሊያወጡ ይችላሉ፡፡
3. የፌደራል ሕብረት ሥራ ኤጀንሲ ይህንን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1 መሠረት የወጣውን ደንብ ለማስፈጸም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**77.<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ታህሳስ 14 ቀን 2009 ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ**

**ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## ደንብ ቁጥር 106/1996

## የኅብረት ሥራ ማኅበራት አዋጅ ቁጥር 147/1991 [109]ለማስፈጸም የወጣ

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኅብረት ሥራ ማኅበራት አዋጅ ቁጥር 147/1996 አንቀጽ 59 እና የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 4/1987 አንቀጽ 5 መሠረት ይህን ደንብ አዉጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የኅብረት ሥራ ማኅበራት አዋጅ ቁጥር 147/1991 ለማስፈጸም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 106/1996" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፥

1. "አዋጅ" ማለት የኅብረት ሥራ ማኅበራት አዋጅ ቁጥር 147/1991 ነው።[110]
2. "መደበኛ ስብሰባ" ማለት በአዋጅ ቁጥር 147/1991 አንቀጽ 23 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚደረግ ጠቅላላ ጉባዔ ማለት ነው።[111]
3. "የኅብረት ሥራ ማኅበር" ማለት በአዋጁ አንቀጽ 2(2 የተጠቀሰው ትርጉም ይኖረዋል፡፡
4. "አግባብ ያለው ባለሥልጣን" ማለት በአዋጅ ቀጥር 274/1994 አንቀጽ 2(1 መሠረት የተቋቋመ የኅብረት ሥራ ኮሚሽን[112] እና በየክልሉ የተቋቋሙ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ማደራጃና ማስፋፊያ ቢሮዎችና ጽሕፈት ቤቶችን ይጨምራል።
5. "ኅብረት" (ዩኒየን ማለት ከአንድ በላይ የሆኑ ተመሳሳይ ዓላማ ያላቸው መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ኅብረት ነው፡፡
6. "ፌዴሬሽን" ማለት ከአንድ በላይ የሆኑ ተመሳሳይ ዓላማ ያላቸው ኅብረቶች (ዩኒየኖች እና የሕብረት ሥራ ማኅበራት ስብስብ ነው፡፡
7. "ሊግ" ማለት የኅብረት ሥራ ማኅበራት በአገር አቀፍ ደረጃ የሚመሠርቱት የኢትዮጵያ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ሊግ ነው፡፡

---

[109] በ23)7 (2009 አ. 985 አንቀፅ 74(1 ተሻረ፡፡
[110] በ23)7 (2009 አ. 985 አንቀፅ 74(1 ተሻረ፡፡
[111] በ23)7 (2009 አ. 985 አንቀፅ 74(1 ስለተተሻሩ በሻሪዉ አዋጅ አንቀፅ 33 የተመለከተዉ ይሆናል፡፡
[112] በ12)1 (1998 አ. 471 አንቀፅ 33(2 መሠረት ኤጀንሲ ስለሆነ፣ በደንቡ ዉስጥ "ኮሚሽን" የሚለዉ "ኤጀንሲ" በሚል ይነበብ፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለ ኅብረት ሥራ ማኅበራት አመሠራረት

### 3. የመሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማኅበራት አመሠራረት

1. መሠረታዊ ማኅበር በተወሰነ አካባቢ በሚኖሩ ወይም በሚሠሩ ወይም በተወሰነ ሙያ በተሰማሩ ፈቃደኛ ግለሰቦች ይቋቋማል፡፡ የመሥራች አባላት ቁጥር ከአሥር አያንስም፡፡ አግባብ ያለው ባለሥልጣን ከኢኮኖሚያዊ ብቃት አኳያ ተመልክቶ የአባላትን መነሻ ቁጥር ለመወሰን የአፋጻጸም መመሪያ ያወጣል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚመሠረት መሠረታዊ ማኅበር የሥራ ክልል በአንድ ክልል ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ክልሎችን የሚሸፍን ሊሆን ይችላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 2 በተመለከተው የሥራ ክልል ውስጥ ከአንድ በላይ የተለያዩ ዓይነቶች መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ሊመሠረቱ ይችላሉ።

### 4. የኅብረት ሥራ ኅብረት (ዩኒየን አመሠራረት

1. የዚህ ሕግና ሌሎች የኅብረት ሥራ ማኅበራትን የሚመለከቱ ሕጎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ተመሣሣይ ዓላማ ያላቸው መሠረታዊ ማኅበራት የሕብረት ሥራ ኅብረት (ዩኒየንሊመሠርቱ ይችላሉ፡፡
2. በዚህ ሕግና በሌሎች ሕጎች የተደነገገው እንደተጠበቁሆነውከኅብረቱ ጋር ተመሣሣይ ተግባር የሚያከናውንና የማኅበሩን መርሆች የተቀበለ ግለሰብ የኅብረቱ (ዩኒየን አባል ሊሆን ይችላል፡፡

### 5. የኅበረት ሥራ ፌዴሬሽን አመሠራረት

1. የዚህ እና የሌሎች ሕጎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ተመሣሣይ ዓላማ ያላቸው ኅብረቶች በፌዴራል ደረጃ ፌዴሬሽን ሊመሠርቱ ይችላሉ፡፡
2. የዚህ እና የሌሎች ሕጎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ከፌዴሬሽኑ ጋር ተመሣሣይ ተግባር የሚያከናውን የሕብረት ሥራ ማኅበር እና ግለሰብ አባል ሊሆን ይችላል፡፡

### 6. የኅብረት ሥራ ሊግ አመሠራረት

1. የዚህ እና የሌሎች ሕጎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበራት፣ ኅብረቶች እና ፌዴሬሽኖች በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ማኅበራትን የሚወክል ሊግ ሊመሠርቱ ይችላሉ፡፡

2. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚመሠረት ሊግ ቁጥር ከአንድ ሊበልጥ አይችልም።

7. **የሥራ ክልል**

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 4 ወይም 5 የተመሠረተ ማንኛውም ኅብረት ወይም ፌዴሬሽን የሥራ ክልል በኅብረቱ ወይም በፌዴሬሽኑ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ይወሰናል፡፡
2. የሊጉ የሥራ ክልል በአገር አቀፍ ደረጃ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የኅብረት ሥራ ማኅበራት ተግባራትና ዓይነቶች

8. **የኅብረት ሥራ ማኅበራት ተግባራት**

ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማኅበር የማምረት ወይም አገልግሎት የመስጠት ወይም የማምረትና አገልግሎት የመስጠት ተግባራት ሊኖሩት ይችላሉ፡፡

9. **የማምረት ተግባር የሚያከናውን የኅብረት ሥራ ማኅበር**

የማምረት ተግባር የሚያከናውን የኅብረት ሥራ ማኅበር በማምረት ሥራ ላይ የተሰማራ ወይም ጥሬ ዕቃ ወደ አላቂ ዕቃ የሚቀይር ወይም በከፊል የተሠሩትን ወደ አላቂ ምርትነት የሚቀይር ይሆናል፡፡

10. **የአገልግሎት ተግባር የሚያከናውን የኅብረት ሥራ ማኅበር**

የአገልግሎት ተግባር የሚያከናውን የኅብረት ሥራ ማኅበር ለአባላት የተለያዩ አገልግሎቶችን የሚሰጥ ወይም እንዲያገኙ የሚያደርግ ይሆናል፡፡

11. **የማምረትና የአገልግሎት ተግባር የሚያከናዉን የኅብረት ሥራ ማኅበር**

የማምረትና የአገልግሎት ተግባር የሚያከናውን የኅብረት ሥራ ማኅበር በዚህ ደንብ በአንቀጽ 9 እና 10 የተመለከቱትን ተግባራት በጣምራ የሚያከናውን ይሆናል፡፡

12. **የኅብረት ሥራ ማኅበራት ዓይነቶች**

1. የተለያዩ የኅብረት ሥራ ዓይነቶች ሀገሪቱ በሚኖራት ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ የሥራ ዘርፎች ውስጥ ሊደራጁ ይችላሉ፡፡
2. የኅብረት ሥራ ማኅበራት ዓይነተኛ መለያ ባሕሪያቸው፣ በሚሠሩበት የሥራ አካባቢ፣በአመሠራረታቸው፡ በተግባራቸውና በሚኖራቸው የሕጋዊ ሰውነት የሚለይ ይሆናል፡፡
3. ስለኅብረት ሥራ ማኅበራት ዓይነተኛ ባሕሪያት አግባብ ያለው ባለሥልጣን መመሪያ ያወጣል።

## ክፍል አራት

## ስለ ኅብረት ሥራ ማኅበራት ምዝገባ እንቅስቃሴ

### 13. ምዝገባ

1. ሊጉን እና ፌዴሬሽኑን ጨምሮ በብሔራዊ ደረጃ የሚቋቋሙትን ዩኒየኖች የኅብረት ሥራ ኮሚሽን ይመዘግባል።
2. በዚህ ደንብ መሠረት የተመዘገበ ማንኛውም ማኅበር ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ሕጋዊ ሰውነት ያገኛል።

### 14. የኅብረት ሥራ ማኅበር መተዳደሪያ ደንብ ስለሚይዛቸው ዝርዝሮች

በአዋጁ አንቀፅ 11[113] የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የማናቸውም የኅብረት ሥራ ማኅበር መተዳደሪያ ደንብ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፡

ሀ) የማኅበሩን ዓላማ፡ የኅብረት ሥራ እሴቶችና መርሆች፤

ለ) የማኅበሩን አስተዳደራዊ መዋቅር፤

ሐ) የማኅበሩን የበጀት ዓመት፤

መ) የማኅበሩን ገንዘብ አያያዝና አጠቃቀም፤

ሠ) የማኅበሩን ብድር አወሳሰን፤

ረ) አባላት ከማኅበሩ ሲለቁ፡ ሲሰናበቱ ወይም በሞት ሲለዩ ተፈጻሚ የሚሆን ሥርዓት፤

ሰ) የማኅበሩ የስብሰባ ሥነ ሥርዓትና ለአባላት የሚሰጥ ማስታወቂያ፤

ሸ) የማኅበሩ ሥራ አስኪያጅ እንዲሁም ሌሎች ኃላፊዎች የሚቀጠሩበት፡የሚመረጡበት ሥርዓት፡ ሥልጣንና ተግባራቸው እንዲሁም የሥራ ዘመናቸው፤

ቀ) የማኅበሩ ሠራተኞች አስተዳደር፤

በ) ልዩ ውሣኔና የምልዓተ ጉባዔ ውሣኔ የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች፤

ተ) የማኅበሩን መተዳደሪያ ደንብ ለማሻሻል ተፈጻሚ የሚሆን ሥርዓትን ማኅበሩ ሲከፈል፡ ሲፈርስ ወይም ከሌሎች ማኅበራት ጋር ሲዋሃድ ተፈጻሚ የሚሆን ሥርዓት፤

ቸ) ሌሎች አግባብነት ያላቸው ጉዳዮች፡፡

### 15. የኅብረት ሥራ ማኅበር አባላት የዕጣ ሰርተፊኬት

1. ማንኛውም አባል ለገዛው ሙሉ የዕጣ መጠን ሰርተፊኬት ይሰጠዋል።
2. የዕጣ ሰርተፊኬቱ በምስጢር የሚታተም ሆኖ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፤

   ሀ) የማኅበሩ ስም፤ አድራሻና ዓርማ፤

[113] በ23/7 (2009) አ. 985 አንቀፅ 12 ሆኗል፡፡

ለ) ማኅበሩ የተመዘገበበት ቀንና የምዝገባ ቁጥር፤

ሐ) የዕጣ ሰርተፊኬት መለያ ቁጥር፤

መ) የአንድ ዕጣ ዋጋ፤

ሠ) የአባሉ ስም፤ የአባልነት መለያ ቁጥር፤

ረ) የገዛው የዕጣ መጠንና ዋጋ፤

ሰ) ማኅበሩን ለመምራት ሥልጣን ያለው ሰው ፊርማ፤

ሸ) የማኅበሩ ማኅተም፤

ቀ) ሰርተፊኬቱ የተሰጠበት ቀን ወርና ዓመተ ምህረት፡፡

3. የኅብረት ሥራ ማኅበሩ ዕጣ ከአንድ የማኅበሩ አባል ወደ ሌላ አባል ወይም ከአንድ የማኅበሩ አባል ወደ ሦስተኛ ወገን ሊተላለፍ አይችልም።

16.<u>የሕብረት ሥራ ማኅበር አባላት ስለሚሰናበቱበት ሁኔታ</u>

1. ግዴታውን ያልተወጣ አንድ አባል ከማኅበሩ ይሰናበታል። አባሉ ግዴታውን እንዳልተወጣ የሚቆጠረው፤

ሀ) በተወሰነው የጊዜ ገደብ የዕጣ ክፍያን ያላጠናቀቀ እንደሆነ፤

ለ) በማኅበሩ በሚሰጠው የሥራ ዘርፍ ከሁለት ጊዜ በላይ ግዴታውን ያልተወጣ፣

ሐ) ማኅበሩ በሚሰጣቸው አገልግሎቶች ወይም ግብይቶች ለአንድ ዓመት ያልተሳተፈ፤

መ)ያለበቂ ምክንያት ለሁለት ተከታታይ ጊዜ በመደበኛ ስብሰባዎች ላይ ያልተሳተፈ እንደሆነ ነዉ።

2. ጥፋት የፈጸመ አንድ አባል ከማኅበሩ ይሰናበታል፡፡ አባሉ ጥፋት እንደፈጸመ የሚቆጠረዉ፣

ሀ) ከማኅበሩ ዓላማ ጋር የሚጻረር ተግባር የፈጸመ፤

ለ) በማኅበሩ ንብረቶች ላይ ሆነ ብሎ አደጋ ያደረሰ ወይም እንዲደርስ ያደረገ፤

ሐ) በተለያየ ምክንያት በእጁ የገባውን የማኅበሩን ንብረት ለግል ጥቅሙ ያዋለ፤

መ) የማኅበሩን ገንዘብ ሆነ ብሎ ያጎደለ ወይም ሁኔታዎችን ያመቻቸ፤

ሠ) በማኅበሩ ስም መደለያ ወይም ጉቦ የሰጠ ወይም የተቀበለ፤

ረ) በማኅበሩ የሚገዙ ወይም የሚሸጡ ንብረቶችን ጥቅም ለማግኘት ሲል ከገበያ ዋጋ በታች የሸጠ ወይም ከገበያ ዋጋ በላይ የገዛ ወይም እንዲሸጥ ወይም እንዲገዛ ያደረገ፤

ሰ) ለማኅበሩ የሚያቀርበውን ምርት ወይም አገልግሎት ዋጋ እንዳያገኝ ጥራቱን ያጓደለ ወይም መጠኑን የቀነሰ እንደሆነ ነው፡፡

**17.ስለ ክፍያ**

ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማኅበር የምስክር ወረቀት ለማውጣት ወይም ምትክ የምስክር ወረቀት ለማግኘት ከዚህ ደንብ ጋር ተያይዞ በሚገኘው ሠንጠረዥ ላይ የተመለከተውን ክፍያ ለመንግሥት ይከፍላል፡፡

**18.ምትክ የምስክር ወረቀት ስለመስጠት**

1. የተሰጠው የምስክር ወረቀት የጠፋበት ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማኅበር ምትክ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው አግባብ ያለውን ባለሥልጣን ሊጠይቅ ይችላል፡፡
2. አግባብ ያለው ባለሥልጣን ጥያቄው በቀረበለት በ10 ቀን ጊዜ ውስጥ ምትክ የምስክር ወረቀቱን ይሰጣል፡፡
3. አግባብ ያለው ባለሥልጣን ስለ ምትክ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል።

**19.ምዝገባ ስለሚከለከልበት ሁኔታ**

ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማኅበር፡

1. አስቀድሞ ከተመዘገበ ማኅበር ጋር ተመሣሣይ ስምና ዓርማ ያለው ከሆነ፤
2. የራሱ የሆነ የፕሮጀክት ጥናት የሌለው ከሆነ፤
3. በዚህ ደንብ እና በአዋጁ መሠረት ለምዝገባ የሚያስፈልጉ ሁኔታዎችን ያላሟላ ከሆነ፤
4. ዓላማው ይህን ደንብ፡ አዋጅ ወይም አግባብ ባለው ባለሥልጣን የወጡ መመሪያዎችን የሚፃረር ከሆነ፤ ተመዝግቦ የምስክር ወረቀት ማግኘት አይችልም፡፡

## ክፍል አምስት

## ስለ ኅብረት ሥራ ማኅበሩ ስብሰባዎች

**20.መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ**

1. ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማኅበር ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ያደርጋል፡፡
2. ከጠቅላላ ጉባዔው አባላት ከግማሽ በላይ ሲገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡፡
3. መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ተጠርቶ ምልዓተ ጉባዔዉ ካልተሟላ በ15 ቀናት ውስጥ ሁለተኛ ጠቅላላ ጉባዔ ይጠራል፡፡ ለሁለተኛ ጊዜ የተጠራው መደበኛ ጠቅላለ ጉባዔ ምልዓተ ጉባኤ ካልተሟላ በተገኙት አባላት መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ይካሄዳል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ምልዓተ ጉባዔ ሳይኖር የተካሄደ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ የሚያሳልፋቸው ውሣኔዎች ሁሉም የጉባዔው አባላት በተገኙበት እንደተላለፈ ይቆጠራል።

21. **<u>አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ</u>**

1. በአዋጁ አንቀጽ 22[114] መሠረት የተጠራው አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ምልዓተ ጉባኤው ካልተሟላ በ15 ቀናት ውስጥ የሥራ አመራር ኮሚቴው ለሁለተኛ ጊዜ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ይጠራል፡፡ ለሁለተኛ ጊዜ የተጠራው አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ምልዓተ ጉባዔ ካልተሟላ አግባብ ያለው ባለሥልጣን ጥሪ የማድረግ ሥልጣን ይኖረዋል።
2. ከጠቅላላው አባላት ሁለት ሦስተኛው ሲገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡፡

22. **<u>ጥሪ ስለማድረግ</u>**

በዚህ አዋጅ መሠረት አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ከመደረጉ ከ15 ቀን በፊት የማኅበሩ የሥራ አመራር ለአባላቱ ሀገር አቀፍ ሥርጭት ባለው ጋዜጣ ወይም አመቺ ሆኖ በተገኘው መንገድ ጥሪ ማድረግ አለበት፡፡

23. **<u>የሕብረት ሥራ ማኅበር የድምጽ አሰጣጥ ሥርዓት</u>**

1. በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ በተለየ ሁኔታ ካልተገለጸ በቀር በመደበኛ ወይም በአስቸኳይ ጉባዔው የሚተላለፉ ውሣኔዎች በአባላቱ የአብላጫ ድምጽ ይሆናል፡፡
2. የድምጽ አሰጣጥ እኩል በኩል የተከፈለ ሲሆን የጉባዔው ሰብሳቢ ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡

## <u>ክፍል ስድስት</u>

## <u>ስለ ሕብረት ሥራ ማኅበር ንብረትና ገንዘብ</u>

24. **<u>የተጣራ ትርፍ አደላደል</u>**

1. ከማኅበሩ የተጣራ ትርፍ ላይ 30 በመቶ እየተቀነሰ በመጠባበቂያ ሂሣብ ይቀመጣል፡፡ የመጠባበቂያ ሂሣቡ የሚቀመጠው ከማኅበሩ ካፒታል 30 በመቶ እስከሚደርስ ብቻ ነው፡፡
2. በየዓመቱ ከማኅበሩ የተጣራ ትርፍ ውስጥ እየተቀነሰ በመጠባበቂያ የሚመደበው ገንዘብ በማኅበሩ ስም የቁጠባ ሂሣብ ተከፍቶለት ይቀመጣል፡፡ ስለአጠቃቀሙ አግባብ ያለው ባለሥልጣን መመሪያ ያወጣል፡፡

[114] በ23)7 (2009 አ. 985 አንቀፅ 33 ሆኗል፡፡

25.<u>ስለሕብረት ሥራ ማኅበር የማይከፋፈል ንብረት</u>

ማንኛውም የማኅበሩ ንብረት፥

ሀ) በመጠባበቂያ ሂሣብ ውስጥ የተመዘገበ ከሆነ፤

ለ) በስጦታ ወይም በውርስ የተገኘ ከሆነ የወል ንብረት ይሆናል፡፡

26.<u>የሕብረት ሥራ ማኅበር ሲፈርስ ስለሚኖረዉ ንብረት አከፋፈል</u>

ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማኅበር በሕግ መሠረት ሲፈርስ በአዋጁ አንቀጽ 44 ንዑስ አንቀጽ 4[115] መሠረት ሕብረት ሥራ ለማኅበሩ ገንዘብ ጠያቂዎች ተከፍሎ የሚቀረው ንብረት ሕብረት ሥራ ማኅበሩ ሲፈርስ ለነበሩ አባላት፥ ሕብረት ሥራ ማኅበሩ ከመፍረሱ በፊት ያለጥፋት ለተሰናበቱ አባላትና ለሟች አባላት ተተኪዎች እንደየ ድርሻቸው ይከፋፈላል። ስለ አከፋፈሉ አግባብ ያለው ባለሥልጣን መመሪያ ያወጣል፡፡

27.<u>የተሻሩ ሕጎች</u>

ይህን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ ወይም መመሪያ ተፈጻሚነት የለውም።

28.<u>መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

አግባብ ያለው ባለሥልጣን ይህን ደንብ ለማስፈጸም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

29.<u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሰኔ 21 ቀን 1996 ዓ)ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስትር**

[115]በ23)7 (2009 አ. 985 አንቀፅ 59 (4 ሆኗል፡፡

## የፍትህ ሚኒስቴር

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

## የኅብረት ሥራ ኮሚሽን

## የምስክር ወረቀት አገልግሎት ክፍያ ሠንጠረዥ

| ተ.ቁ | የምስክር ወረቀት | የክፍያ መጠን)ብር | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ ምዝገባ | 60 | |
| 2 | ምትክ | 30 | |
| 3 | ጊዜያዊ | 30 | |